
መድሎት
በኢትዮጵያ ፖለቲካ የ3ኛ አማራጭነት ሚና
ልደቱ አያሌው
2002

መግቢያ ..... 4

ክፍል  አንድ ..... 12

በአገራችን ፖለቲካ የብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነት ..... 12

1.1 ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ ..... 12

1.2 ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ ..... 15

1.4 የብሔራዊ ዕርቅ መድረክ ..... 64

ክፍል ሁለት ..... 70

የአገራችን ፖለቲካ ተዋናዮችና ሚናቸው ..... 70

2.1 ኢህአዴግና የፖለቲካ ትግሉ ..... 70

2.2 ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ትግሉ ..... 95

2.2.2 በትግል ስልት ዙሪያ የሚነሡ አማራጮች ..... 130

2.3 ሕዝብና የፖለቲካ ትግሉ ..... 145

2.4 በውጭ አገር  የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የፖለቲካ ትግሉ ..... 174

2.6 የአገራችን መገናኛ ብዙኃን ..... 193

ክፍል ሦስት ..... 205

ከርእዮተ-ዓለሙና ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር የሚነሡ የልዩነት ነጥቦች ..... 205

3.1 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የሊበራል ዴሞክራሲ ንጽጽር ..... 209

3.1.1 አብዮታዊ ዴሞክራሲ ..... 209

3.1.2 ሊበራል ዴሞክራሲ ..... 216

3.2 ርእዮተ-ዓለማዊ ታማኝነታችን እስከ ምን ድረስ? ..... 226

3.2.1 ዴሞክራሲ ጥያቄ ሊነሣበት አይችልም? ..... 233

3.2.2 ዴሞክራሲ ሂደት ነው ሲባል ምን ማለት ነው? ..... 239

3.2.3 ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምን ያህል ዝግጁ ናት?....253

3.2.4 የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአገራችን መቼና እንዴት? ....259

3.3 ነፃ-ገበያ እንዴትና እስከ ምን?....269

3.4 ለዘላቂ ዕድገት የሚያበቃን ምን ዓይነት የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነው? ....279

3.5 መሬትና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ....307

ክፍል አራት ....329

አከራካሪ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች....329

4.1 በሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ሊነሡ የሚገቡ ጥያቄዎች....331

4.2 የአገራችን ፌደራሊዝምና በዙሪያው የሚነሡ ጥያቄዎች ....345

4.3 የመገንጠል መብትና በዙሪያው የሚነሡ ጥያቄዎች....358

4.4 በሥልጣን ቁጥጥርና ክፍፍል ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች ....382

ክፍል አምስት ....402

የውጭ ጉዳያችን የትኩረት አቅጣጫ ....402

5.1 በውጭ ግንኙነታችን ዙሪያ የሚታዩ መሠረታዊ ድክመቶች ....404

5.2 የውጭ ግንኙነታችን የትኩረት አቅጣጫ በዓለም-አቀፍና በአሕጉር ደረጃ....408

5.3 የውጭ ግንኙነታችን የትኩረት አቅጣጫ በአፍሪካ ቀንድ ደረጃ....414

ክፍል ስድስት....**Error! Bookmark not defined.**

አሉባልታና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ....436

6.1 አሉባልታ በቅድመ ምርጫ 97 ....442

6.2 አሉባልታና የቅንጅት የመጨረሻ አወዳደቅ ....471

6.3 አሉባልታና የመጨረሻ ውጤቱ ....**Error! Bookmark not defined.**

*6.4 አዲስ ተስፋ የፈነጠቀ ታሪካዊ ጅማሮ*....**Error! Bookmark not defined.**

*መደምደሚያ*....431

ኢዮጋ ኢዮጋ ኢዮጋ

# መግቢያ

ይህንን ዓይነት ከእኔ የግል ግንዛቤና አስተሳሰብ አንጻር የኢትዮጵያን ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ በድፍረት ከመተቸት ተነሥቶ የወደፊቱን አቅጣጫ ለማመላከት የሚሞክር ጽሑፍ ለማሥነበብ ያሰብኩት ከስድስት ዓመት በፊት ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ በኩል የተለያዩ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ የፓርቲና የግል ጉዳዮች እያጋጠሙኝ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድፍረት በተሞላበት ሁኔታ ራሴን፣ አባል የሆንኩበትን ፓርቲ፣ ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችንና የእነዚህ ሁሉ መሠረት የሆነውን ኅብረተሰብ እንደ ኅብረተሰብ መተቸት ሊያስከፍል የሚችለውን ዋጋ በመፍራት ለረዥም ጊዜ ያሰብኩትን ለመፈጸም ሳልችል ቀረሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለእኔ ዓይነቱ በአገሪቱ ወቅታዊ የፖለቲካ መድረክ ጉልህ ተሳትፎ እያደረገ ለሚገኝ ሰው እንዲህ ዓይነቱን ትችት ደፍሮ መጻፍ ተገቢና ጠቃሚ ነውን? ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት በራሱ ቀላል ጊዜ የሚጠይቅ አልነበረም፡፡

ከአራት ዓመት በፊት እነዚህን ፍላጎቴን የገቱ ምክንያቶች ከራሴ ጋር ታግዬ በማሸነፍ ያሰብኩትን ለማድረግ ስዘጋጅ ምርጫ 97 መጣና ወደ አልተጠበቀ አቅጣጫ ገፈተረኝ፡፡ ከምርጫውና ከድኅረ-ምርጫው ሂደት ጋር በተያያዘ ተቃዋሚው ጎራ ውስጥ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት እኔው ራሴ በሕዝቡ ውስጥ የመወያያ አጀንዳ በመሆኔ ምክንያት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ለመተቸት የነበረኝ ዕቅድ ለጊዜው ቀረና በራሴ ላይ የተቀሰቀሰብኝን የአሉባልታ ዘመቻ ማዕበል ለማረጋጋት የሚያስችል ሥራ ውስጥ ለመግባት ተገደድኩ፡፡ በአጭር ጊዜም የፖለቲካ ትግሉን ከተቀላቀልኩበት ጊዜ ጀምሮ ያለፍኩበትን አጠቃላይ ሂደትና ምርጫ 97ን ተከትሎ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን እውነታ ሊያሳይ ይችላል ብዬ በማስከብ የአረም እርሻን ጽፌ ለንባብ አበቃሁ፡፡

የአረም እርሻ እውነታውን አንብቦ ለመረዳት የሥነ-ልቦና ዝግጅት የነበረውን የኅብረተሰብ ክፍል መድረስ በቻለችበት መጠን ልዩነት ያመጣች ቢሆንም የማንበብ ባህል የሌለውንና በፈጠራ አሉባልታ የተበከለውን በርካታ የኅብረተሰብ ክፍል በመለወጥ ረገድ ግን የአረም እርሻ ሚና እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም፡፡ ይልቁንም ስለ እኔ በመላው አገሩ የተነዛው አሉባልታ እየተገፈፈ መምጣት የጀመረው እኔ ስለ ራሴ መናገርና መጻፍ ስለሞከርኩ ሳይሆን ጊዜና ሂደት በራሳቸው ቀስ በቀስ ሃቁን እየገለጡት በመምጣታቸው ነበር፡፡

ዛሬ ላይ ቆሜ ወደ ኋላ ሳስብ ይህ መጽሐፍ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት አለመጻፉ የሚያፀፅት ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ ምክንያቱም ላለፉት አራት ዓመታት በተለይም በምርጫ 97

ዙሪያ በትግሉ ውስጥ በነበረኝ ቆይታ የተማርኳቸው ቁምነገሮች እጅግ ብዙ ስለሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ የፖለቲካ ሂደቱ የነውጥ ማዕበል ውስጥ በገባባቸው ዓመታት ስለ ገዢው ፓርቲ፣ ስለ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና በአጠቃላይም ስለ የኢትዮጵያ ሕዝብ የነበረኝ ቀደምት ግንዛቤ በብዙ ርቀት መለወጥና መዳበር ችሏል፡፡ ስለዚህ ይህንን መጽሐፍ ተሳክቶልኝ ከዛሬ አራት ዓመት በፊት ለንባብ አብቅቸው ቢሆን ኖሮ በአለፉት አራት ዓመታት ያለፍኩበትን ሂደት እያስታወስኩ "ምነው ዛሬ ጽፌው በነበር" እያልኩ መፀፀቴ አይቀርም ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ ከሂደት ለመማርና ራሱን ለማረም ለተዘጋጀ ሰው "ዛሬ ቢሆን ኖሮ" የሚለው መፀፀት እስከ ሕይወት ፍጻሜ አብሮት የሚቀጥል ቢሆንም አሁን በምገኝበት የአስተሳሰብ ደረጃ የወቅቱን የአገራችንን የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት እንደምመለከተው በአሁኑ ወቅት ለአንባቢ ማካፈል ጠቃሚና ወቅታዊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ጠቃሚና ወቅታዊ ነው ብዬ እንዳምን ያደረጉኝ ዋና ዋና ምክንያቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት ከኢህአዴግ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ መንግሥት ከደርግ ዘመን አንድ ዓመት በልጦ እስካሁን አገሪቱን ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ያህል አስተዳድሯል፡፡ በዚህ ረዥም ሊባል የሚችል የአስተዳደር ዘመን ውስጥ ኢህአዴግ ባለፉት ስድስት ዓመታት ትምህርትን፣ ጤናን፣ መሠረተ - ልማትን በመሳሰሉና በሌሎችም የተለያዩ ጉዳዮች አበረታች ውጤቶችን ማምጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አገራችን ከሰላም መስፈን፣ ከሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ ከዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታና በአጠቃላይም ከመልካም አስተዳደር መኖርና ከድህነት ቅነሳ አንጻር ዛሬም ወደኋላ የቀረች አገር ሆና ቀጥላለች፡፡ በተለይም ከሰብአዊ መብት ጥሰት አኳያ አገራችን ዛሬም እንደ ትናንቱ የበርካታ ዓለም ዓቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ውግዘት ያልተለያት አገር መሆንዋ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኢኮኖሚ ረገድም መሠረታዊ መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት ባለመቻልዋ ዛሬም በዝናብና በኋላቀር አስተራረስ ላይ የተመሠረተ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ጥገኛ ሆና ቀጥላለች፡፡ ኢህአዴግ አስራ ስምንት አመት ሙሉ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ትኩረት ሰጥቶ ሲሠራ ቢቆይም አገራችን በምግብ እህል ራሷን መቻል ይቅርና ከርሃብም መላቀቅ አልቻለችም፡፡ በዚህ ምክንያት አገራችን ከድህነት መላቀቅ የምትችልበትን ትክክለኛ አቅጣጫ እስካሁን በአግባቡ መቆናጠጥ አልጀመረችም፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ አሁንም ራሱን ከስህተትና ከድክመት የጸዳ ድርጅት አድርጎ ከማየቱም በላይ የአገሪቱን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ መወሰን የምችለውና የሚገባኝ እኔው ብቻ ነኝ የሚል አቋም በመያዝ አገሪቱን ወደፊትም ለሃያ እና ሰላሣ ዓመታት በብቸኝነት ሊመራት እየተመኘ ብቻ ሳይሆን አቅዶ እዬሰራ ይገኛል፡፡

ሁለተኛ - ኢህአዴግን ታግለን በማሸነፍ ለአገሪቱ የተሻለ ሥርዓት እናመጣለን ብለን የተሰለፍነው ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ምክንያታዊ ፖለቲካ ማራመድና ለትግሉ የሚመጥን የአመራር ብቃት ማሳየት ተስኖን እየተጠናከርን ከመምጣት ይልቅ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እየተዳከምንና ከሕዝቡ ልብ እየራቅን መምጣት ጀምረናል፡፡ ከጥላቻ ፖለቲካ፣ ከዘረኝነት፣ ከድርጅታዊ መዋቅር ድክመትና በአጠቃላይም ከዴሞክራሲያዊ ባህል እጦት አኳያ ተቃዋሚዎች ውስጣችን ተገልጦ ቢታይ ገዥው ፓርቲ በሚከሰስባቸው ድክመቶችና ጥፋቶች እኛም ተከሳሽ ከመሆን አንድንም፡፡ በተግባር የምንገኝበት እውነታ ይህ ሆኖ እያለ የሌለንን ድርጅታዊ ጥንካሬና የሕዝብ ድጋፍ እንዳለን አስመስለን እየተኩራራን፤ ራሳችንን ከድክመትና ከስህተት የጸዳን አድርገን እየተመጻደቅን፣ አንድ ቦታ ላይ ቆም ብለን ራሳችንን ገምግመን ከማረም ይልቅ ለአገሪቱ ችግሮች በሙሉ ጣታችንን ወደ ገዥው ፓርቲ ብቻ በመቀሰር ወደፊት የሚያጠናክረንን ሳይሆን የበለጠ የሚያዳክመንንና ተሸናፊ የሚያደርገንን የተሳሳተ አቅጣጫ በመከተል ላይ እንገኛለን፡፡

ሦስተኛ - ገዥውም ፓርቲ ሆነ ተቃዋሚዎች የፈለቅንበትና የአገሪቱ ዋና ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለጥቅሙና ለፍላጐቱ የሚበጁትን ፓርቲዎች ለመፍጠር የሚያስችለውን ተገቢ ጥረት እያደረገ አይደለም፡፡ ሕዝቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚደግፍበትና የሚቃወምበት መመዘኛ፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ያለው ግንዛቤ፣ በፖለቲካ ሂደቱ ውስጥ ያለው ተሳትፎና እያበረከተ የሚገኘው አስተዋፅኦ በብዙ ድክመቶችና ችግሮች የተሞላ በመሆኑ ፓርቲዎችን ወደ በጎ አቅጣጫ የመግፋት አቅም ያለው የለውጥ ኃይል ለመሆን ገና አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በርካታ በጎ ጎኖች ያሉት ጠንካራ ሕዝብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለንተናዊ መልኩ የበቃና የመጠቀ ምንም ዓይነት እንከን የማይወጣለት ሕዝብ እንደሆነ ተደርጎ ያለመጠን እየተሞካሸ የአገሪቱ ችግሮች የመፍትሄ አካል ከመሆን ይልቅ የአገሪቱ ችግሮች አካል ሆኖ እንዲቀጥል እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተለይም የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ ስላለው ጠንካራና ደካማ ጐኖች በቂ ግንዛቤ ሳይኖረው ወደ መጭው አገር አቀፍ ምርጫ የሚገባበትና ምንአልባትም ደግሞ - ደጋግሞ የተሳሳተ አቋምና አቅጣጫ ሰለባ ሊሆን የሚችልበት ዕድል ዛሬም ሰፊ ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአገራችን የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ገዢ ፓርቲና ተቃዋሚ በሚል ሁለት ጎራ ተከፍለው "ከእኛ ጋር ካልሆንክ - ከእነሱ ጋር ነህ" በሚል የጽንፈኝነት ፖለቲካ አንዱ ሌላውን ተከሳሽና ተጠያቂ ለማድረግ ሲጥሩ ከማየት በስተቀር ሕዝቡ መሠረታዊ አገራዊ አጀንዳዎችን በተመለከተ በፓርቲዎቹ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በውል

የሚገነዘብበት በቂ ዕድል አላገኘም፡፡ በአንድ በኩል ለገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎቹ ዋናው ቁምነገር የኢህአዴግ በሥልጣን ላይ የመቆየት ጉዳይ ሆኖ ስለሚታይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ዋናው ቁምነገር የኢህአዴግ ከሥልጣን የመወገድ ጉዳይ ሆኖ ስለሚታይ የአገሪቱን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ የሚወስኑት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች በምርጫ ወቅት በቁንፅል ከሚደመጡ አስተያየቶች በስተቀር ተገቢውን ትኩረት አግኝተው በሰፊው ውይይት እየተደረገባቸው አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ሕዝቡ ፓርቲዎችን የሚደግፍበትና የሚቃዎምበት መመዘኛ ገዥ ፓርቲ ወይም ተቃዋሚ ከመሆን ጥቅልና ትርጉም የለሽ መስፈርት ወጥቶ በተጨባጭ አገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች ላይ የሚመሠረትበትና ወደ በሰለ የምክንያታዊነት ደረጃ የሚሸጋገርበት ዕድል ሊፈጠር አልቻለም፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ይህንን መጽሐፍ ለንባብ ለማብቃት በዋናነት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እንደ ገዥ ፓርቲ፣ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲና እንደ ሕዝብ ያሉብንን መሠረታዊ ድክመቶች በአግባቡ ውይይት ሳይደረግባቸውና የጠራ ግንዛቤ ሳይያዝባቸው ምርጫ 2002 ከፊታችን በመምጣቱ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሦስት መሠረታዊ ችግሮች ርስ በርስ ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ ሆነው ምን ያህል የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ተብትበው እንዳሰሩት በግልጽ እየታየ ቢሆንም፣ የተሟላውን ሃቅ ደፍሮ የሚናገርም ሆነ የሚጽፍ የፖለቲካ ሰው ወይም የፖለቲካ ሂደቱን የሚከታተል ጸሐፊ እምብዛም አይታይም፡፡ የዚህ ዓይነት ጽሑፍ በእኔ ዓይነቱ የፖለቲካ ቀጥተኛ ተዋናይ የሆነ ሰው ከሚጻፍ ይልቅ በገለልተኛ የምርምር ሰው ቢጻፍ የሚሻል የነበረ ቢሆንም ደፍሮ ይህንን ሚና ሊወስድ የቻለ አካል እስካሁን አልታየም፡፡ በገዥው ፓርቲ ዙሪያ ያሉ ፖለቲከኞችና ምሁራን ስለተቃዋሚው ጎራ ድክመትና ክፋት፣ በተቃዋሚው ጎራ ዙሪያ የምንገኝ ፖለቲከኞችና ምሁራን ደግሞ ስለ ገዥው ፓርቲ ድክመትና ክፋት ከመናገርና ከመጻፍ ባለፈ እስካሁን የራስንና የሕዝብን ድክመት የአገሪቱ ችግሮች አካል አድርጎ በድፍረትና በጥልቀት ለመተቸት ሲሞከር እየታየ አይደለም፡፡ በአገራችን የፖለቲካ ባህል መንግሥትን መተቸት እንደ ጀግናና ዐዋቂ የሚያስቆጥር የመሆኑን ያህል፣ የራስንና የሕዝብን አመለካከት ለመተቸት መሞከር ግን የፖለቲካ ነውር (politically incorrect) ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ በተለይም የሕዝብን አመለካከት ለመተቸት መሞከር ከፖለቲካዊ ነውርነትም አልፎ ቁጣና ውግዘትን ሊቀሰቅስ የሚችል ከአላዋቂነት የሚመነጭ ድፍረት ተደርጎ ሲታይ ኑሯል፡፡

በተለያዩ ወቅቶች ታዋቂ የነበሩ አንዳንድ የአገራችን ደራሲዎች በግጥምና በልብ ወለድ መልክ ከመንግሥት በተጨማሪ የሕዝብ አስተሳሰብን ለመተቸት ሲሞክሩ የታዩ ቢሆንም ባለፉት

መቶ ዓመታት ውስጥ ግልጽና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ የሕዝብን ድክመት ለመተቸት እንደ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ የደፈረ ጸሐፊ በአገራችን አልታየም ማለት ይቻላል። ገብረሕይወት ባይከዳኝ የዴሞክራሲ ጭላንጭል በአገራችን ጭራሽ ባልነበረበት በ20ኛው ክፍለ-ዘመን መጀመሪያ ላይ ስለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጻፍ የደፈረውን እውነት እኛ የ21ኛው ክፍለ-ዘመን ፖለቲከኞችና ምሁራን ግን ሊቃጣብን የሚችል ቁጣና ውግዘትን በመፍራት ብቻ ልንደፍረው አልቻልንም። ይህ በራሱ ሰፊ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ አስገራሚ ዕንቆቅልሽ ቢሆንም የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ይህንን የፍርሀት ድባብ በተቻለ መጠን ሰብሮ በመውጣት ሁላችንም እንደ ገዥ ፓርቲ፣ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲና እንደ ሕዝብ የአገራችን ችግሮች ምንጭና የመፍትሄውም አካል ነን የሚል አዲስ አቅጣጫ ለማመላከት መሞከር ነው።

የተለያዩ አንባብያን ከተለያዩ ግምትና ግንዛቤ በመነሣት "አንተ ይህን ለማድረግ ለምን ደፈርክ?" የሚል ጥያቄ ሊያነሡ እንደሚችሉ ከወዲሁ መገመት አስቸጋሪ አይሆንም። መልሱ ግልጽና አጭር ነው። በቂ የአሉባልታ ክትባት የወሰድኩና በራሴም ሆነ በሌሎች ግፊት ከይሉኝታና ከእወደድ ባይነት /populist/ ፖለቲካ ነፃ መውጣት የቻልኩ ሰው በመሆኔ ነው። ይኸውም በአንድ በኩል እኔና ሌሎች የፖለቲካ ጓደኞቼ ከተለመደው የአገራችን የፖለቲካ ባህል በተለየ ከሕዝብ ጋር ጭምር የሚያጋጩ፣ ነገር ግን ትክክለኛና ጠቃሚ ናቸው ብለን ያመንባቸውን አቋሞች በድፍረት እያራመድን መታገልን ከመረጥንበት ጊዜ ጀምሮ ምን ጊዜም ራስን ሆኖ እንደመገኘት ለሰው ልጅ ከፍተኛ ነፃነት የሚያጐናፅፍ ኃይል እንደሌለ በሚገባ ማጣጣም ችለናል። በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚህ ድፍረት የተሞላባቸው አቋሞቻችን ምክንያትና በሌሎች ሰዎች ክፋትና መሰሪነት ጭምር፣ በተለይም በእኔ ላይ ሊወራ የሚችለው አሉባልታ በሙሉ በአለፉት ዓመታት ተሟጦ በመወራቱ ምክንያት ከእንግዲህ ይወራብኛል ብዬ የምገምተውና የምፈራው አዲስ አሉባልታ የለም። በሌላ ሳይሆን በእነዚህ ሁለት ምክንያቶች ሌሎችን ቀይዶ ከያዛቸው የፍርሀት ወጥመድ ራሴን ቀድሜ ነፃ የማውጣት ዕድል ስላገኘሁ ከሌሎች በተለየ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ድፍረት ማግኘት ችያለሁ ብዬ አምናለሁ።

በሌሎች አገሮች እንደተለመደው በኛም አገር ፖለቲካ ማለት አንዳንድ ጊዜ የማያምኑበትን እየተናገሩና በተግባር የማይፈጽሙትን ጭምር ቃል እየገቡ ተቀባይነት የማግኘት ጉዳይ ተደርጐ ይታያል። የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ከሕዝቡ በተለየ የምናውቃቸው በርካታ ሃቆች ቢኖሩም እውነቱን መናገር ጉጅና ፖለቲካዊ ስህተት (Politically incorrect) መስሎ ስለሚታዩን እውነቱን አንሻፈን የምናቀርብበት ወይም ዝምታን የምንመርጥበት ጊዜ ብዙ

ነው፡፡ በእኔ በኩል እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ጨዋታ በሁለንተናዊ መልኩ እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኘው የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የማይመጥንና የማይገባ ቅንጦት ነው የሚል አቋም ላይ በመድረሴ የማውቀውንና የሚሰማኝን ሁሉ በግልጽና በድፍረት እንደወረደ ተናግሬ ከመሸብኝ ማደርን መርጫለሁ፡፡

ከላይ ይህንን ዓይነት ጽሑፍ ለማሥነበብ ምክንያት ሆነውኛል ብዬ ካስቀመጥኳቸው መሠረታዊ ምክንያቶች በመነሣት በመጽሐፉ በተካተቱት የተለያዩ ምዕራፎች አመች መስሎ በታዬኝ ቅደም-ተከተል በአገራችን የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ በሆኑ የተለያዩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ያለኝን አመለካከትና አቋም በግልጽና በድፍረት ለማሳየት ሞክሬአለሁ፡፡ ከእነዚህ አገራዊ አጀንዳዎች ጋር በተያያዘና ከሌሎች በፖለቲካ ትግሉ ሂደት ሊተገበሩ ከሚገባቸው ስትራቴጂዎችና ስልቶች አንጻርም ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የእነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ምንጭ የሆነው ሕዝብ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በዝርዝር ለመገምገምና የወደፊት አቅጣጫቸው ምን ሊሆን እንደሚገባው ለማመላከት ሞክሬአለሁ፡፡ በእነዚህ መሠረታዊ ርእሶች ላይ የደረስኩባቸው መደምደሚያዎች እኔ በግሌ በአገሪቱ ፖለቲካ ባሳለፍኩት የዐሥራ ሰባት ዓመት የትግል ሂደት የደረስኩበትን የአስተሳሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከሞላ ጎደል በአመራርነት የምሳተፍበትን የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲን (ኢዴፓ) የሦስተኛ አማራጭነት ሚና የሚያንፀባርቁ ጭምር ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ በጽሑፉ ውስጥ ተብራርተው የቀረቡት አቋሞችና ትንታኔዎች ኢዴፓ በ4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ከሞላ ጎደል መነሻ በማድረግ የቀረቡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ኢዴፓ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያዘጋጃቸውን ሰነዶችም የሚቻለውን ያህል በዚህ ጽሑፍ ምንጭነት ለመጠቀም ሙከራ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ በአገራዊ አጀንዳዎች ላይም ሆነ በፖለቲካ ተዋናዮች ላይ የሚኖረኝ ግምገማ አባል ከሆንኩበት ፓርቲ ከኢዴፓ አቋም ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው ነው፡፡ ነገር ግን ፓርቲው አቋም ባልወሰደባቸው የተለያዩ ጉዳዮች የራሴን አቋሞች ልገልጽ የምችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ለእነዚህ አቋሞቼ ሙሉ በሙሉ ተጠያቂና ኃላፊ እኔ እንጂ አባል የሆንኩበት ፓርቲ አለመሆኑን ለአንባብያን ከወዲሁ ማረጋገጥ እወዳለሁ፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በተለያዩ የፖለቲካ ተዋናዮች ላይ ወቀሳና ትችት ሳቀርብም ራሴን ከስህተትና ከተጠያቂነት ነፃ በማድረግ ሳይሆን በትግሉ ውስጥ ባለፍኩበት ሂደት በተሠሩ አንዳንድ ጥፋቶችና ስህተቶች የራሴም የተጠያቂነት ድርሻ መኖሩን አስቀድሜ በማመን ጭምር

ነው። በጽሑፉ የተለያዩ ክፍሎች የአንዳንድ ግለሰቦችን ስም ለመጥቀስ የተገደድኩትም ከግለሰቦቹ ጋር የተለየ የግል ጠብና ጉዳይ ኖሮኝ ሳይሆን በትግሉ ውስጥ ያሉትን ችግሮች አንባቢ በአግባቡ ይገነዘባቸው ዘንድ ስማቸው መጠቀሱ የግድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል። ማንም በጎ አንባቢ የሆነ ሰው በግለሰቦች ዙሪያ የሚያነጣጥርን ጽሑፍ ማንበብ የሚጠላውን ያህል እኔም በበኩሌ ስለ ጉዳዮች እንጂ ስለ ግለሰቦች ፈጽሞ መጻፍ ባልችል በወደድኩ ነበር። ምክንያቱም የቱንም ያህል የራሱ መነሻና ምክንያት ቢኖረውም የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ያልተቋረጠ የርስ በርስ ንትርክ በሕዝቡ ዘንድ ሁላችንንም ተሸሸን እንድንታይ አድርጉናልና አንድ ቦታ ላይ ቢቆም የሚመረጥ መሆኑ አከራካሪ አይደለም። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ጉዳዮችና ድርጅቶች ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ መሪ የሆኑ ግለሰቦችም በችግርም ሆነ በመፍትሄ አካልነት በፖለቲካ ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ስለ ግለሰቦቹ ሳናወራና ሳንጽፍ ችግሩንም ሆነ መፍትሄውን በተሟላ ሁኔታ ማሳየት አስቸጋሪ ይሆናል። በዚህ ረገድ ግዴታ ሆኖብኝ በጽሑፌ ውስጥ በስም ደጋግሜ የምጠቅሳቸው የፖለቲካ መሪዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ይህ የሚሆንበትን ምክንያት አንባቢ ከላይ በጠቀስኩት መልኩ ቢረዳው ተገቢ ይሆናል። በርግጥ የእኔን ስም በአግባቡም ሆነ አግባብ ባልሆነ መንገድ በየመድረኩ የማብጠልጠል ልዩ ፈቃድ ያላቸው መስሎ የሚታያቸው አንዳንድ ግለሰቦች እኔ የነሱን ስም ሳነሣ ግን ጉዳዩ የግል ጉዳይ መስሎ ቢታያቸው እንዲህ ዓይነቱ ችግር አስቀድሞ የሚጠበቅና የማያስደንቅ ይሆናል። በተቻለኝ መጠን ግን የጽሑፌ ትኩረት ከግለሰቦች ይልቅ በጉዳዮችና በድርጅቶች ላይ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት አድርጌአለሁ።

ሌላው አንባብያን አስቀድመው እንዲገነዘቡት አስፈላጊ የሚሆነው ቁም ነገር ከመጽሐፉ ውስጥ አንድን ክፍል አንብበው ሌላውን ክፍል ሙሉ በሙሉ ባላነበቡበት ሁኔታ የቸኮለና አጠቃላይ የሆነ ጉረጃና ትችት ውስጥ ከመግባት ይልቅ በትዕግስት ሙሉ በሙሉ የመጽሐፉን ይዘት ካነበቡ በኋላ ለመተቸት ቢሞክሩ ገንቢ ሚና የሚኖረው መሆኑን ነው። ከወቅቱ የአገራችን የተካረረ የፖለቲካ ሁኔታ አኳያም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ አመለካከቶችና አቋሞች ለጊዜው ከሚያስደስቱት ሰው ይልቅ የሚያስከፉት ሰው ሊበዛ እንደሚችል ከወዲሁ ለመገመት አስቸጋሪ አይደለም። ሁልጊዜም ራሳቸው እውነትና ትክክል ነው ብለው ከሚያስቡት አስተሳሰብና አቋም ውጭ የተለየ ሐሳብን ማዳመጥ የማይፈልጉ ሰዎች ይህንን መጽሐፍ በማንበብ ረገድ ብዙ ርቀት መሄድ ሳይችሉ በመሃል ቀደው ሊጥሉት፣ ወይም በአሉታዊነት ፈርጀው ጥላቻን ሊቀሰቅሱበት ይችላሉ። በተወሰነ ደረጃ ከዚህ ዓይነቱ ስህተት ለመዳን የመጽሐፉን ሙሉ ይዘት አንብቦ መረዳት ተገቢ ይሆናል። በተጨማሪም ጸሐፊውን በተመለከተ ካለን የዬራሳችን ነባር አመለካከት በመነሣት የጽሑፉን ዓላማና ይዘት አስቀድመን

ፈርጀን ለማንበብ ከመሞከርም ይልቅ አእምሮአችንን ለተወሰነ ጊዜ ነፃና ክፍት አድርገን የጽሑፉን ጭብጥ በአግባቡ አንብበን ለመረዳት ብንሞክር የተሻለ ይሆናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ "በአብዛኛው" "በከፊል" "ጥቂት" "ብዙዎች" "አንዳንድ" "በዋናነት" "ሁሉም" የሚሉትና እነዚህን የመሣሰሉት ቅጽሎች (Adjectives) አንባቢን ወደ አልተፈለገ አጠቃላይ ፍረጃ (Generalization) ላለማስገባት ተብለው ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆናቸው በአንባብያን ዘንድ ልዩ ትኩረት ቢሰጣቸው ተገቢ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው "ሕዝብ" የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በፖለቲካው ሂደት ቢያንስ የደጋፊነትና የተቃዋሚነት የጎላ የተሳታፊነት ሚና ያለውን በቁጥር ውስን የሆነ የኅብረተሰብ ክፍል እንጂ በቀጥታ የአገሪቱን አጠቃላይ ሕዝብ የሚወክል ተደርጎ ባይታይ ይመረጣል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ለትምህርት (Academic) እና ለምርምር ጉዳይ ታስቦ ያልተጻፈ በመሆኑ ምክንያት የምርምር ጽሑፍ መመዘኛዎችን አሟልቶ ያልቀረበና ሥነ-ጽሑፋዊ ይዘቱም የሚገባውን ያህል ጥንቃቄ ያልተደረገበት በመሆኑ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅሁ አንብቦ የመረዳትን ጥቅም ከልብ በመገንዘብ መጽሐፉን ማንበብ ለጀመራችሁ አንባብያን በሙሉ መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

## ክፍል አንድ

## አንቀጽ አንድ

### *በአገራችን ፖለቲካ የብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነት*

### *1.1 ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ*

በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ መድረክ ስለ ዴሞክራሲ፣ ስለ ሰብአዊ መብት፣ ስለ ሐሳብ ነፃነት፣ ስለ ጾታ እኩልነት፣ ስለ መድብለ - ፓርቲ፣ ስለ ነፃ-ገበያና ስለተለያዩ አማላይ ጉዳዮች የዘፈን ያህል በተደጋጋሚ ሲነገር ማድመጥ የተለመደ ሆኗል። በየመድረኩ ከሚነገረውም በላይ ስለ እነዚህ ጉዳዮች የተጻፉ በርካታ የሚያማምሩ የፓርቲ ፕሮግራሞችና የመንግሥት ሕጎች አሉን። የአገራችን ወግና ባህል በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የራሱ የዳበረ መነሻ ያለው ቢሆንም ከዘመናዊ ፖለቲካና የኢኮኖሚ እድገት ጋር በተያያዘ የምናቀነቅናቸው አብዛኛዎቹ አመለካከቶች ግን ከውጭ አገራት የቀዳናቸው ንድፈ-ሐሳቦች ናቸው ማለት ይቻላል። ለራሳችን ችግሮች መፍትሔ የሚሆን በቂ ሐሳብ በራሳችን ማፍለቅ እስካልቻልን ድረስ ይህንን የውስጥ ክፍተታችንን ለመሙላት የሚያስችል ሐሳብና ተመኩሮ ከውጭ አገራት መቅሰማችን ተገቢም የማይቀርም ይሆናል። በተለይም የግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን ከገባበት ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ የመጤ አመለካከቶች ቤተ-ሙከራ ሆና ቆይታለች።

ነገር ግን እነዚህ ከውጭ አገራት የቀዳናቸው ንድፈ-ሐሳቦች ሌሎቹን አገራት ወደ ሥልጣኔ ባሸጋገሩበት መንገድ እኛን ለምን ሊያሸጋግሩን እንዳልቻሉ ሁልጊዜ ራሳችንን የምንጠይቅና የምንቆጭ ቢሆንም እስካሁን ሁላችንንም ሊያግባባ የሚችል መልስ ኖሮን አያውቅም፡፡ የውጭ ንድፈ-ሐሳቦችን እንደ ወረደ መኮረጅና ከራስ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሳያጣጥሙ ለመተግበር መሞከር ለውጤት የማያበቃ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭ የቀዳናቸውን ንድፈ-ሀሳቦች በአግባቡ በተግባር ለማዋል መሠረትና መደላድል ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ከብሔራዊ መግባባትና ከመቻቻል ፖለቲካ ጋር የተያያዙ ሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮችን በአግባቡ ሳንኮርጅ መቅረታችን ውጤታማ እንዳንሆን ካደረጉን ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በየአደባባዩ የአፋችን ማሚሻ ያደረግናቸውም ሆኑ በየፖለቲካ ፕሮግራሞቻችን ታጭቀው የሚነበቡት እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸው ንድፈ-ሐሳቦች የቱንም ያህል ተደጋግመው ቢነገሩና ቢጻፉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ብሔራዊ መግባባትንና የፖለቲካ መቻቻልን በተግባር በአገራችን እስካልፈጠርን ድረስ ከውጭ የተቀዱት ንድፈ-ሐሳቦች ሁሉ ጥሬ ንድፈ-ሐሳቦች ሆነው ከመቅረት ባለፈ ወደምንፈልገው ደረጃ ሊያደርሱን አይችሉም፡፡

ኢትዮጵያውያን በታሪካችን የተዩ አንዳንድ በጎ ገጽታዎችን ብቻ በምሳሌነት በመጥቀስ ራሳችንን ከሌላው ዓለም በተሻለ እንግዳ ተቀባይ፣ ሰው አክባሪ፣ ታጋሽ፣ ሰላምና አገር ወዳድ አድርገን በማየት ርስ በርስ ስንሞከሻሽ የኖርን ቢሆንም በተግባር ግን የእነዚህ ባህሪዎች መሠረታዊ መገለጫ የሆኑት ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ ትናንትም ሆነ ዛሬ በእጅጉ ርቀውን የሚገኙ እውነታዎች ሆነዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የምንገኝ የፖለቲካ ሰዎች በሌሎች ያደጉ አገሮች የሚገኙ ፖለቲከኞች አገራዊ ጥቅሞቻቸውን በተመለከተ ምን ያህል ጠንካራ ብሔራዊ መግባባት እንዳላቸውና በርስ በርስ ግንኙነታቸውም ምን ያህል የመቻቻል ፖለቲካን እንዳዳበሩ በዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን አማካይነት በየአንዳንዱ ቀን በቀላሉ መማር የምንችልበት ዕድል ያለን ቢሆንም በሚገርምና በሚያስፈራ ሁኔታ ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ የበለጠ እያራቁን ሄደው ጥላቻ በፖለቲካችን ላይ የበላይነት የያዘበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ በራሱ ሰፊ ምርምርና ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም በጸሐፊው ዕምነት ሁለት ጉዳዮች በዋና ምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው ከጥንት ጀምሮ ሲዎርድ ሲዋረድ ይዘነው ከመጣነው ባህላዊ ዕምነታችን ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከግራ ፖለቲካ ወይም ከስታሊናዊ ርእዮት ጋር ተያይዞ የመጣብን ጣጣ ነው፡፡ በአገራችን ሥር ሰዶ የኖረው የፖለቲካ ባህል በጦርነት አሸናፊ ሆኖ ማስገበርን መሠረት ያደረገ

ከመሆኑም በላይ አማፂነትና ሽፍትነት በአገራችን ባህል ለክብርና ለዝና እንደሚያበቁ በጎ ድርጊቶች እንጂ እንደነውር እምብዛም አይቆጠሩም፡፡ ሽፍትነት በአገራችን ባህል የሚዘፈንለትና ባለዝና የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ በለስ ሲቀናም ለሹመትና ለንግሥና መንጠላጠያነት የሚያበቃ አንድ ወሳኝ የሕይወት መሰላል ሆኖ ያገለግል ነበር፡፡ በአገራችን የፖለቲካ ሥልጣን በዘር ውርስ /Hereditary/ ወይም በምርጫ የሚገኝ ስላልነበር የንጉሥና የራስ ልጆችም ጭምር ተዋግተው ማሸነፍ እስካልቻሉ ድረስ ለመሪነት የመብቃት ዕድል አልነበራቸውም፡፡

ሌላው ዓለም ከእንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህል በሂደት ተላቆ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲሸጋገር እኛ እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በነባራዊው ባህላችን በመቀጠላችን ከመቻቻል ፖለቲካ እርቀን ኖረናል፡፡ በ20ኛውና በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በርካታዎቹ የዓለማችን አገሮች የሊበራሊዝም አመለካከት አራማጅ በመሆን የመቻቻል ፖለቲካ ባለቤት ለመሆን ሲበቁ እኛ ግን ከፍጹማዊ የንጉሣዊ አስተዳደር በቀጥታ ወደ ስታሊናዊ ወይም የግራ ፖለቲካ አመለካከት በመሸጋገራችን ወደ መቻቻል ፖለቲካ የምንገባበት ሳይሆን የመቻቻል ፖለቲካ ተቃራኒ የሆነው ባህላዊ የፖለቲካ አስተሳሰባችን የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት አጋጣሚ ተፈጥሯል፡፡ የ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በወረቀት ላይ የሚያውቃቸው የእነ ማኦ፣ የእነ ቺ-ጉቤራ፣ የእነ ሆችሚኒና የእነ ስታሊን አድናቂ በመሆን "የፋኖ ተሰማራ" ዘማሪና የግራ ፖለቲካ አቀንቃኝ ለመሆን የበቃው ከወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የርእዮተ-ዓለሙን ትክክለኛነት ተገንዝቦት ሳይሆን የቆየው ባህላዊ አመለካከታችን እንዲህ ዓይነቱን የአመፅና የነውጥ ርእዮተ-ዓለም በቀላሉ ለመቀበል የሚያስችል መሠረት ስለነበረው ነው ማለት ይቻላል፡፡ የግራ አመለካከት በሥር-ነቀል አብዮታዊ ለውጥ የሚያምን፣ ከፍጹማዊ የበላይነት ያነሰ ውጤትን የማይቀበል፣ ከአንድ በላይ የሆኑ አማራጮችን የማይቀበልና ልዩነትን ከሌሎች ጋር የማቻቻል ፍላጐት የሌለው በመሆኑ ከባህላዊ የፖለቲካ አስተሳሰባችን በባሰም መጠን የመቻቻል ፖለቲካ ከአገራችን እንዲርቅ ምክንያት ሆኗል፡፡

የግራ ፖለቲካ በጎ ያልሆነውን የፖለቲካ ባህላችንን ከማጠናከሩም በላይ ለመቻቻል ፖለቲካ የራሱን በጎ አስተዋፅኦ ያበረክት የነበረውን "የፈሪሃ ፈጣሪ" ዕምነት በቁስ አካላዊ አመለካከት ለመተካት በመሞከሩ አገሪቱ ቀይ ሽብርን የመሰለ አሰቃቂ የርስ በርስ እልቂት እንዲከሰትባት ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚያ የግራ ፖለቲካ የተለከፉ የትውልድ አባላት ለአለፉት 40 ዓመታት (ዛሬም ጭምር) የአገሪቱን የፖለቲካ መድረክ በብቸኝነት ተቆጣጥረው የቀጠሉ በመሆናቸውም ነው ማለት ይቻላል - ዛሬም እንደትናንቱ አገራችን ከብሔራዊ መግባባትና ከመቻቻል ፖለቲካ ርቃ ለመኳዝ የተገደደችው፡፡ በአጠቃላይ በአንድ አገር ውስጥ የምንገኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች

በሁሉም አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖረን አቋም ሙሉ በሙሉ የተለያየ ከሆነ የመጨረሻ ውጤቱ ዴሞክራሲን መገንባት ሳይሆን አገር መፍረስን የሚያስከትል ቢሆንም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ይህንን አደጋ እስካሁን በአግባቡ የተረዳነው አንመስልም።

የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ከብሔራዊ መግባባትና ከመቻቻል ፖለቲካ አንጻር ከሌሎች አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ምን ያህል እጅግ ወደ ኋላ የቀረ መሆኑን መረዳት ውስብስብ ጉዳይ አይደለም። የእኛው ዓይነት አባዜ የተጠናወታቸው እኛን መሰል ጥቂት አገሮች ካልሆኑ በስተቀር በብዙ አገሮች የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከብሔራዊ መግባባትና ከመቻቻል ፖለቲካ አንጻር ጥያቄ ሊያሥነሣ የሚችል መሠረታዊ ልዩነት በመካከላቸው አይታይም። አብዛኛውን ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ዘመቻ ወቅት ሲከራከሩባቸው የሚደመጡ አጀንዳዎች የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አፈጻጸምን፣ ታክስን፣ ድኀነትን፣ ስደተኝነትን፣ የአካባቢ ጥበቃን፣ የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን፣ ውርጃን፣ የሞት ቅጣትን፣ ጤናንና ትምህርትን በተሻለ መጠንና ጥራት ማዳረስና የመሳሰሉ አጃንዳዎችን የሚመለከቱ ናቸው። በእኛ አገር የፖለቲካ ሁኔታ ግን እነዚህን በሌሎች አገሮች የሚታዩትን አብዛኛዎቹን ጉዳዮች ጨምሮ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የልዩነት ነጥብ ያልሆነ አጀንዳ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። በሌሎች አገሮች ልዩነት ሊነሣባቸው የማይችሉ ከብሔራዊ መግባባትና ከመቻቻል ፖለቲካ ጋር የተያያዙ ብሔራዊ መዝሙርንና የአገር ሠንደቅ ዓላማን የመሳሰሉ በርካታ ጉዳዮች ጭምር ሳይቀሩ በእኛ አገር ያላግባብና በሚያስገርም ሁኔታ የልዩነት አጀንዳዎች መሆናቸውን በሚከተሉት ንዑሳን አንቀጾች ዘርዘር አድርገን በማየት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምን ያህል ሥር በሰደደ ችግር ውስጥ እንደሚገኝ መረዳት እንችላለን።

## *1.2 ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ*

በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ መንግሥት ለፓርቲዎች የሚሰጠው ሕጋዊ ዕውቅና እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ተፎካካሪ ፓርቲዎች አንዳቸው ለሌላቸው ልባዊ ዕውቅና ባልሰጡበት ሁኔታ ሰላማዊ ትግልም ሆነ የምርጫ ፖለቲካ በአግባቡ ሊካሄድ አይችልም። በአጭሩ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን አራምዳለሁ በሚል አንድ አገር ውስጥ ፓርቲዎች አንዳቸው ለሌላቸው የሚሰጡት ዕውቅናና አክብሮት ለብሔራዊ መግባባትና ለመቻቻል ፖለቲካ የግድ መኖር ያለበት ቅድመ-ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል።

አንዱ ፓርቲ ሌላውን ፓርቲ የአገር ጠላት አድርጎ በሚያይበትና ከሌላው ጋር መቼም ቢሆን አብሮ ላለመሥራት አስቀድሞ ምሎ-ተገዝቶ በወሰነበት ሁኔታ "ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን

በአገሪቱ መገንባት ይቻላል" ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡ ዴሞክራሲ ሊገነባ የሚችለው ውይይት፣ ክርክር፣ መከባበር፣ መግባባትና መቻቻል ባለበት ሁኔታ በመሆኑ እነዚህ ቁምነገሮች በሌሉበት በእኛ ዓይነት አገር፣ ዴሞክራሲ በሚፈለገው መጠን መጠናከር ይቅርና እግሩን ተክሎ ሊግተረተር የሚችልበት መሠረት የለውም፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የምንገኝ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተግባር እየተጓዝን የምንገኘው በዚህ ዓይነቱ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የማያበቃን የተሳሳተ ሃዲድ ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን ለሌላችን ተገቢ ዕውቅናና አክብሮት ባልሰጠንበት ሁኔታ እንዲያው ድከሙ ብሎን እንጂ በሌላ የተለየ አቋራጭ መንገድ አልፈን ዴሞክራሲን ልንገነባ አንችልም፡፡ በአገር ደረጃም የሕዝብ ዕውቅና /Legitimacy/ ያለው መንግሥት እስካልኖረ ድረስ ከጽንፈኝነት ፖለቲካ፣ ከርስ በርስ ግጭት አዙሪትም ሆነ ከአብዮት ድግግሞሽ በቀላሉ መላቀቅ አይቻልም፡፡ እስካሁንም አገራችን በእንዲህ ዓይነቱ አዙሪት ውስጥ እንድትኖር ያደረጋት አንዱ ምክንያትም ፓርቲዎች ወይም መንግሥታት በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታም ጭምር የሕዝብ ተቀባይነት /Legitimacy/ ለማግኘት ሲሉ የሚፈጥሩት ግብግብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል መንግሥት ሆኖ አገር እያስተዳደረ የሚገኘው ኢህአዴግ አገር በማስተዳደሩ ሂደት ያለበት አንዱ ታሪካዊ ኃላፊነት ለብዙኃን ፓርቲ ሥርዓት መጠናከር አመች የሆነ ኅብረተሰብ መፍጠር መሆኑን በመዘንጋት ከሱ የተለየ አመለካከት ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ አገር አፍራሾች አድርጎ ሲከስና "እኔ ከሌለሁ አገሪቱ አትኖርም" በማለት ግልጽ የሆነ ፀረ-ዴሞክራሲ አቋም ሲያራምድ ይደመጣል፡፡ ገዥው ፓርቲ ባለበት የመንግሥትነት ኃላፊነት አገሪቱ የግድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መኖር እንደሚያስፈልጋት ሕዝብን በማስተማር ረገድ አርአያ ሆኖ መገኘት ሲገባው ራሱ በሚመራው መንግሥት የሕግ ዕውቅና የተሰጣቸውን ፓርቲዎች ሳይቀር "የንጉሡና የደርግ ሥርዓት ናፋቂዎች ናቸው" ብሎ በጭፍን ከመፈረጅ ጀምሮ ሲያስፈልገውም የሩዋንዳን ጭፍጨፋ በኢትዮጵያ ለማምጣት የሚፈልጉ "ኢንተርሃሞይ" እንደሆኑ አድርጎ ይቀሰቅሳል፡፡ አንድ ገዥ ፓርቲ ሲችል ተቃዋሚ ፓርቲዎች ትክክለኛ አቅጣጫ ይዘው እንዲጠናከሩ መደገፍና ማበረታታት ሲገባው፣ ቢያንስ ግን ተገቢውን አክብሮትና ዕውቅና መስጠት ካልቻለ ከእነማን ጋር ሆኖ የመድብለ -ፓርቲ ሥርዓትን በአገሪቱ ለመገንባት እያሰበ እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ መንግሥትነቱ የራሱን ደጋፊዎች ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎቹን ጭምር በእኩልነት የማስተዳደር ኃላፊነቱን በአግባቡ እስካልተገነዘበ ድረስ ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ በአገራችን ሊኖር አይችልም፡፡

በሌላ በኩል በአገሪቱ የምንገኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለገዥው ፓርቲ ዕውቅናና አክብሮት በመስጠት ረገድ ተመሳሳይ የከረረ አቋም ነው የምናራምደው፡፡ አብዛኛዎቹ "ሰላማዊ ትግል እናራምዳለን" ብለን የተደራጀን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳንቀር እስካሁን ድረስ ኢህአዴግ የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት መሆኑን ከልባችን አምነን ያልተቀበልን ሲሆን፣ እንዲያውም አንዳንዶቻችን ኢህአዴግን የምናየው አገርን ለማፈራረስ የመጣ የውጭ ወራሪ ኃይል አድርገን ነው፡፡ ለኢህአዴግ ምንም ዓይነት ዕውቅና ላለመስጠት ካለን የከረረ ፍላጐት በመነጨም የአራት ድርጅቶች ግንባር የሆነውን ኢህአዴግን እስካሁን የምንጠራው "ወያኔ" በሚል ቁንፅል ስም ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ ከህወሃት በስተቀር ሌሎቹን የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ህልውናቸውን ከመካድ ጀምሮ የምንቆጥራቸው የራሳቸው የፖለቲካ አመለካከት ጭራሽ እንደሌላቸው የህወሃት አሻንጉሊት አድርገን ነው፡፡

ተቃዋሚዎች አንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ለኢህአዴግ ዕውቅናና አክብሮት የመንፈግ አቋም ለትግላችን የሚጠቅም ስልት አድርገን ስለወሰድነውና ደጋፊዎቻችንም በዚህ ዓይነቱ ጭፍን አስተሳሰብ ስለ ቀረፅናቸው ይህ የቆምንበት መሠረት እንዳይሸረሸርብን በመስጋት ኢህአዴግ የሚሠራውን ሥራ በሙሉ ጐጅም ይሁን ጠቃሚ በጭፍን ከመቃወም ወደኋላ የማንል የፖለቲካ ኃይሎች ሆነናል፡፡ በእስካሁኑ የትግል ሂደት በተግባር እንደታየው እንዲህ ዓይነቱ የከረረ አቋም ያለን የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሔራዊ መግባባትንና የመቻቻል ፖለቲካን መሠረት ያደረገ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገራችን እንዲገነባ የሚያስችል በጎ አስተዋፅኦ ሊኖረን አይችልም፡፡ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱን ጭፍን ተቃውሞ ዓላማው ያደረገ የፖለቲካ ፓርቲ ሊኖረው የሚችለው ሚና በተቃራኒው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት መሆን ነው፡፡

ምክንያቱም አንድን በመንግሥት ሥልጣን ላይ የተቀመጠ ገዥ ፓርቲ በዚህ መጠን ዕውቅና ከነፈግነውና የአገር ጠላት አድርገን ከፈረጅነው በኋላ በውይይትና በምክክር የአገርን ችግር ለመፍታት መሞከርም ሆነ በምርጫ ፉክክር ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ማየት በቀላሉ የሚቻል አይሆንም፡፡ ዛሬ ዕውቅና የነፈግነው መንግሥት ነገ በምርጫ ሥልጣኑን ቢለቅ የፖለቲካ ሥልጣኑ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናው አደጋ ውስጥ እንደሚወድቅ ስጋት ስለሚያድርበት ዴሞክራሲን ለማስፈንም ሆነ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫን ለማካሄድ ሊገፋፋ አይችልም፡፡ ይልቁንም የተቆናጠጠውን ሥልጣን እንደ ነብር ጅራት በመቁጠርና የያዘውን ለቆ ህልውናውን ላለማጣት በመስጋት "መጣንብህ" የሚሉትን ተቃዋሚዎቹን በሙሉ የማዳከም ተግባር ውስጥ ለመሰማራት ይገደዳል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች እያካሄድነው ያለነው ትግል በእውነትም ለውጤት እንዲበቃ የምንፈልግ ከሆነ ይህንን ለኢህአዴግ ዕውቅና የመስጠት ጉዳይ የፍላጎትና የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር አድርገን ልናየው የሚገባ ነው፡፡ ኢህአዴግ ለመንግሥት ሥልጣን ከመብቃቱ በፊት ለዐሥራ ሰባት ዓመታት ከሰው ኅሊና በቀላሉ ሊጠፋ የማይችል መራራ መሥዋዕትነት የከፈለ ድርጅት ነው፡፡ የዚህ ድርጅት አባላት ለዚህን ያህል ረዥም ጊዜ የወጣትነት ዕድሜአቸውን በጦርነት ከማሳለፋቸውም በላይ ብዙዎቹ በጦርነቱ ሂደት የቅርብ ዘመዶቻቸውንና የልብ ጓደኞቻቸውን ሕይወት የተነጠቁ፣ አንዳንዶቹም ከፊል አካላቸውን ያጡና በብዙ የሥነ-ልቦና ፈተናዎች ውስጥ ያለፉ ሰዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያው ይዘውት የተነሱትም ሆነ የታገሉለት ዓላማ በእኛ እይታ ጠቃሚም ይሁን ጉጂ፣የታሰበለትን ውጤት ያምጣም አያምጣም ቢያንስ ደርግን ለመደምሰስ ለ17 ዓመታት ለከፈሉት መሥዋዕትነት ተገቢውን አክብሮትና አድናቆት መስጠት ሲገባን ኤርትራን በሚመለከት የወሰዱትን የተሳሳተ አቋም እንደ አጠቃላይ የማንነታቸው መገለጫ አድርገን በመውሰድ አገርን ቅኝ ለመግዛት እንደመጡ የውጭ ወራሪዎች በመቁጠር በንቀትና በመጠየፍ ልናያቸው ስንሞክር ሰዎች ናቸውና በውስጣቸው ስለ እኛ ሊያዳብሩት የሚችሉትን የጥላቻ አስተሳሰብ በቀላሉ መገመት የለብንም፡፡ በተለይም ደግሞ ሰማይና መሬት ቢደባለቅ ከነሱ ጋር አብረን ለመሥራት ፈጽሞ እንደማንፈልግና በለስ ቀንቶን ወደፊት ሥልጣን ስንይዝም ልንበቀላቸው የምንፈልግ መሆኑን በግልጽ እየነገርናቸው ባለንበት በአሁኑ ወቅት እንደገና መልሰን እነዚህኑ ሰዎች ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂደው ሥልጣናቸውን በቀላሉ እንዲለቁልን መጠበቃችን በእውነት የየዋህነት ፖለቲካ ነው፡፡ ማናችንም ብንሆን በዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ልንወስደው ስለሚገባን ርምጃ ራሳችንን በእነሱ ቦታ አስቀምጠን በሃቅ ለመፍረድ ብንሞክር ርምጃችን ከእነሱ የተለየ መሆኑ በእጅጉ ያጠራጥራል፡፡

ምርጫ 97 ላይ በኢህአዴግና በቅንጅት መካከል የነበረው ፍጥጫ በመጨረሻ ያስከተለው ውድመትም የሚያስተምረን ይህንኑ ነው፡፡ በአንድ በኩል በቅንጅት ውስጥ የነበሩና ከኢህአዴግ ጋር መቼም ቢሆን አብረው ላለመሥራት አስቀድመው ምለው ተገዝተው ሰላማዊ ትግሉን ያለ ቦታቸው የተቀላቀሉ ኃይሎች ከመንግሥት በታች የሆነን ውጤት ላለመቀበል መወሰናቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ በምርጫ አማካይነት የቅንጅቱን ወደ ሥልጣን የመምጣት ጉዳይ ሥልጣንን የማጣት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናን የማጣት አደጋ አድርጎ በማየቱ የምርጫው የመጨረሻ ውጤት የዴሞክራሲውን ሂደት የበለጠ ማጠናከር ሳይሆን ወደኋላ መቀልበስ ሆኖ ተጠናቋል፡፡

በተለይም ከምርጫ 97 ልንማር የምንችለው ቁምነገር የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ዕውቅናና አክብሮት ከመስጣጣትም አልፈን በወደፊትዋ ኢትዮጵያ አብሮ መሥራት የምርጫና የፍላጐት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ግዴታም ጭምር መሆኑን ነው፡፡ ማለትም የምርጫ ሂደት አገራችን ውስጥ መካሄዱ እስከቀጠለ ድረስ ኢህአዴግ የቱንም ያህል ጠንካራና አፋኝ ድርጅት ሆኖ ቢቀጥልም ምርጫ 97 ላይ እንደታየው ወደፊት በሁሉም የአገሪቱ የምክር ቤት እርከኖች ሙሉ በሙሉ አሸናፊ ሆኖ የመቀጠል ዕድሉ እየጠበበ መምጣቱ አይቀርም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የቱንም ያህል ጠንካራ ብንሆን የአገሪቱን አጠቃላይ ማለትም ከፌዴራል ፓርላማ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉ ምክር ቤቶችን በአንድ ምርጫ አሸንፈን ኢህአዴግን ሙሉ በሙሉ ከሁሉም የአገሪቱ መዋቅር ከሥልጣን የምናስወግድበት ዕድል አይኖርም፡፡ ተቃዋሚዎች በሆነ ተአምር የአጠቃላዩን ሕዝብ ድጋፍ ብናገኝ እንኳን በአገራችን የፌዴራልና የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ከወረዳና ከቀበሌ ምክር ቤት ምርጫዎች ጋር በአንድ ጊዜ ስለማይካሄድ ሁሉንም መዋቅሮች በአንድ ምርጫ የማሸነፍ ዕድል በርግጠኛነት በአገራችን የለም፡፡ ይህንን ጉዳይ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ ማየት እንችላለን፡፡

በምርጫ 97 ወቅት ቅንጅት በርግጠኛነት ካሸነፋቸው በርካታ የፓርላማና የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች በተጨማሪ የአዲስ አበባ መስተዳድርን ለመረከብ ፈቃደኛ ሆኖ ቢሆን ኖሮ የመንግሥትን ሥልጣን ከያዘው ከኢህአዴግ መንግሥት ጋር እየተመካከረ መሥራት መብቱ ብቻ ሳይሆን ግዴታውም ይሆን ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በሰላም ጉዳይ ከፌደራል ፖሊስ፣ ከደኅንነትና ከመከላከያ መዋቅሮች ጋር ጭምር ተባብሮ መሥራት ለቅንጅት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ይሆን ነበር፡፡ ምክንያቱም አዲስ አበባም ሆነች ሌሎች የአገሪቱ ክልሎች በራሳቸው የሥልጣን ክልል በተናጠል ከሚሠሯቸው ብዙ ጉዳዮች በተጨማሪ የበጀት ድጐማ ከማግኘት ጀምሮ ሌሎች ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር የግድ አብረው ሊሠሯቸው የሚገቡ ጉዳዮች ስላሉ አብሮ አልሠራም ብሎ በመወሰንና የራስን ደሴት በመፍጠር ክልሎችን ማስተዳደር አይቻልም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ መንግሥትን የተቆጣጠረው ኢህአዴግም ጭምር አዲስ አበባን ከሚያስተዳድረው ቅንጅት ጋር ተባብሮ መሥራት ግዴታው ይሆን ነበር፡፡ በመንግሥት ደረጃ ያሉትን ትላልቅ ጉዳዮች ትተን ኢህአዴግ በድርጅት ደረጃ አዲስ አበባ ላይ ሕዝባዊ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ቢፈልግ በራሱ በኢህአዴግ አሠራር መሠረት በቅንጅት ከሚመራው የአዲስ አበባ መስተዳድር ፈቃድ ማግኘት የግድ ይሆንበት ነበር፡፡ ከድርጅት ደረጃ ወረድ ብለን ጉዳዩን በግለሰብ ደረጃ ለማየት ብንሞክር አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የኢህአዴግ

አባላት ንግድ ፈቃድ ማውጣት፣ ቦታ መመራት፣ የጋብቻና የልደት ሠርተፊኬት ማውጣትና የመሳሰሉትን ከዕለት-ተዕለት ኑሮአቸው ጋር የተገናኙ አገልግሎቶችን ለማግኘት በቅንጅት የሚመራውን አስተዳደር መጠየቅ የግድ ይሆንባቸው ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የቅንጅት አስተዳደርም ወደደም ጠላ ለኢህአዴግ አባላት ጭምር አገልግሎት መስጠት ግዴታው ይሆን ነበር፡፡

የሚገርመው ግን በአንድ በኩል ቅንጅት የዲያስፖራውን ጫናና የጋዜጦችን ትችት መቋቋም ተስኖት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ ያጠመደው ወጥመድ ውስጥ በመግባት የአዲስ አበባ መስተዳድርን ላለመረከብ ወሰነ እንጂ፣ ቅንጅት አዲስ አበባን ለመረከብ ወስኖ ቢሆን ኖሮ ኢህአዴግም በቅንጅት ሥር ሆኖ እስከሚቀጥለው የአካባቢ ምርጫ ድረስ ላለመሥራት በመወሰን በወቅቱ በዞንና በቀበሌ ደረጃ በእሱ ቁጥጥር ሥር የነበሩትን የአዲስ አበባ መዋቅሮች ለማፍረስና "ቅንጅት እንደፈለገ ያድርገው" ለማለት ወስኖ ነበር፡፡ ኢህአዴግ በወቅቱ ይህንን ለማድረግ የወሰነው ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ የበለጠ እንዲጠናከር ከመጨነቅ ይልቅ የአዲስ አበባን መዋቅር በሙሉ ባዶ አድረጐ ቅንጅት የሚይዝ የሚጨብጠውን እንዲያጣና ውስጣዊ ድክመቱ እንዲጋለጥ ለማድረግ ነበር፡፡ ይኸ የሚያሳዬን አገር የሚያስተዳድረው ኢህአዴግም ሆነ ከኢህአዴግ የተሻለ ዴሞክራሲን ወደፊት እናመጣለን የምንለው ተቃዋሚ ፓርቲዎች አብረን ላለመሥራት በመወሰን ምን ያህል ዴሞክራሲን የሚያጠናክር ሳይሆን የሚያጠወልግ ተግባር እየፈጸምን የምንገኝ መሆኑን ነው፡፡ አበው "ቂም ይዞ ፀሎት ጭድ አዝሎ ወዘት" እንደሚሉት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች አብረን ለመሥራት ሳንምስን ዴሞክራሲን እንገነባለን ብለን ማሰባችን ከንቱ ድካም ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የፓርቲዎች አስተሳሰብ ወደፊትም የሚቀጥል ከሆነ ዴሞክራሲን የሚያጠወልግ ብቻ ሳይሆን አገርንም ሊያፈርስ የሚችል አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በአንድ ወቅት ተቃዋሚዎች በኢህአዴግ ሥር ሆነን፣ በሌላ ወቅት ደግሞ ኢህአዴግ በተቃዋሚዎች ሥር ሆኖ አብረን የመሥራታችን ጉዳይ አይቀሬና ግዴታ መሆኑን ከወዲሁ አምነን በመቀበል የሥነ-ልቦና ዝግጅት ካላደረግን በስተቀር ወደፊት በአገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ምንአልባት ወደ ግጭትና ሲከፋም ወደ ንፁሃን ሰዎች ደም መፋሰስ እንጂ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግሩን ሂደቶች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ወደፊት የተጀመረው የምርጫ ሂደት እስከቀጠለ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ፓርቲ ሁሉንም የአገሪቱ መዋቅሮች ሙሉ በሙሉ ይዞ የሚቀጥልበትም ሆነ በምርጫ አሸንፎ የሚይዝበት ዕድል አይኖርም፡፡ መቸም ኢህአዴግ የተፈጥሮንና የፖለቲካን የለውጥ ሕግ ለመጀመሪያ ጊዜ ሽሮ

ለዘለዓለም በኢትዮጵያ ሥልጣን ይዤ እኖራለሁ ካላለ በስተቀር፣ አንድ ወቅት ላይ በኃይልም ሆነ በምርጫ የመንግሥትነት ሥልጣኑን ማጣቱ አይቀርም፡፡

በኃውንና መሆን የሚገባውን እናስብና ኢህአዴግ መንግሥታዊ ሥልጣኑን በምርጫ ቢያጣ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ መዋቅሮች በሙሉ በአንድ ጊዜ ይሸነፋል ማለት አይደለም፡፡ በሁሉም የአገሪቱ መዋቅሮች ምርጫዎች በአንድ ጊዜ አለመካሄዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቃዋሚዎች ፌዴራላዊ መንግሥቱንና የአዲስ አበባ ዓይነት ክልሎችን ቀድመው ቢቀሙት እንኳ ቢያንስ የተወሰኑትን እንደ ትግራይ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላና ቤንሻንጉል የመሳሰሉትን ክልሎች ለተወሰነ ጊዜ ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶቹ ይዘው የመቀጠል ከተቃዋሚው ጐራ የተሻለ ሰፊ ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ ስለዚህ ምርጫ እንዲህ ዓይነቱን ውጤት ሲያስከትል ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚዎች አብሮ መሥራትን ግዴታቸው አድርገው እስካልተቀበሉ ድረስ ውጤቱ የአገርን ህልውና አደጋ ውስጥ ሊከትም የሚችል መሆኑ የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡

የአገራችን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ በምርጫና በምርጫ ብቻ እንዲወሰን የምንፈልግ ከሆነ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በቅድሚያ ተገቢውን ዕውቅናና መከባበር መሰጣጣት፣ አብሮ መሥራት ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታም መሆኑን አምኖ መቀበል ይጠበቅብናል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ እንደ እስካሁኑ የተበላሸ የፖለቲካ ባህላችን በአንድ በኩል ሌላውን ጐራ የአገሪቱ ችግሮች ብቸኛ ተጠያቂ እያደረግን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ ችግሮች መፍትሄ የሚገኘው "ከኛ ብቻ ነው" እያልን በግብዝነት የምንቀጥል ከሆነ ዴሞክራሲ በተግባር የምንጨብጠው ሳይሆን እየተመኘነው የምንኖር ባዶ ተስፋ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ ጤናማ ካልሆነውና ለዘመናት አብሮን ከኖረው የነተበ የፖለቲካ ባህላችን ሁላችንም ሰብረን በመውጣት "ሁላችንም የአገሪቱ ችግሮች አካል ነን፣ ሁላችንም የአገሪቱ ችግሮች የመፍትሄ አካልም እንሆናለን" ወደሚል አዲስና ደፋር አቋም መሸጋገር አለብን፡፡

ገዥው ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እስካሁን ወደዚህ ለአገርና ለሕዝብ የሚበጅ አቅጣጫ ለመምጣት ያልቻልነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ እንደ አገር የኖርንበትም ሆነ እንደ ትውልድ ያደግንበት የጥላቻና የመጠፋፋት የፖለቲካ ባህል አጥንታችን ድረስ ዘልቆ የገባ ስለሆነ በቀላሉ ሊላቀቀን አልቻለም፡፡ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ገዥው ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚዎች የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርገን በዋናነት የተጠቀምንበት አጀንዳ አንዳችን ሌላችንን የሥጋትና የአደጋ ምንጭ አድርገን ማቅረብን ነው፡፡ ይህንን አቋማችንን ለውጠን ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ ብንጀምር ከአግባብ በላይ ደጋግመን በመናገር የማይለወጥ "እውነት"

ካስመሰልነው ከራሳችን የተሳሳተ አቋምና በዚህ አቋማችን ካሰባሰብነው ደጋፊያችን ጋር መጣላት ሆኖብን ተቸግረናል፡፡

አንዳንዶቻችን ወደዚህ ዓይነቱ ለውጥ መግባት ምን ያህል ለአገራችን የፖለቲካ ዕድገት እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ፍንትው-ብሎ እየታየን እያለ የእወደድ ባይነት (Populist) ፖለቲካ እስረኛ ሆነን ይህንን አቋም በመውሰድ ሊከተል የሚችለውን ከሃዲ፣ ቅጥረኛ፣ ተለጣፊ፣ ከፋፋይና ተነጣይ የሚል ጊዜያዊ ሃሜትና ፍረጃ ፈርተን የማናምንበትን እየሠራን መቀጠልን መርጠናል፡፡ ከተቃዋሚው ጐራ መካከል ኢዴፓ የዕውቅናና የአብሮ መሥራት ፖለቲካ ፋና ወጊ ለመሆን የሚያስችለውን የ3ኛ አማራጭነት ሚና በድፍረት ይዞ እየወጣ ቢሆንም አብዛኛው ተቃዋሚና ገዥው ፓርቲ ባሉበት እየረገጡ በመሆኑ አጠቃላዩ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ የቱንም ያህል ሊለወጥ አልቻለም፡፡ አብዛኛዎቹ በገዥው ፓርቲም ሆነ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የምንገኝ የፖለቲካ አመራሮች ከ1960ዎቹ ጀምሮ በአገሪቱ በተፈራረቁ የተለያዩ ሥርዓቶችና የግራ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ እየገባን እስከ ደም መፋሰስ በደረሰ የሽኩቻና የቂም-በቀል የፖለቲካ ሂደት ውስጥ አሸናፊና ተሸናፊ እየሆን ስለመጣን ዛሬ ላይ ሆነን የምናደርገው ትግል ስለትናንቱ ቁርሾ እንጂ ስለዛሬዋና ስለነገዋ ኢትዮጵያ መሆን አልቻለም፡፡ የፖለቲካ ትግላችንም ሁላችንም የአንድ አገር ዜጐች እንደመሆናችን መጠን የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ መሆን ሲገባው የተለያየ አገር ዜግነት ይዘው እንደሚታገሉ ኃይሎች "የነፃ አውጭነት" ትግል ሆኖ ቀጥሏል፡፡

ከዚህ ዓይነቱ የማያቋርጥ የጥላቻና የቂም በቀል ሽክርክሪት (vicious circle) በርግጠኛነት ሊያላቅቀን የሚችለው ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዱ ለሌላው ልባዊ ዕውቅና ሰጥቶ አብሮ መሥራት ሲጀምር በሚፈጠረው አዲስ የፖለቲካ ባህል ውስጥ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዱ ለሌላው ህልውና የስጋት ምንጭ መሆናቸው ቀርቶ በተቃራኒው አንዱ ለሌላው ህልውና ዋስትና ሰጪ መሆን ይጀምራሉ፡፡ ፓርቲዎች አብሮ በመሥራት ሂደት ቀስ በቀስ በሚያዳብሩት የመቻቻል ፖለቲካ በመካከላቸው ልዩነት ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ መግባባት ሊፈጥሩበት የሚገባ በርካታ የጋራ አገራዊ አጀንዳ ያላቸው መሆኑን እየተገነዘቡ ስለሚመጡ በምርጫ ወቅት ሊከሰት የሚችለው መሸናነፍ ጊዜያዊ ሥልጣንን እንጂ አጠቃላይ ህልውናን የሚያሳጣ አደጋ እንዳልሆነ ዋስትና እያገኙ ይመጣሉ፡፡ በተለይም የመንግሥት ሥልጣን ይዞ የሚገኘው ገዥው ፓርቲ ሥልጣኑን በምርጫ ተሸንፎ ሲለቅ እንደ ድርጅት ተቃዋሚ ፓርቲ የመሆን መብቱ ተከብሮ ድርጅታዊ ህልውናው በአገሪቱ ፖለቲካ የሚቀጥልበት፣ የድርጅቱ አባላትም እንደ ዜጋ መብታቸው ተጠብቆ ግላዊና ቤተሰባዊ

ኑሮአቸውን በሰላም የሚቀጥሉበት ዋስትና መኖሩን ሲያውቅ የሥልጣን ተቀናቃኞቹን እንደ አገር ጠላት በመቁጠር ማሳደድና ማፈኑን አቁሞ አንድ ቦታ ላይ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂዶ ታሪኩን ለማሳመር መወሰኑ የማይቀር ይሆናል፡፡

ገዥው ፓርቲ ወደዚህ ዓይነቱ ውሳኔ የሚመጣው በአንድ በኩል የህልውና ዋስትና በማግኘቱ ምክንያት ወዶና ፈቅዶ መሆኑ የማያጠርጥር ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ግን ተቃዋሚዎች ለገዥው ፓርቲ ተገቢውን ዕውቅና በሰጡበትና ከሱም ጋር በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አብረው ለመሥራት ልባዊ ዝግጁነታቸውን ባሳዩበት ሁኔታ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚገደድ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተቃዋሚዎች ከጭፍን የጥላቻና ፍረጃ ፖለቲካ ወጥተን የዕውቅናና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ ማራመድ ስንጀምር ገዥው ፓርቲ እንደለመደው ተቃዋሚዎችን የህልውና ስጋት ምንጭ አድርጐ በማስፈራራት የራሱን አባላት ድጋፍ ይዞ መቀጠል አይችልም፡፡ የገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ምክንያታዊ ኃይሎች እየሆን በመጣን ቁጥር የፓርቲያቸው የኢህአዴግ ከሥልጣን መውረድ በእያንዳንዳቸው ህልውና ላይ የሚያስከትለው ቀጥተኛ አደጋ አለመኖሩን እየተገነዘቡ ስለሚመጡ እንደ እስካሁኑ የምርጫ ጉዳይን የሞት የሽረት ጥያቄ አድርገው በማየት ተቃዋሚዎችን በማፈንና በማሳደድ ድርጊት የኢህአዴግ ተባባሪ ሆነው የሚቀጥሉበት ምክንያት አይኖርም፡፡

እንዲያውም ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ የበለጠ እየዳበረ በመጣ መጠን ከአንድ ፓርቲ ወደ ሌላ ፓርቲ የመሸጋገርም ጉዳይ እንደ ከሃዲነትና አፍራሽነት መታየቱ እየቀረ ስለሚመጣ ኢህአዴግ በተግባር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መሆን እስካልቻለ ድረስ በቀላሉ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ የመነጠልና በከፍተኛ ፍጥነትም የመናድና የመፍረስ አደጋ ሊገጥመው ይችላል፡፡ ኢህአዴግ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊት እየፈጸመም ቢሆን አሁን እንደሚታየው ጠንካራ ድርጅት ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው ተቃዋሚዎች በድፍረት ወደ ዕውቅናና አብሮ የመሥራት ምክንያታዊ ፖለቲካ መግባት ተስኖን የተለመደ ጭፍን ጥላቻችንን በማራመድ ለኢህአዴግና ለአባላቱ በአስፈሪ ጠላትነት የምንታይ የስጋት ምንጭ ሆነን እስከቀጠልን ድረስ ብቻ ነው፡፡

ኢህአዴግ "ወዮላችሁ! እኔ ከሌለሁ እናንተም የላችሁም" በማለት እያስፈራራ የአባሎቹንና የደጋፊዎቹን አንድነት ጠብቆ እስካሁን በሥልጣን ላይ ለመቆዬት የቻለውም በሌላ ምሕታሀታዊ ምስጢርና ተአምር ሳይሆን በዚሁ በእኛ የተሳሳተ ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አሁንም ተቃዋሚዎች ከዐሥራ ስምንት ዓመት እንቅልፍ መንቃት ተስኖን በአንድ በኩል "መጣንብህ! በአንተ መቃብር ላይ ነው አዲሱን ሥርዓታችንን የምንመሠርተው" እያልን እያስፈራራነው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ይህንኑ በሕልውናህ መጣንብህ እያልን የምናስፈራራውን ሥርዓት ነፃና

ፍትሐዊ ምርጫ አካሂዶ ሥልጣኑን እንዲለቅልን በመጠዬቅ ሁለት አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ተቃራኒ ስልቶችን ማራመዳችንን የምንቀጥልበት ከሆነ በኢህአዴግ መቃብር ላይ አዲስ ሥርዓት የመመሥረቱም ሆነ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ በአገራችን የማየቱ ጉዳይ የህልም እንጀራ ሆኖ ለረዥም ጊዜ እንደሚቀጥል አያጠራጥርም። ይህ የሚሆነው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ኢህአዴግ ስለሆነም ብቻ ሳይሆን እንደኛ ዓይነት ተቃዋሚ ባለበት አገር ውስጥ እኛም መንግሥት ሆነን ቢሆን ኖሮ አሁን ኢህአዴግ ሊወስድ ከመረጠው የተለየ አቋም ወስደን ሕልውናችንን አደጋ ውስጥ እንጥለው ነበር? የሚለውን ጥያቄ ራሳችንን ደጋግመን መጠዬቅ ይገባናል።

ስለዚህ በአገራችን በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት የምንገኝ ፓርቲዎች ከዚህ በላይ ሊገለፅ በተሞከረው መልኩ አንዳችን ለሌላቸው ተገቢውን ዕውቅናና አክብሮት ላለመስጠት ወሥነን እስከቀጠልን ድረስ በአገራችን ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ በቀላሉ ይፈጠራል ብሎ ማሰብ አይቻልም። በመካከላችን የቱንም ያህል አገራዊ አጀንዳዎችን በተመለከተ የከረረ የአቋም ልዩነት ቢኖር አሁን የያዝነው አቅጣጫ በመጨረሻ ሁላችንንም ተሸናፊ እንጂ አንዳችንንም በተለየ ሁኔታ አሸናፊ አያደርገንም። በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በእውነት ልባዊ እምነት ካለን እየመረረንም ቢሆን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን ለሌላችን የግድ ተገቢውን ዕውቅናና አክብሮት መስጠት አለብን። ይህንን ቀዳሚ ርምጃ መውሰድ ስንችል ብቻ ነው ስለ ሰላማዊ ትግል፣ ስለ ምርጫ ፖለቲካ፣ ስለ ብሔራዊ መግባባት፣ ስለ መቻቻል ፖለቲካ፣ በአጠቃላይም ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የምናወራውና የምንጽፈው ሁሉ የአንገት ሳይሆን የልብ መሆኑ ሊረጋገጥ የሚችለው።

በነገራችን ላይ ሁላችንም ስሜታዊ ሆነን ጥቅምና ጉዳቱን በወቅቱ ማመዛዘን ተስኖን ነው እንጂ በሽግግር መንግሥቱ ወቅት አብሮ የመሥራትና ዕውቅና የመስጠት የፖለቲካ ባህልን ለማዳበር የሚያስችል አንድ ዕድል አምልጦናል። በሽግግር መንግሥቱ ወቅት እነ አቶ ክፍሌ ወዳጆ፣ አቶ ነቢዩ ሳሙኤል፣ አቶ ተስፋዬ ኃቢሶ፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ዶ/ር ኃይሌ ወ/ሚካኤል፣ አቶ አሰፋ ጩቦና አቶ ኤፍሬም ዘሚካኤልን የመሳሰሉት ሰዎች ጀምረውት የነበረው ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ፖለቲካ የበለጠ እየሰፋና ሌሎችንም ተቃዋሚዎች እያቀረበ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ አሁን ያለንበት ሁኔታ በእጅጉ የተለየ በሆነ ነበር። ነገር ግን በአንድ በኩል በገዥው ፓርቲ ተፅዕኖ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ብዙዎቻችን በዚያን ወቅት ኢህአዴግ አገር የማፍረስ ተልዕኮውን በአጭር ጊዜ ፈጽሞ ከአገራችን በኖ የሚጠፋ ውጫዊ ወራሪ ኃይል ይመስለን ስለነበር ለምን ከኢህአዴግ ጋር አብረው ለመሥራት ሞከሩ ተብሎ በተካሄደባቸው

የማጥላላት ዘመቻ ብዙዎቹ በሽግግር መንግሥቱ ወቅት በፖለቲካው መድረኩ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ለዘብተኛ ፓርቲዎች የአክራሪውን ኃይል ተፅዕኖ መቋቋም ተስኗቸው ሊከስሙ ችለዋል፡፡ አንዳንዶቹም የሥርዓቱን ተፅዕኖና የአሉባልታውን ውርጅብኝ መቋቋም ተስኗቸው ጽንፈኛውን የተቃዋሚነት ጐራ ተቀላቅለዋል፡፡

ሌላው ቀርቶ የመንግሥት ሥልጣን ጭምር ተጋርቶ አብሮ መሥራት ጀምሮ የነበረውና በወቅቱ ከሥልጣን ጥያቄ ውጪ ከኢህአዴግ የተለየ ምንም ዓይነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም ያልነበረው ኦነግ ሰላማዊ ሂደቱን ለቆ ጫካ ከመግባት ይልቅ ተፅዕኖዎችን እንደምንም ተቋቁሞ በአብሮ መሥራቱ ሂደት ቀጥሎበት ቢሆን ኖሮ በአገራችን የመቻቻል ፖለቲካን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ይኖረው ነበር፡፡ የኦነግ አመራሮች ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች በርካታ የሚኒስትርነት ቦታ ከመያዝም አልፎ የሽግግር መንግሥቱ ምክትል ፕሬዝዳንትና ጸሐፊ እስከመሆን ደርሰው የነበሩበት ያ- ሁኔታ የበለጠ ተጠናክሮ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የአገራችን ዴሞክራሲና የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ብዙ ርምጃዎች ተራምዶ በተገኘ ነበር፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን የፖለቲካ ሂደት ትልቅ እንቅፋት ሆኖ የኖረውን ይህንን በጭፍን ዕውቅናና አክብሮት የመነፋፈግ ባህል ሁላችንም በድፍረት አንድ ጊዜ ከሰበርነው በዙሪያችን የተሰለፈው ሕዝብም ውሎ አድሮ ይህንኑ አቅጣጫ መከተሉ የማይቀር ይሆናል፡፡ ሕዝቡን ወደ ትክክለኛ አገርና ትውልድ የሚጠቅም አቅጣጫ አስገብተን በአግባቡ መምራት የሚገባንና ይህንንም ታሪካዊ ኃላፊነት በእጃችን የያዝነው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ብልሹ የሆነው የፖለቲካ ባህላችን እንዲለወጥ ከፈለግን በቅድሚያ ራሳችን በድፍረት መለወጥ ይኖርብናል፡፡ የተቃዋሚዎች ደጋፊ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል በአሁኑ ወቅት "አቦይ ስብሃትና ልደቱ ተገናኙ" ሲሉት ነውር መስሎ የሚታየው፣ ፓርላማ ገብቶና አዲስ አበባን ተረክቦ ከገዥው ፓርቲ ጋር አብሮ መሥራት ክህደት መስሎ የሚታየው፣ ኢህአዴግ የሚሠራቸውን በጎ ነገሮች አምኖ መቀበልና ድክመቱን ነጥሎ መቃወም ሽንፈት መስሎ የሚታየው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ሕዝቡ በተፈጥሮው ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-መቻቻል የሆነ ባህሪ ኖሮት ሳይሆን ከሱ የተሻልን ነን ብለን የፖለቲካ ድርጅት ያቋቋምነው የፖለቲካ መሪዎቹ ከእነ ስታሊንና ማኦ ተውሰን በሕዝቡ ውስጥ ራሳችን ዘርተን ያበቀልነው ይህንን ዓይነት የጥላቻ የፖለቲካ ባህል በመሆኑ ነው፡፡

ነገር ግን በፖለቲካ ሂደት አንድ ፓርቲ የመጣበት መንገድ የተሳሳተና የማይጠቅም፣ የኋላ ኋላም ለውጤት የማያበቃ ሆኖ ሲያገኘው የቱንም ያህል ከነባር የራስ አቋምና ከደጋፊ ሕዝብ

አስተሳሰብ ጋር የሚጋጭና የሚቃረን ቢሆንም አዲስ አቅጣጫንና አስተሳሰብን በድፍረት መያዝ የክህደትና የሽንፈት ሳይሆን የብልህነትና የአሸናፊነት ውሳኔ ነው፡፡ "ፖለቲካ ሊሆን የሚቻለውን የመሆን ጥበብ ነው" የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአገራችን ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ እንዳይፈጠር ቀዳሚ እንቅፋት ሆኖ የኖረው ይህ የዕውቅናና የአብሮ መሥራት ፖለቲካ ባህል እጦት ቢሆንም ሌሎች ከዚህ በታች በቀረበው ርእስ ሥር በዝርዝር ልናያቸው የምንሞክር አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንድ ዓይነት የመግባባት ደረጃ ላይ ልንደርስ አለመቻላችን ተጨማሪ ምክንያት መሆኑን ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 1.3 ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርባቸው የሚገቡ ሌሎች ጉዳዮች

በብዙ የጋራ ሊሆኑ በሚገባቸው አገራዊ ጉዳዮች ላይ በመለያየት ረገድ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በዓለም ወደር የለንም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው ልዩነት ገደብ ወይም ድንበር አለው ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ብዙ ርቀት የተጓዙትን ያደጉ አገሮችን ትተን ራሳችንን ከሌሎች በእኛ የእድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ አፍሪካዊ አገሮች ጋር ለማነጻጸር ብንሞክር እንኳ በብሔራዊ መግባባት ረገድ ደረጃችን እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የምንለያይባቸው ጉዳዮች ጥልቀትና ብዛት ሲታይ ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል የጋራ አጀንዳ ብቻ ሳይሆን የጋራ አገርም አለን ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል፡፡ በሌሎች አገሮች እንደሚገኙ ፓርቲዎች በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ አጀንዳዎች ያሉንን ጤናማ ልዩነቶች ለጊዜው ትተን (በሌላ ክፍል እናያቸዋለን) በአንድ አገር ውስጥ የምንኖር እንደመሆናችን መጠን ፓርቲዎች ልንለያይባቸው የማይገባን፣ ነገር ግን በተግባር የተለያየንባቸውን አገራዊ ጉዳዮች እንደሚከተለው ዘርዝር አድርገን ለማየት እንሞክር፡፡

### 1.3.1 ስለታሪካችን ያለን ግንዛቤ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የመጀመሪያው ልዩነታችን የሚነሣው ለአገራችን ታሪክ ባለን ግንዛቤ ነው፡፡ እያንዳንዱ አገር የታሪክ ሂደት ውጤት በመሆኑ በዚህ ረገድ ልዩነት መኖሩ የሚጠበቅ ቢሆንም በታሪክ ትንታኔ ዙሪያ በእኛ አገር የሚታየው ልዩነት ግን ከልክ ያለፈ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ በተመለከተ በአገራችን የፖለቲካ መድረክ በዋናነት ሁለት ጽንፍ ላይ የቆሙ አስተሳሰቦች ይደመጣሉ፡፡ የብሔር ማንነትን መሠረት አድርገው የተደራጁ በገዥው ፓርቲም ሆነ በተቃዋሚው ጎራ ዙሪያ የሚገኙ ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ የኢትዮጵያን

ታሪክ የባላባትና የጭሰኛ፣ የወራሪና የተወራሪ፣ በአጠቃላይም የጨቋኝና የተጨቋኝ ግንኙነት ብቻ አድርገው በማየት የኢትዮጵያን ታሪክ በጎ ያልሆነ ገጽታ አጉልቶ የሚያሳይ አቋም ሲያራምዱና ከዚህ የተለየ ዕይታ ያላቸውን ኃይሎች ሁሉ በቀድሞ ሥርዓት ናፋቂነትና በትምክህተኛነት ሲከሱ ይታያሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ኅብረ-ብሔራዊነትን መሠረት አድርገው የተደራጁት ፓርቲዎች ደግሞ ብዙውን ጊዜ የኢትዮጵያን ታሪክ የብዙ ሥልጣኔዎች ምንጭ ከመሆን፣ የቀደምት መንግሥት መሥራችና የኃይማኖቶች ቀዳሚ ተቀባይ ከመሆን፣ ከውጭ ወራሪ ራስን ጠብቆ ከማቆዬት፣ በተለያዩ መስተጋብሮች የመዋሐድና አንድ የመሆን ታሪካዊ ሂደት ጋር አያይዘው በማየት ብቻ የአገሪቱን ታሪክ በጎ ገጽታ አጉልቶ የሚያሳይ አቋም ሲያራምዱና ከዚህ የተለየ ዕይታ ያላቸውን ኃይሎች ሁሉ በጠባብነትና ባአገር አፍራሽነት ሲከሱ ይታያል፡፡

እነዚህ ሁለት የፖለቲካ ጎራዎች የሚያራምዱትን የፖለቲካ አጀንዳ በታሪክ ትንታኔ ጭምር ለማስደገፍ ሲሉ ከእነርሱ አቋም ጋር የሚጣጣመውን የታሪክ ክስተት ብቻ እንደሰበዝ እየመዘዙ ወይም እንደ ቡፌ ምግብ እየመረጡ ለመጠቀም ይሞክራሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሙከራ ተገቢ ባይሆንም ሁለቱ ኃይሎች በየበኩላቸው የሚጠቅሱት የታሪክ ገጽታ የራሱ እውነት የሌለው ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህ ስህተት አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከኢትዮጵያ እውነተኛ የታሪክ ገጽታ አንጻር የተሟላ እውነት ሊሆን የሚችለው ግን ሁለቱም ጎራዎች በተናጠል የሚያነሡት የታሪክ ገጽታ አንድ ላይ ተዳምሮ መቀመጥ ሲችል ነው፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም ጎራዎች ለማቅረብ እንደሚሞክሩት የአገራችን ታሪክ ወጥ በሆነ መልኩ የመጥፎ ወይም የጥሩ ክስተቶች መገለጫ ብቻ ሳይሆን ሁለቱም የታሪክ ገጽታዎች ሲፈራረቁበት የኖረ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን እንደ ትውልድ የምንወርሰው ሁለቱንም የታሪክ ገጽታ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ በተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች ድክመትና ጥንካሬ፣ ሽንፈትና ድል፣ ርኅብና ጥጋብ፣ ሥልጣኔና ኋላቀርነት፣ ጥበትና ስፋት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰላምና ጦርነት ሲፈራረቁበት የኖረ መሆኑ ለማንም የታሪክ መዛግብትን በጥቂቱ ለማገላበጥ ለሞከረ ሰው አከራካሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንኳንስ የሺ ዓመታት ዕድሜ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክና የጥቂት ዓመታት የመንግሥትነት ታሪክ ያለው ማንኛውም አዲስ አገር ሙሉ በሙሉ ጥሩ ወይም ሙሉ በሙሉ መጥፎ የሚባል ታሪክ አይኖረውም፡፡ ከፖለቲካ በተለየ ታሪክ በአድልዎ ስለማይፈርድም ጥሩውን ከመጥፎ እየለዬ ራሱን ጎደሎ አድርጎ የሚያቀርብበት ሁኔታ የለም፡፡ በርግጥ ዛሬ ላይ ሆነው አጼ ዮሐንስ ወይም አጼ ምኒሊክ ለምን ዴሞክራት የአገር መሪ አልነበሩም? ብለው ለመውቀስና በዚህም ምክንያት የኢትዮጵያን ታሪክ አጨልመው ለመመልከት

የሚፈልጉ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ያልተረዱት ቁምነገር ዛሬ ላይ ቆመው ትናንትን መፍረድ ቀላል፣ ግን ደግሞ ወደ ትክክለኛ ድምዳሜ የማያደርስ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ዛሬ ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ምሳሌ አድርገን የምናየው ዓለም ሁሉ ኢትዮጵያ ባለፈችበት የታሪክ ሂደት በተመሳሳይ ያለፈ መሆኑን ነው፡፡ ሌሎች አገሮች በጎ ያልሆነውን የታሪክ ገጽታቸውን በሂደት ወደ በጎ ገጽታ መቀየር የቻሉት ባለፈው ታሪካቸው ተከፋፍለው ርስ በርስ ስለተዎቃቀሱ ወይም ካሳ ጠያቂና ካሳ ከፋይ ስለሆኑ ሳይሆን በጎ ገጽታ ያለው አዲስ ታሪክ በጋራ ቆመው መሥራት በመቻላቸው ነው፡፡

ዛሬ በሁለንተናዊ ውጤታቸው የምንቀናባቸው አብዛኛዎቹ የዓለም አገራት የሴቶችን፣ የሕፃናትንና የባሪያ ጉልበትን ያለ አግባብ በዝብዘውና ዓለምን በክለው አገራቸውን የገነቡ፣ ሰውን ከሰው-በላ አራዊት ጋር በማፋለም ትርኢት ይዝናኑ የነበሩ፣ በብዙ ደም አፋሳሽና አውዳሚ የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ያለፉና እስከ ቅርብ ጊዜ ማለትም እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ድረስ ጎረቤቶቻቸውን ብቻ ሳይሆን ውቅያኖሶችን ተሻግረው በመዝመት የሌላ አሕጉር ሕዝቦችን በቅኝግዛት ሲያማቅቁ የነበሩ አገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ ያለፉ ድርጊቶች ሰብዓዊ ያልነበሩ መሆኑ የማያከራክር ቢሆንም ዛሬ ላይ ቆመን ግን ያን ሁሉ ያለፈ የታሪክ ሂደት ስህተት ነበር ብለን መውቀስ በራሱ እኛን ትክክለኛ አያደርገንም፡፡

ምክንያቱም እያንዳንዱ የታሪክ ሂደት ሊፈረድ የሚገባው ታሪኩ በተከናወነበት ወቅት በነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /Context/ እንጂ ዛሬ በደረስንበት የንቃተ-ኅሊና ደረጃ መሆን ስለሌለበት ነው፡፡ ግዛትን ማስፋፋትና ሌሎች ሕዝቦችን በኃይል ማስገበር የአንድ አገር መንግሥት የብቃት ማረጋገጫ ተደርጎ ይታይ በነበረበት በዚያን ወቅት አጼ ዮሐንስ ወይም አጼ ምኒሊክ ለምን ዴሞክራት አልሆኑም ብለንና የሕዝቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ለምን አላከበሩም? ብለን መውቀስ በየትኛውም መመዘኛ ተገቢ ወቀሳ ሊሆን አይችልም፡፡ እንኳን በኛ አገር ሁኔታና የመርሁ ፈጣሪ በሆኑትም አገሮች ጭምር ዴሞክራሲና ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በዚያን ወቅት የተከበሩበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ በዓለም ውስጥ በዚያን ወቅት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያራምዳሉ የሚባሉት አገሮች ቁጥርም ከዐሥራ አንድ የሚበልጥ አልነበረም፡፡ በዚያ ብዕርና ወረቀት እንኳ በአግባቡ ባልነበረበት ዘመን እነ አፄ ሚንሊክ ከፍየል ስልቻም ቢሆን የምርጫ ኮሮጆ ሰርተው ለምን የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብት አላከበሩም ብሎ መጠየቅ ቅንነት የጐደለው ወቀሳ ይሆናል፡፡

በተለይም ደግሞ በአሁኑም የሠለጠነ ዘመን የሚገኘው ትውልድ ዴሞክራሲን በአግባቡ ማስፈን ባልቻለበትና የሌሎችን መብት በሚገባው መጠን ገና ባላከበረበትና ርስ በርስ ደም

እየተፋሰሰ ባለበት ሁኔታ አንድ ዘመን ወደ ኋላ ተመልሶ የዚያን ዘመን ትውልዶችና መሪዎች ለመውቀስ መሞከር ከሺ ዋቢ ራሱ ቆራቢ እንዲሉ "ለመሆኑ እኛ ማነንና? እኛስ በመጭው ትውልድና በወደፊቱ ታሪክ ምን ተብለን እንፈረዳለን?" የሚል የሞራል ጥያቄ ማሥነሳቱ አይቀርም፡፡ ከኛ በተለየ ችግራቸውን ፈተው ራሳቸውን በብዙ ርቀት ከኛ በተሻለ ደረጃ ያስቀመጡ ሕዝቦች እንኳ የቀድሞ መሪዎቻቸውን እንደኛ በጭካኔ ሲያንቋሽሹ አይታዩም፡፡ ስልሣ የተለያዩ ግዛቶችን በመሣሪያ ኃይል አንድ በማድረግ የሚታዎቀው ጀርመናዊው ቢስማርክ፣ ዐሥራ ሦስት ግዛቶችን በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ያደረገው ጣሊያናዊው ጋሪባልዲ ዛሬም ጭምር የየአገሮቻቸው ታላቅ ጀግኖች ተደርገው የሚዎደሱ እንጂ እንደኛ ቀደምት መሪዎች ነፍጠኞች እየተባሉ የሚሰደቡ አይደሉም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በአገራችን የታሪክ ሂደት ገዥዎች ራሳቸውን ልዩ ፍጡርና ከሕግ በላይ አድርገው በመቁጠር በሕዝብ ላይ ሲፈጽሙት የኖሩትን አሰቃቂ ግፍና በደል ፈጽሞ እንዳልነበረ በመቁጠር የአገራችን ታሪክ የሚያኮራና በጥሩ ነገሮች ብቻ የተሞላ እንደነበር አድርጎ ማቅረብ በዚያው መጠን ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ታሪካችን ብዙ ሊኮራባቸው የሚገቡ በጎ ገጽታዎች የነበሩትን ያህል በዚያው መጠን የአገራችን ታሪክ ቢያንስ ልንፀፀትበት የሚገባና አሁን ለምንገኝበት አገራዊ ችግሮችም አሉታዊ አስተዋፅኦ ያበረከተ በርካታ መጥፎ ገጽታዎችም እንደነበሩት አምኖ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ዋናው የዚህ ትውልድ ጥያቄ መሆን ያለበት በተመሳሳይ የታሪክ ሂደት ያለፉት ሌሎቹ የዓለም አገሮች በሂደት ችግሮቻቸውን ፈተው ሕዝባቸውንና አገራቸውን ለላቀ ሥልጣኔ ሲያበቁ እኛ ለምን ዛሬም በአለንበት እንረግጣለን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሞከር እንጂ በሁለት ጎራ ተከፍሎ በታሪክ ጉዳይ ላይ መካሰስ መሆን የለበትም፡፡

የእኛ አገር በርስ በርስ መናቆርና መገዳደል ሂደት ውስጥ ያለፈችውን ያህል ሌሎችም አገሮች በተመሳሳይ ምንአልባትም በባሰ የታሪክ ሂደት ውስጥ አልፈዋል፡፡ ነገር ግን በሌሎች አገሮች የሚገኙት ሕዝቦች አንዱ ሌላውን በኃይል ደምስሶ በመጨረስ ድሉን የመጨረሻ ማድረግ እንደማይቻል በመገንዘብ በመቻቻልና በእኩልነት መኖርን ሲመርጡ እኛ ግን ማንም በማንም ላይ ዘላቂ የሆነ የበላይነት ድል እንደማያገኝ ተገንዝበን የመጣላታችንን ሂደት አንድ ቦታ ላይ ልናቆመው አልቻልንም፡፡ ክርክራችን ማተኮር ያለበት እንደ ሌሎቹ ሕዝቦች ይህንን ጠባችንን የትና እንዴት እናቁመው? በሚለው ቁምነገር ላይ ነው እንጂ በተለመደውና ማንኛችንንም አሸናፊ በማያደርገን /self defeating/ ክርክር ላይ መሆን የለበትም፡፡ በታሪክ ጉዳይ መከራከር

ለምርምር ሰዎችም ጭምር አስቸጋሪ በመሆኑ አስቀድመን ላለመስማማት በተስማማን የፖለቲካ ሰዎች መካከል የሚደረገው የታሪክ ክርክር ጉንጭ አልፋ ከመሆን ያለፈ ፋይዳም አይኖረውም፡፡

የሚገርመው የኢትዮጵያን የፖለቲካ ኃይሎች የሚያጣላን የአገራችን የታሪክ ይዘት ብቻ ሳይሆን የአገራችን የታሪክ ዕድሜም ጭምር ነው፡፡ ሁለቱ የፖለቲካ ጎራዎች የራሳቸውን ፖለቲካዊ አጀንዳ ለማጠናከር ሲሉ የአገሪቱን ታሪክ በራሳቸው መንገድ ሊተረጉሙት እንደሚሞክሩ ከዚህ በላይ እንዳየነው ሁሉ የኢትዮጵያን የታሪክ ዕድሜ በተመለከተም ግልጽ የሆነ የአቋም ልዩነት ሲያራምዱ ይታያል፡፡ በአንድ በኩል ለብሔረሰቦች መብት ተቆርቋሪ ነን የሚሉትና የመገንጠልን መብት የሚደግፉት የፖለቲካ ኃይሎች የአገሪቱ ታሪክ የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ነው በማለት አምርረው የሚሚገቱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢትዮጵያ አንድነት የበለጠ ተቆርቋሪ ነን የሚሉት የፖለቲካ ኃይሎች የአገሪቱን ታሪክ የሦስት ሺህ ዘመን ዕድሜ ያለው ነው ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

የአገሪቱ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው ብለው የሚከራከሩት ኃይሎች ክርክራቸውን አሳማኝ ለማድረግ የሚሞክሩት አሁን የምንኖርባት ኢትዮጵያ የወቅቱን ቅርፅና ይዘት ያገኘችው አጼ ሚኒሊክ ወደ ደቡብ የመስፋፋት ዘመቻ አድርገው ከዚያ በፊት በነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ቁጥጥር ሥር ያልነበሩትን ሕዝቦች ወደ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ካጠቃለሉ በኋላ ነው የሚል ነው፡፡ በዚህ የመከራከሪያ ሐሳብ ውስጥ የተካተቱት ነጥቦች በራሳቸው ውሸት ወይም ስህተት አይደሉም፡፡ እንዲያውም በራሳቸው ይዘት ብቻ ሲመዘኑ ጥሬ ሃቆች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ችግር የሚፈጠረው ወይም እውነትነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባው ይህ እውነታ በራሱ የአገሪቱን የዕድሜ መጠን የሚያረጋግጥ ወይም የሚወስን ተደርጎ ሲቀመጥ ነው፡፡

ምክንያቱም ከሌሎች የረዥም ጊዜ ታሪክ ካላቸው አገሮችም ሆነ ከራሳችን አገር ታሪክ እንደምንረዳው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አንድ ወጥ ቅርጽና ይዘት ይዞ የኖረ አገርና መንግሥት የለም፡፡ የአንድ አገር ምሥረታ ሂደት ከአንድ ጠባብ አካባቢ ተጀምሮ በሂደት እየሰፋ የሚሄድ፣ መስፋፋቱ ችግር ሲያጋጥመው ደግሞ በአለበት ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ወይም እንደገና እየጠበበ የሚመጣ እንጂ ሲጀመር በነበረበት ፀንቶ ለዘለዓለም የሚኖር አይደለም፡፡ ለምሳሌ የጣሊያን የመጨረሻው ውኅደት የተፈጸመው በ1871 ቢሆንም ጣሊያኖች ስለታሪካቸው ሲጽፉና ሲናገሩ ከጥንቱ የሮማን ኢምፓየር እንጂ ከ1871 ጀምረው አይደለም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ቱርክ የወቅቱን ቅርጿን የያዘችው ከአንደኛው ዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ቢሆንም የጥንቱን የኦቶማን ኤምፓዬር ዘመንም የታሪኳ አካል አድርጋ ነው የምታዬው፡፡ ይህ የታሪክ ሂደት በማንኛውም

የአገር ምሥረታ ሂደት ውስጥ ባለፈ አገር የተከሰተ ቢሆንም በተለይ ኢትዮጵያ በረዥም ዘመን ታሪኳ ባሳለፈችው ውጣ ውረድ ስትጠብና ስትሰፋ የኖረች አገር ነች።

ስለዚህ ከዚህ ለሺህ ዓመታት ሲፈራረቅ ከኖረ የአገር የስፋት መጠን ውስጥ ለራስ የፖለቲካ አጀንዳ የሚጠቅመውን ከአጼ ምኒሊክ መስፋፋት በኋላ ያለውን አንድ ቁንፅል ወቅት ብቻ ወስዶ የኢትዮጵያ ዕድሜ በዚህ ይወሰናል ማለት አሳማኝ መከራከሪያ አይሆንም። እንዲህ ዓይነቱ ጠባብ መከራከሪያ አሳማኝ ነው ከተባለ የኢትዮጵያ ዕድሜ መቶ ዓመት ነው የሚለው ክርክር ትክክል የማይሆንበትን አንድ የቅርብ ጊዜ ግልጽ ምሣሌ ማቅረብ ይቻላል። ይኸውም በአሁኑ ወቅት (በ2002) የምንኖርባት ኢትዮጵያ በ1983 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከመገንጠሏ በፊት ከነበረችው ኢትዮጵያ የጠበበች አገር ነች። ስለዚህ ይህንን አገሪቱ ውስጥ በአንድ የታሪክ አጋጣሚ የተከሰተን ለውጥ በቁንፅል ወስደን እንጠቀምበት ካልን የኢትዮጵያ ዕድሜ ዐሥራ ስምንት ዓመት እንጂ መቶ ዓመት አይሞላም ማለት ነው። በተለይም ይህንን አስተሳሰብ የበለጠ በከረረ ሁኔታ ሲያጠነጥኑት የሚታዩት ለኦሮሞ ሕዝብ መገንጠል እንታገላለን የሚሉ አንዳንድ ኃይሎች መሆናቸው ሲታይ ጉዳዩ ሌላም ክርክር ሊያሥነሣ ይችላል። ይኸውም ይህ ዓይነቱ የክርክር ሎጅክ የአንድን አገር ዕድሜ ለመወሰን የሚሠራ ከሆነ ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት በፊት ወደነበረችበት ሁኔታ ትመለስ ሲባል፣ በተመሳሳይ የክርክር ሎጅክ የኦሮሞ ሕዝብም ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ወደነበረበት ሁኔታ ይመለስ ቢባል እየቀረበ ያለው መከራከሪያ በምንም ዓይነት ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የማይገባውን የኦሮሞ ሕዝብ ህልውና ጭምር ያላግባብ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ እንደሚሆን መጤን ነበረበት።

ምክንያቱም በኢትዮጵያ ታሪክ በአጭር ጊዜ የሕዝብ የመስፋፋት እንቅስቃሴ እንደ ኦሮሞ ሕዝብ ብዙ የራሳቸው ማንነት የነበራቸውን ሕዝቦች ውጦ ሰፊ ግዛትን መቆጣጠር የቻለ ሕዝብ የለም። ያለፈውን ታሪክ እያነሱ መዎቃቀስና ሂሣብ ማዎራረድ አስፈላጊ ነው ከተባለ በኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴ የተገፉና የጠበቡ ብቻ ሳይሆን ህልውናቸውን ያጡ ብሔረሰቦች በቁጥር ቀላል አይደሉም። ኢትዮጵያ ከመቶም ሆነ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት ወደ ነበረችበት ሁኔታ ትመለስ የሚል ክርክር ማንሣት ትርጉም የለሽ የሚሆነውም የኢትዮጵያ ሁኔታ የኦሮሞን ሕዝብ የመስፋፋት እንቅስቃሴ ጨምሮ በተለያዩ ታሪካዊ መስተጋብሮች ወደኋላ ሊመለስ በማይችል መጠን እየተለወጠ የመጣ በመሆኑ ነው። ሌላው ቀርቶ በቅርቡ በደርግና በኢህአዴግ ዘመን ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰቱት አንዳንድ ለውጦች ወደድናቸውም ጠላናቸውም መልሰው በማይለዎጡበት ደረጃ የታሪካችን አካል ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ "ወደ ነበርንበት እንመለስ" የሚል ክርክር መቋጫ ወደሌለው ሌላ ክርክር እያስገባን የሚሄድና

ችግራችንን የበለጠ የሚያወሳስብ እንጂ አገራችን አሁን ላለችበት ችግር መፍትሄ እንደማይሆን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

ይህ "ወደ ነበርንበት እንመለስ" የሚለው ክርክር አስቸጋሪ የሚሆነው ከኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ አኳያ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የአገሪቱ ብሔር-ብሔረሰቦች ታሪክ ጋርም የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ ከ16ኛው ክፍለ-ዘመን በፊት በኢትዮጵያ አሁን በሚታየው ቅርጽና ይዘት በኦሮሞነት የሚታወቅ ሕዝብ ያልነበረውን ያህል በሰሜኑ የአገራችን ክፍልም ወደ አገሪቱ የኋላ ታሪክ ራቅ ብለን ስንመለስ በአንድ የታሪክ ወቅት የአገው ሕዝብ እንጂ አማራም ሆነ ትግሬ በመባል የሚታወቅ ሕዝብ አልነበረም፡፡ ልዩነቱ የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው እንጂ በኢትዮጵያ አንድ የተለየ ብሔረሰብ እኔ ከሌላው የበለጥኩ ኢትዮጵያዊ ነኝ ሊል የሚችልበት የታሪክ መሠረት የለም፡፡

የኢትዮጵያን ዕድሜ በመቶ ዓመት በመገደብ ረገድ ኢህአዴግም ቀደም ሲል ከእነ ኦነግ ጋር ተመሳሳይ አቋም እንደነበረው በግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም እንዴትና ለምን አቋሙን እንደለወጠ እስካሁን ባይነግረንም መሪዎቹ በቅርቡ የአገሪቱ የሚሊኒየም በዓል ሲከበር ከአንድ መቶ ዓመት በፊት የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ በየንግግራቸው እያጣቀሱ በድፍረት መናገር በመጀመራቸው በዚህ ረገድ ኢህአዴግ አቋሙን በትክክል እየቀየረ መምጣቱን መረዳት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ የኢህአዴግ የአቋም ለውጥ በተድበሰበሰ መልኩ ብቻ ሳይሆን የበለጠ ግልጽ በሆነ መንገድ ተጠናክሮ ቢወጣ ሌሎች በዚህ ረገድ የተሳሳተ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎችም ወደ ትክክለኛው መንገድ እንዲመጡ ወይም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባላስፈላጊ ውዝግብ ውስጥ እንዳይቀጥል ሊያግዝ በቻለ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ለኢትዮጵያ አንድነት የበለጠ ተቆርቋሪ ነኝ የሚለው የፖለቲካ ኃይል የኢትዮጵያ ታሪክ የሦስት ሺ ዓመት ዕድሜ አለው በማለት የሚያራምደው አቋም አንዳንድ የአቀራረብ ችግሮች ያሉበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጠቃላይ ይዘቱ ግን ስህተት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የመጀመሪያው የአቀራረብ ስህተት በተለምዶ "ሦስት ሺ ዘመን" እየተባለ የሚጠቀሰው ቁጥር በየትኛውም የአገሪቱ የታሪክ መረጃ ላይ ቃል በቃል ተጠቅሶ የማይገኝ በመሆኑ ግልጽ የሆነ የአቀራረብ ስህተት አለበት ሊባል ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ የአገር ምሥረታ ሂደት ከተጀመረ ከሦስት ሺም በላይ የሚቆጠሩ ዓመታትን እንዳስቆጠረ የሚያረጋግጡ በውስጥም ሆነ በውጭ የተገኙ በታሪክ ተቀባይነት ያገኙ መረጃዎች አሉ፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ በሺ ዓመታት የሚቆጠር ዕድሜ ያለው ስለመሆኑ ርግጠኛ ሆኖ መከራከር ይገባል እንጂ በተለምዶ ቁርጥ ባለ ሁኔታ ሦስት ሺ እየተባለ የሚጠቀሰው ቁጥር ተገቢ አቀራረብ አይሆንም፡፡

ሁለተኛው የአቀራረብ ስህተት የአገሪቱን ታሪክ የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለው ነው ብለው የሚያምኑትን የፖለቲካ ኃይሎች የምናይበት መንገድ ነው። እንዲህ ዓይነት አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎችን በሐሳብና በመረጃ ተከራክሮ ለማሳመን መሞከር ሲገባ አስተያየቱን የሚያቀርቡትን የፖለቲካ ኃይሎች አገር አፍራሽና ከሃዲ አድርጎ ለማቅረብ የሚደረገው ሙከራ ክርክሩን የበለጠ አቅጣጫ እያሳተውና እያወሳሰበው የመጣ መሠረታዊ የአቀራረብ ስህተት ነው። ሲቻል ተከራክሮ መተማመን፣ ሳይቻል ደግሞ በልዩነት ተከባብሮ መኖር ሲቻል ከኛ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ኃይሎች በደፈናው እያንኳሰስንና እያራከስን ለማየት መሞከር በአገራችን እንዲፈጠር ለምንፈልገው ብሔራዊ መግባባት የሚያግዘን አይሆንም። በአጠቃላይ በታሪክ ትንታኔ ዙሪያ የሚኖረን ልዩነት ተገቢና ወደፊትም የሚቀጥል ቢሆንም ቢያንስ ግን ታሪካችን የጥሩና የመጥፎ ገጽታዎች ድብልቅ መሆኑን፣ የአገር ግንባታችን ሂደትም በሺ የሚቆጠር ዓመታት ዕድሜ ያለው መሆኑንና በአጠቃላይም በአገራችን አንዱ ወገን በሌላው ላይ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ በሚያደረገው ሙከራ ብዙ ግጭቶችና የጭቆና ሂደቶች እንደነበሩና ከዚህ ጐን ለጐንም ኢትዮጵያውያን በሰላም ጊዜ በፍቅርና በአንድነት አብሮ የመኖርና የውጭ ወራሪ በሚመጣበት ወቅት በጋራ ቆመን ጣላትን በመመከት ያዳበርናቸው የጋራ እሴቶች እንዳሉንና ይህም መጥፎ የታሪክ ገጽታችን በማረምና መልካሙን ገጽታ በማጠናከር ለመጭው ትውልድ አንድ ጠንካራ አንድነትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሰፈነባትን አገር ማስረከብ እንደሚያስችለን መተማመን ብንችል በአገራችን ብሔራዊ መግባባትን ለመፍጠር የሚያግዘን አንድ በጎ ርምጃ ይሆናል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ የመካከለኛው ምሥራቅ ብሂልን ጠቅሰን ብናልፍ ትምህርት ሊሰጠን ይችል ይሆናል። ይኸውም ሁለት በበርሃ ጉዞ ላይ የተገናኙ ጓደኛሞች ወደ አንድ ሩቅ ቦታ በመሄድ ላይ እያሉ በመካከላቸው ድንገት አለመግባባት ይፈጠርና ይጣላሉ። በዚህ ጊዜ ትዕግስቱን መቆጣጠር ያልቻለው ሰው ጓደኛውን ክፉኛ በጥፊ ይመታዋል። የተመታው ሰው ጥፊው ቢያመውም ስሜቱን እንደምንም ተቆጣጥሮ በዝምታ ጉዞውን መቀጠል ይመርጣል። ትንሽ እንደተጓዙም መንገዳቸው ላይ ባገኘው የበርሃ አሸዋ ላይ ጐንበስ ብሎ "ዛሬ ጓደኛዬ ክፉኛ በጥፊ መታኝ" በማለት ይጽፍና ጉዞውን ከጓደኛው ጋር አብሮ ይቀጥላል። በዚያ የበርሃ ጉዞ ላይ እንዳሉም ድንገት ባህር ያገኙና ውሃ ጠጥተው ጥማቸውን ካረኩ በኋላ ባህሩ ውስጥ ገብተው ገላቸውን መታጠብ ይጀምራሉ። እየታጠቡ እያለ ቀደም ሲል በጓደኛው በጥፊ የተመታው ሰው በድንገት ባህሩ ውስጥ ይሰምጣል። በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል የመታው ጓደኛው እንደምንም ጠልቆ በመዋኘት ከባህሩ አውጥቶ ሕይወቱን አተረፈውና ጉዞአቸውን መቀጠል ቻሉ። ትንሽ እንደተጓዙም ከሞት የተረፈው ሰው በአካባቢው አሸዋ ሳይሆን አለት ድንጋይ ፈልጐ አገኘና

አለቱን በመውቀር “ዛሬ ጓደኛየ ህይወቴን ከሞት አተረፋት” በማለት ይጽፋል፡፡ በዚህን ጊዜ ቀደም ሲል በጥፊ የመታውና በኋላ ላይ ደግሞ ከሞት ያተረፈው ጓደኛው “ቅድም በጥፊ መታኝ ብለህ በአሸዋ ላይ ነበር የጻፍከው፣ አሁን ደግሞ ህይወቴን አተረፈኝ ብለህ በአለት ላይ ነው የጻፍከው - ለምንድነው?” ብሎ በመገረም ጠየቀው፡፡ ጓደኛውም ሲመልስ “በባህላችን ሰዎች ክፉ ነገር ሲፈጽሙብን ድንገት የይቅርታ ነፋስ መጥቶ እንዲያጠፋው በማሰብ ድርጊቱን የምንጽፈው በአሸዋ ላይ ነው፡፡ ሰዎች በጎ ነገር ሲሠሩልን ግን ድርጊቱን ለዘለዓለም እንዳንረሳው በማሰብ በአለት ላይ ነው የምንጽፈው” በማለት መለሰለት ይባላል፡፡ ኢትዮጵያውያን ያለፈ ታሪካችንን በተመለከተ ብሂሉን በአርአያነት ብንጠቀምበት ተጠቃሚ ሊያደርገን ይችል ይሆናል፡፡

### 1.3.2. ሕገ-መንግሥቱን በተመለከተ የምናራምደው አቋም

በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርበት የሚገባ፣ ነገር ግን እስካሁን ዋና የልዩነት ማዕከል ሆኖ የቀጠለው ሌላው ጉዳይ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት በሚመለከት ፓርቲዎች የምናራምደው የተለያዩና የከረረ አቋም ነው፡፡ ልዩነት ሲባል ሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በተካተቱት የተለያዩ አንቀጾች ያሉንን ልዩነቶች ማለት ሳይሆን በጥቅሉ ሕገ-መንግሥቱን እንደ አንድ የአገር ሰነድ የምናይበትን መንገድ ለማለት ነው፡፡ ሕገ-መንግሥታዊ በሆኑ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ስለ አለን ልዩነትና አንድነት ራሱን ችሎ በሌላ ክፍል ስለሚቀርብ አሁን አናነሣውም፡፡

የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት በሚመለከት በአሁኑ ወቅት ሦስት ዓይነት አመለካከት ሲራመድ ይስተዋላል፡፡ የመጀመሪያው ከኢህአዴግ በኩል የሚነሣ ሲሆን ይኸውም ማንኛውም ተቃዋሚ ፓርቲ ሕገ-መንግሥቱን አምኖ መቀበል፣ ማክበርና በሕገ-መንግሥቱም መገዛት አለበት የሚል ዓይነት አመለካከት ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ በሕዝቡ በጎ ፈቃድ ተረቆ የጸደቀ የአገሪቱ የበላይ ሕግ ነው ከሚል አስተሳሰብ በመነሣትም ኢህአዴግ ሕገ-መንግሥቱን የሚቃወሙ ኃይሎችን እንደ ወንጀለኛ ቆጥሮ ሲያወግዝ በተደጋጋሚ ይደመጣል፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የኢህአዴግ አባላት ሕገ-መንግሥቱ የፖለቲካ ሰነድ መሆኑን በመዘንጋት ጭምር እንደ ሃይማኖታዊ ሰነድ እንዲመለክና ጨርሶ እንዳይተች የሚጠይቅ ዓይነት አቋም ሲያራምዱ ይደመጣሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለይም የትጥቅ ትግል ለማካሄድ የሚፈልጉና በውጭ አገራት በስደት የሚገኙ ፓርቲዎች “ሕገ-መንግሥቱ የወያኔ የፖለቲካ ፕሮግራም ቅጂ የሆነና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይፈቅድና ሳይመክርበት በግድ በላዩ ላይ የተጫነበት ሰነድ በመሆኑ በፍጹም አንቀበለውም” የሚል አቋም ያራምዳሉ፡፡

ከእነዚህ በሁለት ጫፍ ላይ የቆሙ ተቃራኒ አስተሳሰቦች በተለየ የሚቀርበው ሦስተኛው አመለካከት በኢዴፓና አሁን አሁን በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭምር እየተያዘ የመጣው አቋም ነው፡፡ ኢዴፓ ሕገ-መንግሥቱ በአረቃቀቁና በአጸዳደቁ ሂደት ከፍተኛ ችግሮች የነበሩበትና በይዘቱም ለአገሪቱ አንድነትና ኢኮኖሚያዊ እድገት የማይበጁ በርካታ አንቀጾች የተካተቱበት ሰነድ እንደሆነ ያምናል፡፡ ነገር ግን በየትኛውም አኳኋን ይሁን ይህ ሕገ-መንግሥት የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ሆኖ አንድ ጊዜ ከጸደቀና ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ሕገ-መንግሥቱን ሊያከብረውና ሊገዛበት ይገባል ብሎ ያምናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ "ማንኛውም ፓርቲም ሆነ ዜጋ ሕገ-መንግሥቱን የመተቸትና ከመተቸትም አልፎ በሕዝብ ውሣኔ እንዲሻሻል ማድረግ የሚያስችል ሰላማዊ ትግል የማድረግ መብት ጭምር አለው" ብሎ ያምናል፡፡

ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት ኢዴፓ የሚያራምደው ዓይነት የልዩነት አቋም በተለያዩ አገሮች በሚገኙ ፓርቲዎችም መካከል የሚኖርና የተለመደ ሲሆን በኢህአዴግና በሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የሚታየው ዓይነት በሁለት ጫፍ ላይ የቆመ የከረረ ልዩነት ማየት ግን ብዙም የተለመደ አይደለም፡፡ ሕገ-መንግሥትን በሚመለከት እንዲህ ዓይነት የከረረ ልዩነት ይዞም ብሄራዊ መግባባት መፍጠር የቻለ ነገር የለም፡፡ በእኛም አገር በሁሉም በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ በእኩል መጠን ዛሬም ሆነ ወደፊት ሙሉ በሙሉ መተማመን የማይቻል ቢሆንም ቢያንስ ለጊዜው ሕገ-መንግሥቱን በጥቅሉ እንዴት ልናየው እንደሚገባ፣ እንዴትስ ልዩነታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገ-መንግሥቱን ብሔራዊ መግባባት ሊያሳጣን በማይችል ደረጃ በጋራ ልንጠቀምበት እንደምንችል አንድ ዓይነት መግባባት ላይ ሳንደርስ ብሔራዊ መግባባት በአገራችን መፍጠር የሚቻል አይሆንም፡፡ ስለሆነም በሁለት የተካረረ ጫፍ ላይ የቆሙት እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች የሚያራምዱት ጽንፈኛ አቋም ምን ያህል በአገራችን ብሔራዊ መግባባት እንዳይፈጠር ምክንያት እንደሆነ በመገንዘብ ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት ምክንያታዊ አቋም ሊይዙ ይገባል፡፡

በዚህ ረገድ አቋሙን ፈትሾ ሊያስተካክል የሚገባው የመጀመሪያው አካል ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ነው፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን ሁልጊዜ የሚጠይቀን ሕገ-መንግሥቱን እንድናከብርና በሕገ-መንግሥቱም እንድንገዛ ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱን "እንድናምንበት" ጭምር ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱን ልታከብሩትና በሕገ-መንግሥቱም ልትገዙ ይገባል የሚለው የኢህአዴግ ጥያቄ ተገቢ ነው፡፡ በየትም አገር ሕግ ሳይከበርና ለሕግ ተገዥ ሳይሆኑ ስለ ሰላማዊ ትግልም ሆነ በአጠቃላይ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ማውራት አይቻልም፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ ሕገ-

መንግሥቱን እንድናምንበት እያቀረበልን ያለው ጥያቄ ትክክል አይደለም ብቻ ሳይሆን ከዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብም ጋር የሚጋጭ ወደ አምልኮ ያጋደለ አቋም ነው።

በመጀመሪያ አንድን ነገር “ማመን” ከመቀበልና ከመገዛት ጋር ሰፊ ልዩነት አለው። ከሕግ አንጻር የማያምኑበትን ነገር ማክበርም ሆነ በማያምኑበት ነገር መገዛት ይቻላል። ነገር ግን እምነት ከግላዊ የሰዎች የውስጥ አስተሳሰብ ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው ጉዳይ ስለሆነ ሰዎችን በሚያከብሩትና በሚገዙበት ነገር ሁሉ እንዲያምኑ ለማድረግ አይቻልም ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊም አይደለም። በተለምዶና በቀላል ትርጉሙ “እምነት” በአንድ ጉዳይ ላይ ሰዎች ያላቸውን የሐሳብ ስምምነት ለመግለጽም ጥቅም ላይ ሊውል ቢችልም፣ በእኛ አገርም ሆነ በሌሎች አገሮች የሕግና የፖለቲካ ተሞክሮ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ዜጎች በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የግድ ማመን አለባቸው ሊባል ግን አይችልም።

ዜጎች ማንኛውንም ነገር ሰላማዊ በሆነ መንገድ የመቃወም መብት ያላቸው መሆኑንም ራሱ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጧል። ተቃዋሚዎች በሕገ-መንግሥቱ የግድ ማመን አለባቸው የሚለው የኢህአዴግ ጥያቄ ስህተት ብቻ ሳይሆን ከዴሞክራሲም ሆነ ከራሱ ከሕገ-መንግሥቱ መንፈስ ጋር የሚቃረን ነው ሊባል የሚችለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ስለዚህ ኢህአዴግ በገዥ ፓርቲነቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-መንግሥቱን እንዲያከብሩትና እንዲገዙበት ማድረግ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገ-መንግሥቱን መተቸትና መቃወም ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግሥቱን ሰላማዊ በሆነና ራሱ ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው መንገድ ለማሻሻልም ሆነ ለመለወጥ ፓርቲዎች ያላቸውን መብት ሳያድበሰብስ መቀበል አለበት። ይህንን በግልጽ ማድረግ ሲችል ነው ሕገ-መንግሥቱን አክብሩት የሚለውም ግፊቱ ተቀባይነት የማግኘት ጉልበት የሚኖረው።

በአጠቃላይም ኢህአዴግ ራሱም ጭምር በየቀኑ ሲጥሰው የሚውለውን ሕገ-መንግሥት ትችትና ተቃውሞ ሊነሣበት የማይገባ ቅዱስ-መጽሐፍ ወይም ቅዱስ-ቁራን አድርጐ ከማቅረብ ይልቅ ሕገ-መንግሥቱ በሰዎች የተጻፈ ሰነድ እንደ መሆኑ መጠን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ሊሻሻል የሚገባው ሰነድ መሆኑን አባላቱንና ደጋፊዎቹን ማስተማር ይጠበቅበታል። ኢህአዴግ ከዛሬ ዐሥራ አምስት ዓመት በፊት የሥልጣን ዘመኑን እንዴት አድርጐ አስጠብቆ ሊቀጥል እንደሚችል እየተጨነቀ በነበረበትና የአገሪቱን ውስብስብ ችግሮች እንደዛሬው ለረዥም ጊዜ መንግሥት ሆኖ ባላዬበት ወቅት ያረቀቀውን ሕገ-መንግሥት ዛሬ አጽድቆት ቢሆን ኖሮ በቅርጽም ሆነ በይዘት ምን ያህል የተለየ ሕገ-መንግሥት ሊሆን ይችል እንደነበረ ከኢህአዴግ አመራሮች በላይ ሊገነዘብ የሚችል ሰው ይኖራል ተብሎ

አይገመትም፡፡ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት እያሰበው እንደሚገኘው ለረዥም ጊዜ በኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ የሚቀጥል ከሆነም ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ጉዳይ አስፈላጊ መሆኑ የበለጠ ግልጽ እየሆነለት የሚመጣው ለራሱ ለኢህአዴግ ስለሆነ ሕገ-መንግሥቱ ወደፊት ሊሻሻል እንደሚችል የደጋፊዎቹን አስተሳሰብ ከወዲሁ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አቋማቸውን ፈትሸው መቀዬር የሚገባቸው “ለሕገ-መንግሥቱ ዕውቅና አንሰጥም፣ ልንገዛበትም አይገባም” የሚሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የወቅቱን የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት “ልናከብረውም-ልንገዛበትም አይገባም” በማለት ለያዙት አቋም የሚያቀርቡት ዋና መከራከሪያ ነጥብ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ሕገ-መንግሥቱ ሲረቀቅም ሆነ ሲጸድቅ ሕዝቡ ያልመከረበትና የኢህአዴግ ፕሮግራም ግልባጭ ነው የሚል ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱን ሕዝብ አልመከረበትም የሚለውን የተቃዋሚዎች መከራከሪያ ኢህአዴግ እስካሁን ፈጽሞ የማይቀበለው ቢሆንም ያለ ምክንያት የሚቀርብ መከራከሪያ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ በወቅቱ የሕገ-መንግሥቱ ረቂቅ በተለያዩ መድረኮች ለሕዝብ ውይይት የቀረበና በመጨረሻም በሕዝብ የተመረጠ ነው በተባለ የሕገ-መንግሥት አጽዳቂ ጉባኤ የጸደቀ ቢሆንም ሂደቱ በአገራችን በደርግ ጊዜ ይደረግ እንደነበረውና በሌሎች የአፍሪካ አገሮች እንደሚካሄደውም ለይስሙላ ተብሎ የተደረገ ስለመሆኑ የፖለቲካ ሀሁ ለሚገባው ማንኛውም ሰው አጠራጣሪ አልነበረም፡፡

በዚያን ወቅት ኢህአዴግ ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት እንኳን ነፃ የሕዝብ ሐሳብ ሊቀበልና ሕገ-መንግሥቱን እንዲያረቁ ራሱ የሾማቸውን እንደነ አቶ ክፍሌ ወዳጆ ያሉትን ሰዎች ሐሳብ ወይም ምክር እንኳ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ በነገራችን ላይ አቶ ክፍሌ ወዳጆ የሕገ-መንግሥቱን አጠቃላይ ይዘት የሚያደንቁና የሚደግፉ ሰው የነበሩ ቢሆንም አንቀጽ 39ን በተመለከተ ግን የጠነከረ ቅሬታ እንደነበራቸው በድፍረት ይናገሩ ነበር፡፡ የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘትም ምን ያህል ከኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራም ጋር በተግባር እንዲጣጣም ተደርጐ መቀረፁ ሲታይም ሕገ-መንግሥቱን የሕዝብ ውይይት ውጤት እንደሆነ አድርጐ መከራከር ደረቅ የፖለቲካ ክርክር ከመሆን አልፎ ማንንም ሊያሳምን አይችልም፡፡

ነገር ግን ሕገ-መንግሥቱን ሕዝብ በአግባቡ እንዳልተወያዬበትና የኢህአዴግ የፖለቲካ ፕሮግራም ግልባጭ ስለመሆኑ የቱንም ያህል አሳማኝ መከራከሪያ ቢኖርም በአሁኑ ወቅት ሕገ-መንግሥቱን ላለማክበርና በሕገ-መንግሥቱ ላለመገዛት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ አንድ ኅብረተሰብ ወይም ዜጋ ሕግን የሚያከብረውና ለሕግ ተገዥ የሚሆነው ሕጉን በማርቀቅ ሂደት ስለተሳተፈ ወይም የሕጉን ይዘት ስለሚያምንበት አይደለም፡፡ በእኛ አገርም ሆነ በሌላው ዓለም

ሕዝብ ለሕግ ተገዥ ሆኖ መኖር የጀመረው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ከመጀመሩና ሕግ ከላይ ወደታች ከገዥዎች ለተገዥዎች ይሰጥበት ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ እ.ኤ.አ ከ1931 ጀምሮ በአገራችን የተፈራረቁት ሁሉም ሕገ-መንግሥቶች ሕዝብ ያልመከረባቸውና የሕዝብ ፍላጐት ሳይሆን የየሥርዓቱ ርእዮት መገለጫ የነበሩ ናቸው፡፡ በዚያ ሁሉ ሂደት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕግን አክባሪና የሕግ ተገዥ ሆኖ ነው የኖረው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ከኢህአዴግ ወደ ሥልጣን መምጣት በፊት ሕገ-መንግሥት የነበራት አገር መሆኗን የማንጠራጠር እስከሆነ ድረስ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለውን ሕገ-መንግሥት ዕውቅና የምንነሳበት አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፡፡

ይልቁንም የወቅቱን ሕገ-መንግሥት በጭፍን ዕውቅና በመንፈግ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች የሚፈልጉት ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ ነው እያለ በተደጋጋሚ የሚያቀርብብን ክስ የበለጠ እንዲጠናከርና ተቃዋሚዎችን የማፈኛ ሰበብ እንዲሆነው ዕድል ከመስጠት ይልቅ ተቃዋሚዎች ከእነድክመቶቹና ስህተቶቹ ጭምር ለሕገ-መንግሥቱ ዕውቅና ሰጥተን ኢህአዴግ ራሱ ለአረቀቀውና ላጸደቀው ሕገ-መንግሥት እንኳ ምን ያህል በተግባር ተገዥ እንዳልሆነ ተጨባጭ መረጃዎችን ለሕዝብ እያቀረብን በመታገል ሕገ-መንግሥቱን ለራሳችን የትግል መሣሪያነት ልንጠቀምበት ብንችል የተሻለ የብልህነት ስልት በሆነ ነበር፡፡ ይህንን ማድረግ ባለመቻላችን ግን ኢህአዴግ ሁልጊዜ ራሱን እንደ ሕግ አስከባሪ፣ ተቃዋሚውን ጉራ ደግሞ እንደ ሕገ-ወጥ አካል አድርጐ በማቅረብ ለሚፈጽመው የአፈና ድርጊት አሳማኝ ምክንያት አድርጐ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡

ሌላው ሕገ-መንግሥቱን በተመለከተ የከረረ አቋም የያዙትን ተቃዋሚዎች አስተሳሰብ ደካማ የሚያደርገው ነጥብ "ሕገ-መንግሥቱ ሆን ተብሎ አገሪቱን ለማፈራረስ የጸደቀ ሰነድ ስለሆነ ተቀዶ ሊጣል ይገባዋል" የሚለው መከራከሪያ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ መከራከሪያ አንደኛ ሌሎች ለአገር መፍረስ ምክንያት የሚሆኑ ግባቶች እስካልተከሰቱ ድረስ አዲስ ሕገ-መንግሥት በመጻፍ ብቻ አንድን አገር በቀላሉ ማፈራረስ የማይቻል መሆኑን፣ ሁለተኛ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው በርካታ በጎ አንቀጾች የተካተቱበት መሆኑን፣ ሦስተኛ ሕገ-መንግሥቱ ተቀዶ መጣል አለበት የሚለው አስተሳሰብ ኢትዮጵያውያን ባለው ላይ ከመገንባት ይልቅ ሁልጊዜ የነበረውን እያፈረስን ከዜሮ የመጀመር በሽታ ዛሬም ያለቀቀን መሆኑን የሚያሳይ አቋም በመሆኑ ኢህአዴግ "ተቃዋሚዎች በጭፍን እኔን ከመቃወም ያለፈ ሌላ አማራጭ የላቸውም" እያለ የሚያቀርበውን ክስ የበለጠ የሚያጠናክር ሆኖ እያገለገለ ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ አገር አፍራሽ ነው የሚለውን መከራከሪያ ለማጠናከር በብዙዎች ዘንድ አብዛኛውን ጊዜ በምሳሌነት የሚቀርበውን አንቀጽ 39ን በራሱ ለይቶ በማውጣት በአግባቡ

መተቸት ሲቻል ብዙ በጎ ነገሮችን ጭምር አካቶ የያዘውንና የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጐበት ሊቀጥል የሚችለውን ሕገ-መንግሥት በጥቅሉ ዕውቅና መንፈግና ማውገዝ ለብሔራዊ መግባባት መፈጠር ትልቅ እንቅፋት በመሆኑ ሊስተካከል የሚገባው አቋም ነው፡፡ በተጨማሪም እንደኛ ዓይነት ከፍተኛ የብሔራዊ መግባባት ችግር ባለበት አገር ወደፊትም ቢሆን ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚያስማማና የሚያግባባ አዲስ ሕገ-መንግሥት በአንድ ጊዜ ማግኘት ይቻላል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡

ስለሆነም ሕገ-መንግሥቱን በተመለከተ በሁለት ጫፍ ላይ የከረረ አቋም ይዘው የሚገኙት ኢህአዴግና ሌሎች ተቃዋሚዎች የያዙት አቋም ለራስም ሆነ ለአገር ጥቅም የማያዛልቅ መሆኑን በማመን ኢዴፓ የሚያራምደው አስታራቂና ምክንያታዊ አቋም ላይ በመገናኘት ሕገ-መንግሥቱን የቅራኔ ሳይሆን የብሔራዊ መግባባት ማዕከል ሊያደርጉት ይገባል፡፡

1.3.3 ብሔራዊ ሠንደቅ ዓላማ፣ ብሔራዊ መዝሙር፣ አገራዊ ካርታና ርእሰ ከተማ

ከላይ የዚህ ክፍል መንደርደሪያ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው መቸም እንደ እኛ አገር ብሔራዊ መግባባት የጠፋበት ሌላ አገር አለ ማለት አይቻልም፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ ሌላ የጠለቀ ምርምር ውስጥ መግባትም አያስፈልግም፡፡ በየትኛውም አገር የልዩነት አጀንዳ ሊሆኑ በማይችሉና በማይገባቸው የሠንደቅ ዓላማ፣ የብሔራዊ መዝሙር፣ የአገር ካርታና የርእሰ ከተማ ስያሜን በመሳሰሉ ጉዳዮች ሳይቀር በመካከላችን ምን ያህል ልዩነት እንዳለ በማየት ከብሔራዊ መግባባት ያለንን ርቀት በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን የሚወድ በመሆኑ የአገሩ መለያ ዓርማ የሆነውን ሠንደቅ ዓላማውን ከልቡ ይወዳል፡፡ በአምልኮ ቦታ፣ በሠርግ፣ በለቅሶ፣ በስፖርት ሜዳ፣ በተለያዩ አልባሳትና ጌጣጌጦች ላይ ሠንደቅ ዓላማችንን ማየት የተለመደው ያለ ምክንያት ሳይሆን ሕዝቡ ለአገሩ ካለው ልባዊ ፍቅር በመነጨ ነው፡፡ እንዲያውም የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ የ9/11 የሽብር ጥቃት በተፈጸመ ሰሞን አሜሪካን አገር ሄጀ ሕዝቡ ለሠንደቅ ዓላማው ያለውን ከፍተኛ ፍቅር ከማየቴ በፊት እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ለሠንደቅ ዓላማ ልዩ ፍቅር ያለው ሌላ ሕዝብ በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም ነበር፡፡ የሠንደቅ ዓላማ ፍቅር እንዲሁ ቀለምን ወይም ጨርቅን የማፍቀር ጉዳይ ሳይሆን ከአገር ፍቅር ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ያለው በመሆኑ የበለጠ መጠናከር የሚገባው ቁም ነገር ነው፡፡

ሠንደቅ ዓላማ የሌለው አገርና ሕዝብ በዓለም የሌለ ቢሆንም የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ግን ልዩ ታሪካዊ ማንነት ያለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ነፃነትዋን አስጠብቃ

ለመኖር የቻለች ብቸኛ አገር በመሆንዋ ምክንያት ሠንደቅ ዓላማዋ ከራስዋም አልፎ የፓን አፍሪካ መለያ ተደርጐ የሚታይ ነው። በዚህም ምክንያት ቶጐን፣ ሴኔጋልን፣ ጋናንና ማሊን የመሳሰሉ በርካታ የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን ሲያገኙ የቀለማቱን አቀማመጥ በመቀያየር የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ በመነሻነት የተጠቀሙበት ሲሆን በርካታ የጃማይካ ዜጐችና የሬጌ አቀንቃኞችም የኢትዮጵያን ሠንደቅ ዓላማ የአፍሪካ ብቻ ሳይሆን የመላው ጥቁር ሕዝብ ዓርማ አድርገው ሲጠቀሙበት ይታያል። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ድሮም ሆነ ዛሬ ለሠንደቅ ዓላማ ያለን ፍቅር ጠንካራ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የአገሪቱን ሠንደቅ ዓላማ በሚመለከት በመካከላችን በፈጠርነው ተገቢ ያልሆነ ልዩነት ለሠንደቅ ዓላማ ያለንን ፍቅር እየጐዳነው እንገኛለን።

ኢህአዴግ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ በሆነው ሠንደቅ ዓላማ መሃል ላይ ጨረር ያለው የኮኮብ ዓርማ (አሽሚጣጮች አንባሻ ይሉታል) ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች አገር መሆኗን እንዲወክል በማሰብ በመጨመሩ ምክንያት በሕዝቡ ውስጥ አለመግባባት ተፈጥሯል። የኢህአዴግ ደጋፊ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል በሠንደቅ ዓላማው ላይ የተቀመጠውን ተጨማሪ ዓርማ በጸጋ የተቀበለው ቢሆንም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ግን ተጨማሪውን ዓርማ ከልቡ አልተቀበለውም። በዚህም ምክንያት በቅርቡ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እስከተሰጠበትና ጉዳዩን የሚመለከት አዋጅ እስካወጣበት ጊዜ ድረስ በአገራችን ኮከቡ ያለበትንና ኮከቡ የሌለበትን ሁለት ዓይነት ሠንደቅ ዓላማ ማየት የተለመደ ሆኖ ቆይቷል። ኮከቡ ያለበትን ሠንደቅ ዓላማ የሚጠቀሙ ሰዎችን እንደ ሥርዓቱ ደጋፊዎች፣ ልሙጡን ሠንደቅ ዓላማ የሚጠቀሙ ሰዎችን ደግሞ እንደ ሥርዓቱ ተቃዋሚዎች አድርጐ በቀላሉ መፈረጅም የተለመደ ሆኗል። በዚህ ምክንያት መንግሥት ኮከቡ የሌለበትን ሠንደቅ ዓላማ መጠቀም ሕገ-ወጥነት እንደሆነና ቅጣትም እንደሚያስከትል አዋጅ ጭምር ለማውጣት ሲገደድ ታይቷል።

ኢህአዴግ ሕዝቡ ምን ያህል ለሠንደቅ ዓላማው ቀናኢ እንደሆነና በተለይም ኢህአዴግ አገሪቱን እንደተቆጣጠረ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ስለ ሠንደቅ ዓላማው በሰጡት አስተያየት ሕዝቡ ምን ያህል ቅሬታ ተሰምቶት እንደነበረና ተቃዋሚዎችም ጉዳዩን ከመጠን በላይ በማራገብ እየተጠቀሙበት መሆኑን እያወቀ አዲስ ዓርማ ሠንደቅ ዓላማው ላይ ባይጨምር የተሻለ በሆነ ነበር። በርግጥም ሠንደቅ ዓላማው ላይ ተጨማሪ ዓርማ ማስፈለጉ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ትርጉም ያለው ፋይዳ ቢኖረው ኖሮ ለውጥ መደረጉ ባልከፋ ነበር። ነገር ግን ኢህአዴግ ባለጨረሩን ኮከብ የአገሪቱ ሠንደቅ ዓላማ ላይ እንዲቀመጥ ያደረግሁት አገሪቱ የብዙ

ኪዮፓ ኪዮፓ ኪዮፓ

ብሔር-ብሔረሰቦች አገር መሆኗን ለማሳየት ነው ቢልም፤ ባለጨረሩ ኮከብ እንዴትና በምን ሁኔታ የብዙ ብሔር-ብሔረሰቦችን መኖር ይወክላል ሊባል እንደሚችል ግን ግልጽነት የለውም፡፡

ስለዚህ በሠንደቅ ዓላማው ላይ ተጨማሪ ዓርማ ማስቀመጡ በተወሰነም ደረጃ ቢሆን የሕዝብ ቅሬታ የሚፈጥር መሆኑ ከታወቀና ዓርማውም ይወክላል የተባለውን ጉዳይ ግልጽና አሻሚ በሆነ መጠን የሚወክል ሆኖ ካልተገኘ በወቅቱ ሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ ጥያቄ አንስቶበት የማያውቀውን አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሠንደቅ ዓላማ እንዳለ ይዞ መቀጠል የተሻለ በሆነ ነበር፡፡ እንዲያውም የነበረውን ይዞ መቀጠል የሚፈጥረው ችግር እስከ ሌለ ድረስ ውሳኔው የአገሪቱ ሠንደቅ ዓላማ ጉዳይ አዲስ መንግሥት በመጣ ቁጥር የማይለዋወጥ ቋሚ የሕዝብ ዓርማ ሆኖ እንዲቀጥል አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችል ነበር እንጂ ሌላ ጉዳት አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም በሠንደቅ ዓላማችን ላይ የሚቀመጠው ዓርማ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ያለማቋረጥ ሲለዋወጥ የኖረ ነው፡፡ እንዲያውም ከአፄ ምኒሊክ ዘመን በኋላ የሠንደቅ ዓላማችን አቀማመጥ ከቀይ -ቢጫ -አረንጓዴ ወደ ዛሬው አረንጓዴ -ቢጫ -ቀይነት ተቀይሯል፡፡

በኢህአዴግ ዘመን የተደረገው ለውጥም አስፈላጊ ያልነበረና የብዙዎችን ስሜት የጐዳ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያትም ቢሆን ኮከብ የተቀመጠበት ሠንደቅ ዓላማ አንድ ጊዜ የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ መሆኑ የሕገ-መንግሥት አካል ሆኖ ከታወጀ በኋላ ለሠንደቅ ዓላማው ዕውቅና አለመስጠትም ሆነ ጉዳዩን የልዩነት አጀንዳ አድርጐ ለመጠቀም መሞከር አገሪቱ ካሉባት በርካታ አሳሳቢ ችግሮች አኳያ ተገቢ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስችሉ ሦስት ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

አንደኛ- እንደ አገሪቱ ሕገ-መንግሥት ሁሉ የወቅቱ ሠንደቅ ዓላማም አንድ ጊዜ የአገሪቱ ሠንደቅ ዓላማ ሆኖ ከታወጀ በኋላ ይህ በራሱ የአገሪቱ አንድ ሕግ ስለሆነ ስህተቱ እንዲታረም የምናደርገው ትግል መቀጠሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የወቅቱን ሠንደቅ ዓላማ ልናከብረውና ዕውቅና ልንሰጠው ይገባል፡፡ ሁለተኛ- በሠንደቅ ዓላማው ላይ እንዲጨመር የተደረገው ኮከብ የብዙ ዜጐችን ስሜት የጐዳና አስፈላጊ ነው ሊባል የሚችል ባይሆንም ኮከብ በራሱ መጥፎ ምልክት ስላልሆነ በሠንደቅ ዓላማው ላይ መቀመጡ በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለው የከፋ አደጋም የለም፡፡ የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ በመሠረታዊነት አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ መሆኑንም የሚቀይር ነገር አይደለም፡፡ ሦስተኛ- ኢህአዴግ የነካውን ነገር ሁሉ በተለየ ሁኔታ ለመቃወም ካልፈለግን በስተቀር በኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ላይ ሌላ ተጨማሪ ዓርማ ማስቀመጥ በኢህአዴግ የተጀመረ ነገር አይደለም፡፡ በንጉሡ ጊዜ የአገሪቱ ሠንደቅ ዓላማ ላይ መስቀል ያነገበ አንበሳ በአርማነት ይቀመጥ የነበረ ሲሆን፣ ወጥ ባልሆነም ሁኔታ ቢሆን በደርግም ጊዜ ተመሳሳይ ድርጊት ይፈጸም

ነበር፡፡ በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥቱ ወቅት ማረሻና ሞፈር፣ በኋላም ላይ የኢህዲሪ ዓርማ በሠንደቅ ዓላማችን ላይ ቢያንስ በከፍተኛ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀመጥበት ጊዜ ነበር፡፡

በሠንደቅ ዓላማችን ላይ ሌላ ምንም ዓይነት አርማ መቀመጥ የለበትም የሚል አንድ ሰው በሁሉም ሥርዓቶች የተፈጸሙትን ድርጊቶች እንዳልነበሩ ቆጥሮ በኢህአዴግ ዘመን ብቻ የተሠራውን እንደ ስህተት አድርጐ ሲቆጥር ከታዩ እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት አድሏዊና የማይጠቅም ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ግን ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር የሚገናኝ ብዙ አሳሳቢ ችግሮች ባሉበት አገር ውስጥ እንዲህ ዓይነቱን ከስሜት ጋር የተያያዘ በሂደት ሊስተካከል የሚችል ልዩነት መነታረኪያ አጀንዳ አድርጐ መቀጠል ተገቢ አይሆንም፡፡

የሚገርመው ይህንን ጉዳይ ትልቅ የልዩነት ነጥብ አድርገው የሚያራግቡት ሰዎች በአንድ በኩል ኢህአዴግ የኮከብ ዓርማ ሠንደቅ ዓላማው ላይ ማስቀመጡን እያወገዙ በሌላ በኩል ግን የቁልፍ መያዣቸው ላይ፣ የመኪናቸው ባምፐር ላይ፣ የሚለብሱት ካኒተራ ወይም ባርኔጣ ላይ ለጥፈውት የሚዞሩት መስቀል ያነገበ አንበሳ ያለበትን የንጉሡን ዘመን ሠንደቅ ዓላማ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ በራሱ የእያንዳንዱ ሰው መብት ነው ሊባል ቢችልም ሠንደቅ ዓላማችን ላይ ምንም ዓይነት ዓርማ መቀመጥ የለበትም ብለን አምርረን የምንከራከር ከሆነ ግን በንጉሡ፣ በደርግም ሆነ በኢህአዴግ ዘመን የተሠራውን ስህተት እኩል ማውገዝ አለብን እንጂ አቋማችን አድሏዊ ሆኖ መቅረብ የለበትም፡፡

እንዲያውም ሠንደቅ ዓላማችን ላይ ዓርማ ማስቀመጥ ስህተት ነው ከተባለ ወደ ኋላ ተመልሶ መውቀሱ የሚጠቅም ባይሆንም የበለጠ ስህተት የሚሆነው ኢህአዴግ ካስቀመጠው ዓርማ በላይ በንጉሡ ጊዜ የነበረው ዓርማ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም አንበሳን ዓርማ ማድረግ ብዙም ችግር የሌለው ቢሆንም አንበሳው ያነገበው መስቀል መሆኑ ሲታይ ግን ሃይማኖታዊ ይዘት ያለውና ሙስሊም የሆነውን የአገራችንን ሕዝብ የማይወክልና የማያስደስት በመሆኑ የአገር ዓርማ መሆን የማይገባው ነበር፡፡ በአሁኑ ሠንደቅ ዓላማ ላይ ግን የኮከብ ዓርማ በመቀመጡ ደስተኛ የማንሆን በርካታ ሰዎች ብንኖርም ቢያንስ ግን በዓርማው ትርጉም ምክንያት በተለየ ሁኔታ መገለል ሊሰማው የሚችል የኅብረተሰብ ክፍል አለ ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ በሕገ-መንግሥቱ እንደሰፈሩት ሌሎች አንቀጾች ሁሉ ወደፊት አስፈላጊ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የሠንደቅ ዓላማውም ጉዳይ በሕዝብ ውሳኔ ሊሻሻል የሚችልበት ዕድል መኖሩን ታሳቢ በማድረግ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ላለው ሠንደቅ ዓላማ ከነድክመቱ ዕውቅና በመስጠት በዚህም ረገድ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕዝብ ሠንደቅ ዓላማን ከመሳሰሉ አገራዊ ጉዳዮች ጋር ያለው ቁርኝነት ከሕግና ከሎጅክ አንጻር ብቻ የሚታይ ሳይሆን በዋናነት ከውስጣዊ ስሜት /emotional attachment/ ጋር የተያያዘ በመሆኑ እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ሕዝብ በጫናና በግዳጅ እንዲቀበለው መሞከር ብዙም ውጤት ሊያመጣ አይቻልም፡፡ ጫናና ግዳጅ ምንጊዜም ቅራኔውንና ልዩነቱን የበለጠ የሚያሰፋ በመሆኑ ቢያንስ በሠንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠውን ዓርማ ግዳጅ የማድረግ ጉዳይ በመንግሥትም ሆነ በግል ተቋሚት ላይ ተፈፃሚ እንዲሆን በማድረግ ግለሰቦች ግን በግዳጅ ሳይሆን በፈቃዳኝነት እንዲተገብሩት ቢደረግ የተሻለ በሆነ ነበር፡፡

ሌላው ያለአግባብ የጋራችን ልናደርገው ያልቻልነው ጉዳይ የአገራችን ብሔራዊ መዝሙር ነው፡፡ የአገሪቱን ብሔራዊ መዝሙር የኢህአዴግ ደጋፊ የሆነው ኅብረተሰብ የራሴ ነው ብሎ በኩራት የሚዘምረው ቢሆንም አብዛኛው የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው ኅብረተሰብ ግን ብሔራዊ መዝሙሩን ገና የኔ ነው ብሎ አላመነበትም ማለት ይቻላል፡፡ ያላመነበት በመሆኑም ምክንያት በኩራት ሊዘምረው ይቅርና ጭራሽ አንብቦት የማያውቀው ሕዝብ በቁጥር ቀላል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ እንዲያውም አዲስ አበባ ስታዲዬምን በመሳሰሉ አንዳንድ የሕዝብ መገናኛ ቦታዎች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በደርግ ጊዜ የነበረው የቀድሞው ብሔራዊ መዝሙር ሲዘምር ይደመጥ ነበር፡፡

ሰዎች የቀድሞውን ብሔራዊ መዝሙር የሚዘምሩት በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለው ብሔራዊ መዝሙር ይዘቱ መጥፎ ሆኖባቸው ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ የሚገርም ባልሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን የአሁኑን መዝሙር በአግባቡ ላነበበ ሰው ምንም ዓይነት የሚያስከፋና እንዲጠላ የሚያደርገው አባባል በውስጡ የለበትም፡፡ ምንአልባት ጸጉር ልሰንጥቅ ለሚል ሰው አንድ ቦታ ላይ "ሕዝቦች" ሌላ ቦታ ላይ "ሕዝብ" የሚል አባባል በውስጡ መኖሩን ለመተቸች የሚችል ቢሆንም መዝሙሩ በዋናነት የሚያወሳው ምን አልባትም በተጋነነ ሁኔታ ስለ ኢትዮጵያ ታላቅ አገርነት ነው፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግን የአገር ፍቅር ይጐለዋል ብለን ለምንተች ሰዎች መዝሙሩ የበለጠ መወደድ የሚገባው በኢህአዴግ ሰዎች ሳይሆን በተቃዋሚው ጐራ ደጋፊዎች መሆን ነበረበት፡፡

ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ የነካውን ነገር ሁሉ የመጥላት በሽታ ባይጠናዎትንና ጉዳዩን ጤናማ በሆነ አእምሮ ተመልክተነው ቢሆን ኖሮ በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ ከነበረው ብሔራዊ መዝሙር ቢያንስ በአንድ አሳማኝ ምክንያት የወቅቱ ብሔራዊ መዝሙር የተሻለ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ምክንያቱም በንጉሡ ጊዜ የነበረው መዝሙር ስለ ንጉሡ የማይደፈር የበላይነት፣ በደርግ ጊዜ የነበረው ደግሞ የሥርዓቱ ርእዮተ-ዓለም ስለነበረው ስለኅብረተሰብአዊነት የሚያወሱ

ሲሆን የአሁኑ መዝሙር ግን ከወቅቱ የኢህአዴግ መንግሥት ርእዮተ-ዓለም ጋር የሚያገናኘው ምንም ዓይነት ይዘት የለውም። በዚህም ምክንያት የወቅቱ የአገራችን ብሔራዊ መዝሙር ወደፊት መንግሥታት በአገራችን ሲለዋወጡ ለረዥም ጊዜ ሳይለወጥ የመቀጠል ሰፊ ዕድል ያለው መዝሙር ነው ማለት ይቻላል። ቢያንስ ይህንን ሁላችንንም ሊወክል የሚችልና ችግር የሌለበት ብሔራዊ መዝሙር በጋራ በመዘመር ብሔራዊ መግባባትን ልናጠናክርበት ሲገባ ያለ አግባብ የልዩነት አጀንዳ እንዲሆን ማድረጋችን አሁንም የሚያሳዬው ፖለቲካችን ምን ያህል ከምክንያታዊነት የራቀ መሆኑን ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ዕውቅና የተነፈገው የአገራችን የወቅቱ ካርታ ነው። በተፈጠረው መጥፎ የታሪክ አጋጣሚ ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ በ1983 ዓ.ም. እንደገና ከተነጠለች በኋላ በብዙ ኢትዮጵያውያን ቤት ተሰቅሎ የሚታየው የአሁኑ ሳይሆን ከኤርትራ መነጠል በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ካርታ ነው። አገራችንን ከማንም በላይ እንወዳለን የምንለው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን የማንም አገር ሕዝብ ቢቻል አገሩ እየሰፋለት ቢመጣ እንጂ እያነሰበት ሲመጣ ሊደሰት አይችልም። በተለይም የኤርትራና የቀይ ባህር ከኢትዮጵያ የመነጠል ጉዳይ የካርታችንን ውበት ከማሳነሱም በላይ ከወደፊቱ የኢኮኖሚና የጸጥታ ህልውናችን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ አሳሳቢ ጉዳይ ስለሆነ የወቅቱን የአገራችን ካርታ ባየነው ቁጥር ስሜታችን መጐዳቱ የሚጠበቅ ነው። የዛሬው ትውልድ አባላት እንዲህ ዓይነት ያነሰና መሠረታዊ ጥቅሙን ያጣ አገር ለመጭው ትውልድ ማስረከባችንም የሚያሳፍር ብቻ ሳይሆን በወደፊቱ ትውልድና ታሪክ በተጠያቂነት ቦታ የሚያስቀምጠን መሆኑም የማይቀር ነው። ምክንያቱም በኢህአዴግ ዘመን ከወቅቱ ሠንደቅ ዓላማችንም ሆነ ከብሔራዊ መዝሙራችን በተለየ በተጨባጭ የቅርጽም ሆነ የይዘት ትርጉም ያለው ለውጥ የተከሰተው በአገራችን ካርታ ላይ ስለሆነ የወቅቱን የአገራችን ካርታ ባዬነው ቁጥር በውስጣችን የተሸናፊነትና የተጠያቂነት ስሜት ቢሰማን የሚደንቅ አይሆንም።

ነገር ግን በአገራችን ካርታ ላይ በተከሰተው ለውጥ የቱንም ያህል እንድንቆጭ የሚያደርገን አሳማኝ ምክንያት ቢኖረንም በሌላ በኩል የዓለም አካል ነንና እየጐመዘዘንም ቢሆን ዓለም በሚገዛበት ሕግ ለመገዛት እንገደዳለን። ምክንያቱም የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የአፍሪካ ኅብረት፣ የተባበሩት መንግሥታትና እያንዳንዱ የዓለም አገር ለኤርትራ ነፃ አገርነት ዕውቅና በሰጠበት ሁኔታ የቱንም ያህል ከፍላጐታችንና ከስሜታችን ውጭ ቢሆንም ለኤርትራ ነፃ አገርነት ዕውቅና መንፈግ ተገቢ ሊሆን አይችልም።

ስለዚህ ወደፊት በሌላ በጎ የታሪክ አጋጣሚ ኤርትራና ኢትዮጵያ እንደገና ወደ አንድ አገርነታቸው በሰላምና በሕዝብ ፈቃድ ሊመለሱ የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ተስፋ በማድረግ የወቅቱን የሚመር እውነታ አምነን መቀበል ይገባናል፡፡ የወቅቱን ነባራዊ እውነታ መቀበል ተስኖን ለኤርትራ ዕውቅና በመንፈግ የምናራምደው አቋምም ሁለቱ አገሮች እንደገና ወደ ዘላቂ አንድነት ለመመለስ የሚኖራቸውንም ዕድል የበለጠ የሚያርቅና የሚያወሳስብ ውጤት ሊያስከትል ስለሚችል ተመራጭ ስልት አይሆንም፡፡ እንደ አንድ ኃላፊነቱን በአግባቡ የሚወጣ ትውልድ ከኛ ይጠበቅ የነበረው በታሪክ አንድ የነበሩት ኤርትራና ኢትዮጵያ ከመጀመሪያው የማይለያዩበትን መፍትሔ መፈለግ ነበር እንጂ በራሳችን ስህተትና ድክመት ጭምር ሁለቱ አገሮች በተግባር ከተለያዩ በኂላ ይህንን ተከትሎ በአገሪቱ ካርታ ላይ የመጣውን ለውጥ መቃወሙ ብዙም ትርጉም የለውም፡፡ ስለዚህ ከተጨባጩ እውነታ ጋር እየተጋጨን መቀጠል ስለማይጠቅመን እየመረረንም ቢሆን የወቅቱን እውነታ መቀበላችንን የምንገልጽበት አንዱ መንገድ በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ ያለውን የአገራችንን ካርታ የኛ መሆኑን አምነን በመቀበል ነው፡፡ ይህንን ማድረግም በአገራችን እንዲፈጠር ለምንፈልገው ብሔራዊ መግባባት የራሱ በጎ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞከረው ኢትዮጵያውያን እርስ በእርሳችን የምንወዛገብበት ሁለት ሠንደቅ ዓላማ፣ ሁለት ብሔራዊ መዝሙር፣ ሁለት የአገር ካርታ ያለን መሆኑ ለማንም የውጭ ታዛቢ በጣም የሚያስገርም ጉዳይ ቢሆንም፣ የበለጠ የሚያስገርመው ግን አንዷን የአገራችንን ርእሰ-ከተማ እንኳ በአንድ ስም ለመጥራት መስማማት አለመቻላችን ነው፡፡ አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ “አዲስ አበባ” ብሎ የሚጠራት ርእሰ-ከተማችን ቁጥራቸው ቀላል ባልሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ዘንድ በአሁኑ ወቅት የምትጠራውና የምትታወቀው “ፊንፊኔ” በሚል ስም ነው፡፡ ተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የሚገኙት ኦብኮና ኦፌዴን፣ ገዥው ፓርቲ ውስጥ የሚገኘው ኦህዴድ፣ ለኦሮሞ ሕዝብ መገንጠል ወይም ነፃነት የሚታገለው ኦነግና በርካታ የኦሮሞ ተወላጆች ርእሰ-ከተማችንን የሚጠሯት “ፊንፊኔ” ብለው ነው፡፡ “አዲስ አበባ” የሚለው የአገራችን ርእሰ-ከተማ መጠሪያ ስም በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የተደነገገ መሆኑ እየታወቀ በሚገርም ሁኔታ የአገሪቱ አንድ የክልል መንግሥት በሆነው በኦሮሚያ መስተዳድር ሳይቀር ርእሰ ከተማችን በኦፊሴል “ፊንፊኔ” ተብላ ነው የምትታወቀው፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳም ራሳቸው ፈርመው ባፀደቁት ሕገ-መንግሥት የአገሪቱ ርእሰ ከተማ አዲስ አበባ ተብላ የምትጠራ መሆኗን በመዘንጋት ርእሰ-ከተማችንን የሚጠሯት “ፊንፊኔ” ብለው ነው፡፡

አዲስ አበባ መጀመሪያ የተቆረቆረችበት የፍልውሃ አካባቢ በወቅቱ “ፊንፊኔ” ይባል እንደነበር የሚያሻማና የሚያከራክር አይደለም፡፡ ያ-የፍልውሃ አካባቢ ዛሬም ቢሆን ፊንፊኔ ተብሎ ቢጠራ ተገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከዚያች ፊንፊኔ ተብላ ትጠራ ከነበረው ጠባብ አካባቢ በንግሥት ጣይቱ ስም የወጣላትና በምኒሊክ ዘመን የተቆረቆረችው አዲስ አበባ ከተማ ዛሬ በሁለንተናዊ መልኩ የሰፋችና የገዘፈች፣ በውስጧም ከሁሉም የኢትዮጵያ አቅጣጫዎች የመጣ በሚሊየን የሚቆጠር ሕዝብ ሀብት ንብረት አፍርቶ የሚኖርባት የአገር ርእሰ-ከተማ ነች፡፡ ከተማዋ ከኢትዮጵያውያንም አልፋ ዛሬ የአፍሪካ መዲና በመባል የምትታወቅ ነች፡፡ ይህችን የፊንፊኔ ዓይነት በሺ የሚቆጠሩ ትናንሽ ሠፈሮችን ከመቶ ዓመት በላይ በሆነ የጊዜ ሂደት እያካተተች በመምጣት የአገር ርእሰ-ከተማ ለመሆን የበቃችን ግዙፍ ከተማ የአንድ ጠባብ ሰፈር ወይም የፀበል ቦታ መጠሪያ በሆነ “ፊንፊኔ” በሚል ስም ለመጥራት መሞከር የተለየ የፖለቲካ ትርጉም ከሌለው በስተቀር ምንም ዓይነት የታሪክ ጭብጥ የለውም፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ሃቁን ደፍረን እንነጋገረው ከተባለ ለጉዳዩ ከጀርባው ምንም ዓይነት የፖለቲካ ትርጉም ሳይሰጡት በተለምዶ ጤናማ በሆነ መልኩ አዲስ አበባን “ፊንፊኔ” እያሉ የሚጠሩ ብዙ የኦሮሞ ተወላጆች የመኖራቸውን ያህል፣ አዲስ አበባ ከተማ በተለየ ሁኔታ “የኛ ነች” ከሚል ፖለቲካዊ አጀንዳ “ፊንፊኔ” የሚለውን መጠሪያ ሆን ብለው መጠቀም የሚፈልጉ የተደራጁ ኃይሎች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገውም አንድ ርእሰ-ከተማ በሁለት ስም መጠራቷ ሳይሆን ”ፊንፊኔ” በሚለው መጠሪያ ጀርባ ያለው የፖለቲካ አጀንዳ ነው፡፡

ከየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ መጥቶ አዲስ አበባ ላይ ሕይዎቱን የመሠረተውና በተለያዩ የልማት መስኮች ጥሪቱን እያፈሰሰ የሚገኘውን በሚሊየን የሚቆጠር ሕዝብ ስጋት ውስጥ የሚከት እንዲህ ዓይነት ጤናማ ያልሆነ አስተሳሰብ ለኢኮኖሚ ዕድገታችን እንቅፋት ከመሆኑ በተጨማሪ በአገራችን ብሔራዊ መግባባት እንዳይፈጠርም የሚያደርግ ከፍተኛ ችግር ነው፡፡ ስለዚህ ሁላችንም የአገራችን ርእሰ-ከተማ አዲስ አበባ መሆኗን አምነን በመቀበል በሁለት ሳይሆን በአንድ ስም ልንጠራት ይገባል፡፡ መንግሥትም እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በዝምታ ሊያዩው አይገባም፡፡ የወቅቱን ሠንደቅ ዓላማና ብሔራዊ መዝሙር ሕዝቡ እንዲያከብረው ሁልጊዜ ሲወተውት የሚደመጠውን ያህል የአገሪቱ የመንግሥት መዋቅሮችም ሆኑ ሕዝቡ የአገሪቱ ርእሰ-ከተማ አዲስ አበባ ተብላ የምትጠራ መሆኑን በተግባር እንዲያከብሩ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በነገራችን ላይ የአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን የሌሎች አንዳንድ የአገራችን ከተሞች ስምም በአሁኑ ወቅት እየተቀየረ ነው፡፡ በርግጥ ቢሸፍቱንና አዳማን የመሰሉ ከተሞች ከመጀመሪያውም በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ስማቸው እንዲቀየር የተደረገው ያለአግባብና በዘፈቀደ የሹማምንት ውሣኔ ቢሆንም ስሙ የተቀየረ ከተማና አካባቢ ሁሉ ወደነበረበት ይመለስ ከተባለ ግን ማቆሚያ የሌለው ውዝግብ ውስጥ የሚያስገባ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በኛም አገር ሆነ በሌሎች አገሮች በተለያዩ አጋጣሚዎች ነባር ስሞች እየተለወጡና አዳዲስ ስሞች እየተፈጠሩ መምጣታቸው ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ያልተቋረጠ የታሪክ ሂደት ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉም ነገር ወደነበረበት ይመለስ የሚለው አመለካከት መቆሚያ የሚኖረው ባለመሆኑ የሚሻለው የተደረጉትን ለውጦች በአግባቡ በታሪክ መዝገብ ላይ እንዲቀመጡ ተደርጎ ነባራዊውን ሁኔታ ይዞ መቀጠል ነው፡፡

የስም ለውጥ ጥያቄ ለምን ኦሮሚያ ላይ በተለየ ሁኔታ እንደገነነ ግልጽ ባይሆንም ችግሩ ግን በመላው አገሪቱ ያለ ነው፡፡ ለምሳሌ በዐማራ ክልል ኦሮምኛ መጠሪያ ያላቸው አካባቢዎች በጣም በርካታ ሲሆኑ ጭራሽ ትርጉማቸው ምን እንደሆነ በማይታወቅ መጠሪያ የሚጠሩ አካባቢዎች ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በአጠቃላይም በኦሮሞ ሕዝብ ፈጣን የመስፋፋት ሂደት በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች ስማቸው ከመቀየርም አልፎ ህልውናቸውን ያጡ ሕዝቦች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለምና እንዲህ ዓይነቱ ጀምረን የማንጨርሰው ጣጣ ውስጥ መግባት ብሔራዊ መግባባትን ከማሻከር አልፎ የሚሰጠን ጥቅም ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አይታይም፡፡

### 1.3.4 አገራዊ ተቋማትና የአገር መሪ

ሌላው የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ብሔራዊ መግባባት ያጣንበት ጉዳይ አገራዊ ተቋማትን የሚመለከተው ነው፡፡ በአገራችን በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ የሚገኙት አንዳንዶቹ መንግሥታዊ ተቋማት ከተቋቋሙ ከግማሽ ዘመን በላይ ዕድሜ ያሳለፉ ቢሆንም የመንግሥት ለውጥ በመጣ ቁጥር የፖለቲካ ኃይሎች የውዝግብና ያለመግባባት ምንጭ መሆናቸው ግን አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ በአንድ አገር የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት እንዲጣልም ሆነ የበለጠ በሂደት እየዳበረና እየተጠናከረ እንዲሄድ አስተማማኝ ዋስትና መስጠት የሚችሉት ተቋማት ቢሆኑም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች እስካሁን ለአገሪቱ ተቋማት ተገቢውን አክብሮትና ትኩረት መስጠት አልቻልንም፡፡ በየጊዜው በአገሪቱ ወደ መንግሥት ሥልጣን የሚመጡ የፖለቲካ ኃይሎች የነበረውን እያፈረሱ እንደገና ለራሳቸው የሥልጣን የበላይነት በሚጠቅም ሁኔታ ተቋማቱን በአዲስ መልክ ስለሚያደራጁአቸው አገራችን የአንድ መንግሥት ዕድሜ መሻገር

የሚችሉ ጠንካራ ተቋማትን ማግኘት አልቻለችም፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ የፖለቲካ ባህላችን ቀድመው በተገኙት በጎ ነገሮች ላይ የበለጠ እየገነባ ከመሄድ ይልቅ ቀድሞ የነበረውን በጎ ነገር ጭምር የማጣጣል፣ የማፍረስና እንዳልነበረ የማድረግ አባዜ የተጠናወተው ነው፡፡ እንዲያውም በሚገርም ሁኔታ የአገራችን የፖለቲካ ባህል የተጠናወተው በሽታ በጎ በጎውን እየመረጠ ያለመያዝ ብቻ ሳይሆን በጎ ያልሆኑትን ነገሮች እየመረጠ የመያዝ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ችግሩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው እስከ አሁን በዚህ ዓይነቱ አገርን የማይጠቅም መንገድ መጓዛችን ብቻ ሳይሆን አሁንም የመድብለ-ፓርቲ አሠራር ተጀምሯል በምንልበት አገራችን ተቋማትን በተመለከተ ተመሳሳይ ችግር ሊቀጥል የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ በአንድ በኩል ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በአገሪቱ ሕዝብ ሀብትና ንብረት የተቋቋሙትን ተቋማት ሌሎችን ለማጥቃትና ራሱን ከሌሎች ጥቃት ለመከላከል በሚያስችለው ሁኔታ አደራጅቶ ስለሚጠቀምባቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በየተቋማቱ ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶችና ድክመቶች በአግባቡ በመተቸት ተቋማቱ በሂደት ችግራቸውን ፈተው የአገር ተቋማት ሆነው እንዲቀጥሉ ከመፈለግ ይልቅ ሙሉ በሙሉ ለተቋማቱ ዕውቅና መንፈግንና አዲስ ተቋም ማቋቋምን ስለምንመርጥ ይህ የገዥው ፓርቲና የተቃዋሚዎች አቋም እርስ በርሱ እየተመጋገበ ለአገራዊ ተቋማት ግንባታ እንቅፋት መሆኑን ቀጥሏል፡፡

ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን፣ የፍትህ ተቋማት፣ የምርጫ ቦርድና የጸጥታ አስከባሪ ተቋማት ከፍተኛ ሚና ያላቸው ከመሆኑ አንጻር በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ኃይሎች የውዝግብ ማዕከል ሆነው ይገኛሉ፡፡ ገዥው ፓርቲ እነዚህን ተቋማት ሕግን ብቻ መሠረት አድርገው ሥራቸውን የሚያከናውኑና ገለልተኛ ተቋማት እንደሆኑ አድርጐ ሁልጊዜ ሲከራከር የሚደመጥ ቢሆንም ጉዳዩ "ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ" መሆኑ ለማንም የፖለቲካ ሀሁ ለቆጠረ ሰው ግልጽና የማያሻማ ነው፡፡ በርግጥም የዕውቅናና የመቻቻል ፖለቲካ ገና ባልተፈጠረበት አገር ገዥው ፓርቲ እንዲህ ዓይነቱን ስልት መጠቀሙ እንደማይቀር አስቀድሞ የሚገመት ነው፡፡ ማንም ሥልጣኔን ከተነጠኩ ህልውናዬንም አጣለሁ በሚል ስጋት ውስጥ የሚገኝ የፖለቲካ ኃይል ቁልፍ የሆኑ የአገሪቱን ተቋማት ከራሱ ቁጥጥር ነፃ አድርጐ የሰላም እንቅልፍ ሊተኛ እንደማይችል ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ኢህአዴግም በአሁኑ ወቅት ተቋማቱን በበላይነት ለመቆጣጠር የሚፈልግበት ምክንያት ከዚህ የተለየ ሌላ ምስጢር አይኖረውም፡፡

ነገር ግን እነዚህ ተቋማት በገዥው ፓርቲ የተለየ ቁጥጥር ሥር እንደሚገኙ የቱንም ያህል ርግጠኞች ብንሆንም ለተቋማቱ ዕውቅና መንፈጋችንና ተገቢ ክብር አለመስጠታችንን

ሰላማዊ ትግል እናደርጋለን ለምንል ኃይሎች ትክክለኛና ጠቃሚ ስልት አያደርገውም፡፡ ከላይ ስለ ሕገ-መንግሥቱና ስለ ሌሎች ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርባቸው ስለሚገባ አገራዊ ጉዳዮች ልንይዘው ይገባል በማለት ለማመላከት የሞከርነው ስልት ለእነዚህ ተቋማትም የሚሠራ ይሆናል፡፡ እነዚህን ተቋማት እንደ አንድ ራሱን የቻለ የኢህአዴግ ግንባር በመቁጠር “እናፈርሳችኂለን” በማለት ተቋማቱ እኛኑ መልሰው እንዲታገሉን ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ይልቅ በአንድ በኩል እንደ አገር ተቋማት ተገቢውን ዕውቅናና አክብሮት በመስጠት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውስጣቸው የሚታዩ ስህተቶችንና ችግሮችን በተጨባጭ ነቅሰን እያወጣን እንዲሻሻሉ ብንታገል የእኛ አጋዥ ሊሆኑ ባይችሉም (እንዲሆኑም አይጠበቅም) በሂደት ገለልተኛ የመሆን አቋም እዩያዙ እንዲመጡ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ተቋማት መካከል የመከላከያ፣ የፖሊስና የደኅንነት ተቋማትን በተመለከተ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የምንገኝበትን ውዝግብ በምሳሌነት አንስተን ልናየው ብንሞክር ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ለማድረግ ሊረዳን ይችላል፡፡ እነዚህ የጸጥታ ተቋማት በተለይም መከላከያና ደኅንነት ከደርግ ውድቀት በኂላ ሙሉ በሙሉ ፈርሰው በአዲስ መልክ የተደራጁ ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ሙሉ በሙሉ ፈርሰው የሠራዊቱ አባላት ከተበተኑ በኂላ አገሪቱ ሰላም አግኝታ መቀጠሏ በራሱ አስደናቂና የበለጠ ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ ቢሆንም ኢህአዴግ ከኀምሳ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለውን የአገሪቱን ሠራዊት እንደ ደርግ ሥርዓት የግል ሠራዊት በመቁጠር እንዲበተን ማድረጉ ስህተት ከመሆኑም በላይ ተገቢ ያልሆነ ልምድ /Precedence/ በአገሪቱ ፈጥሮ አልፏል፡፡

ኢህአዴግ በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ የፖለቲካ ተሿሚዎችንና በወንጀል ተሳታፊ የነበሩ አዛዦችን ከቦታቸው በማንሣትና በዋናነት በሠራዊቱ ውስጥ የአሠራርና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ሠራዊቱ የአገሪቱ ሠራዊት ሆኖ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችል ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ርምጃም ኢህአዴግን በሕዝቡ ዘንድ ከመጀመሪያው እንደ አገር መንግሥትነት የመታየት የተሻለ ተቀባይነት (Legitimacy) እንዲያገኝ በማድረግ ቀጣይ ጉዞውን ለስላሳ ያደርግለት ነበር፡፡ ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ሠራዊት ሳይሆን እንደ ደርግ ሠራዊት ተቆጥሮ በኢህአዴግ ተበትኖ በመላው አገሪቱ ከየቤተሰቡ ጋር የተቀላቀለው በመቶ ሺዎች የሚቆጠር የሠራዊት አባል ሌላ ነገር ለማድረግ አቅሙን ባያገኝም ቢያንስ ኢህአዴግን ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል እንደሆነ አድርጐ በሕዝቡ ውስጥ በመቀስቀስና እስካሁንም ድረስ የሥርዓቱ ዋና ተቃዋሚ ሆኖ በመቀጠል በኢህአዴግ ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ነገር ግን በጊዜው ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ይጨነቅ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ እንዴት መቀጠል እንደሚችል ስለነበር ሙሉ በሙሉ የቀድሞውን ሠራዊት በትኖ በራሱ ኃይል መተካትን መርጧል። ኢህአዴግ አንድ ጊዜ ይህንን ስህተት ከሠራ በኋላ ሠራዊቱን ስለ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት በማስተማርና ተዋጽኦውን በማመጣጠን ገለልተኛ የአገር ሠራዊት አድርጌዋለሁ ቢልም የሚያምነው አላገኘም። አለመታመኑም ከተጨባጭ ምክንያት የመነጨ ስለሆነ የሚጠበቅ ነው። ኢህአዴግ አብዛኛዎቹ በመከላከያ ሠራዊቱም ሆነ በደህንነቱ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች የአንድ የፖለቲካ ድርጅት አባል በነበሩና በዐሥራ ሰባት ዓመቱ መራር የትጥቅ ትግል ውስጥ አብረው ሲታገሉ በኖሩ ጓደኛሞች በተያዙበት ሁኔታ ሕዝብንና ተቃዋሚዎችን ይቅርና ሠራዊቱና ደህንነቱ ነፃና ገለልተኛ ናቸው ብሎ ራሱንም ከልቡ ሊያሳምን አይችልም።

እነዚህ ተቋማት በእውነትም ገለልተኛ አለመሆናቸውን ለማወቅ ብዙም ምርምር ሳይጠይቅ የተቋማቱን የአፈጣጠር ሂደት ብቻ በማየት በቀላሉ መረዳት ቢቻልም ተቋማቱ ገለልተኛ አለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን አለመሆናቸው በውስጡ የያዘውን አደጋ አንድ ምሳሌ በመጥቀስ በቀላሉ መረዳት ይቻላል። በ1993 ዓ.ም. በህወሃት አመራር መካከል ከፍተኛ አለመግባባት ሲፈጠር የአገር ሠራዊት ነው የተባለው ተቋም አመራሮች ጉዳዩ እኛን አይመለከተንም ብለው ዝምታን አልመረጡም። ህወሃት ውስጥ የተፈጠረው ችግር በተዘዋዋሪ ሳይሆን ቀጥተኛ በሆነ መልኩ የሠራዊቱና የደኅንነቱ አመራር ውስጥም በመከሰቱ በመጨረሻ የደኅንነት ኃላፊ ለነበሩት ለአቶ ክንፈ ገብረመድኅን መገደልና የሠራዊቱ ኢታማዦር ሹም ለነበሩት ለሜጀር ጀኔራል ጻድቃን ገብረተንሣይና ለሌሎችም ከፍተኛ ወታደራዊ መኰንኖች ከኃላፊነት መውረድ ምክንያት ሆኗል። ይህ የሚያሳዬን የኢህአዴግ አንድ አባል ድርጅት በሆነው በህወሃት ውስጥ በተከሰተው አለመግባባት ሠራዊቱና ደኅንነቱ ውስጥ ይህንን ያህል ከፍተኛ ቀውስ ከተከሰተ፣ አለመግባባቱ በአጠቃላይ በኢህአዴግ ደረጃ ማለትም በህውሃትና በሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል ወይም በመንግሥት ደረጃ ቢከሰት ኖሮ ምን ያህል የአገራችንን ደኅንነት አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል ችግር በእነዚህ የጸጥታ ተቋማት አማካይነት የመፈጠር ዕድል እንዳለ የሚያሳይ ነው።

ስለዚህ የቱንም ያህል እነዚህ የጸጥታ ተቋማት ገለልተኛ እንዳልሆኑ ርግጠኞች ብንሆንም ተቋማቱ በታሪክ አጋጣሚ ከአገራችን ህልውና ጋር የተሳሰረ ሚና እንዲኖራቸው ስለተደረገ እነሱን በሚመለከት የምናራምደው አቋም ከአገራችን ደኅንነት አንጻር አርቆ የሚያይና ጥንቃቄ የተሞላበት ሊሆን ይገባዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ተቃዋሚዎች ልንረዳው የሚገባን ቀዳሚ ቁምነገር እነዚህ የጸጥታ ተቋማት የገዥውን ፓርቲ ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ እንጂ ምንም

ዓይነት አገራዊ ሚና እንደሌላቸው አድርገን የምናቀርበው ወቀሳ ሊስተካከልና ሚዛናዊነት ሊኖረው ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ የመከላከያ፣ የደኅንነትና የፖሊስ ተቋማት በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል የፖለቲካ አለመግባባት በሚፈጠርበት ወቅት ገለልተኛ አቋም አይኖራቸውም ማለት ብንችልም፣ ተቋማቱ በዕለት-ተዕለት ሥራቸው ግን አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት የአገሪቱንና የሕዝብን ደኅንነት በማስከበር ተግባር ላይ ተሰማርተው መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚህ በውስጣቸው ያለውን ድክመትና ስህተት መተቸታችን ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ ግን ለአገሪቱና ለሕዝቡ ጥቅም ለሚያከናውኑት ተግባር የዛኑ ያህል ተገቢውን ዕውቅናና ክብር መስጠት ይገባናል፡፡

ሁለተኛ - ተቋማቱ ገና ገለልተኛ ናቸው ሊባል በሚያስችል ደረጃ የማይገኙ ቢሆንም እኛ በምንፈልገው መጠንም ባይሆን በውስጣቸው የለውጥ ሂደትም እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ መከላከያ ሠራዊትን ብናይ ከቅርፁም ሆነ ከይዘቱ አንጻር የዛሬ ዐሥራ ስምንት ዓመት በነበረበት ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ አይገኝም፡፡ ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የሠራዊቱ አባላት የነበሩ በርካታ ሰዎች በሂደት ወደ ሲቪል ኃላፊነት ውስጥ በመግባታቸው፣ በጤናና በዲሥፕሊን ምክንያት በርካታ የሠራዊቱ አባላት በየጊዜው በመሰናበታቸው፣ አንዳንዶችም ከንግድ ሥራ ጀምሮ ወደ ተለያዩ የግል የሕይወት አቅጣጫዎች ሠራዊቱን እየለቀቁ በመግባታቸው፣ የሠራዊቱን ተዋጽኦ ለመጠበቅ ተብሎ በተሠራው ሥራም ጭምር ብዙ የሠራዊቱ አባላት ወደ ግብርና ሥራ በመግባታቸው በሂደት የሠራዊቱ ቅርጽና ይዘት እየተቀዬረ መጥቷል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ የሠራዊት ምልመላ በመካሄዱ የሠራዊቱ ተዋጽኦ ከመቀየሩ በላይ በሠራዊቱ ውስጥ የቀድሞ ታጋዮችን ቁጥርም በዚያው መጠን ያነሰ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በሌላ በኩል ሠራዊቱ ውስጥ አንድ ሰው በሥራ ላይ ሊቆይ የሚችልበትን ዕድሜ ለማየት ብንሞክር አብዛኛዎቹ ኢህአዴግ አገሪቱን ሲቆጣጠር የሠራዊቱ አባል የነበሩት የቀድሞ ታጋዮች በአሁኑ ወቅት ከአርባ አምስት ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡ ይህም ማለት ከተራ ወታደር እስከ ሻምበል ማዕረግ ድረስ ያሉ የሠራዊቱ አባላት ጡረታ የሚወጡበት የዕድሜ ጣራ 45 ዓመት ስለሆነ ቢበዛ ከዛሬ 5 ዓመት በኋላ በሠራዊቱ ውስጥ የቀድሞ ታጋይ የነበረ ሰው ፈልጐ ማግኘት ብርቅ የሚሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ቁልፍ የአመራር ቦታዎች ላይ የሥርዓቱ ታማኝ ሰዎች እስካሉ ድረስ ሠራዊቱን ገለልተኛ ነው ለማለት አስቸጋሪ ቢሆንም ቢያንስ በቅርጽ ደረጃ ሠራዊቱ ከዚህ በኋላ የአገር ሠራዊት እየሆነ መምጣቱ ብዙም አጠራጣሪ አይሆንም፡፡

ሦስተኛ- ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዋናነት ልንረዳው የሚገባን ቁም ነገር፣ ሠራዊቱን የአገር ሳይሆን የኢህአዴግ ሠራዊት እንደሆነ አድርገን እየከሰስንና እኛ ወደፊት ሥልጣን ስንይዝ እንደምናፈርሰው እየዛትንበት የምንቀጥል ከሆነ መቼም ቢሆን ሠራዊቱ ገለልተኛ ሚና ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም እኛ ሥልጣን ስንይዝ በእውነትም ሠራዊቱን የምንበትነው ከሆነ ለራሱ ህልውና ሲል ከኢህአዴግ ጐን ቁሞ እኛ ወደሥልጣን እንዳንወጣ የሚችለውን ያህል ቢከላከል ድርጊቱ ሕገ-መንግሥታዊ ባይሆንም ፖለቲካዊ ስህተት ግን ሊሆን አይችልም፡፡ በቅርቡ በሶማሊያ ውስጥ የኢትዮጵያ ሠራዊት የነበረውን ተሳትፎ በተመለከተ አንዳንድ በተቃዋሚው ጐራ ደጋፊነት የሚታወቁና በውጭ አገር የሚገኙ ድህረ ገፆች ከራሳቸው አብራክ በወጡ የሠራዊቱ አባላት ስብእና ላይ በመሳለቅ ጭምር ያቀርቡት የነበረው ዘግናኝ ዘገባ ሲታይ ሠራዊቱ ተቃዋሚውን ጐራ በጥርጣሬና በስጋት ዓይን ቢያየው የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡

ስለዚህ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ሠራዊቱን በተመለከተ ተቃዋሚዎች እያራመድነው ያለነው አቋም በፕሮፓጋንዳ ደረጃ ኢህአዴግን የሚጐዳ ቢመስልም በመጨረሻ ውጤቱ ግን ራሳችንንና አገራችንን የሚጐዳ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ የሠራዊቱ ጉዳይ በምሳሌነት ተጠቀሰ እንጂ ሁሉንም የመንግሥት ተቋማት በተመለከተ እየሆነ ያለው ተመሳሳይ ነው፡፡ ተቋማቱንና በተቋማቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሞራል የሚፈታተንና ህልውናቸውን ስጋት ላይ የሚጥል ስልት እየተከተልን እንደገና ከእነዚህ ተቋማት ለእኛ የሚጠቅም ምላሽ መጠበቁ እርስ በርሱ የሚቃረን አቋም ነው፡፡ በተቋማቱ ውስጥ የሚታየውን ድክመትና ስህተት በተጨባጭ በመረጃ እያስደገፍን እየተቸን በዚያው መጠን ለተቋማቱ ተገቢውን ዕውቅና ብንሰጥና ለሚሠሯቸው በጎ ነገሮችም ተገቢውን አድናቆት ብንሰጣቸው እነሱም እኛን የሚያዩበት መንገድ በሂደት እየተቀየረ ሊመጣ ይችላል፡፡

በምክንያትና በኃላፊነት ስሜት የምንተቻቸው መሆኑን እየተረዱ በመጡ ቁጥር በየተቋማቱ ያሉት ሰዎች እንደኛው ከዚሁ ኅብረተሰብ የተፈጠሩና የተሻለ አገር እንዲኖራቸው የሚፈልጉ ዜጐች በመሆናቸው ከመንገድ ወጥተው ሊረዱን ባይችሉም እንኳ ቢያንስ ግን በሂደት ገለልተኛ አቋም ይዘውና ሕግን ተከትለው እኛንም በአግባቡ ለማገልገል የማይፈልጉበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህንን ማለት የሚቻለው በይሆናል ግምትም ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚዎች ለተቋማቱ ያለን አቀራረብ እንደዚህ ብልሹ በሆነበት በአሁኑ ወቅት እንኳ በየተቋማቱ ያሉ በርካታ ሲቪልና ሚሊታሪ ሰዎች ማመን በሚከብድ ደረጃ (ዝርዝሩን መግለጽ ባያስፈልገኝም) ለተቃዋሚዎች በጎ አመለካከት ያላቸው መሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች በተግባረ መታየት ስለቻለ ነው፡፡ ስለዚህ ከትግል ስልትም አኳያ ለተቋማቱ ተገቢ ዕውቅናና አክብሮት መስጠታችን የሚጠቅመን እንጂ

የሚጉዳን እስካልሆነ ድረስ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለእነዚህ የአገሪቱ ተቋማት ዕውቅና በመስጠት ብሔራዊ መግባባትን በአገራችን ለማጠናከር ብንጠቀምበት ድርብ ተጠቃሚ ሊያደርገን ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ብሔራዊ መግባባት ያጣንበት ሌላው ጉዳይ የአገር መሪ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን መሪዎቻችንን በአግባቡ መርጠን ለሥልጣን ማብቃት ብቻ ሳይሆን እስካሁን መሪዎቻችንን በአግባቡ አልቅሰን ለመቅበርም ታድለን አናውቅም፡፡ በታሪካችን በመሪነት ሥልጣን ላይ እያሉ በሕዝቡ መወደድና መመስገን የቻሉ ብዙ መሪዎች ያልነበሩን ቢሆንም በዚያው መጠን ከሞቱ በኋላ ሳይመሰገኑና ሳይደነቁ የቀሩ መሪዎቻችን ጥቂቶች ናቸው፡፡

ይህ ችግር ከታሪካችን ጋር እጅግ የተቆራኘና ሥር የሰደደ መሆኑን ገብረሕይወት ባይከዳኝ የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ በጻፉት ጽሑፍ "…ወዮለት ለዚያው ንጉሥ የዛሬውን ከደማችን ጋር የተዋኀደውን የድንቁርና ሥርዓታችንን ሊለውጥ ለሚነሣው፡፡ ለኋላ ስም ያገኛል እንጂ በሥጋው አይጠቀምም" በማለት አሥነብበውናል፡፡ "…አእምሮ የሌለው ሕዝብና ልጅ ጠቃሚውን አይወድም" የሚሉት ገብረሕይወት ባይከዳኝ፣ የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ በርሳቸው ዘመን የነበረው ችግር ዛሬም በኛ ዘመን ጉልቶ ይታያል፡፡

በቅርቡ የአገራችን ታሪክ ሥልጣናቸውን ካጡ በኋላ በሕይወት ለመኖር የበቁ ብቸኛ የአገራችን መሪ ኰሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ቢሆኑም እርሳቸውም በአገርና በሕዝብ ላይ የፈጸሙት በደል ሁሉ በአንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተረስቶ አንድ ወቅት ላይ ፎቶግራፋቸው የጋዜጦች ማሻሻጫ ሆኖ እንደነበረና፣ በአንድ ወቅት ለአንድ ጋዜጣ ቃለ-መጠይቅ የሰጡ በልመና የሚተዳደሩ ሰውም የርሳቸውን ፎቶግራፍ ደረታቸው ላይ ለጥፈው "ስለ መንግሥስቱ ኃይለማርያም! ስለ ፍራጡ መሪያችን!." እያሉ በመለመን ብዙ ገንዘብ ማግኘት መቻላቸውንም አንብበናል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ የግፍ አገዛዝ በእጅጉ ተማሮ የነበረና በተለይም በቀይ ሽብር ዘመን በሰው ልጅ ኅሊና በቀላሉ ሊፋቁ የማይችሉ በርካታ ዘግናኝና አሠቃቂ ድርጊቶችን ያዩ ቢሆንም ኢህአዴግ ሥልጣን ይዞ የቀይ ሽብር ተጠርጣሪዎችን ለፍርድ ባቀረበበት ወቅት ግን ምስክር ሆኖ ፍርድ ቤት የሚቀርብ ሰው በማጣት ተቸግሮ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙውን ጊዜ የወደቀን መንግሥትና መሪ የማመስገንና የማወደስ እንጂ የመጥላት ባህሪ የሌለው መሆኑን ነው፡፡

መሪዎች በሕይወት እያሉም ሆነ ከሞቱ በኋላ ይብዙም ይነሱም የሚኮሩባቸውም ሆነ የሚያፍሩባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መኖራቸው የተለመደ ቢሆንም ቢያንስ ግን ሥልጣናቸውን ካጡ ወይም ከሞቱ በኋላ "የኢትዮጵያ መሪ ነበሩ" የሚለው ዕውቅና

አይነፈጋቸውም፡፡ ይህም በ2000 ዓ.ም. ሚሊኒየም በዓላችንን ስናከብር የኮሌኔል መንግሥቱን ጨምሮ ከአፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የተፈራረቁ የሁሉም መሪዎቻችን ምስል መስቀል አደባባይ ላይ በክብር ተሰቅሎ በማየታችን ተረጋግጧል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በጎ ልምድ መሪዎቻችን ሥልጣናቸውን ካጡ በኋላ ብቻ ሳይሆን በሥልጣንም ላይ እያሉ ቢለመድ ብሔራዊ መግባባትን በማጠናከርና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን በአገራችን በማምጣት ረገድ የማይናቅ አስተዋጽኦ በኖረው ነበር፡፡

በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን በሚመለከት የፖለቲካ ኃይሎች ያላቸው አቋም ከላይ በአንዳንድ አገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ እንዳየነው በሁለት የተካረረ ጫፍ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ኢህአዴግና የኢህአዴግ ደጋፊ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል ጠቅላይ ሚኒስትሩን በኢትዮጵያ ታሪክ እስካሁን ከታዩት መሪዎች ሁሉ በዕውቀታቸው የላቁ፣ አርቆ አሳቢና አዲስ ሐሳብ አፍላቂ፣ በአጠቃላይ አገሪቱን ወደ አዲስና የላቀ ምዕራፍ እያሸጋገሩ የሚገኙ ጠንካራና ታላቅ የአገር መሪ አድርገው ያደንቋቸዋል፡፡ አንዳንዶቹ ደጋፊዎቻቸውም ለእርሳቸው ካላቸው ከአድናቆትም አልፎ ወደ አምልኮት የተጠጋ አስተሳሰብ ርሳቸውን ካጣች ይህች አገር ምን ይውጣታል? በማለት ሲጨነቁ ይታያሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ የሚገኘው ኅብረተሰብ ደግሞ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በኢትዮጵያ እስካሁን ከታዩት መሪዎች ሁሉ የአገር ፍቅር ስሜት የሌላቸውና አገርን የሚጐዳ በርካታ ታሪካዊ ስህተት የፈጸሙ፣ በዕውቀት ሳይሆን በተንኮልና በሴራ የተካኑ አድርገው ያዩአቸዋል፡፡ አንዳንዶችም ከዚህ በከረረ ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ኢትዮጵያዊ ያልሆኑና ከጀርባቸው ድብቅ ዓላማ ይዘው አገርን የማፈራረስ ተልዕኮ እየፈጸሙ የሚገኙ ጠላት አድርገው ስለሚቆጥሯቸው ርሳቸውን የኢትዮጵያ መሪ ናቸው ብለው ዕውቅና መስጠትም አይፈልጉም፡፡ አንዳንዶችም ከጥላቻቸው ጥልቀት በመነጨ አቶ መለስ የአገር ጠላት ናቸው ብለው ከልባቸው ከማመንም በላይ እስካሁን ድረስ አቶ መለስ ከአቶ ኢሳያስ ጋር በድብቅ በስልክ እየተመካከሩ ሁለቱን አገሮች በጦርነት የሚያፋጁ መሪ እንደሆኑ አድረገው ለማማት ሲሞክሩም ይታያሉ፡፡

ይህንን ጉዳይ በአግባቡ ለመፍረድ የምንሞክር ከሆነ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ደጋፊዎችም ሆኑ ተቃዋሚዎች በሁለት የከረረ ጫፍ ላይ ቆመን የምናራምደው አቋም በውስጡ የየራሱ መጠነኛ እውነት ያለው ቢሆንም እጅግ የከረረና ሚዛኑን የሳተ መሆኑ ግን ግልጽ ነው፡፡ የአገር መሪዎች አንድን አገር ወደ በጎም ሆነ ወደ መጥፎ አቅጣጫ ለመምራት ያላቸው ሚና ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር ኢትዮጵያውያን በአገራችን መሪ ላይ እንዲህ ዓይነት የተካረረ አቋም

እያራመድን ብሔራዊ መግባባትም ሆነ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በቀላሉ እንፈጥራለን ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆኑ እርሳቸው ከሚመሩት ፓርቲ ጋር ሰፊ ሊባል የሚችል የፖለቲካና የኢኮኖሚ አመለካከት ልዩነት ያለን ሰዎች የጠቅላይ ሚኒስትሩ ደጋፊዎች እንደሚሉት እርሳቸው ታላቅና ወደር የሌላቸው የአገር መሪ ናቸው ብለን ልናምን እንደማንችል ግልጽ ነው፡፡ በዐሥራ ሰባት ዓመቱ የትጥቅ ትግል ዘመናቸውም ሆነ ለዐሥራ ስምንት ዓመት የአገር መሪ ሆነው ባሉበት ወቅት በርካታ በጎ ነገሮችን የሠሩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገሪቱን ጥቅም የሚጐዱ ስህተቶችም ፈጽመዋል ብለን ስለምናምን ርሳቸውን መቃወም ብቻ ሳይሆን የሚመሩት ፓርቲ መንግሥታዊ ሥልጣኑን በሰላማዊ ትግል እንዲያጣ ጭምር ጠንክሮ መታገል ለአገራችን ይጠቅማል ብለንም እናምናለን፡፡ ለዚህም ነው ተቃዋሚ ፓርቲ መሥርተን ኢህአዴግን በመታገል ላይ የምንገኘው፡፡

ይህ አቋም እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው ቢሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩን የቱንም ያህል ቢጠላቸውና ቢቃወማቸውም ያለ አግባብ ርሳቸውን ለማዋረድና ለማጥላላት የሞራልም ሆነ የሕግ መብት አለው ብሎ ማመን ግን አይቻልም፡፡ የቱንም ያህል የሚያራምዱትን አቋም ብንጠላው፣ የቱንም ያህል ራሳቸውን እንደ አንድ አገር መሪ እንዳይታዩ የሚያደርግ ስህተት ሲፈጽሙ ቢታይ የርሳቸውን ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ውስጥ ማስገባትና ድብቅ ዓላማ ይዘው አገርን እያፈረሱ የሚገኙ የአገር ጠላት አድርጐ መፈረጅ ግን ከገደብ ያለፈ የፖለቲካ ስህተት ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያዊ ጨዋነት ጋር አብሮ የማይሄድ ነውርም ጭምር ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚያራምዱትን አቋም በሚመሩት ድርጅት ዙሪያ በአባልነትና በደጋፊነት የሚገኘው በርካታ ኢትዮጵያዊ ሕዝብ የሚያምንበት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚህ ርሳቸውን ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የአገር ጠላት አድርገን ለማንቋሸሽ ስንሞክር የእርሳቸው አስተሳሰብ ደጋፊ የሆነውን በርካታ ኢትዮጵያዊ ሕዝብም መብት ያለ አግባብ እየተጋፋን መሆኑን ማገንዘብ አለብን፡፡

ሁለተኛ - አንድ ለዐሥራ ሰባት ዓመት መራራ የትጥቅ ትግልን የመሩና ለዐሥራ ስምንት ዓመት ውስብስብ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ችግር ያለባትን ድሀ አገር ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው የመሩን ሰው ዕውቀት የለሽና ደካማ አድርጐ ለመቁጠር መሞከር ግብዝነት ነው፡፡ እኛ እንደምናስበው በእውነትም አቶ መለስ ደካማና ምንም ዓይነት ዕውቀት የሌላቸው ሰው ቢሆኑ ኖሮ እርሳቸው የሚመሩት ፓርቲ በመጀመሪያ ደርግን ያህል ግዙፍ መንግሥት ለመጣል፣ ቀጥሎም ለዐሥራ ስምንት ዓመታት አገርን ለመግዛት ባልበቃ ነበር፡፡

ሦስተኛ - ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት ኢህአዴግ የሠራቸው አገርንና ሕዝብን የሚጐዱ ብዙ ስህተቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በርሳቸው አመራር አማካይነት አገራችን ውስጥ በትምህርት፣ በጤና፣ በመሠረተ ልማት ግንባታና በሌሎችም ጉዳዮች ብዙ በጎ ለውጦች መምጣታቸውን ሽምጥጥ አድርገን በመካድ ጠቅላይ ሚኒስትሩን አገርን እያፈረሱ የሚገኙ ጠላት አድርጐ መክሰስ በየትኛውም መመዘኛ ጤናማ አስተሳሰብ ሊሆን አይችልም።

አራተኛ-ኮሎኔል መንግሥቱን ጨምሮ ሁሉም ቀደምት የአገሪቱ መሪዎች ከበጎም ሆነ ከመጥፎ ታሪካቸው ጋር የኢትዮጵያ መሪዎች እንደነበሩ ባልተካደበት አገር በተለየ ሁኔታ ለአቶ መለስ የአገር መሪነት ዕውቅና ለመንፈግ መሞከር በየትኛውም መመዘኛ አሳማኝ አይሆንም። ከሌሎች የአገሪቱ መሪዎች በተለየ መልኩ አቶ መለስን እንደዚህ ምክንያታዊና አሳማኝ ያልሆኑ ገደብ የለሽ ክሶችን እየደረደርን ልናወግዛቸው ስንሞክር፣ በአደባባይ በግልጽ ባንናገረውም ዞሮ ዞሮ ርሳቸውን በሚመለከት የምናቀርበው ትችት በተዘዋዋሪ “ትግሬ የሆነ ሰው ለምን ይመራናል?” ወደሚል ደረጃውን ያልጠበቀና የሕዝብን አመለካከት የማይወክል ዘረኛ ትችት ይወርድና ጠቅላይ ሚኒስትሩን ብቻ ሳይሆን ሕዝብን ያለአግባብ የሚያስከፋ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ክርክርም ኢህአዴግ ያለአግባብ እየለጠጠና እያዛባ ጭምር በተቃዋሚው ጐራ ላይ የሚያቀርበውን ክስ ከማጠናከር ባለፈ ተቃዋሚውን ጐራ የሚጠቅም ፋይዳ የለውም። በአጠቃላይ ከፍተኛ ሥልጣን በእጁ የተቆጣጠረውን የአገሪቱን መሪ በዚህ ደረጃ እየፈረጅንም መልሰን ይህንኑ ዕውቅና የነፈግነውን መሪ “ለምን ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂደህ ሥልጣንህን አትለቅም?” እያልን መጠየቅ ከራሳችን አቋም ጋር የሚቃረንና የምንፈልገውን ውጤት የበለጠ የሚያርቅብን የተሳሳተ ስልት ይሆናል።

አብዛኛዎቹ ጠቅላይ ሚኒስትሩን “ኢትዮጵያዊ አይደሉም” ብለው የሚያምኑት ሰዎች መከራከሪያ አድርገው የሚያቀርቡት ነጥብ አቶ መለስ ኤርትራዊ ደም አላቸው የሚል ነው። የሚገርመው ግን እነዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የአገር ጠላት ናቸው ብለው የሚከሱ ሰዎች አቶ መለስን ለምን ይህንን ያህል አምርረው እንደሚጠሉ ሲጠየቁ የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ምክንያት “መለስ ኤርትራን ከእናት አገርዋ ከኢትዮጵያ ያስገነጠለ ጠላት ነው” የሚል ነው። ነገር ግን እንደዚህ ብለው ለመከራከር የሚሞክሩት ሰዎች- “ኤርትራ ከኢትዮጵያ በመገንጠልዋ እንደዚህ የምትንገበገቡት የኤርትራ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነው ወይም ነበር ብላችሁ ስለምታምኑ አይደለም ወይ?” ተብለው ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ ያለጥርጥር “አዎ” የሚል ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህን ሰዎች ከዚህ የራሳቸው አቋም በመነሣት- “ታዲያ እውነተኛ እምነታችሁ ኤርትራውያን ኢትዮጵያውያን ናቸው የሚል ከሆነ አቶ መለስ ኤርትራዊ ደም

ቢኖራቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን እንድትጠራጠሩ ለምን ያደርጋችኋል?” ተብለው ሲጠየቁ ማጣፊያው ሲያጥራቸው ይስተዋላል፡፡

በመሠረቱ ኢትዮጵያዊነትን ከበጎም ሆነ ከመጥፎ ድርጊት ጋር በማያያዝ ለማንም ሰው ለመሸለምም ሆነ ለመንፈግ መሞከር የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡ በፖለቲካም ሆነ በማንኛውም መስክ በጎ ተግባር እያከናወኑ ኢትዮጵያዊ መሆን የሚቻለውን ያህል ተገቢ ባይሆንም መጥፎ ድርጊትም እየፈጸሙ ኢትዮጵያዊ ሆኖ መኖር ይቻላል፡፡ ዜግነት በኛም ሆነ በሌሎች አገሮች ከመወለድና ከሕጋዊነት አኳያ እንጂ ከበጎም ሆነ ከክፉ ተግባራት ጋር ተያይዞ የሚታይ ስላልሆነ ተግባራቸው ምንም ይሁን ምን ለአቶ መለስም የተለየ መመዘኛ አውጥተን ኢትዮጵያዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ተገቢ አይሆንም፡፡ አቶ መለስ መወደድም ሆነ መጠላት ካለባቸው በኢትዮጵያ መሪነታቸው በሚያራምዷቸው አቋሞች ነው እንጂ በሕግም ሆነ በራሳቸው እምነት ጥያቄ ውስጥ ባልገባው ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸው መሆን የለበትም፡፡

በሌላ በኩል አቶ መለስ የኢትዮጵያ መሪ ናቸው ብለው ዕውቅና መስጠት የማይፈልጉት ብዙዎቹ ሰዎች የሚያቀርቡት ምክንያትም “እኚህ መለስ በእውነተኛ የሕዝብ ምርጫ የተመረጡ መሪ ስላልሆኑ ዕውቅና ልንሰጣቸው አይገባም” የሚል ነው፡፡ የአድዋ ሕዝብም ሆነ ኢህአዴግ አቶ መለስን የመረጠው በተጭበረበረ ምርጫ ነው የሚል በመረጃ የተደገፈ ክስ ማቅረብ ባይቻልም ለአንድ የአገር መሪ ዕውቅና ማግኘት በእውነተኛ የሕዝብ ምርጫ መመረጥ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ ነው የሚባል ከሆነ ከአቶ መለስ በፊት ኢትዮጵያን ለሺ ዓመታት የመሩ የአገራችን መሪዎች በሙሉ አንዳቸውም በሕዝብ ምርጫ የተመረጡ አልነበሩም፡፡ እንኳንስ የተመረጡ ሊሆኑና ምርጫ ራሱ በአገራችን ኖሮ አያውቅም፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ሰዎች አባባል ኢትዮጵያ በታሪኳ መሪ ኖሯት የማታውቅ አገር ናት ማለት ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ የክርክር ውጥንቅጥ የምንረዳው ቁም ነገር እንደሌሎቹ አገራዊ ጉዳዮች ሁሉ የአገራችንን መሪም በተመለከተ በድጋፍም ሆነ በተቃውሞ የምናራምደው አቋም ምን ያህል ሚዛኑን የሳተ መሆኑን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ኅብረተሰቡ በዚህ ዓይነት ሚዛኑን ያልጠበቀ ፍረጃ ውስጥ ቢገባ ብዙ የማያስደንቅ ቢሆንም የፖለቲካ የመሪነት ሚና አለን የምንል ሰዎች ግን እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ በኃላፊነት ስሜትና በጥንቃቄ ማየት ይጠበቅብናል፡፡ በአቶ መለስ ዙሪያ ደጋግመው በመወራታቸው ምክንያት ብቻ እውነት አድርገን የወሰድናቸው ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመገመት አቶ መለስ በመሪነት ዘመናቸው ስለፈጸሙት ተግባርና ስለአራመዱት አቋም ከተራ ጥላቻና ፍረጃ ራሳችንን ነፃ አድርገን በመረጃ የተደገፈ ግንዛቤ

እንዲኖረን ብናደርግ በአገራችን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር እንዲኖር የራሱ የማይናቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ይህንን ለማድረግ ስንሞክርም ምንአልባትም ከሻዕቢያ ጋር በተያያዘና ህወሃት የኢትዮጵያ አንድነትን በተመለከተ ካራመዳቸው ቀደምት አቋሞች አኳያ ከሌሎች የህወሃት አመራሮች በተለየ አቶ መለስን በተዛባ ሁኔታ እንደተረዳናቸው ልንገነዘብ እንችል ይሆናል፡፡ “አቶ መለስ ኢትዮጵያን ሆን ብለው ለማዳከም ሠርተዋል” ከሚለው ሚዛኑን ያልጠበቀ አመለካከትም በተለየ ሰውዬው በቁጥር አናሳ መጠን ያለውን የትግራይን ሕዝብ እወክላለሁ ከሚለው ከህወሃት መሪነት ተነስተው ወደ የኢህአዴግና ከዚያም ወደ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪነት በሂደት መሸጋገራቸው እንደ አንድ የአገር መሪ ሙሉ ትኩረታቸውን በአገር ጉዳይ ከማድረግ ይልቅ በፖለቲካ የኃይል ሚዛን (Power Politics) ላይ እንዲያተኩሩ ነባራዊ ሁኔታ ያስገደዳቸው መሪ መሆናቸውንም መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ መሪዎች አንድን ድርጅትም ሆነ አገር ወደ በጎም ሆነ መጥፎ አቅጣጫ የመምራት የማይናቅ ሚና ያላቸው ከመሆኑም አንጻር አቶ መለስን ከኢህአዴግ አመራሮች መካከል የበለጠ የከፋ ሰው አድርገን በማሰብ እሳቸውን ልዩ የጥቃት ዒላማ አድርገን የምናደርገው ርብርብ ጠቃሚ ስልት አይሆንም፡፡ እንዲያውም በአሁኑ ወቅት ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡትና እንደሚመኙት ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ አቶ መለስ በሆነ አጋጣሚና ምክንያት ሥልጣናቸውን ቢለቁ የኢትዮጵያ የወቅቱ ችግር ይሻሻላል ወይም አይሻሻልም ብሎ ርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ አቶ መለስ ከ18 ዓመት በላይ በሥልጣን ላይ መቆየታቸው በርሳቸው አስተዳደር አገሪቱ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለሚታይበት እውነተኛ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ያልበቃች መሆኑን በራሱ የሚያረጋግጥ ቢሆንም አቶ መለስ በግላቸው ሥልጣንን የሙጥኝ ብለው ከዚህ በላይ መቆዬት እስካላሳፈራቸው ድረስ ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በሥልጣን ላይ መቀጠሉ የማይቀር ከሆነ ከሌላ የኢህአዴግ አመራር ይልቅ አቶ መለስ መሪ ሆነው ቢቀጥሉ ለአገሪቱ በአንፃራዊነት የተሻለ ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረው በዋናነት በሦስት ምክንያቶች ነው፡፡

አንደኛ - ከኢህአዴግ አመራሮች መካከል አንዱን ከሌላው መምረጥ አስፈላጊ ነው ከተባለ ከሌሎቹ የኢህአዴግ አመራሮች ይልቅ አቶ መለስ የተሻለ ለዘብተኛ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እስካሁን በኢህአዴግ ውስጥ ተፈጠሩ ከተባሉ የአቋም ልዩነቶች አንጻርም ሆነ በፓርላማም ውስጥ ሆነ በተለያዩ መድረኮች የተለያዩ የኢህአዴግ አመራር አባላት የሚያራምዱትን አቋም

ስናይ አቶ መለስ በአንጻራዊነት ከሌሎቹ በተሻለ ለዘብተኛና ከሁኔታዎች ጋር ተለዋዋጭ /flexible/ የሆነ አቋም የማራመድ ባህሪ ይታይባቸዋል፡፡

ሁለተኛ - አቶ መለስ በመሪነት በነበራቸው የረዥም ጊዜ ቆይታ እያጠፉም - እያለሙም የአገሪቱን ውስጣዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችም ሆነ አገራችን በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ እያንዣበበባት ያለውን የብሔራዊ ደኅንነት ስጋት በተሻለ ሁኔታ የመገንዘብና ከዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲው ጋርም በተሻለ የመግባባት ልምድ አዳብረዋል፡፡ ስለዚህ ዞሮ ዞሮ ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ እስከቆዬ ድረስ ከሌላ የአገሪቱን ችግሮች ለማወቅ ተጨማሪ ጊዜ ከሚጠይቅ የኢህአዴግ አባል የሆነ አዲስ መሪ ይልቅ አገራችን በአቶ መለስ መሪነት የተሻለ ልንጠቀም ትችላለች ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ሦስተኛ- አቶ መለስ ለዚህን ያህል ረዥም ጊዜ የአገር መሪ ሆነው ከቆዩ በኋላ እንደገና ወደፊት ለምን ያህል ጊዜ አገሪቱን ለመግዛት እንደሚችሉ ተጨንቀው የማሰባቸው ዕድል ከእንግዲህ የጠበበ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ ርሳቸው በውስጣቸው ምን እንደሚያስቡ ርግጠኛ መሆን ባይቻልም ከዚህ በኋላ የአቶ መለስ ጭንቀት የሚሆነው በዚህ ዓይነት ስጋትና ውጥረት በበዛበት ሥልጣን ላይ ተወስኖ መኖርን ሳይሆን በወደፊቱ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚኖራቸው ቦታ (Legacy) ምን እንደሚሆን፣ ከሥልጣን የሚለቁበት ሁኔታም እንዴት ሰላማዊ (Safe Exit) ሊሆን እንደሚችልና የወደፊቱ የርሳቸውና የቤተሰባቸው ቀሪ ሕይወትና ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል መሆኑን መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

ርሳቸው የያዙትን ሥልጣን ይዘን ያላዬን ሰዎች የርሳቸውን ቦታ ለማግኘት የምንመኘውን ያህል፣ ርሳቸው ከዚህ በኋላ በበኩላቸው የሚመኙትና የሚናፍቁት እንደኛ በነፃነት በሕዝቡ ውስጥ እንደ አንድ ዜጋ መኖርን ሊሆን እንደሚችል ቢያንስ ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ በመነሣት መገመት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይም የአቶ መለስን ጉዳይ በጥልቀትና በስክነት ልናየው ከሞከርን ከእንግዲህ እሳቸው አደጋ የሚሆኑ ከሆነ ከምንም በላይ አደጋ የሚሆኑት ለሚመሩት ፓርቲ ለኢህአዴግ ይሆን እንደሆነ እንጂ ለኢትዮጵያ ሊሆን እንደማይችል ልብ ማለት ይገባል፡፡ በአሁኑ ወቅትም "ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ አመራር የነበርን ሰዎች ሁላችንም ሥልጣናችንን ልንለቅ ይገባል" በማለት አቶ መለስ በተደጋጋሚ እየገለፁት ያለውንና በቅርቡም ድርጅታዊ ተቀባይነት እንዲያገኝ የተደረገውን አቋምም ከዚሁ ጋር አያይዞ ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡

የአቶ መለስ ተቃዋሚዎች ይህንን የርሳቸውን ሁኔታ በአግባቡ ተገንዝበን ከሁኔታው ጋር የሚጣጣም ስልት ማራመድ የምንችል ከሆነም አቶ መለስ በመጨረሻ የሥልጣን ዘመናቸው

አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሸጋግሩበትን ዕድል እንዲፈጥሩ የሚያግዝ ሚና ሊኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ ምንም ዓይነት መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ እንደ ድርጅት ባላመጣበት ሁኔታና በተለይም በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመን ላይ ገደብ /Term Limit/ ሳይጣል አቶ መለስ ሥልጣናቸውን ለቀው ኢህአዴግ በሌላ ሰው መሪነት መንግሥት ሆኖ የሚቀጥል ከሆነ ምንአልባት ኢህአዴግ እንደ ድርጅት የበለጠ ሊጠናከር ቢችልም የአገሪቱ ችግሮች ግን ከመቃለል ይልቅ የበለጠ የመባባስ ዕድል ሊያጋጥማቸው እንደሚችል መገመትም ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በአፍሪካም ሆነ በአገራችን ከተለመደው የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር በአቶ መለስ ምትክ ሥልጣን ላይ የሚቀመጠው ሰው - "እኔስ እንዴት አድርጌ ነው የአቶ መለስን ያህል ጊዜ በሥልጣን ላይ የምቆዬው?" የሚል ቀመር ውስጥ ከገባ የአገራችን ጉዳይ ከድጡ ወደ ማጡ የመግባት የከፋ ዕድል ሊያጋጥመው ይችላል፡፡

ከኢህአዴግ የአደረጃጀት ተፈጥሮ አኳያም ከአቶ መለስ ሥልጣን መልቀቅ በኋላ የትኛው የኢህአዴግ ባለሥልጣን ከየትኛው የኢህአዴግ አባል ድርጅት ለሥልጣን ይበቃል? የሚለው ጥያቄ ከድርጅትም አልፎ አገራዊ ቀውስ በማያስከትል ሁኔታ በቀላሉ ሊሣካ ይችላል ብሎ ማሰብም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ዋናው የቤት ሥራ የራሱ የኢህአዴግ ቢሆንም የአገሪቱ ህልውና ሆን ተብሎ ከኢህአዴግ ህልውና ጋር ተቆላልፎ ከሚገኝበት ከወቅቱ ሁኔታ አንጻር የኢህአዴግ ውስጣዊ ሁኔታ ሁላችንንም ሊያሳስበን ይገባል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በዚህ መልክ ስለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አስተያየት መስጠት የደፈረውም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠበቃ ለመሆን በማሰብ ሳይሆን አንድ የአገር መሪ አንድን አገር ወደ በጎም ሆነ መጥፎ አቅጣጫ በመምራት ረገድ የሚኖረው ሚና ቀላል እንደ ማይሆን ከመገንዘብ በመነጨ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስና ኢህአዴግም ከጠበበ ድርጅታዊ አመለካከት ራሳቸውን በማውጣት በአሁኑ ወቅት በሰፊው እያወሩለት የሚገኘው የሥልጣን መተካካት ጉዳይ በአንድ ፓርቲ ውስጥ የሚካሄድ የሥልጣን መተካካት ብቻ ሳይሆን በአገርም ደረጃ የፓርቲዎች የሥልጣን መተካካት እንዲፈጠር መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን አምጥቻለሁ ብሎ ሊመጻደቅ የሚችለውና የሚገባው እነ አቶ መለስን በሌሎች ሰዎች ሊተኩ የሚችሉ አመራሮች በማድረግ ብቻ ሳይሆን ራሱን ኢህአዴግን ጭምር በሌሎች ፓርቲዎች ሊተካ የሚችል ድርጅት ማድረግ ሲችል ነው፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎችም ሆን ሕዝቡ ልናበረክት የምንችለው አስተዋፅኦ መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አቶ መለስ እንደ መሪ፣ ኢህአዴግ ደግሞ እንደ ገዥ ፓርቲ ቢያንስ በመርህ ደረጃ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓትን በአገሪቱ ለመጀመሪያ

ጊዜ ዕውቅና እንደሰጠ አካል ልዩ ታሪካዊ ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ አቶ መለስ እኔ ለረዥም ጊዜ ከገዛሁ በኋላ ይህንን ማድረግ አይገባኝም የሚል ይሉኝታ ካልያዛቸው በስተቀር ከሥልጣን ከመውረዳቸው በፊት በአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሥልጣን ዘመን ላይ ሕጋዊ ገደብ እንዲጣል ቢያደርጉ የሥልጣን መተካካቱ ጉዳይ በድርጅት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአገርም ደረጃ ሕጋዊ መሠረት እንዲኖረው ሊያደርግ ይችላል።

በአጠቃላይ አንድን የአገር መሪ በሚያራምደው አቋምና በሚፈጽመው ተግባር ለመተቸትና ለመቃወም፣ ከዚያም አልፎ ለአገርና ለሕዝብ አይጠቅምም ብለን እስካሰብን ድረስ ከሥልጣኑ እንዲወርድ በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ያለን መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ ግን እንደማንኛውም የአገሪቱ ተቋም ለአገሪቱ መሪም ተገቢውን የመሪነት ዕውቅናና አክብሮት በመስጠት በአገራችን እንዲመጣ የምንፈልገውን ብሔራዊ መግባባት ማጠናከር ይገባናል።

ከዚህ በላይ ለማየት የሞከርናቸው ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርባቸው የሚገባ ዋና ዋና ጉዳዮች ቢሆኑም እንደቀላል የምናያቸውን ለብሔራዊ መግባባት እንቅፋት የሆኑን ሌሎች ጉዳዮች የሉም ማለት ግን አይደለም። የአገሪቱ ብሔራዊ ቀን ሆኖ እየተከበረ በሚገኘው በግንቦት 20 ዙሪያ፣ በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ባሉ መታሰቢያነት በሚተከሉ ኀውልቶች ዙሪያና አማርኛ ቋንቋ ብሔራዊ መግባቢያ በመሆኑ አስፈላጊነት ዙሪያ ሁሉ ገና አንድ ዓይነት መግባባት ላይ አልደረስንም። ግንቦት ሃያን ከፊሎቻችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃ የወጣበት ታላቅ ዕለት አድርገን በማየት በደስታ ስናከብረው፣ ከፊሎቻችን ደግሞ ግንቦት ሃያን በኃሳ የተከፋፈልንበትና አገራዊ አንድነታችን አደጋ ውስጥ የገባበት ክፉ ቀን አድርገን በማየት ስንረግመው እንታያለን። በዚህም ምክንያት ግንቦት 20 የድርጅት ይሁን የአገር ክብረ-በዓል እስካሁን በሕዝቡ ውስጥ ግልጽ የሆነ ግንዛቤና ተቀባይነት አልተፈጠረም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ቢያንስ ለአለፉት 40 ዓመታት በአገራችን በተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት በየትኛውም የፖለቲካ ጐራ ተሰልፎ ሕይወቱን መሥዋዕት ያደረገውን ትውልድ በሙሉ የሚወክል ሁላችንም የኛ ነው ብለን የምናምንበት አንድ አገራዊ የመታሰቢያ ሐውልት እስካሁን ሊኖረን አልቻለም። ለማንኛውም በጎ ታሪክ ለፈጸመ ድርጅትም ሆነ ግለሰብ የመታሰቢያ ሃውልት ማቆምና ገድሉ እንዲወሳ ማድረግ ተገቢና ጠቃሚ ቢሆንም አንድን አምባገነናዊ ሥርዓት ለመገርሰስ በተደረገ የአንድ ወቅት ትግል አንድ ሁሉን አቀፍ የሆነ አገራዊ ሃውልት ማቆም ሲቻል ለቀይ ሽብር ሰለባዎች አንድ ሐውልት፣ ለህወሃት ሰማዕታት አንድ ሐውልት፣ ለብአዴን ሰማዕታት አንድ ሐውልት፣ ለኦህዴድ ሰማዕታት ሌላ አንድ ሐውልት በየፊናችን በመትከል ሐውልትንም በበኩሉ የአንድነት ሳይሆን የከፋፋይነት ትርጉም እንዲኖረው

እያደረግነው እንገኛለን፡፡ በአገራችን ከአንድ በላይ ከሆኑ ብሔረሰቦች የተወለደው ሕዝብ በሚሊየን የሚቆጠር መሆኑ እየታወቀ መታሰቢያ ኃውልትን ጭምር በብሔረሰባዊ ማንነት መትከል አንድነታችን ለማጠናከር የሚጠቅም አይሆንም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በድርጅት ስም በየክልላችን የምናቆማቸው ኀውልቶች በእነዚህ ድርጅቶች ዙሪያ መሥዋዕትነት የከፈሉ ሰማዕታት ወላጆችን ሊያስደስቱ የሚችሉትን ያህል ለአገር አንድነት ብለው በኤርትራና በኦጋዴን መሥዋዕትነት የከፈሉና እስካሁን ሐውልት ያልተሠራላቸውን የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላት ወላጆችን ልብ የሚሰብሩ ኀውልቶች መሆናቸውን ማጤን ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለ ሰማዕታት ሐውልት ባሰብን ቁጥር ከአንድ እናት አብራክ የተወለዱ ልጆች አንዱ ኢህአፓ፣ አንዱ ህወሃት፣ አንዱ ደግሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት አባል የሆኑበት በርካታ እውነታ በአገራችን እንደነበረ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንድ እንዲህ ዓይነት ገጠመኝ ያላት ኢትዮጵያዊ እናት ከሦስቱ ልጆቿ ተነጥሎ ለአንዱ ልጇ ለተሠራው የመታሰቢያ ሐውልት የተሟላ ፍቅር ይኖራታል ብሎ ማሰብ ይከብዳል፡፡ ለምሳሌ ትግራይ ውስጥ የተሠራውን የሰማዕታት ሃውልት ብናይ ሃውልቱ ቢያንስ በትግሉ ወቅት መሥዋዕትነት ለከፈሉ ለሁሉም የትግራይ ልጆች መታሠቢያ እንዲሆን ቢደረግ ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን በሃውልቱ ላይ በተለየ ሁኔታ የአንድ ድርጅት ማለትም የህውሃት አርማ የተቀረጸበት ስለሆነ ቢያንስ ደርግን ለመጣል በተደረገ የትጥቅ ትግል ኢህአፓና ኢዲዩ ሆነው በትግሉ ሕይወታቸውን ያጡ የትግራይ ልጆችን የማይወክል ሆኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ባህርዳር ላይ የተሠራውን የሰማዕታት ሃውልት ብናይም ተመሳሳይ ችግር እናይበታለን፡፡ ሃውልቱ በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ታቅፈው ደርግን ለመጣል የታገሉትን የዐማራ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን ደርግ ከመውደቁ በፊትና ኢህዴን ወደ ብአዴንነት ከመቀየሩ በፊት የኢህዴን አባል በመሆን መሥዋዕትነት የከፈሉትን የሌሎች ብሔረሰቦች ታጋዮችን የረሳ ሃውልት ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ ሐውልትን በሚመለከት አሁን የሚታየው አስተሳሰብና ጅምር በዚሁ ከቀጠለና ሁሉም በራሱ ድርጅትና ዓላማ ዙሪያ ለተሠዋው የትግል ጓዱ ሐውልት ያቁም ከተባለ የሐውልት ተከላው ሥራ የት ላይ እንደሚቆም ለማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ውጤቱም የበለጠ መከፋፈልን የሚያጠናክር እንጂ ብሔራዊ መግባባትን የሚያጠናክር ሊሆን አይችልም፡፡ ለብሔራዊ መግባባት ሊያበቃን የሚችለው ሐውልት በዬቀያችን ለራሳችን የቅርብ ጓዶች የምንተክለው ሳይሆን - ያለምንም የርእዮተ-ዓለምና የፓርቲ ልዩነት በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በዚች አገር በጎ ለውጥ አመጣለሁ ብሎ በማሰብ ኢህአፓም፣ መኢሶንም፣ ኢሠፓም፣ ኢዲዩም፣

ህወኃትም፣ ብአዴንም፣ ኦህዴድም፣ ወዘተ…ሆኖ በግራም በቀኝም ለተሠዋው የትውልድ አባል ሁሉ መታሰቢያ እንዲሆን የምንተክለው አንድ ብሔራዊ ሐውልት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል አሸናፊዎች ብቻ የራሳቸውን ታሪክ የሚጽፉበትና ሁሉንም ጥቅም ጠቅልለው የሚወስዱበት፣ ተሸናፊዎች ደግሞ ሙሉ በሙሉ የሚወገዙበትና በጭካኔ የሚቀጡበት ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ሁላችንም የምንሻው ለውጥና ውጤት በሌላው ላይ ፍጹማዊ አሸናፊነትና የበላይነት ማግኘት ይሆንና በአገራችን ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካ ሳይሆን ጽንፈኝነትና መጠፋፋት የበለጠ የሚጠናከርበት ዕድል ያገኛል፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎች ከዚህ በላይ ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርባቸው ይገባል ብለን የዘረዘርናቸውን ጉዳዮች ሲያዩ "በዚህ ሁሉ ጉዳይ ብሔራዊ መግባባት ከተፈጠረማ ኢህአዴግን ልንታገልበት የሚገባን ምን አጀንዳ ይተርፈናል? ብለው ሊጠይቁና ሊጨነቁ ይችላሉ፡፡ ይህ ግን ቢያንስ በሁለት ምክንያቶች ተገቢ ጥያቄም ሆነ ጭንቀት ሊሆን አይገባውም፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት በእነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥር ይገባል ሲባል ለጉዳዮቹ ተገቢውን ዕውቅናና አክብሮት መስጠት አለብን ማለት ነው እንጂ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ልዩነት ወይም ተቃውሞ ሊኖረን አይገባም ማለት አይደለም፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በእነዚህ ጉዳዮች ብሔራዊ መግባባት ከመፍጠርም በላይ በጉዳዮቹ ዙሪያ ያሉን ልዩነቶች ከኢህአዴግ ጋር ጉራ ለይቶ ለመታገል ከበቂ በላይ የሚያስችሉ መሆናቸው ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ኢትዮጵያውያን ከላይ ለመጠቃቀስ ከተሞከሩት በርካታ ጉዳዮች በተጨማሪ በብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋ አስፈላጊነት ዙሪያም የተሟላ ብሔራዊ መግባባት ገና መፍጠር አልቻልንም፡፡ በአንድ በኩል አገራችን የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት መሆኗ ልዩ ፀጋና ጥቅም መሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉም የአገሪቱ ቋንቋዎች ህልውናቸው ተጠብቆ እንዲቀጥል ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያውያን አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ሆነን መቀጠላችን አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ሁላችንም ልንገለገልበት የሚገባን ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋ የሚያስፈልገን መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ በተጨማሪም በአገር ደረጃ ሊኖረን የሚገባው የመግባቢያ ወይም የሥራ ቋንቋ አንድ ብቻ ይሁን ወይንስ ከአንድ በላይ? በሚለው ጉዳይ ጤናማ ውይይትና ክርክር ማካሄድ አስፈላጊ ቢሆንም አማርኛ ቋንቋ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ከሚገኝበት የዕድገት ደረጃ አንጻር ቀዳሚ ምርጫ ሆኖ መቀጠሉ አጠያያቂ አይሆንም፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ባለመቻላችን በአሁኑ ወቅት አገራችን የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንጂ በአገር ደረጃ ጥቅም ላይ ሊውል

የሚችልና ሁሉንም የአገሪቱ ዜጎች ሊያግባባ የሚችል ብሔራዊ ቋንቋ የላትም። ሌላው ቀርቶ አማርኛ የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋ መሆኑን ከልባቸው መቀበል የማይፈልጉና ከዚያም በላይ አማርኛ ቋንቋን የገዥዎች ቋንቋ አድርገው በመቁጠር ሲጸየፉትና ሲያጥላሉት የሚታዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአገራችን ቀላል ቁጥር ያላቸው አይደሉም። እንዲህ ዓይነቱ የታሪክን ሂደት በተዛባ መንገድ ከመረዳት የሚመነጭ ጠባብ አመለካከት በአሁኑ የግሎባላይዜሺን ዘመን የትም ሊያደርሰን አይችልም። የሌላውን ዓለም ቋንቋ ጭምር ዐውቆ የውድድር አሸናፊ መሆን የግድ አስፈላጊ እየሆነ በመጣበት በአሁኑ ዘመን ታሪካዊ አመጣጡ ምንም ይሁን ምን አማርኛ ቋንቋን በጋራ መግባቢያነት ብንጠቀምበት ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም። በአፍ መፍቻ ቋንቋችን የመማር፣ የመሥራትም ሆነ የመዳኘት መብታችን ሳይሸራረፍ መከበር እስከቻለ ድረስ በአገር ደረጃ የመግባቢያ ቋንቋ ኑሮን በመላው አገሪቱ ተዘዋውረን የመሥራትና የመኖር ዕድላችን የበለጠ ቢጠናከር የራሳችንንም ሆነ የመጭውን ትውልድ ሁለንተናዊ ሕይወት የሚያሻሽል እንጂ የሚጎዳ አይሆንም። ስለሆነም በዚህ ረገድ የተሻለ ብሔራዊ መግባባት ፈጥረን አማርኛ ቋንቋን ከፌደራል የሥራ ቋንቋነት በተጨማሪም ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋችን ብናደርገው አንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ያለንን ፍላጎት የበለጠ የሚያጠናክርና የሚያፋጥን ይሆናል።

### *1.4 የብሔራዊ ዕርቅ መድረክ*

በአገራችን ብሔራዊ መግባባትና የመቻቻል ፖለቲካን ለመፍጠር ያግዙናል በማለት ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየናቸው ጉዳዮች ዝም ብለን ስለተመኘናቸው ብቻ የምናገኛቸው አይደሉም። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች እስካሁን ከመጣንበት የተበላሸ የፖለቲካ ባህል ተላቀን ወደዚህ ዓይነቱ ዕውቅና የማስጠትና አብሮ የመሥራት አዲስ የፖለቲካ ባህል ለመግባት ከምኞት ባለፈ አንድ ዓይነት ወደ ተግባር የመሸጋገሪያ ስልት (Mechanism) ያስፈልገናል። ይኸውም ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ለመግባት የወሰኑ የፖለቲካ ኃይሎች በመካከላቸው የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ልዩነቶች መኖራቸው እንደተጠበቁ ሆኖ ከላይ ብሔራዊ መግባባት ሊፈጠርባቸው ይገባል ባልናቸው አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ፊት ለፊት ተነጋግረው የጋራ አቋም ለመያዝ የሚያስችላቸው አንድ ዓይነት መድረክ መፍጠር ይኖርባቸዋል። እንዲህ ዓይነቱን መድረክም "የብሔራዊ ዕርቅ መድረክ" ብለን ልንጠራው እንችላለን።

ነገር ግን ይህ "ብሔራዊ ዕርቅ" የሚባለው አስተሳሰብም በዚሁ የፖለቲካ ኃይሎች የመደማመጥ ባህል ማጣት ምክንያት ራሱም የልዩነት ምንጭ ከሆኑት አጀንዳዎች ውስጥ አንዱ

በመሆኑ፣ በቅድሚያ በብሔራዊ ዕርቅ ይዘትና ትርጉም ላይም የጠራ መግባባት መፍጠር ይጠበቅብናል፡፡ ኢዴፓ የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄን በተመለከተ ያለውን አቋም በሰነድ ደረጃ አዘጋጅቶ ያቀረበ ቢሆንም ሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ግን በጉዳዩ ላይ ወጥና ግልጽ የሆነ አቋም ሲያራምዱ አይታዩም፡፡ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ የጠነከረ አቋም ላይ የሚገኝ መስሎ ሲታያቸው፣ የብሔራዊ ዕርቅ መድረክን አዲስና ከሁሉም ፓርቲዎች የተውጣጣ ጊዜያዊ የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ጥያቄ አድርገው የሚያቀርቡት ሲሆን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ኢህአዴግ በሆነ አጋጣሚ የተዳከመ መስሎ ከታያቸው በብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ ሰበብ የኢህአዴግ ዕድሜ እንዳይራዘም በመስጋት አጀንዳውን ራሳቸው መልሰው ሲያወግዙት ይደመጣሉ፡፡

በኢህአዴግ በኩል የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ ከመጀመሪያው ጀምሮ ተቀባይነት አግኝቶ አያውቅም፡፡ ኢህአዴግ ሲያስፈልገው “ኢትዮጵያ ውስጥ የተጣላ ሰው የለም” በማለት በጥያቄው ላይ የሚያሾፍበት ሲሆን፣ ሲያስፈልገው ደግሞ ለራሱ በሚያመቸው መልክ በመተርጐም ጥያቄው ሕገ-መንግሥታዊ ባልሆነ አቋራጭ መንገድ ሥልጣን የመያዝ ጥያቄ ነው በማለት ሲያወግዘው ይደመጣል፡፡

ኢህአዴግ ጥያቄውን በቅንነት ተመልክቶ በአገራችን ብሔራዊ መግባባት የምንፈጥርበትን ዕድል ለማመቻቸት ከመሞከር ይልቅ “የተጣላ ሰው የለም” እያለ ለማሾፍ መሞከሩ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ የፖለቲካ ጉዳይ አገራችን ውስጥ ሰዎች ከማጣላትም አልፎ በተደጋጋሚ ለብዙ ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነ ግጭት እየፈጠረ ባለበት አገር በዚህ መልኩ ጥያቄውን ለማራከስ መሞከር ስህተት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ታግለን ማግኘት ያልቻልነውን የፖለቲካ ሥልጣን ሁልጊዜ በብሔራዊ ዕርቅ አማካይነት በጥምር መንግሥት ወይም በሽግግር መንግሥት ወይም በአንድነት መንግሥት ማቋቋም ሰበብ ለማግኘት የምናደርገው ጥረትም በዚያው መጠን ስህተት ነው፡፡ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ከጅምሩ ሊቀበለው እንደማይችል በግልጽ እየታወቀ “የሽግግር መንግሥት ይቋቋም” እያሉ ሁልጊዜ መጮህ የኢህአዴግ መሳቂያና መሳለቂያ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ የለውም፡፡

በርግጥም ከአሁን በኋላ ፓርቲዎች እየተጠራራን የምንመሠርተው መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የለበትም፡፡ መንግሥት ሊቋቋም የሚችለው በሕዝብ ምርጫ ብቻ እስከሆነ ድረስ በሕዝብ ምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ለመያዝ ጥርስን ነክሶ መታገል እንጂ በማንኛውም ዓይነት ሌላ ሰበብ መንግሥት ለማቋቋም መሞከር ተገቢ አይሆንም፡፡ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም የሚፈለገው ሁልጊዜ እንደሚባለው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሄድበትን ሁኔታ በአገራችን

ለመፍጠር ተብሎ ከሆነም፣ ኢህአዴግ ይህንን ለማድረግ ቁርጠኛ ከሆነ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ሳያስፈልገው በራሱ ተግባራዊ ሊያደርገው ይችላል። ስለዚህ የሚያዋጣው መንገድ ኢህአዴግ ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ተገዥ እንዲሆን መታገል ነው እንጂ በእጅ አዙር በሽግግር መንግሥት ጥያቄ አስታኮ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ለማቅረብ መሞከር ትርጉም የለሽ ይሆናል።

ከሽግግር (Transition) አስተሳሰብ አንጻርም አገሪቱን አሁን ከምትገኝበት ሁኔታ ወደ አንድ የተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የግድ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጠራርተን አንድ “የሽግግር” ወይም “የአንድነት” የሚባል መንግሥት ማቋቋማችን አስፈላጊ አይሆንም። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የዕውቅናና አብሮ የመሥራት የፖለቲካ መርህን ተቀብለን ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር ብንችል በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘውን የኢህአዴግ መንግሥት በራሱ ወደ አንድ ጥሩ የፖለቲካ ምዕራፍ መሸጋገሪያ ድልድይ አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን። የግድ እኛ የገባንበት መንግሥት አስቀድሞ ካልተቋቋመ በስተቀር አገሪቱ ወደ በጎ አቅጣጫ ልትሸጋገር አትችልም ብለን ከወዲሁ ከደመደምን ግን ከመጀመሪያው የሽግግር የሚባለው መንግሥት በኢህአዴግ ተቀባይነት አግኝቶ ሊቋቋም የማይችል ሲሆን፣ በሆነ ተአምር ሊቋቋም ከቻለም አስቀድመው የርስ በርስ መተማመን ባልፈጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚፈጠር በመሆኑ ምን አልባትም አሁን ካለንበት ሁኔታ በባሰ የሽኩቻና የብጥብጥ መድረክ ከመሆን አልፎ አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ ሊያሸጋግራት የሚችል አይሆንም።

ስለዚህ የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄን በተመለከተ ኢህአዴግ “የተጣላ የለም” የሚለውን ሹፈቱን አቁሞ፣ ተቃዋሚዎችም ጉዳዩን በሽግግር መንግሥት ስም የሥልጣን ጥያቄ አድርገን ማቅረባችንን አቁመን አንድ ዓይነት መግባባት ላይ መድረስ ይጠበቅብናል። ይኸውም የብሔራዊ ዕርቅ ጥያቄ ሳይደመርና ሳይቀነስ ብሔራዊ መግባባት ልንፈጥርባቸው በሚገቡ አገራዊ አጀንዳዎች ላይ አንድ ዓይነት አቋም መያዛችንንና አንዳችን ለሌላችን ልባዊ ዕውቅና መስጠታችንን፣ በአገራችን እስካሁን በተካሄደው የፖለቲካ ትግል ለተከሰተው ደም መፋሰስና ለተሠራው ጥፋት በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይቅር መባባላችንን፣ ከእንግዲህም በመካከላችን ያለውን ልዩነት የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ለሕዝብ አቅርበን የሕዝቡን ውሳኔ ሁላችንም በጸጋ ለመቀበል መወሰናችንን በሕዝብ ፊት ተገናኝተን የምናውጅበትና ቃል የምንገባበት አንድ ታሪካዊ መድረክ መፍጠር መሆኑን በግልጽ መተማመን ይገባናል።

ስለዚህ በአገራችን እንዲካሄድ የምንፈልገው የብሔራዊ ዕርቅ መድረክ የመጨረሻ ውጤት የዕውቅናና አብሮ የመሥራት አዲስ የፖለቲካ ባህል በአገራችን መጀመሩን በሕዝብ ፊት ቃል

ከመግባትና ከማብሠር ባለፈ የሽግግር መንግሥት ማቋቋምም ሆነ አሁን አገሪቱ ውስጥ ካለው ሕግ ውጭ ወቅቱን ያልጠበቀ አዲስ ምርጫ ማካሄድ የሚሆንበት ዕድል አይኖርም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በሕዝብ ፊት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለመጀመሪያ ጊዜ ከልብ በመነጨ ትምምን ርስ በርስ ዕውቅና ከተሰጣጣንና በጋራ አገራዊ ጉዳዮቻችን አብረን ለመሥራት ከወሰን፣ ከዚያ በኋላ በአገራችን የሚካሄደው ምርጫ በሂደቱም ሆነ በውጤቱ አገርን በሚጠቅምና ሁላችንንም አሸናፊ በሚያደርግ ሁኔታ የመጠናቀቅ ዕድሉ ሰፊ እንደሚሆን ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን ለሌላችን ካለን ጥላቻ በላይ የአገራችንን ጥቅም ለማስቀደም ከልባችን ከወሰን አሁን ከገባንበት የችግር አዙሪት ሊያወጣን የሚችለው ብቸኛ አማራጭ በዚህ መንገድ የዕውቅናና አብሮ የመሥራት ፖለቲካን በድፍረት መጀመር ነው፡፡

ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይህንን የዕውቅናና አብሮ የመሥራት የፖለቲካ ባህል ለአገራችንም ሆነ ለራሳችን ጠቃሚ መሆኑን በማመን በአንድ ላይ ተቀብለን ተግባራዊ ብናደርገው ያለ ጥርጥር አገራችን በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የፖለቲካ መቻቻል የነገሠባት አገር ለመሆን ትበቃለች፡፡ ይህ ዓይነቱ ተግባርም እንደ ትውልድ ሊያኮራን የሚገባና ዘላለማዊ ሐውልት ሊተከልለት የሚገባ ታሪካዊ ገድል ለመሆን ሊበቃ ይችላል፡፡ ነገር ግን ገዥው ፓርቲ ከአገሪቱ ጥቅም በላይ የራሱ የፖለቲካ የበላይነት በልጦበትና ከስጋት ፖለቲካው መውጣት ተስኖት በተለመደው መንገድ መቀጠሉን ቢመርጥ እንኳን፣ ተቃዋሚዎች ከሱ ጋር እልህ መጋባታችንን ትተን የዕውቅናና አብሮ የመሥራት ፖለቲካን በድፍረት ማራመድ ብንጀምር ትግላችን አሁን ካለበት ደካማ ሁኔታ በአጭር ጊዜ ወደ ተሻለ ደረጃ የሚሸጋገርበት ዕድል ሊፈጠር ይችላል፡፡

ምክንያቱም ተቃዋሚዎች እስካሁን ስናራምደው የነበረው የትግል ስልት በፕሮፓጋንዳ ደረጃ ጧሂ የሆነና ኢህአዴግን የሚጐዳና የሚያዳክም የሚመስል ቢሆንም በአጠቃላይ ውጤቱ ግን ኢህአዴግን የበለጠ የሚያጠናክርና የሚጠቅም ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን የማያዋጣና ተሸናፊ ያደረገንን ስልት እርግፍ አድርገን በመተው ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ምክንያታዊ የፖለቲካ ስልት ማራመድ ብንጀምር፣ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችን በሕገ-ወጥነት እየፈረጀ የሚያፍንበትንና “እኔ ከሌለሁ እናንተ የላችሁም” በማለት የራሱን ደጋፊዎች የሚያስፈራራበትን አጀንዳ ከእጁ ላይ ማስጣል ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ስልት ማራመድ በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች በሕዝቡና በዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲው ያለንን ተሰሚነትና ድጋፍ እያጠናከረ የሚሄድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በህልውና ስጋት ምክንያት በኢህአዴግ ዙሪያ ተሰባስቦ የሚገኘው ኃይል በሂደት ሌሎች አማራጮችን ማየት የሚችልበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡

እንደዚህ ዓይነቱ መሠረታዊ የኃይል ሚዛን ለውጥ መምጣት ሲጀምርም ኢህአዴግ የማይቀር የህልውና ፈተና አፍጥጦ ስለሚመጣበት የዕውቅናንና አብሮ የመሥራት ፖለቲካን ለመቀበል የሚገደድበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህንን አቋም መውሰድ ከተሣነውም እየተጠናከረ በሚመጣው ምክንያታዊ የሕዝብ ትግል ሽንፈቱን ለመቀበል የማይገደድበት ምክንያት አይኖርም። ይህም ነው - ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን በአገራችን ለማምጣት የሚያስችለን ብቸኛ የትግል ስልት።

ተቃዋሚዎች የዚህ ስልት ኃያልነት አልታየን ብሎ እንደተለመደው ጭፍን ጥላቻንና በገዥው ፓርቲ ዙሪያ ያለውን ኃይል የህልውና ስጋት የሚያባብስ የተለመደና ተፈትኖ የወደቀ ስልት ይዘን የምንቀጥል ከሆነ ግን እኛ የበለጠ እየተዳከምን፣ በአንፃሩ ግን ኢህአዴግ የበለጠ እየተጠናከረ እንደሚሄድ የሚያጠራጥር አይሆንም። ተዋቂው ሳይንቲስት አንስታይን "እብደት አንድን ነገር ደግመው ደጋግመው እየሠሩ የተለየ ውጤት መጠበቅ ነው። /Insanity is doing the same thing over and over and expect a different out come/" እንዳለው ሁሉ እኛም የተሸነፍንበትን ስልትና መንገድ ደግመን ደጋግመን ብንሞክረው ከእስካሁኑ የተሻለና የተለየ ውጤት ሊያመጣልን አይችልም። በዚህ መንገድ የሚመጣ ለውጥ ቢኖር ኖሮ ያሳለፍነው ዐሥራ ስምንት ዓመት እጅግ ከበቂ በላይ በሆነ ነበር። በአሁኑ ወቅት እየታየ ያለው ሁኔታም ይህንኑ አደጋ በግልጽ የሚያመላክት ነው። ገዥው ፓርቲ ስለወደፊት ህልውናው አስተማማኝ ዋስትና እስካላገኘ ድረስ በዚች አገር ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሊካሄድ ይችላል ብሎ መገመትም የዋህነት ነው። ኢህአዴግ እንደ ድርጅት በሆነ ተአምር ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ቢወስን እንኳን በሚሊየን የሚቆጠረው ከታች ያለው የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ የሆነው ሕዝብ ከድርጅቱ ዕውቅናና ትዕዛዝ ውጭም ለራሱ ህልውና ሲል በራሱ መንገድ ምርጫን ለማጭበርበር መሞከሩ የማይቀር ይሆናል። ስለዚህ የተቃዋሚዎች የወደፊቱ ህልውና በዋናነት ተንጠልጥሎ የሚገኘው ይህንን ስልት ለመቀበልና ላለመቀበል በምንወስደው አቋም ነው ማለት ይቻላል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዛሬ የመንግሥት ሥልጣን ባልያዝንበት ወቅት አዲስ የፖለቲካ ባህል በአገሪቱ እንዲፈጠር መታገል ካልቻልን በሆነ አጋጣሚ መንግሥት የመሆን ዕድል ብናገኝ እንኳ እኛንም ወደፊት የሚገጥመን ጽንፈኛና ጥላቻን የሚያራምድ ተቃዋሚ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ተቃዋሚ ፓርቲ እያለን ያልገነባነው የፖለቲካ ባህልም በሆነ ተአምር መንግሥት ስንሆን ሊኖረን ስለማይችል እኛም በተራችን በሕግ የበላይነትና በሰላም ማስከበር ስም ተቃዋሚዎቻችን ማፈናችን አይቀርም። ተቃዋሚዎች እስካሁን በአገራችን ከተፈራረቁት መንግሥታት የተሻለ ሥርዓት በአገሪቱ እንደምናመጣ ርግጠኛ መሆን የሚቻለው ነባራዊውንና ብልሹውን የፖለቲካ ባህል እንዳይመለስ አድርገን የሰበርነው መሆኑን መንግሥት ከመሆናችን

በፊት በማያሻማ ሁኔታ ማሣየት ስንችል ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚከተለው የሩቅ ምሥራቅ ብሂል ጠቃሚ ትምህርት ሊሠጠን ይችል ይሆናል፡፡

ይኸውም በቀድሞ ዘመን በሩቅ ምሥራቅ ባህል  አንድ ሰው ሲያረጅ ወደ ሩቅና ሰው የማይደርስበት ተራራ ተወስዶ ይጣልና በርኀብና በመጠለያ እጦት እንዲሞት ይደረግ ነበር ይባላል፡፡ ታዲያ አንድ ቀን ይህንን ባህል ለመፈጸም አንድ ቤተሰብ ይዘጋጃል፡፡ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ወደ ተራራው እንዲጣሉ የተዘጋጁት አያት፣ ልጃቸው፣ የልጃቸው ሚስትና የልጅ ልጃቸው ይኖሩ ስለነበር የልጅ ልጅ አያቱ ወደሚጣሉበት ቦታ አብሬ ካልሄድኩ ብሎ አባቱን ያስቸግራል፡፡ የልጅ አባትም - "አባቴን ወስጄ ተራራ ላይ ጥዬ የምመጣው እኔ ነኝ፣ አንተ ልትሄድ አትችልም" ብሎ ቢከለክልም ልጅ በምሬት በማልቀስ ጭምር አብሬ ካልሄድኩ ሞቼ እገኛለሁ ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ አባት በሆነው ነገር ተገርሞ ልጁን ለምን መሄድ እንደፈለገ ይጠይቀዋል፡፡ ልጅም - "አንተም እንደ አያቴ ወደፊት ስታረጅ የት ወስጄ እንደምጥልህ ዛሬ ማየት አለብኝ" የሚል መልስ ይሰጠዋል፡፡ በልጁ መልስ የራሱን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ለማስታወስ የተገደደው አባትም ድንጋጤ ይሰማውና ጉዳዩን ደግሞ ደጋግሞ ያስብበታል፡፡ በመጨረሻም የአረጁ አባቱን ተራራ ላይ ወስዶ የመጣል ሀሳቡን በመቀየር እስከመጨረሻው ከራሱ ጋር አስቀምጦ ሲሞቱ በወግ በማዕረግ እንዲቀበሩ አደረገ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሩቅ ምሥራቅ አዛውንቶችን ሲያረጁ አንደ አሮጌ ዕቃ እያወጡ መወርወር በአገሩ ባህል ቀረ ይባላል፡፡

ይህ ታሪክ እውነት ይሁንም - አይሁንም ብሂሉ ግን ትውልድን ማስተማሪያ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ የአገራችን ብልሹ የፖለቲካ ባህል አዙሪትም ዛሬና በዛሬው ትውልድ መቆም እንዳለበት የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከብሂሉ ልንማር እንችላለን፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በቀረበው አንድ ክፍል ብሔራዊ መግባባትና የፖለቲካ መቻቻል በአገራችን ለመፍጠር የሚያስችሉንን አገራዊ አጀንዳዎች በዝርዝር ለማየት ሞክረናል፡፡ ነገር ግን እነዚህን አጀንዳዎች በሐሳብ ደረጃ ከመቀበል ጀምሮ ወደ ተግባር በመለወጡ ሂደት ገዥው ፓርቲ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የእነዚህ ኃይሎች መፍለቂያና የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነው ሕዝቡ ያሉበት ሁኔታ የማይተካ ሚና አለው፡፡ ከእነዚህ ከዋና ዋና የፖለቲካ ተዋናዮች በተጨማሪም በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ መገናኛ ብዙኃንና ሲቪክ ማኅበራት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ የዬራሳቸው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ድርሻ አላቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ በአገራችን የፖለቲካ ሂደት ወሳኙን ሚና የሚጫዎቱት አካላት በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙና በውስጣቸውም ያለው ጥንካሬና ድክመት ምን እንደሚመስል መገምገሙ ጠቃሚ ስለሚሆን በሚቀጥለው ክፍል ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክራለን፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የአገራችን ፖለቲካ ተዋናዮችና ሚናቸው

### 2.1 ኢህአዴግና የፖለቲካ ትግሉ

በ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ በጎላ ሁኔታ የሚታወቁትን ኢህአፓን፣ መኢሶንና ኢዲዩን ጨምሮ በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ታዋቂ ፓርቲዎች በተለየ ራሱን አጠናክሮ በመውጣት በመጨረሻ ደርግን ደምስሶ ለመንግሥት ሥልጣን የበቃው ድርጅት በብዙዎች ዘንድ በንቀት ይታይ የነበረው የአራት ድርጅቶች ግንባር የሆነው ኢህአዴግ ነው፡፡ የደርግ መንግሥት በሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት "እንደ አይጥ የሚሽሎከሎኩ ገንጣይ አስገንጣዮች" በሚል ንቀት በማየት እስከ 1981 ዓ.ም. ድረስ ለህወሃት ዕውቅና የመስጠትም ሆነ እጁን ለድርድር ለመዘርጋት ፍላጐት አልነበረውም፡፡ ኢህአዴግ አዲስ አበባ አጠገብ ድረስ መጥቶ አምቦ አካባቢን እስከተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስም በደርግ ዙሪያ በነበሩ ሰዎች ዘንድ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ መንግሥት ለመሆን ይበቃል የሚል ግምት አልነበረም፡፡

ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ ቤተ-መንግሥት ገብቶ ገና ሥልጣን ከመቆናጠጡም በርካታ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ከየአቅጣጫው መሰማት በመጀመራቸው የኢህአዴግ የመንግሥትነት ዕድሜ ቢበዛ ከአንድና ከሁለት ዓመት አይበልጥም ብለን የምንገምት ሰዎች ጥቂቶች አልነበርንም፡፡ በወቅቱ የኢህአዴግ ዕድሜ በርግጠኛነት ከአምስት ዓመት አይዘልም የሚል የጠነከረ እምነት የነበራቸው አንዳንድ ሰዎችም ኢህአዴግ መንግሥት በሆነ ሰሞን በየመጽሔቱ ጭምር እየታተመ ይወጣ የነበረውን የሸህ ሁሴን ጅብሪል ትንቢት ዋና ማረጋገጫ አድርገው ያዩት ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ "ኢህአዴግ ዘንድሮ ወይም ከርሞ አለቀለት" የሚለው ትንቢት ሁልጊዜ ስጋት የከረመ ቢሆንም ትንቢቱ ሁሉ ሳይሰምር ቀርቶ ኢህአዴግ የደርግን ዕድሜ በሁለት ዓመት በልጦ 19ኛ ዓመት "የንግሥና" በዓሉን በዘንድሮ ዓመት ለማክበር ተቃርቧል፡፡

የሚገርመው ነገር ይህ ሁሉ ትንቢት እስካሁን ሳይሰምር መቅረቱ ብቻ ሳይሆን፣ "ኢህአዴግ አልቆለታል" የሚለው ትንቢት ዛሬም ሳይቋረጥ የቀጠለ መሆኑ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ደግሞ እነዚህ ትንቢት ተናጋሪዎች ከፖለቲካ ትግሉ ርቀው የሚገኙ ተራ ዜጐች ብቻ ሳይሆኑ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ከፍተኛ የመሪነት ሚና ያላቸው "አንቱ" የተሰኙ ጉምቱዎች ጭምር መሆናቸው ነው፡፡ በምርጫ 97 ማግሥት ዋና ዋናዎቹ የቅንጅት አመራሮች ሳይቀሩ "ኢህአዴግን ልንጥለው የቀረን አንድ ኪሎ ሜትር ነው፤ ኢህአዴግ ሞቷል አሁን

ጥያቄው እንዴት አድርገን እንቅበረው ነው፤ ኢህአዴግ ከእንግዲህ አንድ ሰኔን ካለፈ ምላሳችን ይቆረጥ" በማለት በርግጠኛነት ሲተነብዩ ማዳመጥ በየዕለቱ የተለመደ ነበር። ታዲያ እነዚህ ኢህአዴግ አልቆለታል እያሉ ያለማቋረጥ የሚተነብዩ ሰዎች፣ ኢህአዴግ ከእነሱ ትንበያ በተቃራኒ ሥልጣን ላይ ይህንን ያህል ጊዜ ለምን መቆዬት እንደቻለ አሳማኝ ምክንያት ለማቅረብ ሲሞክሩ አይታዩም። በተለይም ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ ለዚህን ያህል ጊዜ መቆዬት የቻለው እንደ አንድ ድርጅት ጠንካራ ስለሆነ ነው ወይንስ የሱ ተቃዋሚ የሆን ድርጅቶች ደካማ ስለሆን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሲደፍሩ አይታዩም።

በኢህአዴግና በተቃዋሚዎች መካከል ያለው የአገራዊ አጀንዳ ልዩነት የራሱ የተለየ ሚዛን ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢህአዴግ እስካሁን በሥልጣን ላይ የመቆዬቱ ምስጢር ግን በአንድ በኩል እንደ ድርጅት ጠንካራ ከመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሱ ተቃዋሚዎች እንደ ድርጅት ደካማ ከመሆናችን ውጭ ሌላ ምክንያት አይኖርም። በመሠረቱ አንድ ድርጅት በአስተሳሰቡ፣ በድርጅታዊ መዋቅሩ፣ በሕዝብ ድጋፉ ወይም በአመራር አባላቱ ጥንካሬ፣ ከእነዚህ ምክንያቶች ውስጥ ቢያንስ በአንዱ ወይም በሁለቱ ጠንካራ ሳይሆን አንድን አገር በዘፈቀደ ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ሊያስተዳድር ወይም ባምባገነንነት አፍኖ ሊገዛ ይችላል ብሎ ማሰብ አይቻልም።

ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ጠንካራ ሊሆን የቻለበት ከልምዱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ በርካታ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም በተቃዋሚዎቹ ዘንድ ከመጠን በላይ የተናቀና የተጠላ ድርጅት መሆኑ በራሱ ለኢህአዴግ ጥንካሬ ትልቅ ድርሻ አበርክቷል ማለት ይቻላል። ተቃዋሚዎች ሁልጊዜ ኢህአዴግን በሕዝብ የተጠላና ያለቀለት ድርጅት እንደሆነ አድርገን ማየታችን በአንድ በኩል በኢህአዴግ ዙሪያ ትልቅ የህልውና ስጋት በመፍጠር ሌት ከቀን ተግቶ በመሥራት ተጠናክሮ እንዲወጣ ያደረገው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢህአዴግ ካለን ንቀትና ገደብ ያለፈ ጥላቻ አንጻር ኢህአዴግን እንደ ድርጅት እየገመገምን ከሱ ጥንካሬና ድክመት አንጻር የሚቃኝ ውጤታማ ስልት በመቀየስ ራሳችንን አጠናክረን እንድንወጣ አላስቻለንም። ተቃዋሚዎች ምርጫ 97ን ተከትሎ የፈጸምነው ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ስህተትም ከዚሁ ስለ ኢህአዴግ ከነበረን የተሳሳተ ግምገማ የመነጨ ነበር ማለት ይቻላል። ስለዚህ የኢህአዴግን ድክመትና ጥንካሬ በአግባቡ የመገምገም ጉዳይ ዐሥራ ስምንት ዓመታት የዘገዬ መሆኑ በራሱ የሚያሳዝን ቢሆንም ቢያንስ ዛሬ ላይ ሆነን ይህንን ማድረግ የማንችል ከሆነ ግን ተቃዋሚዎች አሁን ከምንገኝበት ተቋማዊ (Structural) ችግር ወጥተን የትም መድረስ አንችልም።

የአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥንካሬና ድክመት በዋናነት ሊመዘን የሚችለው በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ነው ማለት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ማለትም የድርጅቱ አመራር አካላት፣ የበታች አባላት፣ እነሱን የሚያገናኘው መዋቅርና መዋቅሩ ሥራውን የሚተገብርበት ስልት በአጠቃላይ ያለውን ጥንካሬና ድክመት የሚመለከት ሲሆን፤ ሁለተኛው ድርጅቱ የዓላማው መሠረት አድርጐ የሚያራምዳቸውን አገራዊ አጀንዳዎች ጥንካሬና ድክመት የሚመለከት ነው፡፡

በአፍሪካም ሆነ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንድ ድርጅት ድርጅታዊ ጥንካሬ መፍጠር እስከቻለ ድረስ ጠንካራ አገራዊ አጀንዳ ሳይኖረውም ለሥልጣን የሚበቃበት ዕድል ይኖራል፡፡ በሌሎች ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች ያለው እውነት ከዚህ የተለየ ቢሆንም እኛን በመሳሰሉ አገሮች ግን አንድ ድርጅት የቱንም ያህል ጠንካራ አገራዊ አጀንዳዎች ቢኖሩት ድርጅታዊ ጥንካሬ እስካልፈጠረ ድረስ ለሥልጣን የሚበቃበት ዕድል የጠበበ ነው፡፡ ሥልጣን በመጨበጥ ደረጃ የዚህ ዓይነት ልዩነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነገር ግን በእኛ አገር ደረጃ ድርጅታዊ ጥንካሬንና ጠንካራ አገራዊ አጀንዳዎችን አጣምሮ መያዝ ያልቻለ ድርጅት ራሱን ለሥልጣን ከማብቃት አልፎ አገሪቱን ወደ ሁለንተናዊ የዕድገት ደረጃ ለማሸጋገር አይቻለውም፡፡ ከዚህ አንጻር ኢህአዴግ በቅድሚያ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር፣ ቀጥሎ ደግሞ ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ያለውን ጥንካሬና ድክመት ለማየት እንሞክር፡፡

ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር የመጀመሪያው የኢህአዴግ ጥንካሬ የሚመነጨው ከአመራር አባላቱ ነው፡፡ በአራቱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች ውስጥ ያሉት የኢህአዴግ አመራሮች ሚና እንደየ ፓርቲዎቹ ልምድና ጥንካሬ የተለያዬ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በጥቅሉ ግንባሩን በዋናነት እየመራው የሚገኘው የአመራር ኃይል ቀላል የማይባል አቅምና ችሎታ ያለው ነው፡፡ አመራሩ በታሪክ አጋጣሚ የአንድ ትውልድ አባላትና በተቀራረበ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸው፣ በአብዛኛው ከልጅነት ጀምሮ የሚተዋወቁና በዋናነትም ብሔረሰባዊ ማንነታቸውን መሠረት አድርገው የተደራጁ በመሆናቸው ምክንያት እስካሁን በሌሎች የአገራችን ፓርቲዎች ባልታዬ መጠን ጠንካራ የርስ በርስ መተማመንና ውስጣዊ ልዩነትን አቻችሎ ይዞ የመታገል ብቃት ያላቸው አድርጓቸዋል፡፡

ለኢህአዴግ አመራሮች ትግሉ የትርፍ ጊዜ ሥራ ሳይሆን እስከ ውድ ሕይወታቸው ድረስ መሥዋዕት ለመሆን ቆርጠው የገቡበት ሞያቸው፣ እንጀራቸውና ሕይወታቸውም ጭምር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተቃዋሚዎቻቸው ሃቁን መቀበል የሚተናነቀን ቢሆንም የኢህአዴግ አመራሮች በአካባቢያቸው ያለውን የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ በአግባቡ ገምግመው መረዳት የሚችሉ፣

ተቃዋሚዎቻቸውን የማይንቁ፣ ለድርጅታቸው የበላይነት የሚጠቅማቸውን አቋም በፍጥነት መያዝና የያዙትንም አቋም በአባሎቻቸውና በደጋፊዎቻቸው በፍጥነት ለማስጨበጥ እንደ አንድ ሰው መንቀሳቀስ የሚችሉ፣ ለውጤት የሚያበቃቸውን ሐሳብ የማፍለቅና ተገቢ ስትራቴጂ የመንደፍ ብቃት ያላቸው፣ ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋርም ራሳቸውን በፍጥነት ማጣጣም የሚችሉና ፈጣን ውሳኔ የመስጠት አቅም ያላቸው፣ በቀላሉም ተስፋ የማይቆርጡና አስደናቂም የሥራ ትጋት ያላቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይም ዘመናዊና የተደራጀ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በአገራችን ከተጀመረ ጀምሮ የኢህአዴግ አመራር በጥንካሬው ተወዳዳሪ የማይገኝለት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ለኢህአዴግ ውጤታማነት ጊዜና አጋጣሚዎች የራሳቸው የማይናቅ ድርሻ ቢኖራቸውም አመራር አካሉ ያለውን ጥንካሬ በጥቂት አርጌ ጠቅላንዋዎች የያዙ ወጣቶች በደደቢት በረሃ የተጀመረውን ትግል በሂደት በማጠናከርና ይዘቱንና ቅርፁን ጭምር በመለዋወጥ ደርግን ያህል ግዙፍ መንግሥት በመደምሰስና ለሥልጣን በመብቃት በተግባር አስመስክሯል፡፡

አንድ ድርጅት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ብዙ ውስጣዊና ውጫዊ ግብኣቶች መሟላታቸው የግድ አስፈላጊ ቢሆንም የአመራር አካሉ የሚጫወተው ሚና ግን ምትክ የሌለው ነው፡፡ አንድ ድርጅት የቱንም ያህል ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ፕሮግራም ቢኖረው፣ የቱንም ያህል የሕዝብና የውጭ መንግሥታት ድጋፍ ቢኖረው፣ የቱንም ያህል የገንዘብና የሰው ኃይል አቅም ቢኖረው - በትጥቅም ይሁን በሰላማዊ ትግል ሂደት መነሻና መድረሻውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ጠንካራ አመራር እስከሌለው ድረስ የትም ሊደርስ አይችልም፡፡ በአገራችን ከህወሃት የበለጠ አገራዊ አጀንዳ ያራምዱ የነበሩና ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ በዙሪያቸው ማሰለፍ ችለው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ እንደ ጉም በነው የቀሩት በተለየ ርግማንና እድለቢሥነት ሳይሆን በዋናነት ተቻችሎ መሥራት የሚችልና በየወንዙ መማማል የማያስፈልገው የህወሃት ዓይነት ጠንካራ አመራር በውስጣቸው መፍጠር ሳይችሉ በመቅረታቸው ነው፡፡

በ1960ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ኢህአፓንና መኢሶንን የመሳሰሉት ታዋቂ ፓርቲዎች አቅጣጫ አጥተው ከተማ ላይ ይተራመሱ በነበሩበት ወቅት ህወሃት ደርግን ከመሰለ ሥርዓት ጋር የሚደረገው ትግል መካሄድ የሚገባው ከገጠር ወደ ከተማ ነው በማለት ቀድሞ ወደ ትጥቅ ትግል መግባቱ፣ ከሌሎቹ በአገሪቱ ከነበሩ አብዛኛዎቹ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት የሚከተሉና አገራዊ አጀንዳ ከሚያራምዱ ድርጅቶች በተለየም ህወሃት በወቅቱ ብሔረሰባዊ አደረጃጀትንና የብሔር ጥያቄን ቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ መምረጡ፣ የትጥቅ ትግል ከጀመረ በኋላም ምንአልባትም እንደ ድርጅት ተጠናክሮ ለመውጣት የሚያስችለውን ሁለንተናዊ ድጋፍ ከሻዕቢያ ለማግኘት በማቀድም ህወሃት የኤርትራ ጥያቄ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ነው የሚለውን

ምንም ዓይነት የታሪክ ድጋፍ የሌለውን አቋም መቀበሉ፣ ከደርግ ጋር ወደፊት የሚያደርገው ትግል ከኋላና ከጐን የመጐተትና የመጐንተል አደጋ እንዳይገጥመው በማሰብም ህወሃት አስቀድሞ ኢዲዩና ኢህአፓን የመሳሰሉ ድርጅቶችን ከትግራይ መሬት ጠራርጐ ለማስወጣት መቻሉ፣ ትግሉ ተጠናክሮ ትግራይን ነፃ ለማውጣት የሚችል መሆኑ ርግጠኛ እየሆነ ሲመጣም ትግሉን ወደ ሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ለማሸጋገርና አገራዊ ይዘት እንዲኖረው ለማስቻል በማሰብ ህወሃት ኢህአዴግን መመሥረት መቻሉ፣ በዓለም ላይ የቀዝቃዛው ጦርነት ሲያከትምና ሥልጣን ለመጨበጥ ሲቃረብም የአልባንያ ሶሻሊዝም የሚለውን ዕምነቱንና "ኢንፔሪያሊዝምን እናወድማለን" የሚለውን መፈክሩን እርግፍ አድርጐ በመተው ከአሜሪካን ባለሥልጣኖች ጋር በፍጥነት በመዶዳጀት የካፒታሊስታዊ ሥርዓት አራማጅ ነኝ ማለቱ ሲታይ ኢህአዴግ ያሰበበት ለመድረስ ምን ያህል ተለዋዋጭና ተግባርን መሠረት ያደረገ (Pragmatic) ስልት የሚጠቀም አመራር ያለው ድርጅት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ኢህአዴግ ይህንን ዓይነት ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የሚለዋወጥ ስልት በመከተል ለሥልጣን ከበቃ በኋላም የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት፣ የመሬት ፖሊሲ፣ የፌዴራል አደረጃጀትን በተመለከተ ያራመዳቸው አቋሞችና የአገሪቱን ኢኮኖሚና መንግሥታዊ ተቋማት ለመቆጣጠር ሲል በየደረጃው የወሰዳቸው ርምጃዎች ሁሉ የሚያሳዩን የኢህአዴግ አመራር ምን ያህል ከራሱ ጥቅምና የፖለቲካ የበላይነት አንጻር የሚሠራውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ጠንካራ አመራር መሆኑን ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን አሸንፈን ለሥልጣን መብቃት ያልቻልንበት አንዱ ምክንያትም ከዚህ ዓይነቱ የኢህአዴግ አመራር የበለጠ ብቃት ያለው ብቻ ሳይሆን በተወሰነ ደረጃ እንኳ መመጣጠን የሚችል አመራር መፍጠር ባለመቻላችን ነው፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የኢህአዴግን አመራር ደካማና አላዋቂ አድርጐ ለማጣጣል መሞከር የራስን ደካማነት የበለጠ ከማረጋገጥ ያለፈ ትርጉም የለውም፡፡ እውነቱን ለመናገር ከርእዮተ-ዓለምም ሆነ ከአጠቃላይ አገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ከኢህአዴግ ጋር መጣጣም ስለማይቻል እንጂ፣ በአንድ የፖለቲካ ትግል ውስጥ እንደ የኢህአዴግ ዓይነቱ የሚሠራውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ጠንካራ የድርጅት አመራር ጋር አብሮ እንደ መሥራት የሚፈለግ አጋጣሚ አለ ማለት አይቻልም፡፡

ሌላው የኢህአዴግ ጠንካራ ጐን የሚታየው በድርጅት አባላቱ ዘንድ ነው፡፡ የኢህአዴግ አባላት በትግሉ ውስጥ ከነበራቸው ቆይታና ትግሉን ከተቀላቀሉበት የተለያዩ አቅጣጫ አንጻር ጉራማይሌ ባህሪና ማንነት ያላቸው ቢሆንም በአንፃራዊነት ከሌሎች በአገራችን ካሉ ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር ጠንካራ ጐናቸው የጐላ ነው፡፡ በተለይም የኢህአዴግ አብዛኛዎቹ ነባር አባላት ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን አካላቸውንና ውድ

ሕይወታቸውን ጭምር ለዓላማቸው መሥዋዕት ለማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እንደ አመራሩ ሁሉ አብዛኛዎቹ የኢህአዴግ አባላት በትግሉ ሂደት በሚያጋጥማቸው አስቸጋሪ ሁኔታ በቀላሉ ተስፋ የማይቆርጡ፣ ከሽንፈታቸው ወይም ከድክመታቸው እንደገና ለማንሰራራት ብርታቱ ያላቸውና ሕዝብን በድርጅታቸው ዙሪያ ለማሰባሰብ ሌት ከቀን የመሥራት ትጋትና ዕልህ ያላቸው ናቸው፡፡

ከሁሉም በላይ የኢህአዴግ አባላትን ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት የሚለያቸው በመካከላቸው ጠንካራ ጓዳዊ ግንኙነት የሚታይባቸውና በተለይም ደግሞ በድርጅታቸውና በመሪዎቻቸው ላይ ጠንካራ እምነት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ የቱንም ያህል ድርጅታቸው ወይም መሪዎቻቸው የተሳሳተ አቋም ሲያራምዱ ቢያዩ፣ የኢህአዴግ አባላት በርግገው ከፓርቲያቸው የመራቅ ወይም ከሌላው ሕዝብ ጋር ሆነው ድርጅታቸውንና መሪዎቻቸውን የማማት ባህል የላቸውም፡፡ በተለያዩ የዲሥፕሊን ርምጃ ከኃላፊነታቸው ዝቅ የተደረጉ ወይም ከድርጅታቸው የተባረሩ የኢህአዴግ አባላት ጭምር የደረሰባቸውን ችግር በድርጅቱ ውስጥ ካሉ ግለሰቦች ከማያያዝ አልፈው አብዛኛውን ጊዜ ድርጅታቸውንና መሪዎቻቸውን ለማማትና ለመውቀስ ሲሞክሩ አይታዩም፡፡ እንዲያውም ልዩነታቸውንና ቅሬታቸውን በውስጣቸው አምቀው በመያዝ ጭምር የድርጅታቸውንና የመሪዎቻቸውን ስምና ክብር ከጥቃት ለመከላከል ሲጥሩ ይታያሉ፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የኢህአዴግ አባላት አቋም አገራዊ ዴሞክራሲ እንዳይጠናከር በማድረግ ረገድ የራሱ ጉዳት እንዳለው ግልጽ ቢሆንም ድርጅታቸው ውስጣዊ ችግሩን አቻችሎ ጠንካራ ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ረገድ ግን አስተዋጽኦው ቀላል አይደለም፡፡ ኢህአዴግ ላለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተነሱበትን ተቃውሞዎች በሙሉ ተቋቁሞ መንግሥት ሆኖ መቀጠል መቻሉና በተለይም ምርጫ 97ን ተከትሎ ከደረሰበት አደጋ ሁሉ እንደገና አገግሞ ዛሬ በአገሪቱ ከ4 ሚሊየን በላይ አባላት አፍርቻለሁ ለማለት መብቃቱ በተግባር የሚያረጋግጥልን ኢህአዴግ የተለየ ምትሐታዊ ኃይል ያለው ሳይሆን፣ በውስጡ ቢያንስ በብዙ አሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ጠንካራ አባላት ያሉት ድርጅት መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ “ኢትዮጵያውያን በጋራ መብላት እንጂ በጋራ መሥራት አይችሉም” የሚለውን የተለምዶ፣ ነገር ግን ምክንያታዊ የሆነ አባባል በተወሰነ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ውድቅ ማድረግ የቻለ ድርጅት ቢኖር ኢህአዴግ ነው ሊባል ይችላል፡፡ በርግጥም እንኳንስ በፖለቲካ በሃይማኖት፣ በንግድም ሆነ በተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ኢትዮጵያዊያን ያለብን አብሮ የመሥራት ችግር ሲታይ በኢህአዴግ ዙሪያ የሚታየው አብሮ የመሥራት ጽናት የሚያስቀና ነው፡፡

ሌላው ብዙዎቻችን በአግባቡ የማንገነዘበው የኢህአዴግ ጥንካሬ በውስጡ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ባህል ያለው ድርጅት መሆኑን ነው፡፡ ኢህአዴግ ድርጅታዊ ህልውናውን በሚመለከት ያሰመረውን “ቀይ መስመር” ለመዝለል የሞከረን ማንኛውንም ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ኃይል በማንኛውም ዓይነት ርህራሄ በሌለው መንገድ ለመተናኮል ወደኋላ የማይል አምባገነናዊ ድርጅት ቢሆንም ከ “ቀዩ መስመር” በመለስ ባሉ ጉዳዮች ግን የተሻለ ውስጣዊ ዴሞክራሲ ያለው ድርጅት ነው፡፡ ኢህአዴግ በተለይም የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ በተወሰነ ደረጃ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የነበረው የእኩልነት ስሜትና ዴሞክራሲያዊ ባህሪ በብዙ ርቀት የተቀዩረና ከሕዝብ ጋር ባለው ውጫዊ ግንኙነት የሚመሰገን ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌለው ድርጅት እየሆነ ቢመጣም ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር ግን ኢህአዴግ የተሻለ ውስጣዊ ዴሞክራሲ ያለውና ራሱን በራሱ ለመብላት የማይቸኩል ድርጅት ስለመሆኑ ተቃዋሚውን ጐራ በሚገባ ለማወቅ ዕድል ላገኘን ሰዎች የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

ኢህአዴግ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባህሪ በተለየ ከትጥቅ ትግሉ ወቅት ጀምሮ በውስጡ የሐሳብ ልዩነት ያነሱ አመራሮችን የክርክር መድረክ ፈጥሮ የማወያየት፣ በውይይት ሲሸነፉም የተለያዩ አማራጮችን ማለትም የሐሳብ ሽንፈትን ተቀብሎ ትግሉን የመቀጠል ወይም ትግሉን ትቶ የመቀመጥና የመሰደድ አማራጮችን ለአባላቶቹ በመስጠት በውስጡ የሚነሡ ልዩነቶችን በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመፍታት ባህል ያዳበረ ድርጅት ነው፡፡ በርግጥ እስካሁን ድረስ አከራካሪና ዕንቆቅልሽ ሆነው የቆዩ ከእሥራት፣ ከአፈናና ከግድያ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ገመናዎችም በኢህአዴግ ውስጥ መኖራቸው ብዙም አጠያያቂ አይሆንም፡፡

ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ ድርጅታዊ ጉባኤዎቻቸውን በአግባቡ የሚያካሂዱ ከመሆኑ በተጨማሪ የማያቋርጥና አታካች የሆነ የውይይትና የግምገማ ባህል ያላቸው ናቸው፡፡ የኢህአዴግ አባላት አገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮችን ከመገምገምም በተጨማሪ አባላት እርስ በርሳቸው የሚያደርጉት ግምገማ በድርጅቱ ውስጥ እንደ አንድ ጠቃሚ ተግባር ተቆጥሮ በተከታታይ የሚከናወን ነው፡፡ የግምገማ መድረኮቻቸውም ከሕዝቡ ጋር ካላቸው ግንኙነት በተለየ ግልጽነትና ድፍረት የተሞላባቸውና በድርጅቱ ውስጥ ከላይ እስከታች ባሉ ሁሉም መዋቅሮች የሚካሄዱ ናቸው፡፡ የሚካሄዱት ውይይቶችና ግምገማዎች ባልተቋረጠ ሁኔታ የሚካሄዱ በመሆናቸውም የድርጅቱ አባላት ከላይ እስከታች ድረስ እርስ በርሱ የማይጋጭ ተመሳሳይ አቋም እንዲያራምዱ በማድረግና የድርጅቱ አስተሳሰቦች በከፍተኛ ፍጥነት ለሁሉም አባላት እንዲዳረሱ በማድረግ ረገድም ከፍተኛ ብቃት ፈጥሮላቸዋል፡፡ ይህ የኢህአዴግ የግምገማ ባህል አንዳንድ ጊዜ በማያገባው እየገባ የአባላቱን የግል ነፃነት ጭምር ያለ አግባብ የሚጋፋ

ከመሆኑ አንጻር የራሱ ደካማ ጉን ያለው ቢሆንም ድርጅቱ በየጊዜው የሚገጥሙትን ድክመቶች እየገመገመና እያረመ ጠንካራ ሆኖ እንዲቀጥል አድርጉታል፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግ በውስጡ ጠንካራ አመራር፣ ብዙ ጠንካራ አባላትና በአንፃራዊነት ጠንካራ ውስጣዊ ዴሞክራሲ ያለው ድርጅት መሆኑ ኢሠፓን ጨምሮ በአገራችን እስካሁን ከታዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ከድርጅታዊ መዋቅር አንጻር የበለጠ ጠንካራ ድርጅት እንዲሆን አስችሎታል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በትግሉ ውስጥ ከምንገኘው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ሲመዘን ኢህአዴግ ከሌሎቻችን በእጅጉ በራቀ የጥንካሬ ደረጃ ላይ የሚገኝ ብቸኛ ጠንካራ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መሠረታዊ ምክንያቶች ድርጅታዊ ጥንካሬው የሚያመዝንና ግዙፍ ድርጅት ለመሆን የበቃ ቢሆንም፣ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ሊጠቀሱ የሚችሉ ድክመቶችም አሉበት፡፡ የመጀመሪያው ድክመቱ ከውስጣዊ ዴሞክራሲው በተቃራኒ ከሕዝብ ጋር ባለው ግንኙነት ግልጽነትና ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌለው ድርጅት መሆኑ ነው፡፡ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱን ወቀሳ አምኖ ለመቀበል ፈቃደኛ ባይሆንም ለዓመታት በተግባር እንዳየነው ግን፣ ከእኔ አመለካከት በስተቀር የሌላው አመለካከት ሁሉ አገር አጥፊና በሕዝብ የማይደገፍ ነው ብሎ ያላግባብ የሚያምን፣ የሱ የፖለቲካ ባላንጣዎች የሆኑ ኃይሎችን በሙሉ የአገሪቱ ጠላቶች አድርጐ ያላግባብ የሚፈርጅ (አሁን አሁን አንዳንድ በጎ ለውጦች እየታዩ ቢሆንም)፣ ያለፈ ስህተትን ለሕዝብ በይፋ የማመንና ለአጠፋው ጥፋትም ሕዝብን ይቅርታ የመጠየቅ ፍላጐትና ድፍረት የሌለው፣ ሲያስፈልገውም አባላቱም ሆነ ድርጅቱ የፈጸሙትን ስህተት ሽምጥጥ አድርጐ የሚክድ፣ የአገር ሕግንና የመንግሥት ተቋማትን ያለ ይሉኝታ ለራሱ ድርጅታዊ ፍላጐት የመጠቀም ብልጠት የሚያበዛ፣ ራሱን ሁልጊዜ ሞተው ከተቀበሩት ከንጉሡና ከደርግ ሥርዓቶች ጋር ያላግባብ ሲያነፃፅር የሚኖር፣ በአጠቃላይም በቁጥጥሩ ሥር ባዋላቸው የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን አማካይነት የሌሎች ሐሳብ እንዳይደመጥ በመገደብና የራሱን አስተሳሰብ ደግሞ ደጋግሞ በመናገር ሕዝብን በእልህ ለማሳመን የሚጥርና በአጭሩ አጉል እልህና ምንችክና የሚያበዛ ድርጅት ነው፡፡ ከዚህ አንጻርም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት አገርንና ሕዝብን በሚመለከት ከሠራቸው በርካታ ስህተቶች በላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለበትና የብዙ ሕዝብ ድጋፍ ያሳጣው ምክንያት ይህ እስካሁን ድረስ ሳይቋረጥ እየተጠቀመበት የሚገኘው የተሳሳተ የፕሮፓጋንዳ ስልቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተለይም ኢህአዴግ ለሥልጣን የበቃው የርስ በርስ ጦርነትን አሸንፎ መሆኑንና በጦርነቱ ሂደትም የተገዳደሉት የአንድ አገር ልጆች መሆናቸውን በመዘንጋት ለዐሥራ ስምንት ዓመት

ሙሉ ያለመታከት "ጉሮ ወሸባዬ" በማለት በድል አድራጊነት ሲዘምር መክረሙ ሕዝቡን ክፉኛ የሚያቅለሸልሽ ፕሮፓጋንዳ ሆኗል፡፡ እንዲያውም የኢህአዴግን የፕሮፓጋንዳ ቋሚ መርህ ልብ ብሎ ለተከታተለው ሰው ኢህአዴግ ያለጠላት ራሴን ችዬ ልኖር አልችልም ብሎ የወሰነ የሚያስመስል ነው፡፡ "ሰላምና ዴሞክራሲያችንን ሊያሳጣን"፣ ወይም "ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓታችንን በኃይል ሊያፈርስ እየመጣብን ነው" ተብሎ በጠላትነት የተፈረጀ አንድ የውጭ ወይም የውስጥ ድርጅት በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን አፍ ውስጥ የግድ እንዲኖር ማድረግ በኢህአዴግ የፕሮፓጋንዳ ስልት ቋሚ አሠራር ተደትጐ የተያዘ ይመስላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ጠላት እየፈጠሩ የራስን ህልውና ለማጠናከር የመሞከር ስልት ማን ለማን ቀድሞ እንዳስተማረ ባይታወቅም በዚህ ረገድ ሻዕቢያና ኢህአዴግ ተመሳሳይ ባህሪ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ የምንረዳው የኢህአዴግ አንዱና ትልቁ ችግሩ በአንድ በኩል "እኛና እነሱ" ከሚል ሁልጊዜ በልዩነት ላይ መቆም ከሚፈልግ የግራ አስተሳሰብ መላቀቅ አለመቻሉ ነው፡፡ በአገራችን ቀደም ሲል የነበሩ የግራ ፖለቲካ አራማጆች ልዩነት ለመፍጠር ሲሉ ብቻ በቃላትና በፊደል ልዩነት ፈጥረው ይጣሉ እንደነበረው ሁሉ ኢህአዴግም ከተቃዋሚዎቹ ጋር በሁሉም ነገር ላይ ልዩነት አለኝ ማለትን ባህሉ አድርጐ ይዞታል፡፡ ይህ ኢህአዴግ ተወልዶ ያደገበት ልዩነትን አክርሮና አጋኖ የመጠቀም ባህሪ በአገሪቱ የመቻቻል የፖለቲካ ባህል እንዳይዳብር ትልቅ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ሌላው የኢህአዴግ ድክመት ሁልጊዜ ከአሸናፊነትና ከተሸናፊነት የወታደርነት ወይም የጦረኝነት አባዜ (trauma) መላቀቅ አለመቻሉ ነው፡፡ ኢህአዴግ ለመንግሥትነት ከበቃም በኋላ በሰላማዊ ትግሉ ውስጥ ያለውን ሚና ከወታደራዊ አስተሳሰብ ለይቶ ለማየት ባለመቻሉ መቻቻልን ከመፍጠር ይልቅ ተቃዋሚዎቹን እያሳደደ በማጥቃት ምንጊዜም የተሟላ (absolute) የበላይነትንና ድልን ማግኘት የሚሻ ድርጅት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ "በድል ተጠናቀቀ"፣ "በቁጥጥር ሥር ዋለ"፣ "አከርካሪው ተመታ" የሚሉት ቃላቶች ሁልጊዜም ከኢህአዴግ አፍ የማይነጠሉት ከዚሁ ሁሉንም ነገር በጦርነት ዓይን ከማየት ባህሪ የመነጨ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የወቅቱ የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት የተከዜ ግድብን ሲመርቁ "ተከዜ በቁጥጥር ሥር ዋለች" ነበር ያሉት፡፡ ሌላው ከተሳሳተ የፕሮፓጋንዳ ስልቱ ጋር በተያያዘ የብዙ ሰዎችን ቆሽት የሚያሳርረው የኢህአዴግ ብልሹ አመለካከት "እኔ ከሌለሁ ኢትዮጵያ አትኖርም" በማለት ሲናገር የሚደመጥ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሆነ ገና 20 ዓመት ያላስቆጠረው ኢህአዴግ የሺ ዘመናት ዕድሜ ያላትን አገር "እኔ ከሌለሁ አትኖርም" በማለት በድፍረትና በትዕቢት ሲናገር በሕዝብ ዘንድ ምን ዓይነት ያነሰ ግምት ሊያሰጠው እንደሚችል በውል የተገነዘበው አይመስልም፡፡

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችለው የኢህአዴግ ድክመት የድርጅቱ አባል የሆነን ሰው ሁሉ ታማኝና ትክክለኛ አመለካከት ያለው፣ የድርጅት አባል ያልሆነውን ሰው ሁሉ ደግሞ የማይታመንና ብቃት የሌለው አድርጐ ማየቱ ነው፡፡ ስም መጥቀስ ባያስፈልግም እንዲያውም አንዳንዶቹ የኢህአዴግ አመራር አባላት የኢህአዴግ አባል ያልሆነ ወይም ኢህአዴጋዊ አመለካከት የሌለው ሰው ሁሉ ፖለቲካ የማይገባው ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ዘገምተኛ መስሎ የሚታያቸው ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ የተሳሳተ የኢህአዴግ አመለካከት ድርጅቱ በሚያራምደው አጠቃላይ ፕሮፓጋንዳም ሆነ በተለይም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በሚያካሂዷቸው የኃላፊነት ምደባዎች ጉልቶ የሚታይ ስለሆነ ሕዝቡ በኢህአዴግ ላይ ያለውን ቅሬታ በማባባስ ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ተጫውቷል፡፡ በተለይም ከምርጫ 97 በኂላ ኢህአዴግ ከፍተኛ የአባላት የምልመላ ዘመቻ ውስጥ በመግባቱ አሁን አሁን የኢህአዴግ አባል ያልሆነ መንግሥት ሠራተኛ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል፡፡ ሌላው ቀርቶ በአካባቢ የፅዳት ሠራተኛነት ወይም በመኪና አጣቢነት ተደራጅቶ ለመሥራት ሳይቀር በይፋ ባይታወጅም በውስጣዊ አሠራር ኢህአዴግ መሆን የግድ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡

እንዲህ ዓይነቱን የድርጅታቸውን አስተሳሰብ እንደ ወረደ ትክክለኛ አድርገው የተቀበሉና በተለይም ትግሉን ዘግይተው የተቀላቀሉ የድርጅቱ አባላት ከሕዝቡ ጋር ባላቸው ግንኙነት ራሳቸውን በተለየ ሁኔታ የአገር ተቆርቋሪ አድርገው እንዲያዩና ከእነሱ አስተሳሰብ የሚቃረን አስተሳሰብ ያለውን ሰው ሁሉ ደግሞ እንደ አገር ጠላት በመቁጠር አፈና እንዲፈጽሙ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡ በድርጅቱ እምነት ኖሯቸው ሳይሆን በሥርዓቱ ዙሪያ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅማ-ጥቅም ለመቀራመት በማሰብ ዘግይተው የኢህአዴግ አባል የሆኑ ሰዎችም፣ አባል በመሆናቸው ብቻ ድርጅቱ የሰጣቸውን እምነት በመጠቀም በተለያዩ የአገሪቱ የመግሥት መዋቅሮች ተሰግስገው ሕዝቡን በሙስናና በአፈና በማማረር ኢህአዴግን እንዲጠላ የማድረግ ሚናቸው ቀላል አይደለም፡፡ ከዛሬ ስድስትና ሰባት ዓመት በፊት በአነስተኛ የንግድ ሥራና በሾፌርነት ወይም በዝቅተኛ የሥራ መደብ ላይ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም ሥራ ፈት የነበሩ በርካታ ሰዎች ሊታመን በማይችል ፍጥነት ሚሊዬነር ሆነው የትልቅ ኩባንያ ባለቤት ወይም የግዙፍ ሕንጻ ባለንብረት ሆነው መታየታቸውም ሥርዓቱ በሕዝብ ዘንድ ያለውን ታማኝነት በእጅጉ ጉድቶታል፡፡

በተለይም ደግሞ የድርጅት አባል ይሁኑም-አይሁኑም የማይታወቁ አንዳንድ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎች፣ ከሕዝቡ ጋር ባላቸው ግንኙነት ራሳቸውን በተለየ ሁኔታ ለአገሪቱና ለሥርዓቱ ተቆርቋሪ አድርገው ሲያቀርቡ መታየታቸው በድርጅቱ ላይ ትልቅ ጉዳት አስከትሏል

ማለት ይቻላል፡፡ በደርግ ጊዜ የኢሠፓ አባልና የቀበሌ ተመራጭ ሆነው ሕዝቡን ሲያምሱ የነበሩ አንዳንድ ትግርኛ ተናጋሪ ሰዎች ሳይቀሩ በኢህአዴግ ዘመን እንደገና ራሳቸውን እንደ “ንጉሣዊ ቤተሰብ” በመቁጠር የሚያሳዩት የትምክህት ባህሪ ሕዝቡ በኢህአዴግ ላይ ብቻ ሳይሆን በትግራይም ሕዝብ ላይ የተዛባ አመለካከት እንዲይዝ ምክንያት ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡

ኤርትራውያን ከአገሪቱ ከወጡ በኋላ በተወሰነ ደረጃ የቀነሰ ቢሆንም በየቀበሌው ተሽቀዳድመው የኃላፊነት ድርሻ የሚይዙት፣ በየመንግሥት ቢሮ ውስጥ ተራ ሠራተኛ ሆነው እያለ የአለቃነት ሥነ-ልቦና ይዘው ሳይሾሙ አዛዥ ሆነው የሚገኙት፣ በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ጉዳይ ለማስፈጸም አማላጅ ሆነው የሚቀርቡት፣ በየሠፈሩ የጸጥታ ጉዳይ ተቆርቋሪ ሆነው የሚቀርቡትና የሚፈሩት፣ በየአምልኮት ቦታው ሰባኪና አስተናጋጅ ሆነው የሚታዩት፣ በየታክሲውና በየዕድር ስብሰባውም በኩራት በማንኛውም በሚያውቁትም ሆነ በማያውቁት ጉዳይ ላይ ትንታኔ ለመስጠት ሲደፍሩ የሚታዩት በአብዛኛው ትግርኛ ተናጋሪዎች በመሆናቸውና ኢህአዴግም ለጉዳዩ ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ ችግሩን የሚያርም ግልጽ ርምጃ ለመውሰድ ሲሞክር አለመታዬቱ ኢህአዴግንና ሕዝብን በማራራቅ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

የህወሃት አባላት በዐሥራ ሰባት ዓመቱ የትጥቅ ትግል ወቅት በቁጥር ብዛትም ሆነ በአጠቃላይ ተሳትፎ የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ከመሆኑ አንጻር ከድሉ በኋላም በበርካታ የመንግሥት ኃላፊነት ቦታዎች ጉልተው መታየታቸው የሚጠበቅና በማንኛውም የለውጥ ሂደት የሚከሰት ቢሆንም፤ በአንዳንድ እንደ መከላከያ፣ ደኅንነት፣ኢምግሬሽን፣ ኤርፖርቶች፣ የጉምሩክ ቢሮዎች፣ ውጭ ጉዳይና ፖሊስ በመሳሰሉት መሥሪያ ቤቶች ቁልፍ የሚባሉ ቦታዎች ከአግባብ በላይ ትግርኛ ተናጋሪ በሆኑ ሰዎች መያዛቸውና ይህም በየቀኑ በአገሪቱ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያ መግለጫ በሚሰጡ ባለሥልጣኖች ማንነት ሊካድ በማይችል ደረጃ ጉልቶ የሚታይ መሆኑ ሕዝቡ ኢህአዴግን ያለጥርጥር በህወሃት ልዩ ተጽዕኖ ሥር የሚገኝ ድርጅት አድርጐ እንዲያየው ዋና ምክንያት ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኢህአዴግ በእጅ አዙር አቋቁሞ የሚጠቀምባቸው 69 የሚሆኑ የድርጅት የኢኮኖሚ ተቋማት ያሉት ሲሆን ከእነዚህ የኢኮኖሚ ተቋማት ውስጥ ኀምሳ ስድስቱ ወይም ከ95% በላይ የሚሆነውን ካፒታል የሚያንቀሳቅሱት ተቋማት የህወሃት በመሆናቸው ይህ ዓይነቱ ግልጽ የበላይነት ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች እንደተለጣፊና ተጐታች አካል እንዲታዩ ከማድረጉም በላይ ህወሃት የቱንም ያህል ጥሩ ነገር ቢሠራና ቢናገር በሕዝብ እንዳይታመን አድርጐታል፡፡ ህወሃት የዚህ ዓይነት የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ የበላይነት በኢህአዴግ ውስጥ መያዙ ሳያንሰው በዚህ ረገድ የሚቀርብበትን ትችትና ወቀሳ ሁልጊዜ

ሽምጥጥ አድርጐ የሚክድ መሆኑም በሕዝቡ ዘንድ ይሉኝታ የለሽና አይነደረቅ ተደርጐ እንዲታይ አድርጐታል፡፡

ከሁሉም በላይ ኢህአዴግን በሕዝብ እንዳይታመን ያደረገው ምክንያት በአደባባይ ሲናገረው የሚውለውና በተግባር ሲፈጽመው የሚታየው ድርጊት ብዙውን ጊዜ የማይጣጣም መሆኑ ነው፡፡ የሕዝቡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ስለመከበራቸው አሰልቺ በሆነ መጠን ኢህአዴግ ሲናገር የሚደመጥ ቢሆንም ሕዝቡ በዕለት-ተዕለት ውሎው በየአካባቢው የሚያዬው እውነታ ግን ከሚነገረው በእጅጉ የተለየ በመሆኑ ኢህአዴግ የሚናገረውን ነገር ሁሉ ሕዝቡ አምኖ መቀበል እንዳይችል አድርጐታል፡፡ ኢህአዴግ ቢያንስ አንዳንድ ጊዜ ከሰብአዊ መብትና ከዴሞክራሲ ጋር በተያያዘ ጥፋት የተሠራ መሆኑን አምኖ የመቀበልም ሆነ ጥፋት በሠሩ ሰዎች ላይ ግልጽና አስተማሪ ርምጃ የመውሰድ ፍላጐት ያለው ሆኖ ስለማይታይ በርካታ ሕዝብ ኢህአዴግን ሆን ብሎ ጥፋት የሚያጠፋ ብቻ ሳይሆን ከጥፋቱም ለመማር ፍላጐት የሌለው ድርጅት አድርጐ እንዲያዬው ምክንያት ሆኗል፡፡ ብዙዎቹ የኢህአዴግ አመራሮችና አባላትም በዚህ ረገድ ሕዝቡ የሚያሰማውን ሮሮ በቅንነት ተቀብለው የድርጅታቸውን ውስጣዊ አሠራር ለመፈተሽ ከመሞከር ይልቅ ሮሮውን በደፈናው ምክንያት የለሽና የጠላት ወሬ አድርገው ማየትን ይመርጣሉ፡፡

አንዳንዶቹ የኢህአዴግ ሰዎች በዚህ ረገድ የሚሳሳቱትም እውነቱን ለመካድ ካላቸው ፍላጐት ብቻ ሳይሆን ስለ ራሳቸው ድርጅትም ካላቸው የተሳሳተ እምነት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የኢህአዴግ ዓይነት ባህሪና ማንነት ባለው ድርጅት አማካይነት የሚፈጸም የአፈና ድርጊት በደርግ ጊዜ ይደረግ እንደነበረው በግልጽ በወረቀት ላይ ተቀምጦና በድርጅት ስብሰባ ላይ በአጀንዳ እየቀረበ የሚወሰን ሳይሆን ራሱን በቻለ በግልጽ የማይታይ (Invisible) መዋቅርና ቡድን የሚወሰን ቢሆንም ብዙ የኢህአዴግ አባላት ከእነሱ ዕውቅናና ዕይታ ውጭ በድርጅታቸው ውስጥ ምንም ዓይነት ሕገ ወጥ ድርጊት እንደማይፈጸም አድርገው በመገመት ሲሳሳቱ ይታያሉ፡፡ ድርጅታቸው እነሱ ከሚያውቁት መዋቅርና አሠራር ውጭ በእንዲህ ዓይነቱ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ሊሰማራ እንደሚችል በመገመት የውስጥ ትግል አድርገው ችግራቸውን ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በድርጅታቸው ላይ የሚቀርበውን ወቀሳና ክስ በሙሉ በጭፍን ሲክዱ ስለሚታዩ የሕዝቡን ልብና አእምሮ የማሸነፍ አቅም ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

በውስጣቸው ሃቁን ምን ያህል እንደሚነጋገሩበት ባይታወቅም የኢህአዴግ ትልቅ ድክመት ሆኖ የሚታየው ሌላው ጉዳይ ኢህአዴግ በሕዝቡ ዘንድ ያለውን ድጋፍ የሚመዝንበት መንገድ ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ አብዛኛው የአዲስ አበባና የአንዳንድ የአገሪቱ ከተሞች ሕዝብ ለኢህአዴግ ምን ዓይነት አመለካከት እንዳለው በማያከራክር ሁኔታ ከብዙ ዓመት በፊት የማውቅ

ብሆንም ለመጀመሪያ ጊዜ የማልጠብቀውና አመለካከቴን የሚፈትን አስገራሚ ሁኔታ ያዬሁት በ95 ዓ.ም. ኢዴፓ መቀሌ ከተማ ላይ ውጤታማ ሕዝባዊ ስብሰባ ባካሄደበት ወቅት ነበር። ከዚያ ስብሰባ በፊት እኔም እንደ ሌላው ኅብረተሰብ የተሳሳተ የፖለቲካ አመለካከት ሰለባ ሆኘ በግልጽ ባልናገረውም በውስጤ የትግራይን ሕዝብ በሚመለከት በተወሰነ ደረጃ የተዛባ አመለካከት ስለነበረኝ ያ - የመቀሌ ስብሰባ አመለካከቴን በማስተካከል ረገድ ትልቅ እገዛ አድርጐልኛል።

የመቀሌ ነዋሪ አሉላ አባነጋ አውሮፕላን ማረፊያ ከደረስን ጊዜ ጀምሮ በጨዋነት ያሳዩን አቀባበል ያልጠበቅነውና ያስገረመን ከመሆኑም በላይ በስብሰባችን ላይ የተገኘው ሕዝብ የተከራዬነው የመዘጋጃ ቤት አዳራሽ ሊያስተናግደው ከሚችለው ከእጥፍ በላይ ነበር። በዚያ ስብሰባ ላይም ሆነ ከስብሰባው በኂላ የመቀሌ ከተማ ተወላጅ የሆኑ ሰዎችን አነጋግረን ለመረዳት እንደቻልነው አብዛኛው የመቀሌ ነዋሪ የኢህአዴግ ተቃዋሚ ነው ሊባል ባይችልም እጅግ ከምንገምተው በላይ ኢህአዴግን የሚቃወም ሰው ትግራይ ውስጥ መኖሩን በማወቃችን በጣም ተገርመን ነበር። ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የትግራይ ተወላጆች በአጠቃላይ በሥርዓቱም ሆነ በህወሃት ላይ የሚያቀርቡትን የመረረ ትችትና ተቃውሞ ስንሰማ ጥቂት በሥርዓቱ ውስጥና በሥርዓቱ ዙሪያ ያሉ ሰዎች የሚፈጽሙትን ተግባርና የሚያገኙትን ጥቅም በማየት ብቻ ሁሉንም የትግራይ ሕዝብ እንደ ተጠያቂና ተጠቃሚ መቁጠር ምን ያህል ከባድ ስህተት እንደሆነ የበለጠ የተረዳነው ያኔ ነበር።

ከዚያ በኂላ 97 ምርጫ ከመካሄዱ ከሰባት ወራት በፊት ለምርጫ ዝግጅት የሚረዳ ሥራ ለመሥራት ለአንድ ወር ያህል ከሌሎች የፓርቲያችን አመራሮች ጋር በመሆን ከጋምቤላና ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች በስተቀር ሁሉንም የአገሪቱን ክልሎች የሚያዳርስ የመኪና ጉዞ አድርገን ነበር። በዚያ ጉዞ በየገጠሩ ቀበሌ እየገባን እንዳየነው ገበሬው ሳይቀር ለኢህአዴግ የነበረው ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን ጥላቻ፣ እኛንም ከማስገረም አልፎ ያስደነገጠን ነበር። አንዳንድ በኢህአዴግ ዘመን ተጠቃሚ መሆናቸው በግልጽ በሚታይ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎችና በቀጥታም ከሥርዓቱ ጋር ባላቸው ግንኙነት በግላቸው ተጠቃሚ መሆናቸው የሚታወቅ ግለሰቦች ሳይቀሩ ሥርዓቱን አምርረው ሲቃወሙ ስናይ ኢህአዴግም ሆነ አመራር አባላቱ በመዋቅራቸው አማካይነት የሚያገኙት መረጃ ወይም መረጃውን የሚተረጉሙበት መንገድ ችግር ያለበት መሆኑን ለመገመት አስቸጋሪ አልነበረም። የምርጫ 97 ውጤት ለኢህአዴግ አስደንጋጭ የመሆኑ ጉዳይም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ኢዴፓ ፓርላማ ከገባ በኂላ በ1999 ዓ.ም ከተካሄደው ከመጀመሪያው ዙር የኢህአዴግና የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርድር መጠናቀቅ በኂላ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቅላይ

ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ከሌሎች ሦስት የኢዴፓ አመራሮች ጋር ሆኘ በጽሕፈት ቤታቸው ሳገኛቸው የጠየቅኋቸው አንዱ ጥያቄ ይህንኑ የሚመለከት ነበር፡፡ ከላይ የጠቀስኩትንና በአገሪቱ በአካል ተዘዋውሬ ያየሁትን እውነታ በመግለጽ ኢህአዴግ ሁልጊዜ ሲናገር በሚደመጠው መጠን የሕዝብ ድጋፍ ያለው መሆኑን እርሳቸውም የሚያምኑበት መሆኑን ለማወቅ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግልጽና ቀጥተኛ መልስ ባይሰጡኝም ምርጫ 97 ያስተማራቸው ነገር መኖሩን ግን ሳይጠቅሱ አላለፉም ነበር፡፡ ከዚሁ ከምርጫ 97 ጋር በተያያዘ በተገኘው ትምህርት ይመስላል- ኢህአዴግ "የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ትግልና አብዮታዊ ዴሞክራሲ" በሚል ርእስ መጋቢት 1999ዓ.ም ባሳተመው አንድ የግምገማ ሰነድ ላይ ዴሞክራሲ ሀለት ስለት ያለው አደገኛ መሣሪያ መሆኑን በመግለፅ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወደፊት ያለ አግባብ ሊዘረርበት የሚችል አደጋ መኖሩን በግልጽ ያሰፈረው፡፡ በዚህ ሰነድ ላይ ኢህአዴግ የሕዝብ ድጋፍ ማጣቱን በግልጽ አምኖ ባይቀበልም በአገሪቱ ብሔራዊ መግባባት ከመፈጠሩ በፊት በሕዝብ ምርጫ ሊዘረር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችልና ይህም በአገሪቱ ላይ እጅግ መሠረታዊና ከባድ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ስጋቱን ገልጿል፡፡ ኢህአዴግ በራሱ ድርጅታዊ ግምገማ እንዲህ ዓይነቱን ስጋት በድፍረት ቢያቀርብም ይፈጠራል ብሎ የሚሰጋውን አደጋ ለማስወገድ ሲጥር የሚታየው ግን በተግባር ብሔራዊ መግባባትን በመፍጠር ሳይሆን ሕዝቡን አሰልች በሆነ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ለማሳመን በመሞከርና ራሱን ለረዥም ጊዜ በሥልጣን ላይ ለማቆዬት በማቀድ ነው፡፡

ዞሮ ዞሮ ኢህአዴግና አመራሩ በሕዝብ ዘንድ ስላላቸው ድጋፍ በውስጣቸው እውነታውን ያጡታል ተብሎ ባይገመትም አንድን ድርጅት ወደ ከፍተኛ አደጋ ሊመራ የሚችለው ጉዳይ የደጋፊዎቹን መጠን በአግባቡ መለካት አለመቻል በመሆኑ፣ ኢህአዴግ የድጋፍ መጠኑን በአግባቡ መለካት አለመቻሉም ሆነ ወይም ለክቶ ያወቀውን በግልጽ አምኖ ለመናገር አለመድፈሩ አንዱ የድርጅታዊ ድክመቱ መገለጫ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ድርጅታዊ ጥንካሬ ጦርነትን ተዋግቶ ለማሸነፍ ወይም የተለያዩ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎችን በብቃት ለማካሄድ የሚያስችለውን ያህል፣ በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ የሚካሄድን የሕዝብ ምርጫ በርግጠኛነት ለማሸነፍ ስለማያስችል ኢህአዴግን ለመሰለ ድርጅት በድርጅታዊ ጥንካሬ ከመተማመን በላይ የበለጠ የሚጠቅመው የሕዝብን ልብና አእምሮ በማሸነፍ ረገድ ያለውን ብቃት መለካት ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር በጥንካሬና በድክመት ከተጠቀሱት ነጥቦች ውስጥ በጠንካራ ጐንነት የተጠቀሱት ሚዛን የሚደፉ ሆነው ስለሚታዩ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ከሌሎች ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር ኢህአዴግ በብዙ ርቀት ጠንካራ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ኢህአዴግ ያለውን ጥንካሬና ድክመት ለመመዘን ስንሞክር ግን እውነታው ከድርጅታዊ ጥንካሬ አኳያ ከሚገኝበት ሁኔታ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እንደማንኛውም ድርጅት ኢህአዴግም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳወቹ አገሪቱን የሚጠቅሙ ናቸው ብሎ አክርሮ የሚከራከር ቢሆንም ኢህአዴግ ከአጠቃላይ ታሪካዊ አመጣጡ፣ ከተዋቀረበት የአደረጃጀት ስልትና ከወቅታዊ የአገራችን የተካረረ የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር ፍላጐቱ ቢኖረውም እንኳ ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ አጀንዳዎችን በሚፈለገው መጠንና በሙሉ ልቡ ሊያራምድ የሚያስችል ተፈጥሮ ያለው ድርጅት አይደለም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ከታሪካዊ አነሳሱ አንጻር ስናየው የኢህአዴግን ቀዳሚ ትግል ከመጠንሰስ ጀምሮ ለመንግሥታዊ ሥልጣን እንዲበቃ በማድረጉ ሂደት ዋናውን ሚና የተጫወተውና ዛሬም ድረስ የግንባሩ ሞተር ሆኖ የሚያገለግለው ህወሃት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ህወሃት በድርጅታዊ ጥንካሬውና ግንባሩን ለድል ለማብቃት ከተጫወተው የመሪነት ሚና አንጻር ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሁሉ ጠንካራው ሆኖ እያለ በፓርላማ ካለው መቀመጫና ከሚወክለው የሕዝብ መጠን አንጻር ግን ከግንባሩ አባል ድርጅቶች ውስጥ የመጨረሻው አናሳ ድርጅት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ከሚከተለው ብሔረሰባዊ አደረጃጀት አንጻር ግንባሩ የግድ የጋራ ህልውናውን ጠብቆ እስካልቀጠለ ድረስ አንዱ የግንባሩ አባል ድርጅት ለብቻው ተነጥሎ መንግሥት ሊሆን የሚችልበት ዕድል የለውም፡፡

በአሁኑ ወቅት ህወሃት ባለው የወሳኝነት ሚና የህአዴግ ድርጅቶችን አንድ አድርጐ የመምራት ብቃት ያለው ከመሆኑ አንጻር ኢህአዴግን በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ እንደ አንድ ወጥ ድርጅት መቁጠር የሚቻል ቢሆንም ከሕግና ከብሔረሰባዊ አደረጃጀት አኳያ ዞሮ ዞሮ ኢህአዴግ የአራት ድርጅቶች ጥምረት ስለሆነ የወቅቱ የአገራችን መንግሥት በአንድ ወጥ ፓርቲ የሚመራ ሳይሆን "የጥምር መንግሥት" ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተጣምሮ አገርን የማስተዳደር ሂደት በድርጅታዊ ውስጣዊ ክፍፍል ወይም ከተጣማሪ ፓርቲዎች መካከል አንዱ በሕዝብ ምርጫ ቢሸነፍ፣ ኢህአዴግ በቀላሉ መንግሥታዊ ሥልጣንን ለማጣትም ሆነ ለውስጣዊ የኃይል ሚዛን መናጋት አደጋ ለመጋለጥ ያለው ዕድል ሰፊ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ እንደ አቶ መለስ ዜናዊ ዓይነቱ በድርጅቱ ሕይወት ውስጥ ወሳኝ ድርሻ ያለው መሪ በአገሪቱ ከሚገኙት አምስት መቶ አርባ ሰባት የምርጫ ክልሎች ውስጥ አንዱ በሆነው በአድዋ ወረዳ ሕዝብ ለፓርላማ አባልነት ሳይመረጥ ቢቀር በድርጅትም ሆነ በአገር ደረጃ ሊያስከትል የሚችለው የፖለቲካ የኃይል ሚዛን ለውጥ ቀላል የሚባል አይሆንም፡፡

ከዚህ የምንረዳው ቁም ነገር በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ ድርጅቶች አንዳቸው ለሌላቸው ህልውና የግድ አስፈላጊ መሆናቸውን ብቻ ሳይሆን በእንደዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ውስጥ የግንባሩ አባል ድርጅቶች በተለይም ህወሃት የኃይል ሚዛኑን ለመጠበቅ የሚያስችል ልዩ ልዩ ድርጅታዊ ቀመሮችን ካልተጠቀመ በስተቀር ግልጽና ዴሞክራሲያዊ የሆነ አሠራርን በመከተል ብቻ የበላይነቱን ወይም ህልውናውን አስጠብቆ መቀጠል የሚቸገር መሆኑን ነው። ኢህአዴግ በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በራሱ ውስጥም ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን ማምጣት አስቸጋሪ የሚሆነበትም በዚሁ የአባል ድርጅቶቹ ሚዛኑን ያልጠበቀ የኃይል አሰላለፍ ምክንያት ነው።

ሁለተኛ- ከወቅታዊው የአገራችን የተካረረ የፖለቲካ ሁኔታ አንጻር ኢህአዴግ ከፍተኛ የህልውና ስጋት ውስጥ ያለ ድርጅት ነው። የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ በዛሬዋና በነገዋ ኢትዮጵያ የሚኖረውን ድርጅታዊ ህልውና በይፋና ከልብ አምነን መቀበል እስካልቻልን ድረስ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለኢህአዴግ ከሥልጣን የመውረድና የመውጣት ጥያቄ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናውን የማጣትና ያለማጣት ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ኢህአዴግ የቱንም ያህል ከተቀናቃኞቹ የራቀና የበለጠ ድርጅታዊ ጥንካሬ ቢኖረው በሚስጢር በሚካሄድ የሕዝብ ምርጫ ወቅት አሸናፊ ለመሆን የሚያስችለው የሕዝብን ልብ አሸንፎ መገኘት እንጂ ድርጅታዊ ጥንካሬ በራሱ ፋይዳ ስለሌለው ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለኢህአዴግ ምንጊዜም ከፍተኛ የህልውና ስጋት ነው። ከእነዚህ ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች በመነጨ ኢህአዴግ የሚያራምዳቸውን ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች በይዘታቸው፣ በአፈጻጸም ሂደታቸውና በመጨረሻ ውጤታቸው ጭምር ከራሱ የሥልጣን ቀጣይነትና የበላይነት ጋር የግድ ተጣጥመው እንዲገኙ ለማድረግ ይገደዳል።

እነዚህ የፖለቲካ ሥልጣን የበላይነትን ለማስጠበቅ ተብለው ተግባር ላይ የሚውሉ አጀንዳዎች ደግሞ በአገሪቱ መልካም አስተዳደርንና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማምጣት ከሚያስችሉ አገራዊ አጀንዳዎች ጋር ተፈጥሮአዊ ተቃርኖ መፍጠራቸውና የሕዝብ ድጋፍ የማግኘት አቅም የሚያሳጡ መሆናቸው የማይቀር ነው። ኢህአዴግ በአንድ በኩል በፖለቲካው ረገድ ከአንድነት ይልቅ ለልዩነት፣ ከግለሰብ መብት ይልቅ ለቡድን መብት፣ ሁለንተናዊ ይዘት ካለው ፌዴራሊዝም ይልቅ ለቋንቋ ፌዴራሊዝም ትኩረት ሲሰጥ የምናየውና ቁልፍ የሚባሉ መንግሥታዊ ተቋማት ከቁጥጥሩ ውጭ እንዳይሆኑ ሲጥር የምናየው፤ በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚውን በተመለከተ የአገሪቱ መሬት ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥሩ ሥር እንዲሆን ያደረገውና የተለያዩ የንግድ ድርጅቶችን አቋቁሞ በእጅ አዙር ሲነግድ የሚታየው ከዕውቀት

ኢዬጋ ኢዬጋ ኢዬጋ

ማነስ ወይም ሆን ብሎ አገርን ለመጉዳት በማሰብ ሳይሆን ከዚሁ የፖለቲካ ሥልጣኑን የበላይነት ጠብቆ ለመቀጠል ከመነጨ ፍላጐቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ ለፖለቲካ የኃይል ሚዛን የበላይነት /power politics/ የሚሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያትም በአገራችን በሚያራምዳቸው አጀንዳዎች በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት የዴሞክራሲ፣ የነፃ ምርጫ፣ የነፃ ፕሬስና የሕዝባዊ ተቋማት ግንባታ ሂደቶች እንዳልተጠናከሩ እየታየ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም ይልቅ የራስን የሥልጣን የበላይነት ያስቀደመ ስልትም ኢህአዴግን የተሟላ የሕዝብ ተቀባይነት /Legitimacy/ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ደካማ አቋም ያለው ድርጅት እንዲሆን አድርጐታል ማለት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ ጠንካራና በአብዛኛው ሕዝብ ተቀባይነት ያገኙ አገራዊ አጀንዳዎች ሳይኖሩት ድርጅታዊ ጥንካሬውንና የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ድክመት በመጠቀም ለረዥም ጊዜ በሥልጣን ላይ የመቆየት ዕድል ሊኖረው ቢችልም፣ በዚህ አቅጣጫ ተጉዞ የአገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች በዘላቂነት መፍታትም ሆነ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ ልባዊ ተቀባይነት ማግኘት ግን አይችልም፡፡ በዚህ አቋም እስከገፋበት ድረስም የወደፊቱ የአገሪቱ ታሪክ የሚኖረው ቦታ አሉታዊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መጨረሻ ላይም የሚፈራው የህልውና አደጋ በከፋ መልኩ አፍጥጦ መምጣቱ የማይቀር ይሆናል፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ እንደ ድርጅታዊ ጥንካሬው ከአገራዊ አጀንዳዎችም አንጻር እንዴት ጠንካራ ድርጅት ሊሆን ይችላል? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ስንሞክር ዞርዞሮ የምንሄደው ወደ አብሮ የመሥራትና የዕውቅና የፖለቲካ ባህል ጉዳይ ይሆናል፡፡

በመጀመሪያ ኢህአዴግ የሚያራምዳቸውን አገራዊ አጀንዳዎች የሥልጣን የበላይነቱን ከማስጠበቅ ዓላማ በፀዳ መልኩ ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም አንጻር ብቻ መዝኖ ማራመድ የሚችለው በአብሮ መሥራትና ዕውቅና በመስጠት የፖለቲካ ባህል መፈጠር የህልውና ስጋቱ ሲወገድለት ነው፡፡ የኢህአዴግ የህልውና ስጋት ሲወገድም ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ተጠቃሚ የሚሆን ከመሆኑም በላይ አገሪቱም ለሁለንተናዊ እድገትዋ የሚበጁ አጀንዳዎችን የማግኘትና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን የማስተናገድ ዕድሏ በዚያው መጠን የሰፋ ይሆናል፡፡

የአብሮ መሥራትና ዕውቅና የመስጠት የፖለቲካ ባህል ሊፈጠር የሚችለው በኢህአዴግና በተቃዋሚ ፓርቲዎች የጋራ ጥረት ቢሆንም ኢህአዴግ በአባል ድርጅቶቹ መካከል ከሚታዩው ያልተመጣጠነ የኃይል ሚዛን ችግር መውጣት የሚችለው ግን በራሱ ጥረት ብቻ ነው፡፡

ይኸውም ከህወሃት የመጀመሪያ የምሥረታ ታሪክ ጀምሮ ኢህአዴግ መንግሥት ለመሆንና ዐሥራ ስምንት ዓመትም በሥልጣን ላይ ለመቆየት የተጠቀመበት ስልት አንድ ቦታ ላይ እድገቱን ጨርሶ ተቃራኒ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በመገንዘብ በድርጅቱ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ ማካሄድ ይገባዋል። ይህ መሠረታዊ ለውጥም በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል ያለውን የብሔር አጥር አፍርሶ ወደ አንድ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅትነት ከመለወጥ ያነሰ ሊሆን አይችልም። ይህ መሆን ሲችል ነው በአገሪቱ ውስጥ የኢህአዴግ፣ በኢህአዴግ ውስጥ ደግሞ የህወሃት የህልውና ስጋት ተፈቶ የአገሪቱን ፖለቲካ ወደ አንድ አዲስ የተሻለ ምዕራፍ ሊያሸጋግረው የሚችለው።

ኢህአዴግ የትጥቅ ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣትና መንግሥትም ሆኖ በሥልጣን ላይ ለመቆዬት የሚያስችሉት ብዙ ደፋርና መራራ አቋሞችን እየወሰደ ከዛሬ ለመድረስ የበቃ ድርጅት ነው። አሁንም የትግሉ የመጨረሻ ውጤት አገሪቱን ወደ ተሻለ ደረጃ በማሸጋገርና ኢህአዴግንም በበጎ የታሪክ ምዕራፍ ላይ በማስቀመጥ እንዲቋጭ ለማድረግ ከፈለገ ዛሬም ለሠላሳ ዓመታት ያራመደው አቋም ላይ ተቸክሎ ማሰብ የለበትም። ምክንያቱም ኢህአዴግ በ1960ዎቹ መጨረሻ የትጥቅ ትግል ሲጀምር አገሪቱ ከነበረችበት ሁኔታ በ1983 ዓ.ም. ለሥልጣን ሲበቃ አገሪቱ የነበረችበት ሁኔታ እጅግ የተለየ የመሆኑን ያህል፣ በ1983 ዓ.ም. የነበረችበትም ሁኔታ ከዐሥራ ስምንት ዓመታት የኢህአዴግ አስተዳደር በኋላ ዛሬ በ2002 ዓ.ም. ከምትገኝበት ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ በእጅጉ የተለየ ነው። ኢህአዴግ የቆምኩበት መሠረት ነው ብሎ የሚያምንበት የብሔር-ብሔረሰቦች ጥያቄም በአለፉት 34 ዓመታት አገሪቱ ካለፈችበት የለውጥ ሂደት ጋር ተያይዞ የተለየ ቅርፅና ይዘት እየያዘ መጥቷል።

ኢህአዴግ በአግባቡ የተረዳው ባይመስልም ላለፉት ሦስት ዐሥርት ዓመታት አገሪቱ ያለፈችበት የለውጥ ሂደት ቀላል የሚባል አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ራሱ ትውልዱም እንደ ትውልድ በከፍተኛ መጠን ተቀይሯል። ኢህአዴግ የብሔር ጭቆናን ዋና መነሻ አድርጎ የዛሬ 35 ዓመት ወደ ጫካ ከገባ በኋላ የተወለደው የአገሪቱ ዜጋ ዛሬ ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ ከ60% በላይ ሆኗል። ይኸ ሰፊ ትውልድ ኢህአዴግ ከ35 ዓመት በፊት ያስብ በነበረው መጠን አሁንም የአገሪቱ አንገብጋቢ ችግር የብሔር ጥያቄ ነው ብሎ ያስባል ማለት ያስቸግራል። በሌላ በኩልም ዛሬም ጭምር በተለያዩ አገራዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች የአገሪቱ አንገብጋቢ ችግር የብሔር ጥያቄ ነው ብለው የኢህአዴግን አቋም ይጋራሉ የሚባሉት የኅብረተሰብ ክፍሎችም ቢሆኑ ከ18 ዓመታት የኢህአዴግ አገዛዝ በኋላም የብሔር ጥያቄአችን ተመልሶልናል ብለው በሌላ አገራዊ አጀንዳ ዙሪያ ሲያተኩሩ እየታየ አይደለም። ዛሬም በአገሪቱ ዩኒቨርስቲዎች ከብሔር መብት ጋር

በተያያዘ የተለያየ ጥያቄ እያነሱ ኢህአዴግን ሲፈታተኑ የሚታዩት ወጣቶች ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ ገና በአንቀልባ ታዝለው የነበሩና በራሱ በኢህአዴግ የትምህርት ፖሊስና የኀብረተሰብ ዕነፃ (Social engineering) ተኰትኩተው ያደጉ ናቸው። ከዚህ የምንረዳው ኢህአዴግ ድጋፍ እያጣ የመጣው ለአገር አንድነት የበለጠ ትኩረት እሰጣለሁ በሚለው የኀብረተሰብ ክፍል ብቻ ሳይሆን ለብሔር ጥያቄ የበለጠ ትኩረት በሚሰጠው የኀብረተሰብ ክፍል ጭምርም መሆኑን ነው።

በኢህአዴግ ዘመን ተወልደውና የኢህአዴግን ፕሮፓጋንዳ እያዳመጡ ያደጉ ወጣቶች ሳይቀሩ የብሔር ጭቆና ዛሬም አለ ብለው ኢህአዴግን ሲታገሉ የሚታይ ከሆነ ይህ የሚያሳየው ኢህአዴግ ጫካ ለመግባት ምክንያት ሆኖኛል የሚለውን የብሔር ጥያቄ እየፈታው ሳይሆን በራሱ የአገዛዝ ዘመንም እንደ አዲስ እየፈጠረውም ጭምር መምጣቱን ነው። በምርጫ 97 ወቅት ቀላል የማይባል የአገሪቱ ሕዝብ የአንድነት ጠበቃ ነኝ የሚለውን ቅንጅትን ብቻ ሳይሆን የብሔር ጥያቄን ቀዳሚ አጀንዳ አድርገው የተደራጁትን በእነ ፕሮፌሰር በየነ፣ ዶ/ር መረራና አቶ ቡልቻ የሚመሩትን ድርጅቶች ጭምር ሲመርጥ መታየቱም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። ኢህአዴግ 18 ዓመታት ሙሉ በብሔር ጥያቄ ዙሪያ ሲሰራ ኖሮ በመጨረሻ የሚያገኘው ውጤት በምርጫ 97 እንደታየው ዓይነት የሁለቱንም ጐራ ማለትም የአንድነትም ሆነ የብሔር ጥያቄ ደጋፊ ነኝ የሚለውን ኀብረተሰብ ድጋፍ ማጣት የኖ የሚቀጥል ከሆነ ከዚህ በላይ የያዘውን አጀንዳም ሆነ የአደረጃጀት ስልቱን ቆም ብሎ እንዲፈትሽ ኢህአዴግን የሚያስገድድ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም።

ወደፊትም በዚህ ረገድ እየታየ ያለው ችግር የበለጠ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑና በአገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ጥያቄዎችም ይዘታቸውን በዚያው መጠን እየቀየሩ መምጣታቸው የማይቀር ይሆናል። በተለይም ኢህአዴግ ራሱ እየተናገረው እንደሚገኘው በአሁኑ ወቅት የብሔር ብሔረሰቦች መብት በመርህ ደረጃም ብቻ ሳይሆን በተግባርም በአገራችን ተከብሯል ብሎ የሚያምን ከሆነና የወቅቱ የአገራችን አንገብጋቢ ጥያቄ ከድህነት የመላቀቅ ጉዳይ ከሆነ ኢህአዴግም ከወቅቱ የአገሪቱ ችግሮች ጋር የሚጣጣም አዲስ የአደረጃጀትና የአጀንዳዎች ይዘት ለውጥ ማድረግ ይጠበቅበታል። ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ሕዝቡ ባልተቋረጠ ሁኔታ እያቀረበው ያለውን ተቃውሞና በየአካባቢው የሰው ሕይወት መጥፋትን ያስከተሉ በርካታ የፖለቲካ ግጭቶች መከሰታቸውን በተቃዋሚዎቹ እኩይነት ወይም በሕዝቡ የግንዛቤ ማነስ እያሳበበ አቃሎ ማየቱን የሚቀጥልበት ከሆነ ውሎ አድሮ አጠቃላይ የህልውና አደጋ ሊፈጥር የሚችል የሕዝብ ተቃውሞ መከሰቱ አይቀርም። የሕዝብ ብሶት በዋናነት ርባና

የሌለው ለውጥ /Reform/ ከማጣትና መተንፈሻ ከሚያሳጣ አፈና የሚመነጭ መሆኑን ተገንዝቦ ኢህአዴግ ድርጅታዊም ሆነ አገሪዊ ተጨባጭ የለውጥ ርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡

አሁን አሁን ኢህአዴግ የውጤት መለኪያ አድርጐ እያቀረበው የሚገኘውም ሆነ በኅብረተሰቡም ዘንድ የተሻለ ተቀባይነት እያገኘበት የመጣው ጉዳይ ፖለቲካ ሳይሆን የልማት ሥራ መሆኑ የሚያሳየውም ከምንም ነገር በላይ የአጀንዳ ለውጥ አስፈላጊነትን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ የፖሊሲ ችግርና ድክመት አለብኝ ከማለት ይልቅ የአፈጻጸም ድክመት አለብኝ ማለትን የሚመርጥ ቢሆንም የአፈጻጸም ችግር ዞሮ ዞሮ በዋናነት ከፖሊሲ ችግር የሚመነጭ መሆኑን የዘነጋው ይመስላል፡፡ አንድ ፖሊሲ ሲቀረጽ የፖሊሲው ትክክለኛነት በዋናነት የሚለካው “ፖሊሲው በአግባቡ ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል ወይ?” የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ባለው ብቃት ስለሆነ በአሁኑ ዘመን ፖሊሲን ከአፈጻጸም ለይቶ ማየት የሚቻል አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድ ፖሊሲ በወረቀት ላይ ስለሰፈረ ብቻ ጥሩ ፖሊሲ ነው ሊባል የሚችል ከሆነ በወረቀት ላይ የሚያማምሩ ፖሊሲዎችን ቀርጾ የማቅረብ ጉዳይ ለማንኛውም አካል ከባድና የተለየ ጥረትና ዕውቀት የሚጠይቅ ሥራ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ብዙውን ጊዜ በአፈጻጸም ላይ የሚታዩት የኢህአዴግ ድክመቶች ዞሮ ዞሮ የፖሊሲ ቀረጻ ድክመት ከመሆን ሊድኑ አይችሉም፡፡

የብሔር ጥያቄ ኢህአዴግን ዛሬ ላይ ለማድረስ ቀላል የማይባል ሚና መጫዎቱ የማይካድ ቢሆንም፣ ዛሬ የብሔር ጥያቄ መልስ አግኝቷል ከተባለ ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በኋላ ጥያቄው ለኢህአዴግ ተመሳሳይ አገልግሎት እየሰጠ ወደፊት መቀጠል ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ በዚህ ረገድ መሠረታዊ የአቋም ለውጥ ቢያመጣ የአገሪቱንም ሆነ የራሱን ድርጅታዊ ደኅንነት ከከፋ አደጋ የሚታደግ ታሪካዊ ርምጃ ሊሆን ይችላል፡፡ በጉዳዮች ተፈጥሯዊ የለውጥ ሂደት /evolution/ ለጋ የነበረው እየጠነከረ፣ ጠንካራ የነበረው እየዛለና እያረጀ መምጣቱ ስለማይቀር በኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል ያለው የኃይል ሚዛን እንደነበር ይቀጥላል ብሎ ማመን አይቻልም፡፡ ኢህአዴግ ሥልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ኢህዴንን ወደ ብአዴንነት መቀዬሩ አስፈላጊ ሆኖ እንደአገኘው ሁሉ ከዚህ በኋላ ደግሞ ኢህአዴግን ወደ አንድ ወጥ አገራዊ ፓርቲነት መቀዬር ለራስ ድርጅታዊ ህልውናም ሆነ ለአገር ደኅንነት የሚጠቅም ወቅታዊ ርምጃ ይሆናል፡፡ ከምንም ነገር በላይ ኢህአዴግ በድርጅት ደረጃ ሊወስድ የሚችለው አቋም ወሳኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም በመጨረሻ የሥልጣን ዘመናቸው ለዚህ ጉዳይ የተለየ ትኩረት ቢሰጡ የሕይወት ተልኮአቸውን በበጎ ተግባር ለመደምደም የሚያስችላቸው በጎ አጋጣሚ ሊሆን ይችላል፡፡

ኢህአዴግ በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች እንዲህ ዓይነቱን ደፋር መዋቅራዊ ለውጥ በራሱ ላይ ለማካሄድ ሲደፍር ባይታይም አገሪቱ እያለፈችበት የምትገኘው የለውጥ ሂደት በራሱ ኢህአዴግን ቀስ በቀስ ወደ አንድ አዲስ አቅጣጫ እየገፋው መሆኑን ግን እያዬን ነው፡፡ ኢህአዴግ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክና ስለ ኢትዮጵያ አንድነት፣ ስለ ኤርትራና ሶማሊያን የመሰሉ ጐረቤት አገሮችና የመገንጠል ጥያቄን ስለሚያራምዱ የፖለቲካ ድርጅቶች ሥልጣን በያዘባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የነበረው አቋምና ዛሬ ከዐሥራ ስምንት ዓመታት መንግሥትነት በኋላ እነዚህንና እነዚህን በመሳሰሉ ሌሎች አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያለው አቋም አንድ ዓይነት ነው ሊባል አይችልም፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግ ከሽንፈት የመነጨ መለወጥ እንዳይመስልበት እየሰጋ በይፋ ሊናገረው አይፈልግም እንጂ በውስጡ ያለው ለውጥ ረዥም ርቀት የተጓዘ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡

በተቃዋሚው ጎራ ዙሪያ ያሉ ብዙ ሰዎች ኢህአዴግ "አልተለወጠም" ብቻ ሳይሆን "ሊለወጥም አይችልም" የሚል ጠንካራ አቋም ያላቸው ሲሆን፣ እንደዚህ ብለው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ምክንያት ግልጽ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ኢህአዴግ ሊለወጥ ይችላል ብሎ ማሰብ በራሱ ከጭፍን የፖለቲካ አመለካከት አስወጥቶ ወደ ምክንያታዊ ፖለቲካ የሚያስገባቸው አመለካከት ስለሚሆን ተጨባጭ ለውጥ ቢያዩም ባያዩም ሆን ብለው ሊቀበሉት አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ኢህአዴግ በአንድ ጉዳይ ላይ ተለውጧል ወይም ወደፊት ሊለወጥ ይችላል የሚል አመለካከት መያዝ ከተጀመረ የጭፍን ተቃውሞ መሠረት የሆነውና "ኢህአዴግ አገሪቱን ለማዳከምና ለመበታተን የመጣ ኃይል ነው" የሚለውን የጥላቻ አቋም ከመሠረቱ ስለሚንደውና በአጠቃላይም የተቃውሞውን ትግል አጠቃላይ ይዘት ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት እየተከተለው ወደሚገኘው ምክንያታዊ ፖለቲካ ስለሚቀይረው ሊቀበሉት አይፈልጉም፡፡ በድርጅት ደረጃም ባይሆን አንዳንድ ሰዎች ግን እንዲህ ዓይነቱን አቋም የሚያራምዱት ሆን ብለው ጭፍን ፖለቲካ ለማራመድ ብለው ሳይሆን ቀደም ሲል የጠቃቀስናቸው ኢህአዴግ ለሥልጣን የበላይነቱ ከሚገባው በላይ ቀናዒ በመሆን የሚያራምዳቸውና የሚፈጽማቸው ተገቢ ያልሆኑ አቋሞች በዚህ መልኩ እንዲያስቡ ምክንያት ስለሚሆናቸው ነው፡፡ ሌሎቹን ከአገራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን በርካታ ጉዳዮች ለጊዜው ትተን የሚከተሉትን ምሳሌዎች ብቻ ለማየት ብንሞክር ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል፡፡

ይኸውም አንድ የአገሪቱን ውስብስብ የፖለቲካ ሁኔታ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መዝኖ ለማየት የሚቸገር፣ ነገር ግን ለአገሩ ተቆርቋሪ የሆነ ዜጋ በኢህአዴግ ዘመን አገሪቱ የኤርትራ ቅኝ ገዥ ነች ተብላ ስትከሰስ፣ አገሪቱ ኤርትራንና የባህር በሯን ቀይ ባህርን እንድታጣ ሲደረግ፣

ኢዴፓ

ኤርትራ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች በኋላ ኤርትራውያን በኢትዮጵያ ጉዳይ አዛዥ-ናዛዥ ሆነው ሲታዩ፣ አገሪቱ የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ያላት አዲስ አገር ናት ተብላ ስትንኳሰስና ከሌሎች አገሮች በተለየ በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ውስጥም መገንጠል መብት ሆኖ ሲካተት ሲያይ ለአገሩ ተቆርቋሪ በመሆን ብቻ ኢህአዴግ አገሬን ሊያፈርስብኝ ነው ብሎ ቢያስብና ቢሰጋ የሚያስደንቅ አይሆንም።

ሌላውን ነገር ሁሉ ትተነው ህወሃት በኢህአዴግ አባልነቱ አገሪቱን ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ካስተዳደረ በኋላም "የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት" የሚለውን ቤተ-መዘክር ውስጥ ሊቀመጥ የሚገባውንና ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በፍጹም አብሮ የማይሄድ መጠሪያ ስሙን መለወጥ አለመፈለጉን ሲያይ ህወሃት ከኢትዮጵያ አንድነት የሚቃረን ድብቅ ዓላማ ይኖረዋል ብሎ አንድ ቀና ዜጋ ቢጠራጠር የሚያስደንቅ አይሆንም። ሌላው ኢህአዴግን በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ በስጋትና በጥርጣሬ እንዲታይ የሚያደርገው ምክንያት የኢትዮጵያን አንድነት በሚመለከት በሚያራምደው የተንሻፈፈ አቋም ነው። ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ ከአንድነት ይልቅ በልዩነት ጉዳይ ላይ ትኩረት የሚሰጥ ድርጅት ከመሆኑ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ኢትየጵያዊ ሆነው መኖር የሚችሉት መብታቸው ሳይሸራረፍ ከተከበረና ከአንድነት ተጠቃሚ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው በማለት ኢትዮጵያዊነትን በብሔር ብሔረሰቦች ላይ እንደተጫነባ ዕዳና ሸክም አድርጐ በተደጋጋሚ ስለሚገልጽ በሕዝቡ ዘንድ የአገር ፍቅርና ተቆርቋሪነት የሌለው ድርጅት ሆኖ እንዲታይ አድርጐታል። አንድ ዜጋም ሆነ ብሔር ብሔረሰብ የእኩልነት መብቱ ሙሉ በሙሉ መከበር ያለበት መሆኑ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ባይሆንም ኢትዮጵያዊ ሆኖ መኖር የሚገባው ሲደላውና ሲመቸው ብቻ ሳይሆን መከራውንና ችግሩን ጭምር እየተካፈለ መሆን ይገባዋል። ነገር ግን ኢህአዴግ ከእኔ ያልተመቸችኝ አገር "ገደል ትግባ" ዓይነት አቋም ስለሚያራምድ የአገር አንድነትን በተመለከተ የሕዝቡን የተሟላ ዕምነት እንዳያገኝና በጥርጣሬ እንዲታይ አድርጐታል። ስለዚህ ኢህአዴግ አልተለወጠም ወይም አይለወጥም ለሚለው አስተሳሰብ መኖር - በአንድ በኩል ሆን ብለው ጭፍን ፖለቲካን የሚያራምዱ ኃይሎች፣ በሌላ በኩል ደግሞ የራሱ የኢህአዴግ አንዳንድ አቋሞችና አመለካከቶች የየራሳቸው ድርሻ አላቸው ማለት ይቻላል።

ኢህአዴግ አልተለወጠም ወይም ሊለወጥ አይችልም የሚለው አመለካከት ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የራሱ ምክንያትና መነሻ ያለው ቢሆንም "ኢህአዴግ ሊለወጥ የማይችል ድርጅት ነው" የሚለውን አስተሳሰብ አምኖ መቀበል ግን አስቸጋሪ ነው። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢህአዴግ የፖለቲካ ሥልጣኑን በብቸኝነት ተቆጣጥሮ በመቀጠል ረገድ እስካሁን ምንም ዓይነት መሠረታዊ የአቋም ለውጥ ያላሳዩ ድርጅት ቢሆንም በእሱ ቁጥጥር ሥር ያለችው ኢትዮጵያ

አንድነቷ እንዲጠበቅና በልማት እንድታድግ ከመፈለግም አልፎ ሁኔታው በፈቀደለት መጠን ይህንን ዓላማ ለማሳካት ተግቶ እየሠራ መሆኑን ግን መካድ አይቻለም፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረው በተጨባጭ በአገር ውስጥ እየታየ ካለው የልማት እንቅስቃሴና ከአገሪቱ ብሔራዊ ደኅንነት አንጻር በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ እንደ መሪ ፓርቲ እያከናወናቸው የሚገኙ ድርጊቶችን በመገንዘብ ብቻ ሳይሆን፣ የአንድ አገር መንግሥት ሆኖ ለረዥም ጊዜ ከመቆየት ጋር በተያያዘም አንድ ድርጅት በአንድ ወቅት ከአንድ የጠበበ ፍላጎት ተነሥቶ ቀስ በቀስ የአገር አንድነትና ደኅንነት ጠበቃ የሚሆንበት ሰፊ ዕድልና አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩን በመገንዘብ ጭምር ነው፡፡

በአገራችን ታሪክ በዘር ሐረግ የውርስ ንግሥና ብቻ ሳይሆን የአካባቢ የጉበዝ አለቃ ለመሆን ትግል ጀምረው በመጨረሻ ለንግሥና የበቁ የአገር መሪዎች ጭምር በሥልጣን ዘመናቸው ሰፊና ጠንካራ አገር ለመፍጠር ሲደክሙ ኑረው ነው ያለፉት፡፡ ብዙዎቹ የአገራችን መሪዎች ወደ ሥልጣን ለመውጣት በሚያደርጉት የትግል ሂደት በአንፃራዊነት የፈጸሟቸው ስህተቶች ስለመኖራቸው በተደጋጋሚ በታሪክ ሲወሳ አይተናል፡፡ መሪዎቻችን በየዘመናቸው የፈጸሟቸው በጎ ነገሮች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከስህተት የጸዳ ነው ሊባል የሚችል መሪ ግን አገራችን ኖሯት አያውቅም፡፡

ለምሳሌ - አፄ ዮሐንስ አፄ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ሲሉ ከእንግሊዞች ጋር ማበራቸው፤ አፄ ምኒሊክ አፄ ዮሐንስን ለማጥቃት ሲሉ ከጣሊያኖች ጋር ውስጥ ውስጡን ማበራቸውና ከአድዋ ጦርነት ድል በኋላም ኤርትራን ከጣሊያን እጅ ማስመለስ አለመቻላቸው፤ አፄ ኃይለሥላሴም የኢትዮጵያና የኤርትራን ፌደሬሽን ለማፍረስ ውስጥ ውስጡን አላስፈላጊ ግፊት ማድረጋቸውና ዕድሜያቸው እስኪጃጅ ድረስ የአስተሳሰብም ሆነ የሥልጣን ለውጥን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆናቸው፣ ኮሎኔል መንግሥቱም ስልሳዎቹን ባለሥልጣናት በአሰቃቂ ሁኔታ በመረሸናቸውና በአንድ ትውልድ ወጣቶች ላይ በፈጸሙት ጭፍጨፋ በየታሪክ መዛግብቱ ሲወቀሱ አይተናል፡፡ እነዚህ ሁሉ መሪዎች ወደ ሥልጣን ለመውጣት ሲሉ፣ ወይም የሥልጣን የበላይነታቸውን ለማጠናከር ሲሉና ወይም ደግሞ ያሰቡትን ለመፈጸም አቅም ባነሳቸው ጊዜ በየወቅታቸው ታሪካዊ ሊባል የሚችል ስህተት ሲፈጽሙ የታዩ ቢሆንም ሁሉም መሪዎች ግን የአገራቸውን አንድነትና ገናናነት ከልባቸው ይፈልጉ እንደነበርና ለዚያም ዓላማ አቅምና ሁኔታ በፈቀደላቸው መጠን ይሠሩ እንደነበር የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ መሪዎቻችን ለሥልጣን ርስ በርስ ለመሻኮት ወደኋላ ብለው የማያውቁ ቢሆንም አንዳቸው ለሌላቸው ሰብአዊ ክብርን የሚነፍጉ ግን አልነበሩም፡፡ ለምሳሌ አፄ የሐንስ አፄ ቴዎድሮስ መሞታቸውን ሲሰሙ ሐዘን

የተቀመጡ ሲሆን አፄ ምኒሊክም ለአፄ ቴዎድሮስ ካላቸው ከፍተኛ አክብሮት የተነሣ ከማሪያም ቀጥሎ የሚምሉት በሳቸው ስም ነበር ይባላል፡፡

የታሪክ ጸሐፊዎቻችን ከየግል የአመለካከት ዝንባሌያቸው (Bias) የተነሣ የአንዱን መሪ ጠንካራ ጐን፣ ወይም የሌላውን መሪ ደካማ ጐን ያለአግባብ አጉልተው የሚያሳዩበት ሁኔታ የተለመደና እስካሁንም ድረስ ያለ ቢሆንም አንዱ መሪ ከሌላው ይሻላል ወይም ያንሳል ከመባሉ በስተቀር ግን ሁሉንም የታሪክ ጸሐፊ በሚያስማማ ሁኔታ የተዋጣለት ተብሎ የሚመሰገን መሪ አገራችን ኖሯት አያውቅም፡፡ የጉዳዩ ክብደትና ጊዜው የተለያዩ ቢሆንም በወደፊቱ የአገሪቱ ታሪክ ኢህአዴግ የሚዳኝበት ሚዛንም ካለፉት መሪዎቻችን ብዙም የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ የትጥቅ ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣትና ኋላም ላይ መንግሥታዊ ሥልጣኑን አስጠብቆ ለመቀጠል ሲል በአገሪቱ ላይ የፈጸማቸው ስህተቶች ዴሞክራሲ ሰፍኗል በሚባልበት በእኛ ዘመን የተፈጸሙ የዛሬ እውነታዎች በመሆናቸው ምክንያት የበለጠ የሚያስቆጨንና ገነው የሚታዩን ቢሆንም ከዚህ በኋላ ለአገሪቱ አንድነትና ደኅንነት ተቆርቋሪ ከመሆን አንጻር የኢህአዴግም ሚና ካለፉት የአገራችን መንግሥታት ሚና የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡

ምክንያቱም አንድ የፖለቲካ ኃይል የመንግሥት ሥልጣንን ተቆናጦ አንድ ጊዜ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ማጣጣም ከጀመረ በኋላ በዚያ መንግሥታዊ ሥልጣን በያዘበት አገር በሚመጣ ጉዳትና አደጋ ሁሉ ቀድሞ የሚጠቃው ራሱና በርሱ ዙሪያ ያሉ ወገኖች ጥቅም እንደሚሆን ስለሚረዳ ለአገሪቱ አንድነትና ደኅንነት ተቆርቋሪ የመሆኑ ጉዳይ ከፍላጐትና ከኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ከበለጠ ተጠቃሚነትም የሚመነጭ ነው፡፡ ከእኛም ሆነ ከሌሎች አገሮች ታሪክ ለመረዳት እንደምንችለው የአንድን አገር ወይም የአንድን መንግሥት ምሥረታ ሂደት በቀዳሚነት የመራው ኃይል ምንጊዜም የአገር አንድነት ጠበቃ ሆኖ መገኘቱ የተለመደ ክስተት ነው፡፡ በአገራችን የዐማራው ኤሊት ከሌላው ብሔረሰብ ኤሊት በበለጠ እስካሁን የአንድነት ጠበቃ ሆኖ ሲታይ የቆዬውም በአገር አንድነት ጉዳይ ከሌላው ሕዝብ የተለየ ደምና ተፈጥሮ ኖሮት ሳይሆን በአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳይ አንፃራዊ ተጠቃሚነት ስለነበረው ነው፡፡ የትግራይ ኤሊቶች የዐማራውን ኤሊት ሚና ተክተው በሚገኙበት በአሁኑ ወቅትም ለአገሪቱ አንድነትና ደኅንነት የበለጠ ተቆርቋሪ እየሆኑ የማይመጡበት አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፡፡

በተግባርም አሁን እንደምናየው በርካታ የአንድነት ጠበቃ ነን ሲሉ የነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይቀሩ ከሻዕቢያና የመገንጠል ዓላማ ከሚያራምዱ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ለመተባበር እየሞከሩ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ ኦነግና ኦብነግን አምርሮ ከመዋጋት ጀምሮ

በኤርትራና በሶማሊያም ሆነ በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድ ደረጃ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዱ አደጋዎችን ለመከላከል ኢህአዴግ በትጋት እየሠራ መሆኑን እያዬን ነው፡፡ ኢህአዴግ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ወይም ሥልጣን በያዘበት የመጀመሪያ ዓመታት የመገንጠል ጥያቄንና የአፍሪካ ቀንድን ፖለቲካዊ ሁኔታ በተመለከተ የነበረው አመለካከት በአሁኑ ወቅት ቢያንስ 90 ዲግሪ የተጠመዘዘ መሆኑ ብዙም የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡ አስተውለን ለመታዘብ ከሞከርንም በአሁኑ ወቅት እንደ ኢህአዴግና በኢህአዴግ ዙሪያ እንደተሰባሰቡ ኤሊቶች ስለ አገሪቱ ሰላምና አንድነት ደጋግሞ ሲያወራና ሲጨነቅ የሚደመጥ ሰው አለ ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህም ነው ኢህአዴግ ከሠላሳ ዓመታት በላይ ይዞት ከተጓዘው ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ካደረገ አደረጃጀት ወጥቶ ከወቅቱና ከወደፊቱ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ሊከተል ይገባዋል ማለትን አስፈላጊና ወቅታዊ የሚያደርገው፡፡

ምክንያቱም ከእንግዲህ አገራዊ ፖለቲካው ብቻ ሳይሆን ከአገራዊ ፖለቲካው አጠቃላይ ለውጥ ጋር በተያያዘ በኢህአዴግ ውስጥም ያለው የኃይል አሰላለፍ በሂደት እየተለወጠ መምጣቱ ስለማይቀር ያ-ለውጥ ከኢህአዴግ አልፎ የአገርም አደጋ እንዳይሆን ከተፈለገ መፍትሄው የኢህአዴግን አደረጃጀት ወጥ ወደ ሆነ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት በተቻለ ፍጥነት መለወጥ ነው፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው እንዲህ ዓይነቱ ለአገር የበለጠ ተቆርቋሪ የመሆን ጉዳይ የግድ ሰዎች ስለፈለጉና አገራቸውን ስለሚወዱ ብቻ የሚፈጠር አስተሳሰብ ሳይሆን በሥርዓቱ እምብርት ዙሪያ ሆነው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከመብቃታቸውም ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ በርግጥም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የኤሊቱ ክፍል የአገር ደኅንነት ተቆርቋሪነት መነሻ ምክንያት የሚሆን ቢሆንም በዚህ መነሻነት ኤሊቱ የሚያቀነቅነው አገራዊ አስተሳሰብም ቀስ በቀስ ከጥቅም ተጋሪነት በራቀውና የኤሊቱ ተከታይ በሆነው የታችኛው የኅብረተሰብ ክፍልም ተቀባይነት እያገኘና እየሰረፀ መመጣቱ አይቀርም፡፡ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ ምንም ዓይነት ጥቅም አግኝቶ የማያውቀው የዐማራውም ሆነ የትግራይ ድሀ አርሶ አደር ሕዝብ ሳይቀር አገርን በሚመለከት ብዙውን ጊዜ የኤሊቱን አስተሳሰብ ሲጋራ የሚታየው በሌላ ሳይሆን በዚሁ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ዛሬ ለአንዳንዶቻችን የአገር አንድነት ስጋት መስለው የሚታዩን በኦነግ ዙሪያ ያሉ የኦሮሞ ኤሊቶችም ነገ እንደ ዐማራውና የትግሬው ኤሊት በአገሪቱ ፖለቲካና ኢኮኖሚ የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ዕድል ቢያገኙ እነሱም በተራቸው የአገሪቱ አንድነትና ሰላም ጠበቃ የማይሆኑበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም የአገሪቱ ሕዝቦች የራሳቸውን አካባቢ በራሳቸው የማስተዳደራቸውና በአገሪቱ ማዕከላዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ትርጉም ያለው

ተሳትፎ እንዲኖራቸው የማድረግ ጉዳይ ለወደፊቱ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ የግድ አስፈላጊ የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም በአገሪቱ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት ውስጥ ጥቂቱ ወይም ከፊሉ ኅብረተሰብ ብቻ ተጠቃሚ በሆነበት ሁኔታ ሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ በአገሪቱ የአንድነትና የሰላም ጉዳይ ላይ ወጥ የሆነ ብሔራዊ መግባባት ሊፈጥር አይችልም፡፡

በአጠቃላይ በዛሬውና በወደፊቱ ፖለቲካችን ኢህአዴግን "አልቆለታል" እያልን በስሜት ሞቱን መመኘትም ሆነ ከዛሬ 15 እና 16 ዓመት በፊት ስንል እንደነበረው ኢህአዴግ አገሪቱን በየቀኑ እያፈረሳት ነው እያልን በጭፍን መራገሙ ተቃዋሚዎችን፣ ሕዝቡንም ሆነ አገሪቱን የትም አያደርስም፡፡ ኢህአዴግ ራሱንም ሆነ አገሪቱን ከህልውና አደጋ ለመታደግ ተጨባጭ የለውጥ ርምጃ መውሰድ ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቃዋሚዎችና የአገሪቱ ሕዝብም በየበኩላችን ከእንግዲህ ኢህአዴግ የአገሪቱ ችግሮች አካል ብቻ ሳይሆን የወደፊቱ የአገሪቱ መፍትሄዎች አካልም ጭምር መሆኑን አምነን መቀበል ይገባናል፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ በአገሪቱ ሁለንተናዊ ሕይወት ውስጥ ጠልቆ ከመግባቱ አንጻር አንዳንዶቹ በአገሪቱ ወደፊት እንዲመጡ የምንፈልጋቸው በጎ ለውጦች ወደድንም ጠላንም ያለኢህአዴግ ተሳትፎ የማይመጡ በመሆናቸው ነው፡፡ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱን የህልውና ስጋት የሚያስወግድ ልባዊ ዕውቅና በተቃዋሚዎችና በአጠቃላዩ ሕዝብ እስካገኘ ድረስም የተፈጥሮን ሕግ ሽሮ ዘለዓለም በሥልጣን ላይ ለመቀመጥ ከመሞከር ይልቅ በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሥልጣኑን ለመልቀቅ ከልቡ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግ በወደፊቱ የአገሪቱ ታሪክ በአስተማማኝ ሁኔታ ደማቁን ስፍራ ሊያገኝ የሚችለው አንድ ጊዜ በሕዝብ ምርጫ ከሥልጣን ወርዶ እንደገና በሌላ የሕዝብ ምርጫ አሸንፎ ለዳግም መንግሥትነት መብቃት ሲችል ነው ማለት ይቻላል፡፡

## *2.2 ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፖለቲካ ትግሉ*

ተቃዋሚው ጐራ እንደ ኢህአዴግ ተመሳሳይ የሆነ አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና አገራዊ አጀንዳ ያላቸው ፓርቲዎችን ያካተተ ሳይሆን በውስጡ የተለያዩ አደረጃጀት፣ የትግል ስልትና አገራዊ አጀንዳ የሚያራምዱ ጉራማይሌ ቅርጽና ይዘት ያላቸው ፓርቲዎችን ያቀፈ ስለሆነ እንደ አንድ ወጥ ማንነት ያለው የፖለቲካ ኃይል የተወሰኑ መመዘኛዎችን አስቀምጦ ለመገምገም ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጋሯቸውን ዋና ዋና ነጥቦችና ባህርያት መሠረት በማድረግ ኢህአዴግን ለመገምገም ከሞከርንበት ከድርጅታዊ መዋቅርና ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ተቃዋሚው ጐራ የሚገኝበትንም ሁኔታ በጥቅሉ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ለአለፉት ዐሥራ ሰባት ዓመታት ከአብዛኛዎቹ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች ተገናኝቶ በተደጋጋሚ የመወያየት ወይም አብሮ የመሥራት ዕድል አግኝቷል፡፡ በዚህ የረዥም ጊዜ ሂደት ያለምንም መሻሻል እስካሁን የተቃዋሚው ጐራ መገለጫ ሆኖ ያየው ባህሪ የኢህአዴግንም ሆነ የራስን የውስጥ ሁኔታ መገምገም ተገቢ ትኩረት የማይሰጠው ብቻ ሳይሆን ከነውርም የሚቆጠር ተግባር መሆኑን ነው፡፡

አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የሚታገለውን ኃይል ደካማና ጠንካራ ጐን በአግባቡ ገምግሞ ባላወቀበት ሁኔታ ትግሉን በአሸናፊነት ሊወጣ እንደማይችል ግልጽ ቢሆንም፣ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ በሕዝብ የተተፋው ያለቀለት ድርጅት ነው ብለን አስቀድመን ስለደመደምን እሱን መገምገም ጠቃሚና አስፈላጊ መስሎ አይታየንም፡፡ በዚህም ምክንያት ነው እስካሁን ተቃዋሚው ጐራ ያካሄደው ትግልም ሆነ የቅርብ ጊዜው የቅንጅት አካሄድ የተቃዋሚውን ጐራ ትግል በማዳከም ብቻ ሳይሆን በኢህአዴግ ውስጥ የሚገኘውን አክራሪ ኃይልና አስተሳሰብ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የማጠናከር ውጤት ሲያስከትል የታየው፡፡ ችግሩን የበለጠ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢህአዴግን መገምገም አለመቻላችን ብቻ ሳይሆን ራሳችንንም ግን ድክመትና ጥንካሬ አለን ብለን ለመገምገም የማንፈልግ መሆናችን ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ያለምንም በቂ ግምገማ ገዥውን ፓርቲ ደካማና ያለቀለት አድርገን እንደምናየው ሁሉ ራሳችንን ደግሞ በየትኛውም መመዘኛ ጠንካራና እንከን የለሽ አድርገን በመቁጠር ሁልጊዜ ራሳችንን ያለ አግባብ በመሸንገል ጥሩ እንቅልፍ መተኛትን የምንመርጥ ነን፡፡

እንዲያውም ራሳችንን መገምገም አጥብቀን የምንጠላና የምንፈራ በመሆናችን ምክንያት በውስጣችን ግምገማ እንዲደረግ የሚፈልግ ኃይል ከመካከላችን ብቅ ሲል ካዬን ጥያቄውን በቅንነት ተቀብሎ ራስን ለመገምገም ከመሞከር ይልቅ ጥያቄውን ያቀረበውን አካል በሰርጐ-ገብነት፣ በአፍራሽነትና በከፋፋይነት በመክሰስ ማሸማቀቅን እንመርጣለን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት አልፎ አልፎ ወይም በተለዩ አጋጣሚዎች ብቻ የሚፈጸም ሳይሆን በአብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ቋሚ አሠራር ተደርጐ በመወሰዱ ምክንያት ተቃዋሚዎች ድክመታችንን አርመን ተጠናክረን የምንወጣበትን ዕድል የዘጋብን ከመሆኑም በላይ በውስጣችን ሁልጊዜ ክፍፍልና አንጃኝነት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ሆነ ኢዴፓ እስካሁን በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ በነበረን የትግል ተሳትፎ በብዙ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ጥርስ ውስጥ ያስገባን ይኸው የምንታገለውን ኢህአዴግንና ራሳችንን በአግባቡ እየገመገምን ከወቅቱ

ትግል የሚመጥን አቅጣጫ ካልያዝን በስተቀር የትም ልንደርስ አንችልም የሚለው ቋሚ አቋማችን ነበር፡፡

ተቃዋሚዎች ልንጠናከርና ለድል ልንበቃ የምንችለው እንወክልሃለን የምንለው ሕዝብ በዙሪያችን ተሰባስቦ ሊያጠናክረን ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ለሕዝቡ ሁልጊዜ የምንነግረው ኢህአዴግ ደካማ መሆኑንና እኛ ደግሞ ጠንካራ መሆናችንን ስለሆነ ሕዝቡ ሁልጊዜ የሚያስበው ተቃዋሚዎችን እንዴት አድርጌ ላጠናክራቸው ብሎ ሳይሆን "ጠንካራዎቹ" ተቃዋሚዎች "ደካማውን" ኢህአዴግን መቼ ከሥልጣን እንደምናስወግድለት ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ከእንዲህ ዓይነቱ የበለጠ የመዳከም አዙሪት ሰብረን በመውጣት ራሳችንን ልናጠናክር የሚያስችለንን ትክክለኛ አቅጣጫ እስካሁን ድረስ ደፍረን መያዝ አልቻልንም፡፡

ምክንያቱም ራሳችንን በአግባቡ ገምግመን ተቃዋሚዎች ሊጠናከር የሚገባው ድክመት አለብን ብለን እውነቱን ብንናገር ኢህአዴግን ማስደሰት፣ ኢህአዴግንም በአግባቡ ገምግመን ደካማ ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ጐንም አለው ብለን ብንናገር ሽንፈትና በሕዝቡ ፊት አንሶ መታየት መስሎ ስለሚታዬን በድብብቆሽ ጨዋታው ውስጥ መቀጠልን መርጠናል፡፡ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ ያካሄድነው ትግል የትም እንዳልደረሰና እንዲያውም ከምርጫ 97 በኋላ ትግሉ ከመዳከምም አልፎ ወደ ከፍተኛ የህልውና ፈተና ውስጥ በገባበት ወቅት ስለ ራሳችን መዳከም ኢህአዴግን ተጠያቂ ከማድረግ በስተቀር ራሳችንን እንገምግም ብለን መግደርደር እንኳ አልፈለግንም፡፡ የሚገርመው ሁልጊዜ ራሳችንን ጠንካራ፣ ኢህአዴግን ደካማ አድርገን በምንከስበት አፋችን እንደገና መልሰን በትግሉ ውጤታማ መሆን ያልቻልነው ኢህአዴግ በውስጣችን እየገባ ስለሚያዳክመንና አፈና ስለሚፈጽምብን ነው ብለን ስንከስ እንደመጣለን፡፡ ኢህአዴግን ልንጥለው አንድ ሰኔ ቀርቶናል እያልን ደጋፊዎቻችን አስጨብጭበን ሳናበቃ ራሳችን ተንኮታኩተን ስንወድቅ ከድርጅትም ወርደን የአንድን ግለሰብ ስም በመጥራት ለውድቀታችን ምክንያት አድርገን ስንከስ እንታያለን፡፡ ነገር ግን "የኢህአዴግን ሠርጐ ገብነትና አፈና ተቋቁማችሁ ለድል የማትበቁ ከሆነ የእናንተ ጠንካራነት እና የኢህአዴግ ደካማነት የቱ ላይ ነው?" ተብለን ብንጠዬቅ የምናቀርበው አሳማኝ መልስ የለንም፡፡

ተቃዋሚው ጐራ ራሱን በመገምገም ረገድ ስለአለበት መጠን ያለፈ ፍርሀት (Phobia) በእኔ በኩል ሳስብ ሁልጊዜ የሚያስታውሰኝ ከጥቂት ዓመታት በፊት ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በተመለከተ አገራችን የነበረችበትን ሁኔታ ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ወደ አገራችን ገብቶ መስፋፋቱ ከታወቀ በኋላ ወደ አሥር ዓመት ያህል ስለ ጉዳዩ በአደባባይ በይፋ መነጋገር አስፈርቶን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን ሕይወት አጥተናል፡፡ ብዙ ሰዎች በዚያን ወቅት

በበሽታው ተይዘው ሕይወታቸው ሊያልፍ ሲያጣጥሩ የሚጨነቁት ውድና መተኪያ የሌለውን ሕይወታቸውን ስለማጣታቸው ሳይሆን ከሞቱ በኋላ በሰዎች ዘንድ የሞቱት በኤድስ ሕመም ነው ተብሎ እንዳይወራባቸው ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን ከሞቱ በኋላ ብቻ ሳይሆን በቁማቸውም እያሉ እውነታውን ተጋፍጠው "በእኛ ይብቃ" የሚሉ እነ ዘውዱንና ብርሃኔን የመሰሉ ጀግኖች ከመካከላችን ተፈጥረው ዝምታውን መስበር በመቻላቸው የብዙዎቻችንን ሕይወት ለመታደግ በቁ፡፡

የዛሬው የአገራችን የፖለቲካ ሂደትም የሚፈልገው "ዝምታ ወርቅ ነው" ብለው ወደ መቃብር የሚገቡትን ዓይነት ሕመምተኞች ሳይሆን እንደነ ዘውዱና ብርሃኔ ዝምታውን ሰብረው ከሞት የሚታደጉትን ጀግኖች ነው፡፡ በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የነገሰው የግብዝነት ድባብ ዛሬ ላይ በድፍረት ካልተሰበረ በስተቀር ከትናንቱ የግራ ፖለቲካ አራማጅ ትውልድ የወረሥነው የፖለቲካ ወረርሽኝ ወደ ነገው ትውልድም እንደሚሸጋገር አያጠራጥርም፡፡ ስለዚህ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የሚታየው ቀዳሚና ሥር የሰደደ ድክመት የግምገማ ባህል ማጣትና ከራስ ድክመትና ስህተት ለመማር አለመቻል ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ደካማ ጐናችን ምክንያትም ተቃዋሚዎች ውስጣዊ ድርጅታዊ ሁኔታችንን፣ የገዥውን ፓርቲ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴና በአጠቃላይም የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ እየገመገምን ከወቅቱና ከሁኔታዎች ጋር የሚጣጣም አቋም በመያዝ ትግሉን የሚያጠናክርና ለውጤት የሚያበቃ ስልት መከተል አልቻልንም፡፡

አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጊዜውን የጠበቀ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የማናካሂድ፣ የአመራር ቦታዎችን በጥቂት ግለሰቦች እርስትነት ያስያዝን፣ በአመራራችንና በአባሎቻችን መካከልም ጓደዊ ስሜት ሳይሆን የጌታና የሎሌ ግንኙነት ያዳበርን፣ በውስጣችንም የመቻቻል መንፈስና ጤናማ የሐሳብ ፍጭትን የሚያስተናግድ ዴሞክራሲያዊ ባህል የሌለን ነን፡፡ ባለፉት ዓመታት በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በተደጋጋሚ እንደታየው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በውስጣችን አንድ ዓይነት የሐሳብ ወይም የስልት ልዩነት ሲፈጠር ሕገ-ደንባችን መሠረት ባደረገ አሠራርና የውይይት መድረክ ለመፍታት ስንሞክር አንታይም፡፡ በአንድ ፓርቲ የትግል ሂደት የሚፈጠሩ ማናቸውም ዓይነት ውስጣዊ ልዩነቶች በውይይት የማይፈቱበት ምንም ዓይነት አሳማኝ ምክንያት ባይኖርም ተቃዋሚዎች ግን ቀላልና አቋራጭ የልዩነት መፍቻ መንገድ መስሎ የሚታየን በውስጣችን የተለየ ሐሳብ የሚያቀርቡ ሰዎችን በልዩ ተልዕኮ አራማጅነት በመፈረጅ ልዩነትን በአድማ፣ በስም ማጥፋት ዘመቻና ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ውጫዊ ግፊት መጨፍለቅ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ አሠራር በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ከመታረም

ይልቅ የበለጠ እየተጠናከረ እንዲሄድ በማድረግ ረገድም የተቃዋሚዎችን ውስጣዊ ሁኔታ በቅርበት ሳያውቅ ፍርድ ለመስጠት የሚሞክረው ደጋፊ ሕዝብ፣ የተቃዋሚዎችን ውስጣዊ ችግር ማባባስ የሚፈልገው ኢህአዴግና በጋዜጠኝነት መርህ የማይገዙና የግለሰቦች የፖለቲካ አቋም ማራመጃ ሆነው የሚያገለግሉ አንዳንድ መገናኛ ብዙኃን የየራሳቸውን አፍራሽ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ተቃዋሚዎች በዚህ ዓይነቱ መሠረታዊ ችግር ውስጥ እንድንወድቅ ያደረገን አንዱ ምክንያት ለወቅቱ ትግል የሚመጥን የአመራር አካል ማግኘት አለመቻላችን ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራር አባላት ለአመራርነት የሚመረጡት ከፖለቲካ ትግል ልምድና ብቃት ጋር ግንኙነት በሌላቸው መስፈርቶች መሆኑ የመጀመሪያው ችግር ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ለአመራር አባልነት የሚያበቃው ትልቁና ዋናው መመዘኛ የትምህርት ደረጃና ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ በሀብት ወይም በማንኛውም ሌላ ምክንያት ያላቸው ታዋቂነት ነው፡፡ የትምህርት ደረጃና የሃብት መጠን በራሳቸው አንድ የውጤት መለኪያ ቢሆኑም አንድ ሰው በማንኛውም መስክ ወይም ከፖለቲካ ጋር ምንም ዓይነት ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ግንኙነት በሌለው የተፈጥሮ ሳይንስ መስክ የዶክትሬት ዲግሪ ያገኘ ከሆነ፣ ወይም በውርስም ሆነ በግል ጥረቱ ዳጐስ ያለ ሀብት አካብቷል ከተባለ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር ለመሆን እድሉ የሰፋ ነው፡፡

በፓርቲዎቹ ብቻ ሳይሆን ደጋፊያችን በሆነው ሕዝብም ጭምር ዲግሪ ያለው ሰው ሁሉ የትግል መሪነት ዕውቀት እንዳለው፣ ሀብት ያለው ሰው ደግሞ ለግል ጥቅሙና ፍላጐቱ ሳይሆን ለአገሩ ጥቅም በመቆርቆር ብቻ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንደሚቀላቀል ተደርጐ ነው የሚታየው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን መስፈርት ማሟላት የሚችሉ ሰዎች ሲጠፉ ብቻ ነው ዲግሪ ያልያዙና የኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች የአመራር ቦታ ለማግኘት ዕድሉ የሚኖራቸው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ሆንኩ አባል የሆንኩበት ፓርቲ ኢዴፓ በአንድ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ አቋም ላይ ስለነበርን ነው በብዙ ድካምና መሥዋዕትነት ፓርቲውን ያቋቋሙ ብቁ ወጣቶች በውስጣችን እያሉን በየቤታቸው እየሄድን ደጅ በመጥናትና አማላጅ በመላክ ዶክተሮችን የፓርቲያችን ቁንጮ መሪዎች ስናደርግ የነበረው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊታችን በወቅቱ በሕዝቡ ዘንድ ለመደመጥና ለመታመን የረዳን ቢሆንም በሂደት ግን በራሳችን ፓርቲ ውስጥም ሆነ በኋላ ላይ በቅንጅት ውስጥ በነበረን ተሳትፎ ከፍተኛ ዋጋ ስላስከፈለን ዛሬ ከዚያ የተሣሣተ አቋማችን በሚገባ መማር ችለናል፡፡

የሚገርመው ግን በምርጫ 97 ወቅት ትግሉን በአናቱ መጥተው የተቆጣጠሩት ምሁራን ቅንጅቱን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ትግሉን ምን ያህል መቀመቅ ውስጥ እንዳስገቡት በተግባር ከታዬ በኋላም ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሆነ ደጋፊያችን የሆነው ኅብረተሰብ ከዚያ ዓይነቱ የተሳሳተ አመለካከት ዛሬም መላቀቅ አልቻልንም፡፡ በዚህ ዓይነቱ በቂ ያልሆነ መመዘኛ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎች በመሆናቸው ብቻ ከየአቅጣጫው ተሰባስበው የፖለቲካ አመራር ለመሆን የሚበቁት እነዚህ ሰዎች በአገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ አንድ ዓይነት አቋምና ዓላማ ማራመድ ይቅርና እርስ በርሳቸውም በአግባቡ ይተዋወቃሉ ብሎ ለማመን ያስቸግራል፡፡

አብዛኛዎቹ አመራሮች ለፖለቲካ አመራርነት የሚያበቃ በቂ የድርጅት ልምድና ዕውቀት የሌላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ እንደሚመጣ ያልገመቱት አደጋ ድንገት ካልጠለፋቸው በስተቀር ትግሉ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ለመክፈልም ዝግጁዎች አይደሉም፡፡ ውድ ሕይወታቸውንና ኑሯቸውን ይቅርና ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን እንኳ በአግባቡ ለትግሉ መሥዋዕት ሲያደርጉ አይታዩም፡፡ ሙሉ ጊዜያቸውን ዩኒቨርስቲ ውስጥ እያስተማሩ፣ እየነገዱ ወይም ለአንድ የግል ድርጅት ተቀጥረው እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ ነው ከማኅበራዊ ኑሯቸው ጭምር በምትተርፋቸው አጭር ጊዜ ለፖለቲካ ድርጅት ሠርተው ትግሉን ለውጤት ለማብቃት የሚፈልጉት፡፡

እነዚህ ሰዎች ቢያንስ የፖለቲካ ጉዳይ አያገባኝም ብሎ በየቤቱ ዘግቶ ከተቀመጠው የአገሪቱ ምሁራን በተሻለ ትግሉ ውስጥ ተሳትፎ እያደረጉ ስለሆነ በዚህ ረገድ ሊመሰገኑ እንደሚገባ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቶቹ የፖለቲካ አመራሮች ሌት ከቀን ሳይታክቱ የሚሠሩትን የኢህአዴግን አመራሮች የሚመጥን የአመራርነት ሚና ተጫውተው ትግሉን ለድል ያበቁታል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ እስካሁንም ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ሳይቋረጥ የተደረገው ትግል የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ሳይችል የቀረበት አንዱ ምክንያትም እንደ ኢህአዴግ አመራር አባላት ለትግሉ ራሱን መሥዋዕት ሊያደርግ የተዘጋጀ፣ ያለመታከት ጥርሱን ነክሶ ሌት ከቀን የሚሠራ፣ ለቆመለት ዓላማ ርስ በርስ በመተማመን በየወንዙ መማማል የማያስፈልገውና ግምገማን ባህሉ ያደረገ ጠንካራ አመራር በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ መፈጠር ባለመቻሉ ነው፡፡ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ በተግባር እንደታየው የተቃዋሚው ጐራ መሪዎች አዳዲስ ሐሳቦችን እያፈለቅንና ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ስትራቴጂዎችን እየነደፍን ትግሉን በተገቢው መንገድ እየመራነው ሳይሆን እኛው ራሳችን በጊዜያዊ ሁኔታዎችና በሕዝብ ስሜት እየተመራን የምንገኝ ነን፡፡ ወደፊትም በዚህ ረገድ ያለብንን ድክመት በሃቅ ገምግመን ራሳችን

ለማረም የማንችል ከሆነና በአጠቃላይም ለፖለቲካ አመራርነት የምንጠቀምበትን መመዘኛ መቀዬር የማንችል ከሆነ ትግሉን መርተን ወደምንፈልገው ግብ ልናደርሰው አንችልም፡፡

ለዚህ ደግሞ ለውጤት መብቃት ተስኗቸው በትግሉ ውስጥ ሲንገጫገጩ ለዓመታት ከኖሩት በርካታ ፓርቲዎች በላይ እንደ ቅንጅት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል የለም፡፡ አገርን ይመራሉ ተብለው በሕዝብ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቷቸው የነበሩት የቅንጅት ጐምቱ-ጐምቱ መሪዎች ትግሉን ከተቀላቀሉበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በእጃቸው ውስጥ የገባውን ታላቅ የአገር ጉዳይ እረስተው ምን ያህል በቅንጭብጫቢ ግላዊ ጉዳዮች ርስ በርስ ሲነታረኩ እንደሚውሉ ታይቷል፡፡ እነዚህ ምሁራን ለብዙ ዓመታት ዳር ቆመው ሌሎች ፓርቲዎችንና መንግሥትን በመተቸትና በመኰንተል ሲመጻደቁ እንዳልኖሩ ዛሬ የሥልጣን መቆናጠጫው ጊዜ ደረሰ ብለው ፓርቲ ውስጥ በመግባት ራሳቸው የውሳኔ ሰጭነቱን ቦታ ሲይዙት ግን ምን ያህል ትግልን መምራት "ከበሮ በሰው እጅ" ሆኖባቸው ቅጥ አንባሩ እንደጠፋባቸውና እነሱ ሌሎችን ይተቹ በነበረበት መጠን ለሌሎች ትችት መጋለጣቸው በገሃድ ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከትርፍ ጊዜ ስሜታዊ የፖለቲካ ግርግር ተላቀን በውስጣችን ጥራትና ብቃት ያለው የፖለቲካ ሞያተኝነት /political Professionalism/ መገንባት እስካልቻልን ድረስ በቀላሉ ተጠናክረን ልንወጣ አንችልም፡፡

በተቃዋሚው ጐራ አመራሮች ዙሪያ የሚታየው ችግር በዚህ ደረጃ መሆኑ የማይጠበቅና የሚያሳዝን ቢሆንም - ችግራችን የልምድ፣ የዕውቀት፣ የጊዜ፣ የቁርጠኝነት፣ የትጋትና ራስን የመገምገም ባህል ማጣት ብቻ ቢሆን ብዙም ላያስደንቅ በቻለ ነበር፡፡ ነገር ግን ማንም አብሮ በመሥራቱ ሂደት ውስጥ ያላለፈ የውጭ ተመልካች ሊያምነውና ሊገምተው በማይችል መጠን በተቃዋሚው ጐራ አመራሮች ዙሪያ ያለብን ቅንነት የማጣት፣ ሃቀኛ ያለመሆንና ጨካኝ የመሆን ባህሪ በዚያው መጠን ሥር የሰደደ ነው፡፡ አንዳንድ በሕዝቡ ዘንድ የወደፊት የአገር መሪ ይሆናሉ ተብለን የምንገመት አንቱ የተባልን ሰዎች በአደባባይ በጋዜጣና በሬዲዮ ሳይቀር ሕዝብን ምን ያህል እንደምንዋሽ፣ ለትግሉ ከምናጠፋው ጊዜና ጉልበት በላይ ለግል የሥልጣን ጥማችንና ለዝና እንዴት በርትተን እንደምንሠራ፣ ለእኛ ሥልጣንና ዝና ተቀናቃኝ ይሆናል ብለን የምናስበውን ሰው ከትግሉ ሜዳ ድምጥማጡን ለማጥፋት ምን ያህል እንቅልፍ አጥተን ሴራ እንደምንሸርብ ሲታይ ኢትዮጵያ እስካሁን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ቀላል ለማይባል ጊዜ የመሪዎች ድሀ ሆና ልትቀጥል እንደምትችል በግልጽ ያመላክታል፡፡

ጉዳዩን የበለጠ አስፈሪ የሚያደርገው ጥቂት የተቃዋሚ መሪዎች እንዲህ ዓይነት ባህሪ ያላቸው መሆኑ ሳይሆን ሕዝቡ ስለ እነዚህ ሰዎች ያለው ግንዛቤ ከእውነታው በእጅጉ የራቀ

በመሆኑ ምክንያት ወደፊት እንደዚህ ዓይነት እኩይና አደገኛ ባህሪ ያላቸው ሰዎች በሕዝብ ድጋፍ ጭምር በዴሞክራሲያዊ ምርጫ መንግሥታዊ ሥልጣን ላይ የሚወጡበት ሰፊ ዕድልና አጋጣሚ የሚኖር መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ዛሬ ራሳቸው ገና በተቃዋሚነት ደረጃ ላይ እያሉ የነሱን አቋም የማይጋሩ ሌሎች የተቃዋሚ አመራሮችን ከትግሉ ሜዳ ለማስወገድ ሲሉ የሚጠቀሙበት የጭካኔ ድርጊት ሲታይ፣ ነገ እነዚህ ሰዎች ሁሉን ነገር ለማድረግ የሚያስችል መንግሥታዊ ሥልጣን ይዘው በአገር መሪነት ቦታ ቢቀመጡ የእነሱን ሐሳብ የሚቃወም ተቃዋሚ ፓርቲም ሆነ ነፃ ፕሬስ በዚች አገር ሊኖር ይችላል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ዛሬ ተቃዋሚ እያሉ ከኢዴፓ ጋር ተቀምጠን በአገር ጉዳይ አንወያይም የሚሉ ተቃዋሚዎች ነገ መንግሥት ሲሆኑ በፖለቲካ ተቀናቃኞቻቸው ላይ እንደ ደርግ ዘመን "የፍየል ወጠጤን" እየዘፈኑ አብዮታዊ ርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ ይላሉ ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡

የኢዴፓ ሰዎች በቀድሞ ቅንጅትም ውስጥ ሆነ ከዚያ ውጭ ያሉ አንዳንድ የተቃዋሚ መሪዎች የሚፈጽሙትን ድርጊት ስናይ፣ አገርን ያህል ትልቅ ነገር እንደ አይጥና ዝንጀሮ የምርምር መሞከሪያ ሊሆን አይገባውም እንጂ "የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ሰዎች ለሦስት ወር ያህል የመንግሥት ሥልጣን ይዘው በተግባር ባያቸው" ብለን እንመኛለን፡፡ በአጠቃላይ በፖለቲካ መድረኩ ዙሪያ በአሁኑ ወቅት በአመራርነት የምንገኝ አብዛኛዎቹ ሰዎች ምን ያህል በክፋት የተሞላን እንደሆን ሲታይ፣ የሚያስገርመው አገራችን ኢትዮጵያ ድሀና ኋላቀር መሆኗ ብቻ ሳይሆን እንደ አገርም ህልውናዋን ጠብቃ መኖር መቻልዋ ነው፡፡

ከዚሁ ከአመራር አካላት ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚገባው ሌላው ችግር በሌሎችም መስኮች እንደሚታየው ሁሉ የአንድ ወቅት ትውልድ አባላት የተቃዋሚውን ጐራ የአመራርነት ድርሻም በበላይነት የተቆጣጠሩት መሆኑ ነው፡፡ አሁን አሁን በአንዳንድ ፓርቲዎች ዙሪያ ውስን የሆነ ለውጥ እየታየ ቢሆንም አብዛኛዎቹ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት የሚገኙ ፓርቲዎች እየተመሩ የሚገኙት በ1960ዎቹ በአገራችን በነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ በግራ ኃይልነት ተሳታፊ በነበሩት የትውልድ አባላት ነው፡፡ የዚያን ዘመን አባላት ዛሬም በትግሉ ተሳታፊ መሆናቸው በራሱ ችግር የለውም፡፡ እንዲያውም ባለፉበት የትግል ውጣ ውረድ የቀሰሙትን በጎ ልምድ ተጠቅመው የወቅቱን ትግል ጤናማና አገር የሚጠቅም በማድረግ ረገድ ከነሱ የበለጠ ይጠበቃል፡፡ ምክንያቱም የዚያ ትውልድ አባላት ከባድ መሥዋዕትነት የከፈሉ ቢሆኑም በዘመናቸው መሥራት የሚገባቸውን ትክክለኛ ሥራ ሠርተው ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንጻር ለዛሬው ትውልድ ጥሩ አገር ባለማስረከባቸው ከዚህ ቁጭት ተነስተው የዛሬውን ትውልድ ለመካስ ቢሠሩ የሚጠበቅና የሚገባ በሆነ ነበር፡፡

ነገር ግን በተጨባጭ እየታየ እንደሚገኘው እነዚህ ለአለፉት አርባ ዓመታት የፖለቲካ መሪነቱን ቦታ ይዘውት የሚገኙ ሰዎች በጎ ነገር በመሥራት ትውልዱን ለመካስ እየጣሩ አይደለም፡፡ በተቃራኒው በእነሱ ጥፋት ምክንያት በሁለንተናዊ መልኩ የተበላሸ አገር የወረሰውን አዲሱን ትውልድ በጥፋተኝነት እየወቀሱ የወቅቱንም የፖለቲካ ትግል መሪነት እነሱው በበላይነት ተቆጣጥረው በተለመደው ብልሹ ባህል እንዲቀጥል እያደረጉት ይገኛሉ፡፡ በገዥው ፓርቲም ሆነ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የሚገኙ የእነዚህ አመራሮች አንዱ መሠረታዊ ችግር ያለፈውን ስህተታቸውን አምነው የመቀበልም ሆነ የመፀፀት ባህል የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ አንዳንዶች "ብንሳሳትም ለአገር የጠቀምን መስሎን ነው" በማለት ተቀባይነት ያለው አነጋገር ሲጠቀሙ የሚደመጥ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ከተማሪው እንቅስቃሴ ጀምሮ በትግሉ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩ ኃይሎች ግን በሂደቱ ለተሠራው ስህተት ሁሉ በሌሎች ላይ ጣታቸውን ከመቀሰር አልፈው ራሳቸውን የችግሩ አካል አድርገው ሲቆጥሩ አይታይም፡፡

ከሁሉም በላይ የሚገርመው ሁሉም የግራ ፖለቲካ አራማጅ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች ሲታገሉ የኖሩት ለዴሞክራሲና ለእኩልነት ሳይሆን ለወዝአደሩ መደብ ፍጹማዊ የበላይነት ቢሆንም ከ"ያ ትውልድ" ጀምሮ እስከ "ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ" ድረስ በጻፏቸው ድርሳናት ሁሉ ራሳቸውን የዴሞክራሲና የእኩልነት ጠበቃ አድርገው ለማቅረብ ሲሞክሩ ታይቷል፡፡ የ1960ዎቹ ትውልድ አባላት በወቅቱ ሙሉ በሙሉ መሃይም ከነበረ ኅብረተሰብ ውስጥ ተፈጥረው የኮሌጅን በር ለመርገጥ በመብቃታቸው ምክንያት በውስጣቸው በፈጠሩት የተሳሳተ የሥነ-ልቦና ችግር ራሳቸውን እንደ ሊቀ - ሊቃውንት ቆጥረው በዚያ የ18 እና 19 ዓመት ለጋ ዕድሜአቸው በጥራዝ ነጠቅነት ወዝአደር በሌለበት አገር የወዝአደሩን የበላይነት ለማስፈን የስታሊን ርእዮት አቀንቃኝ መሆናቸው ላያስገርም ይችላል፡፡ ምክንያቱም ያኔ የግራ ፖለቲካ አራማጅ በመሆን "ፋኖ ተሰማራን" መዘመር አፍሮ የማበጠርና ቦርሼት የመልበስ ያህል የሥልጣኔ መገለጫ የሆነ ፋሽን ስለነበር በዚያ ሂደት ተሳታፊ ሆኖ ማለፍን እንደ ስህተት መቁጠር ያስቸግራል፡፡

ነገር ግን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ የስታሊን ርእዮት አውዳሚ መሆኑ በተግባር በተረጋገጠበት በአሁኑ ወቅት የትናንት የግራ ፖለቲካ አራማጆች ዛሬም ራሳቸውን የአገር ባለውለታ አድርገው መቁጠርና መመጻደቃቸውን አላቆሙም፡፡ ሌላውና መሠረታዊው የግራ ፖለቲካ አራማጆች ችግር - ከተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ በተለያየ ጐራ ተሰልፈው እስከ መገዳደል በደረሰ የፖለቲካ ፍጥጫና ሽኩቻ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው ከዚያ የጥላቻና የቂም በቀል አዙሪት በቀላሉ መላቀቅ አለመቻላቸው ነው፡፡ በእነዚህ አመራሮች ምክንያት የወቅቱ

የአገራችን የፖለቲካ ትግል ዋና ትኩረቱ ስለ ዛሬዋና ስለ ወደፊትዋ ኢትዮጵያ መሆን ሲገባው የእነዚህ ሰዎች የቆየ የፖለቲካ ቂም በቀል ሂሣብ ማወራረጃ ሆኖ ቀጥሏል።

በዚህ ምክንያት የዛሬዋና የነገዋ ኢትዮጵያ ዋና ባለቤት የሆነው አዲሱ ትውልድ የራሱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በሚወሥነው የወቅቱ የፖለቲካ ትግል ውስጥ የሚገባውን ሚና እንዳይጫዎት እድሉ ተነፍጐታል። አብዛኛዎቹ የ1960ዎቹ ትውልድ አባላት በሕይወት እስካሉ ድረስ የፖለቲካ ጡረታ ላለመውጣት በመወሰናቸው ምክንያት አዲሱን ትውልድ የሚፈልጉት መፈክርና ሠንደቅ ዓላማ አውለብላቢ ጀሌ ሆኖ የነሱ ትግል ተከታይና አድማቂ እንዲሆን ነው እንጂ የራሱን ዘመን ችግር በራሱ መንገድ እንዲፈታ እያረጉት አይደለም። እውነቱን በድፍረት እንነጋገር ካልን የአገራችን የፖለቲካ ባህል መሻሻልና ወደፊት ፈቀቅ ማለት ያልቻለው በዋናነት የፖለቲካ አመራርነት ድርሻው በአንድ ትውልድ አባላት ቋሚ ርስትነት ተይዞ አዲስ ተዋናይና አዲስ አስተሳሰብ /Fresh blood/ ሊጨመርበት ባለመቻሉና በአግባቡ ከትውልድ ትውልድ መሸጋገር ባለመቻሉ ነው። በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ትግሉን እየመሩት የሚገኙት ሰዎች ከወጣትነት ዕድሜአቸው ጀምሮ በተሰለፉበት የትግል ጐራ ሁሉ ውጤት ለማምጣት ሳይችሉ የቀሩ የተሸናፊዎች ስብስብ በመሆናቸው ለዛሬውና ለወደፊቱ ትግልም እዳና ሸክም /Liability/ እንጂ ጠቃሚ ሀብት /Asset/ ሊሆኑ አልቻሉም።

ከአመራር አባላቱ ሚና ወረድ ብለን ስናይ፣ ሌላው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ የሚታየው ድክመት በፓርቲ አባላት አካባቢ የሚገኝ ነው። አንድ ፓርቲ የቱንም ያህል ጠንካራ አመራርና ጠንካራ ዓላማ ቢኖረው በሕዝቡ ውስጥ ገብተው የፓርቲውን ዓላማ በአግባቡ የሚያስተዋውቁና የፓርቲው አባላት ለመሆን የወሰኑ ሰዎችን በአግባቡ በፓርቲው ዙሪያ የሚያደራጁ ጠንካራ አባላት እስከሌሉት ድረስ የትም ሊደርስ አይችልም። በዚህ ረገድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የምንገኝበት ሁኔታም በጣም አሳሳቢ ነው። አንዳንድ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አባላት እንዳሏቸው የሚናገሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሉ ቢሆንም በተግባር ግን ተቃዋሚዎች ያለንበት ሁኔታ ከሚጠራው ቁጥር ጋር የሚጣጣም አይደለም። የሚጠራው ቁጥር አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆነን ሰው ሁሉ አንድ ጊዜ ከመመዝገብ አንጻር ከሆነ ስህተት ላይሆን ቢችልም በተግባር ግን በእያንዳንዱ ተቃዋሚ ፓርቲ ለፓርቲያቸው ተግተው የሚሠሩ በመቶዎች እንኳ የሚቆጠሩ አባላትን ማግኘት ያስቸግራል።

የቅንጅት እንቅስቃሴ ከፍተኛ የሕዝብ ትኩረት የሳበበት ምርጫ 97 ላይ የቅንጅቱ አባል ከነበሩት አራት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ የሆነው መኢአድ ብቻውን ከአንድ ሚሊየን በላይ አባል እንዳለው ይናገር ነበር። ነገር ግን በዚያን ወቅት ቅንጅት በ130 የአገሪቱ ወረዳዎች አንድ

ለፓርላማ የሚወዳደር አባል እንኳ ማግኘት ባለመቻሉ ለፓርላማ እጩ ተወዳዳሪ ማቅረብ ከሚገባው 547 ወረዳዎች ውስጥ በ417 ወረዳዎች ብቻ ነበር እጩዎችን ማቅረብ የቻለው። በምርጫው ዕለት በየአንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በአካል ተገኝተው ምርጫውን እንዲታዘቡለት ለማድረግ ቅንጅት ከዘጠና ሺህ በላይ ታዛቢዎችን ማሠማራት ይጠበቅበት ነበር። ነገር ግን በዚያን ወቅት አባላትን ብቻ ሳይሆን ደጋፊዎችን ጭምር ለምርጫ ታዛቢነት ለማሰማራት በተደረገው ጥረት ቅንጅት ለአንድ ቀን መሥዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጁ ከ15 ሺህ በላይ ታዛቢዎችን በመላው አገሪቱ ማሠማራት እንኳን አልቻለም ነበር።

የአባላትን ብዛት አስፈላጊ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ ከገንዘብ ምንጭነት ጋር የተያያዘ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አባላት አለን ከሚሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አንድ ሺህ የሚሞሉ አባላቱ ወርሃዊ መዋጮአቸውን በአግባቡ የሚከፍሉትና የአንድ አነስተኛ የመርካቶ ነጋዴ ያህል ገንዘብ ማንቀሳቀስ የሚችል አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ እንኳ አገራችን ውስጥ አለ ማለት አይቻልም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጭን በሚመለከት በውጭ አገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጥገኛ ሆነን የምንታዩውም ያለምክንያት ሳይሆን አብዛኛዎቹ አገር ውስጥ ያሰባሰብናቸው አባላት ሲቻል ከፓርቲያቸው የገንዘብ ድጋፍ የሚሹ እንጂ ለፓርቲያቸው በቂ ገንዘብ ለማዋጣት የሚችሉ ባለመሆናቸው ነው። በአጠቃላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ጠንካራና በቂ መጠን ያላቸው አባላት በዙሪያችን ማቀፍ ስላልቻልን እስከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል የወረደ ጠንካራ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ከሕዝብ ጋር የሚያገናኙ የራሣችን ጠንካራ የሚዲያ አውታሮችና በሕዝቡ ውስጥ በቂ የማደራጀትና የማንቃት ሥራ የሚሠሩ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች /ካድሬዎች/ የሌሉን ደካማ ፓርቲዎች እንድንሆን አድርጎናል።

ተቃዋሚዎች ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ስለአለብን ድክመት የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ተጨማሪ ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል። የመጀመሪያው ምክንያት ከራሳችን ውስጣዊ ድርጅታዊ ድክመት የሚመነጭ ነው። ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠንካራ የአመራር አካል፣ ጠንካራ አባላትና አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ ባልፈጠርንበት ሁኔታ በሆነ ተአምር ድርጅታዊ ጥንካሬ ሊኖረን እንደማይችል የታወቀ ነው። በተለይም ከውስጡ ጠንካራ አመራርና አስተማማኝ ፋይናንስ ሊመነጭበት የሚችል ጥራት ያለው የአባላት ስብስብ እስካልፈጠርን ድረስ ድርጅታዊ ጥንካሬ ሊኖረን አይችልም። ይህንን ለማድረግ ያላስቻለን አንዱ ምክንያት ደግሞ አብዛኛዎቹ አባሎቻችን ለፓርቲ አባልነት ለመመልመል ወይም ለመመዝገብ የበቁት የፓርቲዎቻችንን ዝርዝር አስተሳሰብና ዓላማ በውል በመረዳት ሳይሆን በዋናነት በአንድ

የኢህአዴግ አባል ወይም መዋቅር በደል ሲፈጸምባቸው ወይም አገራዊ በሆነ ምክንያት ኢህአዴግን የሚቃወሙና የሚጠሉ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡

እነዚህ አባሎቻችን በአንዱ ተቃዋሚ ፓርቲና በሌላው ተቃዋሚ ፓርቲ፣ ወይም አባል በሆኑበት ፓርቲና በገዥው ፓርቲ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነትና አንድነት በደንብ ጠንቅቀው በማወቅ አባል ለመሆን የበቁ ሳይሆኑ በተለያዩ አካባቢያዊና ፖለቲካዊ ብሶቶች የተሰባሰቡ በመሆናቸው ፓርቲያቸው ከእነሱ የሚጠብቀውን ኃላፊነት በአግባቡ የሚወጡ አልሆኑም፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ አባላት ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን በአግባቡ እያበረከቱ ፓርቲያቸው በእነሱ ድጋፍ ተጠናክሮ ለለውጥ እንዲሆኑ የሚታገሉ ሳይሆኑ በሆነ ተአምር ፓርቲያቸው ኢህአዴግን ከሥልጣን አስወግዶ ማየትን የሚናፍቁ ሆነው ይታያሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምኞታቸው በቀላሉ የማይሳካ መስሎ ሲታያቸውም ቶሎ ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ውስጥ ይገቡና አባልነታቸውን ማቋረጣቸውን እንኳ ባላሳወቁበት ሁኔታ የሌላ ተቃዋሚ ፓርቲ፣ አንዳንድ ጊዜም የኢህአዴግ አባል ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ በተደጋጋሚ ይታያል፡፡ በፓርቲያቸው ላይ አሉባልታ ሲነዛ ወይም ከገዥው ፓርቲ በኩል አንድ ዓይነት ጥቃት መሠንዘር ሲጀመርም አስቀድመው ሲናዱ የሚታዩት በዓላማ ሳይሆን በግል ብሶት ምክንያት በየፓርቲው ዙሪያ የሚሰባሰቡት የዚህ ዓይነቶቹ አባላት ናቸው፡፡

ሁለተኛው ተቃዋሚዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዳይኖረን ያደረገው ምክንያት በገዥው ፓርቲ የሚፈጸም ተጽዕኖና የአፈና ድርጊት ነው፡፡ ኢህአዴግ አንድም ጊዜ በተቃዋሚዎች ላይ የአፈና ድርጊት እንደሚፈጽም አምኖ የተቀበለበት አጋጣሚ ባይኖርም ኢህአዴግ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ የተለያዩ የአፈና ድርጊቶችን እንደሚፈጽም ተራ የፖለቲካ ድብብቆሽ እንጫወት ካልተባለ በስተቀር ከማንም የተደበቀ ምስጢር አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የኢህአዴግ ዐይን ያወጣ ደረቅ ክርክር በትግሉ ውስጥ እንደ በግ እየታሠርንና እየተፈታን የኖርን የፓርቲ ሰዎችን ይቅርና ከቀጥተኛ የትግል ተሳትፎ ርቆ የሚገኘውን ሕዝብና የውጭ ዲፕሎማቶችን እንኳ ሊያሳምን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ተጠናክረው የሥልጣን የበላይነቱን እንዳይፈታተኑት ለማድረግ በተለይም በምርጫ ወቅት በተቀነባበረና በተጠና ሁኔታ ከፍተኛ የአፈና ድርጊት በዘመቻ መልክ ይፈጽማል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ተቃዋሚዎች ትንሽ ጐላ ያለ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ባካሄድን ቁጥር በገሃድ የምናየው ሃቅ ከመሆኑም በተጨማሪ ቢያንስ እንደ እኔ ዓይነቱ የኢህአዴግን ጠንካራ ጐንና የተቃዋሚዎችን ደካማ ጐን ጭምር በድፍረት እየተቸ የሚገኝ ሰው ኢህአዴግን በዚህ ጉዳይ ያለምንም በቂ ምክንያት ሊወቅስ ይችላል ተብሎ መታሰብ ያለበትም አይመስለኝም፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቅት ከተፈረመው የፓርቲዎች የምርጫ

የሥነ-ምግባር አንጻር ኢህአዴግ ምን ያህል ተጨባጭ የባህሪ ለውጥ እንዳመጣ ወደፊት በተግባር የሚታይ ይሆናል፡፡

በፓርቲ አባላት ላይ የተለያዩ ተጽዕኖዎችን ከመፈጸም በተጨማሪም ተቃዋሚዎች ከመንግሥት የገንዘብ ድጐማ እንዳያገኙ በማድረግ፣ ከምርጫ ወቅት ውጭ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንን በበቂ መጠን እንዳይጠቀሙ በማድረግ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ መቀጠር እንዳይችሉ በማድረግና በሌሎች የተለያዩ ስልቶች በመጠቀም ተቃዋሚዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዳያገኙ የሚያስችለውን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት በመፈጸምም በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ የተሰባሰቡ አባላት እየተማረሩና ተስፋ እየቆረጡ እንዲበተኑ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሌላው ኅብረተሰብም በፍርሀት ተሸማቆ ተቃዋሚዎችን በመርዳት እንዳያጠናክር በማድረግ ረገድ ኢህአዴግ ሊካድ የማይችል አፍራሽ ሚና ይጫዎታል፡፡

ነገር ግን ኢህአዴግ ይህንን ሁሉ በደል እየፈጸመ አንድም ቀን ጥፋቱን በይፋ አምኖ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኖ አያውቅም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድርጊቱ አፍጥጦ ሊደበቅ በማይችል ደረጃ ሲታይበትም አንዳንድ አባላቱ በራሳቸው ተነሳሽነት የሚፈጽሙት ስህተት እንደሆነ አድርጐ ሲገልጽ ይደመጣል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የኢህአዴግ አባባል ልባዊ አለመሆኑን የምንገነዘበው ግን መቸውንም ጊዜ ቢሆን በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላት ላይ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ፈጽሟል የሚባል አንድም የኢህአዴግ አባል ላይ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በይፋ አስተዳደራዊ ርምጃ እንኳ ሲወሰድ አይተን ባለማወቃችን ነው፡፡ ይህም የሚያሳዬን ኢህአዴግ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አባሎቹ በተቃዋሚዎች ላይ የፈለጉትን ርምጃ እንዲወስዱ ይሁንታ የሰጠ መሆኑን ነው፡፡ ምርጫ 97 ላይ ከፍተኛ ደባ በአገራችን መፈጸሙን የሚያትተውን የካርተር ማዕከልን ሪፖርት ኢህአዴግ አምኖ ከተቀበለ በኋላ በአንድም የምርጫ አስፈጻሚ ላይ እስካሁን ግልጽ ርምጃ ሲወስድ ያልታዬውም በዚህ ተመሳሳይ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአገራችን ተቃዋሚዎች አፈና እንደሚፈጸምባቸውና ምርጫም እንደሚጭበረበር ሊካድ በማይችል ደረጃ ያፈጠጠ እውነት ሆኖ እያለ የኢህአዴግ አመራሮች ግን ይህንን ሃቅ ሽምጥጥ አድርገው ሲክዱ ትንሽም የኀፍረት ስሜት አይታይባቸውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ባህርያቸውም ነው አብዛኛውን ጊዜ ኢህአዴግ ሊለወጥ የማይችል ድርጅት ነው የሚሉ ሰዎችን አስተሳሰብ ሲያጠናክር የሚታየው፡፡

ከዚሁ ከኢህአዴግ የአፈና ድርጊት ጋር በተያያዘ ሕዝቡ ወደ ተቃዋሚዎች እንዳይጠጋ በማድረግ ረገድ ራሳችን ተቃዋሚዎችም የምንፈጽመው ስህተት መኖሩ ይታያል፡፡ ይኸውም ኢህአዴግ በእኛ ላይ ስለሚፈጽመው አፈና ደጋግመንና አጋነን ማውራት በአንድ በኩል ኢህአዴግን የበለጠ እንዲጠላ ለማድረግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሳችንን ከሌሎች ተቃዋሚ

ፓርቲዎች የበለጠ እውነተኛ ተቃዋሚዎች ያስመስለናል ብለን ስለምናስብ ጉዳዩን ከአግባብ በላይ ለጥጠን ስናራግበው እንታያለን። የኢህአዴግን የአፈና ድርጊቶች በአግባቡ ማጋለጥ መቻል ተገቢና የሚጠቅም ስልት ቢሆንም፣ ተቃዋሚዎች ሁኔታዎችን በጣም አጋነን በማቅረብ በዚህ አገር ተደራጅቶ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ የሚቻልበት ሁኔታ ፈጽሞ እንደሌለ አድርገን ስንቀሰቅስ ግን ውጤቱ መልሶ እኛኑ ራሳችንን ጭምር የሚጐዳ ይሆናል።

ይህንን ለማለት የሚያስደፍረን የመጀመሪያው ምክንያት አገሪቱ ውስጥ ፈጽሞ ተደራጅቶ መሥራት አይቻልም የምንል ከሆነ በእውነትም አንዳንድ ድርጅቶች በአገራችን ለውጥ ለማምጣት የትጥቅ ትግል ነው የሚያዋጣው የሚል አቋም መያዛቸውን ትክክለኛ አቋም ያደርገዋል ማለት ነው። የእነዚህ ኃይሎች አቋም ትክክለኛ ይሆናል ብቻም ሳይሆን በዚች አገር በሰላማዊ መንገድ ተደራጅቶ መታገል አይቻልም ካላችሁ ታዲያ ለምን ሰላማዊ ትግሉን አታቆሙትም? የሚል አጣብቂኝ የሚያስገባ ጥያቄ በሕዝብ ዘንድ ሊያሥነሣም ይችላል። ሁለተኛው ምክንያት ከላይ በተለያዩ ክፍሎች ለመግለጽ እንደተሞከረው ተቃዋሚዎች የኢህአዴግን ተጽዕኖና አፈና ተቋቁማችሁ ትግሉን በአሸናፊነት መወጣት የማትችሉ ከሆነ ታዲያ የእናንተ ጥንካሬ የቱ ላይ ነው? የሚል ጥያቄም ያሥነሳል። ሦስተኛው ምክንያት የኢህአዴግ አፈና ፈጽሞ የሚያሠራ አይደለም የሚለውን ሮሮ ከመጠን በላይ ለጥጠን በማቅረብ ሕዝቡን እያስፈራራን ባለንበት ወቅት እንዴት አድርጐ ሌላው የኅብረተሰብ ክፍል ደፍሮ ወደኛ ሊመጣና ሊያጠናክረን እንደሚችል ግልጽ አይደለም። ስለዚህ ተቃዋሚዎች ስለሚደርስብን አፈና ከመጠን በላይ አጋነንና ደጋግመን የምንናገረው ነገር በውጤቱ እኛን ምን ያህል እየጠቀመን እንደሆነ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። በአሁኑ ወቅት የአገራችን የፖለቲካ ምህዳር ስለመጥበቡ በዘመቻ መልክ እያደረግን ያለው ቅስቀሳም ሕዝቡ በሰላማዊ ትግል ያለው እምነት ተሟጦ እንዲያልቅ በማድረግ የፖለቲካ ምህዳሩ ጠቦ በሚታይባቸው አካባቢዎች ዙሪያ ችግሩ የበለጠ እንዲባባስ ከማድረግ ይልቅ የበለጠ እንዲጠብና ጭራሹኑ እንዲጠፋ የማድረግ ውጤት እንዳያስከትል ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ይሆናል።

ሌላውና ዋናው ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ ማጣት በውጫዊ ምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለው በሕዝባችን ውስጥ ያለው የፖለቲካ ባህል ዝቅተኛነት ነው። ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከወቅቱ የተበላሸ የፖለቲካ ባህላችን አንጻር በአገራችን የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባል መሆን ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የብዙኃን ፓርቲ አሠራር በአገራችን ከተጀመረ ገና ዐሥራ ስምንት ዓመት ብቻ በመሆኑና አገራችንም ገና መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብ (Middle Class) ያልተፈጠረባት የድሀ አርሶ አደር አገር በመሆንዋ ምክንያት

የፖለቲካ ባህላችን ገና ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ገና ያልተጠናከረ በመሆኑ ምክንያት አገራችን ውስጥ በሥራ መቀጠርም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች የኢኮኖሚ ጥቅም ሊገኝ የሚችለው በዋናነት በመንግሥት ዙሪያ ስለሆነ፣ በተጨማሪም የመንግሥት ሥልጣን የያዘ ፓርቲ አባል መሆንም በሰዎች የግል ሕይወት ላይ የሚያስከትለው ስጋት ስለሌለ ሰዎች የገዥው ፓርቲ እንጂ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባል ለመሆን የሚፈልጉበትና የሚችሉበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው፡፡

ኢህአዴግ በሚሊየን የሚቆጠር አባል በሥሩ ማሰባሰብ መቻሉን በሕዝብ ዘንድ ያለውን ድጋፍ ማሳያ አድርጐ ሊጠቀምበት ሲፈልግ የምናይ ቢሆንም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የገዥ ፓርቲ አባል መሆን አብዛኛውን ጊዜ ከግል ጥቅምና ከኑሮ ዋስትና እንጂ ከፖለቲካዊ እምነት ጋር የተያያዘ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በደርግ ዘመንም ብዙ ሰዎች በአማላጅና ደጅ በመጥናት ጭምር የኢሠፓ አባል ይሆኑ የነበሩት የፖለቲካ እምነት ኖሯቸው ሳይሆን በዋናነት በሥርዓቱ ዙሪያ የሚገኘውን ጥቅማ ጥቅም ለመቀራመት ሲሉ ነበር፡፡ ስለዚህ ከላይ በጠቆምናቸው የተለያዩ ምክንያቶች ሕዝቡ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ ተደራጅቶ የመታገል ባህሉ ገና ዝቅተኛ በመሆኑ ተቃዋሚዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ እንዳይኖራቸው አንድ ምክንያት ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ደካማ ካደረጓቸው ከእነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ - በሰላማዊ ትግል ላይ ያላቸው አቋም ወላዋይ መሆኑ፣ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በሚል ውጫዊ ግፊት የማይጣጣሙ ፓርቲዎች በአንድ ኅብረት ውስጥ አብረው ለመሥራት የሚያደረጉት ሙከራና በገንዘብ ድጋፍ በኩል የዲያስፖራው ጥገኛ መሆናቸውም ተጨማሪ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ ከወቅቱ ትግል ውስብስብ ባህሪና ከገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ሲመዘን በአሁኑ ወቅት የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ አባል የሆነበትን ፓርቲ ኢዴፓን ጨምሮ በአገሪቱ አንድም ጠንካራ ሊባል የሚችል ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አለ ማለት አይቻልም፡፡

ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጥንካሬና ድክመት ለመገምገም ስንሞክር ተቃዋሚ ፓርቲዎች መንግሥታዊ ሥልጣን ያልያዙ በመሆናቸው ምክንያት ቢያንስ በመርህ ደረጃ ከገዥው ፓርቲ በተሻለ አገርንና ሕዝብን የሚጠቅም አጀንዳ ቀርፀው የመቅረብ የተሻለ ዕድል ያላቸው ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች በዚህም ረገድ መሠረታዊ ችግር ያለባቸው ሆኖ ይታያል፡፡ መንግሥታዊ ሥልጣን በሰላማዊ መንገድ ከአንድ ፓርቲ ወደ ሌላው ፓርቲ ሲሸጋገር ገና ባልታዩበት በእኛ አገር ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎች በየወቅቱ በሚፈራረቁባቸው ዴሞክራሲያዊ አገሮች ጭምር ብዙውን ጊዜ በተቃዋሚነት የሚገኙት ፓርቲዎች በሥልጣን ላይ

ከሚገኙ ፓርቲዎች የተሻለ በሕዝብ ተቀባይነት ያለው አጀንዳ በምርጫ ወቅት ይዘው ሲቀርቡ ይታያሉ፡፡ የተቃዋሚዎቹ አጀንዳ በተግባር ያልተፈተነና ምን አልባትም በሥልጣን ላይ ከሚገኙት ፓርቲዎች ያልተሻለ በሆነበትም ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ዜጐች የተሻለ ለውጥ ለማየት ካላቸው ከፍተኛ ፍላጐትና ጉጉት የተነሣ የተቃዋሚዎችን አጀንዳ መደገፍን ሲመርጡ ይታያሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ነው በብዙ ዴሞክራሲ በዳበረባቸው አገሮች ቢያንስ ከሁለት የሥልጣን ዘመን (Term) በኋላ በሥልጣን ላይ የሚገኙ ፓርቲዎች በምርጫ የሚሸነፉበት ዕድል የሰፋ ሆኖ የምናየው፡፡

አንድም ጊዜ ተቃዋሚ ፓርቲ ገዥውን ፓርቲ በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን ይዞ በማያውቅበት በእኛ አገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ የተሻለ አገራዊ አጀንዳ በጎላ ሁኔታ ይዘን መገኘት የሚጠበቅብን ቢሆንም ይህንንም ዕድልና አጋጣሚ በአግባቡ ስንጠቀምበት አይታይም፡፡ ለዚህም ሁለት ምክንያቶችን በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት አብዛኛዎቹ በአገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ በተመሳሳይ ብሔርን ወይም ብሔረሰብን መሠረት አድርገው የተደራጁ መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የመንግሥት ሥልጣን ላይ የማይገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመሆናቸው በስተቀር በአደረጃጀት ቅርጽ ብቻ ሳይሆን ከአገራዊ አጀንዳ ይዘት አንጻርም ከገዥው ፓርቲ ብዙም የተለየ አቋም ያላቸው አይደሉም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ባላነሰ ሁኔታ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በሚገኙ ሁሉም አንቀጾች ጠንካራ እምነት ያላቸው ሆነው ሳለ ከኢህአዴግ ጋር ያላቸው መሠረታዊ ልዩነት ሕገ-መንግሥቱ በአግባቡ ተግባር ላይ አልዋለም የሚል ነው፡፡ ከእነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ደቡብ አካባቢ የሚንቀሳቀሱት ቀድሞም ከኢህአዴግ ጋር ተመሳሳይ አጀንዳ ይዘው የሽግግር መንግሥቱ አባል ሆነውና የመንግሥት ሥልጣን ጭምር ተጋርተው ከኢህአዴግ ጋር አብረው ሲሠሩ የነበሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጅቶች ከሽግግር መንግሥቱ ወጥተው ተቃዋሚውን ጐራ የተቀላቀሉት ቀድሞውንም ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ከኢህአዴግ የተለየ መሠረታዊ ልዩነት ኖሯቸው ሳይሆን በማዕከላዊ መንግሥትና በሚንቀሳቀሱባቸው ክልሎች የኢህአዴግና የአባል ድርጅቶቹ የሥልጣን የበላይነት እየተጠናከረ በመምጣቱና በተለያዩ የአፈጻጸም ጉዳዮች መስማማት ባለመቻላቸው ነው፡፡

በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚገኙ ዘግይተው የተቋቋሙ ኦብኮንና ኦፌዴንን የመሳሰሉ የኦሮሞ ድርጅቶችም በአዲስ ፓርቲነት ለመመሥረት የበቁት አዲስ አገራዊ አጀንዳ ይዘው ሳይሆን በዋናነት ሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀመጡት የብሔር-ብሔረሰብ መብቶች በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል አልቻሉም ብለው ነው፡፡ በቅርቡ ከኢህአዴግ ተነጥለው

ተቃዋሚውን ጐራ የተቀላቀሉት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳም በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በተቀመጠው መሠረት የኦሮሞ ሕዝብ ከኢትዮጵያ መገንጠል ስለመፈለጉና አለመፈለጉ በሕዝበ-ውሳኔ ይወሰን የሚል እንጂ በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ አባል ሆንኩ እስካሉበት ጊዜ ድረስ በሌላ በአንድም ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳይ ከኢህአዴግ የተለየ አቋም አለኝ ሲሉ አልሰማንም፡፡ ከህወሃት የተነጠሉት እነ አቶ ገብሩ ዐሥራትም ከኢህአዴግ ጋር ሕገ-መንግሥታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ መሠረታዊ ልዩነት አለን ብለው እስካሁን በድፍረት ሲናገሩ አላዳመጥንም፡፡

ስለዚህ እነዚህ ፓርቲዎች የመንግሥት ሥልጣን ላይ ስለማይገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተብለው የሚታወቁ ቢሆንም በገዥው ፓርቲ ዙሪያ የሚታየው የአገራዊ አጀንዳ ድክመት በእነሱም ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ ይታያል፡፡ ይኸውም ከላይ ስለ ኢህአዴግ ድክመትና ጥንካሬ ለመገምገም ስንሞክር እንዳየነው፣ ብሔርን ወይም ብሔረሰብን መሠረት አድርጐ የተደራጀ ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል በራሱና በሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን የኃይል ሚዛን የሚያይበት መንገድ አገራዊ አጀንዳዎችን ከመቅረጽ አኳያ ምክንያታዊ ከሆነ ስጋትና ምክንያታዊ ካልሆን አካባቢያዊና ግላዊ ራስ ወዳድነት የሚመነጭ የራሱ ውስንነት ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ራሱን በብሔረሰባዊ ማንነቱ ያደራጀ ቡድን በአንድ በኩል "እኛና -እነሱ"" የሚል ፋክክር ውስጥ ብቻሚነት የሚኖር በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እያንዳንዱን አገራዊ ጉዳይ "የእኔ" ከሚለው ጥቅም ጋር አያይዞ ለማየት ስለሚገደድ ምንጊዜም ሠፊ አገራዊ ተቀባይነት ያለው አጀንዳ የማራመድ ውስንነት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ እነዚህ እነ ፕሮፌሰር በየነን፣ አቶ ገብሩ ዐሥራትን፣ ዶ/ር መረራንና አቶ ቡልቻን በመሰሉ ታዋቂ ግለሰቦች የሚመሩ በርካታ ድርጅቶች ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ተቃዋሚው ጐራ ከኢህአዴግ በጎላ መጠን ተሽሎ እንዳይታይ በማድረግ ረገድ አሉታዊ ሚናቸው ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከእነዚህ ብሔርን ወይም ብሔረሰብን መሠረት አድርገው ከተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለየ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከኢህአዴግም ሆነ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ከሌላቸው ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሻለ አገርና ሕዝብ የሚጠቅም አገራዊ አጀንዳ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ድርጅቶች አጀንዳ፣ በየፕሮግራማቸው ላይ የሠፈረና አንዳንድ ጊዜም በተለያዩ መድረኮችና የምርጫ ዘመቻዎች ወቅት ባልተብራራ ሁኔታ ለሕዝብ ሲቀርብ የሚደመጥ ቢሆንም አገራዊ አጀንዳቸው የሚጠበቀውን ያህል በጉላ ሁኔታ በኢህአዴግ ላይ የበላይነት ይዞ አይታይም፡፡ ይህ የሆነበት አንዱ ምክንያት ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ፓርቲዎቹ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ደካማ ደረጃ ላይ የሚገኙና አስተሳሰባቸውን በአግባቡ ወደ ሕዝቡ ውስጥ የማስረጽ ድርጅታዊ ብቃት

የሌላቸው በመሆኑ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ አገራዊ አጀንዳዎቻቸው በፖለቲካ መድረኩ ውስጥ ጉልተው እንዳይታዩ ያደረጉባቸው ሌሎች ምክንያቶችም አሉ፡፡

በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ እነዚህ ኅብረ-ብሔራዊ ፓርቲዎች ከላይ ከጠቀስናቸው ኅብረ-ብሔራዊ ያልሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ብዙውን ጊዜ በአንድ ኅብረት ውስጥ አብሮ የመሥራት ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም በአገራችን የወቅቱ የፖለቲካ ባህል በፓርቲዎች መካከል ካለው የአገራዊ አጀንዳ ልዩነት በላይ ተቃዋሚ ፓርቲ ሆኖ መገኘት በራሱ እንደ አንድ ዋና የጋራ አጀንዳ ስለሚቆጠር እነዚህ ኅብረ-ብሔራዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሕዝቡን "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚል ምክንያታዊ ያልሆነ ግፊት ለማስተናገድ ሲሉ ከላይ ከጠቀስናቸው ከኢህአዴግ ብዙም የተለየ አገራዊ አጀንዳ ከሌላቸውና በብሔር ወይም በብሔረሰብ ደረጃ ከተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በአንድ ኅብረት ውስጥ ታቅፈው ለመሥራት ስለሚገደዱ አገራዊ አጀንዳቸው የመደብዘዝ አደጋ ሲያጋጥመው ይታያል፡፡

ምክንያቱም በእነዚህ ሁለት ዓይነት አደረጃጀት በሚከተሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለው የአገራዊ አጀንዳ ልዩነት ጉልቶ በመውጣት አብሮ መሥራቱን አደጋ ውስጥ እንዳይከተው ስለሚሰጋ ብዙውን ጊዜ የሚመርጡት ኢህአዴግን በሚመለከት ያላቸውን የጋራ ተቃውሞ ለማስተጋባት እንጂ የሚያራምዱትን አገራዊ አጀንዳ አጉልቶ ለማሳየት አይደለም፡፡ እነዚህ ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ምንም ዓይነት አንድነት ሳይኖራቸው ተቃዋሚነታቸውን ብቻ የአንድነት መገለጫ አድርገው በአንድ ኅብረት ውስጥ አብረው ለመሥራት የሚሞክሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በግልጽ ለሕዝብ ቢያቀርቡት ኅብረ-ብሔራዊ በሆኑትና ባልሆኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለው የአገራዊ አጀንዳ ልዩነት በይዘቱ ኅብረ-ብሔራዊ በሆኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎችና በኢህአዴግ መካከል ካለው መሠረታዊ ልዩነት የተለየና ያነሰ አይሆንም፡፡ ይህም የሚያሳየው የውስጥ ልዩነታቸውን ለጊዜው አለባብሰው በሆነ አጋጣሚ በጋራ ኢህአዴግን ለማሸነፍ የሚችሉበት ዕድል ቢፈጠር እንኳ የጋራ አገራዊ አጀንዳ ሊያራምድ የሚችል አንድ መንግሥት ሊያቋቁሙ የማይችሉ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነቶቹ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ" በሚል አጉል ቀመር የሚጣመሩ የፖለቲካ ኃይሎች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ የሶሻል ዴሞክራሲና የሊበራል ዴሞክራሲ ቅልቅሎች ስለሆኑ አገሪቱን ወደ ሁለት ወይም ሦስት እንጂ ወደ አንድ አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችል የጋራ አጀንዳ አላቸው ማለት አይቻልም፡፡

ስለዚህ በእነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ይህንን ዓይነት መሠረታዊ ልዩነት መኖሩን ሕዝቡ ከተገነዘበው ኅብረ-ብሔራዊ የሆኑና ያልሆኑ ተቃዋሚዎች በአንድ ኅብረት ውስጥ አብሮ የመሥራትን ጉዳይ ትርጉም የለሽ ስለሚያደርገው ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ኅብረ-ብሔራዊ

ድርጅቶች ያላቸው የተሻለ አጀንዳ ጐልቶ እንዳይወጣ አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡ ኅብረ-ብሔራዊ ፓርቲዎች በዚህ ዓይነቱ ደካማ አስተሳሰብ በአገራዊ አጀንዳ ከማይመሳሰሏቸው ፓርቲዎች ጋር በተለመደው ሁኔታ በአንድ ኅብረት ውስጥ መሥራትን እስከቀጠሉበት ድረስም ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ያላቸው የተሻለ ዕድል ወደፊትም እንደደበዘዘ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ሁለተኛው ኅብረ-ብሔራዊ የሆኑትም ሆነ በአጠቃላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር በኢህአዴግ ላይ የጐላ የበላይነት እንዳይኖራቸው ያደረገው ምክንያት ጭፍን ተቃዋሚነት ያስከተለው ችግር ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የወደፊቱ የህልውናችን ዋናው መሠረት የያዝናቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎቻችንን በሕዝብ ውስጥ ማስረጽና እውነተኛ አማራጭ ፓርቲ ሆኖ መቅረብ መሆኑን በመዘንጋት፣ ኢህአዴግን በጭፍን መቃወምና ማጥላላትን ዋነኛ አጀንዳችን አድርገን መያዛችን ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ተጠናክረን እንዳንወጣ አድርጎናል፡፡

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ኢህአዴግ ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ብዙ ስስ ብልቶች ያሉት ድርጅት ነው፡፡ በአንድ በኩል መንግሥታዊ ሥልጣን ላይ የሚገኝ ድርጅት በመሆኑና የሥልጣን የበላይነቱን አስጠብቆ ለመቀጠል ሲል የሚያራምዳቸው አንዳንድ አጀንዳዎች በተፈጥሯቸው የሕዝብ ድጋፍ ሊያስገኙ የማይችሉ በመሆናቸው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መጀመሪያ እንወክለዋለን ከሚሉት ብሔረሰባዊና አካባቢያዊ ጥቅም ተነስተው ቀጥለው ወደ አገራዊ አጀንዳዎች የሚሻገሩ በመሆናቸው ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር ደካማ የመሆናቸው ጉዳይ ከፍላጐትና ከዕውቀት ማነስ ሳይሆን ከአደረጃጀት ባህሪያቸው ጋር ተፈጥሯዊ ቁርኝት ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚዎች ትኩረታችንን በዚህ የኢህአዴግ ስስ ብልት ላይ አድርገን አገርንና ሕዝብን በተሻለ ሁኔታ የሚጠቅሙ አገራዊ አጀንዳዎችን በተጨባጭ ለሕዝቡ በማቅረብ የአጀንዳና የሐሳብ የበላይነት ማግኘት ሲገባን ትኩረታችንን ጭፍን ተቃውሞና ውግዘት ማቅረብ ላይ ስላደረግነው በተቃራኒው ኢህአዴግ እኛን አማራጭ ሐሳብ የሌለን አድርጐ እንዲከሰን ዕድል ፈጥረንለታል፡፡

ሦስተኛው ምክንያት ከዚሁ ከጭፍን ፖለቲካ ማራመድ ጋር በተያያዘ ተቃዋሚዎች የትግላችንን የመጨረሻ ግብ ኢህአዴግን ከሥልጣን ማስወገድ አድርገን ስለምናቀርብና በዚህ ቅኝት የተቀረፀው ደጋፊያችን የሆነው ሕዝብም ትግሉን የነፃ አውጭነት ወይም የአርበኝነት ትግል አድርጐ ስለሚያየው በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚዎች መካከል ስለአለው የአገራዊ አጀንዳ ልዩነት ትኩረት ሰጥቶ እንዳይከታተል አድርጐታል፡፡ ደጋፊያችን የሆነው አብዛኛው ኅብረተሰብ ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ ጋር ያለንን ልዩነት በደፈናው አገርን የመውደድና የመጥላት ልዩነት

ኢዴፓ ኢዴፓ ኢዴፓ

አድርጐ ስለሚያየው፣ በተቃዋሚዎች መካከል ያለውን ልዩነት ደግሞ የሃቀኛና የታማኝ ተቃዋሚ ልዩነት አድርጐ ስለሚያየውና እኛም በሕዝቡ የበለጠ ተቀባይነት ለማግኘት ስንል የምንጠቀምበት ስልት የተሻለ አገራዊ አጀንዳ ያለን መሆኑን አጉልተን በማሳየት ሳይሆን ኢህአዴግን ያለፍርሀትና በጭፍን በመቃወምና በማውገዝ ከሌላው የበለጥን መሆኑን በማሳየት ሆኗል። እንዲህ ዓይነቱ የአስተሳሰብ ድክመትም የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ ከጥላቻና ከጭፍን ተቃውሞ ተላቆ የአማራጭ አጀንዳዎች (Issue Politics) ትግል እንዳይሆን አድርጐታል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊነሣ የሚገባው አራተኛው ምክንያት የእወደድ ባይነት (Populist) የፖለቲካ ስልት ነው። ይኸውም ተቃዋሚዎች ለአገርና ለሕዝብ ይጠቅማሉ ብለን የምናምንባቸውን አገራዊ አጀንዳዎች በሳል በሆነ ሁኔታ ለሕዝብ ከማቅረብ፣ ምንአልባትም ሕዝቡ ያልተገነዘበው ጉዳይ ኖሮ አጀንዳዎቻችንን አልቀበለን የሚልበት አጋጣሚ ሲፈጠርም በአቋማችን ጸንተን በመገኘት ሕዝቡን በሂደት ለማሳመን ከመሞከር፣ አንዳንድ ጊዜም ሕዝቡ ተገቢ ያልሆነ ስሜታዊ አቅጣጫ ሲይዝ ከሕዝቡ ጋር ተጋፍጠንም ቢሆን ሕዝቡን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ለማስገባት የሚያስችል የአመራርነት ሚና ከመጫዎት ይልቅ ብዙውን ጊዜ ሕዝቡ ሊያዳምጠው ወይም ለጊዜው ሊደሰትበት ይችላል ብለን የምናምንበትን ጉዳይ ነው መናገርና መሥራት የምንፈልገው። አንዳንድ ጊዜ በሕዝቡ ውስጥ የሚንሸራሸሩ አንዳንድ አስተሳሰቦች ትግሉንም ሆነ አገሪቱን ጐጂ መሆናቸውን ውስጣችን በደንብ እያወቀው ጭምር የሕዝብን አስተሳሰብ መቃወም የፖለቲካ ነውር እንደሆነ አድርገን በመቁጠር የተሳሳተን አቋም እስከ መቀበል የምንደርስበት ሁኔታ አለ። ማለትም ለእኛ ትልቁ ቁምነገር የጉዳዩ ትክክል መሆንና አለመሆን ሳይሆን ሕዝቡን ማስደሰቱና በስሜት ማስጨብጨብ ሆኖ ይታየናል።

ይህ የእወደድ ባይነት ባህርያችንም በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የምንገኝ የፖለቲካ መሪዎች ሕዝቡን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የምንመራ እውነተኛ የፖለቲካ መሪዎች ሳንሆን በሕዝብ ጊዜያዊ ስሜት የምንመራ እወደድ ባዮች አድርጐናል። ቅንጅት ምርጫ 97ን ተከትሎ ፓርላማ ላለመግባትና አዲስ አበባ መስተዳድርን ላለመረከብ የወሰነውም በራሱ ውሣኔ መተማመን አቅቶት የዚህ ዓይነቱ የእወደድ ባይነት ፖለቲካ ሰለባ በመሆኑ ነው። በወቅቱ ለቅንጅት የበለጠ ያሳስበው የነበረው ትልቁ ቁምነገር ለሕዝቡና ለትግሉ የሚጠቅም ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን-አለመወሰኑ ሳይሆን ሕዝቡ ለጊዜው ይወደዋል ተብሎ የሚታሰበውን አቋም አራምዶ ከጊዜያዊ ወቀሳና ትችት ነፃ ሆኖ መገኘት ነበር። እንዲህ ዓይነቱ ሕዝቡን በስሜታዊና ጊዜያዊ ጉዳይ በማስጨብጨብ ጀግና መስሎ መታየት በወደፊቱ የትግሉ ህልውናና የደጋፊዎቻችን ሞራል ላይ ምን ዓይነት አደጋ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ማስተዋል አልተቻለም ነበር።

እነዚህ ከዚህ በላይ ያየናቸው ከጭፍን ተቃውሞ ጋር የተያያዙ ስልቶች ተቃዋሚዎች በኢህአዴግ ላይ የጐላ የሐሳብ የበላይነት እንዳናገኝ ያደረጉን መሰናክሎች ሆነውብናል፡፡ ወደፊትም እነዚህን መሰናክሎች ከፊታችን ጠራርገን አስወግደን ምክንያታዊ ፖለቲካ ማራመድ እስካልቻልን ድረስ ድርጅታዊ ጥንካሬአችን ደካማ እንደሆነው ሁሉ ከአገራዊ አጀንዳ አንጻርም እየተዳከምን መምጣታችን አይቀርም፡፡ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ እያየናቸው ያሉ አንዳንድ ምልክቶችም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጡት፡፡ በአገርና በሕዝብ አንድነት ጉዳይ ላይ ከኢህአዴግ የበለጠ አጀንዳ አለን ብለን ስንመጻደቅ የኖርን ኀብረ-ብሔራዊ የሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቀስ በቀስ ከአገርና ከሕዝብ አንድነት ጋር የተያያዙ አጀንዳዎችን ሳይቀር በኢህአዴግ እየተነጠቅን እንገኛለን፡፡

ከማንኛውም ጉዳይ ጋር በተያያዘ ኢህአዴግን በጭፍን ለመቃወም እየታየ ካለው ፍላጐት በመነጨ በቅርቡ በሶማሊያ ጉዳይ እንደታየው ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ያላቸውን ኀይሎች ጭምር በመደገፍ አጉል የፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ ለመግባት እየተሞከረ በመሆኑ ቀስ በቀስ ኢህአዴግ የአገር አንድነት ጠበቃ ሆኖ የመቅረብ ዕድሉ እንዲሰፋ ተቃዋሚዎች ራሳችን ሁኔታዎቹን እያመቻቸንለት እንገኛለን፡፡ ቀደም ሲል ተቃዋሚዎች በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንድናገኝ ያስቻለን አንዱ አጀንዳ በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ላይ የነበረን አቋም ቢሆንም ኢህአዴግ በግልጽ ባይናገረውም ቀስ በቀስ በዚህ ረገድ የነበሩንን አጀንዳዎች ቀምቶናል፡፡ ከከተማ ልማትና ከመሠረተ ልማት መስፋፋት ጋር የምናነሣቸው አጀንዳዎችም ኢህአዴግ ቀስ በቀስ የራሱ እያደረጋቸው በመምጣቱ በሂደት ተቃዋሚዎችና ኢህአዴግ ቦታችንን የመቀያየር አዝማሚያ ውስጥ ስንገባ እየታየ ነው፡፡ የሚገርመው ራሳችን ተቃዋሚዎች ስናራምደው የነበረውን አጀንዳ ኢህአዴግ ሲያራምደው ስናይ ተቃዋሚዎች እንዲህ ዓይነቱን አጋጣሚ የመስመራችንን ትክክለኛነት ማሳያ አድርገን ልንጠቀምበት ሲገባ በተቃራኒው የራሳችንን የቀድሞ አጀንዳ ጭምር ተፃረን ስለምንቆም "የተቃዋሚዎች አጀንዳ ኢህአዴግን መቃወም ብቻ ነው" እያለ ኢህአዴግ በተደጋጋሚ የሚያቀርብብንን ክስ ራሳችን ይበልጥ እያጠናከርነው መጥተናል፡፡

ሌላውና ሳይጠቀስ ሊታለፍ የማይገባው በተቃዋሚዎች ዙሪያ የሚታየው ድክመት በተለምዶ አነጋገር "ዘረኝነት" የምንለው አካባቢያዊ ስሜት ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ብዙውን ጊዜ ገዥውን ፓርቲ በዘረኝነትና በጠባብነት ስንከስ የምንደመጥ ቢሆንም ወደ ውስጣችን ገባ ብሎ ላዬን ሰው ግን ችግሩ በእኛም ውስጥ የበለጠ ሥር የሰደደ ሆኖ ይገኛል፡፡ በይፋ ባንናገረውም ኀብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያለንና ከማንም በላይ ለአገሪቱ አንድነት ጠበቃ ነን ስንል የምንደመጠው ፓርቲዎች ውስጥ ውስጡን በብሔር-ብሔረሰብ ደረጃ የተደራጀውን ፓርቲ ሁሉ

ሥልጣን ላይ ያለም ይሁን ተቃዋሚ በጥቅሉ ጕሰኛ፣ ጠባብና አገር ከፋፋይ አድርገን ነው የምናየው፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳንዶቹ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኅብረ-ብሔራዊ ካልሆኑ ፓርቲዎች ጋር በአሁኑ ወቅት አብረው ለመሥራት ሲሞክሩ የሚታዩት በእውነት አብሮ ለመሥራት የሚያስችል የጋራ አጀንዳ አለን ብለው በማመን ሳይሆን ኢህአዴግን ለመጣል በሚደረገው ትግል ለጊዜው ልንጠቀምባቸው እንችላለን ከሚል የአጉል ብልጣ ብልጥነት ፍላጐት በመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንዳንዶቹ ራሳቸውን በብሔር-ብሔረሰብ ደረጃ ያደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ በአፋቸው ሲናገሩ የሚደመጡት የተለየ ቢሆንም ኅብረ-ብሔራዊ የሆኑትን ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም የመሃል አገርና የሶማሌን ሰው የሚመራውን ፓርቲ ከኢህአዴግ ወይም ከህወሃት ነጥለው አያዩትም፡፡ ለአንዳንዶቹ የኦሮሚያና የደቡብ ድርጅቶች አቶ መለስ ዜናዊ፣ ኢንጂነር ኃይሉ ሻወልም ሆኑ ልደቱ አያሌው ሁሉም “የነፍጠኛው ሥርዓት” ርዝራዦችና ተቀጥላዎች ተደርገው ነው የሚታዩት፡፡ ሌላው ቀርቶ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ባለው የተቃዋሚ ጐራ ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ሰዎች አመለካከት ከሸዋ ያልተወለደ ሰው ዛሬም እንደ ትናንቱ የኢትዮጵያ ሥርወ መንግሥት ወራሽ የመሆን መብት እንዳለው ተደርጐ አይታይም፡፡ በእንዲህ ዓይነቶቹ የወቅቱን ትግል እጅግ በጠበበ አመለካከት የሥልጣን ጥያቄ ብቻ አድርገው በሚያዩ አንዳንድ ሰዎች ዐይንም አቶ መለስ ዜናዊም ሆኑ ልደቱ አያሌው የሸዋን ሥርወ መንግሥት የሚቀናቀኑ ሰሜነኞች ተደርገው ነው የሚታዩት፡፡ በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን መከፋፈል ተከትሎ በተካሄደው የአሉባልታ ዘመቻ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ በግለሰብነቱ ብቻ ሳይሆን በወሎየነቱ ጭምር ሲሰደብ ያየነው ያለምክንያት ሳይሆን ከዚሁ ከዘረኝነት በሽታ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ደፍረን በግልጽ ባንናገረውም እንዲህ ዓይነቱን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ፖለቲካ የማይመጥን አሳፋሪ ገመና በውስጣችን ይዘን ነው ስለ ዴሞክራሲ ሥርዓትና ስለ አገር አንድነት ጠበቃ ነን እያልን ስንመጻደቅ የምንታዬው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ተቃዋሚዎች ግልጽ በሆነና በማያከራክር ሁኔታ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር ከኢህአዴግ ጋር ሊነፃፀር በማይችል ደካማ ደረጃ ላይ የምንገኝ ነን፡፡ ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያለን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢያንስ በወረቀት ላይ ከኢህአዴግ የተሻለ ጥንካሬ ላይ የምንገኝ ቢሆንም ትግሉን የምናካሂድበት ስልት በተጨባጭ አገራዊ አጀንዳዎችን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ለማድረግ ባለመቻላችን በዚህም ረገድ በኢህአዴግ ላይ ጐልቶ የሚታይ የበላይነት ማግኘት አልቻልንም፡፡ ተቃዋሚዎች በእነዚህ መሠረታዊና መዋቅራዊ ድክመቶቻችን ዙሪያ ግልጽና ጥልቅ ውይይት አካሂደን ራሳችንን

የማስተካከልና የማደስ አቋም በድፍረት ካልወሰድን በስተቀር በአሁኑ ወቅት እያራመድነው የምንገኘው አቋምና ስልት ወደምንፈልገው ውጤትና ግብ ሊያደርሰን ይቅርና ለህልውናችን መጥፋት ሰፊ በር የሚከፍት የፖለቲካ ጨዋታ ነውና ብልህና አስተዋይ አመራር ካላገኘ በስተቀር አደጋው የከፋ ነው፡፡

## 2.2.1 የተቃዋሚ ፓርቲዎች የኅብረት ጥያቄ

በተቃዋሚው ጎራ ዙሪያ በሚገኘው ኅብረተሰብ እንደ ኅብረት የመፍጠር ጥያቄ ያለማቋረጥ ደጋግሞ የሚነሣና ትኩረት የሚስብ ጥያቄ አለ ማለት አይቻልም፡፡ እንዲያውም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተቃዋሚዎች ኅብረት የመፍጠር ጉዳይ ሌላ አማራጭ የሌለውና ትግሉን ለውጤት ለማብቃት ብቸኛ መፍትሄ ተደርጐ ስለሚታይም "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በሚል ለሌሎች አማራጮች ዕድል በማይሰጥ የከረረና የጠበበ መፈክር ታጅቦ ሲቀርብ ይታያል፡፡ ተቃዋሚዎች ሲቻል ቢተባበሩ፣ ሳይቻል ደግሞ ሳይሰባበሩ ተከባብረው በተናጠል ቢጓዙ የሚሻል ቢሆንም፣ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚለው ምክንያታዊ ያልሆነ መፈክር በአንድ በኩል የሕዝቡ የግፊት መሣሪያ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የብልጣብልጥ ፖለቲከኞች መወደጃና መንጠላጠያ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የፈጠሯቸው ከዘጠኝ የማያንሱ የተለያዩ ኅብረቶች ከአንድ ወይም ከሁለት ዓመት በላይ ዕድሜ ሳይኖራቸው ያለ ውጤት ፈርሰዋል፡፡ እነዚህ ሲመሠረቱ የሕዝብን ቀልብ ስበው የነበሩ በርካታ ኅብረቶች ለምንና እንዴት ያለ ውጤት ሊፈርሱ እንደቻሉ ግን እስካሁን አንድም ጊዜ ለመገምገም ያልተሞከረ ቢሆንም ዛሬም እንደትናንቱ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚለው ስሜታዊና ትርጉም የለሽ ጥያቄ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ኅብረትን የመፍጠር ጥያቄ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ /popular/ የሆነ ጥያቄ ከመሆኑም በላይ ጥያቄው በራሱ ቅንና ተገቢ በመሆኑ ምክንያት የፖለቲካ ሰዎች ገንቢ በሆነ ሁኔታም ቢሆን እስካሁን ሊተቹት ሲደፍሩ አልታየም፡፡ በዚህም ምክንያት ከአሉባልታ ቀጥሎ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" እንደሚለው ስሜታዊ ጥያቄ ለተቃዋሚው ጐራ መዳከም ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ የሚችል ሌላ ችግር አለ ማለት ያስቸግራል፡፡ የኅብረት ጥያቄ በተደጋጋሚ እንደታየው በራሱ ውጤታማ ለምን መሆን እንዳልቻለ፣ ውጤታማ አለመሆኑ በትግሉ ላይ ያስከተለው ችግር ምን እንደሚመስልና ከዚህ ችግር ተላቆ ውጤታማ እንዲሆን የሚያስችሉት መፍትሄዎችም ምን እንደሆኑ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡፡

ኢዮጋ ኢዮጋ ኢዮጋ

የመጀመሪያው በኅብረት ጥያቄ ዙሪያ የሚታየው ችግር የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው ኅብረተሰብ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመካከላቸው ያለውን ልዩነትና አንድነት ግምት ውስጥ ሳያስገባ ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድ ኅብረት ውስጥ እንዲካተቱ መፈለጉና ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የደጋፊያቸውን ግፊት መቋቋም እየተሳናቸው በትግል ስልት፣ በአደረጃጀት ቅርፅ፣ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ፕሮግራም ይዘት ከማይመስሏቸውና ከድርጅት አቅም አንጻርም ከማይመጣጠኗቸው ፓርቲዎች ጋር በአንድ ኅብረት ውስጥ ለመካተት መሞከራቸው ነው። ከላይ በሌላ ርእሰ-ጉዳይ ለማየት እንደሞከርነው ከባህሪና ከፖለቲካ ባህል አኳያ ያላቸው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በትግል ስልት፣ በአደረጃጀት ቅርፅም ሆነ በአገራዊ አጀንዳ ይዘት ጉራማይሌ ናቸው።

እስካሁን በነበረው ሂደት በደፈናው የሥርዓቱ ተቃዋሚ መሆን ዋና የመተባበሪያ አጀንዳ ተደርጐ ስለሚታይ የትጥቅ ትግል አካሂዳለሁ የሚለው በሰላማዊ መንገድ ከሚታገለው፣ በውጭ አገር በስደት ላይ የሚገኘው አገር ውሰጥ እየታገለ ከሚገኘው፣ በብሔር ማንነቱ የተደራጀው ኅብረ-ብሔራዊ ሆኖ ከተደራጀው፣ ለአንድ ክልል ነፃነት እታገላለሁ የሚለው ለኢትዮጵያ አንድነት እታገላለሁ ከሚለው፣ ሕገ-መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ በተግባር መዋል አለበት ብሎ የሚያምነው ሕገ-መንግሥቱ ተቀዶ መጣል አለበት ከሚለው፣ መሬት የመንግሥት ሆኖ ይቀጥል የሚለው መሬት ሊሸጥ ሊለወጥ ይገባዋል ከሚለው ጋር ተደበላልቆ አንድ ኅብረት ውስጥ እንዲካተት ሲሞከር በመኖሩ የኅብረት ጥያቄ ለውጤት መብቃት ሳይችል ቀርቷል።

አንዳንዶቹ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሌሎቹ በብሔር ማንነት ከተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሁለንተናዊ መልኩ ያላቸው ልዩነት ከገዥው ፓርቲ ጋር ካላቸው ልዩነት የተለየ ወይም የጠበበ አይደለም። ሌላው ቀርቶ አገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ ትግላቸውን እያራመዱ በሚገኙት በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ኢህአዴግን ከመቃወምና ኢህአዴግን ከሥልጣን ለማስወገድ በጋራ ከመታገል ያለፈ ወደፊት በሆነ አጋጣሚ መንግሥት ለመሆን ቢበቁ በጋራ ሊያስፈጽሙት የሚችሉት የጋራ አገራዊ አጀንዳ በመካከላቸው አለ ማለት አይቻልም። በእነዚህ ፓርቲዎች መካከል ዛሬ ተፈጠሩ የተባሉ ኅብረቶች ነገ ፈረሱ ሲባሉ የምንሰማውም ያለ ምክንያት ሳይሆን የሥርዓቱ ተቃዋሚ በመሆናቸው ብቻ እንጂ እውነተኛና ትክክለኛ የአስተሳሰብና የዓላማ አንድነት ኖሮአቸው ከመጀመሪያው የተመሠረቱ ኅብረቶች ባለመሆናቸው ነው። በቅርቡ በተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥምረት ተመሠረተ የተባለው “መድረክ” ውስጥ አብዮታዊ ዴሞክራት ነን የሚሉት የቀድሞ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ሊበራልና ሶሻል ዴሞክራት ነን ከሚሉት ሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር በአንድ

ኀብረት ውስጥ ታቅፈው ለመሥራት ሲሞክሩ መታየታቸውም የዚሁ “የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው” የሚል አመለካከት መሠረታዊ ድክመት መገለጫ ነው፡፡

ድርጅቶቹ ከዚህ በላይ በጠቀስናቸው ነጥቦች የተለያዩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ኀብረት የሚመሠርቱት ተመጣጣኝ ድርጅታዊ ጥንካሬ ኖሯቸው ስላልሆነ አንዳንዶቹ ኀብረቶች መሬት ላይ የሚጨበጥና የሚዳሰስ እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ፓርቲዎች የተመሠረቱ ሳይሆኑ የግለሰቦች ስብስብ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በተለይም አንድ ጊዜ ፓርቲ ከመሠረቱ በኋላ በሕዝቡ ውስጥ ገብተው የሚጨበጥ ሥራ ለመሥራት ያልቻሉ የፖለቲካ መሪዎች አብዛኛውን ጊዜ በአገሪቱ ፖለቲካ ተሰሚነት ለማግኘት የሚጥሩት በኀብረት ስም በሚቋቋም ስብስብ ውስጥ የአመራር ቦታ ላይ በመንጠላጠል ሲሆን ይታያል፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ ግለሰቦች የሚመሯቸው ኀብረቶች ቀድሞውንም በሕዝብ ውስጥ ሕይወት ባላቸው ፓርቲዎች የተመሠረቱ ስላልሆኑ በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ የሚያስችላቸው የሽግግር ወይም የአንድነት መንግሥት ምሥረታ ጥያቄ ለመንግሥት ከማቅረብ አልፈው ትግሉን የሚያጠናክር ተጨባጭ ተግባር ሲያከናውኑ አይታዩም፡፡ በዚህም ምክንያት በተወሰነ ደረጃ በራሳቸው ተጠናክረው ሊወጡ የሚችሉ አንፃራዊ ጥንካሬ ያላቸው ፓርቲዎች ሳይቀሩ ኀብረቱን ለግል ዝናቸውና የሥልጣን ጥማቸው መንጠላጠያነት በሚጠቀሙበት ሰዎች ታግተው አብረው ለመዳከም የሚገደዱበት ሁኔታ ደጋግሞ ታይቷል፡፡

ስለዚህ ወደፊት እንዲፈጠሩ የምንፈልጋቸው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ኀብረቶች እንደ አለፉት ኀብረቶች በተመሠረቱ ማግስት በነው እንዳይጠፉ ከተፈለገ ተቃዋሚነትን ብቸኛ መስፈርትና መመዘኛ አድርገው ሊመሠረቱ አይገባም፡፡ በመካከላቸው ያለውን አንድነትና ልዩነት ከሕዝብ ግፊት በፀዳ ስሜት በአግባቡ በመገምገም በአደረጃጀት ቅርፅና በትግል ስልት ከሚመስሏቸውና በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች ከሚቀራረቧቸው ፓርቲዎች ጋር ብቻ ኀብረት ሊፈጥሩ ይገባል፡፡ በእነዚህ መሠረታዊ መስፈርቶች መቀራረብና መመሳሰል በማይታይባቸው ፓርቲዎች ኀብረት ለመፍጠር ብቻ ተብለው የሚመሠረቱ ኀብረቶች ተጠናክረው በመውጣት ለውጥ ለማምጣት የማይችሉ ከመሆናቸው በላይ በሆነ አጋጣሚ የመንግሥት ሥልጣንን የሚጨብጡበት ዕድል እንኳን ቢያገኙ መልሰው እርስ በርሳቸው ወደ አዲስ የትግል ግብግብ ውስጥ ከመግባት አልፈው አገሪቱን በብቃትና በሰላም አረጋግተው ሊመሩ የሚችሉበት ዕድል ይኖራል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ምንም ዓይነት ጥቅም በማይገኝበትና መሥዋዕትነት በሚያስከፍል የተቃዋሚነት ሚና ላይ እያሉ ልዩነቶቻቸውን ማቻቻል የተሳናቸው የዚህ ዓይነቶቹ የይስሙላ ኀብረቶች በርካታ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ጥቅሞችን ሊያስገኝ

በሚችል የመንግሥት ሥልጣን ላይ ሲቀመጡ ተቻችለው ይሠራሉ ብሎ ማሰብ የማይቻል ነው፡፡ ዋናው የጋራ አጀንዳቸው ኢህአዴግን ከሥልጣን ማስወገድ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ኢህአዴግ ከሥልጣን ተወግዶ የጋራ አጀንዳ መሆኑ ሲቀር በመካከላቸው ያለው ልዩነት ፈጦ መውጣቱና ርስ በርስ ለመበላላት ምክንያት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ተቃዋሚዎች እንኳንስ የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ገብቶና ገና ሥልጣን በእጃችን ሊገባ ይችላል ብለው ገምተው በነበረበት በምርጫ 97 አንዳቸው ሌላቸውን አስቀድመው ለመዋጥ ያደረጉት ጥረት በቅንጅት ውስጥ በገሃድ ታይቷል፡፡

በትጥቅ ትግልና በተቃራኒው በሰላማዊ ትግል የሚያምኑ ፓርቲዎች ትግላቸው በምን ሕጋዊ መሠረት ተቀናጅቶ ሊካሄድ ይችላል? የሚለው ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ትግላቸው ለድል የሚበቁበት አጋጣሚ ቢፈጠር እንኳን ስለ ዴሞክራሲ፣ ስለ መድብለ-ፓርቲና ስለ ምርጫ ሥርዓት መኖር ተመሳሳይ አቋም ሊያራምዱ ይችላሉ ብሎ መጠበቅ ከራሳችን አገር ታሪክና ልምድ ጋር የማይጣጣም ስህተት ነው፡፡ ለነፃነት እንታገላለን የሚሉትና ለአገር አንድነት እንታገላለን የሚሉት ፓርቲዎችም ከድል በኋላ በጋራ የሚመሩት መንግሥት ይቅርና በጋራ የሚኖሩበት አገር ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የብሔር አደረጃጀትን የሚከተሉና ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀትን የሚከተሉ ፓርቲዎችም ከድል በኋላ የአገሪቱን ሕገ-መንግሥትና ፌደራላዊ አደረጃጀት በተመለከተ በአንድ ጥምር መንግሥት ሥር አብሮ የሚያሠራ አቋም ይኖራቸዋል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው፡፡

አንድ ኅብረ ብሔራዊ አደረጃጀት ያለው ድርጅት በአገር ደረጃ የበላይነቱን ለማረጋገጥ የሚሠራ የመሆኑን ያህል በብሔር ደረጃ የተደራጀው ድርጅትም በብሔሩ ውስጥ የበላይነቱን ለማረጋገጥ ስለሚሰራ ሁለቱ አደረጃጀቶች በአንድ መንግሥት ውስጥ አብሮ ለመሥራት የማያስችል ተፈጥሯዊ ተቃርኖ አላቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት የነበረውን ኢህዴንን ወደ ዐማራ ድርጅትነት ማለትም ብአዴንነት ለመቀየር የተገደደው፡፡ ምክንያቱም ኢህዴን ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀቱን ይዞ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ በሂደት ራሱ የኢህአዴግን ሚና የመተካትና ህወሃትን ለመሰሉት ድርጅቶች የህልውና አደጋ እየሆነ መምጣቱ አይቀሬ ነበር፡፡

ስለዚህ የሥርዓቱ ተቃዋሚ መሆንን ብቸኛ የመተባበሪያ አጀንዳ አድርጎ ኅብረት ለመፍጠር መሞከር መቆም አለበት፡፡ ይህ ሲባል ግን እነዚህን ዓይነት ልዩነቶች ያሉአቸው ፓርቲዎች ጭራሽ በጋራ ሊሠሩት የሚገባ የጋራ አገራዊ አጀንዳ ሊኖራቸው አይችልም ማለት አይደለም፡፡ ማለት የተፈለገው በአንድ የፓርቲ መዋቅር ውስጥ ሆነው የጋራ መንግሥት

ሊመሰርቱ አይችሉም ወይም አይገባቸውም ነው እንጂ የቱንም ያህል ልዩነት በውስጣቸው ቢኖር በኢትዮጵያ አንድነት ላይ መሠረታዊ ልዩነት እስከሌላቸው ድረስ ምንጊዜም ቢሆን የጋራ አገራዊ አጀንዳ በመካከላቸው የግድ ይኖራል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ፓርቲዎች በማንኛውም የሠለጠነ አገር እንደሚታየው የልዩነት አጀንዳቸው አሸናፊ እንዲሆን በምርጫ እየተፋለሙ በጋራ አገራዊ አጀንዳዎቻቸው ዙሪያ ግን ተባብረው ሊሠሩ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ግንኙነትም ተቃዋሚዎች ርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት ብቻ የሚሠራ ሳይሆን ከገዥው ፓርቲም ጋር ባላቸው ግንኙነት በተመሳሳይ ሁኔታ ሊሠራ የሚገባው ነው፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ ስለሆነ እንደ ዘላለማዊ ጠላት የሚታይበት፣ ከኢህአዴግ ተመሳሳይ አቋምና ባህሪ ያለው ሌላ ፓርቲ ደግሞ ተቃዋሚ ስለሆነ ብቻ እንደ ቋሚ ወዳጅ የሚታይበት አስተሳሰብ ግን "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ" ከሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ ባለፈ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ አመለካከት ነው ሊባል አይችልም፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአንድ በኩል ለኢትዮጵያ አንድነት ከእኛ በላይ ጠበቃ የለም እያሉ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግን ቀደም ሲል የሻዕቢያ ቡችላ አድርገው ይከሱት እንደነበር ረስተውት ዛሬ እነሱ በተራቸው ኢህአዴግን ከሻዕቢያ፣ ከኦነግና ከኦብነግ ጋር ሳይቀር ተባብረው ለማስወገድ ሲሞክሩ የምናያቸው በሌላ ምክንያት ሳይሆን ፖለቲካቸው "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ" ከሚለው የተሳሳተ አስተሳሰብ ገና ያልተላቀቀ በመሆኑ ነው፡፡ ምክኒያቱ ይህ ባይሆን ኖሮ በምንም መመዘኛ እነ ሻዕቢያና ኦብነግ ለኢትዮጵያ የሚጠቅሙ ኃይሎች ይሆናሉ ተብሎ ከኢህአዴግ በላይ ለወዳጅነትና ለትብብር ባልተፈለጉ ነበር፡፡

ፓርቲዎች በተናጠል የሚያደርጉት የትግል ጉዞ የትም እንደማያደርሳቸው ካወቁ ቀዳሚው መፍትሄ በአደረጃጀትና በዓላማ ከማይመሳሰሉት ፓርቲ ጋር ዝም ብሎ ኅብረት መፍጠር ሳይሆን በቅድሚያ በአንድ ኅብረትም ሆነ በአንድ መንግሥት ውስጥ ከማን ጋር ተጣጥመው ሊሠሩ እንደሚችሉ በጥንቃቄ ማጥናትና መምረጥ ይገባቸዋል፡፡ በፓርቲዎች መካከል መሠረታዊ ልዩነቶች እያሉ ከልዩነቶቹ በላይ በአንድ ኅብረት ውስጥ አብሮ የመሥራቱ ጉዳይ ለራስም ሆነ ለአገር ጥቅም የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም መፍትሄው በቅድሚያ የአደረጃጀትና የዓላማ ማሻሻያ በማድረግ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል ቅርፅና ይዘት መፍጠር ነው እንጂ ልዩነታችንን ከድል በኋላ እንመለስበታለን ብሎ የዘፈቀደ ኅብረት መፍጠር የትም አያደርስም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመካከላቸው የአደረጃጀትና የዓላማ መቀራረብ መፍጠር እስካልቻሉ ድረስ ግን ገዥውን ፓርቲ እንደሚታገሉት ሁሉ እርስ በርሳቸውም በዴሞክራሲያዊ አግባብ ታግለው አሸናፊ ሆነው መውጣትን አማራጭ አድርገው ማየትም ይገባቸዋል፡፡ መሠረታዊ ልዩነታቸውን

አለባብሰው በኅብረት በመሥራት የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ቢበቁ እንኳን መልሰው እርስ በርሳቸው ትግል መጀመራቸው ስለማይቀር ከወዲሁ ሕዝቡ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት ዐውቆ ከማን ጋር መቆም እንዳለበት ምርጫውን እንዲያስተካክል ዕድል ሊሰጡት ይገባል፡፡

ምክንያቱም ተቃዋሚዎች በጠራ የጋራ ራእይ መሠባሰብ ካልቻሉ፣ ወይም ከውስጣቸው አንዳቸው አሸናፊ ሆነው ካልወጡ በስተቀር የሚፈጥሩት ኅብረት ጥልቅ በሆነ ጥርጣሬና አለመተማመን ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን አንድ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ሲደረስ በውስጣቸው የማይቀር ቅራኔ ፈንድቶ እንደሚወጣ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ሕዝቡም ተቃዋሚ የሆነውን ፓርቲ ሁሉ በጭፍን “ተባባሩ ወይም ተሰባበሩ” እያለ በስሜት የማያዛልቅ ኅብረት እንዲፈጥሩ ያልተገባ ግፊት ከማድረግ ይልቅ በአደረጃጀትና በዓላማ ጥቅሜን ያስከብሩልኛል የሚላቸውን ፓርቲዎች ለይቶ ማወቅና ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

በአሁኑ ወቅት የኅብረት ጥያቄ ከሚገባው በላይ ተለጥጦና ትርጉሙን ስቶ ጥያቄ ሊነሣበት የማይገባ መስሎ ቢታዩንም በማይግባቡ የፖለቲካ ኃይሎች በሕዝብ ግፊት የሚፈጠር ኅብረት ውጤት እንደማያመጣ ለማወቅ በእኛ አገር በተደጋጋሚ በተግባር የታዬ በመሆኑ ብዙ ምርምርና ፍልስፍና የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ በአካላዊ ብቃታቸውም ሆነ ስለ ኑሮ ባላቸው ትርጉም ተቀራራቢ አመለካከት የሌላቸው አንድ ወንድና ሴት ጋብቻ ለመፈጸም ሲባል ብቻ በግፊት እንዲጋቡ ቢደረግ ጋብቻቸው እንደማይሰምር ሁሉ ኅብረት መፍጠርን ብቻ ግብ አድርጐ መሠረታዊ ልዩነት ባላቸው ፓርቲዎች መካከል የሚፈጠር ኅብረትም ለውጤት ሊበቃ አይችልም፡፡ በመሠረቱም የኅብረት ጥያቄ መታየት ያለበት ትግሉን ለማጠናከር እንደሚጠቅም አንድ መሣሪያ ተደርጐ እንጂ - በራሱ መድረሻ ግብ ተደርጐ መታየት አይገባውም፡፡

የደካሞች መሸሸጊያና የብልጣብልጦች መንጠላጠያ ሆኖ ከሚያገለግል ኅብረት ይልቅ ራሳቸውን ለውጤት ለማብቃት ተግተው የሚሠሩ አንድና ሁለት የተናጠል ፓርቲዎች እንዲኖሩ መታገል የበለጠ የተሻለ ይሆናል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ድፍረቱ ካለን በዚህ ረገድ ከህወሃትም ብዙ ልንማር እንችላለን፡፡ ህወሃት የትጥቅ ትግል እንደ ጀመረ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚል ዕሳቤ ብቻ ከኢህአፓና ከኢዲዩ ጋር ግንባር ፈጥሮ ቢሆን ኖሮ ለዛሬው ውጤት ይበቃ ነበር ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ህወሃት ከኢህአፓና ከኢዲዩ ጋር አንድ የሚያደርገው ተፈጥሮ እንደሌለውና ከነሱ ጋር እየተሻኰተ ተጠናክሮ መውጣት እንደማይችል አስቀድሞ በማወቅ ከእነሱ ጋር መፋለምን እንጂ የማያዛልቅ ግንባር መፍጠርን ባለመምረጡ በወቅቱ በአካባቢው ብቸኛ ጠንካራ ኃይል ሆኖ ለመውጣትና በኋላም ለድል ለመብቃት እረድቶታል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ከድርጅታዊ ጥንካሬም አንጻር ኅብረቶች በራሳቸው መቆም ያቃታቸው ፓርቲዎች የድክመት መሸፈኛና የግለሰቦች የዕውቅና መንጠላጠያ መሆን የለባቸውም፡፡ ኅብረት የሚያስፈልገው ከየአባል ፓርቲዎቹ የሚገኘውን የሰው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ኃይል በማሰባሰብ የተሻለ ጥንካሬ ለመፍጠር ነው እንጂ ከግለሰብ የተሻለ ሚና የሌላቸውን በተግባር እንዳሉ የማይቆጠሩ ደካማ ፓርቲዎችን አሰባስቦ ይህንን ያህል ፓርቲዎች ኅብረት ፈጠሩ ለማለት ብቻ መሆን የለበትም፡፡ በተለያዩ ኅብረቶች በተግባር እንደታየው እስካሁን በአገራችን የነበሩት ኅብረቶች ሳምሶናይትና ማኅተም ከመያዝ ያለፈ እውነተኛ ድርጅታዊ አቅም ባላቸው ሰዎች የተፈጠሩ አልነበሩም፡፡

በአንድ ወቅት ገናና የነበረውንና አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በመባል ይታወቅ የነበረውን ኅብረት በምሳሌነት ብናይ ይህ ምክር ቤት በሠላሳ ስድስት ፓርቲዎች የተመሠረተ ሲሆን በተግባር ግን ሠላሳ ስድስት ድርጅቶች ይቅርና ሙሉ ጊዜአቸውን ለፖለቲካው ትግል የሰጡ ሠላሳ ስድስት ግለሰቦች በውስጡ አልነበሩትም፡፡ ምክር ቤቱ በውስጡ የነበሩት ግለሰቦችም በሂደት ተነው አልቀው ፕሮፌሰር በየነ ሌላ ተተኪ ኅብረት አግኝተው ስሙን መጥራት እስካቆሙበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ አማራጭ ኃይሎች የሚባለው ምክር ቤት የእሳቸው የግል የፖለቲካ መጠሪያና መታወቂያ ሆኖ ነበር፡፡ ሰሜን አሜሪካ በዐሥራ አራት ፓርቲዎች የተቋቋመው ኢዴኃህም በመጨረሻ የፕሮፌሰር በየነና የዶ/ር መረራ የስም መጠሪያ ሆኖ ከመቅረት የተሻለ ዕድል አልገጠመውም፡፡ ስለዚህ ፓርቲዎች ኅብረት ከመፍጠራቸው በፊት የኅብረቱ አባል የሚሆኑ ፓርቲዎች ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር የሚጨበጥና የሚዳሰስ አቅም ያላቸውና አባል የሚሆኑበትን ኅብረት በትክክል ሊያጠናክሩ የሚችሉ ፓርቲዎች መሆናቸው ግልጽ በሆነ መመዘኛ መረጋገጥ አለበት፡፡ የዚህ ዓይነት መመዘኛ ጥቅም ላይ ባልዋለበት ሁኔታ ግን እስካሁን በተግባር እንደታየው የግለሰቦች እንጂ የጠንካራ ፓርቲዎች ኅብረት መፍጠር የማይቻል ይሆናል፡፡

ሁለተኛው ከዚህ በላይ ካዩነው ምክንያት የሚመነጨው ሌላው በኅብረት ዙሪያ የሚታየው ችግር ኅብረቶች በራሳቸው አመራርም ሆነ ደጋፊያቸው በሆነው ሕዝብ ዓይን የአባል ፓርቲዎችን ሚና የሚተኩ ተደርገው መታየታቸው ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ኅብረቶች ሲፈጠሩ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በኅብረቱ አመራርነት የሚሰበሰቡት ሰዎች በራሳቸው መቆም ያልቻሉና ኅብረቱን ለግል ዕውቅና መንጠላጠያነት መጠቀም የሚፈልጉ በመሆናቸው ምክንያት አንድ ጊዜ ኅብረቱ ተፈጠረ ከተባለ በኋላ የኅብረቱ አባል ድርጅቶች በተናጠል እንዲንቀሳቀሱም ሆነ ድርጅታዊ ነፃነታቸው እንዲከበር ሲፈልጉ አይታዩም፡፡ ኅብረት የሚፈጠረው ፓርቲዎች

ህልውናቸውን ጠብቀው የተወሰነ መለስተኛ ፕሮግራምን በጋራ ለማስፈጸም ቢሆንም የኅብረቱ አመራሮች እንወክላቸዋለን የሚሏቸውን ፓርቲዎች በመርሳት ገንዘብ የማሰባሰብ፣ አባላት የመመልመልም ሆነ የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ሙሉ በሙሉ በኅብረቱ ስም በመሥራት እንደ አንድ ወጥ ፓርቲ መታየትን ይመርጣሉ፡፡

ይህ ዓይነቱ ዝንባሌ ኅብረቱን ከሕዝቡ የትግል እንቅስቃሴ ተነጥሎ በአየር ላይ እንዲንጠለጠል የሚያደርገው ሲሆን፣ በኅብረቱ ውስጥ ባሉ የተሻለ ጥንካሬ ባላቸውና ከግለሰብ የተለየ ሚና በሌላቸው ፓርቲዎች መካከልም ግጭት ይፈጥራል፡፡ ለደካማዎቹ ፓርቲዎች የጠንካራዎቹ ፓርቲዎች በተናጠል መጠናከር የህልውና አደጋ ስለሚሆንባቸውና በተመሳሳይ ሁኔታም ለጠንካራዎቹ ፓርቲዎችም በኅብረቱ ስም ድርጅታዊ ነፃነታቸው ጥያቄ ውስጥ መውደቁ የህልውና ጉዳይ ስለሚሆንባቸው በመካከላቸው የሚፈጠረው ልዩነት ተፈጥሯዊና የማይታረቅ እየሆነ መምጣቱ የማይቀር ይሆናል፡፡ የኅብረቱ ደጋፊ የሆነው ኅብረተሰብም ከመጀመሪያው በኅብረቱ አባል ድርጅቶች መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ ስለማያውቀው አንድ ጊዜ ኅብረት ተፈጠረ ከተባለ በኋላ የኅብረቱ መሠረት የሆኑትን የተናጠል ፓርቲዎች እየረዳ ማጠናከር ይቅርና ስማቸውንም መስማት እየጠላ ይመጣል፡፡ ይህ ዓይነቱ ስሜታዊ የሕዝብ አመለካከት ለግል ዕውቅናቸው በኅብረቱ አመራርነት ከተንጠላጠሉ ሰዎች ፍላጐት ጋር በመመጋገብ በሚያስከትለው ውጤትም በኅብረቱ ውስጥ ያሉ ጠንካራ ፓርቲዎችም አብረው የመዳከም አደጋ ያጋጥማቸዋል፡፡ ዞሮ ዞሮ በኅብረቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ፓርቲዎች ሲዳከሙ ኅብረቱም በተመሳሳይ ሁኔታ መዳከሙ ስለማይቀር የመጨረሻ ውጤቱ መበታተን ይሆናል፡፡ እስካሁን በአገራችን ተፈጥረው የነበሩት ኅብረቶች የታሰበላቸውን ግብ ሳይመቱ ሲፈርሱ የታዩት በሌላ ምክንያት ሳይሆን በአንድ በኩል፣ አንዱ ሌላውን ውጦና በሌላው ህልውና ላይ ተንጠላጥሎ ኅብረቱን የራሱ የግል መጠቀሚያ ሊያደርገው ሲሞክር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሌላኛው የፓርቲ ህልውናውን አስጠብቆ ለመቀጠል በሚያደርገው መፍጨርጨር በሚፈጠር ግብግብ ነው፡፡

የሚገርመው ሁሉም ኅብረቶች ሲመሠረቱ በኅብረቱና በአባል ፓርቲዎቹ መካከል የሚኖረውን የሥራ ክፍፍል በአግባቡ ለይቶ የሚያስቀምጥ መተዳዳሪያ ደንብ አዘጋጅተውና ተፈራርመው ቢሆንም አንድ ጊዜ ኅብረቱ ተፈጠረ ከተባለ በኋላ ግን የሚመራቸው የሕዝቡ ግፊትና የመሪዎች የግል ፍላጐት ነው እንጂ መተዳደሪያ ደንቡ ሲሆን አይታይም፡፡ የኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ በኅብረቱ አመራሮች በመጣሱ ምክንያት አንድ የኅብረቱ አባል የሆነ ፓርቲ መብቱን ለማስከበር ሲል በአግባቡ ከኅብረቱ ቢነጠል ብዙውን ጊዜ “አፍራሽ” ተብሎ የሚኮነነው

መብቱን ለማስከበር ጥረት ያደረገው ፓርቲ ነው እንጂ ደንቡን የጣሱት የኅብረቱ አመራሮች አይደሉም። ይህ እውነት መሆኑ እስካሁን ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በመሯቸው ኅብረቶችም ሆነ በቅንጅት ውስጥ ምርጫውን ተከትሎ በተፈጠረው ልዩነት በግልጽ ታይቷል። ኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ ሲነጠልም ሆነ ዐሥራ አራት ድርጅቶች የመሠረቱትን ኅብረት እነ ፕሮፌሰር በየነ ሁለት ድርጅቶችን ብቻ ይዘው ኅብረቱን እንወክላለን ብለው ሲቀጥሉ፣ አብዛኛዎቹ የግል መገናኛ ብዙኃንም ሆኑ የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው ሕዝብ በስሜት አንዱን አካል "አፈንጋጭ" ብሎ ከማውገዝ በስተቀር የፓርቲዎቹ የስምምነት ሰነድ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ሲሞክሩ አልታየም።

በዚህ ረገድም ተቃዋሚዎች ከገዥው ፓርቲ ብዙ መማር እንችላለን። ኢህአዴግ የአራት ድርጅቶች ግንባር ሲሆን ይህ ግንባር ለአለፉት ሃያ ዓመታት ባሳለፈው የትግል ሂደት አባል ድርጅቶቹን የሚተካ ሚና ኖሮት አያውቅም። የግንባሩ ህልውና ሁልጊዜም በአባል ድርጅቶቹ ህልውና ላይ የተመሠረተ ሲሆን ሕዝቡን በማደራጀትም ሆነ በማስተዳደር ዋናውን ሚና የሚጫወቱት አባል ድርጅቶቹ ናቸው እንጂ ግንባሩ አይደለም። ግንባሩና አባል ድርጅቶቹ ያላቸው ሚናም በግልጽ የሚታወቅና የሚጠበቅ ስለሆነ አባላት የሚመለምሉት፣ የምርጫ ዕጩ የሚያቀርቡትና የገንዘብ መዋጮ የሚሰበስቡት አባል ድርጅቶቹ እንጂ ግንባሩ አይደለም። የኢህአዴግ አመራሮች፣ አባላትም ሆኑ ደጋፊዎች ይህንን የግንባሩንና የአባል ድርጅቶቹን ግንኙነት በውል የተረዱ ስለሆኑም ብዙ ጊዜያቸውንና ትኩረታቸውን የሚያጠፉት የዬራሳቸውን ድርጅት በማጠናከር ነው እንጂ በአባል ድርጅቶች ህልውና ላይ የተመሠረተውን ግንባር በማጠናከር አይደለም። ተቃዋሚዎች አንድ ኅብረት ፈጠሩ ሲባል ግን ኅብረቱን የፈጠሩት አባል ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ይረሱና የኅብረቱ መሪዎች፣ አባላትም ሆነ ደጋፊዎች ትኩረት በኅብረቱ ዙሪያ ብቻ ይሆናል። ይህም ለኅብረቱ መሠረት የሆኑት አባል ድርጅቶች እንዲዳከም ስለሚያደርግ የመጨረሻ ውጤቱም የኅብረቱ መዳከምና መፍረስ ይሆናል። ስለዚህ የኅብረቶች ህልውና በዋናነት የአባል ድርጅቶችን ህልውና መሠረት ካላደረገ የመጨረሻ ውጤቱ ትርምስና መፈራረስ ከመሆን አይዘልም።

ከዚሁ ከድርጅቶች ነፃነት ጋር በተያያዘም በውስጣቸው ሰፋ ያሉ ልዩነቶች ያሉባቸው ኅብረቶች በጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎች በመግባባት ውሳኔ (consensus) ላይ የተመሠረተ ቢሆን የተሻለ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ውሳኔዎች እንዲወሰኑ የሚደረጉት በአብላጫ ድምፅ ስለሆነ በኅብረቶች ውስጥ አንድ የልዩነት ሐሳብ በተፈጠረ ቁጥር የመለያየት አደጋ አብሮ የሚመጣበት አጋጣሚ የተለመደ ነው። ፓርቲዎች ነፃነታቸውንና ህልውናቸውን

የሚጋፋ ውሳኔ ጭምር በአብላጫ ድምፅ ስም እንዲጫንባቸው ስለሚደረግ አብሮ ከመሥራት ይልቅ መነጠልን ለመምረጥ የሚገደዱበት አጋጣሚ ቀላል አይደለም፡፡ ስለዚህ ወደፊት የሚፈጠሩ ኅብረቶች የተሻለ ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ የአባል ፓርቲዎችን መብትና ነፃነት አክብረው መሥራት ይገባቸዋል፡፡ በፓርቲዎቹ መካከል ያለው ግንኙነትም መወሰንና መዳኘት ያለበት በሕዝብ ግፊትና በመሪዎቹ ፍላጐት ሳይሆን በጋራ ለመሥራት በተስማሙበት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆን ይገባዋል፡፡ ፓርቲዎች የተስማሙበትን መተዳደሪያ ደንብ በስሜትና በሰሞነኛ የሕዝብ ግፊት ከመተካት አባዜ ሊላቀቁ ካልቻሉ ነገ መንግሥት የመሆን ዕድል ሲያገኙም ለሕግና ለሥርዓት ተገዥ እንደሚሆኑ ርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡

ሦስተኛውና እነዚህን ከላይ ለማብራራት የተሞከሩትን ድክመቶች ለመፍታት ያላስቻለውና በኅብረት ዙሪያ የሚታየው ሌላው ችግር፣ ሁልጊዜ አዳዲስ ኅብረቶች የሚፈጠሩት የቀድሞዎቹ ኅብረቶች በምን ምክንያትና እንዴት እንደፈረሱ ግምገማ ሳይደረግ በመሆኑ ነው፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ኢዲኅቅን፣ ደኢህዴህን፣ አማራጭ ኃይሎችን፣ ጋፖመን፣ ኢተፖድህን፣ ትዴኢን፣ ኢዴኅህን፣ ትነዴንና፣ ቅንጅትን የመሳሰሉ ከዘጠኝ የማያንሱ ኅብረቶች ተቋቁመው የተስማሙበት ፊርማ ሳይደርቅ ውጤታማ ሳይሆኑ የቀሩ ቢሆንም በፈረሰው ኅብረት ምትክ እንደገና አዲስ ኅብረት ለማቋቋም ከመቻኮል በስተቀር የተቃዋሚው ጐራ አንድም ቀን ስለፈረሱት ኅብረቶች ድክመትና ጥንካሬ ቁጭ ብሎ ግምገማ ለማድረግ ሞክሮ አያውቅም፡፡ የሚገርመው አዲስ ኅብረት በተቋቋመ ቁጥር ሕዝቡ ትግሉ የተሻለ ደረጃ ሊደርስ ነው ብሎ በማሰብ ደስታውን በስሜት ተውጦ ሲገልፅ የሚደመጥ ቢሆንም እንደዚያ የሞቀ ስሜቱን የገለፀባቸው ኅብረቶች ፈረሱ ሲባል ግን እንደገና አዲስ ኅብረት እንዲፈጠር ከመመኘትና ግፊት ከማድረግ በስተቀር ላለፈው ኅብረት መፍረስ ምክንያቱና ተጠያቂው ማነው? ብሎ ለመጠየቅ ሞክሮ አያውቅም፡፡

በዚህ ምክንያት እንደ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ዓይነቶቹ የፖለቲካ መሪዎች ግማሽ ደርዘን የሚሆኑ ኅብረቶች መሥርተው በመምራት ውጤታማ ሳይሆኑ የቀሩ ቢሆንም አንድም ቀን ተሳስተው ሲመሩት የነበረው ኅብረት ለምንና እንዴት እንደፈረሰ ለማንኛውም አካል ሪፖርት ሲያቀርቡ ታይተው አያውቅም፡፡ ነገር ግን እንደገና አዲስ ኅብረት ፈጠርን ብለው ወደ ፖለቲካ መድረኩ ብቅ ሲሉ ሕዝቡ የትናንትናውን ኅብረት የት ጣላችሁት? ብሎ ለመጠየቅ ሳይሞክር፣ እንደገና በጋለ ጭብጨባ ይቀበላቸዋል፡፡ እነሱም የዚህ ዓይነቱ ስልት የሕዝቡን ድጋፍ በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል ሆኖ ስላገኙት ሕዝቡ ውስጥ ገብቶ የሚጨበጥ የማደራጀትና የማንቃት ሥራ ሠርቶ ትግሉን በዘላቂነት ለማጠናከር ከመሞከር ይልቅ አዲስ ኅብረት ፈጥሮ ብቅ-ማለትን

በሕዝቡና በውጭ ዲፕሎማቶች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ቀላልና አቋራጭ ስልት አድርገው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

እነዚህ በራሳቸው ፓርቲ ብቃት ተጠናክረው መውጣት የማይችሉ ሰዎች በአገሪቱ ብሔራዊ ፖለቲካ ዕውቅናና ተሳትፎ ሊኖራቸው የሚችለው በኅብረት አመራርነት መንጠላጠያ ሲያገኙ ብቻ እንደሆነ ስለገባቸው ኅብረት እያቋቋሙ መሪ መሆንን የግል ርስትና ቋሚ ሥራ አድርገው ይዘውታል፡፡ የእነሱ ይሉኝታ ማጣት በራሱ አስገራሚ ቢሆንም የበለጠ የሚያስገርመው ግን ይህንን ሁሉ ኅብረት መሥርተው ሲያፈርሱ አንድ ቦታ ላይ "አይበቃችሁም?" ብሎ የሚጠይቃቸው ሰው አለመኖሩ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የአገራችን ጋዜጠኞች አዲስ ኅብረት ተፈጠረ ሲባል ዜና ከመጻፍና ለምን በኅብረት አትሠሩም? እያሉ ኅብረቱ ውስጥ ያልተካተቱን ፓርቲዎች ከመውቀስ አልፈው የቀድሞዎቹ ኅብረቶች የትኛው ቤርሙዳ ትሪያንግል ውስጥ እየገቡ እንደሚሰምሩ ለመጠዬቅ ሲሞክሩ አይታዩም፡፡ ስለዚህ ወደፊት የተሻለ ውጤታማ የሚሆን ኅብረት እንዲፈጠር ከተፈለገ በቅድሚያ ያለፉት ኅብረቶች ለምንና እንዴት እንደፈረሱ በቂ ግምገማ መደረግ አለበት፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በውጭ አገር እንደ ኢህአፓ፣ በአገር ውስጥ ደግሞ እንደ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ዓይነቶቹ የፖለቲካ ኃይሎች ከእንግዲህ በሚፈጠሩ ኅብረቶች የሚኖራቸው ሚና በጥንቃቄ መታየት ካልቻለ ለውጤት የሚያበቃ ኅብረት ይፈጠራል ብሎ መጠበቅ ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ኅብረቶች ለምንና እንዴት እንደፈረሱ በአግባቡ ተገምግሞ ለኅብረቶቹ መዳከምም ሆነ መፍረስ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸው ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች በአግባቡ እስካልታወቁ ድረስ እስካሁን ኅብረትን በማዳከምና በማፍረስ የጐላ ሚና የነበራቸው ሰዎችና ድርጅቶች ተመሳሳይ ችግር እየፈጠሩ መቀጠላቸው የማይቀር ይሆናል፡፡ እስካሁን በነበረው የኅብረት ጥያቄ ሂደት የሚያስቆጨው ነገር የሚፈለገው ኅብረት መፈጠር አለመቻሉ ብቻ አይደለም፡፡ ኅብረቱ ሳይፈጠር ቀርቶ ሌላ ጉዳት የማያስከትል ቢሆን ኖሮ እምብዛም ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን ትልቁ ችግር የኅብረት ጥያቄ በራሱ ፓርቲዎች በተናጠል ተጠናክረው እንዳይወጡ ቀያጅ የሆነ እንቅፋት መሆኑ ነው፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ተቃዋሚዎች ካልተባበሩ በስተቀር ለውጤት አይበቁም የሚል የተሳሳተ አመለካከት አንድ ጊዜ የሕዝቡ አእምሮ ውስጥ ስለተተከለ ፓርቲዎች ይህንን አስተሳሰብ ሰብረው በተናጠል ተጠናክረው መውጣት አልቻሉም፡፡ ከዚህ የሕዝብ አመለካከት በተጨማሪ በራሳቸው ተጠናክረው መቆም የማይችሉት ፓርቲዎችና ግለሰቦች በራሱ ተጠናክሮ ለመውጣት የሚጥርን ፓርቲ ጠልፈው ለመጣል የሚጠቀሙበት ስልት በዚሁ መከረኛ የኅብረት

ጥያቄ አማካይነት ሆኗል፡፡ እነዚህ ኃይሎች በአገሪቱ አንድ ፓርቲ እንደ ምንም በራሱ ተጠናክሮ በመውጣት የሕዝቡን ድጋፍ ማግኘት ሲጀምር ቶሎ ብለው የኅብረት አጀንዳ ይዘው በመቅረብና የሕዝቡን ግፊት በመጠቀም መጠናከር የጀመረውን ፓርቲ በውስጣቸው አስገብተው ያፍኑታል፡፡ ያ - ፓርቲ ኅብረቱ ሊያስከትልበት የሚችለውን ጉዳት ተገንዝቦ ብቻውን ለመጓዝ ከሞከረም "አፈንጋጭ" "ፀረ-ኅብረት" "አፍራሽ" የሚል ታርጋ ይለጠፍበትና ሕዝቡ የዚያን ፓርቲ ተልዕኮ ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገባው የሚያደርግ ቅስቀሳ ይካሄድበታል፡፡ የፖለቲካ ጨዋታው ያልገባው ኅብረተሰብም "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በሚለው መፈክሩ መሠረት በበቂ ምክንያት መተባበር ያልፈለገውን ፓርቲ እንዲሰባበር ይፈርድበታል፡፡ ስለዚህ የኅብረት ጥያቄ በቁጥር አንድ ለትግሉ መጠናከር ጠቃሚ ጉዳይ ተደርጐ የሚታመን ቢሆንም በተግባር ግን ሚናው አንድም ፓርቲ በአገራችን ተጠናክሮ እንዳይወጣ ማድረግ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለዚህም ነው በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ከአሉባልታ ቀጥሎ ለትግሉ መዳከም የኅብረት ጥያቄ ዋና ተጠያቂ ነው ለማለት የተሞከረው፡፡

አራተኛው ለተቃዋሚዎች ኅብረት መዳከም ሊጠቀስ የሚችለው ምክንያት ፓርቲዎች በኅብረት ውስጥ የበለጠ ወሳኝ ለመሆን ሲሉ ተደራራቢ ውክልና እንዲኖራቸው ማድረግ የሚሞክሩ መሆኑ ነው፡፡ በአንድ ኅብረት ውስጥ የሚኖሩ ፓርቲዎች እኩል ውክልና ሊኖራቸው የሚገባ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ በተለዩ ዘዴዎች ተደራራቢ ውክልና እንዲያገኙ የሚፈልጉ ፓርቲዎች ስላሉ እንዲህ ዓይነቱ ስግብግብነት ለኅብረት መዳከም እንቅፋት የሚሆንበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ችግር ከፕሮፌሰር በየነና እርሳቸው አሉኝ ከሚሏቸው ፓርቲዎች የተሻለ ማሳያ የሚሆን ምሳሌ አይኖርም፡፡ የፕሮፌሰር በየነ እናት ፓርቲ የሐድያ ሕዝቦች ዴሞክራሲዊ ድርጅት (ሐብዴድ) ሲሆን ይህ ድርጅታቸው የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ኅብረት አባል ነው፡፡ ዐሥራ ስድስት አባላት ያሉት የደቡብ ኅብረት በአንድ ወቅት ፕሮፌሰር በየነ በሚመሩት የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በአባል ድርጅቶቹ ልክ ዐሥራ ስድስት መቀመጫ ስለነበረው በወቅቱ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ሊቀመንበር የነበሩት ፕሮፌሰር በየነ የሐድያም የደቡብ ኅብረትም ሊቀመንበር ስለነበሩ በዚህ ተደራራቢ ውክልና ምክር ቤቱን በበላይነት ለመቆጣጠር ችለው ነበር፡፡ ፕሮፌሰር በየነ ዐሥራ ስድስት ውክልና ይዘው በኅብረት ውስጥ መግባታቸው ኋላ ላይ ተቀባይነት እያጣ ቢመጣም ከዚያ በኋላ በተቋቋሙ ኅብረቶች ውስጥም ቢያንስ በደቡብ ኅብረትና በአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ስም ሁለት ውክልና ማግኘትን ቋሚ መብት አድርገውት ኖረዋል፡፡

ፕሮፌሰር በየነ የሐድያ፣ የደቡብ ኅብረትና፣ የአማራጭ ኃይሎች ሊቀመንበር መሆናቸውን በቋሚነት ይዘው እንደገና በአሜሪካን የተቋቋመው ኅብረት ማለትም የኢዴኃህ ሊቀመንበር ለመሆን የበቁ ሲሆን፣ ይህም አልበቃቸው ብሎ በቅርቡ የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ የሚል አዲስ ድርጅት አቋቋምኩ በማለትና በቅርቡ እንደገና ሌላ የተቃዋሚዎች የምክክር መድረክ በማቋቋም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ብዙ ድርጅት በማቋቋምም ሆነ በአንድ ጊዜ የብዙ ድርጅት መሪ በመሆን ክብረ-ወሰኑን ይዘውታል፡፡ ምንአልባትም ፕሮፌሰር በየነ መቸ የአንድ ኅብረት ሊቀመንበር መሆን እንደሚጠቅም በደንብ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ የሚመጣው ምርጫ አካባቢ የመድረኩ ሊቀመንበር በመሆን በራሳቸው እጅ የተያዘውን የሊቀመንበርነት ሪከርዳቸውን ሊያሻሽሉት ይችላሉ፡፡ አንድ ሰው ሁልጊዜ በየጊዜው የሚቋቋሙ ኅብረቶች ሊቀመንበር እየሆነ ውጤት ሳያመጣ ሲቀር አንድ ቦታ ላይ “ምን እየተሠራ ነው?” ብሎ ኅብረተሰቡ መጠዬቅ ካልቻለ ግለሰቦች በኅብረት ጥያቄ ስም እየቀለዱ መቀጠላቸው አይቀርም፡፡ በተለይም እስካሁን ድረስ ከስድስት ያላነሱ የተለያዩ ኅብረቶችን መርተው አንዱንም ውጤታማ ማድረግ ሳይችሉ የቀሩት ፕሮፌሰር በየነ እንደ አንድ አሳሳቢ ችግር ታይተው ጥንቃቄ ካልተደረገባቸው በኅብረት ጥያቄ ዙሪያ  እስካሁን የታዩት ችግሮች ዘላቂ ሆነው መቀጠላቸው የማይቀር ነው፡፡

በነገራችን ላይ ከተጨባጭ ድርጊታቸው በመነሣት የሚቀርብባቸውን ትችት ፕሮፌሰር በየነ አንድም ቀን ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነው አያውቁም፡፡ እንዲያውም ትችት የሚያቀርብባቸውን ማንኛውንም ሰው እንደ ግል ደመኛቸው በመቁጠር አቅማቸው በፈቀደ መጠን ሁሉ ለማጥቃት ወደ ኋላ የማይሉ ሰው ናቸው፡፡ በተለይም ትችት የሚያቀርብባቸው ሰው ከሰሜን አካባቢ የተወለደ ከሆነ ቶሎ ብለው ጉዳዩን ከዘርና ከጨቋኝ ተጨቋኝ ግንኙነት ጋር ሊያይዙት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ የፕሮፌሰር በየነ የቅርብ ሰው የሆኑትና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ፕሮፌሰሩ በሚመሯቸው ድርጅቶች ውስጥ በከፍተኛ አመራርነት ሲሠሩ የነበሩት አቶ ኤርጫፎ ኤርዲሎ ነሐሴ 27 ቀን 2001 ዓ.ም ለንትመት በበቃው ሠንደቅ ጋዜጣ ላይ በሰጡት ቃለ-መጠይቅ ላይ ፕሮፌሰር በየነን በሚከተለው መልኩ ገልፀዋቸዋል፡፡

*“.... ከፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ጋር በሠራንባቸው ዓመታት ብዙ ችግሮችን አብረን አሳልፈናል፡፡ ነገር ግን እርሳቸው አመራር ቦታ ሁልጊዜ መቀመጥ ይፈልጋሉ፡፡... ፕሮፌሰር በየነ ከጐናቸው አንድ ሰው ተነስቶ አመራር እንዲሆን አይፈልጉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማይፈልጓቸው ብሔረሰቦች ጭምር ወደ ሥልጣን እንዲመጡ አይፈልጉም፡፡ ‘መጡብን’ የሚል ጭንቀት አለባቸው፡፡*

*አሁንም ፕሮፌሰር በየነ መድረኩ ውስጥ ቦታ የማያገኙ ከሆነ ቀድመው ከሚወጡ ሰዎች አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡”*

ፕሮፌሰር በየነ እንዲህ ዓይነቱን የፖለቲካ ጨዋታ ሥራዬ ብለው ስለያዙት በአሁኑ ወቅት የሐድያ ድርጅትን በሊቀመንበርነት፣ የደቡብ ኀብረትን በበላይ ጠባቂነት፣ ኢዲኃህን በሊቀመንበርነት፣ የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲን በሊቀመንበርነት በቅርቡ የተቋቋመውን መድረክ በሥራ አመራር አባልነት እየመሩ ይገኛሉ፡፡ ከሁሉም በላይ የሚገርመው ፕሮፌሰሩ የተለያዩ ኀብረቶችን ያለ ገደብ በመምራት ሻምፒየን መሆናቸው አልበቃቸው ብሎ በአንድ አገር ውስጥ ሁለት ወጥ ማንነት ያላቸው ፓርቲዎችን በአንድ ጊዜ በመመራት ምንአልባት በዓለም የመጀመሪያው ሰው ሆነዋል፡፡ ቢጠቅምም ባይጠቅምም የተለያዩ የፓርቲ ኀብረቶችን መምራት የሚቻል ቢሆንም አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የብሔር ድርጅት የሆነው የሐድያ ብሔር ድርጅትና ኀብረ-ብሔራዊ ነኝ የሚለው የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ መሪ መሆን የሚችልበት ሁኔታ በእኛ አገር ሕግ እንዴት እንደተቻለ አጠያያቂ ቢሆንም ከፖለቲካ አንጻር ግን ፈጽሞ ሊሆን የማይገባው ነው፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ አሠራር በፖለቲካ ያስኬዳል ከተባለ አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የኦፍዴንና የመኢአድ፣ ወይም የህወሃትና የመኢአድ አባል መሆን ይችላል እንደ ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ወደፊት የተሻለና ለውጤት የሚበቃ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ኀብረት መፍጠር ይቻል ዘንድ ከሕዝብ ጊዜያዊና ስሜታዊ ግፊት የጸዳ፣ በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረተ፣ መሠረቱን አገር ውስጥ ያደረገ፣ እውነተኛ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉና ተመጣጣኝ ድርጅታዊ ጥንካሬ ያላቸው ፓርቲዎችን ያቀፈ፣ የግልጽነትና የተጠያቂነትን መርህ የሚያከብር፣ ለግለሰቦች የዝናና የሥልጣን ምኞት መንጠላጠያ የማይሆን፣ ፓርቲዎች በአደረጃጀት ቅርፅና በአገራዊ አጀንዳዎች ያላቸውን መቀራረብ መሠረት ያደረገ ትርጉም ያለው ኀብረት እንዲመሠረት የሚያስችል ጥረት መደረግ አለበት፡፡ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ኀብረት በርግጠኛነት ለመፍጠር እንዲቻልም “ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ” የሚለውን ምክንያታዊ ያልሆነ ግፊት ለጊዜው ረገብ አድርጎ ለጠንካራ ኀብረት መፈጠር መሠረት የሚሆኑ ጠንካራ ፓርቲዎች በቅድሚያ እንዲኖሩ ተገቢ ዕድልና ፋታ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

### *2.2.2 በትግል ስልት ዙሪያ የሚነሡ አማራጮች*

በአገራችን የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ ከሆኑ ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የትግል ስልት ጥያቄ ነው፡፡ ደርግ ሥልጣን ላይ በወጣ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት በኀቡእም ሆነ

በይፋ በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ጥቂት ፓርቲዎች ስለነበሩ በትግል ስልት ዙሪያ የነበረው ክርክር በዚያው መጠን የጋለ ነበር፡፡ ቢያንስ ኢህአፓ፣ መኢሶንና ህወሃትን የመሰሉ ድርጅቶች በየፊናቸው አቋም ይዘው የሚከራከሩባቸው አማራጭ የትግል ስልቶች ነበሯቸው፡፡ ኢህአፓ በከተማ የአመፅ ትግል፣ መኢሶን ከደርግ ጋር አብሮ በመሥራት በሚደረግ ትግል፣ ህወሃት ደግሞ ከገጠር ወደ ከተማ በሚካሄድ የትጥቅ ትግል ላይ የየራሳቸው ስልት ነበራቸው፡፡ ቆዩት ብሎ ደርግ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ የሚከለክል አዋጅ በይፋ ካወጀና በተለይም ቀይ ሽብርን ማፋፋም ከጀመረ በኋላ ግን ብቸኛው አማራጭ በትጥቅና በአመፅ መታገል ስለነበር በትግል ስልት ዙሪያ በጎላ ሁኔታ የሚያከራክር አማራጭ ሐሳብ አልነበረም ማለት ይቻላል፡፡ ጉዳዩ የበለጠ አከራካሪ ሆኖ እንደገና የወጣው ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘና የመደራጀት መብት ሕገ-መንግሥታዊ ዕውቅና ካገኘ በኋላ ነው፡፡

ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በፖለቲካ መድረኩ አከራካሪ ሆነው የቆዩት የትግል ስልት አማራጮች በዋናነት የትጥቅ ትግልና የሰላማዊ ትግል የሚሉት ሲሆኑ፣ አልፎ አልፎ “ሁለገብ” የሚል የትግል ስልትም በአማራጭነት ሲቀርብ ይታያል፡፡ የእነዚህ አማራጭ ስልቶች ባህሪና ምንነት ብዙም በማያከራክር ሁኔታ ግልጽ የሚታወቅ ቢሆንም ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች በእነዚህ አማራጭ የትግል ስልቶች ዙሪያ ጠንካራና የጠራ አመለካከት አላቸው ማለት ግን ያስቸግራል፡፡ በተለይም አብዛኛዎቹ ሰላማዊ ትግል እናካሂዳለን የምንል ኃይሎች በሰላማዊ ትግሉ ላይ የያዝነው አቋም ከልባዊ እምነት የመነጨ አለመሆኑ ለትግሉ በሚፈለገው መጠን አለመጠናከር አንዱ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከአገራችን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር የትኛውን የትግል ስልት ማራመድ ተገቢና ትክክል እንደሚሆን ከማየታችን በፊት በቅድሚያ “ትግል” የሚለውን ቃል ለእኛ አገር ወቅታዊ ሁኔታ መጠቀም ተገቢ ስለመሆንና አለመሆኑ ለማየት ብንሞክር የተሻለ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች “ትግል” የሚለውን ቃል ከሰላማዊ ሁኔታ ጋር ተፃራሪ እንደሆነ አድርገው ስለሚያስቡ ጉዳዩን ግልጽ አድርጎ ማለፉ ተገቢ ይሆናል፡፡

የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ በሕግና በተግባር በተከበሩባቸውና ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር የተለመደ ባህል በሆነባቸው አገሮች የፖለቲካ ሥራ የሚከናወነው በውይይት፣ በድርድር፣ በክርክርና በምርጫ ፉክክር ብቻ በመሆኑ በዚህ ዓይነት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ባሉ አገሮች “ትግል” የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ሲውል አይታይም፡፡ ይዋልም ቢባል ተገቢ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በእነዚህ አገሮች የፖለቲካ ተዋናዮች ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ከሌሎች ተግባራት በተለየ ሁኔታ የሚደርስባቸው ተፅዕኖና የሚከፍሉት ከባድ ሊባል የሚችል

መሥዋዕትነት ስለማይኖር "ትግል" የሚለውን ኃይለ-ቃል መጠቀም ለእነሱ ሁኔታ የሚመጥን አይሆንም። ነገር ግን የፖለቲካ ምህዳሩ ሙሉ በሙሉ ባልሰፋበትና የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሕግም ሆነ በተግባር ባልተከበሩበት አገር፣ ወይም የፖለቲካ ተዋናዮች በፖለቲካው ሂደት የሚያደርጉት ተሳትፎ ከሕገ-ወጥ ተፅዕኖ አልፎ የአካልና የሕይወት መሥዋዕትነት ጭምር በሚጠይቅበት በእኛ ዓይነቱ አገር፣ "ትግል" የሚለውን ቃል መጠቀም ተገቢና ምክንያታዊ ነው ማለት ይቻላል።

በእንደኛ ዓይነቱ ታዳጊ አገር በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚካሄደውን ግብግብ ብቻ ሳይሆን መንግሥታት ወይም ገዥ ፓርቲዎች በሕዝብ ውስጥ ያለን ኋላቀር አስተሳሰብና ጎጂ ባህልን ለማስወገድ የሚያደርጉትን ጥረት ጭምር የ"ትግል" ሂደት አድርገው ያዩታል። ከዚያም አልፎ ሰዎች በግል ሕይወታቸው ከኑሮ ውጣ ውረድ ጋር የሚያደርጉትን ግብግብ "ትግል" ብለው ሲጠሩት መስማት የተለመደ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ትግል እየተካሄደ ነው ሲባል ጉዳዩን ከሰላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ የወጣ አድርጐ ማየት ተገቢ አይሆንም። በሰላማዊና ሕጋዊ ማዕቀፍ ውስጥም ቢሆን የእኛ አገር የፖለቲካ ሁኔታ ከሌሎች የአደጉ አገሮች በተለየ መውደቅ መነሣትን የሚጠይቅና ከባድ ዋጋ የሚያስከፍል የትግል ሂደት መሆኑን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል።

ከትግል ስልት አንጻር የወቅቱን የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከማየታችን በፊትም ከላይ የተጠቀሱት ሦስት አማራጭ የትግል ስልቶች በምን ዓይነት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመሥርተው ተግባር ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ በጥቅሉ ለማየት እንሞክራለን። ነገር ግን ከዚያ በፊት ሦስት ናቸው የምንላቸው የትግል ስልት አማራጮች ወደ ሁለት ዋና ዋና አማራጭነት ሊጠቃለሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማየት መሞከሩ በጉዳዩ ላይ የምናደርገውን ውይይት የበለጠ ግልጽና አጭር ሊያደርገው ይችላል።

ይኸውም "ሁለገብ" የሚባለው የትግል ስልት ባንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎች እንደተገቢና ትክክለኛ ስልት የሚታይ ቢሆንም በራሱ የተሟላ ትርጉም የማይሰጥ ከመሆኑም በላይ በይዘቱም ሆነ በውጤቱ ከአመፅና ከትጥቅ ትግል ተለይቶ የሚታይ ስልት አይደለም። ሁለገብ ትግልን እንደ አንድ አማራጭ የሚወስዱት ኃይሎች አቋማቸው መነሻ የሚያደርገው በየትኛውም አቅምና ሁኔታ በፈቀደው መንገድ ሁሉ ሥርዓቱን ለመጣል መታገል ያስፈልጋል ከሚል "የትም ፍጭው ዱውቄቱን አምጭው" ዓይነት አስተሳሰብ ነው። ማለትም በአንድ በኩልና በዋናነት የትጥቅ ትግል እያካሄድን፣ የሚቻል እስከሆነ ድረስም በሰላማዊ መድረክም ሥርዓቱን ማዋከብ የተፋጠነ ድል ለማግኘት ሊጠቅም ይችላል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ሰላማዊና የትጥቅ ትግልን እያጣቀሰ ለመጠቀም የሚሞክር ስልት ዞሮ ዞሮ በሕገ-ወጥነት ከመፈረጅ ስለማያድን ሊካሄድ የሚችለው የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ በሕግም በተግባርም በታገዱበት ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ በኩልም የትጥቅ ትግል ስልትን ለመጠቀም የፈለገ ማንኛውም ኃይል ከመጀመሪያውም ሰላማዊ ትግልን ማካሄድ የማይፈልገው “ስልቱን መጠቀም አያስፈልግም” ከሚል እምነት ሳይሆን ስልቱ ውጤት ሊያመጣ አይችልም ከሚል መነሻ ስለሆነ ዞሮ ዞሮ ሁለገብ የሚለው ስልት ከትጥቅ ትግል ስልት ተለይቶ ሊታይ አይችልም፡፡ እንዲያውም ይህ ሁለገብ የሚባለው ስልት በስልቱ አራማጆች ግልጽ ገደብ ተቀምጦለት ካልታዬ በስተቀር “የትም ፍጭው” ከሚለው ጭፍን አስተሳሰብ ጋር በተያያዘ የሽብርተኝነት ተግባር መፈጸምንም ሊያካትት ስለሚችል ከአመፅና ከትጥቅ ትግልም የከፋ አውዳሚ ገጽታ የሚይዝበት አጋጣሚና ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በሌላ በኩልም አንድ ኃይል ራሱን ለሁለት ከፍሎ በአንድ በኩል የትጥቅ ትግልን እያካሄደ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰላማዊና ሕጋዊ ትግልን በአንድ ላይ አጣምሮ ሊያካሂድ የሚችልበት ዕድልም ሊኖር ስለማይችል ሁለገብ የሚለው የትግል ስልት ከዓመፅና ከትጥቅ ትግል ተለይቶ በራሱ ብዙም የተለየ ትርጉም የማይሰጥ ነው፡፡

የፖለቲካ መብቶች በሕግም ሆነ በተግባር ሙሉ በሙሉ ዕውቅና ባላገኙበት በአንድ አገር ውስጥ የትጥቅ ትግልን ማካሄድ ምክንያታዊና አማራጭ የሌለው ምርጫ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የመደራጀት መብትና የብዙኃን ፓርቲ አሠራር ሕጋዊ ዕውቅና ባላገኘበት በአንድ አገር ውስጥ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለመደራጀትም ሆነ ተደራጅቶ ሰላማዊ ትግል ለማካሄድ የሚያስችለው ሕጋዊ መሠረት ስለማይኖረው ብቸኛ ምርጫው የአመፅና የትጥቅ ትግል መሆኑ የግድ የማይቀር ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለአንድ መደራጀትንና ሰላማዊ ትግልን ቢያንስ በሕግ ደረጃ ዕውቅና ያልሰጠ መንግሥት የአመፅን ወይም የትጥቅ ትግልን ሕገ-ወጥ አድርጐ ማውገዝ አስቸጋሪ ስለሚሆን በዚያ ዓይነቱ ሥርዓት ውስጥ የሚካሄድ የአመፅ ወይም የትጥቅ ትግል በሕግ ላይ ባይሰፍርም ምክንያታዊና ፍትሐዊ ተደርጐ መወሰዱ የማይቀር ነው፡፡

ነገር ግን የፖለቲካ መብቶች በሕግ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ዕውቅና ባገኙበት በአንድ አገር ውስጥ እነዚያ በሕግ ዕውቅና ያገኙ መብቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር የሚውሉበት ሁኔታ የተመቻቸ ቢሆንም - ባይሆንም በዚያ ዓይነቱ አገር ላይ የአመፅ ወይም የትጥቅ ትግልን ለማካሄድ መሞከር በሕገ-ወጥነት የሚያስፈርጅ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ባለበት አገር በሕገ-ወጥነት ሳይፈረጁ ማካሄድ የሚቻለው ሰላማዊ ትግልን ብቻ ሲሆን የሰላማዊ ትግሉ ቀዳሚ ትኩረትም በሕግ ዕውቅና ያገኙት የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ

በተግባር ጥቅም ላይ የሚውሉበትንና የፖለቲካ ምህዳሩ የሚሰፋበት ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ ጊዜ የፖለቲካ መብቶቹ በሕግም ሆነ በተግባር ሙሉ በሙሉ ከተከበሩ በኋላ ግን በዚያ አገር ሊኖር የሚችለው የፖለቲካ ሂደት "ትግል" መሆኑ ቀርቶ በሌሎች የዳበረ ዴሞክራሲ ባለባቸው አገሮች እንደሚታየው የፖለቲካ ውይይት፣ ክርክር፣ ድርድርና የምርጫ ፉክክር ይሆናል ማለት ነው፡፡

ከዚህ አጠቃላይ ግንዛቤ ተነሥተን የአገራችንን የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ለማየት ስንሞክር ዛሬ በአገራችን ኢትዮጵያ የፖለቲካ መብቶች ሙሉ በሙሉ ሕገ- መንግሥታዊ ዕውቅና ያገኙ ሲሆን እነዚህን ሕጋዊ ዕውቅና ያገኙ መብቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር በማዋል ረገድ ግን በርካታ መሠረታዊ ጉድለቶችና ችግሮች ይታያሉ፡፡ ስለዚህ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በዚህ ዓይነቱ መብቶች በሕግ ዕውቅና አግኝተው እያለ ነገር ግን በአግባቡ በተግባር መዋል ባልቻሉበትም ሁኔታ ቢሆን ሰላማዊ ትግልን ማካሄድ ሕጋዊ ብቻ ሳይሆን ተገቢና ጠቃሚ ስልት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ባለበት አገር የትጥቅ ትግልን ማካሄድ ሕገ-ወጥ የሆነ ተግባር ቢሆንም ተገቢና ጠቃሚ ነው ብሎ በማመን ሊያካሂደው የሚፈልግ አካል ካለ ግን ሊካሄድ የሚችልበት ዕድል የለም ማለት አይደለም፡፡ ሊካሄድ እንደሚችል በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ የብዙኃን ፓርቲ ሥርዓት እናራምዳለን በሚሉ በሌሎች በርካታ አገሮች ጭምር የሚካሄድበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር ልናያቸው በምንሞክራቸው ምክንያቶች በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ከማካሄድ ባለፈ የትጥቅ ትግልንም ሆነ ሁለገብ የሚሉትን ዓይነት ትግል ማካሄድ ምን ያህል አስቸጋሪ፣ ተገቢ ያልሆነና የምንፈልገውን ውጤት ሊያመጣ የማይችል ስለመሆኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት ሰላማዊ ትግልን በአገሪቱ ውስጥ ማካሄድን የሚፈቅድ የሕግ ዕውቅና ባለበትና በብዙ ችግሮች የተሞላና የጠበበም ቢሆን ሰላማዊ ትግልን በተግባር ማካሄድ እንደሚቻል በግልጽ እየታየ ባለበት አገር ውስጥ የትጥቅ ትግልን ለማካሄድ መምረጥ በበቂ ምክንያት የተደገፈ ስልት ነው ማለት አይቻልም፡፡ በአገሪቱ ወደ 93 የሚሆኑ ፓርቲዎች ሰላማዊ ትግል እያደረጉ በሚገኙበት በአሁኑ ወቅት በትጥቅ ትግል ዓላማን ለማስፈጸም መሞከር በአገሪቱ ሕግ በሕገ-ወጥነት የሚያስፈርጅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን በተጨባጭ እየታየ እንደሚገኘው በቂ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ መጠናከርና ለውጤት መብቃት የሚችል ስልት አይደለም፡፡ ሰላማዊ ትግልን ለማካሄድ የሚያስችለውን ሕጋዊ መብት ተጠቅሞ በአፈጻጸም ደረጃ የሚታየውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ጠንካራ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ እየተቻለ

አውዳሚ ወደሆነና ስለመጨረሻ ውጤቱም ርግጠኛ መሆን ወደማይቻል የትጥቅ ትግል አማራጭ መግባት ለአገርና ለሕዝብ ደኅንነት ከመጨነቅ የኃላፊነት ስሜት የሚነሣ ስልት ሊሆን አይችልም፡፡

ሁለተኛው ምክንያት እስካሁን በአገራችን ታሪክ ከሰላማዊ መንገድ ውጭ በሆነ የኃይል መንገድ ለሥልጣን የበቁ መንግሥታት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአገሪቱ መገንባት እንዳልቻሉ አዬታወቀ ከዚህ ታሪካዊ ሂደቱ ካረጋገጠው እውነታ በተቃራኒ በትጥቅ ትግል አዲስ ተአምር እፈጥራለሁ ብሎ መነሣት ሕዝብን በቀላሉ ማሳመን የሚያስችል አማራጭ ሊሆን አይችልም፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገኝ የሚችለው በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ ራሱንና ሕዝብን ተሳታፊ በማድረግና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በመገንባት ሂደት መሆኑ አዬታወቀ በተቃራኒው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በትጥቅ ትግል መንግሥትን በመደምሰስ ለማምጣት መሞከር በአገሪቱ እስካሁን የታዩትን ታሪካዊ ስህተቶች መልሶ ከመድገም የተለየ ውጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡ በሆነ ተአምር የትጥቅ ትግል በአገራችን መጠናከር የሚችልበት ዕድል ቢያገኝ እንኳ ሄዶ ሄዶ እንደተለመደው የመንግሥትን ለውጥ ከማምጣት አልፎ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዋስትና እንደማይሰጠን ከወዲሁ መገመትና በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል ለማድረግ ሲታሰብም ጦርነቱ ተጠናቋል ሊባል የሚችለው አራት ኪሎ ቤተ-መንግሥት ያሉ ሰዎችን በማባረር የማይቆምና በየክልሉ ያሉትንና ሥልጣንን እያጣጣሙ የሚገኙትን መንግሥታትም በኃይል ማንበርከክን የሚጠይቅ ይሆናል፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አገሪቱ ወደ የርስ በርስ ጦርነት ሳትገባ እንዲህ ዓይነቱ ምኞት በቀላሉ ማሳካት ይቻላል ብሎ ማሰብ የዋህነት ይሆናል፡፡

በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የትጥቅ ትግል የመንግሥት ለውጥን ለማምጣት የሚያስችልበት ዕድል አለ ቢባል እንኳ የዴሞክራሲ ሥርዓትን ለመገንባት ግን የተሻለ መንገድ እንዳልሆነ በእኛም አገር ሆነ ኤርትራን፣ ዩጋንዳን፣ ሩዋንዳን፣ ዚንባቡዌን በመሳሰሉ የአፍሪካ አገሮች በተጨባጭ ታይቷል፡፡ በተለይም የተቋሰለና የተካረረ የፖለቲካ ቁርሾ ባለበት በእኛ ዓይነቱ አገር በትጥቅ ትግል አሸናፊ የሆነ ኃይል ሥልጣንን የደምና የአጥንት ካሣ አድርጐ ከማየቱም በላይ ዴሞክራሲ “በጠላትም” እጅ የመውደቅ አደጋም ሊያመጣብኝ ይችላል ብሎ ስለሚሰጋ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን አሜን ብሎ ለመቀበል መቸገሩ አይቀሬ ይሆናል፡፡ በሌሎች አገሮችም ሆነ በእኛ አገር በተግባር እንደታየውም ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ስልት ምንጊዜም ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ውጤት እንደሚያስከትል በግልጽ የታየ እውነታ ነው፡፡ በዚህ ረገድ “የትም ፍጭው ዱውቄቱን አምጭው” የሚለው ባህላዊ አባባላችንም ሆነ “ውጤቱ

የስልቱን ትክክለኛነት ያረጋግጣል /The end justifies the means/” የሚለው የማኪያ ቬሊ አባባል ሊሠራ አይችልም፡፡

ስለ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአግባቡ መጨነቅ ካለብን የዱውቂቱ መገኘት ብቻ ሳይሆን ዱውቂቱ የትና እንዴት እንደሚፈጭ ማዎቅም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በትክክለኛ የዴሞክራሲያዊ ሂደት የስልቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥልን ውጤቱ ሳይሆን የውጤቱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥልን ስልቱ ነው፡፡ ለዚህም ነው ዴሞክራሲ ሰፍኖባቸዋል በሚባሉ አገሮች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ፍትሐዊ እስከሆኑ ድረስ በምርጫው አሸናፊ የሆነው ኃይል ደካማም ይሁን አንግባለን የግድ ዕውቅና ማግኘት አለበት የሚባለው፡፡ ምክንያቱም በዴሞክራሲ አግባብ የውጤቱን ትክክለኛነት የበለጠ የሚያረጋግጠው የስልቱ ትክክለኛነት /The means justifies the end/ በመሆኑ ነው፡፡ የትጥቅ ትግል ግን ዘላቂ ውጤት አያመጣም ብቻ ሳይሆን ሂደቱም በዚያው መጠን አውዳሚና ዘግናኝ የሆነ ስልት ነው፡፡ የጦርነት ሂደት የአገር ሃብትና የሕዝብ ሕይወት አውዳሚ ከመሆኑም በላይ ተሸናፊን ብቻ ሳይሆን አሸናፊንም የማያስደስት በቀላሉ የማያገግም የኅብረተሰብ ህመም (trauma) የሚፈጥር ስልት ነው፡፡

ሦስተኛው ምክንያት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ድህነት የኑሮ ብቻ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከእንግዲህ አገራችን ውስጥ የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የትጥቅ ትግል ቢያንስ በዝቅተኛ ግምት አሥር ዓመታት ብቻ ሊፈጅ ይችላል ቢባል እንኳ የአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ በዚያው መጠን መስተጓጐሉና በርካታ የአገሪቱ ሀብትና ንብረትም በጦርነቱ ሂደት መውደሙ አይቀርም፡፡ ይህች ድሀ አገራችን ከእንግዲህ አንድ የተራዘመ አውዳሚ ጦርነት ካስተናገደች በኋላ ችግሮቿ ተፈትተው የዴሞክራሲ አገር መሆኗ ይቅርና ህልውናዋ እንደ አገር ይቀጥላል ብሎ ማሰብም አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለዚህ የአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴዎች ሳይቋረጡና አገሪቱ አሁን የምትገኝበትን አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት እንደያዘች የሥርዓት ለውጥ ማምጣት የሚቻልበትን የሰላማዊ ትግል ከማራመድ ይልቅ በዚች በቋፍ ባለች አገር እንደገና የጦርነት ትግል ለማቀጣጠል መሞከር በእምነት እንኳን ባይሆን ቢያንስ ሊያስከትል በሚችለው ውጤት አገርን የማፍረስ አማራጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

አራተኛው ምክንያት የትጥቅ ትግል ሂደቱም ሆነ ውጤቱ አገርና ሕዝብን የማይጠቅም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዐቅምና ከአካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታም አንጻር የትጥቅ ትግል በአሁኑ ወቅት የሚያዋጣ ስልት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ በዓለምም ሆነ በአካባቢያችን በተከሰቱት ለውጦች ምክንያት የትጥቅ ትግልን ለማካሄድ

የሚያስችል በቂ ድጋፍ ከውጭ ኃይሎች ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አገር ውስጥ የሚገኘው የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ሕዝብም ከኢኮኖሚ አቅምም ሆነ ከሞራል አንጻር የተራዘመ ጦርነት ለመሸከም የማይችልበት ሁኔታ መፈጠሩ በግልጽ እየታየ መጥቷል፡፡ ሕዝቡ የትጥቅ ትግሉን ለረዥም ዓመታት ለመሸከም ሊወስን ቀርቶ የትጥቅ ትግሉን በአፍ ሳይሆን በተግባር ለመምራት ቆርጠው የተነሱ ጥቂት የፖለቲካ ኤሊቶች በአገራችን አለመኖራቸውም ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በተግባር ታይቷል፡፡

ከእነዚህ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በተጨማሪም አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘው ገዥ ፓርቲ ራሱ በጫካ ትግል ያለፈና ጠንካራ ጉኑም ጦርነት የሆነ ኃይል ነው፡፡ ይህንን ኃይል ደካማ ጉኑ በሆነው የሐሳብና የምርጫ ፉክክር ለማሸነፍ ከመታገል ይልቅ ጥርሱን ነቅሎ ባደገበትና ጠንካራ ጐኑ በሆነው የትጥቅ ትግል ለማሸነፍ መሞከርም አቅምን ያላገናዘበ ስልት ይሆናል፡፡ በርግጥ በአንድ በኩል የሕዝብ ብሶት ሲጠናከር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ የድሎት ኑሮን የበለጠ እየለመደው ሲመጣ ነገሮች ሊለዋወጡ የሚችሉ ቢሆንም አሁን ባለው ሁኔታ ኢህአዴግ የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴዎችን በእንጭጩ ለማኮላሸት የሚያስችል አቅም ይኖረዋል፡፡ በተግባርም እየታየ ያለው ይኸው ነው፡፡

በአጠቃላይ ከእነዚህ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በመነሣት የትጥቅ ትግል ለአገራችን የወቅቱ ፖለቲካ የማይገባ ብቻ ሳይሆን የማያዋጣ ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በየትኛውም መመዘኛ ልንመረምረው ብንሞክር በአሁኑ ወቅት የትጥቅ ትግልን ከሰላማዊ ትግል ተመራጭና የተሻለ የሚያደርገው የሕግም ሆነ የፖለቲካ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡ እውነታው ይህ ባይሆን ኖሮ በትጥቅ ትግል ዓላማችንን እናስፈጽማለን ብለው ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ሲፎክሩ የኖሩት የፖለቲካ ኃይሎች እስካሁን አንድ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ውጤት ላይ ደርሰው ባዬናቸው ነበር፡፡ የወቅቱን የአገራችንን ፖለቲካ በስሜትና በጥላቻ ሳይሆን በምክንያታዊ ኃላፊነት ለማየት ለሚሞክር ለማንኛውም ዜጋ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሳማኝ ሆነው እያለ አንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎች ለምን ከሰላማዊ ትግል ይልቅ የትጥቅ ትግልን እንደሚመርጡ መነሻ ምክንያታቸውን ትንሽ ወደኋላ መለስና- ጠለቅ ብሎ መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

የትጥቅ ትግልን የሚደግፉ ሰዎች ምክንያታቸው በዋናነት ከሁለት አቅጣጫ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የተወሰኑት የትጥቅ ትግልን የሚደግፉት ከልብ በመነጨ እምነት ሲሆን፣ ከፊሎቹ ግን የትጥቅ ትግልን እንደግፋለን የሚሉት ከልባቸው አምነውበት ሳይሆን ራሳቸውን ከሰላማዊ ትግሉ ጭምር ለማራቅና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ላለመወጣት በማሰብ

የሚጠቀሙበት የመሸሻ ዘዴ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ የትጥቅ ትግልን በአማራጭነት የሚያዩ ኃይሎች የወቅቱን ትግል ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚደረግ ትግል አድርገው ከማየት ይልቅ ትግሉን የነፃነት ትግል አድርገው በመመልከት ለሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ ዕውቅና መንፈግ ስለሚፈልጉ ሆን ብለው ከሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ጋር ራሳቸውን ማነካካት አይፈልጉም፡፡ የሰላማዊ ትግሉ ሂደት የአገሪቱን ሕግና ተቋማት የማክበር፣ በምርጫ የመሳተፍና ሲቻልም በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከገዥው ፓርቲ ጋር ጭምር በመቻቻል አብሮ መሥራትን የሚያስከትል ስለሆነና እንዲህ ዓይነቱ ሂደት ውስጥ መግባት ደግሞ ለሥርዓቱ ዕውቅና መስጠት ስለሚሆንባቸው የቱንም ያህል ምቹ ሁኔታ በአገሪቱ ቢፈጠር "የእናቴ መቀነት አሰናከለኝ" የሚል ምክንያት እየፈጠሩ ራሳቸውን ከሰላማዊ ሂደቱ ማራቅ እንጂ ተሳትፎ ማድረግን አይመርጡም፡፡

በተጨማሪም የእነዚህ ኃይሎች ዓላማና ግብ ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ ለማምጣት ሳይሆን የመንግሥት ለውጥ በማምጣት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ስለሆነና እንዲመጣ በሚፈልጉት ለውጥም መጭው ትውልድ እንዲጠቀም የሚጨነቁ ሳይሆኑ በለውጡ ውጤት ራሳቸውን ተጠቃሚ አድርገው ለማየት የሚጓጉ በመሆናቸው ባለው ላይ ከሚገነባና በሂደት ከሚመጣ አስተማማኝ ለውጥ ይልቅ ሥርዓቱን በጦርነት ሙሉ በሙሉ በመደምሰስ የሚመጣን ሥር-ነቀል ለውጥ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ከጥቅም አንጻር ብቻ ሳይሆን በአገራችን ቀደምት ባህልም ሆነ በግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ሽፍትነትና ፋኖነት የጀግንነት መግለጫና የአገር ፍቅር ማሳያ ተደርጎ የሚታይ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜም ከስሜታዊነትና ከተሳሳተ ግንዛቤ በመነሣት የሚወሰድ ምርጫ ነው፡፡ በተለይም የዚህ ስልት አብዛኛዎቹ አቀንቃኞች የግራ ፖለቲካ አራማጆች የነበሩ ስለሆነ በማሌ የመደብ ትንታኔ መሠረት አንዱ ሌላውን ሙሉ በሙሉ ደምስሶ ፍጹማዊ የበላይነቱን ማረጋገጥ እስካልቻለ ድረስ በድርድርም ሆነ በሌላ ሰላማዊ መንገድ ቅራኔአችን ሊታረቅ ወይም ሊቻቻል ይችላል የሚል እምነት ስለሌላቸው ብዙውን ጊዜ ምርጫቸው የትጥቅ ትግል ሲሆን ይታያል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ጽንፈኛ አመለካከት ያላቸውን ኃይሎች እንኳንስ ብዙ ጉድለትና ችግር ባለበት በወቅቱ የአገራችን ሁኔታና የተሟላ የሕግና የአፈጻጸም ሥርዓት በአገሪቱ በመዘርጋትም ሰላማዊ ትግሉን እንዲቀላቀሉ ማሳመን አስቸጋሪ ነው፡፡ ሥርዓቱን አንድ ጊዜ እንደ ውጭ ወራሪ ኃይል በማየት ሙሉ በሙሉ ዕውቅና መንፈግን የመረጡ ስለሆኑ ለእነሱ ሰላማዊ ትግሉን መቀላቀል ሁል ጊዜ ሲሉት እንደሚደመጠው አገርን መክዳትና ባንዳነት ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ኃይሎች የወቅቱ የኢህአዴግ ሥርዓት በሥልጣን ላይ እስካለ ወይም እነሱን በአቋራጭ

የሥልጣን ባለቤት የሚያደርግ የፖለቲካ ሁኔታ አገሪቱ ውስጥ እስካልተፈጠረ ድረስ ሰላማዊ ትግሉን መቀላቀል በቀላሉ የማይዋጥላቸው መሆኑ እስካሁን ባሳለፍነው ሂደት በበቂ ሁኔታ ታይቷል፡፡

ከሰላማዊ ትግሉ ራሳቸውን ለማሸሽና ለትግሉ ምንም ዓይነት አስተዋፅኦ ላለማበርከት አቅሙ ወይም ፍላጐቱ ያጠራቸው አንዳንድ ሰዎችም የትጥቅ ትግል ለአገራችን እንደማይጠቅምና እንደማይሠራ እየተረዱትም የትጥቅ ትግል ደጋፊ መስለው ለመታየት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ በተለይም በውጭ አገር ኗሪ የሆኑ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ለሰላማዊ ትግሉ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ሲጠየቁ የተጠየቁትን ለማድረግ ምንአልባት አቅሙ ወይም ፍላጐቱ የለንም ከማለት ይልቅ ቀላልና አቋራጭ ሆኖ የሚታያቸው መልስ በሰላማዊ ትግል እምነት የለንም ማለት ሆኖ ይታያል፡፡ የሚገርመው እነዚህ ሳያምኑበት የሚያዋጣው የትግል ስልት የትጥቅ ትግል ነው ሲሉ የሚደመጡት ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ ከልባቸው የትጥቅ ትግልን እንደግፋለን የሚሉትም ኃይሎች ቢሆኑ ምናልባት በዓመት 20 እና 30 ዶላር ከማዋጣት አልፈው የትጥቅ ትግሉ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት በጥቂቱም ቢሆን ለመክፈል ዝግጁ አይደሉም፡፡ በአውሮፓና በአሜሪካ ሆነው አገር ውስጥ የሚካሄደውን ሰላማዊ ትግል ከማንቋሸሽ አልፈው በተግባር እናምንበታለን የሚሉትን የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ስላልወሰኑ እስካሁን በዐሥራ ስምንት ዓመታት ውስጥ አንድ ወረዳ ወይም ቀበሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ተቆጣጥረው ሊያሳዩን አልቻሉም፡፡

የእነሱ የትጥቅ ትግል እምነት ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ ሆኖ በኢንተርኔት የቃላት ጥይት ከመለባለብ አልፎ አያውቅም፡፡ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት እምነታችን የትጥቅ ትግል ነው ሲሉን የከረሙት የኢህአፓ ሰዎችም ሆኑ በቅርቡ ይህንኑ ጐራ መቀላቀላቸውን ያወጁት የግንቦት 7 ሰዎች ከፖቶማክ ወንዝ መናፈሻ ወጥተው በኢትዮጵያ ተራሮችና ሸለቆዎች ራሳቸው ደፋ-ቀና ብለው የሚያምኑበትን ትግል ማካሄድ ይቅርና ጐረቤት አገር እንኳ ተቀምጠው እናምንበታለን የሚሉትን ስልት ለመፈጸም ሲግደረደሩ አልታዩም፡፡ እነዚህ ሰዎች የድሀው ገበሬ ልጅ በጦርነት አካሉንና ሕይወቱን ገብሮ እነሱን ቀይ ምንጣፍ አንጥፎ ለቤተ-መንግሥት ሥልጣን እንዲያበቃቸው ሲቀሰቅሱ የሚደመጡት አትላንቲክ ማዶ በሞቀ ቤታቸው ተቀምጠው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዐሥራ ሰባት ዓመት ትግል መንግሥት ለመሆን ይቅርና እስካሁን አንድ ወረዳ እንኳን ተቆጣጥረው ሊያሳዩን አልቻሉም፡፡ ሰላማዊ ትግሉ ግን በብዙ ችግሮችም ውስጥ ሆኖ በ97ዓ.ምቱ ምርጫ ተቃዋሚዎች ቢያንስ የአገሪቱን ርእሰ ከተማና በአገሪቱ ፓርላማ ከ170 በላይ ወረዳዎች መቀመጫ ማሸነፍ እንዳስቻለን ለእነዚህ የዜሮ ድምር የፖለቲካ ኃይሎች

ሊታያቸው አልቻለም፡፡ የእነሱ የውጤትና የድል መለኪያ የመንግሥት ለውጥ ብቻ ስለሆነ ከዚያ በታች የተገኘ ውጤትና ለውጥ ሁሉ ለእነሱ ትርጉምና ፋይዳ የለሽ ነው፡፡

የሆነ ሆኖ "የትጥቅ ትግልን እንደግፋለን" የሚሉ ኃይሎች ሰላማዊ ትግል አያዋጣም ለሚለው ክርክራቸው በተደጋጋሚ የሚያቀርቡት ምክንያት ኢህአዴግ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አካሂዶ ሥልጣኑን በሰላም ለመልቀቅ ፍላጐት የለውም የሚልና፣ በአጠቃላይም በጠመንጃ ሥልጣን ላይ የወጣን ኃይል በዚያው በጠመንጃ እንጂ በሰላማዊ መንገድ ማውረድ አይቻልም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ኃይሎች በውል ያልተገነዘቡት ቁምነገር በመጀመሪያ ደረጃ በነፃና በፍትሐዊ ምርጫ ሥልጣኑን በፈቃደኛነት ለመልቀቅ ዝግጁ የሆነ መንግሥት በአገራችን ቢኖር ኖሮ- እነኳን የትጥቅ ትግልና ሰላማዊ ትግል ማድረጉም ባላስፈለገ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል መንደርደሪያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በሕግ ደረጃ የተቀመጡት መብቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ የሚሆኑበት ሁኔታ በአገራችን ተመቻችቶ ቢሆን ኖሮ በአደጉት አገሮች እንደምናየው የምርጫ ፉክክርና ውድድር እንጂ የሕይወት መሥዋዕትነት ጭምር የሚጠይቅ የሰላማዊ ትግል ግብግብ ውስጥ ባልተገባ ነበር፡፡

ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ የሚችለው ሁኔታዎች በተመቻቹበት አገር ብቻ ሳይሆን አምባገነናዊ ሥርዓቶች ባሉባቸው አገሮች ጭምር መሆኑ ቀድሞም ሆነ ዛሬ በተለያዩ አገሮች እየታየ ያለ እውነታ ነው፡፡ ከእኛ አገር የዎቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ በተለየና በባሰ ሁኔታ በቅኝ ግዛትና በአፓርታይድ ሥርዓት ሥር በነበሩ አገሮች ጭምር ሰላማዊ ትግል ሲካሄድና ውጤት ሲያመጣ የታዬ ስለሆነ ስልቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ውጤት አያመጣም ብሎ መደምደም ምክንያታዊ አስተሳሰብ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲያውም በአገራችን ሁኔታ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ ሰላማዊ ትግል ይሠራል -አይሠራም? የሚለው ሳይሆን ለመሆኑ እስካሁን ሰላማዊ ትግል በአገራችን በበቂ ሁኔታ ተሞክሯል ወይስ አልተሞከረም? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው፡፡

በጠመንጃ ሥልጣን የያዘ ኃይል በሰላማዊ መንገድ ሥልጣኑን ሊለቅ አይችልም የሚለው ክርክርም ውሃ የሚቋጥር ክርክር አይደለም፡፡ አንድ ሕዝብ ተገቢ ዓላማ ይዞ ሰላማዊ ትግልን በአግባቡ ማካሄድ ከቻለ ማንኛውንም ዓይነት የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚያግደው ነገር የሌለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በጠመንጃ ሥልጣን የያዘ ኃይል ያለ ጠመንጃ ከሥልጣኑ አይወርድም የሚለው ክርክር በሆነ ተአምር እውነት ሊሆን ይችላል ብለን ብናምን እንኳን እንዲህ ዓይነቱ ክርክር አሁን በሥልጣን ላይ ለሚገኘው መንግሥት ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በጠመንጃ ለውጥ እናመጣለን ለሚሉት ኃይሎች በእኩል መጠን የሚሠራ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በጠመንጃ የመጣ ኃይል ያለጠመንጃ ከሥልጣን የማይወርድ ከሆነ

የኢትዮጵያ ሕዝብ በምን የተለየ ምክንያት ዛሬ በጠመንጃ ትግል ለውጥ እናመጣለን ብለው የሚያስቡት ኃይሎች ነገ ሥልጣን ሲይዙ ከአሁኑ መንግሥት በተለየ እነሱ በምርጫ ከሥልጣን ሊወርዱ ይችላሉ ብሎ ሊተማመን እንደሚችል ግልጽ መልስ ማቅረብ አይቻልም፡፡ በጠበንጃ ኃይል ወደ ሥልጣን የተቆናጠጡት አቶ መለስ ዜናዊ በሰላማዊ መንገድ ፈጽሞ ከሥልጣን አይወርዱም ብለን መደምደም የምንችል ከሆነ፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በጠበንጃ ኃይል ወደ ሥልጣን ቢወጡ ሥልጣናቸውን መልሰው በሰላማዊ ትግል ሊያስረክቡ ፈቃደኛ እንደሚሆኑ በምን ዓይነት የደም ምርመራ አስቀድሞ ማወቅና ማረጋገጥ እንደሚቻል ግልጽ አይደለም፡፡

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጠቃሚ ቁምነገር ማንኛውም በትጥቅ ትግል ለሥልጣን የሚበቃ ኃይል ሥልጣኑን በሰላማዊ መንገድ እንደሚለቅ ርግጠኛ መሆን የማይቻል ከሆነ ሌላ አዲስ የፖለቲካ ኃይል በሌላ የተራዘመ ጦርነት የብዙ ዜጐችን ሕይወትና የአገር ንብረት አውድሞ ለሥልጣን ከበቃ በኋላ አዲስ የሰላማዊ ትግል ከመጀመር ይልቅ አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኘው አምባገነናዊ ኃይል ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን እንዲቀበል የተጀመረውን ሰላማዊ ትግል የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ከሚጠይቀው ጊዜም ሆነ በሕይወትና በንብረት ላይ ከሚያስከትለው መሥዋዕትነት አንጻር የሚመረጥ መሆኑን ነው፡፡

ስለዚህ በጠመንጃ የመጣ ኃይል ያለ ጠመንጃ አይወርድም የሚለው ክርክር ዞሮ ዞሮ አገራችን ከዚህ የማያቋርጥ አዙሪት ልተወጣ የምትችለው በሰላማዊ ትግል እንጂ በትጥቅ ትግል አለመሆኑን በራሱ የሚያረጋግጥ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የቱንም ያህል ጊዜና መሥዋዕትነት ቢጠይቅ ዘላቂ ዋስትና ሊሰጠን የሚችለውና ውጤቱ ወደ ኋላ በማይመለስ ደረጃ የአዲስ ሥርዓትና የፖለቲካ ባህል ባለቤት ሊያደርገን የሚችለው ሰላማዊ ትግል እንጂ የትጥቅ ትግል አይደለም፡፡ የወቅቱ ትውልድ ካለፉት ትውልዶች በተለየና በተሻለ ሁኔታ ሊያስመካ የሚችል ኃውልት ሊተከልለት የሚገባ ተግባር አከናውኖ ማለፍ ካለበትም ከምንም ነገር በላይ ታሪካዊ ሊሆን የሚችለው ለሁሉም በጎ ነገር መነሻ መሠረት የሚሆነውን ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን በዚች አገር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተክሎ ማለፍ ከቻለ ነው፡፡

ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው የትጥቅ ትግል አማራጭ እየቀረበ ያለው እየተካሄደ የሚገኘው የሰላማዊ ትግል ጅምር ጭራሽ ምንም ዓይነት ውጤት ማሳየት ባልቻለበት ሁኔታ ቢሆን ኖሮ እምብዛም ባላስገረመ ነበር፡፡ ነገር ግን ሰላማዊ ትግል እንኳን በበቂ መጠን ተሞክሮ ከሽፏል ሊባል ይቅርና ገና በበቂ መጠን ባልተሞከረበትም ሁኔታ ተጨባጭ ውጤት እያሳዬን ይገኛል፡፡ ለዚህም ቀላልና ግልጽ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው ምሳሌ ምርጫ 97 ነው፡፡ ከምርጫ 97 በፊት በነበሩት ዓመታት በሰላማዊ ትግል ዙሪያ በተሠሩ ተከታታይ ሥራዎች ውጤታማነት

ምክንያት በምርጫ 97 የኢትዮጵያ ሕዝብ “በጠመንጃ የመጣን በጠመንጃ” ከሚለው ሥር የሰደደ ልማዳዊ አስተሳሰቡ ሰብሮ በመውጣት በምርጫ ሂደት ውጤት ለማምጣት በነቂስ ወጥቶ ተሰልፏል፡፡ በሰላማዊ ትግል እምነት በመፍጠርም ከምርጫው አንድ ሳምንት በፊት በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚሊየን የሚቆጠር ሕዝብ መስቀል አደባባይ ወጥቶ ስሜቱን በሰላማዊ መንገድ ገልጾ ወደየቤቱ በሰላም መመለስ ችሏል፡፡ በምርጫው ወቅት ከሌሊቱ 10 ሰዓት ጀምሮ በየምርጫ ጣቢያው በነቂስ ወጥቶ በመሰለፍ ዓለምን ያስደመመ የምርጫ ተሳትፎ አሳይቷል፡፡ ቢያንስ በገዥው ፓርቲ የታመነውን የምርጫ ውጤት ካዬንም ሕዝቡ ተቃዋሚዎች አዲስ አበባ ከተማን ሙሉ በሙሉ እንዲያሸንፉና ከ170 ባላነሱ ወረዳዎች ምርጫውን በማሸነፍ በአገሪቱ ፓርላማ የማይናቅ ውክልና እንዲኖራቸው በማድረግ በአገሪቱ ፖለቲካ ከፍተኛና የመጀመሪያ ሊባል የሚችል የለውጥ እመርታ አሳይቷል፡፡

ከዚህ ውጤት እንደምንረዳው ተቃዋሚዎች በዚያ ምርጫ ላይ ሕዝቡ የሰጣቸውን ውጤት በአግባቡ በእጃቸው ይዘው ተጠቅመውበት ቢሆን ኖሮ በሚቀጥለው ምርጫ መንግሥት ለመሆን የሚያስፈልጋቸው በ97 ምርጫ የተገኘውን ውጤት ቢበዛ በ50% ብቻ ማሳደግ መቻል ነበር፡፡ “የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች” እንደሚባለው የቅንጅት መሪዎች ዕድሜ ልካቸውን ሲመኙት የኖሩትን የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ለማስገባት አምስት ዓመት መታገስ ባያቅታቸውና የተገኘውን ውጤት ተገቢ ባልሆነ ጉጉትና ምኞት ተገፋፍተው ሜዳ ላይ ባይበትኑት ኖሮ የሕዝቡ ሰላማዊ ትግል በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለመንግሥትነት የማይበቃበት ምክንያት አልነበረም፡፡ አንደኛ - ተቃዋሚዎች ምርጫ 97 ላይ ተፈጥሮ የነበረውን የሕዝብ የተሳትፎ ስሜት በአግባቡ ጠብቀን ማስቀጠል ችለን ቢሆን ኖሮ፤ ሁለተኛ -ፓርላማን ገብተንና አዲስ አበባ መስተዳድርን ተረክበን ከኢህአዴግ የተሻለ ሕዝብን የማስተዳደር ብቃት ያለን መሆኑን በተግባር ማሳየት ችለን ቢሆን ኖሮ፤ ሦስተኛ - ኢህአዴግንም ወደፊት በምርጫ አሸንፈን ለሥልጣን ስንበቃ ቂም ይዘን ልንበቀለው የማንፈልግና ከልዩነቶቻችንም ባሻገር በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አብረነው ልንሰራ የምንችል መሆኑን ማሳመን ችለን ቢሆን ኖሮ በመጭው የ2002 ምርጫ ተቃዋሚዎች መንግሥታዊ ሥልጣንን ከመጨበጥም አልፎ የሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን ባህል በአገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲተከል ለማድረግ የማንችልበት ምክንያት አልነበረም፡፡

ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ትግል ምንአልባትም ከሚጠበቅበት ፍጥነት በላይ ውጤት እያሳዬ መሆኑን በብዙ መረጃዎችና ምሳሌዎች አስደግፎ መናገር ይቻላል፡፡ ችግሩ ሰላማዊ ትግሉን በብቃት መምራት የተሳነን የፖለቲካ መሪዎች የእኛን ድክመትና ውድቀት

በሰላማዊ ትግሉ ሂደት ላይ ለማሳበብ መሞከራችን ነው፡፡ አንዳንዶቻችን ለሥልጣን ካለን ከፍተኛ ጥማትና ለኢህአዴግ ካለን ሥር የሰደደ ጥላቻ አንጻር ኢህአዴግ በአንድ ምርጫ እንደ ጉም ተኖ እንዲጠፋ ስለምንፈልግ ሰላማዊ ትግሉ ያለ ተፈጥሮውና ባህሪው የእኛን ግላዊ ስሜት ሊያረካ የሚችል ግብታዊ ድል እንዲያጐናፅፈን እንፈልጋለን፡፡ ይሄ የእኛ የአስተሳሰብ ችግር እንጂ የሰላማዊ ትግል ስልት ችግር አይደለም፡፡ ሰላማዊ ትግል ከፍተኛውን ለውጥ ለማምጣት የሚችለው ከአጠቃላይ የኅብረተሰብ የአስተሳሰብ ለውጥና ከዴሞክራሲያዊ ተቋሚት መጠናከር ጋር ተያይዞ ስለሆነ ግብታዊ ለውጥ እንዲያመጣ መጠበቅ የለብንም፡፡ አይደለም ቀርቶ የሕዝብን ልብና አእምሮ ነፃ የማውጣት ጥያቄ የሆነው ሰላማዊ ትግልና ተራራና ጫንዛን ነፃ በማውጣት ሊገለፅ የሚችለው የትጥቅ ትግል ስልትም ለዐሥርት ዓመታት ያሚቆጠር አታካች ሂደትን ሊጠይቅ እንደሚችል በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ታሪክ በተጨባጭ አይተናል፡፡

በአንፃሩ የሰላማዊ ትግል ተፃራሪ የሆነው የትጥቅ ትግል ስልት ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በአገራችን ምን ውጤት አመጣ? ብለን ለማየት ስንሞክር ግን በአዎንታዊ ጐኑ ሊጠቀስ የሚችል ውጤት መናገር የሚቻል አይሆንም፡፡ በዐሥራ ስምንት ዓመቱ የፖለቲካ ትግል ሂደት ከሰላማዊ ትግሉ ይልቅ በየፖለቲካ መድረኩ የበለጠ ጐልቶ የሚሰማው የትጥቅ ትግል አስፈላጊነት ቢሆንም በዚህ ስልት እስካሁን አንድም የተጨበጠ ውጤት አላዬንም፡፡ ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎች አመች በነበሩበት ወቅት በ17 ዓመት የትጥቅ ትግል ሂደት ኢህአዴግ መንግሥት ለመሆን የበቃ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የትጥቅ ትግል እናካሂዳለን የሚሉ ኃይሎች ግን በዐሥራ ስምንት ዓመት ሂደት አንድ ወረዳ ወይም ቀበሌ መቆጣጠር አልቻሉም፡፡

የዐሥራ ስምንት ዓመት ውጤታቸው ይህ ከሆነ በስንት ዓመት አገርን በጦርነት ተቆጣጥረው እነዚህ ኃይሎች መንግሥት ሊሆኑ እንደሚችሉ ፈጣሪ ይወቅ፡፡ ይልቁንም እነዚህ ኃይሎች ውጤት የማያመጡበትን የትጥቅ ትግል ስልት በየመድረኩ በማቀንቀንና የሕዝቡን ትኩረት በመበተን ሰላማዊ ትግሉ እንዳይጠናከር ምክንያትና እንቅፋት ሆነዋል፡፡ ዛሬ አገራችን የምትገኝበት ሁኔታ ከውጫዊም ሆነ ከውስጣዊ ይዘቱ አንጻር ላለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ከነበረችበት የተለየ አይደለምና ወደፊትም የትጥቅ ትግል አቀንቃኞች በሰላማዊ ትግሉ ሊገኝ የሚችለውን ውጤት የበለጠ እንዲራዘም ከማድረግ አልፈው ሌላ የተለየ በጎ ውጤት ያመጣሉ ብሎ መገመት ምክንያታዊ አስተሳሰብ ሊሆን አይችልም፡፡

ከሁሉም በላይ የሚገርመውና የሚደንቀው በትጥቅ ትግል እናምናለን የሚሉ ሰዎች ሰላማዊ ትግልን የፈሪዎችና አገርን የማይወዱ ሰዎች ተግባር አድርገው ለማየት የሚያደርጉት ሙከራ ነው፡፡ በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ሰላማዊ ትግልን እንደ አማራጭ የሚያይ የፖለቲካ

ድርጅት ወይም ሰው ፈሪ፣ አድር ባይ፣ አገሩን የማይወድና በሥልጣን ላይ ያለውን ሥርዓት ለመርዳት ሲል የባንዳነት ተግባር የሚፈፅም ደካማ ድርጅት ወይም ሰው ተደርጐ ይወገዛል፡፡ በአሁኑ ወቅት አሜሪካን አገር ተቀምጠው በአምስት መቶ ዶላር መዋጮ የኢትዮጵያዊ አርበኝነት ማዕረግና ሰርቲፊኬት በመሸጥ ላይ የሚገኙት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ትናንት የቅንጅት አመራር በነበሩበት ወቅት አንድ የደህንነት መኪና በተከተላቸው ቁጥር ዘለው ኤምባሲ ውስጥ ይገቡ እንዳልነበረና ሚያዚያ 30 ቀን 97 ዓ.ም ቅንጅት በመስቀል አደባባይ ባካሄደው ታሪካዊ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ መገኘት እንኳ ፈርተው ተደብቀው እንዳልነበር ረስተውት ዛሬ ከማንም በላይ ሰላማዊ ትግል ማካሄድን የፈሪዎችና የከኃዲዎች ተግባር አድርገው የሚያወግዙ ሰው ሆነዋል፡፡

እነዚህ የወቅቱን የአገራችንን ፖለቲካዊ እውነታ በአግባቡ መመዘን የተሳናቸው ሰዎች የትጥቅ ትግልን ከኂላ ሆኖ የድሀውን ገበሬ ልጅ በውክልና እያዋጉ ከማካሄድ በላይ ሰላማዊ ትግሉን ከፊት ለፊት ሆኖ መምራት ምን ያህል ግንባር ቀደም ዋጋ እንደሚያስከፍልና የጀግንነት ተግባር እንደሆነ፤ ለገዥው ፓርቲ ህልውና ተጠናክሮ መቀጠል የበለጠ የሚጠቅመውም ተቃዋሚ ኃይሎችን በሰላማዊ ትግል ሳይሆን ልምድ ባካበተበት የትጥቅ ትግል መፋለም መሆኑን፣ በአጠቃላይም በዘመኑ አስተሳሰብ አገር መውደድ ማለት አገሪቱን በጦርነት ቋያ አቀጣጥሎ በገበሬው ልጆች አስከሬን ላይ ተረማምዶ ቤተ-መንግሥት መግባት ሳይሆን ራስን በሰላማዊ ትግሉ ግንባር ቀደም ተሰላፊ በማድረግ በውጤቱ ራስን ሳይሆን መጭውን ትውልድ ተጠቃሚ ማድረግ መሆኑን አለመገንዘባቸው ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ምን ያህል በእጅጉ ወደ ኂላ እንደቀሩ የሚያሳይ ነው፡፡

እስካሁንም በአለፈው የዐሥራ ስምንት ዓመት የትግል ሂደት በተግባር እንዳየነው የመታሰርም ሆነ የመሞት ዕጣ-ፈንታ የደረሰባቸው አገር ውስጥ በሰላማዊ ትግሉ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ መሪ የሆኑ ሰዎች እንጂ ባህር ማዶ ሆነው ስለ ትጥቅ ትግል በሬዲዮና በኢንተርኔት ሲያቀነቅኑ የሚውሉት የስደት ፖለቲካ መሪዎች አይደሉም፡፡ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በሰላማዊ ትግሉ ሂደት ስለሚታሰሩና ስለሚገደሉ ሰዎች መግለጫ እያወጡ ሰላማዊ ትግሉ እንደማይሠራ አድርጐ ለማሳየት ከሚያደርጉት ከንቱ ሙከራ ያለፈ አንድም የትጥቅ ትግል መሪ ነኝ የሚል ተዋቂ የድርጅት መሪ ሕይወቱንም ሆነ አካሉን በትግሉ ሂደት አጣ ሲባል ተሰምቶ አያውቅም፡፡ ስለዚህ የትጥቅ ትግል አገርንና ሕዝብን አይጠቅምም የሚል የከረረ አቋም ያለን ሰዎች እነዚህ የትጥቅ ትግል ምርጫችን ነው የሚሉ ኃይሎች እምነታቸውን በተግባር ሲፈጽሙት ብናይ ኖሮ ቢያንስ ስልታቸው የእኛ እምነት ባይሆንም ለያዙት አቋም ተገቢ

ኢዮፕ ኢዮፕ ኢዮፕ

አክብሮት በነበረን ነበር፡፡ ነገር ግን እነዚህ ኃይሎች ራሳቸው ያዋጣል ብለው ያመኑበትን አቋም ሌሎች እየሞቱ እንዲፈጽሙት ባህር ማዶ ሆነው ከመመኘትና ትግሉን በርቀት ለመምራት ከመሞከር አልፈው በተግባር ራሳቸው ሊፈጽሙት ያልወሰኑ በመሆኑ ለያዙት አቋም የእኛ አክብሮት የሚገባቸው ኃይሎች አይደሉም፡፡ እነዚህ ኃይሎች እነሱ በሞቀ ቤታቸውና ሰላማዊ በሆነ አገር ውስጥ እየኖሩ የደሃውን ልጅ ውድ ሕይወት በዶላር መግዛት የሚፈልጉ በመሆናቸው ድርጊታቸው ከፖለቲካ አንጻር ስህተት ከመሆኑም በላይ ሰብዓዊነት የሚጐለው ድርጊት ነው፡፡

በርግጥ ከሰላማዊ ትግል መጠናከር አንፃር አቋማቸውን በዋናነት ፈትሸው መለወጥ ያለባቸው አላማችንን በትጥቅ ትግል እናራምዳለን የሚሉት የፖለቲካ ኃይሎች ቢሆኑም አገር ውስጥ የምንገኘውና ዓላማችንን በሰላማዊ ትግል እናራምዳለን የምንለው ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በዚህ ረገድ መታረም የሚገባው ድክመት በዙሪያችን የለም ማለት አይደለም፡፡ ኢህአዴግም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአፋችን የምንናገረውን ያህል ስለ ሰላማዊ ትግል በቂ ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ቢኖረን ኖሮ ምርጫ 97 በዚያ አስቀያሚ ሁኔታ ሊጠናቀቅ ባልቻለ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ምርጫ 97 ላይ ቅንጅት ሕዝብ የሰጠውን ውጤት በአግባቡ መጠቀም ተስኖት ራሱን ወደሚያዳክምና ወደሚያፈርስ እንቅስቃሴ ውስጥ መግባቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ የምርጫው ውጤት ያመጣውን ለውጥ በአግባቡ ማስተናገድ ተስኖት ሲደነባበርና ወደ አፈና ርምጃ ሲገባ የታየው ያለምክንያት ሳይሆን ሁለቱም ወገኖች ሰላማዊ ትግልን በአግባቡ ለማካሄድና ይዞት የሚመጣውን ውጤት በጸጋ ለመቀበል የሚያስችል በቂ ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት ስላልነበራቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የወደፊቱ የአገራችን ዕጣ-ፈንታ ሊወሰን የሚችለውም ሆነ የሚገባው በሰላማዊ ትግል እንጂ በአመፅና በትጥቅ ትግል አይደለም፡፡ ትጥቅ ትግል የራሱ ታሪካዊ ሂደት እንዳረጋገጠውም ሆነ ከወቅቱ የአገራችንና የአካባቢያችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በአሁኑ ወቅት በቀላሉ ሊካሄድ የማይችል ብቻ ሳይሆን አገርንና ሕዝብን በዘላቂነት የሚጠቅም ውጤት ሊያመጣ የማይችል ስልት ነው፡፡

### *2.3 ሕዝብና የፖለቲካ ትግሉ*

ከዚህ በላይ ባዩናቸው ሁለት ርእሶች በአገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ገዥው ፓርቲና ተቃዋሚዎች ምን ያህል የችግሩ አካል እንደሆኑና ወደፊትም የመፍትሄው አካል ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማየት ሞክረናል፡፡ ነገር ግን የእነዚህን በመንግሥትነትና በተቃዋሚነት የሚገኙ

የፖለቲካ ኃይሎች ጥንካሬና ድክመት ብቻ ተችተን የእነሱ መፍለቂያ የሆነውን “ሕዝብ” ጥንካሬና ድክመት ሳንተች ብንቀር ጉዳዩ “ውሃ ቅዳ - ውሃ መልስ” ከመሆን ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም ገዥውም ፓርቲ ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከሕዝቡ የመነጩና በባህሪያቸውም የሕዝቡ አጠቃላይ ሁኔታ መገለጫዎች በመሆናቸው ዞሮ ዞሮ በፓርቲዎች ላይ የሚታየው ችግር በሕዝቡም ውስጥ ያለ ችግር መሆኑ ተፈጥሯዊ ነው፡፡

ሕዝቡ ፍላጐቱንና ጥቅሙን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ ለፍላጐቱና ለጥቅሙ የሚሠሩትን የፖለቲካ ኃይሎች በአግባቡ መመዘንና በተግባርም ደግፎ ማጠናከር የሚችል የበቃ ሕዝብ መሆን እስካልቻለ ድረስ በሆነ ተአምር ከሱ በተለየ የበቁ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማግኘት አይችልም፡፡ በተለምዶም “አንድ ሕዝብ የሚገባውን ሥርዓት ያገኛል” የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ አገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ያልቻለች ድሀና ኋላቀር አገር ሆና ለመገኘትዋ ሁልጊዜ ተጠያቂ የምናደርገው የፖለቲካ ኃይሎችን በተለይም ሥልጣን ላይ የሚገኝ መንግሥትን ነው፡፡ በአገራችን መንግሥት፣ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ታሪክ ጸሐፊዎችና ጋዜጠኞች ሳይማከሩ ተስማምተው የሚገኙበት አንድ የጋራ ባህሪም ሕዝብን ለመተቸት አለመድፈር ሆኖ ይታያል፡፡

ትናንትም ሆነ ዛሬ ለአገሪቱ ችግሮች ሕዝብ መንግሥትን፣ ተቃዋሚዎች መንግሥትን፣ መንግሥት ተቃዋሚዎችን፣ ታሪክ ጸሐፊዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ኃይሎችን ሲከሱና ተጠያቂ ሲያደርጉ የኖሩ ቢሆንም የችግሩ ዋና ምንጭ የሆነውን “ሕዝብ” ደፍሮ የሚተችና ተጠያቂ የሚያደርግ ጸሐፊም ሆነ ፖለቲከኛ እምብዛም ባለመኖሩ ችግሩ ከምንጩ መድረቅ አልቻለም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው የፖለቲካ ሰዎች በንግግራቸው፣ ጸሐፊዎች በጽሁፋቸው አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ሕዝብን በማድነቅና ማወደስ ሆኖ ይታያል፡፡ ሁልጊዜም ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሲነገርና ሲጻፍ - ታታሪ፣ ታጋሽ፣ አስተዋይ፣ ዐዋቂ፣ አርቆ አሳቢ፣ ጀግና፣ ኩሩ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ሰላም ወዳድ የሚሉትንና የመሳሰሉትን ቅጽሎች (Adjectives) ማዳመጥ የተለመደ ነው፡፡ ይህ መሆኑ በራሱ በጐ ነው፡፡ ነገር ግን ደማችን ድረስ ዘልቆ እስከሚዋሐደን ድረስ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ሁሉ ሙገሳዎች እየሰማን አንድም ጊዜ “ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ያህል የላቀና የበቃ ሕዝብ ከሆነ በታሪኩ ለአንድ ጊዜ እንኳ ለምን የሚገባውን መንግሥታዊ ሥርዓት መፍጠር አልቻለም?” ብለን ለመጠዬቅ ደፍረን አናውቅም፡፡

ምክንያቱም ከልጅነታችን ጀምሮ በወላጆቻችን፣ በፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች፣ በታሪክ ጸሐፊዎች፣ በገጣሚዎች፣ በዘፋኞችና በአጠቃላይም በትምህርት ቤትና በመገናኛ ብዙኃን እስከ ዛሬ ድረስ ሲነገረን የኖረው ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት ስለሆነ በማንኛውም ጉዳይ ሕዝብን

ደፍሮ መተቸት የማይቻል ብቻ ሳይሆን የማይታሰብም እየሆነብን መጥቷል፡፡ በተለይም “ታሪክ ሠሪው ሰፊው ሕዝብ ነው!” የሚለውን ጯሂ መፈክር አቀንቃኝ የሆነው የግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን ከገባ በኋላ ሕዝብን በደፈናው የማሞካሸት ነባር ባህላችን የበለጠ እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ ዜጐችና የታሪክ ጸሐፊዎች ብቻ ሳይሆኑ በሕዝብ ላይ የአፈናና የጭፍጨፋ ድርጊት ለመፈጸም ወደ ኋላ የማይሉ በአገራችን የተፈራረቁ አምባገነን የአገር መሪዎች ሳይቀሩ አንዳንድ ጊዜ ሳያስቡት ሲባርቅባቸው ካልሆነ በስተቀር የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን እንጂ የሕዝብን ድክመትና ስህተት ለመተቸት ሲደፍሩ ታይተው አያውቁም፡፡

በርግጥ አንዳንድ የቀድሞ የአገሪቱ መሪዎች ከሌሎች መንግሥታት ጋር በሚያደርጓቸው የደብዳቤ ልውውጦች ሕዝባቸውን አምርረው የሚወቅሱባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ታዋቂው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ከ7 ዓመታት በፊት በአንድ የውይይት መድረክ ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ እንደገለጹት አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውንና ሕዝቡን “እውር”፣ “ደንቆሮ፣ “አህያ” ብለው እስከመውቀስ የደረሱበት ጊዜ ነበር፡፡ አፄ ቴዎድሮስ የሕይወታቸው ፍጻሜ በተቃረበበት ወቅትም ለጄኔራል ናፒየር በጻፉት ኑዛዜ መሰል ደብዳቤ “ያገሬ ሕዝብ ገብር፣ ስራት ግባ ብዬ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ፡፡ እናንተ ግን በሥርዓት በተገዛ ሰው አሸነፋችሁኝ” በማለት የሽንፈታቸውን ምክንያት እንደገለጹ ፕሮፌሰር ባህሩ አሥነብበውናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ቅሬታዎችና ቁጭቶች በመሪዎቻችን ኩሪያ የነበሩ ቢሆንም ሕዝብን በይፋ መውቀስና መተቸት ግን የተለመደ አልነበረም፡፡ እንዲያውም በፖለቲካ መሪዎች ዘንድ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት ማውራት የፖለቲካ ሊቅነት ተደርጐ ስለሚታሰብ ብዙውን ጊዜ የአገራችን ፖለቲከኞች የአፍ ማሟሻ ሕዝብን በደፈናው ማድነቅና ማመስገን ሆኖ ይታያል፡፡ ለዚህም ነበር በመግቢያዬ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ነጋድራስ ገብረ-ሕይወት ባይከዳኝ የተባለው ልዩና ደፋር ጸሐፊ የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ ለንባብ ያበቃው ጽሑፍ በእጅጉ ቀልቤን የሳበኝና ያስደመመኝ፡፡

ገብረ-ሕይወት ከኛ ዘመን ሁኔታ በእጅጉ ወደኋላ በራቀ ወግ አጥባቂ ኅብረተሰብ ውስጥ እየኖረ ለመጻፍ የደፈረውን ሃቅ እኛ ዛሬ ስለ ዴሞክራሲና የሐሳብ ነፃነት በየቀኑ ሳንሰማ የማንውል የአሁኑ ዘመን ፖለቲከኞችና ጸሐፊዎች ግን በሕዝባችን ውስጥ የምናየውን ድክመት በድፍረት መናገርና መጻፍ አልቻልንም፡፡ በአንድ በኩል የሚያስገርመው በአሁኑ የዴሞክራሲ ዘመን እንደ ገብረ-ሕይወት ዓይነት ደፋር ጸሐፊ አለማግኘታችን ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን የበለጠ የሚያስገርመው የዛሬ አንድ መቶ ዓመት በእነ ገብረ-ሕይወት ዘመን በሕዝባችን ውስጥ የነበረው ድክመት ብዙም ሳይቀነስና ሳይጨመር ዛሬም ያለ መሆኑ ነው፡፡ ገብረ-ሕይወት በዚያን ዘመን

ባሥነበበን ጽሑፍ በአፄ ምኒሊክ አስተዳደር ላይ ምክንያታዊና ደፋር የሆነ ትችት ከማቅረቡ በተጨማሪ በየጽሑፉ ጣልቃ ሕዝቡንም በድፍረት ሲተች ታይቷል፡፡

በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥትን በብዕር ደፍሮ በመተቸት ረገድ አገራችን እንደነ በዓሉ ግርማ ያሉ በርካታ ጀግኖችን ያፈራችና አሁንም ከበቂ በላይ ያሉዋት ብትሆንም ሕዝብን ደፍሮ በመተቸት ረገድ ግን ቢያንስ በአለፉት አንድ መቶ ዓመታት ከገብረ ሕይወት የሚስተካከል ጸሐፊ በአገራችን ታይቷል ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ ለአንባብያን ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ገብረ-ሕይወት ከመቶ ዓመት በፊት ስለ ሕዝቡ የሰጣቸውን አንዳንድ አስተያየቶች ቀነጫጭበን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡፡ ገብረ-ሕይወት በጽሑፉ ላይ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኘውን ሕዝብ አመለካከት ከተቸ በኋላ በወቅቱ የመንግሥት መቀመጫ አካባቢ የነበረውን ሕዝብ በተመለከተ በአቀረበው ትችት እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

*"እንግዲህ ከጸሐፊው ልብ ውስጥ ፍርሀት ተነሣ - የሸዋዎችን አሳብ ሊመረምር ነውና፡፡ ዘመናይ ሁሉ ሊያመሰግኑት እንጂ ሊወቅሱት አይወድም፡፡ ስለዚህ ብዙ የሸዋ ሰው ሳይቆጣ አይቀርም፡፡ ነገር ግን ሰውን ፈርቶ እውነቱን የሚሸሽግ ሰው እንደ ወንድ ይቆጠራልን፤ መንግሥቱንም የሚወድ ሰው ያ-ቅዱስ ቅዱስ የሚለው አይደለም ጥፋቱን ይገልጽለታል እንጂ፡፡"*

ከዚህ ከአምስት መስመር ባልበለጠ የገብረ-ሕይወት ባይከዳኝ አባባል ብዙ ልንማር እንችላለን፡፡ "እንግዲህ ከጸሐፊው ልብ ውስጥ ፍርሀት ተነሣ..." በሚለው አባባሉ በወቅቱ የሕዝብ አስተሳሰብን መተቸት እንዴት የሚያስፈራ ከባድ ነገር እንደነበረ ያሳየናል፡፡ "ዘመናይ ሁሉ ሊያመሰግኑት እንጂ ሊወቅሱት አይወድም" በማለት ደግሞ በዚያን ወቅት ሕዝቡ መመስገንን እንጂ መወቀስን እንደማይወድ ያሳየናል፡፡ "ሰውን ፈርቶ እውነቱን የሚሸሽግ ሰው እንደ ወንድ ይቆጠራልን?" በማለትም ጸሐፊዎች ድፍረት እንደሚያስፈልጋቸው ይነግረናል፡፡ በተጨማሪም "መንግሥቱንም የሚወድ ሰው ያ-ቅዱስ ቅዱስ የሚለው አይደለም ጥፋቱን የሚገልጽለት እንጂ" በማለት ደግሞ መተቸት ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለመንግሥትም የሚጠቅም መሆኑን ያስረዳናል፡፡

ገብረ-ሕይወት በሌላ የጽሁፉ ክፍል ደግሞ የሚከተለውን ይላል___፤

*"መብራት ሳይነድ አያበራም፡፡ ስለዚህ የዓለምን ታሪክ ብንመለከት አዲስ ሥርዓት የሚያወጣ ንጉሥ ሁሉ - በሕይወት ሳለ መከራ አይለየውም፡፡ ሕዝቡ እንደ አውራ ደመኛው ያየዋልና፡፡ ደግነቱም የሚታወቅ ብዙ ዓመታት ከሞተ በኋላ ነው፡፡*

*የአዳምን ዘር ባህሪ በጠቅላላው ብንመለከት አዲስን ነገር የሚወድ ወገን አናገኝም፡፡ ካባቶቹ የቆየውን ካልሆነ በቀር ይልቁንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያባቶቹን ልማድ ሲለውጡበት ዝም ብሎ ባልተቀበለም - ጢስ እንደገባበት ንብ በተሸበረ - በተናወጠም ነበር እንጂ፡፡ ወዮለት ለዚያው ንጉሥ የዛሬውን ከደማችን ጋር የተዋኀደውን የድንቁርና ሥርዓታችንን ሊለውጥ ለሚነሣው፡፡ ለኋላ ስም ያገኛል እንጂ በሥጋው አይጠቀምም፡፡ ... አእምሮ የሌለው ሕዝብና ልጅ ጠቃሚውን አይወድም፡፡ ... የድሮውም ያሁኑም ኑሮዋችን እጅግ ያሳዝናል፡፡ በመላው ዓለም ላይ ሰላም ሲሰፋ - አእምሮ ስትበራ እኛ በጨለማ እንኖራለን፡፡ እርስ በርሳችን መጠራጠርንም አልተውንም፡፡ ሕዝቦችም ሁሉ እርስበርሳቸው በአንድነት ሁነው ሲደክሙ እኛ አንድ ዘርና ወንድማማች መሆናችን ገና አልተገለፀልንም፡፡ እርስ በርሳችን መፋጀትም እስከዛሬ ድረስ ጀግንነት ይመስለናል፡፡ ... የሰውም ክብረቱ ሥራና አእምሮ መሆኑን ገና አላወቅንም፡፡... ስለዚህ ወዮለት በድንቁርናው ለሚቀመጥ ሕዝብ ውሎ አድሮ ይደመሰሳልና፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ከፈረንጆች ጋር ከተዋወቅን ብዙ ጊዜ አልፏል፡፡ ነገር ግን እስካሁን ድረስ አንዳች አልተማርንም፡፡ ስለዚህም መንግሥታችን እንዳትጠፋ ያሰጋል፡፡ የኢትዮጵያችን ሰው ግን ይህንን ቢነግሩት እንዲህ ሲል ይመልሳል - እግዚአብሔር አገራችንን አሳልፎ ለባዕድ አይሰጣትም፡፡ የመንግሥታችንም መኳንንት ይህንን እያሉ በስንፍና ይኖራሉ፡፡ እውነትም ቸሩ እግዚአብሔር የመንግሥታችን አርነት እንዳትጠፋ ብዙ ጊዜ ከለከለ፡፡ እኛ ግን እስከ ዛሬ ለቸርነቱ የተገባ ሕዝብ መሆናችንን አላሳየንም፡፡ በዚህ ምክንያት ውሎ አድሮ እንዳይፈረድብን እንጠንቀቅ-እንትጋም፡፡...”*

ገብረ-ሕይወት ባይከዳኝ ከዛሬ 100 ዓመት በፊት ጽፎ ባሥነበበው በዚህ ጽሁፉ ሰውዬው ሕዝብንም ሆነ መንግሥትን ለመተቸት ምን ያህል ደፋር እንደነበርና ስለወደፊቱ የአገሪቱ ዕጣ-ፈንታ ምክንያታዊ ትንበያ የመስጠት አቅም ያለው ጸሐፊ እንደነበር እናያለን፡፡ ከሰማኒያ ዓመት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ገብረ-ሕይወት ባይከዳኝ ዛሬ የመቃብር አፈሩን አራግፎ ከሞት ቢነሳ በሁለት ነገሮች የሚገረምና የሚከፋ ይመስለኛል፡፡ በመጀመሪያ የዛሬው ዘመን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ከሱ ዘመን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ በአስተሳሰብ ብዙም ያልተለዬ በመሆኑ፤ በመቀጠልና ከዚያ በበለጠ ደግሞ የሱ ዓይነት ደፋር ብዕረኛ በዚች አገር ዳግም ባለመፈጠሩ፡፡

ከዚህ የገብረ-ሕይወት ባይከዳኝ ጽሑፍ የምንረዳው ገብረ-ሕይወት ለአንድ አዲስ የሥርዓት ግንባታ የኅብረተሰብ የአስተሳሰብ ለውጥ ምን ያህል አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ መሆኑን ተገንዝቦ

እንደነበረ ነው፡፡ ነገር ግን በገብረ-ሕይወት ዘመን የነበሩትም ሆኑ ለአንድ ሙሉ ዘመን ከዚያ በኋላ በሃገራችን የተፈራረቁት የፖለቲካ ኃይሎችና ጸሐፊዎች የገብረ ሕይወትን ፈለግ ሊከተሉ ባለመቻላቸው የችግሮቻችን ዋና መፍለቂያ ምንጭ የሆነው የሕዝብ አስተሳሰብ መሠረታዊ ለውጥ ሳያመጣ ባለበት ቀጥሏል፡፡ ዛሬም ዓለም በሁለንተናዊ የዕድገት መመዘኛ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በ21ኛው ክፍለ-ዘመን እንደ ኅብረተሰብም ሆነ እንደ ዜጋ በየአንዳንዳችን ውስጥ ያለውን የአስተሳሰብ ደዌ በድፍረት መርምረን ራሳችንን መለወጥ ሲገባን በአገራችን እየደረሰ ለሚገኘው መከራና ሰቆቃ በሙሉ ከራሳችን አብራክ የተፈጠሩና በጓዳችን ውስጥ ያደጉ ገዥዎችን ብቸኛ ተጠያቂዎች አድርገን ስንወቅስ እንኖራለን፡፡

ኢትዮጵያውያን ይህንን እውነት ሸሽተን የትም መድረስ አንችልም፡፡ በየጊዜው በሥልጣን ላይ የሚፈራረቁ ገዥዎቻችን አምባገነንና ጨቋኝ ሆነው የሚታዩት አንዳንድ የዋሆች እንደምናስበው ፈጣሪ እኛን ለመቅጣት ብሎ በመንበሩ ላይ ስላስቀመጣቸው ነው ማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌላው ዓለም ሕዝብ ምን የተለየ ኃጢአት ፈጽሞ ነው ፈጣሪ ሁልጊዜ አምባገነኖችን እየላከ ሲቀጣው የሚኖረው? እንዲያው ተጠያቂነቱን ያለ አግባብ ወደ ፈጣሪ እንወርውረው ካላልን በስተቀር አምባገነኖችንና ጨቋኞችን የፈጠርናቸውም ሆነ እንዲቀጡን የፈቀድንላቸው እንደ ሕዝብ እኛው ራሳችን ነን፡፡

እስካሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፍና በኖረው ማኅበራዊና ቤተሰባዊ የአኗኗር ዘይቤ ማለትም በባልና በሚስት፣ በአባትና በልጅ፣ በአስተማሪና በተማሪ፣ በአሠሪና ሠራተኛ፣ በታላቅና በታናሽ፣ በተማረና ባልተማረ፣ በሀብታምና በድሀ መካከል የነበረው ግንኙነታችን አምባገነኖችን እንጂ ዴሞክራቶችን ሊያፈቅል የሚችል አልነበረም፡፡ አምባገነን ለመሆን የበቁት የፖለቲካ መሪዎቻችን በሙሉ፣ ያደጉበት ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ነው መገለጫቸው የሆነውን ባህሪ ሁሉ ቀርፆ የሰጣቸው፡፡ እንደ እነሱ በተመሳሳይ ቤተሰባዊና ማኅበራዊ ሁኔታ ያደግን ሰዎች ሁሉ ተራው ደርሶን ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የመውጣት ዕድል ቢያጋጥመን ተቀርፀን ካደግንበት ማኅበረሰብ በተለየ ዴሞክራት ልንሆን አንችልም፡፡ ስለዚህ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንጻር ተቀርፀን በምናድግበት ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ የአስተሳሰብ ችግር በአግባቡ መተንተን፣ መገምገም፣ መተቸትና ብሎም ማስወገድ እስካልቻልን ድረስ ምን ጊዜም ከእኛ መካከል የሚፈጠረው የፖለቲካ ሥርዓት የእኛው ማንነት ነጸብራቅና መገለጫ እየሆነ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡ በአገራችን መቻቻል የማጣት ችግር በፖለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትና የስፖርት ተቋማትን ጨምሮ በብዙ ቦታዎች ሲከሰት የምናየው ያለምክንያት ሳይሆን በዚህ ረገድ ያለብን ችግር ጥልቅና የራሱ ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት ያለው በመሆኑ ነው፡፡

ዛሬ በኢህአዴግ መሪዎች ዙሪያ የምናየውን አምባገነናዊ ባህሪ በተለያዩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና በየአካባቢያችን ባሉ የቀበሌ ሹማምንቶች ዙሪያ በተመሳሳይ ሁኔታ እያዬን ያለነው ያለምክንያት ሳይሆን ሁላችንም የተቀዳነው ከአንድ ምንጭ በመሆኑ ነው፡፡ የሁሉም መሠረት በሆነው በቤተሰብ ውስጥ እናቱ በአባቱ ስትደበደብና ስትጨቆን እያዬ ያደገ ልጅ፣ የገዛ አባቱ በሰው መሃል እንዳይናገር ሲከለክለውና በዱላ ሲቀጣው ያደገ ልጅ፣ የድርሻ ዳቦውን በታላቅ ወንድሙ እየተቀማና እየተኮረኮመ ያደገ ልጅ፣ ተልኮ ከቤቱ በወጣ ቁጥር በሠፈር ጉረምሳ በካልቾና በጥፊ እየተመታ ያደገ ልጅ፣ በትምህርት ቤትም በገዛ አስተማሪው "ደደብ" ተብሎ እየተሰደበና በአለንጋ እየተገረፈ ያደገ ልጅ፣ ከሁሉም በላይ በአገሩ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያ "ገዳይ እወዳለሁ" የሚል ዘፈን እያዳመጠ ያደገ ልጅ - የሚያስገርመው የአገር መሪ ለመሆን ሲበቃ አምባገነን መሆኑ ሳይሆን ከመጀመሪያው ድፍረት ኖሮት የአገር መሪ መሆን እችላለሁ ብሎ ማሰብ መቻሉ ነው፡፡

ዛሬ ዛሬ በአገራችን የከተሞች አካባቢ በተወሰነ ደረጃ በጎ የልጅ አስተዳደግ መታየት የጀመረ ቢሆንም ያለማጋነን ከ99 በመቶ የማናንስ የአገሪቱ ጉልማሶች ከላይ ለማሳየት በተሞከረው ቤተሰባዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ነው ያደግነው፡፡ በዚህም ምክንያት ነው - በአሁኑ ወቅት በየአንዳንዱ ዕለት ስለ ዴሞክራሲና የመቻቻል ፖለቲካ እያነበብንና እያዳመጥን፣ አንዳንዶቻችንም በአሜሪካና በአውሮፓ ታላላቅ ዩኒቨርስቲዎች ተምረን ለመመረቅ በቅተን፣ አንዳንዶቻችንም ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው በእነዚያ የበለፀጉ አገሮች ለሃያና ለሠላሳ ዓመታት የመኖር ዕድል ካገኘንም በኋላ ያ - በልጅነት አስተዳደጋችን የደነደነው አምባገነናዊ ባህርያችን አለቀን ብሎ ስንቸገር የሚታየው፡፡ በአሁኑ ወቅት በየመሥሪያ ቤቱ ጉዳይ ለማስፈጸም ስንሄድ እንደምናየው ከጥበቃና ከመዝገብ ቤት ሠራተኛው ጀምሮ እስከ ከፍተኛው የቢሮ ኃላፊ ድረስ ደመወዝ የሚከፈለበትን ሥራ በአግባቡ ከመሥራት ይልቅ ካላጉበደዳችሁልኝና ደጅ ካልጠናችሁኝ በማለት ያለአግባብ ሲያጉላላን የምናየው ሁሉም በቢሮክራሲው ውስጥ ተቀጣሪ የሆነው ሠራተኛ የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ስለሆነ ሳይሆን ሁሉም ከአንድ የደፈረሰ ምንጭ የተቀዱ ዜጎች በመሆናቸው ነው፡፡

ስለዚህ ገዥዎቻችን ከተለዬ ዓለም መጥተው እንደተጫኑብን ልዩ ፍጡሮች በመቁጠር እነሱን ብቻ ስናማርር ከመኖር ይልቅ ራሳችንንም እንደ ኅብረተሰብም ሆነ እንደ ዜጋ የአገራችን ችግሮች አካል አድርገን ማየት መጀመር አለብን፡፡ ራሳችንን የችግሩ አካል አድርገን ማየት እስካልጀመርን ድረስ የመፍትሄው አካል መሆንና ችግሩን ከምንጩ ማድረቅ አንችልም፡፡ ራሳችንን ማታለል እስካልፈለግን ድረስ ታላቅና ዐዋቂ እየተባለ ሁልጊዜ የሚሞገስ እንደ

ኢትዮጵያዊ ያለ ሕዝብ በሌላ የተለየ ምክንያትና ተአምር አምባገነናዊ ሥርዓት ሲፈራረቅበት የሚኖር ሕዝብ ሊሆን አይችልም፡፡ በአንድ የበቃ ኅብረተሰብ ባለበት አገር በሆነ ታሪካዊ አጋጣሚ አምባገነኖች ወደ ሥልጣን ሊወጡ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊፈጠር የሚችል ቢሆንም እንኳ ታላቅና ዐዋቂ በሚባል ሕዝብ ጫንቃ ላይ አምባገነኖች ለረዥም ጊዜ ተፈናጠው የሚቆዩበት ዕድል አይኖርም፡፡ ዕድሉን አግኝተው ወደ ሥልጣን ቢፈናጠጡም የበቃ ኅብረተሰብ ባለበት አገር የነሱን ጠመንጃና አለንጋ ይዞ ሕዝብን የሚገልና የሚቀጣ ተከታይና ጋሻ ጃግሬ ሊያገኙ አይችሉም፡፡

በደርግ ዘመን የኮሎኔል መንግሥቱ ዓላማ አስፈጻሚ በመሆኑ አሰቃቂ ጭፍጨፋ ሲፈጽሙ የነበሩ በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠሩ አብዮት ጠባቂዎችና የፖለቲካ ካድሬዎች ዛሬም በኢህአዴግ ዙሪያ ተሰልፈው ኅብረተሰቡን በሙስናና በቢሮክራሲ ውጣ ውረድ ከማሰቃየት ጀምሮ ተቃዋሚዎችን በማፈንና ምርጫን በማጭበርበር ተግባር ላይ የሚሰማሩት በብዙ መቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ካድሬዎች ከየትም የመጡ ሳይሆኑ ከኛው ማጀትና ጓዳ ተፈጥረው ያደጉ ወንድምና እህቶቻችን ናቸው፡፡ ተቃዋሚዎች ነገ ለሥልጣን ብንበቃ የበቃ ዜጋን እንደ ሸቀጥ ከውጭ ሸምተን ልናስገባ ስለማንችል እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ከችግሩ ጋር አብረን መቀጠላችን አይቀርም፡፡ ከዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳት ኢትዮጵያውያን ራሳችንን መጠዬቅና መገምገም ይኖርብናል፡፡ ጸሐፊዎችና የፖለቲካ ሰዎች በሕዝብ ውስጥ የሚታዩ የአስተሳሰብ ድክመቶችን ደፍረው ለመተቸት ሲሞክሩ የበለጠ ሊደፋፈሩ ይገባል እንጂ ሕዝብን እንደሚንቁና እንደሚሳደቡ ተደርጐ መቆጠር የለበትም፡፡

ኅብረተሰብ ሊሳሳት አይችልም እየተባለ በፖለቲከኞች ተደጋግሞ ሲነገር የምናዳምጠው አባባልም እንዲሁ የተለመደ የፖለቲካ አባባል እንጂ በአሳማኝ ምክንያት ሊደገፍ የሚችል እውነት አይደለም፡፡ ኅብረተሰብ ጤናማ ባልሆኑ መሪዎች ሲመራና በስሜታዊ ሁኔታዎች ሲዋጥ መሳሳት ብቻ ሳይሆን ከሰውነት ባህሪ ሊወጣ እንደሚችል ጀርመንን፣ ደቡብ አፍሪካንና ሩዋንዳን በመሰሉ አገሮች በገሃድ ታይቷል፡፡ በርግጥ ሕዝቡን ለመገምገም ሲሞከር - የኢትዮጵያ ሕዝብ በውስጡ የአንድነቱና የርስ በርስ ትስስሩ መገለጫ የሆኑ በርካታ የጋራ ጉዳዮች የመኖራቸውን ያህል በዚያው መጠን በባህል፣ በቋንቋ፣ በእምነት፣ በአስተሳሰብ ደረጃና በኢኮኖሚ አቅም በውስጡ በርካታ ልዩነቶችን ያካተተ (Heterogeneous) ሕዝብ በመሆኑ ምክንያት ከፖለቲካ አኳያ የአጠቃላዩን ሕዝብ ነባራዊ ሁኔታ ወጥ በሆነ መንገድ ሊያሳይ የሚችል ግምገማ ማካሄድ ያስቸግራል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሊሰመርበት የሚገባው ሌላው ቁምነገር ከፖለቲካ አስተሳሰብ አንጻር ኅብረተሰብ ሊተች ይገባዋል ሲባል ሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ በፖለቲካ ረገድ የበቃ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል ተብሎ ይጠበቃል ማለት አይደለም፡፡ እንኳን በእኛ አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ ድሀ አርሶ አደርና ማንበብና መጻፍ የማይችል መሃይም በሆነበት አገርና በአደጉትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተዋል በሚባሉት አገሮች ውስጥም የጐላ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርገው ሕዝብ በቁጥር እጅግ ያነሰው ነው፡፡ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ በአለፈችው በአሜሪካ እንኳ በአካባቢ ምርጫዎች የሚሳተፈው ሰው ለመምረጥ ዕድሜው ከደረሰው ሕዝብ ውስጥ ከዐሥር በመቶ የማይበልጠው ብቻ ሲሆን ትልቅ ትኩረት በሚሰጠው የፕሬዝደንታዊ ምርጫ ወቅትም በአብዛኛው ተሳታፊ የሚሆነው ከመራጩ ሕዝብ በአማካይ ከኀምሳ አምስት በመቶ የማይበልጠው ሕዝብ ነው፡፡ ውስብስብ የሆነ የፖለቲካ ሁኔታን መረዳት ይቅርና በአሜሪካ የአገሩን ምክትል ፕሬዝዳንት ስም የማያውቀው ሕዝብ ቁጥር ቀላል የማይባል ነው፡፡

ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ "ኅብረተሰቡ" ወይም "ሕዝቡ" እየተባለ አንዳንድ ትችቶች ሲቀርቡ፣ ትችቱ በዋናነት የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባል የሆነውን ወይም ፓርቲዎቹን በመደገፍም ሆነ በመቃወም ቢያንስ የሐሳብ ልውውጣ የሚያደርገውን የኅብረተሰብ ክፍል የሚመለከት እንጂ ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌለውን አብዛኛውን የአገራችንን ሕዝብ የሚመለከት አይደለም፡፡ በደርግ ጊዜ ይባል እንደነበረው እኛም "ታሪክ ሠሪው ሰፊው ሕዝብ ነው" እያልን ማስመሰል ካልፈለግን በስተቀር በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፖለቲካውን ወደ በጎም ሆነ በጎ ያልሆነ አቅጣጫ በመምራት ረገድ ሚና ያለው የኅብረተሰብ ክፍል እጅግ በጣም ጥቂት በመሆኑ የዚህ ጽሑፍ ትችት የሚያተኩረውም በዚሁ ጥቂት የፖለቲካ ኅብረተሰብ ላይ መሆኑ ግንዛቤ ሊሰጥበት ይገባል፡፡ በመንደርደሪያነት ይህን ያህል ከተባለ ይህ የፖለቲካ ኅብረተሰብ በወቅቱ የፖለቲካ ትግል አኳያ ጠንካራና ደካማ ጐኑ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አንድ የረዥም ዘመን የመንግሥትነት ታሪክ ያለው ሕዝብ በብዙ ውጣ ውረዶች ተፈትኖ ያለፈና የብዙ በጎና አኩሪ ታሪኮች ባለቤት ለመሆን የበቃ ታላቅ ሕዝብ ነው፡፡ ሆኖም ከዚህ በጎ የታሪክ ገጽታው በተፃራሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ከመገንባትና ድህነትን ከማሸነፍ አንጻር ከፍተኛ ድክመት የሚታይበት ሕዝብ መሆኑን የወቅቱ የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ በገሃድ እየመሰከረ ይገኛል፡፡ አገራችን ለረዥም ጊዜ በርስ በርስ የጦርነትና የቅራኔ ሂደት ውስጥ ያለፈች፣ የተለያዩ አምባገነናዊና ጨቋኝ መንግሥታት

ሲፈራረቁባት የኖረች፣ አብዛኛውም ሕዝቧ የዘመናዊ ትምህርት ዕድል ያላገኘና በኢኮኖሚ አቅሙም መሠረታዊ ፍላጐቱን ገና ያላሟላ ሕዝብ በመሆኑ ምክንያት በአሁኑ ወቅት የምትገኝበት የማህበረ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በቀላሉ ለመገንባት አላስቻላትም።

ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ሕዝቡ ከሚገኝበት ዝቅተኛ የማህበረ-ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ አንጻር የፖለቲካ አመለካከቱም በዚያው መጠን ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነው። ወደፊትም 84% የሚሆነው የአገራችን ሕዝብ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ እርሻ (Subsistence Agriculture) ተዳዳሪና አብዛኛው ሕዝብ ማንበብና መጻፍ የማይችል ሕዝብ ሆኖ ለረዥም ጊዜ የሚቀጥል ከሆነ በአገራችን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የሚሆን መካከለኛ ገቢ ያለው (Middle Class) የፖለቲካ ማኅብረተሰብ በቀላሉና በአጭር ጊዜ ሊፈጠር አይችልም። በሌላ አባባል በየደረጃው የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትና ችግር ፈች የሆነ የትምህርት ሥርዓት በፍጥነት በአገራችን እንዲስፋፋ ማድረግ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥረታችን አዝጋሚ እንዳይሆን በማድረግ ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ይሆናል ማለት ነው።

የአንድ አገር የማህበረ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚኖረው ጠቀሜታ አጠያያቂ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በእኛ አገር ሁኔታ ግን ይህንን አጠቃላይ አመለካከት የሚፈታተኑ እውነታዎች ይታያሉ። ይኸውም በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የፖለቲካ አመለካከት ብስለትን ከሰዎች የትምህርት ደረጃና የኢኮኖሚ አቅም ጋር አያይዞ ማየት አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ አለ። ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በአደጉ አገሮች ታዋቂ ዩኒቨርስቲዎች የተማሩና በሀብት ደረጃ ሚሊየነር የሆኑ ታዋቂ የአገራችን ዜጐች ሳይቀሩ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት የሆነ ኋላቀር የፖለቲካ አመለካከት ሲያራምዱ ይታያሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኘው የተቃዋሚው ጐራ ነው። በዚህ የፖለቲካ ጐራ ውስጥ ከገዥው ፓርቲ በተሻለ በትምህርት ደረጃቸውና በኢኮኖሚ አቅማቸው አንቱ የተሰኙ ብዙ ሰዎች መኖራቸው የሚታይ ቢሆንም እስካሁን ግን በውስጣቸው ዴሞክራሲያዊ ባህልና አስተሳሰብ ያለው አንድ ጠንካራ የፖለቲካ ኃይል መፍጠር አልቻሉም።

በተለይም በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ምን ያህል ከመቻቻልና ከምክንያታዊ ፖለቲካ በእጅጉ የራቀ ጽንፈኛ አመለካከት እንደሚያራምዱ ሲታይ የትምህርትና የኢኮኖሚ የኑሮ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ የዳበረ ዴሞክራሲ ባለበት አገር ኗሪ መሆን

እንኳ በርግጠኛነት ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ሊፈጥር እንደማይችል ያሳየናል። ከዚህ የምንረዳው ዋና ቁም ነገር ከምንም ነገር በላይ በልጅነት ዘመናችን ያደግንበት ቤተሰባዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ባህሪን በመቅረጽ ረገድ ምን ያህል ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ነው። ባህላዊ አስተሳሰባችን የፈጠረው ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውጭ ቀላውጠን ያመጣነው የግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ባህላዊ ችግሩን በማባባስና አዳዲስ ተጨማሪ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪዎችን በመፍጠር ረገድ የተጫወተው ሚና ቀላል የማይባል ነው። ምክንያቱም የግራ ፖለቲካ አራማጆች ከ1960ዎቹ ጀምሮ ሲያራምዱት የቆዩት ስታሊናዊ አቋም ዴሞክራሲንና መድበለ ፓርቲ ሥርዓትን በአገሪቱ ለማምጣት ሳይሆን የወዝ አደሩን የበላይነት ለማስፈን ስለነበር እስካሁን ድረስ በአፍ እንጂ በተግባር “አብዮት ልጆችዋን ትበላለች” ከሚለው አስተሳሰባቸው መላቀቅ አልቻሉም። አሁን እየታየ ያለው የፖለቲካ ጥንፈኝነት ድንገት የተፈጠረ ሳይሆን በየግራ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ውስጥ ከድሮ ጀምሮ የነበረና ለእነ ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ ጌታቸው ማሩ፣ አጥናፉ አባተ፣ ኃይሌ ፊዳ፣ መሃሪ ተክሌ (ሙሴ)፣ ክንፈ ገ/መድህንና ሙሉዓለም አበበ ለመሳሰሉት የግራ ፖለቲከኞች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነ ነው።

ስለዚህ ከባህላዊ አስተሳሰቦችንና ከግራው ፖለቲካ ጋር ተያይዞ በአገራችን የተንሰራፋው ፀረ-ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከሰንኮፉ እስካልተነቀለ ድረስ በዚህ ዓይነቱ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል ጥርሳችንን ነቅለን ያደግን ሰዎች ዩንቨርሲቲ ገብተን ስለተማርንም ሆነ በአደጉት አገሮች ውስጥ ስለኖርን ችግሩ መፍትሔ ሊያገኝ አይችልም። ወደፊትም የዳበረ የፖለቲካ ባህል በአገራችን ሊፈጠር የሚችለው የተወሰኑ ዜጎቻችን ዩኒቨርስቲ ገብተው ዲግሪ ለመያዝ ስለበቁ ወይም ባለጸጋ ሆነው የቁሳቁስ ፍላጐታቸውን ማሟላት ስለቻሉ ብቻ ሳይሆን በሁለንተናዊ መልኩ የሶሽዮ-ኢኮኖሚክ እድገቱ በዳበረ ቤተሰብና ኅብረተሰብ ውስጥ ከልጅነታቸው ጀምሮ ዴሞክራሲያዊ ባህል አዳብረው ያደጉ ብዙ ዜጎች በአገራችን እየተፈጠሩ ሲመጡ ነው።

በአንድ አጋጣሚና ምክንያት ከሌለው ኅብረተሰብ የተሻለ የትምህርት ዕድል ማግኘትም ሆነ ሀብትና ንብረት ማፍራት በራሱ የመቻቻል ባህልን ለመፍጠር የማያበቃ መሆኑን ሌላ ብዙ ምርምር ሳያስፈልገን ለአንድና ለሁለት ሰዓታት በአዲስ አበባ ከተማ መኪና በማሽከርከር ብቻ ለመገንዘብ እንችላለን። በትምህርትም ሆነ በኑሮ ደረጃው የተሻለ ኅብረተሰብ በሚገኝባት በርእሰ-ከተማችን በአዲስ አበባ አንድ የትራፊክ መብራት በጠፋ ቁጥር ምን ያህል ርስ በርስ መተሳሰብ ተስኖን በስግብግብነት የትራፊክ መጨናነቅ እንደምንፈጥር ሲታይ፣ አንዳንድ አሽከርካሪዎችም ራሳቸው ላጠፉት ጥፋት ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ ይባስ ብለው ሌላውን ሥነ-ሥርዓት አክባሪ የሆነ አሽከርካሪ እጃቸውን እያወራጩ በጩኸት ሲሳደቡ ስናይ፣ አንዳንድ አሽከርካሪዎችም

መብራት ላይ ሲቆሙ ፀሐይ እንዳይመታቸው በመጨነቅ ከመብራቱ ርቆ በሚገኝ ጥላ ሥር ላይ በመቆም መንገድ ዘግተው ችግር ሲፈጥሩ ስናይ፣ አንዳንድ የሚሊየን ብር ዋጋ የሚያወጣ ውድ ተሽከርካሪ የሚነዱ ከራባት ያሠሩ ሰዎችም የሙዝና የማስቲካ ልጣጭ በመስኮት እየወረወሩ የከተማውን አስፋልት ሲያቆሽሹ ስናይ፣ ሌላው ቀርቶ ሕይወትን የማዳን ኃላፊነት የያዘ አምቡላንስና የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ ጥሩምባ እየነፋ ሲመጣ መንገድ ላለመልቀቅ የምናንገራግር መሆናችን ሲታይ፣ በአጠቃላይም በከተማዋ ውስጥ የሚታየው የአሽከርካሪዎች ከልክ ያለፈ መንቀዥቀዥና የጡርንባ ጫጫታ ሲታይ የአለመቻቻል ችግራችን በፖለቲካ ሥልጣን ላይ ስንቀመጥ ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዳችን የግል ባህሪ ውስጥ ሥር ሰዶ የሚገኝ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፡፡ በፖለቲካ ምክንያት ጠበንጃ ይዘን ስንዋጋ ብቻ ሳይሆን ትዕግሥት ያጣን አሽከርካሪዎች በመሆናችን ምክንያት በየዕለቱ የምናጠፋው የወገን ሕይወት በዓለም ወደር ያልተገኘለት እየሆነ መጥቷል፡፡ በነገራችን ላይ የትራፊክ ደንብን ያለማክበር ችግራችን ምን ያህል ሥር የሰደደ እንደሆነ የሚያሳየው በየእለቱ መኪና የምናሽከረክር ሰዎች ብቻ ሳንሆን ብዙ ጥንቃቄ ተደርጉባቸው ሊሰሩ በሚገባቸው የአገራችን ፊልሞች ውስጥ ሳይቀር አርቲስቶቻችን የመንገድ መስመር ሳይጠብቁ ሲነዱ ማየት የተለመደ ነው፡፡

ለብዙ ዓመታት በአርባ እና በሃምሳ ብር ደመዎዝ ውድ ጉልበታቸውን ስንበዘብዛቸው የኖርን የቤት ሠራተኞች ደመወዝ ለምን ጨመረብን ብለን ኑሮን ስናማርር የሚታየው፣ በአንድ በኩል ለመንግሥት ምንም ዓይነት ግብርና ቀረጥ ላለመክፈል ጥረት እያደረግን በሌላ በኩል መንግሥት መሠረተ-ልማት አልሠራልንም ብለን ስናማርር የሚታየው፣ አብዛኛዎቹ የአገራችን ባለሀብቶችም በየግቢያቸው ከአውሮፓና ከአሜሪካን የኑሮ ደረጃ በሚመጣጠን ንፁህና ያማረ ግቢ ውስጥ የራሳቸውን ደሴት ፈጥረው እየኖሩ ከግቢያቸው በር እንደዎጡ ግን በራሳቸው ሰፈር ውስጥ በቆሻሻ ክምርና በፈራረሰ ኮረኮንች መንገድ ላይ ሲነዱ የምናያቸው ያለ ምክንያት ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ከትንሹ አካባቢያዊ ጉዳይ እስከ ትልቁ አገራዊ ጉዳያችን ድረስ ተባብሮና ተቻችሎ የመሥራት መሠረታዊ ችግር ያለብን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ሌላው ቀረቶ የመቻቻል አርዓያ ሆነው ብዙ ሊያስተምሩን የሚገባቸው በአምልኮ ቦታዎች የሚሠሩ የዕምነት አባቶች ከመጠን በላይ የሆነ የድምጽ ማጉያን የማጮህ (sound pollution) ፉክክር ውስጥ ገብተው መታየታቸው የአለመቻቻል ችግር በአገራችን ምን ያህል ሥር የሰደደ ማህበራዊ መሠረት ያለው መሆኑ ነው፡፡ በርግጥ የዚህ ዓይነቱ ድክመታችን በሠርግና በቀብር ባህላችን ዙሪያ ብዙም አይታይም፡፡

የፖለቲካ ባህልን በአዋጅና በአንድ ወቅት ትምህርት መፍጠር የማይቻል መሆኑ ግልጽ ቢሆንም በአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታውን ሂደት ሊያፋጥኑ የሚችሉ በርካታ

ጠንካራ ጉኖችም በሕዝባችን ውስጥ አሉ ማለት ይቻላል። በሕዝባችን ውስጥ በአንፃራዊነት የሚታየው የሕግ ተገዥነትና የሕግ አክባሪነት፣ የአገርና ታሪክ ወዳድነት፣ የሃይማኖትና የባህላዊ እሴት ቀናኢነት፣ የማኅበራዊ ትስሥርና የሰላም ወዳድነት ባህሪዎች በአግባቡ ከተጠቀምንባቸው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታው ሂደት አጋዥ የሚሆኑ በጎ ጉኖቻችን ናቸው። የገዳና የዕድር ሥርዓትን የመሰለ ዴሞክራሲያዊ ባህል ባለባት አገር በአግባቡ ከተጠቀምንበት የተፋጠነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችሉን ብዙ እርሾዎች አሉን። ነገር ግን እነዚህን በጎ እሴቶቻችንን በአግባቡ በመጠቀም የአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ቢያንስ አዝጋሚም በሆነ መጠን የሚገባውን ያህል እንዳይጠናከር እንቅፋት በመሆን ረገድ የሚከተሉት ምክንያቶች ጉልህ ተጽዕኖ አሳድረዋል ማለት ይቻላል።

በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የሚፈጥረው እንቅፋት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ ወደ ተሻለ የፖለቲካ ባህል እንዳትሸጋገር በማድረግ ረገድ የመጀመሪያው ተጠያቂ አካል የአገሪቱ የፖለቲካ ኤሊት (የተማረ ክፍል) ነው ማለት ይቻላል። ሕዝቡ የራሱን የፖለቲካ መሪዎች በመፍጠር ረገድ የማይተካ ሚና መጫወት የሚጠበቅበት ቢሆንም ዞሮ ዞሮ በአሁኑ ወቅት የትግሉ ግንባር ቀደም መሪ ሊሆን የሚገባው የፖለቲካ ኤሊት የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታና የፖለቲካ ቅራኔዎች በአግባቡ መተንተንና ትክክለኛ መፍትሄ ማመንጨት የሚችል የአስተሳሰብ ታላቅነት ያለው ኃይል ሊሆን ባለመቻሉ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገው የፖለቲካ ትግል የሚገባውን ያህል ስክነትና ብስለት ሊያሳይ አልቻለም። በተለይም የአገራችን ምሁራን በተደራጀ ሁኔታ ሳይሆን በየፊናቸው መሽገው በሥልጣን ላይ የወጣውን መንግሥት ሁሉ እያሽሟጠጡና እየጉነተሉ የተሻለ የሞራል የበላይነት ያላቸው መስለው ለመታየት ከመሞከር ባለፈ አገሪቱን ለመምራት የሚያስችል ብቃት መፍጠር ስላልቻሉ እስካሁን ድረስ የአገሪቱ ችግሮች አካል እንጂ መፍትሄ አመንጭ መሆን አልቻሉም። የዚህ ዓይነት ከፍተኛ የአመራር ክፍተት በመኖሩ ምክንያትም ለአገሪቱ መድኅን የሚሆን ብሔራዊ ራእይ መፍጠር ካለመቻሉም በላይ በሕዝቡ ውስጥም ለዘመናት ተንሰራፍተው የኖሩ የአረጁ አስተሳሰቦችንም በሚገባው መጠንና ፍጥነት በአዲስና ገንቢ አስተሳሰብ መተካት አልተቻለም።

ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ትምህርትን መቅሰም ከጀመርን ከአንድ መቶ ዓመት በላይ እየሆነን ቢሆንም በዚህ ረዥም ዘመን የተቀሰመው ዘመናዊ ትምህርት ለተማሩት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ማኅበራዊ ክብር ያስገኘላቸው ቢሆንም አገሪቱን ከኋላ ቀርነትና ከችጋር አላቆ እስካሁን ወደ ዘመናዊነት ሊያስገባት አልቻለም። ይህ ለምን እንደሆነ በራሱ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ጉዳይ ቢሆንም ስለ ትምህርት ካለን የተዛባ አመለካከትና ከትምህርት ሥርዓታችን

ጋር የተያያዙ አንዳንድ ድክመቶችን በምክንያትነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ችግር ለረዥም ጊዜ በአገራችን ይሰጥ የነበረው ትምህርት ዕውቀት (Academic) ተኮር እንጂ ተግባር ተኮር ያልነበረ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ የተዛባ የትምህርት ሥርዓት ጋር ተያይዞ በአገራችን ዘመናዊ ትምህርት የሚታየው ችግሮችን ለማስወገድ እንደሚያስችል አቅምና መሣሪያ ሳይሆን በራሱ እንደመጨረሻ ውጤትና ግብ ነው፡፡ በሌሎች አገሮች ትምህርት ወይም ክሂሎት በዋናነት ከሙያተኛነት (professionalism) ጋር ተቆራኝቶ የሚታይ ሲሆን በእኛ አገር ግን እንደ ደጃዝማችነትና ፊትአውራሪነት ማኀበራዊ ክብር የሚያስገኝ ማዕረግ ተደርጎ ሲታይ ኖሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው አብዛኛዎቹ የአገራችን የተማሩ ሰዎች አገራችን ጥገኛ ከሆነችበት የግብርናም ሆነ ወደፊት ከምታመራበት የኢንዱስትሪ መስክ ውጭ የተሰማሩ ሆነው የምናገኛቸው፡፡

ሌላው በትምህርት ሥርዓታችን ዙሪያ የሚታየው ድክመት የምንማረው ትምህርት ሳይንሳዊ ዕውቀትን እንጂ ሁለንተናዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚያስችል ሳይንሳዊ አስተሳሰብን ሊያጐናፅፈን ያልቻለ መሆኑ ነው፡፡ አገራችን በውጭ አገራት ጭምር አንቱ የተሰኙ በርካታ ምሁራንን ያፈራች ቢሆንም እነዚህ ምሁራን ከዕውቀት ጋር አብረው መዳበር ያለባቸውን ሙያ አክባሪነትን፣ አገር ወዳድነትን፣ ሰብአዊነትን፣ ቅንነትን፣ ታማኝነትንና ቀጥተኝነትን የመሳሰሉ በጎ እሴቶችን የሚጠበቀውን የህል ተላብሰው አይታዩም ፡፡ በዚህም ምክንያት ያገራችን ምሁራን ከሌላው ያልተማረ ሕዝብ በተሻለ አገሪቱን ወደ ብልፅግናም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የማሸጋገር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ካለመቻላቸውም በላይ ራሳቸው የአገሪቱ ችግሮች ዋና መፍለቂያ ሆነው ኖረዋል፡፡

የአገሪቱ የፖለቲካ ኤሊት የጠራ አስተሳሰብና ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ፈጥሮ የአገሪቱን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ትክክለኛ አቅጣጫ እስካልያዘ ድረስ በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩትን አሉታዊ አስተሳሰቦች መለወጥ በራሱ አስቸጋሪ ጉዳይ ቢሆንም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩት አሉታዊ አስተሳሰቦች ጥልቅና ውስብስብ በመሆናቸው ለጠንካራ የፖለቲካ ኤሊት አለመፈጠር ዋነኛ ምክንያቶች ሆነው ይታያሉ፡፡ ከፖለቲካ ትግሉ ሂደት ጋር በተያያዘ በሕዝባችን ውስጥ ጐልተው የሚታዩት የጨለምተኛነት፣ የጥላቻ፣ የጽንፈኝነት፣ የተጠራጣሪነት፣ የአሉባልተኝነትና የተስፋ ቆራጭነት ባህሪዎች የግራው ፖለቲካ ካመጣብን አውዳሚ ስልት ጋር ተደምሮ በአገራችን ብቃት ያለው የፖለቲካ ኤሊት እንዳይፈጠር በማድረግ ረገድ ከራሱ ከፖለቲካ ልሂቁ ደካማ ባህሪዎች ጋር ርስ በርስ ተመጋጋቢ በመሆን ከፍተኛ መሰናክል ሆነዋል፡፡

በተለይም በአገራችን ገና ትምህርት የተሻለ መስፋፋት በጀመረበት ወቅት ዕድለ ቢስ ጭምር ሆነን በግራ ፖለቲካ በመጥለቅለቃችን ምሁራኖቻችን የውጭ አስተሳሰብ /Intellectual colonialism/ ሰለባ በመሆን አገር በቀል ራእይ ለመፍጠር ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ይህ ችግር ዛሬም በነበረበት የቀጠለ ቢሆንም አዲሱ ትውልድ ይህንን ክፍተት ተገንዝቦ የራሴን ጊዜ ችግር በራሴ መንገድና አስተሳሰብ ልፈታው እችላለሁ - ይገባኛልም የሚል የራስ መተማመን መንፈስ መፍጠር አልቻለም፡፡ ኢዴፓም እስካሁን የዚሁ የተሳሳተ አመለካከት ሰለባ ስለነበር ነው - ባለፈው ትውልድ የፖለቲካ ተዋናዮች ዙሪያ በነበረው የተሳሳተ ግምት ምክንያት ለተለያዩ ችግሮች ተጋላጭ የሆነው፡፡ በአጠቃላይ ጠንካራ የፖለቲካ ልሂቅ እንዳይፈጠር በማድረግ ረገድ ሆነ የወቅቱ የፖለቲካ ትግል ወደ ተጠናከረና የተሻለ ደረጃ እንዳያሸጋግር በማድረግ ረገድም በሕዝባችን ውስጥ የሚታዩት የሚከተሉት ድክመቶች የጐላ ድርሻ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያው ድክመት አብዛኛው ሕዝብ ፖለቲካን በሚመለከት ያለው አመለካከት የተዛባ መሆኑ ነው፡፡ ፖለቲካ የራስን፣ የመጭውን ትውልድና በአጠቃላይም የአገርና የሕዝብን ዕጣ-ፈንታ የሚወስን ታላቅና ምትክ የሌለው ቁም ነገር መሆኑን ባለመገንዘብ አብዛኛው ሕዝብ በተዛባ መንገድ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ በአንድ በኩል ኅብረተሰቡ በፖለቲካ ተሣትፏቸው ምክንያት የሕይወትና የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እያስታወሰ "ፖለቲካና ኮረንቲ በሩቅ" በሚል ተገቢ ያልሆነ አስተሳሰብ ከፖለቲካ ተሳትፎ ራስን ማራቅ እንደ ብልህነት አድርጐ የሚያይ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉ ዜጐች በቡድንም ሆነ በተናጠል የሚፈጽሟቸውን አንዳንድ አፀያፊ ተግባራት በማየት ብቻ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት የሚፈጽሙ ግለሰቦችን ብቻ ሳይሆን ራሱ ፖለቲካን እንደ ቆሻሻ ተግባር የመፀየፍ አዝማሚያ ኅብረተሰቡ ውስጥ ይታያል፡፡

ይህ ዓይነቱ የኅብረተሰብ አመለካከት የራሱ መነሻ ያለው ቢሆንም መለወጥ ያለበት ነው፡፡ የቱንም ያህል የፖለቲካ ተሳትፎ ዋጋ ሲያስከፍልም ሆነ በፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ ግለሰቦች የቆሸሸ ተግባር ሲፈጽሙ ቢታይም ራሳችን ከፖለቲካ ተሳትፎ ለማራቅም ሆነ ፖለቲካን ቆሻሻ ተግባር አድርጐ ለማየት በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን በአንድ አገር የፖለቲካና የፖለቲከኞች መኖር የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ ያለ ፖለቲከኞችና ያለ ፖለቲካ አገርና መንግሥት ሊኖረን ስለማይችል መፍትሄው ራስን ከፖለቲካ ማራቅና ፖለቲካን መጥላት ሳይሆን በፖለቲካ ውስጥ ጨዋነት የተላበሰ ተሳትፎና ትግል እያደረጉ የፖለቲካ ተሳትፎ የዜጐች መብት መሆኑንና ፖለቲካ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም የግድ አስፈላጊ የሆነ በጎ ተግባር መሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡

ሁለተኛው ድክመት ፖለቲካ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን የምንረዳ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ብንሆን ያለን የመደራጀት ባህል ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ ብዙዎቻችን የአገራችን የወቅቱ የፖለቲካ ባህል እንዲለወጥም ሆነ የተሻለ መንግሥታዊ ለውጥ እንዲመጣ የምንፈልግ ቢሆንም በፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ በተለያዩ የጥቅም አስከባሪ ሲቪክ ማኅበራት ዙሪያ በመደራጀት በጉልበት፣ በዕውቀት፣ በጊዜና በገንዘብ ከኛ የሚፈለገውን አስተዋጽኦ ለማበርከት ስንሞክር አንታይም፡፡ እኛ የዳር ተመልካች ሆነን የምንፈልገው ለውጥ በሌሎች መሥዋዕትነት እንዲመጣልን የምንመኝ ሲሆን ይባስ ብለን ሌሎቹ ከእኛ በተሻለ ተደራጅተው የሚታገሉት ሰዎች የምንፈልገውን ለውጥ ለምን በአንድ ጀንበር ሊያመጡልን አልቻሉም ብለን ገደብ የለሽ ወቀሳና ትችት ስናቀርብ እንደመጣለን፡፡ ነገር ግን ወደፊትም ቢሆን (ሁሉም ሰው የፖለቲካ ተሳትፎ ማድረግ አለበት ባይባልም) በምናምንበት ድርጅት ዙሪያ ሳንደራጅና ከእኛ የሚጠበቀውን አስተዋጽኦ ማበርከት ሳንችል የቱንም ያህል ውጤት ብንመኝ የምንፈልገውን ለውጥ ማግኘት አንችልም፡፡ ሌሎችን ለመተቸትና ለመውቀስ የሞራል ብቃት የሚኖረንም በመጀመሪያ ከእኛ የሚጠበቀውን አስተዋጽኦ መወጣት የምንችል ዜጎች ሆነን ስንገኝ ነው፡፡

ዛሬ እኛ የምንቀናባቸው አገሮች በከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ላይ መገኘት የቻሉት ዜጎቻቸው ቁጭ ብለው የሚፈልጉት ለውጥ በሌሎች መሥዋዕትነት እንዲመጣ ስለጠበቁ ሳይሆን ራሳቸውን በተለያዩ የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች ዙሪያ በማደራጀት እንደ ዜጋ የሚጠበቅባቸውን መሥዋዕትነት መክፈል በመቻላቸው ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በምርጫ 97 ወቅት ለአንድ ቀን ስብሰባ መስቀል አደባባይ በመገኘታቸውና ለአንድ ቀን ለሦስትና አራት ሰዓታት ተሰልፈው ምርጫ በመምረጣቸው ብቻ ከፍተኛ መሥዋዕትነት እንደከፈሉ በመቁጠርና በመመጻደቅ በፖለቲካ ፓርቲዎችና በሰላማዊ ትግሉ ላይ የሚያቀርቡትን ገደብ የለሽ ትችት ስንሰማ የምንረዳው ቁም ነገር ኢትዮጵያውያን ከሰላማዊ ትግል አኳያ መሥዋዕትነት ከፍለን ለውጥ ለማምጣት ገና በአግባቡ ያልተዘጋጀን መሆኑን ነው፡፡

አንዳንዶቻችን በተግባር እንዳየነው አገራችን ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ ምን አልባት ከግል ጉዳዩ ጋር የተያያዘ ጥቅም ካልታዬው በስተቀር ቀደም ሲል ለመጠቃቀስ በተሞከሩት የተለያዩ ምክንያቶች ለአገር ጉዳይ ብሎ የፓርቲ አባል የመሆን ባህሉ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች የፓርቲ አባል ለመሆን ሩጠው ወደ ፓርቲዎች ቢሮ ሲመጡ የምናያቸው ውጭ አገር ለመሰደድ ቪዛ ካገኙና ቲኬት ከቆረጡ በኋላ ሲሆን ይታያል፡፡ አገራችን ውስጥ ውጭ አገር ሄዶ ጥገኝነት ለማግኘት ሲል የፓርቲ አባል ለመሆን የሚፈልገውን ሰው ያህል ልባዊ የመደራጀት እምነት ኖሮት የፓርቲ አባል የሚሆን ሰው ቢኖር ኖሮ ተቃዋሚዎች እስካሁን

የተሻለ የጥንካሬ ደረጃ ላይ በደረስን ነበር፡፡ ከሕዝብ ድጋፍም አንጻር አርሴናልንና ማንቸስተር ዩናይትድን (አርሴና ማንቸ) የመሰሉ የአውሮፓ የእግር ኳስ ክለቦች በኢትዮጵያ ካላቸው ደጋፊ አንድ አራተኛውን ያህል ልባዊ ደጋፊ ፓርቲዎች ብናገኝ ኖሮ አገራችን ውስጥ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ትልቅ እመርታ ባሳዩ ነበር፡፡ በተለይም ኢትዮጵያውያን የውጭ ወራሪ መጣ ሲባል ሆ-ብለን ለመዝመት ከምናሳዬው ወኔና ቁርጠኝነት ቢያንስ ሩቡን ያህል እንኳን ለሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ተሳትፎ የማዋል ልምድ ኖሮን ቢሆን ዛሬ በዴሞክራሲ ረገድ የት በደረስን ነበር፡፡

በርግጥ የአገራችን ፖለቲካ በቅንነትና በብሩህ ራእይ የሚመራ ሳይሆን ከበቀልና ከጥላቻ ጋር በተቆራኘ ደመ-መራርነት የሚመራ ስለሆነ 90 ደቂቃ ልብ የሚያንጠለጥለውን የአርሴና የማንቸ ጨዋታን ያህል ትኩረት ሳይስብ ቢቀር የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡ ይህንን የተቃዋሚዎች የውስጥ ገመና መጻፍ ያስፈለገው ሰዎች በተቃዋሚው ጐራ ላይ ዕምነት እንዲያጡ ወይም ተስፋ እንዲቆርጡ ለማድረግ አለመሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ ሕዝቡ ለውጥ ያመጣሉ ብሎ የሚጠብቃቸው ተቃዋሚዎች ምን ያህል ከግምቱ ባነሰ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ተገንዝቦ በእልህና በቁጭት ሊያጠናክራቸው ይገባል ለማለት ነው፡፡ በአጠቃላይም ጥራትና ብቃት ያለው የፖለቲካ ሙያተኛነት (political professionalism) በአገራችን የሚፈለገውን ያህል ሊጠናከር ያልቻለው በሕዝባችን የፖለቲካ ተሳትፎ ዝቅተኛነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሦስተኛው ድክመት ለለውጥ ያለን የተዛባ ትርጉም ነው፡፡ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር የተያያዘ ለውጥ ከአጠቃላይ የኅብረተሰብ የአስተሳሰብ ለውጥና ከተቋማት ግንባታ ጋር በተያያዘ በሂደት የሚመጣ ለውጥ ሆኖ እያለ እኛ ግን የምንፈልገው ግብታዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ መጥቶ ማየት ነው፡፡ ግብታዊ ለውጥ ከመፈለጋችንም በላይ “ለውጥ” የሚባለው ነገር ትርጉም ያለው መስሎ የሚታዬን ከመንግሥታዊ ለውጥ ጋር ሲያያዝ ብቻ ነው፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ በግብታዊነት እንደማይመጣ የዓለም አገሮች ሁሉ ያለፉበት ሂደት በተጨባጭ ያስተምረናል፡፡ እንኳን የእኛ ዓይነቱ አምባገነናዊ ሥርዓቶች ሲፈራረቁበት የኖረና በዝቅተኛ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ድሀ አገርና እንደ እነ አሜሪካን ያሉ ከሁለት መቶ ዓመታት በላይ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ያለፉ አገሮችም እስከ የቅርብ ጊዜው የፕሬዝደንት ኦባማ ምርጫ ድረስ ገና በለውጥ ሂደት ላይ እንዳሉ አይተናል፡፡

የሚፈለገው ለውጥ ሁሉ የግድ ከመንግሥት መለወጥ ጋር ተያይዞ ሊመጣ እንደማይችልም ሩቅ ሳንሄድ የራሳችን የፖለቲካ ታሪክ በቂ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ መንግሥት ስለተለወጠ የሚፈለገው ለውጥ የሚመጣ ቢሆን ኖሮ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ

ከየትኛውም አገር ባላነሰ በታሪኳ በርካታ የመንግሥታት ለውጥ የተፈራረቀባት አገር በመሆኗ ዛሬ ከማንኛውም አገር በላይ አድጋና ሰልጥና በተገኘች ነበር፡፡ ስለዚህ በአንድ በኩል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ በሂደት የሚመጣ መሆኑን በመገንዘብና በሂደቱ ውስጥ ቀድመውና ፈጥነው በሚመጡ ለውጦች ተጠቃሚወች እየሆን ለሌላ የበለጠና የተሻለ ለውጥ ተግተን የመሥራት አዲስ ባህል ካላዳበርን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምንፈልገው ለውጥ ከመንግሥት ለውጥ ያለፈ ሰፊ ትርጉም ያለውና በቀላሉ ወደኋላ ሊመለስ በማይችል ደረጃ በሕዝቡ ውስጥ ባህል ሆኖ የሚተከል ለውጥ መሆኑን ካልተገነዘብን በስተቀር የለውጥ ምኞታችንን የበለጠ ሩቅና ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ እስካሁንም በአገራችን የተከሰቱ የለውጥ አጋጣሚዎችንና ዕድሎችን በአግባቡ መጠቀም ሳንችል የቀረነውም ስለ ለውጥ ባለን የተዛባ ትርጉምና ቀቢሰ ተስፋነት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ያለብን ሌላው ችግር አብዛኞቻችን እንዲመጣ በምንፈልገው ለውጥ ራሳችንን ተጠቃሚ አድርገን ማየት የምንፈልግ መሆኑ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የዜሮ ድምር ፖለቲካ እንድናራምድ የሚያስገድደንም እንዲህ ዓይነቱ ቀቢፀ-ተስፋ ነው፡፡ ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው በየሂደቱ ቀድመውና ፈጥነው በሚገኙ መለስተኛ ለውጦች ተጠቃሚ መሆናችን የማይቀር ቢሆንም አገራችን ልትደርስበት የምንመኘውን ለውጥ ሁሉ በእኛ ዘመን ካላዩነው ብለን ማሰብ ግን ከለውጥ የተፈጥሮ ሕግ ጋር መጋጨት ስለሚሆን፣ ስለ ለውጥ ስናስብ ጉዳዩ ከእኛም በላይ የመጭው ትውልድ ጉዳይ መሆኑን አምነን መቀበል ይኖርብናል፡፡ ለውጥን ከመንግሥት ለውጥ ጋር ብቻ አያይዞ ማየትና "እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል" እንዳለችው እንስሳ በሚገኘው የለውጥ ሂደት ትውልድን ሳይሆን ራስን ተጠቃሚ ለማድረግ ያለአግባብ መቋመጥም ምን ያህል የበለጠ ጉዳትና አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ከምርጫ 97 እና ከቅንጅት በላይ ሊያስተምረን የሚችል ክስተት አይኖርም፡፡

በአንድ ዴሞክራሲ ሥር ባልሰደደበት አገር የሚመጣ የመንግሥት ለውጥ፣ ጠቃሚ ለውጥን ብቻ ሳይሆን ሥርዓትንና አገርን /state/ የሚንድና የነበረውን በጎ ነገር የሚያሳጣ አደጋ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል መገመትም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተለይም የተቋሰለና የተካረረ አገራዊ የፖለቲካ ሁኔታና ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ያደረገ የጐረቤት ባላንጣነት እየዳበረ በመጣበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር የሚከሰት ለውጥ ከተራ ዝርፊያና ግድያ ጀምሮ የአገርን ህልውና የሚፈታተን አደጋ ይዞ ሊመጣ የሚችልበት ዕድል መኖሩንም ደጋግሞ ማጤን ያስፈልጋል፡፡ የከፋውን ነገር ትተን ለአንድ ሳምንት እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት የማይኖርበት ክፍተት ቢፈጠር የብዙ ዜጐች ሕይወትና ዕድሜ ልክ ተለፍቶ የካበተ ሀብትና ንብረት

እንዳልነበር ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ብዙ ጾም አዳሪ ዜጐች በየአካባቢያችን ባሉበት ሁኔታ ነጭ ማርቸዲስ እየነዳንና በየቪላ ቤታችን ውስጥ ተንደላቀን የምንኖር ሰዎች እንዲህ ዓይነቱ ኑሮ በመንግሥት አልባ አገር ለአንድ ቀን እንኳን የሚቻል መስሎ የሚታዬን ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጣሊያን ወረራ ወቅት ጀምሮ በደርግም ሆነ በኢህአዴግ ዘመን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲከሰት ተስተውሏል፡፡ ስለዚህ ስለ ለውጥ ስናስብ ሁላችንም ዙሪያችንን በአግባቡ ማስተዋልና ሁለት ሦስት ጊዜ በጥንቃቄ ደጋግመን ማሰብ ይኖርብናል፡፡

አራተኛው ድክመት ስለ ዴሞክራሲ ያለን ግንዛቤና የምንሰጠው ትርጉም የተዛባ መሆን ነው፡፡ ዴሞክራሲ በዘመናዊ ትርጉሙ ከምርጫና ከሕዝብ ተሳትፎ ያለፈ ሰፊ ትርጉምና መገለጫዎች ያሉት ጽንሰ-ሐሳብ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በአዋጅ የሚሰጠን፣ የምንቀበለው፣ ወይም አንብበን በማወቅ ብቻ በቀላሉ የምንተገብረው ጉዳይ ሳይሆን በየዕለት ተዕለት የርስ በርስ ግንኙነታችን ጭምር አብሮን ሊኖር የሚገባ አንድ ዓይነት የአኗኗር ዘይቤ ነው፡፡ ዴሞክራሲ የብዙ መብቶች መገለጫና መገኛ የመሆኑን ያህልም በዚያው መጠን እንደዬ ኅብረተሰቡ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ አስፈላጊ ሕጋዊ ገደቦች ሊጣሉበት የሚችልና መብትን ማጐናፀፍ ብቻ ሳይሆን ግዴታዎችንም በዜጐች ላይ የሚጥል የፖለቲካ ሥርዓት ነው፡፡

ዴሞክራሲ በአግባቡ ለሚጠቀምበት ኅብረተሰብ ከፍተኛ የለውጥና የዕድገት ኃይል ሆኖ የሚያገለግል ጠቃሚ የፖለቲካ መሣሪያ የመሆኑን ያህል በአግባቡ ሊጠቀምበት ላልቻለ ኅብረተሰብ ደግሞ ሥርዓት አልበኝነትን የሚያስከትል አደገኛ መሣሪያ የመሆን ዕድል ይኖረዋል፡፡ በዴሞክራሲ ስም ጥቂቶች ብዙዎችን ከፋፍለው የሚገዙበት አጋጣሚ የመኖሩን ያህልም ብዙዎች የሕናሳዎችን መብት ለማፈን ዴሞክራሲን መጠቀሚያ ሊያደርጉት የሚችሉበት ዕድል ይኖራል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው - ዴሞክራሲያዊ በሆኑ አገሮች የአናሳዎችን መብት በተለየ ሁኔታ ለማስከበር የሚያስችል የተለየ የሕግ ከለላ /Anti-discrimination law/ እንዲኖር የሚደረገው፡፡ ዴሞክራሲ እንዲህ ዓይነት ውስብስብ ባህርያትና መገለጫዎች ያሉት ቢሆንም በእኛ አገር ግን ብዙ ሰዎች ቁንጽልና የተዛባ ትርጉም ሲሰጡት ይታያል፡፡

በግለሰቦች ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ የአገራችን የፕሬስ ውጤቶች ጭምር እንደሚታየው ዴሞክራሲን የሌሎችን ስም ለማጥፋት፣ መንግሥትን በጭፍን ለማውገዝና የሌሎችን አስተሳሰብና እምነት ለማንቋሸሽ እንደተገኘ መብት አድርገው የሚያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብዙ ናቸው፡፡ ከዚያም በባሰ መልኩ ዴሞክራሲን በመንገድ ላይ ለመፀዳዳት ሳይቀር የተገኘ መብት አድርገው የሚያስቡ ዜጐች አሉ፡፡ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ወደሚገኙ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች ስንመጣም፣ ዴሞክራሲን አብዛኛው ሕዝብ የሚያምንበትን ነገር ሁሉ መቀበልና

መፈጸም አድርገው በቁንጽል የሚተረጉሙት በቁጥር ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት ከምንገኝበት የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ አንጻር ዴሞክራሲን በአግባቡና በጥንቃቄ የማንጠቀምበት ከሆነ ችግራችን ከመፍታት ይልቅ የማባባስ ውጤት ሊያስከትል ስለሚችል ስለ ዴሞክራሲ ያለን ግንዛቤ የጠራና የበሰለ ሊሆን ይገባዋል፡፡

አምስተኛው ድክመት ጀግንነትንና የአገር ፍቅርን በሚመለከት በኅብረተሰባችን ውስጥ የሚታየው የተዛባ ትርጉምና አመለካከት ነው፡፡ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የጀግንነትና የአገር ፍቅር ትርጉም ከ21ኛው ክፍለ ዘመን ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ሆኖ አይታይም፡፡ በኅብረተሰባችን ውስጥ ጀግንነትና አገር ወዳድነት ዛሬም እንደ ጥንቱ ከአርበኝነትና ከተጋፋጭነት ጋር እንጂ ሥራ አፍቃሪ በመሆን ድህነትን ከመታገል፣ ከመቻቻል ፖለቲካና ከሰላማዊነት ጋር ተዛምደው ሊታዩ አልቻሉም፡፡ ብዙውን ጊዜ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ መሪዎች ስለ ሰላማዊ ትግል መጠናከር፣ ስለመቻቻል ፖለቲካና ስለ አብሮ መሥራት የጠነከረ አቋም ሲያራምዱ ከታዩ እንደ ፈሪ፣ አድርባይና ከሃዲ ተደርገው ይፈረጃሉ፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ሰላማዊ ትግልን አውግዘው ወደ ውጭ አገር ከተሰደዱ፣ ወይም ከመንግሥት ጋር ተጋፍጠው እሥር ቤት ከገቡ የሚያራምዱት አቋም ምንም ይሁን ምን እንደ ጀግናና አገር ወዳድ ይቆጠራሉ፡፡ በግለሰብ ደረጃም በአሁኑ ወቅት በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ እንደ ጀግናና አገር ወዳድ የሚታዩት ሰዎች መንግሥትን በጭፍን የሚያወግዙ፣ የኢህአዴግ አባል የሆነን ሰው የሚጠየፉና የማያናግሩ፣ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሰው ቤት ገብተው የማይበሉና የማይጠጡ፣ የኢትዮጵያን ቴሌቪዥንና ሬዲዮ አናዳምጥም የሚሉ፣ በአገሪቱ የቀድሞ ታሪክና መሪዎች ገድል ሲኮሩ የሚታዩ፣ ስለ ብሔር ብሔረሰቦች መብት መስማት የማይፈልጉ፣ ከአንድነት በስተቀር ስለ ልዩነት መስማት አንፈልግም የሚሉና በደፈናው ስለ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ታላቅነትና ስለ ሠንደቅዓላማ ክብር ሳይታክቱ መናገር የሚችሉ ሰዎች ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ የአፄ ኃይለሥላሴን ፎቶ ግራፍ ወይም ኮከብ የሌለበትን ሠንደቅ ዓላማ ደረቱ ላይ ወይም መኪናው ላይ ለጥፎ የሚሄድን ሰው፣ ወይም ጧት ጧት በመንግሥት ላይ የጠነከረ ጥላቻ አለው የሚባልን ጋዜጣ ክንዱ ውስጥ ሸጉጦ የሚታይን ሰው አገር ወዳድነት የሚጠራጠር የለም፡፡

ይህ ዓይነቱ አመለካከት ተቃዋሚውን ጐራ በሚደግፈው የኅብረተሰብ ክፍል ዙሪያ የሚታይ ሲሆን ኢህአዴግን ጨምሮ በብሔር ደረጃ የተደራጁ ፓርቲዎችን የሚደግፈው የኅብረተሰብ ክፍልም በዚህ ረገድ በይዘቱ የተለየ መሠረታው ችግር አለበት፡፡ ኢህአዴግና መሰል

ድርጅቶች በዋናነት ትኩረት የሚሰጡት ለብሔራዊ /ክልላዊ/ ማንነታቸው በመሆኑ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የተያያዘ የአገር ፍቅር በነሱ ዘንድ ብዙም ትኩረት የማይሰጠው ከመሆኑም በላይ የብሔር-ብሔረሰቦችን መብት እንደሚፃረር ጊዜ ያለፈበት አመለካከት ተደርጐ ሲቆጠር ይታያል፡፡ በዚህ ጐራ ዙሪያ የአገር ወዳድነትና የጀግንነት ትርጉም - ከሁሉም በላይ ለብሔረሰባዊ ማንነትና ጥቅም ተቆርቋሪ ከመሆን፣ የኢትዮጵያን ቀደምት መሪዎችና ታሪክ ከማጥላላት፣ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀትንና የአንድነት ጥያቄን ከማንቋሸሽና ከዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ራስን ከማራቅ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ ለጀግንነት ያለን ትርጉም ከዘመኑ ትርጉም በብዙ ርቀት ወደኋላ ርቋል ሊባል ይችላል፡፡ እስከዛሬ ድረስ የምንመኩበት ጀግንነት በጦርነት ለፈፀምነው አካላዊ ጀግንነት /physical courage/ ነው እንጂ ለሞራላዊ ጀግንነት አይደለም፡፡ ያጠፋነውን ጥፋት በገሃድ ማመንና በድፍረት ይቅርታ መጠየቅ፣ እውነትን በድፍረት መናገር፣ ከሻጥርና ከመሠሪነት የጸዳን ሆነን መገኘት፣ ሙሰኝነትን ተጠያፊ መሆን፣ ከግላዊ ጥቅም በላይ ለማኅበራዊ ደኅንነት መጨነቅ የመሳሰሉት የሞራል ጀግንነት መግለጫዎች በአገራችን በአካላዊ ጀግንነት ላይ ገና የበላይነት ማግኘት አልቻሉም፡፡

ደፍረን እንነጋገረው ካልን በአሁኑ ወቅት ጀግኖችና አገር ወዳድ እየተባሉ የሚሞካሹት አንዳንድ ሰዎች ዐውቀውም ይሁን ሳያውቁ እንወዳታለን የሚሏትን አገር እየገነቡ ሳይሆን እያፈረሱ ያሉ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ስለዚህ የጀግንነትና የአገር ወዳድነት ትርጉም ከዚህ ዓይነቱ ርባና የለሽ ፍረጃ ወጥቶ በትክክል ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም ጋር ተያይዞ የማይታይ ከሆነ አገራችን ወደፊት እውነተኛ ጀግኖችና አገር ወዳጆችን ታፈራለች ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በትጥቅ ትግልና በአመጽ መንግሥትን ከሥልጣን እናስወግዳለን ብለው የሚያስቡ ሰዎችን ሕዝቡ እንደ ጀግኖችና አገር ወዳዶች በመቁጠር በይፋም ሆነ በድብቅ የሚያሳዬው ድጋፍ ሰላማዊ ትግሉንም ሆነ በአጠቃላይ አገሪቱን እየጐዳት ይገኛል፡፡ ሕዝቡ በግማሽ ሳይሆን በሙሉ ልብ ሰላማዊ ትግሉን የሚደግፍበት ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ የአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የበለጠ የሚዘገይ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡

ስድስተኛው ድክመት ኅብረተሰባችን የተማሩ ሰዎችን በተመለከተ ያለው የተዛባ አመለካከት ነው፡፡ የተማሩ ሰዎች በተማሩበት መስክ ራስን፣ አገርንና ሕዝብን የሚጠቅም አቅም እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡ ለተማሩ ሰዎች ተገቢውን አክብሮትና አድናቆት መስጠትም ተገቢ ነው፡፡ ነገር ግን በፖለቲካው ዙሪያ ለሚገኙ አንዳንድ የተማሩ ሰዎች ኅብረተሰቡ ያለው አመለካከት ከተገቢው አድናቆትና አክብሮት አልፎ ወደ አምልኮት ደረጃ የተጠጋ ነው ማለት

ይቻላል፡፡ በ1960ዎቹ የማሪዎች እንቅስቃሴ የኮሌጅን ደጅ የረገጠው ለጋ ወጣት ሁሉ እንደ ምሁር ተቆጥሮ "የተማረ ይግደለኝ" እየተባለ ያላግባብ በመሞካሸት ለብዙ ጥፋት እንደተዳረገው ሁሉ ዛሬም ተመሳሳይ ስህተት እየተሠራ ይገኛል፡፡ ከላይ በሌላ ክፍል ለመግለጽ እንደተሞከረው በማንኛውም የተፈጥሮም ሆነ የማኅበራዊ ሳይንስ ዲግሪ ያለውን ሰው ሁሉ የፖለቲካ ሊቅ እንደሆነ አድርጐ ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ በተለይም "ዶክተር" እና "ፕሮፌሰር" የሚለውን ቅጽል የያዘ ምሁር የሙያ መስኩ ሕክምናም ይሁን ሕንፃ ቀያሽ የፖለቲካ መሪና ተንታኝ ለመሆን የማይገሰስ ፈቃድ ያለው ሰው ተደርጐ ይታያል፡፡

እነ አቶ መለስና እነ አቶ አዲሱ ለገሠ በተቃዋሚው ጐራ አንዳንድ ደጋፊዎች የተናቁ ሰዎች ሆነው የሚቀርቡትም በዋናነት ይኸው "ዶክተር" እና "ፕሮፌሰር" የሚል የዘመናችን የፖለቲካ ፊታውራሪነት ማዕረግ የሌላቸው መሆኑ እየተጠቀሰ ነው፡፡ ቅንጅት ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም. መስቀል አደባባይ ባካሄደው ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባም አንዱ ጐልቶ ይደመጥ የነበረው የአንዳንድ ሰዎች መፈክር "ከእንግዲህ በቃን! በአቶዎች መገዛት" የሚል ነበር፡፡ የተማረ ሰው ካልተማረ ሰው በተሻለ ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫ የማመዛዘን ችሎታ እንደሚኖረውና እንደማንኛውም ሰውም በማንኛውም መስክ የተማረ አንድ ምሁር ጥሩ የፖለቲካ ዐዋቂም የሚሆንበት አጋጣሚ ቢኖርም የተማረን ሰው ሁሉ የፖለቲካ ዕውቀት ያለው አድርጐ ማየት ግን ስህተትና አደገኛ አመለካከት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት እውነት ቢሆን ኖሮ ዛሬ በሠለጠኑት ዓለማት የምናያቸው የአገር መሪዎች ሁሉ ሳይንቲስቶች ብቻ በሆኑ ነበር፡፡

ለምሳሌ በዓለም ተዋቂ የአገር መሪዎች ለመሆን ከበቁት ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት ዊንስተል ቸርችል በትምህርት ለመግፋት የተሳካላቸው እንዳልነበሩ ግለ ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ በመጥፎ ጐኑ የበለጠ የሚታወቅ ቢሆንም ገናናው መሪ አዶልፍ ሂትለር በትምህርቱ ለተደጋጋሚ ጊዜ እየወደቀ የተቸገረ ሰው ነበር፡፡ በቅርቡ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ተዋቂው ጆን ሜጀርም ከ10ኛ ክፍል የዘለለ የትምህርት ደረጃ አልነበራቸውም፡፡ ጆን ሜጀር በአንድ ወቅት ስለ አለመማራቸው ለቀረበባቸው ትችት "ከሕይወትና ከልምድ ያገኘሁት ዲግሪ አለኝ /I have a BA degree from life and experience/" ብለው በመመለስ የአመራር ብቃት ከትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን ከሌላ የሕይወት ልምድም እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡ የዓለማችን የሳይንስ ሊቅ የነበረው አልበርት አንስታይን በአንድ ወቅት ለፕሬዝዳንትነት እንዲወዳደር በተጠየቀበት ወቅት "እኔ የተፈጥሮን ችግር ለመፍታት እንጂ ማኅበራዊ ችግርን ለመፍታት ችሎታ የለኝም" በማለት የመለሰ መሆኑ የሚያሳየንም የፖለቲካ መሪነት ልዩ ክሂሎት የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ የፖለቲካ መሪ የሚፈለገው ሁሉንም ነገር

ዐውቀ እንዲገኝ ወይም በአንድ ጉዳይ ላይ የጠለቀ ዕውቀት እንዲኖረው ሳይሆን ሌሎች በየመስኩ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች በአግባቡ ተጠቅሞና አስተባብሮ ሕዝቡን በትክክለኛ አቅጣጫ እንዲመራ በመሆኑ ነው፡፡

በእኛም አገር ታሪክ ብልህና ታላቅ መሪ ተደርገው የሚጠቀሱት መሪዎቻችን የኮሌጅ ደጅን ለማየት የታደሉ አልነበሩም፡፡ ብዙ አገራዊ እንቆቅልሾችን በመፍታት የሚታወቁትን ብልሁን የፖለቲካ ሰው ፊት አውራሪ ኃብተጊዮርጊስን (አባ መላን) በምሳሌነት ብናይ እንኳንስ ዘመናዊ ትምህርት የረባ የቤተክህነት ትምህርት የተማሩ አልነበሩም፡፡ ምሁራን የተሻለ የፖለቲካ ጥበብ ቢኖራቸው ኖሮም በቅርቡ የአገራችን ታሪክ እንደታየው የተሻለ የተማረ ሰው ስብስብ ከነበራቸው መኢሶንን ከመሰሉ ድርጅቾች ይልቅ ከወታደራዊ ካምፕ የመጡ የደርግ መኰንኖችና ከበረሃ የመጡ የኢህአዴግ ሽምቅ ተዋጊዎች የአገሪቱ የሥልጣን ኮርቻ ላይ ሊፈራረቁበት ባልቻሉ ነበር፡፡ ከእኛም አገር ሆነ ከሌሎች አገሮች የመሪዎች ታሪክ እንደምንረዳው አገራቸውንም ሆነ ዓለምን የመለወጥ ሚና የተጫወቱት የፖለቲካ ሰዎች ልዩ የመሪነት ክሂሎት (Wisdom) የነበራቸው እንጂ ዲግሪ የሰበሰቡ ሰዎች አልነበሩም፡፡ በርግጥ ልዩ የመሪነት ጥበብ በትምህርት ሲታገዝ የበለጠ የመሪነትን አቅም እንደሚያጠናክር የሚያከራክር አይደለም፡፡

በብዙ አገሮች ተጨባጭ ልምዶች እንደሚታየው በሌላ የትምህርት መስክ ይቅርና በፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪነት ጭምር ብዙውን ጊዜአቸውን ዩኒቨርስቲ ውስጥ ያሳለፉ ምሁራን ጥሩ የፖለቲካ ሰው የመሆን ዕድላቸው የጠበበ ነው፡፡ ምክንያቱም በምርምር ሥራ ላይ የቆዩ ምሁራን በአንድ በኩል ምርምር የሚያካሂዱት በአንድ የጠበበና የጠለቀ መስክ ላይ እየሆነ በመጣ ቁጥር በሌሎች አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸው ትኩረትና ዕውቀት በዚያው መጠን የጠበበ ስለሚሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የምርምር ሰዎች ብዙውን ጊዜ በርግጠኛ መረጃና በመርህ ላይ ተወስኖ የመሥራት ልምድ ስለሚያዳብሩ ራሱን ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር በፍጥነት እያጣጣመ መሄድ የሚችል ጥሩ የፖለቲካ መሪ ሲሆኑ አይታይም፡፡ ለዚህም ነው በብዙ የአደጉ አገሮች በምርምር ሥራ የካበተ ልምድ ያላቸው ምሁራን ብዙውን ጊዜ በፖለቲካው መስክ ከመሪነት ይልቅ የአማካሪነት ሚና ሲኖራቸው የምናየው፡፡

ኅብረተሰባችን የተማሩ ሰዎችን የፖለቲካ መሪ እንዲሆኑ የሚፈልገው ዕውቀቱ ይኖራቸዋል ብሎ ከማመኑም በተጨማሪ የተማሩ ሰዎች ወደ ፖለቲካ መድረኩ ሲመጡ ለአገር ከመቆርቆር ያለፈ የሥልጣን ጥም ይኖራቸዋል ብሎ ስለማያስብና የተማረ ሰውም አምባገነናዊ ባህሪ አይኖረውም ብሎ ስለሚገምት ጭምር ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ቀደም ሲል አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብቶ ከሰባት ዓመት በላይ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪውን ከመሥራቱ በፊትና

ከብዙ ምሁራን ጋርም በፖለቲካ አመራርነት አብሮ የመሥራት ዕድል ከማግኘቱ በፊት ሙህራኑን በሚመለከት ተመሳሳይ አመለካከት ስለነበረው ሰዎች እንዲህ ብለው ማሰባቸው አያስገርመውም፡፡ ነገር ግን ቀረብና ገባ ብለን ስናየው እውነታው በብዙ ርቀት ከግምታችን የተለየ ነው፡፡

እነዚህ ምሁራን ፖለቲካን በተሻለ የመረዳት አቅም እንደሚኖራቸው ባያጠራጥርም የቱንም ያህል በትምህርት ገበታ ላይ ቢቆዩ ሁላችንም ባደግንበት ቤተሰባዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ተቀርፀው ያደጉ በመሆናቸው ምክንያት አንዳንዶቹ የሥልጣን ጥመኛ ከመሆንም ሆነ ለምባገነናዊ ባህሪ ከማዳበር አኳያ ከሌላው ኅብረተሰብ የተሻለ ባህሪ እንደሌላቸው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ በግምት ሳይሆን ለረዥም ዓመታት ተማሪያቸው በመሆንና በፖለቲካ አመራርነት በተግባር አብሬአቸው በመሥራት ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ስለዚህ ኅብረተሰቡ የፖለቲካ መሪነት ብቃትን ከትምህርት ደረጃ ጋር ብቻ አያይዞ የሚያይበትን የተሳሳተ አመለካከት መለወጥ እስካልቻለ ድረስ የተማረ ያድነኝ ሳይሆን "የተማረ ይግደለኝ" የሚለው የሕዝባችን ብሂል ተራ አባባል ሳይሆን የምር ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡

ሰባተኛውና ኅብረተሰባችን ውስጥ በከፋ ሁኔታ የሚስተዋለው ድክመት ጭፍን ተቃዋሚ ወይም ጭፍን ደጋፊ መሆን ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የጭፍን ተቃዋሚነትና የጭፍን ደጋፊነት ሚና ኅብረተሰቡ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ሲንፀባረቅ የሚስተዋል ነው፡፡ የአገራችን ፖለቲካ ከጭፍን ድጋፍና ተቃውሞ ተላቆ የአጀንዳዎች /Issues/ ፖለቲካ ለመሆን አለመቻሉ በ97 እና በ2000ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በተካሄዱት ምርጫዎች በግልጽ ታይቷል ማለት ይቻላል፡፡ በ97 ዓ.ምቱ ምርጫ ሙሉ በሙሉ የቅንጅት እጩዎች በተመረጡበት ከተማ እንደገና ሦስት ዓመት ሳይቆይ በ2000 ዓ.ምቱ ምርጫ ከ97 ምርጫ ብዙም ያላነሰ ሕዝብ በመራጭነት ተሳትፎ ሙሉ በሙሉ የኢህአዴግ እጩዎች ሲመረጡ ታይቷል፡፡ በሁለቱም ምርጫዎች ሁሉም ባይባልም አብዛኛው የአዲስ አበባ ሕዝብ ያካሄደው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎችን መሠረት ያደረገ ምርጫ ሳይሆን የጭፍን ተቃውሞና የጭፍን ድጋፍ መገለጫ የሆነ ህዝበ-ውሳኔ /Referendum/ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምክንያቱም በሁለቱ ምርጫዎች አንዱ ፓርቲ ከሌላው ያገኘው ብልጫ በሌሎች አገሮች እንደሚታየው በ40 እና በ60% መካከል የሚገኝ ሳይሆን 100% የተጠጋ ልዩነት መሆኑ የሚያሳየን የአገራችን ፖለቲካ በጭፍኑ ከመውደድና ከመጥላት አላስፈላጊ መመዘኛ ወጥቶ ገና ወደ የአጀንዳዎች /Issues/ ፖለቲካ መሸጋገር ያልቻለ መሆኑን ነው፡፡ በሁለቱም ምርጫዎች የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎችን መሠረት አድርገው ድምጻቸውን የሰጡ ሰዎች መኖራቸው

የሚጠበቅ ቢሆንም በሁለቱ ምርጫዎች መካከል የታየው ውጤት ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ሆኖ መገኘቱ የሚያረጋግጥልን ግን በኢትዮጵያ ምክንያታዊ ፖለቲካ ገና ያልዳበረ መሆኑን ነው፡፡

የአገራችን ፖለቲካ በእንዲህ ዓይነቱ መሠረታዊ ችግር ውስጥ እንደሚገኝ ለማዎቅ ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት ከገጠመው አስቸጋሪ ሁኔታ በላይ አስረጅ መሆን የሚችል ምሳሌ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት ፓርላማ ውስጥ ገብቶ በሚያቀርበው የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ሐሳብ የማይደሰቱ ሰዎች በቁጥር ቀላል የማይባሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ፓርላማው ውስጥ ለውይይት የቀረበን አንድን አጀንዳ ኢዴፓ ሲደግፍ ካዩ “ኢዴፓ ለይቶለት ወያኔ ሆነ” በማለት የሚያሙ ሲሆን፣ እንደገና በሌላ የፓርላማ ውይይት ላይ ኢዴፓ አንድን አጀንዳ ሲቃዎም ካዩ እነዚሁ ሰዎች ኢዴፓን አስመሳይ ተቃዋሚ አድርገው ለማማት ሲሞክሩ ይታያሉ፡፡ ብዙ ሰዎች እስካሁን ድረስ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስን አምርረው ሲያዎግዙ ከሚደመጡባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያሳዩት ንቀት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ኢዴፓ የሶማሌን ጉዳይ አስመልክቶ የወሰደውን አቋም በግልጽ ፓርላማ ውስጥ ሲያመሰግኑ በመደመጣቸው በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ያሉ በርካታ ሰዎች በኢዴፓ ሲንጨረጨሩ እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጎ ለውጥ አሳዩ ብለው ለመደሰት ወይም ለማመስገን ሲሞክሩ አልታዩም፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ገዥው ፓርቲ አፈና ሲፈጽምም ሆነ ጥሩ ነገር ሲሰራ ጨጓራቸው የሚላጥ የጭፍን ፖለቲካ አራማጅ የሆኑ ሰዎች ስለ ዴሞክራሲና የመቻቻል ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው በዚች አገር እንዲመጣ የሚፈልጉትን ለውጥ በውል ያውቁታል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡

ከላይ በዚህ ክፍል መንደርደሪያ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኅብረተሰባችን ራሱን የአገሪቱ ችግሮች አካል አድርጐ ስለማያስብ ሁልጊዜ ለአገሪቱ ችግሮች ሌሎችን ተጠያቂ አድርጐ ማየትና መፍትሔውንም ከሌሎች ቁጭ ብሎ መጠበቅን ይመርጣል፡፡ በተለይም በተቃዋሚ ዙሪያ ያለ ኅብረተሰብ የአገሪቱ ችግሮች መንስኤ በሥልጣን ላይ የተቀመጠው መንግሥት ብቻ እንደሆነ አድርጐ ስለሚያስብ ራሱም ሆነ አገሪቱ ከገጠማቸው ሁሉም ዓይነት ችግሮች የሚገላገሉት መንግሥት ከሥልጣን ሲወርድ እንደሆነ አድርጐ ይገምታል፡፡ በዚህም ምክንያት በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት እስከተቃወሙ ድረስ በውስጣቸው የሚያራምዱት አሠራርና ዓላማ ምን ይዘት እንዳለው እንኳ ለማወቅ ጥረት ሳያደርግ ሁሉንም ተቃዋሚ ድርጅቶች በጭፍን ሲደግፍና ሲያደንቅ ይደመጣል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ስሜታዊ አስተሳሰብ በመነጨም በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ሳያጤን “ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ” በሚል መፈክር ሁሉም ተቃዋሚዎች ተጨፍልቀው አንድ እንዲሆኑ የማድረግ ጫና በማሳደር ከመካከላቸው አንድም

ፓርቲ ራሱን ችሎ ተጠናክሮ እንዳይወጣ የሚያደርግ አቋም ያራምዳል፡፡ እደግፋቸዋለሁ የሚላቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከራሱና ከአገሩ ትክክለኛ ጥቅም አኳያ በአግባቡ መመዘን ሲገባው ስሜታዊና ጊዜያዊ በሆኑ ምክንያቶች ተገቢ ያልሆነ ድጋፍ ስለሚሰጣቸው እነሱም ከአገራዊ አጀንዳ አንጻር የበሰለና ምክንያታዊ ፖለቲካ ከማራመድ ይልቅ የእወደድ ባይነት (Populist) ፖለቲካ ማራመድን እንዲመርጡ አድርጓቸዋል፡፡

በዚህ ረገድ በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የሚገኘው የኅብረተሰብ ክፍል ምን ያህል ሥር የሰደደ ድክመት ውስጥ እንደሆነ በአንድ ምሳሌ ልንረዳ እንችላለን፡፡ ይኸውም እስካሁን ድረስ ከኢህአዴግ በተለያዩ ምክንያት ተለይተው ተቃዋሚውን ጐራ የተቀላቀሉት ሰዎች በሙሉ የደረሱበት የአቋም ለውጥ ምን እንደሆነ እንኳን ባልታዎቀበት ሁኔታ የጀግና አቀባበል ሲደረግላቸው ነው የታዬው፡፡ እስካሁን ይህንን ዕድል ያላገኙት የተቃዋሚውን ጐራ ለመቀላቀል ያልፈለጉት አቶ ታምራት ላይኔ ብቻ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ አቶ ታምራት በራሳቸው ምክንያት የተቃዋሚውን ጐራ መቀላቀል ስላልፈለጉ ብቻ ይኸው እንደ ኃጢያት ተቆጥሮባቸው የቀድሞ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ከነበሩት ከእነ አቶ ስዬና አቶ ገብሩ በተለየ ዛሬም በድሮ አቋማቸው ሲተቹና ሲወገዙ እየታየ ነው፡፡ የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው አብዛኛው ሰው የአንድን ሰው አገር ወዳድነት በዋናነት የሚለካው የሥርዓቱ አክራሪ ተቃዋሚ በመሆኑ ሲሆን ይታያል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ነገም በሆነ አጋጣሚ አቶ መለስ ዜናዊም ምንም ዓይነት የአመለካከት ለውጥ ሳያመጡ ነገር ግን ከድርጅታቸው በድንገት አፈንግጠው ወይም ተባረው ተቃዋሚውን ጐራ ቢቀላቀሉ በደመቀ እልልታ ተቀባይነት ሊያገኙ የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ የኢህአዴግ ዋና ጠላት ሆነው በመቆማቸው ብቻ ትናንት ሲባሉ የነበሩት ነገር ሁሉ ተረስቶ ዛሬ በርሳቸው ዙሪያ ተሰባስበው ኢህአዴግን ለመፋለም በርካታ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በአስመራ ዙሪያ ለመሰባሰብ ሲጥሩ ማየታችንም ይህንኑ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ቅጥ እያጣ የመጣውን ቅዠት የሚያሳይ ነው፡፡

ከጭፍን ተቃውሞና ከጭፍን ድጋፍ ጋር በተያያዘ በገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች ዙሪያ የሚታየው ችግርም ምንአልባት ይብስ እንደሆነ እንጂ ያነሰ አይደለም፡፡ የገዥው ፓርቲ ደጋፊዎች አገርንና ሕዝብን የሚጠቅምም ጉዳይ ቢሆን በተቃዋሚው ጐራ እስከቀረበ ድረስ በጭፍን መቃወምን የሚመርጡ ሲሆን፣ በዚያው መጠን አገርንና ሕዝብን የሚጐዳም ጉዳይ ቢሆን በገዥው ፓርቲ በኩል እስከቀረበ ድረስ ያለምንም ጥያቄና ማቅማማት በጭፍን ይደግፋሉ፡፡ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ከማንም በላይ የዴሞክራሲ ጠበቃ ነን ብለው ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ ቢሆንም በአገሪቱ ፓርላማ ውስጥ በግልጽ እንደሚታየው የነሱ የዴሞክራሲ

ትርጉም ከሌላው ዓለም ሁሉ በተለየ ኢህአዴግ የሚያቀርበውን ሐሳብ መቶ በመቶ መደገፍና ተቃዋሚው የሚያቀርበውን ሐሳብ መቶ በመቶ መቃወም ሲሆን ይታያል፡፡

ከአንድ ዓመት በፊት የኑሮ ውድነት በአገራችን ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ወቅት ኢዴፓ ለመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ እንዲጨመር ያቀረበውን ጥያቄ የኢህአዴግ አባላት ሙሉ በሙሉ እጃቸውን በማውጣት ከተቃወሙ በኋላ ኢህአዴግ አዲስ የደመወዝ ጭማሬ ሕግ ለማዎጅ አንድ ወር አልፈጀበትም ነበር፡፡ የማስታወቂያ ሚኒስትር መሥሪያ ቤትን ኃላፊነትና ሥልጣን ለመወሰን ለፓርላማ የቀረበውን ረቂቅ ሕግ ኢዴፓ “ማስታወቂያ ሚኒስትር ተጨማሪ ሥልጣን ሊሰጠው የሚገባ ሳይሆን ሊፈርስ የሚገባው መሥሪያ ቤት ነው” በማለት ያቀረበውን ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ውድቅ ካደረጉት በኋላ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ማስታወቂያ ሚኒስትር እንዲፈርስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማው ኃሣብ ሲያቀርቡ የኢህአዴግ አባላት መቶ በመቶ እጃቸውን አውጥተው ሲደግፉ ትንሽ እንኳን ኀፍረት አልተሰማቸውም ነበር፡፡ በአጠቃላይ ለኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች ድርጅታቸው ሊያጠፋም ሆነ ሊያለማ የሚችል የፖለቲካ ተቋም ሳይሆን ያለ ምንም ጥርጣሬና ጥያቄ ሊመለክ የሚገባው ጣኦት ዓይነት ተደርጐ ነው የሚታየው፡፡

ከዚሁ ከጭፍን ደጋፊነትና ተቃዋሚነት ጋር በተያያዘ ሊነሣ የሚገባው ሌላው ነጥብ በቁጥር ቀላል ሊባል የማይችል የኅብረተሰቡ ክፍል ግላዊና አካባቢያዊ ጥቅሙን ከአጠቃላዩ የአገርና የሕዝብ ጥቅም ጋር በሚዛናዊነት ማየት አለመቻሉ ነው፡፡ ኅብረተሰባችን ብዙውን ጊዜ ከራሱ ሃይማኖት፣ ከራሱ ብሔረሰባዊ ማንነት፣ ከራሱ የታሪክ ግንዛቤና ከራሱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም አኳያ ብቻ በመነሣት የአገሪቱን ችግሮች ያለአግባብ አቃሎ ወይም አወሳስቦ ሲመለከት ይታያል፡፡ ሁልጊዜ ማዳመጥ የሚፈልገው የራሱን አመለካከትና አቋሞች የሚያጠናክሩለትን የፖለቲካ ኃይሎች ሲሆን ምን አልባት የያዝኩት አመለካከት ችግር ሊኖርበት ይችላል ብሎ በመገመት ራሱን በሌሎች ጫማ ውስጥ በማስገባት የአገሪቱን ችግሮች በሚዛናዊነት ለመረዳት ጥረት ሲያደርግ አይታይም፡፡ ይህ ዓይነቱ መሠረታዊ ችግር ተቃዋሚውንም ሆነ ገዥውን ፓርቲ በጭፍን የሚደግፈው የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ ጐልቶ የሚታይ ነው፡፡

ሌላው ምክንያታዊ ፖለቲካ በአገራችን ተጠናክሮ እንዳይወጣ በማድረግ ረገድ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ የሚገኘው ኅብረተሰባችን ፖለቲካንና አሉባልታን ለያይቶ ለማየት አለመቻሉ ነው፡፡ ታላቁና ደፋሩ ጸሐፊ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ የዛሬ መቶ ዓመት በጻፈው በዚያ ጽሁፉ__፣

*"... አሁን ድንገት አንድ መኰንን ታሞ በሸዋ መሬት ቢሞት እግዚአብሔር ገደለው አይባልም። ነገር ግን ያጤ ምኒልክ መድኃኒት።... ሌላስ ይቅርና ሰማይ ዝናብን ባይሰጥ እርሻም ብዙ አላፈራም ቢል ትምህርት የሌለው ሕዝብ በንጉሡ ያመካኛል።"*

በማለት የገለጸው የአሉባልተኛነት በሽታ ዛሬም በእኛ ዘመን ምን አልባትም የበለጠ ተባብሶ ቀጥሏል። ገብረ- ሕይወት በሱ ዘመን ብዙ የተማረ ሰው ስላልነበረ አሉባልተኛነትን ካለመማር ጋር አያይዞ ያቀረበው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአገራችን እንደሚታየው ከሆነ ግን አሉባልታን በማስፋፋት ረገድ ተምሯል የሚባለው ሰው ያልተማረውን ሰው በእጥፍ የሚያስከነዳ ሆኗል። በአገራችን በየካፌቴሪያው፣ በየጸጉር ቤቱ፣ በየቢራ ቤቱ፣ በየጫት ቤቱ፣ በየአውቶቡሱና በየታክሲው የፖለቲካ ተንታኝ ሆነው ሲደመጡ የሚውሉት ብዙ ፊደል ቆጥረናል የሚሉ ሰዎች በእውነቱ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያጠፉት እነሱ እንደሚመስላቸው ፖለቲካ ሳይሆን አሉባልታ ሲያወሩ ነው ማለት ይቻላል። ከሰዎችም አልፎ በውጭ አገር የሚገኙ አንዳንድ ሬዲዮ ጣቢያዎች፣ አንዳንድ የኢንተርኔት ብሎጉች፣ ፓልቶኮችና በአገር ውስጥም የሚገኙ አንዳንድ ጋዜጦች በፖለቲካና በአሉባልታ መካከል ያለውን ልዩነት ገና ለይተው ያወቁት አይመስሉም።

በፖለቲካ ዙሪያ የሚካሄድ የሰዎች ውይይት በዋናነት ከተለያዩ አማራጭ አስተሳሰቦች ጋር በተያያዘ የሚካሄድ የሐሳብ ግጭትና ፍጭት ቢሆንም በእኛ አገር ግን በአንድ ስም ማጥፋትን ዓላማው ወይም እንጀራው ባደረገ ግለሰብ በኢንተርኔትና በጋዜጣ ላይ የተጻፈ የፈጠራ ወሬ ሁሉ እንደ ፖለቲካ ተቆጥሮ የድጋፍና የተቃውሞ ማጣቀሻ ሆኖ አገሩን ሲያምሰው ይስተዋላል። የሰው ልጅ በተፈጥሮው የታደላቸው የስሜት ህዋሳት ብዙዎች ቢሆኑም በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ግን ከስሜት ህዋሳቶቻችን ውስጥ አንዱ የሆነው ጆሮአችን የሰማውን ብቻ እንደ እውነት ተቀብሎን ማስተጋባት በየዕለት ውሎአችን የተለመደ ተግባር ሆኗል። እንዴት? መቼ? የት? የሚሉትን ጥያቄዎች በአግባቡ ራስንም ሆነ ሌሎችን ጠይቆ ለመረዳት ሳይሞከር ፖለቲከኞችን ሲያስፈልግ ጀግናና አገር ወዳድ ብሎ ማድነቅ፣ ሲያስፈልግ ደግሞ ከሃዲና ቅጥረኛ ብሎ ማውገዝ ቀላልና የተለመደ ነገር ሆኗል።

ተቃዋሚዎችን ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግን መተቸት የሚገባን በሚያራምደው ፖለቲካዊ አቋምና በሚተገብረው ፖሊሲ መሆን ያለበት ቢሆንም በአብዛኛው ስናወራ የምንውለው በባለሥልጣናቱ የግል ሕይወት ዙሪያ ሲሆን ይታያል። በአንድ የኢህአዴግ ባለሥልጣን ዙሪያ አንድ ነገር ሲወራ የተወራውን ወሬ እውነትና ውሸትነት ትንሽ እንኳ መጠራጠር ሳያስፈልገን ወሬውን ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ እንጣደፋለን። በኢህአዴግ ቁንጮ ባለሥልጣናት

የሚወራውን ትተን በወ/ሮ አዜብ መስፍን ዙሪያ የሚወራውን ብናይ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ አገሪቱ ውስጥ አንድ የጉላ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በታየ ቁጥር በወ/ሮ አዜብ ባለቤትነት ወይም ሽርክና መታማቱ የተለመደ ሆኗል፡፡ በተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ማለትም በአገር አቋራጭ አውቶብስ፣ በሃይገር ባስ፣ በባጃጂ፣ በጀነሬተርና በጫት ንግድ ሳይቀር የወ/ሮ አዜብ ስም የማይነሳበት ቦታ የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በቅርቡ አሜሪካን አገር በከፍተኛ ደረጃ በሬዲዮ ሳይቀር የመወያያ ርእስ ሆኖ የነበረው ጉዳይ የወ/ሮ አዜብ የጤፍ እንጀራ ነጋዴነት ነበር፡፡ የሚገርመው እንዲህ ዓይነት ሊመስል የማይችልና ግምት ውስጥ የሚያስገባ ወሬ በተወራ ቁጥር ወሬውን ተቀብሎ ለሌላ ከማስተላለፍ በስተቀር "ኧረ ይሄስ የማይመስል ወሬ ነው፣ ሴትየዋ ምን ቸግሯቸው የእንጀራ ንግድ ውስጥ ይገባሉ?" ብሎ ለመጠየቅና ለማነጋገር የሚሞክር ሰው እምብዛም አይታይም፡፡ የሚገርመው ስለመጥፎ ነገር ሲወራ ያለምንም መጠራጠር ለመቀበል ዝግጁ ሆነን የምንታየውን ያህል ስለጥሩ ነገር ሲወራ ግን ሳንጠራጠር በቀላሉ አምነን ለመቀበል ስንቸገር እንታያለን፡፡

ይህንን ዓይነቱን ተገቢ ያልሆነ አስተሳሰብ ገብረሕይወት ባይከዳኝ በጥሩ አባባል እንደገለጸው ከባህላችን ጋር የተቆራኘ ቢሆንም ይበልጥ እየተጠናከረና እየተባባሰ የመጣው ግን ከግራው ፖለቲካ ወደ አገራችን መምጣት ጋር ተያይዞ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአገራችን ባለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ የግራ ፖለቲካ አራማጅ የሆኑ ፓርቲዎችም ሆኑ መንግሥታት ስም ማጥፋትንና ፍረጃን ቋሚ የትግል መሣሪያቸው አድርገው ሲጠቀሙበት ታይቷል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ብልሹ አስተሳሰብ የበለጠ እየተጠናከረ የመጣው ከግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን መምጣት ጋር ተያይዞ ቢሆንም የሕዝባችን አጠቃላይ ባህሪና ባህልም ለዚህ ዓይነቱ ብልሹ አስተሳሰብ አለመለወጥ የራሱ አሉታዊ ድርሻ አለው ማለት ይቻላል፡፡ እውነቱን በድፍረት መነጋገር ከተቻለ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቃሚም ይሁን ጐጂ ነባራዊ አስተሳሰቡን እንደያዘ ለመቀጠል የሚፈልግና አዳዲስ አስተሳሰቦች ክፉኛ የሚኰስኩሱት ሕዝብ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በየጊዜው የሚፈጠሩ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ጥቅምና ጉዳታቸውን ገና በአግባቡ ሳይመዝን በመቃወምም ሆነ ከጊዜያቸው ቀደም ብለው የተፈጠሩ አዳዲስ ሐሳብ አፍላቂ "ጉዱ ካሳዎችን" በጭካኔ እየኰረኰመ ከራሱ ጋር ተስተካክለው እንዲቀጥሉ በማድረግ ረገድ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ብርታት ያለው ሌላ ሕዝብ አለ ማለት አይቻልም፡፡ በአገራችን ከእያንዳንዱ ቤተሰብና መንደር ጀምሮ እስከ መንግሥት አስተዳደር ድረስ ባለው የኅብረተሰብ መዋቅር ውስጥ እንደ ወፌፌና ሥርዓት አልበኛ እየተፈረጁ አዳዲስ አስተሳሰባቸው እንዳይደመጥ በራሱ በኅብረተሰቡ አፈና የሚፈጸምባቸው "ጉዱ ካሳዎች" በቁጥር ቀላል አይደሉም፡፡

ስለዚህ የአገራችን ፖለቲካ ከአሉባልታ ተለይቶ በአማራጭ አስተሳሰቦች ዙሪያ የሚካሄድ ውይይትና ክርክር መሆን እስካልቻለ ድረስ በአገራችን ምክንያታዊ ፖለቲካ ሊዳብርም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአግባቡ ሊጠናከር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የድክመት ነጥቦች ልንረዳ የምንችለው ቁምነገር ኅብረተሰባችን ከፖለቲካ ግንዛቤ አንጻር ምን ያህል በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ እንደተለመደው በደፈናው "የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐዋቂ ነው" እያልን የራሱን ችግሮችና ድክመቶች እንዳያይ ከማድረግ ይልቅ የአገሪቱ ችግሮችም ሆነ መፍትሄዎች አካል ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ ለአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚገባውን ሚና እንዲጫወትና የምክንያታዊ ፖለቲከኞች መፍለቂያ የሚሆን የበቃ ሕዝብ እንዲሆን ሁላችንም መጣር ይኖርብናል፡፡

ይኸውም - በአንድ በኩል የፖለቲካ ትግሉን ተገቢ አቅጣጫ አስይዞ መምራት የሚገባው የአገራችን የፖለቲካ ልሂቅ ለእነዚህ በሕዝባችን ውስጥ የሚገኙ ችግሮችና ድክመቶች ተገቢውን ዕውቅናና ትኩረት ሰጥቶ መታገል ከቻለ፤ በሌላ በኩልና በዋናነት ደግሞ ትምህርትንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በአገራችን በማፋጠን የኅብረተሰቡን የሶሽዮ-ኢኮኖሚ ደረጃ ማሳደግ ከቻልን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የበቃ ኅብረተሰብና አገር ተገቢ በሆነ ፍጥነት ሊኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሕዝቡም ሆነ የፖለቲካ ልሂቃኑ የአገራችንን ችግር ከዚህ አንጻር ማየት ከተሳናቸውና እንደ እስካሁኑ ለአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች በሥልጣን ላይ የሚገኝ መንግሥትን ብቸኛ ተጠያቂና መፍትሄ አመንጭ አድርገው ማየት የሚቀጥሉ ከሆነ የአገራችን የፖለቲካ ችግሮች ከመቃለል ይልቅ ይበልጥ እየተባባሱ ሊሄዱ እንደሚችሉና አገራችንም ለተጨማሪ ብዙ ዓመታት በአንድ ፓርቲ የበላይነት እየተገዛች፣ ወይም የተለያዩ አምባገነናዊ ኃይሎች እየተፈራረቁባት የምትቀጥልበት ዕድል ሰፊ መሆኑን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

### *2.4 በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የፖለቲካ ትግሉ*

በአሁኑ ወቅት በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከአጠቃላዩ የአገራችን የሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸሩ በጣም አነስተኛ ቢሆኑም በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሂደት ላይ ያላቸው ተጽዕኖ ቀላል የማይባል ስለሆነ የእነሱንም ሚና ለመገምገም መሞከር ተገቢ ይሆናል፡፡ ከዚህ ከአንድ ሚሊየን በላይ ይሆናል ተብሎ ከሚገመተውና በተለያዩ የዓለማችን አሕጉሮች ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ውስጥ በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ትግል ዙሪያ ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲያደርግ የሚታየው ኢትዮጵያዊ ምን አልባት ከሦስትና ከአራት በመቶ የማይበልጠው ቢሆንም በአገራችን ውስጥ በሚካሄደው የፖለቲካ ትግል የዚህ ኅብረተሰብ ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

እንዲያውም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ያለውን ሁኔታ ስናይ ትግሉ በከፍተኛ መጠን የእነዚህ በውጭ የሚኖሩ ጥቂት ወገኖቻችን ጥገኛ የሆነበትን ሁኔታ እናያለን።

በውጭ አገር ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ በፖለቲካ አስተሳሰቡም ሆነ በሌሎች ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መመዘኛዎች የተለያዩ ይዘት ያለው ኅብረተሰብ ከመሆኑ በተጨማሪ አብዛኛው በውጭ ኗሪ የሆነው ሕዝብ ውጤት አልባ በሆነው የትግል ሂደት ተሰላችቶና ተስፋ ቆርጦ፣ ወይም በየግል የዕለት ተዕለት ሕይወቱ ተጠምዶ በአሁኑ ወቅት ጉልህ የሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ የማያደርግ (Silent Majority) በመሆኑ ትክክለኛ የፖለቲካ አመለካከቱን በተጨባጭ መገምገም አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህ ይህ አጠቃላይ ግምገማ የሚያተኩረው በሁሉም በውጭ ኗሪ በሆነው ኢትዮጵያዊ ዙሪያ ሳይሆን በዋናነት በተለያዩ መንገዶች ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እያደረገ በሚገኘው ውስን የኅብረተሰብ ክፍል (Political Diaspora) ላይ ብቻ ይሆናል።

ከወቅቱ የአገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ አንጻር በውጭ ኗሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሚና በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ዝርዝር ውስጥ ገብተን ከማየታችን በፊት በቅድሚያ በአገር ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ በውጭ ነዋሪ ስለሆነው ኢትዮጵያዊ ያለውን አመለካከትና ግንዛቤ ለማየት መሞከር ጠቃሚ ይሆናል። በውጭ ነዋሪ የሆኑ ወገኖቻችን በአንፃራዊነት አገር ውስጥ ከሚኖረው ሕዝብ የተሻለ ሠርተው ገንዘብ የማግኘት፣ ተምረው ዕውቀት የመሸመት ዕድል እንዳላቸውና አብዛኛዎቹም በበለጸጉና በሠለጠኑ አገሮች ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው ብቻ አገር ውስጥ ነዋሪ በሆነው በአብዛኛው ሕዝብ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እንዳላቸው ተደርገው ይገመታሉ። በዚህም ምክንያት በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሂደትም ሆነ በወደፊቱ የአገር ግንባታ ሂደት በዕውቀታቸውና በገንዘባቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ አገር ውስጥ ኗሪ በሆነው ሕዝብ ያለው ተስፋና ግምት በጣም ከፍተኛ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን ይህ የሕዝብ ተስፋና ግምት ከአብዛኛው በውጭ ነዋሪ ከሆነው ወገናችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በተወሰነ ደረጃ የሚጣጣም እውነታ ቢኖረውም በአሁኑ ወቅት ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እያደረገ ከሚገኘውና በቁጥር አነስተኛ ከሆነው የኅብረተሰብ ክፍል (Political Diaspora) ጋር ግን የሚጣጣም ወይም የሚቀራረብ ነው ማለት አይቻልም። አብዛኛው ሕዝባችን በውጭ አገር ኗሪ ከሆኑ ወገኖቻችን እንዲመጣለት የሚጠብቀው አዲስ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ቢሆንም በአብዛኛው ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ሲገባ የሚታየው ግን በአንድ በኩል ያረጀና ያፈጀ የጥላቻ የፖለቲካ አመለካከት፣ በሌላ በኩል ደግሞ አዲስ ልብስና አዲስ መኪና ሆኖ ይታያል።

በአጠቃላይ በውጭ አገር ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊም ብቻ ሳይሆን ይህ ቀጥተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እያደረገ የሚገኘው ጥቂቱ የኅብረተሰብ ክፍልም ተቀራራቢ የሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብና

ዓላማ አለው ብሎ ማሰብ አይቻልም። ከዚህ የፖለቲካ ተሳትፎ እያደረገ ከሚገኝ የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ አብዛኛው ገዥውን ፓርቲ በጭፍን የሚቃወምና ተቃዋሚዎችን በጭፍን የሚደግፍ ሲሆን፣ በቁጥር አነስ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ደግሞ ገዥውን ፓርቲ በጭፍን የሚደግፍና ተቃዋሚዎችን በጭፍን የሚቃወም ሆኖ ይታያል።

ከእነዚህ ሁለት የተለያዩ ጽንፎች ላይ የቆሙ የፖለቲካ ተዋናዮች በተለየ ደግሞ የተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያዊ ፓስፖርት ይዘው ከተሰደዱ በኋላ "ኢትዮጵያዊ አይደለንም" የሚል አቋም በመያዝ የኦነግንና የኦብነግን የመገንጠል ዓላማ በመደገፍ ገዥውን ፓርቲም ሆነ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የሚቃወሙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ከእነዚህ በሁለት ጽንፍ ላይ ቆመው ጭፍን ፖለቲካ ከሚያራምዱና ኢትዮጵያዊ አይደለንም በማለት የመገንጠል ዓላማ ከሚያራምዱ የፖለቲካ ኃይሎች በተለየ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ በመገንዘብ ምክንያታዊና ገንቢ የፖለቲካ ትግል ለማካሄድ የሚጥሩ ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎች ቢኖሩም የእነዚህ ኃይሎች ሚና ጽንፈኛ አቋም በሚያራምዱት ኃይሎች ጫጫታ ተውጦና ደብዝዞ የሚገኝ ነው።

ከእነዚህ ጽንፈኛ አቋም ከሚያራምዱ የፖለቲካ ኃይሎች ውስጥ ገዥውን ፓርቲ በጭፍን የሚደግፉት የፖለቲካ ኃይሎች በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት ችግር የሌለባትና በኢኮኖሚም ሆነ በዴሞክራሲያዊ ሂደት በዕድገት ጐዳና እየተጥለቀለቀች የምትገኝ "የምድር ገነት" እንደሆነች አድርገው ለማቅረብ ሲሞክሩ ይታያሉ። ከዚህ በተቃራኒ ተቃዋሚውን ጐራ በጭፍን የሚደግፉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት በጎ ነገር የማይታይባትና በየዕለቱ በመፈራረስ ሂደት ላይ የምትገኝ "የምድር ሲኦል" እንደሆነች አድርገው ለማቅረብ ሲሞክሩ ይታያሉ።

እነዚህ በዚህ ዓይነት የተካረረና የተራራቀ አቋም ላይ የሚገኙ ሁለት የፖለቲካ ኃይሎች በዚህ መልክ የሚያራምዱትን ጽንፈኛ አመለካከት በውጭ አገር ነዋሪ በሆነው ኢትዮጵያዊ ሕዝብና አገር ውስጥ በሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች ላይ ያለ አግባብ ለመጫንም የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። የተለያዩ የኢንተርኔት፣ የሬዲዮ፣ የቴሌቪዥንና የኅትመት የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ራሳቸውን በተለያዩ ነፃ መሰል ኮሚኒቲዎች ስም በማደራጀት፤ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የድጋፍ ሰጪ ኮሚቴዎችን በማቋቋም፤ አንዳንድ ጊዜም አሥነዋሪ በሆነ ሁኔታ የበጎ አድራጐት ማኅበራትንና የእምነት ተቋማትን ሳይቀር መሥርተው ለራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ በመጠቀም የየራሳቸውን ጽንፈኛ የፖለቲካ አመለካከት ውጭ አገር ነዋሪ በሆነው ሕዝብ ላይ

ለመጫን በመሞከር ሕዝቡ ከልዩነቶቹ ባሻገር በጋራ የአገሩ ጉዳዮች ላይ ተባብሮ የሚሠራበት ዕድል እንዳይኖረው አድርገውታል፡፡

አገር ውስጥ በአሁኑ ወቅት ከምናየው የተካረረና ክፍፍል የበዛበት የፖለቲካ እንቅስቃሴ በእጅጉ በላቀ መጠንና ሊታመን በማይችል ሁኔታ በውጭ አገራት የሚገኙት የፖለቲካ ኃይሎች ርስ በርስ መደማመጥና መከባበር የተሳናቸው ናቸው፡፡ በአዳራሽ ተሰብስበው ወይም በሬዲዮና በኢንተርኔት ላይ ሲወያዩ ለሚያዳምጣቸው ሰው እነዚህ ሰዎች ከፖለቲካ ግንዛቤ አንጻር አሜሪካንና አውሮፓን በመሰሉ የሰለጠኑ አገራት ነዋሪ መሆናቸውንና ከጨዋነትም አንጻር ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን አምኖ መቀበል ያስቸግራል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ከስምንትና ከዘጠኝ ዓመታት በፊት እንደ ሌላው አገር ውስጥ የሚኖር ሕዝብ በውጭ ስለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የነበረኝ ግንዛቤ እጅግ የተዛባ ስለነበር ለመጀመሪያ ጊዜ በውጭ አገራት ተዘዋውሬ ተጨባጩን ሁኔታ ሳይ የገጠመኝ ድንጋጤና የአመለካከት ቀውስ ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡

ከዚያ ጊዜ በኂላ ለተከታታይ ስምንት ዓመታት ያህል በየአመቱ በየአገራቱ እየተዘዋወርኩ በውጭ ነዋሪ የሆኑ የፖለቲካ ኃይሎችን የበለጠ ለማወቅ ዕድል ያገኘሁ ቢሆንም በየዓመቱ የማዬውና የምታዘበው አጠቃላይ ክስተት በአንዳንድ ግለሰቦች ላይ በጎ ለውጥ ማየቴ እንደተጠበቀ ሆኖ በእነዚህ ኃይሎች የበለጠ ተስፋዬ እንዲሟጠጥ የሚያደርግ እንጂ በጥቂቱም ቢሆን የተስፋ ጭላንጭል የሚታይበት ሆኖ አላገኘሁትም፡፡ በዚህም ምክንያት ነበር በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች የሚያራምዱት አቋም ምን ያህል አገር የሚጐዳ መሆኑን ከተገነዘብኩ በኂላ ወደ ተስተካከለ አቅጣጫ እንዲገቡ በማሰብ የበኩሌን ገንቢ አስተያየት ማቅረብ መጀመሬ እንደ ትልቅ ድፍረት ተቆጥሮብኝ ለአለፉት ዐሥር ዓመታት የእነዚህ ኃይሎች የአሉባልታ ዘመቻ ሰለባ ለመሆን የበቃሁት፡፡ በርግጥም በዚህ ሂደት ውስጥ ባገኘሁት ተጨባጭ ልምድ ጭምር ነበር አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውያን የፈለገውን ያህል ዩኒቨርስቲ ገብተን ብንማርና ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች ለዓመታት ብንኖር ፖለቲካዊ ባህርያችንን በመቅረጽ ረገድ ያደግንበት ቤተሰብና ማኅበረሰብ ከምንም ነገር በላይ የበለጠ ድርሻ እንዳለው ለመገንዘብ የበቃሁት፡፡

እነዚህ በውጭ አገር የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች ርስ በርስ መደማመጥ፣ መከባበር፣ በጋራ አገራዊ ጉዳይ አብረው መሥራት የማይችሉና በአጠቃላይም ከሚኖሩበት አገር በተቃራኒ ዴሞክራሲያዊ ባህሪ የሌላቸው ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው በዘርና በሃይማኖት የተከፋፈሉ በመሆናቸው ምክንያት በእነሱ ዙሪያ ያለው ችግር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአገር ውስጡንም ፖለቲካ የመበከልና የማባባስ አቅሙ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ እዚህ አገር ውስጥ በወቅቱ

የአገራችን ፖለቲካ በኦሮሞነት፣ በዐማራነት፣ በትግሬነትና በሌሎች ብሔሮች ደረጃ የመከፋፈል አደጋ ውስጥ እየገባን ነው ብለን የምንሰጋ ዜጎች ውጭ አገር ሄደን በአንድ በኩል ብዙ የኦሮሞና የኢትዮጵያ ሶማሌ ተወላጆች ምን ያህል ኢትዮጵያዊነትን እየተጠዩፉት እንደሆነ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነት ጠበቃ ነኝ የሚለው የተቃዋሚው ጐራ ሳይቀር ከብሔር ማንነትም ወርዶ ምን ያህል በክፍለ አገርና በአውራጃ ደረጃ ተከፋፍሎ እንደሚገኝና ሃይማኖቱን እንኳን በጋራ ማምለክ ተስኖት በየቤተክርስቲያኑ ምን ያህል እንደተከፋፈለ ጠለቅ ብለን ለማወቅ ዕድሉን ብናገኝ የአገራችን ጉዳይ በገዥው ፓርቲ ዙሪያ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚውም ጐራ ዙሪያ ከስጋትም አልፎ እጅግ አስደንጋጭ ወደ ሆነ አቅጣጫ እያመራ መሆኑን የበለጠ እንረዳለን፡፡

በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ትግል ወይም የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ለማጠናከር በውጭ አገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን በዋናነት የሚጠበቀው ሚና ትግሉን በገንዘብ ርዳታ ማገዝ፣ ለሰብአዊ መብት መከበርና ለዴሞክራሲ መጠናከር የሚረዳ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲፈጠር ማድረግና የአገሪቱን ትክክለኛ ገጽታ የሚያሳይ መረጃ የማሰራጨት ሥራ መሥራት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በተጨባጭ እያከናወኑት የሚገኘው ተግባር ግን በአብዛኛው ከዚህ ተቃራኒ ሆኖ ይታያል፡፡ ገዥውን ፓርቲ በጭፍን ሲደግፉ የሚታዩት የፖለቲካ ኃይሎች ብዙውን ጊዜ ከሥርዓቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ከብሔረሰባዊ ማንነታቸው ወይም ከግል ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው ጋር አያይዘው ስለሚያዩት ስለ ሥርዓቱ ጥሩነት የሚያራምዱት አቋም ከሚዛናዊነትና ከተጨባጩ እውነታ በእጅጉ የራቀ ከመሆኑም በላይ የሚወዱትን መንግሥትና ሕዝቡን የበለጠ በማራራቅ ረገድ የሚጫወቱት አሉታዊ ሚና ከፍተኛ ሆኖ ይታያል፡፡

በሥርዓቱ ላይ ልባዊ እምነት ያላቸውና በሃቅ ሥርዓቱን የሚደግፉ ሰዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አብዛኞዎቹ ግን በሥርዓቱ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሥርዓቱን ከልብ ለመደገፍ ሳይሆን ራሳቸውን በሥርዓቱ አማካይነት ተጠቃሚ ለማድረግ በመሆኑ ብዙውን ጊዜ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚደረገውን ትግል ከማገዝ አኳያም ሆነ ራሱን ሥርዓቱን ከመርዳት አኳያ ያላቸው ሚና ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ነው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ኃይሎች በአንድ በኩል ሥርዓቱን በመደገፍ የሚያደርጉት የዲፕሎማሲ ዘመቻና የመረጃ ሥርጭት በኢትዮጵያ የሚገኙ የየአገራቱ አምባሳደሮች የሚያውቁትን ተራ እውነት ጭምር በመካድና በማስተባበል ላይ የሚያተኩር በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከሥርዓቱ ጋር ባላቸው ልዩ ግንኙነት ከሌላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በተለየ ተጠቃሚ መሆናቸው በግልጽ የሚታይበት አጋጣሚ ብዙ ስለሆነ እነዚህ ኃይሎች የሚያከናውኑት ተግባር ሥርዓቱ መሠረታዊ ችግር

ያለበት መሆኑን የበለጠ የሚያረጋግጥ እንጂ የሥርዓቱን በጎነት የሚያረጋግጥ ሲሆን አይታይም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የተቃዋሚውን ጐራ በጭፍን በመደገፍ ላይ የሚገኙት አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ኃይሎች ከላይ ከተጠቀሱት የገንዘብ፣ የዲፕሎማሲና የመረጃ ፍሰት ድጋፍ አንጻር በቂም ሆነ ተገቢ ሊባል የሚችል አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከገንዘብ ድጋፍ አኳያ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚያዋጡት ገንዘብ ከሚገመተው በጣም ያነሰ ቢሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአገር ውስጥ የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት ከውጭ የሚገኘው ገንዘብ ጠቃሚ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ከሚሰጠው ጥቅም በላይ ከገንዘቡ ጋር ከውጭ አብሮ የሚመጣው “ኮንትሮባንደ አጀንዳ” ትግሉን በራሱ እንዳይቆምና የበለጠ እንዳይጠናከር የሚያደርግ በመሆኑ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ነው፡፡ ምክንያቱም አገር ውስጥ የምንገኝ ተቃዋሚዎች ርስ በርስ እንድንናቆር በማድረግና በአጠቃላይም አገራችን ውስጥ የመቻቻል ፖለቲካ እንዳይጠናከር በማድረግ ረገድ ውጭ ያለው ኃይል አገር ውስጥ ባለው ኃይል ላይ የሚፈጥረው ጫና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

የቅንጅት መሪዎች የውጩን ኃይል ድጋፍ ላለማጣት ሲሉ ፓርላማ እንዳይገባና አዲስ አበባ መስተዳድርን ላለመረከብ በመወሰናቸው ትግሉ ምን ያህል ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት አይተናል፡፡ ቅንጅት ከውጩ ኃይል የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ቀርቶበት አዲስ አበባ መስተዳድርን ተረክቦ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በገንዘብም ሆነ በአጠቃላይ ድርጅታዊ ጥንካሬ ከኢህአዴግ ጋር በእኩል የሚፎካከር ግዙፍ ፓርቲ ለመሆን በበቃ ነበር፡፡ ወደፊትም ተቃዋሚው ጐራ ከውጩ ኃይል ጥገኝነት ራሱን ነፃ እስካላወጣ ድረስ የትም ሊደርስ አይችልም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ከውጭ የሚገኘው የገንዘብ ርዳታ መጠን ጊዜያዊ ችግርን ለማቃለል ካልሆነ በስተቀር ትግሉን ወደፊት ፈቀቅ ሊያደርግ የሚችል አቅም የለውም፡፡ በዚህ መጠን የሚገኘው ርዳታም ቢሆን ከአገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት ጋር ተያይዞ ሰዎች ታሰሩና ተፈቱ ሲባል በወረት የሚወጣና የሚወርድ እንጂ በአስተማማኝ ሁኔታ በቋሚነት የሚገኝ አይደለም፡፡

አብዛኛው በውጭ አገር ገንዘብ የሚያዋጣው ሰው አገር ውስጥ ሰው ታሰረና ተገደለ የሚል ወሬ ካልሰማ፣ ወይም ፖለቲካው በሆነ ምክንያት ሞቅ ሞቅ ብሎ ኢህአዴግን ያንገዳገደ መስሎ ካልታዬው በስተቀር ገንዘብ የማዋጣት ፍላጐት የለውም፡፡ ብዙኀኑ ደጋፊ ትግሉ በሂደት ተጠናክሮ ለውጤት ይበቃል ብሎ በማሰብ ርዳታ የሚሰጥ ሳይሆን ዘንድሮ አሥር ዶላር እረድቶ በሚቀጥለው ዓመት ኢህአዴግ ከሥልጣን ተወግዶለት ማየት የሚፈልግ ነው፡፡ አንዳንዱ ጥገኝነት የማግኘት ችግር ያለበት ሰውም ገንዘብ የሚያዋጣው ለተቃዋሚዎች ልባዊ ድጋፍ

ኖሮት ሳይሆን ለፖለቲካ ጥገኝነት መረጃ ሆኖ የሚያገለግል መታወቂያና የገንዘብ ደረሰኝ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ለማግኘት ሲል ነው፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚዎች በሽተኛ አጀንዳ ከኋላው ያላዘለ ጤናማ የገንዘብ ድጋፍ በውጭ አገር ነዋሪ ከሆነው ኢትዮጵያዊ ቢያገኙ ጠቃሚ መሆኑ የማያከራክር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው እያገኙት ያለው የገንዘብ ድጋፍ ግን እንደ ፓናዶል ዕለታዊ ህመምን ከማስታገስ ያለፈ ሚና የለውም፡፡

ከዲፕሎማሲያዊ ድጋፍ አኳያ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የተሻለ ሚና እየተጫወተ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቢያንስ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ሲታሰሩና በሕዝቡ ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲፈጸም ኢትዮጵያውያኑ ሰላማዊ ሰልፍ በማካሄድና የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅት ተወካዮችን በማነጋገር የሚፈጥሩት ጫና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ይህ ዓይነቱ ግፊታቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደው የፖለቲካ ትግል የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ትኩረት እንዲስብና ዕውቅና እንዲያገኝም አድርጓል፡፡

ነገር ግን በዚህ ረገድም ቢሆን እየተደረገ ያለው ድጋፍ በብዙ ችግሮች የተሞላ ነው፡፡ በአንድ በኩል የኢህአዴግ ደጋፊዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊዎችም የውጭ መንግሥታት የአገሪቱን የየዕለት ሁኔታ ሥራዬ ብሎ የሚከታተል አምባሳደርና የተሟላ ዝግጅት ያለው ኤምባሲ ያላቸው መሆኑን በመዘንጋት አገሪቱ ውስጥ የሚታየውን በጎ ያልሆነ ድርጊት ከመጠን በላይ ለጥጠውና አጋነው ስለሚያቀርቡትና በጎ ነገሮች መኖራቸውንም ሽምጥጥ አድርገው ክደው ስለሚቀርቡ እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ አቀራረብ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመታመን ችግር እየፈጠረ መጥቷል፡፡ ሚዛናዊ ሆኖ በመቅረብና በገሃድ የሚታዩትን በጎ ነገሮች አምኖ በመቀበል የተሻለ ውጤት ማግኘት ሲቻል አገሪቱን ሁልጊዜ “ሲኦል” አድርጐ በማቅረብ የውጭ መንግሥታትን ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው ጥረት በሂደት ተመልሶ ራስን የሚጐዳ ውጤት እያስከተለ ይገኛል፡፡

ሁልጊዜ ኢትዮጵያ በኢህአዴግ እየፈራረሰች እንደሆነ ተደርጐ የሚነገራቸው የውጭ ዲፕሎማቶች ቢያንስ በልማት ዙሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ በጎ ለውጦች መኖራቸውን በሂደት እየተገነዘቡ በመምጣታቸው ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከደጋፊዎቻቸው የሚነገራቸውን ነገር ሁሉ በከፍተኛ ጥርጣሬ ማየት ጀምረዋል፡፡ ከጥርጣሬም አልፎ አንዳንድ ጊዜ ከተቃዋሚዎች የሚነገራቸውን እውነት የሆነ መረጃ ሳይቀር የተለመደ ሥርዓቱን የማጥላላት ዘመቻ አድርገው በማሰብ አምነው ለመቀበል የማይፈልጉበት አደጋ እየተፈጠረ መጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአብዛኛው በውጭ አገር የሚገኘው የተቃዋሚ ኃይል ከምርጫና ከፖለቲካ መቻቻል ጋር የማይጣጣሙ የአመፅና የጦርነት ቅስቀሳዎችን በይፋ ስለሚያካሂዱና ይህንንም የውጭ

ዲፕሎማቶቹ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ተቃዋሚውን ጉራ ኃላፊነት የሚጣልበትና ሰላምና መረጋጋትን በአካባቢው ሊያመጣ የሚችል ኃይል ነው ብለው ለማመን ይቸገራሉ፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ በውጭ ያሉ ተቃዋሚዎች ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ የኢህአዴግን መንግሥት የምዕራባውያን ጉዳይ አስፈጻሚና ተላላኪ እንደሆነ አድርገው በመቀስቀስ ኢህአዴግ የበለጠ በምዕራባውያኑ ድጋፍ የሚያገኝበትን የተሳሳተ ስልት ሲያራምዱ ይታያሉ፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር የሚያካሂዱት የዲፕሎማሲ ጥረት ኢህአዴግንና አገሪቱን ለያይቶ ለማየት ባለመቻሉ ኢህአዴግን ለመጉዳት ተብሎ የሚሠራው ሥራ አገሪቱንና ሕዝቧን ጭምር በጅምላ የሚጐዳ እየሆነ ነው፡፡ ኢህአዴግን ሊያጥላላ የሚችልን አጀንዳ ሁሉ ከአገርና ከሕዝብ ጥቅም ጋር ሳይመዝኑ ማራመድ የተለመደ እየሆነ በመምጣቱ በውጭ የሚገኘው ተቃዋሚ ኃይል የሚያካሂደው ዘመቻ የመገንጠል ዓላማ የሚያራምዱ ኃይሎችንና ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ያላቸውን እንደ ሻዕቢያ ዓይነት የውጭ ኃይሎች ጭምር የሚያግዝ እየሆነ መጥቷል፡፡ አገሪቱ ላይ የውጭ መንግሥታት ማንኛውንም ዓይነት የጅምላ ዕቀባ እንዲጥሉ የሚደረገው ተከታታይ ዘመቻም ተገቢ ጥንቃቄ የሚደረግበት ባለመሆኑ ኢህአዴግን ብቻ ሳይሆን ድሀውን ኢትዮጵያዊ ሕዝብ ጭምር የሚቀጣ ውጤት እንዳያስከትል ያሰጋል፡፡ ወንጀል ፈፃሚ የሆኑ ባለሥልጣናትን ብቻ ለይቶ የማይቀጣና ተገቢ ጥንቃቄ ያልተደረገበት የጅምላ ዕቀባ ዴሞክራሲን ከማምጣት ይልቅ አምባገነናዊ አገዛዝን የበለጠ የሚያጠናክር ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በርማንና ኪዩባን በመሣሰሉ አገሮች በግልጽ ታይቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በአሜሪካን አገር አዲስ መሪ በተመረጠ ቁጥር ኢህአዴግን ከሥልጣን የማስወገድ ርምጃ እንደሚወስድ እየታሰበ የሚካሄደው ዘመቻ (Lobbying) የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ተማምኖ በአገሩ ጉዳይ ላይ ለውጥ የሚያመጣ ትግል እንዳያደርግ የሚያዘናጋና በውጭ ኃይል ጥገኛና ተስፈኛ የመሆን ከኢትዮጵያ ሕዝብ የቆዬ ባህሪ ጋር የማይሄድ አዲስ ባህል እየፈጠረም ይገኛል፡፡ የውጭ መንግሥታት አግባብ ያለው እገዛ እንዲያደርጉ የሚያስችል የማግባባት ሙከራ /lobbying/ ማድረግ ተገቢና ጠቃሚ ቢሆንም ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ሚዛናዊነቱን ያጣና አቅጣጫውን የሳተ ሲሆን ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ የበለጠ ይሆናል፡፡

ከመረጃ ፍሰትም አኳያ በውጭ ያለው ኃይል የሚጫወተውን ሚና ስናይ ከዚህ በላይ በዲፕሎማሲው ረገድ ካዬነው ሁኔታ ብዙም የተለየ አይደለም፡፡ ስለ ኢትዮጵያ በውጭ አገር በሬዲዮና በኢንተርኔት የሚሠራጩውን መረጃ ለሚያነብና ለሚሰማ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሥት አለ ብሎ ለማሰብም ሆነ አገሪቱ ወደፊት የሚቀጥል ህልውና አላት ብሎ ለመገመት

ያስቸግራል። ዋሽንግተን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ሬዲዮ ጣቢያዎች ስለ ኢትዮጵያ የሚያወሩትን ወሬ ለአንድ ቅዳሜ ለአዳመጠ ሰው ኢትዮጵያ ሄጄ ገንዘቤንና ዕውቀቴን በማፍሰስ የልማት ሥራ ልሥራ ብሎ ማሰብ ይቅርና ጧት ለሥራ ከቤቱ የወጣ ሰው ማታ ወደ ቤቱ በሰላም ይመለሳል ብሎ ለማመን ይቸገራል።

በአሁኑ ዘመን የብዙ አገራት ዜጎች የኢንተርኔት ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ችግሮቻቸውን እያቃለሉ ባሉበት ወቅት አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ግን ቴክኖሎጂውን ችግርን ለማቃለል ሳይሆን የአገራቸውን ችግር የበለጠ ለማባባስ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። የጋዜጠኝነትን ሙያ መማር ይቅርና ጋዜጣ የማንበብ ልምድ የሌላቸው ሰዎች ሳይቀሩ ፓልቶክና ሬዲዮ ጣቢያ ከፍተው የፈጠራ አሉባልታን መኝታ ቤታቸው ውስጥ ሆነው በማሰራጨት "ታጋይ-ጋዜጠኛ" የመሆን ዕድል አግኝተዋል። በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ በውጭ የሚገኙ መገናኛ ብዙኃን ትክክለኛ መረጃና ሚዛናዊ አስተሳሰብ ለኅብረተሰቡ የሚያቀርቡ ሳይሆን የአሉባልታ ፋብሪካዎች ሆነዋል ማለት ይቻላል።

የሚገርመው ነገር እነዚህ የስማቸው መጠሪያ፣ ጊዜ ማሳለፊያና ትንሽ ትንሽም የገቢ ምንጭ መፍጠር የቻሉ ሰዎች "ጋዜጠኞች ነን" ብለው መሰለፋቸው ሳይሆን ከእነሱ ጠቃሚ ቁምነገር አገኛለሁ ብሎ በቁጥር ቀላል የማይባል የኅብረተሰብ ክፍል ጊዜውንና ጆሮውን ሰጥቶ የሚያዳምጣቸው መሆኑ ነው። ይህ ሁኔታ መለወጥ የማይችል ከሆነ በውጭ አገራት የሚካሄደው የፖለቲካ ትግል ወደ ገንቢ አቅጣጫ ይሸጋገራል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ይሆናል። በአጠቃላይ እነዚህ በውጭ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ትግል በአግባቡ እያገዙና እየረዱ ሳይሆን፣ የእነሱ ፍላጐት የአገር ውስጡን ትግል ውጭ አገር ሆኖ በበላይነት መምራትና መቆጣጠር ነው ማለት ይቻላል።

እነዚህ ኃይሎች አንድ ዓይነት ቅርጽና ይዘት ያላቸው ሳይሆኑ በተለያዩ መነሻ ምክንያት ትግሉን የተቀላቀሉና በውስጣቸውም ሰፊ የአስተሳሰብና የዓላማ ልዩነት ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ ኃይሎች ውስጥ አንዳንዶቹ ከቀድሞ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ በንጉሡ፣ በደርግና በኢህአዴግ ዘመን ፖለቲካዊ በሆነ ምክንያት አገራቸውን ለቀው የተሰደዱ ሲሆኑ - እነዚህ ኃይሎች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር በተለያዩ ወቅቶች በጠላትነት ተሰልፈው ርስ በርስ ይታገሉ (ይገዳደሉም) የነበሩና በመካከላቸውም ከፍተኛ የሆነ ርእዮተ-ዓለማዊ ልዩነት ያለ በመሆኑ የኢህአዴግን መንግሥት ከሥልጣን ከማስወገድ ያለፈ የጋራ አገራዊ አስተሳሰብና ራእይ በመካከላቸው ያላቸው ኃይሎች ናቸው ማለት አይቻልም። ከእነዚህ ጥቂት የፖለቲካ ስደተኞች በተጨማሪ በአብዛኛው በውጭ አገር የተቃውሞ ትግሉን ተቀላቅለው የሚገኙት ወገኖች በውጭ

አገር ነዋሪ ለመሆን የተገደዱበት ዋነኛው ምክንያት ፖለቲካዊ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ ቢሆንም በየሚኖሩባቸው አገሮች ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ካላቸው ፍላጐትና ስደተኛ መሆን ከሚፈጥረው የግል የሞራል ጥያቄ ጋር በተያያዘ ራሳቸውን ከኢኮኖሚ ይልቅ የፖለቲካ ጥገኛ አድርገው መቁጠር የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ በትክክለኛ የፖለቲካ ምክንያት የተሰደዱትና በአሁኑ ወቅት በፖለቲካ ትግሉ ዙሪያ ተሳትፎ እያደረጉ የሚገኙት ሰዎች አንዱ መሠረታዊ ችግራቸው ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እየዳበረ በመጣ ራስን የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤት የማድረግ ጠንካራ ፍላጐት ምኞት ውስጥ መውደቃቸው ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ላቱ ይወድቅልኛል ብላ በጉን ስትከተል እንደምትውለው ቀበሮ ሁልጊዜም መንግሥት ነገ ይወድቅና አገር ውስጥ ገብተን ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የመሆን ምኞታችን ይሳካል ብለው ዕቃቸውን ቀርቅበው በተጠንቀቅ የሚጠባበቁ ተስፈኞች ሆነዋል፡፡ ትልልቆቹ የድርጅት መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ አንዳንዱ የኢንተርኔትና የሬዲዮ ጣቢያ አርበኛም ከድል በኋላ ሲቻል ማስታወቂያ ሚኒስትር፣ ሳይቻል ደግሞ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያ ሥራ አስኪያጅ የሚሆንበትን ቀን እየናፈቀ ነው የሚሠራው፡፡ በርግጥም አንዳንዶቹ በፓርቲም ሆነ በመገናኛ ብዙኃን ዙሪያ የሚሠሩት ሰዎች የሚያራምዱት አቋም ትክክልም ይሁን ስህተት ለግል ፍላጐታቸው ብቻ ሳይሆን አገርንና ሕዝብን እንጠቅማለን ብለው እየሠሩ እንደሆነ ግን መጠራጠር አይቻልም፡፡

አንድ የዛሬ አምስት ዓመት ዋሽንግተን ዲሲ የነበረኝ ገጠመኝ ውጭ አገር ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችን መሠረታዊ ችግር ሁልጊዜ ያስታውሰኛል፡፡ ይኸውም በ1995 ዓ.ም. ክረምት ላይ ኢዴኃህን ለማቋቋም በተጠራ ስብሰባ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ የኢህአፓ አመራር አባል ጋር ተገናኝቼ የማውራት ዕድል አግኝቼ ነበር፡፡ ከሰውዬው ጋር የሻይ ሰዓት ላይ ኮሪደር ላይ ቆመን ስናወራ ትንሽ ስለ አገር ውስጡ ፖለቲካ ከተነጋገርን በኋላ ኢህአፓ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጠየቅሁት፡፡ ሰውዬው ለጥያቄዬ ቀጥተኛ መልስ ሊሰጠኝ አልፈለገም ነበር፡፡ ከሚከተለው ምሳሌ ጋር አያይዞ ግን ጥያቄዬን መለሰልኝ፡፡ ቃል በቃል በትክክል ላስቀምጠው ባልችልም፣ ሰውዬው እንደሚከተለው ነበር ያለኝ____፤

> *“የእሥራኤል ልጆች በዚያ በመከራ ዘመን አገራቸው ላይ ችግር ሲደርስባቸው በመላው ዓለም እንደጨው ዘር ተበተኑ፡፡ ከብዙ ዘመን በኋላ ጊዜው ደርሶ የጥሪው ደወል ሲደወል ግን ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ እሥራኤል ተመልሰው አገርና መንግሥት ለመመሥረት በቁ፤ ኢህአፓም እንዲሁ ነው፡፡ ቀኑ ደርሶ የጥሪ ደውሉ ሲደወል ከየአለበት ተጠራርቶ አገሩ ይገባል፡፡”*

ኢህአፓ የሚጠብቀው የጥሪ ደወል መቼ እንደሚደወል፣ ከየት እንደሚደወልና ማን እንደሚደውለው ግልጽ ባይሆንልኝም አባባሉ ግን ምን ያህል በውጭ የሚኖሩ የፖለቲካ ኃይሎች በራሳቸው የህልም ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩ ተጨማሪ ማሳያ የሆነኝ ነበር፡፡ ብዙ የኢህአፓም ሆነ የሌሎች በውጭ የሚገኙ ድርጅቶች አንዳንድ አባላት አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለሚያካሂዱት ትግል መሥዋዕት ስለሚያደርጉ በቂ የግል ጥሪት ሳያፈሩ፣ ወይም ተምረው ሕይወታቸውን ሳይለውጡና አንዳንዶቹም ትዳርና ልጅ ሳያፈሩ አርባ ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ በስደት ለመኖርና ወደ እርጅና እየተሸጋገሩ የሚገኙት ይህ አንድ ቀን መንግሥት የመሆን ምኞት ከድሮ እስከ ዘንድሮ በውስጣቸው ጠጥሮ የኖረ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት ራሳቸው ዋና ባለቤትና መሪ ሆነው የማይቆጣጠሩት ሰላማዊ ትግል በአገር ውስጥ ተጠናክሮ የማየት ፍላጐት የላቸውም፡፡

በአገር ውስጥ በሂደት እየተጠናከረ የሚመጣ ሰላማዊ ትግል እነርሱን ከትግሉ ሜዳ የሚያገልልና የሕይወት ዘመን የሥልጣን ምኞታቸውን የሚያመክን አደገኛ እንቅስቃሴ ሆኖ ስለሚታያቸው ሁልጊዜም አገር ውስጥ የሚደረገውን ትግል በተለያዩ ዘዴዎች በመጥለፍ ሲቻል በእነሱ ቁጥጥር ሥር የሚመራ ትግል ለማድረግ፣ ካልተቻለ ደግሞ ለመበታተንና ለማፈራረስ ይጥራሉ፡፡ ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚሠራጩ ሬዲዮ ጣቢያዎችን በመጠቀምና አንዳንድ ጊዜም በአገር ውስጥ የሚታተሙ አንዳንድ የግል ጋዜጦችን በጥቅም ደልሎ የራስ ልሳን በማድረግ የራሳቸውን ጽንፈኛ አስተሳሰብ በሕዝብ ላይ በመጫን የአገር ውስጡን ትግል በራሳቸው አቅጣጫ ሊመሩት ይሞክራሉ፡፡ ለዚህም ነው ተቃዋሚ ፓርቲዎች እስካሁን በእነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ዙሪያ የፈጠሯቸውና ውጤታማ ሳይሆኑ የቀሩ እነ ኢተፖድህንና ኢዲኃህን የመሰሉ ኅብረቶች ውጭ አገር ተመሥርተው ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ያዩነው፡፡

ብዙውን ጊዜም ለእነዚህ ኅብረቶች እነማን መሪዎች መሆን እንዳለባቸውም በድርጅታዊ ሥራ የሚወስኑት ውጭ የሚገኙት ድርጅቶች ናቸው፡፡ ለሚመርጧቸው መሪዎች ዋናው መመዘኛቸውም የእነሱን መመሪያ አሜን ብሎ የሚቀበል ሰው መሆን ነው፡፡ እነ ፕሮፌሰር በየነ ከምርጫ 97 በኋላ ፓርላማ ለመግባት ሲወስኑ ከውጭ ወዳጆቻቸው ጋር ለመቆራረጥ የበቁትም በሌላ ምክንያት ሳይሆን ለውጭ ወዳጆቻቸው ቀደም ሲል "ከቃላችሁ አንወጣም" በማለት ገብተው የነበሩትን ቃል ጥሰው በመገኘታቸው ነው፡፡

አገር ውስጥ የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብም በተሳሳተና በተጋነነ ግምት በውጭ አገር ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችን ለአገሪቱ የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ወሳኝነት ያላቸው የአገሪቱ የቁርጥ ቀን ልጆች እንደሆኑ አድርጎ ስለሚያስብ አብዛኛውን ጊዜ የእነሱ የተሳሳተ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሲሆን

ይታያል፡፡ እውነቱን በድፍረት እንነጋገር ከተባለ ግን እነዚህ በውጭ የሚኖሩ የፖለቲካ ተዋናዮች አገራቸውን የሚወዱ ሰዎች መሆናቸው የማያከራክር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነገር ግን የቁርጥ ቀን ልጆች ናቸው ተብለው እንዲናፈቁ የሚያደርጋቸው አሳማኝ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የመንግሥት አፈናና ተጽዕኖ ሊደርስበት በማይችል ርቀት አትላንቲክ ማዶ ላይ ራስን አስቀምጦ መታገል አገር ውስጥ ለሁሉም ጥቃት ራስን አጋልጦ ከመታገል ጋር ሲነጻጸር የሚያመጻድቅ መሥዋዕትነት አይደለም፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ በአሁኑ ወቅት ውጭ አገር ሆነው ጀግና መባል የሚፈልጉት ሰዎች እውነተኛ አገር ወዳድ የሆኑት ጓደኞቻቸው በኢህአፓ ዘመን አገር ውስጥ ከደርግ ጋር ተጋፍጠው ሲታገሉ፣ ሲታሰሩና ሲገደሉ እነሱ በብልጠት ሾልከው በመውጣት ሕይወታቸውንና ኑሯቸውን ማትረፍ የመረጡ ሰዎች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ውጭ አገር በስደት ላይ ያሉ ፓርቲዎች ለአለፉት አርባ ዓመታት አደረግነው በሚሉት ትግል የኢትዮጵያን ችግር የበለጠ ከማወሳሰብ አልፈው እስካሁን የሚጨበጥና የሚዳሰስ ውጤት ሲያመጡ አልታየም፡፡ እንዲያውም በዚህ ጸሐፊ እምነት በውጭ አገር እየኖሩ እንታገላለን የሚሉት ኃይሎች ጭራሹኑ በትግሉ ውስጥ ተሳትፎ ባይኖራቸው ኖሮ ኢትዮጵያ ውስጥ የጉዳዩ ባለቤት በሆነው ሕዝብ ውስጥ የሚደረገው ትግል አሁን ከሚገኝበት በእጅጉ የተሻለ ውጤት ላይ ሊደርስ ይችል ነበር፡፡ ይህ ሲባልም የአገር ውስጡ ትግል በውጭ አገሩ ትግል በአግባቡ ሊታገዝ አይገባም ለማለት ሳይሆን የውጩ ትግል የአገር ውስጡን ትግል ማገዝ ሲገባው በተግባር ግን አሁን እንደምናየው አቅጣጫውን ስቶ የማዳከም ሚና የሚጫወት ከሆነ ጭራሹኑ ባይኖር ይመረጥ ነበር ለማለት ነው፡፡

አንዳንድ በኢኮኖሚ ችግሮችና በተለያዩ ፖለቲካዊ ምክንያቶች በስደት የሚኖሩ ወገኖቻችን በበኩላቸው ከሚወዷት አገራቸው ተነጥለው በስደት የመኖራቸውን ጉዳይ ሞራላቸውን በሚያጽናና መንገድ ምክንያታዊ ለማድረግ ስለሚፈልጉ በአገሪቱ በጎና ጥሩ ነገር ሲወራ ከመስማት ይልቅ ስለ ውድቀትና ችግር እየተወራ ለስደተኛነታቸው የማያቋርጥና የሚያጽናና ምክንያት ማግኘት የሚመርጡ መስለው ይታያሉ፡፡ በተለይም ወደ አገር ውስጥ ተመልሰው ራሳቸውን ችለው ለመኖር የሚያስችል ጥሪት መቋጠር ያልቻሉ ሰዎች “አገር ቤት ለመመለስ የሚያስችል አቅም አጣን” ከማለት ይልቅ “አገራችን የፖለቲካ ችግር ውስጥ ስለሆነች ልንመለስ አልቻልንም” ማለትን ይመርጣሉ፡፡

አገር ውስጥም ኢንቨስተር ለመሆን ብለው ገብተው በአገሪቱ የቢሮክራሲ ማነቆ ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም የግል ድክመት ገንዘባቸውን ያላግባብ አባክነው ውጤታማ መሆን ያልቻሉና

ወደመጡበት የተመለሱ አንዳንድ ሰዎች ሳይቀሩ "አገሪቱ አታሠራም" ብለው መክሰስን እንጂ በራሳችን ጥፋት ኪሣራ ውስጥ ገባን ማለትን አይፈልጉም፡፡ የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉት አብዛኛዎቹ ሰዎች የገንዘብ ጥቅም ከማግኘት አኳያ የበለጠ ተጉጂ ቢሆኑም ጥቂት ግለሰቦች ግን የተቃውሞ ትግሉን የማያቋርጥ የገንዘብ ምንጭና የግል ኑሮ መደጎሚያ አድርገው ስለሚጠቀሙበት ይህንን የገቢ ምንጭ ሊያደርቅ የሚችል ለውጥ በአገር ውስጥ እንዳይፈጠር በመስጋት የጽንፈኝነት ፖለቲካው የበለጠ ተካሮ እንዲቀጥል ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ አገር ውስጥ የፖለቲካ ጭርታ ሲፈጠር የማይወዱ ከመሆናቸውም በላይ አገር ውስጥ ጥሩ ነገር ተሠራ ተብሎ ሲወራ ከመስማት ይልቅ ኢህአዴግ ሕዝቡ ላይ ግፍ ፈጸሞ ለእነሱ የሚጠቅም ዜና እንዲፈጠር በጸሎት ጭምር የሚማፀኑ ዓይነት ናቸው፡፡

የሚገርመው የዚህ ዓይነቱ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል አራማጅ ከሆኑት በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን መካከል ምንአልባት ከ99% በላይ የሆኑት በቅርቡ በአሜሪካን አገር በተካሄደው የፕሬዘደንታዊ ምርጫ ወቅት የባራክ ኦባማ ልባዊ ደጋፊዎች የነበሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ኦባማን በአሜሪካን ሕዝብ ተመራጭ ለመሆን ያበቃቸው ዋና ምክንያት ከጥላቻ የራቀ የፖለቲካ ስልት በማራመዳቸው መሆኑን የሚገነዘቡ ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህል በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ጥረት ሲደረግ ግን መቃወምን እንጂ ድጋፍ መስጠትን ሲመርጡ አይታዩም፡፡ ይህ ለምን እንደሚሆን ለማወቅም የተለየ ጥናትና ምርምር አይጠይቅም፡፡ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ ለመጠቃቀስ እንደተሞከረው የአገራችን የፖለቲካ ባህል ጥላቻ ማራመድን እንደ አንድ ተመራጭና የሚያዋጣ ስልት የመጠቀም አባዜ የተጠናወተው በመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ከግራ ፖለቲካ ጋር የተነካኩ የፖለቲካ ኃይሎች የፖለቲካ ተቀባይነት ለማግኘት የሚጥሩት ፍቅርንና መቻቻልን በመስበክ ሳይሆን ኅብረተሰቡን በመደብ ወይም በዘር ከፋፍለው የጥላቻ ቅስቀሳ በማራገብ ነው፡፡

እነዚህ ኃይሎች በፖለቲካ ትግሉ ዙሪያ ከሚፈጽሙት አፍራሽ ድርጊት በተጨማሪ በውጭ ነዋሪ የሆነው አብዛኛው ጤናማ አስተሳሰብ ያለው ሕዝብ (Silent Majority) ኢህአዴግ ከሥልጣኑ እስካልተወገደ ድረስ አገር ውስጥ ገብቶ በገንዘቡና በዕውቀቱ የልማት ተሳታፊ እንዳይሆን የሚያካሂዱት አፍራሽ ቅስቀሳ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በልማት መስክ ሊመጣ የሚችለው ለውጥ ሕዝቡን ቢጠቅምም ባይጠቅምም ኢህአዴግን ሊያስመሰግነው ይችላል የሚል ስጋት ስለሚፈጥርባቸው አገር ቤት ገብቼ አለማለሁ የሚልን ሰው ሁሉ ኢህአዴግን ለመጥቀም እንጂ ራሱንና አገሩን ለመጥቀም የሚሠራ ሰው ነው ብለው ለማመን አይፈልጉም፡፡

እንደ ዋሽንግተን ዲሲ ዓይነቱ አካባቢማ አገር ውስጥ ገብቶ በልማት ውስጥ መሠማራት ይቅርና የመኖሪያ ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራትም ሆነ አንዳንድ ጊዜም ቤተሰብን ለመጠዬቅ ወደ ኢትዮጵያ ደገምገም አድርጐ መመላለስ በወያኔነት የሚያስፈርጅ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ ሕዝቡ የኢትዮጵያ አየር መንገድን እንዳይጠቀም፣ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን እንዳያይ፣ በአሜሪካ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ እንዳይታይና ከኢትዮጵያ ተጋግሮ የመጣ ጤፍ እንጀራ እንዳይበላ ጭምር መቀስቀስ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ እንደ ጀግናና አገር ወዳድ ዜጋ የሚያስቆጥር ነው፡፡ የዲሲ አካባቢ ፖለቲከኞች ማን እውነተኛ ፖለቲከኛ እንደሆነና እንዳልሆነም ብቻ ሳይሆን ማን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እንደሆነና እንዳልሆነም ዜግነት ሲሰጡና ሲነጥቁ የሚውሉት እነሱው ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ቢያንስ የራሳቸውንም ፍላጐት እውን ለማድረግ የሚያስችላቸው ትክክለኛ ስልት ምን እንደሆነ በአግባቡ ቢገነዘቡት ኖሮ እንዲህ ዓይነቱን ሁሉንም ነገር ለኢህአዴግና ለደጋፊዎቹ አሳልፎ የሚሰጥ የተሳሳተ ስልት ባልተከተሉ ነበር፡፡ እነዚህ ኃይሎች አገር ውስጥ የሚካሄደውን ሰላማዊ ትግልና የልማት ተሳትፎ እያወገዙ ራሳቸውን ከሂደቱ ከማራቅ ይልቅ አገር ውስጥ በሙሉ ኃይላቸው ገብተው በፖለቲካውም ሆነ በልማቱ መስከ የሚችሉትን ያህል ተረባርበው ቢሆን ኖሮ ኢህአዴግና ደጋፊዎቹ በአገሪቱ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ በአሁኑ ወቅት የፈጠሩት የበላይነት በእጅጉ የጠበበና ያነሰ በሆነ ነበር፡፡

እነዚህ ጽንፈኛ ኃይሎች በአንድ ጊዜያዊ ገዥ ፓርቲና በአገር መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት መገንዘብ ተስኗቸው ገዥውን ፓርቲ ለማራከስ ብለው የሚያራግቡት ገደብ የለሽ ቅስቀሳ የአጠቃላዩን ሕዝብና የአገር ገጽታ የሚያጐድፉ ጭምር እየሆነም መጥቷል፡፡ ለሥርዓቱ ያላቸው ጭፍን ጥላቻ ገደብ እያለፈ በመምጣቱም የጠላቴ ጠላት ወዳጅ በሚል የማይገባ ስሌት አሁን አሁን ግልጽ የሆነ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ካላቸው ኃይሎች ጋር ጭምር ለመተባበር ሲሞክሩ እየታየ ነው፡፡ ከሂደት ፖለቲካ በቀጥታ ወደ መንግሥታዊ የሥልጣን ባለቤትነት ሊያሸጋግራቸው የሚችለው አቋራጭ መንገድ የመንግሥት ለውጥ ብቻ እንደሆነ አድርገው ስለሚያስቡም በምርጫና በዴሞክራሲያዊ ሂደት (Political Process) ሊመጣ የሚችልን ጠቃሚ ለውጥ ሁሉ በጭፍን ሲቃወሙና በአቋራጭ መንገድ ሊመጣ የሚችልን የትኛውንም ዓይነት ግብታዊ የመንግሥት ለውጥ እየተመኙ ይገኛሉ፡፡

ውጤቱን በአግባቡ ለሚገነዘበው ሰው ግን እነዚህ ኃይሎች ገዥውን ፓርቲ የጐዱ መስሏቸው የሚያራምዷቸው አቋሞች በአብዛኛው ኢህአዴግን የበለጠ የሚያጠናክሩ እንጂ አገርንም ሆነ የተቃዋሚውን ጐራ ትግል የሚጠቅሙ አይደሉም፡፡ ትግሉ ከመጠናከር ይልቅ በሂደት የበለጠ እየኮሰመነ የመጣውና ብዙ የአክራሪ ፖለቲካው ፊትአውራሪዎች የነበሩ ሰዎችም

አሁን አሁን ወደ አገራቸው መመለስ መጀመራቸውም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የሚገርመው እነዚህ ኃይሎች ይህንን ያህል አገርንና ሕዝብን የሚጐዳ ድርጊት እየፈጸሙ እየታየ በአደባባይ ደፍሮ የሚተቻቸው ተቃዋሚ ድርጅትም ሆነ ታዋቂ ሰው የለም፡፡ ስም የማጥፋት አቅማቸው ቀላል የማይባል ስለሆነ መንግሥት ከሆነው ከኢህአዴግም በላይ የሚፈሩ ናቸው፡፡

በርካታ የኅብረተሰቡ ክፍል እነዚህ ኃይሎች የሚነዙትን የፈጠራ አሉባልታ በቀላሉ አምኖ ሲቀበል ስለሚታይ የሚጠሉትን ሰው ከፖለቲካ መድረኩ ብቻ ሳይሆን ከማኅበራዊ ኑሮውም የማፈናቀል አቅማቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊም ቀደም ካሉ ዓመታት ጀምሮ በእነዚህ ኃይሎች ላይ ይህንን መሰል ትችት ለማቅረብ የሚደፍረው በሱ ላይ ጉዳት የማድረስ አቅማቸውን አሳንሶ በማየት ሳይሆን አንድ ቦታ ላይ ተደፍሮ እውነቱ ሊነገራቸው ካልቻለ በስተቀር በትግሉ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ቀላል እንደማይሆን ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ስለተሰማው ነበር፡፡

በውጭ አገር የሚካሄደው የፖለቲካ ትግል በሂደት ከአፍራሽነት ወደ ገንቢነት ሊቀዬር የሚችለው በአንድ በኩል ራሱን ከፖለቲካ ተሳትፎ አግልሎ የተቀመጠው አብዛኛው በውጭ አገር የሚኖረውና እውነተኛ አገር ወዳድ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል (Silent Majority) ራሱን አጠናክሮ በመውጣትና ምክንያታዊ ፖለቲካ በማራመድ እነዚህን ጥቂት ኃይሎች ማሸነፍ ሲችል፣ ወይም አገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የጋራ አቋም ወስደው ራሳቸውን ከእነዚህ ኃይሎች ጥገኝነት ነፃ ማውጣት ሲችሉ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ምክንያታዊ ፖለቲካ በአገሪቱ እንዲጠናከር ከልቡ መደገፍ ከፈለገ የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት አገር ውስጥ ያሉ ፓርቲዎችን በገንዘብ መደጐም ይኖርበታል፡፡ አገር ውስጥ የሚገኘው የቢዝነስ ማኅበረሰብም ለጥቅሜ ሊቆሙልኝ ይችላሉ ብሎ የሚያምንባቸውን ፓርቲዎች በገንዘብ በመርዳት ከውጭ ጥገኝነት እንዲላቀቁ ሊያግዛቸው ይገባል፡፡

ይህ በውጭ የሚታየው የተበላሸ የፖለቲካ ባህል እንዲለወጥ በጎ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችለው ሌላው አካል የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ነው፡፡ በውጭ አገራት እንዲህ ዓይነቱ ጽንፈኛ የፖለቲካ አመለካከት እንዲጠናከር በማድረግ ረገድ በየአገራቱ የሚገኙት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንጽላ ጽሕፈት ቤቶች የራሳቸው አሉታዊ ድርሻ አላቸው፡፡ እነዚህ ጽሕፈት ቤቶች የአገሪቱ ዜጐች የፖለቲካ አመለካከት ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩል ዓይን ማየትና ማገልገል ሲገባቸው በተግባር ገባ ተብሎ ሲታይ ግን እነዚህ የአገሪቱ ኤምባሲ ጽሕፈት ቤቶች ከኢህአዴግ ጽሕፈት ቤትነት የተለየ መልክና ይዘት ሲኖራቸው አይታይም፡፡ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ሲያጠፉ የሚታዩትም የፕሮፓጋንዳ ሥራ በመሥራት እንጂ

ኢትዮጵያዊያኑ የፖለቲካ ልዩነቶቻቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ የአገራቸው ጉዳይ ላይ አብረው የሚሠሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት አይደለም፡፡ እስካሁንም በውጭ አገራት ጽንፈኛ አቋም የሚያራምዱት የፖለቲካ ኃይሎች የበላይነት አግኝተው መኖር የቻሉት የሕዝቡ የጋራ ቤት መሆን የሚገባቸው የኤምባሲ ጽሕፈት ቤቶች ግልጽ በሆነ ሁኔታ የገዥው ፓርቲ ተጽዕኖ የአጠላባቸው ተቋማት ሆነው በመገኘታቸው ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ በውጭ ነዋሪ የሆነው ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ አመለካከቱ ምንም ይሁን ምን ቢያንስ በጋራ የአገሩ ጉዳይ መግባባት እንዲችል የኤምባሲ ጽሕፈት ቤቶች ከፖለቲካ ተጽዕኖ ነፃ የሆኑ የአገሪቱ ገለልተኛ ተቋማት ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.5 የአገራችን ሲቪክ ማኅበራት ሚና

በአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊጠናከር የሚችለው፣ ተገቢ የሕግ ማዕቀፍና ብዙ ፓርቲዎች በመኖራቸው ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡን የተለያዩ ጥቅሞችና ፍላጐቶች የሚወክሉ ጠንካራና በርካታ ሲቪክ ማኅበራት ሲኖሩ ጭምር ነው፡፡ በአገራችን የሚገኙት ማኅበራት ግን በቁጥርም ሆነ በይዘት ከሌሎች አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነጻጸሩ በጣም ጥቂትና ደካማ በመሆናቸው እንዳሉም ሊቆጠሩ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የሆነ ሆኖ በገዥው ፓርቲ፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎችና በሕዝቡ ዙሪያ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ለመገምገም እንደሞከርነው ሁሉ የእነዚህን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ጠቃሚና የማይተካ ሚና ያላቸውን ሲቪክ ማኅበራት ሁኔታም ጠቅለል ባለ መልኩ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሲቪክ ማኅበራት ከተቋቋሙበት ዓላማና ከሚወክሉት ጥቅም አንጻር በይዘታቸው የተለያዩ ስለሆኑ በዚህ ግምገማ የሚተኰርባቸው በቀጥታ ከፖለቲካ ጉዳይ ጋር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ግንኙነት ያላቸውን ሲቪክ ማኅበራት ብቻ ይሆናል፡፡

በአገራችን የሚገኙ ሲቪክ ማኅበራት በቁጥር አነስተኛ መሆናቸውም ሆነ በይዘት ጠንካራ አለመሆናቸው በሌሎቹ የፖለቲካ ተቋማት እንዳየነው ሁሉ ከአጠቃላዩ የኅብረተሰብ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል አብዛኛው የአገራችን ሕዝብ አርሶ አደርና በተለያዩ ጥቅሞች ሊወከል የማይችል መካከለኛ ገቢ ያለው (Middle Class) ኅብረተሰቡ አለመሆኑ በርካታ ሲቪክ ማኅበራት እንዳይፈጠሩ ምክንያት የሆነ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአገራችን ማቆጥቆጥ የጀመሩ ሲቪክ ማኅበራት በአግባቡ እንዳይጠናከሩ በማድረግ ረገድ የመንግሥትና የፖለቲካ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በዋና ምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የአንድ ሕዝብ ጥንካሬ የሚለካውና ጥቅሙም በተገቢው መንገድ ሊወከልና ሊጠበቅ የሚችለው በተለያዩ ሲቪክ

ማኅበራት ዙሪያ ተደራጅቶ በፖለቲካ ኃይሎች ላይ በሚያሳድረው ጫናና ግፊት ቢሆንም በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ግን የማኅበራት ሚና ከዚህ ተቃራኒ ሆኖ ይታያል፡፡

ማኅበራቱ በምርጫ ወቅትና በሕግ አወጣጥ ሂደት በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ የሕዝብ ነፃ ተቋማት መሆን ሲገባቸው በተቃራኒው የፖለቲካ ኃይሎች ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጐት የሚጠቀሙባቸው የይስሙላ ተቋማት ሆነው ይታያሉ፡፡ በአገራችን አንዳንድ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት የሚሞክሩ ማኅበራት መኖራቸው ባይካድም አብዛኛዎቹ ማኅበራት ግን እንወክለዋለን ለሚሉት ኅብረተሰብ ሳይሆን በደርግ ጊዜ ይታይ እንደነበረው በግልጽ ባይሆንም በተግባር ግን የፖለቲካ ወገንተኝነት ይዘው የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ናቸው፡፡

ገዥው ፓርቲ በበኩሉ ሲቪክ ማኅበራት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የማይተካ ሚና ያላቸው መሆኑን አምኖ በመቀበል ማኅበራቱ በገለልተኝነትና በነፃነት የሚሠሩበትን ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ይልቅ የራሱ የፖለቲካ መሣሪያና መጠቀሚያ እንዲሆኑ በሚያስችል ዘዴ ሆን ብሎ ስለሚቆጣጠራቸው ሚናቸው የአገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያጠናክር ሳይሆን በተቃራኒው የሚያደናቅፍ ሆኖ ይታያል፡፡ ባለፉት ዓመታት በገሃድ እንደታየው ገዥው ፓርቲ ከራሱ ፍላጐት ጋር አብረው የሚቆሙትን ማኅበራት በተለያዩ መንገዶች የሚደግፈውን ያህል ከሱ ፍላጐት ጋር የማይቆሙትን ደግሞ በዚያው መጠን በተለያዩ ተጽዕኖዎች ለማዳከም ይጥራል፡፡ ብዙውን ጊዜ በአገራችን በአንድ ጉዳይ ተመሳሳይ ዓላማ አለን የሚሉ ሁለት ማኅበራት እየተፈጠሩ ርስ በርስ ሲሻኮቱና በሕጋዊ ዕውቅና ጥያቄ ላይ ሲካሰሱ የምናየውም በዋናነት በዚሁ የገዥው ፓርቲ የጣልቃ ገብነትና ማኅበራቱን በመሣሪያነት የመጠቀም ፍላጐት ነው፡፡ ማኅበራት የየራሳቸው ድክመት ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ገዥው ፓርቲ ከራሱ አስተሳሰብና ብሔረሰባዊ አደረጃጀት የማይጣጣሙ የሙያ ማኅበራትን ያለርኅራኄ ሆን ብሎ ማዳከምና ማክሰም እንደሚፈልግ በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርና በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ላይ በተደጋጋሚ በፈጸመው ተግባር በግልጽ አሳይቷል፡፡

በመስከረም ወር 2001 ዓ.ም. ለኅትመት በበቃው ራእይ የሚባል የድርጅቱ ልሳን ኢህአዴግ ጠቃሚ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ብዙኃን ማኅበራት ዕቅድና በጀት ይዞ እንደሚያጠናክራቸው የገለፀ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የበጎ አድራጐት ድርጅቶችን በተመለከተ በተመሳሳይ ዓመት እንዲጸድቅ ባደረገው አዲስ አዋጅ ከራሱ ፍላጐትና ጥቅም ጋር አይሄዱም ብሎ የሚያምንባቸውን ማኅበራት ከጥቅም ውጭ ለማድረግ ምን ያህል ቆርጦ እንደተነሳ በተግባር አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር ኢህአዴግ የሲቪክ ተቋማትን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን

ለማጠናከር ሳይሆን ራሱን ከሌሎች ጥቃት ለመከላከያነትና ሌሎችን ለማጥቃት የሚጠቀምባቸው መሆኑ ሊካድ በማይችል መጠን በተደጋጋሚ በተግባር ታይቷል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ምንም እንኳ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ ገዥው ፓርቲ ለራሳቸው ጥቅምና ፍላጐት የሚሠሩ ሲቪክ ማኅበራትን የማቋቋም አቅም የሌላቸው ቢሆኑም በማኅበራቱ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የላቸውም ሊባል ግን አይችልም፡፡ አንዳንዶቹ ሲቪክ ማኅበራት ከተመሠረቱበት ዓላማና ሕገ-ደንብ አንጻር የሚጣጣሙ እንቅስቃሴዎችን እያካሄዱ ከሥርዓቱ የሚቃጣባቸውን ተጽዕኖ በአግባቡ መቋቋም ሲገባቸው ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላነሰ የከረረ የፖለቲካ አቋም በማራመድና አንዳንድ ጊዜም ከተቃዋሚው ጐራ ጋር በግልጽ በአደባባይ አብረው በመሰለፍ ሥርዓቱን ሲያወግዙ ስለሚታዩ የገለልተኛነት ሚናቸው በሂደት በሕዝብ ዘንድ ጥያቄ ውስጥ እየገባ ከመምጣቱ በተጨማሪ ከስልት አንጻርም ራሳቸውን ለገዥው ፓርቲ ጥቃት አመቻችተው ሲያቀርቡ ታይቷል፡፡ የሞያ ማኅበራት በምርጫ ወቅት ጥቅሜን ያስከብርልኛል ብለው የሚያምኑበትን የፖለቲካ ፓርቲ መደገፍ መብታቸውና የተለመደ ቢሆንም አንዳንዶቹ የሞያ ማኅበር መሪዎች ግን ከራሳቸው ሕገ-ደንብ በማይመጥን ሁኔታ ልክ እንደ አንድ የፓርቲነት ፈቃድ እንዳለው የፖለቲካ ድርጅት የሥርዓቱ አክራሪ ተቃዋሚ ከመሆንም አልፈው ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በግልጽ አብረው እስከመሥራት የደረሱበት ወቅት ስለነበር (በአንድ ወቅት ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ጸሐፊ ሆነው ነበር) ገዥው ፓርቲ በሙያ ማኅበርነት ሳይሆን በፖለቲካ አጀንዳ አራማጅነት ፈርጆ ጥቃት እንዲሰነዝርባቸው የሚያስችል ዕድል ፈጥረውለታል፡፡ በአገራችን የጐላ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉት ማኅበራት ውስጥ እስካሁን ሳይከፋፈልም ሆነ ራሱን ለገዥው ፓርቲ የከፋ ጥቃት ሳያጋልጥ የተሻለ ሥራ መሥራት የቻለው የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ የሲቪክ ማኅበራት አመራሮችም ወደ ውጭ አገር ተሰደው ከሄዱ በኋላ በግልጽ የተቃዋሚ ድርጅት አመራር አባል ሆነው በመሥራት ገዥው ፓርቲ በማኅበራቱ ላይ የሚያቀርበውን "አጀንዳቸው ፖለቲካዊ ነው" የሚለውን ክስ የሚያጠናክር ተግባር ሲፈጽሙ ተስተውሏል፡፡

ብዙውን ጊዜ ኅብረተሰቡ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አንዳንድ የነፃው ፕሬስ አባላት የሲቪክ ማኅበራትን ጥንካሬና ትክክለኛነት ሲመዝኑ የሚታየውም ለቆሙሉት ዓላማና ኅብረተሰብ ባላቸው ታማኝነት ሳይሆን መንግሥትን በመቃወምና በመተቸት ረገድ ከሚያሳዩት ድፍረት አንጻር ሆኖ ይታያል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ገለልተኛነት ጥያቄ ውስጥ የመግባት ችግር በተጨማሪም አንዳንዶቹ ማኅበራት ከፍተኛ የግልጽነትና የተጠያቂነት ጉድለት ያለባቸው ስለሆኑ ከቆሙለት ዓላማ ይልቅ የግለሰቦች ዝናና ጥቅም ማጋበሻ ሆነው የሚያገለግሉበት ሁኔታ

ይታያል፡፡ ብዙውን ጊዜ በቀላሉ የገዥው ፓርቲ የጥቃት ሰለባ ሲሆኑ የሚታዩትም እንወክለዋለን ከሚሉት የኀብረተሰብ ክፍል ጋር የጠበቀ ግንኙነት መሥርተው በተግባር የማኀበራቱ ወኪሎች ሆነው ከመገኘት ይልቅ ራሳቸውን ከአባላቱ ነጥለው በመንሳፈፍ የውጭ መንግሥታትንና ድርጅቶችን ደጅ በመጥናትና በጋዜጦች ላይ መግለጫ በማውጣት ተወሥነው ስለሚቀሩ ነው፡፡ የአገራችን ሲቪክ ማኀበራት በአንድ በኩል ለራሳቸው ሕገ-ደንብና ለአባላቶቻቸው ጥቅም በጽናት በመቆም ነፃነታቸውን ከማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ጠብቀው ተጠናክረው ቢወጡ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በምርጫ ወቅት ከስሜት በፀዳ መልኩ ለአባሎቻቸው ጥቅም በትክክል ለሚቆም የፖለቲካ ፓርቲ ምክንያታዊ ድጋፍ ቢሰጡ ኖሮ ከራሳቸው አባላት ጥቅም በተጨማሪም የአገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሂደት በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫዎት በቻሉ ነበር፡፡

ሲቪክ ማኀበራት በሚፈለገው መጠንና ይዘት ተጠናክረው በመገኘት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የሚገባቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉት በዋናነት ከሕዝቡ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃና ከአጠቃላዩ የሕዝብ የፖለቲካ ባህል መዳበር ጋር በተያያዘ ቢሆንም ቢያንስ አሁን ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ እንዲወጡ ከመንግሥት፣ ከሕዝብና ከራሳቸው ከማኀበራቱ የሚጠበቅ ድርሻ ይኖራል፡፡ መንግሥት ወይም ገዥው ፓርቲ ማኀበራትን የራሱ የፖለቲካ ጥቅም ማስከበሪያ ተቋማት ለማድረግ ከመፈለግ ይልቅ ከተመሠረቱበት ዓላማ አንጻር በነፃነትና በገለልተኝነት እየሠሩ ለአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና ተገቢ የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል፡፡ ኀብረተሰቡም ሲቪክ ማኀበራት የገዥው ፓርቲ መጠቀሚያ ሲሆኑ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎችም መጠቀሚያ ሆነው ሲያገኛቸውም በድፍረት ሊያወግዛቸው ይገባል፡፡

ራሳቸው ሲቪክ ማኀበራቱም የተቋቋሙበትን ዓላማ እየዘነጉ የገዥው ፓርቲም ሆነ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መጠቀሚያ ከመሆን ይልቅ ለቆሙለት ዓላማና ለሚወክሉት ኀብረተሰብ ብቻ ተጠሪና ተጠያቂ በመሆን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በመወጣት ለአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የሚጠበቅባቸውን ተገቢ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሕዝቡም ሲቪክ ማኀበራት የተለያዩ የኀብረተሰብ ጥቅሞችና ፍላጐቶችን በማስጠበቅ ረገድም ሆነ በአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ላይ ተገቢ ክትትልና ግፊት በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና ምትክ የሌለው መሆኑን በመገንዘብ በተለያዩ ጥቅሜንና ፍላጐቴን ይወክላሉ በሚላቸው ማኀበራት ዙሪያ ተደራጅቶ ሁለንተናዊ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነቱን አግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡ መንግሥት፣ ሕዝቡና

ራሳቸው ማኀበራቱ የየበኩላቸውን ኃላፊነት በዚህ መልክ በአግባቡ እስካልተወጡ ድረስ ግን ሲቪክ ማኀበራት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማጠናከር ረገድ በአገራችን የሚኖራቸው ሚና ለረዥም ጊዜ የቀጨጨና የደበዘዘ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል፡፡

## *2.6 የአገራችን መገናኛ ብዙኃን*

የመገናኛ ብዙኃን በተለይም የኀትመት ሥራ በአውሮፓና በአሜሪካ የተጀመረው በ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ ዓመታት እንደሆነ ይነገራል፡፡ በመገናኛ ብዙኃን ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው የጋዜጠኝነት ሙያም በዚያው መጠን ረዥም ዕድሜ ያለው ቢሆንም የሞያው ታላቅነት እየገነነ የመጣው በዋናነት ከ1871 የፈረንሳይና የጀርመን ጦርነት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በወቅቱ የፈረንሳዩ ናፖሊዮን III ከ100,000 ሺ ሠራዊታቸው ጋር በመማረካቸው ሽንፈቱ ለፈረንሳይ ሕዝብ ቅስም ሰባሪ ሆኖ ስለነበር ለዚያ ሽንፈት እውነተኛው ተጠያቂ ማነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በተፈጠረው ውዝግብ የጋዜጠኞች ሚና ገኖ ሊወጣ ችሏል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ 1974ቱ የፕሬዝደንት ኒክሰን የሙስና ቅሌት /water gate scandal/ ድረስ የመገናኛ ብዙኃን ሚና በተለያዩ ታሪካዊ አጋጣሚዎች ጭምር እየገነነ መጥቶ በብዙ አገሮች መገናኛ ብዙኃን እንደ አራተኛ የመንግሥት ምሰሶ /the fourth pillar of states/ የሚቆጠርበት ደረጃ ላይ ለመድረስ በቅቷል፡፡

ወደ አገራችን የኀትመት ታሪክ ስንመጣ ኢትዮጵያ ጽሑፍ በመጠቀም ረገድ ረዥም ዘመን ያሳለፈች ቢሆንም የጋዜጣ ኅትመት ሥራ የጀመረችው በ1904 ነበር፡፡ የኅትመት ሥራ በዚያ ጊዜ ተጀመረ ቢባልም በወቅቱ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ የነበሩት ጋዜጠኞች በሞያው ዙሪያ ምንም ዓይነት ዕውቀትና ልምድ ስላልነበራቸው ከነገሥታት ዜና መዋዕል ጸሐፊነት ያለፈ ሚና አልነበራቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ከጣሊያን ወረራ በኋላም ቢሆን የጋዜጠኞቻችን ተግባር የንጉሡን ፍጹሙታዊ ሥልጣን ከመስበክ ባለፈ የዘመናዊ የጋዜጠኝነት መስፈርትን የሚያሟላ አልነበረም፡፡ በደርግ ዘመን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ወቅት ከግራ ፖለቲካ መስፋፋት ጋር በተያያዘ የኅትመት ውጤቶች በመጠን ደረጃ ማደግ የቻሉበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም ብዙም ሳይቆይ የጋዜጠኝነት ሥራ በቅድመ ምርመራ አሠራር ነፃነቱን እንዲያጣ በመደረጉና ሥርዓቱ የአማራጭ ሐሳቦችን መደመጥ የማይፈቅድ የነበረ በመሆኑ ጋዜጠኛነት አሰልች ፕሮፓጋንዳ ከማስተጋባት ያለፈ ሚና አልነበረውም፡፡ በዘመነ ኢህአዴግ የፕሬስ ነፃነት ዕውቅና ማግኘቱና ቅድመ ምርመራ መነሣቱ በራሱ ትልቅና በጎ ርምጃ ቢሆንም የአገራችን መገናኛ ብዙኃን ዛሬም በቁጥር እንጂ በይዘት መሠረታዊ ለውጥ አምጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡

አሁን ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መገናኛ ብዙኃን ሲባል በመንግሥትና በግል ባለቤትነት ተይዘው የሚገኙትን ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ መጽሔትና ጋዜጣ የመሳሰሉትን የዜና ማሰራጫዎች የሚመለከት ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን በሌላው ዓለም ከፍተኛ የመገናኛ አውታር እየሆነ የመጣው ኢንተርኔት ቢሆንም በአገራችን ያለው ተጠቃሚ ከ1% በጣም ያነሰ ነው፡፡ በርግጥ ሕዝቡን በመድረስ ረገድ የጋዜጦችም ሚና ከኢንተርኔት ብዙም የማይለይና በቁጥር ደረጃ ገና እዚህ ግባ ሊባል የሚችል ባይሆንም በፖለቲካው ረገድ ቢያንስ በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ያለው ሚና የሚናቅ አይደለም፡፡ እንደ ሌሎቹ የአገራችን ጉዳዮች ሁሉ የመገናኛ ብዙኃንም በሚፈለገው መጠንና ይዘት በአገራችን ተጠናክረው ሊገኙ የሚችሉት ከሕዝቡ አጠቃላይ የሶሽዮ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃና ከፖለቲካ ባህሉ መዳበር ጋር ተያይዞ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በቅርቡ በኢንተር አፍሪካ ግሩፕና በዘ ስቲዲ-ማን ግሩፕ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የግል ሬዲዮ ያለው ሕዝብ ቁጥር ከአጠቃላዩ ሕዝብ 48% የሚሆነው ሲሆን ቴሌቪዥን ያላቸው ሰዎች ቁጥር ደግሞ 7% የሚሆኑት ብቻ ናቸው፡፡ መገናኛ ብዙኃን በሽፋን ደረጃ ያላቸው ውስንነት አንድ ችግር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ወቅት አገራችን ከምትገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲመዘን የመገናኛ ብዙኃን ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደቱ መጐልበት የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ እየተወጡ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ እንዲያውም ብዙዎቹ (አሁን አሁን የተወሰነ በጎ ለውጥ ቢኖርም) የመንግሥትም ሆኑ የግል የመገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ የጋዜጠኝነት ሙያና ሥነ-ምግባር ጉድለት ያለባቸው በመሆኑ ምክንያት የሚጫወቱት ሚና በተቃራኒው የአገራችንን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የሚያደናቅፍ ነው ማለት ይቻላል፡፡

መሠረታዊ የጋዜጠኝነት ተግባራት የሚባሉት ዜናና ሐሳብ ማመንጨትን ጨምሮ ኅብረተሰብን የማስተማር፣ የማሳወቅ፣ የማዝናናትና በአንድ የተወሰነ ዓላማ ላይ የሕዝብ ንቅናቄ መፍጠርን የመሳሰሉ ሰፊ ተግባራትን የሚያካትት ቢሆንም የእኛ አገር ጋዜጣዎች ግን በመንግሥት በኩል የሚገኙት የታማኝነት፣ በግሉ በኩል ያሉት ደግሞ የተቃውሞ ወይም የአሉታዊነት /Adversary/ አቋም ከማራመድ ባለፈ ሚዛናዊነት ያለው ተግባር ሲያከናውኑ እምብዛም አይታዩም፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን የመንግሥት ጋዜጠኞች ሚና "ልማታዊ ጋዜጠኝነት" ነው ተብሎ በመንግሥት በኩል ጥቅልና ጠባብ የሆነ መጠሪያ ስም በይፋ ተሰጥቶታል፡፡

የአገራችን መገናኛ ብዙኃን በዚህ የማይጠበቅ ደረጃ ለመገኘታቸው ዋናውን ተጠያቂነት መውሰድ የሚገባው መንግሥት ወይም ገዥው ፓርቲ መሆኑ ብዙም አከራካሪ አይደለም፡፡

አገሪቱ በአንድ ጊዜ በግል መገናኛ ብዙኃን መጥለቅለቅ አለባት ብሎ ማመን በራሱ ችግር ያለበትና የአገሪቱን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ አመለካከት ቢሆንም፣ ኢህአዴግ ለዐሥራ ስምንት ዓመታት በነበረው የመንግሥትነት ቆይታ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉት መገናኛ ብዙኃን በአግባቡ ሕዝቡን እንዲያገለግሉ በማድረግም ሆነ አግባብ ባለው መጠን የግል መገናኛ ብዙኃን እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ በማድረግ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ አልተወጣም፡፡ ለዚህም እስካሁን በዐሥራ ስምንት ዓመታት ሂደት ውስጥ አንድም የግል ቴሌቪዥንና የአጭርና የመካከለኛ ሞገድ ሬዲዮ ጣቢያ በአገራችን አለመኖሩ በቂ ማረጋገጫ ነው፡፡

እነዚህ የግል መገናኛ ብዙኃን በአገራችን እንዳይኖሩ የተደረገው ሆን ተብሎ ካልሆነ በስተቀር እንዳይኖሩ ስለመደረጋቸው ሌላ ምንም ዓይነት ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ እንዲያውም በየትኛውም ዓይነት የመገናኛ ብዙኃን ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ የግል ባለሀብቶች ባሉበት ሁኔታ መንግሥት እስካሁን ከከተሞች ርቀው መሠራጨት የማይችሉ የግል ጋዜጦችንና ሁለት ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎችን ብቻ ለይቶ መፍቀዱ በግልጽ የሚያሳዩው አብዛኛውን የአገሪቱን ሕዝብ መድረስ የሚችል መገናኛ ብዙኃን እንዳይኖሩ የጠነከረ ፍላጐትና እምነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ለእኛ አገር የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ የግል መገናኛ ብዙኃን ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ኢትዮጵያ አንድ ብቸኛ የቴሌቪዥን ቻናል ያላት አገር ለመሆኗ ግን ማንንም ሊያሳምን የሚችል ምክንያት ማቅረብ አይቻልም፡፡ የሆኖ ሆኖ የአገራችን መገናኛ ብዙኃን የሚገኙበትን ሁኔታ በአግባቡ መገምገም ይቻል ዘንድ የመንግሥትንና የግል መገናኛ ብዙኃንን ለያይቶ ለማቅረብ መሞከሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በቅርብ ዓመታት በምርጫ ወቅት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች መድረክ ለመስጠት ያደረጉት ጥረት፣ መንግሥት የሚያከናውናቸውን የልማት ተግባራት ለሕዝብ በማስታወቅ ረገድ ያላቸው ከፍተኛ ሚናና በተለያዩ ባህላዊና ማኀበራዊ ጉዳዮች በተለይም የብሔር-ብሔረሰቦችን ባህል በማስተዋወቅ ረገድ የሚሠሯቸው ፕሮግራሞች ጠቃሚ መሆናቸው፣ በተጨማሪ ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን በመከላከል ረገድና በተለያዩ መሰል ጉዳዮች የሚጫዎቷቸው ሚናዎች በጠንካራና በበጎ ጐንነት ሊጠቀሱላቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ተቋማት በሕዝብ ሀብት የተቋቋሙና የሚተዳደሩ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ከመሆናቸው አኳያ ከገለልተኝነትና ሁሉንም የኀብረተሰብ ክፍል በሚዛናዊነት ከማገልገል አንጻር ብዙ ጉድለትና ድክመት ያለባቸው ናቸው፡፡

ይኸውም ከምርጫ ወቅት ውጭ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሐሳብ አብዛኛውን ጊዜ የማያስተናግዱ መሆናቸው፣ በተለያዩ አገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ከገዥው ፓርቲ አቋም የተለየ ነፃ የሕዝብ አስተያየቶችን በስፋት የማያቀርቡ መሆናቸው፣ በውስጣቸውም የሚሠሩ አብዛኛዎቹ ጋዜጠኞች ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ወገንተኝነት አቋማቸውን የሚያንፀባርቁ መሆናቸው፣ የዜናና የተለያዩ ፕሮግራሞች አቀራረባቸው ከሌሎች አገሮች መገናኛ ብዙኃን የጥራት ደረጃ ጋር የሚመጣጠን ብቻ ሳይሆን የሚቀራረብ አለመሆኑ፣ አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች በአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ውጤታማ የሆኑ ጉዳዮችን (Success Story) ብቻ እንጂ ሌሎች በአገሪቱ የሚታዩ ድክመቶችንና ችግሮችን በሚዛናዊነት የማያቀርቡ በመሆናቸው፣ በአጠቃላይም አብዛኛዎቹ የሚያቀርቧቸው ፕሮግራሞቻቸው በደረቅ ፕሮፓጋንዳ የተሞሉና ገዥው ፓርቲ የሚያደሉ በመሆናቸው ምክንያት የመደመጥ መስህብ የሌላቸውና የአብዛኛውን ሕዝብ አመኔታ ያጡ መሆናቸው በደካማ ጐንነት ሊጠቀሱባቸው የሚችሉ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡

በእነዚህ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ተቀጥረው የሚሠሩትን ጋዜጠኞችም ስናይ አንዳንድ አቅምና ሁኔታው በፈቀደላቸው መጠን ሞያውን አክብረው ሊሠሩ የሚሞክሩ ጋዜጠኞች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንዶቹ ግን ኃላፊነታቸው መንግሥትን ማወደስ ብቻ መስሎ የሚታያቸውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን የአፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊ ከነበሩት ከደብተራ ዘነብ ያልተሻለ ሚና ያላቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የወቅቱ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በይዘታቸው በደርግ ጊዜ ከነበረው ብዙም ያልተለዩ ስልት በመከተል የገዥው ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ሆነው መቀጠላቸው፣ በአንድ በኩል ሕዝቡ ስለ አገሩ ጉዳይ እውነተኛ መረጃ ለማግኘት ሲል ትኩረቱን ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ወደሚተላለፉ ሬዲዮ ጣቢያዎችና ወደ ግሉ ፕሬስ እንዲያደርግ ግፊት የፈጠረ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚሠራጩ ሬዲዮ ጣቢያዎችም ሆኑ የግሉ ፕሬሶች በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን የመረጃ ክፍተት በማየት በአብዛኛው የመንግሥትን ደካማ ጐን በመተቸትና በማሳጣት ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ ምክንያት ፈጥሮላቸዋል፡፡

በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኙት መገናኛ ብዙኃን ሁልጊዜ ቪ-ኦ-ኤን፣ ዶቸ ቬለንና የግሉን ፕሬስ በአድሏዊነት ከመክሰስ ይልቅ የመንግሥትን በጎ ውጤቶች ብቻ ሳይሆን ድክመቶችና ችግሮች ጭምር በአግባቡ የሚዘግቡ ቢሆን ኖሮ ሕዝቡ የመንግሥትንም ሆነ የግሉን መገናኛ ብዙኃን የሚያይበትና የሚመዝንበት መንገድ ከወቅቱ ሁኔታ በእጅጉ በተለየ ምክንያታዊ በሆነ ነበር፡፡ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በዚህ ዓይነቱ የተበላሸ አቋም ላይ መገኘታቸው የአገሪቱን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ብቻ ሳይሆን ራሱን ገዥውን ፓርቲ ጭምር በእጅጉ

እየጐዳ የሚገኝ ነው፡፡ ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ከፈጸማቸው አገርን የሚጐዱ ድርጊቶች በላይ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ሕዝብንና ገዥውን ፓርቲ በማራራቅና ሆድና ጀርባ በማድረግ ረገድ የተጫወቱት ሚና ቀላል የማይባል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ ለዐሥራ ሰባት ዓመታት ያህል በትጥቅ ትግል በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ በደርግ የፕሮፓጋንዳ ሥራ ምን ያህል እንደተሰላቸና ሕዝቡም በእውነትና በፕሮፓጋንዳ መካከል ያለውን ልዩነት በመረዳት ረገድ ያለውን ብቃት በአግባቡ ሳያጤን ከደርግ የሚመሳሰል ስልት ይዞ መቀጠሉ ትልቁ ስህተቱ ነው፡፡

ኢህአዴግ ለሕዝብ ተገቢ መረጃ መስጠት ብቻ ሳይሆን "አንድን ነገር ከመጠን በላይ ደግሞ ደጋግሞ በመናገር ሕዝብን ማንቃትና ማሳመን ይቻላል" የሚል ኋላ ቀር ፖለቲካ አስተሳሰብ የመነጨ የተሳሳተ ስልት በመከተሉ ሕዝቡ ከመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የበለጠ እንዲርቅና በእነሱም ላይ ያለው እምነት የበለጠ እየተሟጠጠ እንዲሄድ አደረገ እንጂ ሕዝብና መንግሥትን ማቀራረብ አልቻለም፡፡ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡት ፕሮግራሞች አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይና አሰልቺ ናቸው፡፡ አንድ የቢሮ ኃላፊ ወይም አርሶ አደር ለሰዓታት ቃለ-መጠይቅ የሚሰጥበት አሰልቺ ፕሮግራም ከእኛ አገር ውጭ በሌላ በየትኛውም አገር አለ ማለት አይቻልም፡፡ ስለ ጐተራ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድይ ወይም ስለ ተከዜ የኃይል ማመንጫ ግድብ ያለማጋነን በመቶዎች ለሚቆጠር ጊዜ ዜና የሚያቀርብ መገናኛ ብዙኃን በሕዝቡ ይወደዳል ብሎ መንግሥት እንዴት ሊያስብ እንደሚችል ምክንያቱን መረዳት ይከብዳል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ሕዝቡ ወደ የሚያዳምጣቸው እንደ ኀምሳ ሎሚ፣ ሻይ ቡና፣ ዐውደ-ሰብ፣ ፊት ለፊትና ኢትዮጵያን አይደል (ሻይ ቡናና ኢትዮጵያን አይደል በቅርብ ጊዜ ሥራ ጀምረዋል) ዓይነቶቹ ቶክሾዎች ብቅ ባሉ ማግስት በአጭር እንዲቀጩ መደረጉን ስናይ ኢህአዴግ መገናኛ ብዙኃንን በሚመለከት ምን ዓይነት ጊዜ ያለፈበትና ከደርግ አሠራር ብዙም ያልተለየ ፍልስፍና እንዳለው ያሳየናል፡፡ ዓለም እየጠበበችና መረጃ በድንበር የማይገደብ በሆነበት በአሁኑ ወቅት እንዲህ ዓይነቱ ስልት የትም እንደማያደርስ ግን ኢህአዴግ ብዙም የተገነዘበው አይመስልም፡፡

መንግሥት ይጠቅመኛል ብሎ ካሰበ የራሱን መገናኛ ብዙኃን በዚህ መልክ ቢጠቀምባቸው የማያስደንቅ ቢሆንም፣ ነገር ግን መንግሥት ይህንን የሚያደርገው ሕዝቡ ሌሎች አማራጭ የብዙኃን መገናኛዎች እንዳያገኝ ሆን ብሎ አማራጭ አሳጥቶ መሆኑ ሲታይ ግን በሐሳብ ነፃነት መከበር ላይ ሥርዓቱ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ችግር ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ መንግሥት እንዲህ ዓይነቱን የተሳሳተ የፕሮፓጋንዳ ስልት በገፋበት ቁጥር እሱ በሚፈልገው መጠን ሕዝብን ማሳመን ይቅርና የሚያስተላልፋቸው እውነተኛና ትክክለኛ መረጃዎች ጭምር በሕዝቡ ዘንድ

አብዛኛውን ጊዜ በጥርጣሬ እንዲታዩ የሚያደርግ አደጋ እየፈጠረ መጥቷል፡፡ መንግሥት በራሱ የተሳሳተ የፕሮፓጋንዳ ስልት የቱንም ያህል አገርና ሕዝብን የሚጠቅሙ ተግባራትን ቢያከናውን በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ሊያገኝ የማይችልበትን አደጋ በራሱ ላይ እየፈጠረ እንደሚገኝ በግልጽ ይታያል፡፡ ኢህአዴግ አምስት ዓመት ሙሉ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የሚያስተላልፈው ፕሮፓጋንዳ ከምርጫ ቅስቀሳ ያልተለየ ይዘት የሚታይበት በመሆኑ ወደፊት በምርጫ ወቅት ጭምር የሚኖረውን የመደመጥ ዕድል የበለጠ የሚያጠብ የተሳሳተ ስልት እየተጠቀመ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው፡፡ እንዲያውም አሁን አሁን ከሳተላይት ዲሽ መስፋፋት ጋር ተያይዞ የገንዘብ አቅማቸው የሚፈቅድላቸው ሰዎች ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጋር እንዳይገናኙ ሆነው ከተሰነባበቱ ቆይተዋል፡፡

ለዚህም ነው በቅርቡ መነጋገሪያ በነበረ አንድ ቀልድ የወቅቱ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አንባቢዎች ዜና ከማንበባቸው በፊት "ዲሽ የሌላችሁ እንደምን አመሻችሁ" በማለት ንግግራቸውን እንደሚጀምሩ ሲነገር የሰማነው፡፡ ሳተላይት ዲሽ አሁን ካለበት ዋጋ ወደፊት በግማሽ ቢወርድ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በምን ዓይነት አደጋ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ የሚገርመው በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የሚታየው ድክመት ሊያከራክር በማይቻልበት ሁኔታ ግልጽ ሆኖ እየታየ ባለበት በአሁኑ ወቅትም ገዥው ፓርቲ ከብዙ ጊዜ ጩኸት በኋላ ማስታወቂያ ሚኒስቴርን በአዋጅ ያፈረሰ ቢሆንም በተግባር ግን አዲስና የተሻለ አሠራር ሲፈጥር እየታየ አይደለም፡፡ እንዲያውም ከምርጫ 97 በኋላ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ለተለያዩ አመለካከቶች ራሳቸውን ክፍት በማድረግ ረገድ የበለጠ እየጠበቡ እንጂ እየሰፉ አልመጡም፡፡

ኢህአዴግ ሁሌጊዜ በሥሩ የሚገኙት መገናኛ ብዙኃን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ እንደሆነ ሽንጡን ገትሮ ሲከራከር የሚደመጥ ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱ ክርክር ቢያንስ እንደ እኔ ዓይነቱን በቀጥታ የችግሩ ሰለባ የሆነ ሰው ሊያሳምን አይችልም፡፡ ፓርላማ ውስጥ ለአምስት ወይም ለስድስት ደቂቃ ያህል በአንድ ጉዳይ ላይ ከማቀርበው ድጋፍም ተቃውሞም ተቀላቅሎ የቀረበበት ንግግሬ ውስጥ- "ክቡር ሚኒስትር - ሪፖርቱ ስለቀረበ በጣም አመሠግናለሁ" የምትልን ሐረግ ቆርጦ በማውጣትና በመዘገብ መንግሥትን ሙሉ በሙሉ የደገፍኩ አስመስሎ የድጋፍ ዜና የሚሠራን መገናኛ ብዙኃን በየትኛውም መመዘኛ ኃላፊነት የሚሰማውና ገለልተኛ ነው ብዬ ላምን አልችልም፡፡

አንድ መገናኛ ብዙኃን በተቃውሞም ሆነ በድጋፍ የተሰጡ አስተያየቶችን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በመዘገብ ምክንያታዊ የፖለቲካ ባህልን ማጠናከር ሲገባው የድጋፍ ሐሳቦችን ብቻ

እየመረጠ ማቅረቡ ተቋሙ ምን ያህል ጭፍን ድጋፍን ቋሚ ፖሊሲው አድርጐ የሚያራምድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የድጋፍ ሐሳብን ለፖለቲካ መጠቀሚያነት የሚያውል አሠራርም ተቃዋሚዎች ጭፍን ተቃውሞ አራማጅ መሆናቸውን የበለጠ የሚያጠናክር እንጂ ወደ ምክንያታዊ ፖለቲካ እንዲገቡ የሚያበረታታ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከንግግራቸው ውስጥ የድጋፍ ንግግራቸው ብቻ እየተቆረጠ ለሕዝብ ተዛብቶ የሚቀርብ ከሆነ ተቃዋሚዎች ለመንግሥት ጋዜጠኞች ይህንን ዕድል ላለመስጠት ሲሉ ምንም ዓይነት የድጋፍ ንግግር ሳይጨምሩ ተቃውሞአቸውን ብቻ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን የገዥው ፓርቲ የፕሮፖጋንዳ መሣሪያ ሆነው የሚያገለግሉ፣ በአሠራራቸው ተገቢ ተጠያቂነትና ሚዛናዊነት የማይታይባቸው፣ ወገንተኛዊነት ተግባራቸውም የሕዝቡን እምነት ያጡና ሕዝብንና መንግሥትን በማራራቅ ረገድ ከፍተኛ አሉታዊ ሚና እየተጫወቱ የሚገኙ ተቋማት ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ወደፊትም በዙሪያቸው የሚታየው የአሠራር ችግር መሠረታዊ በሆነ መልኩ ለውጥ እስካልተደረገበት ድረስ ለአገራችን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ በአግባቡ ሊወጡ ይችላሉ ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የግል መገናኛ ብዙኃን የሚገኙበትን ሁኔታ ለመገምገም ስንሞክር በቅድሚያ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ ከሥርጭት ስፋት አንጻር ለመሆኑ በአገራችን የግል መገናኛ ብዙኃን “አለ” ሊባል በሚችልበት ደረጃ ላይ ይገኛል ወይ? የሚል ይሆናል፡፡ ከላይ በመንደርደሪያችን ላይ ለማየት ከሞከርነው መረጃ አንጻር የግሉን መገናኛ ብዙኃን ሽፋን ለመገምገም ስንሞክር በርግጥም እንዳለ የሚቆጠር አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአገራችን በቅርቡ ሥርጭታቸው በአዲስ አበባ ከተማ የተወሰነ ሁለት የግል ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ሥራ ከመጀመራቸው በስተቀር በአገራችን አንድም ቴሌቭዥን ሆነ ከአዲስ አበባ ውጭ የሚሰማ በመካከለኛና አጭር ሞገድ የሚተላለፍ ሬዲዮ ጣቢያ የለም፡፡ ስለዚህ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የግል መገናኛ ብዙኃንን መኖር ወክለው በሥራ ላይ የሚገኙት ጥቂት የግል ጋዜጦች ብቻ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የእነዚህን የግል ጋዜጦች ሥርጭት ለማየት ስንሞክር ደግሞ በአንድ ከፍተኛ ሥርጭት አለበት በሚባል ቀን በመላ አገሪቱ ታትመው የሚሠራጩት ጋዜጦች ድምር ቢበዛ ከ60 ሺህ ቅጅዎች የሚበልጥ አይደለም፡፡ ይህንን ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ጋር ስናነፃፅረው መድረስ የሚችለው የሕዝብ ብዛት ከ0.1% ያነሰ በመሆኑ የግል መገናኛ ብዙኃን በተግባር በአገራችን አለ ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ የሆነ ሆኖ እነዚህ ጥቂት ጋዜጦችም ቢሆኑ በአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ላይ የራሳቸው አወንታዊም ሆነ አሉታዊ

ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ስለሆነ እነሱ የሚገኙበትንም ሆኔታ ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለመገምገም መሞከሩ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በአገራችን የሚገኙ የግል ጋዜጦች ከመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በተለየ የመንግሥትን ጉድለቶችና ድክመቶች በድፍረት በማጋለጥ፣ በየጊዜው በሕዝቡ ላይ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በማውገዝ፣ ለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ለሌሎች ነፃ አስተሳሰብ ላላቸው የኀብረተሰብ ክፍሎችና ግለሰቦች መድረክ በመፍጠርና የሕዝቡን የንባብ ባህል በማዳበር ረገድ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የተጫወቱት ሚና በጠንካራ ጐንነት ሊጠቀሱላቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች ናቸው፡፡ በራሳቸው ድክመትና ጥፋት ለችግር የሚጋለጡ አንዳንድ ጋዜጠኞች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖም የሥርዓቱን ገመናዎች ማጋለጣቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው ለአፈና፣ ለእሥራትና ለስደት የተዳረጉት ጋዜጠኞችም በቁጥር ቀላል የሚባል አይደሉም፡፡

የግል ጋዜጦችን ደካማ ጐን ለማየት ስንሞክር በግል ጋዜጠኝነትም የሚሠሩት ዜጐች እንደ ሁላችንም የዚሁ ኅብረተሰብ ውጤት በመሆናቸውና በመስኩም ያላቸው ልምድ ገና ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያት በሁላችንም ላይ የሚታየው ድክመት በነሱም ውስጥ ይታያል፡፡ በነፃ ጋዜጦች ዙሪያ ቀደም ሲልም ሆነ በአሁኑ ወቅት ገለልተኛ አቋም ይዘው ሕዝቡን ለማገልገል የሚሞክሩ ጥቂት ጋዜጠኞች ያሉ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ለኀትመት የበቁት (ብዙዎቹ ከስመዋል) የግል ጋዜጦች ግን ሚናቸው ዴሞክራሲንና የሐሳብ ነፃነትን የሚያጠናክር ሳይሆን የሚጻረር ነበር ማለት ይቻላል፡፡

አብዛኛዎቹ የግል ጋዜጠኞች "ጋዜጠኛ" ለመባል የሚያበቃ ሥነ-ምግባርና ዕውቀት ያልነበራቸው፣ ከመንግሥት መገናኛ ብዙኃን በተቃራኒ መንግሥትን በጭፍን የሚነቅፉና ተቃዋሚዎችን በጭፍን የሚደግፉ፣ ያለምንም ተጨባጭ መረጃ የአገርን፣ የድርጅትንና የግለሰብን ስም የሚያጐድፍ የፈጠራ ወሬ የሚያሠራጩ፣ ለአገር ብሄራዊ ደኅንነት ደንታ የሌላቸውና ዋና ዓላማቸውንም በርካሽ ፕሮፖጋንዳ ገንዘብ መሰብሰብን ያደረጉ እንደነበሩ በግልጽ ታይቷል፡፡ አንዳንዶቹም ከምርጫ 97 በፊት በሥራ ላይ የነበሩ የግል ጋዜጠኞች ለእነሱ አስተሳሰብ የተመቸ ሁኔታ ቢያጋጥማቸውና በተለይም የሬዲዮ ጣቢያ ዓይነት ጉልበት ያለው መገናኛ ብዙኃን በእጃቸው ቢገባ፣ ኢትዮጵያ ሩዋንዳ ላስተናገደችው ዓይነት ዘግናኝ አደጋ ልትጋለጥ የማትችልበት ምክንያት ይኖራል ብሎ በርግጠኝነት ለመገመት አይቻልም፡፡

አንዳንዶቹ የግል ጋዜጠኞች ከሞያው ሥነ-ምግባር በጣም በራቀ ዝቅጠት ላይ የሚገኙ ከመሆናቸው የተነሣ በጋዜጣቸው የፊት ገጽ ላይ ምን ዓይነት ጯሂ ዜና ይዘው መውጣት እንዳለባቸው ብዙውን ጊዜ የሚመክሯቸው ጋዜጣ እያዞሩ የሚሸጡት የ12 እና 13 ዓመት ልጆች ነበሩ። የአንባቢውን ቀልብ የሚስብና የተሻለ ገበያ የሚፈጥር እስከሆነ ድረስ የማይጠቅም ብቻ ሳይሆን ያልተከሠተ ዜና ፈጥሮ መጻፍም ለእነዚህ ጋዜጠኞች የሚከብድ ነገር አልነበረም። የወደዱትን ሰው ጀግና ማድረግና የጠሉትን ሰው ከሃዲና ባንዳ አድርጐ ማቅረብም ፈቃድ ያወጡበት ሥራ ያህል የተለመደ ነው።

በአንድ ወቅት እነዚህ ጋዜጠኞች ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ አሥነዋሪ ሥራ መስክ ፈጥረው ጭምር ታላቅ በሆነው የጋዜጠኛነት ሙያ ይነግዱበት ነበር። ይኸውም አንድ ሰው ወደ ውጭ አገር ለመሰደድ ሲፈልግ ወይም ተሰዶ ከአገር ከወጣ በኋላ ፎቶ ግራፉን ለእነዚህ ጋዜጦች ይሰጥና "ከቤቱ እንደወጣ ቀረ" በሚል ርእስ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ በአምስት መቶ ብር ክፍያ ጋዜጣው ላይ ይወጣለታል። ከዚያ በኋላ ስደተኛው የፖለቲካ ጥገኝነት ለሚጠይቅበት አገር ፍርድ ቤት የፖለቲካ ስደተኛ መሆኑን ለማሳመን መረጃ ሆኖ የሚቀርበው ይኸው ጋዜጣ ይሆናል ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜም ስደተኞቹ ጠቀም ያለ ገንዘብ መክፈል ከቻሉ በታጣቂዎች ታፍነው ታስረው እንደነበርና ድብደባም እንደደረሰባቸው ተደርጐ ሰፊ የፈጠራ ዜናና ሃተታ ይሰራላቸዋል።

የሚገርመው በዚህ ሁኔታ በጋዜጠኛነት ሙያ ላይ የሚነግዱት ሰዎች በዚህ መልክ በሚፈጸሙት ወንጀል በሕግ የመጠዬቅ አደጋ እንዳይገጥማቸው በማሰብ ስማቸው በዋና አዘጋጅነት ጋዜጣው ላይ እንዲሰፍር አይደረግም። ስማቸውን በሳምንት ሃምሣ ብር እያከራዩ የሚተዳደሩ ድሀ ወጣቶች ስላሉ ጋዜጣው ላይ ዋና አዘጋጅ ተብሎ ስማቸው የሚጻፈውና የሕግ ተጠያቂነትም ሲመጣ ተይዘው የሚታሰሩት እነዚህ ድሀ ወጣቶች ናቸው። የበለጠ የሚገርመው በነፃ ፕሬስ ስም እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ወንጀል እንደሚፈጸም የጋዜጠኞች ማኅበርም ሆነ ሌሎች ሞያውንና ሕግን አክብረው የሚሠሩት ጋዜጠኞች እውነቱን በሚገባ እያወቁ ለሕዝብ ለማጋለጥ ግን ደፍረው አያውቁም። ሌላው ቀርቶ የመንግሥት ጋዜጠኞችን ያለርኅራሄ ስናወግዝ የምንደመጠው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃ ፕሬስ ስም እንዲህ ዓይነት አፀያፊ ተግባር እንደሚፈጸም በሚገባ እያወቅን እነዚህ ጋዜጦች በመንግሥት ተጽዕኖ ደረሰባቸው ብለን እናወግዛለን እንጂ ስህተታቸውን እንዲያርሙ ለመናገር አንደፍርም።

በ1993 ዓ.ም. በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ አዘጋጅነት በተካሄደ አንድ የፓርቲዎች የክርክር መድረክ ላይ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡና

ገንዘብ ካልሰጣችሁን ስማችሁን እናጠፋለን የሚሉ ጋዜጠኞች በአገራችን ስለመኖራቸው በመናገሬ “ኢትኦጵ” በመባል ይታወቅ የነበረው ጋዜጣ የኔንና አባል የሆንኩበትን ፓርቲ ስም ማጥፋት የጀመረው ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነበር፡፡ ከዚህ ዓይነቱ የጋዜጦች የተበላሸ የአሠራር ባህል የምንረዳው ገዥው ፓርቲ ለራሱ የፖለቲካ ጥቅም የሚፈጽመው አፈና መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እስካሁን በመንግሥት በኩል ሲደርስባቸው ለነበረው ተጠያቂነት አንዳንድ የነፃው-ፕሬስ ጋዜጠኞች የራሳቸው ከፍተኛ ድርሻም የነበራቸው መሆኑን ነው፡፡ በአገራችን የጋዜጠኝነት ሙያንና ሕግን አክብረው የሚሠሩ ጋዜጠኞችን መብት የማይጋፋ፣ ነገር ግን ሥርዓት አልበኛ በሆኑ ጋዜጠኞች ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የፕሬስ ሕግ አስፈላጊ የሚሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በርግጥ ጋዜጦች ከፖለቲካ ቫይረስ ተሸካሚነትና ከክፋት በመነጨ የሚፈጽሙት ስህተት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የጋዜጠኝነትን ሥነ-ምግባር አክብረው የሚሠሩ በርካታ ጋዜጠኞች በአገራችን ላለመኖራቸው እስካሁን በአገራችን ጋዜጠኞችን በብቃት ለማሠልጠን የሚችል ጠንካራ ተቋም አለመኖሩም አንዱ ምክንያት ነው ሊባል ይችላል፡፡

እነዚህ ኃላፊነት የማይሰማቸው ጋዜጠኞች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ከሚፈጽሙት እርካሽ ተግባር በተጨማሪ ኅብረተሰቡ በአሁኑ ወቅት የተካረረ የፖለቲካ አቋም እንዲይዝና የአገራችን ፖለቲካም ከብሔራዊ መግባባትና ከምክንያታዊ ፖለቲካ እንዲርቅ በማድረግ ረገድም የነበራቸው ድርሻ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በእነዚህ ጽንፈኛ አቋም ባላቸው ጋዜጠኞች የሚመሩት ጋዜጦች የተቃዋሚ ፓርቲዎችና የሕዝቡ ብቸኛ መገናኛ መንገዶች ስለነበሩ ከተቃዋሚ ፓርቲዎቹ በላይ ሕዝቡን በራሳቸው መንገድ የመቅረጽ አቅም ነበራቸው፡፡ በአንድ በኩል ተቃዋሚዎች የተለያዩ አገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በየጊዜው ከሚያራምዷቸው አቋሞች ውስጥ ለእነሱ የሚጥማቸውን አጉልተው ወደ ሕዝብ በማሠራጨት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸውንና በውጭ አገር ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚላኩላቸውን ጽንፈኛ አቋሞች የሕዝቡ አቋሞች አስመስለው በማራገብ ይጫወቱ የነበረው አፍራሽ ሚና ቀላል አልነበረም፡፡ በአጠቃላይ የተቃውሞውን ጉራ የፖለቲካ አጀንዳ በሚፈልጉት አቅጣጫ የሚመሩት በዋናነት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይሆኑ ጋዜጦች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ በርካታ የህበረተሰብ ክፍል በጋዜጣ ላይ የተጻፈና በሬዲዮ የተነገረ ወሬ ሰዎች በአፋቸው ሲናገሩት ካዳመጠው በተለየ እውነተኛና ትክክለኛ ወሬ እንደሆነ አድርጐ ስለሚያስብ ጋዜጦች እውነትም ይጻፉ ውሸት በኅብረተሰቡ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጐታል፡፡

እነዚህ ጋዜጦች ከእነሱ አጀንዳ ጋር የሚሄደውን ፓርቲ ጀግናና አገር ወዳድ በሚል ሙገሳ የመሸለም፣ ከእነሱ አጀንዳ ጋር የማይሄደውን ፓርቲ ደግሞ ከሃዲና ባንዳ በሚል ፍረጃ

የመቅጣት አቅም ስለነበራቸው እንደ መንግሥት የራሳቸው ፖሊስና እሥር ቤት ባይኖራቸውም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ በጣም የሚፈሩ ኃይሎች ነበሩ፡፡ ተቃዋሚው ጐራ በሰከነ መንገድ ለራሱ፣ ለትግሉና ለአገሪቱ የሚጠቅመውን ምክንያታዊ ፖለቲካ እንዳያካሂድ በማድረግ ረገድ ጋዜጦች የነበራቸው ሚና ቀላል እንዳልነበረ ምርጫ 97 ላይ በገሃድ ታይቷል፡፡ ለተቃዋሚው ጐራ በጎ ምክር ይሰጡ የነበሩ የተወሰኑ ጋዜጦች የነበሩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅንጅት ፓርላማ እንዳይገባና አዲስ አበባ መስተዳድርን እንዳይረከብ በማድረግ ረገድ ከራሱ ከኢህአዴግና በስደት ላይ ከሚገኙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ባላነሰ ትልቁን ሚና የተጫወቱት ጋዜጦች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ የቅንጅት መሪዎች በወቅቱ ከእነዚህ ጋዜጦችና በስደት ላይ ከሚገኙት የፖለቲካ ኃይሎች ሊሠነዘርባቸው የሚችለውን ጊዜያዊ የስም ማጥፋት ዘመቻ ባይፈሩ ኖሮ ፓርላማ ለመግባትም ሆነ አዲስ አበባን ለመረከብ ይወስኑ እንደነበር ጥርጥር የለውም፡፡

ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት አብዛኛዎቹ የግል ጋዜጦች ያለፉበትን ሂደት ስናይ አንዳንድ በጎ ሚና የተጫዎቱ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፖለቲካ ትግሉ ደኅንነትና መጠናከር አንጻር የነበራቸው አጠቃላይ ሚና ሲታይ ግን ከጥቅማቸው ይልቅ ጉጅነታቸው ያመዝን ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ እነዚህ የግል ጋዜጦች ራሳቸው ጽንፈኛ የፖለቲካ አቋም አራማጅ ሆነው የአገሪቱን የፖለቲካ አየር ከመበከል ይልቅ መንግሥትን በድፍረት የሚተቹትን ያህል ተቃዋሚውን ጐራም በተወሰነ ደረጃ በሃቅ የመገምገምና የመተቸት ድፍረት አግኝተው ቢሆን ኖሮ እስካሁን በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የጐላ የተጠያቂነትና የግልጽነት ባህል ይዳብር ነበር፡፡ ትግሉም በጥላቻ አዙሪት ውስጥ ተተብትቦ በየጊዜው እየተዳከመ ከመሄድ ይልቅ እስካሁን ወደ ምክንያታዊ ፖለቲካና የመጠናከር አቅጣጫ ሊሸጋገር ይችል ነበር፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቅት የዚህ ዓይነቱ ርካሽና ጽንፈኛ አቋም የሚያራምዱት የግል ጋዜጦች ሙሉ በሙሉ ባይጠፉም በከፍተኛ መጠን እየቀነሱ በመምጣታቸው የተቃውሞ ትግሉም ወደ በጎ አቅጣጫ የሚገባበት የተሻለ ዕድል ሊኖረው ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ አብዛኛዎቹ የአገራችን ጋዜጠኞች ማለትም፣ የመንግሥት ጋዜጠኛም ይሁን የነፃው-ፕሬስ ጋዜጠኞች ተመሳሳይ ተግባር ሲፈጽሙ የሚታዩት በሌላ ምክንያት ሳይሆን እነሱም እንደ ሁላችን የዚሁ ኅብረተሰብ ውጤቶች በመሆናቸው ነው፡፡ የአገራችን ጋዜጠኞች ከአገር ውጭም ሄደው በውጭ አገር ሬዲዮ ጣቢያዎች ተቀጣሪ ሲሆኑ የአገራችንን ፖለቲካ በተመለከተ ተመሳሳይ አድልዎ ሲፈጽሙ የምናያቸው ችግሩ በዋናነት በእያንዳንዳችን ውስጥ ያለ የባህሪ ችግር ከመሆኑ በመነጨ ነው፡፡

በአጠቃላይ በአገራችን የመንግሥትም ሆነ የግሉ መገናኛ ብዙኃን አሁን ከሚገኙበት መሠረታዊ የአስተሳሰብና መዋቅራዊ ችግር ወጥተው ለአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የሚጠበቅባቸውን በጎ አስተዋፅኦ በአግባቡ ይወጡ ዘንድ የየበኩላቸውን የእርምት ርምጃ በድፍረት መውሰድ ይገባቸዋል፡፡ በአንድ በኩል መንግሥት በሞኖፖል አንቆ የያዘውን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ተገቢ ከሆነ የቁጥጥር ሥርዓት ጋር ለውድድር ክፍት ካላደረገ፣ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ የሚገኙ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንም ከአንድ ፓርቲ ብቸኛ ቁጥጥር ወጥተው ሕዝቡንና ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎችን በገለልተኝነት ማገልገል የማይችሉ ከሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የግል ጋዜጦችም የሞያውን ሥነ-ምግባር ጠብቀውና ሕግን አክብረው በገለልተኝነት ለሕዝቡ ትክክለኛ መረጃ በማቀበል ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የማይወጡ ከሆነና ነፃ ጋዜጦችን አንባቢ የሆነው ሕዝብም ጋዜጦችን መርጦ የሚገዛበት መመዘኛ የተሻለ ብስለት ማሳየት የማይችል ከሆነ መገናኛ ብዙኃን ሚናቸው ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ማጐልበት ሳይሆን ማደናቀፍ ሆኖ ሊቀጥል ይችላል፡፡

ምክንያቱም ፕሬስ ለአንድ የሐሳብ ነፃነትን አከብራለሁ ለሚልም ሆነ በአጠቃላይም ዴሞክራሲን እገነባለሁ ለሚል አገር ተጨማሪ ዳረጐት ሳይሆን ዋና መሠረት ነው፡፡ ሕዝቡ በለት ተዕለት ኑሮውም ሆነ በምርጫ ወቅት ለጥቅሙ የሚበጁትን አማራጭ ሀሳቦች በአግባቡ ሊገነዘብና በማናቸውም አስፈላጊ ጉዳዮች ዙሪያ በቂና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት የሚችለው በዋናነት በፕሬስ አማካይነት ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን ከባድ ኃላፊነት የተሸከመ የፕሬስ አካል በአንድ በኩል ከመንግሥትና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ በገለልተኝነት የሚያገለግልበት ሁኔታ ካልተመቻቸ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱ ፕሬሱ ኅብረተሰቡን በአግባቡ ለማገልገል ነፃነት ብቻ ሳይሆን የጋዜጠኝነት ሥነ-ምግባርን የማክበርና የኅብረተሰብን ደኅንነት የሞራል ዳኛ ሆኖ የመጠበቅ ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት መሆኑን በውል ካልተገነዘበ ድርሻው አዎንታዊ ሊሆን አይችልም፡፡ በአጠቃላይ በመንግሥትም ይሁን በግሉ መገናኛ ብዙኃን የሚሠሩ ጋዜጠኞች ሕግንና የሙያውን ሥነ-ምግባር በአግባቡ አክብረው እስከሠሩ ድረስም በየትኛውም አገር እንደሚታየው ለአንድ ርዕዮተ-ዓለምም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲ የወገንተኝነት ዝንባሌ ቢኖራቸው፣ ወገንተኝነታቸውን የሚያሳዩበት መንገድ ጤናማና ምክንያታዊ እስከሆነ ድረስ የሚጠቅም እንጂ የሚጐዳ አይሆንም፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ ሦስት

### *ከርእዮተ-ዓለምና ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር የሚነሡ የልዩነት ነጥቦች*

በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ በአገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች በተለያዩ አገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የሚያራምዷቸው አቋሞች በብዙ መልኩ ልዩነትም አንድነትም አጣምረው የያዙ ቢሆኑም በኅብረተሰቡ ዘንድ በዋናነት በእነዚህ በሚያራምዷቸው አጀንዳዎች ጠቃሚና ጉጅነት ሲመዘኑ አይታይም፡፡ በተለይም በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ የብሔር ጉዳይ ገዥ አጀንዳ እየሆነ ከመጣ በኋላ ርእዮተ-ዓለማዊ ክርክር ቦታ እያጣ መጥቷል ማለት ይቻላል ፡፡

ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ በአብዛኛው ኅብረተሰብ ሲደገፉ ወይም ሲነቀፉ የሚስተዋለው በአንድ በኩል የመንግሥት ሥልጣን ላይ በመቀመጣቸው ወይም የሥርዓቱ ተቃዋሚ በመሆናቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብሔረሰባዊ ማንነታቸው ወይም ስለ አገር አንድነት ባላቸው ጥቅል አቋም ነው፡፡ ኅብረተሰቡ ፓርቲዎችን የሚለካበት መንገድ በእነዚህ ጥቅልና ቁንፅል መመዘኛዎች ላይ የተንጠለጠለ ባለመሆኑ ምክንያትም በአገሪቱ የሚገኙ ፓርቲዎችም የሚያራምዷቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎች አጉልተው በማሳየት በዙሪያቸው የሕዝቡን ድጋፍ ለማሰባሰብ ከመጣር ይልቅ በሌሎች ጊዜያዊና ስሜታዊ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ትኩረት በማድረግ ጊዜያዊ ድጋፍን ለማግኘት ሲጥሩ ይታያሉ፡፡

በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዘመናዊው የዓለማችን የብዙኃን ፓርቲ አሰላለፍ አንጻር በየትኛው የርእዮተ-ዓለም ማዕቀፍ ውስጥ እንደሚገኙ ማወቅን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ከምንም ነገር በላይ የሥርዓቱ ተቃዋሚ መሆን የጋራ አጀንዳ ተደርጐ ስለሚታይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አሰላለፍ የቀኝ ይሁን የግራ ተለይቶ የማይታወቅበት ውጥንቅጥ ተፈጥሯል፡፡ ለዚህም ይመስላል በተቃዋሚው ጐራ የሚገኙ የተለያዩ አደረጃጀት፣ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አጀንዳ የሚያራምዱና ደካማና ጠንካራ የሆኑ ፓርቲዎች በሙሉ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በሚል የሕዝብ ግፊት አንድ ላይ ተጨፍልቀው እንዲቆሙ ሲፈለግ የሚታየው፡፡

የሆነ ሆኖ አገራችን ውስጥ በእንቅስቃሴ ላይ ከሚገኙ ፓርቲዎች ውስጥ እስካሁን ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫቸውን በሰነድ ደረጃ ተንትነው ለማቅረብ የሞከሩት ፓርቲዎች ኢህአዴግና ኢዴፓ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ በግልጽ አብዮታዊ ዴሞክራት ነኝ ብሎ

ራሱን የፈረጀ ሲሆን ኢዴፓም ሊበራል ዴሞክራት ነኝ ብሎ በግልጽ አውጇል፡፡ ሌሎቹ ፓርቲዎች ጥቅል የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ከመያዝና አንዳንድ ጊዜም ፈራ ተባ እያሉ በጥቅሉ ሊበራሎች ነን ወይም ሶሻል ዴሞክራቶች ነን ከማለት አልፈው ግልጽና ዝርዝር በሆነ ሁኔታ ራሳቸውን ያልፈረጁ ቢሆንም እናራምደዋለን ከሚሉት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቋም አንጻር ወደ የትኛው ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ ሊጠጋጉ እንደሚችሉ መገመት ይቻል ይሆናል፡፡ እነሱ ራሳቸውን ባልፈረጁበት ሁኔታ "የቀኝ ወይም የግራ ኃይል ናቸው" ብሎ በርግጠኛነት መናገር ተገቢም -አስፈላጊም ባይሆንም ቢያንስ ግን ኢህአዴግና ኢዴፓ ካላቸው ርእዮተ-ዓለማዊ ልዩነት አንጻር በተቃዋሚው ጐራ የሚገኙ የተለያዩ ድርጅቶች ለየትኛው ጐራ ቀረቤታ እንዳላቸው መገመት ይቻላል፡፡

በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ብሔረሰባዊ አደረጃጀት ያላቸው ድርጅቶች ከፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳ አንጻር ከኢህአዴግ ጋር የአፈጻጸም እንጂ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ልዩነት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ እነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ አቶ ገብሩ ዐሥራት የሚመሯቸው ፓርቲዎች መሠረታዊ የኢህአዴግን አስተሳሰቦች አካቶ በያዘው የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ላይ የአፈጻጸም እንጂ መሠረታዊ የይዘት ልዩነት እንዳላቸው ብዙውን ጊዜ ሲናገሩ አይደመጡም፡፡ የእነዚህ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች ዋነኛ ጥያቄ "በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ኢህአዴግ በአግባቡ እያከበራቸውና እየተገበራቸው አይደለም" የሚል እንጂ በሚከተሉት የአደረጃጀት ስልትም ሆነ ቁልፍ በሆኑ የፖለቲካና የኢኮኖሚው ጥያቄዎች ዙሪያ ከኢህአዴግ ጋር መሠረታዊ ልዩነት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡

ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ በአገሪቱ ፖለቲካ አንገብጋቢው ጥያቄ የብሔር ጥያቄ መሆኑን፣ የብሔር ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚለው የጆሴፍ ስታሊን መርህ ሕገ-መንግሥታዊ መብት መሆኑ ተገቢ መሆኑን፣ ከግለሰብ መብት ይልቅ የቡድን መብት ቀዳሚ መሆኑን፣ የአገሪቱ ፌደራላዊ አደረጃጀት ቋንቋን ወይም ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ያደረገ መሆኑን፣ መሬት በመንግሥት ቁጥጥርና ባለቤትነት ሥር መዋል አለበት የሚለውን የኮሚኒስት ርእዮት ከሞላ ጐደል የራሳቸው አጀንዳ አድርገው የተቀበሉ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ታቃዋሚ ድርጅቶች በአንዳንድ ውስን ጉዳዮችና በአፈጻጸም ደረጃ ያላቸው ልዩነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ አኳያ ከኢህአዴግ ያልተለዩና ግራ-ዘመም ሊባሉ የሚችሉ ድርጅቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት የሚከተሉትን እንደ መኢአድና የአንድነት ፓርቲ ዓይነቶቹን ድርጅቶች ስንመለከት ደግሞ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የሚያራምዷቸው አቋሞች ግልጽነት የሚጐድላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በበርካታ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከኢዴፓ ጋር ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ አቋም አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ እንደ መኢአድ ዓይነቶቹ ድርጅቶች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ከልክ ያለፈ ወግ-አጥባቂነት የሚታይባቸው ቢሆኑም ኢዴፓን ጨምሮ አብዛኛዎቹ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የሚገኙ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ፓርቲዎች በአንፃራዊነት ቀኝ-ዘመም ወይም ለዘብተኛ ኃይሎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

በኢህአዴግና በሌሎቹ የብሔር አደረጃጀትን የሚከተሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል መሠረታዊ የአስተሳሰብ አንድነት ኖሮ የአፈጻጸም ልዩነት የመኖሩን ያህል፣ በኢዴፓና በሌሎቹ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ባላቸው ድርጅቶች መካከልም በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አጀንዳዎች ዙሪያ መሠረታዊ የአስተሳሰብ መቀራረብ ያለ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለያዩ የትግል ስትራቴጂዎች፣ መርሆዎች፣ ታክቲኮችና አሰራሮች ዙሪያ በዚያው መጠን ልዩነት መኖሩም ግልጽ ነው፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ከፖለቲካና ኢኮኖሚ አጀንዳ አንጻር ከኢህአዴግ በጣም የተለዩ ቢሆኑም ከሚያራምዱት ጭፍን የፖለቲካ ባህል አንጻር ከኢህአዴግ ጋር አንድ ዓይነት ባህሪ የሚጋሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ኢዴፓ በአንድ በኩል የሕዝቡ የተቃውሞና የድጋፍ መመዘኛ በደፈናው ገዥ ፓርቲነት ወይም ተቃዋሚነት መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በሚል ስሜታዊ መፈክር ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሙሉ በጅምላ በአንድ ላይ ተባብረው እንዲቆሙ የሚያቀርበውን ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ለመቃወም የተገደደው በአገሪቱ የሚገኙት የፖለቲካ ኃይሎች ከተለያዩ መመዘኛ አንጻር ምስቅልቅል ባህሪና ማንነት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ጥቅል በሆነ መልኩ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎችን አሰላለፍ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ሁሉም ተቃዋሚዎች በጅምላ አንድ እንዲሆኑ የሚቻልበትም ሆነ የሚያስፈልግበት ተጨባጭ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡ የፓርቲዎች የትብብር ጥያቄ ገዥ ፓርቲና ተቃዋሚ ፓርቲ ከመሆን የጠበበ መመዘኛ ወጥቶ ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ ወይም ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር መፈጸም ይገባዋል ወደሚል ምክንያታዊ መመዘኛ መለዎጥ ከቻለ አብዛኛዎቹ በብሔር ደረጃ የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አብረው መቆም ያለባቸው ከኢህአዴግ ጋር እንጂ ከሌሎቹ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ሊሆን አይገባውም፡፡ ምክንያቱም በመካከላቸው የሚታየው መሠረታዊ ልዩነት የፖለቲካና የኢኮኖሚ

አጀንዳ ሳይሆን በዋናነት የአፈጻጸም ልዩነት ስለሆነ በተለያዩ ጐራ ቆመው ከመፋለም ይልቅ በአንድነት ቆመው የአፈጻጸም ልዩነታቸውን በሂደት ለመፍታት ቢጥሩ የተሻለ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ኅብረ-ብሔራዊ የሆኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተቃዋሚነትን ብቻ እንደዋነኛ መመዘኛ በመውሰድ ከአገራዊ አጀንዳዎችም ሆነ ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ አንጻር ከማይመሳሰሏቸው በብሔር የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አብረው ለመሥራት መሞከራቸው ጊዜያዊ የሕዝብ ግፊትን ከማርገብ አልፎ ለራሳቸውም ሆነ ለአገሪቱ ዘለቄታዊ መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም፡፡ ኅብረ -ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአገራዊ አጀንዳዎች አንጻር ተቀራራቢ አቋም እስካላቸው ድረስ በትግል ታክቲክና አቀራረብ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አጥብበው አንድ ላይ ለመቆም መሞከር ነበባቸው እንጂ በርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ ከማይቀራረቧቸው ፓርቲዎች ጋር በጭፍን ኅብረት ለመፍጠር መሞከር የለባቸውም፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍን ግምት ውስጥ ያላስገባ የትብብር ግንኙነት ዞሮ ዞሮ በገዥው ፓርቲ ላይ ጊዜያዊ ተፅዕኖ ለማሳደር ይጠቅም እንደሆነ እንጂ የኋላ ኋላ አንድ የጋራ መንግሥት መሥርቶ አገርን ለማስተዳደር የሚያስችል ግንኙነት አይሆንም፡፡ በሆነ ተአምር ኢህአዴግ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ተኖ ቢጠፋ፣ ዛሬ የሥርዓቱ ተቃዋሚ በመሆናቸው ብቻ ወዳጅነት ለመፍጠር እየሞከሩ ያሉት ኅብረ- ብሔራዊ እና ብሔረሰባዊ አደረጃጀት ያላቸው የቀኝና የግራ ዘመም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ነገ እንደገና በሁለት ጐራ ተከፍለው አዲስ የፖለቲካ ግብግብ ውስጥ መግባታቸው የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ በማይዘልቅ ግንኙነት አዲስ መንግሥት ፈጥሮ በማግሥቱ እንደገና ከመፍረስና ሕዝቡን ከማሳዘን ይልቅ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ከወዲሁ ከገዥነትና ከተቃዋሚነት ቁንፅል መስፈርት ወጥተው ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ አንጻር ከሚቀራረቧቸው ፓርቲዎች ጋር ዘላቂና የሚያዋጣ ግንኙነት መመሥረት ይገባቸዋል፡፡

የሆነ ሆኖ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከርእዮተ-ዓለም አሰላለፍ አንጻር በአገራችን የሚገኙትን የሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎች አቋም ማወቅም ሆነ መተቸት አስቸጋሪ ነው፡፡ ቢያንስ ግን በአገራችን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ መሠረታዊ የልዩነት ምንጭ ሆነው በሚታዩት በሊበራል ዴሞክራሲና በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በመገምገም ቢያንስ በኢህአዴግና በኢዴፓ መካከል ያለውን ግልጽ የአስተሳሰብ ልዩነት ለማወቅ ስለሚቻል በሁለቱ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫዎች መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚከተለው በንጽጽር ለማየት እንሞክራለን፡፡

## 3.1 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እና የሊበራል ዴሞክራሲ ንጽጽር

### 3.1.1 አብዮታዊ ዴሞክራሲ

አብዮታዊ ዴሞክራትነት ከኢህአዴግ አመለካከት አንጻር የሚገለጽባቸው ባህርያቶች ምን ዓይነት እንደሆኑ ፓርቲው አሳትሞ ባሰራጫቸው በብዙ ሠነዶች ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ቢሆንም ከኢህአዴግ አመለካከት አንጻር የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አጭር ትርጉም /Definition/ ምን እንደሆነ ግን በየትኛውም የድርጅቱ ሰነድ ላይ ተጽፎ አይገኝም፡፡ ኢህአዴግ ከስያሜው ጀምሮ በእያንዳንዱ በሚያሰራጫቸው ሠነዶች ላይ ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህርያት ሳይገልጽ ያለፈበት አጋጣሚ ባይኖርም በትርጉም /Definition/ ደረጃ ግን ሆን ተብሎ ይሁን አይሁን ባይታወቅም አንድም ቦታ ላይ ተጽፎ አይገኝም፡፡ ስለዚህ መገለጫ ባህሪዎቹን በማየት ብቻ በኢህአዴግ አመለካከት አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምን ትርጉም እንደተሰጠው ለማየት መሞከር የሚቻል ቢሆንም በአጠቃላይ በንድፈ-ሐሳብ ደረጃ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ምን ማለት እንደሆነ በተሻለ ለመረዳት ግን በቅድሚያ የፅንሰ-ሐሳቡን ታሪካዊ አመጣጥ ማወቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ታሪካዊ አመጣጥ ለማወቅ በምናደርገው ጥረት የትኛውንም ዓይነት የጽሑፍ ሰነድም ሆነ መዛግብተ ቃላት ብናገላብጥ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለውን ፅንሰ-ሐሳብ ልናገኝ የምንችለው ሙሉ በሙሉ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ንድፈ-ሐሳብ ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ይህ ፅንሰ-ሐሳብ ቀደም ሲል ማለትም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሶሻሊዝምን የመመሥረት ዓላማ በነበራቸው የፖለቲካ ኃይሎች በተለያዩ ጊዜና ሁኔታ ሲንፀባረቅ የቆየ ፅንሰ-ሐሳብ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በተለይም በፈረንሳይ፣ በጀርመንና በሩሲያ በካፒታሊስትና በሠራተኛው መደብ መካከል ትግል ይካሄድ በነበረበት ወቅት ከሠራተኛው የመደብ ትግል ጐን ቆመናል ብለው የሚያምኑ ተራማጅ ኃይሎች ለትግላቸው አብዮታዊ ገጽታ ለመስጠት በወቅቱ የተጠቀሙበት ስልት “አብዮታዊ ዴሞክራት ነን” በማለት ነበር፡፡

እነዚህ የሠራተኛው መደብ ወገን ነን የሚሉ ተራማጅ ኃይሎች ይህንን አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለውን ፅንሰ-ሐሳብ መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት የማርክሲዝም ሌኒኒዝም የቲዎሪ መሠረት ሆኖ ያገለግል የነበረው ተምኔታዊ (Utopian) ሶሻሊዝም የሚባለው ፅንሰ-ሐሳብ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት በተምኔታውያኑ አመለካከት የኅብረተሰብ ሁለንተናዊ ለውጥ በአብዮታዊ የመደብ ትግል ሳይሆን በትምህርትና በመንፈሳዊ ተኃድሶ በሂደት ከሚፈጠር የአመለካከት ለውጥ ጋር ተያይዞ እንደሚመጣ ይታሰብ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ የተምኔታውያኑ አስተሳሰብ የካፒታሊዝምን ውድቀትና የሶሻሊስታዊ ሥርዓትን መምጣት በሐሳብ ከመመኘትና ከመፈለግ

በስተቀር ለውጡ እንዴትና በማን ሊመጣ እንደሚችል ተጨባጭና ግልጽ መፍትሔ አያስቀምጥም ተብሎ በቀረበበት ትችት በሂደት ይህ ተምኔታዊ አስተሳሰብ ወደ አብዮታዊ አስተሳሰብ እየተቀየረ እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተለይም ሩሲያውያኑ ቸርኒሽቭስኪና ሔርትዘን "በሩሲያ ሶሻሊዝም ሊመሠረት የሚችለው የጋርዮሽ መርህን መሠረት ባደረጉ የገጠር ማህበረሰቦች ወይም በሕዝቡ አምራች ማኅበራት ነው" የሚለውን የቆዬ አመለካከታቸውን ቀስ በቀስ "የሕዝብ አብዮት ያስፈልጋል" ወደሚል ተራማጅ አቋም በመቀየር አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለውን ፅንሰ-ሐሳብ የትግላቸው ርእዮተ-ዓለማዊ መገለጫ ሆኖ እንዲስፋፋ አድርገውታል፡፡

ይህ አዲስ አስተሳሰብ የማርክሲዝም ሌኒንዝም ንድፈ-ሐሳብ የበለጠ ተጠናክሮ እንዲወጣ የረዳ ሲሆን በተለይም ኋላ ላይ በእነ ሌኒን ዘመን ይበልጥ ዳብሮ በዓለም አቀፍ ፀረ-ካፓታሊዝም ትግል ውስጥ እንደ አንድ የፖለቲካ አደረጃጀት የራሱን ቅርፅና ይዘት ይዞ ለመውጣት የቻለ አመለካከት ለመሆን በቅቶ ነበር፡፡ በተለይም በ1917 በሩሲያ የተከሰተው አብዮት በፈጠረው ከፍተኛ አብዮታዊ መነቃቃት ዓለም-አቀፍ የሠራተኞች ፀረ-ካፒታሊዝም ትግል እያዬለ በመምጣቱ ሶሻሊዝም በዳበሩ ካፒታሊስት ሀገሮች ብቻ ሳይሆን በቅድመ ካፒታሊስት የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገሮችም ውስጥ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አማካይነት ሊመሠረት ይችላል የሚለው ቲዎሪ እየተስፋፋ መምጣት ችሎ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም በእድገት ወደኋላ የቀሩና በቅድመ ካፒታሊዝም የእድገት ደረጃ የሚገኙ አገሮች ካፒታሊዝምን መገንባት ሳያስፈልጋቸው በቀጥታ ወደ ሶሻሊዝም ሊሸጋገሩ ይችላሉ የሚለውን የእነ ሌኒን አስተምህሮ በመከተል ከተከሰቱት ካፒታሊስታዊ የዕድገት ደረጃ ያልሆኑ አቋራጭ የእድገት አቅጣጫዎች አብዮታዊ ዴሞክራሲ አንድ አማራጭ ለመሆን ችሎ ነበር፡፡

በዚህም መሠረት ግባቸውን ሶሻሊዝም ያደረጉና የተለያዩ ቅድመ-ካፒታሊስት የእድገት ደረጃ ላይ የነበሩ የምሥራቅ አገሮች በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ ለማለፍ የሞከሩ ሲሆን የእኛዋ አገር ኢትዮጵያም በደርግ ዘመን "ብሔራዊ ዴሞክራሲ አብዮት" በሚባል ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር ተመሳሳይ ይዘትና ዓላማ ባለው አቅጣጫ ውስጥ ለማለፍ ሞክራለች፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ታሪካዊ ሂደት ልንገነዘብ የምንችለው ቁምነገር አብዮታዊ ዴሞክራሲ የካፒታሊስት ሥርዓት ተፃራሪ የሆነና በቅርፅም ሆነ በይዘቱ የሌላ ሳይሆን የማርክሲዝም ሌኒንዝም ቲዎሪ አካል ብቻ የሆነ ፅንሰ-ሐሳብ መሆኑን ነው፡፡ እንዲያውም በካፒታሊስታዊ ሥርዓት አስተሳሰብ ውስጥ ፅንሰ-ሃሣቡ ተዋቅሮ የተፈጠረባቸው ሁለቱ ማለትም፣ አብዮታዊ እና ዴሞክራሲ የሚባሉት ቃሎች ርስ በርስ የሚቃረኑ እንጂ አንድ

ላይ ተጣምረው ሊቆሙ የሚችሉ አይደሉም። በካፒታሊስታዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ ዴሞክራሲን ገንብተዋል በሚባሉ የዓለም አገሮች እግራችን እስኪነቃ ብንዞር፣ ወይም ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሲጻፉ የኖሩ መዛግብትን ስናገላብጥ ብንውል አብዮታዊ የሚባል የዴሞክራሲ ዓይነት ልናገኝ አንችልም። እስካሁን በዓለማችን ለቋንቋ ማጣቀሻነት የተጻፉ መዛግብተ-ቃላትን ብናገላብጥም የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ትርጉም ልናገኘው የምንችለው በማርክሲዝም ሌኒንዝም መዛግብተ-ቃላት ብቻ ነው። ስለዚህ ከማርክሲዝም ሌኒንዝም ክልል የወጣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባል ፅንሰ-ሐሳብ በዓለም ላይ አለ ከተባለ በአሁኑ ሰዓት ሊገኝ የሚችለው በኢህአዴግ እየተመራች በምትገኘው በእኛዋ አገር በኢትዮጵያ ብቻ ነው። ኢህአዴግ በአንድ በኩል የማራምደው ነጭ የካፒታሊስት ሥርዓት ነው እያለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሶሻሊስታዊ ሥርዓት ግንባታ ተለይቶ ሊታይ የማይችለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አራማጅ ነኝ ማለቱ እርስ በርሱ የሚቃረን እንቆቅልሽ የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ቀድመው ፅንሰ-ሐሳቡን ከፈጠሩት አካሎች አንጻር ምን ማለት እንደሆነ ከዚህ በላይ ያየነው ታሪካዊ አመጣጡ በራሱ ገላጭ ቢሆንም አብዮታዊ ዴሞክራሲ በማርክሲዝም ሌኒንዝም መዛግብተ-ቃላት የተቀመጠለትን ትርጉም /Definition/ ብናይ ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል። እ.ኤ.አ በ1982 በእንግሊዝኛ ቋንቋ የታተመ የፖለቲካ ቃላት አጭር መመሪያ መዛግብተ-ቃላት አብዮታዊ ዴሞክራሲን___፣

*"... አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከከተማው ንዑስ ከበርቴ፣ ከገበሬውና ከተራማጅ ምሁራን መካከል በፖለቲካ ንቁ የሆኑትንና ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ካፒታሊስት የሆነውን ትግል የሚደግፉትን ክፍሎች፣ እንዲሁም የእነዚህን ፍላጐትና ጥቅም የሚገልፁ ፓርቲዎችን፣ ድርጅቶችንና ቡድኖችን የያዘ ነው። የሠራተኛው መደብ ገና በመፈጠር ላይ ባለባቸው አገሮች እንደዚሁ ሠራተኞችን ይጨምራል"* በማለት ይተረጉመዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በ1978 ዓ.ም በአገራችን በአማርኛ ቋንቋ የታተመው የማርክሲዝም ሌኒንዝም መዛግብተ-ቃላት ደግሞ ___፤

*"አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከፊል ካፒታሊስትና በአብዛኛው በቅድመ-ካፒታሊስት የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ አገሮች ሥልጣን በመጨበጥ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ካፒታሊስት የሆነውን ትግል በማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅት*

*ግንባር ቀደም መሪነት የሚያራምድ ኃይል ነው"* በማለት አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይተረጉመዋል፡፡

ከላይ ከታሪካዊ አመጣጡ እንዳየነውም ሆነ ከእነዚህ የመዛግብተ-ቃላት ትርጓሜዎች በግልጽ እንደምንረዳው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከካፒታሊስታዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ የሌለውና ከመደባዊ ትግል ትንታኔ ውጭ ሊታይ የማይችል ፅንሰ-ሐሳብ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በላይ በመደባዊ ትግሉ ውስጥ አሉኝ ወይም ቆሜላቸዋለሁ የሚላቸውን ጠላቶችና ወዳቹን በግልጽ ዘርዝሮ ያስቀመጠ የፖለቲካ መስመር ነው፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በጠላትነት ከፈረጃቸው ጠላቶቹ ውስጥም አንዱ ካፒታሊዝም በመሆኑ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ካፒታሊዝምን መገንባት የማያስችል ብቻ ሳይሆን ከሱ ተቃራኒ የሆነ ሥርዓትን መገንባት ዓላማው ያደረገ ፅንሰ-ሐሳብ መሆኑ የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፡

እዚህ ላይ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አፈጣጠር፣ ታሪካዊ አመጣጥም ሆነ ትርጓሜ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሆኖ እያለ ኢህአዴግ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አማካይነት በምን ተአምር የነፃ-ገበያና የብዙኃን ፓርቲ፣ ወይም እሱ እንደሚለው የነጭ ካፒታሊስት ሥርዓት በኢትዮጵያ ሊገነባ እንደሚችል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም፡፡ ቀደም ሲል በዚህ ክፍል መንደርደሪያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ኢህአዴግ ለሚያራምደው የአብዮታዊ ዴምክራሲ አቅጣጫ ትርጉም /Definition/ ያልሰጠ ቢሆንም በተለያዩ ሠነዶቹ ላይ ስለ አበዮታዊ ዴሞክራሲ መገለጫ ባህሪዎች የጠቃቀሳቸውን ሐሳቦች ወስደን አንድ ዓይነት ግንዛቤ ማግኘት እንችላለን፡፡ በ1998 ዓ.ም ኢህአዴግ በአሳተመው አንድ ሰነድ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ እድገት" በሚል ርእስ ሥር ባሰፈረው ሐሳብ የሚያራምደው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ የሚመነጭ መሆኑን በሚከተለው መልኩ አስፍሮታል______፤

*"የደርግን አምባገነን መንግሥት ለመገርሰስ በወቅቱ በአገራችን ተራማጅ ኃይሎች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቶ በነበረው የግራ ርእዮተ-ዓለም በመመራት የተደራጁ የተለያዩ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች በሂደት የጋራ ግንባር ፈጥረው፣ የደርግን አምባገነን አገዛዝ ገርስሰው በዋናነት በአርሶ አደሩ ላይ ተመሥርተው አገሪቱን ከተቆጣጠሩ በኋላ ያለው የአገራችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዞ ከኢህአዴግ ጉዞና ከኢህአዴግ አስተሳሰብ እድገት ጋር አብሮ የተያያዘ ነው..."* ይላል፡፡

ከዚህ የኢህአዴግ የቅርብ ጊዜ አባባል በግልጽ ልንረዳ የምንችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከግራ ርእዮተ-ዓለም የመነጨ አስተሳሰብ መሆኑን ያመነበት መሆኑን ነው፡፡ ከግራ ርእዮተ-ዓለም

በመነጨ አስተሳሰብ እንዴት ተደርጐ የቀኝ ርእዮተ-ዓለም ሥርዓት የሆነው ካፒታሊዝም በአገራችን ሊገነባ እንደሚችል በራሱ ግራ የሚያጋባ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሰው የኢህአዴግ አባባል መቋጫው ላይ ኢህአዴግ በያዘው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ በሂደት የአስተሳሰብ እድገት ያሳዬ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ እነዚህ የአስተሳሰብ እድገት ወይም ለውጥ ተብለው የተጠቆሙትን ሁለት ፍሬ ሐሳቦችንም በዚያው የኢህአዴግ ሰነድ ላይ ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን፡፡ የመጀመሪያው ከመድብለ-ፓርቲ ጋር የተያየዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከነፃ-ገበያ ሥርዓት ጋር የተያያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከዚህ ሰነድ እንደምንረዳውም ኢህአዴግ ኢትዮጵያን እስከተቆጣጠረበት ጊዜ ድረስ በመድብለ ፓርቲና በነፃ ገበያ መኖር ላይ እምነት ያልነበረው ድርጅት መሆኑን ነው፡፡ በሠነዱ ላይ የሰፈሩት ሐሳቦች እንደሚከተለው ይነበባሉ፤

ከመድብለ ፓርቲ ጋር የተያያዘው ሐሳብ___፣

*“____ኢህአዴግ በሕዝቦችና ዜጐች የዴሞክራሲ መብት መከበር ላይ ገና ከጅምሩ ከነበረው ጠንካራ አቋም በመነሣት፣ በሕዝቡ በተለይም በአርሶ አደሩ ውስጥ በነበረው ተቀባይነት በመተማመን ዴሞክራሲን እንደ ብቸኛ ምርጫ መውሰዱ የነበረ አቋም እንጂ አዲስ አስተሳሰብ ሊባል የሚችል አልነበረም፡፡ በከፊል አዲስ ሊባል የሚችለው አቋም ይኸው ዴሞክራሲ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መልኩ መገለፅ አለበት ተብሎ መቀመጡና በሕገ-መንግሥቱም በግልጽ እንዲሰፍር መደረጉ ነው”* ይላል፡፡

ከዚህ የኢህአዴግ አባባል በግልጽ የምንረዳው ኢህአዴግ ከዚያ በፊት ለዴሞክራሲ የነበረው ትርጉም በደርግ ጊዜ እንደነበረው ወይም በአሁኑ ወቅት በቻይና እንደሚታየው በአንድ ፓርቲ የበላይ አመራርነት የሚኖር ዴሞክራሲ እንጂ የመድብለ ፓርቲ- ሥርዓትን የሚያካትት ዴሞክራሲ እንዳልነበረ ነው፡፡

ከኢኮኖሚ ጋር በተያየዘ በዚያው ሰነድ ላይ የሠፈረው ሐሳብ ደግሞ___፣

*“----በሽግግሩ ሂደት በኢህአዴግ በተለይም የግራ ርእዮት በነበራቸው የኢህአዴግ አባላት ዘንድ የመጣው መሠረታዊ የአመለካከት ለውጥ በሚገነባው ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ባህሪ ላይ ነው፡፡ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ኢትዮጵያ በነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ከማደግ ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌላት እጅግ በሚበዙት የኢህአዴግ አባላትና አመራር አካላት ዘንድ ግልጽ የሆነበት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው፡፡ ይህ አቋም በሰፊውና በዝርዝር ውይይት ተደርጐበት የተወሰደ*

*ሳይሆን በነባራዊነት በሁሉም ዘንድ ከሞላ ጐደል እየሰፈነ የመጣ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ --- በነባራዊነቱ የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ አማራጭ ተወስዶ ይኸው በሕገ-መንግሥቱ እንዲሰፍርና እንዲንፀባረቅ መደረጉ በተግባር አንድ መሠረታዊ የአመለካከት ለውጥ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በዚሁ ሂደት ባንድ በኩል በዓለም የገንዘብ ድርጅቶች የመንግሥትን ድርሻ ወደ ዜሮ ለማውረድ የሚደረገውን ሙከራ የመከላከል፣ በሌላ በኩል መሬትን ለመሸጥና ለመለወጥ የሚደረግ ሙከራን ለማክሰምና የእዝ ኢኮኖሚን ለመናድ የሚደረገው ጥረት እነዚህንም አብሮ እንዳይንድ የተሳካ የመከላከል ሥራ ተሠርቷል፡፡ ---- የመንግሥት ድርሻ ሊበራሊዝም በሚያስቀምጠው መልኩ እንዳይሆን የተደረገውም በአንድ በኩል ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋሞች (commanding heights) በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን ይገባቸዋል ከሚልና በግል ባለሀብቱ ላይ ከነበረ ጥርጣሬ የሚመነጭ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የልማታዊ መንግሥታት ልምድ በከፊል መወሰድ ጀምሮ የነበረ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነበር”* ይላል፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የሰፈሩት ሐሳቦች በግልጽ እንደሚያሳዩት ኢህአዴግ መንግሥት ከመሆኑ በፊት በነፃ-ገበያ ሥርዓት ላይ እምነት ያልነበረው መሆኑን ነው፡፡ እንዲያውም መንግሥት ከሆነም በኋላ የነፃ-ገበያ ሥርዓትን ለመቀበል የተገደደው በነባራዊው ሁኔታ መለወጥ አስገዳጅነት እንጂ በጉዳዩ ላይ በድርጅቱ ውስጥ በቂ ውይይት ተደርጎና መተማመን ላይ ተደርሶ እንዳልሆነ በግልጽ ያሳያል፡፡ በተጨማሪም ኢህአዴግ የነፃ-ገበያ ሥርዓትን አማራጭ ስለሌለኝ ተቀብዬዋለሁ ቢልም መሬትን ጨምሮ ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው እንዲቀጥሉ እንዳደረገና በግል ባለሀብቱ ላይም የተሟላ እምነት እንደሌለው በዚህ ሠነዱ ላይ በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ከዚህ አጠቃላይ አስተሳሰብ ልንረዳ እንደምንችለው ኢህአዴግ በግራ ርእዮተ-ዓለም መመራቱን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ያልቀየረ መሆኑን፣ ነገር ግን በሂደት የሚያራምደው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቅጣጫ በሁለቱ ጉዳዮች ማለትም በመድብለ ፓርቲና በነፃ-ገበያ አስፈላጊነት ላይ የአስተሳሰብ እድገት ያሳዬ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው ኢህአዴግ ከወቅቱ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ራሱን ለማጣጣም የተገደደ ቢሆንም የሊበራል አስተሳሰብ ወይም የካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ በሚጠይቀው መጠን የመድብለ ፓርቲና የነፃ-ገበያ አስተሳሰብን በተሟላ ሁኔታ ተቀብሎ ለማራመድ ገና ከልቡ ያልወሰነ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ የሚመራበትን የራሱን ርእዮተ-ዓለማዊ መስመር መምረጥም ሆነ ራሱን “አብዮታዊ

ዴሞክራት" ብሎ መጥራት መብቱ ቢሆንም ቢያንስ ግን ሁለት ሃቆችን አምኖ መቀበል ይኖርበታል፡፡

የመጀመሪያው ራሱ ኢህአዴግ ከላይ በተጠቀሰው ሠነዱ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠው አብዮታዊ ዴሞክራሲ የግራ ርእዮተ-ዓለም የፖለቲካ መስመር እንጂ ከቀኝ ርእዮተ-ዓለም ወይም ከካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ፅንሰ-ሐሳብ መሆኑን ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር አመጣሁት ባለው የአስተሳሰብ እድገት የመድብለ ፓርቲንና የነፃ-ገበያ ሥርዓት አስፈላጊነትን ተቀብያለሁ ቢልም መሠረታዊ በሆነ መልኩ የግራ ርእዮተ-ዓለም አራማጅ እስከሆነና የአገሪቱ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉትም ሆነ የሚገባው በእኔ መስመር ብቻ ነው የሚለውንና ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው መቀጠል አለባቸው የሚለውን እምነቱን እስካልቀየረ ድረስ በያዘው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር የካፒታሊስት ሥርዓትን ሊበራሊዝም ሊገነባው በሚችለው መጠን በኢትዮጵያ ሊገነባ የማይችል ድርጅት መሆኑን ነው፡፡

ኢህአዴግ ከራሱ የተኃድሶ እንቅስቃሴ በኂላ በ1994ዓ.ም ባሰራጨው ሰነድ ላይ "ኢህአዴግ ከሌለ ኢትዮጵያ ትበታተናለች" የሚል አደገኛና ደፋር አስተሳሰቡን ከመግለፁም በላይ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሊበራል ዴሞክራሲን ሊያስተናግድ የሚችል ማኀበራዊ መሠረት እንደሌለና ሊበራል ዴሞክራሲ በዚህች አገር መገንባት አለበት የሚል ሌላ ምርጫም መወሰድ ካለበት ይህንኑ ኃላፊነት መሸከም የሚችለው ኢህአዴግ ብቻ ነው የሚል ከመድብለ - ፓርቲ አስተሳሰብ ጋር ፈጽሞ የማይሄድ አቋሙን በግልጽ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የኢህአዴግ ሰነድ በግልጽ ሠፍሮ እንዳየነውም ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው መቀጠል አለባቸው የሚል ከነፃ-ገበያ ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም አቋሙን በማያሻማ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ስለዚህ አንድ ፓርቲ የአገሪቱ ዕጣ-ፈንታ በየትኛውም መንገድ ሊወሰን የሚችለው በእኔና በእኔ ብቻ ነው ብሎ በግልጽ አቋም በወሰደበትና ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆነው መቀጠል አለባቸው የሚል ግልጽ አቋም በያዘበት ሁኔታ የቱንም ያህል ስለ መድብለ ፓርቲና የነፃ-ገበያ አስፈላጊነት ቢያወራና ቢጽፍ እንዲህ ዓይነቱ ድርጅት ሙሉ በሙሉ የካፒታሊስት ሥርዓት አራማጅ ነኝ ማለት የሚችልበት አሳማኝ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

በአጠቃላይ የኢህአዴግን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከቀድሞው የእነ ሌኒን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የሚለየው በአንድ በኩል ኢህአዴግ ከልባዊ የርእዮተ-ዓለም ለውጥ በመነጨ ሳይሆን ራሱን ከወቅታዊው የዓለም ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም ሲል

የመድብለ - ፓርቲና የነፃ-ገበያ ሥርዓት አስፈላጊነትን በመርህ ደረጃ መቀበሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጠላትና ወዳጅን በተመለከተ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የራሱን አዲስ መጠሪያ /Term/ የሚጠቀም መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም በእነ ሌኒን ዘመን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ ካፒታሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ተብለው በግልጽ የተቀመጡ ሲሆን፣ ኢህአዴግ እነዚህን ሁሉ በአንድ ላይ ጠቅልሎ "ኪራይ ሰብሳቢ" በሚል ይጠራቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በእነ ሌኒን ዘመን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወዳጆች "የከተማ ንዑስ ከበርቴ፣ ገበሬ፣ ላብአደሮችና ተራማጅ ምሁራን" ተብለው የተቀመጡ ሲሆን ኢህአዴግም ከዚህ ብዙም ባልተለዩ መልኩ ወዳጆቹን በጥቅሉ "አርሶ አደርና ልማታዊ ባለሀብት" ብሎ ይጠራቸዋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከእነ ሌኒን ዘመኑ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከስልታዊ አቀራረብና ከተወሰኑ የስያሜ ለውጦች በስተቀር መደባዊ የግራ ርእዮተ-ዓለም አስተሳሰብ ከመሆን አኳያ መሠረታዊ የሚባል ለውጥ የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም የምንረዳው በአንድ በኩል አገራችን ከአንድ ፓርቲ የበላይነትና ከእዝ-ኢኮኖሚ ወደ መድብለ ፓርቲና የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመሸጋገር ምን ያህል ፈተና እንደገጠማት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት አገርን የመምራት ኃላፊነት ላይ ያለው ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ከአማፂነት ወደ ሲቪል አስተዳደር ብቻ ሳይሆን ከሶሻሊስታዊ አስተሳሰብ ወደ ካፒታሊስታዊ አስተሳሰብ ለመሸጋገር ቀላል የማይባል ድርብ ፈተና የገጠመው መሆኑን ነው፡፡ በነገራችን ላይ ህወሃት በጫካ ትግሉ ወቅት የመሠረተውንና ማርኪሲዝም ሌኒንዝም ሊግ ትግራይ (ማሌሊት) የሚባለውን ርእዮተ-ዓለማዊ ድርጅቱን እስካሁን በይፋ አለማፍረሱ፣ ወይም የት እንደጣለው አለመታወቁም የሚያሳዩው ኢህአዴግ የማሌ ርእዮትን ርግፍ አድርጐ በመተው ረገድ መንታ ልብ ሆኖ የተቸገረ ድርጅት መሆኑን ነው፡፡ ኢህአዴግ ከሶሻሊስታዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር ቁርኝት ያለውን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርን በአሁኑ ወቅት እከተላለሁ ማለቱ በምን አሳማኝ ምክንያት እንደሆነ ራሱ ሊመልሰው የሚገባ እንቆቅልሽ ቢሆንም፣ በተግባር እያከናወነ ከሚገኘው ተግባር አንፃር ግን በቻይና እየታየ እንዳለው ሁሉ ወደ ካፒታሊስታዊ ሥርዓት የሚያመሩ በርካታ ተግባራት በአገራችን እየተከናወኑ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

### *3.1.2 ሊበራል ዴሞክራሲ*

ሊበራል ዴሞክራሲ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በብዙ አገሮች ተቀባይነት ያገኘና በአሁኑ ወቅትም በዓለማችን በስፋት የሚታወቅ የፖለቲካ አስተሳሰብ ስለሆነ ፅንሰ-ሐሳቡን በቀላሉ ለመረዳት አስቸጋሪ የሚያደርገው አሻሚ ትርጉም አለ ማለት አይቻልም፡፡ ምንአልባት ከሊበራል ዴሞክራሲ ጋር የሚመሳሰል አሻሚ ትርጉም አለ ከተባለም ራሱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመባል

የሚታወቀው ጥቅል አጠራር ነው። ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን ዘመናዊ የሚባለውን የሊበራል አስተሳሰብ በአጠቃላይ ከዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ነጥሎ ማየት የማይቻልበት ሁኔታ እየተፈጠረ በመምጣቱ ነው። ሊበራሊዝም ረዥም ዘመን ባስቆጠረ ሂደት በየወቅቱ ራሱን እያሻሻለና እያደሰ የመጣ አስተሳሰብ ከመሆኑ አንጻር በዚያው መጠን የተለያዩ ትርጓሜዎች /Definitions/ የተሰጡት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ከደረሰበት ደረጃ ጋር ሊጣጣም የሚችለውን የቅርብ ጊዜ ትርጉሙን በማየት ስለ ምንነቱ በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን።

ስለ ሊበራሊዝም ከተመራመሩ ምሁራን መካከል አንዱ የሆኑት ጆርጅ ኤች ሳቢን “የፖለቲካ ንድፈ ሐሳብ ታሪክ” በሚለው መጽሐፍ ለሊበራሊዝም የሰጡትንና ብዙዎችን የሚያስማማ ትርጉም ለማየት ብንሞክር፣

> *“ሊበራሊዝም በጠባብ ትርጉሙ ለለውጥ የተመቸ፣ ነገር ግን የሚያናጋ ለውጥን የሚቃወም፣ በወግ አጥባቂነትና በሶሻሊዝም መካከል ላይ የሚገኝ የፖለቲካ አቋምን ለመግለፅ የሚጠቅም ነው”* ይሉታል።

ይህም ማለት ሊበራሊዝም በአንድ በኩል ኮሚኒስቶች ከግራ ወገን ቆመው የሚያራምዱትን አብዮት ወይም አመፅና ነውጥ አይደግፍም ማለት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ወግ አጥባቂዎች ከቀኝ ወገን ቆመው የሚያራምዱትን ሁሉንም ነገር ሳይታደስና ሳይለወጥ እንደነበር ይቀጥል የሚለውን አስተሳሰብ አይቀበልም ማለት ነው። ይህንን ሁኔታ ከእኛ አገር የወቅቱ ሁኔታ ጋር አዛምደን ለማየት ብንሞክር ከላይ በተገለፀው መልኩ የግራና የቀኝ አስተሳሰብን በከረረ መልኩ የሚያራምዱ ፓርቲዎች በአሁኑ ወቅት በአገራችን አሉ ማለት ባይቻልም ኢህአዴግንና ሌሎች ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን በብሔር ማንነት የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በግራ ዘመምነት፣ እንደ ኢዲዩ፣ መኢሕድና ሞ-ዐንበሳ የመሳሰሉትን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ በወግ አጥባቂነት በመውሰድ፣ የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ኢዴፓን በመሰሉ ለዘብተኛ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ሊገኝ የሚችል አስተሳሰብ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል። በርግጥ አሁን ባለው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ መንግሥት በአገሪቱ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሕይወት ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን በሕግ የተገደበ ጊዜያዊ ሚና ኢዴፓ በውል ስለሚገነዘብና ስለሚቀበል በቀኝ ኃይሎች ጐራነት ሳይሆን በመሃል ቀኝ ዘመምነት /center right/ የሚገኝ ድርጅት ነው ማለት ይቻላል።

ሊበራሊዝም በቀጥተኛ ትርጉሙ የካፒታሊዝም ሥርዓት ማኅበራዊ ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ርእዮተ-ዓለም ነው ማለት የሚቻል ሲሆን፣ ከዚህ ዘርዘር ባለ መልኩ

ደግሞ፣ ሊበራሊዝም የተለያዩ አስተያየቶችና አመለካከቶች የሚቻቻሉበት፣ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶች ወይም ደግሞ የእያንዳንዱ ግለሰብ ነፃነት የተረጋገጠበትና የነፃ-ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓትን የሚፈቅድ ፅንሰ-ሐሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የሊበራሊዝም አመለካከት በዋናነት ሁለት እርስ-በርስ ተደጋጋፊ የሆኑ ቁም ነገሮች አካቶ የያዘ ነው፡፡ ይኸውም - የመጀመሪያው ማንም ግለሰብ ወይም ዜጋ ከራሱ ፈቃድ ውጭ የሆነ ሌላ ኃይል (መንግሥትን ጨምሮ) በግል ሕይወቱ ውስጥ ጣልቃ ሊገባበት አይገባም የሚል ይዘት ያለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እያንዳንዱ ግለሰብ ያለውን አመለካከት በሕግ ሥር ለማራመድ፣ የሚፈልገውን የሕይወት አቅጣጫ ለመከተል፣ ነፃ ሆኖ ለማሰብ፣ ለመሥራትና ለመኖር መብት አለው የሚል ነው፡፡ ሊበራሊዝም የሚታወቅበት ሌላው ባህሪው -አዳዲስ አስተሳሰቦችና አሠራሮችን ለመቀበል ክፍት የሆነ፣ በየጊዜው በሚፈጠሩ አዳዲስ ዕውቀቶችና ልምዶች ራሱን የሚያድስ፣ ከየአገሩ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ራሱን እያዳበረና እያጣጣመ የሚሄድ አስተሳሰብ መሆኑ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም ሊበራሊዝም በጥናትና በአርቆ አስተዋይነት ላይ የተመሠረተ፣ የሰውን ልጅ ነፃነትና መብት የሚያከብር የሰከነ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ በአንድ አገር መኖር አለበት ብሎ የሚያምን አመለካከት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት የማያቋርጥ ለውጥና መሻሻል በዘላቂነት እንዲኖርም ልዩ ልዩ አመለካከቶች በነፃነት መንሸራሸር የሚችሉበት ዕድል መፈጠርና መመቻቸት አለበት ብሎ ያምናል፡፡

ቀደም ሲል ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ሊበራሊዝም በግራ ኃይሎችና በቀኝ ወግ አጥባቂዎች መካከል ያለውን ስፍራ የሚይዘው እነዚህ በሁለት ጫፍ ላይ የቆሙ ጽንፈኛ ኃይሎች የሚያራምዱትን አገርንና ሕዝብን የማይጠቅም የከረረ አቋም በማስወገድ የአንድ አገር ሕዝቦች ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል አብረው የሚኖሩበትን ሰፊ ዕድል መፍጠር ይቻላል ከሚል እምነት በመነሻ ነው፡፡ ሊበራሊዝም ለዚህ አቋሙ መሠረት አድርጐ የሚወስዳቸውና ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው እሴቶች ደግሞ -ግለሰባዊነት፣ በበቂ ምክንያት መመራት፣ ነፃነት፣ ወንድማማችነት፣ እኩልነት፣ ፍትሐዊነትና መቻቻል የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ዘመናዊው የሊበራሊዝም ትርጉም "ዴሞክራሲ" እየተባለ ከሚጠራው አጠቃላይ ፅንሰ-ሐሳብ ጋር አንድ አካልና አንድ አምሳል እየሆነ ከመምጣቱም በላይ ሊበራል ዴሞክራሲ በአሁኑ ወቅት የሰው ልጆች ተመራጭ አስተዳደር ለመሆን በቅቷል፡፡ ከዚህ የሊበራሊዝም አጠቃላይ ይዘትና ትርጉም ልንረዳ እንደምንችለው ሊበራሊዝም ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ በተለየ ከማንኛውም ማኅበራዊ መደብ ወይም ቡድን ጋር የማይወግንና የእያንዳንዱን ግለሰብ መብት መከበርና የነፃ-ገበያ ሥርዓትን በመደገፍ ትክክለኛ የካፒታሊስት ሥርዓትን ለመገንባት የሚያስችል የፖለቲካ አቅጣጫ መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዓለማችን

ታሪካዊ ሂደት እንደምንረዳው በአንድ አገር ውስጥ ያለን አሮጌ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዘይቤን አገራዊ ህልውናን በማያናጋ አግባብ በማስወገድና የካፒታሊስታዊ ሥርዓትን በመገንባት ረገድ እንደ ሊበራል ዴሞክራሲ ዓለምን በአግባቡ ለመቀዬር የቻለ ሥርዓት አለ ማለት አይቻልም፡፡

ሊበራሊዝም የማንኛውም ዓይነት የቡድን መብትን ጨምሮ የሁሉም መብቶች መነሻ የግለሰብ ወይም የእያንዳንዱ ዜጋ መብት ነው ብሎ የሚያምን በመሆኑ እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአንድ አገር ሕዝብ ውስጥ ጠላትና ወዳጅ ብሎ የሚፈርጀው የኅብረተሰብ ክፍል የለውም፡፡ ብዙውን ጊዜ የግራ ኃይሎች በሊበራሊዝም ላይ የሚሰነዝሩት ትችት ሊበራሊዝም በማንኛውም ጉዳይ የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት የሚቃወምና የዘፈቀደ /ለሴፌር/ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓትን የሚያራምድ የካፒታሊዝም ፖለቲካዊ ቲዎሪ ነው የሚል ነው፡፡ በርግጥም ሊበራሊዝም በመነሻው ወቅት የለሴፌር ተከታዮች የሚያራምዱትን መስመር በማቀንቀን የመንግሥትን ጣልቃ ገብነት /በሁሉም መስክ/ የማያስፈልግና አደገኛ ነው በሚል አጥብቆ ይቃወም ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ የቀድሞ የሊበራሊዝም አስተሳሰብ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ጀምሮ የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል በሚያስፈልጉ ጉዳዮች መንግሥት በሕግ የተገደበና የተመጠነ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል ወደሚል አዲስ የሊበራሊዝም አስተሳሰብ ተሻሽሏል፡፡

በተለይም ከ1920ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በካፒታሊስት አገሮች ውስጥ ሥራ አጥነትን፣ የኑሮ ውድነትን፣ ድህነትንና የሕይወት ዋስትና ማጣትን ያስከተለ የኢኮኖሚ ድቀት በብዙ የዓለም አገሮች ተከስቶ ስለነበር የተከሰተውን ችግር በመፍታት ረገድ የመንግሥት ሚና የግድ አስፈላጊ መሆኑ ጎልቶ ወጥቷል፡፡ በመሆኑም የዋጋ ማረጋጊያ፣ የሥራ አጥነትን ችግር መፍቻ፣ የኑሮ ውድነትና የድህነት መቀነሻ መንገዶች በመንግሥት ተቀይሰው ሥራ ላይ እንዲውሉ በመደረጉ የመንግሥት ተሳትፎ የግል ነፃነትን በማይፃረር መንገድ እስከ ተፈጸመ ድረስ አስፈላጊነቱ እንደማያከራክር ታምኖበታል፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በመንግሥት ቁጥጥር የማይደረግበት ካፒታሊዝም ትርፉ አዲስ ዓይነት ማኅበራዊ ቀውስ መፍጠር እንደሚሆን ስለታመነበት የመንግሥት ተሳትፎ አስፈላጊነት በዘመናዊ ሊበራሊዝም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

እንዲያውም በካፒታሊስት ሥርዓት ማዕቀፍ ውስጥ የማኅበራዊ ደኅንነትን የሚያረጋግጡ ሶሻል ዌልፌር (ማኅበራዊ ድጐማ የሚያደርጉ) መንግሥታት ጀርመንን በመሰሉ አገሮች መፈጠር የጀመሩት ከ1880ዎቹ ጀምሮ ነው፡፡ በሂደት በርካታ የዌልፌር መንግሥታት እየተፈጠሩ መምጣታቸውም ካፒታሊዝም ከፍተኛ የሀብት ክፍፍል አለመመጣጠንን ይፈጥራል

የሚለውን የእነ ማርክስ ፍርሀት በአንፃራዊነት ማስወገድ ችሏል፡፡ ይህም የወቅቱን የካፒታሊስት ሥርዓት አራማጆች የገቢ መዋቅር ቅርፅ እንደ ፒራሚድ ብዙ ድሆችና ጥቂት ባለሀብቶች የሚገኙበት ሳይሆን እንደ አልማዝ (diamond) ቅርፅ ጥቂት ድሆች፣ ብዙ መካከለኛ ገቢ ያላቸውና ጥቂት ሀብታሞች የሚታይበት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በአጠቃላይም በ21ኛው ክፍለ ዘመን የዌልፌርን ሥርዓት ተግባራዊ የማያደርግ የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጅ አገር አለ ማለት አይቻልም፡፡ በዚህም ምክንያት ዘመናዊው ሊበራሊዝም አንዳንዴ ማኅበራዊ ሊበራሊዝም ወይም የማኅበራዊ ደኅንነት ሊበራሊዝም እስከ መባል ደርሷል፡፡ ሩቅ ሳንሄድ በቅርቡ በአሜሪካና በበርካታ የኤዥያና የአውሮፓ አገሮች በተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ መንግሥታት ለትልልቅ ባንኮችና የኢንሹራንስ ካምፓኒዎች ሳይቀር የኪሳራ ማካካሻ ገንዘብ በመመደብ ኢኮኖሚው እንዲያገግም ምን ያህል ጥረት እንዳደረጉ ማየታችን ዘመናዊ የሊበራሊዝም አስተሳሰብ መሠረታዊ ይዘቱን ሳይለቅ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የሚደረግን የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የሚደግፍ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ኢህአዴግ የወቅቱን ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ቀውስ በተዛባ ሁኔታ የሊበራሊዝም አስተሳሰብ ውድቀት ማሳያ አድርጐ ለማሳየት እዬሞከረ ቢሆንም ምዕራባውያኑ በሥርዓታቸው ሂደት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት እየሞከሩ ያሉት ከድህነት አውጥቶ ለብልፅግና ያበቃቸውን የሊበራሊዝም አስተሳሰብ ጥያቄ ውስጥ በማስገባት ሳይሆን ያንኑ የያዙትን ሥርዓት የበለጠ አጠናክሮ ለማስቀጠል በሚያስችል የአሠራር ማሻሻያ ነው፡፡ ከወቅቱ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ቀውስ አንጻር ምዕራባውያኑ መተቸት ካለባቸው በሥርዓታቸው አጠቃላይ ሂደት ውስጥ የዘረጉት የአሠራር ስልት በማንኛውም አሠራር ሊከሰት እንደሚችለው ከሁኔታዎች መለዋወጥ ጋር በተያያዘ በሂደት የማርጀት አደጋ ሊገጥመው እንደሚችል አስቀድሞ በመገመት በተገቢው ወቅት እንዲታደስ ባለማድረጋቸው እንጂ የሊበራል አስተሳሰብ አራማጅ በመሆናቸው አይደለም፡፡ እንዲያውም ምዕራባውያኑ በሥርዓታቸው ውስጥ ያልተለመደ አደጋ ሲገጥማቸው ያልተለመደ ርምጃ በመውሰድ ጭምር ችግራቸውን ለማስወገድ ሲጥሩ መታየታቸው ሊበራሊዝም ምን ያህል ከተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር ራሱን እያጣጣመ የሚገጥሙትን ችግሮች እየፈታ መሄድ የሚችል ግትር ያልሆነ /flexible/ ሥርዓት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ "ዓለም የወዛደሮች ትሆናለች - አንጠራጠርም!" በማለት ሲፎክር የኖረው የግራው የፖለቲካ ርእዮት ግን ከሰው ልጅ አካባቢያዊ ለውጥ ጋር ራሱን ማጣጣም ተስኖት ማርኪሲስቶች ይሉት እንደነበረ የታሪክ ሃቅ ሳይሆን የታሪክ ቅሪት ሆኖ አልፏል፡፡ ሃቁ ይህ ሆኖ እያለ ኢህአዴግን የመሰሉ የግራ ኃይሎች ሊበራሊዝምን ለመተቸት ሲሞክሩ የሚታዩት ዛሬ በዓለማችን ዘመናዊው

የሊበራሊዝምን አስተሳሰብ ከደረሰበት የዕድገት ደረጃ አንጻር ሳይሆን ከመቶ ዓመት በላይ ወደኋላ ዘለው በመሄድ ጊዜ ያለፈበትንና የተረሳውን የለሴፌር አስተሳሰብ እንደ አዲስ በመጥቀስ ነው፡፡

ሊበራሊዝም የዘፈቀደ /ለሴፌር/ አስተሳሰብ አራማጅ ነው ከሚለው የቆዬ ትችት በተጨማሪ ኢህአዴግ ሁለት ዓይነት ትችቶችን በተደጋጋሚ በሊበራል ዴሞክራሲ ላይ ሲያቀርብ ይደመጣል፡፡ የመጀመሪያው ትችት “ሊበራል ዴሞክራሲ የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሚፈታው መጠን አይመልስም” የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው ትችት ደግሞ “ሊበራል ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችል ማኅበራዊ መሠረት በአገራችን የለም” የሚል ነው፡፡ የመጀመሪያውን ትችት በተመለከተ፣ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በይዘቱም ሆነ በትርጉሙ በሌላው የምሥራቅ ዓለም ይታወቅ ከነበረው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፈጽሞ የተለየና አዲስ ነው ካልተባለ በስተቀር የብሔር -ብሔረሰቦችን የመብት ጥያቄ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሊበራል ዴሞክራሲ በተሻለ ይመልሳል ሊባል የሚችልበት አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡

ምክንያቱም ታሪካዊ አመጣጡንና ትርጉሙን ከላይ ለማየት እንደሞከርነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቅራኔ ከመደብ ትግል አንጻር የሚተነትን በመሆኑ ከመደብ ቅራኔ ጋር ግንኙነት  የሌለውን የብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄን በተለየ ሁኔታ ሊመልስ አይችልም፡፡ ይልቁንም ከመገንጠል ጥያቄ በስተቀር በአገራችን በብሔር ብሔረሰቦች ዙሪያ የሚነሡት የቡድን መብትና ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ በግለሰብ መብት ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው አስተማማኝና የተሟላ መልስ ሊያገኙ የሚችሉት የእያንዳንዱን ዜጋ የግልም ሆነ የቡድን መብት መከበርን  ሙሉ በሙሉ በሚቀበለው በሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ነው፡፡ ለዚህም ነው አሜሪካንና ምዕራብ አውሮፓን በመሳሰሉ የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጅ አገሮች የቡድን መብት በተሻለ ሁኔታ ሲከበር የምናየው፡፡ ሌላው ቀርቶ አማርኛ ቋንቋ የዋሽንግተን ዲሲ ተጨማሪ የሥራ ቋንቋ ሆኖ ሊመረጥ የበቃው አሜሪካ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አራማጅ አገር በመሆኗ አይደለም፡፡ በሌሎች ሠልጥነዋል በምንላቸው የአውሮፓ አገሮች የሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም፣ ባህላቸውን የመንከባከብና የመጠበቅ፣ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ወሳኝ የመሆን የተሻለ መብት አግኝተው ከእኛ አገር በተሻለ ሁኔታ ሲጠቀሙ የምናየው እነዚያ አገሮች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አራማጆች ስለሆኑ ሳይሆን ይልቁንም የግለሰብን መብት መከበር መነሻ አድርጉ የቡድንንም መብት ለማክበር የሚችለው የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አራማጆች ስለሆኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ከተለያዩ አገራት ወደ አሜሪካና አውሮፓ አገሮች የተሰደዱ ሰዎች የራሳቸውን ኮሚኒቲ አቋቁመው፣ በራሳቸው ቋንቋ የሚግባቡበት ሬዲዮ ጣቢያ ከፍተው፣

ባህሎቻቸውን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ዕምነታቸውን ጭምር በነፃነት በማራመድ እንዲጠቀሙ የመንግሥት የገንዘብ ድጐማ ጭምር ሲደረግላቸው የምናየው ሊበራል ዴሞክራሲ የግለሰብን መብት ብቻ ሳይሆን ዞሮ ዞሮ ከግለሰብ መብት የሚመነጨውን የቡድን መብት ለማክበር ቁርጠኛ አቋም ያለው በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ የሕዝቦችን የመገንጠል መብት በተግባር በሕዝበ-ውሳኔ እንዲዎሰን በማድረግ ረገድ በዓለማችን በቀዳሚ ምሳሌነት የምትጠቀሰው ካናዳ እንኳን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሳይሆን በዋናነት የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የነገሠባት አገር ነች፡፡ ስለዚህ ከዚህ የብሔር-ብሔረሰቦች ጥያቄም አኳያ ኢዴፓ እያራመደው የሚገኘው አቋም የብሔር-ብሔረሰቦችን መብት ማክበር አይገባንም የሚል ሳይሆን እንዲያውም ከኢህአዴግ በተሻለ መብቱን በተግባር ልናከብረው የምንችለው እኛ የሁሉም ዓይነት መብት መነሻና መሠረት ሆኖ የሚያገለግለው የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጆች ነን የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው የኢህአዴግ ትችት ሊበራል ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችል ማኀበራዊ መሠረት በአገራችን የለም የሚል ነው፡፡ ከዚህ መከራከሪያ አንጻር በአንድ በኩል ሊበራሊዝምን ለመገንባት የሚያስችል ማኀበራዊ መሠረት በአሁኑ ወቅት በአገራችን የለም የሚለው የኢህአዴግ ክርክር እውነት ሆኖ እያለ፣ በሌላ በኩል ግን ይህ ማኀበራዊ መሠረት ስለሌለ ሊበራል ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ መገንባት አይቻልም የሚለው የኢህአዴግ ክርክር ትርጉም የለሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ትርጉም የለሽ ነው የሚያስብለው ምክንያት ማንኛውም የግራም ሆነ የቀኝ የፖለቲካ ኃይል አንድን ርእዮተ-ዓለም እመራበታለሁ በማለት መርጦ የሚይዘው ሊደርስበት ከሚፈልገው ግብና ወደፊት ሊፈጥረው ከሚፈልገው አገርና ኅብረተሰብ አንጻር እንጂ በአንድ የተወሰነ ወቅት በአገሪቱ ካለው የማኀበራዊ መሠረት ስፋትና ጥበት አንጻር አይደለም፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በእኛም ሆነ እኛን በመሰሉ የገበሬ አገሮች የግራ ኃይሎች ሠራተኛው የበላይ የሚሆንበትን የሶሻሊስት ሥርዓት ለመመሥረት ባልታገሉ ነበር፡፡ ብዙዎች በአሁኑ ወቅት የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጅ የሆኑት አገሮችም ከመቶ ዓመት በፊት ሊበራል ዴሞክራሲን ለማራመድ ሲወስኑ በዚያን ወቅት በአገራቸው ሊበራል ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችል በቂ ማኀበራዊ መሠረት ነበር ማለት አይቻልም፡፡ አብዛኛዎቹ አገሮች ዛሬ እኛ ከምንገኝበት ዓይነት ማኀበራዊ መሠረት ተነስተው ነው በረዥም ጊዜ ሂደትና በሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ተመርተው ዛሬ የደረሱበትን ማኀበራዊ መሠረት መፍጠር የቻሉት፡፡

የማኀበራዊ መሠረት መኖርን ዋና ቅድመ-ሁኔታ አድርገን እንውሰደው ካልን ሊበራል ዴሞክራሲን ብቻ ሳይሆን የሱ ዋና መገለጫ የሆነውን የነፃ-ገበያ ሥርዓትንም በአገራችን እናራምዳለን ማለት አንችልም፡፡ ራሱ ኢህአዴግ የነፃ-ገበያ ሥርዓት አራምዳለሁ እያለ የሚገኘው

ዛሬ በአገራችን ለነፃ-ገበያ መመሥረት አመች የሆነ ማኅበራዊ መሠረት፣ ማለትም መካከለኛ ገቢ ያለው /Middle class/ ኅብረተሰብና ሰፊ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ /Private sector/ ኖሮ አይደለም፡፡ ሁላችንም የነፃ-ገበያ ሥርዓት እናራምዳለን የምንለው ነፃ-ገበያ አገራችን ወደፊት በሂደት እንድትደርስበት የምንፈልገው ግብ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ ሊበራል ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችል ማኅበራዊ መሠረት በአሁኑ ወቅት በአገራችን አለመኖሩ እውነት መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም፣ ይህ እውነት መሆኑ ግን የሊበራል ዴሞክራሲን አስተሳሰብ በኢትዮጵያ ማራመድ ላለመቻል ምክንያትና ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡

በዚህ ሎጂክ መሄድ አለብን ከተባለ የነፃ-ገበያም ሆነ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አራማጆች ነን ብሎ ማለት ስለማይቻል የምንገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ እንጂ እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ልንደርስበት የምንፈልገውን ግብ የርእዮተ-ዓለማችን መነሻ ማድረግ አንችልም እንደማለት ነው፡፡ አንድን ርእዮተ-ዓለም ለመምረጥና ለማራመድ ከወቅታዊ ማኅበራዊ መሠረት ጋር የግድ መያያዝ አለበት ከተባለ የወቅቱ የአገራችን ማኅበራዊ መሠረት አርሶ አደርነት ስለሆነ እኛው ለመጀመሪያ ጊዜ እዚሁ እንፍጠረው ካላልን በስተቀር የአርሶ አደርነት መገለጫ የሆነ ርእዮተ-ዓለም ከቀድሞዋ የማኦ ቻይና ካልሆነ በስተቀር ከየትም ፈልገን ልናገኝ አንችልም፡፡ ከርእዮተ-ዓለም ምርጫ አንጻር ሊሰመርበት የሚገባው ዋናው ቁምነገር ልንደርስበት የሚገባንና የምንፈልገው ግብ ነው እንጂ አሁን የምንገኝበትና አብረነው ልንኖር የማንፈልገው ሁኔታ አይደለም፡፡ ስህተት ሊሆን የሚችለው በምዕራቡ ዓለም በአሁኑ ወቅት በሚገኝበት መጠን ሊበራል ዴሞክራሲን ዛሬውኑ በአገራችን ልንገነባው እንችላለን ከተባለ ነው እንጂ ራሱን የወቅቱን ማኅበራዊ መሠረታችንን በሂደት በመቀየር አገራችንን ወደፊት ሊበራል ዴሞክራሲ የሰፈነባት አገር ለማድረግ ከአሁኑ አቅጣጫን መርጦ መጓዝ ስህተት ሊሆን አይችልም፡፡

በአጠቃላይ ለተሻለ ንጽጽር ይረዳን ዘንድ ኢህአዴግ አራምዳለሁ በሚለው በአብዮታዊ ዴሞክራሲና ኢዴፓ በሚያራምደው ሊበራል ዴሞክራሲ መካከል ያሉትን መሠረታዊ ልዩነቶች በሚከተለው መልኩ በአጭሩ አጠቃሎ ማየት ይቻላል፡፡

- ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ አንጻር - ሊበራል ዴሞክራሲ በካፒታሊዝም ፖለቲካዊ ቲዎሪ ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝና ግቡም ካፒታሊስታዊ ሥርዓት መገንባት የሆነ የቀኝ ኃይሎች ፅንሰ-ሐሳብ ሲሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግን በሶሻሊስታዊ የፖለቲካ ቲዎሪ ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝና ከካፒታሊስታዊ ሥርዓት ተፃራሪ የሆነ አመለካከት የሚያራምድ የግራ ኃይሎች ፅንሰ-ሐሳብ ነው፡፡

- መብትን ከማክበር አንጻር-ሊበራል ዴሞክራሲ የእያንዳንዱን ግለሰብ ወይም ዜጋ መብት ማክበርን መሠረት አድርጐ ከግለሰብ መብት የሚመነጨውን የቡድን መብትም የሚያከብር ሲሆን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግን (ከጽንሰ ሀሳቡ ታሪካዊ አነሳስ አንፃር) መሠረቱ መደባዊ የሆነ የኅብረተሰብ የኃይል አሰላለፍ ሲሆን ቅድሚያ የሚሰጠውም ለግለሰብ ሳይሆን ለቡድን መብት መከበር ነው፡፡

- ከለውጥ ስልት አንጻር - ሊበራል ዴሞክራሲ የተጠናና የሰከነ ለውጥን የሚደግፍና የሚያናጋ ግብታዊ ለውጥን የሚቃወም ሲሆን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በበኩሉ ሥር ነቀል የሆነ አብዮታዊ እንቅስቃሴና ለውጥን የሚደግፍ ነው፡፡

- ከመንግሥት ሚና አንጻር - ሊበራል ዴሞክራሲ በግለሰብ ነፃነትም ሆነ በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥትን በሕግ ያልተገደበ ጣልቃ ገብነት የሚቃወም ሲሆን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ደግሞ መንግሥት በሁሉም መስክ የመሪነትና የበላይነት ሚና እንዲኖረው የሚፈልግ ነው፡፡

- ከፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ አንጻር -ሊበራል ዴሞክራሲ በአንድ ኅብረተሰብ ውስጥ ጠላትና ወዳጅ ብሎ የሚፈርጀው በመደብ መልክ የሚገለፅ የኅብረተሰብ ክፍል የሌለው ሲሆን፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግን ኅብረተሰብን በተለያዩ መደባዊ ጠላትነትና ወዳጅነት ከፋፍሎና ፈርጆ ትግል የሚያካሂድና በዚህ ፍረጃ ውስጥም ካፒታሊዝምን በጠላትነት የሚያይ ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡

ከእነዚህ ዋናዋና መመዘኛ ነጥቦች አኳያ ሲታይ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ግልጽ የሆነ ርእዮተ-ዓለማዊ ወይም የኢኮኖሚና የፖለቲካ የአጀንዳ ልዩነት አለ ከተባለ፣ ይህ ልዩነት በግልጽ የሚታየው በኢህአዴግ እና በኢዴፓ መካከል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሊበራል ዴሞክራሲን እናራምዳለን የሚሉ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ያሉ ቢሆኑም በተግባር የሚያካሂዱት ፖለቲካ ከሊበራል አስተሳሰብና ስልት እጅግ የራቀና ጽንፈኝነት ያጠላበት በመሆኑ እነሱን በሐሳብ ደረጃ እንጂ በተግባር የሊበራል ርእዮተ ዓለም አራማጆች ናቸው ብሎ መቀበል ያስቸግራል፡፡ በኢህአዴግና በሌሎች ኅብረ-ብሔራዊ ባልሆኑ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ግን ከርእዮተ-ዓለማዊ አሰላለፍ ወይም ከአገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳ አንጻር መሠረታዊ የሚባል ልዩነት አለ ማለት አይቻልም፡፡ ለዚህም ነው በፓርቲዎች የኅብረት ጥያቄ ላይ የአደረጃጀትና የአገራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራም መቀራረብ ቀዳሚ መስፈርት መሆን አለበት በማለት ኢዴፓ የሚከራከረው፡፡

በአጠቃላይ ኢህአዴግ የአስተሳሰብ እድገት በማምጣት የመድብለ - ፓርቲና የነፃ- ገበያ ሥርዓትን እንዲያካትት አድርጌዋለሁ ባለው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰቡም ቢሆን ሊበራል ዴሞክራሲ ሊያመጣው በሚችል የለውጥ ደረጃ የመድብለ -ፓርቲንና የነፃ-ገበያ ሥርዓትን በተሟላ ሁኔታ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአገራችን ሊያመጣ አይችልም፡፡ በርግጥ ከመሠረታዊው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ጋር በማይጣጣም ሁኔታም ቢሆን በኢህአዴግ አማካይነት በተወሰነ ደረጃ ካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የመድብለ - ፓርቲ እንቅስቃሴ በአገራችን ማቆጥቆጥ መጀመሩን መካድ አይቻልም፡፡ ነገር ግን ይህንን የማቆጥቆጥ ጉዳይ በተጨባጩ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ በመገደድ ራስን ከአበዳሪ ድርጅቶችና ከዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ጋር ለማቀራረብ ሲባል ከሚወሰድ መለስተኛ ታክቲካዊ ርምጃ በላይ ወደ እውነተኛ የመድብለ ፓርቲና የነፃ-ገበያ ሥርዓት እንዲያድግ ማድረግ የሚቻለው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሳይሆን በሊበራል ዴሞክራሲ መስመር ነው፡፡ የዓለም ታሪካዊ ሂደትና የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያረጋግጠውም ይህንኑ እውነታ ሲሆን በኢህአዴግ ሰነድ በግልጽ ተቀምጦ እንዳየነው ኢህአዴግ "እኔ ከሌለሁ አገሪቱ ትፈራርሳለች" የሚል አቋም በያዘበትና ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው ብሎ ባመነበት ሁኔታ የአገራችን ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታ ሊያስተናግደው በሚችለው መጠንም ቢሆን እውነተኛ መድብለ ፓርቲንም ሆነ የነፃ-ገበያ ሥርዓትን በኢትዮጵያ መገንባት ይቻላል ብሎ ማመን ያስቸግራል፡፡

ከ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ የግራ ፖለቲካ አቀንቃኝ የነበሩት የኢህአዴግ ሰዎች የሶሻሊዝም ርእዮት የውድቀት መገለጫ የሆነችውን አልባንያን ከማምለክና ኢምፔሪያሊዝምን ከማውደም መፈክር ወጥተው ዛሬ የካፒታሊስት ሥርዓት አራማጆች ነን ማለታቸው ቢያንስ በሐሳብ ደረጃ በብዙ ርቀት መለወጣቸውን ያሳያል፡፡ ነገር ግን በየሂደቱ በሚፈፅሟቸው ተግባራት ከልጅነት ጀምሮ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ስታሊናዊ አመለካከት ከውስጣቸው ሲተናነቃቸውና የማይናቅ ተፅዕኖ ሲያሳድርባቸው ይስተዋላል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአሁኑ ወቅት ደጋግመው እንደሚናገሩት ርሳቸውን ጨምሮ በትግሉ ውስጥ ረዥም ጊዜ የቆዩት ነባር አመራሮች ከኢህአዴግ ተጠራርገው መውጣቸው የማይቀር ከሆነ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባውና ከአመራሮቹ ጋር አብሮ ተጠራርጐ መውጣት ያለበት በኢህአዴግ ውስጥ ሸንኮፉ አልነቀል ብሎ ያስቸገረው ስታሊናዊ አመለካከት ነው፡፡ ነፃ-ገበያም ሆነ የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በአገራችን በሚፈለገው መጠን መምጣት የሚችለው በኢህአዴግ ውስጥ የአመራር አባላት ብቻ ሳይሆን መሠረታዊ የአመለካከት ለውጥ መምጣት ሲችል ጭምር ነው፡፡

### 3.2 ርእዮተ-ዓለማዊ ታማኝነታችን እስከ ምን ድረስ?

የአገርን ችግር ይፈታል ተብሎ እስከታመነበት ድረስ የፖለቲካ ኃይሎች ግልጽ የሆነ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ የሌለው የፖለቲካ ድርጅት አቅጣጫ አመላካች መሣሪያ /compass/ እንደሌለው መርከብ መሄጃ መንገዱንና መድረሻውን በአግባቡ የማያውቅ ከመሆኑም በላይ ለጥቅማችሁ ቆሜአለሁ ከሚላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችም ጋር ከስሜት ያለፈ መግባባትና መተዋወቅ ሊኖረው አይችልም፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶች በአገራችን መደራጀት ከጀመሩበት ከ1960ዎቹ ጀምሮ እስከ የደርግ ዘመን ማክተሚያ ድረስ ብዙዎቹ የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች የነበረባቸው ችግር ከርእዮተ-ዓለም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ከድጋፍ አልፎ ወደ አምልኮት የተጠጋ መሆኑ ነበር፡፡ ከ1983ዓ.ም በኋላ በፖለቲካ መድረኩ ተዋናይ የሆኑ ብዙዎቹ የፖለቲካ ኃይሎች መሠረታዊ ችግር ደግሞ ከቀድሞዎቹ በተቃራኒ ምንም ዓይነት በግልጽ የሚታወቅ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ የሌላቸው መሆኑ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ አንዳዶቹ ዛሬም ከቀድሞው ስታሊናዊ አመለካከታቸው ጋር ተጣብቀው የሚገኙ መሆናቸውን ድርጊታቸው የሚያሳይ ቢሆንም አቋማቸውን በግልጽ ለማራመድ ሲደፍሩ አይታዩም፡፡

ደርግን ጨምሮ በ1960ዎቹ እና 70ዎቹ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ባልተገናዘበ ሁኔታ ኢንዱስትሪ በሌለበት አገር "የወዝ አደሩን የበላይነት እናሰፍናለን" በማለት ለምሥራቁ ዓለም የግራ ርእዮተ-ዓለም የበለጠ ታማኝ መሆናቸውን ለማሳየት ርስ በርስ ሲፎካከሩ ኖረዋል፡፡ በዚያ ለማሌ ርእዮት የበለጠ ታማኝ የመሆን ፉክክር ውስጥ የአሁኑ መንግሥት ኢህአዴግም ሥልጣን ላይ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ የአልባኒያ ሶሻሊዝም ደቀ-መዝሙር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግን ጨምሮ ሌሎች የግራ ፖለቲካ አራማጅ የነበሩ ድርጅቶች በሙሉ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ ለሦስት ዐሥርት ዓመታት በፍቅር አቅፈውት የኖሩትና ሲገሉና ሲሞቱለት የኖሩት ርእዮተ-ዓለም መንኮታኮቱን ሲያዩ ያለምንም ይሉኝታ ሁሉም በአንድ ጊዜ ቀኝ ኋላ ዞረው የካፒታሊስት ሥርዓት ጠበቃ የመሆን ፉክክር ውስጥ መግባታቸውን አይተናል፡፡ እነዚህ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች ወደዚህ ዓይነቱ ተቃራኒ አቋም ራሳቸውን ያሸጋገሩት በራሳቸው ውስጥ በሂደት በተፈጠረ የአስተሳሰብ ለውጥ ሳይሆን የርእዮተ-ዓለሙ ግንባር ቀደም መሪ የነበረችው ሶቪዬት ኅብረትና ሌሎች የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች አቋማቸውን በመቀየራቸው ምክንያት የቀዝቃዛው ጦርነት በምዕራቡ ዓለም ርእዮተ-ዓለም አሸናፊነት ስለተጠናቀቀና ዓለማችን በሁለት የርእዮተ-ዓለም ጉራ መከፈሉ ስለአከተመ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነት አስገዳጅ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ባይፈጠር ኖሮ አገራችን ከደርግ ፍጻሜም በኋላ

ከመድብለ - ፓርቲና ከገበያ ኢኮኖሚ ለረዥም ጊዜ ርቃ መኖርዋ የማይቀር በሆነ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ምን ያህል ከራሳችን ተጨባጭ ሁኔታ የራቀና የማይጣጣም የውጭ አስተሳሰብ ኮራጆች ሆነን መኖራችንን ነው፡፡

ሶሻሊስታዊ አመለካከት ከፖለቲካዊ ዕምነትም በላይ የአንድ ትውልድ አምልኮት ሆኖ ለአንድ ትውልድ እልቂት ምክንያት እንዳልሆነ ሁሉ ዛሬ እንደ አሮጌ ቁና ተወርውሮ የትናንት አምላኪዎቹ በሙሉ የሚጠየፉት አመለካከት ሆኗል፡፡ ትናንት ከኛ ወዲያ ማርክሲስትነት ላሣር ነው ብለው ሌሎችን በከሃዲነት፣ በበራዥነት፣ በመደብ አስታራቂነትና በኢምፔሪያሊዝም ቡችላነት በመፈረጅ በመገዳደል ሂደት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ዛሬ ከማንም በላይ የምዕራቡ ዓለም ርእዮት ጋሻ ጃግሬ ሆነዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ትናንትም ሆነ ዛሬ የውጭ ርእዮት አቀንቃኝ እየሆን ያለነው ርዕዮቱ አገርንና ሕዝብን ይጠቅማል ከሚል ዕምነትና ግንዛቤ በመነጨ ሳይሆን ከሌሎች ጋር ግልጽ ልዩነት ፈጥረን ለመታገልና የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር የሚያስችለን መሣሪያ አድርገን ስለምናየው ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጠቃሚ ሆኖ የተገኘን የውጭ አስተሳሰብ በአግባቡ ኮርጆ መጠቀም ስህተት ባይሆንም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለራሣችን አገርና ሁኔታ መፍትሄ የሚሆን አገር በቀል /Indigenous/ አስተሳሰብ በማመንጨት ረገድ አእምሮአችን የተዘጋ ሆኖ ኖሯል፡፡ ስለ ድህነታችንና ኋላቀርነታችን ብዙ ምክንያቶችን ስንደረድር የምንደመጥ ቢሆንም የሐሳብ ድሀ ከመሆናችን የበለጠ ለምንገኝበት ሁኔታ ተጠያቂ የሚሆን ምክንያት አለ ማለት ግን አይቻልም፡፡ ችግሩ እኛ ኢትዮጵያውያንም ሆነ በአጠቃላይ አፍሪካውያን በሐሳብ ድህነት የተጠቃን መሆኑን አምነን መቀበል ራስን ማሳነስና ፖለቲካዊ ስህተት መስሎ ስለሚታዬን ለኋላ ቀርነታችን የባሪያ ንግድን፣ ቅኝ ገዥነትን፣ የተፈጥሮ አደጋን፣ አምባገነናዊ ሥርዓትን፣ የርስ በርስ ጦርነትን፣ በሽታንና ማይምነትን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መረገምን፣ አሁን አሁን ደግሞ ግሎባላይዜሽንን ተጠያቂ አድርገን ማቅረብን እንመርጣለን፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ አንዳንዶቹ ለኋላ ቀርነታችን ምክንያቶች መሆናቸው እውነትና ሊካድ የማይችል ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ግን እንደሌላው ዓለም ሁሉ እነዚህን ችግሮች እንደ አመጣጣቸው ተቋቁመን ለማሸነፍ ያላስቻለን ዋናው ምክንያት የሐሳብ ድህነት መሆኑን ሊቀይረው አይችልም፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ዛሬ ላይ የምንገኝበት ሁኔታ ከአለፉት ሦስትና አራት ዐሥርት ዓመታት በአንፃራዊነት የተሻለ ነው ሊባል ቢችልም ለራሳችን ችግሮች ዘላቂ መድኀን የሆነ አገር በቀል /Indigenous/ አስተሳሰብ አመንጭቶ በማራመድ ረገድ ግን መሠረታዊ ለውጥ አምጥተናል ማለት አይቻልም፡፡ የወቅቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ቀዳሚ ችግር የምንከተለው

ሊዮን ሊዮን ሊዮን

ርእዮተ-ዓለም ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ትክክል የመሆን የአለመሆኑ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ጭራሽም የምንከተለው ርእዮት ምን እንደሆነ ግልጽነት የሌለን መሆኑ ላይ ነው፡፡ በመንግሥትነት ደረጃ የተቀመጠውን ገዥውን ፓርቲ ስናይ በደፈናው “አብዮታዊ ዴሞክራት ነኝ” ከማለት ባለፈ ከመጀመሪያ ከማሌ ርእዮት ወደ መድብለ - ፓርቲና የነፃ-ገበያ አራማጅነት በምን ሁኔታና አግባብ እንደተሸጋገረ ግልጽነት ያልነበረው ሲሆን “ወደዚህ ዓይነቱ ለውጥ ተሸጋግሬአለሁ” ካለም በኋላ የሚያራምደው ርእዮት ሶሻሊስታዊ ይሁን ካፒታሊስታዊ፣ ወይም አገር በቀል የሆነ አዲስ ቲዎሪ ግልጽነት የለውም፡፡

ኢህአዴግ ሲያስፈልገው “አገሪቱ እኔ ከሌለሁ ትፈራርሳለች” የሚልና “በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር መንግሥት ነው” በሚል ፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-ካፒታሊስት የሆነ አቋም በይፋ ሲያራምድ የሚታይ ሲሆን፤ ሲያስፈልገው ደግሞ “የመድብለ - ፓርቲም ሆነ የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚን ለማራመድ ከእኔ የተሻለ የለም” በማለትና “ነጭ - ካፒታሊስታዊ ሥርዓት ለመገንባት የምታገል ነኝ” በማለት የምዕራቡ ዓለም ርእዮት ወዳጅ ሆኖ ለመቅረብ ሲሞክር ይታያል፡፡ ሲያስፈልገው “ሊበራል ዴሞክራሲ የጥቂት ካፒታሊስቶች ጠበቃ የሆነና በአገራችን ምንም ዓይነት ማኅበራዊ መሠረት የማይኖረው ለአገራችን የማይበጅ መስመር ነው” ብሎ ያወግዝና፣ ሲያስፈልገው ደግሞ “የሊበራል ዴሞክራሲ ዋና መገለጫ የሆኑትን ማለትም የመድብለ - ፓርቲና የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን ማራመድ ለአገራችን ህልውና የግድ አስፈላጊ ነው” ብሎ ሲከራከር ይደመጣል፡፡ ሲያስፈልገው በብዙ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የምዕራብ አገሮች ተከታይና አወዳሽ ሆኖ የሚቀርብ ሲሆን፣ ሲያስፈልገው ደግሞ ራሱን ከማንም በላይ የቻይና ፈለግ ተከታይና አድናቂ አድርጐ ሲያቀርብ ይታያል፡፡

በእነዚህና በተለያዩ በየጊዜው ከሚያሰራጫቸው ሠነዶቹ ሊጠቀሱ የሚችሉ ርስ በርስ ተቃራኒ በሆኑ ምሳሌዎች ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ግራ ዘመም ኃይል ከመሆን ባለፈ ግልጽ የሆነ የርእዮተ-ዓለም አቅጣጫ የሌለው፣ ወይም ለመያዝ ያልፈለገ መሆኑን ማሳየት ይቻላል፡፡ በተለይም ገዥው ፓርቲ በወረቀት ላይ እምነቴ ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸውን በርካታ መርሆዎች በተግባር ምን ያህል እንደማያከብራቸው ስንታዘብ ገዥው ፓርቲ የጠራ አቅጣጫ አለማራመድን ራሱን እንደቻለ አንድ ጠቃሚ ስልት አድርጐ የመውሰድ ጨዋታ ውስጥ እንደሚገኝ የበለጠ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ አንድ ፓርቲ ይጠቅመኛል ብሎ የሚያምንበትን ስልት የመጠቀም መብት ያለው መሆኑ፣ የአገርን ተጨባጭ ሁኔታም ከርእዮተ-ዓለም እስረኝነት ወጣ ባለ የተግባራዊነት /pragmatic/ መንገድ ለማየት ቢሞክር ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ኢህአዴግ

በሚገኝበት ደረጃ ከአጠቃላይ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ አንጻር ግራ አጋቢና ተተንባይ አለመሆን (Unpredictable) ግን በየትኛውም መመዘኛ ተገቢ ነው ሊባል አይችልም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚገኙበትን ሁኔታ ስናይ፣ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በትግሉ ውስጥ ተዋናይ ከሆኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ኢህአዴግን ከመቃወምና ከማውገዝ ያለፈ የተጨበጠ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫም ሆነ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አማራጭ አላቸው ለማለት ያስቸግራል። ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ ኢዴፓ በ1995 ዓ.ም የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጅ ነኝ ብሎ በእያንዳንዱ አገራዊ አጀንዳ ላይ ዝርዝር አቋሙን ይዞ ከወጣ በኋላ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሊበራል ዴሞክራሲና የሶሻል ዴሞክራሲ አራማጆች ነን ሲሉ የሚደመጡ ቢሆንም እነዚህ ፓርቲዎች እናራምደዋለን ስለሚሉት አቅጣጫ በዝርዝር ያስረዱበት ሁኔታ የሌለ ከመሆኑም በላይ በተግባር የሚያራምዱት አቋምም ከሊበራልም ሆነ ከሶሻል ዴሞክራቶች ባህሪ በእጅጉ የተለየና የሚቃረን ሆኖ ስለሚታይ እነዚህ ፓርቲዎች ራሳቸው በውል የተረዱት የጠራ ርእዮተ- ዓለማዊ አቅጣጫ አላቸው ብሎ ለማመን ያስቸግራል። ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ራሱን እየገመገመና እያረመ ከመጣው ከኢዴፓ በስተቀር አብዛኛዎቹ የሊበራል ዴሞክራሲ አራማጆች ነን ሲሉ የሚደመጡት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በእያንዳንዱ አገራዊ ጉዳይ ላይ እጅግ የከረረ፣ በጥላቻ የተሞላ፣ ለድርድርና ለመቻቻል ፖለቲካ በር የማይከፍትና ለሊበራል ባህሪ ተቃራኒ የሆነ የአብዮታዊነት ይዘት ያለው ጽንፈኛ አቋም ሲያራምዱ ይታያሉ።

እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ከወቅቱ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በወረቀትና በሐሳብ ደረጃ ሊበራል መስሎ መታየትን የሚመርጡ ቢሆንም እያንዳንዱን ተግባራዊ እንቅስቃሴአቸውን ስንመለከት ግን ከሕዝባዊ ርምጃ (mob justice) ወይም ከየትም ፍጭው ዱውቄቱን አምጭው (the end justifies the means) አመለካከት ገና እንዳልተላቀቁ በግልጽ ይታያል። መንግሥትን ለመጣልና ወደ ሥልጣን ለመውጣት ያበቃናል ብለው እስከ ገመቱ ድረስ የትኛውንም ዓይነት የውሸት፣ የቅጥፈት፣ የተንኮልና የመጠፋፋት ስልት ጭምር ከማራመድ ወደ ኋላ እንደማይሉ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን በተከሰተው የፖለቲካ ሁኔታ በግልጽ ታይቷል።

የሶሻል ዴሞክራሲ አራማጅ ነን ሲሉ የሚደመጡት አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ጽንፈኝነትና ጭፍን ጥላቻ የተሞላበት ፖለቲካ ማራመዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ "መንግሥት ሙሉ በሙሉ በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳትፎ ሊኖረው አይገባም" የሚል አቋም በግልጽ ሲያራምዱ ስለሚታይ እነዚህ ኃይሎች ሶሻል ዴሞክራሲን ስሙን እንጂ በተግባር ምን ማለት እንደሆነ በውል እንዳልተረዱት በግልጽ ይታያል። እንዲያውም በአገሪቱ የሚገኙ ተቀዋሚ ፓርቲዎች

በወቅታዊ አገራዊ ጉዳዮች ከኢህአዴግ አስተሳሰብ ተቃራኒ የሆኑ መግለጫዎችን ከማውጣት፣ ኢህአዴግ የሚያራምዳቸውን አቋሞችና የሚፈጽማቸውን ተግባራት በጭፍን ከመቃወም፣ በምርጫ ዘመቻ ወቅትም በጥቅሉ ከማንም በላይ የሰብአዊ መብት፣ የዴሞክራሲና የነፃ-ገበያ ጠበቃ ነን እያሉ ከመከራከር ያለፈ የጠራ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ መያዝንም ሆነ ግልጽ የሆነ አማራጭ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አጀንዳ ማራመድን በፖለቲካ ትግሉ ሂደት ውስጥ እንደ አንድ አስፈላጊና ጠቃሚ ቁምነገር አድርገው ገና አልወሰዱትም ማለት ይቻላል፡፡ እውነታው ይህ ባይሆን ኖሮ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በውስጣቸው ስላለው አገራዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳ ምንም ዓይነት ትኩረት ሳይሰጡ የኢህአዴግ ተቃዋሚ መሆንን ብቻ እንደ ዋነኛና ብቸኛ መመዘኛ በመውሰድ ሁልጊዜ የጋራ ኀብረት ለመፍጠር ሲደክሙ ባልታዩ ነበር፡፡

ከዚህ በላይ ለማሳየት የተሞከረው የማንኛው ፓርቲ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ ለአገራችን እንደሚጠቅም ወይም እንደሚጐዳ ሳይሆን በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት በአገራችን የሚገኙ ፓርቲዎች ጭራሽም ይህ ነው የሚባል የጠራ ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ አንድ ፓርቲ ከዓለም አቀፍ የፖለቲካ አሰላለፍ አንጻር የግድ አንዱን መርጦ መያዝ ይገባዋል ሊባል ባይቻልም፣ ቢያንስ በወቅቱ የዓለማችን የፖለቲካ አሰላለፍ የትኛውን ርእዮተ-ዓለማዊ አቅጣጫ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ሊጠቀምበት እንደሚፈልግ፣ አሊያም ከየትኛውም የውጭ የፖለቲካ ጐራ ያልተቀዳና ያልተነካካ አዲስ አገር በቀል (Indigenous) የሆነ አቅጣጫ የሚያራምድ መሆኑን እወክለዋለሁ ለሚለው ሕዝብ በግልጽ መናገርና ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ የሆነ ሆኖ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች በዚህ ረገድ የአስተሳሰብ ንጥፈት የሚታይባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ከ1983 ዓ.ም በፊት የማሌ ርእዮት የበለጠ ወዳጆች ነን የሚል ፉክክር ውስጥ ገብተው የነበረውን ያህል በአሁኑ ወቅት ደግሞ ሁሉም በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት የሚገኙ ፓርቲዎች የዴሞክራሲና የነፃ-ገበያ ሥርዓት የበለጥን ወዳጆች ነን የሚል አዲስ ፉክክር ውስጥ እንደገቡ በግልጽ እየታየ ነው፡፡

በዚህ ምክንያት በአሁኑ ወቅት “ዴሞክራሲ” የሚለውን ቃል በመጠሪያ ስሙ ውስጥ ያልሻጠ አንድም ፓርቲ በአገራችን የማይገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ እየአንዳንዱ ፓርቲ አለኝ የሚለው እምነትና ሲያከናውን የሚታየው ተግባር ምንም ይሁን ምን በዴሞክራሲና በነፃ-ገበያ ላይ ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን ገንቢ ትችትም ለማቅረብ ሲደፍር አይታይም፡፡ በ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ በደርግ ወቅት የማሌን አስተሳሰብ መቃወም አንደ አላዋቂ፣ እንደ ኋላ ቀር፣ ከዚያም በላይ አልፎ በፀረ-ሕዝብነት ያስፈርጅ የነበረውን ያህል በአሁኑ ወቅትም

ዴሞክራሲን ለመተቸት መሞከር በተመሳሳይ ሁኔታ ያስፈርጃል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፍረጃ ቢያንስ ማንኛውንም ዓይነት ሐሳብ መቃወም መቻል መብት መሆኑን አምኖ ከሚቀበለው ከራሱ ከዴሞክራሲ ቀዳሚ መርህ ጋር የሚጋጭ ቢሆንም፣ ከሁሉም በላይ ግን እንዲህ ዓይነቱ አንድን ዓይነት የውጭ የፖለቲካ አመለካከት በጭፍን የማምለክ ባህርያችን የራሳችንን አገር በቀል /Indigenous/ አስተሳሰብ አመንጭቶ ከመጠቀም አንጻር ትልቅ እንቅፋት ሆኖብናል ማለት ይቻላል፡፡

ዴሞክራሲ የወቅቱ የዓለማችን መዝሙር ስለሆነ፣ ወይም ደግሞ ዴሞክራሲን መቃዎም በአሉታዊነት የሚያስፈርጅ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ለአገራችን ወቅታዊና የወደፊት የፖለቲካ ሁኔታ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው ብሎ ስለሚያምን የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊም የዴሞክራሲ ደጋፊ ነው፡፡ በዚህ ላይ በአንባብያን ዘንድም አንድ ዓይነት መግባባት ሊኖር እንደሚችል መገመታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ጸሐፊው ምንአልባትም እስካሁን በአገራችን የፖለቲካ መድረክ በድፍረት ተነሥቶ በማያውቅ መጠን “ዴሞክራሲን እንዴትና በምን ሁኔታ በአገራችን ልንተገብረው እንደሚገባ ሰፊ ውይይትና ክርክር ሊካሄድ ይገባዋል” ብሎ ያምናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በዴሞክራሲ ላይ የሚነሣ ጥያቄ በአፍሪካም ሆነ በሌሎች ዓለማት በሚገኙ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች ተደጋግሞ የሚነሣ ቢሆንም በእኛም አገር ሆነ በሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት በሚፍጨረጨሩ እኛን መሰል ታዳጊ አገሮች ውስጥ በሚገኙ የፖለቲካ ሰዎች ግን ጉዳዩ በጎላ መጠን ውይይት ሊካሄድበት የማያስፈልግና የማይገባ ነውር /Taboo/ ተደርጐ ይታያል፡፡

በኢዴፓ ውስጥም አልፎ አልፎ ጥያቄው እንደ ጥያቄ ብልጭ ያለበትና አመራር አባላቱ ሐሳብ የተለዋወጡበት ተደጋጋሚ አጋጣሚ ቢኖርም በጉዳዩ ላይ የፓርቲ አቋም መያዝ በሚያስችል ደረጃ ጥልቀት ያለው ውይይት ተካሂዶ አያውቅም፡፡ አሁንም በዚህ ጉዳይ ላይ ጥያቄ በማጫርም ደረጃ ቢሆን የሚነሡት ጉዳዮች በግል ኃላፊነቴ እንጂ በፓርቲ ኃላፊነት የሚነሡ አቋሞች አይደሉም፡፡ ይህንን ዓይነት የሚፈራ ሐሳብ ለውይይት ማቅረብ በብዙ ሰዎች ውስጥ በጎ ያልሆነ ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ቢቻልም የኢዴፓም ሆነ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የወቅቱ ተልዕኮ በፖለቲካ ባህላችን ውስጥ ያለአግባብ ነውር /Taboo/ ተደርገው የሚታዩትን ሐሳቦች በድፍረት አንስቶ በመድረክ ላይ መወያየት መቻል ስለሆነና፣ እንዲህ ዓይነቱን አከራካሪ ሐሳብ ለውይይት ለማቅረብም በአንድ በኩል ተቃዋሚ መሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአሉባልታ ፈንጣጣ የወጣለት ሰው መሆን የተሻለ ዕድል እንደሚሰጥ በማመን ጸሐፊው ሃሣቡን ለውይይት ለማቅረብ ደፍሯል፡፡ የጸሐፊው ተልዕኮ ጉዳዩን ለውይይት እንዲበቃ

የሚያስችል ጥያቄ ከማጫር ያለፈ ይዘትና ዓላማ እንደሌለው የአንባብያን መረዳት አስፈላጊ ሲሆን፣ ጥያቄ የማጫሩ ተልዕኮ ከዚህ በላይ ላዩነው "የርእዮተ-ዓለም ታማኝነታችን እስከምን ድረስ?" ለሚለው ርእስ በሚመጥን መልኩ ብቻ እንደሚከተለው ለማቅረብ ይሞከራል።

ኢዮፓ
ኢዮፓ
ኢዮፓ

### *3.2.1 ዴሞክራሲ ጥያቄ ሊነሣበት አይችልምን?*

ማንኛውም ጥሩ ወይም ጠቃሚ የሚባል አስተሳሰብ አገልግሎቱ በአንፃራዊ ሁኔታዎች ሊሰፋ ወይም ሊጠብ የሚችልበት የራሱ ገደብ ይኖረዋል፡፡ ዴሞክራሲም ጠቃሚ ነው ሲባል በሁሉም አካባቢና ሁኔታ በተመሳሳይ መጠን ይጠቅማል ወይም ሊተገበር ይችላል ማለት አይደለም፡፡ በዘመኑ የዓለም ተጨባጭ ሁኔታ በዴሞክራሲ ላይ በጥቅሉ ይጠቅማል አይጠቅምም የሚል የጠበበ ክርክር ማንሣት አስፈላጊ ባይሆንም፣ ዴሞክራሲ በምን ዓይነት ማኅበራዊ ሁኔታ፣ በምን ዓይነት ቅደም ተከተልና በምን ዓይነት ፍጥነት በአንድ አገር ላይ ሊተገበር እንደሚችል ግን የጐላ ጥያቄ ሊነሣበት የሚገባ ፅንሰ-ሐሳብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የራሱ የዴሞክራሲ አንዱ መገለጫ የሆነው የሐሳብ ነፃነት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው አንድ ኅብረተሰብ ወይም የሰው ልጅ ማንኛውንም ነገር የመተቸትም ሆነ የመቃወም መብት ቢኖረው ለራሱ ለኅብረተሰቡ እድገት ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት ስለሆነ ዴሞክራሲም ከሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ተለይቶ በራሱ መርህ ጥያቄ ሊነሣበት የሚገባ ፅንሰ-ሐሳብ ከመሆን የሚድንበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ከራሱ ከዴሞክራሲ መርህ በተጨማሪ ዴሞክራሲን ጥያቄ እንዲነሣበት የሚያደርገው ምክንያት ፍጹማዊ /Perfect/ የመንግሥት ሥርዓት አለመሆኑ ነው፡፡ ዊኒስተን ቸርችል በአንድ ወቅት እንዳሉት - ዴሞክራሲ እስካሁን ተፈትነው ከወደቁትና ከሌሎች አማራጮች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ነው ሊባል የሚችል እንጂ በራሱ የተዋጣለት ሊባል የሚችል ሥርዓት አይደለም፡፡ በዴሞክራሲ አግባብ የሚፈጸሙ ተግባራትና የሚወሰኑ ውሳኔዎች ከሌሎች ዘዴዎች የተሻሉ ሆነው ተገኙ እንጂ ዴሞክራሲ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ተግባራት ወይም ውሳኔዎች ሙሉ በሙሉ ተገቢና ጠቃሚ ሆነው ተገኝተዋል ማለትም አይደለም፡፡ ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጥስ እንዲገደል የተወሰነበት በዴሞክራሲያዊ አግባብ (በሕዝብ ውሳኔ) ቢሆንም ውሳኔው ፍትሐዊ አልነበረም የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ ዴሞክራሲ የዓለም ገዥ ሐሳብ በመሆን ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው የብዙኀኑ አስተሳሰብ ተቀባይነት የሚያገኝበትና የበላይ የሚሆንበት አሠራር በመሆኑ ነው እንጂ በዴሞክራሲያዊ አግባብ የሚወሰን ውሳኔ ሁሉ ትክክለኛ ነው ከሚል መነሻ አይደለም፡፡

ዴሞክራሲ በትርጉም ደረጃ በዓለም ላይ አንድ ዓይነት ወጥ ይዘት ያለው ቢሆንም በተለያዩ አገሮች በተለያዩ አግባቦች ሲተገበር የምናየውም በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ በተመሳሳይ ሁኔታ ሊተገበር የማይችልበት ተፈጥሯዊ ውስንነት ስላለው ነው፡፡ በዚህ ውስንነቱ

ምክንያትም ዴሞክራሲ የብዙ ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሄ ሆኖ ያገለገለውን ያህል አዳዲስ ችግሮችን የሚፈጥርበት፣ ወይም ነባራዊ ችግሮችን ሊያባብስ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩም በተደጋጋሚ ታይቷል። በዚህም ምክንያት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተጠቅመዋል በሚባሉ አሜሪካንን በመሰሉ አገሮች ሳይቀር በርካታ ከወታደራዊ፣ ከፍትሕና ከፋይናንስ ጉዳይ ጋር የተያያዙ ተቋማት በአሁኑ ወቅት ጭምር ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ ዘዴ /political appointment/ እንዲደራጁ ይደረጋል። ስለዚህ አንድ ፍጹማዊ ያልሆነ ወይም የራሱ ድክመቶችና ጉድለቶች ያሉበት ሥርዓት እነዚህ ድክመቶቹና ጉድለቶቹ ይሻሻሉ ዘንድ ለትችት ወይም ለጥያቄ ክፍት ሊሆን የግድ ይለዋል።

ዴሞክራሲ ጥያቄ ወይም ትችት ሊነሣበት የሚገባው ፍጹማዊ ሥርዓት ስላልሆነ ብቻም ሳይሆን እንደ ማንኛውም ሥርዓት በተፈጥሮ ሕግ የማደግና የማርጀት አደጋ ሊገጥመው የሚችል ሥርዓት በመሆኑም ጭምር ነው። የአብዛኛውን ሕዝብ የበላይነት ለማረጋገጥ ተብለው በዴሞክራሲያዊ አግባብ የተካሄዱ ለውጦች በሂደት አቅጣጫቸውን እየሳቱ ውጤታቸው የጥቂቶች የበላይነትን ማስፈን ሲሆን ታይቷል። ይህም ዓይነቱ ችግር ዴሞክራሲ ዘግይቶ ወይም በአዲስ መልክ ተቀባይነት ባገኘባቸው አገሮች ብቻ ሳይሆን በዴሞክራሲ የረዥም ጊዜ ሂደት በምሳሌነት በምትጠቀሰው አገር በአሜሪካን ሳይቀር እየታየ በመምጣቱ "ለአሜሪካን ከእንግዲህ የሚያስፈልጋት የበለጠ ዴሞክራሲያዊ መሆን ሳይሆን ዴሞክራሲያዊነትን መቀነስ ነው" የሚል አዲስ ዓይነት ክርክር እያሥነሳ ይገኛል። ድሮውንም በሁለት ፓርቲዎች የበላይነት ብቻ ተወስና የብዙኃን ፓርቲዎች አገር መሆን ያልቻለችው አሜሪካ አሁን አሁን እነዚህ ያሉዋት ሁለት ፓርቲዎችም ትርጉም የለሽ እየሆኑ የአገሪቱ ፖለቲካ በግለሰቦች ታዋቂነትና ተሰሚነት ላይ የተንጠለጠለበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

ቀደም ሲል እንደ ዛሬው በአሜሪካ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ሕዝቡን የመድረስ ጉልበት ባልነበራቸውና የፖለቲካ ተመራጮችና መራጩ ሕዝብ በቀላሉ መገናኘት በማይችሉበት ወቅት የምርጫ እጩ ተወዳዳሪዎች ለምርጫ የሚቀርቡት የፓርቲያቸው ነጸብራቅ ሆነው ነበር። አሁን አሁን ግን ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ፓርቲዎች የእጩዎቻቸው ነጸብራቅ እየሆኑ ነው። እንዲያውም እጩዎች ፓርቲያቸውን ወክለው ለምርጫ ለመቅረብ በቅድሚያ ርስ በርስ በሚወዳደሩበት /Primary election/ ወቅት የራሣቸውን ፓርቲ አሠራርና አስተሳሰብ ሳይቀር እየተቃወሙ የምርጫ ዘመቻ ማድረግ ለመመረጥ የተሻለ ዕድል እየሆነላቸው መጥቷል። ለአገሪቱ ፕሬዘዳንትነት የሚወዳደሩ እጩዎች ሳይቀሩ የቱንም ያህል ከፓርቲያቸው አቋም የሚጻረር አቋም ቢያራምዱ በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የሰፈረውን የእጩነት መስፈርት እስካሟሉ

ድረስና በየምርጫ አካባቢው ያለው የፓርቲ ደጋፊ /Electoral college/ ለፓርቲው እጩ እንዲሆኑ እስከደገፋቸው ድረስ ፓርቲው በእጩዎቹ ላይ የተለየ ውሳኔ የመስጠት መብት የለውም፡፡ ከመጀመሪያውም ለርስ በርስ የቅድሚያ ውድድር /Primary election/ ሪፐብሊካንን ወይም ዴሞክራት ፓርቲን ወክለው ለምርጫ የሚቀርቡት ራሳቸው እጩዎቹ ናቸው እንጂ ፓርቲው እጩዎችን መልምሎ የሚመድብበት አሠራር የለም፡፡ የፓርቲው መብት ለፓርቲው እጩ እንዲሆኑ ደጋፊዎች የመረጧቸውን እጩዎች በጉባዔ /convention/ ዕውቅና መስጠትና ለምርጫ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ የማሰባሰብ ድጋፍ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ እጩው ፓርቲውን ወክሎ ለምክር ቤት አባልነትም ሆነ ለፕሬዝዳንትነት ከተመረጠ በኋላም ከፓርቲ ትዕዛዝ የመቀበልም ሆነ የፓርቲውን አስተሳሰብ የሚደግፍ አቋም የማራመድ ግዴታ የለበትም፡፡ በሚቀጥለው ምርጫ ላልመረጥ እችላለሁ ብሎ እስካልሰጋ ድረስ ሙሉ በሙሉ ፓርቲውን የሚጻረር አቋም ቢያራምድ እንኳ ሊወሰድበት የሚችል ርምጃ የለም፡፡

ፓርቲዎቹ በተለምዶ በማራመድ ከሚታወቁባቸው አንዳንድ ከውርጃ፣ ከተመሳሳይ ፆታ ጋብቻ፣ ከሞት ፍርድ፣ ከጦር መሣሪያ ባለቤትነት፣ ከመንግሥት ስፋትና ጥበት ጋር ከተያያዙና እነዚህን ከመሰሉ ሌሎች ዋና ዋና አስተሳሰቦች በስተቀር ዝርዝር የሆነ የፖለቲካ ፕሮግራምም ሆነ በተመረጡ አባሎቻቸው ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ሥልጣን የላቸውም፡፡ አንድ የፓርቲ አባል ተመራጭ ሆኖ ባገለገለበት ወቅት ሙሉ በሙሉ ከፓርቲው የሚጻረር አቋም ሲያራምድ ከርሞ እንደገና ለዚያው ፓርቲ በእጩነት ቀርቦ ለመወዳደር ቢፈልግ እንኳ ፓርቲዎቹ ሰውዬው ምን ያህል ከፓርቲው የሚጻረር አቋም ሲያራምድ እንደቆዬ ለመራጩ ሕዝብ መረጃ በማቀበል ድጋሜ እንዳይመርጡት ከመሞከር ባለፈ በድጋሜ እጩ ሆኖ እንዳይወዳደር የማድረግ መብት የላቸውም፡፡ ስለዚህ በተግባር ሲታይ በአሜሪካ በፓርቲ ስም የፖለቲካ ተዋናይ የሆኑ ግለሰቦች እንጂ ቋሚ የሆነ አጀንዳና የሚጨበጥ ሥልጣን ያላቸው ፓርቲዎች አሉ ማለት ያስቸግራል፡፡

የፓርቲ ውክልና ይዞ ለአገሪቱ ፕሬዝዳንትነት የተወዳደረው እጩም አንድ ጊዜ በመራጩ ሕዝብ ተመርጦ ኋይት ሃውስ ከገባ በኋላ በፓርቲው ስም የአገሪቱን አስተዳደር የሚያቋቁመው ራሱ ፕሬዝዳንቱ ነው እንጂ ፓርቲው አንድም ሰው የመመደብ መብት የለውም፡፡ አስተዳደሩ ከተቋቋመ በኋላም ፕሬዝዳንቶች ብዙውን ጊዜ ሥራቸውን ሲያከናውኑ የሚታዩት በዋሽንግተን ዙሪያ በተሰባሰቡ የተለያዩ የጥቅም አስከባሪ ተቋማት ተወካይ በሆኑ ሎቢስቶችና የማኅበራት ተወካዮች በሆኑ ግፊት እንጂ ለመረጣቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሆን አይታይም፡፡ በዚህም ምክንያት በአብዛኛው ሕዝብ የተመረጠውና ለአብዛኛው ሕዝብ ጥቅም ይሠራል ተብሎ የሚጠበቀው

አስተዳደር በውጤቱ የአናሳዎች ጥቅም አስጠባቂ የሚሆንበት አጋጣሚ በአሜሪካ ተደጋግሞ የሚታይ እውነታ ሆኗል።

በአሜሪካ ፖለቲካ የአገልግሎት ዘመናቸው ሁለት ዓመት ብቻ በመሆኑ ምክንያት በተሻለ ሁኔታ የሕዝብን ፍላጐት ለማዳመጥ ሲገደዱ የሚታዩት የኮንግረስ አባላት ናቸው። የኮንግረስ አባላት የሥራ ዘመናቸው በጣም አጭር በመሆኑ ምክንያት ስለሚቀጥለው ምርጫ መጨነቅ የሚጀምሩት ገና ሥራ በጀመሩ በመጀመሪያው ቀን ነው ማለት ይቻላል ። የኮንግረስ አባላቱ ከምንም ነገር በላይ የሚጨነቁት ከሁለት ዓመት በኂላ እንደገና ለመመረጥ በመሆኑም ብዙውን ጊዜ ድምፅ ለመስጠት የሚፈልጉት አገሪቱንና ሕዝቡን ለሚጠቅሙ ጉዳዮች ሳይሆን ለጊዜው መራጩን ሕዝብ ያስደስተዋል ብለው ለሚያስቡት ጉዳይ ሲሆን ይታያል። የዚህ ዓይነቱ የኮንግረስ አባላት የእወደድ ባይነት /Populist/ ስልትም ኮንግረሱ ጥራት ያለው ሕግ እንዳያወጣ ምክንያት እየሆነ ነው የሚሉ ስጋቶችን እየፈጠረ መጥቷል።

እንዲያውም አሁን አሁን የፖለቲካ ሰዎችን ህልውና በመወሰን ረገድ ከመራጩ ሕዝብ የበለጠ ጉልበት ያላቸው በጥቂት ካምፓኒዎች ቁጥጥር ሥር ያሉ የመገናኛ ብዙኃን እየሆኑ መጥተዋል። ሕዝቡን በቀላሉ ለማግኘት ያላቸውን ዕድል በመጠቀምም ከፖለቲካ ድርጅቶችና መሪዎች የበለጠ ሕዝቡን በሚፈልጉት አቅጣጫ የመምራት አቅም ያላቸውም እነዚህ በጥቂት የግል ባለሀብቶች የሚመሩ ሚዲያዎች ሆነዋል። ይህ ዓይነቱ የመገናኛ ብዙኃን የበላይነትም የአሜሪካንን የምርጫ ዘመቻ ከተጨባጭ የአገራዊ ጉዳዮች ክርክር ይልቅ የእወደድ ባይነት መፈክር የበለጠ የሚያጠላበት እያደረገው መጥቷል።

በእነዚህ ምክንያቶች በአሜሪካን አገር በዴሞክራሲ አግባብ የሚመረጡ አካላት ጥራት ያለው /effective/ ሥራ ማከናወን የማይችሉበትና የሕዝብን እምነት የማያገኙበት አደጋ እየተፈጠረ መጥቷል። በአሜሪካ በሕዝብ አመለካከት /perception/ ላይ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩትም በቀዳሚነት ሕዝብ የሚወዳቸውና እምነት የሚጥልባቸው ተቋማት ሆነው የተገኙት እንደ ኮንግረስ ዓይነቶቹ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ሳይሆኑ ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ የሚቋቋሙት ማለትም - የፌደራል ፍርድ ቤት /Supreme court/፣ መከላከያ ሠራዊትና የፌደራል ባንክ /Federal Reserve system/ የመሳሰሉት ተቋሚት ሆነው ተገኝተዋል።

የአሜሪካን ዴሞክራሲ ስጋት ውስጥ እየገባ መሆኑን የሚያሣዩው ሌላው ቁም ነገር የመራጮች ቁጥር እያሽቆለቆለ መምጣት ነው። የመራጩ ሕዝብ ቁጥር በሂደት የበለጠ

እየጨመረ መምጣት ሲጠበቅበት ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ በሚታይበት የፕሬዝደንትነት ምርጫ በ1960ዎቹ ለመምረጥ መብቱ ካለው ሕዝብ ውስጥ በምርጫ ይሳተፍ የነበረው 64% ሲሆን ይህ መጠን በሂደት እያሽቆለቆለ በመምጣት በ1996 ዓ.ም ወደ 50% ወርዷል፡፡ እንዲያውም በአሁኑ ወቅት በአካባቢ ምርጫ የሚሳተፈው የአሜሪካን መራጭ ሕዝብ ከ10% ያልበለጠ እየሆነ መጥቷል፡፡ የመራጩ ሕዝብ ቁጥር በመጠኑ እንደገና ማንሰራራት የጀመረው በዋናነት ከ9/11 ጥቃት ጋር ተያይዞ ባለፉት 10 ዓመታት ነው፡፡

ከእነዚህ የአሜሪካ ወቅታዊ ሁኔታዎች የምንረዳው ቁምነገር የአሜሪካ ዴሞክራሲ በሂደት አሳሳቢ ችግሮች ከየገጠሙት እንደመጣና መሠረታዊ የሆነ የተኃድሶ ለውጥ እየጠዬቀ መሆኑን ነው፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በመጀመሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ቀጥለው ደግሞ የፖለቲካ መሪዎች በአሜሪካ ቀስ በቀስ የመደመጥና የመወሰን ጉልበት እያጡ መምጣታቸውንና በአንፃሩ ደግሞ መገናኛ ብዙኃን፣ የጥቅም አስከባሪ ወኪሎች /Lobbyists/ እና ጊዜያዊ የሕዝብ ስሜቶች /Public opinions/ በውሳኔ ሰጭነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ ይህ አደጋ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ስጋት እያደረባቸው የመጡ አንዳንድ ምሁራንና ጸሐፊዎች በአሁኑ ወቅት የአሜሪካን ዴሞክራሲ የበለጠ መስፋት ሳይሆን መጥበብ ይገባዋል የሚል ጥያቄ እያነሱ ቢሆንም አሜሪካ እንዴት ተመሥርታ የዓለም ልዕለ-ኃያል ለመሆን እንደበቃች እየረሳ የመጣውና ዴሞክራሲ ያሞላቀቀው አዲሱ ትውልድ ግን በቀላሉ ሊገታ በማይችል መጠን አሁንም ዴሞክራሲው የበለጠ እንዲሰፋ እየወተወተ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ብቁ የሆነ አስተዳደር ማጣት አሜሪካ ለዴሞክራሲ ስትል እየከፈለችው የሚገኝ ከባድ እዳ እየሆነባት ነው፡፡ ይህ የአሜሪካ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳዬን ዴሞክራሲ እየተመለከ መቀጠል የሚገባው ሳይሆን ገንቢ የሆነ ትችትና ጥያቄ እየቀረበበት ራሱን እያደሰና ከጊዜና ከሁኔታዎች ጋር እያጣጣመ መምጣት የሚገባው መሆኑን ነው፡፡

በዴሞክራሲ ላይ ትችትና ጥያቄ እንዲነሣ አስገዳጅ የሚሆነው ዴሞክራሲ ብዙ ዘመን በኖረባቸው አሜሪካንን በመሰሉ አገሮች የመዛግና ጉጅ የሆነ ውጤት የማስከተል አደጋ እየታየበት ስለመጣ ብቻም አይደለም፡፡ ይልቁንም ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታና ጥቅም አንጻር በዴሞክራሲ ላይ ገንቢ ትችትና ጥያቄ ማንሣትን ተገቢና አስፈላጊ የሚያደርገው የምዕራብ ዴሞክራሲን በአዲስ መልክ በተቀበሉ አገሮች እየታየ ያለው አሳሳቢ ሁኔታ ነው፡፡ ዴሞክራሲ በአንድ አገር በአግባቡ እንዲቆናጠጥ የሚያስችሉት ቅድመ- ሁኔታዎች በአግባቡ ባልተመቻቹባቸው አገሮች እንዲሠራ ሲሞከር ዴሞክራሲ ምን ያህል ያለአግባብ የአምባገነኖችና የአክራሪ አጀንዳ አራማጅ መሪዎች መጠቀሚያ ሊሆን እንደሚችል በብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮችና

በተለያዩ የኤዥያ፣ የላቲን አሜሪካና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ታይቷል፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኂላ አሜሪካ ዴሞክራሲን በሶማሊያ፣ በሄይቲና በባልካን አገሮች ለማስፋፋት ያደረገችው ጥረት ምን ያህል በደም መፋሰስና በብጥብጥ ታጅቦ እንደከሸፈ ታይቷል፡፡

ምርጫን በተለያዩ ስልቶች በሚያጭበረብሩ መሪዎች ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በተካሄደባቸው ቬኒዙዌላን በመሳሰሉ የደቡብ አሜሪካ አገሮች፣ በኢራን፣ በፓልስታይንና በቅርቡም በደቡብ አፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ምን ያህል አክራሪ አጀንዳ ያላቸውን መሪዎች የበለጠ እንደሚጠቅም ታይቷል፡፡ ለነገሩ በጀርመን አዶልፍ ሂትለርን የመሰለ በዓለም ወደር ያልተገኘበት ጨካኝ ሰው ለሥልጣን የበቃውም በትክክለኛ የምርጫ ሂደት ነበር፡፡ ዴሞክራሲ በዚህ መልክ የአምባገነንና የአክራሪ መሪዎች መጠቀሚያ መሆኑም በላይ የምርጫ ሂደት በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ደም ለማፋሰስ የሚያበቃ የርስ በርስ ግጭት መነሻ ምክንያት እየሆነ መምጣቱ ባለፉት አራት ዓመታት ብቻ በኢትዮጵያ፣ በኬንያና በዚምባቡዌ ታይቷል፡፡ ከጊዜያዊ ግጭትም በላይ አንዳንድ ጊዜ ዴሞክራሲ የአጠቃላይ የሰላም እጦት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በተለያዩ አገሮች ታይቷል፡፡ ለምሳሌ ዩጉዝላቪያ በማርሻል ቲቶ፣ ኢንዶኔዥያ ደግሞ በሱሃርቶ ይገዙ በነበረበት ወቅት ዛሬ በዴሞክራሲ እንመራለን ከሚሉበት ወቅት በብዙ ርቀት የተሻለ ሰላምና መረጋጋት ይታይባቸው ነበር፡፡ በሌሎች መመዘኛዎች የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ናቸው ሊባል ቢችልም ከሰላምና መረጋጋት አንጻር ኢራቅ፣ አፍጋኒስታንና ፓኪሽታንም በዴሞክራሲ ያገኙት ጥቅም እንደሌለ በግልጽ እየታየ ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ ልንረዳ የምንችለው በብዙ አገሮች ውጤታማ ሆኖ እስከታዬ ድረስ ዴሞክራሲን አያስፈልግም የሚያስብል በቂ ምክንያት እስካሁን የሌለ ቢሆንም እንደዬ አገሮች ተጨባጭ ሁኔታ በአተገባበሩ ሂደት ላይ ዴሞክራሲ ገንቢ ትችትና ጥያቄ ሊነሣበት የሚችል ብቻ ሳይሆን የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ለብዙ ዓመታት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማራመድ የምትታወቀውና በጥሩ ዴሞክራሲ አርዓያነት ከሚጠቀሱት አገሮች አንዷ የሆነችው ስዊድን ሳትቀር በቅርብ ጊዜ አዲስ የዴሞክራሲ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ስታቋቁም የታዬው ዴሞክራሲ ምን ያህል ባልተቋረጠ ሂደት አሁንም ራሱን እያደሰና እያሻሻለ መሄድ የሚገው ሥርዓት በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ጀማሪ ለሆነ አገር ዴሞክራሲን እንዴትና በምን ሁኔታ መገንባት ጠቃሚ እንደሚሆን ግልጽና ገንቢ ውይይት ማካሄድ አስፈላጊና ወቅታዊ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### *3.2.2 ዴሞክራሲ ሂደት ነው ሲባል ምን ማለት ነው?*

*ዴሞክራሲ በሂደት እንጂ በአንድ ጀምበር ሊገነባ እንደማይችል አከራካሪ አይደለም፡፡ በሂደት ይገነባል ሲባልም መገለጫው የሆኑ አብዛኛዎቹን መመዘኛዎች አሟልቶ የሚገኝበትን ሁኔታ ለመግለፅ እንጂ ዴሞክራሲ በአንድ ወቅትና ሁኔታ ላይ ሂደቱን አጠናቆ ይቆማል ማለት አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ በአንድ ወቅትና ሁኔታ ላይ በደረሰበት ደረጃ ለአንድ አገርና ሕዝብ የሚጠበቅበትን አገልግሎት እየሰጠ በቋሚነት እየጐለበተ የሚቀጥል ሂደት ነው፡፡ በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ መድረክ ዴሞክራሲ በሂደት የሚጠናከር መሆኑ በቀጥታ አከራካሪ ባይሆንም ተዘዋዋሪ በሆነ መንገድ ግን የፖለቲካ ፓርቲዎችን ሲያወዛግብ ይታያል፡፡*

*በአንድ በኩል በትግሉ ዙሪያ የምንገኝ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መጠናከር የሚያግዙ የተለያዩ ጠቃሚ ተግባራት በአገራችን የተከናወኑ መሆናቸውን በጭፍን ዕውቅና በመንፈግ አገራችን ውስጥ በአንድ ጊዜ የተዋጣለት ዴሞክራሲ ለምን አልተፈጠረም ብለን ስናማርር ሲታይ ዴሞክራሲ በብዙ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላትና በበቂ ሂደት ሊገነባ የሚችል ጉዳይ መሆኑን በአግባቡ እንዳልተረዳነው ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊከናወኑ የሚችሉ የተለያዩ ተግባራትን ለምን በአግባቡ እንዳላከናወነ ሲጠዬቅ ብዙውን ጊዜ የሚያቀርበው ምክንያት "ዴሞክራሲ የሚገነባው በሂደት ነው" የሚል መሆኑን ስናይ፣ ኢህአዴግ ምን ያህል የሂደትን ጉዳይ ራሱን ዴሞክራሲያዊ ሂደቱን አዝጋሚ ለማድረግ ሆን ብሎ እየተጠቀመበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡*

*የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በዚህ ጉዳይ ላይ ያለን የተራራቀ ልዩነት በራሱ ለዴሞክራሲያዊ ሂደቱ መጠናከር ጉጂ ስለሚሆን አንድ ዓይነት መግባባት ላይ መድረስ ይጠበቅብናል፡፡ በቅድሚያ ሁላችንም በርግጠኛነት መግባባት ላይ መድረስ የሚገባን በአገራችን ዴሞክራሲ በሂደት የሚገነባ ብቻ ሳይሆን "ዴሞክራሲያዊ" ተብለው የሚታወቁ አገሮች ወደሚገኙበት ደረጃ ለመድረስ በቀላሉ የማይገመት ጊዜ ትግል የሚጠይቀን መሆኑን ነው፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረው ምክንያት ምን እንደሆነ ለመረዳትም በሚከተሉት ሁለት ጉዳዮች፣ ማለትም ዴሞክራሲ በዓለም ላይ ያለፈበትን ታሪካዊ ሂደትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት በተቻለ መጠን መሟላት ወይም ተመቻችተው መገኘት የሚገባቸውን ቅድመ-ሁኔታዎች በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል፡፡*

በአሁኑ ወቅት በጥቅሉ "ዴሞክራሲ" እያልን የምንጠራው የመንግሥታዊ ሥርዓት ዓይነት በውስጡ ሁለት ዋና ዋና ፅንሰ-ሐሳቦችን ማለትም የሰው ልጅ ነፃነትን /Liberty/ እና የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትን /Popular sovereignty/ አካቶ የያዬዘ ነው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ሁለት ዋና ዋና ፅንሰ-ሐሳቦች ውስጥ አንዱ የሆነው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትም ሆነ የሁለቱ ድምር ውጤት ሆኖ በአሁኑ ወቅት የሚታወቀው ዴሞክራሲ የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ ወይም ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት (constitutional Liberalism) ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረ ከብዙ ዘመን በኋላ ዘግይተው ጥቅም ላይ መዋል የጀመሩ በአንፃራዊነት የቅርብ ጊዜ ፅንሰ-ሐሳቦች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ ከሮማን ኤምፓዬር ጀምሮ የነበረ ሲሆን የሕግ የበላይነትን መነሻ አድርጎ በሂደት ለግል ሀብት፣ ለሃይማኖት ነፃነትና ለፖለቲካ ነፃነት ዕውቅና በመስጠት እየሰፋና እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ የሕዝብ ሥልጣን የበላይነት /Popular sovereignty/ በዋናነት የተጀመረው በፈረንሳይ አብዮት ወቅት ሲሆን የበለጠ የተጠናከረውና በብዙ አገሮች ሥር እየሰደደ መምጣት የጀመረው ግን ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው፡፡ ከዚያ በፊት የሕዝብ የሥልጣን የበላይነት የሰው ልጅ ነፃነትን /Liberty/ አደጋ ውስጥ የሚያስገባ ውጤት ያስከትላል ተብሎ ይፈራ ስለነበር አገሮች በቀላሉ ሊቀበሉት አይደፍሩም ነበር፡፡ የሕዝብ ሥልጣን የበላይነትም ሆነ በሰፋ ትርጉሙ ዴሞክራሲ ከ19ኛው ክፍለ-ዘመን በፊት በዓለም ላይ ጥሩ ስም አልነበረውም፡፡

በአሜሪካም ሆነ በብሪታንያ ዴሞክራሲ አደገኛ፣ አውዳሚና ለሰው ልጅ ነፃነት ተፃራሪ የሆነ የመንግሥት ዓይነት ተደርጎ ነበር ይሚታየው፡፡ ዴሞክራሲን በመጥፎ እንዲታይ ያደረገው ምክንያትም በጥንት ጊዜ በግሪክ፣ በሮማን ሪፐብሊክና በጣሊያን የከተማ መንግሥታት /city states/ ዴሞክራሲ የመጨረሻ ውጤቱ ሕግ አልባነትና ጭቆና ሆኖ ስለነበር ነው፡፡ በኋላም ላይ በፈረንሳይ አብዮት ወቅት በናፖሊዮን ቦናፓርትና በሉዊስ ናፖሊዮን ዘመን በሕዝብ የተመረጡ መሪዎች በፖለቲካ ነፃነት ላይ እገዳ በመጣል ሽብርና አምባገነንነትን ሲያሰፍኑና የግል ሀብትን ሲወርሱ በመታየቱ ዴሞክራሲ ለረዥም ጊዜ አደገኛ ሥርዓት ተደርጎ ይታይ ነበር፡፡

በዚህም ምክንያት ብሪታንያና አሜሪካ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በአንፃራዊነት የሰው ልጅ ነፃነትና እኩልት /Liberty/ የሰፈነባቸው አገሮች የነበሩ ሲሆኑ፣ ነገር ግን በዚያን ወቅት ሁለቱም አገሮች ዴሞክራሲያዊ አልነበሩም፡፡ በአሜሪካ ሕገ-መንግሥትም ሆነ የነፃነት አዋጅ ላይ ዴሞክራሲን ተጽፎ የማናገኘውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ የሕዝብ የሥልጣን የበላይነት ወይም በሰፊ ትርጉሙ ዴሞክራሲ ተቀባይነት እያገኘና የሕዝብ ተቀባይነት

/Legitimacy/ መገለጫ እየሆነ የመጣው በ20ኛው ክፍለ-ዘመን ከተከሰተው የንጉሣዊ ሥርዓትና የትልልቅ ኤምፓዬሮች መፈራረስ ጋር በተያያዘ ነበር፡፡ በዚያ ወቅት ቀደም ሲል የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ ያልነበራቸው አገሮች ጭምር በቀጥታ ዴሞክራሲን በመቀበል የኢ-ሊበራል /illiberal/ ዴሞክራሲ አራማጅ መሆን ችለዋል፡፡

ከዚህ በላይ ካዬነው ታሪካዊ ሂደት የምንረዳው ዴሞክራሲ ከሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ ምን ያህል ዘግይቶ የመጣ ክስተት መሆኑንና፣ ዘግይቶ የመጣው ይህ ዴሞክራሲም በ20ኛው ክፍለ ዘመን የሰው ልጅ ነፃነትን/Liberty/ እና የሕዝብ የሥልጣን የበላይነትን አጣምሮ የያዘ ተመራጭ የመንግሥት ሥርዓት እየሆነ መምጣቱን ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ1900 በዓለም ላይ ዴሞክራሲን የተቀበሉ አገሮች አሥር ብቻ የነበሩ ሲሆን ከ75 ዓመት በኋላ ማለትም እ.ኤ.አ በ1975 ዴሞክራሲን የተቀበሉ አገሮች ቁጥር ማደግ የቻለው ወደ 30 ብቻ ነበር፡፡ የዴሞክራሲ ተቀባይነት ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ በከፍተኛ መጠን በመጨመሩ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ከሚገኙት አገሮች ውስጥ አንድ መቶ ዐሥራ ዘጠኙ ዴሞክራሲን ተቀብለዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሂደትና በተለያዬ ደረጃ በዚህ መልክ በተለያዩ አገሮች ተቀባይነት እያገኘ ቢመጣም የዴሞክራሲ ዋና መገለጫ ሆኖ የሚታየው ሁሉን አቀፍ ምርጫ (universal suffrage) ዴሞክራሲን ቀድመው በተቀበሉት አገሮች ሳይቀር እጅግ አዝጋሚ ተቀባይነት ነው የነበረው፡፡

እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ውስን ምርጫ ያካሂዱ የነበሩ አገሮች ብሪታኒያና አሜሪካ ሲሆኑ ሁሉን አቀፍ ምርጫ (universal suffrage) በእነዚህ አገሮች ጭምር እየሰፋ የመጣው በጣም አዝጋሚ ሆኖ ነው፡፡ በብሪታንያ እ.ኤ.አ በ1832 የተኃድሶ አዋጅ / Reform Act/ ከመውጣቱ በፊት የመምረጥ መብት ከነበራቸው ባለሀብት ወንዶች ውስጥ በምርጫ የሚሳተፉት 1.8% ብቻ ነበሩ፡፡ ከተኃድሶ አዋጁ በኋላ ይህ ቁጥር ወደ 2.7% ያደገ ሲሆን ይህ መጠን ወደ 12.1% የደረሰው ከኀምሳ ዓመታት በኋላ እ.ኤ.አ በ1884 ነበር፡፡ በብሪታንያ ሴቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የመምረጥ መብት ያገኙትም የተኃድሶ አዋጁ ከወጣ ከአንድ መቶ ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ በ1930 ነበር፡፡

የአሜሪካንን የምርጫ ሂደትም ስናይ በተመሳሳይ ሁኔታ አዝጋሚ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እ.ኤ.አ በ1828 በአሜሪካ የመምረጥ መብት ከነበራቸው ነጭ ባለሀብት ወንዶች ውስጥ 50% መራጮች የነበሩ ሲሆን ይህ ቁጥር እያደገ መሄድ ሲገባው የመራጮች ቁጥር መብዛት ተቃውሞ እየገጠመው ስለመጣ እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ድረስ እንደገና እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በአሜሪካ ሴቶች የመምረጥ መብት ያገኙት እ.ኤ.አ በ1920 ሲሆን የጥቁሮች የመምረጥ መብት

የተከበረው እጅግ ዘግይቶ በ1960ዎቹ ውስጥ ነው፡፡ በእነዚህ የዴሞክራሲ ሞዴል በሆኑት ሁለት አገሮች የመምረጥ መብት በቅድሚያ ባለሀብት ለሆኑ ነጭ ወንዶች፣ ከዚያም ሴቶችንና ጥቁሮችን እያካተተ በረዥም ጊዜ ሂደት እየሰፋ እንደመጣው ሁሉ ምርጫዎች በተሟላ መጠን በአገር ደረጃ መካሄድ የቻሉትም በተመሳሳይ ሁኔታ ቀስ በቀስ ነው፡፡ በአጠቃላይም የምርጫ ሂደት አሁን በሚገኝበት ደረጃ ለመድረስ ከ200 ዓመታት ያላነሰ ጊዜ ወስዷል፡፡ ከዚህም የምንረዳው አንድ አገርና ሕዝብም ሆነ አምባገነናዊ ሥርዓት ወደኂላ ሊመለስ በማይችል ደረጃ ተፈጥሯዊና ጤናማ በሆነ ሂደት /evolution/ ዴሞክራሲን በአግባቡ እንዲገነባ ከተፈለገ ተገቢ ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑን ነው፡፡

ዴሞክራሲ የሚገነባው በሂደት ነው ሲባል ሂደቱ የሚያስፈልገው ዝም ብሎ ጊዜን ለመቁጠር ወይም ኢህአዴግ እንደሚያደርገው ሂደቱን ሆን ብሎ አዝጋሚ ለማድረግ ሳይሆን ዴሞክራሲን ለመመሥረት የሚያበቁት ቅድመ-ሁኔታዎች በአንድ ጊዜ በበቂ መጠን ተሟልተው ሊገኙ የማይችሉና የተራዘመ ጊዜን የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው፡፡ ለእያንዳንዱ ቅድመ-ሁኔታ በበቂ መጠን መሟላት የሚጠይቀው ጊዜ በየአገሮቹ ነባራዊ ሁኔታ የሚወሰንና ትክክለኛውን ጊዜ በርግጠኛነት ገምቶ ለመናገር የማይቻል ቢሆንም ቢያንስ አንፃራዊ የሆነ ጥቅል ግምት ለመስጠት የቅድመ-ሁኔታዎቹን ዓይነትና ብዛት በቅድሚያ ዘርዝር አድርጐ ማየትና መረዳት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በአንድ አገር ውስጥ ዴሞክራሲ ሊመሠረት የሚችለው ስለተፈለገና ጠቃሚ ነው ተብሎ ስለታሰበ ብቻ ሳይሆን በዋናነት በዚያ አገር ለዴሞክራሲ መመሥረት የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሮ ሲገኝ ነው፡፡ አንዳንድ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች ዴሞክራሲን የሚመስሉት እንደ አንድ የዕፅዋት ተክል ነው፡፡ አንድ ዕፅ ተተክሎ፣ አድጐና አፍርቶ የሚፈለግበትን ጥቅም እንዲሰጥ በቅድሚያ የዳበረ አፈር፣ ውሃና ተስማሚ የአየር ፀባይ ወዘተ ያስፈልገዋል፡፡ እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች እስካልተሟሉ ድረስ የቱንም ያህል ብርቱካንም ሆነ መንደሪን ከጓሮአችን ቀጥፈን ለመብላት ብንመኝ ምኞታችን ምኞት ሆኖ ከመቅረት ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ዴሞክራሲም በአንድ አገር ተቀባይነት አግኝቶ፣ ተጠናክሮና ተስፋፍቶ የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ አስቀድመው ሊመቻቹለት የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎች አሉት፡፡

አንዳንድ በተለየ አጋጣሚና ሁኔታ ዴሞክራሲን ከቅድመ-ሁኔታዎች መመቻቸት በፊት ሲገነቡ የተስተዋሉ አገሮች (exceptions) ቢኖሩም እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች በበቂ መጠን እስካልተመቻቹ ድረስ የአንድ አገር ሕዝብ እንዲያው በስሜት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖረው ከፍተኛ ፍላጐት ቢኖረውም ሆነ ዴሞክራሲን እንዲቀበል የሚያስገድድ ውጫዊ

ግፊት ቢደረግበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን አይበቃም፡፡ የዴሞክራሲ ባለቤት ለመሆን አለመብቃትም ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲን በስሜታዊ ፍላጐትም ሆነ በውጫዊ ግፊት እንዲቀበል የሚገደድ አገርና ሕዝብ የማይጠበቅና የማይፈለግ አደጋ ውስጥም ሊገባ ይችላል፡፡ የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ባልተሟሉበትና ተገቢውን ሂደት ባልጠበቀ መንገድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ያለተፈጥሮው በአቋራጭ ለመገንባት የተሞከረባቸው አገሮች ምን ዓይነት አስከፊ ችግር ውስጥ እንደገቡ በዓለማችን በበቂ መጠን ታይቷል፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውጤታማ ለመሆን የበቁ አገሮች ካለፉበት ታሪካዊ ሂደት ለመረዳት እንደምንችለው ቅድመ-ዴሞክራሲ ማኅበረሰብ /Pre-democratic structure/ በሚገኝባቸው እንደ አፍሪካ ያሉ አገሮች ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስፈልጉ በርካታ ቅድመ-ሁኔታዎች አሉ፡፡ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ የሌሎች አገሮችን ታሪካዊ ሂደት በማንበብም ሆነ በተለያዩ የጥናት ጽሑፎች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ቅድመ-ሁኔታነት ተበታትነው የተጠቀሱ የተለያዩ ጉዳዮችን በማገናዘብና ያገኛቸውን መረጃዎችና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ቅድመ-ሁኔታዎቹ በፈርጅ ተከፋፍለው እንዲቀመጡ ለማድረግ ባደረገው ሙከራ ኢትዮጵያን የመሰሉ ቅድመ-ዴሞክራሲ ማኅበረሰብ በሚገኝባቸው አገሮች የሚከተሉት ሰባት ቅድመ-ሁኔታዎች ከሞላ ጐደል አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያምናል፡፡

የመጀመሪያው ቅድመ-ሁኔታ የሰው ልጅ ነፃነትና /Liberty/ የሕግ የበላይነት መኖር ነው፡፡ ከላይ ታሪካዊ አመጣጡን ለማየት እንደተሞከረው የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ ከጥንታዊው የሮማን ኤምፓየር ዘመን ጀምሮ የሕግ የበላይነትን መነሻ አድርጐ ለግል ሀብት፣ ለሃይማኖት ነፃነትና ለፖለቲካ ነፃነቶች ዕውቅና በመስጠት እየሰፋና እየተጠናከረ የመጣ ሲሆን፣ በዋናነትም መንግሥት በግለሰቦች ነፃነት ጣልቃ ሳይገባ እንዴት ሥራውን በአግባቡ ሊሠራ እንደሚችል የሚጨነቅ ፅንሰ ሐሳብ ነው፡፡ በዓለማችን ውጤታማ ዴሞክራሲ ለመገንባት የቻሉት አገሮች የሰው ልጅ ነፃነትን /Liberty/ ቀድመው የተቀበሉ አገሮች ሲሆኑ እነዚህ አገሮች የሰው ልጅ ነፃነትን /Liberty/ ዘግይቶ ከመጣው ከሕዝብ የሥልጣን የበላይነት /popular sovereignty/ ጋር በሂደት በአግባቡ ማጣጣም በመቻላቸው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን በቅተዋል፡፡ በርግጥ እነዚህ አገሮች የሰው ልጅ ነፃነትን በተቀበሉበት ወቅት የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ አንፃራዊ ትርጉም የነበረውና ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በእኩልነት የማያካትት ነበር፡፡

የሰው ልጅ ነፃነትና የሕግ-የበላይነት ባልሰፈነበት ሁኔታ የዴሞክራሲ የወቅቱ ዋና መገለጫ የሆነውን የሕዝብ ሥልጣን የበላይነት /popular sovereignty/በቀላሉ ለማስፈን መሞከር የማይቻል ነው ብቻ ሳይሆን እንዲቻልም ከተሞከረ መጠኑን መገመት የሚያስቸግር አደጋ

ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሰው ልጅ ነፃነትና የሕግ የበላይነት ባልሰፈነበት ሁኔታ አንድ አገር በሕዝብ የሥልጣን የበላይነት /popular sovereignty/ ይመራ ቢባል የብዙኃን አምባገነንነትን /Tyranny of the majority/ ሊያሰፍን ይችላል ብቻ ሳይሆን ከዘር፣ ከጐሣና ከሃይማኖት አንጻር በአንድ አገር ያሉ አናሳ ቁጥር ያላቸው ሕዝቦች በኃይልና በጦርነት ጭምር እንዲጠፉ የሚያደርግ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሰው ልጅ ነፃነትና የሕግ የበላይነት በሌሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲን መገንባት የማይቻል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሰው ልጅ ነፃነትን፣ የሕግ የበላይነትንና ዴሞክራሲን በአንድ ጊዜ ተቀብለው ተግባራዊ ለማድረግ የሞከሩ አገሮችም ከችግር ነፃ መሆን አልቻሉም፡፡ የከፋ ችግር አልደረሰባቸውም የሚባሉ አገሮች ቢኖሩም እንደ ኢራን፣ ፔሩና ዚምባቡዌን የመሳሰሉት አገሮች ኢ-ሊበራል /illiberal/ ዴሞክራሲ እንጂ እውነተኛ ዴሞክራሲ ለመመሥረት አልበቁም፡፡

ከዚህ ቅድመ-ሁኔታ አንጻር የኢትዮጵያን ሁኔታ ለማየት ብንሞክር በአንፃራዊነት ቢያንስ በመርህ ደረጃ የሕግ የበላይነት በአገሪቱ ከጥንት ጀምሮ ነበር ሊባል ቢችልም የሰው ልጅ ነፃነትም /liberty/ ሆነ የሕዝብ የሥልጣን የበላይነት /popular sovereignty/ በአንድ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ በሕገ-መንግሥት ደረጃ ተቀባይነት ያገኙት በኢህአዴግ ዘመን ነው፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ እንደ ሌሎቹ አገሮች የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ በተከበረበት ሥርዓት ውስጥ ቀድማ ስላላለፈች መረጋጋትና መቻቻል የሰፈነበት አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስካሁን መገንባት አልቻለችም፡፡ ስለዚህ በሌሎች አገሮችም ሆነ በራሳችን አገር ወቅታዊ ተሞክሮ በግልጽ እንደምናየው የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ እና የሕግ የበላይነት መከበር ለዴሞክራሲ መኖር የግድ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው፡፡

ሁለተኛው ቅድመ-ሁኔታ የኢኮኖሚ ዕድገት ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት በአንድ አገር ዴሞክራሲን ለመመሥረት አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታ ነው ሲባል ፈርጀ ብዙ ትርጉም ያለው ነው፡፡ በዓለማችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት የቻሉት አብዛኛዎቹ አገሮች ጠንካራ ኢኮኖሚና መሠረታዊ ፍላጐቱን ያሟላ ሕዝብ ያለባቸው አገሮች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የኢኮኖሚ እድገት ሲባል በዐረብ አገሮች እንደሚታየው ድንገት በተገኘ ነዳጅን በመሰለ የተፈጥሮ ሀብት መበልፀግን የሚመለከት ሳይሆን ካፒታሊስታዊ ሥርዓትን በማራመድና በተለይም ከፈጠራ እድገት ጋር በተያያዘ ኢንዱስትሪያዊ አገር በመሆን የሚገኝ የኢኮኖሚ እድገትን የሚመለከት ነው፡፡ በካፒታሊስታዊ ሥርዓት ሂደት ውስጥ ያላለፈና አብዛኛው ሕዝቡ መካከለኛ ገቢ የሌለው አገር ዴሞክራሲን በቀላሉ ሊገነባ ያስቸግረዋል፡፡ ይህም የሚሆነው በአንድ በኩል ሰዎች ብዙውን ጊዜ ስለ ፖለቲካዊ መብታቸው መከበር ማሰብና መሳተፍ የሚጀምሩት

በቅድሚያ በልተው ማደርና የቁሳቁስ /material/ ፍላጐታቸውን ሲያሚሉ በመሆኑና በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ የሚነሣሱት በሌሎች ኃይሎች ሊነካባቸው የሚችል ጥቅም ሲኖራቸው ስለሆነ ነው። አንድ ሰው በእጁ ውስጥ የገባና ሊያስጠብቀው የሚፈልገው ወይም ወደፊት ላገኘው እችላለሁ ብሎ የሚጠብቀው ጥቅም በአካባቢው እስከሌለው ድረስ አብዛኛውን ጊዜ በፖለቲካ ሂደት መሣተፍ መብቴ ነው በሚል ብቻ ሊሳተፍ ስለማይችል ነው።

ምክንያቱም የፖለቲካ ተሳትፎ የያዙትን ጥቅም እስካላስከበረ ወይም ሌላ አዲስ ጥቅም እስካላስገኘ ድረስ ተሳትፎው በራሱ ትርጉም ያለው ሊሆን አይችልም። ሰዎች የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉት ለአገር ጥቅም ብለው ብቻም ሳይሆን ለራስ ጥቅምም ብለው መሆኑ ተፈጥሯዊ ነው። ሰዎች በዙሪያቸው የሚኖረውና ሊታገሉለት የሚገባው ጥቅም ብዙ ዓይነት ሊሆን ቢችልም የኢኮኖሚ ጥቅም ከህልውና ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ስለሆነ ከዴሞክራሲ ግንባታ ጋር ያለው ግንኙነት በዚያው መጠን ከፍተኛ ነው። የዴሞክራሲ ቀዳሚ አራማጆች በነበሩ አሜሪካንን በመሰሉ አገሮች ባለሀብት መሆን በምርጫ ለመሣተፍ ቀዳሚ መስፈርት ተደርጐ ይወሰድ የነበረውም የፖለቲካ ተሳትፎ የኢኮኖሚ ጥቅምን የማስከበር ጉዳይ ተደርጐ ይወሰድና ሀብት ያለው ሰውም ከሌለው ሰው በተሻለ በጉዳዮች ላይ ኃላፊነት የተሞላበት ውሳኔ የመስጠት ነፃነትና ነገሮችን ከሌሎች ጋር የማቻቻል ችሎታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰብ ስለነበር ነው።

የጥቅም ጉዳይ ብዙ ፈርጅዎችና መገለጫዎች ያሉት እየሆነ በመምጣቱ ምክንያት የሀብት መጠን የምርጫ ተሳትፎ መስፈርት መሆኑ ከቀረ ብዙ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም የኢኮኖሚ ጥቅም ለምርጫ ተሳትፎ ምክንያት መሆኑ ግን የበለጠ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በቀጥታ ከሚቀርቡ የኢኮኖሚ የመብት ጥያቄዎች በተጨማሪ ብዙውን ጊዜ ከፖለቲካ ሥልጣንና ከነፃነት ጋር ተያይዘው የሚነሡ ጥያቄዎች ጭምር በተዘዋዋሪ በሀብት የበለጠ ተጠቃሚ የመሆን ጥያቄ ሆነው የሚገኙበት አጋጣሚ ቀላል ስላልሆነ የኢኮኖሚ እድገት በዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ያለው ሚና መቼም ቢሆን አጠያያቂ የሚሆን አይደለም። ዜጐች ይህ ነው የሚባል የግል ሀብት በሌላቸውና አገራቸውም እንደ አገር ድህነት ውስጥ ባለበት ሁኔታ ዴሞክራሲን በአግባቡ ለመገንባት አድካሚ ትግል እንደሚሆን የአፍሪካና የደቡብ አሜሪካ አገሮች በቂ ምሳሌ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ። ከመንግሥት ነፃ የሆኑ ቡድኖችና ድርጅቶች ተጠናክረው እንዲወጡና የጥቅም ማስከበር ትግል ውስጥ እንዲገቡ የሚያስችለው የግል ሀብትና ነፃ-ገበያ በታዳጊ አገሮች ገና እንዳለ የሚቆጠር ስላልሆነ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያስችለው ዋናው ቅድመ-ሁኔታ ጉሎባቸዋል ማለት ይቻላል።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩትም የዜጎቻቸው የቀን ገቢ ግማሽ ዶላር፣ ወይም በዓመት ከ180 ዶላር በታች የነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው አገሮች ብዙውን ጊዜ ዴሞክራሲ ለአደጋ የሚጋለጥባቸው አገሮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ለሁሉም የሚበቃ ቂጣ ባልተጋገረበት ወቅት ላይ በሕዝቡ ውስጥ የመደብ፣ የጐሣና የሃይማኖት ትግል እየተቀሰቀሰ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት እንዳይሆን ማድረግ የሚቻለው በቅድሚያ የኢኮኖሚ እድገትን በማረጋገጥና አብዛኛው ሕዝብ የእድገቱ ተቋዳሽና ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ነው፡፡ ከኢኮኖሚ እድገት አንጻር አገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ ለማየት ስንሞክርም እጅግ ወደኋላ የቀረች ሆና እናገኛታለን፡፡ አገሪቱ ከሌሎች የአደጉ አገሮች በተፃራሪ ኋላቀር የሆነ የእርሻ ኢኮኖሚ ጥገኛ ስትሆን፣ ከ84% የማያንሰው ሕዝቧም ገና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የድህነት ኑሮ የሚኖር አርሶ አደር ነው፡፡ የግሉ ክፍለ- ኢኮኖሚም ሆነ ነፃ-ገበያ ገና ያልተጠናከረባት ከመሆኗም በላይ በእጁ ጥሪት መጨበጥ የጀመረ መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብ ገና ስላልተፈጠረ ከኢኮኖሚ አንጻር ለዴሞክራሲ ግንባታ የሚጠበቅባትን ቅድመ-ሁኔታ በበቂ መጠን ለማሟላት አገራችን ገና ብዙ ርቀት መጓዝ ይጠበቅባታል፡፡

ሦስተኛው ቅድመ-ሁኔታ ትምህርት ነው፡፡ አብዛኛው ሕዝብ መሃይም በሆነበት አገር ዴሞክራሲን በሚፈለገው መጠን መገንባት ይቻላል ተብሎ አይታሰብም፡፡ የሰው ልጅ ዕውቀት ሊያገኝበት የሚችል የተለያዩ መንገድና ምክንያት ቢኖርም አስተሳሰቡ የበለጠ ሊሰፋና ሊዳብር የሚችለው በትምህርት ነው፡፡ በአንድ በኩል የፈጠራ ክሂሎት የሌለው ሕዝብ ኢንዱስትሪያዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚቸገር ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ያልተማረና በአንድ ሥርዓት ውስጥ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅምና ጉዳት በአግባቡ ማመዛዘን የማይችል ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በበቂ መጠን የተመቸ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በአሁኑ ወቅት የሌኒንን ጥቅስ መጠቀም ነውርና ስህተት ተደርጐ እየታየ ቢሆንም ሌኒን “ያልተማረ ሰው ከፖለቲካ ውጭ ነው” ያለው ያለምክንያት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ማንኛውም ሕዝብ ቢማርም ባይማርም ከዕለት-ተዕለት ኑሮው ጋር የተያያዙ ጥቅሞቹን በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅ የሚችል ቢሆንም በተለይም ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ ያልተማረን ኅብረተሰብ ጥቂት የራሳቸውን ጥቅም በሕዝብ ስም የሚያሳድዱ ብልጣብልጥና የንግግር ችሎታ ያላቸው የፖለቲካ ሰዎች ወደ ፈለጉት አቅጣጫ እየመሩ ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ትምህርት ይህንን ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት የሆነ ችግር በመቅረፍ ረገድ የማይናቅ የራሱ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡

በተግባርም እንደሚታየው በዓለማችን ቀድመው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መቆናጠጥ የቻሉት አብዛኛዎቹ አገሮች ቀደም ብለው የተሻለ የተማረ ሕዝብ መፍጠር የቻሉ አገሮች

ናቸው፡፡ ከትምህርት አኳያ አገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ ለማየት ስንሞክር፣ በአሁኑ ወቅት አበረታች ውጤት እየታየ ቢሆንም የአገሪቱ አብዛኛው ሕዝብ አሁንም ያልተማረ ብቻ ሳይሆን ገና ማንበብና መጻፍ የማይችል ነው፡፡ ማንበብና መጻፍ የማይችል ኅብረተሰብ ደግሞ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት በአግባቡ አንብቦ ለመረዳትም ሆነ በምርጫ ጊዜ ከሌሎች ተጽእኖና መጠቀሚያነት ነፃ በሆነ መንገድ መብቱን በአግባቡ ለመጠቀም የሚኖርበትን የአቅም ውስንነት በቀላሉ መገመት አይቻልም፡፡

አራተኛው ቅድመ-ሁኔታ መካከለኛ ገቢ ያለው /middle class/ ኅብረተሰብና የሲቪል ማኅበረሰብ መኖር ነው፡፡ መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብና ሲቪል ማኅበረሰብ በሌለበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአግባቡ ይገነባል ተብሎ አይታሰብም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ኅብረተሰብ ሊፈጠር የሚችለው ደግሞ ከላይ በሁለተኛና በሦስተኛ ቅድመ-ሁኔታነት ከተጠቀሱት ከኢኮኖሚ እድገትና ከትምህርት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በታክስ ከፋይነት የአገርን ኢኮኖሚ የሚሸከም አብዛኛውን ሕዝብ የሚያካትት መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብ ባልተፈጠረበትና ጥቅሙን ለማስከበር ሲል በመራጭነትም ሆነ በተመራጭነት የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ የሚችል የነቃ ኅብረተሰብ በሌለበት አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በበቂ መጠን ሊጠናከር አይችልም፡፡ ዜጎች በግልም ሆነ በቡድን በዙሪያቸው ያለውን ጥቅም ለማስከበር ሲሉ በየዘርፉ ተደራጅተው በፖለቲካ ኃይሎች ላይ ግፊትና ጫና ማሳደር በማይችሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በበቂ መጠን መኖርም ሆነ መጠናከር አይችልም፡፡

በተግባርም በአሁኑ ወቅት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ሆነው የምናያቸው አገሮች አብዛኛው ሕዝባቸው ባለ መካከለኛ ገቢ /middle class/ የሆነባቸውና የሕዝቡን የግልና የጋራ ጥቅም ለማስከበር የሚታገሉ ከመንግሥት ተፅዕኖ ነፃ የሆኑ ሲቪክ ማኅበራት በበቂ መጠን ተደራጅተው የሚገኙባቸው አገሮች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ለማየት ስንሞክርም መካከለኛ ገቢ ያለው ቡርዣ ኅብረተሰብም ሆነ ሲቪክ ማኅበራት ገና በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኙበት እንጂ እንዳሉ የሚቆጠሩበት ደረጃ ላይ አይደለንም፡፡ አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ ገና ከድህነት ወለል በታች በሆነ የኑሮ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን፣ በአገራችን ያሉት ሲቪክ ማኅበራትም በአፍሪካ ደረጃ ሲመዘኑ እንኳ እጅግ በጣም ጥቂቶች ከመሆናቸው በተጨማሪ ከድርጅታዊ ጥንካሬና ከገለልተኛነትም አንጻር ገና በደካማ አቋም ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡

አምስተኛው ቅድመ-ሁኔታ የተጠናከሩ መንግሥታዊ ተቋማት /Institutions/ መኖር ነው፡፡ በአንድ አገር ዴሞክራሲ በዘላቂነት እየተጠናከረ እንዲቀጥል ከምንም ነገር በላይ ዋስትና

የሚያገኘው በጠንካራና ገለልተኛ የፖለቲካ ተቋማት መኖር ነው፡፡ በአንድ አገር በየወቅቱ መንግሥታትም ሆኑ የፖለቲካ ባለሥልጣናት በተፈራረቁ ቁጥር ለዴሞክራሲ ሥርዓት መኖር በቋሚነት ዋስትና ሆነው የሚቀጥሉት የአንድ መንግሥት ወይም ትውልድ ዕድሜን መሻገር የሚችሉ ተቋማት ሲኖሩ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት በቋሚነት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩና ሕዝቡ ከባለሥልጣናትና ከጊዜያዊ መንግሥታት በላይ እምነት የሚጥልባቸውና የኔ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው እውነተኛ ተቋማት በሌሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲም የአንድ ወቅት ክስተት ሆኖ ብልጭ ብሎ ድርግም ሊል የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው፡፡ ተቋማት ሲባልም ግኡዝ የሆነውን አካላዊ መዋቅራቸውን /Hard ware/ የሚመለከት ሳይሆን በውስጣቸው አቅፈው የሚይዙትን የዳበረ የአሠራር ባህልና /Discipline/ የሞያ ክሂሎት ያለውን ቢሮክራሲ የሚመለከት ነው፡፡ አንድ አገር በሂደት የደረጀና የአገራዊ ሥርዓቱ ህዋስ /cell/ ሆኖ የሚያገለግል ቢሮክራሲ ሳይኖረው ከላይ የጠቀስናቸውን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ቅድመ-ሁኔታዎች በበቂ መጠን ሊፈጥር አይችልም፡፡

በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመሠረቱ አገሮች መንግሥታትና ሹማምንት ሲለዋወጡ ሥርዓታቸው ግን ያለምንም መናጋት ተረጋግቶ ሲቀጥል የምናየው የአጠቃላዩ ሥርዓት ህዋስ /cell/ ሆኖ የሚያገለግል የዳበረ ቢሮክራሲ ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡ ተቋማት በበቂ መጠን ባልተገነቡባቸው፣ ወይም የመንግሥት ለውጥ በመጣ ቁጥር ሁልጊዜ እየፈረሱ እንደገና ከዜሮ ተጀምረው የሚገነቡ ያልደለቡ ተቋማት ባሉባቸው ኢትዮጵያን በመሰሉ አገሮች የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ዋስትና አለው ማለት አይቻልም፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን በአንፃራዊነት ከዴሞክራሲና ከሰብአዊ መብት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተቋማት ግንባታ ሂደት በተሻለ ሁኔታ የሚታይ ቢሆንም በአገራችን ያሉ ተቋማት ከድርጅታዊ ጥንካሬ፣ የመንግሥት ዕድሜ ተሻጋሪ ከመሆንም ሆነ ከገለልተኝነት አንጻር ሲመዘኑ ገና እንዳሉ በማይቆጠሩበት ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ የአገራችን ተቋማት መንግሥታት ሲለዋወጡ ብቻ ሳይሆን ባለሥልጣናት በተለዋወጡ ቁጥር ቅርፅና ይዘታቸውን የሚለዋውጡና በነጋሪት ጋዜጣ ላይ እንጂ በሕዝቡ ልብ ውስጥ ተገቢውን ዕውቅናና አክብሮት ያላገኙ ናቸው፡፡

ስድስተኛው ቅድመ-ሁኔታ የኅብረተሰብ የባህል ለውጥ ነው፡፡ በአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገነባ የሚችለው በአዋጅ ዕውቅና ስለተሰጠውና እሱን የሚያስፈፅሙ ተቋማት ስለተቋቋሙ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ በዕለት-ተዕለት ኑሮውና የርስ በርስ ግንኙነቱ ዴሞክራሲን ባህሉ አድርጎ ሲጠቀምበት ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ማንኛውም ዓይነት ባህል መለዎጥ የለበትም የሚል ከፍተኛ የአስተሳሰብ ፋሽን የሚታይ ቢሆንም ባህል የአንድን ሕዝብ የወደፊት ሁለንተናዊ

ዕጣ-ፈንታ በመወሰን ረገድ የማይናቅ ድርሻ አለው፡፡ ዴሞክራሲ የአንድ ሕዝብ ባህል ሊሆን የሚችለውም በአንድ በኩል ዴሞክራሲን ለመቀበል እንቅፋት የሆኑ ሌሎች ነባራዊ ባህሎችን በመተውና በማስወገድ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ ዴሞክራሲን የመንግሥት ባህሪ መገለጫ አድርጐ ብቻ ሳይሆን የራሱ የአኗኗር ዘይቤ /way of life/ አድርጐ ሲጠቀምበት ነው፡፡ ዛሬ በዓለማችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የራሳቸው መገለጫ አድርገው በቋሚነት እየተጠቀሙበት ያሉ አገሮች ገና ከመነሻው ለዴሞክራሲ የተመቹ ሆነው ተፈጥረው ሳይሆን በሂደት የማይጠቅመውን ባህላቸውን በአዲስና በሚጠቅም ባህል እየተኩትና እያሻሻሉት በመምጣታቸው ነው፡፡ አንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብቷል ሊባል የሚችለው ሕጐቹንና ተቋማቱን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን ነባራዊ ባህል ዴሞክራሲያዊ /Democratized/ በማድረግ ጭምር ነው፡፡

አንድ በፊውዳላዊ ወይም በወታደራዊ አምባገነን መንግሥት እየተገዛ የኖረ ሕዝብ በአለቃና በበታች ሠራተኛ፣ በወንድና በሴት፣ በባልና በሚስት፣ በአባትና በልጅ፣ በአስተማሪና በተማሪ፣ በአጠቃላይም በተለያዩ ኃይማኖቶችና ጐሳዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ዴሞክራሲያዊ ይዘት እንዲኖረው ካላደረገ በስተቀር ነባራዊ ባህሉን ሙሉ በሙሉ እንደያዘ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በበቂ ሁኔታ ሊገነባ አይችልም፡፡ የአንድ ሕዝብ የባህል ለውጥ ሲባልም ስለ አገር ፍቅር፣ ስለ ጀግንነት፣ ስለ መቻቻል፣ ስለ ሥልጣን፣ ስለ ሕግ የበላይነትና ስለ ለውጥ ያለንን አመለካከት ሁሉ የሚመለከት ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ስለወደፊቱ ከማሰብና ከመሥራት ይልቅ ባለፈ ታሪኩ መኩራራትንና መመጻደቅን ብቻ የሚፈልግ ሕዝብ /Frozen in the past/ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በቀላሉ መገንባት አይችልም፡፡

በአጠቃላይ ዴሞክራሲንም ሆነ አንድ የሠለጠነ አገርና ሕዝብ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት የባህልና የአስተሳሰብ ሥርገት በሂደት ማጋጠሙ የማይቀር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ የወቅቱን የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ከዚህ ቅድመ-ሁኔታ አንጻር ስናየው ብዙ አበረታች አይደለም፡፡ ኢትዮጵያውያን በብዙ ጉዳዮች ላይ "ድሮ ቀረ" ማለትን የምንመርጥ ስለሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት የሚሆኑ ነባራዊ ባህሎቻችንን በድፍረት ለመተውም ሆነ ለማሻሻል በበቂ መጠን እየሠራን አይደለንም፡፡ ልንጠቀምባቸውና ልንንከባከባቸው የሚገቡ ጠቃሚ ባህሎች ያሉን ቢሆንም በዚያው መጠን መለወጥ የሚገባቸው ጐጂ ባህሎች አሉን፡፡ በተለይም በፖለቲካ አስተሳሰብ ረገድ የግራ የፖለቲካ አስተሳሰብ ወደ አገራችን ገብቶ ከመንሰራፋቱ ጋር በተያያዘ የበለጠ እየተጠናከረ የመጣውን ነባራዊ የፖለቲካ ባህላችንን በአግባቡ ሳንሞርደው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በቀላሉ ልንገነባ አንችልም፡፡

ሰባተኛው ቅድመ-ሁኔታ የሕዝብ ብሔራዊ መግባባትና የአገር አንድነት ጉዳይ ነው፡፡ በአንድ አገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመመሥረት፣ በዚያ አገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ዜጐች ቢያንስ በዋና ዋና አገራዊ አጀንዳዎች፣ በሕግ የበላይነት፣ በተቋማት ነፃነትና በፖለቲካ የመጫወቻ ሜዳው ደልዳላነት ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተለይም ሕዝቡን ለመምራት ኃላፊነት የወሰዱ የፖለቲካ ኃይሎች ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አገራዊ ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት መግባባት ላይ ባልደረሱበት ሁኔታ የሚያደርጉት የፖለቲካ ትግል በሂደቱም ሆነ በውጤቱ ዴሞክራሲያዊ ሊሆን አይችልም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የአንድ አገር ሕዝብ በዘር፣ በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በሀብትና በሥልጣን ክፍፍል በቅራኔ የተወጠረ ከሆነና እነዚህን ልዩነቶች ተሻግሮ በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት የማይችል ከሆነ በየትኛውም አቋራጭ መንገድ ሄዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ሊገነባ አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ አገር በውስጡ በሚገኙ ክልሎች መካከልም ሆነ ከጐረቤት አገሮች ጋር ግጭት ውስጥ የሚያስገባ የድንበር ውዝግብ ካለበት፣ በራሱ ውስጥ የመገንጠል ጥያቄ የሚያነሳ የፖለቲካ ኃይል ካለና ሌላ ውጫዊ ኃይል በግዛት ጥያቄ ምክንያት የወረራ ጥቃት የሚሰነዝርበት ከሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በቀላሉ ለመገንባት ይቸገራል፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነቶቹ የውስጥም ሆነ የውጭ ቅራኔዎች የመቻቻል፣ የመረጋጋትና የሰላም እጦትን ስለሚያስከትሉ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት ይሆናሉ፡፡

በውስጣቸው መከፋፈልና ግጭት በነገሠባቸው አገሮች የሚኖሩ ዜጐች፣ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ መንግሥታት ብዙውን ጊዜአቸውንና ጉልበታቸውን የሚያጠፉት አንዳቸው በሌላው ላይ የአሸናፊነት ድልን ለመጐናፀፍ እንጂ የጋራ አገራቸውን ወደ አንድ የዕድገት ደረጃ ለማድረስ አይሆንም፡፡ ስለዚህ ከዚህ ቅድመ-ሁኔታ አንጻር አገራችን የምትገኝበትን ሁኔታ ለማየት ስንሞክር በዚህ መጽሐፍ ሌላ ክፍል ለማየት እንደሞከርነው በብዙ መሠረታዊ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት የሌለባት አገር ነች፡፡ በውስጥ ፖለቲካዋ ብዙ ዓይነት መከፋፈልና ቅራኔ የሚታይባት ከመሆኗም በላይ ከብዙዎቹ የጐረቤት አገሮቿ ጋርም አስተማማኝ የሚባል ሰላማዊ ግንኙነት የሌላት አገር ነች፡፡

እንግዲህ ከእነዚህ በጥቅሉ የቀረቡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑ ሰባት ቅድመ-ሁኔታዎችም ሆነ ቀደም ሲል ለማየት ከሞከርነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ታሪካዊ ሂደት የምንረዳው ቁምነገር በርግጥም ዴሞክራሲን የመገንባት ሂደት ከባድና በቂ ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን እውነታ አምኖ መቀበልና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ያስፈልጋል የሚባለውን የ"ሂደት" ጉዳይ የመብት ጥያቄዎችን ለማፈንና

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ሂደት ለማንተት ሆን ብሎ መጠቀሚያ ማድረግ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአንድ ጊዜ እንደ መና ለምን ከመንግሥት አልወረደልንም ብለው እየጠየቁ መሆናቸው ከፍተኛ ስህተት የመሆኑን ያህል፣ ዛሬ አገሪቱ በምትገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ልታስመዘግብ የሚገባትን ውጤቶች በሂደት ሰበብ ሆን ብሎ ለማዘግየት ኢህአዴግ እያደረገ ያለው ጥረትም በዚያው መጠን ከባድ ስህተትና ከፍተኛም አደጋ ሊያስከትል የሚችል አስተሳሰብ ነው፡፡ የትኛውም ማኀበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ለውጥ አግባብ ባለው መጠን በዴሞክራሲያዊ ለውጥ ካልታገዘ መልሶ የመፍረስ ዕድሉ የሰፋ ይሆናል፡፡

ሌሎች በርካታ ዝርዝር ጉዳዮችን ማንሣት ትተን አንድ ሁለት ቀላልና ግልጽ ምሳሌዎችን ለማየት ብንሞክር፣ ኢህአዴግ ሆን ብሎ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃንና የተለያዩ የመብት አስከባሪ ተቋሚት በኢትዮጵያ በአግባቡ እንዳይስፋፉና እንዳይጠናከሩ እያደረገና ምን ያህል የ“ሂደት”ን ጉዳይ በተዛባ ሁኔታ እየተጠቀመበት እንደሚገኝ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኸውም ኢህአዴግ ከልቡ በተሰለፈበት የመንገድ ግንባታ ልማት ብዙ እመርታ እያሳዬ ቢሆንም በአለፉት የዐሥራ ስምንት ዓመታት የሥልጣን ዘመኑ ግን ኢትዮጵያን አሁን ካላት አንድ ብቸኛ አገር አቀፍ የቴሌቪዥን ቻናል ሌላ አንድ ተጨማሪ የግል ቴሌቪዥን ጣቢያ እንዲኖራት ማድረግ ተስኖታል፡፡ አገሪቱ እስካሁን አንድም ተጨማሪ የግል የአጭር ሞገድ ሬዲዮ ጣቢያም ያላገኘች ሲሆን የሚገርመው እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ለማስፈጸም በሕግ የተቋቋመው የብሮድካስት ኤጀንሲ በአዋጅ ከተቋቋመ በኋላ ሥራ ለመጀመር ከአምስት ዓመታት በላይ አስፈልጎታል፡፡ ኤጀንሲው ከአምስት ዓመታት በኋላ ሥራ ሲጀምርም ፈቃድ መስጠት የቻለው ለሁለት ከአዲስ አበባ ውጭ መድመጥ ለማይችሉ የኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያዎች ሲሆን ከዚያ በላይ ለምን መፍቀድ እንዳልቻለ ሲጠዬቅ የሚያቀርበው መልስ የበጀት አቅም እጥረት አለብኝ የሚል ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በአገሪቱ የእንባ ጠባቂና የሰብአዊ መብት ኮሚሽን እንዲቋቋም አዋጅ ከወጣ በኋላ ተቋሚቱ በአግባቡ ሥራ እንዲጀምሩ ለማድረግ ከሰባት ዓመት በላይ ጠይቋል፡፡ ተቋሚቱ ሥራ ከጀመሩ ከአራት ዓመት በኋላም በቂ ሥራ ለምን መሥራት እንዳልቻሉ ሲጠየቁ የሚሰጡት መልስ የበጀት እጥረት አለብን የሚል ነው፡፡ ለማንም ቅን ለሚያስብ ምክንያታዊ ሰው እነዚህ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ተቋማት በአግባቡ እንዲጠናከሩ የሚያስችል አቅም ኢትዮጵያ የላትም ብሎ ሊያምን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ መንገድ ለመገንባት ከልቡ ቆርጦ የተነሣውን ያህል እነዚህን ተቋሚት ከልቡ ለማጠናከር ቢፈልግ ኖሮ ከጊዜም፣ ከሰው ኃይልም፣ ከገንዘብ አቅምም አኳያ በአገሪቱ እየገነባቸው ከሚገኘው በብዙ

መቶዎች የሚቆጠሩ አውራ መንገዶች ውስጥ የአንዱ መንገድ በጀት ብቻ እነዚህን ተቋሚት በሙሉ በበቂ መጠን ለማጠናከር ይበቃ ነበር፡፡ እንዲያውም በርከት ያሉ የቴሌቭዥንና የሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲኖሩ ቢፈለግ ከመንግሥት የሚጠበቀው ጣቢያዎቹ ሥራቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸውን የሕግና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ነው እንጂ ጣቢያዎቹን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ወጭ የሚሸፍኑት ባለሀብቶች ናቸው፡፡ ዕድሉን አላገኙም እንጂ፣ ብዙ ባለሀብቶች በመስኩ ለመሰማራትም ፍላጐታቸውን ሲያሳዩ ቆይተዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመንግሥት ማግኘት የሚገባቸውን ድጐማ በተመለከተ ለማየት ብንሞክር ተጨማሪ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ የአገሪቱ ሕግ ለፖለቲካ ፓርቲዎች መንግሥት ድጐማ ማድረግ እንዳለበት በግልጽ ያስቀመጠ ቢሆንም ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት መንግሥት ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ምንም ዓይነት ድጐማ አድርጐ አያውቅም፡፡ በ1999 ዓ.ም ፓርላማ ውስጥ የምንገኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጉዳዩ ላይ ከገዥው ፓርቲ ጋር ባደረግነው ድርድር የድጐማ አሰጣጥን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ በፓርላማው እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲደረግ የተስማማን ቢሆንም በተለያዩ አሳማኝ ያልሆኑ ምክንያቶች ተቃዋሚዎች እስካሁን ከመንግሥት ድጐማ ሳያገኙ ቀርተዋል፡፡ በፓርቲዎቹ የድርድር ስምምነት መሠረት ለፓርላማ ቀርቦ የጸደቀው አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ለመታተም አንድ ዓመት የፈጀበት ሲሆን፣ አሁንም ሕጉ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣ አንድ ዓመት የሞላው ቢሆንም ድጐማ የመስጠቱ ጉዳይ እስካሁን ተግባራዊ ሳይደረግ ቀርቷል፡፡ በሕጉ መሠረት አንድ በፓርላማ የጸደቀ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ መታተም ያለበት ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቢሆንም ኢህአዴግ ለምን ይህንን እንዳደረገ በወቅቱ ሲጠዬቅ ያቀርብ የነበረው መልስ "ሕጉ በነጋሪት ጋዜጣ ሊታተም ያልቻለው የእንግሊዝኛው ትርጉም ስላልደረሰ ነው" የሚል ነበር፡፡ ኢህአዴግ ራሱ የሚፈልጋቸው ሕጐች ሲሆኑ ግን አንድ ወር መጠበቅም ሳይስፈልግ በሁለት ሳምንት ውስጥ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታተሙ ሲደረግ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡

ከእነዚህ ሊያከራክሩ የማይችሉ ቀላልና ግልጽ ምሳሌዎች ልንረዳ የምንችለው ረዥም ሂደት መጠበቅ ሳያስፈልጋት አገሪቱ ልታከናውናቸው የሚገባትንና አቅሟም የሚፈቅድላትን ተግባራት ሳይቀር ኢህአዴግ ተገቢ ባልሆነ ሰበብ አስባብ ሆን ብሎ ሊያዘገዬው እንደቻለ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብና አሠራር ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚገነባው በሂደት ነው ከሚለው አስተሳሰብ ጋር የሚጋጭ እንጂ ፈጽሞ የሚጣጣም አይደለም፡፡ ዴሞክራሲ ነባራዊ ሁኔታና አቅም በፈቀደ መጠን ዛሬ ላይ መሥራት የሚገባንን በአግባቡ እየሠራንና በየሂደቱም

ተጠቃሚ እዬሆን የምንገነባው ሥርዓት እንጂ፣ ሲያስፈልገን አንድ ቦታ ላይ እያቆምንና እየቀጠልን ለተለዬ የፖለቲካ ፍላጐታችን መጠቀሚያ ልናደርገው የሚገባ ሥርዓት አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ዴሞክራሲ ሊገነባ የሚችለው በሂደት መሆኑ የማያከራክር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ነገር ግን የዓለማችን ወቅታዊ ሁኔታ ዴሞክራሲን ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ፍጥነት እንድንገነባው የፈጠረልንን ዕድል በመጠቀም እስካሁን ከተጓዘበት ረዥም ሂደት በብዙ እጥፍ ባነሰ ጊዜ ዴሞክራሲን በአንፃራዊ ፍጥነት በአገራችን ልንገነባው ይጠበቅብናል፡፡ ከዚህ በላይ ዘርዘር ባለ መልኩ ልናየው ከሞከርነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ታሪካዊ ሂደት ዝልገትና ዴሞክራሲን በአግባቡ ለመገንባት አስፈላጊ ናቸው ተብለው ከሚታመንባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ስፋት አንጻር፣ አገራችን ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነችና ከየትስ ተነሥታ የት መድረስ እንደሚጠበቅባት እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

### *3.2.3 ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ምን ያህል ዝግጁ ናት?*

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የምንሞክረው ከላይ በመንደርደሪያችን ልናየው ከሞከርነው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ታሪካዊ ሂደትና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት ናቸው ካልናቸው ቅድመ-ሁኔታዎች አንጻር መሆን ይገባዋል፡፡ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ታሪካዊ ሂደት ስናይ ዴሞክራሲን በማራመድ ፋና ወጊ የሆኑት አገሮች አሁን ያሉበት ደረጃ ለመድረስ ከሁለት መቶ ዓመት ያላነሰ ጊዜ ጠይቋቸዋል፡፡ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ድረስ ዴሞክራሲን የተቀበሉና በአሁኑ ወቅት የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙ በርካታ አገሮችም ዛሬ ላይ የደረሱበት ደረጃ ላይ ለመድረስ እንደየ አገሮቹ ተጨባጭ ሁኔታ ከአርባ እስከ አንድ መቶ ዓመት የሚሆን ጊዜ ወስዶባቸዋል፡፡ እነዚህ አገሮች የዴሞክራሲ ፋና ወጊ ከሆኑት አገሮች በተሻለ ፍጥነት ዴሞክራሲን ለመገንባት የበቁትም ቀደም ሲል በካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ያለፉና ለዴሞክራሲ አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ-ሁኔታዎች ከሞላ ጐደል አሟልተው የነበሩ በመሆናቸው ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ቀሪዎቹና አብዛኛዎቹ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ የዴሞክራሲን ጐራ ተቀላቅለናል የሚሉ የዓለማችን ታዳጊ አገሮች ዴሞክራሲን በመርህ ደረጃ የተቀበሉ ቢሆንም በተግባር ግን አብዛኛዎቹ ኢ-ሊብራል /illiberal/ የሆነ ዴሞክራሲ እንጂ በምዕራቡ ዓለም የሚታየው ዓይነት በአንፃራዊነት ጤናማና ትክክለኛ ሊባል የሚችል ዴሞክራሲ ለመገንባት ገና አልበቁም፡፡ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ዴሞክራሲን ለመቀበል የወሰኑት ገና በቅርቡ ከመሆኑ በላይ

ዴሞክራሲን ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑት ቅድመ-ሁኔታዎች በበቂ መጠን የማይገኙባቸው በመሆናቸው ነው፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ከሁለት ዓመት በኋላ ዴሞክራሲን ተቀብያለሁ ያለችው የኛዋ አገር ኢትዮጵያም ሂደቱ ውስጥ የቆዬችው ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ ከሌሎቹ በተመሳሳይ ጊዜና ሁኔታ ዴሞክራሲን ተቀብለናል ካሉ ታዳጊ አገሮች በተለየ ኢ-ሊበራል /illiberal/ ዴሞክራሲ ከመሆን አልፋ ዴሞክራሲን በበቂ መጠን መገንባት ገና አልቻለችም፡፡ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ኢህአዴግ መሥራት የሚገባውን ሥራ በአግባቡ ባለመሆኑና ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አንጻር ዐሥራ ስምንት ዓመት በቂ ያልሆነ ጊዜ በመሆኑና ለዴሞክራሲ ግንባታ መሠረት መሆን የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች እንደ ሌሎቹ ታዳጊ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም በበቂ መጠን የማይገኙ በመሆናቸው ጭምር ነው፡፡

ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ታሪካዊ ሂደት አንጻር ኢትዮጵያን በመሰሉ ታዳጊ አገሮች የሚደረገውን የለውጥ ሂደት የተለየ ብቻ ሳይሆን የበለጠ አስቸጋሪም የሚያደርገው በዋናነት የጊዜው መርዘምና ማጠር ሳይሆን የለውጥ አመጣጡ መንገድ ነው፡፡ የአደጉት አገሮች ዴሞክራሲን የተቀበሉት በቅድሚያ አስፈላጊ የሚባሉት የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ከሞላ ጐደል በነበሩበት ሁኔታ ሲሆን፣ ታዳጊ አገሮች ዴሞክራሲን የተቀበሉት ግን እነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች ጭራሽ በሌሉበት ሁኔታ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአብዛኛዎቹ የአደጉ አገሮች ዴሞክራሲ ተቀባይነት ሊያገኝና ሊገነባ የቻለው ቅድመ-ሁኔታዎች ከፊት ከፊት እየተመቻቹ በተገኙበት ተፈጥሯዊ ሂደት ነው፡፡ በተለይም የዴሞክራሲ ፋና ወጊ በሆኑት እንደ ብሪታንያና አሜሪካን በመሳሰሉ አገሮች ዴሞክራሲ ተቀባይነት ያገኘው ዴሞክራሲ እንዲመጣ ተብሎ አስቀድሞ በነበረ ፍላጐትና እቅድ ሳይሆን የቅድመ-ሁኔታዎቹ መመቻቸት በራሱ በፈጠረው ግፊት ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ ታዳጊ አገሮች ግን ዴሞክራሲ እንዲመጣ እየተደረገ የሚገኘው ቅድመ-ሁኔታዎች ኖረውና ግፊት ፈጥረው ሳይሆን በአንድ በኩል በዓለም አቀፍ ውጫዊ ግፊት፣ በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱ ዴሞክራሲን ለመቀበል ባሳዩችው ፈቃደኛነትና አስቀድሞ በታቀደ ሁኔታ ነው፡፡

እንኳንስ ዴሞክራሲን የመሰለ ውስብስብና ልዩ ባህሪ ያለው ትልቅ ጉዳይና አንድን አነስተኛ ጉዳይም ተፈጥሯዊ በሆነ ለስላሳ መንገድ ማምጣትና፣ አስቀድሞ በተቀመጠ እቅድ ተመርቶ ማምጣት የተለያዩ ጉዳዮች ስለሆኑ ዴሞክራሲን በታዳጊ አገሮች መገንባት አስቸጋሪ የሚያደርገው አንዱ ምክንያት ይኸው ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ሂደትን ጠብቆ የሚመጣ ለውጥ ተመራጭ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ በአሁኑ ዘመን ዴሞክራሲ ተፈጥሯዊ እድገቱን ጠብቆ በራሱ እስኪመጣ ድረስ እንጠብቀው ሊባል ስለማይችል ዴሞክራሲን ለመመሥረት ዝግጁ ነን ወይስ

አይደለንም? የሚለውን ጥያቄ በብቃት ለመመለስ የምንችለው ከዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች አንጻር በደረስንበት ተጨባጭ ሁኔታ ተመሥርተን ይሆናል። ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ልናየው ከሞከርን፣ ከላይ ካዬናቸው ሰባት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎች አኳያ ኢትዮጵያ የምትገኝበት ደረጃ ገና በጅምር ላይ የሚገኝ ነው። ኢትዮጵያ አሁን ከምትገኝበት ከዚህ ጅምር ሊባል የሚችል ደረጃ ተነሥታ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአግባቡ ለመገንባት በሚያስችላት መጠን ቅድመ-ሁኔታዎችን ለማሟላት ገና ረዥም ጉዞ መጓዝ ይጠበቅባታል።

ከኢኮኖሚ ዕድገትና ተያያዥነት ካላቸው ቅድመ-ሁኔታዎች አንጻር ኢትዮጵያ ገና የኋላ ቀር ግብርና ጥገኛ የሆነችና ከ84% በላይ የሆነው ሕዝቧ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የድህነት ኑሮ በገጠር የሚኖርባት አገር ነች። በዚች አገር የቱንም ያህል የተዋጣለት የኢኮኖሚ ፖሊሲና የአፈጻጸም ብቃት ያለው መንግሥት ሥልጣን ላይ ቢወጣ መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ፈጥሮ አገሪቱን ከእርሻ ጥገኝነት ይልቅ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ ጥገኛ እንድትሆን ለማድረግ፣ አብዛኛው ሕዝቧንም በዚያው መጠን የከተማ ኗሪና መካከለኛ ገቢ ያለው ሕዝብ እንዲሆን ለማድረግ ጠንካሮችም ዕድለኞችም ሆነን ከተገኘን ቢያንስ ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ ዓመት ያላነሰ ጊዜ ሊጠይቀን እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ከትምህርት መስፋፋት አኳያ ከኢኮኖሚው ዕድገት በተሻለ ውጤት ልናመጣ እንችላለን። በትምህርት ረገድ ኢህአዴግ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በአከናወናቸው በጎ ተግባሮች ምክንያት የጥራት ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን በቂ ሊባል የሚችል የትምህርት ሽፋን እየታየ ነው። በአሁኑ ወቅት በትምህርት ገበታ ከአስራ ሰባት ሚሊየን በላይ የሆነ ተማሪ እንደሚገኝ ስለሚገመት የጥራት ጉድለቱ ተሻሽሎ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ ከዐሥራ አምስት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተማረ የሚሆንበት ዕድል እንደሚኖር መገመት ይቻላል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን ኢትዮጵያ ብቃት ላለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በቂ ነው የሚባል የተማረ ሕዝብ ገና የላትም።

ከዚሁ ከኢኮኖሚ ዕድገትና ከትምህርት መስፋፋት ጋር በተያያዘ ጠንካራና በቂ ቁጥር ያላቸው የሲቪክ ማኅበራት፣ በቂ የሚባሉ ገለልተኛ የዴሞክራሲ ተቋማትና በቂ የሥራ ክሂሎት ያለው ቢሮክራሲ በአገሪቱ እንዲኖር ቀላል የማይባል ጊዜ ማስፈለጉ አይቀርም። ጤናማና ገንቢ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች በአገሪቱ ተፈጥረውና በሕዝቡ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚታዩት የተለያዩ ቅራኔዎች ረግበው በቂ የሚባል ብሔራዊ መግባባት በአገራችን እስኪፈጠር

ድረስም አሁን እያዬነው ካለው ሁኔታ አንጻር ቢያንስ ከሁለት እስከ ሦስት የምርጫ ዘመን ማስፈለጉ አይቀርም፡፡

ከሁሉም በላይ ለኢትዮጵያውያን ከባድና አስቸጋሪ የሚሆንብን እንደ ዜጋ፣ እንደ ቤተሰብ፣ እንደ ሕዝብና አገር ነባራዊ የሆነውን ባህላችንን ዴሞክራሲያዊ /Democratized/ ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም የ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያዊያን እስካሁን ይዘነው የኖርነውን ሥነ-ልቦናዊ፣ ማኅበራዊም ሆነ ግላዊ አመለካከታችንን ሳናሻሽልና ሳንለውጥ በታማኝነት እንደነበረ ይዘነው የምንቀጥል ከሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በአግባቡ ለመገንባት ስለማያስችለን ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት መማራችንና ኢኮኖሚያዊ አቅማችን መጠናከሩ ብቻውን በቂ ባይሆንም ከወቅቱ የግሎባላይዜሽን ፈጣን ሂደት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱ አይቀርም፡፡ ግለሰቦችና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአጭር ጊዜ ለውጡን ሊጋሩ የሚችሉበት ዕድል ቢኖርም አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበቂ ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ባህል የተላበሰ ሕዝብ ለመሆን ሊበቃ የሚችለው ግን ቢያንስ በአሁኑ ወቅት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በኮሌጅ ደረጃ ያለው አዲሱ ትውልድ በሁለንተናዊ መልኩ በአገሪቱ የመሪነት ድርሻ ሲኖረው ነው፡፡ ወደዚህ ደረጃ ለመድረስ ደግሞ ከኢኮኖሚና ከትምህርት አኳያ የበቃ ደረጃ ላይ ለመድረስ ያስፈልገናል ያልነውን ጊዜ ያህል መጠየቁ የግድ አይቀርም፡፡ በርግጥ በግራ ፖለቲካ ተኮትኩቶ ያደገውና ከብልሹ የፖለቲካ ባህል መላቀቅ የተሳነው የፖለቲካ ኤሊት በፍላጐትም ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ አስገዳጅነት ከፖለቲካ መድረኩ እስኪወገድ የዛኑ ያህል ጊዜ መጠየቁ አይቀርም፡፡ በአሁኑ ወቅት ቢያንስ በሕግ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘው የሰው ልጅ ነፃነት /Liberty/ና የሕግ-የበላይነትም ዞሮ ዞሮ በብቃት በአገራችን ሊተገበር የሚችለው ከኅብረተሰቡ አጠቃላይ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዕድገት ጋር ተያይዞ በመሆኑ በመርህ ብቻ ሳይሆን በተግባር የአገራችን መገለጫ ለመሆን የራሱን ረዘም ያለ ጊዜ መውሰዱ አይቀርም፡፡

ስለዚህ እነዚህ ሁሉም የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች በአገራችን በአንፃራዊነት በቂ በሚባል መጠን እንዲገኙ /ወደፊት አገሪቱን ሊያስተዳድር በሚችለው ወይም ሊያስተዳድሩ በሚችሉት መንግሥታት ማንነትና ባህሪ ሊያጥርም ሊረዝምም ቢችልም/ አንፃራዊ ሰላምና መረጋጋት የሚኖረን ከሆነ በአማካይ ከሃያ እስከ ሠላሳ ዓመት መጠየቁ እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሥርተዋል የሚባሉ አገሮች ወደ አሉበት ደረጃ አገራችን እንድትደርስ ቢያንስ የአንድ ተሸጋጋሪ ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል ማለት ነው፡፡ ይህም እውን ሊሆን የሚችለው በማንኛውም ሁኔታ ነው ማለት አይደለም፡፡ አገራችን ለዚህ ውጤት ልትበቃ የምትችለው በአንድ በኩል የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ተገቢ

ሂደትና ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑን አምነን በመቀበል ለውጤቱ ሁላችንም በቅንነት፣ በትጋትና በመተባበር መሥራት ስንችል ነው። ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በቅፅበት በእኛ ጊዜ ተፈጥሮ እኛው በዕድሉ እንድንጠቀምበት የምንፈልግ ከሆነ ግን እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የዴሞክራሲን መምጣት የበለጠ ከአገራችን የሚያርቅ እንጂ የሚያፋጥን ሊሆን አይችልም። መሟላት የሚገባቸውን አንፃራዊ ቅድመ-ሁኔታዎች ባላገናዘበ ሁኔታ ዴሞክራሲን በሩጫ እንገንባ ብንል ሂደቱን የበለጠ የሚያዘገይ ውጤት ብቻ ሳይሆን በድንገት ተሰባብሮ መውደቅንም ሊያስከትል ይችላል። በሂደቱ በሚገኘው ውጤት በተወሰነ ደረጃ የአሁኑ ትውልድ ሰዎችም ልንጠቀም የምንችልበት ዕድል ቢኖርም በዋናነት ግን የዚህ ትውልድ ድርሻ ወደፊት ለሚመጣው ትውልድ አስተማማኝ መሠረት ለመጣል የሚያስችል መሥዋዕትነት የመክፈል እንጂ የውጤቱ ዋና ተጠቃሚ መሆን አይደለም። ብዙውን ጊዜ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዙሪያ የሚታየው ዴሞክራሲ ያለተፈጥሮው በአንድ ጊዜ አገሪቱን አጥለቅልቋት የማየት ፍላጐትም ከዚሁ የተሳሳተና ግለኛ የሆነ አመለካከት በመነጨ ነው።

በሌላ በኩል በመንግሥት ሥልጣን ላይ የተቀመጡ የፖለቲካ ኃይሎች የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታና አቅም በሚፈቅደው መጠን ዴሞክራሲን በተቻለ ፍጥነትና ትጋት በሃቅ ለመገንባት ከመጣር ይልቅ ለራሳቸው የግልና የቡድን ጥቅም ሲሉ ሂደቱን ሊያስተጓጉልና ሊያዘገይ የሚችል ተግባር ላይ ከተሰማሩ ዴሞክራሲን ከላይ ለመገመት በተሞከረው ጊዜ ውስጥ በበቂ መጠን ማስፈን አይቻልም። መሠረታዊ በሚባሉ አገራዊ ጉዳዮች የአገሪቱ ፓርቲዎች ብሔራዊ መግባባት ካልፈጠሩ፣ በአገሪቱም አንፃራዊ ሰላምና ፖለቲካዊ መረጋጋት መኖር ካልቻለና በአገሪቱ የተጀመረው የልማት እንቅስቃሴ ሳይቋረጥ ካልቀጠለ በስተቀርም የአገሪቱ የዴሞክራሲ ምኞት በአግባቡ ሊሳካ አይችልም ብቻ ሳይሆን የአገሪቱ አጠቃላይ ህልውናም ያልታሰበ አቅጣጫና አደጋ ውስጥ ሊገባ ይችላል።

በአጠቃላይ በአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ካሳለፈው አጭር ጊዜ አኳያም ሆነ የዴሞክራሲ ግንባታ ቅድመ-ሁኔታዎች ካሉበት ዝቅተኛ ደረጃ አንጻር ኢትዮጵያ በሌሎች ዴሞክራሲያዊ አገሮች በሚታዬው መጠንና ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲን ለማስፈን የበቃች ነች ማለት አይቻልም። አሁን በምትገኝበት ደረጃ በበቂ መጠን ዝግጁ ናት ማለት ባይቻልም ዞሮ ዞሮ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ይጠቅመኛል ብላ በሕገ-መንግሥት ደረጃ ከተቀበለችና ሂደቱን እየተንገዳገደችም ቢሆን ከጀመረችው ዐሥራ ስምንት ዓመት ሆኗታል። በአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ዴሞክራሲን በአገሪቱ ለመገንባት በተደረገው ጥረት ከታዩት ድክመቶችና ችግሮች ጭምር የታዬው በጎ ውጤትም ቀላል የሚባል አይደለምና ዛሬ ወደኋላ ተመልሰን ኢትዮጵያ

የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ፈጽሞ ባልነበሩበት በ1983 ዓ.ም ዴሞክራሲን መቀበል ነበረባት ወይስ አልነበረባትም? የሚል ክርክር ማንሣት ተገቢና ወቅታዊ አይሆንም፡፡

ነገር ግን በዚያ የመንግሥት ለውጥ ወቅት የአገሪቱን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ በመወሰን ረገድ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች በመካከላቸው ብሔራዊ መግባባት የነበራቸውና የአገሪቱን ጉዳይ ከውጫዊ ግፊትና ከውስጣዊ ሽኩቻ ነፃ በሆነ መንገድ የሚያዩበት ዕድል ቢኖራቸው ኖሮ ኢትዮጵያ መቼና እንዴት ዴሞክራሲን ትቀበል? በምን ዓይነት የቅደም ተከተል አግባብስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ይገንባ? የሚለው ጥያቄ ቢያንስ አከራካሪ ሆኖ ሲቀርብ በቻለ ነበር፡፡ ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ በኋላ በአንድ በኩል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እያራመድን ነው እያልን፣ በሌላ በኩል ግን ከፍተኛ ደም መፋሰስ ጭምር ያስከተሉ ግጭቶችን ማስተናገዳችንና አሁንም ውጥረትና ፍጥጫ በነገሠበት የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ መገኘታችን የሚያሳዬው ከመጀመሪያውም እንደ አንድ አገርና ሕዝብ ዴሞክራሲን መቼና እንዴት ተቀብለን እናስፍነው? በሚለው ጥያቄና በአተገባበሩ ቅደም-ተከተል ዙሪያ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙና አገር በቀል የሆኑ አማራጭ ሐሳቦች በበቂ ሁኔታ ቀርበው ስላልታዩ ጭምር ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዐሥራ ስምንት ዓመት በኋላ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ማንሣት የዘገዬ ነው መባሉ አከራካሪ ባይሆንም፣ ነገር ግን ሁላችንም ስለ ዴሞክራሲ አስፈላጊነት እያወራን ባለንበት በአሁኑ ወቅት ለምን ከግጭትና ከፍጥጫ ፖለቲካ መላቀቅ እንዳልቻልን ለመገንዘብና ወደፊትም በአገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ የተቀራረበ አመለካከት እንዲኖረን በማድረግ ረገድ ሊያግዘን ስለሚችል ዴሞክራሲን መቼና እንዴት መቀበል ይሻል ነበር? ወይም ይሻላል? በሚለው ጥያቄ የተወሰኑ ሐሳቦችን ፈንጥቆ ማለፍ ተገቢ ይሆናል፡፡

### *3.2.4 የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአገራችን መቼና እንዴት?*

ከዚህ ዴሞክራሲን መቼና እንዴት? ከሚለው ጥያቄ ጋር በተያያዘ መጀመሪያ መነሣት የሚገባው ጥያቄ ዴሞክራሲ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛዎቹ የዓለም አገራት ተቀባይነት ያገኘ ሥርዓት ስለሆነ ብቻ ሁሉም የዓለም አገራት የግድ ሊቀበሉት ይገባል ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይብዛም ይነስም የለውጥ ሂደት በእያንዳንዱ አገር የማያቋርጥ ክስተት በመሆኑ አንድ አገር ዝንተ-ዓለም ዴሞክራሲን መቀበል አይችልም ወይም አይገባውም ብሎ መደምደም የሚቻል አይሆንም፡፡ ዴሞክራሲ በአሁኑ ዓለም ብዙም ተፎካካሪ የሌለው ዋና የፖለቲካ ሥርዓት በመሆኑ አስፈላጊቱ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንድ አገርና ሕዝብ በአንድ ወቅት ላይ ከሚገኝበት አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ በመነሣት በአንድ ጊዜ ዴሞክራሲን ከነ ሙሉ ባህሪያቱና መገለጫዎቹ መቀበል ይጠቅመዋል ወይም አይጠቅመውም? የሚለው ጥያቄ በሚገባ አከራካሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በዚህ በአለንበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ አገሮች በንጉሣዊ ሥርዓት፣ አንዳንድ አገሮች በሶሻሊስታዊ ሥርዓት፣ አንዳንድ አገሮች በአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ ሥርዓት፣ አንዳንድ አገሮች ደግሞ በሃይማኖታዊ ሥርዓት እየተዳደሩ የሚገኙት፣ በርግጥም የምዕራቡ ዴሞክራሲ አያስፈልገንም ወይም አይገባንም የሚል አስተሳሰብ በአንዳንድ አገሮች በጠነከረ ሁኔታ ስላለ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱን አስተሳሰብ አንዳንድ ጊዜ አምባገነናዊ ኃይሎች ሥልጣናቸውን ለማራዘምና የሕዝብን መብት ላለማክበር ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት አጋጣሚ መኖሩ ግልጽ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን በትክክለኛና በአሳማኝ ምክንያትም ጭምር የሚቀርብ አስተሳሰብ መሆኑ ሊካድ አይችልም፡፡ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው አንድ ከምዕራቡ ዓለም ፈጽሞ በተለየ ታሪካዊ ሂደት አልፎ የመጣና የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ፈጽሞ ያላቆጠቆጡበት አገርና ሕዝብ ዴሞክራሲን ላለመቀበል ቢወስን ተሳስቷል ተብሎ ሊወገዝ አይችልም፡፡ እንዲያውም ስህተት የሚሆነው አንድ አገር ዴሞክራሲን ለመቀበል የሚያስችሉ ታሪካዊ ሂደቶችና ቅድመ-ሁኔታዎች በሌሉበት ሁኔታ በውጫዊ ግፊት ወይም በሌላ የተሳሳተ ምክንያት "ዴሞክራሲን ተቀብያለሁ" ቢል ነው፡፡

ምክንያቱም ለአንዳንድ አገሮች ዴሞክራሲን መቀበል አስቸጋሪ ብቻ ሳይሆን መጥፎ ምርጫም ሊሆን ይችላል፡፡ በተለያዩ አገሮች ተመክሮ በተጨባጭ እንደታየውም ዴሞክራሲን ለመቀበል የሚያስችል ማኀበራዊ መሠረት ሳይኖራቸው በአንድ ጊዜ ከአምባገነናዊ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲ ዘለው የሚገቡ አገሮች በአምባገነናዊ ሥርዓት እየተገዙ ከቀጠሉ አገሮች ይልቅ

ለጦርነትና ለብጥብጥ የመጋለጣቸው አደጋ ከፍተኛ ሆኖ ታይቷል፡፡ የግድ ዴሞክራሲን ለማስፈን ተብሎ የሚወሰድ ያልተጠና ርምጃ የአንድን አገር ሰላማዊ ኑሮ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ አገራዊ ህልውናንም ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ለውጥ ምንጊዜም አንፃራዊ ነውና አንድን አገር ያለአግባብ የዴሞክራሲ መሞከሪያ አድርጎ ወደ የርስ በርስ ብጥብጥና የህልውና አደጋ ውስጥ ከማስገባት ይልቅ በአምባገነናዊ ሥርዓት ሥር አገራዊ ህልውናውን ጠብቆ እንዲቆይ ማድረግ ሊመረጥ ይችላል፡፡

የወቅቱን የሶማሊያ፣ የኢራቅና የአፍጋኒስታን ሁኔታ ስናይ ሶማሊያ በሲያድባሬ፣ ኢራቅ በሳዳም፣ አፍጋኒስታን በታሊባን በአንፃራዊነት ከዛሬ የተሻሉ ሰላማዊ አገሮች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ በቅርቡ በአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች እንዳየነውም የምርጫ ሂደት የመጨረሻ ውጤት አፍሪካውያንን ርስ በርስ የሚያስተራርድ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ፣ ነባራዊ ሁኔታዎች በተሻለ ሁኔታ እስከሚመቻቹ ድረስ ምርጫ ከመኖሩ ይልቅ አለመኖሩ ሊመረጥ ይችላል፡፡ በኬንያና በዚምባቡዌ በቅርቡ እንደታየው የብዙ ዜጎችን የሕይወት መሥዋዕትነት ከጠየቀም በኋላ ሁለቱ አገሮች መንግሥት መፍጠር የቻሉት የሕዝቡ ፍላጐት በተገለፀበት የምርጫ ውጤት አማካይነት ሳይሆን ሕገ-መንግሥታዊና ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ፣ ማለትም በፖለቲካ ሰዎች ድርድርና "የሥልጣን ቅርጫ" ስምምነት ነው፡፡ ስለዚህ መለስተኛ አለመግባባቶችና ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ ብሎ በመስጋት ምርጫን እንዳይካሄድ ማድረግ አስፈላጊ ባይሆንም፣ ነገር ግን የሚያስከትለው ውጤት ምንም ይሁን ምን በማንኛውም ዓይነት የታሪክ ሂደትና ማኅበራዊ ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮች በሙሉ "የግድ የምዕራባውያንን ዴሞክራሲ መቀበል አለባቸው" ብሎ ማመን ትክክለኛ አስተሳሰብ ሊሆን አይችልም፡፡

ምዕራባውያን ብዙውን ጊዜ ዴሞክራሲን ላለመቀበል የሚወሰድ አቋምንም ሆነ ዴሞክራሲን ከመቀበል በኋላ በአንዳንድ አገሮች የሚፈጠርን ችግር የሁለት ዓለም የሥልጣኔ ግጭት /clash of civilization/ አድርገው ሊያዩት ይሞክራሉ፡፡ ጉዳዩ ግን እነሱ እንደሚሉት የሥልጣኔ ግጭት ሳይሆን ምዕራባውያን ለሌሎች አገሮች ጥቅም በመጨነቅ ሳይሆን በዋናነት በተለያዩ የራሳቸው ምክንያቶች በቅድመ-ዴሞክራሲ ማኅበራዊ ሁኔታ /pre democratic structure/ ውስጥ የሚገኝ አገር የግድ ዴሞክራሲን ካልተቀበለ ብለው ያለአግባብ የሚፈጥሩት ግፊት የፈጠረው ችግር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በልዩ ታሪካዊ ሂደት ያለፈችውና አብዛኛዎቹን የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች በማሟላት ላይ የምትገኘው ቱርክ ዴሞክራሲን መቀበል ስለቻለች ብቻ ሌሎችም የአረብ አገሮች ዴሞክራሲን ካልተቀበሉ በስተቀር ከሥልጣኔ ጋር ተጋጭተዋል ብሎ ማሰብ በራሱ ሥልጣኔ የጐደለው አስተሳሰብ ነው የሚሆነው፡፡

ምክንያቱም አንዳንዶቹ የአረብ አገሮች ቱርክ ካለፈችበት በተለየ ታሪካዊ ሂደት ያለፉና ገና የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ያላቆጠቆጡባቸው አገሮች ስለሆኑ በቅርብ ጊዜ ዴሞክራሲን እንዲቀበሉ መጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መቀበል የአንድ አገር ብቸኛ የተቀባይነት /Legitimacy/ መገለጫ አድርጐ ማየትም ተገቢ አይሆንም፡፡ ዴሞክራሲ የመንግሥት ሥርዓት ዓይነት ከመሆኑ በፊት በሕዝባቸው ዘንድ ተቀባይነት /Legitimacy/ የነበራቸው ብዙ መንግሥታት የመኖራቸውን ያህል ዛሬም ቢሆን አንድ መንግሥት ለአገሩ ሕዝብ የኢኮኖሚ ዕድገት እስካመጣና ሰላም እስካሰፈነ ድረስ ያለ ዴሞክራሲም የሕዝብ ተቀባይነት /Legitimacy/ ሊያገኝ ይችላል፡፡ እንዲያውም ዴሞክራሲን ተቀብለናል ብለው በሕዝብ ስም አገር እናስተዳድራለን ከሚሉ በርካታ ኢ-ሊበራል /illiberal/ ከሆኑ መንግሥታት ይልቅ ሶሻሊስታዊ ወይም ንጉሣዊ ሥርዓትን የሚከተሉ አንዳንድ መንግሥታት በሕዝባቸው የተሻለ ተቀባይነት /Legitimacy/ ሲኖራቸው ይታያል፡፡ በሕዝባቸውም ብቻ ሳይሆን በርካታ አምባገነናዊ መንግሥታት ከምዕራባውያኑ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ተግባር እስካልፈፀሙ ድረስ በውጭ መንግሥታትም ተመሳሳይ ተቀባይነት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ምዕራባውያን ለነሱ ጥቅም መጠበቅ የሚጠቅም ሆኖ ሲገኝ ዴሞክራሲን የጫና መፍጠሪያ መሣሪያ አድርገው የሚጠቀሙበትን ያህል ጥቅማቸውን የሚጐዳ ሆኖ ሲያገኙት ግን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ የሕዝብ መንግሥትንም ዕውቅና ከመንፈግ ጀምሮ በኃይል የማስወገድ ሴራ ውስጥ እንደሚሰማሩ በተለያዩ አጋጣሚዎች ታይቷል፡፡ ምክንያቱም በዴሞክራሲ አግባብ የሚቋቋሙ መንግሥታት ከማንም በላይ ተጠያቂነታቸው ለራሳቸው ሕዝብ ስለሚሆን ለምዕራባውያኑ ጥቅም ታዛዥ የመሆናቸው ዕድል የጠበበ ሊሆን ይችላል፡፡ አሜሪካኖች ኢራቅን ለመውረር ባደረጉት ዘመቻ በወቅቱ በሚፈልጉት ሁኔታ የቱርክ መንግሥትን ድጋፍ ሳያገኙ የቀሩት ያለምክንያት ሳይሆን የቱርክ መንግሥት ከሌሎቹ የአረብ አገሮች ይልቅ የሕዝብ ተጠያቂነትና ተጠሪነት ያለው መንግሥት በመሆኑ ነበር፡፡ የአሜሪካ ቁርጠኛ ወዳጅ የሆነችው ሳውድ አረቢያ ነገ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ማግኘት ብትችል የአሜሪካ ጥቅም አስጠባቂ አገር /Clint state/ ሆና ልትቀጥል ትችላለች ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ከተቀባይነት /Legitimacy/ አንጻርም ዴሞክራሲን የዓለም አገራት በሙሉ የግድ ሊቀበሉት ይገባል ብሎ መደምደም ተገቢ አይሆንም፡፡

ሁለተኛው በዚህ ዴሞክራሲ መቼና እንዴት? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ሊነሣ የሚገባውና የበለጠ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ጥያቄ አገሮች ከደረሱበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ራሳቸውን

ገምግመው ዴሞክራሲን ለመቀበል ዝግጁ ነን ብለው ካመኑ ዴሞክራሲን የሚገነቡበት ቅደም ተከተል ምን ዓይነት ሊሆን ይገባዋል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ይህንን ጥያቄ ማንሣት አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁለት መነሻ ምክንያቶች አሉ ማለት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የተለያዩ ዴሞክራሲን ተቀብለው ለመገንባት የሚወስኑ አገሮች በሁለንተናዊ መልኩ በተለይም ከዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች አንጻር አንድ ዓይነት ደረጃ ላይ ሊገኙ ስለማይችሉ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምክንያት በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲን በአዲስ መልክ የሚቀበሉ ታዳጊ አገሮች የዴሞክራሲ መገለጫ ናቸው የሚባሉትን ተግባራት በቅደም-ተከተል ሳይሆን በአንድ ጊዜ አዥጐድጉደው ለመተግበር በሚያደርጉት ሙከራ ችግሮች ሲገጥሟቸው ስለሚታይ ነው፡፡

በተለያዩ አገሮች የተለያዩ ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ አገሮች ዴሞክራሲን የተቀበሉበት መንገድ ስናየው የቅደም- ተከተል የአተገባበር ስልትን የተከተለ ሳይሆን ሁሉንም የዴሞክራሲ መገለጫዎች በአንድ ጊዜ ተግባራዊ ለማድረግ የሞከረ ነው፡፡ ዴሞክራሲን በአዲስ መልክ የተቀበሉ አገሮች ቀድመው ዴሞክራሲን የገነቡ አገሮች ባለፉበት አዝጋሚ ሂደት ይጓዙ ሊባል ባይችልም በሁሉም የዴሞክራሲ መገለጫ የሆኑ ተግባራት በአንድ ጊዜ ነባራዊ ሁኔታቸው ሊሸከመው በማይችለው መጠን ሲጥለቀለቁ ለአደጋ የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ይሆናል፡፡

በእዝ ኢኮኖሚ ውስጥ የነበረ አንድ አገር በአንድ ጊዜ ልቅ ወደሆነ ነፃ-ገበያ ሲገባ፣ በአንድ አምባገነናዊ ሥርዓት ሥር የነበረ አንድ አገር በአንድ ጊዜ በርካታ ፓርቲዎች ወደሚፎካከሩበት የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ሲገባ፣ ሐሳብን የመግለፅ ነፃነት ያልነበረው አንድ ሕዝብ በአንድ ጊዜ በነፃ-ፕሬስ ውጤቶች ሲጥለቀለቅ፣ ምርጫ አካሂዶ የማያውቅ አንድ ሕዝብ በአንድ ጊዜ ከማዕከል እስከ ቀበሌ በየአምስት ወይም አራት ዓመቱ ምርጫ እንዲያካሂድ ሲደረግ ከአገሩ ማኀበራዊ መሠረት ጋር የተጣጣመና የሰከነ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ማካሄድን አስቸጋሪ እንዲሆን ማድረጉ አይቀርም፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ራሳቸው ታዳጊ አገሮች ለማድረግ ሲሞክሩ የሚታየውም ሆነ ምዕራባውያን ከአንዳንድ ታዳጊ አገሮች ሲጠብቁ የሚታዩት ዴሞክራሲ ያለምንም የአተገባበር ቅደም ተከተል በተዥጐደጐደ ሁኔታ በአንድ ጊዜ ሥራ ላይ እንዲውል ነው፡፡

ዴሞክራሲ በሂደት የሚገነባ ሥርዓት ነው መባሉ የማያከራክር ሃቅ መሆኑ ተቀባይነት ካለው፣ ዴሞክራሲን በተዥጐደጐደ ሁኔታ ያለምንም ቅደም-ተከተል እንዲተገበር ማድረግ ወይም መጠዬቅ በራሱ ዴሞክራሲ በሂደት የሚገነባ ሥርዓት ነው ከሚለው ገዥ መርህ ጋር የሚቃረን አስተሳሰብ ይሆናል፡፡ በእውነትም ዴሞክራሲ የሂደት ጉዳይ ከሆነ አንድ አገር በቅድሚያ

የኢኮኖሚ ነፃነቶችን አውጆ ቀጥሎ ወደ ፖለቲካ ነፃነቶች ቢሸጋገር፤ አንድ አገር በቅድሚያ ከሁለት ወይም ከሦስት ባልበለጡ ፓርቲዎች ፋክክር ጀምሮ ቀጥሎ ወደ ተሟላ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ቢሸጋገር፤ አንድ አገር በቅድሚያ ከቀበሌና ከወረዳ ምክር ቤቶች ምርጫ ጀምሮ በሂደት ወደ አጠቃላይ አገራዊ ምርጫ /universal suffrage/ ቢሸጋገር፤ አንድ አገር በዘጠኝ ወይም በስምንት ዓመት አንድ ጊዜ ከሚካሄድ የመንግሥት ምርጫ ጀምሮ በሂደት በአራት ወይም በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ወደሚካሄድ የመንግሥት ምርጫ ቢሸጋገር፤ አንድ አገር በቅድሚያ ከጥቂት የግል መገናኛ ብዙኃን ተነሥቶ በሂደት ወደተሟላ የፕሬስ ነፃነት ቢሸጋገር፤ አንድ አገር በከፊል የሥልጣን ክፍፍል ጀምሮ በሂደት ወደተሟላ የፌደራል አደረጃጀት ቢሸጋገር የዴሞክራሲ ሥርዓት ግባታውን ሂደት ጤናማና አደጋ የለሽ /Risk free/ ሊያደርገው ይችላል፡፡

እንደየ አገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ይህንን መሰል የአተገባበር ቅደም-ተከተሎችን መሠረት ያደረገ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ቢኖር መንግሥታት ዴሞክራሲ ያልታሰበ አደጋ ያመጣብናል በሚል የሚኖራቸውን ስጋት በማለዘብ፣ የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች ግንባታው ሂደትም ከውጫዊ ተፅዕኖ ይልቅ የራሱ አገራዊና ተፈጥሯዊ ባህሪ እንዲኖረው በማድረግ፣ የዴሞክራሲ ሂደቱንም ሕዝቡ ቀስ በቀስ ከራሱ ባህልና አስተሳሰብ ጋር እያጣጣመው እንዲመጣ በማድረግ፣ በአጠቃላይም ዴሞክራሲን መቀበል በአገር ህልውናና ሰላም ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ቀውስና አደጋ በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱን ዴሞክራሲን በተገቢ ቅደም ተከተል የመገንባት አማራጭ አስተሳሰብም እንደ ኢህአዴግ ዴሞክራሲን ሆን ብሎ ከማዘግየት አኳያ ሳይሆን የሚገነባውን ሥርዓት ቀጣይና አስተማማኝ ከማድረግ አኳያ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በርግጥ የቅደም-ተከተሉን አስፈላጊነት ሆን ብለው ለግልና ለቡድን ጥቅማቸው ሊጠቀሙበት የሚፈልጉ የፖለቲካ ኃይሎች ባሉበት ሁኔታ ጉዳዩ ትርጉም የለሽ ብቻ ሳይሆን ውጤቱም የበለጠ ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አደጋ እንዳይፈጠር ዴሞክራሲን የመተግበሪያ ቅደም-ተከተሎቹ የአንድን የፖለቲካ ኃይል ጥቅም ለማስጠበቅ ሆን ብለው የታለሙ አለመሆናቸውን ማረጋገጥና በቅደም- ተከተሎቹም ላይ ብሔራዊ መግባባትን አስቀድሞ መፍጠር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሕዝቡ የዴሞክራሲ የመተግበሪያ ቅደም-ተከተሎቹ አስፈላጊ የሆኑት ለአንድ የፖለቲካ ኃይል የተለየ ጥቅም ሳይሆን ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ መሆኑን ከልቡ እምነት የሚፈጥርበት ሁኔታ ከተመቻቸ ሕዝቡ ለእንደዚህ ዓይነቱ የዴሞክራሲ አተገባበር ሙሉ ተባባሪ መሆን የማይችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በተለይም እንዲህ ዓይነቱ የዴሞክራሲ የቅደም-ተከተል አተገባበር የአገር መሪዎች የሥልጣን ዘመን /Term/ አስቀድሞ በተወሰነበት ሁኔታ የሚካሄድ ከሆነ ጉዳዩ ከሥልጣን

ጥቅም ጋር በጥርጣሬ መታዬቱ በርግጠኛነት ስለሚያከትም ሕዝባዊ ተቀባይነቱና ውጤታማነቱ የበለጠ የመሆን ዕድል ይኖረዋል፡፡

ከዚህ የዴሞክራሲ አተገባበር ቅደም-ተከተል አንጻር አንድ አገር አንድ ጊዜ ዴሞክራሲን ከተቀበለ በኋላ በምን ዓይነት የቅደም-ተከተል አተገባበር ሊመራ ይገባል? የሚለው ጥያቄ እስካሁን የክርክር አጀንዳ የሆነበት ሁኔታ ጉልቶ የማይታይ ቢሆንም ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ ነፃነት የትኛው ቀድሞ ሊተገበር ይገባዋል? የሚለው ጉዳይ በዓለም የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ ሆኖ የቆዬና አሁንም ያለ አስተሳሰብ ነው፡፡ በአንድ በኩል የፖለቲካ ነፃነት ከሌለ የኢኮኖሚ ነፃነት ሊኖር አይችልም ብለው የሚያምኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነትን ጉን ለጉን ማስኬድ እንጂ ሁለቱን ነጣጥሎ ማየት አይቻልም በማለት የሚከራከሩ ብዙ የፖለቲካ ሰዎችና ምሁራን ያሉ ቢሆንም፣ አሁን አሁን በአንዳንድ የኤዥያ አገሮች ከታዬው የተለየ የውጤታማነት መንገድ ጋር በተያያዘ ከፖለቲካ ነፃነት በፊት የኢኮኖሚ ነፃነትና ዕድገት ቀድሞ ቢመጣ ይመረጣል የሚለው አስተሳሰብ የበለጠ ትኩረት የሚስብ እየሆነ መጥቷል፡፡

በርግጥ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ የምዕራቡ ዴሞክራሲ ጥያቄ ሊነሣበት የማይገባ የተዋጣለት ሥርዓት እየመሰለ ስለመጣ እንጂ ራሱ ዴሞክራሲ ውጤታማ የሆነባቸው አብዛኛዎቹ የአደጉ አገሮች ታሪካዊ ሃደት የሚያሳዬው ከዴሞክራሲ በፊት ቀድሞ የመጣውና ለዴሞክራሲ መምጣትም መደላድል ሆኖ ያገለገለው የኢኮኖሚ እድገት መሆኑን ነው፡፡ ዴሞክራሲ ዋና የመንግሥት ሥርዓት መገለጫ ከመሆኑ በፊት በተለየ ታሪካዊ ሁኔታ /Exception/ ያለ በቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ዴሞክራሲያዊ መሆን የቻሉ ህንድን የመሰሉ አገሮችን ሳይጨምር ብዙዎቹ የአደጉት አገሮች በካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ብዙ ርቀት ተጉዘው ራሳቸውን ኢንዱስትራላይዝድ ማድረግና የቡርዣ ኅብረተሰብ መፍጠር ችለው ነበር፡፡ እነዚህ የአደጉ አገሮች ዴሞክራሲን ቀድመው ለመቀበል ምክንያት የሆናቸውም በኢኮኖሚ ዕድገታቸው ምክንያት አብዛኛዎቹን የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች አሟልተው በመገኘታቸው ነበር፡፡ በኋላም ላይ ከአንደኛውና ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ዴሞክራሲን በቀላሉ በመገንባት ረገድ የተሻለ ውጤታማ መሆን የቻሉት አብዛኛዎቹ አገሮች ቀደም ሲል ካመጡት የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተያያዘ መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብ መፍጠር የቻሉት አገሮች ነበሩ፡፡ በአሁኑ ወቅት ጠንካራ ኢኮኖሚ ገንብተው ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ዴሞክራሲ መግባት ያልቻሉት አገሮች በቁጥር ጥቂት ሲሆኑ፣ ያደገ ኢኮኖሚ ሳይኖራቸው በልዩ ሁኔታ /Exception/ ወደ ዴሞክራሲ መግባት የቻሉት አገሮችም በዚያው መጠን በጣም ጥቂት ናቸው፡፡

በተለይም ደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣ ታይላንድና ማሌዥያን የመሳሰሉ አገሮች በአንድ ፓርቲ ወይም ወታደራዊ ጁንታ አገዛዝ ሥር ሆነው ያለዴሞክራሲ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ካሳዩ በኋላ ከዴሞክራሲ በፊት የኢኮኖሚ ዕድገትን ማምጣት ይቻላል ብቻ ሳይሆን ይሻላል የሚለው አስተሳሰብ እየተጠናከረ መጥቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ቻይና ዓለምን በሚያስጋ መጠን ማደግ የቻለችው የኢኮኖሚ ተኃድሶን ከፖለቲካ ተኃድሶ በፊት ለማራመድ በመምረጧ መሆኑን እያወደሱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሩሲያ እንደ ቻይና ውጤታማ መሆን ያልቻለችው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ተኃድሶን በአንድ ላይ ለማካሄድ በመምረጧ ነው በማለት ሲተቹ ይደመጣሉ፡፡ በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጸሐፊዎች በአሁኑ ወቅት ሲመክሩ የሚደመጡት የኢኮኖሚ አቅም በበቂ መጠን ተጠናክሮ የፖለቲካ ነፃነትን በአግባቡ መሸከም የሚችልበት ሁኔታ እስከሚፈጠር ድረስ አገሮች የፖለቲካ ተሃድሶን ቢያዘገዩት ይመረጣል በማለት ነው፡፡

በርግጥም የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የርእዮተ-ዓለም እስረኛ ከመሆን በወጣ የተግባራዊነት /Pragmatic/ ስልት የቻይናን ሕዝብ ከህንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በበለጠ ለኢኮኖሚ ዕድገት የተመቸ ሲያደርገው ታይቷል፡፡ ብዙ ጸሐፊዎችም የቻይና የኢኮኖሚ ዕድገት በዚህ መልክ ማደጉን ከቀጠለ ማይምነት እየቀነሰ፣ የግል ሀብት እየሰፋና እያደገ፣ በዚያው መጠንም መካከለኛ ገቢ ያለው ኅብረተሰብና በመንግሥት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ የተለያዩ የጥቅም ቡድኖች በአጭር ጊዜ እየተፈጠሩ ስለሚመጡ ቻይና ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የምትገባበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን ይገምታሉ፡፡

በበርካታ የእሲያ አገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ያለ ዴሞክራሲ ሲመጣ እየታየ ያለው ያለ ምክንያት ሳይሆን ብዙውን ጊዜ የኢኮኖሚ ተኃድሶዎች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይልቅ በአምባገነናዊ ሥርዓት በመሆኑ ጭምር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አምባገነናዊ በሆነ ሥርዓት የሚመሩ አገሮች ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የተለያዩ የጥቅም አስጠባቂ ቡድኖችና ነፃ መገናኛ ብዙኃን ስለማይኖሩ የተኃድሶ እንቅስቃሴን በቀላሉ ለማደናቀፍ የሚችል ተቀናቃኝ ኃይል አይኖርም፡፡ በርግጥም በዓለም ታሪክ ቡርዧ ኅብረተሰብ ቀድመው ሲፈጥሩ የታዩት ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ /Authoritarians and monarchs/ ሥርዓቶች ናቸው፡፡

ዛሬ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ተሟጋች የሆኑት አገሮች ከፍተኛ የካፒታሊስት ብልፅግና ላይ የደረሱት የመብት ተሟጋችና የጥቅም አስከባሪ ድርጅቶች ባልነበሩበት ጊዜ የህፃናትን፣ የሴቶችንና የባሪያ ጉልበትን በዝብዘው፣ ከዚያም በላይ ሌሎች አገሮችን በቅኝ-ግዛት

በመያዝ የሰው ጉልበትንና የተፈጥሮ ሀብትን በመዝረፍ ጭምር ነው፡፡ ታዳጊ አገሮች ግን በኢኮኖሚ መበልፀግ ይቅርና ገና ጠግበው መብላት ሳይጀምሩ የመብት ትግል ከፊታቸው ቀድሞ ስለ ቆመ ወደዱም ጠሉም የበለፀጉት አገሮች ባደጉበት መንገድ ያሻቸውን ሰርተው የመበልፀግ ዕድል የላቸውም፡፡ እንዲያውም የዓለም አካባቢን በብቸኝነት ሲበክሉ የኖሩት የበለፀጉ አገሮች ዛሬ የአካባቢ ደኅንነት ቀዳሚ ተቆርቋሪ ሆነው ስለ ቆሙ ታዳጊ አገሮች የዕለት ኑሮአቸውን በኢንዱስትሪ ልማት ጭምር ለማሸነፍ የሚያደርጉት ጥረት ከአካባቢ ብክለት ጋር በተያያዘ ቀላል የማይባል ፈተና ገጥሞታል፡፡ ስለዚህ የኢኮኖሚ ተኃድሶ ከፖለቲካ ተኃድሶ በፊት ቢመጣ የተሻለ ይሆናል እየተባለ ያለውና ለታዳጊ አገሮች ዴሞክራሲን በቅድሚያ ተቀብሎ ኢኮኖሚን መገንባት የከበደ የሚያደርገው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ዴሞክራሲን በአዲስ መልክ የሚቀበሉ ታዳጊ አገሮች የዴሞክራሲ አተገባበር ቅደም-ተከተል እንዲኖራቸው አስፈላጊ የሚሆነውም በዚሁ ተመሳሳይ ምክንያት ነው፡፡

ከዚህ የዴሞክራሲ አተገባበር ቅደም-ተከተል አኳያ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለማየት ስንሞክር ምንም ዓይነት የዴሞክራሲ አተገባበር ቅደም-ተከተል ሳይኖረን ዐሥራ ስምንት ዓመት በሂደቱ ውስጥ ማለፋችን በተወሰነ ደረጃ ችግራችንን አወሳስቦታል፡፡ ገና አገሪቱ ዴሞክራሲን ከመቀበሏ በፊት፣ ስለአገራችን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ በሰከነ መንገድ ለመመካከር የሚያስችል ዕድል ቢኖር ኖሮ ያኔ ከኢኮኖሚ ተኃድሶና ከዴሞክራሲ ተኃድሶ ለየትኛው የበለጠና ቅድሚያ ትኩረት ብንሰጥ ይሻላል የሚል የቅደም-ተከተል ጥያቄ ሊነሣ በቻለ ነበር፡፡ ያ ዕድል ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ በተወሰነ ደረጃ ለኢኮኖሚ ጉዳዮች የበለጠና ቅድሚያ ትኩረት መስጠት የተሻለ ይሆን ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሲባል ኢኮኖሚው በበቂ ሁኔታ ማደግ እስኪችል ድረስ የዴሞክራሲ ጉዳይ ይዘግይ ማለት ሳይሆን አንዱ የሌላው መሠረት እየሆነ ወደ ኋላ የማይመለስና እንደ እንቧይ ካብ የማይናድ ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የአፈጻጸም ቅደም-ተከተል የማስቀመጥ ጉዳይ ነው እንጂ በአሁኑ ዘመን ከእነጭራሹም የዴሞክራሲና የልማት ጥያቄን ለያይቶ ማየት አይቻልም፡፡ በሐሳብ ደረጃ ሁሉንም ጐን በጎን ሳይዛነፉ እንዲመጡ ማድረግ ይቻላል ሊባል ቢችልም ከአጠቃላይ የዓለም አገሮች ሂደት አንጻር ቀደም ብለን ለማየት እንደሞከርነው ግን የዴሞክራሲ ቅድመ-ሁኔታዎች በበቂ መጠን ባልተሟሉበት ሁኔታ በተግባር ይህንን መፈጸም እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ዴሞክራሲንና ነፃ-ገበያ ሥርዓትን በአንድ ጊዜ ተቀብለናል ባልንበት በ1983 ዓ.ም በአገራችን እንዲገነባ ስለሚፈለገው ሥርዓት በተሻለ ብሔራዊ መግባባት መመካከር የሚቻልበት ዕድል ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ ቢያንስ በዚያን ወቅት የዴሞክራሲም ሆነ የነፃ-ገበያ

አተገባበር ቅደም-ተከተላችን እንዴት ይሁን? የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይችል ነበር፡፡ ኢኮኖሚውም ሆነ ዴሞክራሲው በአንድ ጊዜ በተዥጐደጐደ ሁኔታ ሳይሆን ከላይ ለማስቀመጥ በተሞከረው መልኩ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ወይም ከጥቂት ወደ አጠቃላይ እየሰፋ በሚሄድ የአተገባበር ቅደም-ተከተል ታቅዶ ሊከናወን ይችል ነበር፡፡ እንደ አገርና ሕዝብ ይህንን ማድረግ ችለን ቢሆን ኖሮም ዛሬ የምንገኝበትን ደረጃ ከዛሬ አሥር ዓመት ገደማ በፊት ልንደርስበት እንችል ነበር ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

ዞሮ ዞሮ ከአሁን በኋላ ወደኋላ ለመመለስ የምንችልበት ዕድልም ሆነ፣ መመለሱ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡ በዐሥራ ስምንት ዓመቱ ሂደት ያጣናቸው ዕድሎችና ያገኘናቸው ውጤቶች ስላሉ በዴሞክራሲውም ሆነ በኢኮኖሚው ግንባታ ሂደት በአሁኑ ወቅት የሚታዩትን የፖሊሲና የአፈጻጸም ችግሮች እየፈታን ከመጓዝ በስተቀር እስካሁን ለደረስንበት ውጤት ቅድመ-ሁኔታዎቹ አልተሟሉም ወይም ሊሟሉ ይገባ ነበር ብለን እንደገና ወደኋላ ልንመለስ አንችልም፡፡ ነገር ግን የወደፊቱ ሂደታችን የተሳካ ሆኖ ከላይ ለማስቀመጥ በተሞከረው ግምት አገራችን በኢኮኖሚና በዴሞክራሲ ግንባታው ሂደት የበለጠ ውጤታማ እንድትሆን ከተፈለገ ቢያንስ ከዚህ በላይ በተለያዩ ንዑሳን-ክፍሎች በቀረቡት ኃሣቦች ላይ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የተሻለ መግባባት ላይ ለመድረስ መሞከር ይጠበቅብናል፡፡

ይኸውም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ለአንድ ከውጭ የተቀዳ ርእዮተ- ዓለም ታማኝ መሆን የሚገባን ርእዮተ-ዓለሙ የአገራችንን መሠረታዊ ችግሮች ለማቃለል ወይም ለመፍታት እስከጠቀመን ድረስ ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ የአገርን ችግር ለመፍታት የሚያስችልን አስተሳሰብ ከየትም ይምጣ ከየት ተቀብሎ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዋናነት ግን የፖለቲካ ኃይሎች የውጫዊ ርእዮት "ቀላዋጭ" ከመሆን ይልቅ የአገራችንን ተጨባጭ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ውጤት ተኮርና ተዛማጅ /Pragmatic/ የሆነ አገር በቀል ስልት ማራመድ ይጠበቅብናል፡፡ "ኢትዮጵያዊ" የሚባል የተለየ ዴሞክራሲ መፍጠር ያለብን ባይሆንም ቢያንስ ግን ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣምና ኢትዮጵያዊ የሆነ የዴሞክራሲ የአተገባበር ስልት ሊኖረን ይገባል፡፡ ዴሞክራሲን ጨምሮ ማንኛውም በዓለም ላይ መግነን የቻለ አስተሳሰብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ገንቢ ጥያቄና ትችት ሊነሣበት የሚገባና በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ እንደወረደ ጥቅም ላይ ሊውል የሚገባው ሳይሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከነባራዊ ሁኔታችን ጋር እንዲጣጣምም ሊሞረድና ሊስተካከል የሚገባው፣ በራሳችን የአተገባበር ቅደም-ተከተል መሠረትም ታቅዶ ሊተገበር የሚገባው መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ዴሞክራሲ የሂደት ጉዳይ ከመሆኑ ጋር በተያያዘም ኢትዮጵያ ውስጥ የምንገኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዴሞክራሲን ከሰማይ እንደሚወርድ መና በአንድ ጊዜ አገራችንን አጥለቅልቋት ለማየት ያለንን ስሜታዊ ምኞት መግታት ይጠበቅብናል፡፡ ተቃዋሚዎች ዴሞክራሲ ሂደት ብቻ ሳይሆን፣ ሂደቱም በአንፃራዊነት ቀላል የማይባል ጊዜንና የተለያዩ ግብኣቶችን የሚጠይቅ መሆኑን አምነን በመቀበል፣ በአገራችን ዴሞክራሲ ላለመኖሩ መንግሥትን በብቸኝነት ተጠያቂ ማድረጋችንን አቁመን ራሳችንን ጭምር የመፍትሔው አካል ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እንደእስካሁኑ ጣታችንን በሌሎች ላይ እየቀሰርን ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው የራሳችንን ልባዊ አስተዋፅኦ በተግባር ማበርከት የማንችል ከሆነ ግን ትግላችን ከተራ የሥልጣን ጥያቄ አልፎ ለዴሞክራሲ የሚካሄድ ትግል ሊሆን አይችልም፡፡የአገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደትም እስካሁን እንደታየው በብጥብጥና በደም መፋሰስ ጭምር የታጀበና ከምርጫ 97 በኋላ እንደታየው አንድ ርምጃ ወደፊት ተራምዶ ሁለት ርምጃ ወደ ኋላ የሚመለስ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

በገዥው ፓርቲ በኩል ከሁሉም በፊት ዴሞክራሲም ሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ ሊመጣ የሚችለው "በእኔ መሪነት ብቻ ነው፣ እኔ ከሌለሁም አገሪቱ የመፈራረስ አደጋ ይገጥማታል" ከሚለው በራሱ ፀረ-ዴሞክራሲ ከሆነ ግትር አቋሙ መላቀቅና በግንባታው ሂደት የሌሎችንም የማይተካ ሚና ማወቅ ብቻ ሳይሆን በተግባር አምኖ መቀበል ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገዥው ፓርቲ ዴሞክራሲ "ሂደት" የመሆኑን ጉዳይ በተዛባ ሁኔታ ለራሱ ቡድናዊ ፍላጐት በመጠቀም የሂደቱን ፍጥነትና ዕድገት የሚያደናቅፍ ተገቢ ያልሆነ ስልት ሆን ብሎ ማራመዱን ሙሉ በሙሉ ማቆም አለበት፡፡ አገራችን ውስጥ እንኳንስ የዴሞክራሲውን ሂደት የሚያደናቅፍ ወይም የሚያዘገይ ተግባራትን ሆን ብለን እየፈጸምንና በሙሉ ብሔራዊ መግባባት፣ በሙሉ ትኩረትና ትጋት ሰርተንም የምንመኘው ደረጃ ላይ አገራችንን ለማድረስ የሚጠብቀን ፈተና ቀላልና የዋዛ ሊሆን አይችልም፡፡

በአጠቃላይ በእነዚህ በዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ዙሪያ በተነሱት ጉዳዮችና በዚህ መጽሐፍ በተለያዩ የመወያያ ርእሶች ባነሳናቸው ጉዳዮች በአገራችን ብሔራዊ መግባባት መፍጠርና አንፃራዊ የፖለቲካ ሰላምና መረጋጋት ማስፈን ከቻልን ባሰብነው ጊዜ አገራችንን እንደሌሎቹ የምንቀናባቸው አገሮች ዴሞክራሲና ኢኮኖሚያዊ ብልፅግና የሰፈነበት አገር ሆና ማየት የማንችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በዚህ ደረጃ የአገራችንን ወቅታዊ ችግሮች ጥልቀትና ስፋት መገንዘብ ተስኖን፣ በግራም በቀኝም የምንገኝ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ከእስካሁን ዓይነት የተበላሸ የፖለቲካ ባህላችን ተላቀን ወደ ዕውቅና የመስጠት፣ የመቻቻልና በጋራ አገራዊ ጉዳዮች አብሮ የመሥራት አዲስ የፖለቲካ ባህል መሸጋገር የማንችል ከሆነ ግን ኢትዮጵያ በተገቢ

ፍጥነት ያሰበችበት ልትደርስ አትችልም ብቻ ሳይሆን አገራዊ ህልውናዋ አደጋ ውስጥ አይገባም ብሎ መተማመን ያስቸግራል፡፡

### *3.3 ነፃ ገበያ እንዴትና እስከ ምን?*

የነፃ-ገበያ ሥርዓት አስተሳሰብ ከሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ጋር በተያያዘ ከየት ተነሥቶ በአሁኑ ወቅት ምን ላይ እንደደረሰ የሚያሳዩውን ታሪካዊ አመጣጥ አብዮታዊ ዴሞክራሲንና ሊበራል ዴሞክራሲን በንጽጽር ባየንበት ርእስ ላይ ስላዩነው እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ በዚህ ርእስ ላይ በጥቅሉ ቀድሞ የነበረው ገበያ በአቅርቦትና በፍላጐት ራሱን በብቃት መምራት ስለሚችል መንግሥት ሙሉ በሙሉ ከኢኮኖሚ ጉዳይ እጁን ማውጣት አለበት የሚለው የሊበራል አስተሳሰብ ከአንደኛው የዓለም ጦርነትና ከ1930ዎቹ የዓለም የኢኮኖሚ ውድቀት በኋላ እንደተቀዬረና በሂደትም መንግሥት ለዜጐች ሥራን በመፍጠር፣ ገበያን በማረጋጋት፣ የዜጐችን ማኅበራዊ ደኅንነት በመጠበቅና በአጠቃላይም በኢኮኖሚው ውስጥ የተገደበ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል የሚለው አስተሳሰብ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን አይተናል፡፡

በዓለማችን የዘመኑ የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ከሶሻል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ተለይቶ ሊታይ በማይችልበት መጠን በዚህ ደረጃ መድረሱ የማያከራክር ቢሆንም ጉዳዩን ከታዳጊ ወይም ገና ከእዝ-ኢኮኖሚ ሥርዓት ወደ ነፃ-ገበያ ሥርዓት ከሚሸጋገሩ አገሮች አንጻር ስናየው ግን ሌላ አከራካሪ ነጥብ መነሣቱ አይቀርም፡፡ ይኸውም በአደጉት አገሮች መንግሥት በኢኮኖሚ ጉዳይ በሕግ የተገደበ ጣልቃ ገብነት ሊኖረው ይችላል ወይም ይገባል ሲባል በዋናነት ከቁጥጥር /Regulation/ እና ከማኅበራዊ ደኅንነት ጋር በተያያዘ እንጂ በኢኮኖሚው ውስጥ ገብቶ ነጋዴ ወይም አምራች ከመሆን ጋር የተያያዘ ስላልሆነ በታዳጊ አገሮች ሊኖር ከሚገባው ወይም ከሚጠበቀው የመንግሥት የኢኮኖሚ ተሳትፎ ጋር የሚመጣጠን አይደለም፡፡

ምክንያቱም በአንድ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ገና ከእዝ-ኢኮኖሚ ወደ ነፃ-ገበያ የሚሸጋገርና በሚፈለገው መጠን የግል ክፍለ-ኢኮኖሚና የገበያ ውድድር ባልተፈጠረበት አገር መንግሥት የኢኮኖሚው የአሠራር ሁኔታ ላይ ቁጥጥር ከማድረግና ማኅበራዊ ደኅንነትን ከመጠበቅም በላይ በንግድና በማምረት ሂደት ውስጥ እንዲሳተፍ የሚያስገድደው አግባብ ሊኖር ስለሚችል ይህ ተሳትፎው እስከምን ድረስ ሊሆን ይገባል የሚለው ነጥብ አከራካሪ ነው፡፡ በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ መድረክ በግልጽ እንደምናየውም ጉዳዩ አከራካሪ ከሆኑ ዋና ዋና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ለመሆን ችሏል፡፡

በወቅቱ የአገራችን ሁኔታ የመንግሥት ተሳትፎ እስከምን ድረስ ሊሆን ይገባዋል? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ በዋናነት ሁለት ዓይነት አመለካከቶች አሉ ማለት ይችላል፡፡ የመጀመሪያው አመለካከት ገዥው ፓርቲና ኢዴፓን የመሰሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያራምዱት ማለትም፣ መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ በሕግ የተገደበ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ አንዳንድ የሊበራል ብቻ ሳይሆን የሶሻል ዴሞክራሲ ተከታዮች ነን የሚሉ ተቃዋሚዎች ሳይቀሩ የሚያራምዱት- ማለትም መንግሥት ሙሉ በሙሉ እጁን ከኢኮኖሚው ማውጣት አለበት በማለት የሚያራምዱት አቋም ነው፡፡ በመርህ ደረጃ ኢህአዴግና ኢዴፓ በጉዳዩ ላይ ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ቢሆንም በተግባራዊ አፈፃፀሙ ላይ ግን ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡ ይህ ልዩነት ምን እንደሆነ ከማየታችን በፊት ግን ኢህአዴግና ኢዴፓ በአንድ በኩል፣ ሌሎች ተቃዋሚዎች ደግሞ በሌላ በኩል በዚህ ጉዳይ ያላቸውን የመርህ ልዩነት ማየት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ኢህአዴግና ኢዴፓ "መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የተገደበ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል" በማለት የሚያራምዱት አቋም ከወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ከርእዮተ-ዓለም ወይም ከተለያዩ አማራጮች መካከል አንድን አማራጭ ከመምረጥ ጋር ተያይዞ መታየት የሚችል ሳይሆን አማራጭ የሌለው ምርጫ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደ ኢትዮጵያ ባለ ገና ከእዝ-ኢኮኖሚ ወደ ነፃ-የገበያ ሥርዓት የሚሸጋገር አገር፣ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ተሳትፎ አይኑረው ማለት ተገቢ ያልሆነ ብቻ ሳይሆን በተግባር ሊፈጸም የማይችል አስተሳሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም በአገራችን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በብዙ ዘርፎች ገና በቂ የገበያ ውድድር አልተጀመረም ብቻ ሳይሆን ጭራሽም የግሉ ዘርፍ መሳተፍ ያልጀመረባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች በርካታ ስለሆኑ ነው፡፡ በቴሌኮሙኒኬሽን፣ በመብራት፣ በውሃና በመሳሰሉት አገልግሎቶች የግሉ ዘርፍ ምንም ዓይነት ሚና ባልጀመረበትና በብዙ የሸቀጥ ዓይነቶች ሳይቀር የአምራችነት ሚና ባልጀመረበት ሁኔታ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ አይኑረው ቢባል ነፃ-ገበያ ይቅርና ከእነ ጭራሹም አገራዊ ኢኮኖሚ ሊኖር አይችልም፡፡

የግሉ ዘርፍ ጭራሽ ባልገባባቸው ዘርፎችም ብቻ ሳይሆን የግሉ ዘርፍ ገብቶባቸው ነገር ግን ገና በቂ የገበያ ፉክክር ባልተጀመረባቸው ዘርፎችም መንግሥትን እጅህን ሙሉ በሙሉ ከኢኮኖሚ አውጣ ብሎ መጠዬቅ አገርንም ሆነ ሕዝብን የሚጠቅም አስተሳሰብ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት የግል ሆስፒታሎችና ዩንቨርሲቲዎች መከፈት ስለጀመሩ ብቻ መንግሥት በእጁ የሚገኙትን የሕዝብ ሆስፒታሎችና ዩንቨርሲቲዎች ወደ ግል ይዞታነት ይቀየር ቢባል፣ ወይም የመብራት ኃይልና የውሃ ልማት ሥራ ዛሬውኑ ከመንግሥት እጅ ይውጣ ቢባል

የሚያስኬድ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም የግሉ ዘርፍ ገና በቂ የገበያ ፉክክር ውስጥ ባልገባበትና ሕዝቡም በግሉ ዘርፍ የሚጠዬቀውን የአገልግሎት ዋጋ ለመክፈል የሚያስችለው አቅም ገና ባልፈጠረበት ሁኔታ የግሉ ዘርፍ ይህንን ኃላፊነት ብቻውን ይወጣው ቢባል ነፃ-ገበያ መኖሩ ይቅርና አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ እነዚህን መሠረታዊ አገልግሎቶች የሚያገኝበት ዕድል አይኖረውም፡፡

በገጠር ይቅርና በአገሪቱ ዋና ከተማ ሳይቀር የስልክ፣ የመብራትና የውሃ አገልግሎት ገና በበቂ መጠን ባልተዳረሰበት ሁኔታ መንግሥት በእነዚህ የአገልግሎት ዘርፎች ያለውን ተሳትፎ ያቋርጥ ቢባል ሕዝቡ አግባብ ባልሆነ የክፍያ ጥያቄ ይሰቃያል ብቻ ሳይሆን ከእነ ጭራሹ አገልግሎቱን ሳያገኝ የሚቀርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ እንዲያውም በእኛ ዓይነቱ አገር የግሉ ዘርፍ ሊገባባቸው አቅምና ፍላጐት ባጣባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች መንግሥት በማምረትና በንግድ አገልግሎት ሳይቀር ሊገባ የሚገደድበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ስለዚህ በአንድ በኩል የግሉ ዘርፍ በበቂ መጠን ተጠናክሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ባልገባበት ሁኔታ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኀብረተሰቡን ጥቅም በአግባቡ ሊያስጠብቅ በሚችል መጠን በቂ የገበያ ፉክክር ባልተፈጠረበትና መሠረታዊ የሚባሉ መሠረተ ልማቶች በአገሪቱ በበቂ መጠን ባልተዳረሱበት ሁኔታ በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ መኖር የምርጫና የፍላጐት ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡

የመንግሥት ተሳትፎ ስህተትና አላስፈላጊ ሊሆን የሚችለው የግሉ ዘርፍ በቂ ተሳትፎና የገበያ ፉክክር ባለበት ሁኔታ መንግሥት ራሱን ተጫማሪ ተወዳዳሪ ለማድረግና ትርፍን ለማግኘት ብሎ ኢኮኖሚው ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ አገሪቱ ነፃ-ገበያን አራምዳለሁ ስላለች ብቻ መንግሥት ከሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፍ እጁን ማውጣት አለበት ተብሎ የሚቀርበው ጥያቄ ስለ አገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ከማጣት ወይም ዝም ብሎ መንግሥትን ለመቃወም ተብሎ የሚቀርብ ጥያቄ ከመሆን ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ መንግሥት እንዲያደርግ ሊጠዬቅ የሚገባው የገበያ ጉድለት በማይታይባቸው ዘርፎች ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለግሉ ዘርፍ እየለቀቀ እንዲወጣ ነው እንጂ በየትኛውም ሁኔታ መንግሥት ተሳትፎ አይኑረው ብሎ መከራከር ከኢኮኖሚ ዕውቀትም ሆነ ለአገር ከማሰብ የሚመነጭ ክርክር ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ኢህአዴግና ኢዴፓ በመርህ ደረጃ የሚጋሩት አቋም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህንን በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው አቋም ወደ ተግባር በመለወጥ ሂደት በኢህአዴግ ዙሪያ የሚታየውን የአፈጻጸም ችግር እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡፡

በዓለም ላይ የሚገኙ ሁሉም የበለፀጉ አገራት መንግሥታት ለምን "ልማታዊ መንግሥታት" ሊባሉ እንደማይችሉ ግልጽ ባይሆንም ኢህአዴግ በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ እስከምን ድረስ መሆን አለበት የሚለው ጥያቄ ላይ በተግባር የሚያራምደው አቋም ከነፃ-ገበያ አስተሳሰብ ተቃራኒ ሆኖ የሚታየው ስለ ልማታዊ መንግሥትነት ካለው የተዛባ ትርጉም ነው ማለት ይቻላል፡፡ የልማት ጥያቄ ዞሮ ዞሮ የኅብረተሰብን የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ከመፍታት ጋር ተያይዞ የሚታይ እንደ መሆኑ መጠን ልማታዊ መንግሥትነትን ከሌሎች የበለፀጉ አገሮች መንግሥታት ባህሪ ነጥሎና ታይዋንና ደቡብ ኮሪያን ከመሳሰሉ አገሮች መንግሥታት ባህሪ ጋር ብቻ አያይዞ ለማየት መሞከር በራሱ ችግር ያለው አስተሳሰብ ነው፡፡

በተለይም "ልማታዊ መንግሥትነት" በተለየ ሁኔታ ከታይዋንና ከደቡብ ኮሪያ ተሞክሮ ጋር ተያይዞ ሲቀርብ ልማታዊ መንግሥትነት በቅድሚያ ለልማት ብቻ እንጂ ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መከበር ደንታ ቢስ የመሆን ትርጉምን ያስከትላል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን በዓለማችን የልማት ጥያቄ ሲሚንቶና አሸዋ አቡክቶ ድልድይና ሕንጻ ከመሥራትም በላይ ከዴሞክራሲና ከሰብአዊ መብት መከበር ጋር በጥብቅ የተቆራኘ የሰፋ ትርጉም እየያዘ ስለመጣ ነው፡፡ ነገር ግን ታይዋንና ደቡብ ኮሪያን የመሳሰሉት አገሮች የልማት ዕድገት መሰላልን መቆናጠጥ የጀመሩት ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን በማያከብሩበት ወቅት ስለ ነበር ኢህአዴግ ስለ ልማታዊ መንግሥትነት ያለው ትርጉም ከእነዚህ አገሮች ተሞክሮ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሲቀርብ ለኢህአዴግ የልማት ጥያቄ ከዴሞክራሲና ከሰብአዊ መብት መከበር ተነጥሎ የሚታይና የልማታዊ መንግሥት ትርጉሙም ከሁሉም በላይ የልማት ዕድገትን ለማምጣት የሚጥር መንግሥት ማለት እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ኢህአዴግን በአንድ በኩል ወሳኝ የሆኑ የኢኮኖሚ ተቋማት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆን ይገባቸዋል ወደሚልና ለአገሪቱ ዕድገትም "መንግሥት የማይተካ ሚና ያለው አንቀሳቃሽ ሞተር ነው" ወደሚል አስተሳሰብ የወሰደው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የግሉ ሴክተር አገርን በልማት የማሳደግ ኃላፊነት ሊሸከም የማይችል "ኪራይ ሰብሳቢ አካል ነው" የሚል የተዛባና ከነፃ-ገበያ መርህ ጋር የሚጋጭ አስተሳሰብ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ኢህአዴግ በዚህ የተዛባ አስተሳሰቡ የግሉን ሴክተር እየከሰሰ በሌላ በኩል ግን በተዘዋዋሪ መንገድ የራሱን የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች በማቋቋም፣ በገበያ ውድድር ሊተኩ የሚችሉ የልማት ድርጅቶችን ጭምር በመንግሥት ቁጥጥር ሥር እንዲቆዩ በማድረግና ከዚያ አልፎ ከ5 ብር ጀምሮ የሚከራዩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የቀበሌና የኪራይ ቤቶች በመንግሥት

እጅ ሆነው እንዲከራዩ በማድረግ ራሱ ዋና "የኪራይ ሰብሳቢነት" ባህሪ መገለጫ ሆኗል፡፡ ኢህአዴግን በዋናነት ወደዚህ ዓይነቱ የተሳሳተ አስተሳሰብ ያስገባው ምክንያት በአገሪቱ እንዲመጣ የሚፈልገው የልማት ዕድገት የራሱን ድርጅታዊ የፖለቲካ የበላይነት ባስጠበቀ መልኩ እንዲሆን በመወሰኑና ከዚሁም ጋር በተያያዘ ከሌሎች በርካታ ለብልጽግና የበቁ የዓለም አገሮች ተሞክሮ ይልቅ ከራሱ ፍላጐት ጋር ይጣጣማሉ ብሎ ያሰባቸውን የታይዋንና የደቡብ ኮሪያን ተሞክሮዎች በተዛባ ሁኔታ ተርጉሞ ለመውሰድ በመሞከሩ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የታይዋንና የደቡብ ኮሪያ ገዥ ፓርቲዎች ልማትን የሞት የሽረት ጉዳይ አድርገው በተንቀሳቀሱበት በ1960ዎቹ አካባቢ በርግጥም ከኢህአዴግ ጋር ተመሳሳይ ድርጅታዊ ፍላጐትና ዓላማ ነበራቸው ሊባል ቢችልም ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ በወቅቱ እንደ አገርም ሆነ እንደ ሕዝብ የነበሩበት ተጨባጭ ሁኔታ ግን ከወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በብዙ መመዘኛ የሚጣጣም ስላልነበር የእነሱ ተሞክሮ ለኢህአዴግ እንጂ ለኢትዮጵያ በርግጠኛነት ይጠቅማል ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡ በወቅቱ ታይዋንና ኮሪያ በቀዝቃዛው ጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ርዳታ ከእነ አሜሪካ ያገኙ የነበሩ፣ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብትን የማክበር ቅድመ-ሁኔታ ይቀርብባቸው ያልነበሩ፣ ወደ ውጭ የሚልኩትን ምርት በአሜሪካን ገበያ እንደልባቸው የመሸጥ መብት የተሰጣቸው፣ በርካታ የአሜሪካን ኩባንያዎች ከፍተኛ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት/FDI/ ያደረጉባቸው የነበሩ፣ ጠንካራ ፀረ-ኮሚኒስት አቋም ያለውና ከሙስና የጸዳ መንግሥት የነበራቸው፣ ጠንካራ ብሔራዊ ስሜት ያለውና በጎሣና በሃይማኖት ያልተከፋፈለ ሕዝብ የነበራቸውና በአጠቃላይም በታሪካዊ አመጣጣቸውም ሆነ በአላቸው የተፈጥሮ ሀብት ዓይነት ከኢትዮጵያ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው አገሮች ስላልሆኑ እነሱን ከሌላው ዓለም በተለየ ለኢትዮጵያ ጥሩ ሞዴል አድርጐ መውሰድ ብዙም ጠቃሚ አይሆንም፡፡

የሆነ ሆኖ ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ ከመጀመሪያው የተፋጠነ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የገቡት ነፃ-ገበያን እናራምዳለን በማለት ቢሆንም የነበሩበትን ልዩ አካባቢያዊና ወቅታዊ ሁኔታ በመጠቀም በአንድ በኩል ፀረ-ኮሚኒስት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሥርዓት ይዘው ለመቆዬት ከመቻላቸውም በላይ በኢኮኖሚ ውስጥ ቀላል የማይባል ተሳትፎ ብቻ ሳይሆን ጣልቃ ገብነት ጭምር የነበራቸው አገሮች ናቸው፡፡ በተለይም የታይዋን ገዥ ፓርቲ ከመንግሥት ባለቤትነትም በተጨማሪ የራሱ የንግድ ድርጅቶች አቋቁሞ ለራሱ ድርጅታዊ ሥራ ጥቅም ላይ የሚውል ከፍተኛ ገቢ ይሰበስብ የነበረበት ሁኔታ ነበር፡፡ ኢህአዴግ እነዚህን ተሞክሮዎች እንደ በጎና ጠቃሚ ተሞክሮዎች በመውሰድ ይመስላል፣ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ሚና በሕግ ከተገደበ ተሳትፎ አልፎ የጣልቃ-ገብነት ድርሻ ያለው ሆኗል፡፡ ኢህአዴግ ቁልፍ የመንግሥት

ተቋማትን መንግሥት መቆጣጠር አለበት ብሎ ከማመኑና የግሉን ዘርፍ አገርን የማሳደግ ኃላፊነት ሊወጣ የማይችል ኪራይ ሰብሳቢ አካል አድርጐ ከማየቱ በተጨማሪ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ጣልቃ ገብነት በዋናነት በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡

የመጀመሪያው በቀድሞው ሥርዓት የመንግሥት የነበሩ የማምረቻና የማከፋፈያ የንግድ ድርጅቶችን ኢህአዴግም በተመሳሳይ ሁኔታ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚል ስም ይዞ ለመቀጠል ባሳዬው ፍላጐት ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡ ከእነዚህ የልማት ድርጅቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ በግሉ ዘርፍና በገበያ ውድድር ሊሸፈኑ የሚችሉ ሆነው እያለ ኢህአዴግ ለዐሥራ ስምንት ዓመታት በእጁ ይዞ አቆይቷቸዋል፡፡ ብዙውን ጊዜ ኢህአዴግ በዚህ የሚያቀርበው ምክንያት ድርጅቶቹ ሊሸጡ አይገባም የሚል ሳይሆን እንዲሸጡ ዝግጅት እየተደረገ ነው የሚልና ከቢሮክራሲ ውጣ ውረድ ጋር የተያያዙ ሌሎች ምክንያቶችን ነው፡፡ አሁን አሁን ደግሞ ከገበያ ዋጋ በታች የሆነ የጨረታ ውጤት በምክንያትነት ሲቀርብ ይደመጣል፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ የቱንም ያህል ምክንያት ቢደረድር ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ እነዚህን ድርጅቶች በእጁ ይዞ ስለማቆዬቱ ሊያቀርበው የሚችል አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፡፡

ኢህአዴግ እነዚህን ድርጅቶች መሸጥ አለባቸው ብሎ ከመጀመሪያው ከልቡ ወስኖ ቢሆን ኖሮ ይህንን ተፈፃሚ ለማድረግ ዐሥራ ስምንት ዓመት ይቅርና አራትና አምስት ዓመትም ከበቂ በላይ የበዛ ጊዜ ነው፡፡ የጨረታ ዋጋዎች ከገበያ ዋጋ በታች ሆኑ የሚለው ምክንያትም በነፃ-ገበያ አምናለሁ ለሚል መንግሥት አሳማኝ መልስ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም በነፃ-ገበያ አቅርቦትና ፍላጐት ዋጋን የመወሰን አቅም አላቸው ብለን እስካመን ድረስ፣ አንድ ንብረት በግልጽ ጨረታ ቀርቦ ከተሰጠው ዋጋ የበለጠ ዋጋ ያወጣል ማለት የሚቻልበት ሁኔታ የለም፡፡ እንዲያውም ብዙውን ጊዜ በጨረታ የሚወሰን ዋጋ በሰዎች ዘንድ በሚፈጠር የፉክክር መንፈስ ምክንያት ከገበያ ዋጋ በላይ እንጂ ከገበያ ዋጋ በታች የመሆን ዕድል አይኖረውም፡፡ ስለዚህ መንግሥት በእጁ የያዛቸው አንዳንድ ድርጅቶች አክሳሪ ሆነው እያለና አንዳንዶቹም ሆቴሎችን የመሰሉ ድርጅቶች እየበሰበሱ ባሉበት ሁኔታ ለዐሥራ ስምንት ዓመታት በእጁ ይዞ ማቆዬቱ በተለየ ምክንያት ሳይሆን ከግራ አመለካከቱ ጋር በተያያዘ የመንግሥትን ተሳትፎ ለመገደብ ቁርጠኛ አቋም ለመያዝ ካለመቻሉ የመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የኢህአዴግ ችግር የግሉ ዘርፍ ሊገባባቸው የሚችሉ ተቋማትን በፍጥነት ለመሸጥ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን የግሉ ዘርፍ ሊገባባቸው ያልቻለ ተቋማትም በሂደት ከእጁ እንዲወጡ የሚያስችል ጥረት ሲያደርግ አለመታየቱ ጭምር ነው፡፡ በመንግሥት እጅ ያሉና የግሉ ዘርፍ ሊገባባቸው ያልቻሉ ተቋማት በአክስዮን ሽያጭ አማካኝነት ወደ ሕዝብ (public) ንብረትነት

በከፊልና በሙሉ በሂደት የማሸጋገር አማራጭ ያለ ቢሆንም መንግሥት ይህንን ለማድረግ ሲሞክር አይታይም፡፡ አነስተኛ የሚባሉ ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ ቴሌኮምንኒኬሽንና መብራት ኃይልን የመሳሰሉ ተቋማት ጭምር ከመንግሥት እጅ በሂደት የሚወጡበት የተለያየ አማራጭ ያለ ቢሆንም መንግሥት ብዙውን ጊዜ ሲጨነቅ የሚታየው ተቋማቱን እንዴት የበለጠ አትራፊ ማድረግ እንደሚችል ነው፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ ተቋማት በግሉ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ሊሸፈኑ አለመቻላቸውን ብቻ ምክንያት በማድረግ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እጅ ተይዘው እንዲቀጥሉ ከማድረግ ይልቅ በተቋማት ውስጥ የሚሠራውን መሠረታዊ ሥራ መንግሥት ራሱ እየሠራ አገልግሎቱን ወደ ሕዝቡ የማከፋፈሉን ሥራ ቀስ በቀስ የግሉ ዘርፍ እንዲይዘው ለማድረግ የሚያስችል ርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ ነገር ግን መንግሥት በዚህ ረገድ የተሟላ ቁርጠኝነት ስለሌለው በየቤቱ መስመር የመዘርጋቱንና ቆጣሪ የመትከሉን ጥቃቅን ሥራ ሁሉ ራሱ በሞኖፖል እየሠራው ይገኛል፡፡

ሁለተኛውና የበለጠ አሳሳቢው የዚህ ችግር መገለጫ፣ ኢህአዴግ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚቆጣጠራቸው የንግድ ድርጅቶች ያሉት መሆኑ ነው፡፡ በነፃ-ገበያ ሥርዓት ውስጥ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የንግድ ድርጅቶች አቋቁሞ ለመነገድ የሚያስችለው ምንም ዓይነት አሳማኝ ምክንያት ሊኖረው አይችልም፡፡ በወቅቱ የአገሪቱ ሕግም የፖለቲካ ድርጅቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የንግድ ሥራ ሊሠሩ እንደማይችሉ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ የአገሪቱን ሕግ ለማንም ባልተሰወረ ዘዴ ሸውዶ ለማለፍ በመሞከር አንድን ድርጅት የሌላው ድርጅት ባለአክሲዮን ድርሻ በማድረግና በየድርጅቶቹ አንዳንድ የድርጅቱን የበላይ አመራር አባላት የአነስተኛ የአክሲዮን ድርሻ ባለቤት በማድረግ ያስመዘገባቸው 69 አካባቢ ከፍተኛና መካከለኛ የንግድ ድርጅቶች አሉት፡፡ ከእነዚህ የንግድ ድርጅቶች ወደ ኀምሳ ስድስቱ በህወሃት፣ አምስቱ በብአዴን፣ ሰባቱ በኦህዴድ፣ አንዱ በዴኢህዴግ የተቋቋሙ ሲሆኑ እነዚህ በተለያዩ የንግድና የማምረቻ ሥራዎች የተሰማሩ ድርጅቶች ከስድስት ዓመት በፊት በነበራቸው አቅም /1996 ላይ/ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል የሚያንቀሳቅሱ ናቸው፡፡

ኢህአዴግ እነዚህን በኢንዶውመንት ስም ያቋቋማቸውን የንግድ ድርጅቶች በተመለከተ እስካሁን የሚያቀርበው ምክንያት ማንንም ሊያሳምን የሚችል ሆኖ አያውቅም፡፡ ኢህአዴግ ሥልጣን በያዘ ሰሞን ስለ እነዚህ የንግድ ድርጅቶች መኖር ያቀርብ የነበረው ምክንያት “በትጥቅ ትግሉ ወቅት ያፈራነው ገንዘብ ስላለ ይህንን ገንዘብ የት እንጣለው?” የሚል ነበር፡፡ ይህ ምክንያት ብዙም አሳማኝ መሆን አልችል ሲል ደግሞ፣ “ድርጅቶቹ የሕዝብ ድርጅቶች ናቸው”

ማለት ተጀመረ፡፡ ይህም አላዋጣ ሲል ቆዬት ተብሎ ደግሞ “ድርጅቶቹ በኢንዶውመንት ሕግ የተቋቋሙ ሕጋዊ ድርጅቶች ስለሆኑ በነፃ-ገበያው ሥርዓት በአግባቡ መወዳደር እስከቻሉ ድረስ የሚፈጥሩት ችግር የለም” ማለት ተጀመረ፡፡

“በትግሉ ወቅት ያፈራነውን ገንዘብ የት እንጣለው?” የሚለው አባባል ቢያንስ በአንድ ምክንያት አሳማኝ አይደለም፡፡ ይኸውም በትጥቅ ትግሉ ወቅት የተገኘው አብዛኛው ገንዘብ ከደርግ ጋር በተካሄደው ጦርነት ከወቅቱ የአገሪቱ መንግሥት በምርኮ የተገኘ ገንዘብ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ መልሶ ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እንዲውል ማድረግ ሲቻል “የት እንጣለው?” ብሎ ጥያቄ ማንሣትም ሆነ መጨነቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ተገቢ ጥያቄ ባይሆንም ደርግን ለመጣል ለተዋጋንበት የደም ካሳ ያስፈልገናል ከተባለም ገንዘቡ ለንግድ ሥራ ሳይሆን በጦርነቱ ወቅት ሕይወታቸውን ላጡ ታጋዮች ቤተሰቦችና አካላቸውን ላጡ ታጋዮች ጥቅም እንዲውሉ ማድረግ ይቻል ነበር፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጅቶቹ የሕዝብ ናቸው የሚለው አባባልም አሳማኝ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ድርጅቶች በተለያዩ የፓርቲ ባለሥልጣናት የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች የአክሲዮን ድርሻ እንጂ በሕዝብ ስም የተመዘገቡ ድርጅቶች ስላልሆኑ ከሕግ አንጻር ይህንን ለማለት የሚያስችል መሠረት የለም፡፡ ሁለተኛ እነዚህ ድርጅቶች በተለየ ሁኔታ የሕዝብ ንብረት ሊሆኑ የሚችሉበት ዕድል አለ ከተባለም ድርጅቶቹ ግልጽ በሆነ አሠራር በሕዝቡ የሚተዳደሩና ከድርጅቶቹ የሚገኘው ትርፍም በትክክል ለሕዝቡ ጥቅም ብቻ ሲውል የሚታይ መሆን ነበረበት፡፡ በተግባር እየሆነ ያለው ግን ከዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ሕዝቡ በእነዚህ ድርጅቶች መጠቀም ይቅርና ድርጅቶቹ እንዴትና ለማን ጥቅም እንደሚሠሩ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ቢያንስ እነዚህ ድርጅቶች በአክሲዮን ሽያጭ አማካኝነት ሰፋ ያለ ቁጥር ያለው ሕዝብ (public) ንብረት እንዲሆኑ ሙከራ ሲያደርግ አይታይም፡፡ ጉዳዩ ኢህአዴግ እንደሚለው በአንድ ታሪካዊ አጋጣሚ በእጅ የገባን ገንዘብ የት እንጣለው? ከሚል ጭንቀት የመነጨ ችግር አለመሆኑን የሚያረጋግጠው ሌላው ምክንያት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ከፍተኛ ንብረት ያካበተው ህወሃት ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም ከድል በኂላ የተመሠረቱ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችም ጭምር በተመሳሳይ ተግባር ውስጥ እንዲሰማሩ መደረጉ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ችግሩ በሆነ ታሪካዊ አጋጣሚ የተፈጠረ ሳይሆን ሆን ተብሎና አስፈላጊነቱ ታምኖበት የሚፈጸም ተግባር መሆኑን ነው፡፡

ከእነዚህ ከኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ካላቸው የንግድ ድርጅቶችም ሆነ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች መኖር ጋር በተያያዘ ለሚነሣው ጥያቄ ኢህአዴግ በነፃ-ገበያው ሥርዓት በአግባቡ እስከተወዳደሩ ድረስ ድርጅቶቹ የሚፈጥሩት ችግር የለም በማለት የሚያቀርበው

ምክንያትም ከመሠረታዊ የነፃ-ገበያ መርህ ጋር የሚቃረን እንጂ አሳማኝ የሆነ ምክንያት አይደለም፡፡ ከመጀመሪያው በመንግሥትም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲዎች እጅ ያሉ የንግድ ድርጅቶች በነፃ-ገበያ ሥርዓት እስከተወዳደሩ ድረስ ችግር የለውም የሚል ተቀባይነት ያለው አስተሳሰብ ቢኖር ኖሮ በዓለም የኢኮኖሚ ታሪክና ቲዎሪ ውስጥ የነፃ-ገበያ የሚባል ሥርዓት ጭራሽም ባልተፈጠረ ነበር፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያው ገበያን ነፃ ለማድረግ የተፈለገው ከማንም ሳይሆን፣ ፖሊሲ አውጭና ተቆጣጣሪ መሆን ከሚገባው የፖለቲካ ባለሥልጣን ወይም ከመንግሥት ስለሆነ "በነፃ-ገበያ ሥርዓት እስከተወዳደረ ድረስ የመንግሥት ነጋዴነትም ችግር የለውም" ብሎ ማመን የነፃ-ገበያ መርህን መፃረር ብቻ ሳይሆን ከሥር ከመሠረቱ እንደመናድ የሚቆጠር ነው፡፡

ከላይ የጠቀስናቸውና መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ ተሳትፎ ሊያደርግ ይገደዳል ያልንባቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ - መንግሥት የአገሪቱ ፖሊሲ አውጭ፣ የንግድ ሥርዓቱ ተቆጣጣሪ፣ ግብርና ቀረጥ ሰብሳቢ ከመሆን አልፎ ራሱ አምራችና ነጋዴ በሆነበት አገር የነፃ-ገበያ ሥርዓት አለ ማለት አይቻልም፡፡ አትራፊ ለመሆን በማቀድ የራሱን የንግድ ድርጅቶች ያቋቋመ የፖለቲካ ኃይል በነፃ-ገበያ ሥርዓቱ በሃቅ ተወዳድሮ ሲቻል ማትረፍን፣ ሳይቻል ደግሞ መክሰርን በጸጋ ይቀበላል ብሎ ማሰብም የዋህነት ነው፡፡ በነፃ-ገበያ ሥርዓት የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ዋነኛው የለውጥና የእድገት ኃይል ተደርጐ የሚታየው ያለምክንያት ሳይሆን ፖሊሲ የማውጣትና የመቆጣጠር ሚና ሳይኖረው በአቅርቦትና በፍላጐት ሕግ ብቻ ለመገዛት የሚገደድ ክፍል በመሆኑ ነው፡፡ አንድ መንግሥት በደፈናው "እመኑኝ" በማለት መታመን የሚችልና የሚገባው ቢሆን ኖሮ ነፃ-ገበያ ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎች የመንግሥት ሥልጣንን ለመያዝ በምርጫ የሚፈራረቁበት የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓትም ባላስፈለገ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ኢህአዴግ "እመኑኝ" በማለት የሚያቀርበው መከራከሪያ በሕዝቡ ዘንድ ይበልጥ በጥርጣሬና በስጋት እንዲታይ እንጂ በጭራሽ እንዲታመን አልረዳውም፡፡

ኢህአዴግ ከላይ የጠቃቀስናቸውን የተልፈሰፈሱ ምክንያቶች እያቀረበ በኢኮኖሚው ውስጥ ነጋዴ በመሆን መቀጠሉ በነፃ-ገበያ ሥርዓት ላይ ልባዊ እምነት የሌለው መሆኑን ብቻ ሳይሆን "ኢኮኖሚውን በመቆጣጠር ፖለቲካውን መቆጣጠር" የሚል የጠነከረ እምነት ያለው መሆኑን ማሳያ ሆኗል፡፡ ይህም ጉዳይ ኢህአዴግ ስለ ነፃ-ገበያም ሆነ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ አሳቢና ተቆርቋሪ መስሎ የሚታየው የፖለቲካ የሥልጣን የበላይነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ አደጋ እስካልተፈጠረ ድረስ ብቻ እንደሆነ ብዙዎች ከልባቸው እንዲያምኑ፣ በዚህም ምክንያት

ኢህአዴግ የሚሠራቸውን በጎ ሥራዎች ጭምር በጥርጣሬ እንዲያዩና ከዚያም አልፈው በጭፍን እንዲቃወሙ የሚያስችላቸው ምክንያት ሆኖላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

በአገሪቱ ሕግ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በንግድ ሥራ ላይ መሠማራት እንደማይችል በተከለከለበት አገርና በአገሪቱ ሕግ መሠረትም ኢንዶውመንት ማለት ለትርፍ የማይሠራ በጎ አድራጐት ድርጅት መሆኑ በግልጽ በተቀመጠበት ሁኔታ ኢህአዴግ በአሳማኝ ምክንያት ሳይሆን በድርቅና እነዚህን የንግድ ድርጅቶች በእጁ ይዞ እስከቀጠለ ድረስም የቱንም ያህል ሌሎች በጎ ነገሮችን ቢሠራ የሕዝቡን የተሟላ ልባዊ እምነት ሊያገኝ ይችላል ብሎ ማመን ያስቸግራል፡፡ ኢህአዴግ የሥልጣን የበላይነቱን ተገን አድርጐ እንዲህ ዓይነት ተቋማዊ ሙስና እየፈጸመ ባለበት ሁኔታም አገሪቱ ውስጥ ሕግን ለማስከበርም ሆነ ሙስናን ለመዋጋት የሚያስችል የሞራል የበላይነት ይኖረኛል ብሎ ማሰቡም ግብዝነት ነው፡፡ እንኳንስ ራስን ለሕግና ለሥርዓት በሃቅ ተገዥ ሳያደርጉ፣ ከሰው ልጅ ባህሪ ውጭ በሆነ ተአምራዊ ሁኔታ ከስህተትና ከድክመት ሙሉ በሙሉ የፀዱ ሆኖ መገኘት ቢቻል እንኳ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነትን ማግኘት እንዲህ በዋዛ የሚቻል አይሆንም፡፡

ስለዚህ በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢ ተሳትፎ እያደረገ ነው ሊባል የሚችለው ከሁሉም በፊት በሕጉ በተቀመጠው መሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በገበያ ውስጥ ተሳትፎ እያደረጉ የሚገኙ በገዥው ፓርቲ ተዘዋዋሪ ባለቤትነት የሚታወቁ የንግድ ድርጅቶችን ሙሉ በሙሉ ከገበያ ውጭ እንዲሆኑ በማድረግ ነው፡፡ መንግሥት ይህንን ተገቢ ርምጃ መውሰድ ከቻለ በመንግሥትነቱ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ተሳትፎ በሕዝብ ዘንድ የተሻለ ተቀባይነትና እምነት ሊያገኝ ይችላል፡፡ ሕዝቡ የመንግሥት ተሳትፎ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ነው የሚል እምነት መፍጠሩ ትልቅ ትርጉምና ጥቅም ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ማናቸውም ተሳትፎ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ በአገራችን የሚገኘው የንግዱ ኅብረተሰብ ገደብ ካጣ የግለኝነትና የስግብግብነት ባህሪ እስኪላቀቅ፣ የግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ በበቂ መጠን እስኪጠናከርና የኅብረተሰቡን ጥቅም የሚያስከብር በቂ የገበያ ፉክክር እስኪፈጠር ድረስ በአገራችን ኢኮኖሚ የመንግሥት ተሳትፎ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ምትክ የሌለው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በቂ የገበያ ፉክክር ባልተፈጠረባቸው መስኮች መንግሥት በማምረትና በንግድ ሥራ ጭምር ሊሳተፍ የሚገባው ሲሆን፣ በዚያው መጠን በቂ የገበያ ፉክክር የተፈጠረባቸውን መስኮች ያለ ምንም ማቅማማት “የእናቴ መቀነት” የሚል ሰበብ አስባብ ሳይፈጥር ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ

ለቆ በመውጣት የነፃ-ገበያ ሥርዓትን በአገሪቱ ለማስፈን ቁርጠኛ አቋም መውሰዱን ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡ መንግሥት በአንድ በኩል የገበያ ክፍተቱን በአግባቡ መሙላትና በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ከቻለ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዘላቂነት አገሪቱን ለዕድገትና ለብልጽግና ማብቃት የሚችለው የግሉ መስክ መሆኑን ከአንገት ሳይሆን ካንጀት በማመን ለዘርፉ መጠናከር አስፈላጊ የሆነውን ምቹ ሁኔታ ከፈጠረ አገራችን በአጭር ጊዜ በአንፃራዊነት ወደ ተሟላ የነፃ-ገበያ ሥርዓት መግባት የማትችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡

### ***3.4 ለዘላቂ ዕድገት የሚያበቃን ምን ዓይነት የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነው?***

አንድ አገር የነፃ-ገበያ ሥርዓትን ስለተቀበለና ስለአራመደ ብቻ ባርግጠኛነት ያድጋል ማለት አይቻልም፡፡ የሚቻል ቢሆን ኖሮ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከቅኝ ግዛት ነፃ የወጡና የነፃ-ገበያ ሥርዓት ማራመድ የጀመሩ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ዛሬ በልጽገው በተገኙ ነበረ፡፡ በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲን በተቀበሉ ብቻ ሳይሆን በአምባገነናዊ አገዛዝ ሥር በሚገኙ በርካታ አገሮች ጭምር የነፃ-ገበያ ኢኮኖሚ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እያራመዱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት የተሳናቸው አገሮች የመኖራቸውን ያህል፣ በለዬለት አምባገነናዊ አገዛዝ ሥር የሚገኙ ቻይናን የመሰሉ አገሮች ደግሞ አስደናቂ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት ማሳየት ችለዋል፡፡ በርግጥም ከወቅቱ የዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ እንደምንረዳው በአምባገነናዊ አገዛዝ ሥር በሚገኝ አገር ውስጥ የነፃ-ገበያና የግል ክፍለ-ኢኮኖሚ ሊኖርም ላይኖርም የሚችልበት ዕድል ያለ ቢሆንም፣ ዕድገት ያምጣም-አያምጣም ዴሞክራሲያዊ በሆነ አገር ውስጥ ግን የግል ክፍለ-ኢኮኖሚና የነፃ-ገበያ ሥርዓት መኖሩ የግድ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ አገር ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመጣ ዋስትና የሚሆነው የነፃ-ገበያ ሥርዓት መኖሩ በራሱ ሳይሆን በነፃ-ገበያ ሥርዓቱ ማዕቀፍ ውስጥ የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት ያደረገና ከየት ተነሥቶ የት ሊደረስ እንደሚችል ግልጽ አቅጣጫ የሚያመላክት የኢኮኖሚ ስትራቴጂ መኖር ነው፡፡

ትክክለኛ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ መኖሩ አገሮችን ወደ እድገት አቅጣጫ መውሰዱ የማይቀር ቢሆንም በምን ያህል ፍጥነት ዕድገቱን ማምጣት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ በመወሰን ረገድ ግን እንደየ አገሩ ውስጣዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ብዙ ግብኣቶች የወሳኝነት ድርሻ ያላቸው መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ አንድ አገር ከሚገኝበት ፖለቲካዊ ሁኔታ በተጨማሪ ከሰብአዊና የተፈጥሮ ሀብት፣ ከመሠረተ ልማት መስፋፋት፣ ከቢዝነስ ካፒታልና ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ክሂሎት አንጻር ያለበት ደረጃ ለዕድገቱ መፋጠን የሚኖረው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡ በአሁኑ ዘመን በተሻለ ፍጥነት የማደግ ዕድል ያለ ቢሆንም ብሪታንያን የመሰሉ አገሮች ከሌላው ዓለም ቀድመው

በኢንዱስትሪ አብዮት እንዲበለጽጉ ያደረጓቸው የራሳቸው ልዩ ሁኔታዎች ነበሯቸው፡፡ ለምሳሌ ብሪታንያን ቀድማ እንድትበለጽግ ያበቃት - የፖለቲካ ነፃነትን የሚያጠናክሩ ተቋማትን መገንባትዋ፣ ለግለሰቦች ፈጠራና ለሕዝብ ነፃ እንቅስቃሴ ሰፊ ትኩረት መስጠትዋ፣ የሳይንስ ዕድገት አብዮት ማካሄዷ፣ ቀዳሚ የእንፋሎት ኃይል ተጠቃሚ መሆኗ፣ ለባህር ላይ ንግድና ለእርሻ ምርት ዕድገት ትኩረት መስጠትዋና ከሁሉም በላይ ከሌሎች ጐረቤቶችዋ በተሻለ በጠላት ላለመጠቃት የሚያስችል ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ስለነበራት ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲመጣ የሚያስችሉት ግብኣቶች ዓይነት በተወሰነ ደረጃ የተቀዬረ በመሆኑና ሁሉም አስፈላጊ የሚባል ግብኣት በሁሉም አገር የግድ ተሟልቶ መገኘት አለበት መባል ባይችልም በአንፃራዊነት አገሮች ከወቅቱ አስፈላጊ ግብኣቶች አንጻር የሚገኙበት ሁኔታ በዕድገታቸው ፍጥነት ላይ የማይናቅ ድርሻ አለው፡፡ ዕድገታቸው አዝጋሚ ከመሆኑም በላይ በከፋ የድህነት ወጥመድ (Poverty trap) ውስጥ ወድቀው የሚታዩት አብዛኛዎቹ የዓለም አገራት ድሀ የመሆናቸው ምስጢር በዋናነት ከመጥፎ የጂኦግራፊያዊ ሁኔታ፣ ከአስተዳደራዊ ውድቀት፣ ከጐታች ባህላዊ ሁኔታ፣ ከፈጠራ ድርቀት፣ ከሕዝብ ብዛትና ከመሳሰሉ ችግሮቻቸው ጋር በተያያዘ መሆኑ ተጨማሪ ምርምር የማያስፈልገው እውነታ ሆኗል፡፡

ከዚህ የምንረዳው በአገራችን ኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በሆነ ተአምር ብሔራዊ መግባባት ፈጥረው የተዋጣለት ሊባል የሚችል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ለመንደፍ ቢበቁ እንኳ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን በአገራችን በፍጥነት ማምጣት ምን ያህል አስቸጋሪና ፈታኝ እንደሚሆን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አገራችን የኋላ ቀር የእርሻ ኢኮኖሚ ጥገኛ የሆነች፣ አብዛኛው ሕዝቧ ያልተማረና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ያልሆነ፣ መልካም አስተዳደር ገና ያልሰፈነባት፣ ብዙ ጐጂ ባህሎችና አስተሳሰቦች ያሉባት፣ በውስጧም ሆነ ከጐረቤቶችዋ ጋር አስተማማኝ ሰላም ያልፈጠረች፣ በፖለቲካ ፓርቲዎቿ መካከል ብሔራዊ መግባባት ያልተፈጠረባት፣ በርካታ የዘርና የሃይማኖት ልዩነቶች ያሉባት፣ ሙሉ በሙሉ ከፖለቲካ ተጽዕኖ የጸዳ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የማይቀረጽባት፣ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እያደገ የሚገኝባትና የባህር በር የሌላት አገር መሆኗ ሲታይ ለወቅቱ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ወደፊት በአገሪቱ ወደ ሥልጣን ሊመጡ ለሚችሉ የፖለቲካ ኃይሎችም ጭምር ፈጣንና ዘላቂ ዕድገት ማምጣት ፈታኝ ጥያቄ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል፡፡

ከእነዚህ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ችግሮች በተጨማሪ ፈጣን ዕድገትን ማምጣት አስቸጋሪ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ በአሁኑ ወቅት (ችግሩን ማምለጥ የሚቻልበት ዕድል የሌለ ቢሆንም)

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ገና ጀማሪ አገር መሆናችን ነው፡፡ ብዙዎቹ በዓለማችን የሚገኙ የበለፀጉ አገሮች የእድገት መሰላልን መቆናጠጥ የቻሉት ዴሞክራሲን እና ሰብአዊ መብትን የማክበር ጉዳይ ገና ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ መቅረብ ባልጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ በተለያዩ አገሮች ተግባራዊ ተሞክሮ በግልጽ እንደታየውም የኢኮኖሚ ተኃድሶዎች በቀላሉ ተቀባይነት አግኝተው ሊተገበሩ የሚችሉት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ጀማሪ ከሆነ አገር ይልቅ አምባገነናዊ አገዛዝ ባለበት አገር ነው፡፡ ምክንያቱም በረዥም ጊዜ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ብዙውን ጊዜ ጊዜያዊ ችግር የማስከተል ባህሪ ስላላቸው ጀማሪ ዴሞክራሲ ባለበት አገር እንዲህ ዓይነቶቹ ፖሊሲዎች ለሕዝብ ተቃውሞና እምቢተኝነት የተጋለጡ የመሆን ዕድላቸው ሰፊ በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ ከዚህ በላይ ለመጥቀስ ከተሞከሩት የአገሪቱ ውስጣዊና አካባቢያዊ ነባራዊ ችግሮችና በተጨማሪም የወቅቱ መንግሥት ለፖለቲካ የበላይነቱ ሲል ሆን ብሎ ከሚፈጥራቸው የፖሊሲ ስህተቶች አኳያ ሲታይ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ብዙ ጦም አዳሪዎች ያሉ ቢሆንም በአንፃራዊነት እየታየ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት “የባሰ አታምጣ” የሚያስብል እንጂ የከረረ ምሬት ሊያስከትል የሚገባው ነው ማለት አይቻልም፡፡ በርግጥ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንኳንስ የኢኮኖሚ ዕድገትና አንድም ሊመሰገን የሚገባው የልማት ሥራ በአገሪቱ ተሠርቷል ብለው ለማመን የማይፈልጉ ቢሆንም ለማንኛ ምክንያታዊ አስተሳሰብ ላለው ሰው በአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩ አከራካሪ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሚሆነው እየታየ ያለው ዕድገት ዘላቂና ፍትሐዊ የመሆን-ያለመሆኑ ጉዳይ ነው እንጂ ዓይንም ሆነ ኅሊና ላለው ጤናማ ሰው በአገራችን ዕድገት የመኖሩ ጉዳይ አጠራጣሪ አይደለም፡፡

ብዙ ሰዎች ዕድገት የለም ለሚለው የፖለቲካ አቋማቸው መከራከሪያ አድርገው ከሚያቀርባቸው የተለያዩ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ በመንግሥት የሚቀርበው የቁጥር መረጃ (Data) ሊታመን አይችልም የሚል ነው፡፡ በርግጥም በእወደድ ባይነት አለቆቹን ለማስደሰትና የተሻለ ሥልጣን ለማግኘት ድንጋይ ሲፈነቅል የሚውል በርካታ ካድሬ ባለበት አገር የቁጥር መረጃዎች ተዛብተው ወይም ተጋነው የሚቀርቡበት ዕድል መኖሩ ባያጠራጥርም፣ ዞሮ ዞሮ የቁጥሩ መዛባትም ሆነ መጋነን የዕድገቱን መጠን በተወሰነ ደረጃ ሊጨምረው ይችላል እንጂ ዕድገት መኖሩን ሊያስቀረው አይችልም፡፡ መንግሥት “ኢኮኖሚው ከዐሥር በመቶ በላይ አድጓል” በሚልበትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችም በየዓመቱ ኢኮኖሚው ቢያንስ ከስምንት በመቶ በላይ ማደጉን እየመሰከሩ ባሉበት ሁኔታ መንግሥት የሚያቀርበው የቁጥር መረጃ በሲሶ ወይም

በአንድ ሦስተኛ መጠን ተጋኗል ቢባል እንኳ ቢያንስ ከሰባት በመቶ ያላነሰ የኢኮኖሚ ዕድገት በአገሪቱ አለ ማለት ይቻላል፡፡

ሌላው በአገሪቱ ዕድገት የለም ለሚለው የአንዳንድ ተቃዋሚዎች አቋም መከራከሪያ ሆኖ የሚቀርበው ነጥብ በአገሪቱ የዋጋ ንረት መከሰቱና በረኀብ የሚሞት ሰው የመኖሩ ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን የኢኮኖሚ ዕድገት ባለበት አገር ሁሉ የዋጋ ንረት (Inflation) አይከሰትም የሚል የኢኮኖሚ ቲዎሪ የሌለ ሲሆን በአንድ አገር ኢኮኖሚ ማደግ በጀመረ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በተአምር ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ ጠግቦ ያድራል ወይም ሁሉም ዜጋ በአንድ ጊዜ የዕድገቱ ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ ስለማይጠበቅም እነዚህ ምክንያቶች የዕድገት አለመኖር ማረጋገጫ ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የኢኮኖሚ ዕድገት ባለበትም ሁኔታ የዋጋ ግሽበት በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት የሚችል ሲሆን ገና ማደግ የጀመረ የአንድ አገር ኢኮኖሚም ወዲያው የእያንዳንዱን ዜጋ ኀዳ ሊያሟላ ስለማይችል ለተወሰነ ጊዜ በረኀብ የሚሞት፣ ለስደት የሚዳረግ፣ ለሥራ አጥነት የሚጋለጥ፣ በኑሮ ውድነትና በመጠለያ እጦት የሚሰቃይ የኀብረተሰብ ክፍል ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ ኢኮኖሚ ገና ማደግ በጀመረበት ወቅት ሁሉንም የኀብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአንድ ጊዜ ጠራርጎ እንደሚያስወግድ አድርጐ በማሰብ "የኢኮኖሚ ዕድገት የለም" እየተባለ የሚቀርበው ደካማ ክርክር ዞሮ ዞሮ የጭፍን ተቃዋሚነት መገለጫ ከመሆን ያለፈ ትርጉም የለውም፡፡

የቁጥር መረጃውን መጠራጠር ቢቻል እንኳ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት ስለመኖሩ ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ዕውቀትና ምርምር ሳያስፈልግ በዓይን አይቶ ለመመስከር የሚያስችሉ በርካታ መረጃዎች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሌላውን ትተን ባለፉት አምስት ዓመታት በአገሪቱ የስሚንቶ ፍጆታ ከዐሥር እጥፍ በላይ ማደጉን ስናይ ምን ያህል አገሪቱ በመሠረተ ልማት ግንባታ እመርታ ላይ መሆኗን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ሌላ ውስብስብ የኢኮኖሚ ትንተና ውስጥ መግባት ሳያስፈልግም ባለፉት ስድስት ዓመታት የአገሪቱ ዓመታዊ በጀት ከ7.3 ቢሊዮን ወደ 64.5 ቢሊዮን ብር ማደጉ ሲታይ ሃቁን ደፍሮ ለመቀበል ለማይተናነቀው ለማንኛውም ሰው በአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት የመኖሩ በቂ ማሳያ ይሆናል፡፡ ይህ በስድስት ዓመት ውስጥ የታዬው ዓመታዊ የበጀት ዕድገት ወደ 900% ያደገ መሆኑ ሲታይ ይህ መጠን በአገሪቱ ከተከሰተው የዋጋ ግሽበት ጋር ተቀናንሶም በአገሪቱ ቀላል የማይባል የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን አጠራጣሪ ባልሆነ ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡

በአገሪቱ ዕድገት መኖሩን መጠራጠር ባይቻልም የሚታየውን ዕድገት በገዥው ፓርቲ ልዩ ትጋትና የፖሊሲ ጥራት ብቻ እንደመጣ አድርጐ በመቁጠር የሚታየው ከልክ ያለፈ መመጻደቅም

በዚያው መጠን ሊተች የሚገባው ስህተት ነው፡፡ ኢህአዴግ በራሱ አገዛዝ ሥር ሆና አገሪቱ እንድታድግ የሚፈልግ ከመሆኑ አንጻር በርካታ ጠቃሚና ትክክለኛ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን ያወጣ መሆኑና እነዚህ ፖሊሲዎችም ለወቅቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የራሳቸው በጎ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑ የማይካድ ቢሆንም፣ ኢህአዴግ ለሥልጣን የበላይነቱ ሲል የሚያራምዳቸው ለአገር ጠቃሚ ያልሆኑ ፖሊሲዎችም በዚያው መጠን ዘላቂ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዳይመጣ እንቅፋት መሆናቸውን መካድ አይቻልም፡፡ በቅድሚያ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚገባው ቁምነገር ከአጠቃላይ የአገር የምርት ዕድገት (GDP) ጋር በተያያዘ አገራችን ውስጥ ዕድገት መታዬቱ በኢህአዴግ ዘመን የተጀመረ አዲስ ነገር አለመሆኑን ነው፡፡ ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ ያለውን የኢኮኖሚ ማህደር (Record) መለስ ብለን ብናገላብጠው ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነትና የዝናብ እጥረት በሌለባቸው ወቅቶች አብዛኛውን ጊዜ የኢኮኖሚ እድገት ይኖራል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የፖሊሲ ለውጦች ለተገኘው ውጤት አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ ተከታታይ ዕድገት ባሳዬችበት ያለፈው አምስት ዓመት የታዬው ዕድገት በአንፃራዊነት በአገሪቱ ጦርነት ያልነበረና በቂ ዝናብ የነበረ በመሆኑ ምክንያት ጭምር የመጣ እንጂ በአስተማማኝ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ምክንያት የመጣ ዕድገት ነው ሊባል አይችልም፡፡ ለኢኮኖሚው እድገት መምጣት ተጨማሪ ምክንያት የሆኑት እንደ የኮንስትራክሽን ዘርፉ ዕድገት ያሉት ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ እንዳሉ ሆነው አያድርገውና የአንድ ክረምት ዝናብ ብቻ በአገራችን ቀጥ ቢል የሚወራለት የኢኮኖሚ ዕድገት ሁሉ በአንድ ጊዜ ወደ ዜሮ ሊመለስ እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም፡፡

ዘመናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በአጠቃላይ የአገር ምርት (GDP) መጨመር ወይም በዜጐች የገቢ መጨመር ብቻ የሚመጣ ሳይሆን በዋናነት በኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ለውጥ ማለትም - በከተሞች ዕድገት፣ በኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ መስፋፋት፣ በሕዝብ እንቅስቃሴ መጨመር፣ በቤተሰብ መዋቅራዊ ለውጥ፣ በሕዝብ ቁጥር መመጠን፣ በሴቶች ሚና ማደግ፣ በትምህርትና በፈጠራ ክሂሎት መስፋፋት እና በተመሳሳይ መዋቅራዊ ለውጦች የሚመጣ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በግብርናው ዘርፍ ውስጥ የተወሰኑ መዋቅራዊ ለውጦች የመፈጠር ምልክቶች እየታዩ ነው ሊባል ቢችልም አጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ግን በአገራችን ገና እየመጣ አይደለም፡፡

አገራችን ዛሬም እንደትናንቱ የኋላ ቀር ግብርና ጥገኛ ስትሆን ግብርናችንም ሙሉ በሙሉ የዝናብ ጥገኛ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ዛሬም እንደ ትናንቱ ከ84% ያላነሰ ሕዝባችን ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የግብርና ሥራ የሚተዳደር ሲሆን የዛኑ ያህል ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚኖረው በገጠር ነው፡፡

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገትን ገና ያልተቆናጠጥን ሲሆን የሕዝባችን ቁጥርም ከኢኮኖሚ ዕድገታችን በማይመጣጠን መጠን እያደገ ይገኛል፡፡ በተወሰነ ደረጃ የገበሬውን ምርታማነት በማሳደግ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎትን በማዳረስና መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት ረገድ አበረታች ሥራዎች እየተከናወኑ ቢሆንም መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር (Structural Transformation) በአገራችን ገና በበቂ መጠን መምጣት ግን አልጀመረም፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የአንድ ክረምት ዝናብ መቅረት እንዳልነበረ ሊያደርገው የሚችል ኢኮኖሚ ውስጥ ሆነን ዕድገት አመጣን እያልን መመጻደቁ የትም ሊያደርሰን አይችልም፡፡ እየመጣ ያለው ዕድገት በቁጥጥራችን ሥር ያለና ዘላቂነት ያለው መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ለተወሰኑ ዓመታት 10% ብቻ ሳይሆን 20% ኢኮኖሚያችን ማደግ ቢችል እንኳን ከጊዜያዊ ፕሮፓጋንዳ ያለፈ ዘለቄታዊ ትርጉም ሊኖረው አይችልም፡፡ በጥሩ ጊዜያዊ አጋጣሚዎች ለአጭር ጊዜ በሁለት አኀዝ ከማደግ ይልቅ ኢኮኖሚያችን በዘላቂነት በ6% ወይም በ7% ቢያድግ ይመረጣል፡፡ ዛሬ የዓለም የዕድገት ቁንጮ ለመሆን የበቁት የእነ አሜሪካ የዕድገት ምስጢር ፈጣን ዕድገት የማስመዝገብ ጉዳይ ሳይሆን ቋሚ ዕድገት (Sustainable Growth) ማምጣት መቻል ነው፡፡

አሜሪካ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1820 እስከ 2000፣ ማለትም ለ180 ዓመት ያሳዬችውን የኢኮኖሚ ዕድገት ስናይ ኢኮኖሚዋ በዓመት በአማካይ መጠን 1.7% ብቻ ነው ያደገው፡፡ ነገር ግን ዕድገትዋ ከትክክለኛ መዋቅራዊ ሽግግር የመነጨ ተከታታይና ቀጣይ ዕድገት ስለነበረ አሜሪካንን ለብልጽግና ሊያበቃት ችሏል፡፡ በዚህ የ180 ዓመት ጉዞ የአሜሪካን የኢኮኖሚ ዕድገት የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ከ25 እጥፍ በላይ ያሳደገው ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱ ዜጋ የነፍስ ወከፍ ገቢም ከ1200 ዶላር ወደ 30,000 ዶላር ማደግ ችሏል፡፡ እኛ እጅግ ወደኋላ የቀረን ከመሆናችን አንጻር ፈጣን ዕድገት ማስመዝገብ ለህልውናችን የግድ አስፈላጊ መሆኑ የማያጠያይቅ ቢሆንም ዕድገቱ ቀጣይና ተከታታይ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በአንድም ሆነ በሁለት አኀዝ ብናድግ ዞሮ ዞሮ አጠቃላይ ውጤቱ የትም አያደርሰንም፡፡ ስለዚህ በአገራችን ቀጣይና ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲመጣ ካስፈለገ ወሳኙ ጉዳይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መፍጠር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ከፍተኛ እንቅፋት የሆነው አገሪቱ የምትከተለው እርሻ መር የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ በአገራችን በዋናነት የሚገኘው ሀብት መሬትና የሰው ጉልበት በመሆኑ ይህንን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም በአገራችን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማምጣት የሚቻለው እርሻ መር የሆነና ገጠርንና አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በመከተል ነው የሚል አቋም

ያራምዳል፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የኢኮኖሚ ምሁራን ደግሞ የአገሪቱን ኢኮኖሚ የመምራት ሚና ሊኖረው የሚገባው እርሻ ሳይሆን ኢንዱስትሪ ነው የሚል አቋም ሲያራምዱ ይደመጣሉ፡፡ በሌሎች ጉዳዮች እንደሚታየው ሁሉ በዚህም ጉዳይ ላይ የሚነሣውን ክርክር አስቸጋሪ የሚያደርገው በሁለት ጫፎች ላይ የተንጠለጠለ ክርክር መሆኑ ነው፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል የአገራችን የእርሻ ኢኮኖሚ እጅግ ኋላቀርና የሕዝቡን ሆድ ለመሙላት ያላስቻለ መሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአገራችን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት የኢኮኖሚ ዘርፎች ገና ከዜሮ እየተነሱ ያሉና እንዳሉ የማይቆጠሩ ከመሆናቸው አንጻር ሲታይ አንዱን የኢኮኖሚ መስክ መሪ፣ ሌላውን ደግሞ ተመሪ ለማድረግ የሚደረገውን ክርክር ጉንጭ አልፋ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም የአገራችን የኢኮኖሚ ዘርፎች ሁሉም ደካማና በራሳቸው መቆም የቻሉ ካለመሆናቸው አንጻር እንኳን መሪና ተመሪ ሆነው ይቅርና እርስ በርሳቸው ተደጋግፈውና ተመጋግበው አገር ለማሳደግም ብዙ ፈተና የሚጠብቃቸው ናቸው፡፡

በየትኛውም አማራጭ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ፈታኝ ሁኔታዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዘርፎች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈውና ተመጋግበው የአገርን ኢኮኖሚ እንዲያሳድጉ ከማድረግ ይልቅ አንዱን መሪ፣ ሌላውን ተመሪ የማድረግ አማራጭ ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል የአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ብቻ ሳይሆን የአለፉት ሃምሣ ዓመታት ልምዶቻችን በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ በንጉሡ ዘመን ከ1950 ዓ.ም. እስከ 1965 ዓ.ም. የቆዩ ሦስት የአምስት ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅዶች የነበሩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በተለይም ሦስተኛውና የመጨረሻው አገራዊ መሪ ዕቅድ በዋናነት በግብርና ላይ ትኩረት ያደረገ ነበረ፡፡ የጭላሎ ግብርና ልማት፣ የወላይታ ግብርና ልማት፣ የአድአ ወረዳ ልማት፣ የታች አዲያቦና ሀድጊት ልማት፣ የደቡብ ክልላዊ ልማትና የሁመራ ግብርና ልማት ፕሮጀክቶች ተግባራዊ የተደረጉት በዚህ አገራዊ መሪ ዕቅድ መሠረት ነበር፡፡ የእነዚህ ፕሮጀክቶች ዋና ዋና ዓላማዎች በሰብልና በእንስሳት ምርት ላይ ምርምር ማካሄድ፣ ምርታማ የእርሻ አሠራርን መፍጠር፣ የተፈተሹ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካይነት ማሰራጨት፣ የእርሻ ሥራ ብድርና የገበያ አገልግሎት ማቅረብ፣ መጋቢ መንገዶችንና የገጠር ውሃ አቅርቦት የመሳሰሉ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን መሥራት፣ የአፈር ጥበቃ ማካሄድና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣ አርብቶ አደሮችን ማስፈርና ዘላቂ ኑሮ እንዲመሠርቱ ማስቻል የሚሉ ቢሆኑም የሚጠበቀውን ውጤት ሳያመጡ ቀርተዋል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በደርግ ዘመንም በየአምስት ዓመቱ የሚተገበር የአሥር ዓመት አገራዊ መሪ ዕቅድ ወጥቶ ወደ ሰባት የሚደርሱ የአካባቢ ልማት ፕሮግራሞች ተግባራዊ የተደረጉ

ቢሆንም የታሰበላቸውን ውጤት ሳያመጡ ቀርተዋል። በአጠቃላይ በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ በአንዳንድ መስኮች ላይ መጠነኛ መሻሻል ያሳዩ ፕሮጀክቶች ቢኖሩም የግብርና ልማትን መሪና መሠረት በማድረግ አገሪቱን ወደ ዘላቂ ልማት ለማሸጋገር የተደረጉት ጥረቶች በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች ጭምር ውጤታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል። የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ስያሜው ለዩት ብሎ "ግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪ (ADLI)" ይባል እንጂ በመሠታዊ ዓላማዎቹና ይዘቶቹ ካለፉት መንግሥታት ሙከራዎች ብዙም የተለዩ ናቸው ማለት አይቻልም። የኢህአዴግ የግብርና መር ስትራቴጂ ዋና ዓላማዎች በምግብ እህል ራስን መቻል፣ የሥነ-ምህዳር መጉዳትን መከላከል፣ የአገሪቱን የግብርና ምርት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ ማድረግና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህ ዓላማዎች በሙሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአለፉት ሥርዓቶች ተሞክረው ውጤታማ ሳይሆኑ የቀሩ ናቸው።

እነዚህ በግብርና ዙሪያ የተደረጉ ጥረቶች የሚጠበቅባቸውን ውጤት ሳያመጡ የቀሩ ቢሆንም የግብርና ጉዳይ ተስፋ ተቆርጦ ሊተው የሚችል ወይም የሚገባው ጉዳይ ነው ማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያን በመሰለ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የግብርና ጥገኛ በሆነበትና ከ84% ያላነሰ ሕዝብ አርሶአደር በሆነበት አገር ለግብርና ትኩረት መስጠት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታም ጭምር ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያን በመሰለ የአርሶ አደር አገር የግብርናውን መስክ ለአፍታም ቢሆን ዘንግቶ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ አገር የማስተዳደርን ጉዳይ ማሰብ አይቻልም። አርሶ አደሩ በአሁኑ ወቅት ከግብርና ውጭ ሕይወቱን የሚደጉምበት ምንም ዓይነት አማራጭ በአጠገቡ ስለሌለው የግብርናው ዘርፍ ለአፍታ ቢዘነጋ በአገሪቱ ሊከሰት የሚችለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ቀላል አይሆንም።

ነገር ግን ለግብርናው መስክ የቱንም ያህል ትኩረት ብንሰጥ በመጨረሻ ግብርና በምግብ እህል ራሳችንን ከማስቻል አልፎ ወደ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግና ሊያስገባን አይችልም። ሌላውን የእህል ሰብል ምርት ትተን ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣውን የቡና ምርትን በምሳሌነት ብናይ ግብርና በወቅቱ የዓለማችን የኢኮኖሚ ውድድር ምን ያህል ኋላ ቀርና አዋጭ ያልሆነ ሴክተር መሆኑን ለመረዳት እንችላለን። በአሁኑ ወቅት በአገራችን በቡና ምርት ላይ ይሳተፋል ተብሎ የሚታመነው በቀላሉ ከ15 ሚሊየን የበለጠ ሕዝብ ነው። ይህ ሁሉ ሕዝብ ተሳትፎ አድርጐ በዓመት የሚመረተው የቡና መጠን በአማካይ 320 ቶን አካባቢ ሲሆን ይህ የቡና መጠን በዓለም ገበያ ተሸጦ የሚያስገኘው ገቢም በአማካይ 400 ሚሊየን ዶላር አካባቢ ነው። ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ለማዳበሪያ፣ ለዘር፣ ለመፈልፈያ፣ ለጆንያና ለማጓጓዥ የሚወጣውን

ወጭ ቀናንሰን ቀሪውን ገንዘብ ለ15 ሚሊየን አርሶ አደር ብናከፋፍለው ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚደርሰው ገንዘብ ከዕለት ጉርስ አልፎ ኑሮውን ሊያሻሽልበት የሚችል አይደለም፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ቡናን በፋብሪካ ፕሮሰስ አድርጐ በካፍቴሪያ አገልግሎት መልክ ለገበያ የሚያቀርበው ስታር-ባክስ የሚባለው ኩባንያ ግን በየዓመቱ በቢሊዬን የሚቆጠር ዶላር በማግኘት በአሜሪካን የገበያ ልውውጥ /stock exchange/ ውስጥ የማይናቅ ድርሻ ያለው ግዙፍ ድርጅት ለመሆን በቅቷል፡፡ በዚህ ኩባንያ ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞችም በነፍስ ወከፍ በየወሩ ከ1500 ዶላር ያላነሰ ገቢ ያገኛሉ፡፡ ይህን ጉዳይ ከውጭ ንግድ አንጻር /balance of trade/ ለማየት ስንሞክርም አንድ ዘመናዊ ቶዮታ የመስክ መኪና ወደ አገራችን ለማስገባት በመቶዎች በሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ልፋት የተመረተ ከ1000 ኩንታል ያላነሰ የቡና ምርት ወደ ውጭ መላክ አለብን ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ገበያ አንድ የመስክ አዲስ ቶዮታ(v8) ለመግዛት ሁለት ሚሊየን አንድ መቶ ሺህ ብር ገደማ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት የውጭ ንግዳችንም የግብርና ጥገኛ በመሆኑ አገራችን ከውጭ የምታስገባው ዕቃ ወደ ውጭ ከምትልከው በገንዘብ መጠን ከሦስት እጥፍ በላይ ሲሆን ልዩነቱ በቶን ክብደት ይሰላ ቢባል ግን ወደ ውጭ የምንልከው ወደ ውስጥ ከምናስገባው ከ40 እጥፍ በላይ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ከሌሎች የአደጉ አገሮችም የዕድገት ሂደት በሚገባ እንደምንረዳው የግብርና ዕድገት በምግብ እህል ራስን ከማስቻልና ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ደጋፊና አጋዥ ከመሆን አልፎ በራሱ አገርን ወደ ብልጽግና የማሸጋገር ሚና ተጫውቶ አያውቅም፡፡ ለአንድ አገር ዕድገት ግብርና በራሱ ምትክ የሌለው ሚና ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአለፉት ሁለትና ሦስት መቶ ዓመታት በየዘመናቸው ወደ ብልጽግናው ጐራ የተቀላቀሉ አገሮች በዋናነት የኢንዱስትሪና የአገልግሎት የኢኮኖሚ ዘርፉ እንጂ ግብርና ምኞታቸውን ዕውን አድርጐላቸው አያውቅም፡፡

በረዥም ጊዜ አዝጋሚ ሂደት ያደጉትን አገሮች ትተን ባለፉት ሠላሳና አርባ ዓመታት በዕድገት መሰላል ላይ መንጠላጠል የቻሉትና ኢህአዴግም ጭምር በአርአያነት የሚጠቅሳቸው የኤዥያ አገሮች የዕድገት ምስጢራቸው ግብርና ሲሆን አልታየም፡፡ በግብርናው መስክ "አረንጓዴው ዘመቻ" የሚባል ታዋቂ እንቅስቃሴ ያደረገችውን አገር ህንድን በቀዳሚ ምሳሌነት ለማየት ብንሞክር፣ ህንድ በ1970ዎቹ ለአሥር ዓመታት የአረንጓዴውን ዘመቻ አካሂዳ በምግብ እህል እራሷን ቻለች እንጂ በግብርና አማካይነት ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ግን አልቻለችም፡፡ ፈጣን ዕድገት ማምጣት ተስኗት ስትንፏቀቅ የኖረችው ህንድ ወደ ዕድገት መሰላል

መንጠላጠል የበቃችው እ.ኤ.አ ከ1991 በኋላ ከፍተኛ የገበያ ተኃድሶ በማድረግ ኢኮኖሚዋ ከተማን መሠረት ባደረገ የማኒፋክቸሪንግና የአገልግሎት ዘርፍ እንዲመራ ካደረገች በኋላ ነው፡፡ ለህንድ ዕድገት አረንጓዴው ዘመቻ የራሱ የማይናቅ አስተዋጽኦ የነበረው ቢሆንም በዋናነት ግን ለህንድ ዕድገት ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪና ሌሎች የኢንዱስትሪ መስኮች ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት የዓለም አስገራሚ ምሳሌ በመሆን የምትጠቀሰውና ከኢህአዴግ አፍም የማትለዬው ቻይናም በዚህ ዓለምን ባስገረመ ፍጥነት ማደግ የጀመረችው ለረዥም ጊዜ ስታካሂደው በኖረችው የባህልና የግብርና አብዮት ሳይሆን እ.ኤ.አ ከ1979 ጀምሮ ከፍተኛ የገበያ ተኃድሶ በማካሄዷና እራሷን ለዓለም ገበያ ክፍት ካደረገች በኋላ ነው፡፡ ለቻይና ዕድገት ዋና ምስጢርም ግብርና ሳይሆን ባላት ርካሽ የሰው ጉልበት ምክንያት ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትና የቴክኖሎጂ ፍሰት ወደ አገሯ ማስገባት በመቻልዋ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በ1980 ሃያ ቢሊዮን ዶላር ብቻ የነበረው የቻይና ኤክስፖርት በአሁኑ ወቅት ከ400 ቢሊዮን ዶላር በላይ ለመሆን በቅቷል፡፡ የቻይና ዋናው የዕድገት ምስጢር ከዚሁ ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት ከማግኘቷና ከውጭ ንግድ ዕድገቷ ጋር በተያያዘ የአገር ውስጥ የጥቃቅንና የአነስተኛ የዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪዋን በከፍተኛ መጠን ማስፋፋት በመቻሏ ነው፡፡ የጥቃቅንና የአነስተኛ ዕደ-ጥበብ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ የመቋቋሚያ ካፒታል የማይጠይቅ፣ የውጭ ምንዛሪ ፍላጐቱ መጠነኛ የሆነ፣ የአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን በሰፊው የሚጠቀምና ከፍተኛ የሥራ ዕድል የሚፈጥር የኢኮኖሚ ዘርፍ በመሆኑ ምክንያት ለቻይና ቀጣይነት ያለው ፈጣን ዕድገት ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡

ኢህአዴግ በዕድገት አርአያነት በየመድረኩና በየመጣጥፎቹ ደጋግሞ የሚገልፃቸውን ደቡብ ኮሪያንና ታይዋንን ብናይም ለዕድገት የበቁት ሩዝና ቡና ሸጠው ወይም በዋናነት በግብርና ኢኮኖሚ አይደለም፡፡ ሁለቱ አገሮች ከእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በብዙ ጉዳዮች የተለዩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ ዕድገት መሰላል መንጠላጠል የቻሉበት ሁኔታም ከእኛ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ብቻ ሳይሆን የሚቀራረብም አይደለም፡፡ ሁለቱ አገሮች በቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ወቅት በየአካባቢያቸው ካሉ የሶሻሊዝም ሥርዓት አራማጅ አገሮች ተነጥለው ከምዕራቡ ዓለም ጋር መቆም የቻሉ አገሮች ስለነበሩ ለዕድገት ያበቃቸው አንዱ ምክንያት ከምዕራቡ ዓለም ያገኙት የነበረው ከፍተኛ የገንዘብ ርዳታና የገበያ ዕድል ነበር፡፡

ደቡብ ኮሪያ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ትኩረቷን በዋናነት በኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ያደረገች አገር ስትሆን ለሦስት ዐሥርት ዓመታት ባደረገችው ጥረትም በጨርቃጨርቅ፣ በታሸጉ

ምግቦች፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በአውቶሞቢል፣ በኬሚካል፣ በሴራሚክስ እና በተለያዩ የፍጆታ ዕቃዎች ምርት ባሳዬችው እመርታ ነው ወደ ዕድገት ጐራ ለመቀላቀል የበቃችው፡፡ የታይዋን የዕድገት ሂደትም ከደቡብ ኮሪያ ብዙም የተለየ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ታይዋን ቀደም ሲል በእርሻ ምርት ረገድ በሩዝ፣ በስንዴ፣ በሸንኮራአገዳና በስኳር ድንች ጥሩ ምርት የነበራት አገር ብትሆንም ወደ ዕድገት መሰላል መንጠላጠል የቻለችው ግን ከ1970ዎቹ ጀምሮ ትኩረትዋን ከግብርና ይልቅ በዋናነት በኢንዱስትሪ ላይ ማድረግ ከጀመረች በኋላ ነው፡፡ ታይዋን ለቀላል ኢንዱስትሪዎች መስፋፋትና ለኤክስፖርት ዕድገት ልዩ ትኩረት ሰጥታ ማደግ የቻለች አገር ስትሆን በተለይም በኤሌክትሮኒክስ ምርት ትልቅ እመርታ የፈጠረች አገር ነች፡፡ ከኤሌክትሮኒክስ ምርት በተጨማሪም በኬሚካል፣ በተሽከርካሪ ሞተር፣ በተለያዩ ማሽነሪዎችና በአገልግሎት ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ለውጥ በማምጣት ማደግ የቻለች አገር ነች፡፡

የእርሻ ኢኮኖሚ በእነዚህ ሁሉ አገሮች የዕድገት ሂደት የራሱን የማይተካ ሚና የተጫወተ መሆኑ ባይካድም የእርሻ ኢኮኖሚ በምግብ ምርት ራስን ከማስቻልና ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ከመደገፍ አልፎ በዋናነት የዕድገት መወጣጫ መሰላል ሆኖ ግን አያውቅም፡፡ በአጠቃላይም ከኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ አብዛኛዎቹ የዓለም አገሮች ከዕድገት ወደ ዕድገት እየተሸጋገሩ የመጡበትን ደረጃ ስናይ የእርሻ ምርት ዕድገት እጅግ ዘግይቶ የመጣ ክስተት ነው፡፡ የመጀመሪያው የዓለማችን የዕድገት ደረጃ ከብረት፣ ከጨርቃጨርቅና ከተለያዩ የከፍተኛ ደረጃ የፋብሪካ ምርቶች ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን፤ ሁለተኛው የዓለማችን የዕድገት ደረጃ ከባቡር፣ ከቴሌግራፍ፣ ከመርከብ፣ ከዓለም አቀፍ ንግድ፣ ከስዊዝ ካናልና የፓናማ ካናል መገንባትና ከመሳሰሉ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ጋር ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ ሦስተኛው የዓለማችን የዕድገት ደረጃ በዋናነት ከኤሌክትሪክ ኃይልና ከተለያዩ የትራንስፖርትና መገናኛ መሣሪያዎች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን የእርሻ ምርት ለአገር ኢኮኖሚ የተሻለ አስተዋጽኦ ማበርከት የቻለው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ናይትሮጂንን መሠረት ያደረገ ማዳበሪያ ለምግብ ምርት መጠቀም ከተጀመረ በኋላ ነው፡፡

ዞሮ ዞሮ ከማዳበሪያ መፈጠር በፊትም ሆነ በኋላ የእርሻ ኢኮኖሚ የሕዝብ ቀለብና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ተጨማሪ ግብኣትና አጋዥ ከመሆን አልፎ በራሱ አገሮችን ለዕድገት አብቅቶ አያውቅም፡፡ በእኛም አገር ለእርሻው ኢኮኖሚ የቱንም ያህል ትኩረት ሰጥተን ብንሠራ የመጨረሻ ውጤቱ በምግብ እህል ራሳችንን ከማስቻልና ለሌሎች ሴክተሮች አጋዥ ከመሆን አልፎ ለሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያበቃን አይችልም የምንለው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ በብዙ ያደጉ አገሮች ከአጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚ የእርሻ ድርሻ ዝቅተኛ ሆኖ የምናገኘውና

በተለይም በእርሻ ላይ የሚሰማራው የሰው ኃይል በአማካይ ከ5 እና ከ6% በላይ ሆኖ የማናገኘው ያለምክንያት ሳይሆን የእርሻ ምርት የቱንም ያህል ቢያድግ በአገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡

እንዲያውም በቅርብ ዓመታት የምግብ ምርት ዋጋ በዓለም ደረጃ የመጨመር አዝማሚያ ከማሳዬቱ በፊት አንዳንድ ብሪታንያን በመሰሉ የአውሮፓ አገሮች ገበሬዎቻቸው ብዙ ምርት እንዲያመርቱ ሳይሆን እንዳያመርቱ የገንዘብ ድጐማ ይሰጡ የነበሩት ያለምክንያት ሳይሆን የግብርና ምርት ተሸጦ ከሚያወጣው ዋጋ በላይ ለትራንስፖርትና ለመጋዘን ኪራይ የሚወጣበት ወጪ የበለጠ ሆኖ ስለሚገኝና ከውጭ ተገዝቶ ቢገባ የበለጠ የሚረክስ ስለሆነ ነው፡፡ በተጋነነ ሁኔታም ቢሆን አንዳንድ አገሮች የእህል ምርትን ወደ ውቅያኖስ እንደሚደፉ የምንሰማው እህል ሕዝብን መቀለብ ከቻለ በኋላ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ያለው ፋይዳ ብዙም ትርጉም የሌለው በመሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም የእህል ምርት የቱንም ያህል ቢያድግ ወሳኝ የሆነ የፍላጐት መጨመርን ሊያስከትል ስለማያችል፣ በተበጣጠሰ መሬት ላይ የሚገኝ የእህል ምርት እድገትም ከፍተኛ የካፒታል ክምችት መፍጠር ስለማይችልና የማምረት አቅሙን በማሳደግ ደረጃ የሚኖረው ሚና በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር አንፃር ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያመጣ የሚችል አይደለም፡፡ የሮስቶቭ ሞዴል በመባል በሚታወቀው የኢኮኖሚ አስተሳሰብ መሠረትን የአንድ አገር ኢኮኖሚ ለረዥም ዘመን ረግቶ ከኖረበት ጥንታዊና ልማዳዊ ደረጃ ተላቆ እንደ አውሮፕላን ተሽከሙብኩቦ ምድር ለቆ መነሣትና (take off) ምጥቀት ማሳየት የሚችለው ያኑ የኖረበትን የግብርና ኢኮኖሚ ይዞ በመቀጠል ሳይሆን ኢንደስትሪንና አገልግሎትን ለመሳሰሉት አዳዲስ ዘርፎች አዲስ ትኩረት በመስጠት ነው፡፡

በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ የእርሻ ኢኮኖሚ እንኳንስ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን መርቶ ወደ ዕድገት ሊያደርሰንና በምግብ እህልም ራሳችንን እንድንችል ካለማድረጉም በላይ ከምጽዋት ልመና አላድነን ብሎ ተቸግረናል፡፡ በምግብ እህል ራሳችንን እስከምንችልና እርሻ ለሌሎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎችም የሚገባውን አስተዋጽኦ ማበርከት እስከሚችል ድረስ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠውና የበለጠ ርብርብ ሊደረግበት የሚገባ ቢሆንም የአገራችን እርሻ በዚህ ደረጃ ለሚጠበቅበት ውጤት እንዲበቃ ለማድረግም በአገራችን ያሉት እንቅፋቶች ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ የአገራችን መሬት ከረዥም ዘመን አገልግሎት ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ደረጃ የተራቆተና ለምነቱን ያጣ መሆኑ፣ የአገራችን ግብርና ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መጠን የዝናብ ጥገኛ መሆኑ፣ በከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ምክንያት የገበሬው የመሬት ይዞታ በጣም ትንሽና የተበጣጠሰ መሆኑ፣ የአገራችን ገበሬዎች የመሬት የባለቤትነት ዋስትና የሌላቸው

በመሆኑ ምክንያት በይዞታቸው ሥር በሚገኘው መሬት ላይ ዘላቂ እንክብካቤ ማድረግ የማይችሉ መሆኑ፣ ለምርት ዕድገት የምንጠቀምባቸው የግብርና ቴክኖሎጂዎችና ግብኣቶች ሙሉ በሙሉ ከውጭ የሚመጡና ውድ መሆናቸው ከሌሎች አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ችግሮቻችን ጋር ተዳምረው የእርሻ ምርት ዕድገታችንን ፈታኝና ውጣ ውረድ የበዛበት እንዲሆን አድርገውታል፡፡

ስለዚህ በዚህ ሁሉ ችግር የተከበበው የአገራችን ግብርና ውጤታማ ሆኖ በቅድሚያ የምግብ ምጽዋት ከመለመን ነፃ አውጥቶን ከዚያም ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎቻችንን በመምራት ለዕድገት ያበቃናል ብሎ መጠበቅ በቀላሉ የሚቻል አይሆንም፡፡ የሚቻል ቢሆን ኖሮ የቀድሞዎቹ ሥርዓቶች በመስኩ የደከሙበትን ጊዜ ሳይጨምር ኢህአዴግ ለግብርና ከፍተኛውን ትኩረት ሰጥቶ የሠራበት ያለፈው ዐሥራ ስምንት ዓመት ቢያንስ ተጨባጭ የዕድገት ወይም የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ምልክት በአገራችን ለማሳየት የሚያንስ ጊዜ አልነበረም፡፡ ከመዋቅራዊ ሽግግር አኳያ ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በአገራችን የተገኘውን ውጤት ለማየት ብንሞክር ኢህአዴግ በ1983 ዓ.ም. አገሪቱን ሲረከብ በግብርና የሚተዳደረውና በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ቁጥር 85% የነበረ ሲሆን ይህ ቁጥር ከዐሥራ ስምንት ዓመት ጉዞ በኋላ ዝቅ ማለት የቻለው ወደ 83.7% ነው፡፡ ግብርናችን 97% የዝናብ ጥገኛ ከመሆኑ ምንም የተለወጠ ነገር የሌለ ሲሆን ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ከመጠቀም ባለፈ በኋላ ቀር የአስተራረስ ዘዴአችን ላይም የተደረገ ምንም ዓይነት ተጨባጭ ለውጥ የለም፡፡

ከዐሥራ ስምንት ዓመት የግብርና አብዮት በኋላ አሁንም የአገራችን ኢኮኖሚ በዋናነት የግብርና ጥገኛ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን የውጭ ንግዳችንም ከግብርና መላቀቅ ባለመቻሉ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ነዳጅን ከመግዛት ብዙም ያለፈ መጠን ሊኖረው አልቻለም፡፡ በኢህአዴግ ዘመን የአገሪቱ ኢኮኖሚ በተወሰነ ደረጃ መንቀሳቀስና ለውጥ ማሳየት የጀመረው ባለፉት አምስት ዓመታት ሲሆን ይህም ለውጥ በዋናነት የመጣው በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከመጣው ከፍተኛ ዕድገት ጋር ተያይዞ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢህአዴግ ከራሱ የውስጥ የተኃድሶ እንቅስቃሴ በኋላ “ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ” የሚለውን መዝሙሩን በአዋጅም ባይሆን በተግባር ለወጥ- አድርጐ ለከተሞች ዕድገትና ለመሠረተ ልማት ግንባታ ትኩረት ባይሰጥ ኖሮ አሁን የታዬው አንፃራዊ ዕድገት ሊመጣ ባልቻለ ነበር፡፡

ግብርናው የቱንም ያህል ብቻውን ቢያድግ ከአገራዊ ኢኮኖሚ አንጻር ትርጉሙ ዝቅተኛ መሆኑን ከዐሥር ዓመት በፊት በአገራችን ከፍተኛ የእህል ምርት መገኘት በቻለበት ወቅት በግልጽ ታይቷል፡፡ በዚያን ወቅት በከተሞችና በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዙሪያ የነበረው እንቅስቃሴ እንዳሁኑ የተነቃቃበት ሁኔታ ላይ ስላልነበረ ገበሬው አንድ ኩንታል በቆሎ በከተማ

ሦላሳ ብር፣ በገጠር ደግሞ እስከ ሃያ ብር ድረስ ለመሸጥ በመገደዱ ለተጨማሪ ምርት የማይተጋበት አደጋ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የገበሬውን ምርት በበቂ ሁኔታ ሊሸምት የሚችል የኅብረተሰብ ክፍል በሌሎች ኢንቨስትመንቶችና በተለይም በኮንስትራክሽን ዘርፉ መፈጠር ስለቻለ የገበሬው ምርት አብዛኛው የከተማ ኗሪና የመንግሥት ሠራተኛ አቅም ሊሸከመው በማይችል መጠን ውድ ዋጋ ማውጣት ችሏል፡፡

ከዚህ የምንረዳው በኢኮኖሚው ውስጥ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችን የማነቃቃት አቅም ያለው ግብርና መሆኑን ሳይሆን ሌሎቹ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪን የመሳሰሉት ዘርፎች ምን ያህል የግብርናውን ዘርፍ የማነቃቃትና የማሳደግ አቅም ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ግብርናው የምግብ ብቻ ሳይሆን የጥሬ ዕቃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል የሚችለው ባቀድሚያ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ሲጠናከርና የጥሬ ዕቃ ፍላጐት ሲኖረው ነው እንጂ የግብርናው ምርት ማደጉ በራሱ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ሊፈጥረው አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን እየታየ ያለው የኮንስትራክሽን ዘርፍ ዕድገት ባንድ በኩል፣ ከኤክስፖርትና ከፍጆታ ዕቃ ምርት ጋር የተያያዙ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት ደግሞ በሌላ በኩል የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ከቻለ ግብርናው በእነዚህ ዘርፎች አማካይነት የሚፈጠረውን ፍላጐት ለማሟላት ሲል ማደጉ የግድ አይቀርም፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ግብርናው ከምርት ብዛትና ጥራት አንጻር ማደጉ እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በዚያው መጠን ከፍተኛ የሰው ኃይል መቅጠር ስለሚችል በግብርናው ዘርፍ የተሰማራው የሰው ኃይል ቁጥር በፍጥነት እየቀነሰ ይመጣል፡፡ ብዙ አርሶ አደሮችና የአርሶ አደር ልጆች ከግብርና ውጭ በሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ የመሥራት ዕድል ስለሚያገኙ በዚያው መጠን በገጠር የሚኖረው ሕዝብ እየቀነሰና እያንዳንዱ አርሶ አደር ቤተሰብ ሊያለማው የሚችለው መሬት የሰፋ የሚሆንበት ዕድል ይፈጠራል፡፡ የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ግብኣቶችን የመጠቀምና ዘመናዊ የአመራረት ዘዴ መጠቀምም በዚያው መጠን እያደገ ስለሚመጣ በሂደት የምርት መትረፍረፍና መርከስ እየተፈጠረ ይመጣል፡፡ መላውን ሕዝብ የሚቀልቡና ለፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃ የሚያቀርቡትም በሌሎች ያደጉ አገሮች እንደምናየው ብዙ ማምረት የሚችሉ፣ ግን በቁጥር ጥቂት አርሶ አደሮች እየሆኑ ይመጣሉ፡፡

አብዛኛው ሕዝብ የከተማ ነዋሪና የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፍ ተቀጣሪ እየሆነ ሲመጣም በዚያው መጠን የወሊድ መጠን እየቀነሰ፣ የቁጠባ ባህል እያደገ፣ የፈጠራ አቅምና ቴክኖሎጂን የመጠቀም ዕድል እየሰፋ ይመጣል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መዋቅራዊ ሽግግር ሲፈጠርና አገሪቱ ከግብርና ዘርፍ ጥገኝነት ወደ ኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ ጥገኝነት ስትሸጋገር ነው በአገራችን ዘላቂነትና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ተፈጠረ ብለን መመካት የምንችለው፡፡ ይህንን

በበቂ ሁኔታ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ ለግብርናና ለገጠሩ የአገሪቱ ክፍል ከሌሎቹ ዘርፎች የተለየና የበለጠ ትኩረት በመስጠት ሳይሆን ሁሉም ዘርፎች ማለትም ግብርናው፣ ኢንዱስትሪውና አገልግሎት ዘርፉ ተመጣጣኝና ተገቢ ትኩረት አግኝተው ርስ በርስ ተደጋግፈውና ተመጋግበው እንዲያድጉ በማድረግ ነው፡፡ በአገራችን አስተማማኝ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት የሚቻለው የኢኮኖሚ ዘርፎቹን የግድ አንዱን መሪ ሌላውን ተመሪ በማድረግ ሳይሆን አንዱ ሌላውን ቆሞ ለመጠበቅ በማይገደድበት ሁኔታ ተደጋግፈው እንዲያድጉ የሚያደርግ ሁሉን አቀፍ ስትራቴጂ በማራመድ ነው፡፡ በተለይም ግብርናው የመሪነት ሚና ተጫውቶ ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች ያሳድጋል ብሎ መጠበቅ ከፈረሱ ጋሪው ዓይነት አስተሳሰብ ነው፡፡ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኙበት ሁኔታ ግብርና የቱንም ያህል ተመንድጎ ቢያድግ ከረሃብ እንጂ ከአጠቃላይ ድህነት አላቆ ለብልፅግና ሊያበቃን አይችልም፡፡ እስካሁንም ከእርሻ ኢኮኖሚ ያገኘነው ጥቅም ድህነትንና ተደጋጋሚ ረሃብን በቋሚነት ቀጣይ ማድረግ እንጂ ብልፅግናን ማግኘት ሲሆን አልታየም፡፡ ግብርና እንኳንስ አጠቃላይ የአገሪቱን የኑሮ ደረጃ ሊቀይርና ራሱንም ትርጉም ባለው መጠን መለወጥ አልቻለም፡፡ የዛሬው ግብርናችን የዛሬ ዐሥር ሺህ ዓመታት ገደማ የያዘውን መዋቅራዊ ቅርፅና ይዘት (ከአደን ወደ እርሻ የተቀየረበት) ዛሬም ይዞ እንደቀጠለ ይገኛል፡፡

እንዲያውም የወቅቱ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዕድገት በአሁኑ ወቅት በአገራችን በጎ ጅምር መሆኑን በምሳሌነት በመጥቀስ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ያለ ኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉ ዕድገት ግብርናው ቢያድግም ባያድግም ትርጉም ያለው ሚና በኢኮኖሚው ውስጥ መጫወት የሚችልበት ዕድል የለውም፡፡ ስለዚህ የአገራችን የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ገጠሩን ብቻ ሳይሆን ከተማውን፤ ገበሬውን ብቻ ሳይሆን ነጋዴውን- ወዝአደሩን- ምሁራኑንና የመንግሥት ሠራተኛውን፤ ግብርናውን ብቻ ሳይሆን ኢንዱስትሪውንና አገልግሎት ዘርፉን ጭምር ማዕከል ያደረገ የተቀናጀና ሁሉን አቀፍ ስትራቴጂ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ለግብርናው ትኩረት ሰጥቼ ሠርቻለሁ ቢልም አገራችን በምግብ እህል ራሷን መቻል ይቅርና ገና ከረሀብም (famine) መላቀቅ አልቻለችም፡፡ ይህ እየሆነ ያለው ግብርናው በበቂ ሁኔታ ባለማደጉም ብቻ ሳይሆን ከግብርናው የምርት ዕድገት ባላነሰ ወይም በላይ በልቶ ማደር ያለበት የሕዝብ ቁጥራችን በዚያው መጠን እያደገ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን ወደፊትም የሚቀጥል የሕዝብ ዕድገት ሌሎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች የበለጠ ትኩረት አግኝተው በፍጥነት እስካላደጉ ድረስ ግብርና ብቻውን ተሸክሞት ሊቀጥል አይችልም፡፡

በአሁኑ ወቅት በገጠር ልማት ረገድ ኢህአዴግ በአንፃራዊነት አበረታች ተግባር እያከናወነ ነው ሊባል ቢችልም የገጠር ልማቱን ቀጣይና ዘላቂ ለማድረግ በርካታ ጉዳዮች ገና ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል በአገሪቱ የገጠር ክፍል የዕደ-ጥበብ ሥራዎችን በማስፋፋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በገጠር አካባቢ የሚገኙትን የአገሪቱን ከተሞች የኢንዱስትሪ ማዕከላት በማድረግ በእርሻ ሥራ ላይ የተሰማራውን ሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነትና መጠን እንዲቀንስ ማድረግ ይገባል፡፡ የመስኖ ልማትን በከፍተኛ መጠን በማስፋፋት፣ የአፈር ለምነትን በመንከባከብ፣ የተለያዩ የምርት ግብኣቶችን ለገበሬው በማቅረብ፣ መሠረተ-ልማትን በማስፋፋት፣ ተጨማሪ መሬት እንዲለማ በማድረግ፣ የወሊድ መጠንን በመቀነስ፣ የቁጠባ ባህልን በማሳደግ፣ ከአገሪቱ የተፈጥሮ ኃብት ሥርጭት ጋር የሚመጣጠን የሕዝብ አሰፋፈርን በማመቻቸት፣ የእንስሳት ሀብት ምርታማነትን በማሳደግ፣ የአደጋ ጊዜ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሠራርን በማጠናከር - የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የግብርናው ምርታማነት ማደግ ይገባዋል ሲባልም የአርሶ አደሩ ሕዝብ ቁጥር እንዲቀንስ ለማድረግና በአሁኑ ወቅት በአማካይ ግማሽ ሄክታር የሆነው የአርሶ አደሩ የመሬት ይዞታ ቢያንስ ወደ ሁለት ሄክታር ከፍ እንዲል በማድረግና አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ በዓመት እስከ ሦስት ጊዜ የሚያመርትበትን ሁኔታ በማመቻቸት በቂ ዝናብ ቢኖርም ባይኖርም የግብርናው ዘርፍ በአስተማማኝ ከ7% በላይ ዓመታዊ ዕድገት እንዲኖረው ማድረግ ማለት ነው፡፡ ግብርናው በውስጡ መሠረታዊ መዋቅራዊ ሽግግር ፈጥሯል ሊባል የሚችለውም በዋናነት ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ አገሪቱን ከምግብ ምጽዋት ልመና ማላቀቅ ሲችል፣ ከእንዲህ ዓይነቱ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የምርት ሂደት ወጥቶም የአገሪቱን ኢንዱስትሪ በጥሬ እቃ ምንጭነት በመደገፍና የአገሪቱን የውጭ ንግድ በማሳደግ ረገድ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መጫወት ሲጀምር ነው፡፡

የአገራችን አርሶ አደር በአንድ በኩል ይዞታው በጣም ትናንሽና የተበጣጠሰ መሬት በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሚያካሂደው ግብርና ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መጠን የዝናብ ጥገኛ በመሆኑ በትክክል ቢታሰብና ቢደመር በዓመት ውስጥ ከኀምሳ ቀናት በላይ ሙሉ ጊዜውንና ጉልበቱን የሚጠይቅ ሥራ ይሠራል ለማለት አይቻልም፡፡ ይህንን በዓመት ውስጥ ከሦስት መቶ የሥራ ቀናት በላይ ባይተዋር የሆነ ከፍተኛ ትርፍ የሰው ጉልበት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው በግብርና ውስጥ ብቻ መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ሳይሆን በዋናነት ከፍተኛ የሥራ ዕድል ፈጣሪ የሆኑትን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በፍጥነት በማስፋፋት ነው፡፡ በአገራችን 63% የሚሆነው አርሶአደር በይዞታነት የሚጠቀምበት የመሬት

መጠን አንድ ሄክታርና ከአንድ ሄክታር ያነሰ በመሆኑ፣ የአገራችን አርሶአደር አይደለም ቀርቶ በዚህ የመሬት መጠን ከሦስት ሄክታር ባነሰ የመሬት መጠን ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች ለማሳደግ የሚያስችል ካፒታል ማፍራትም ሆነ የአገሪቱን ሕዝብ የምግብ ፍጆታ በበቂ መጠን መሸፈን አይቻልም፡፡ ከግብርና ጋር በተያያዘ ያለን የውጭ ንግድም በዚያው መጠን መሠረታዊ መዋቅራዊ ሽግግር ያስፈልገዋል፡፡ የግብርናን ወይም የተፈጥሮ ሀብት ውጤትን በጥሬው ወደ ውጭ መላክ በተዘዋዋሪ መንገድ የብዙ ዜጎቻችንን የኑሮ ደረጃ ሊያሻሽል የሚችልን የሥራ ዕድል ለውጭ ዜጎች አሳልፎ መስጠት ስለሚሆን በከፊልም ሆነ በሙሉ ተለውጠውና እሴት ተጨምሮባቸው እንዲላኩ ሊደረግ ይገባል፡፡

በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር መፍጠር አስፈላጊና በራሱ ምትክ የለሽ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መዋቅራዊ ሽግግርን በአገራዊ ኢኮኖሚ ደረጃ ከማምጣትና ዘላቂ ልማትን ከማረጋገጥ አኳያ ግን ከሁሉም በላይ ትልቁን ኃላፊነት ሊሸከም የሚችለው የኢንዱስትሪው ክፍለ-ኢኮኖሚ ነው፡፡ በዓለማችን የዕድገት ታሪክ በግልጽና በተደጋጋሚ እንደታየው ኢንዱስትሪ በባህሪው ጠቅላላ አገራዊ ኢኮኖሚን የማንቀሳቀስና የተሳሰረ ዘላቂ ሽግግርን የማምጣት አቅም ያለው ዘርፍ ነው፡፡ አንድ አገር የዕድገት መሰላልን በአግባቡ ለመቆናጠጥ ከፈለገ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታም ነው፡፡ ኢንዱስትሪው የሚጠበቅበትን ያህል ተጠናክሮ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ሌሎችን ጐትቶ የማሳደግ ሚና እንዲጫወት ለማድረግም በእኛ አገር ደረጃ ገና በርካታ ፈርጀ ብዙ ጥረቶችን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

የኢንዱስትሪ ልማታችን እንዲጠናከር ባህላዊና ኋላቀር ከሆነው ግብርናችን በተጨማሪ የማዕድን፣ የኮንስትራክሽን፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ኢኮኖሚያችን ወደ ዘመናዊ አደረጃጀትና አሠራር መሸጋገር ይኖርበታል፡፡ የአገራችን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ዋና ዓላማና ግብ ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ትርጉም ያለው የኑሮ መሻሻልና ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት በአገሪቱ ማረጋገጥ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህንንም በብቃት ተግባራዊ ለማድረግ በአገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመሠረተ አግሮ ኢንዱስትሪን የሚያስፋፋ፣ ኤክስፖርትን በጥራትና በዓይነት ማሳደግ የሚችል፣ የሰው ጉልበት ተጠቃሚ የሆነ፣ በቂ የግብርና ግብአቶችን ማምረት የሚችል፣ ከፍተኛ የቴክኒክ ዕውቀት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት የሚችል፣ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን መተካት የሚችል፣ በአጠቃላይም ሌሎቹን የኢኮኖሚ ዘርፎች በብቃት ማስተሳሰር የሚችል ሁለገብ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ሊገነባ ይገባል፡፡ የአንድ አገር ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ዕድገት ዘላቂነቱ የሚሰምረው ሳይንሳዊ የፈጠራ ብቃት ሲጠናከርና የሕዝቡ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ዳብሮ

የኢኮኖሚ ግብኣቶችን በብቃት የመጠቀም አቅሙ ሲጠናከር ስለሆነ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ረገድም ያለንበት ወደ ዜሮ የተጠጋ ደረጃ እንዲሻሻል ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይገባል።

በዚህ ረገድ መንግሥትና የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚኖራቸው የማይተካ ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ የውጭ ርዳታ ግኝትንና ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከአገሪቱ ዜጎችና ተወላጆች የሚላከውን የገንዘብ (Remittance) መጠን ማጠናከር አስፈላጊ ይሆናል። ከአገሪቱ የአገልግሎት ዘርፍ ጋር በተያያዘም የንግድና የቱሪዝም እንቅስቃሴን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ያስፈልጋል። በአምራቹና በሸማቹ ሕዝብ፣ በአገልግሎት ሰጪውና በተጠቃሚው ሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ምቹና ቀልጣፋ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይም ከአገሪቱ የንግድ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥን፣ የግብርና የታክስ አወሳሰንን፣ የገበያ መረጃ ልውውጥንና አቅርቦትን፣ የደረጃ ምደባና የጥራት ቁጥጥርን፣ የሕገ-ወጥ ንግድ ቁጥጥርን፣ የንግድ ማዕከላት ማስፋፋትን በተመለከተ የተጠናከረ ሥራ በመሥራት የንግድ እንቅስቃሴን ቀልጣፋ ማድረግ የሚያስችል ፈርጀ ብዙ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። አሁን ከምንገኝበት የዕድገት ደረጃ አንጻር በቴክኖሎጂ የመጠቀም ብቃት ያለው የሰው ኃይል፣ በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ ሽቀጥና አገልግሎት፣ ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሠረተ ልማትና መልካም አስተዳደር በበቂ ጥራትና መጠን ከመፍጠር አኳያ ማከናወን የሚጠበቅብን ተግባር ገና ብዙ ድካምና ትግል የሚጠይቅ ነው።

ባለፉት ሦስትና አራት ዐሥርት ዓመታት ከከፋ ድህነት ተነስተው በፍጥነት ማደግ የቻሉ ቻይናን፣ ቬትናምን፣ ማሌዥያን፣ ታይዋንን፣ ደቡብ ኮሪያን፣ ሆንግኮንግንና ሲንጋፖርን የመሳሰሉ የኤዥያ አገሮች ወደ ዕድገት መሰላል መንጠላጠል የቻሉት ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በማራመድ ወይም አንዱን መሪ ሌላውን ተመሪ በማድረግ ሳይሆን ለሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች እንደየተጨባጭ ሁኔታቸው ተገቢና ተመጣጣኝ የሆነ ትኩረት በመስጠት ነው። የእኛ አገር የውስጥ ሁኔታ የቱንም ያህል የራሱ ልዩ ባህሪ ያለው ቢሆንም ከሌላው ዓለም ሁሉ በተለየ ተአምር እንፈጥራለን ካላልን በስተቀር ገጠርንና ግብርናን ማዕከል ባደረገ ስትራቴጂ ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት የምናመጣበት ዕድል አይኖርም።

ኢኮኖሚን በማሳደግ ረገድ ብቁ የኢኮኖሚ አስተዳደር፣ በቂ የመሬት አቅርቦትና የመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ በቂ የልማት ማበረታቻ፣ የንብረት የባለቤትነት ዋስትና ነፃ የፍትህ ሥርዓት፣ በአጠቃላይም የተመቻቸ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ መኖሩ የግድ አስፈላጊ ቢሆንም ሰላምና አስተማማኝ የፖለቲካ መረጋጋት በሌለበት አገር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እውን ሊሆን አይችልም። በዚህ መጽሐፍ ሌላ ክፍል ላይ ለማየት እንደሞከርነው የአገራችን የሰላምና

የፖለቲካ መረጋጋት ጉዳይ ገና በቋፍ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የቱንም ያህል ጥሩ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ብንነድፍ፣ የቱንም ያህል በልማት ሥራ ላይ ውጤት ለማምጣት ተግተን ብንሠራ በአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ብሔራዊ መግባባት ካልተፈጠረና አስተማማኝ የፖለቲካ መረጋጋት ካልነገሠ በስተቀር ዘላቂ ዕድገቱ ቀድሞውንም አይገኝም ብቻ ሳይሆን በሃያ እና ሠላሳ ዓመታት ጉዞ የተገኘ የኢኮኖሚ ዕድገትም በአጭር ጊዜ የሰላም ዕጦት እንዳልነበረ የሚሆንበት አደጋ ሊፈጠር ይችላል፡፡ የበለጠ ጉዳዩን አሳሳቢ የሚያደርገው የኢኮኖሚ ዕድገት ባልመጣበትና የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ባልተሻሻለበት ሁኔታ የሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት እጦት የበለጠ እየተባባሰ የሚሄድ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ከአጠቃላይ የአገራችን ህልውና አንጻር የልማትና የፖለቲካ መረጋጋት ጉዳይም አንዱ ሌላውን ይቅደም ወይም ይከተል በማይባልበት ደረጃ አብረው መምጣት ያለባቸው ቁምነገሮች ናቸው፡፡

ከሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት ጋር ተያይዞም በአንድ አገር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት በሕዝቡ ውስጥ ጠንካራና ከፍተኛ ብሔራዊ ስሜትን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ የተለያዩ የሕዝብ መብቶች በተሟላ ሁኔታ መከበር ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕዝቡ ስለአንድነቱና ስለአገሩ ያለው ፍቅር ካልተጠናከረ በስተቀር አንድ ኢኮኖሚያዊ ማኅበረሰብ በቀላሉ መፍጠር አይቻልም፡፡ በአሁኑ ወቅት እንደሚታየው ከአንድነታችን በላይ ለልዩነቶቻችን የበለጠ ትኩረት የምንሰጥ ከሆነና እይታችን በአካባቢያዊ ጉዳዮችም አልፎ አገራዊ ሁኔታዎች ላይ ማተኮር የማይችል ከሆነ በሚፈለገው መጠን አገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ብሔራዊ ስሜትና ጉልበት ሊኖረን አይችልም፡፡ ሌላው ለአፍታም ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ሙስና ነው፡፡ የአገርን ጥሪት እንደነቀዝ ከሥር ከሥሩ የሚቆረጥም ሙስና ባለበት አገር ዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ቀላል አይሆንም፡፡ ሙስናን የሚጸየፍ ትውልድ ባልተፈጠረበትና አንዳንዱም ዜጋ ልጁን በሙስና ለከበረ ሰው አጋብቶ ለመጠቀም ጥረት ሲያደርግ በሚታይበት አገር ሙስና ከፍተኛ የዕድገት እንቅፋት ሆኖ መቀጠሉ የማያጠራጥር ስለሆነ በራሱ ከፍተኛ ትግልን የሚጠይቅ ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቃቀሱት አስቸጋሪ ሁኔታዎች (challenges) መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ከአጠቃላይ የኢኮኖሚ አስተሳሰብም አንጻር በአገራችን የሚታዩት በጎ ጅምሮችም ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ይኸውም ፡- ከሞላ ጎደል ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ የተለያዩ ፖሊሲዎች መውጣታቸው፣ በቢ.ፒ.አር /BPR/ አማካይነት የአገሪቱ ቢሮክራሲ ግልጽና ቀልጣፋ የአሠራር ሂደት እንዲኖረው ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣ ትምህርትን ለዜጐች በማዳረስና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ ሥራ መሠራቱ፣ የጤና ተቋማትን

በማስፋፋትና ወባንና ኤች.አይ.ቪ. ኤድስን የመሳሰሉ ወረርሽኞችን በመከላከል ረገድ የማይናቁ ሥራዎች መሠራታቸው፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችን በመገንባትና በማስፋፋት ረገድ በአገሪቱ ከፍተኛ እመርታ ማሳየት መቻሉ፣ ለአርሶ አደሩ ሕዝብ የተለያዩ የምርት ግብኣቶችንና የብድር አገልግሎቶችን ማቅረብ መቻሉ፣ በከተሞች አካባቢ በቤቶች ግንባታና በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት መሰጠቱ፣ በተወሰነ ደረጃ ወደ ውጭ የምንልካቸው ምርቶች በዓይነትና በመጠን መጨመራቸው፣ የግል ባንኮችና የኢንሹራንስ ኩባንያዎች እንዲስፋፉ መደረጋቸው፣ አገሪቱ በአንፃራዊነት ጠንካራ የሚባል የገንዘብ አጠቃቀም ፖሊሲና አሠራር ያላት መሆኑ፣ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ የአገራችን ዲፕሎማሲ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ትኩረት መስጠት መጀመሩ፣ ከጐረቤት አገሮች ጋር በአንዳንድ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንኙነት ለመፍጠር ሙከራ እየተደረገ መሆኑ፣ በቅርቡም የግብርና ምርት የመገበያያ ማዕከል መቋቋሙና በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ግድቦች መሠራት መጀመራቸው በበጎ ጅምርነት ሊታዩና የበለጠ ተከናክረው ሊቀጥሉ የሚገባቸው ክንውኖች ናቸው፡፡

ከእነዚህ በጎ ጅምሮች ውስጥ በተለይም በትምህርትና በጤና ረገድ እየተሠራ ያለው ሥራ ሰብአዊ ሀብታችንን በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና የሚጫወት ሲሆን በመሠረተ ልማት ግንባታ በተለይም በመንገድ ግንባታ በአገራችን እየታየ ያለው እንቅስቃሴ እጅግ አድናቆት ሊቸረው የሚገባና ለሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች መሠረት ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ክንውን ነው፡፡ ከነዚህ በጎ ክንውኖች ጋር በተያያዘ የጥራት ችግር መኖሩ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ ቢሆንም፣ ጥራት ምን ጊዜም በአንድ ጊዜ ሊገኝ የማይችልና በሂደት እየተሻሻለ የሚመጣ ጉዳይ በመሆኑ የተሠሩትን በጎ ሥራዎች በጅምላ ለማጣጣል በቂ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ አይገባውም፡፡ ስለ ትምህርትም ሆነ የሕክምና ጥራት መጠዬቅ የምንጀምረው በቅድሚያ በሕንፃ ደረጃም ቢሆን ትምህርት ቤቶችና ሃኪም ቤቶች ሲኖሩ ስለሆነ የተቋማቱን መገንባት በቅድሚያ አድንቀን የጥራትን ጥያቄ ብናስከትል ትችታችንን ምክንያታዊና ቀና ሊያደርገው ይችላል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ከ17.5 ሚሊየን ያላነሱ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ መሆናቸው ሲታይ ይህ በራሱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የአገሪቱን ማኅበራዊ መሠረት በመቀዬር ረገድ የሚኖረው ሚና ቀላል የሚባል አይሆንም፡፡ አገሪቱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ እስካሁን መማር የቻለውን ሕዝብ ጨምሮ በቀላሉ ከሠላሳ ሚሊየን በላይ የሆነ የተማረ ሕዝብ ሲኖራት ምን ያህል ማኅበራዊ መሠረትዋ እንደሚቀየርና ለነፃ-ገበያም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የተመቸች አገር እንደምትሆን መገመት አያዳግትም፡፡

በወቅቱ የአገራችን የኢኮኖሚ ተጨባጭ ሁኔታ በድክመት ወይም በችግርነት ቀዳሚ ሆኖ ሊነሣ የሚችለውና በሌላ የዚህ መጽሐፍ ክፍል ለማየት እንደተሞከረው ኢህአዴግ ነፃ-ገበያ ሥርዓትን በተመለከተ የሚያራምደው የተንሻፈፈ አመለካከት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች እንደሚያስቡት ከመሳሳት ወይም ከግንዛቤ እጥረት በመነጨ ሳይሆን ኢህአዴግ ስለ ወደፊት የፖለቲካ የሥልጣን የበላይነቱ ካለበት ስጋት በመነጨ “ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢኮኖሚውን መቆጣጠር” የሚል ያልታወጀ ፖሊሲ ስላለው ይህ አመለካከቱ መንግሥትና ገዥው ፓርቲ ከገደብ ያለፈ ድርሻና ተሳትፎ በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ መንግሥት በልማት ድርጅቶች ስም በገበያ ውድድር ሊሸፈኑ የሚችሉ የማምረቻና የንግድ ተቋማትን በእጁ ይዞ መቀጠሉ፣ ገዥው ፓርቲም በኢንዶውመንት ስም በተዘዋዋሪ የንግድ ድርጅቶች ባለቤት ሆኖ መቀጠሉ ከዚሁ “ፖለቲካውን ለመቆጣጠር ኢኮኖሚውን መቆጣጠር” ከሚለው ያልታወጀ ፖሊሲ የተለየ ሌላ አሳማኝ ምክንያት አለው ማለት አይቻልም፡፡

ሁለተኛው ድክመት ኢህአዴግ ከሚያራምደው የእርሻ መር የኢኮኖሚ ስትራቴጂ የሚመነጭ ነው፡፡ ይህ እርሻ መር የሚባል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ እንደ አንድ አማራጭ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ በአንድ የፖለቲካ ኃይል ሊያዝ የሚችል አቋም ነው ሊባል ቢችልም፣ ይህ ገጠርንና አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ የሚል መርህ የሚገለጥ ስትራቴጂ ግን የፖለቲካ ምክንያት ያልተጫነውና ሙሉ በሙሉ ኢኮኖሚያዊ አመለካከት ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ በተለይም ኢህአዴግ ግብርና መር ለሚለው የኢኮኖሚ ስትራቴጂው የሚያቀርበው መከራከሪያ “እኛ ያለን ሀብት የሰው ጉልበትና መሬት ነው” የሚል ጠባብና አሳማኝ ያልሆነ መከራከሪያ መሆኑ ሲታይ፣ ኢህአዴግ የኢኮኖሚ ስትራቴጂዬ ገጠርንና አርሶ አደርን ማዕከል ያደረገ ነው ማለቱ 84% የሆነውን አርሶ አደር ሕዝብ የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት ሲል የሚጠቀምበት የፖለቲካ ስልት ነው ቢባል መነሻ የሌለው ክርክር ነው ሊባል አይችልም፡፡

በዚህ የኢህአዴግ የተንሻፈፈ አቋም ምክንያት ቢያንስ የተኃድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ እስከገባበት እስከ 1995 ዓ.ም. ድረስ ለዐሥራ ሁለት ዓመታት ያህል የኢንዱስትሪውና የአገልግሎቱ ዘርፍ የሚገባቸውን ትኩረት ሳያገኙና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ምንም ዓይነት መዋቅራዊ ሽግግር ሳይፈጠር ቀርቷል፡፡ ከ1995 ዓ.ም. ወዲህ ኢህአዴግ ከኢኮኖሚ ስትራቴጂ አኳያ የአቋም ለውጥ ያደረገ ስለመሆኑ በግልጽ ባያሳውቅም በተግባር ግን ለከተሞችና ለኢንዱስትሪው ዘርፍ የተሻለ ትኩረት መስጠት ጀምሯል፡፡ በዚህ በደምሳሳው በተካሄደ ለውጥም ቢሆን በአለፉት አምስት ዓመታት በአገሪቱ የተሻለ ለውጥ የመጣ ቢሆንም ቀጣይና አስተማማኝ በሚያደርግ መጠን ኢህአዴግ ለውጡን በግልጽነትና በድፍረት እያራመደው ባለመሆኑ

መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ረገድ የአገራችን ኢኮኖሚ ወደፊትም አዝጋሚ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም፡፡

ከዚሁ እርሻ መር ስትራቴጂ ተያያዥነት ያለውና በሦስተኛነት ሊነሣ የሚችለው ድክመት በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ላይ የአገሪቱ መሬት ሙሉ በሙሉ የመንግሥት እንዲሆን መደረጉ ነው፡፡ "ብሔር-ብሔረሰቦች የመገንጠል መብት ሲሰጣቸው መገንጠልን አይፈልጉም" በሚል አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት የመገንጠልን መብት ያህል አደገኛ ጉዳይ ሕገ-መንግሥታዊ ያደረገው ኢህአዴግ፣ ዜጐች በመሬት ላይ ያላቸውን ጥቅም የማስጠበቅ ብቃት እንደሌላቸው በመቁጠር ግን በመሬት ላይ የተሟላ የባለቤትነት መብት እንዳይኖራቸው በሕገ-መንግሥቱ አማካይነት ነፍጓቸዋል፡፡ ይህ ፖሊሲም ከኢኮኖሚ ትርጉሙ ይልቅ ፖለቲካዊ ትርጉሙ እንደሚያመዝን በወረቀት ላይ ስለሰፈረ ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ ከአርሶ አደሩ ጋር ባለው ግንኙነትም በተግባር ታይቷል፡፡ በአገሪቱ መሬትን እንደገና የማከፋፈል ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በአዋጅ እስካልተዘጋ ድረስ የአርሶ አደሩ የፖለቲካ ነፃነትም በመንግሥት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡ መሬት በዚህ መልክ የፖለቲካ መጠቀሚያ መሆኑ እስከቀጠለ ድረስ ደግሞ በኢኮኖሚው መስክ የሚጠበቅበትን ውጤት ያስገኛል ብሎ መጠበቅ የሚቻል አይሆንም፡፡

ሌላውና በአራተኛነት ሊጠቀስ የሚገባው ድክመት ኢህአዴግ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚና የርዳታ ድርጅቶችን በጥቅሉ እንደ ኪራይ ሰብሳቢዎች ወይም የኪራይ ሰብሳቢዎች መጠቀሚያ አድርጐ የሚያይበት መንገድ ነው፡፡ "ልማታዊ መንግሥት ነኝ" የሚለው ኢህአዴግ ከዚህ አስተሳሰቡ ጋር በተያያዘ መንግሥትን እንደ ዋና የልማት ኃይል የሚያይ በመሆኑ ለግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ ያለው አመለካከት ጤናማና ተገቢ ያልሆነ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአገራችን የግል ሴክተር ገና ታዳጊና የኅብረተሰቡን ጥቅም በኃላፊነት ስሜት ለማስጠበቅ የማያስችሉ በርካታ ጉድለቶች ያሉበት ዘርፍ ቢሆንም የወደፊት ዕጣ ፈንታችን የሚወሰነው በነፃ-ገበያ ሥርዓት ነው እስካልን ድረስ ግን ዞሮ ዞሮ የግሉ ዘርፍ ተጠናክሮ እንዲወጣና በአገሪቱ የኢኮኖሚ ሕይወት የመሪነቱን ሚና እንዲረከብ ከማድረግ የተለየ ወይም የተሻለ አማራጭ የለንም፡፡

የአገራችን የግል ዘርፍ አሁን ባለበት ደረጃ ጠንካራ የመንግሥት ቁጥጥርና ክትትል የሚያስፈልገው ቢሆንም ከሚደረግበት ቁጥጥርና ክትትል ባላነሰ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ቁልፍ ሚና እንዲጫወት የሚያስችለው እገዛና እንክብካቤም ያስፈልገዋል፡፡ ከሁሉ በፊትም መንግሥት በአንድ በኩል ራሱ ጥቃቅን የንግድ ድርጅቶችንና ከአምስት ብር ባነሰ ዋጋ ጭምር የሚከራዩ የቀበሌ ቤቶችን በእጁ ይዞ የኪራይ ሰብሳቢነት ሚና እየተጫወተ፣ በሌላ በኩል የግሉን ሴክተር እንደ ኪራይ ሰብሳቢ ወይም አጭበርባሪና ስግብግብ ኃይል አድርጐ በጥቅል ማየቱን ማቆም

ይገባዋል፡፡ ይህ ሲባል በበርበሬ ውስጥ ቀይ አፈር እየጨመሩ፣ በምግብ ዘይት ውስጥ መርዛማ ፈሳሽ እየቀላቀሉ፣ በአድማ እህልና ሸቀጥን በመከዘን የዋጋ ንረት በድሀው ሕዝብ ላይ እንዲከሰት የሚያደርጉ ሕሊና ቢስ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥርና ክትትል አይደረግ ማለት ሳይሆን በአንድ በኩል ሕገ ወጥ ንግድን በጽናትና በሃቅ ታግሎ ለማክሰም የሚያስችል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጋዊ ነጋዴዎችንና አልሚዎችን በአግባቡ ለመደገፍና ለማጠናከር የሚያስችል የጠራ አመለካከት መያዝ ያስፈልጋል ለማለት ነው፡፡

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በተለያዩና በየደረጃው በሚገኙ የመንግሥት ሹማምንት ዙሪያ ያለው አመለካከት ሲታይ ሕጋዊነትንና ሕገ-ወጥነትን በአግባቡ ለይቶ የሚያይ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ሁሉንም በጅምላ ጨፍልቆ በማየት ጥሩ መኪና ሲነዳና በጥሩ ቤት ውስጥ ሲኖር የታዩን ባለሀብት ሁሉ ሌባና ቀማኛ አድርጐ ማየት፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕጋዊውን ነጋዴና አልሚውን ባለሀብት ያለአግባብ የሚቀጣና በአንፃሩ ደግሞ ሕገ ወጡን ነጋዴና ባለሀብት የበለጠ የሚሸልም ተግባር በመንግሥት ሲፈጸም ይታያል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ተገቢ ያልሆነ አመለካከት በመንግሥት ዙሪያ ባሉ ሹማምንት ተይዞ እስከቀጠለ ድረስ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት አዝጋሚ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉም የረድኤት ድርጅቶች ጤናማና ለሕዝብ ጥቅም የሚሠሩ ናቸው ማለት ባይቻልም እነሱንም በተመለከተ በአሁኑ ወቅት መንግሥት የሚያራምደው አቋም ከችግር የጸዳ አይደለም፡፡ ከሁሉም በፊት በአገር ደረጃ ርዳታ መቀበልን በደፈናው ነውርና ጥገኝነትን የሚያጠናክር አድርጐ ማየት ስህተት ነው፡፡ በርግጥ በአግባቡ ለማይጠቀምበት አገርና ሕዝብ ርዳታ ከነውርነትም አልፎ እንደ አደገኛ ዕጽ ሊቆጠር የሚገባው ጐጂ ነገር ቢሆንም በአግባቡ ለሚጠቀምበት አገርና ሕዝብ ግን ከድህነት ለመላቀቅ የሚደረግ ጥረትን የሚያግዝ ጠቃሚ ቁምነገር ነው፡፡ እንዲያውም ለእኛ ዓይነት አብዛኛው ሕዝብ ከድህነት ወለል በታች ሆኖ በችጋር በሚማቅቅበት አገር ርዳታ ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የግድም አስፈላጊ ነው፡፡

በቅድሚያ ማወቅ የሚገባን ርዳታ መቀበል በእኛ የተጀመረ ሳይሆን አብዛኛዎቹ የዓለም አገራት ያለፉበት ሂደት መሆኑን ነው፡፡ ዛሬ በሀብት የዓለም ቁንጮ የሆነችው አገር አሜሪካ ሳትቀር በነፃነት ትግሉ ወቅት በፈረንሳይ ትረዳ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ የደረሱት በርካታዎቹ የአውሮፓ አገራትና ጃፓን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ ከአሜሪካን ከፍተኛ ርዳታ ሲቀበሉ የነበሩ ናቸው፡፡ ጀርመንንና ፖላንድን የመሳሰሉት አገሮችም በዕዳ ስረዛ አማካይነት ተረጅዎች የነበሩ አገሮች ናቸው፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ እሥራኤልና ግብጽን፣ ከኤዥያ አገሮች ደቡብ ኮሪያና ታይዋንን የመሳሰሉት አገሮች

ሁሉ ከምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ ርዳታ ሲቀበሉ የኖሩ ናቸው። እንዲያውም ከዚህ በላይ የጠቃቀስናቸው አገሮች ካገኙት ርዳታ ጋር በአጠቃላይ አፍሪካም ሆነች አገራችን ኢትዮጵያ እያገኘችው ያለውን ርዳታ ስናየው እንዳለ የሚቆጠርም አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ ምዕራባውያን በታዳጊ አገሮች ላይ በባሪያ ንግድ፣ በቅኝ ግዛት፣ በተለያዩ ብዝበዛዎችና በአካባቢ ብክላ ከፈፀሙት በደል አንጻር ለታዳጊ አገሮች ርዳታ የመስጠት ቢያንስ የሞራል ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ ይገባዋል። ከዚህ አንጻር ምዕራባውያን ለታዳጊ አገሮች ስለሚያደርጉት ርዳታ ብዙ ተጋኖ ሲወራ የሚደመጥ ቢሆንም በተግባር ሲታይ ግን ርዳታቸው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ለምሳሌ አሜሪካ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በማርሻል ፕላን አማካይነት ከአጠቃላይ አመታዊ የምርት መጠንዋ ታደርግ የነበረው 2% ርዳታ በአሁኑ ወቅት ወደ 0.2% ቀንሷል። ሃብታም አገሮች ቀደም ሲል ለድሀ አገሮች ኦፊሻል የልማት ርዳታ ለመስጠት ቃል ገብተው የነበረው ከአጠቃላይ አመታዊ ምርታቸው 0.7% ወይም ወደ ገንዘብ ሲለወጥ 175 ቢሊዮን ዶላር አካባቢ በዓመት ሲሆን አሁን ግን በተግባር እየሰጡት ያለው የርዳታ መጠን ከ15 ቢሊዮን ዶላር የበለጠ አይደለም። የአሜሪካንን አጠቃላይ ዓመታዊ የምርት መጠን ብቻ ብናይ ግን በዓመት ከ25 ትሪሊዮን ዶላር የበለጠ ነው። ለጋሽ አገሮች ከዓመታዊ ገቢያቸው 1.6% ብቻ ቢሰጡ ይህ ገንዘብ ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ አገሮችን መሠረታዊ ፍላጐት ሊያሟላ የሚችል ቢሆንም እንኳንስ ይህን ያህል ገንዘብና ቃል የገቡትን 0.7% መለገስ አልቻሉም።

በተለይም ከሰሃራ በታች የምንገኝ አገሮች እያገኘነው ያለነው ርዳታ ሙሉ በሙሉ በአግባቡ ብንጠቀምበት እንኳ መጠኑ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። አንድ እ.ኤ.አ በ2000 የተካሄደ ጥናት እንደሚያሳዩው ከሰሃራ በታች ለሚገኙ አገሮች የሚሰጠው ርዳታ በነፍስ ወከፍ በዓመት 30 ዶላር አካባቢ ብቻ ነው። ከዚህ 30 ዶላር ውስጥ 5 ዶላሩ ለምክር ሥራ፣ 3 ዶላሩ ለምግብና ለድንገተኛ ርዳታ፣ 4 ዶላሩ ለዕዳ ክፍያ፣ 5 ዶላሩ ለዕዳ ስረዛ ማስፈሚያ ይውልና ለአፍሪካውያኑ ከዚህ ተርፎ በነፍስ ወከፍ በዓመት የሚደርሰን ርዳታ 12 ዶላር ብቻ ነው። 12 ዶላር ማለት በአሜሪካን አገር ለአንድ ተራ የጉልበት ሠራተኛ ለአንድ ሰዓት የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው። ከዚህም የምንገነዘበው እየተገኘ ያለው ርዳታ በተግባር ምን ያህል ዝቅተኛ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በርዳታ ስም የሚመጣው ገንዘብም በተለያዩ የምክር አገልግሎት፣ የዕዳ ክፍያና የዕዳ ስረዛ ማስፈጸሚያ በሚሉ ሰበብ አስባቦች እዚያው በለጋሽ አገሮቹ እጅ የሚቀር መሆኑን ነው።

የሚገርመው ግን የሚገኘው ርዳታ ከፍተኛ እንደሆነ አድርገን ራሳችን እኛ አፍሪካውያን ከምናየው በላይ በራሳቸው በአደጉት አገሮች የሚኖረው ሕዝብም መንግሥታቸው ለታዳጊ አገሮች የሚሰጠው ርዳታ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ አድርጐ ይገምታል። እ.ኤ.አ በ2001 በሜሪላንድ ዩኒቨርስቲ የተደረገ አንድ ጥናት እንደሚያሳዬው አሜሪካኖች አገራቸው በዓመት 20% የሚሆነውን የፌዴራል በጀት ለታዳጊ አገሮች ርዳታ እንደምትሰጥ አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን እውነቱ በተግባር ሲታይ አሜሪካን ለታዳጊ አገሮች የምትሰጠው ርዳታ ሕዝቧ ከሚገምተው በ24 እጥፍ ያነሰ ነው።

ስለዚህ ከማንኛውም አገር በአሁኑ ወቅት የሚገኘውን አነስተኛ ርዳታ በአግባቡ አሟጦ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ የተሻለ ርዳታ ለማግኘት መጣር ተገቢ ነው። በተለይም ከውጭ የሚመጣ ርዳታ ከሙስናና ከብክነት በፀዳ ሁኔታ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል እስከተደረገ ድረስ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም። በርግጥ አንድ አገር ከድህነት ለመውጣት ራሱ ሊያደርግ የሚገባውን ትግል ርዳታ ሊተካው ይችላል ብሎ የሚያስብ ከሆነ ርዳታው መጣም ቀረም ፋይዳ የለውም። በታይዋንና በደቡብ ኮሪያ እንደታየው የሚገኘውን ርዳታ በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ለሚችል አገር ግን የውጭ ርዳታ ጥረት ተደርጐ ሊገኝ የሚገባውና ለዕድገት አጋዥ የሆነ ጠቃሚ ነገር እንጂ ለችግር የሚዳርግ እርግማን (Curse) አይደለም።

አገራችን ኢትዮጵያም በራስ የመተማመን መንፈስዋንና የራሷን ችግር በራሷ ለመፍታት የምታደርገውን ጥረት ጠብቃ በቂ የውጭ ርዳታ የምታገኝበትን ጥረት ማድረግ ካልቻለች በተለይም በውጭ ምንዛሪ ረገድ ያለባትን ጊዜያዊ ችግር ለመቋቋም የምትቸገር አገር ሆና መቀጠልዋ አይቀርም። ኢህአዴግ ከራሱ የፖለቲካ ሥልጣን የበላይነት ጋር በተያያዘ በሰብአዊ መብትና በዴሞክራሲ ስም የረድኤት ድርጅቶች ሊተናኮሉኝ ይችላሉ ብሎ በመስጋት ከእነሱ ጋር መፋጠጡንና የእነሱን የሥራ እንቅስቃሴ የሚያደናቅፉ ድርጊቶችን መፈጸም እስከቀጠለ ድረስ የውጭ ርዳታ ግኝታችን የበለጠ እየቀጨጨ እንጂ እየጨመረ ሊሄድ አይችልም።

ስለዚህ ያለአግባብ የርዳታ ገንዘብን የሚያባክኑም ሆነ በውስጥ ጉዳያችን ላይ ያለአግባብ ለመግባት የሚፈልጉ የረድኤት ድርጅቶች ላይ ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ማድረጉ እንደተጠበቀ ሆኖ የአገሪቱ የወጭ ንግድ በሚፈለገው መጠን እስከሚያድግ ድረስ የውጭ ርዳታ ግኝታችንን ለማሳደግ የሚያስችል ስልት ካልተከተልን በስተቀር የአገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት በውጭ ምንዛሪ እጥረት ብቻ ሊንኮታኮት የሚችልበት ሰፊ አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ሌላው ቀርቶ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ አገር ውስጥ የሚልኩት የውጭ ምንዛሪ በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ ያለው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። በባንኮች በኩልም ሆነ በጥቁር ገበያ

መልክ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ከኢትዮጵያውያኑ የሚገኘው ገንዘብ በአጠቃላይ አገሪቱ በወጭ ንግዷ ከምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ነው የሚገመተው። የአገራችን ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታ አሁን ካለበት የተሻለና ብሔራዊ መግባባት የሰፈነበት ቢሆን ኖሮ ይህ በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ መጠን አሁን ካለበት በሁለትና በሦስት ዕጥፍ ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል።

በርግጥም ይህንን የውጭ ምንዛሪ ምንጭ አገራችን አሟጣ መጠቀም ችላ ቢሆን ኖሮ በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣው በጎ ተጽዕኖ ቀላል ባልሆነ ነበር። ነገር ግን በአንድ በኩል ኢህአዴግ በሚያራምደው ሌሎችን በሚያርቅ የፖለቲካ ስልት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር የሚገኙ አንዳንድ ጽንፈኛ አቋም ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና መገናኛ ብዙኃን በሚያደርጉት ጤናማ ያልሆነ ቅስቀሳ አገራችን ከውጭ ማግኘት የሚገባትን ይህን ጥቅም በአግባቡ ሳታገኝ ቀርታለች። በአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የኢህአዴግ አገዛዝ የወጪና የገቢ ንግዳችን ሚዛን ምንም ዓይነት መዋቅራዊ ሽግግር አለማምጣቱና የገቢ ንግዳችን ከወጪ ንግዳችን የበለጠ እየጨመረ መምጣቱ ሲታይ በርዳታ ድርጅቶችም ሆነ በውጭ አገር ነዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ጥረት ማድረግ ካልቻልን ችግሩ ይበልጥ እየተባባሰ ሊሄድ ይችላል። አያድርገውና የነዳጅ ዋጋ በ2000 ዓ.ም. እንደሆነው መልሶ በበርሜል 150 ዶላር ቢሆንና በዚያ ዋጋ ላይ ሆኖ ለተወሰኑ ወራቶች ቢቀጥል የአገራችን ኢኮኖሚ በቀላሉ ሊያገግም በማይችልበት ደረጃ ሊንኮታኮት ይችላል።

ስለዚህ በአንድ በኩል የአገራችንን የሰብአዊ መብትና የዴሞክራሲ ሁኔታ በማሻሻል ከውጭ መንግሥታት ጋር ያለንን ግንኙነት ማሻሻልና የርዳታና የብድር ግኝታችንን መጨመር፣ በሌላ በኩልም በአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የተሻለ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር በማድረግ ከኢትዮጵያውያኑ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚላከውን የውጭ ምንዛሪ (Remittance) ማሳደግ ይኖርብናል። ለዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ትኩረት ለመስጠት የምንገደደው የጥገኝነት ባህሪ ለማዳበር ሳይሆን በወጪና በገቢ ንግድ ሚዛን ያለብን ጉድለት ከመሠረታዊ መዋቅራዊ ችግር የመነጨና በቀላሉና በአጭር ጊዜ ልንፈታው የማንችል ችግር ስለሆነ ነው።

አንዳንድ ጊዜ በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚደረግ ማበረታቻ የሞራል ጥያቄ የሚያሥነሣ ቢሆንም ትልቁን አገራዊ ጥቅም የበለጠ በማየት አገር ውስጥ ገብተው መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ከእስካሁኑም የበለጠ ማበረታቻ ማድረግ ያስፈልጋል። በርግጥ አገር ውስጥ በድህነት ኑሮ አገሪቱን እያገለገለ የሚኖረው ሕዝብ የአንገቱ መግቢያ መጠለያ ጎጆ መቀለስና ብስክሌት መግዛት ባልቻለበት ሁኔታ ከውጭ አገር ለሚመጡ ዜጐች ሰፊ ካሬ ሜትር

ያለው መሬት መስጠትና የቤት መኪና ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የሚያስችል መብት እንዲኖራቸው ማድረግ ከሞራል አንጻር የሚፈትንና ባይደረግ ይመረጥ የነበረ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ከውጭ የሚመጣው ገንዘብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የድህውን ኑሮ የማሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ማበረታቻውን የበለጠ አጠናክሮ መቀጠል ተገቢ ይሆናል፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን /Foreign Direct Investment/ ከመሳብ አኳያም አገራችን ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት እዚህ ግባ የሚባል ሥራ ሰርታለች ማለት አይቻልም፡፡ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም በዚህ ረገድ ግን ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲን ከሚያደርጉት ከፍተኛ ተሳትፎ በስተቀር በአገሪቱ የጐላ ሥራ እየተሠራ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በቅርቡ ከእርሻ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገራችን የመግባት አዝማሚያ እያሳዩ ቢሆንም ይህም ሙከራ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ “መሬታችን ተቀራመቱት” የሚል አዲስ ዘመቻ ውጭ በሚኖሩ አንዳንድ አክራሪ የፖለቲካ ኃይሎች በኩል ሲካሄድ እያየን ነው፡፡ የውጭ ባለ ሀብቶች ተሳትፎ ከአገር ጥቅም አንጻር በከፍተኛ ጥንቃቄ መያዝ ያለበት ጉዳይ ቢሆንም “መሬታችን ተቀራመቱት” በሚል በጭፍን የምናቀርበው ተቃውሞ ግን አገርን የሚጐዳ እንጂ የሚጠቅም ውጤት ሊያስገኝ አይችልም፡፡ እንዲያው የወቅቱ መንግሥት መውቀስ ያለበት በቂ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት ወደ አገሪቱ እንዳይገባ በማድረጉ መሆን ይገባዋል፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቃቀሱት በወቅቱ የአገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ላይ የሚታዩት መሠረታዊ ድክመቶች እስካልተለወጡ ወይም እስካልተሻሻሉ ድረስ የአገራችን ኢኮኖሚ መሠረታዊ መዋቅራዊ ለውጥ አምጥቶ በዘላቂነት ሊያድግ አይችልም ብቻ ሳይሆን በአንድ ምክንያት ማለትም በአንድ ክረምት ዝናብ መቅረት ወይም በነዳጅ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ምክንያት ብቻ በቀላሉ ሊንኮታኮት ይችላል፡፡ መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ባልመጣበት ሁኔታ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን በመጪው ሃያ እና ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ያላት አገር አደርጋታለሁ በማለት እየተመኘው ያለው በጎ ምኞት እውን ይሆናል ብሎ ማሰብም የሚቻል አይሆንም፡፡ ኢህአዴግ በሚከተለው እርሻ መር የሆነ የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት 85% የነበረውን የአርሶ አደር ሕዝብ ቁጥር መቀነስ የቻለው ወደ 83.7% ከሆነ፣ የግብርና ኢኮኖሚያችን ሙሉ በሙሉ አሁንም የዝናብ ጥገኛ ሆኖ ከቀጠለ፣ የገቢ ንግዳችን ከወጪ ንግዳችን የበለጠ እያደገ ከሄደ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከግብርናው ዘርፍ በብዙ ብልጫ ማደግ እስካልቻለ ድረስ ኢኮኖሚው በዘላቂነት አድጐ አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ትሆናለች ብሎ መጠበቅ የማይቻል ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ አገራችን ወደዚህ ዓይነቱ የማኅበረ-ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ልትገባ የምትችለው

በተፈጥሮ ላይ ጥገኛ ከሆነ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓት በዋናነት ወደ ዕውቀት መር ሥርዓት መሸጋገር ስትችል ነው፡፡

በነገራችን ላይ መካከለኛ ገቢ ያለው አገር መሆን ማለት ኢህአዴግ ሲናገር እንደሚደመጠው ቀላል ነገር አይደለም፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ያለውን የሀብት ወይም የገቢ አሰላለፍ ለማየት ብንሞክር ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት አገሮች አሜሪካን፣ ካናዳን፣ ምዕራብ አውሮፓን፣ ጃፓንንና አውስትራሊያን የሚያካትት ሲሆን የእነዚህ አገሮች አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ20 ሺህ ዶላር በላይ ነው፡፡ እኛ ከሃያ ዓመት በኋላ እንደርስባቸዋለን የምንላቸውና መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገራት የሚባሉት ደግሞ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር፣ ማዕከላዊ የአውሮፓ አገሮች፣ ሩሲያና የላቲን አሜሪካ አገሮች ሲሆኑ የእነዚህ አገሮች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ4 ሺህ እስከ 20 ሺህ ዶላር የሚደርስ ነው፡፡ ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት አገሮች የደቡብ አሜሪካ፣ የደቡብ ኤዥያ፣ የምሥራቅ ኤዥያና የአፍሪካ አገሮች የመሳሰሉት ሲሆኑ የእነዚህ አገሮች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ2 ሺህ እስከ 4 ሺህ ዶላር ነው፡፡ በእነዚህ ሦስት ምድቦች ውስጥ የማይገኙትና ኢትዮጵያን የመሳሰሉት ድሀ የሚባሉት አገሮች ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ደግሞ ከ2 ሺህ ዶላር በታች ነው፡፡ የኛዋ አገር ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያላት ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ 190 ዶላር አካባቢ በመሆኑ በእነዚህ ድሀ በሚባሉት አገሮች የገቢ መጠን ስትመዘን እንኳ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ነች፡፡

ስለዚህ በጎ መመኘት ባይከፋም ይህች “ድህነት” በሚባለው ማዕቀፍ ውስጥ ለመቀመጥ እንኳ ያስቸገረች አገራችን በሆነ መለኮታዊ ተአምር ካልሆነ በስተቀር ከኢኮኖሚ ጋር በተያያዘ ትንታኔ ከሃያ ዓመታት በኋላ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮችን ትቀላቀላለች ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው፡፡ ግምቱን እጅግ አስቸጋሪ የሚያደርገው ገና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር አለማምጣታችን ብቻ ሳይሆን ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የመጣንበት ሂደትም በቀላሉ ወደ መካከለኛ ገቢ ያላቸው አገሮች ጎራ መቀላቀል እንደማንችል የሚያረጋግጥ በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ቀላል ምሳሌ ብናነሣ፣ ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝ የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ አመታዊ ገቢ አንድ መቶ ዶላር አካባቢ የነበረ ሲሆን ዛሬ ከዐሥራ ስምንት ዓመት በኋላ ከፍ ሊል የቻለው ወደ 190 ዶላር አካባቢ ነው፡፡ በዐሥራ ስምንት ዓመት ውስጥ ከተከሰተው የዋጋ ንረት አኳያ ይህ የነፍስ ወከፍ ገቢ ዕድገት ምን ትርጉም አለው? የሚለው ጥያቄ በራሱ አነጋጋሪ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከዚህ በኋላ በሆነ ተአምር አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢዋን በየአመቱ ሳይቋረጥ በመቶ ዶላር ጭማሪ ማሳደግ ብትችል እንኳ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ሳይሆን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን አገሮች ጎራ ለመቀላቀል ቢያንስ ከ20 ዓመታት በላይ ያስፈልጋታል፡፡

ቻይናም ከሁለት ተከታታይ ዐሥርት ዓመታት በላይ በሁለት አኀዝ ማደግ ችላ እስካሁን ከነፍስ ወከፍ ገቢ አንጻር "ታዳጊ አገር" ከመባል መውጣት አለመቻልዋ የሚያረጋግጥልን ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ ስለዚህ እንኳንስ ኢኮኖሚያችን መሠረታዊ መዋቅራዊ ችግር ውስጥ ሆኖና የተስተካከለ ዝናብ ኖሮንና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሳያጋጥመን ነገሮች ሁሉ አልጋ ባልጋ ሆነውልን ማደግ ብንችል እንኳ ከ20 ዓመት በኂላ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን አገሮች ጐራ እንቀላቀላለን ብሎ መገመት እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ በርግጥ አንድ አገር በተስተካከለ አቅጣጫ አንድ ጊዜ የዕድገት መሰላልን ከተቆናጠጠ በኂላ ዕድገቱ የበለጠ ፈጣን ዑደት (Cycle) ውስጥ የሚገባበት ዕድል ያለ ቢሆንም ከላይ በተደጋጋሚ በጠቃቀስናቸው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች ምክንያት ወደዚህ ዓይነቱ የዕድገት ዑደት (Cycle) አገራችን በቀላሉ ትገባለች ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት በተለየ ያሉባትን መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ብታራምድና ትክክለኛው የዕድገት መስመር ውስጥ መግባት ብትችል ቢያንስ በሠላሳ ዓመት ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን አገሮች ጐራ ልትጠጋና በተለይም በመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ ትምህርትና ጤናን የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለሕዝብ በማዳረስ ረገድ ከዐሥር ዓመት በኂላ ከፍተኛ የሚባል ደረጃ ላይ ልትደርስ ትችላለች፡፡

ኢኮኖሚያችን ባሉበት መሠረታዊ የመዋቅር ችግሮች ምክንያት የከፋ ችግር ካላጋጠመውና በአሁኑ ወቅት በመሠረተ ልማት፣ በትምህርትና በጤና አገልግሎቶችና አቅርቦት እየታየ ያለው እጅግ አበረታች ውጤት አሁን እያሳዩ ባለው ፍጥነት መቀጠል ከቻለ ኢትዮጵያ ከነፍስ ወከፍ ዓመታዊ ገቢ አንጻር ብዙ መራመድ ባትችልም ከእነዚህ የመሠረተ ልማት፣ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች አቅርቦት አኳያ ግን በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደምትደርስ አያጠራጥርም፡፡ በእነዚህ ዘርፎች ውጤታማ መሆን በራሱ የአገሪቱን የሰው ሀብት በማጐልበትና አገሪቱን ለኢንቨስትመንት የተመቸች በማድረግ ረገድ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም በኢኮኖሚው ውስጥ አሁን የሚታዩት መሠረታዊ መዋቅራዊ ችግሮች መፍትሄ እስካላገኙ ድረስ ግን በእነዚህም ዘርፎች የሚታየው አበረታች ውጤት ቀጣይና ዘላቂ ስለመሆኑ የሚያስተማምን ዋስትና አለ ማለት አይቻልም፡፡

### *3.5 መሬትና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ*

ከ1960ዎቹ የአገራችን የተማሪዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የዘለቀና በኢኮኖሚ ረገድ ከመሬት ጥያቄ የበለጠ አከራካሪ የሆነ ጉዳይ አልነበረም ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ በርግጥ ከጥቅሙ አኳያ መሬት የኢኮኖሚ ጉዳይ ቢሆንም በእኛ አገር ሁኔታ

ከኢኮኖሚ ጥያቄነቱ ባላነሰ ፖለቲካዊ ጥያቄም ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡ “መሬት ላራሹ” የሚለው የ1960ዎቹ ተወዳጅ (Popular) መፈክር ከአሁኑ ዘመን የካፒታሊስትና የነፃ-ገበያ አስተሳሰብ ጋር የሚጣጣም መሆን-አለመሆኑ በራሱ አከራካሪ ቢሆንም በዚያ ወቅት ግን የመሬት ላራሹ ጥያቄ ከፖለቲከኞች አልፎ የአብዛኛው ሕዝብ ጥያቄ እንደ ነበር የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የመሬት ላራሹ ጥያቄ በኢትዮጵያ የዚያ ወቅት ፖለቲካ የግራ ኃይል የፖለቲካ ድርጅቶች በአብዛኛው ሕዝብ ተቀባይነት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

የደርግ የመሬት ላራሹ አዋጅ እስካሁን ድረስ ደርግን በአብዛኛው ሕዝብ የሚያስመሰግን የለውጥ ርምጃ ተደርጐ የሚታይ ቢሆንም፣ የለውጥ ርምጃው የተሟላ ነበር ወይስ ከፊል? የለውጡ ጠቃሚና ጐጂ ጐንስ ምን ነበር? የሚሉት ጥያቄዎች ግን እስካሁን በቂ ክርክር ተደርጐባቸዋል ማለት አይቻልም፡፡ ደርግ የነካውን ነገር ሁሉ መቃወም የሚቀናው ኢህአዴግ ሳይቀር የደርግን የመሬት ፖሊሲ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ አድርጐ እንዳለ ይዞት በመቀጠሉ የደርግ የመሬት ላራሹ አዋጅ ጥያቄ ሊነሣበት የማይችል የተሟላና ተገቢ መፍትሄ ተደርጐ መታየቱን ይበልጥ አጠናክሮታል፡፡ የሚገርመው በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ የሚያራምደውን የመሬት ፖሊሲ አምርረን የምንቃወም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይቀር ደርግ የወሰደውን የመሬት ላራሹ ርምጃ ብዙውን ጊዜ ስናሞካሽ እንጂ ስንተች አንደመጥም፡፡ ነገር ግን አሁን በስራ ላይ ያለውን የመሬት ፖሊሲ የሚቃዎም ማንኛውም ሰው የደርግን የመሬት ላራሹ ርምጃ የሚደግፍ ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ አቋም እርስ በርሱ የሚጋጭና ምክንያታዊ መሠረት የሌለው ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት እያራመደው የሚገኘው የመሬት ፖሊሲ ሳይደመር ሳይቀነስ የደርግ የመሬት ፖሊሲ ነውና፡፡

“መሬት ላራሹ” የሚለው ብዙ የተጮኸለት ጥያቄ በመጨረሻ ውጤቱ መንግሥትን የመሬት ባለቤት፣ሕዝቡን ደግሞ የመንግሥት ጭሰኛ አድርጐ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ የመሬት ላራሹ ጥያቄ በተገቢው ሁኔታ አልተመለሰም የሚል ጥያቄ የሚገባውን ያህል ጐልቶ ሊወጣ አልቻለም፡፡ በርግጥ አሁን አሁን አንዳንድ የተማሪ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች የመሬት ላራሹ ጥያቄ አቅጣጫውን መሳቱን ሲገልጹ ይደመጣሉ፡፡ ለምሳሌ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በአንድ የውይይት መድረክ ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ የመሬት ላራሹ ጥያቄ ከመሬት ላይ የሚገኘውን ምርት ብቻ ሳይሆን የማምረቻ መሣሪያውን ማለትም መሬቱንም ጭምር ለአምራቹ ለማድረግ የቀረበ ጥያቄ እንደነበር ገልፀዋል፡፡ ይህንን የመሳሰሉ የመሬት ላራሹ ጥያቄ አቅጣጫውን መሳቱን የሚያሳዩ የተለያዩ አስተያየቶች በተለያዩ የጥናት ጽሑፎች ላይ ተጠቅሰው

የሚገኙ ቢሆንም የመሬት ላራሹ ጥያቄ ከመጀመሪያውም መነሣቱ ስህተት ነበር የሚሉ አስተያየቶች እምብዛም ጐልተው አይታዩም፡፡ ነገር ግን በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም አንዳንድ የተማሪው እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ ሰዎች የመሬት ላራሹ ጥያቄ ከመጀመሪያውም ስህተት እንደነበር አምርረው ሲገልፁ ይደመጣሉ፡፡ ለምሳሌ ኢንጂነር ታደሰ ኃይለሥላሴ በአንድ ለውይይት ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ ስለመሬት ላራሹ ጥያቄ ያላቸውን አስተያየት በሚከተለው ሁኔታ ገልፀውታል፡፡

> *“………. በመሬት ጥያቄ የኢትዮጵያዉያኖች ችግር ከዕውቀት ማነስ የተነሣ የምንሰራውን፣ የምንናገረውን አለማወቃችን ላይ ነው፡፡ ተማሪ በነበርኩ ጊዜ መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክር በአዲስ አበባ አውራ ጐዳናዎች አንግበው ከተዘዋወሩት ዜጋዎች አንዱ ነኝ፡፡ ይህ መፈክር የአገራችንን ሕዝብ ብዙ ያበጣበጠ፣ ያጋደለ፣ ሶሻሊዝምን በአገራችን በኢትዮጵያ…….እንዲገባ ያደረገ መፈክር ነው፡፡ ሆኖም ይህን መፈክር 30 ዓመታት ጮህን ጮህን ያመጣነው ውጤት የለም፡፡ የበለጠ እንድንራብ፣ የበለጠ ድሀ እንድንሆን፣ የበለጠ አርስ በርሳችን እንድንካሰስ አድርጐናል፡፡ የዚህ መፈክር ውጤት በዐይኑ የሚታየው የኢትየጵያን ሕዝብ ረሃበተኛ፣ ድሀ ያደረገ ነው!…..የመሬት ላራሹ መፈክርን ያስተጋባን ሁሉ ራሳችንን መርምረን እውነቱ ላይ እንድንደርስ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡ በእኔ ዕምነት ንስሃ፣ ሱባዔ ገብተን መሬት ላራሹ የሚለውን መፈክር በመለወጥ …..ምርታማ ገበሬ የምናፈራበትን ዘዴ መቀየስ አለብን፡፡….. የመሬት ላራሹ መፈክር ተሸክመን በዞርንበት ጊዜ ዴሞክራቲክ መንግሥት ላራሹ! ውሃ ላራሹ! ብለን እነዚህንም ሁለት ጉዳዮች አብረን ዘምረን አስተጋብተን ቢሆን ኖሮ ዛሬ ምርታማ ገበሬ እናገኝ ነበር፡፡”*

በርግጥም ጉዳዩን ጠለቅ ብሎ ለሚመረምረው የመሬት ላራሹ ጥያቄ በተገቢው ሁኔታ አለመመለሱና እንዲያውም አቅጣጫውን ስቶ መንግሥት ለሚባል ዜጐች በቀላሉ የማይጋፉት አዲስ የመሬት ብቸኛ “ከበርቴ” መተላለፉ ግልጽ ቢሆንም በዚህ ዙሪያ ሊነሣ የሚገባው “የመሬት ባለቤት ማን ሊሆን ይገባዋል?” የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ “መሬት ይሸጥ - አይሸጥ?” በሚል ቁንጽል ጥያቄ ደብዝዞ በወቅቱ የአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ የሚገባውን ቦታ እንዳያገኝ ሆኗል፡፡ በመሬት ላራሹ ጉዳይ ላይ ጥያቄ ማንሣትም ሆነ ትችት ማቅረብ የግራ የፖለቲካ ኃይል በፈጠረው ከፍተኛ ጫና ምክንያት ነውር /Taboo/ ሆኖ የኖረ ቢሆንም የመሬት ላራሹ አዋጅ

ብዙ መሬት አልባ የነበሩ ድሀ አርሶ አደሮችን የመሬት ባለ ይዞታ በማድረግ ረገድ የተጫወተውን በጎ ሚና ያህል በአገሪቱ ቀጣይ ሕይወት ላይ ፈጥሮት ያለፈው መጥፎ ጠባሳ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

የመሬት ላራሹ አዋጅ - አንደኛ በሥልጣንና “በባላባትነት” የመሬት ከበርቴ የሆነውን ሰው በግል ጥረትና ገንዘቡ የመሬት ባለቤት ለመሆን የበቃውን አልሚ ሳይለይ በጅምላ የነጠቀና የቀጣ በመሆኑ፤ ሁለተኛ አርሶ አደሩን “ከባለአባቶች” ጭሰኝነት አውጥቶ ወደ መንግሥት ጭሰኝነት በማስገባት ከሲሶ ገባርነት ወደ አጠቃላይ የመንግሥት ሚሊሻነትና አገልጋይነት የቀየረ በመሆኑ፣ በሦስተኛና በዋናነት አገሪቱን ከካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታ ሙሉ በሙሉ አውጥቶ የኋላቀር ግብርናና የገበሬ አገር ሆና እንድትቀጥል ያደረገ በመሆኑ ካስገኘው ጥቅም በላይ በአገሪቱ ላይ ያስከተለው ችግር የበለጠ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የ1967ቱ የመሬት ላራሹ አዋጅ የተለያዩ አማራጮችን ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ከኢኮኖሚ ትርጉሙ ይልቅ ፖለቲካዊ ርምጃ ነው ሊባል የሚችልና በቻይናና በሶቭዬት ኅብረት ከታየው የለውጥ ሂደትም የበለጠ ሥር ነቀል /Radical/ ለውጥ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የሆነ ሆኖ በጠበበ ይዘቱም ቢሆን የመሬት ጉዳይ በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን የመሬትን ጉዳይ በተመለከተ በወቅቱ በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ቢያንስ የሚከተሉት ሦስት ዓይነት አመለካከቶች አሉ ማለት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ኢህአዴግና አንዳንድ በብሔር የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች “መሬት የመንግሥት መሆን አለበት” በማለት የሚያራምዱት አቋም ሲሆን ከዚህ በተቃራኒ የሚነሣውና በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚራመደው አቋም “መሬት መሸጥ መለወጥ የሚችል የግል ንብረት መሆን አለበት” የሚል ነው፡፡ ከእነዚህ መሬት የመንግሥት ወይም የግል ይሁን በሚል በአገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመሬት ስሪት እንዲኖር ከሚፈልጉ የፖለቲካ ኃይሎች በተለየ ሦስተኛ አማራጭ አቋም ያለው ፓርቲ ኢዴፓ ሲሆን፣ ኢዴፓ የሚያራምደው አቋም መሬትን በተመለከተ ሦስት ዓይነት ስሪት ማለትም እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የመንግሥት፣ የወልና የግል የመሬት ይዞታን የሚፈቅድ የመሬት ፖሊሲ በአገራችን ሊኖር ይገባል የሚል ነው፡፡

በመሬት ጥያቄ ዙሪያ በኢህአዴግና በኢዴፓ መካከል ያለውን ልዩነት ከማየታችን በፊት በቅድሚያ በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች “መሬት የግል ንብረት ሆኖ መሸጥ-መለወጥ አለበት” በማለት የሚነሣውን አቋም አንደምታ ለመመልከት ብንሞክር በጉዳዩ ዙሪያ ሊነሣ የሚችለውን ክርክር የበለጠ ግልጽና አጭር ሊያደርገው ይችላል፡፡ መሬት መሸጥ መለወጥ የሚችል የግል ንብረት ይሁን በሚለው አቋም ዙሪያ አቋሙ ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም? የሚል ክርክር

ውስጥ ሳንገባ እንዲህ ዓይነቱ አቋም በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሊተገበር የማይችል መሆኑን በማሳየት ብቻ በዚህ ረገድ ሊነሣ የሚችለውን ክርክር እዚሁ ላይ ልናሳጥረው እንችላለን፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ሰዎች ያልሰፈሩበትና ጥቅም ላይ ያልዋለ ሰፊ መሬት ያለ ከመሆኑ በተጨማሪ አብዛኛው የአገሪቱ መሬት አንድ ቦታ ሰፍሮ በማይኖርና ከቦታ ቦታ በሚንቀሳቀስ አርብቶ አደር ሕዝብ የተያዘ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ የአገሪቱን መሬት ሙሉ በሙሉ ይቅርና፣ አብዛኛውንም መሬት በግል ባለቤትነት እንዲተዳደር ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታ የለም፡፡ ጉዳዩን በቀላል ምሳሌ ለማስረዳት የአርብቶአደሩ ሕዝብ አኗኗር ወደ ቋሚ (Sedentary) አኗኗር ባልተለወጠበት ሁኔታ በአፋር ወይም በሶማሌ ክልል መሬት የግል ንብረት ይሁን ቢባል ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ የአርብቶአደሩ ሕዝብ ኑሮው የተመሠረተው ውሃንና የግጦሽ መሬትን ተከትሎ በየወቅቱ ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ስለሆነ በዚያ ኑሮውን በመሠረተበት ቦታ ላይ ራሱ አርብቶአደሩም ሆነ ከሌላ አካባቢ የመጣ ሰው የመሬት ቋሚ ባለቤት ይሁን ቢባል ሕይወት ራስዋ ትቆማለች እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ፖሊሲ በተግባር ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

ስለዚህ ወጥ በሆነ መልኩ የአገሪቱ መሬት መሸጥ መለወጥ የሚችል የግል ንብረት ይሁን የሚለው የአንዳንድ ተቃዋሚዎች አቋም አሁን ባለው የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የማይሠራ መሆኑን ተገንዝበን ከመሬት መሸጥ-መለወጥ ጋር ሊነሣ የሚችለውን ክርክር ግን ከዚህ ቀጥለን በኢህአዴግና በኢዴፓ መካከል ያለውን ልዩነት ስንዳስስ አብረን የምናየው ይሆናል፡፡ ከእነዚህ በጥቅሉ መሬት መሸጥ መለወጥ የሚችል የግል ንብረት መሆን አለበት በማለት የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ ያላገናዘበ ክርክር ከሚያቀርቡ አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በተለየ የመሬት ጉዳይን አስመልክቶ ከኢህአዴግና ከአንዳንድ በብሔር ከተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተለየ አቋም ያለው ኢዴፓ ነው (በርግጥ አሁን አሁን አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አቋሙን ሲጋሩት እየታየ ነው)፡፡ ነገር ግን ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው "መሬት ይሸጥ-ይለወጥ" የሚለው ቁንጽል ክርክር ገኖ ስለሚደመጥና ኢህአዴግም ከራሱ ድርጅታዊ ጥቅምና ፍላጐት አኳያ ሆን ብሎ ክርክሩን በዚህ ዙሪያ የታጠረ እንዲሆን ስለሚያደርገው ኢዴፓ በመሬት ጉዳይ የሚያቀርበው አማራጭ ጐልቶ የሚደመጥበት ዕድል እስካሁን አላገኘም ማለት ይቻላል፡፡

ከኢህአዴግ ውጭ ያሉትና መሬት የመንግሥት መሆን አለበት ብለው በጠነከረ ሁኔታ የሚያምኑት አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የኦሮሞ ድርጅቶች ሲሆኑ እነዚህ ድርጅቶች ብዙውን ጊዜ ለዚህ አቋማቸው ሊያቀርቡት የሚሞክሩት ምክንያት ሰፊና ለም መሬት የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል በመሆኑ "ነፍጠኞች እንደገና መሬታችንን በግዥ ስም ይነጥቁናል" የሚል ስለሆነ በዚህ ዓይነቱ የጠበበና አንድ ቦታ ላይ ተቸክሎ የቆመ ክርክር ውስጥ ገብቶ መከራከሩ

ብዙም ፋይዳ ስለማይኖረው ኢህአዴግ የሚያቀርባቸው መከራከሪያዎች ላይ ተመርኩዞ ትችት ለማቅረቡ መሞከሩ የተሻለ የሚጠቅም ይሆናል፡፡

ከኢህአዴግ አቋም አንጻር በቅድሚያ ትችት ሊቀርብበት የሚገባው ነጥብ መሬት የመንግሥት መሆን አለበት የሚለው የድርጅት አቋም ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ እንዲሆን መደረጉ ላይ ነው፡፡ የአንድ አገር ሕገ-መንግሥት በተቻለ መጠን በአገር ደረጃ የተሻለ ስምምነት የሚገኝባቸው ጉዳዮች ላይ ማተኮር የሚገባው ሆኖ እያለ በፓርቲዎች ዙሪያ ከፍተኛ የልዩነት ምንጭ የሆነውን የመሬት ጉዳይ በሕገ-መንግሥት ውስጥ እንዲደነገግ መደረጉ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ነው፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት የልዩነት ምንጭ የሆነ አወዛጋቢ ጉዳይ በሕገ-መንግሥት ውስጥ እንዲካተት ከተደረገ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ሥልጣን በተለዋወጡ ቁጥር ሕገ-መንግሥቱን ወደ ማሻሻል ርምጃ ስለሚወስዳቸው በራሱ የፖለቲካ መረጋጋት እንዳይኖር ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ከዚሁ ጉዳዩ ሕገ-መንግሥታዊ እንዲሆን ከመደረጉ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለው ሌላው ችግር በአገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመሬት ፖሊሲ እንዲኖር የሚያስገድድ መሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በመሬት አቀማመጥ፣ በአየር ፀባይ፣ በሕዝብ አሰፋፈርና በአኗኗር ዘይቤ የተለያዩ ሁኔታ ያለባት አገር መሆንዋ እየታወቀ እነዚህን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ አንድ ወጥ የሆነ የመሬት ፖሊሲ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉ የአካባቢ መስተዳድሮች በመሬት ጉዳይ የሚኖራቸውን የመወሰን መብት የነፈገ ከመሆኑም በላይ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አመች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዳይፈጠር እንቅፋት ሆኗል፡፡ የመሬት ጉዳይ ሕገ-መንግሥታዊ ባይደረግ ኖሮ እያንዳንዱ ክልል ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የተለያዩ የመሬት ስሪት ተግባራዊ ሲያደርግ የማየት ዕድል ይኖረን ነበር፡፡ አሁን ግን አንድ ክልል የቱንም ያህል ከሌላው አካባቢ የተለየ ውስጣዊ ሁኔታ ቢኖረው ሕገ-መንግሥቱ እስካልተሻሻለ ድረስ የተለየ የመሬት ፖሊሲ ተግባራዊ የማድረግ መብትና ሥልጣን የለውም፡፡ ይህም በሌላ ርእስ ላይ ለማየት እንደሞከርነው በአገሪቱ ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ ፌዴራሊዝም የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩን የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው የመሬትን ጉዳይ የሚመለከተው ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጽ በሁሉም ክልሎች ስምምነት ብቻ ሊሻሻሉ ከሚችሉት ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት ከአገር መገንጠል ቢፈልጉ በራሳቸው ክልል ህዝበ-ውሳኔ ብቻ መገንጠል የተፈቀደላቸው ክልሎች በመሬት ጉዳይ ላይ ግን ራሳቸውን ችለው ውሳኔ የመስጠት መብት ተነፍገዋል ማለት ነው፡፡ የመሬት ጉዳይ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ መደረጉ

የሚያስከትለው ጉዳት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው አከራካሪ ጉዳይ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግሥት ንብረት መሆን አለበት የሚለው አቋም አገርን ይጠቅማል ወይንስ ይጐዳል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ በቅድሚያ ጉዳዩን ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ አንጻር ልናየው ብንሞክር በዓለም ላይ የነፃ-ገበያ ሥርዓት አራማጅ ሆነው እያለ መሬት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘባቸው ጥቂት አገሮች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ የነፃ-ገበያ ሥርዓት አራማጅ በሆኑት አገሮች ግን መሬት እንደማንኛውም ሀብት በግለሰብ ባለቤትነት ጭምር ተይዞ ሊሸጥና ሊለወጥ የሚችል ንብረት ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ የመሬት ጉዳይ በተነሳ ቁጥር ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ በምሳሌነት የሚያቀርባትና መሬት የማይሸጥና የማይለወጥባት አገር ቻይና ሳትቀር በአንፃራዊነት ከእኛ የተሻለ የመሬት ፖሊሲ አላት፡፡ እስካሁን ድረስ በኮሚኒስት ፓርቲ እየተመራች የምትገኘውን የቻይናን ሁኔታ ከእኛ አገር ሁኔታ ጋር ማነፃጸር በራሱ ተገቢ ባይሆንም በመሬት ፖሊሲ ረገድ ኮሚኒስት ቻይና እንኳ ከኢትዮጵያ የተሻለ ሁኔታ ላይ ትገኛለች ማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም የኢትዮጵያ የመሬት ፖሊሲ ከ1967ዓ.ም ጀምሮ ምንም ዓይነት መሠረታዊ ለውጥ ያልተደረገበት ሲሆን የቻይና የመሬት ፖሊሲ ግን እንደ እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ ጀምሮ እስከ ቅርቡ 2007 ዓ.ም ድረስ በየጊዜው እየተሻሻለ መጥቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ መሬት ሙሉ ሙሉ በመንግሥት እጅ የተያዘ ሲሆን በቻይና ግን መሬት በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በማኅበር ባለቤትነት (collective ownership) የሚያዝበት አሠራር አለ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቻይና የከተማ መሬትን በባንክ ማስያዥነት መጠቀም የሚቻል ሲሆን፣ የገጠር መሬትን የመጠቀም መብትን ደግሞ እስከ 35 ዓመት በሚደርስ የኮንትራት ውል የመሸጥ መብት አለ፡፡ ይህም የሚያሳየው ከኢትዮጵያ ይልቅ በቻይና በመሬት የመጠቀም የተሻለ ዋስትና መኖሩን ነው፡፡

ስለመሬት የመሸጥና የመለወጥ ጉዳይ ሲነሳ ኢህአዴግ አንዳንድ ጊዜ “መሬትን ጠፍጥፎ የሰራ የለም” የሚል አመለካከት ሲያራምድ የሚደመጥ ቢሆንም ሁሉም በዓለማችን ያለና የምንገለገልበት ሀብት ሁሉ ከሰው ጋር አብሮ የተፈጠረ ሳይሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከተፈጥሮ የመነጨ ሀብት በመሆኑ መሬትን በተለየ ሁኔታ ሊሸጥ-ሊለወጥ የማይችል ሀብት ነው ለማለት የሚያስችለን አሳማኝ ምክንያት አይኖርም፡፡ መሬት ሊሸጥ-ሊለወጥ አይችልም የሚያስብል የተለየ አሳማኝ ምክንያት ቢኖር ኖሮ በመሬት ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት፣ ነዳጅ፣ ውሃ፣ ድንጋይ፣ አሸዋና እንጨትን የመሳሰሉ ሃብቶች ሁሉ የግል ንብረት የሚሆኑበት ዕድል አይኖርም ነበር፡፡ እነዚህ ሃብቶች የግል ሀብት ለመሆን የሚበቁት እሴት (Value) ተጨምሮባቸው ወይም ከቦታ ቦታ ተጓጉዘው ነው የሚል መከራከሪያ የሚቀርብ ከሆነም፣ በሰው

ጉልበት የለማና ግንባታ የተካሄደበት መሬት ጭምር በአገራችን ለምን እንዳይሸጥና እንዳይለወጥ እንደተከለከለ የተለየ አሳማኝ መልስ ማቅረብ የሚቻል አይሆንም፡፡

ዞሮ ዞሮ መሬት መሸጥ መለወጥ የማይችል የመንግሥት ንብረት መሆን አለበት ለሚለው አቋም ኢህአዴግ በዋናነት የሚያቀርበው መከራከሪያ “መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ ከተፈቀደ ገበሬው በጊዜያዊ ችግር አስገዳጅነት ጭምር መሬቱን ሸጦ ሊነቀልና ለችግር ሊጋለጥ ይችላል” የሚል ነው፡፡ ይህ የኢህአዴግ አስተሳሰብ እንደ አንድ አማራጭ አስተሳሰብ ሊታይ የሚገባውና በተወሰነ ደረጃም የራሱ መነሻ ምክንያት ያለው አስተሳሰብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአገራችን የሚጠቅም አስተሳሰብ ነው ወይስ አይደለም? ከሚለው ክርክር አንጻር ግን የተለያዩ ከባድ ጥያቄዎችን ሊያሥነሣ የሚችል አመለካከት ነው፡፡

በመጀመሪያ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ የኅብረተሰብን ጥቅም ያስጠብቃል ተብሎ የሚታመንበትን አንድ ጉዳይ በሕግ መደንገግ ስህተት ነው ሊባል ባይችልም በመሬት ጉዳይ አርሶ አደሩ ሕዝብ የራሱን ጥቅም ለማወቅና ለማስጠበቅ እንደማይችል ተደርጐ መብቱ በሕግ እንዲገደብ መደረጉ ተገቢ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ያለበት ነው፡፡ መቼም በአገራችን አርሶ አደሮች ዙሪያ ጥናት ለማድረግ የሚሞክር ወይም በገጠሩ የአገራችን ክፍል ላደገና ለኖረ ማንኛውም ሰው የአገራችን አርሶ አደር ለመሬት ምን ያህል ከፍተኛ ፍቅርና ተቆርቋሪነት እንዳለው ለመገንዘብ አይቸገርም፡፡ የአገራችን አርሶ አደር ከምንም ነገር በላይ የራሱና የቤተሰቦቹ ሕልውና በመሬት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በመሬቱ ላይ ስላለው ጥቅም ከራሱ በላይ መንግሥትም ይሁን ሌላ አካል ያውቅለታል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው፡፡

እንዲያውም የአገራችን አርሶ አደር ዙሪያ የሚታየው ዋናው ችግር በአንድ በኩል የተሻለ ሕይዎቱን የሚቀይር አማራጭ ቢያገኝ እንኳን መሬቱን ሸጦ ኑሮውን ለመለወጥ የማይፈልግ መሆኑና፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከይዞታው አንድ ስንዝር መሬት በሌላ ድንበርተኛ አርሶ አደር ቢነካበት መተኪያ የሌላትን የሌላ ሰው ሕይወት ለማጥፋትም ሆነ የራሱን ሕይወት መሥዋዕት ለማድረግ ወደ ኋላ የማይል መሆኑ ነው፡፡ በእርሻም ሆነ በግጦሽ መሬት ግጭት በአገራችን ምን ያህል ሰው በየዕለቱ ውድ ሕይወቱን እያጣ እንደሚገኝ ስናይ የምንረዳው ቁምነገር አርሶአደሩ ለመሬቱ ደንታ ቢስ መሆኑን ሳይሆን ምን ያህል የከረረና አንዳንድ ጊዜም ከመጠን ያለፈ የመሬት ፍቅር ያለው መሆኑን ነው፡፡

ስለዚህ የሰው ልጅ ለራሱ ጥቅምና ደኅንነት የመቆም የተፈጥሮ ባህሪ ያለው መሆኑን መቀበል አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአገራችን አርሶ አደር ባህሪና አስተሳሰብ አንጻርም

መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ መብቱን በሕግ ለመገደብ የሚያስገድድ ነባራዊ ሁኔታ በአገራችን አለ ማለት አይቻልም፡፡ የአገራችን ገበሬ እንኳንስ መሬቱን በቀላሉ ሊሸጥ ቀርቶ፣ የሚልስ-የሚቀምሰው ባጣበት የድርቅ ወቅት እንኳ ያስቀመጠውን የእህል ዘር ቆልቶ በመብላት ሕይወቱን ከማትረፍ ይልቅ በረሃብ መሞትን የመምረጥ ጠንካራ አቋም ያለው ሕዝብ ነው፡፡ በማንኛውም ኅብረተሰብ ውስጥ መሬትን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ዓይነት ሕይወታቸው የተመሰረተበትን ጥቅም በንዝህላልነት ሊያጡ የሚችሉ ግለሰቦች መኖራቸው የሚጠበቅ ቢሆንም እነዚህን ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎች ከግል ንዝህላልነታቸው ከሚመነጭ አደጋ ለመከላከል ተብሎ የሁሉንም ሕዝብ መብት በሕግ መገደብ ግን ተገቢ ሊሆን አይችልም፡፡

ለግል ሕይወቱ ኃላፊነት መውሰድ የማይችል ማንኛውም ሰው መሬቱን እንዳይሸጥ እንዳይለውጥ ተከለከለም አልተከለከለም በተለያዬ መንገድ ራሱን ከርስቱ ለመንቀልም ሆነ ለአደጋ ከመጋለጥ ሊድን አይችልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን አደጋ በተወሰነ ደረጃ መቀነስ ይቻላል ተብሎም ከታሰበ በተለያዩ የአፈጻጸም ስልቶች ሽያጭን የማያደፋፍርና አደጋውን ለመቀነስ የሚያስችል አሠራር መፍጠር ነው እንጂ በዚህ ሰበብ የሁሉንም ሕዝብ መብት በሕግ በመገደብ በመንግሥት ጭሰኝነት እንዲኖር ማድረግ ምክንያታዊም - ፍትሐዊም ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሕዝብ ጥቅሙን ስለማያውቅ መብቱን በሕግ እንገድበው የሚል አሠራር ተገቢ ነው ከተባለ አርሶ አደሩን ብቻ ሳይሆን ነጋዴው ሱቁን ሸጦ እንዳይከሥር፣ የቢሮ ሠራተኛው ሥራውን ለቆ ሥራ አጥ እንዳይሆን የሚገድብ ተመሳሳይ ሕግ ማውጣት አለብን እንደማለት ነው፡፡ መንግሥት በዜጐቹ ላይ እንዲህ ዓይነት የአስተዳደር ሳይሆን የሞግዚትነት ሚና ይኑረኝ ካለ ግንኙነቱ የአባትና የልጅ እንጂ የመንግሥትና የዜግነት ሊሆን አይችልም፡፡ በሕዝብ የተመረጠ ወይም የሕዝብ ጥቅም ቆሜአለሁ የሚል አንድ መንግሥትም የሕዝብ አገልጋይ እንጂ የሕዝብ ገዥና ሞግዚት ሊሆን አይገባውም፡፡

የሚገርመው ግን በዚሁ ዜጐች ጥቅማቸውን ሊያስጠብቁ እንደማይችሉ ተገምቶ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በተከለከለበት ሕገ-መንግሥት ላይ ብሔር ብሔረሰቦች የመገንጠል መብት ከተከበረላቸው ከመገንጠል ይልቅ አንድነትን ይመርጣሉ ተብሎ ታስቦ የመገንጠል መብት እንዲኖራቸው ተደርጓል፡፡ ብሔር ብሔረሰቦች ዞሮ ዞሮ የሰዎች ስብስብ ናቸውና እነሱ መብቱ ሲሰጣቸው መገንጠልን አይመርጡም ከተባለ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ "አርሶ አደሮች የመሸጥ የመለወጥ መብታቸው ሲከበር መሬታቸውን ከመሸጥ ይልቅ አለመሸጥን ይመርጣሉ" ለምን ማለት እንደማይቻል ግልጽ አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ግልጽ የምክንያታዊነት ቅራኔ (Fallacy) በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ስናይ የምንገነዘበው ነገር ኢህአዴግ እያንዳንዱን ጉዳይ

በተለየ ሁኔታ የሚመዝንበት ከአገራዊ ጥቅም የተለየ የራሱ ድርጅታዊ ፖለቲካዊ ምክንያት ያለው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-መንግሥቱን በጅምላ የኢህአዴግ የፕሮግራም ግልባጭ አድርገው እንዲያዩትና እንዲያጥላሉት የሚያስችል ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

መሬትን በተመለከተ የሚታየው ሌላው የምክንያታዊነት ቅራኔ ኢህአዴግ ብዙውን ጊዜ “አርሶ አደሩ ሕዝብ መሬቱን መሸጥ-መለወጥ አይፈልግም” በማለት ከሚያቀርበው የመከራከሪያ ነጥብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከአምስት ዓመት በፊት የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር ባካሄደው አንድ ጥናት አብዛኛው አርሶ አደር መሬቱን መሸጥ መለወጥ እንደማይፈልግ በመግለፁ ኢህአዴግ ይህንን የጥናት ውጤት የራሱ የአስተሳሰብ ትክክለኛነት ማረጋገጫ አድርጐ ለማቅረብ ሲሞክር ታይቷል፡፡ በወቅቱ ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማኅበር መሪ የነበሩት ሰዎች ጭምር የጥናት ውጤቱ የኢህአዴግን አስተሳሰብ የሚያጠናክር መስሎ ስለታያቸው አንጉል ምክንያት በማቅረብ የራሳቸውን የጥናት ውጤት “አርሶ አደሩ የተለያዩ አማራጭ ሃሳቦች በክርክር መልክ ቢቀርቡለት የጥናት ውጤቱ የተለየ ሊሆን ይችላል” በማለት ሊያድበሰብሱት ሲሞክሩ ታይቷል፡፡ ነገር ግን በዚያ ጥናት ውጤት መሠረት አብዛኛው ገበሬ መሬቱን መሸጥ መለወጥ የማይፈልግ መሆኑን ማረጋገጡ በመሬት ጉዳይ ላይ ኢህአዴግ የሚያራምደው አቋም ትክክል መሆኑን ሳይሆን ስህተት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነበር፡፡

ምክንያቱም የጥናቱ ውጤት አብዛኛው አርሶ አደር ሕይወቱን ለመሠረተበት መሬት ምን ያህል ፍቅር እንዳለውና በሕገ-መንግሥቱ መሬትን መሸጥ ተፈቀደም አልተፈቀደም መሬቱን ሸጦ ለችግር ሊጋለጥ የሚችልበት ዕድል ዝቅተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳረጋገጠውም ሆነ በተለምዶ እንደሚታወቀው አርሶ አደሩ ሕዝብ መሬቱን የመሸጥ የመለወጥ ፍላጐት የለውም እስከተባለ ድረስ “መሬት መሸጥ-መለወጥ የለበትም” ብሎ በሕገ-መንግሥት መደንገግ ጉዳት እንጂ ጥቅም አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም ከመጀመሪያው መሬቱን መሸጥ-መለወጥ የማይፈልገው አርሶ አደር ጉዳዩ በሕገ-መንግሥት ተፈቀደም-አልተፈቀደም መሬቱን መሸጥ የማይፈልግ ሲሆን፣ በሆነ ጥሩ አጋጣሚ ኑሮአቸውን ለመለወጥ የሚያስችል ዕድል አጋጥሟቸው ለበጎ ለውጥ መሬታቸውን ለመሸጥ ለመለወጥ የሚፈልጉ አርሶ አደሮች ቢኖሩ ግን ሕገ-መንግሥቱ ይህንን መብታቸውን ይነፍጋቸዋል፡፡

ስለዚህ የኢህአዴግ አመለካከት በተወሰነ ደረጃ ትክክል ሊሆን ይችል የነበረው አብዛኛው አርሶ አደር ሕዝብ መሬቱን መሸጥ መለወጥ የሚፈልግ ቢሆን ነበር፡፡ አርሶ አደሩ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሆኖ ቢገኝም እንኳ መብቱን በሕገ-መንግሥት እንዲገደብ ማድረግ

ተገቢ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም አንድ ኅብረተሰብ የቱንም ያህል ለጥቅሙ የማይቆረቆር ነው ተብሎ ቢታመን እንኳን ክልከላን መንግሥት በኃይል ሊጭንበት ይችላል እንጂ “መንግሥት ሆይ -! እባክህን ጥቅሜን ራሴ መጠበቅ አልችልምና በሕገ-መንግሥት መብቴን ገድብልኝ” ብሎ የሚጠይቅ ኅብረተሰብ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግ በተለያዩ አቀራረብ በሕገ-መንግሥቱ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ መከልከሉ የሕዝቡ ፍላጐት እንደሆነ አድርጐ መናገሩ አሳማኝ የሚሆንበት መንገድ የለም፡፡

ከእንዲህ ዓይነቱ የምክንያታዊነት ቅራኔ በተጨማሪ በተግባር አፈጻጸም ላይ የሚታየው ቅራኔ፣ መሬት አንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሕገ-መንግሥት የተከለከለ ቢሆንም ይህ ክልከላ ለዜጐች እንጂ ለመንግሥት የማይሰራ መሆኑ ላይ ነው፡፡ በአንድ ሕገ-መንግሥት ላይ መሬት አይሸጥም-አይለወጥም ተብሎ ከተደነገገ፣ ይህ ዓይነቱ ድንጋጌ ለመንግሥትም ሆነ ለዜጐች እኩል መሥራት ያለበት ቢሆንም በተግባር ግን መንግሥት ከዚህ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ በተቃራኒ መሬትን በመሸጥ ተግባር ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት በተለይም በከተሞች ዙሪያ መንግሥት አርሶ አደሮች የያዙትን መሬት ለካሬ ሜትር በሳንቲም ደረጃ ዝቅተኛ ግምት በመስጠት እያስለቀቀ እሱ ግን ይህንን ከገበሬዎች የወሰደውን መሬት ለግል ባለሀብቶች በካሬ ሜትር በሺህ ብሮች ደረጃ በመሸጥ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡

እዚህ ላይ መንግሥት መሬትን ለግል ባለሀብቶች እየሸጠ ያለው በሽያጭ ሳይሆን በሊዝ ኪራይ ነው የሚል ክርክር ሊነሣ ይችላል፡፡ ነገር ግን በ99 ዓመት የሊዝ ኪራይ መሬትን ለባለሀብቶች በሊዝ መልክ መስጠት ሽያጭ ነው ሊባል አይችልም ከተባለ ይኸው ለ99 ዓመት መሬትን በሊዝ ኪራይ የማስተላለፉ መብት ለዜጐች ጭምር ቢሰጥ ኖሮ መሬት ይሸጥ-አይሸጥ የሚለው ጉዳይም አከራካሪ ጥያቄ ሆኖ ሊነሣ አይችልም ነበር፡፡ መንግሥትም እንዲህ ዓይነቱን መብት ለሕዝቡ ለመስጠት ያልፈለገው በሌላ ምክንያት ሳይሆን መሬትን ለ99 ዓመት በሊዝ ማከራየት መሬትን ከመሸጥ የተለየ ትርጉም እንደሌለው ስለተገነዘበ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ መንግሥት ከመሬት ሽያጭ የሚያገኘውን ገንዘብ መልሶ የሚያውለው ለኅብረተሰብ ጥቅም ስለሆነ መንግሥት መሬትን ቢሸጥ ምን ችግር አለው? የሚል ምክንያታዊ ክርክር ሊነሣ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ክርክር በጥሬው መቃወም ባይቻልም መሠረታዊ የሕግ ጥያቄ ግን ያሥነሳል፡፡ ምክንያቱም መንግሥት መሬትን እንዲሸጥ መፍቀዱ ተገቢ መሆኑ ከታመነበት አስቀድሞ በሕገ-መንግሥቱ ላይ ይኸው በግልጽ መፈቀድ ነበረበት እንጂ መንግሥት በአንድ በኩል የሕዝቡን መብት በሕግ ገድቦ፣ በሌላ በኩል ግን እሱን የመሬት “ባላባት” በመሆን ሕጉን በሊዝ ኪራይ ስም ሸውዶ የሚያልፍበትን አሠራር መጠቀሙ ተገቢ ሊሆን አይችልም፡፡

ይህ ተገቢ ነው ከተባለ እንዲህ ዓይነቱ የአሠራር መብት ለመንግሥት ብቻ ሳይሆን ለሕዝቡም የማይሰጥበት ምክንያት የለም፡፡

የ99 ዓመት የመሬት የሊዝ ኪራይ መሬትን መሸጥ ማለት አይደለም ከተባለ አርሶ አደሩም ሆነ የመሬት ባለይዞታ የሆነው የከተማ ነዋሪ በቀጥታ ከመሬት ፈላጊ ባለሀብቶች ጋር ያለመንግሥት ጣልቃ ገብነት ተደራድሮ መሬቱን ለ99 ዓመት በሊዝ የሚያከራይበት መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ አሁን ባለው አሠራር ግን ራሱ ኢህአዴግ መሬት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ አደረግሁ የሚልበት ዋና ምክንያት አርሶአደሩ የመፈናቀል ችግር ይገጥመዋል የሚል ቢሆንም አርሶአደሩ በራሱ በመንግሥት ርምጃ ከመፈናቀል ያልዳነ ሲሆን ከመሬት ሽያጭ የሚገኘውን ከፍተኛ ጥቅምም እያገኘው ያለው ከመሬቱ ላይ የሚፈናቀለው አርሶአደር ወይም የከተማ ነዋሪ ሳይሆን መንግሥት ነው፡፡ ስለዚህ አርሶ አደሩ የተነፈገው መብት መሬቱን የመሸጥ የመለወጥ ብቻ ሳይሆን መሬቱን ለረዥም ጊዜ የማከራየትና ከኪራዩ የሚገኘውን ጥቅም የማግኘት መብቱን ጭምር ነው ማለት ነው፡፡

መንግሥት መሬትን ቢሸጥ ምን አለበት? የሚለው ክርክር ከሕገ-መንግሥቱ ድንጋጌ አኳያ በግልጽ እስካልሠፈረ ድረስ የሕግ ጥያቄ የሚያስነሣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከነፃ-ገበያ ሥርዓት አስተሳሰብ ጋር በተያያዘም ሌላ ጥያቄ ያሥነሳል፡፡ መንግሥት መሬትን ቢሸጥና ቢለውጥ በራሱ ጠቃሚ እንጂ ጉጂ ባይሆንም መንግሥት እንዲህ ዓይነቱ መብት የሚኖረው ዜጐች መሬታቸውን መሸጥ መለወጥ በተከለከሉበት ሁኔታ ሲሆን ግን መሠረታዊ የነፃ-ገበያ አስተሳሰብን የሚጻረር ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በነፃ-ገበያ ሥርዓት ከመንግሥትም በላይ ለአገርና ለሕዝብ የሚበጅ የልማት ዕድገት ያመጣል ተብሎ የሚታሰበው በግሉ ክፍለ-ኢኮኖሚ የሚደረገው ኢንቨስትመንት ነው፡፡ ግለሰቦች የሚያገኙት ገንዘብ ለግላቸው እንጂ ለአገር እንደማይጠቅም አድርጐ ማሰብ ከነፃ-ገበያ አስተሳሰብ የሚጋጭ ብቻ ሳይሆን ለካፒታሊስት ሥርዓት ግንባታም የማያበቃ አስተሳሰብ ነው፡፡ አንድ ግለሰብ ለራሱ መሠረታዊ ፍላጐቱን ካሟላ በኋላ የሚኖረውን ሀብት በልማት ሥራ ላይ ሲያውለው በዚያ ልማት ዜጐችና አገርም ቀጥተኛ ተጠቃሚ ስለሚሆኑ መንግሥትን በተለየ ሁኔታ ለሕዝብ ጥቅም የሚሠራ፣ ግለሰብን ግን ለራሱ ግላዊ ጥቅም ብቻ የሚሠራ ኪራይ ሰብሳቢ እንደሆነ አድርጐ ማሰብ ከመሠረታዊ የነፃ-ገበያ አስተሳሰብ ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡

በመሬት ጉዳይ ከዚህ በላይ ለመጠቃቀስ የተሞከሩት ከምክንያታዊነት ቅራኔ ጋር የተያያዙ ድክመቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት መመለስ ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ ግን መሬት በኢትዮጵያ የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት ቢሆን ምን ጥቅም ወይም ጉዳት አለው?

የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ከላይ በዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ላይ ለማየት እንደተሞከረው ሁሉም የአገሪቱ መሬት የግል ንብረት ይሁን የሚለው የአንዳንድ ፓርቲዎች ክርክር ከወቅቱ የአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሊሠራ የማይችል መሆኑን ስላዬን፣ አሁን እዚህ ላይ በኢትዮጵያ መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት ቢሆን ምን ጥቅምና ጉዳት እንዳለው ለማየት ስንሞክር እያወራን ያለነው ስለአጠቃላዩ የአገሪቱ መሬት ሳይሆን ስለተወሰነው ወይም ስለ ከፊሉ የአገሪቱ መሬት መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በኅብረተሰቡ ውስጥ አንዳንድ ለግል የሕይወት ደህንነታቸው ኃላፊነት የማይሰማቸው ሰዎች ሊኖሩ ቢችሉም አብዛኛው የሰው ልጅ ግን ለግል ሕይወቱ ተገቢውን ኃላፊነት መውሰድ የሚችል መሆኑንና ከዚህም አንጻር በተለይም የኢትዮጵያ አርሶ አደር ለመሬቱ ልዩ ፍቅር ያለው ሕዝብ መሆኑን ቀደም ብለን ለማየት ሞክረናል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የኢትዮጵያ አርሶ አደር ለግል ሕይወቱ ኃላፊነት መውሰድ የማይችል ደካማ ሕዝብ ነው የሚል ሌላ አሳማኝ ክርክር እስካልመጣ ድረስ አንድ ለግል ሕይወቱ ኃላፊነት የሚሰማው ሰው ንብረቱን መሸጥ ቢፈልግ በበቂ ምክንያትና ለበለጠ ጥቅም እንደሚሆን አከራካሪ አይሆንም፡፡ ይልቁንም ጉዳዩን ከእኛ አገር ሕዝብ የቆዬ አስተሳሰብ አንጻር ስናየው ትልቁ ችግር ሕዝቡ ለመሬት ካለው ልዩና ከገደብ ያለፈ ፍቅር የተነሣ የበለጠ ጥቅም ለሚያገኝበትና ኑሮውን ለመለወጥ ለሚያስችለውም ጉዳይ ጭምር መሬቱን የመሸጥ ፍላጐት የሌለው መሆኑ ነው፡፡

እንኳንስ ሕይወቱን በመሬት ላይ የመሠረተው የአገራችን አርሶ አደር ሕዝብና አብዛኛው የከተማ ኗሪ የሆነው ሰው እስካሁን ድረስ መኖሪያ ቤቱን ወይም የቤት መኪናውን ለመሸጥ ሲፈልግ እንኳ ውስጥ ውስጡን ከደላላ ጋር በመነጋገር ነው እንጂ "ይሸጣል" የሚል ይፋ ማስታወቂያ አውጥቶ ንብረቱን መሸጥ ያሳፍረዋል፡፡ የተሻለ ሥልጣኔ የሚታይበትን የአዲስ አበባ ከተማን እንደ አንድ ምሳሌ ብንወስድ ብዙ በመቶ ሺዎች ገንዘብ የሚያወጣ አሮጌ ቤት የተሠራበት ቦታ ያላቸውና በልቶ ለማደር የሚያቅት የድህነት ኑሮ የሚኖሩ ሰዎች ቤታቸውን ሸጠው ኑሮአቸውን ማሻሻል ሲችሉ፣ ቤት መሸጥን እንደ ነውር በመቁጠር ብቻ በድህነት ሲማቅቁ ኖረው ለመሞት የሚበቁ አሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ በሌላው ዓለም ታዋቂ ሙያ የሆነው ቤትና ቦታን የማሻሻጥ የድለላ ሥራ በእኛ አገር እንደነውር፣ አንዳንድ ጊዜም እንደስድብ የሚቆጠር ነው፡፡

በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ቤትና መሬትን የመሸጥ ጉዳይ ከከተማው በበለጠ በነውርነት የሚታይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስለዚህ የአንዳንድ ግለሰቦች ግዴለሽነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በእንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ውስጥ ያደገና ያለ ሕዝብ ሐፍረቱን ሰብሮ መሬቱን ሊሸጥ

የሚችለው ለተሻለ ጥቅም ስለሚሆን መሬት መሸጥን እንደ ስህተትና ጥፋት አድርጐ መቁጠር ከጅምሩ ተገቢ አስተሳሰብ አይሆንም። ከአስተሳሰብ ባለፈም ጉዳዩን ከተጨባጭ እውነታ ጋር አያይዘን ልናየው ብንሞክር በአሁኑ ወቅት በአገራችን መሬት የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት ቢሆን ከግልም ሆነ ከአገር ጥቅም አንጻር ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ በብዙ እጅ የሚበልጥ ይሆናል። የጥቅምና የጉዳትን ጉዳይ ከማየታችን በፊት በቅድሚያ ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው ቁምነገር መሬትን መሸጥ የሚፈልገው ብቻ ሳይሆን መግዛትስ የሚፈልገው ማን ነው? የሚለው ጥያቄ ነው።

ከወቅቱ የአገራችን ሁኔታ አንጻር እንደምንረዳው ከአጠቃላዩ የአገራችን ሕዝብ ውስጥ መሬት የመግዛት አቅም ያላቸው ሰዎች በቁጥር አነስተኛ ሲሆኑ እነዚህም ሰዎች በአብዛኛው መሬት ለመግዛት የሚፈልጉት ለግብርና ሥራ ሳይሆን ለመኖሪያ ቤትና ለተለያዩ የኢንቨስትመንት ግንባታ ነው። ከአካባቢም አኳያ መሬት የመግዛት ፍላጐት ያለው በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ሳይሆን በዋናነት በአገሪቱ ከተሞች አካባቢ ነው። በአብዛኛው የአገሪቱ የገጠር ክፍል መሬት ሻጭና ገዥ ለመሆን የሚያስችል የአቅም ልዩነት በሕዝቡ መካከል የሌለ ሲሆን በመሬቱ ላይ የሚካሄደው ግብርና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ጥቅም የሚያስገኝ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት መሬትን የመግዛት ፍላጐት ገና አላደገም። በተለይም አብዛኛውን የአገሪቱን ክፍል የሚሸፍነው የአገራችን የሰሜን፣ የምሥራቅና የደቡብ ምሥራቅ ክፍል ለምነቱን ያጣ ወይም የዝናብ እጥረት ያለበት አካባቢ በመሆኑ በዚህ የአገራችን አካባቢ መሬትን የመግዛት የጐላ ፍላጐት የለም።

ከባለሀብቶች ባህሪና ፍላጐት አኳያም የመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ የገበያ አቅርቦትና የሰላም ሁኔታ በቀዳሚነት ግምት ውስጥ የሚገቡ በመሆናቸው በአገራችን መሬትን የመግዛት ፍላጐት ያለው በዋናነት በአዲስ አበባ ዙሪያና በአገሪቱ ዋና ዋና ከተማዎች አካባቢ ነው። ስለዚህ ዋናው ጥያቄ በእነዚህ መሬትን የመግዛት ፍላጐት ባለባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች አርሶ አደሩ መሬቱን ቢሸጥ ከግሉም ሆነ ከአገሪቱ ጥቅም አኳያ ምን ጉዳት አለው? የሚለው ነው። ጉዳዩን ከአርሶ አደሩ ጥቅም አኳያ ስናየው አርሶ አደሩ በአሁኑ ወቅት መንግሥት እያደረገው እንደሚገኘው መሬቱን ከባለሀብቶች ጋር በቀጥታ ተደራድሮ ለ99 ዓመት በሊዝ ቢያከራይ ወይም ቢሸጥ በብዙ መልኩ ይጠቀማል እንጂ አይጐዳም።

በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ከተሞች አካባቢ የሚገኝ መሬት የሚያወጣውን ዋጋ ስናይ የተጋነነውን ዋጋ ትተን አንድ የእርሻ መሬት በአነስተኛ ከ200 ሺህ ብር በላይ ይሸጣል። አንድ ገበሬ ከአንድ ሄክታር ባነሰ እርሻው ላይ በዓመት የሚያመርተውን የእህል ዋጋ ከዚህ መሬቱን

ሽጦ ከሚያገኘው ገንዘብ ጋር ስናነፃጽረው አንድ ገበሬ በ20 እና በ25 ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚያመርተው እህል ተደምሮ 100 ሺህ ብር ሊያወጣ አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት መንግሥት ከእርሻቸው ለሚፈናቀሉ ገበሬዎች በካሳ መልክ ለአሥር ዓመት ቀለብ ብሎ የሚሰጣቸው ገንዘብ ከ10 እስከ 20 ሺህ ብር መሆኑ ሲታይም በራሱ በመንግሥት መረጃም አርሶአደሩ ሕዝብ ከመሬቱ በማምረት የሚያገኘው ገንዘብ ምን ያህል ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አንድ አርሶ አደር ይቅርና አንድ የመጀመሪያ ዲግሪ የያዘ ሰው ሙስና ውስጥ ካልገባ በስተቀር 200 ሺህ ብር ከ20 ዓመት በአነሰ ጊዜ ሠርቶ ሊያገኝ አይችልም፡፡ ጉዳዩን ከአገራችን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ጋር አያይዘን ስናየውም የበለጠ ትርጉም ያለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን በአማካይ የአንድ ዜጋ ዓመታዊ ገቢ 190 (በመንግሥት መረጃ) የአሜሪካን ዶላር አካባቢ ሲሆን በዚህ ስሌት አንድ የአገራችን አርሶ አደር 200 ሺህ ብር ለማግኘት በአማካይ ከ150 ዓመት ያላነሰ ጊዜ ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡

ስለዚህ አንድ አርሶ አደር ዕድሜ ልኩን ከእነ ቤተሰቡ ደክሞ የማያገኘውን ገንዘብ በዜግነቱ በእጁ የያዘውን መሬት ሽጦ በአንድ ጊዜ ቢያገኝና ይህንን ገንዘብ በሌላ የሥራ መስክ ኑሮውን ሊለውጥበት ቢችል አርሶ አደሩ ከመሬት ሽያጩ ተጠቀመ እንጂ ተጐዳ ሊባል አይችልም፡፡ መሬቱን የሚሸጠው አርሶ አደር ያገኘውን ገንዘብ ተጠቅሞ በሌላ የተሻለ መስክ ለመሰማራት የሚኖረው ዕድል እንደተጠበቀ ሆኖ መሬቱን የሚገዙ ባለሀብቶች በሚፈጥሩት የሥራ መስክ እንደገና ተቀጣሪ ሆኖ የመሥራት ዕድልም ሊኖረው ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ባለሀብት በገዛው መሬት ላይ አንድ የጫማ ፋብሪካ ወይም የአበባ እርሻ ቢያቋቁምበት ቢያንስ ከ50 ያላነሱ ሠራተኞች ሊቀጥር ይችላል፡፡ ስለዚህ መሬቱን የሸጠው አርሶ አደር ከመሬቱ ሽያጭ ያገኘውን ገንዘብ በእጁ ይዞ እንደገና በእነዚህ የሥራ መስኮች ተቀጥሮ የመሥራት ዕድልም ሊኖረው ይችላል ማለት ነው፡፡

እንዲያውም መሬቱን የሸጠው አርሶ አደር ራሱ ብቻ ሳይሆን ሚስቱና ለሥራ የደረሱ ልጆቹ ተቀጣሪ ሊሆኑ ስለሚችሉ አርሶ አደሩ እንደ አንድ ቤተሰብ በአንድ እርሻ ላይ ሲያገኝ ከነበረው የበለጠ ጥቅም በጫማ ፋብሪካው ወይም በአበባ እርሻው ተቀጥሮ ሊያገኝ ይችላል፡፡ አንድ አርሶ አደር ከሚስቱና ከሁለት ለሥራ የደረሱ ልጆቹ ጋር ለእያንዳንዳቸው ቢያንስ በ250 ብር የወር ደመወዝ ቢቀጠሩ ቤተሰቡ በወር የ1000 ብር ገቢ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ገቢ በራሱ በእርሻው ላይ ቀድሞ ከሚያገኘው ገቢ የተሻለ ሲሆን አንድ መሬቱን በ200 ሺህ ብር ሽጦ ጥሪት የያዘ አርሶ አደር ይህንን ያህል ደመወዝ በወር የሚያገኝበት ሥራ በአካባቢው ከተፈጠረ መሬቱን በመሸጡ በብዙ እጥፍ ተጠቀመ እንጂ ተጐዳ ሊባል አይችልም፡፡ እንዲያውም እስከ

ወዲያኛው ከድህነት ሊያወጣው ከማይችል የግብርና ሕይወት ራሱም ሆነ ልጆቹ እንዲላቀቁና ወደ አዲስ የሕይወት አቅጣጫ እንዲገቡ ዕድል ሊፈጥርላቸው ይችላል፡፡

ከአርሶ አደሩ የግል ሕይወት ጋር በተያያዘ ያለው ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ጉዳዩን ከአገር አንጻር ስናየውም የበለጠ ጠቃሚ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የመጀመሪያው ከመሬት መሸጥ-መለወጥ ጋር እንደ አገር የሚገኘው ጥቅም መሬት እህል የሚበቅልበት ብቻ ሳይሆን ካፒታል የሚያፈራ ንብረት እንዲሆን ከማድረጉ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአንድ በኩል መሬት በባንክ እንደማንኛውም ንብረት ተገምቶ ብድር ለመበደር የሚያስችል ንብረት የሚሆን ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሩ መሬቱን አስይዞም ሆነ ሸጦ በሚያገኘው ገንዘብ ወደ ንግድ፣ ወደ አገልግሎት፣ ወደ አነስተኛና ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚገባበት ዕድል ይፈጠራል፡፡ ይህም በራሱ በሌሎቹ አገሮች የዕድገት ሂደት እንደታየው የገበሬው ቁጥርና አገሪቱ በግብርና መስክ ጥገኛ መሆኗ በከፍተኛ መጠንና ፍጥነት እየቀነሰ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡

የመሬት መሸጥ-መለወጥ ሁለተኛ ጥቅም ለኢንቨስተሮች ከሚፈጥረው ምቹ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ኢንቨስተሮች በአንድ የሥራ መስክ ለመሠማራት ሲፈልጉ ግምት ውስጥ ካሚያስገቧቸው መስፈርቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ የገበያ አቅርቦትና የሰላም መኖር የመሳሰሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በሌሉበት አካባቢ ለአንድ ኢንቨስተር የቱንም ያህል ሰፊና ለም የሆነ መሬት መንግሥት በነፃ ቢሰጥ ኢንቨስተሮች የማልማት ፍላጐት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን መስፈርቶች በአንፃራዊነት ሊያሟላ የሚችል መሬት ሊገኝ የሚችለው ደግሞ በዋናነት በአዲስ አበባ ዙሪያና በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች አካባቢ ስለሆነ በእነዚህ አካባቢዎች ያለው መሬትም እንደ ማንኛውም የአገሪቱ መሬት በአብዛኛው መሬቱን የመሸጥ የመለወጥ መብት በሌለው አርሶአደር እጅ የተያዘ ነው፡፡

ስለዚህ በእነዚህ አካባቢዎች በአርሶአደሩ እጅ ያሉትን መሬቶች ገዝቶ የማልማት ዕድል እስከሌለ ድረስ ኢንቨስትመንት በአገራችን በሚፈለገው መጠን ሊስፋፋ አይችልም፡፡ ኢንቨስትመንት መስፋፋት ካልቻለ ደግሞ ዞሮ ዞሮ አገሪቱን ከእርሻ ጥገኝነት ሊያላቅቅ የሚችል የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ሊፈጠር ስለማይችል የመሬት መሸጥና መለወጥ ከዚህ አንጻር የሚኖረው ጥቅም ቀላል ትርጉም ያለው አይደለም፡፡ ከእዚሁ ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ በመሬት መሸጥ መለወጥ የሚገኘው ሌላው ጥቅም ሰፊ የሥራ ዕድል የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ በምሳሌነት ለመጥቀስ እንደተሞከረው የአንድ አርሶአደር ይዞታ የነበረ የእርሻ መሬት ቢያንስ ከ50 ሠራተኛ በላይ ሊቀጥር ወደሚችል የጫማ ፋብሪካነት ወይም የአበባ እርሻነት

ሲቀዬር በርካታ ዜጐቻችንን ወደ ሥራ ገበታ በማስገባት ረገድ የሚያመጣው ለውጥ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ የአበባ ኢንቨስትመንት በተጀመረ በጥቂት ዓመታታ ውስጥ ከ55,000 በላይ የሆኑ ሠራተኞችን መቅጠር የቻለ ሲሆን ለአበባ ኢንቨስትመንት ተብሎ ካሣ ተከፍሎት ከመሬቱ የተነሣው የአርሶ አደር ብዛት ግን በመቶዎች የሚቆጠር ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው አንድ አርሶ አደር ከአመቱ ቀናት ውስጥ ለሃምሳ ቀናት እንኳ ሙሉ ጉልበቱንና ጊዜውን ጥቅም ላይ የማያውልበት አንድ የእርሻ መሬት ከሃምሳ በላይ ሠራተኞች ለሙሉ ዓመት ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን ወደሚያፈሱበት የኢንቨስትመንት መስክ ሲቀየር በአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ሊያመጣ የሚችለው የምርት ዕድገት ምን ያህል ከፍተኛ እንደሚሆን የሚያሳይ ነው፡፡

የመሬት መሸጥ-መለወጥ ሊያስገኘው የሚችለው ሦስተኛውና ዋናው ጥቅም ከአካባቢ ጥበቃና ከሕዝብ ቁጥር መቀነስ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ መንደርደሪያ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት መሸጥ-መለወጥ ጉዳይ ትርጉም ያለው መብት ሊሆን የሚችለው ከተሟላ የባለቤትነት መብት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ የተሟላ ባለቤትነትም በራሱ ብቻውን የሚመጣ ጉዳይ ሳይሆን እግረ መንገዱን በአገሪቱ ወደፊት መሬትን እንደገና የማከፋፈልን አሠራር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚያስቀር ውጤት ይዞ የሚመጣ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት አለው ሊባል የሚችለው በእጁ የያዘው መሬት ወደፊት በማንኛውም አካል የማይቀማ ወይም ተሸርፎ ለሌላ የማይሰጥ የግል ንብረቱ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለሆነ መሬት የግል ንብረት እንዲሆን ሲደረግ ከዚያ በኋላ መንግሥት በአርሶ አደሩ ባለቤትነት የተያዘውን መሬት እንደገና መሬት ለሌላቸው ወይም ለአነሳቸው ሰዎች የማከፋፈል መብት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ በርግጥ መንግሥት አንድን በየትኛውም ሁኔታ የተያዘ መሬት ለተሻለ የኅብረተሰብ ጥቅም ሲፈልገው ተገቢ ካሣ ከፍሎ የማስለቀቅ መብቱ ምንጊዜም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡

ስለዚህ ከዚህ የተሟላ ዘላቂ የመሬት የባለቤትነት መብት ጋር በተያያዘ የአካባቢ ጥበቃንና የሕዝብ ቁጥር መቀነስን በተመለከተ የሚገኙ በጎ ለውጦች ይኖራሉ፡፡ የመጀመሪያው አርሶ አደሩ በእጁ የያዘው መሬት እስከ መጨረሻው የራሱ የግል ንብረት መሆኑን በርግጠኝነት ሲያውቅ አፈሩን የመንከባከብና ረዥም ዕድሜ የሚኖራቸውን ዛፎች የመትከል ፍላጐት ስለሚኖረው እንዲህ ዓይነቱ የአርሶ አደሩ ፍላጐት በአካባቢ ጥበቃ ላይ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን አርሶ አደሩ መሬቱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ የሕዝቡ ቁጥር ሲጨምር እንደገና በመንግሥት ተከፋፍሎ ለሌሎች ተቆርሶ ሊሰጥ እንደሚችል ስለሚያውቅ በመሬቱ ላይ ቋሚ የሆነ እንክብካቤ ለማድረግ አይነሳሳም፡፡ በተለይም አብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ ከእርሻ ሥራና

ከከብት እርባታ ጋር በተያያዘ የግብርና ሥራ ላይ የተሰማራ በመሆኑ የአገሪቱ መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየተራቆተ መጥቷል፡፡ መሬቱ ለንፋስና ለጎርፍ አደጋ በመጋለጥና ከአቅም በላይ አገልግሎት በመስጠት ዕረፍት በማጣቱ ምክንያትም ምርታማነቱን ከማጣቱ በላይ በውስጡ ለሚገኙ ነፍሳት መርዛማ እየሆነ መምጣት ጀምሯል፡፡ ይህ ችግር ወደ ፊት እየተባባሰ ከመጣ በአገሪቱ አካባቢያዊ ሁኔታ (environment) ላይ የሚያስከትለው ቀውስ ቀላል አይሆንም፡፡

በተጨማሪም አርሶ አደሩ ወደፊት የመሬት ክፍፍል እንደሚኖር ስለሚያውቅና በዚያ የመሬት ክፍፍል በእጁ የያዘው መሬት እንዳይቀነስበት ስለሚፈልግ ብዙ ልጆችን መውለድን እንደ አንድ መፍትሄና ዋስትና አድርጎ ያየዋል፡፡ መሬቱ እስከወዲያኛው ተቀርሶ የማይሰጥበት መሆኑን ቢያረጋግጥ ግን ተጨማሪ ልጅ መውለድን እንደመፍትሄ ማየቱን ከማቆምም በተጨማሪ የወለዳቸው ልጆች ወደፊት ከመንግሥት መሬት የማግኘት ዕድል እንደሌላቸው ሲያውቅ ከግብርና ውጭ ወደ ሆነ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲገቡ የሚያስችላቸውን ጥረት ማድረግ ይጀምራል፡፡ ይህ በራሱ የሕዝብ ቁጥርን በመቀነስም ሆነ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በማምጣት ረገድ የማይናቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

የመሬት መሸጥ መለወጥ አራተኛ ጥቅም አገሪቱ በሂደት ከተበጣጠቀ የመሬት ይዞታ እንድትወጣና መካከለኛና ሰፋፊ መጠን ያላቸው እርሻዎች እንዲስፋፉ ዕድል የሚፈጥር መሆኑ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የአገራችን አርሶ አደር አማካይ የመሬት ይዞታ ወደ 0.5 ሄክታር እየወረደ ሲሆን በዚህ ይዞታ ኢትዮጵያን በመሰለ አገር አንድ አርሶአደር ቤተሰብ የራሱን ቀለብ ከመቻል አልፎ ለሌላ የሚተርፍ ምርት ያመርታል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ እዚህ ላይ "ታዲያ ትርፍ ካላመረተ ለምን እህል ገበያ እያወጣ ይሸጣል?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ነገር ግን በአሁን ወቅት ገበሬው ገበያ ላይ አውጥቶ ከሚሸጠው ምርት የሚያገኘውን ገንዘብ መልሶ ለሰላሱት (ለወጥ)፣ ለአልባሳትና ለተለያዩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ወጪ የሚያውለው እንጂ ተርፎት በካፒታልነት የሚቆጥበው ወይም ለሌላ ኢንቨስትመንት የሚያውለው ስላልሆነ ዞሮ ዞሮ የአርሶ አደሩ ምርት ከግል ፍጆታ ያለፈ ነው ሊባል አይችልም፡፡ እንዲያውም አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ አንድ ሦስተኛ የሚሆነው የአገራችን አርሶ አደር ርዳታ ካልተሰጠው በስተቀር በማንኛውም የአየር ሁኔታ የዓመት ቀለቡን አምርቶ መሸፈን የማይችል ሲሆን ቀሪው አርሶአደርም የዓመት ቀለቡን መሸፈን የሚችለው የተስተካከለ ጥሩ ዝናብ ከኖረ ብቻ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በውጤታማ ገበሬነት ሲሸለሙ የምናያቸው አብዛኛዎቹ አርሶ አደሮችም ትርፍ አምራች መሆን የቻሉት በተለያዩ ምክንያት ተጨማሪ መሬት ማረስ የቻሉና ከእህል ምርት ውጭ የሆነ ተጨማሪ የሥራ መስክ ውስጥ መሰማራት የቻሉ በመሆናቸው ነው፡፡

ችግሩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው በአገራችን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉ አሁን እየታየ እንዳለው ከግብርናው ዘርፍ በብዙ እጥፍ ማደግ እስካልቻለና አጠቃላይ መዋቅራዊ ሽግግር መምጣት እስካልቻለ ድረስ የአገራችን የእርሻ መሬት ወደፊት የበለጠ የሰው ኃይል ለመሸከም መገደዱ የማይቀር መሆኑ ነው። አሁን ያለው የአገሪቱ የሕዝብ ቁጥር ከ20 ዓመታት በኋላ ወደ 150 ሚሊየን ሲጠጋ የአርሶ አደሩ የመሬት ይዞታ እንደገና በግማሽ ለማነስ ስለሚገደድ ምርታማነት በዚያው መጠን መቀነሱ የማይቀር ይሆናል።

እንደዚያ ዓይነቱ አደጋ በአገራችን ከመከሰቱ በፊት በአንድ በኩል የኢንዱስትሪውና የአገልግሎት ዘርፉ በፍጥነት አድገው የአገራችንን ኢኮኖሚ የመምራት ሚና እንዲረከቡና ብዙ የሰው ኃይል የሚቀበሉበት ሁኔታ ቢፈጠር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመሬት ላይ ጥገኛ ከሆነው ሕዝብ የተወሰነው በመሸጥ-መለወጥ ሂደት ከእርሻ ሥራ እየለቀቀ እንዲወጣ ቢደረግ አገራችን የዕድገት መሰላልን በአግባቡ የምትቆናጠጥበት ዕድል ሊፈጠር ይችላል። አርሶአደሩ በዚህ ሁኔታ ከእርሻ ሥራ ለቆ እንዲወጣ ቢደረግ ጉዳዩ ከኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የመነጨ በጎ ለውጥ እንጂ ኢህአዴግ እንደሚለው አርሶአደሩን እንደገና ወደ ጭሰኛነት የተመለሰ ወይም በአራጣ አበዳሪዎች ተፅዕኖ ሥር የወደቀ ተደርጐ መታየት የለበትም። ሌላው ዓለም ሁሉ ለዕድገት የበቃው በዚህ ዓይነቱ ሂደት ውስጥ አልፎ በመሆኑ አገራችን ኢትዮጵያም እንዲህ ዓይነቱን የለውጥ ሂደት በድፍረት ከመጋፈጥ የተለየ አማራጭ ሊኖራት አይችልም። በየትኛውም ሁኔታ አርሶአደሩ ሕዝብ ከመሬቱ መለዬት የለበትም የሚል አቋም ይዘን የምንቀጥል ከሆነ አገሪቱ የገበሬ አገር እንደሆነች ትኖራለች እንጂ ለብልጽግና ልትበቃ አትችልም።

የመሬት መሸጥ-መለወጥ አምስተኛ ጥቅም ከአርሶ አደሩ የፖለቲካ ነፃነት ጋር የተያያዘ ነው። በአገራችን የእርሻ መሬት የመንግሥት መሆኑና የእርሻ መሬትን እንደገና የማከፋፈል ጉዳይ እስካልቆመ ድረስ አርሶአደሩ ሕዝብ የተሟላ የፖለቲካ ነፃነት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ የሚቻል አይደለም። ሕይወቱን በእርሻ መሬት ላይ የመሠረተው አርሶአደር በምርጫ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘውን ፓርቲ ሳይመርጥ ቢቀር ከምርጫ በኋላ በመሬቱ ላይ ሊከሰት ስለሚችለው ጣጣ በርግጠኛነት ማወቅ ስለማይችል በተሟላ ነፃነት የሚፈልገውን ፓርቲ ሊመርጥ አይችልም። አርሶአደሩ ህልውናው ከመሬት ጋር የተቆራኘ ከመሆኑና ከአገራችን የፖለቲካ ባህል አለመዳበር አንጻር እውነተኛ ዴሞክራሲ በአገራችን ቢሰፍን እንኳን መሬት የመንግሥት ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ አርሶአደሩ በቀላሉ ከፍርሐት ተላቆ ፖለቲካዊ ነፃነቱን በአግባቡ ተግባራዊ ሊያደርግ አይችልም።

ስለዚህ አርሶአደሩ ሕዝብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከጭሰኝነት ተላቆ እስከ መሸጥ-መለወጥ የሚደርስ የተሟላ የባለቤትነት መብት በመሬቱ ላይ ሲኖረው መሬት የፖለቲካ መጠቀሚያ መሆኑ በአገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ያከትማል ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ለማየት እንደሞከርነው የተወሰነው የአገራችን መሬት በአገራችን እንዲሸጥ-እንዲለወጥ ቢደረግ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት ይልቅ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም በብዙ ርቀት የበለጠ ይሆናል፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ እንደሚካሄድ ለውጥ ሁሉ በመሬት ጉዳይም የሚካሄድ ለውጥ የራሱ ጠቃሚና ጉጂ ጐን እንደሚኖረው የሚያጠራጥር ባይሆንም በአገባራዊነት ከጉዳቱ ጥቅሙ እስካመዘነ ድረስ መሬትን በመሸጥ በመለወጥ ሊከሰት የሚችለውን ጉዳት፣ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም በማያስቀር መንገድ የተለያዩ የአፈጻጸም ዘዴዎችን በመጠቀም ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ባይቻል እንኳ መቀነስ ይቻላል፡፡

አሁን ግን በአገራችን ተግባራዊ እየሆነ ያለው መሬትን በመሸጥ በመለወጥ ሊመጣ የሚችለውን አነስተኛ ችግር ለማስወገድ ተብሎ መሬትን በመሸጥ-መለወጥ ሊገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ማንም ኀሊና ያለው ሰው የመሬት መሸጥ መለወጥ ጉዳይ ለአገራችን አይጠቅምም ብሎ ቢያስብ እንኳን ጉዳዩ ምን ያህል አከራካሪ መሆኑን ግን ለመገንዘብ ሊያቅተው አይችልም፡፡ ነገር ግን ኢህአዴግ በመሬት ጉዳይ ላይ እጅግ የከረረና ከምክንያታዊነት የራቀ አቋም በመያዝ “መሬት ሊሸጥ-ሊለወጥ የሚችለው በመቃብሬ ላይ ነው” ማለቱ ሲታይ ኢህአዴግ የመሬትን ጉዳይ ከኢኮኖሚ ጉዳይነት ይልቅ የፖለቲካ ጉዳይ አድርጐ በማየቱ እንደሆነ ለመገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

የመሬት መሸጥ-መለወጥ ጉዳይ በአንድ በኩል ሌሎቹን በመሬት ጉዳይ ሊነሡ የሚገባቸውን አማራጭ ሃሳቦች ያደበዘዘ ጉዳይ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመሬት መሸጥ-መለወጥ ጉዳይም በራሱ ከጉዳቱ ይልቅ ጥቅሙ የሚያመዝን መሆኑን ለማሳየት ሲባል እንጂ የመሬት መሸጥ-መለወጥ ጉዳይ ዋና የመከራከሪያ ርእስ መሆን የሚገባው አይደለም፡፡ የአገራችን አርሶአደር በተለምዶ መሬትን በቀላሉ የመሸጥ-የመለወጥ ፍላጐት የሌለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ባልመጣበት በአሁኑ ወቅት መሬቱን እንዲሸጥ እንዲለወጥ ግፊት ማድረጉ ብዙም ትርጉም የሌለው በመሆኑ ከመሸጥ-መለወጥ ጉዳይ ይልቅ ትልቅ ትኩረት ማግኘት ያለበት ቁምነገር የመሬት የተሟላ የባለቤትነት ዋስትና ጉዳይ ነው፡፡

አርሶ አደሩ ሕዝብ በመሬቱ ላይ የተሟላ የባለቤትነት ዋስትና አለው ሊባል የሚችለው ግን በአንድ በኩል መብቱ እስከ መሸጥ-መለወጥ የሚደርስ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአገራችን ከአሁን

በኋላ ጥቅም ላይ በዋለው የእርሻ መሬት ላይ የሚካሄድ የእንደገና የመሬት ክፍፍል አለመኖሩ ሲረጋገጥ ስለሆነ የባለቤትነትና የዋስትናን ጉዳይ ከመሸጥ-ከመለወጥ መብት ነጥሎ ማየት አይቻልም። ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት አርሶ አደሩ መሬቱን እስከ 15 ዓመት የማከራየት መብት እንዲኖረው አድርጌአለሁ ማለቱና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ማደሉ በየትኛውም መመዘኛ የተሟላ የባለቤትነት ዋስትና ማረጋገጫ ሊሆን አይችልም። አስራ አምስት ዓመት በአንድ መሬት ላይ ቋሚ ኢንቨስትመንት ለማካሄድ የማይበቃ ጊዜ ሲሆን፣ ለአርሶ አደሩ እየተሰጠው ያለው የይዞታ ማረጋገጫ ይዞታ ደብተርም ዞሮ ዞሮ የሚያረጋግጠው ባለቤትነትን ሳይሆን ጊዜያዊ ይዞታን ስለሆነ በየገበሬ ማኅበሩ ጽሕፈት ቤት ከሚገኘው የይዞታ የምዝገባ ሰነድ የተለየ ፋይዳ የለውም።

ስለዚህ መሬት ይሸጥ-አይሸጥ ከሚለው የጠበበ ክርክር በተለየ ለአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የተሻለ አማራጭ ሊሆን የሚችለው ሦስት ዓይነት የመሬት ስሪትን ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይኸውም አንደኛው ስሪት - በአሁኑ ወቅት በአርሶ አደሩ እጅ በእርሻ ጥቅም ላይ ውሎ የሚገኘውንና የከተማ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤት ወይም ሌላ ማናቸውንም ዓይነት ቋሚ ግንባታ ያካሄዱበትን ቦታ መሸጥ-መለወጥን ባካተተ መልኩ የግል ንብረት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን በማድረግ አርሶ አደሩ በግሉም ሆነ አገሪቱ በጥቅል ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሞች እንድታገኝ ማድረግ የሚቻል ሲሆን፣ የከተማ ነዋሪዎች ተመሳሳይ መብት ሲኖራቸውም አሁን መንግሥት በእጁ የያዘውን መሬት እየቆነጠረ በውድ ዋጋ በመሸጥ የሚከተለውን አሠራር በመለወጥ ከፍተኛና ፈጣን ኢንቨስትመንት በከተሞችም እንዲፈጠር ያደርጋል። በአሁኑ ወቅት በከተሞች በግለሰቦች እጅ ተይዞ የሚገኘው መሬት ወደ ገበያ ሥርዓት ቢገባ የመሬት ዋጋ በአንፃራዊነት አሁን ካለው በብዙ እጥፍ ስለሚቀንስ ባለሀብቶች ያላቸውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በመሬት ግዥ ላይ እያዋሉ ለግንባታ ሥራ ወደ ብድር የሚገቡበት ሁኔታም በተወሰነ ደረጃ ስለሚቃለል ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት ረገድ የራሱ የማይናቅ በጎ ሚና ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ መሬት የሚያወጣው ዋጋ ከለንደንና ከኒውዮርክ ዋጋ የሚፎካከር መሆኑ ሲታይ በዚች ገና የዕድገት መሰላልን መቆናጠጥ ባልጀመረች ድሀና ኋላ ቀር አገር መሬት በዚህ መጠን መወደዱ ከእውነተኛ የገበያ ዋጋ ሳይሆን ሆን ተብሎ ከተዘረጋ የፖሊሲ ማነቆ የመነጨ ችግር መሆኑ ግልጽ ነው። መንግሥት መሬትን በእጁ ጨምድዶ በመያዝ ቀስ በቀስ እየቆነጠረ በመሸጥ በሚያገኘው ገንዘብ አገርን በዘላቂነት አለማለሁ ብሎ አጉል ቅዠት ውስጥ ከመግባት ይልቅ መንግሥት የግል ኢንቨስትመንቱን በማጠናከርና የታክስ

መሠረቱን በማስፋት ሥራ ላይ የበለጠ ቢያተኩር አገሪቱ በከፍተኛ ፍጥነት ማደግና የበለጠ ተጠቃሚ መሆን በቻለች ነበር።

ሁለተኛው ስሪት - አርብቶ አደሩ ሕዝብ የሚኖርባቸው የገጠር መሬቶችና በከተማ በቤት ሥራ ማኅበራት የተያዙ ቦታዎች አሁንም የኅብረተሰብ የጋራ መሬት ሆነው እንዲቀጥሉ ማድረግ ነው። አርብቶ አደሩ ሕዝብ በሂደት ሕይወቱ ወደ ሰፋሪነት እየተቀዬረ ሲሄድ የጋራ ይዞታው ቀስ በቀስ ወደ ግል ይዞታነት እየተቀዬረ እንዲሄድ ማድረግ ይቻላል። በከተማ በጋራ የተያዙ ቦታዎችም እንደ አመችነቱ በጋራ ተይዘው ሊቀጥሉም ሆነ በሂደት ወደግል ይዞታነት ሊከፋፈሉ ይችላሉ።

ሦስተኛው ስሪት - በአሁኑ ወቅት በገጠርም ሆነ በከተማ በግለሰብም ሆነ በማኅበር ያልተያዙ መሬቶች በመንግሥት ባለቤትነት ተይዘው እንዲቀጥሉ ማድረግ ነው። እነዚህ በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዙ መሬቶች በአንድ በኩል መንግሥት ለሕዝብ የጋራ ጥቅም በቋሚነት ለሚያገለግሉ ጉዳዮች ሊጠቀምባቸው የሚችል ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት በባለቤትነት የያዛቸውን መሬቶች በሂደት በሽያጭም ሆነ በምሪት ወደ ግልና የጋራ ይዞታነት ሊያስተላልፋቸው ይችላል። ከዚህ ውጭ የአገሪቱን መሬት በጥቅሉ የመንግሥት አድርጎ መቀጠሉም ሆነ የአገሪቱን መሬት በጥቅሉ የሚሸጥ የሚለወጥ የግል ንብረት እንዲሆን ማድረግ ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን ከመሆኑም በላይ አገራችን ወደ ዕድገት መሰላል በአግባቡና በብቃት እንድትቆናጠጥ የሚያስችል አይሆንም።

## ምዕራፍ አራት

### *አከራካሪ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች*

ኢትዮጵያ ለረዥም ዘመናት ከተለያዩ ባህላዊና ልማዳዊ ሕግጋት በተጨማሪ ፍትኃ ነገሥትን በመሰለ ዘውዳዊ አገዛዝን ለማጠናከር ተብሎ ጥቅም ላይ በዋለ የተጻፈ አፈ ታሪክ ቢያንስ ከ14ኛውና ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ስትመራ የነበረች አገር ነች፡፡ የተጻፈ ሕገ-መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት የተቀረጸው በ1924ዓ.ም በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ሲሆን በወቅቱ ይህን ሕገ-መንግሥት ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ለሕዝቡ ጥቅም ተብሎ ሳይሆን የዘውዱን ሥርዓት ፍጹማዊ የበላይነት የበለጠ ለማጠናከርና የአገሪቱን ገጽታ በዓለም አቀፍ መድረክ ለመለወጥ ታስቦ ነበር፡፡ በዚያው በንጉሡ ዘመን የኢትዮጵያንና የኤርትራን እንደገና መዋሐድ ተከትሎ ተሻሽሎ የወጣው ሕገ-መንግሥትም የንጉሡን ዘር ዘላለማዊ አልጋ ወራሽነት ከመደንገግ ያለፈ መሠረታዊ የይዘት ለውጥ አልነበረውም፡፡ ሦስተኛውና በደርግ ዘመን የወጣው ሕገ-መንግሥትም አገሪቱ ከምዕራብ አውሮፓ የፊውዳል ሕገ-መንግሥት በአንድ ጊዜ ወደ ምሥራቅ አውሮፓ የሶሻሊዝም ርእዮተ-ዓለም መሸጋገሯን ከማሳየት ባለፈ አገርና ሕዝብን የሚጠቅም ይዘት አልነበረውም፡፡ የሆኖ ሆኖ እነዚህ ከመንግሥት ለሕዝብ ተሰጡ የተባሉ የተለያዩ ሕገ-መንግሥቶች በየወቅታቸው የአገሪቱ የበላይ ሕግ ሆነው ሕዝቡ ሲገዛባቸውና ሲገለገልባቸው ኖሯል፡፡ ለአራተኛ ጊዜ የወጣው ሕገ-መንግሥት በ1987ዓ.ም ማለትም በአሁኑ የኢህአዴግ ዘመን የጸደቀው ሕገ-መንግሥት ነው፡፡

ይህ በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ የሚገኘው ሕገ-መንግሥት በአረቃቀቁና በአጸዳደቁ ሂደት ላይ ችግሮች የታዩበት ሰነድ ቢሆንም ወደፊት በሕዝብ ውሳኔ እስከሚሻሻል ድረስ አሁን በሚገኝበት ደረጃ ሊከበርና ልንገዛበት የሚገባ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሆኑን አምኖ መቀበል አስፈላጊ መሆኑን ቀደም ሲል ብሔራዊ መግባባትን በተመለከተ ባነሳነው ርእስ ላይ ለማየት ሞክረናል፡፡ ሕገ-መንግሥቱን የማክበርና ለሕገ-መንግሥቱም ተገዥ የመሆን አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የሰፈሩትና ለአገሪቱ አንድነትና የኢኮኖሚ ዕድገት አይጠቅሙም ብለን የምናምንባቸውን አንዳንድ አንቀጾች ግን ወደፊት ራሱ ሕገ-መንግሥቱ በሚፈቅደው አግባብ እንዲሻሻሉ ወይም እንዲለወጡ መታገል በዚያው መጠን አስፈላጊ ይሆናል፡፡

እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ (ሁሉም ማለት ይቻላል) ራሳቸውን በብሔር ማንነት ያደራጁ አገራችን ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት ከኢህአዴግ ጋር የአፈጻጸም እንጂ መሠረታዊ የይዘት ልዩነት የላቸውም፡፡ ከመጀመሪያው

የሽግግር መንግሥቱ አባል የነበሩ ኦነግና ደቡብ ኅብረትን የመሳሰሉ ድርጅቶችም ሆኑ በኋላ ላይ ዘግይተው የተመሠረቱት ኦብኮ፣ ኦፌዴንና አረናን የመሳሰሉ ድርጅቶች ዋናው ጥያቄአቸው ሕገ-መንግሥቱ በትክክል ተግባር ላይ ሊውል ይገባዋል የሚል እንጂ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይገባዋል የሚል አይደለም፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆነ አቋም ይዘው የሚገኙት አንዳንድ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ያሉ በጎ ነገሮችን ሁሉ ዕውቅና በመንፈግ ሕገ-መንግሥቱ እንደተራ ወረቀት ተቀዶ እንዲጣል የሚፈልጉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት ሁለት ጽንፈኛ አቋም የሚያራምዱ የፖለቲካ ኃይሎች በተለየ፣ በአንድ በኩል የወቅቱን ሕገ-መንግሥት ከነ ድክመቶቹና ከነ ችግሮቹ አክብሮ የመገዛት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የሚታዩትን ለአገር አንድነትና ለኢኮኖሚ ዕድገት አይጠቅሙም ብሎ የሚያምንባቸውን አንቀጾች በሂደት ታግሎ የመቀየር ግልጽ አቋም ይዞ የሚገኘው ፓርቲ ኢዴፓ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ምክንያትም በዚህ ጽሑፍ ሕገ-መንግሥቱን በሚመለከት ለማቅረብ የሚሞከረው ትችት በዋናነት (ሙሉ በሙሉ ባይባልም) ከኢዴፓ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ለአገሪቱ አንድነትና የኢኮኖሚ ዕድገት የማይበጁ ድክመቶችና ችግሮች ያሉበትን ያህል እስካሁን አገሪቱ ከነበሯት ሕገ-መንግሥቶች በተሻለና በተለየ የራሱ ጠንካራ ጐኖች ያሉትም ነው፡፡ የወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ መሠረታዊ የሚባሉ የዴሞክራሲ መብቶችንና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን ሙሉ በሙሉ የተቀበለ መሆኑ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብሔር-ብሔረሰቦች እኩልነትና ለቡድን መብት መከበር ዕውቅና መስጠቱ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትንና የፌደራላዊ አደረጃጀትን መቀበሉ፣ ከሌሎች አገሮች ሕገ-መንግሥቶች ጋር ሲነጻጸርም በአንፃራዊነት ጥሩ የሚባል ቴክኒካዊ ይዘት ያለውና በውስጡ የጐላ የርስ በርስ የሐሳብ ቅራኔ የማይታይበት ሰነድ መሆኑ በጠንካራ ጐንነት ሊጠቀሱለት የሚችሉ ነጥቦች ናቸው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ ወደፊት በአገሪቱ ለመንግሥትነት የሚበቃ ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ለረዥም ጊዜ ሳያሻሽል ይዟቸው ሊቀጥል የሚገባቸው እነዚህንና እነዚህን የመሰሉ ሌሎች ጠንካራ ጐኖች ያሉት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት፣ በሕገ-መንግሥቱ ከሰፈረው የፌደራል አደረጃጀት፣ የመገንጠል መብትና የመንግሥት አካላት የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አኳያ በርካታ ትችቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ ድክመቶች አሉበት ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህን ድክመቶች በሚከተሉት ርእሶች ዘርዘር አድርገን ለማየት እንሞክራለን፡፡

### *4.1 በሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ሊነሡ የሚገቡ ጥያቄዎች*

*የአንድ አገር ሕገ-መንግሥት አጠቃላይ ይዘት ሕገ-መንግሥቱ የበላይ ሕግ ሆኖ በሚያገለግልበት አገር የሚገኙ ዜጎችን ልዩ ልዩ እምነቶች፣ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ልዩ ልዩ ፍላጐቶችና አመለካከቶች ከሞላ ጐደል አቻችሎ የሚገኝ ሰነድ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አንጻር በወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት አጠቃላይ ይዘት ላይ ሊነሡ የሚገባቸው የተለያዩ መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የምናራምዳቸው አቋሞችና የምናካሂዳቸው ክርክሮች በዋናነት በሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ማተኮር ሲገባቸው አብዛኛውን ጊዜአችንን ስናጠፋ የሚታየው ግን በሕገ-መንግሥቱ የተለያዩ ክፍሎች ጐልተው በሚታዩት እንደ ፌደራላዊ አደረጃጀት፣ የመገንጠል መብትና የመሬት ባለቤትነት በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በመከራከር ነው፡፡ በእነዚህ የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ መከራከሩ በራሱ ችግር የሌለውና አስፈላጊ ቢሆንም በሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ባህሪና ይዘት ላይ የጠራ ግንዛቤ ሳይኖረን በሕገ-መንግሥቱ የተለያዩ አንቀጾች ላይ በተናጠል የምናደርገው ክርክር የሚገባውን ያህል ግልጽና ቀላል ሊሆን አይችልም የሚል ግምት ስለ አለ በዚህ ጽሑፍ በቅድሚያ በሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት ላይ ሊነሡ የሚገባቸውን ጥያቄዎች ካዬን በኋላ ቀጥለን ከዚህ የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ባህሪና ይዘት በመነጨ አከራካሪ የሆኑትን ዋናዋና ጉዳዮች በተናጠል ለማየት እንሞክራለን፡፡*

*ከሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት አንጻር በቅድሚያ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ በወቅቱ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሠረት "ኢትዮጵያ" የምትባለው አገር ባለቤት ማን ነው? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ በ1987 ዓ.ም በጸደቀው የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሠረት ኢትዮጵያ የወሰደችው ርምጃ አሐዳዊ የነበረውን የመንግሥት አደረጃጀትዋን ወደ ፌደራላዊ የመንግሥት አደረጃጀት የመቀየር ብቻ ሳይሆን ለአገሪቱ አዲስ ባለቤቶች የመፍጠርና በእነዚህ አዲስ የአገሪቱ ባለቤቶች አዲስ ስምምነት መሠረትም አዲስ አገር የመፍጠር ርምጃ ነው፡፡ ይህንን ለማለት የሚቻለው በዋናነት በሁለት ምክንያት ነው፡፡*

*የመጀመሪያው በሕገ-መንግሥቱ መግቢያ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የአገሪቱ ባለቤት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሆኑ ቀርቶ በአገሪቱ የሚገኙ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሆነዋል፡፡ ጉዳዩን በተሻለ ምሳሌ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ፣ ቀድሞ አንድ አገር ያልነበሩት የአሜሪካ ግዛቶች አንድ የጋራ አገር እንዲኖራቸው የተስማሙበት ሕገ-መግሥታቸው በመግቢያው ላይ "እኛ የተባበሩት የአሜሪካ ግዛቶች ሕዝቦች /ዜጐች/* (We the People of United States,)" *ብሎ የሚጀምር ሲሆን ፣ አንድ ሉዓላዊ አገር የነበረችው አገር ኢትዮጵያ*

በ1987 ዓ.ም ያጸደቀችው ሕገ-መንግሥት ግን በመግቢያው ላይ “እኛ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች (We the Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia)” ብሎ ነው የሚጀምረው፡፡ በዚህ ሕገ-መንግሥት መሠረትም ኢትዮጵያውያን የአገሪቱ ባለቤት ነን ልንል የምንችለው ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ብሔር ወይም ብሔረሰቦች ውስጥ የአንዱ አባል በመሆናችን እንጂ የአገሪቱ አንድ ዜጋ በመሆናችን አይደለም፡፡ ሕገ-መንግሥቱ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ራሱን የዚህ ወይም የዚያ ብሔረሰብ አባል ነኝ ብሎ ሊቆጥር የማይፈልግ ወይም ሊቆጥር የማይችል ኢትዮጵያዊ ዜጋ በምን የተለየ መንገድ የአገሪቱ ባለቤትነት ድርሻ አለኝ ሊል እንደሚችል የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ በአጭሩ በዚህ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት መሠረት የአገር ባለቤትነት ጉዳይ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ጋር ተያይዞ መታየቱ ቀርቶ ከቡድን መብት ጋር ተያይዞ የሚታይ ሆኗል፡፡

ምክንያቱም በአዲሱ ሕገ-መንግሥት መሠረት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተብለው ሊጠሩ የሚችሉ ቡድኖች እንጂ ግለሰብ ዜጐች አይደሉም፡፡ በአሜሪካ ሕገ-መንግሥት ላይ በነጠላ /Singular/ ቃል “People” በሚል የተቀመጠው አባባል በሁሉም የአሜሪካ ግዛቶች የሚገኘውን ሁሉንም ዜጋ የሚወክል መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ የተቀመጠ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ግን “ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች” የሚለው አባባል ብቻ ሳይሆን በተባዥ /Plural/ ቃል “ሕዝቦች /Peoples/” በሚል የተቀመጠው አባባል በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ የኅብረተሰብ ቡድንን እንጂ እያንዳንዱን ዜጋ የሚመለከት አይደለም፡፡ እነዚህ የአገሪቱ ባለቤት እንዲሆኑ የተደረጉት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በየራሳቸው ማንን እንደሚወክሉ በሕገ-መንግሥቱ በግልጽ ያልተቀመጠ ከመሆኑም በላይ አንዳቸው ከሌላቸው ያላቸው አንድነትና ልዩነት ምን እንደሆነም በግልጽ አልተቀመጠም፡፡

በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ እነዚህን ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚሉትን አባባሎች በተመለከተ የተቀመጠውን አጭር ትርጉም ብናየው ጉዳዩን የበለጠ ግልጽ ሊያደርግልን ይችላል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 39 ቁጥር 5 ላይ የሰፈረው ትርጉም __፣

> *“በዚህ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ‘ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ` ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለፀውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ የሥነልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክኣ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡”* በማለት ይነበባል፡፡

በዚህ ትርጉም ውስጥ በግልጽ እንደሚታየው ሦስቱም ቃሎች ማለትም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚሉት ቃሎች ግለሰብን ወይም የአገር ዜጋን የማይወክሉና የማይመለከቱ መሆናቸው በግልጽ ሰፍሯል፡፡ የሚገርመው ከዚህ ሕገ-መንግሥቱ ራሱ ካስቀመጠው ትርጉም በግልጽ እንደሚታየው ለሦስቱም ቃላቶች የተሰጠው ትርጉም አንድ ዓይነት ነው፡፡ ነገር ግን የሦስቱም ትርጉም አንድ ዓይነት እስከሆነ ድረስ ሦስት የተለያዩ ቃላት ከመጠቀም ይልቅ ለምን በአንድ ቃል ተጠቃለው "ብሔሮች" ወይም "ብሔረሰቦች" ወይም "ሕዝቦች" ተብለው መቀመጥ እንዳልቻሉ ግልጽ አይደለም፡፡

በዚህ ሕገ-መንግሥቱ ባስቀመጠው ትርጉም ውስጥ ግለሰቦች ወይም ዜጎች ቦታ የሌላቸው መሆኑ በራሱ ግልጽ ቢሆንም የአገሪቱ ባለቤትነት ከዜጎች ወይም ሁሉንም ዜጎች አጠቃሎ ሊገልፅ ከሚችለው "የኢትዮጵያ ሕዝብ /People of Ethiopia/" ወደ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መቀየሩን በተጨባጭ የሚያረጋግጥልን የሚከተለው ሁለተኛ ምክንያት ነው፡፡ ይኸውም በ1987ዓ.ም በጸደቀው በዚሁ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የአገሪቱ ባለቤት እንዲሆኑ የተደረጉት እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰንና የመገንጠል መብት ያላቸው መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአንድ አገር ዜጎች በተናጠል ከአገር የመገንጠል ፍላጐትም ሆነ መብት በሆነ ተአምር ሊኖራቸው ስለማይችል እነዚህ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ተብለው በሕገ-መንግሥቱ ላይ የሰፈሩት የአገሪቱ ባለቤቶችን የሚጠቅሱ ቃላት የቡድን መገለጫዎች እንጂ የግለሰብ ወይም የዜግነት መገለጫ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥልን ይኸው የተሰጣቸው የመገንጠል መብት ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የመገንጠል መብት መኖሩ ግርታ የሚፈጥርብንም በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ ባለቤቶች እነማን መሆናቸውን በአግባቡ ላልተረዳን ሰዎች ነው እንጂ፣ አዲሱ ሕገ-መንግሥት ከጸደቀ በኋላ የአገሪቱ ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ በግልጽ ላወቀ ሰው ግን የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ መኖሩ የሚያስደንቅ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የዛሬዋን ኢትዮጵያ የምትባል አገር በበጎ ፈቃዳችን ተደራድረንና ተስማምተን ፈጠርን ያሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በስምምነት የፈጠሩትን አዲስ አገር መልሰው ቢያፈርሱት ወይም ከመካከል አንዳቸው ተነጥለው መውጣት ቢፈልጉ ውሳኔአቸው ከገቡበት ስምምነት የሚመነጭ የመብት ጥያቄ ተደርጐ ከመታየት ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡

ምክንያቱም በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የመገንጠል መብት እንዲሰፍር የተደረገው በዚያው ሕገ-መንግሥት አማካይነት የአገሪቱ ባለቤቶች ዜጎች መሆናቸው ቀርቶ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሆኑና አገሪቱም በእነዚህ ባለቤቶቹዋ ስምምነት መሠረት በአዲስ መልክ

እንድትመሠረት መደረጉን ተከትሎ ነው፡፡ የመገንጠል መብት መቀመጡ ስህተት ሊሆን ይችል የነበረው የአገሪቱ ባለቤቶች በጥቅሉ "የኢትዮጵያ ሕዝብ /The people of Ethiopia/" ወይም "ኢትዮጵያውያን" ቢሆኑ ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህ ዓይነት አገላለፅ የሚያሳዬው የአገሪቱ ባለቤቶች ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች መሆናቸውን ስለሚሆን እንደ ሌሎች የዓለማችን አገሮች ሕገ-መንግሥቶች የመገንጠል መብት መስጠትን አስፈላጊ አያደርገውም ነበር፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአዲሱ ሕገ-መንግሥት መሠረት የአገሪቱ ባለቤቶች መቀየራቸውን ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘም አዲሱ የፌደራል አደረጃጀት በአገሪቱ ሥራ ላይ የዋለው አንድ ነባር ሉዓላዊነት ያለው አገር የውስጥ ችግሩን ለመፍታት እንደተከተለው አዲስ አደረጃጀት ተደርጐ ሳይሆን የተለያዩ የራሳቸው አገራዊ ማንነት የነበራቸውና ያላቸው ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአንድ አዲስ አገር በጋራ ለመኖር ሲሉ በስምምነት የፈጠሩት አደረጃጀት ተደርጐ ነው፡፡

ስለዚህ ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ያደረገው የአገሪቱ የወቅቱ ፌደራላዊ አደረጃጀትም ሆነ የብሔር-ብሔረሰቦች የመገንጠል መብት በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ላይ እንዲሰፍር የተደረገው የአገሪቱ ባለቤቶች መለወጣቸውን ተከትሎና መነሻ አድርጐ መሆኑን በአግባቡ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በነገራችን ላይ ይህንን ጽሑፍ ለሚያነቡ ለኢህአዴግ አባላት የአገሪቱ ባለቤቶች የመቀየር ጉዳይ በደንብ የሚታዎቅ ስለሆነ ይህ ጉዳይ በዚህ ጽሑፍ ላይ ደጋግሞ መነሣቱ "ምን አዲስ ነገር ኖሮ ነው?" የሚል ግርምታን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ነገር ግን የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ በዚህ ረገድ በተቃዋሚው ጐራና በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የጠራ ግንዛቤ የሌለ መሆኑን በመረዳት ትኩረት ሊሰጠው የፈለገ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

ወደ ተነሣው ነጥብ ስንመለስ በጉዳዩ ላይ የሚኖረን ክርክር በቅድሚያ ማተኮር ያለበት የአገሪቱ ባለቤቶች ማንነት ለምን ተቀየረ? የሚለው መሠረታዊ መነሻ ጥያቄ ላይ ነው እንጂ ይህንን አስተሳሰብ ተከትለው በመጡት ውጤቶች ላይ መሆን የለበትም፡፡ በርግጥ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች እስካሁን የበለጠ ትኩረት ሰጥተን ስንከራከር የኖርነው አገሪቱ በምትከተለው የፌደራል አደረጃጀት መስፈርቶችና በመገንጠል መብት ጉዳይ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ሕገ-መንግሥቱ ለእነዚህ ጉዳዮች ግልጽ የሆነና የማያሻማ መልስ ከላይ ለመግለፅ በተሞከረው ሁኔታ ሰጥቷል፡፡ አገሪቱ በዋናነት ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ የፌደራል አደረጃጀት እንድትከፋፈል የተደረገችውም ሆነ የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ እንዲሰፍር የተደረገው በሌላ ምክንያት ሳይሆን የአገሪቱ ባለቤቶችም ሆኑ አገሪቱን በበጎ ፈቃዳቸው ተስማምተው የፈጠሯት ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው ስለተባለ ነው፡፡ ስለዚህ የፌደራል

አደረጃጀቱም ሆነ የመገንጠል መብት ከዚህ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ የሚመነጭ እንጂ በራሱ የቆመና የተለየ ምክንያት የሚቀርብለት ጉዳይ አይደለም።

በአጠቃላይ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና አጋር ድርጅቶቹ ለምን ብሔረሰባዊ ማንነታቸውን መሠረት አድርገው ለመደራጀት እንደመረጡ፣ አገሪቱ ለምን በዋናነት ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ ፌደራሊዝም እንደተከፋፈለች፣ ብሔር-ብሔረሰቦች ለምን የመገንጠል መብት እንዲኖራቸው እንደተደረገና የፌደሬሽን ምክር ቤትም ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ ለምን ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮችን የመተርጐም ሥልጣን እንደተሰጠው ተያያዥና ወጥ በሆነ መንገድ ሊገባን የሚችለው በቅድሚያ ይህንን በወቅቱ ሕገ-መንግሥት መሠረት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሆኑ መደረጋቸውን በአግባቡ መረዳት ስንችል ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች “ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝቦች” ለሚሉት የፖለቲካ ቃላቶች እንኳ ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት የሚያስችል መግባባት በመካከላቸው ገና ያልፈጠሩ ቢሆንም - ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የአገሪቱ ባለቤቶች ቢሆኑ ምን ችግር አለው? የሚል ቀና መሰል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ኢትዮጵያ እንደ አገር ያለፈችበት ረዥም ታሪካዊ ሂደትና ዛሬ የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ለማድረግ የሚፈቅድ ከሆነ በርግጥም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች (ትርጉማቸው ምንም ይሁን ምን) የአገሪቱ ባለቤቶች ቢሆኑ ችግር የለውም ሊባል ይችላል። ነገር ግን ከአገሪቱ ታሪካዊ ሂደትም ሆነ ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ይህንን ለማለት የማያስችሉ በርካታ ምክንያቶች አሉ።

በመጀመሪያ ከአገሪቱ ታሪካዊ ሂደት ጋር ሊያያዝ የሚችለው ምክንያት ዛሬ ኢትዮጵያ በመባል የምትታወቀው አገር ወጥ በሆነ መልኩ ቀደም ሲል የራሳቸው ሉዓላዊነትና መንግሥታዊ ዕውቅና በነበሯቸው ግዛቶች ስምምነት መሠረት የተፈጠረች አገር አለመሆኗ ነው። ኢትዮጵያ እንደማንኛውም አብዛኛው የዓለም አገራት አብሮ በመኖር ግንኙነት፣ በንግድ፣ በስደትና በጦርነት እንቅስቃሴ በውድም - በግድም /Blood and Iron/ በረዥም ታሪካዊ ሂደትና ውጣ ውረድ የተፈጠረች አገር ነች። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ከሰባ በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ በርካታዎቹ በደቡባዊ የአገሪቱ ክፍል የሚገኙት ብሔር-ብሔረሰቦች ከመቶ ዓመት በፊት ከማዕከላዊው አስተዳደር መዳከም ጋር በተያያዘ የየራሳቸው ባህላዊ አስተዳደር የነበራቸው ቢሆንም እነዚህ ሕዝቦች ቀጣይነት በነበረውና በተለመደው የአገሪቱ ታሪካዊ ሂደት ወደ ኢትዮጵያ አካልነት ለመጠቃለል በቁ እንጂ የየራሳቸው መንግሥታዊ ማንነት ኖሯአቸው ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር በተለየ ድርድርና ስምምነት አልፈጠሯትም።

ይህ ዓይነቱ የአገር ፈጠራ ሂደትም በኢትዮጵያ ብቻ የተጀመረ ሳይሆን በመላው ዓለም የነበረና በወቅቱም ሌላ የተሻለ መተኪያና አማራጭ የሌለው ስልት ነበር፡፡ እንዲያውም አብዛኛዎቹ የዓለማችን አገሮች አሁን የሚገኙበትን የአገር ቅርፅና ይዞት ማግኘት የቻሉት ከመቶ ዓመታት ወዲህ ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ፍጻሜና ከቅኝ ግዛት ነፃ ከመውጣት እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የአገሮች የመስፋፋትና ሌሎችን በኃይል የማስገበር ርምጃ በጠነከረ መልኩ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጻረር ወንጀል ተደርጎ መታየት የጀመረው ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜና ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መመሥረት በኋላ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚያ በፊት ግን አገሮች ነፃነታቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ እርስ በርሳቸው የሚገቧቸው ስምምነቶች የነበሩ ቢሆንም በአጠቃላይ ግን የግዛት መስፋፋትና ሌሎችን በኃይል ማስገበር መቻል የአንድ ጠንካራ መንግሥት መገለጫ ድርጊትና ባህሪ እንጂ ወንጀልና ነውር ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ አልነበረም፡፡

እስከ 2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ድረስ ጥቂት የዓለም ኃያላን አገሮች ውቅያኖስ እየተሻገሩ ጭምር ሌሎች አገሮችን በቅኝ ግዛትነት ሲወሩና ሲያስገብሩ የኖሩት በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ የእኛዋ አገር ኢትዮጵያ የተመሠረተችበት ሂደት ሌሎችም የዓለም አገሮች ከተመሠረቱበት ሂደት የተለየ አይደለም ቢባልም፣ እንዲያውም ሌሎች አገሮች ከተፈጠሩበት ሂደት ጋር የኢትዮጵያን የአገር ምሥረታ ሂደት ስናነፃፅረው እንደ ብዙዎቹ የዓለም አገራት በከፋ የጦርነት ሂደት ሳይሆን በአንፃራዊነት ለስላሳና አዝጋሚ በሆኑ የተለያዩ ታሪካዊ መስተጋብሮች የተከናወነ ምሥረታ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዓይነት በተለያዩ ታሪካዊ መስተጋብሮችና በረዥም ታሪካዊ ሂደት የተመሠረተን የአንድን አገር ባለቤትነት፣ ቀደም ሲል አገሪቱን በተለየ ድርድርና ስምምነት ላልፈጠሩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለሚባሉ የኅብረሰብ ቡድኖች መስጠት ከአገሪቱ ታሪካዊ ሂደት ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ "ራስን እያፈረሱ እንደገና የመፍጠር" ምርምር በእኛ አገር ካልሆነ በስተቀር በሌሎች አገሮች ላይ ተሞክሮ አያውቅም፡፡

ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የአገሪቱ ባለቤቶች ናቸው መባሉ ብዙ አከራካሪ ጥያቄ የሚያስነሣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህ የኅብረተሰብ ቡድኖች በአገሪቱ ላይ ያላቸው የባለቤትነት መብት የአገሪቱን ህልውና ጥያቄ ውስጥ በማያስገባበት ሁኔታ አንድ ቦታ ላይ መቆም የሚችል ቢሆን ኖሮ ብዙም አከራካሪ ባልሆነ ነበር፡፡ ነገር ግን የእነዚህ የኅብረተሰብ ቡድኖች መብት አንድ አዲስ አገርን በአዲስ ስምምነት እንደመፍጠር ተደርጎ በመቆጠሩ ምክንያት ከመገንጠል መብትም ጋር ተያይዞ የተሰጠ የባለቤትነት መብት ስለሆነ፣ በሌላ አገላለፅ

የተሰጠው የአገር ባለቤትነት መብት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አገሪቱንም የማፈራረስ መብት ነው /እንዴት የማፍረስ መብት እንደሚሆን በሚቀጥለው ክፍል እናዬዋለን/፡፡ በሺ ዓመታት በሚቆጠር ረዥም ሂደትና በተለያዩ ታሪካዊ መስተጋብሮች የተመሠረተን አንድ አገር፣ በአገራችን መቀንቀን ከጀመረ የኀምሳ ዓመታት ዕድሜ ባልሞላው የብሔር ብሔረሰቦች መብት ፅንሰ-ሐሳብ አማካይነት አገርን ያህል ታላቅ ነገር “ሲያስፈልግ ይፈርሳል” ብሎ መወሰን የአገሪቱን ታሪካዊ እውነታ ከሥር ከመሠረቱ የሚንድ የተሳሳተ አቋም ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የተሳሳተ አቋም እነ ጆሴፍ ስታሊን ከራሳቸው ወቅታዊና አካባቢያዊ ሁኔታ (context) በመነሣት የጻፉትንና የተናገሩትን ነገር ሁሉ ለሁሉም አገር ሁኔታ እንደሚሰራ መፍትሄ አድርጐ በመውሰድ የተማሪው እንቅስቃሴ በጥራዝ ነጠቅነት ከወሰደው አቋም የመነጨ ስህተት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የክልል መንግሥትነት ደረጃ ያገኙት ብሔር ብሔረሰቦች አሁን በሚገኙበት ቅርፅና ይዘት የራሳቸው ማንነት መገለጫ የሆነ ወጥ አስተዳደር ከ1983 ዓ.ም በፊት በየትኛውም የታሪክ አጋጣሚ ኖሯቸው የማያውቅ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ብሔረሰቦች መብት ሊከበር ይገባዋል የሚለው ጥያቄ ራሱ አከራካሪ በሆነ ሁኔታ በዋለልኝ መኰንን አማካይነት ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ብቅ ያለው የዛሬ አርባ ዓመት ገደማ ነው፡፡ የብሔር ብሔረሰቦች የመብት መከበር ጉዳይ አንድ አጀንዳ ሆኖ መነሣት በጀመረበት በዚያን ወቅት አጀንዳው ተቀባይነት ያገኘው በወቅቱ ሥርዓቱን ለመታገል የሚያስችል ጠንካራ አጀንዳ ለማግኘት ይጥሩ በነበሩ ጥቂት የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ነበር እንጂ በአብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ ውስጥ የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ለማስከበር ተብሎ የሚካሄድ የተደራጀ ትግልም ሆነ በጥያቄው ዙሪያ የሚነሣ የጠራ ግንዛቤ አልነበረም፡፡ እንዲያውም በወቅቱ በጎላ ሁኔታ ይነሳ የነበረው ክርክር “የብሔር ጥያቄን ዋለልኝ መኮንን ፈጠረው? ወይስ ዋለልኝ መኰንንን የብሔር ጥያቄ ፈጠረው?” የሚል ነበር፡፡ ዛሬም ድረስ “ዋለልኝ መኰንን ከኗላው በኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎችና በውጭ የአገሪቱ ጠላቶች ተገፍቶ ያነሳው ጥያቄ እንጂ የብሔር ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ማኀበራዊ መሠረት አልነበረውም” በማለት ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩ የዚያን ወቅት የተማሪዎች እንቅስቃሴው ተሳታፊዎች የነበሩ ሰዎች ቀላል ቁጥር ያላቸው አይደሉም፡፡

ጉዳዩ አከራካሪ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ የብሔር ጥያቄን ዋለልኝ መኮንን ያነሳው ከራሱ በቂ ፖለቲካዊ ግንዛቤና ትንታኔ ተነሥቶ ስለመሆኑና አለመሆኑ ርግጠኛ መሆን ባይቻልም፣ ጥያቄው ቀድሞውንም በኢትዮጵያ የተወሰነ ምክንያታዊ መነሻ ወይም የራሱ

ማኅበራዊ መሠረት ባይኖረው ኖሮ ዋለልኝ ስለ አነሳው ብቻ በአገሪቱ ፖለቲካ ቁልፍ አጀንዳ ለመሆን ይበቃ ነበር ብሎ ለመገመት ግን ያስቸግራል፡፡ ዛሬ በአገራችን በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት ያሉ አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የብሔር ጥያቄን አንድ የአገሪቱ አንገብጋቢ ጥያቄ አድርገው ከማመንም አልፈው ራሳቸውን በብሔር ደረጃ አደራጅተው እየታገሉ የሚገኙት የዋለልኝ መኰንንን መሠረት የሌለው ቲዎሪ መነሻ አድርገው ነው ማለት አይቻልም፡፡ በዚህ ከፍተኛ መጠን የብሔር ድርጅቶች አገሪቱ ውስጥ መፈጠራቸውም ሆነ እነዚህ የብሔር ድርጅቶች የራሳቸው የሆነ ማኅበራዊ መሠረት /constituency/ አገሪቱ ውስጥ ማግኘታቸው በራሱ የብሔር ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ የራሱ ምክንያታዊ መነሻ ያለውና መፍትሔ የሚያሻው የፖለቲካ ጥያቄ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ የግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን ባይገባ ኖሮ የብሔር ጥያቄ በዛሬው መጠን ገዥ የፖለቲካ ጥያቄ ሆኖ ባልተገኘ ነበር፡፡ ምክንያቱም ሶሻሊዝምን ወደ ታዳጊ አገሮች ለማስፋፋት በሚደረገው ሙከራ አብዮትን ለማቀጣጠልና ትግል ለማድረግ የሚያስችል በቂ የሆነ የመደብ ክፍፍል (በከበርቴውና በሠራተኛው መደብ መካከል) ስለማይኖር በታዳጊ አገሮች ሊኖር የሚገባው ቅራኔ የብሔር ቅራኔ ነው የሚል ቲዎሪ እነ ስታሊን ያራምዱ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የግራ ፖለቲካ አራማጆች ይሄንን ቲዎሪ በመቅለብ በብሔር ጥያቄ ዙሪያ በአገሪቱ የነበረውን ችግር ፈልገው ከማግኘት በተጨማሪ አገራዊ የፖለቲካ ጥያቄ ሆኖ ጉልቶ እንዲወጣ የሚያስችል ሥጋና ደም ፈጥሮለታል ማለት ይቻላል፡፡ ዋለልኝ መኰንንም በዚያ የለጋ ዕድሜው የአገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች በውል ለማገናዘብ ከሚኖርበት ውስንነት አንፃር የግራው ርእዮተ-ዓለም ተጽዕኖ ሰለባ አልነበረም ማለት የሚቻል አይሆንም፡፡

እንኳንስ የኢንፎርሜሽን ፍሰት ጠባብና አዝጋሚ በነበረበት በዚያ ወቅትና ዛሬም ዓለማችን መንደር እየሆነች በመጣችበት የኢንፎርሜሽን ዘመን በእነ ዋለልኝ ዕድሜ ለሚገኝ ሰው የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታ በአግባቡ ተገንዝቦ ትክክለኛ ትንታኔ ለመስጠት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሌላው ግንዛቤ ውስጥ ሊገባ የሚገባ ጉዳይ - የእነ ጆሴፍ ስታሊን ተከታዮች የብሔር ጥያቄን አጉልተው ማቀንቀን ይመርጡ የነበረው የብሔር ጥያቄ በአንድ አገር ውስጥ የነበረንና ያለን የሕዝቦች ጥያቄን ለመመለስ ብቻ ሳይሆን አዲስ ብሔራዊ ስሜትና ማንነት ለመፍጠርም ጭምር ይጠቀሙበት የነበረ መሣሪያና ስልት መሆኑን ነው፡፡ ጆሴፍ ስታሊን ራሱ እንደሚለውም የመደብም ሆነ የብሔር ጥያቄ የንዑስ ከበርቴውና የቡርዣው ክፍል ለሥልጣን የበላይነት ርስ በርስ የሚፎካከሩበት የፖለቲካ መሣሪያ ሆኖ ስለሚያገለግል የብሔር ጥያቄ በአገራችን መቀንቀን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከፊታቸው ችግሮች ይልቅ ይበልጥ ያወሳሰባቸው ወይም አዳዲስ የፈጠራቸው ችግሮች ይበዛሉ ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ነው - ኢህአዴግ የብሔር ጥያቄን

መልሻለሁ ካለ ከ18 ዓመት በኋላም በርካታ የነፃ አውጭነት ሚና አለን የሚሉ የአገራችን ንዑስ ከበርቴዎች የራሳችን የሚሏቸውን የብሔረሰብ አባላት ከኋላቸው አሰልፈው በሰላማዊ መንገድም ሆነ በትጥቅ ትግል ኢህአዴግን ሲታገሉት የሚታየው፡፡ ይህም በተጨባጭ የሚያሳየው በርግጥም የብሔር ጥያቄ የነበረንና ያለን ችግር ለመፍታት ብቻ ሳይሆን አዲስ ብሔራዊ ስሜትና ማንነት በመፍጠር ለፖለቲካ ሥልጣንና ለኢኮኖሚ ጥቅም የበላይነት በተለያዩ የኀብረተሰቡ ተቆርቋሪዎች ነን በሚሉ ንዑስ ከበርቴዎች መካከል የሚደረግን ትግል ለማጠናከር የሚያስችል ስልት መሆኑን ነው፡፡

ዞሮ ዞሮ የወቅቱ የፖለቲካ ኃይሎች ክርክር መሆን የሚገባው የብሔር ጥያቄ አለ ወይም የለም? የሚል ሳይሆን፣ ከሌሎች የአገሪቱ ችግሮች ጋር ሲነጻጸር የችግሩ ጥልቀትና ስፋት ምን ያህል ነው? ለችግሩስ ሊሰጠው የሚገባው መፍትሄ ምን ዓይነት ሊሆን ይገባዋል? በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያተኩር መሆን ይገባዋል፡፡ የብሔር ጥያቄ አገሪቱ ውስጥ የፖለቲካ ጥያቄ ሆኖ በአንድ ግለሰብ አማካይነት ብቅ ካለበት የጊዜ ቅርበትና ሁኔታ አንጻር፣ ጥያቄው በራሱ አከራካሪ ሆኖ እስከዛሬ ድረስ ከመዝለቁ አንጻር፣ ጥያቄው በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ሳይሆን በተወሰኑ የአገሪቱ ክፍሎች ጐልቶ የሚታይ ከመሆኑ አንጻር፣ አገሪቱ ውስጥ የሕዝቡን የዕለት ተዕለት ህልውና የሚፈታተኑ ሌሎች በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ችግሮች ከመኖራቸው አንጻር፣ በአገሪቱ ውስጥም የብሔር ብሔረሰብ ማንነትን የተሻገሩ በርካታ የሕዝቡ የአንድነት መገለጫ የሆኑ የተለያዩ የጋራ ጉዳዮች ከመኖራቸው አንጻር የብሔር ጥያቄ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ በርካታ አንገብጋቢ ችግሮች ውስጥ አንዱ እንጂ ዋናውና ብቸኛው ችግር ነው ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡

ስለዚህ ከአገሪቱ በርካታ አንገብጋቢ ችግሮች አንዱ ለሆነው ችግራችን የምንሰጠው መፍትሔ ከዚሁ ከችግሩ ጥልቀትና ስፋት ጋር የሚመጣጠን መሆን ሲገባው ችግሩን የአገሪቱ ዋና ወይም ቀዳሚ ችግር እንደሆነ አድርጐ በመቁጠር የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት አጠቃላይ ይዘትና የአገሪቱን ፌደራላዊ አደረጃጀት ሌሎቹን የአገሪቱን ችግሮች በረሳ ሁኔታ የብሔር-ብሔረሰቦች የመብት ጥያቄ መመለሻ ብቻ አድርጐ ለመጠቀም መሞከር ከባድ ስህተት ነው፡፡ የወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ትልቁ ችግርም ይኸው ነው፡፡ ሕገ-መንግሥት የብሔር ጥያቄን እንደ አንድ አገራዊ የፖለቲካ ችግር በማየት የሚገባውን መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ የብሔር ጥያቄን የአገሪቱ ዋናና ብቸኛ ችግር እንደሆነ አድርጐ በማየት ብሔር ብሔረሰቦች የአገሪቱ ባለቤቶች እንዲሆኑ ከማድረግም አልፎ ሲፈልጉ አገሪቱን የማፍረስ መብት እንዲኖራቸው የማድረግ መብት ሠጥቷቸዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ሚዛኑን የሳተ የችግር አፈታት ዘዴ በአንድ በኩል

መሠረታዊ የሆነውን የግለሰብ መብት ከቡድን መብት በታች ያደረገው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከሚገባው በላይ በልዩነት ላይ በማተኮር የአገርና የሕዝብ አንድነትን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል፡፡

ሕገ-መንግሥቱ ብሔር ብሔረሰቦችን የአገሪቱ ህልውና መሠረትና ባለቤት ሲያደርጋቸው እግረ መንገዱን ዜጐች የአገሪቱ ባለቤት የመሆን መብታቸውን እንዲያጡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ አባባል ምንአልባት ሁሉም የአገሪቱ ዜጐች ዞሮ ዞሮ ከአንዱ ወይም ከሌላው ብሔረሰብ የተወለዱ መሆናቸው ስለማይቀር እነሱም (ዜጐች) በተዘዋዋሪ የአገሪቱ ባለቤቶች መሆናቸው ይቀራል ወይ? የሚል ጥያቄ ሊያሥነሣ ይችላል፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መጀመሪያ ሊነሣ የሚገባው ሌላው ጥያቄ ለመሆኑ የአንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ተወላጅ መሆንን የዜጐች ሁሉ የማንነት መገለጫ ቀዳሚ መስፈርት ያደረገው ማን ነው? የሚለው ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የሰዎች የማንነት መገለጫ “ብሔረሰባዊ ማንነታቸው ነው” የሚል በአንድ አገርም ሆነ በዓለም ደረጃ ወጥ ተቀባይነት ያለው አስተሳሰብ እስካሁን የለም፡፡ ሰዎች ወይም የአንድ አገር ዜጐች ማንነታቸውን የሚገልፁት ከግላዊና አካባቢያዊ ሁኔታቸው በመነሣት በሚፈጥሩት የግል አመለካከት እንጂ ባሌላ ውጫዊ አካል ስለማንነታቸው ከሚነገራቸው ተነስተው አይደለም፡፡ አንድ ሰው ብሔረሰባዊ ትውልዱን የማንነቱ መገለጫ አድርጐ ሊያይ የሚችለውን ያህል ሌሎች ሰዎች ደግሞ ኃይማኖታቸውን፣ ወይም የግል ባህርያቸውን፣ ወይም የትውልድ አካባቢያቸውን፣ ወይም የቤተሰብ የዘር ሐረጋቸውን፣ ወይም የኑሮ ደረጃቸውን፣ ወይም ሥራቸውንና ሞያቸውን፣ ወይም ኢትዮጵያዊነታቸውን፣ ወይም ቀለማቸውን፣ ወይም ደግሞ በጥቅሉ የሰው ዘር መሆናቸውን ከብሔረሰባዊ ትውልዳቸው የበለጠ የማንነታቸው መገለጫ አድርገው ሊያዩ ይችላሉ፡፡

እነዚህ በእያንዳንዱ ሰው ፍላጐትና ስሜት የሚመነጩ የማንነት መገለጫ መንገዶች ሲሆኑ ከፍላጐትም ውጭ ኢትዮጵያ ውስጥ ብሔረሰባዊ ትውልድን የማንነት መገለጫ አድርጐ ለማየት የማያስችሉ ግላዊ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡ አገሪቱ ካለፈችበት የተለያዩ ታሪካዊ መስተጋብሮች አኳያ ከሁለትና ከሁለት በላይ ከሆኑ የተለያዩ ብሔረሰቦች የሚወለዱ ኢትዮጵያውያን በሚሊየን የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከአንድ ብሔረሰብ ተወልደው ነገር ግን በሌላ ብሔረሰብ ቋንቋና ባህል ውስጥ የሚያድጉና ራሳቸውን ከብሔረሰባዊ ትውልድ አንጻር ለማየት የሚቸገሩ ዜጐች በቁጥር ቀላል አይደሉም፡፡ ብዙ ኢትዮጵያዊያን መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ለማውጣት ሄደው ብሔራቸውን ሲጠየቁ በጥቅሉ “ኢትዮጵያዊ ነን” የሚሉት ወይም ብሔረሰባዊ ማንነታቸውን ለመናገር የማይፈልጉት በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት

በአገራችን ሳይፈልጉ ወይም ሳያምኑበት በየቀበሌው መታወቂያ ለመቀበል ሲሉ ብቻ አዲስ ብሔረሰባዊ ማንነት ለመቀበል የሚገደዱ ሰዎችም በቁጥር ቀላል አይደሉም፡፡

በአጠቃላይም የአገሪቱ ሕዝብ በተለያዩ ምክንያቶች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስ፣ በጋብቻና በጉዲፈቻ ሲዋሐድ የኖረ ሕዝብ በመሆኑ አንዳንድ ጊዜ በኢትዮጵያ ሁኔታ ብሔረሰባዊ ማንነት አንድ ኢትዮጵያዊ አሜሪካ ተወልዶ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሆኖ እንደሚያድገው ሁሉ የተወለዱበትን ወይም የሚኖሩበትን አከባቢ ቋንቋ ተናጋሪ ከመሆን የተለየና የበለጠ ትርጉም የማይሰጥበት ሁኔታ ቀላል አይደለም፡፡ ለምሳሌ የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ በአንድ በኩል ተወልጄ ባደግሁበት አካባቢ "ዐማራነት" የኃይማኖት እንጂ የብሔረሰብ ማንነት መገለጫና መጠሪያ ተደርጐ ስለማይታይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዩንቨርስቲ ገብቼ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ለመማር ከሞከርኩ በኋላ ብዙዎቻችን የምንናገረውን ቋንቋ እንደ ዋና የማንነት መመዘኛ በመውሰድ ካልሆነ በስተቀር "የእከሌ ብሔር ነኝ" በማለት ራሳችንን ከሌሎች ለመለየት የምናደርገው ሙከራ ከተለምዶ አባባልና ከሥነ-ልቦና ያለፈ ምንም ዓይነት ታሪካዊ መሠረት የሌለው መሆኑን በመረዳቴ ማንነቴን ከዐማራነት ይልቅ በዜግነትና በሌሎች ግላዊ ባህሪዎችና አስተሳሰቦቼ ለመግለጽ የምመርጥ ሰው ሆኛለሁ፡፡ ሌሎችም ከራሳቸው ግላዊና አካባቢያዊ ሁኔታ በመነሳት ማንነታቸውን በቋንቋም ሆነ በሌላ የተለየ መመዘኛ ሊገልጹት ቢችሉ ስህተት ነው ሊባል አይችልም፡፡ ስለዚህ በእነዚህና እነዚህን በመሰሉ ከግል ፍላጐትና ከአስገዳጅ ሁኔታዎች በመነጨ ራሳቸውን የዚህ ወይም የዚያኛው ብሔረሰብ አባል አድርገው የማይቆጥሩ ዜጐች የአገሪቱ ባለቤት የመሆን መብታቸውን በአዲሱ ሕገ -መንግሥት መሠረት አጥተዋል ማለት ነው፡፡

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ብሔረሰባዊ ማንነትን ብቸኛ የሕዝቦች የአንድነትም ሆነ የልዩነት መገለጫ አድርጐ ማየትም አስቸጋሪ ነው፡፡ የአንድ ብሔረሰብ ተወላጅ የሆኑ ወይም አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎች በሁሉም ነገር ወጥ የሆነ ፍላጐት፣ ጥቅም፣ አመለካከትና ሥነ-ልቦና አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተለያዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች የሚጋሩት ሌላ ጥቅምና ማንነት የለም ማለት አይቻልም፡፡ በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የሀብት፣ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት የመኖሩን ያህል በዚያው መጠን የተለያዩ ቋንቋ በሚናገሩ ሕዝቦች መካከል የኢኮኖሚ ጥቅም፣ የፖለቲካ አስተሳሰብና የሃይማኖት አንድነቶች ይኖራሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ከኢትዮጵያ በላይ ምሳሌ ሊሆን የሚችል አገር አለ ማለት አይቻልም፡፡

አንድ ሰው ከብዙ ጉዳዮች ውስጥ የትኛው ጉዳይ ማንነቱን ለመግለፅ ለሱ እንደሚበልጥበት የሚወሥነውም በግል ጭንቅላቱ አስቦ ነው እንጂ ሁሉንም ነገር ከሌሎች ጋር ተማክሮና "የጋራ

ጭንቅላት” በሚባል የሌለ አካል /organ/ አስቦ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ከሌላው ሰው ጋር የበለጠ አንድ ያደርገኛል ብሎ የሚያስበው አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ ሊሆን የሚችለውን ያህል ሌላው ሰው ደግሞ ከቋንቋ በላይ ሃይማኖት፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም የኑሮ ደረጃ የበለጠ አንድ ያደርገኛል ብሎ ሊያስብ ይችላል፡፡ ሰዎች እንደማንኛውም ጉዳይ አንድነትንና ልዩነትን የሚያዩበት መንገድ የተለያዩ የመሆኑን ያህል የቡድን የሚባል ጭንቅላት ስለሌላቸውም አጠቃላይ ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን ወይም ጥቅማቸውንና ፍላጐታቸውን በብሔረሰባዊ ማንነታቸው በቡድን ፈርጆ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው፡፡

በአንድ ማኅበራዊ ገጽታ ልዩነት ስላለ ብቻ በሌላ ማኅበራዊ ገጽታ ትስሥር እንደማይፈጠር አድርጐ ማሰብና በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ሁልጊዜም ቋሚ ግጭትና ቅራኔ እንደሚኖር አድርጐ ማመንም ስህተት ነው፡፡ ኅብረተሰብ ሁልጊዜም በመካከሉ ያሉ ልዩነቶችን በሌሎች ግንኙነቶች እያካካሰ፣ በሂደት የበለጠ ትስሥርና መቻቻል እየፈጠረ ልዩነቶቹን እያሰፋ ሳይሆን እያጠበበ በጋራ የመኖርና የማደግ ባህሪና ልምድ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ ብሔረሰባዊ ማንነትን የዜጐች ብቸኛ የአንድነትና የልዩነት መገለጫ አድርጐ በማየት የአንድን አገር ህልውና በሕገ-መንግሥት ውስጥ የግድ ከብሔረሰባዊ ማንነት ጋር ለማያያዝ መሞከር የዜጐችን የግል መብት የሚጻረር ከመሆኑም በላይ ዜጐች በልዩነታቸው ላይ የበለጠ እንዲያተኩሩ በመገፋፋት የአገር አንድነትን አደጋ ውስጥ የሚጥል አመለካከት ነው፡፡ ቋንቋ ወይም ብሔረሰባዊ ማንነት በዋናነት የጥቂቶች የሥልጣን መወጣጫ ከመሆን አልፎ የአንድ ሕዝብ ዋና የአንድነት መገለጫ ቢሆን ኖሮ አንድ ዓይነት ቋንቋ ብቻ ሳይሆን አንድ ዓይነት ሃይማኖት ያለባት ሶማሊያ ዛሬ ከርስ በርስ ጦርነት ይልቅ የእኩልነትና የዴሞክራሲ አገር ሆና ባየናት ነበር፡፡ አንድ ቋንቋ መናገር የአንድነት መሠረት ቢሆን ኖሮ ዛሬ በትግራይና በኤርትራ ወይም በእንግሊዝና በአየርላንድ መካከል ያለው ግንኙነት ከመናናቅም አልፎ ወደ ግጭትና ጦርነት ባላመራ ነበር፡፡ ለዚህም ነው የብሔር ጥያቄ የሕዝብን የመብት ጥያቄ በአግባቡ ከማስከበር በላይ በአንድ አገር ውስጥ ለገዥነት የሚፎካከሩ ኤሊቶች ወይም በግራው ፖለቲካ አጠራር ፔቲ ቡርዣዎች መጠቀሚያ በመሆን ያገለግላል የሚባለው፡፡ በነገራችን ላይ ጆሴፍ ስታሊን ራሱ የብሔር ጥያቄን አደገኛነት በመረዳት የሠራተኛው መደብ በዓለም አቀፋዊነት ደረጃ ሊዋጋው የሚገባ ጉዳይ መሆኑን አስምሮበታል፡፡

የብሔር ጥያቄን ከመመለስም ሆነ ማንኛውንም ዓይነት የቡድን መብት ከማክበር አኳያም የቡድንን መብት ከግለሰብ መብት አብልጦና አስቀድሞ ማየት ችግሩን የበለጠ የሚያወሳስብ እንጂ አስተማማኝ መፍትሔ የሚያስገኝ አይሆንም፡፡ የቡድን የሚባል መብት መኖሩና ሰዎች

በተለያዩ መልኩ የአንድ ቡድን አባል በመሆናቸው ምክንያትም ሊደርስባቸው የሚችል በደልና ጥቃት እንደሚኖር አከራካሪ አይደለም፡፡ ነገር ግን በአንድ ቡድን ላይ ይደርሳል የሚባለው በደልና ጥቃት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በእያንዳንዱ የቡድኑ አባል በሆነ ግለሰብ ላይ የሚደርስ በደልና ጥቃት በመሆኑና ችግሩ ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለውም ለችግሩ የሚሰጠው መፍትሄ ለእያንዳንዱ የቡድን አባል የሆነ ግለሰብ መዳረስ ሲችል በመሆኑ፣ ዞሮ ዞሮ የችግሩም ሆነ የመፍትሔው መሠረታዊ መገለጫ የግለሰብ መብት መሆኑን አይቀይረውም፡፡

ሰዎች የአንድ ቡድን አባል በመሆናቸው ጥቃትና በደል ሊደርስባቸው ይችላል ሲባልም የሚደርሰው በደልና ጥቃት ከብሔረሰባዊ ማንነት ጋር ብቻ በተያያዘ ሳይሆን ከሞያና ከፆታ ጀምሮ የተለያዩ ቡድኖች አባል በመሆን ጭምር ሊደርስ የሚችል ነው፡፡ በተለይም ጉዳዩን ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ስናየው ሰዎች በሌሎች ላይ በደልና ጥቃት የሚፈጽሙትም ሆነ የሚፈጸምባቸው በዋናነት የአንድ የተለየ ብሔረሰብ አባል ስለሆኑ አይደለም፡፡ በአገሪቱ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ የተፈራረቁት መንግሥታት ከፈለቁበት ኅብረተሰብ አካባቢ አንጻር በጨቋኝነት ከሚሳተፉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የአንድ ብሔረሰብ ተወላጆች ቁጥር ከሌላው የሚበዛበት ወይም የሚያንስበት ዕድል መኖሩ የማያከራክር ቢሆንም፣ ተጨቋኝ በመሆን ደረጃ ግን አንድ ብሔረሰብ ከሌላው ብሔረሰብ ተለይቶ መዳን የቻለበት የታሪክ አጋጣሚ እስካሁን ድረስ እምብዛም ታይቶ አያውቅም፡፡

በአገራችን እስካሁን በተፈራረቁት አምባገነናዊ ሥርዓቶች ውስጥ በማዕከልና በተዋረድ በሚገኙ የሥልጣን መዋቅሮች የሚኖረው ብሔረሰባዊ ተዋፅኦ የቱንም ያህል የተዛባ ቢሆንም ሕዝቡ በየሚኖርበት አካባቢ /Grass root level/ ግን ጨቋኞቹም ተጨቋኞቹም በዋናነት የአንድ ብሔረሰብ ተወላጆች መሆናቸው እስከ ዛሬም ድረስ በግልጽ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ስለዚህ የግለሰብ መብት በተሟላ ሁኔታ እስካልተከበረ ድረስ ሰዎችን በብሔረሰባዊ ማንነታቸው በማደራጀትም ሆነ የቡድን መብትን ከግለሰብ መብት በማስቀደም ጭቆናን ማስወገድ አይቻልም፡፡ የሁሉም መብቶች መሠረት የሆነው የግለሰብ መብት በቅድሚያ መከበር እስካልቻለ ድረስ የአንድ ብሔረሰብ አባላት ከሌላው ዓለም ሁሉ ተነጥለው በአንድ ደሴት ላይ ብቻቸውን ቢኖሩ በሌሎች ጥቅሞችና ፍላጐቶች እንደገና ተቧድነው ርስ በርስ ጨቋኝና ተጨቋኝ መሆናቸው አይቀርም፡፡ በብሔረሰብ ማንነት አንድ ሆኖ መገኘት የፖለቲካ ችግርን ለማስወገድ መፍትሄ የሚሆን ቢሆን ኖሮ የአንድ ብሔር አገርነት /Nation state/ መስፈርትን ታሟላለች የምትባለው ሶማሊያ ከማንኛውም አገር በላይ ሰላም የሰፈነባትና መብት የሚከበርባት አገር ለመሆን በበቃች ነበር፡፡

ስለ ሰው ልጅ መብት መከበር ስናወራ ከየትኛውም የቡድን መብት በላይ የመብቶች ሁሉ እኩል አካፋይ /common Denominator/ ሆኖ የምናገኘው የግለሰብ መብትን ነው፡፡ ስለ የትኛውም የቡድን መብት መከበር ማውራት ብንፈልግ በግለሰብ መብት ውስጥ የማይገኝ የቡድን መብት የለም፡፡ ራሱ በቡድን መብትን ለማስከበር ተብሎ የሚደረግ የቡድን መደራጀት ከእያንዳንዱ ግለሰብ የመደራጀት መብት የሚመነጭ ነው፡፡ የግለሰብ መብት ያልሆነ የቡድን መብት አለ ከተባለም ያ-ብቸኛ መብት በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ብቻ የሚገኘው የመገንጠል መብት ነው፡፡ ግለሰቦች ከአንድ አገር የመገንጠል መብትም ሆነ ፍላጐት ሊኖራቸው ስለማይችል የመገንጠል መብት ባለቤት ሊሆኑ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ በወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት የመገንጠል መብት መኖሩ አያስደንቅም የተባለውም በሌላ ምክንያት ሳይሆን በዚሁ የአገሪቱ ባለቤቶች ዜጐች መሆናቸው ቀርቶ ብሔር-ብሔረሰቦች እንዲሆኑ ከመደረጋቸው ጋር በተያይዘ ነው፡፡

የአገራችን ሕገ-መንግሥት እንደ ሌሎቹ የዓለማችን ሕገ-መንግሥቶች ሁሉ የመገንጠል መብትን ያላካተተ ቢሆን ኖሮ በአገራችን የግለሰብም ሆነ የቡድን መብት እንዲከበር ለማድረግ ሌላ ፍልስፍና ውስጥ ሳንገባ የተባበሩት መንግሥታትን የሰብአዊ መብቶች መግለጫ በአገራችን ሕገ-መንግሥት መካተቱ ብቻ በራሱ በቂ ይሆን ነበር፡፡ በተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 22 —፣

> *"ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በትውልድ አገር ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ የአንደኛው ክፍል በመሆን፣ በትውልድ ወይም ይህንን በመሰለ ምክንያት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ መግለጫ ውስጥ የተደነገጉት መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ ባለቤት ነው፡፡"* ተብሎ ተደንግጓል፡፡

ከዚህ አገራችን ጭምር ከተቀበለችው ድንጋጌ እንደምንረዳው እንደ አንድ አገር ይህንን ድንጋጌ ተግባራዊ ማድረግ የምንችል ከሆነ ሳይከበር ሊቀር የሚችል የቡድን መብት የማይኖር መሆኑን ነው፡፡

እነዚህን በድንጋጌው ውስጥ የተካተቱ የሰው ልጅ መብቶች ሙሉ በሙሉ እስካከበርን ድረስ እንደ አንድ ሲቭክ ማኀበር ቋንቋችንና ባህላችንን ጠብቀን ለማቆዬት ካልሆነ በስተቀር በፖለቲካ ፓርቲነት በብሔረሰባዊ ማንነት መደራጃት አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያትም አይኖርም፡፡ በርግጥም እነዚህን የሰው ልጅ መብቶች የሕገ-መንግሥታችን አካል ማድረግ ብቻ

ሳይሆን በተግባርም ማስከበር እስከቻልን ድረስ ራስንም ሆነ አገርን በብሔረሰባዊ ማንነት ማደራጀት ለተለዩ የፖለቲካ ጥቅም ተብሎ የሚፈጸም ካልሆነ በስተቀር የብሔር ብሔረሰቦችን መብት የማስከበር ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ እንደ አንድ ቀላል ምሳሌ ብንወስደው የእያንዳንዱ ዜጋና የቡድን መብት ከላይ በተ.መ.ድ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ መሠረት እስከተከበረ ድረስ ከዚያ በኋላ በጋራ ተደራጅተን ለመታገል የምንገደድበት ጉዳይ ከሁሉም በላይ ድህነትን ለማሸነፍ ከሚደረግ ትግል የተለየ አይሆንም፡፡ ድህነትን ለማሸነፍ ደግሞ ለአገሪቱ በሚኖረን አጠቃላይ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ራእይ እንጂ በብሔረሰባዊ ማንነታችን መደራጀትን አስፈላጊና ጠቃሚ አያደርገውም፡፡ ሰው መሆናችን ሁሉንም የመብት ዓይነቶች የሚያጐናፅፈን ሆኖ እስከተገኘ ድረስ በተፈለገው መልኩ መደራጀት መብት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የግድ የዚህ ወይም የዚያ ብሔረሰብ አባል ወይም ቋንቋ ተናጋሪ መሆናችንን እንደ ዋና መመዘኛ በመውሰድ ለፖለቲካ መደራጀትን የምንመርጥ ከሆነ ግን የሰውን ማንነት ከራሱ ከሰው ልጅ መፈጠር በኋላ ከመጣ ቋንቋና ባህል አሳንሶ ከማየት የተለየ ትርጉም አይኖረውም፡፡

ስለዚህ በወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ብሔር- ብሔረሰቦች የአገሪቱ ባለቤቶች መሆናቸው፣ የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት የአገሪቱ ቀዳሚ ችግር የብሔረሰቦች መብት መከበር ጉዳይ እነደሆነ አድርጐ ማየቱና ከግለሰብ መብት ይልቅ የቡድንን መብት ያስቀደመ መሆኑ መሠረታዊ ድክመቱ ነው፡፡ እነዚህ የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ባህሪና ይዘት መገለጫ የሆኑ አስተሳሰቦች የገዥው ፓርቲ የማዕዘን ድንጋይ የሆኑ አስተሳሰቦች መሆናቸውን ስናይም፣ ኢህአዴግ የራሱን አስተሳሰብ እንዴት አድርጐ በቅድሚያ በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት አማካይነት ሕገ-መንግሥታዊ /constitutional/ እንዳደረገውና ቀጥሎም ይህንኑ አስተሳሰቡን አገሪቱ ውስጥ ተግባራዊ ባደረገው የፌደራል አደረጃጀት አማካይነት እንዴት አድርጐ ተቋማዊ /Institutional/ ቅርፅ እንዳላበሰው በግልጽ እንረዳለን፡፡

### 4.2 የአገራችን ፌደራሊዝምና በዙሪያው የሚነሡ ጥያቄዎች

በአገራችን የፖለቲካ መድረክ አከራካሪ ከሆኑትና ብሔራዊ መግባባት ካልተፈጠረባቸው ሕገ-መንግሥታዊ የሆኑ ጉዳዮች ውሰጥ አንዱ አገራችን ምን ዓይነት የፌደራል አደረጃጀት ሊኖራት ይገባል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት መኢአድን የመሰሉ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች "ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሳይሆን አሐዳዊ አደረጃጀት ያስፈልጋታል" የሚል አቋም ስለነበራቸው ክርክሩ በጣም የሰፋ ልዩነት የሚታይበት ነበር፡፡ ነገር ግን በሂደት አሐዳዊ አደረጃጀትን የሚደግፉት ድርጅቶች አቋማቸውን ቀይረው ፌደራላዊ አደረጃትን እየተቀበሉ በመምጣታቸው በአሁኑ ወቅት በጉዳዩ ዙሪያ የሚነሣው ክርክር ፌደራሊዝም ያስፈልገናል ወይስ

አያስፈልገንም? የሚል ሳይሆን ጠበብ ባለ መልኩ አገራችን ምን ዓይነት የፌደራል አደረጃጀት ሊኖራት ይገባል? የሚል ሆኗል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በአንድ በኩል የተማከለ አስተዳደር ቀድሞም ለኢትዮጵያ ባዕድ የነበረና በቅርቡ በአፄ ኃይለሥላሴና በደርግ ዘመን ጥቅም ላይ የዋለ ለአገራችን እንግዳ ሥርዓት በመሆኑ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች፣ አመለካከቶች፣ ጥቅሞችና ፍላጎቶች ላሉባት ኢትዮጵያን ለመሰለ አገር ፌደራሊዝም ተመራጭ የሆነ ሥርዓት መሆኑ ብዙም አከራካሪ ባለመሆኑ ነው፡፡

በፌደራሊዝም ዙሪያ በሚነሣው ክርክር ኢህአዴግና ሌሎች በብሔር የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቋንቋን ዋነኛ መመዘኛ ያደረገውንና በአሁኑ ወቅት በተግባር የዋለውን የፌደራል አደረጃጀት የሚደግፉ ሲሆን፣ ኢዴፓና ሌሎች አንዳንድ ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ አሁን በሥራ ላይ ያለውንና በዋናነት ቋንቋንና ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ያደረገውን የፌደራል አደረጃጀት ይቃወማሉ፡፡ በርግጥ ከኢዴፓ ውጭ ያሉት ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች የወቅቱን የፌደራል አደረጃጀት ሲቃወሙ የእነሱ አማራጭ አደረጃጀት ምን ዓይነት እንደሆነ በአግባቡ አብራርተው ያቀረቡበት ሁኔታ ስለሌለ የዚህ ጽሑፍ ዋና ትኩረት በዋናነት /ሙሉ በሙሉም ባይሆን/ በኢህአዴግና በኢዴፓ መካከል ያለውን ልዩነት መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

ከላይ በጥቅሉ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ኢህአዴግና ኢዴፓ በመካከላቸው ፌደራላዊ አደረጃጀት ለኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነት የላቸውም፡፡ ቢያንስ በመርህ ደረጃ በዋናዎቹ የመንግሥት ምሰሶዎች መካከል የሥልጣን ሚዛንና ቁጥጥር /check & Balance/ መኖር እንዳለበትና ሥልጣንም ወደታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ወርዶ እንዲከፋፈል የማድረግን አስፈላጊነት /Decentralization/ በተመለከተ ሁለቱም ፓርቲዎች በመርህ ደረጃ ልዩነት የላቸውም፡፡ ነገር ግን እነዚህ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን አስተሳሰቦች በትክክል ተግባር ላይ በማዋልና በሌሎች ከፌደራል አደረጃጀት ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ሊባሉ የሚችሉ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ እነዚህን ልዩነቶች በዝርዝር ማየት ከመጀመራችን በፊት ለተሻለ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ የፌደራሊዝምን ታሪካዊ አመጣጥና ትርጉም ጠቅለል ባለ መልኩ ለማየት እንሞክር-፡፡

ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ ፌደራሊዝም የተለያዩ ሉዓላዊ መንግሥታት ለተወሰነ የንግድ ወይም የወታደራዊ ዓላማ ከሚፈጥሩት ከኮንፌደሬሽን ብዙም ያልተለዩ የላላ ትብብርና ኅብረት ተደርጐ ይታይ ነበር፡፡ በሂደት ግን በተለይም ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ከቅኝ አገዛዝ ራሳቸውን ነፃ በማውጣት በአዲስ መልክ የተፈጠሩት የአሜሪካ ግዛቶች በተወሰነ ደረጃ ራሳቸውን

የማስተዳደር ሥልጣናቸውን ጠብቀው ጠንካራ ማዕከላዊ ሚና ያለው የፌደራል መንግሥት ካቋቋሙ በኋላ ፌደራሊዝም የተለየ ትርጉም እያገኘ ሊመጣ ችሏል፡፡ በተለይም በአንድ ሉዓላዊ አገርነት የሚታወቁ አገሮች ውስጣዊ ችግሮቻቸውን በተሻለ መንገድ ለመፍታት ሲሉ በሂደት የፌደራል አደረጃጀትን መጠቀም በመጀመራቸው ፌደራሊዝም በአሁኑ ወቅት በአዲስ መልክ ለሚደራጁ አዲስ አገራት ብቻ ሳይሆን ነባራዊ ሉዓላዊ ማንነት ያላቸው አገራት ጭምር ውስጣዊ ችግራቸውን ለማሻሻል የሚጠቀሙበት አማራጭ አደረጃጀት ለመሆን በቅቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት የዳበረ የፌደራል አደረጃጀት እንዳላቸው ከሚታወቁት አገሮች ውስጥ አሜሪካ፣ ካናዳ፣ ስዊዘርላንድ፣ ሜክሲኮ፣ አውስትራሊያ፣ ህንድና ጀርመንን የመሳሰሉት አገሮች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

ፌደራሊዝም አሁን በደረሰበት ደረጃ ያለው ቀጥተኛ ትርጉም ሕገ-መንግሥታዊ (የተጻፈ) በሆነ አንድ አገር ውስጥ መንግሥታዊ ሥልጣን በተለያዩ አካላት የተከፋፈለበት፣ እያንዳንዱ አካልም በተሰጠው የሥልጣን ክልል ውስጥ የራሱን ኃላፊነት ተግባራዊ የሚያደርግበትና ይህንን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የራሱ ተቋማት አደራጅቶ ጥቅም ላይ ማዋልን የሚፈቅድ የአደረጃጀት ሥርዓት ማለት ነው፡፡ አብዛኞዎቹ የፌደራል አደረጃጀትን ከመረጡ አገሮች ልምድ እንደሚታየውም ለፌደራል አደረጃጀት መሰረር መነሻ የሆኑት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ አንደኛው በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ አመለካከትና አሰፋፈር የመሳሰሉት የተለያዩ ገጽታዎች የሚታዩበት /Heterogeneous/ ኅብረተሰብ መኖር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሰፊ የሆነ ጂኦግራፊያዊ ግዛት መኖር ነው፡፡

የተለያዩ ገጽታዎች የሚታዩበትን ኅብረተሰብ ፌደራላዊ በሆነ ሥርዓት ሥር ማደራጀት ሲባልም የተለያዩ ባህሎች፣ ኃይማኖቶች፣ አመለካከቶችና ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ ተመጣጣኝና ተገቢ ውክልና የሚያገኙበትን ሰፊ ዕድል ከማመቻቸት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ ይህም ማለት ዜጎች በአመለካከት፣ በባህል፣ በሃይማኖትና በሌላም ልዩነት ምክንያት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ ወይም አድልዎ ሳይፈጸምባቸው ነፃነታቸውና እኩልነታቸው በተከበረበት መንገድ ለመኖር የተሻለ ዋስትና የሚያገኙበት ሥርዓት ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰፊ የሆነ ጂኦግራፊያዊ ግዛት ያለውን አገር ፌደራላዊ በሆነ ሥርዓት ሥር ማደራጀት ሲባል ደግሞ፣ በዚያ አገር ውስጥ በስፋታቸው ተመጣጣኝ የሆኑና ለሕዝቡ ቅርበት ያላቸው ያልተማከሉ አስተዳደራዊ ክልሎች ተመሥርተው ሕዝቡ በአንድ በኩል ቀልጣፋና ውጤታማ አስተዳደር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተፋጠነና የተመጣጠነ የልማት ዕድገት የሚያገኝበትን የተሻለ ዕድል መፍጠር ማለት ነው፡፡

በአጭሩ ፌደራላዊ አደረጃጀት ሲባል ዜጎች የፖለቲካና የሲቪል ነፃነቶቻቸውን በሚገባ እንዲጠቀሙ፣ የመንግሥት ሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆናቸውን በተግባር እንዲያረጋግጡና በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ የሚያገኙትን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችላቸው በተማከለ ሥርዓትና ልል በሆነ የኮንፌደሬሽን ግንኙነት መካከል የሚገኝ የአደረጃጀት ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የአንድ የፌደራል መንግሥት አካል የሆኑ ክልላዊ መንግሥታት በየራሳቸው ክልል የሥልጣን የበላይነት የሚኖራቸው ሲሆን አገራዊ ሕገ-መንግሥትን በማሻሻል ረገድም የውሳኔ ሰጭነት ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በአግባቡ የተደራጀ ፌደራሊዝም አስተዳደራዊ ቅልጥፍናና የልማት ዕድገት የማስገኘቱን ያህል፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባህሎቻቸውንና እምነቶቻቸውን በአግባቡ አስጠብቀው መኖር የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡ ፌደራላዊ አደረጃጀት አካባቢያዊ ልዩነቶች በአግባቡ እንዲጠበቁ የማድረጉን ያህልም የአንድነት መገለጫ የሆኑ የጋራ ጉዳዮች በማዕከላዊ መንግሥት በአግባቡ እንዲጠበቁና እንዲራመዱ የማድረግ ዕድል ይፈጥራል፡፡

ፌደራሊዝም ሥልጣንን ወደታችኛው ኅብረተሰብ በማውረድ /Devolution of power/ ዓላማው - በማዕከላዊ መንግሥት አመራር ብቻ ሊሟሉ ያልቻሉትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፍላጎቶች ለማሳካት የሚያስችል የሲቪክ ኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሰፋና ዴሞክራሲ ጥልቀት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡ ወደ ሕዝቡ የቀረቡ በርካታ የሥልጣን መዋቅሮችን በመፍጠርም ኅብረተሰቡ በየፈርጁና በየአካባቢው የተባበረ የልማት ጥረት በማድረግ ድህነትን እንዲያስወግድ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ፌደራሊዝም በመንግሥት ምሰሶዎች መካከል ተመጣጣኝ የሥልጣን ክፍፍልና የርስ-በርስ ቁጥጥር /Check and Balance/ በመፍጠር ዓላማውም በአንድ በኩል በመንግሥት ውስጥ ቀልጣፋና ውጤታማ የሥራ ሂደት እንዲኖር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሥልጣን በአንድ አካል ያለአግባብ ተከማችቶ የሥልጣን ብልግና እንዳያስከትል በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

በአንድ አገር ሃቀኛ የሆነና ችግር ፈች ፌደራላዊ አደረጃጀት አለ ሊባል የሚችለውም - ዜጎች ነፃ ተሳትፎ የሚያደርጉበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲፈጠር፣ የአሠራር ግልጽነትና የሕዝብ ተጠያቂነት ያለው መልካም አስተዳደር ሲመሠረት፣ የመንግሥት አደረጃጀት ያልተንዛዛና ወጭ ቆጣቢ ሆኖ ሲገኝ፣ የአካባቢ ልማትና ገቢ እንዲጠናከር የሚያግዝ የኢንቨስትመንት ሥርጭትና እንቅስቃሴ ሲኖር፣ ፍትሐዊ የሀብት አመዳደብና ሥርጭት ሲኖር፣ ግጭቶችን ለማስወገድና ለመሳሰሉት ጉዳዮች አካባቢያዊ ዘይቤዎችና አሰራሮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲደረግ፣ በአጠቃላይም በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ግልጽነትና

ተጠያቂነት ያለው ሕጋዊ አሠራር በአግባቡ ሰፍኖ ሲገኝ ነው፡፡ በአንድ አገር በዚህ መልክ የሚገለፅ ሃቀኛ ፌደራላዊ አደረጃጀት ሲሰፍን የትብብርና የጋራ ጥቅም ማስከበሪያ ሆኖ በአግባቡ የሚያገለግል ሲሆን፣ በዚህ መልክ ሲገለጥ የማይችል የታይታ /Fake/ ፌደራሊዝም ሲኖር ደግሞ የትርምስና የፍጥጫ ምንጭ ሆኖ አገርን ለዕድገት ሳይሆን ለጥፋት ሊዳርግ ይችላል፡፡ የፌደራሊዝምን አጠቃላይ ትርጉምና ታሪካዊ አመጣጥ በዚህ መልክ በጥቅሉ ካዬን፣ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በአገራችን በአሁኑ ወቅት በተግባር ላይ የዋለው የፌደራል አደረጃጀት ላይ የሚነሡ ልዩነቶችን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

በወቅቱ የአገራችን የፌደራል አደረጃጀት ላይ የሚታየው የመጀመሪያው ችግር ከላይ የሕገ-መንግሥቱን አጠቃላይ ይዘት ለመተቸት ባደረግነው ሙከራ ካነሳነው የአገሪቱ የባለቤትነት ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን ነባር ሉዓላዊነት ያላት አገር እንደመሆንዋ መጠን በዚህች አገር ፌደራላዊ አደረጃጀትን ጥቅም ላይ ማዋል አስፈላጊ የሚሆነው የአገሪቱን ውስጣዊ ችግሮች በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት እንዲቻል ነው፡፡ ነገር ግን አዲሱን የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት መሠረት አድርጐ በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ ተግባራዊ የተደረገው ፌደራላዊ አደረጃጀት አንድ ነባር ሉዓላዊነት ያለው አገር የውስጥ ችግሮቹን ለመፍታት ሲል የሚያደርገው የአደረጃጀት ለውጥ ዓይነት ሳይሆን ቀድሞ ሲል የየራሳቸው ሉዓላዊ ማንነት የነበራቸው የተለያዩ ግዛቶች ወይም አገራት በአንድ አዲስ አገርነት አብረው ለመኖር ሲሉ በስምምነት የሚፈጥሩት ዓይነት ፌደራላዊ አደረጃጀት ነው፡፡

የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት በግልጽ እንደሚያሳዬን በኢትዮጵያ የተከሰተው ለውጥ ቀድሞ የነበረውን የአገሪቱን አሐዳዊ አደረጃጀት ወደ ፌደራላዊ አደረጃጀት የመለወጥ ርምጃ ብቻ ሳይሆን ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ አገሪቱ በብሔር-ብሔረሰቦች አዲስ ስምምነትና ውሳኔ በአዲስ መልክ እንድትፈጠር ያደረገ ለውጥ ነው፡፡ በዚህ ለውጥ ምክንያት የአገሪቱ ባለቤቶች ዜጐች ሳይሆኑ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን፣ እነዚህ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአገር ላይ ያገኙት የባለቤትነት መብት ደግሞ ገደብ የለሽ በመሆኑ ምክንያት ሲያስፈልጋቸው ከአገሪቱ የመገንጠልም ሆነ አገሪቱን የማፍረስ መብት አግኝተዋል፡፡

ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት የራሱ ነባር ሉዓላዊነት የነበረው አገር ሊያራምደው የሚገባው የፌደራል አደረጃጀት አሐዳዊ ሥርዓቱን በፌደራላዊ ሥርዓት ከመተካት፣ በመንግሥት ምሰሶዎች መካከል ተገቢ የሥልጣን ቁጥጥርና ክፍፍል ከመፍጠር፣ የፖለቲካ ሥልጣንን ወደታችኛው የኀብረተሰብ ክፍል ከማውረድ፣ በአገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ልዩነቶች በአግባቡ እንዲከበሩና እንዲጠበቁ ከማድረግ፣ ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ቀልጣፋ አስተዳደርና

ተመጣጣኝ የልማት ዕድገት እንዲያገኙ ከማስቻል አልፎ አገሪቱ እንደ አንድ አገር አንድነቷን ጠብቃ ለመኖር የሚያስችላትን ዋስትና ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለሚባሉት የኅብረተሰብ ቡድኖች አሳልፎ የሚሰጥ መሆን አልነበረበትም፡፡

ኢትዮጵያ ለረዥም ጊዜ (ለስልሳ ዓመት ያህል) በአሐዳዊ አሰተዳደር ሥር የኖረች አገር እንደመሆንዋ መጠን ቀስ በቀስ እየሰፋና እየተጠናከረ በሚሄድ የአተገባበር ቅደም-ተከተል ስልት ወደ ተሟላ የፌደራል ሥርዓት እንድትሸጋገር ማድረግ ሲገባ፣ ሥር ነቀል በሆነ መጠን በአንድ ጊዜ አጠቃላይ የህልውና መሠረቷን ወደሚለውጥና በአንድ ነባር አገር ውስጥ ሳይሆን በተለያዩ ነባር ሉዓላዊነት በነበራቸው አገሮች መካከል ወደሚፈጠር ዓይነት የፌደራል ሥርዓት ውስጥ እንድትገባ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ተግባራዊ የተደረገው ፌደራላዊ አደረጃጀት የመጀመሪያ ድክመት ለአንድ ኢትዮጵያን ለመሰለ የራሷ ነባር ሉዓላዊነት ለነበራት አገር የማይመጥንና የማይገባ ይዘት ያለው አደረጃጀት ከመሆኑ የሚመነጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው በአገሪቱ የፌደራል አደረጃጀት ዙሪያ የሚታየው ድክመት ወይም ችግር የፌደራል አደረጃጀቱ በዋናነት የብሔር-ብሔረሰቦች ጥያቄን ለመመለስ ተብሎ ጥቅም ላይ የዋለ መሆኑ ነው፡፡ ኢህአዴግ ከራሱ እምነትና ፍላጐት ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ቁልፍ የፖለቲካ ጥያቄ የብሔር-ብሔረሰቦች መብት አለመከበር ነው ብሎ ስለሚያምን ለኢህአዴግ ፌደራሊዝም በዋናነት የዚህ ችግር መፍቻ ሆኖ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡፡ በርግጥ ከላይ ከታሪካዊ አመጣጡም ሆነ ከአጠቃላይ ፅንሰ-ሃሣቡ ለማየት እንደሞከርነው ፌደራሊዝም በብሔር - ብሔረሰብም ሆነ በሌላ መልክ ለሚነሳ የቡድን ጥያቄ የተሻለ መልስ ማግኘት የሚያስችል የአደረጃጀት ዓይነት ነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የብሔር -ብሔረሰቦች ጥያቄ ከበርካታ አሳሳቢ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ እንጂ ብቸኛ የአገራችን ችግር አይደለም፡፡ በአገራችን ከብሔር-ብሔረሰቦች የመብት ጥያቄ በተጨማሪ የግለሰብ መብት አለመከበር፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና ከድህነት አረንቋ የመላቀቅ ጥያቄዎች እጅግ አንገብጋቢ ጥያቄዎች በመሆናቸው በአገራችን ጥቅም ላይ የሚውል የፌደራል አደረዳጀት እነዚህን ሁሉ ችግሮች ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውል እንጂ ከብዙ የአገሪቱ አንገብጋቢ ችግሮች ውስጥ አንዱ የሆነውን የብሔር-ብሔረሰቦች ጥያቄ ብቻ ነጥሎ የሚመለከት መሆን የለበትም፡፡ ዞሮ ዞሮ የብሔር- ብሔረሰቦች ጥያቄ የግለሰብ መብቶች ባልተከበሩበት፣ መልካም አስተዳደር ባልሰፈነበትና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ልማት ተጠቃሚነት በሌለበት ሁኔታ ሊመለስ ስለማይችል ኢህአዴግ

የፌደራል አደረጃጀትን በዋናነት ከብሔር-ብሔረሰቦች ጥያቄ ጋር ብቻ አያይዞ ለማየት መሞከሩ ለየትኛውም ጥያቄ የተሟላና አስተማማኝ መልስ ለመስጠት አያስችልም፡፡

ከዚህ የኢህአዴግ የተዛባ አስተሳሰብ ጋር በተያያዘ ሦስተኛው በወቅቱ የፌደራል አደረጃጀት ላይ የሚታየው መሠረታዊ ድክመት የፌደራል ክልሎችን በአገሪቱ ለመፍጠር ጥቅም ላይ የዋለው ዋነኛ መመዘኛ ቋንቋና ብሔረሰባዊ ማንነት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የፌደራል አደረጃጀት ስልት ጠባብና የአገሪቱን አጠቃላይ ችግሮች ለመፍታት የማያስችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ዓይነቱ መመዘኛ ከ70 በላይ ቋንቋዎችን ተናጋሪ የሆኑ ብሔር-ብሔረሰቦች በሚኖሩባት ኢትዮጵያ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አይደለም፡፡ በቋንቋ መመዘኛ ኢትዮጵያ ውስጥ አንዳንድ ክልሎችን ለመፍጠር የተቻለ ቢሆንም እንዲህ ዓይነት መመዘኛ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ሊሠራ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ኢህአዴግ ከራሱ መመዘኛ ጋር በማይጣጣም መልኩ ከኀምሳ በላይ የሆኑ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ ብሔር-ብሔረሰቦች የሚገኙበትን የደቡብ ክልል አንድ ክልል አድርጐ ለመፍጠር እንደተገደደ ታይቷል፡፡

የቋንቋ መስፈርት ጥቅም ላይ የዋለባቸውን ክልሎችም ስናይ የግድ የቋንቋን መስፈርት እንዲያሟሉ ተብሎ በተሠራው ሥራ ምክንያት ሌሎቹን በፌደራል አደረጃጀት ሊገኙ የሚችሉ ጥቅሞችን በሚያሳጣ ሁኔታ በሕዝብ ብዛታቸውም ሆነ በቆዳ ስፋታቸው የማይመጣጠኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አገሪቱ ውስጥ ቋንቋን መሠረት ያደረገ የክልሎች አደረጃጀት ወጥ በሆነ መልኩ መፍጠር እስካልተቻለ ድረስ ሌሎች ጠቃሚ መመዘኛዎችን በመጠቀም በሕዝብ ብዛታቸው፣ በቆዳ ስፋታቸው፣ በመልክአ ምድር አቀማመጣቸው፣ በአስተዳደራዊ አመችነታቸውና በኢኮኖሚ አቅማቸው የተመጣጠነ ቅርፅና ይዘት ያላቸው ክልላዊ መስተዳድሮችን ማደራጀት ሲቻል በመመዘኛ ዓይነትም ሆነ በቅርፅና በይዘት ፈጽሞ  የማይመጣጠኑ የተዘበራረቁ ክልላዊ መንግሥታት በአገሪቱ ተቋቁመዋል፡፡

ከአከላለል መመዘኛ አንጻር በዐማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በአፋርና በመሳሰሉት ክልሎች አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሰዎች የትኛውንም ያህል የሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት ልዩነት በውስጣቸው ቢኖርም የግድ በአንድ ክልላዊ መንግሥት ሥር እንዲካተቱ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ በተቃራኒ ከኀምሳ በላይ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ብሔር-ብሔረሰቦች "ደቡብ" የሚባል የአካባቢ ወይም የሕዝብ ሳይሆን የአቅጣጫ ስም በተሰጠው አንድ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከሕዝብ ቁጥር ብዛት አንጻር ወደ ሁለት ሦስተኛ የሚጠጋው ወይም ከ46 ሚሊየን በላይ የሆነው የአገሪቱ ሕዝብ በሁለት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያና በዐማራ ክልል የሚገኝ ሲሆን፣ በአገሪቱ አምስት ክልሎች ማለትም በአፋር፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ፣

በጋምቤላ፣ በድሬደዋና በሐረሪ ክልል የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በአንድ ላይ ተደምሮ ከሦስት ሚሊየን በላይ አይሆንም። 183 ሺህ የሕዝብ ብዛት ብቻ ያለው የሐረሪ ክልል ራሱን የቻለ አንድ ክልል ሲሆን በደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዳቸው ከ1 እና ከ2 ሚሊየን በላይ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ጉራጌን፣ ጋሞን፣ ወላይታን፣ ሲዳማንና ሐድያን የመሳሰሉ ብሔረሰቦች ግን የክልል መንግሥትነት ደረጃ አልተሰጣቸውም። በአጠቃላይም በአገሪቱ ከተፈጠሩት የክልል መንግሥታት መካከል በሁሉም መመዘኛ በጣም ትልቅ የሚባለውን የኦሮሚያ ክልልና፣ በጣም ትንሽ የሚባለውን የሐረሪ ክልል ስናነጻጽራቸው በሕዝብ ብዛትም ሆነ በቆዳ ስፋት የሰማይና የመሬት ያህል ርቀት ያላቸው ናቸው። ነገር ግን ኦሮሚያ ይህንን ያህል ትልቅ የሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት እያለው ለምን አንድ ክልል ብቻ ሆነ? ወይም ደግሞ ሐረሪ ይህን ያህል ትንሽ የሕዝብ ብዛትና የቆዳ ስፋት እያለው ለምን አንድ ክልል የመሆን መብት አገኘ? ለሚለው ጥያቄ ሊቀርብ የሚችል አሳማኝ መልስ የለም።

የሐረሪ ሕዝብ ክልል የመሆን መብት የተሰጠው አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ስለሆነ ነው እንዳይባል፣ በሐረሪ ክልል ውስጥ ነዋሪ የሆነው ሐረሪ ያልሆነው ሕዝብ ቁጥር ከሐረሪዎች ቁጥር በብዙ እጥፍ የሚበልጥ ነው። በሐረሪ ክልል ከሚኖረው ከ183 ሺ. ሕዝብ ውስጥ 103 ሺ. የሚሆነው ነዋሪ ኦሮሞ፣ 41ሺ. የሚሆነው ነዋሪ ዐማራ ቢሆንም የሐረሪን ክልል የማስተዳደር መብት የተሰጣቸው ሐረሪዎች ግን ቁጥራቸው 15 ሺ. 858 ብቻ ነው። ይህ ዓይነቱ አናሳዎች በብዙኀኑ ላይ የበላይ የሆኑበት የተለየ መብት ለሐረሪዎች በምን ምክንያት እንደተሰጠ በራሱ ዕንቆቅልሽ ቢሆንም ከፍ ሲል የጠቀስናቸው ከሐረሪ ክልል ሕዝብ በብዙ እጥፍ የሕዝብ ብዛት ያላቸው በርካታ በደቡብ ክልል ውስጥ የሚገኙ አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔር-ብሔረሰቦች ይህንን ተመሳሳይ ዕድል አላገኙም። 15 ሺ. የሆኑት ሐረሪዎች የክልልነት መብት ሲያገኙ ብቻውን 3 ሚሊየን የሚሆን ሕዝብ ያለው ሲዳማ ወይም እያንዳንዳቸው 1.8 እና 1.7 ማሊዬን ሕዝብ ያላቸው ጉራጌና ወላይታ ለምን የክልልነት መብት ሊያገኙ እንደማይችሉ ኢህአዴግ ምንም ዓይነት አሳማኝ ምክንያት ሊያቀርብ አይችልም።

ብዙ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች ደቡብ ውስጥ በአንድ ክልል መጠቃለል እስከቻሉ ድረስ ደግሞ ሐረሪ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላንና ድሬዳዋን የመሰሉት ክልሎችም ከሌሎች ብሔር-ብሔረሰቦች ጋር በሌላ ክልል ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም። ደቡብ ውስጥ የሚገኙት ብሔር-ብሔረሰቦች በሌሎች ክልሎች ከሚገኙት ብሔር-ብሔረሰቦች በተለየ በአንድ ክልል አብረው ለመኖር የሚያስችላቸው ልዩ ምክንያት አለ እንዳይባልም መቼም እንደ ደቡብ ክልል በሁለንተናዊ መልኩ ልዩነት የሚታይበት ክልል አለ

ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ክልል ውስጥ አዲስ አበባ አጠገብ በሚኖረው የጉራጌ ሕዝብና ኬንያ ጠረፍ በሚኖረው የሙርሲ ሕዝብ መካከል በቋንቋ፣ በባህል፣ በሥነ-ልቦናም ሆነ በአኗኗር ካለው ልዩነት የበለጠና የተለየ ልዩነት በሌሎች ብሔረሰቦች መካከል ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይሆንም፡፡ የሙርሲና የጉራጌ ሕዝብ በአንድ ክልል ውስጥ መኖር ከቻሉ ኢትዮጵያ ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር በአንድ ክልል ውስጥ አብረው ሊኖሩ አይችሉም የሚባሉ ብሔረሰቦች ሊኖሩ አይችሉም፡፡ ከደቡብ ክልል በተጨማሪ እንደ አዲስ አበባ፣ ናዝሬትና ድሬዳዋ ያሉት ከተሞች የሚያሳዩንም ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ በተለያዩ አስተዳደራዊ ክልሎች ውስጥ አብሮ ለመኖር የግድ በቋንቋ መስመር መከፋፈልና መቧደን የማያስፈልገው መሆኑን ነው፡፡

ኦሮሚያና ዐማራ ክልልን የመሰሉት ክልሎችም ከሌሎቹ ትናንሽ ክልሎች ተለይተው ትልልቅ ክልሎች ለመሆናቸው ሊቀርብ የሚችል አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ በአገሪቱ ተመጣጣኝ ቅርፅና ይዘት ያላቸው ክልሎች ኖረው በፌደራሊዝም አደረጃጀት ሊገኙ የሚገባቸው ጥቅሞች በሙሉ እንዲገኙ ከተፈለገ ኦሮሚያም ሆነ ዐማራ ክልል ከሁለት ወይም ከሦስት ክልል ተከፍለው የማይደራጁበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በአንድ አገር ውስጥ የሚገኝ አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ብሔር ወይም ብሔረሰብ የግድ በአንድ ክልላዊ አስተዳደር መካተት አለበት የሚል ተቀባይነት ያለው ቀመር /Formula/ በየትም አገር የለም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአንድ አገር ውስጥና አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች በተለያዩ አገሮችም ውስጥ ተለያይተው ይኖራሉ፡፡ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ስፓኒሽ፣ ዐረብኛ የሚናገሩ ሕዝቦች በተለያዩ አገሮች ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የዓለማችን አሕጉሮች ተለያይተው ይኖራሉ፡፡ በብዙ የተለያዩ የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች የሚኖሩ ስዋሊህኛ ተናጋሪ ሕዝቦች የመኖራቸውን ያህል - በአፍሪካ ቀንድም ሶማሊኛ የሚናገሩ ሕዝቦች በጅቡቲ፣ በኢትዮጵያና በሶማሊያ፣ ኦሮምኛ የሚናገሩ ሕዝቦች በኢትዮጵያና በኬንያ፣ አፋርኛ የሚናገሩ ሕዝቦች በኢትዮጵያና በጅቡቲ፣ ትግርኛ የሚናገሩ ሕዝቦች በኢትዮጵያና በኤርትራ፣ ወዘተ ተከፋፍለው እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ የዐማራም ሆነ የኦሮሞ ሕዝብ በአንድ አገር ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ክልሎች እንዲኖሩ ቢደረግ ስህተትም ሆነ ነውር የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ጉዳዩ የሕዝብን አንድነት የመጠበቅ ሆኖ የሚታይ ከሆነም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የበለጠ ጥረትና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ነው እንጂ በእያንዳንዱ ብሔር-ብሔረሰብ ውስጥ ያለው አንድነት አይደለም፡፡ በእያንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪ ወይም ብሔር-ብሔረሰብ መካከል ውስጥ የአንድነት ጥያቄ አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው የኢትዮጵያ አንድነት ፈርሶ እያንዳንዱ ብሔር-ብሔረሰብ በራሱ መንግሥት ሆኖ የቆመ እንደሆነ ነው፡፡ የክልል

መንግሥትነት ደረጃ ስላገኙ ብቻ ዛሬ የጠነከረ አንድነት ያላቸው መስለው የሚታዩን የኦሮሞ ወይም የዐማራ ክልል ነገ ከኢትዮጵያ ተገንጥለው በየራሳቸው እንደ አገር ለመቆም ቢሞክሩ በውስጣቸው የሚፈጠረው የአንድነት አደጋ ዛሬ በኢትዮጵያ ከሚታዬው የአንድነት አደጋ የባሰ እንጂ ያነሰ ላይሆን ይችላል፡፡

በአገራችን እንዲህ ዓይነት የይዘትም ሆነ የቅርፅ መመጣጠን የማይታይባቸው ጉራማይሌ ክልሎች እንዲኖሩ ምክንያት የሆነው ቋንቋን ወይም ብሔረሰባዊ ማንነትን በዋናነት መሠረት ያደረገ ፌደራላዊ አደረጃጀት ለመፍጠር ስለተፈለገ ነው፡፡ በደቡብ ክልል እንደሚታየው የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ይህንን ለማድረግ የማያስችል ቢሆንም በአንድ በኩል በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሆኑ ስለተደረገ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ በውስጡ ያቀፋቸው ፓርቲዎችና አጋር ድርጅቶቹ በብሔረሰባዊ ማንነታቸው የተደራጁ ስለሆኑ ብቻ የአገሪቱ የፌደራል አደረጃጀት ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና ችግሮች ጋር ሳይሆን እንደ ጫማ ወይም እንደ ቀሚስ በልክ ተሰፍቶ ከኢህአዴግ አደረጃጀትና አስተሳሰብ ጋር ነው እንዲጣጣም የተደረገው፡፡

በዚህ መልክ የአንድን የፖለቲካ ቡድን አደረጃጀትና አስተሳሰብ በአገሪቱ ተቋማዊ /Institutional/ ይዘት ለማላበስ ተብሎ የሚፈጠር የፌደራል አደረጃጀት ሌሎቹን በፌደራል አደረጃጀት እንዲገኙ የሚፈለጉ ጥቅሞችን ይቅርና ራሱ ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ እቆረቆርለታለሁ የሚለውን የብሔር-ብሔረሰቦች መብት በአግባቡ ለማስከበር አያስችልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ውጥንቅጥ የፌደራል አደረጃጀት በሁሉም የፌደራል ክልሎች የተመጣጠነ የልማት ዕድገትም ሆነ የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ ሥርዓት ሊያስገኝ ስለማይችል ዞሮ ዞሮ የቡድንም ሆነ የግለሰብ የመብት ጥሰት ማስከተሉ አይቀርም፡፡ በሁሉም መመዘኛ ፈጽሞ በማይመጣጠኑት የሐረሪና የኦሮሚያ ክልሎች በየትኛውም መንገድ ከፖለቲካ መብትም ሆነ ከኢኮኖሚ ጥቅም መከበር አንጻር ሚዛናዊ ተጠቃሚነት ማምጣት አይቻልም፡፡ ይልቁንም የተሻለ የሚሆነው ቋንቋንና ብሔረሰባዊ ማንነትን እንደ ብቸኛና ዋና መመዘኛ ሳይሆን ከሌሎች በርካታ ግምት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ መመዘኛዎች ውስጥ እንደ አንድ መመዘኛ ወስዶ ለፌደራል አደረጃጀታችን እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻርም ከቋንቋ ወይም ከብሔረሰባዊ ማንነት በተጨማሪ የመሬት አቀማመጥ፣ የሕዝብ ብዛት፣ የኅብረተሰቡ አብሮ የመኖር ታሪካዊ ትስሥር፣ የአስተዳደራዊ አመችነትና የኢኮኖሚ አቅም የመሳሰሉት ጉዳዮች የፌደራል አከላለል መመዘኛዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ እነዚህ መመዘኛዎች እንደዬ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ

በተናጠልም ሆነ በጣምራ ጥቅም ላይ ቢውሉ በአገራችን በቆዳ ስፋታቸውና በሕዝብ ብዛታቸው ከአሁኑ የትግራይ ክልል በተወሰነ ደረጃ ሰፋ-ሰፋ ያሉ ከዐሥር እስከ ዐሥራ ሁለት የሚደርሱ የተመጣጠኑ ክልላዊ መስተዳድሮችን መፍጠር ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አሁን የክልል ደረጃ ያላቸውና እያንዳንዳቸው 4.3 እና 4.4 ሚሊየን የሕዝብ ብዛት ያላቸው ትግራይና ሶማሊያ በአሉበት ደረጃ ክልል ሆነው ቢቀጥሉ፤ ኦሮሚያ ወደ አራት ክልልነት፣ ዐማራ ወደ ሦስት ክልልነት፣ ደቡብ ወደ ሁለት ወይም ሦስት ክልልነት ቢከፋፈሉና አፋር፣ ሐረሪ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ጋምቤላና ድሬዳዋ በአካባቢያቸው በሚገኙ ሌሎች ክልሎች እንደዬስፋታቸው የልዩ ዞን ወይም የልዩ ወረዳ ደረጃ ተሰጥቷቸው እንዲጠቃለሉ ቢደረግ አገሪቱ ከዋና ከተማዋ ከአዲስ አበባ ውጭ ዐሥራ አንድ ወይም ዐሥራ ሁለት ተመጣጣኝ ክልሎች ሊኖሯት ይችላሉ፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የአከላለል ለውጥ ጥቂት (ከስድስት የማይበልጡ) የክልል ፕሬዝደንቶችን ሊያስከፋ ይችል እንደሆነ እንጂ ከእያንዳንዱ ብሔር-ብሔረሰብም ሆነ ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ ጥቅም አንጻር ሲታይ የሚያስገኘው ጥቅም እንጂ የሚያስከትለው ጉዳት የለውም፡፡ እንዲያውም የክልል ፕሬዝደንቶች ቁጥር ከዘጠኝ ወደ ዐሥር ወይም ዐሥራ ሁለት የሚያድግ ሲሆን በአንድ የክልል ፕሬዝደንት ይወከል የነበረው ኦሮሚያ ክልል በአራት፣ ዐማራ ክልል በሦስት፣ ደቡብ ክልል በሁለት ወይም በሦስት የክልል ፕሬዝደንቶች እንዲወከሉ የሚያስችል የተሻለ ዕድል ይፈጥራል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አደረጃጀትም እግረ መንገዱን በወለጋና በሌሎች የኦሮሚያ አካባቢ ኤሊቶች፣ በሸዋና በሌሎች የዐማራ አካባቢ ኤሊቶች፣ በሲዳማና በወላይታ ኤሊቶች መካከል የሚታየውን ዓይነት ሽኩቻ ለመፍታት ያስችላል፡፡ በትላልቅ ክልሎች የሚገኘው ሕዝብም በልማትም ሆነ በፖለቲካ የተሻለ ያልተማከለ ሥርዓት እንዲፈጠርለትና የምንጃር ሰው ባህርዳር፣ የወለጋ ሰው አዳማ፣ የሃመር ሰው አዋሳ ከተማ ድረስ ፍትህ ለማግኘት እንዳይንከራተትና የቀረበ የክልል ከተማ እንዲኖረው ያስችለዋል፡፡

በነፍስ ወከፍ ድርሻ ሲሰላ ከሌሎች ክልሎች ያነሰ የፌደራል ድጐማ በማግኘት ሲጐዱ የኖሩ ኦሮሚያን፣ ዐማራንና ደቡብን የመሰሉ ሰፋፊ ክልሎችም ፍትሐዊ የበጀት ድጐማ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር የሚያስችላቸው ልዩ ዞን ወይም ወረዳ የማቋቋም መብት እስካገኙ ድረስ በእንዲህ ዓይነቱ አከላለል ወደ ሌላ ክልል ሊጠቃለሉ የሚችሉት አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ክልሎች ሊደርስባቸው የሚችል ምንም ዓይነት ጉዳት ባይኖርም ምንአልባት ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የነበራቸውን የክልል ደረጃ ማጣታቸው ሊያስከፋቸው ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ ክልሎች በላይ በሚሊየን የሚቆጠር የሕዝብ ብዛት ያላቸው በርካታ ብሔር-ብሔረሰቦች በደቡብ ክልል ውስጥ የክልል ደረጃ

ሳይኖራቸው እየኖሩ ባለበት ሁኔታ "እኔ ለምን በተለየ ሁኔታ ክልል አልሆንኩም?" ተብሎ ሊፈጠር የሚችለው መከፋት ምክንያታዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁሉም ተደምረው 3 ሚሊየን የሕዝብ ብዛት የሌላቸው አምስቱ ክልሎች ማለትም -አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉምዝና ድሬዳዋ እያንዳንዳችን ለምን ክልል ሆነን አንቀጥልም? የሚል ጥያቄ ቢያነሱ ብቻውን 3 ሚሊየን የሚጠጋ የሕዝብ ብዛት ያለው የሲዳማ ሕዝብ "እኔስ ለምን የክልልነት ደረጃ አይሰጠኝም?" ብሎ ቢጠይቅ መልሱን እጅግ ፈታኝ ያደርገዋል፡፡

ዋናው ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባው ቁም ነገር አንድ ሰፊ ክልል ሲከፋፈልም ሆነ አንድ ጠባብ ክልል ከሌላ ጋር እንዲዳበል ሲደረግ ሕዝቡ የበለጠ ጥቅም እንዲያገኝ እንጂ የነበረውን ጥቅም እንዲያጣ አለመደረጉ ላይ ነው፡፡ በርግጥ አንዳንድ እንዲህ ዓይነቱ የክልሎች መከፈል ወይም መዳበል የሚለው አስተሳሰብ የሚያስደነግጣቸው ሰዎች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የተሻለ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አስተዳደር ከመፍጠር ጋር የተያያዘ እንጂ በመከፈሉም ሆነ በመዳበሉ ሂደት ከቦታው የሚነቀል መሬትም ሆነ ሕዝብ አይኖርም፡፡ በተለይም ሕዝቦች በየአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው ሳይሸራረፍ እስከተከበረ ድረስ እንዲህ ዓይነቱ የአደረጃጀት ለውጥ የሚያስገኘው ተጨማሪ ጥቅም እንጂ የሚያስከትለው ጉዳት የለም፡፡

ነገር ግን እንዲህ ዓይነት የአከላለል ማሻሻያ በአንድ አገር (በተለይም በኢትዮጵያ) ላይ ማካሄድ በአፍ እንደምናወራውና በወረቀት ላይ እንደምንጽፈው ቀላል ነገር ስላልሆነ በእያንዳንዱ ውሳኔ ላይ የሕዝቡ ሙሉ ፈቃደኛነት እንዲኖር የሚያስችል እስከ ሕዝበ-ውሳኔ የሚደርስ የውሳኔ ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ኢህአዴግን ጨምሮ እስካሁን በአገሪቱ እንደተፈራረቁት መንግሥታት ለራስ አገዛዝ የሚያመችን አደረጃጀት በሕዝብ ላይ በዘፈቀደ መጫን ዘላቂና አስተማማኝ ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል በአከላለል ጉዳይ ላይ የሕዝብ የውሳኔ ተሳትፎ መኖር በሌላ አካል የማይተካ ሚና ተደርጎ ሊታይ ይገባዋል፡፡

በአጠቃላይ እንዲህ ዓይነቶቹ የተመጣጠኑ ክልሎች በአገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጐች ከበጀት ክፍፍል፣ ከልማት ተጠቃሚነት፣ ከአስተዳደራዊም ሆነ ከፖለቲካ ተሳትፎ አንጻር ሚዛናዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማስቻሉም በተጨማሪ በክልሎች መካከል የሚኖርን ጤናማ ያልሆነ የፉክክር መንፈስ በማስወገድ ለአገር አንድነት ዋስትና የሚሆን ፖለቲካዊ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የተለያዩ መስፈርቶችን ግምት ውስጥ የሚያስገባና ቋንቋን ብቸኛ መመዘኛ ያላደረገ የፌደራል አከላለል የብሔር-ብሔረሰቦችን መብት ማስከበር የማያስችል አደረጃጀት አድርጐ ማየትም ስህተት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አገዎች፣ አርጐባዎችና ኦሮሞዎች

በዐማራ ክልል ውስጥ ልዩ ዞን ወይም ልዩ ወረዳ ኖሯቸውና ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው ተከብሮ እየኖሩ እንደሚገኙት፤ ከነምሳ በላይ ብሔር-ብሔረሰቦችም በደቡብ ክልል አንድ ላይ አብረው እየኖሩ እንደሚገኙትም ሆነ በአገራችን የተለያዩ ከተሞች ሕዝቦች የትኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው አብረው እየኖሩ እንደሚገኙት ሁሉ በማንኛውም ዓይነት የክልል አደረጃጀት የብሔር-ብሔረሰቦች መብት በአግባቡ እንዲከበር ማድረግ የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሌላው ቀርቶ ጥቂቱ ሕዝብ በአብዛኛው ሕዝብ ላይ ያለ አግባብ የበላይ እንዲሆን በተደረገበት በሐረሪ ክልልም የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች በሰላምና በፍቅር አብረው ሲኖሩ እያዬን ነው፡፡

አስፈላጊ ሆኖ እስከ ተገኘ ድረስም በእያንዳንዱ ከላይ በተጠቀሱት መመዘኛዎች መሠረት በሚደራጁት ተመጣጣኝ የአገሪቱ ክልሎች ውስጥ ቢያንስ ለሕዝብ አስተዳደር ቅርበት ያላቸው የወረዳና የቀበሌ መዋቅሮች ቋንቋን ወይም ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ መስፈርት እንዲደራጁ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ዓይነቱን አደረጃጀት ከሞላ ጐደል በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች (ከከተሞች በስተቀር) በርግጠኛነት ተግባራዊ ማድረግ የሚቻል ሲሆን ይህም በራሱ ብሔር-ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር፣ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን በማስጠበቅና በመጠበቅም ረገድ ሰፊ ዕድል እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በቀበሌና በወረዳ ብቻም ሳይሆን በዞንና በክልልም ደረጃ ተመጣጣኝ ክልሎችን መፍጠር እስካስቻለን ድረስ እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ቋንቋን ወይም ብሔረሰባዊ ማንነትን ዋነኛ መስፈርት አድርገን ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ በዚህ ሁኔታ የብሔር-ብሔረሰብ መብቶችን ከአገሪቱ አንድነትና ከሌሎች በፌደራል አደረጃጀት ልናገኛቸው ከሚገባን ጥቅሞች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ማክበር እስከቻልን ድረስ የግድ ሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በቋንቋ መስፈርት ብቻ መቋቋም አለባቸው ብሎ መከራከር መብት ቢሆንም ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ የሚቀርብ ክርክር ግን ሊሆን አይችልም፡፡

እንኳንስ በዚህ መልኩ የተለያዩ መመዘኛዎችን (ቋንቋን ጭምር) ባካተተ የፌደራል አደረጃጀት የተደራጁ ክልሎችና - አሜሪካንና ካናዳን በመሰሉ አገሮችና ከዚያም በላይ አሐዳዊ ሥርዓት በሚያራምዱ አገሮች ጭምር የማንኛውም ዓይነት የቡድን እና የአናሳዎች መብት በተሻለ ሁኔታ ይከበራል፡፡ ስለዚህ አገራችን ካሉባት በርካታ አሳሳቢ ችግሮች መካከል የብሔር-ብሔረሰቦች መብት ጉዳይም ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ ችግር መሆኑን ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ሌሎቹንም ከግለሰብ መብት፣ ከመልካም አስተዳደርና ከድህነት ጋር የተያያዙ ፈርጀ ብዙ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚያስችለን ከአሁኑ የተሻለ የፌደራል አደረጃጀት ቢኖረን የተሻለ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያን በመሰለ በርካታ ውስብስብ ችግሮች ባሉባት አገር የብሔር-

ብሔረሰቦችን ጉዳይ ከመጠን በላይ ለጥጠንና አክርረን በማየት ሌሎቹን ችግሮቻችንን የሚያባብስ ብቻ ሳይሆን በሂደት አዳዲስና ለአጠቃላይ የአገር ህልውና አደጋ የሚሆኑ ችግሮችን እንዳንፈጥር መጠንቀቅ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ የምንከተለው የፌደራል ሥርዓት በአንድ በኩል በአገር አንድነትና በልዩነቶች መከበር (unity Vs diversity) መካከል ያለውን ሚዛን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በማዕከላዊ የፖለቲካ መዋቅሩና በዳር አገሩ (center Vs perfairy) መካከል ያለውን ሚዛን በአግባቡ የሚጠብቅ መሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት በአገራችን ፖለቲካ የሚታየው መሠረታዊ ችግር በሁለት የተራራቀና የተካረረ ጫፍ ላይ የቆሙ ማለትም የአገር አንድነት አፍቃሪነት /patriotism/ እና የብሔርተኝነት /ultra nationalism/ ስሜቶች በመኖራቸው በመሆኑ የነዚህን ልዩነቶች ሚዛን በአግባቡ የማይጠብቅ የፌደራል ሥርዓት ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ የወቅቱ የአገራችን የፌደራል አደረጃጀት ከዚህ ሚዛን በተቃራኒ ልዩነት በአንድነት ላይ /diversity over unity/ ወይም ብሔርተኝነት በአገር አንድነት አፍቃሪነት ላይ /ultra nationalism over patriotism/ የበላይነት መያዙን በጎላ ሁኔታ የሚያሳይ በመሆኑ ዘላቂ የፖለቲካ መረጋጋት በአገራችን ሊያመጣ የሚችል አይሆንም፡፡

### *4.3 የመገንጠል መብትና በዙሪያው የሚነሡ ጥያቄዎች*

አሁን አሁን በመጠኑ እየደበዘዘ ቢመጣም በአዲሱ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የመገንጠል መብትን እንደሚፈቅደው አንቀጽ 39 አከራካሪ የሆነ አንቀጽ ነበር ወይም አለ ማለት አይቻልም፡፡ አንቀጽ 39 ትርጉም ያለው አንቀጽ ሊሆን የሚችለው ከዚህ በላይ ለማየት የሞከርናቸውን የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከመሆናቸውና የአገሪቱ የፌደራል አከላለል በዋናነት ቋንቋንና ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ያደረገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ቢሆንም ከእነዚህ ቀዳሚና መሠረታዊ ጉዳዮች ይልቅ እነዚህን ተከትሎ የመጣው የመገንጠል መብት በአገሪቱ የፖለቲካ መድረክ ከሚገባው በላይ የበለጠ የመከራከሪያ ነጥብ ለመሆን በቅቷል፡፡

እንደ ሌሎቹ አከራካሪ ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ሁሉ በኢህአዴግና በአንዳንዶቹ በብሔር የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የመገንጠል መብትን በተመለከተ መሠረታው ልዩነት የሌለ ቢሆንም ሁሉም ኅብረ-ብሔራዊ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አንዳንድ በብሔር የተደራጁ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭምር የመገንጠል መብትን አምርረው ይቃወሙታል፡፡ በርግጥ አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንቀጽ 39 በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተካተተበትን ምክንያት /Logic/

አገሪቱ የብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ንብረት እንድትሆን ከመደረጓ ጋር አያይዘው ስለማይረዱት አንቀጽ 39ን በሚመለከት ብዙውን ጊዜ የሚያነሡት ክርክር ቁንፅልና ሚዛኑን የሳተ ሲሆን ይስተዋላል፡፡

ይኸውም አገሪቱ እንደ አንድ ነባር ሉዓላዊነት ያለው አገር ሳይሆን እንደ አንድ አዲስ አገር በብሔር፣ ብሔረቦችና ሕዝቦች ስምምነት ተመሠረተች ከተባለና በህልውናዋም ላይ ለመወሰን ሕገ-መንግሥታዊ መብት ያላቸው እነዚህ ባለቤቶቿ ናቸው እስከተባለ ድረስ አንቀጽ 39 በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ኖረም አልኖረም ብዙም ልዩነት የለውም፡፡ አንድ ወንድና ሴት ትዳር ሲመሠርቱ ከመዘጋጃ ቤት የሚያገኙት የጋብቻ ሰርቲፊኬት ከጋብቻቸው እንዴት ሲያስፈልጋቸው እንዴት ሊፋቱ እንደሚችሉ የሚገልፀው ነገር እንደሌለው ሁሉ የአገሪቱ መሥራች ባለቤቶች ብሔር-ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆናቸው እስከተገለፀ ድረስ አንቀጽ 39 ኖረም አልኖረም እነዚህ የአገሪቱ ባለቤቶች ሲፈልጉ በበጎ ፈቃዳቸው መሠረቱት ከተባለው አገር የመገንጠል መብታቸውን ሊያስቀረው የሚችል ምክንያት አይኖርም፡፡ ከሌሎች አገሮች ታሪካዊ ሁኔታ በግልጽ እንደምንረዳውም ከሌሎች አገሮች በመገንጠል ሂደት የተፈጠሩ ኤርትራን የመሰሉ በርካታ አገሮች ለመገንጠል የበቁት ሕገ-መንግሥት ውስጥ በሰፈረ የመገንጠል መብት አማካይነት አልነበረም፡፡ የካናዳ ግዛት የሆነችው ኪውቤክ ለሁለት ጊዜ የመገንጠል ሕዝበ-ውሳኔ ያካሄደችው በካናዳ ሕገ-መንግሥት ውስጥ ጭራሽ ስለመገንጠል የሚያወራ አንቀጽ በሌለበት ሁኔታ ነው፡፡ ስለዚህ ለመገንጠል መብት መነሻ ምክንያት በሆኑት መሠረታዊ የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘቶች ላይ መከራከር ሲገባን አንቀጽ 39 መኖር አለበት - የለበትም? እያልን ስንከራከር መክረማችን ብዙም ትርጉም ያልነበረው ጉንጭ አልፋ ክርክር ነበር ማለት ይቻላል፡፡

አሁንም አንቀጽ 39 በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ስለመኖሩና አለመኖሩ ጠቀሜታ መነጋገር ብዙም የማይጠቅመን ቢሆንም ከላይ ከተወያዩንባቸው የሕገ-መንግሥቱ አጠቃላይ ይዘት ጋር በተያያዘ የአገሪቱ ብሔር- ብሔረሰቦች የመገንጠል መብት ያላቸው መሆኑ በአገሪቱ የወደፊት ህልውና ላይ ምን ዓይነት እንድምታ እንደሚኖረው ለማየት እንሞክራለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን የመገንጠል መብትን ታሪካዊ አመጣጥና የፅንሰ-ሐሳቡን ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው ማየት ለተሻለ ግንዛቤ ይረዳን ይሆናል፡፡

ከኢትዮጵያ ውጭ ቀደም ሲል የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚል መብት በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ በማካተት የሚታወቁት አገሮች ሶቭዬት ኅብረትና ዩጎዝላቪያ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት አገሮች ያለፉበት ታሪካዊ ሂደት ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የማይመሳሰል ከመሆኑም በላይ አገሮቹ ይህንን ዓይነት መብት በሕገ-መንግሥታቸው

በማካተታቸው ምክንያት የመጨረሻ ውጤታቸው መፈረካከስ እንጂ አንድነትን ጠብቆ መቀጠል ሲሆን አልታየም፡፡ እንዲያውም በዩጎዝላቪያ የታዬው የመጨረሻ ውጤት በአገር መበታተን ብቻ ሳይሆን ዘግናኝ በሆነ የዘር ማፅዳት ፍጅት መፈራረስ ነው የሆነው፡፡

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ ዋና አቀንቃኝ በነበረችው ሶቭዬት ኅብረት ይህ ፅንሰ-ሐሳብ ተቀባይነት ለማግኘት የቻለበት የራሱ መነሻ ምክንያት ነበረው፡፡ በሩሲያ የዛሩ አገዛዝ ዘመን በታላቁ ፒተር አማካይነት በሩሲያ ግዛት ሥር በኃይል የተጠቃለሉ ሩሲያዊ ያልሆኑ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ በኋላ ላይ በሩሲያ የፖለቲካ የበላይነት እያገኙ የመጡት ኮሚኒስቶች እነዚህ ሩሲያዊ ያልሆኑ ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ ከተከበረላቸው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ ኅብረት ፈጥረው አብረው ለመኖር ይችላሉ የሚል አዲስ ቲዎሪ ፈጥረው በመንቀሳቀስ የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት እ.ኤ.አ በ1917 ለድል እንደበቃ በቀድሞ የሩሲያ አገዛዝ ተፅዕኖ ሥር የነበሩ ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብታቸው እስከ መገንጠል ድረስ የተረጋገጠ መሆኑ በይፋ ታወጀ፡፡ ይህ አዋጅ ከታወጀ ከጥቂት ወራቶች በኋላ ዩክሬይንና ፊንላንድ ነፃ መንግሥት ሆነው ዕውቅና አገኙ፡፡ ከዚያ በኋላ ኮሚኒስቶች "ለአንድነት ሲባል መለያየት /disunity for the sake of unity/" የሚል አስተሳሰብ በማራመድ የተወሰኑ ሌሎች ግዛቶችን አሰባስበው በ1922 ሶቭዬት ኅብረትን /USSR/ ለመመሥረት በቁ፡፡

ይህ ለአንድነት ሲባል መለያየት የሚለው የእነ ሌኒን መርህ በወቅቱ ዐሥራ አምስት ግዛቶችን ያሰባሰበ መንግሥት ለማቋቋም በማስቻሉ የኮሚኒስቶች ቲዎሪ ያስገኘው አዲስ ድል ሆኖ በሰፊው ተሰበከ፡፡ ይሁንና በሶቭዬት ኅብረት የጭቆና አገዛዝ ከቀድሞው በተለየ መልኩ ተንሰራፍቶ የሰዎችን መብትና ነፃነት በአስከፊ ሁኔታ መደፍጠጡን ቀጠለ፡፡ ሆኖም በአንድ በኩል ከሶቪዬት ኅብረት እንደገና ለመገንጠል አገዛዙ ሊፈቅድ የማይችል አፋኝ ስለነበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በኅብረቱ ውስጥ ከነበረው ልዩነት በላይ በወቅቱ በሶቪዬት ኅብረት ግንባር ቀደም መሪነት በብዙ የዓለም አገሮች ተቀባይነት እያገኘ የመጣው የማርክሲዝም ሌኒኒዝም ርእዮተ-ዓለም የበለጠ የማስተሳሰር ባህሪ ስለነበረው ኅብረቱ ረዥም ጊዜ ለመቆዬት ቻለ፡፡ ሶቭዬቶች ይህንን "የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል" የሚለውን አስተሳሰባቸውን ለውስጥ ጉዳያቸውም ብቻ ሳይሆን በወቅቱ በቅኝ ግዛት ሥር ለነበሩ የተለያዩ የዓለም አገሮች ነፃ መውጣት የተቆርቋሪነት ስሜት መግለጫና በዓለም አቀፍ ደረጃም የድጋፍ ማሰባሰቢያ አጀንዳ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ ነገር ግን በኅብረቱ ውስጥ ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ቦምብ /Time bomb/ ተቀብሮ ስለነበር ኮሚኒዝም በቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ተሸንፎ የጉርባቾቭ የፖለቲካና

የኢኮኖሚ ተኃድሶ /Glasnost and perestroika/ ሲበሰር ሶቭዬት ኅብረት ከሰባ ዓመታት ኅብረት በኋላ ጊዜ ጠባቂው ቦምብ ፈንድቶ ፈራረሰች፡፡ በኅብረቱ ውስጥ የነበሩት አገሮችም ወዲያውኑ አንዳቸው የሌላቸው ጠላት ሆነው ከመቆማቸው በላይ በእያንዳንዳቸውም ውስጥ ሌላ የመገንጠል ጥያቄ ከማስተናገድ አልዳኑም፡፡ በጆርጅያ ውስጥ ደቡብ ኦሴሺያ እና አብካዚያ የመገንጠል ጥያቄ ያነሱ ሲሆን ሌላው ቀርቶ አንድ ሆና በኖረችው በሩሲያ ውስጥ ቺቺኒያ ተገንጣይ አቋም ይዛ ብቅ ብላለች፡፡

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ በዮናነት ግልጽ የሆነ ታሪካዊ ሂደት የነበረው በሶቭዬት ኅብረት ውስጥ ቢሆንም “የራስን ዕድል በራስ መወሰን” የሚለው አስተሳሰብ ከአንደኛው ዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ በወቅቱ የአሜሪካን ፕሬዝዳንት በነበሩት በውድሮው ዊልሰን/ Woodrow Wilson/ አማካይነት በጦርነት ተሸናፊ ለሆኑ አገሮች አንድ ዓይነት የፖለቲካ አማራጭ ተደርጐ ይቀነቀን ነበር፡፡ በርግጥ በዚያን ወቅት የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው አስተሳሰብ ይቀርብ የነበረው ለሕዝቦች ነፃነት ተቆርቋሪ በመሆን ሳይሆን በአንደኛው የዓለም ጦርነት ተሸናፊ የነበሩት ጀርመንን የመሰሉ አገሮች በሥራቸው ከነበሩ የተለያዩ ሕዝቦች እንዲነጠሉና እንደገና ተጠናክረው የዓለም ስጋት እንዳይሆኑ ለማድረግ ታስቦ ነበር፡፡ በወቅቱ ፕሬዝዳንት ዊልሰን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ ያቀርቡት የነበረው ሐሳብ ብዙ ጥናትና ጥንቃቄ ያልተደረገበት ስለ ነበር ፕሬዝዳንት ዊልሰን ሃሣቡን ባቀረቡበት ወቅት ምን ያህል ለመቁጠር የሚያታክቱ ብሔር-ብሔረሰቦች በአውሮፓ ውስጥ እንደ ነበሩ እንኳን የሚያውቁ ሰው አይደሉም የሚል ትችት አስከትሎባቸው ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪ “የራስን ዕድል በራስ መወሰን” የሚለው መብት በተለየ ታሪካዊ ሁኔታና ይዘት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው ሐሳብ ሆኖ የተከሰተው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያን ወቅት የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው ሐሳብ በማያሻማ ሁኔታ ይቀርብ የነበረው በቅኝ ግዛት ሥር የነበሩ አገሮች ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁበት ታስቦ እንጂ በአንድ ነፃ አገር ሥር ለሚኖሩ ብሔር-ብሔረሰቦች የሚገባ መብት ተደርጐ አልነበረም፡፡

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ በኢትዮጵያ ያለፈበትን ታሪካዊ ሂደት ለማየት ስንሞክር ከ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ በፊት የመገንጠል ጥያቄ የተነሣበት አጋጣሚ ኖሮ አያውቅም፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥያቄው የተነሣው በኤርትራ የዓርነት ታጋዮች ሲሆን በእነሱም በኩል የመገንጠል ጥያቄ ፌደሬሽኑ እንደ ፈረሰ ሳይሆን ዘግይቶ የመጣ ጥያቄ ነበር፡፡ የኤርትራ ዓርነት ንቅናቄ የትጥቅ ትግል ሲጀምር ዓላማው ያለ አግባብ ፈረሰ

የተባለውን ፌደሬሽን እንደገና ለማስመለስ ነበር እንጂ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል አልነበረም። የኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎች ነፃነትን ብቸኛ አማራጭ አድርገው ማየት የጀመሩት በኋላ ላይ ጦርነቱ እየተባባሰና ወታደራዊ እንቅስቃሴአቸው እየተጠናከረ ከመጣ በኋላ ነው። በተለይም የኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎች በሂደት በብዙ የአረብ አገሮች ሁለንተናዊ ድጋፍ እያገኙ መምጣታቸው የኤርትራን ጉዳይ የፌደሬሽን መፍረስ ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የቅኝ ግዛት ጥያቄ እንዲሆን አድርጎታል።

የሆነ ሆኖ ያኔም ሆነ ዛሬ የራስን ዕድል በራስ መወሰን፣ እስከ መገንጠል የሚለው ፅንሰ-ሐሳብ ለኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎች ራስን ከቅኝ ግዛት ነፃ የማውጣት ጥያቄ እንጂ በአንድ አገር ውስጥ ለሚገኙ ብሔር-ብሔረሰቦች ሊሰጥ የሚገባ መብት ተደርጎ ታምኖበት አያውቅም። ሻዕቢያ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ብሔር-ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የሚል መብት ይገባቸዋል ብሎ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የማያምን ድርጅት ሲሆን በዚህም ምክንያት በአሁኑ ወቅት በርካታ ብሔር-ብሔረሰቦች በኤርትራ ውስጥ ያሉ ቢሆንም ይህ መብት እንዲኖራቸው አላደረገም። በትጥቅ ትግሉ ወቅት በሻዕቢያና በህወሃት መካከል የነበረው አንዱ የአቋም ልዩነትም ይኸው እንደነበር ይነገራል።

ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ይደረግ የነበረው ትግልም በዋናነት ሲቀርብ የኖረው የሶማሌ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የሚያነሳው የግዛት የይገባኛል ጥያቄ ሆኖ እንጂ የኦጋዴን ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት አለው ከሚል አስተሳሰብ ጋር ተያይዞ አልነበረም። እንዲያውም የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር እንቅስቃሴ ከመገንጠል መብት ጋር በተያያዘ ጎልቶ መውጣት የቻለው ሶማሊያ ከፈራረሰችና ኢህአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ነው ማለት ይቻላል።

ከኤርትራ የዓርነት ታጋዮች ቀጥሎ “የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል” የሚለውን መርህ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ሳይሆን ለብሔር-ብሔረሰቦች የሚገባ የመብት ጥያቄ አድርጎ በማመን ለመጀመሪያ ጊዜ ትግል የጀመረው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ህወሃት ነው። በ1967 ዓ.ም የተመሠረተው ህወሃት ይህንን የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚል ስታሊናዊ መርህ ብቻ ሳይሆን የኤርትራ ሕዝብ ጥያቄ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ነው የሚል ዕምነት በመያዝም የኤርትራ የነፃነት አጋር ሆኖ ታግሏል። በጠነከረና ወጥ በሆነ ሁኔታም ባይሆን በዚያን ወቅት ይህንን የህወሃት አቋም ይጋራ የነበረው ሌላው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ኢህአፓ ነበር። ኢህአፓዎች ኅብረ-ብሔራዊ ከሆነው አደረጃጀታቸው በመነጨና ከጅምሩም የመበታተን አደጋ ስለገጠማቸው አጀንዳውን ብዙም ያልገፉበት ሲሆን ህወሃት ግን

አጀንዳው የዳር አገር ሕዝቦችን በተሻለ ሁኔታ በሥርዓቱ ላይ የሚያነሳሳና የውጭ ኃይሎችን ድጋፍ የሚያስገኝ ሆኖ ስለ አገኘው እስከ መጨረሻው ሊገፉበት ችሏል፡፡ በወቅቱ የደርግ መንግሥት ኢህአፓንና መኢሶንን የመሳሰሉ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶችን ከፖለቲካ መድረኩ በኃይል ጠራርጐ ማስወገዱም ህወሃትን ለመሰሉ ብሔርተኛ ድርጅቶች ተጠናክሮ መውጣት የተሻለ በር ከፍቷል ማለት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን ህወኃት ትግራይን ከደርግ ቁጥጥር ነፃ አውጥቶ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ከቻለ በኋላ ለትግሉ መነሻ የሆነውን ትግራይን ነፃ የማውጣት ጥያቄ ሊገፋበት አልፈለገም፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን አስተሳሰቡን ከእጁ ማውጣት ባይፈልግም በሂደት ኢህአዴግን በመፍጠር በኢትዮጵያ ደረጃ የፖለቲካ ሚና መጫወትን መርጧል፡፡ ህወኃት ከመገንጠል መብት ጋር የሚጣጣም አደረጃጀት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገሪቱ የበላይነት እንዲኖራቸው ከነበረው ፅኑ ፍላጐት በመነሣትም ኅብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት የነበረውን ኢህዴንን ወደ ብአዴንነት እንዲቀዩር አድርጓል፡፡

በኢህዴን ውስጥ የነበሩ የኦሮሞና የደቡብ ተወላጆችን፣ በምርኮኝነትና በተለያዩ ምክንያቶች የትጥቅ ትግሉን የተቀላቀሉ ግለሰቦችን በመጠቀምም ኦህዴድና ደኢህዴን የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ሆነው እንዲደራጁ ካደረገ በኋላ የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር-ብሔረሰቦች እንዲሆኑ፣ የመገንጠል መብት የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት የማዕዘን ድንጋይ እንዲሆንና አገሪቱም በዋናነት ቋንቋንና ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ የፌደራል አከላለል እንድትደራጅ ለማድረግ በቅቷል፡፡ ኢህአዴግ ከራሱ አባል ድርጅቶች ቁጥጥር ውጭ የሆኑ የአገሪቱ ሌሎች ክልሎችም በሌሎች ተመሳሳይ አደረጃጀት ባላቸው አጋር ድርጅቶች የበላይነት የሚተዳደሩበትን ሁኔታ አመቻችቷል፡፡ ህወሃት በዚህ ሁኔታ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን ልባዊ እምነቱን በሂደት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥታዊና ተቋማዊ ይዘት ያለው አስተሳሰብ እንዲሆን ለማድረግ በቅቷል፡፡

ከህወሃት በተጨማሪ የመገንጠል ጥያቄን አጀንዳው አድርጐ መታገል የጀመረው የብሔር ድርጅት ኦነግ ነው፡፡ ኦነግ ደርግ ሥልጣን ከያዘ ከሁለት ዓመት በኋላ ማለትም በ1968 ዓ.ም ከመመስረቱ በፊት የመገንጠል ጥያቄን አንስቶ የሚያውቅ አንድም የኦሮሞ ድርጅት አልነበረም፡፡ ለኦሮሞ ሕዝብ የነፃነት ትግል መነሻ ተደርጐ የሚታየው በ1955 ዓ.ም የተመሠረተውና በብርጋዴል ጄነራል ታደሰ ብሩ ይመራ የነበረው የሜጫና ቱለማ የራስ-አገዝ ማኅበር ሲሆን፣ የዚህ ማኅበር ዓላማ የኦሮሞ አካባቢዎች ትምህርት፣ ጤናና መገናኛን በመሰሉ የልማትና ማኅበራዊ ጉዳዮች የነበረባቸውን ችግር የመፍታት እንጂ ኦሮሚያን ነፃ አገር የማድረግ

አልነበረም፡፡ እንዲያውም ማህበሩ በወቅቱ የኦሮሞ ተወላጆችን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ታዋቂ የደቡብ ክልል ሰዎችን ጭምር ያቀፈ እንደነበር ይነገራል፡፡

በዚህ ማኅበርና በመንግሥት መካከል ከፍተኛ ፍጥጫ የተፈጠረውም በ1959 ዓ.ም አንዳንድ የማህበሩ አባላት በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የግድያ ሙከራ አሲረዋል ተብለው ከተወነጀሉ በኋላ ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ ፒያሳ ሲኒማ ኢምፓዬር ውስጥ ከደረሰ የቦንብ ፍንዳታ ጋር በተያያዘ የሜጫና ቱለማ ማኀበር መሪዎች በሥርዓቱ በመወንጀላቸው ማህበሩ ሊፈርስ ችሏል፡፡ ከዚያ በኋላ በ1963 ዓ.ም አካባቢ በሜጫና ቱለማ ማኀበር መሪዎች አማካይነት "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዓርነት ግንባር" የሚል ህቡዕ ድርጅት ተቋቁሞ እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች የሚጠቁሙ ቢሆንም ይህ ድርጅት ምንም ዓይነት የጐላ ተግባር ሳያከናውን ከስሟል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት በ1966 ዓ.ም በፈነዳበት ወቅትም በለውጡ ሂደት ውስጥ የጐላ ሚና ሊጫወት የቻለ የኦሮሞ ድርጅት ያልነበረ ሲሆን እንዲያውም ብዙዎቹ የኦሮሞ ምሁራን ሥርዓቱን ይታገሉ የነበሩት መኢሶንና ኢጭአትን በመሰሉ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች ውስጥ ሆነው ነበር፡፡

የኦሮሞን ሕዝብ ስም በመያዝና የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን መርህ በመያዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1968 ዓ.ም ላመቋቋም የበቃው የፖለቲካ ድርጅት ኦነግ ነው፡፡ ኦነግ በወቅቱ በሻዕቢያ እየተረዳ በሐረርጌ፣ በባሌና በወለጋ አካባቢዎች የሽምቅ ውጊያ ማካሄድ የሞከረ ቢሆንም በደርግ ጊዜ የኦሮሞን ሕዝብ እንቅስቃሴ በመምራት ረገድ ያን ያህል የጐላ ሚናና ተፅዕኖ ኖሮት አያውቅም፡፡ ኦነግ ከድርጅታዊ ጥንካሬ አንጻር እስካሁንም ድረስ ደካማና የውስጥ ክፍፍል ያልተለዬው ድርጅት ቢሆንም በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ግን እንደ አንድ ነፃ አውጭ ድርጅት በመታየት ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ የመጣው ከመቼውም ጊዜ በላይ በኢህአዴግ የሥልጣን ዘመን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከእነዚህ የመገንጠልን ጥያቄ ይዘው ከተነሡ የፖለቲካ ድርጅቶች በተጨማሪ የሲዳማ ዓርነት ንቅናቄን የመሳሰሉ አንዳንድ የብሔር ድርጅቶች ከደርግ ጊዜ ጀምሮ ውስን የትግል እንቅስቃሴ በአገሪቱ የነበራቸው ቢሆንም አብዛኛዎቹ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የሚገኙ የብሔር ድርጅቶች ለመመሥረት የበቁት ግን ኢህአዴግ አገሪቱን ከተቆጣጠረ በኋላ በተለይም በሽግግር መንግሥቱ ወቅት ነው፡፡ በአጠቃላይ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው መርህ በኢትዮጵያ ያለፈበት ታሪካዊ ሂደት በዋናነት ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መልኩ ሲሆን ሂደቱ ተጀምሮ ከዛሬ የደረሰበት ጊዜ በአንፃራዊነት አጭር ነው ሊባል ቢችልም በአሁኑ ወቅት አስተሳሰቡ እንደ አንድ የጐላ አስተሳሰብ የራሱ ማኀበራዊ መሠረት በአገሪቱ ያለው መሆኑን ግን አቃሎ ማየት አይቻልም፡፡

በአሁኑ ወቅት የዚህ መርህ ደጋፊዎች ህወኃትና ኦነግ ብቻ ሳይሆኑ በተቃዋሚነት የሚገኙ ፓርቲዎችን ጨምሮ በርካታ የብሔር-ብሔረሰብ ድርጅቶችና እነሱን የሚደግፈው የማይናቅ መጠን ያለው ሕዝብ የሚጋራው መርህ ለመሆን በቅቷል። ስለዚህ አስተሳሰቡን ወደድነውም ጠላነውም፣ አገርን ይጎዳል ወይም ይጠቅማል ብለን ብናምንም ባናምንም ጥያቄውን እንደ ጥያቄ አቃለን ወይም አንቋሽን ልናይበት የማንችልና የማይገባን ወቅት ላይ መሆናችንን አምኖ መቀበል ይገባል። ይህንን አምነን መቀበል ስንችል ነው - በጉዳዩ ላይ የሰከነ ውይይት ማድረግና ከውይይቱ የሚመነጨው መፍትሔም በአንድ በኩል ብሔር-ብሔረሰቦች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ የሚያስችልና በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን አንድነት ለአደጋ በማያጋልጥ ሁኔታ ለመፍታት እንዲያስችለን ማድረግ የምንችለው።

በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአገራችን የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው መርህ ያለፈበትን ታሪካዊ ሂደት በጥቅሉ በዚህ መልክ ካዬን አሁን ደግሞ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በመርሁ ዙሪያ ሊነሡ የሚገባቸውን ጥያቄዎች እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር። ወደዚያ ከመሻገራችን በፊት ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ግልጽነት ፈጥሮ ማለፍ ተገቢ ይሆናል። ይኸውም አንዳንድ ጊዜ "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" የሚለው መርህ "እስከ መገንጠል" ከሚለው ተለይቶ ሲቀርብ ከመገንጠል በመለስ ያለ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ተደርጎ የሚታይበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን "የራስን ዕድል በራስ መወሰን" የሚለው አባባል በርግጥም ከመገንጠል በመለስ የሚገኝና በአንድ ሉዓላዊ አገር ማዕቀፍ ውስጥ ተሁኖ የሚፈጸም ራስን በራስ የማስተዳደር መብት መሆኑ በግልጽ እስካልተቀመጠ ድረስ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው መርህ ዞሮ ዞሮ የመገንጠል መብትን የሚያካትት መሆኑ አይቀርም። ስለዚህ የራስን ዕድል በራስ መወሰን የሚለው መርህ ትርጉሙ በግልጽ እስካልተቀመጠ ድረስ መገንጠልንም የሚያካትትና በአንድ አገር ውስጥ ሆኖ ራስን በራስ ከማስተዳደር መብት ጋር ሰፊ ልዩነት ያለው መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል በሚለው አጠቃላይ መርህ ላይ ሊነሡ የሚገቡ አከራካሪ ጉዳዮችን ለማየት ስንሞክር በቅድሚያ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ፣ የተሰባጠረ ማንነት ላለው አገርም ሆነ ቋንቋን መሠረት ያደረገ ፌደራላዊ አደረጃጀት ላለው አገር የራስን ዕድል በራስ የመወሰንና የመገንጠል መብት የግድ ያስፈልጋል የሚል ዓለም አቀፋዊ ሕግ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው አስተሳሰብ የሌለ መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት በውስጣቸው የተሰበጣጠረ ማንነት ያላቸው በርካታ የዓለማችን አገሮች የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ የሌለ ሲሆን፣ የቋንቋን መስመር የተከተለ የፌደራል አደረጃጀት ሥራ

ላይ የዋለባቸው ስዊዘርላንድንና ቤልጅዬምን የመሰሉ አገሮችም የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚል መብት የሚሰጥ አንቀጽ በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ አላካተቱም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔር-ብሔረሰቦች አገር ስለሆነችም ሆነ በአሁኑ ወቅት በዋናነት ቋንቋን ወይም ብሔረሰባዊ ማንነትን መሠረት ባደረገ የፌደራል አደረጃጀት ስለተዋቀረች የግድ በሕገ-መንግሥቷ ውስጥ የመገነጠል መብትን ልታካትት ይገባታል የሚያስብል የሌላ አገራት ተመክሮም ሆነ ሌላ የተለየ አሳማኝ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡

በአንድ በኩል ከኢትዮጵያ የበለጠ በርካታ ብሔር-ብሔረሰቦች በውስጣቸው ያሉባቸው ናይጀሪያን የመሰሉ አገሮችና ከ1500 በላይ ቋንቋ የሚነገርባቸው ህንድን የመሰሉ አገሮች የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥታቸው ሳያካትቱ በአንድ አገርነት መኖር ከቻሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ መገንጠል እውነተኛና ተገቢ የሕዝብ ጥያቄ ሆኖ ሲመጣ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ባልሆነበትም ሁኔታ በካናዳ እንደሚታየው ሕዝበ ውሳኔ የሚሰጥበት ዕድል እስካለ ድረስ በኢትዮጵያ የመገንጠል መብትን የግድ ሕገ-መንግሥታዊ ማድረግ ያስፈልጋል የሚያስብል የተለየ ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ልምድ በሌሎች አገሮች የሌለ ቢሆንም ከዓለም በተለየ ለእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ከሌላው ዓለም ሁሉ ተለይተን ብንጠቀምበት ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሌሎች በርካታ የዓለም አገራት ውስጣዊ ሁኔታና ታሪካዊ አመጣጥ ጋር የኢትዮጵያ ሁኔታ ሲነጻጸር እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከሌሎች አገሮች ሁኔታ በተሻለ የአንድነት ይዘት ያለው እንጂ የመገንጠል መብትን በተለየ ሁኔታ ሊያስተናግድ ይገባዋል የሚባል አይደለም፡፡

የአፍሪካ አገሮችን ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር ስናነጻጽራቸው ብዙዎቹ እንደ ኢትዮጵያ እነሱም በውስጣቸው ወጥ ማንነት የሌላቸው ሲሆኑ ከቅኝ ግዛት ተላቀው ራሳቸውን የቻሉ ነፃ አገር ለመሆን የበቁት ገና ባለፉት ሃምሣ ዓመታት ውስጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ግን በየወቅቱ እየሰፋችም እየጠበበችም ለሺ ዓመታት በነፃ መንግሥትነት የቆዬች አገር በመሆኗ ቢያንስ በዚህ ልዩ ታሪካዊ ሂደትዋ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች በተሻለ አንድ አገር ሆና ለመቀጠል የሚያስችል የሕዝብ ትስሥርና የታሪክ ሂደት ያላት አገር ነች ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ የተገላቢጦሽ ሆኖ ሁሉም በቅኝ ገዥዎች ሰው ሰራሽ የድንበር ክፍፍል የተፈጠሩት የአፍሪካ አዳዲስ አገሮች በሕገ-መንግሥታቸው ውስጥ የመገንጠልን መብት ባላካተቱበት ሁኔታ ኢትዮጵያ የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥት ያካተተች ብቸኛ አገር ለመሆን በቅታለች፡፡

በሌላ በኩልም ይህ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው መርህ ከሌሎች (ሁለት አገሮች) የተቀዳ እንጂ አገር በቀል አስተሳሰብ እንዳለመሆኑ መጠን በሌሎች አገሮች

ያስገኘው በጎ ውጤት ኖሮ እኛም ልንጠቀምበት ብንወስን ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን በዓለም ደረጃ የመርሁ ታሪካዊ አመጣጥ ምን እንደሚመስል ከላይ ለማየት እንደሞከርነው በዚህ መርህ ጥቅም አግኝቷል ሊባል የሚችል አንድም አገር በዓለም የለም፡፡ መርሁን ቀድመው የተጠቀሙበት ዩጐዝላቪያና ሶቪዬት ኀብረት የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው መፈራረስ መሆኑን እያዩን እኛ ከእነሱ የተዋሥነውን መርህ በተለየ ሁኔታ ይጠቅመናል ብለን ሙጥኝ ማለታችን ዕንቆቅልሽ ይሆን እንደ ሆነ እንጂ ከተጨባጭ ምክንያት ጋር የተያያዘ ምርጫ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥት ውስጥ ማካተት ኢህአዴግ እንደሚለው የግድ አስፈላጊና ጠቃሚ ቢሆን ኖሮ ከእኛ ቀድመው የግልም ሆነ የቡድን መብትን ማክበር የጀመሩትና በውስጣቸው በርካታ ብሔረሰቦችን ያቀፉ ስልጡን አገሮች አካተውት በተገኘ ነበር፡፡

በቀድሞዋ ሶቭዬት ኀብረትም ሆነ በእኛ አገር የመገንጠል መብት ደጋፊ የሆኑት የፖለቲካ ኃይሎች በተመሳሳይ የሚያቀርቡት ምክንያት የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥት ውስጥ መኖሩ የአንድነት ዋስትና ይሆናል የሚል ነው፡፡ ሶቭዬት ኀብረቶች የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥታቸው ማካተታቸው ዘላቂ ዋስትና እንዳልሆናቸው በአገሪቱ መፈራረስ በተግባር የተረጋገጠ ሲሆን በእኛ አገር እስካሁን የከፋ ሁኔታ ያልተከሰተ ቢሆንም የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ መቀመጡ የአንድነት ዋስትና ሊሆን እንዳልቻለ ግን በቂና አሳማኝ ምክንያቶች እየታዩ ነው፡፡ እስካሁን ድረስ የመገንጠል ጥያቄ አንስተው መታገል ከጀመሩ ድርጅቶች ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን ላይ የሚገኘውን ህወኃትን ጨምሮ የመገንጠል ጥያቄውን እርግፍ አድርጐ የተወ አንድም ድርጅት የለም፡፡ እንዲያውም ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ የመገንጠል ጥያቄ የሚያነሱ ድርጅቶች የበለጠ እየተጠናከሩ መጥተዋል፡፡ ኦነግንና ኦብነግን የመሰሉት ድርጅቶች የሚፈለገውን ያህል ወታደራዊ አቅም ፈጥረው ዓላማቸውን እስካሁን ማሳካት ባይችሉም እንደ አሁኑ የሕዝብንም ሆነ የዓለም አቀፉን ኀብረተሰብ ትኩረት መሳብ የቻሉበት ወቅት በአገራችን አልነበረም፡፡ የእነዚህ ድርጅቶች የነፃነት ትግል በዚህ ደረጃ ትኩረት እንዲያገኝ ያደረገው አንድ ምክንያትም በአገሪቱ ሕገ-መንግሥት የተቀመጠው የመገንጠል መብት የትግላቸውን ዓላማ ሕጋዊነት /Legitimacy/ ያላበሰው በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

ከእነዚህ የመገንጠል ጥያቄ ካላቸው ድርጅቶች በተጨማሪም በኢትዮጵያ የብሔር-ብሔረሰቦች መብት አልተከበረም ብለው የሚታገሉት ድርጅቶች በኢህአዴግ ጊዜ ከመቼውም በላይ ቁጥራቸው የበዛ ሆኗል፡፡ እነዚህ የመንግሥት ሥልጣን ተጋሪ ያልሆኑ ድርጅቶች የመገንጠልም ሆነ የብሔር-ብሔረሰቦች መብት ጥያቄአቸውን አጠናክረው ቢቀጥሉበት

የማያስደንቅ ቢሆንም፣ ሌላው ቀርቶ በሁኑ ወቅት የአገሪቱ ቁንጮ መሪ የሆነው ህወሃት የመገንጠል መብት ሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ስለተካተተ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር አብሮ ለመኖር የተሟላ ዋስትና ተሰምቶታል ማለት አይቻልም። ህወሃት በቂ ዋስትና እንዳገኘ የሚሰማው ቢሆን ኖሮ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ዐሥራ ስምንት ዓመት ሙሉ ሲቆይ "ህወሃት /ሕዝባዊ ወያኔ ኀርነት ትግራይ/" የሚለውን የነፃ አውጭነት ስሙን የመቀየር አስፈላጊነትን ሊረሳው ባልፈለገ ነበር።

አቶ መለስ ዜናዊ በአንደኛው ባርኔጣቸው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው አገርን እየመሩ፣ በሁለተኛው ባርኔጣቸው አገራዊ ይዘት ያለውን ኢህአዴግን በሊቀመንበርነት እየመሩ በሚገኙበት በአሁኑ ወቅት፣ በሦስተኛው ባርኔጣቸው ህወሃት የሚባል የነፃ-አውጭ ድርጅት መሪ ሆነው መቆዬትን መምረጣቸው በአጋጣሚ የተዘነጋ ጉዳይ ሳይሆን መንታ ልብ እንዲሆኑ ያስገደዳቸው የፖለቲካ ሁኔታ በአገራችን መኖሩን የሚያሳይ ይመስላል። ስለዚህ በየትኛውም መመዘኛ አብሮ የመኖር ወይም የአንድነት አስተማማኝ ዋስትና ሊሆን የሚችለው የግለሰቦችንና የብሔር-ብሔረሰቦችን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መብት በአግባቡ ማክበር ነው እንጂ የመገንጠል መብትን ሕገ-መንግሥታዊ በማድረግ አይደለም። በተግባር እንደምናየው በአዲሱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት መሠረት የመገንጠል ጥያቄ የሰጠ ሕጋዊ ሽፋን አግኝቶ ተባባሰ እንጂ አልረገበም። በእውነትም የግለሰቦችም ሆነ የብሔር-ብሔረሰቦች የቡድን መብቶች ኢህአዴግ እንደሚለው በአገራችን በአግባቡ ተከብረው ቢሆን ኖሮ በአገራችን የነፃ አውጭ ድርጅቶችን ብቻ ሳይሆን የብሔር የፖለቲካ ድርጅቶችን መኖርም አስፈላጊ ሊያደርግ የሚችል ፖለቲካዊ ሁኔታ ባልነበረ ነበር።

ምክንያቱም የግልና የቡድን የመብት ጥያቄዎች ተገቢ መፍትሄ በአገኙበት ሁኔታ በአገራችን በዋናነት ቋሚና አንገብጋቢ ሆኖ የሚቀጥለው ጥያቄ የልማትና የዕድገት ጥያቄ ስለሚሆን የብሔር ፖለቲካ ድርጅቶች ማኅበራዊ መሠረታቸውን እያጡ፣ በሌሎች አገሮች እንደምናየው በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡ ኅብረ-ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች እየተጠናከሩ መምጣቸው በተግባር በታየ ነበር። በብሔር-ብሔረሰቦች ዙሪያ የሚነሣው ጥያቄ በአግባቡ ባልተመለሰበት ሁኔታ ብቻም ሳይሆን ጥያቄው በተመለሰበት ሁኔታም የመገንጠል ጥያቄ ሕጋዊ መብት ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ መቼም ቢሆን በቀላሉ ሊቆም የሚችል አይሆንም። ኤሊቱ ወይም "ፔቲ ቡርዣ" የሚባለው የኅብረተሰብ ክፍል በአገር ወይም በማዕከላዊ መንግሥት ደረጃ የሥልጣን የበላይነት ባላገኘ ቁጥር የብሔር ጥያቄን ሽፋንና መቀስቀሻ እያደረገ ክልሉን በመገንጠል የሥልጣን ጥማቱን ለማርካት መሞከሩ አይቀርም።

ብዙውን ጊዜ ኢህአዴግ የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በመካተቱ ምክንያት ስለተገኘው ውጤት ሲመጻደቅ የሚሰማው ከደርግ ውድቀት በኋላ ትፈራርሳለች ተብላ የነበረችው ኢትዮጵያ በአንድነት መቀጠል ችላለች በማለት ነው፡፡ እስካሁን ለቁጥር የሚያታክት የመንግሥት ለውጥ ሲካሄድ ህልውናዋን ያላጣችው ኢትዮጵያ ኢህአዴግ ሥልጣን በያዘበት ወቅት በምን አሳማኝ ምክንያት ልትፈራርስ እንደ ነበር ግልጽ ባይሆንም ኢትዮጵያ ኤርትራን ካጣች በኋላ ዐሥራ ስምንት ዓመት አሁን በምናየው መልኩ በአንድነት መቆዬትዋ ግን ሕገ-መንግሥቱ ጥሩ መፍትሄ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው መርህ ፈጣሪዎች የሆኑት እነ ሌኒን የመሩሃቸው የመጨረሻ ውጤት የአገር መፈራረስ እንደሚሆን እነሱ በሕይወት እያሉ አልተረዱትም ነበር፡፡ የፈጠሩት መርህ አገርን በማፈራረስ የጥፋት አስተሳሰብ ሆኖ መደምደሙ የተረጋገጠው እነሱ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ተከታታይ ትውልዶች ካለፉ ከሰባ ዓመታት በኋላ ነበር፡፡ የአሁኖቹ የኢህአዴግ መሪዎች እንደ አንድ ለአገርና ለትውልድ ኃላፊነት የሚሰማው የፖለቲካ ኃይል የቅርቡን ሳይሆን የሩቁን ማሰብ ካልቻሉ በመቃብራቸው ድንጋይ ላይ የሚፃፍላቸው ታሪክ ከእነ ሌኒን ታሪክ የተለየና የተሻለ ሊሆን አይችልም፡፡

የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ መካተቱ የአንድነት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል የሚቀርበው ክርክር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሆነ ተአምር ዋስትና ይሆናል ቢባል እንኳ ዋስትናው ከማንና እንዴት ነው የሚገኘው? የሚል ተጨማሪ ጥያቄ ማሥነሳቱ አይቀርም፡፡ ኢህአዴግ የመገንጠል መብት ዋስትና ይሆናል ብሎ የሚከራከረው እንዲሁ በደፈናው ሳይሆን፣ ብሔር-ብሔረሰቦች መብታቸው ሳይከበር ሲቀር የመገንጠል መብት እንዳላቸው አስቀድመው ሲያውቁ በአንድነት አብረው መኖርን ይመርጣሉ ከሚል መነሻ ነው፡፡ ነገር ግን ይህን ዓይነቱን ክርክር ገባ ብለን ስናየው በውስጡ የተፋለሰ አመለካከትን የያዘና ውሃ የማይቋጥር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክንያቱም አንድ ብሔር ወይም ብሔረሰብ ለመገንጠል የሚፈልገው የእኩልነት መብቱ ሳይከበርለት ሲቀር ከሆነ፣ እነዚያን ከመገንጠል በመለስ ያሉ መብቶቹን ያላከበረለት መንግሥት የመገንጠል መብቱን በሰላም ያከብርለታል ብሎ ማሰብ ዘበት ስለሆነ ነው፡፡ ወይም በሌላ አባባል፣ አንድ በሕገ-መንግሥት የሰፈረን የመገንጠል መብት በቀላሉ አሜን ብሎ የሚቀበል መንግሥት ከመጀመሪያውም ከመገንጠል በመለስ ያሉ መብቶችን በአግባቡ ስለሚያከብር የመገንጠል ጥያቄን ሊያሥነሣ የሚችል ምንም ዓይነት ምክንያት አይኖርም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ዋናው የአንድነት ዋስትና የጭቆናና የጨቋኝ መንግሥት አለመኖር ነው እንጂ የመገንጠል መብትን በሕገ-መንግሥት ማስቀመጥ አይደለም፡፡ ጭቆናና ጨቋኞች በሌሉበት ሁኔታ የመገንጠልን መብት አስፈላጊ የሚያደርገው ምክንያትም አይኖርም፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ፣ ለመሆኑ የመገንጠል መብት ከጭቆና ነፃ የመሆኛ መፍትሄ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚለው ነው፡፡ በአንድ አገር ውስጥ ጨቋኝ መንግሥትና ጭቆና ሲከሰት ጭቆናውን ባለበት ታግለን ለማስወገድ የማንጥር ከሆነና ለሚደርስብን ጭቆና መገንጠልን መፍትሄ አድርገን የምናይ ከሆነ ጨቋኝ ሥርዓቶች ባሉበት አገር ሁሉ የሚካሄደው ትግል ጨቋኞችን ታግሎ የማስወገድ ሳይሆን የመገንጠል ትግል ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም ጭቆና ደረሰብኝ ብሎ የሚያስብ ብሔር-ብሔረሰብ ለመገንጠል ጥያቄ የሚያቀርብ ከሆነ ደግሞ ጭቆና በቀላሉ ሊወገድ በማይችልባቸው አገሮች የመገንጠል ጥያቄ መቆሚያው የት ላይ እንደሚሆን መገመት አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በርካታ ብሔር-ብሔረሰቦች የሚኖሩባቸው አገሮች እንደ አገር ይቀጥላሉ ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡

ምክንያቱም ከአንድ ጨቋኝ ሥርዓት በአንድ ወቅት ትግል መገንጠል ስለተቻለ ለዘለዓለም ከጭቆና ማምለጥ እንደሚቻል ርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ጭቆናንና ጨቋኞችን በተነሱበትና ባሉበት ቦታ ታግሎ ድል መንሳት እስካልተቻለ ድረስ በየሄድንበት ተከትለውን ሊሄዱ እንደማይችሉ አስተማማኝ ዋስትና ማግኘት አይቻልም፡፡ ጭቆናን በመገንጠል ማምለጥ የሚቻል ቢሆን ኖሮ የኤርትራ ሕዝብ ከደርግ ጭቆና አምልጦ በሻዕቢያ ጭቆና ሥር ባልወደቀ ነበር፡፡ ኤርትራ ከሠላሳ ዓመታት ዘግናኝ ጦርነት በኋላ ከኢትዮጵያ ስለተገነጠለች ነፃ አውጭ ነን ባዮችዋ ይመኙ እንደ ነበሩት የሰላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ደሴት መሆን አልቻለችም፡፡ ነገም እንደ ኦነግ ምኞት ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ መገንጠል ብትችል በሌላ ማለቂያ የሌለው የውስጥ ቅራኔ የማትታመስና እንደገና በውስጧ ሌላ የመገንጠል ጥያቄ ለማስተናገድ የማትገደድ አገር እንደማትሆን ከወዲሁ ርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ሌላው ቀርቶ በአሁኑ ወቅት ትግራይ ውስጥ በአድዋ ተወላጆች ላይ የሚነሣውን የመረረ ቅሬታ ስናጤን ህወሃቶችም በአሁኑ ወቅት አንድ እንዲሆኑ ያስገደዳቸው ሌላ ውጫዊ ሁኔታ በመኖሩ እንጂ በውስጣቸው ከሌላው ሕዝብ የተለየ አስተማማኝና ዘላቂ አንድነት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡

በተለይም ዛሬ በነፃነት ትግል ላይ እያለ ያልተቋረጠ የውስጥ ክፍፍል ሰለባ ለመሆን የተገደደው ኦነግ፣ ነገ የነፃዋ ኦሮሚያ መንግሥት ለመሆን በለስ ቢቀናው የመከፋፈል ብቻ ሳይሆን የመበታተን አደጋ ሊያጋጥመው እንደሚችል ከወዲሁ መገመት ከባድ አይሆንም፡፡ የወለጋ፣ የአርሲ፣ የሐረርና የሸዋ ኦሮሞ ኤሊቶች ከነፃነት በኋላ ሰምና ፈትል ሆነው ተዋደው ይኖራሉ ብሎ መገመት ቀላል እንደማይሆን የሚያሳዩ በቂ ምልክቶች በኦነግ ብቻ ሳይሆን በኦህዴድም ውስጥ ሲታዩ ቆይተዋል፡፡ አካባቢያዊ ስሜት በኦሮሚያ ውስጥ የማይናቅ የቅራኔ

ምንጭ ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚቻል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በኦሮሚያ ውስጥ ወደፊት ሃይማኖትም ለሥልጣን መቆናጠጫነት አዲስ የቅራኔ ምንጭ ሆኖ ሊከሰት እንደሚችል መገመት የማይቻል አይሆንም፡፡ ስለዚህ የሌላ ብሔር ሰው ከሚጨቁነንና ከሚገዛን ይልቅ የራሳችን ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ሰው ቢጨቁነንና ቢገዛን ይሻላል ካልተባለ በስተቀር በመገንጠል ከጭቆናና ከግጭት ሸሽቶ ማምለጥ ይቻላል ብሎ ማሰብ ከአሳማኝ ምክንያት የሚነሣ አስተሳሰብ አይደለም፡፡ ምሥራቅ ቲሞር ከኢንዶኔዥያ፣ ፓኪስታን ከህንድ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ፣ ቦስንያ ከዩጐዝላቪያ፣ የቀድሞ የሶቪዬት ኅብረት ግዛቶች ከሩሲያ ወዘተ… ስለተገነጠሉ የሰላምና መረጋጋት ባለቤት ሲሆኑ አልታየም፡፡ መፍትሄው ኤሊቱ ወይም ፔቲ ቡርዧው ኅብረተሰብ በአንድ አገር በሰላማዊ የምርጫ ውድድር ተፎካክሮ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚበቃበትን አመች ሁኔታ መፍጠር ነው እንጂ የመገንጠል ጥያቄን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በማድረግ በብሔርም ሆነ በሃይማኖት ሰበብ የሚነሡ ጥያቄዎችን ማክሰም አይቻልም፡፡

ሌላው በአንድ አገር የመገንጠል መብትን መኖር የበለጠ አስቸጋሪ የሚያደርገው ጥያቄው በርግጠኛነት ከጭቆና መኖር ጋር ላይያያዝ የሚችልበት ዕድል መኖሩ ነው፡፡ ከግፍና ከጭቆና የሚመነጭ የመገንጠል ጥያቄ መኖሩ የማይካድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የመገንጠል ጥያቄ በአንድ በኩል ከፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች የአገር መንግሥትና መሪ ከመሆን ፍላጐት፣ በሌላ በኩል ደግሞ እኛ የተሻለ የሀብት መጠን ስላለን ብቻችንን ልንጠቀምበት ይገባል ከሚል ስግብግብና ጠባብ ፍላጐትም ሊነሣ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብም በጣፋጭ ፕሮፓጋንዳ ተቀባብቶ ሲቀርብ የፖለቲካ መሪዎችን ብቻ ሳይሆን ሕዝብን እንደ ሕዝብ ሊያማልል የማይችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለዚህ በአንድ አገር ሕገ-መንግሥት ውስጥ የሚቀመጥ የመገንጠል መብት ከትክክለኛ ጭቆና የሚመነጨውን ብቻ ሳይሆን ከግልና ከቡድን ጠባብ ፍላጐት፣ አንዳንዴም ከትምክህትና የበላይነት ስሜት የሚመነጨውን የመገንጠል ጥያቄም ለማስተናገድ የሚገደድበት አደጋ ይኖራል፡፡

የወቅቱ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንዱና መሠረታዊ ድክመቱ በዚህ ዙሪያ ያለ ነው፡፡ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 ብሔር-ብሔረሰቦች ያለምንም ገደብ የመገንጠል መብት ያላቸው መሆኑን - "ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡" በማለት ከማስቀመጡ በስተቀር የብሔር-ብሔረሰቦች መብት በተከበረበት ሁኔታ የመገንጠል ጥያቄ ማንሣት እንደማይቻል ግን አይከለክልም፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አንድ የፖለቲካ ቡድን ከጭቆና መኖር ሳይሆን ከጠባብ የቡድን ፍላጐት ተነሥቶ የመገንጠል ጥያቄ

ቢያነሳ፣ ጭቆና ተወግዷልና የመገንጠል ጥያቄ ልታነሳ አትችልም ብሎ ለመከልከል የሚያስችል አንቀጽ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የለም፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ የቱንም ያህል የብሔር-ብሔረሰቦች መብት ቢከበር አንዳንድ ድርጅቶች መቼም ቢሆን የመገንጠል ጥያቄአቸውን እስከ መጨረሻው ድረስ ሊተውት እንደማይፈልጉ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ስለዚህ ብሔር-ብሔረሰቦች የመገንጠል መብታቸው በሕገ-መንግሥት ከሰፈረ ከመገንጠል ይልቅ አብረው መኖርን ይመርጣሉ የሚለው አስተሳሰብ ባዶ ምኞት ከመሆን አልፎ በተጨባጭ ምክንያት የተደገፈ አይደለም፡፡ የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ እስከሰፈረ ድረስ የጭቆና መኖር ብቻ ሳይሆን የቡድንና የግል ጠባብ ፍላጐትም የመገንጠል አደጋን ይዞ ሊመጣ ይችላል፡፡

ከሁሉም በላይ የመገንጠል መብት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ውስጥ መኖሩን ዘግናኝ የሚያደርገው የአንዳንድ የአገሪቱ ክልሎች መገንጠል በኤርትራ መገንጠል እንደታየው እዚያው ላይ የሚያቆም ሳይሆን ውጤቱ ኢትዮጵያን እንደ አገር የሚያፈርስ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡ መቼም የአንድ ክልል ሕዝብ ከአንድ አገር ለመገንጠል የሚያስችል የቱንም ያህል አሳማኝና በቂ ምክንያት ቢኖረው የዚያ ክልል መገንጠል አጠቃላይ አገሪቱን የሚያፈርስ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ግን እንዲህ ዓይነቱን መብት "መብት" ነው ብሎ ለማክበር መሞከር በየትኛውም የምድር ላይ ሕግ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የመገንጠል መብት መኖሩ ትክክልና ጠቃሚ ነው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች የአንድ ክልል መገንጠል የአጠቃላይ የአገር መፍረስና አለመፍረስ ጥያቄ መሆኑን ለምን ሊገነዘቡት እንደማይችሉ ግልጽ አይደለም፡፡


ይህ አባባል ምን ማለት እንደሆነ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ በአሁኑ ወቅት በዋናነት የመገንጠል ጥያቄ የሚነሣበትን የኦሮሚያን ሁኔታ ማየት ብቻ በቂ ይሆናል፡፡ በሌሎች የጠረፍ አካባቢ ክልሎች የሚነሣውን የመገንጠል ጥያቄ ለጊዜው ወደ ጐን ትተነው በየትኛውም የሚያሳምንም ሆነ የማያሳምን ምክንያት ኦሮሚያ ብቻ ከኢትዮጵያ መገንጠል ብትችል ከዚያ በኋላ አንድ ወጥ የሆነ መልክአ ምድር ያላት "ኢትዮጵያ" የምትባል አገር ልትኖር አትችልም፡፡ ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል ከመቶ ሃያ ዓመታት በላይ በሁሉም ሕዝብ ተሳትፎ ስትገነባ የኖረችው የአገሪቱ ርእሰ ከተማ አዲስ አበባ ብቻ ሳትሆን የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ የጋምቤላና የሐረሪ ክልል ወዲያውኑ የኢትዮጵያ አካል መሆናቸው ያከትማል፡፡ ስለዚህ ከኦሮሚያ መገንጠል በኋላ አንድ ወጥ መልክአ ምድር ኖሮት የሚቀጥል በተጨባጭ ኢትዮጵያ የሚባል አገር ሊኖር የማይችል ሲሆን ለሁለት ተከፍሎ የሚቀረው የኢትዮጵያ ክፍል በካርታ ቁጥር 2 ላይ በሙሉ የጥቁር ቅብ የተገለፀውን ይመስላል ማለት ነው፡፡



ካርታ ቁጥር 1 -የወቅቱ የኢትዮጵያ ካርታ



ካርታ ቁጥር 2 -ኦሮሚያ ክልል ቢገነጠል ለሁለት ተከፍሎ የሚቀረው የኢትዮጵያ ካርታ



በተመሳሳይ ሁኔታእንደ ኦሮሚያ የኦጋዴን ክልል ከኢትዮጵያ ቢገነጠል ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል አሁን ካለው ከአንድ ሦስተኛ ያነሰ መጠን ይኖረዋል ማለት ነው። ወይም ደግሞ

ከኢትዮጵያ ዘጠኝ ክልሎች መካከል ሁለት ክልሎች ብቻ ማለትም ኦሮሚያና አፋር ክልሎች ቢገነጠሉ ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል ከሦስት ተበትኖ እንደ አንድ አገር መኖር በማይችል ደረጃ በሚከተለው ካርታ ቁጥር 3 የሚታየው ዓይነት ቅርፅ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ካርታ ቁጥር 3 -ኦሮሚያና አፋር ክልል ቢገነጠሉ ከሦስት ተከፍሎ የሚቀረው የኢትዮጵያ ካርታ

ከዚህ የምንረዳው የመገንጠል መብት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ውስጥ የመኖሩ ጉዳይ በተዘዋዋሪ ሳይሆን በቀጥታ ለኢትዮጵያ እንደ አገር የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ከአገሪቱ ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ አንዱ ክልል ኦሮሚያ ብቻ ቢገነጠል በካርታ ቁጥር 2 ላይ እንደሚታየው የኢትዮጵያ የሰሜንና የምሥራቁ ክፍል ከአገሪቱ የደቡብ ክፍል ሙሉ በሙሉ አንድ አገር ሆኖ ሊቀጥል በማይችልበት ሁኔታ ይለያያል፡፡ በሌላው የኢትዮጵያ ክፍልና በደቡቡ ክፍል መካከል የሚገኘው ቦታ ባህር ሳይሆን ኦሮሚያ የሚባል አገር ስለሚሆን የደቡብ ብሔር-ብሔረሰቦች፣ የጋምቤላና የሐረሪ ክልል ቱወደደም ተጠላም እነሱ ፈለጉም አልፈለጉም ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር አንድ አገር ሆነው የሚቀጥሉበት ዕድል ስለማይኖር እነሱም ይገነጠላሉ ማለት ነው፡፡ ኦሮሚያ የሚባለውን አገር ሳይነካ ለሁለት የተከፈሉትን የኢትዮጵያ ክፍሎች በየትኛውም አቅጣጫ ሊያገናኝ የሚችል ምንም ዓይነት የምድር ኮሪዶር ስለ ሌለ የኦሮሚያ መገንጠል በውጤቱ እንደ ኤርትራ መገንጠል የአንድ ክልል መገንጠልን ብቻ ሳይሆን አገርን የማፍረስ ውጤት የሚያስከትል ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአንድ ክልል መገንጠል ምክንያት የሚመጣው ውጤት እንደዚህ አገርን የማፍረስ ሲሆን የመገንጠል መብቱ ተግባራዊ ሊሆን የማይችልበትን አማራጭ የአገራችን ሕገ-መንግሥት አላስቀመጠም፡፡ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ከአገር ህልውና ጋር የተያያዘ የመከራከሪያ ሐሳብ ተቀባይነት የሚያገኝበት ምንም ዓይነት ቀዳዳ እንዳይኖር ተፈርቶ ይመስላል፣ የመገንጠል መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የሚጠበቅ መብት ስለመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ላይ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

የበለጠ አስገራሚው ነገር የመገንጠል መብት በሕገ-መንግሥቱ ላይ ከመቀመጡም በላይ የመገንጠል ውሳኔ የሚሰጥበት ሂደት በጣም ቀላል መሆኑ ነው፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ራሱ ሕገ-መንግሥቱን ለማሻሻል ከሚያስፈልገው ሂደት በላይ የመገንጠል ውሳኔን መስጠት እጅግ ቀላል ነው፡፡ አንድ ክልል ከአገሪቱ መገንጠል ከፈለገ የክልሉ ሕግ አውጭ ምክር ቤት በ2/3ኛ ድምፅ፣ የክልሉ ሕዝብ በሕዝበ-ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ብቻ (50+1) ከደገፈው

መገንጠሉን ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በመገንጠሉ ውሳኔ ላይ ከራሱ መገንጠል ከሚፈልገው ክልል ምክር ቤትና ሕዝብ በስተቀር ሌላ ውሳኔ የመስጠቱን ሂደት የመጋራት መብት ያለው አካል የለም፡፡

ነገር ግን በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት የሚገኙትን (የመገንጠል መብትን ጨምሮ) አንቀጾች ማሻሻል ቢያስፈልግ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ከፌደሬሽን ምክር ቤት በተጨማሪ እያንዳንዱ የክልል ምክር ቤት በድምፅ ብልጫ የማሻሻያ ሃሣቡን ሊያጸድቀው ይገባል፡፡ ይህም ማለት በሕገ-መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት ውስጥ የሚገኘን አንድ አንቀጽ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤትና ከዘጠኙ የአገሪቱ ክልሎች ውስጥ ስምንቱ ክልሎች እንዲሻሻል ቢወስኑና ይህንን ውሳኔ ከአገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ከ0.3% በታች የሆነ ሕዝብ የሚገኝበት የሐረሪ ክልል ሳይደግፈው ቢቀር ውድቅ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሰዎች የጻፉትንና ያጸደቁትን ሕገ-መንግሥት ማሻሻል በዚህ መጠን ከባድ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፣ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የአገርን ህልውና የሚመለከተውና ከምንም ነገር በላይ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው የመገንጠል ጉዳይ ግን መገንጠል በሚፈልገው የአንድ ክልል ሕዝብ አብላጫ ድምፅ ብቻ በቀላሉ መወሰን እንዲችል ተደርጓል፡፡

ለምሳሌ የወቅቱ የኦሮሚያ ምክር ቤት ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ መገንጠል አለባት ብሎ በ2/3ኛ ድምፅ ቢወስንና በዚህ ውሳኔ መሠረት የኦሮሞ ሕዝብ ሕዝበ-ውሳኔ አካሂዶ የመገንጠሉን ጥያቄ በአብላጫ ድምፅ (50+1) ቢደግፈው ኦሮሚያ ከኢትዮጵያ ትገነጠላለች ማለት ነው፡፡ ይህ የኦሮሚያ የመገንጠል ጉዳይ በውጤቱ ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር ከሁለት ከፍሎ የሚያፈርሳት ቢሆንም አገራዊ ህልውናውን የሚያጣው ቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ከኦሮሚያ መገንጠል በኋላ ህልውና ሊኖራቸው የማይችለው የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔውን በሆነ መንገድ የመጋራትም ሆነ የመቃወም ምንም ዓይነት ሕገ-መንግሥታዊ መብት የላቸውም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግን ከላይ የተጠቀሰውን የሕገ-መንግሥቱን ክፍል የማሻሻል ውሳኔን የአንድ ክልል ምክር ቤት ብቻውን ውድቅ የማድረግ መብት ተሰጥቶታል፡፡

በአዲሱ ሕገ-መንግሥት መሠረት የአገሪቱ ባለቤት ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ ሳይሆን ብሔር-ብሔረሰቦች መሆናቸውን ለማሳየት ከዚህ በላይ ማስረጃ ሊቀርብ አይችልም፡፡ ወደፊት በአገራችን በሚካሄደው አንድ የምርጫ ወቅት የመገንጠል መብታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚፈልጉ ኃይሎች በለስ ቀንቷቸው የአንዱን ክልል ምክር ቤት በበላይነት ቢቆጣጠሩ፣ በአንድ ታሪካዊ ሂደትና አጋጣሚ ከኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል አንዳቸው የመገንጠል መብታችንን

ተግባራዊ ልናደርገው እንፈልጋለን ወደሚል አቋም ቢመጡና ይህንንም ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ቢፈጥሩ የኢትዮጵያ ዕጣ-ፈንታ ምን ያህል በቀላሉና በድንገት ወደ አደጋ ሊሸጋገር እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም። ዛሬ በሥልጣን ላይ የሚገኘው የኢህአዴግ መንግሥት በአንድ በኩል አሁን በአገሪቱ የሚገኙ ሁሉንም ክልሎች በበላይነት እየመራ የሚገኝ ድርጅት በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት የመገንጠል ፍላጐት ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች ሕገ-መንግሥታዊ የመገንጠል መብታቸውን ወደ ተግባር እንዳይለውጡት የማድረግ ፍላጐት ብቻ ሳይሆን አቅምም ያለው ድርጅት በመሆኑ የአገሪቱ ህልውና ለጊዜው ከአደጋ የራቀ መስሎ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን ይህ የወቅቱ የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ በድንገተኛ ሁኔታ ወይም በማይቀር የለውጥ ሂደት ወደፊት ሲለወጥ የኢትዮጵያ ዕጣ-ፈንታ እንደ ሶቭዬት ኅብረት ከሰባ ዓመታት በኋላ ሳይሆን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ለአደጋ አይጋለጥም ብሎ በርግጠኛነት መናገር አይቻልም። የዚህንም ሁኔታ አይቀሬነት ከ1997 ምርጫ ማግስት በአገሪቱ ፖለቲካ የኃይል አሠላለፍ ለውጥ ሊከሰት ይችላል ተብሎ ስጋት ሲፈጠር የአንዳንድ ክልል አመራሮች በከረረ ሁኔታ ሲያራምዱት ከነበረው አቋም ማስተዋል ተችሏል። ሌላው ይቅርና በአሁኑ ወቅት እነ አቶ መለስ እንደሚሉት ወደፊት በኢህአዴግ ውስጥ በሚያካሂዱት የአመራር አባላት የመተካካት ሂደት ከአምስት ዓመት በኋላ የወቅቱ የኢህአዴግ አመራር ሙሉ በሙሉ በአዲስ አመራር የሚተካ ከሆነ አዲሱ አመራር የአገሪቱን አንድነት በሚመለከት ሊከሰቱ የሚችሉ ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ አደጋዎችን የወቅቱ አመራር ሊቋቋመው በሚችል መጠን ሊያስቀር ይችላል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው። የኢህአዴግ የሥልጣን መተካካት ርምጃ ከመፈጸሙ በፊት የአገሪቱን አንድነት በዘላቂነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ የአደረጃጀት ለውጦችና ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያዎች በአገሪቱ ካልተደረጉ በስተቀር የሥልጣን መተካካት ርምጃው በኢህአዴግ ውስጥ በሚያስከትለው የኃይል አሰላለፍ ለውጥ ምክንያት የአገሪቱንም ህልውና አደጋ ውስጥ ሊከት የሚችል ውጤት እንዳያስከትል ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ስጋት ሊያድርብን ይገባል። ኢህአዴግ በውስጡ ካለበት ከፍተኛ የህልውና ስጋት በመነጨ ላለፉት አስራ ስምንት ዓመታት የራሱን ድርጅታዊ ህልውና ከአገሪቱ አጠቃላይ ህልውና ጋር ሆን ብሎ ለማስተሳሰር የተጠቀመባቸው ሕጐችና ተቋማት በራሱ በኢህአዴግ ከመሻሻላቸው በፊት በድርጅቱ ውስጥ የሚካሄድ የሥልጣን መተካካት ከአገሪቱ አጠቃላይ ደህንነት አንፃር በጐ ለውጥ ብቻም ሳይሆን አደጋም ይዞ ሊመጣ እንደሚችል መጤን አለበት።

በሌሎች አገሮች የታሪክ ሂደት ተደጋግሞ እንደታየው ዘርንና ሃይማኖትን መሠረት ባደረገ ፖለቲካ ውስጥ አንድ ጊዜ የተዘፈቀ አገርና ሕዝብ በቀላሉ ከህልውና አደጋ ሊላቀቅ አይችልም። ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት በአገራችን የብሔረሰቦችም ሆነ የሃይማኖት እኩልነት

ተከብሯል ከተባለ በኋላ ወደ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት መግባት ያልቻልነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ በሰዎች መካከል ሃይማኖትንና ዘርን በተመለከተ የሚፈጠር ፉክክር በስሜት እንጂ በምክንያት የሚገዛ ስለማይሆን እንኳን እንደ ዛሬው ብዙ ጉድለቶች ባሉበት ሁኔታና መብቱ ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታም ጥያቄው መቅረቡ ላይቆም ይችላል፡፡ ተጨቋኝ ነበረ የሚባለው ሕዝብ ባገኘው መብት መርካት አልችል ብሎ "ገና ብዙ ይቀረኛል" እያለ ተጨማሪ ሲጠይቅ፣ ጨቋኝ ነበር የተባለው አካል ደግሞ እየመጣ ያለው ለውጥ አዲስ የህልውና ስጋት እየፈጠረበት "አሁንስ በዛ" እያለ የለውጥ ሂደቱ እንዲገታ ሲጠይቅ እንዲህ ዓይነቱ ውዝግብና አለመግባባት የት ላይ ሊቆም ይችላል? የሚለው ጥያቄ በቀላሉ ሊመለስ የሚችል አይደለም፡፡

የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የመብት መከበር ጉዳይ ከቡድን መብት ይልቅ በዋናነት መመሥረት ያለበት በግለሰብ መብት ላይ ነው ብሎ የሚያምነው ያለምክንያት ሳይሆን በቡድን መልክ የሚነሡ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ከየት ተነስተው የት ሊደርሱ እንደሚችሉ አስቀድመው ውጤቱን በአግባቡ መለካትም ሆነ ማወቅ አስቸጋሪ (ምንአልባትም የማይቻል) መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ ኢህአዴግ ከግለሰብ መብት ይልቅ የቡድን መብትን ማስቀደሙ ከዛሬ ለመድረስ የጠቀመው መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ኢህአዴግ ለረዥም ጊዜ ሥልጣን ላይ የመቀጠል ፍላጐትና የብሔር-ብሔረሰቦችን ያልተገደበ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ ከአደጋ በፀዳ ሁኔታ ለረዥም ጊዜ ተጣጥሞ ይቀጥላል ብሎ በርግጠኝነት መገመት አይቻልም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአንድ ወቅት አሉት እንደሚባለው በኢህአዴግ ውስጥ በቅለው ያደጉ ኦህዴድን የመሰሉ ድርጅቶች ሲፍቋቸው ኦነግ እየሆኑ ከተገኙ፣ ነገ ከነገ ወዲያ በኢህአዴግ ውስጥም ሆነ በአገሪቱ የሚኖረው የፖለቲካ ኃይል አሰላለፍ ሲለወጥ አገሪቱን ምን ዓይነት አደጋ ሊያጋጥማት እንደሚችል ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን ኢህአዴግ በድንገት በኖ እንዲጠፋልን ድንጋይ ስንፈነቅልና ስንጸልይ የምንውል ተቃዋሚዎችና አንዳንድ የኀብረተሰብ ክፍሎች ጭምር በጥልቀት ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በተለይም ኢህአዴግን የጐዳን መስሎን ከኦነግ ጋር የምንተባበርና እንደ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ዓይነቱን እንደ ቀላል ነገር "የኦሮሞ ሕዝብ የመገንጠል መብቱን በሕዝበ-ውሣኔ ሊገልፅ ይገባዋል" የሚል አቋም የሚያራምዱ ሰዎችን እንደ ጥሩ ተቃዋሚ ኃይል በማየት ከእነሱ ጋር ለመተባበር የምንሞክር ሰዎች እንዲህ ዓይነቶቹ ድርጅቶችና ግለሰቦች በሆነ የታሪክ አጋጣሚ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የወሳኝነት ድርሻ ቢኖራቸው ሊከተል የሚችለውን አደጋ ሁለት ሦስት ጊዜ ደጋግመን ብናስብበት የተሻለ ይሆናል፡፡

ከላይ ለማቅረብ ከተሞከረው ትንታኔ አኳያ የመገንጠል መብትን መቃወም እንደ ተራ ነገር "የነፍጠኞች" ወይም የሌሎችን መብት ማክበር የማይፈልጉ ሰዎች አስተሳሰብ እየተደረገ መንቋሸሽ የለበትም። ከሁሉም ነገር በላይ የአገሪቱ አንድነት ጉዳይ ለማንኛውም ዜጋ አሳሳቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫ በመምጣት በአዲስ አበባና በዙሪያው በሚካሄድ ግንባታና ልማት ላይ ሀብት ንብረቱን እያፈሰሰ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ወደፊት ልጆቼ የሚወርሱት አገር አለኝ ብሎ ስለሚያስብ እንጂ የአገሩ ጉዳይ እንደዚህ በቋፍ ላይ ያለ መሆኑን በአግባቡ ቢረዳ ኖሮ ከራሱ የትውልድ ቀየ ርቆ ጉጆ ለመቀለስ ሊደፍር ባልቻለ ነበር። የአንድ ወይም የሁለት ክልሎች ከኢትዮጵያ መገንጠል አጠቃላይ የአገር ህልውናን የሚያፈርስ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ ውጤቱን የመብት ጉዳይ ነው ብሎ ሕዝቡ አሜን ብሎ ይቀበለዋል ብሎ ማሰብ የሚቻል አይሆንም። የመገንጠል ጉዳይ ለአንዱ ወገን የአገር ነፃነት፣ ለሌላው ወገን ደግሞ የአገር ህልውና መጥፋት በሆነበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱን የሌሎችን ህልውና የማያከብር ብቻ ሳይሆን የሚያጠፋን መብት ሕዝብ በጸጋ ይቀበለዋል ወይም ሊቀበለው ይገባል ብሎ ማመን አሳማኝና የሚያዛልቅ ሊሆን አይችልም።

የቱንም ያህል ጉዳዩ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ በተግባር ተፈፃሚ ካደረገ በኋላ ያፈራረሰውን አገር ሊገዛ የሚችል ፓርቲም ሆነ መንግሥት ሊኖር ስለማይችል ውሳኔውን በቀላሉ ለመቀበል የሚችል አምባገነናዊ ብቻ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ መንግሥትም በአገራችን ይኖራል ብሎ መገመት የዋህነት ይሆናል። አይደለም ቀርቶ አገርን የሚያፈርስ የመገንጠል ጥያቄ ማንሳትና - ሲዳማ ክልል የመሆን፣ ወላይታ ደግሞ ዞን የመሆን ሰላማዊና ሕጋዊ ጥያቄ ከማንም በላይ የእንዲህ ዓይነቱ መብት ጠበቃ ነኝ ለሚለው ለኢህአዴግ ከጥቂት ዓመታት በፊት አቅርበው ምን ዓይነት በጭካኔ የተሞላ መልስ እንዳገኙ በሚገባ ታይቷል። አገር መገንጠል የሚመኙ የፖለቲካ ኃይሎች ይህንን እውነታ በውል ቢገነዘቡትና የመብት ጥያቄዎቻቸው በአንድነት ማዕቀፍ ውስጥ በአግባቡ እንዲፈቱ ቢታገሉ ውጤቱ በትክክል የሚጨበጥና ሁሉንም ወገን ተጠቃሚና አሸናፊ ለማድረግ የሚበቃ ይሆናል። አለበለዚያ የራስ ነፃነትን በሌሎች የህልውና እጦት ለማምጣት የሚደረግ ሙከራ ኢትዮጵያን እንደ መካከለኛው ምሥራቅ ወደማያቋርጥ የትርምስ አዙሪት ያስገባት እንደሆነ እንጂ ከቶውንም የሰላምና የዴሞክራሲ አገር ሊያደርጋት አይችልም።

በተለይም በአገራችን ትልቅ ቁጥር ያለውንና የአገሪቱ ምሰሶ የሆነውን የኦሮሞን ሕዝብ እገነጥላለሁ የሚለው ኦነግ አጀንዳውን ከመገንጠል ጥያቄ ይልቅ ወደ ማዕከላዊ የሥልጣን ጥያቄ ቢቀይረው ለራሱ ትግል ውጤታማነትም ሆነ በአጠቃላይ ለአገሪቱ ህልውና ደኅንነት ጠቃሚ

ርምጃ ይሆናል። በኢትዮጵያ ብዙኃንና የአገሪቱ ምሰሶ ለሆነው የኦሮሞ ሕዝብ በተቃራኒው የአናሳ ሕዝብ ጥያቄ የትግል አጀንዳ ሆኖ እንዲቀርብለት መደረጉ ለታላቅነቱ የማይመጥነው ጥያቄ ነው። ምክንያቱም በየትኛውም ዓለም ብዙኃን ሕዝብ (majority) ሆኖ የአናሳ ጥያቄ አቅራቢ መሆን (minority thinker) የተለመደና የሚገባ አይደለም። አይደለም ቀርቶ ብዙኀን የሆነ አካልና አናሳም ሆኖ የአናሳ አስተሳሰብን ከመያዝ ይልቅ የብዙኀን አስተሳሰብን መያዝ የበለጠ ለውጤት ሊያበቃ ይችላል። ለምሳሌ ህወሃት መጀመሪያ ወደ ትግል ይዞት የገባውን የአናሳ አስተሳሰብ በሂደት ወደ ብዙኀን አስተሳሰብ በመቀየር ትግሉን ትግራይን ከመገንጠል ይልቅ በኢትዮጵያ ፖለቲካ የበላይነት ወደ ማግኘት ባይቀይረው ኖሮ አሁን ለደረሰበት ውጤት መብቃት ይቅርና የትግራይን ነፃነት በዘላቂነት ማሳካት ባልቻለ ነበር።

በአሜሪካን ፖለቲካ የባራክ ኦባማ ውጤታማነት የሚያረጋግጥልንም ይኸንኑ እውነታ ነው። ከባራክ ኦባማ በፊት በአሜሪካ የጥቁሮች የነፃነት ትግል ከፍተኛ ተሳትፎ የነበራቸውና የላቀ የሥራ ልምድና የትምህርት ደረጃ የነበራቸው በርካታ አፍሪካ-አሜሪካዊያን ምኞታቸው ስኬታማ ሳይሆን የቀረው ከራሳቸው ዙሪያ የራቀና የላቀ የብዙኃን አስተሳሰብ መያዝ ባለመቻላቸው ነው ማለት ይቻላል። ኦባማ ከሌሎቹ በተለየ ለውጤት መብቃት የቻሉት በዋናነት በሌላ ምክንያት ሳይሆን እንደ ሌሎቹ አናሳ ተፈጥረን ነገር ግን እንደ ብዙኃን ማሰብ በመቻላቸው ነው ማለት ይቻላል። ኦባማ በተከተሉት የብዙኃን አስተሳሰብን የመያዝ ስልት የአሜሪካ ነጮች የኦባማን ጥቁርነት እንዲረሱ ባይገደዱ ኖሮ ኦባማ የመጀመሪያው የአሜሪካን ጥቁር ፕሬዝዳንት ሆነው ለታሪክ ሰሪነት ባልበቁ ነበር። ስለዚህ ኦነግ የያዘው ትግል ውጤታማ እንዲሆን ከፈለገ ከአናሳ አስተሳሰብ ራሱን አላቆ ወደ ብዙኃን አስተሳሰብ መሸጋገር ይኖርበታል። ግዙፍና ታላቅ ለሆነው የኦሮሞ ሕዝብ የሚመጥነው አስተሳሰብም እንዲህ ዓይነቱ የብዙኃንነት አስተሳሰብ ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት የመገነጠል ጥያቄ ተቃዋሚ የሆን የኀብረተሰብ ክፍሎችም መገንጠልን በደፈናው ስለተቃወምነው ወይም አገራችንን ያፈርሳታል ብለን ስለሰጋን ብቻ ጉዳዩ መፍትሔ ያገኛል ብለን ማሰብ የዋህነት ነው። ከሁሉም በፊት ከማንም በላይ የአገር አንድነት ጠበቃ ነን እያልን የምንመጻደቅ የፖለቲካ ኃይሎችና የኀብረተሰብ ክፍሎች እያራመድነው በምንገኝ አንድ ጽንፍ ላይ የቆመ የተሳሳተ አመለካከት የአገሪቱን አንድነት የበለጠ ወደ አደጋ እየገፋነው መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። የአንድነት ጠበቃ ነን የምንል ኃይሎች - የማንነት ጥያቄን የሚያነሱ የብሔር-ብሔረሰብ ድርጅቶችን አገር አፍራሽ ኃይሎች አድርገን እያንቋሸሽን፣ በአገሪቱ ውስጥ ስላሉ ልዩነቶች መስማትን እየጠላን፣ ለማንነትና ለመገንጠል

ጥያቄ መነሻ የሆኑ ግፍና በደሎች በዚች አገር የአገሪቱ ገዥዎች ሰፊጽሙ መኖራቸውን ሽምጥጥ አድርገን እየካድን፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያን አንድነት በማንኛውም ሁኔታ ሊደፈር የማይችል ፖለቲካዊ ሳይሆን መለኮታዊ ጉዳይ እንደሆነ አድርገን እያየን የኢትዮጵያ የአንድነት ጥያቄ በቀላሉ ይፈታል ብለን ማሰብ ከታሪክ መማር አለመቻላችንን የሚያረጋግጥ ግብዝነት ይሆናል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ግትር አቋማችን ቢያንስ ኤርትራን ካጣንበት የስህተት መንገድ ምንም ያህል ያልተማርን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ ለአገሪቱ አንድነት ተቆርቋሪዎች የመሆናችንን ያህል በአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳይ እኩል ተጠቃሚ አልሆንም ብለው ጥያቄ ለሚያነሱ የኅብረተሰብ ክፍሎችም በዚያው መጠን ተቆርቋሪና የመፍትሔው አካል መሆን ይጠበቅብናል፡፡ ብሔር-ብሔረሰቦች ቋንቋቸውን የመጠቀም፣ ባህላቸውን የመንከባከብና የማሳደግ፣ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር፣ በአገሪቱ ልማት እኩል ተጠቃሚና በአገሪቱ ማዕከላዊ ፖለቲካ እኩል ውክልና የማግኘት የማይሸራረፍ መብት ያላቸው መሆኑን ከአንገት ሳይሆን ከአንጀት አምነን መቀበል ይኖርብናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የብሔር-ብሔሰቦች መብት በመርህና በሕገ-መንግሥት ደረጃ አምኖ ከመቀበልም በላይ ሁሉም የአገሪቱ ሕዝቦች በተግባር እኩል የልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ከተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች ተወላጅ የሆኑ ዜጎች በማዕከላዊ መንግሥት የሚኖራቸው የፖለቲካ ሥልጣን የኮታ ማሳያ ሳይሆን እውነተኛ የውሳኔ ሰጭነት ሚና ያለው ኃላፊነት እንዲሆን ማድረግ የአገር አንድነት አደጋ ከምንጩ ለማድረቅ የሚያስችል መፍትሄ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አድልዎና ቅራኔ በሰፈነበት አገር ብሔርተኛነት /Ultra nationalism/ የበለጠ እየተጠናከረ እንጂ እየረገበ ሊመጣ አይችልም፡፡

በብሔር ራሳቸውን ያደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች ለኢትዮጵያ አንድነት ትኩረት እንዲሰጡ ስንፈልግም የአንድነት ጥቅም ከስሜት ባለፈ ምን ዓይነት ተጨባጭ የጋራ ጥቅምን እንደሚያስገኝ በማሳየት እንጂ ብሔረሰብዓዊ ማንነታቸውን እንዲንቁት ወይም እንዲያፍሩበት ለማድረግ በመሞከር መሆን የለበትም፡፡ ማንም ሰው በአንድነት ሊገኝ የሚችለውን የጋራ ጥቅም በውል እስከተረዳ ድረስ በብሔረሰባዊ ማንነቱ እየኮራ በዚያው መጠን በኢትዮጵያዊነቱም የሚኮራ ሰው መሆን የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ ፖለቲከኞች ለራሳቸው የሥልጣን ፍላጎት ሲሉ የሚፈጥሩት የተጋነነ ጫና መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰዎች ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ ጥያቄ ለማንሳት የሚገደዱት የራሳቸው ማንነት መገለጫ አድርገው የሚያዩት ባህል፣ ቋንቋ ወይም ኃይማኖት በሌሎች የሚናናቅበትና እኩልነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ ሲፈጠር መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ የአንድ አገር ዜጎች መብት በእኩልነት መከበር ያለበት መሆኑ ላይ

ጥያቄ እስካልተነሳ ድረስ የእኩልነቱ መገለጫ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ከማንነት ጉዳይም ጋር የተያያዘ የሥነ-ልቦናዊ እኩልነት ጥያቄም ጭምር መሆኑ መጤን አለበት፡፡ በርግጥ ሥነ-ልቦናዊ ጉዳዮች በቀላሉ ሊዳሰሱና ሊለኩ የማይችሉ (subjective) ስሜቶች በመሆናቸው እነሱን ከማክበር በተጨማሪ በዜጎች መካከል የሚኖረው እኩልነቱ በኢኮኖሚና በፖለቲካ ጥቅም በተጨባጭ ተመንዝሮ መታየት ይኖርበታል፡፡

አገሪቱ የዐማራና የትግሬ ብቻ ሳይሆን ብቁ የሆነ የኦሮሞ ተወላጅ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ብቁ የሆነ የሶማሌ ተወላጅ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ብቁ የሆነ የጉራጌ ተወላጅ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ብቁ የሆነ የወላይታ ተወላጅ ኢታማዦር ሹም፣ ብቁ የሆነ የሐረሪ ተወላጅ የደኅንነት ሹም፣ ብቁ የሆነ የሲዳማ ተወላጅ የፖሊስ ኮሚሽነር ወዘተ በመሆን ትርጉም ያለው ሥልጣን /power position/ የሚይዙባት አገር እንድትሆን ሁላችንም ከልብ መታገል አለብን፡፡ እንዲህ ዓይነት ሃቀኛ /Genuine/ የኢኮኖሚና የሥልጣን ተጠቃሚነት በአገራችን መፍጠር የማንችል ከሆነ ግን፣ ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአንድ ወቅት አሉት እንደተባለው ከጐናችን የቆመ የሚመስለን አንድ የኦህዴድ አባል ሲፋቅ ኦነግ ሆኖ መገኘቱና የመገንጠል ስሜት የበለጠ ሥር እየሰደደ መሄዱ የማይቀር ነው፡፡

ቁልፍ የሚባሉትን የፖለቲካ ሥልጣኖች /power positions/ በራሳችን ዙሪያ ጨምድደን ይዘን ኦህዴድን ስንፍቀው ኦነግ ሆነ እያልን ብናማርር፣ ምሬታችን እኛው ራሳችን የፈጠርነውና የነባራዊው ሃቅ መገለጫ እንጂ ዕድለኛ ካለመሆን የሚመነጭ ምሬት ሊሆን አይችልም፡፡ የአንድነት ጠበቃ ነን ብለን የምንመጻደቅ በግራም- በቀኝም የምንገኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ከዚህ በላይ ሊገለፅ በተሞከረው መልኩ የአገር አንድነት ጥያቄአችንን በተገቢው የኃላፊነት ስሜት ካራመድነው ከሌሎች የተሻለ የሞራል የበላይነት የማንይዝበትና የመገንጠል ጥያቄን ከምንጩ ማድረቅ የማንችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የመገንጠል ጥያቄ ለምን የሕገ-መንግሥታችን አካል ሆነ በማለት የምናቀርበው ተቃውሞ አንድነትን መለኮታዊ ጉዳይ አድርጐ ከማየት ባለፈ ከተገቢ የህልውና ስጋት የሚመነጭ ሆኖ እንዲታይና ትግላችንም ለውጤት እንዲበቃ ማድረግ የሚቻለው ቢያንስ አንዳንድ ጊዜ ራሳችንን ከኛ አመለካከት በተፃራሪ በቆሙ ሰዎች ጫማ ውስጥ አስገብተን የአገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለማየት ስንሞክር ነው፡፡

ሌላው ቀርቶ ራሳችንን ያዝናናንና ሰዎችንም ያሳቅን እየመሰለን በየአካባቢያችን በተለያዩ ብሔር-ብሔረሰቦች እንደቀላል ነገር ቀልዶችን እየፈጠርን የምናወራ ዜጐች ከዚህ ዓይነት ድርጊታችን ሙሉ በሙሉ መቆጠብ አለብን፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ በየመዝናኛና በገበያ ቦታው

የምናወራቸው የተለመዱ /stereotype/ ቀልዶች እኛ ከምንገምተው በላይ በሌሎች ሰዎች አእምሮ ውስጥ ጉጅ ስሜት የሚፈጥሩና አገራዊ ፖለቲካውን በመበከል ረገድም የማይናቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡ ችግሩ የራሱ ታሪካዊ መነሻ ያለው ቢሆንም መጨረሻ ላይ በዓለም ወደር ላልተገኘለት የኮሶቮ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ መነሻ ምክንያት የሆነው አንድ በአንድ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ የተላለፈ ተራ ቀልድ ነው፡፡ ስለዚህ የአንድነት ተሟጓች መሆን በቅድሚያ መጀመር ያለበት ለሌሎች ማንነትና አመለካከት ተገቢውን አክብሮት ከመስጠት መሆን ይገባዋል፡፡

### *4.4 በሥልጣን ቁጥጥርና ክፍፍል ዙሪያ የሚነሡ ጥያቄዎች*

በአንድ ፌደራላዊ አደረጃጀትን በሚከተል አገር ውስጥ የሚኖር ሕገ-መንግሥት ሊያራምዳቸው ከሚገባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በሦስቱ የመንግሥት ምሰሶዎች መካከልና በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል የሚኖረውን የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር /check and balance/ በግልጽና በአግባቡ መወሰን ነው፡፡ ይህም የሚደረገው በአንድ በኩል ሥልጣን በአንደኛው የመንግሥት አካል እጅ ያለ አግባብ ተጠራቅሞ የሥልጣን መባለግ እንዳይከሰት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመንግሥት የተለያዩ ተቋማት መካከል የሚኖር ተገቢ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር የመንግሥትን የሥራ ብቃት ያሳድጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ የሥልጣን ቁጥጥርና ክፍፍል ሲባል ምን ማለት እንደሆነ በሚቀጥለው ምሳሌ በቀላሉ ማየት እንችላለን፡፡

በአሜሪካ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ የአገሪቱ ፕሬዝዳንት፣ ኮንግረሱና ሴኔቱ በሕዝብ ቀጥተኛ ምርጫ የሚመረጡና የሚቋቋሙ አካላት ሲሆኑ እነዚህ አካላት በመካከላቸው ግልጽ የሆነ የሥልጣን ክፍፍልና የቁጥጥር ሥርዓት አላቸው፡፡ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያለው የአገሪቱ ኮንግረስ ሕግ የማስፈጸም ሥልጣን ያለውን የአገሪቱን ፕሬዝዳንት የመክሰስ ሥልጣን ያለው ሲሆን ፕሬዝዳንቱ ደግሞ በኮንግረሱ ውሣኔዎች ላይ ድምፅን በድምፅ የመሻር ሥልጣን (veto power) አለው፡፡ ኮንግረሱ በተራው የፕሬዝዳንቱን ድምፅን በድምፅ የመሻር ውሳኔ እንደገና ውድቅ የማድረግ (over-ride) ሥልጣን አለው፡፡ ሌላኛው ሕግ አውጭ አካል ሴኔቱ የኮንግረሱን ውሳኔዎች በምክር ቤቱ ውስጥ በጊዜ የማይገደብ ክርክር በመክፈት ማዘግየት ወይም ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ማድረግ የሚችልበት (Filibuster) የአሠራር ዘዴ አለው፡፡ በዚህ የአሠራር ዘዴ መሠረት አንድ የሴኔት አባል ሲፈልግ ተረት እያወራ ወይም ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌለው መጽሐፍ እያነበበ ከኮንግረስ የመጣው ውሳኔ በሴኔቱ በቀላሉ እንዳያልፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ሴኔቱ ፕሬዝዳንቱ ለዳኝነት የሚያቀርባቸውን እጩ ዳኞች የመደገፍና ያለመደገፍ ሥልጣን ያለው ሲሆን፣ የሕግ ተርጓሚው ወይም የዳኝነት አካሉ ደግሞ በተራው በሕግ-አውጭ አካላቱና በፕሬዝዳንቱ ውሳኔዎች ላይ ሕጋዊ ቁጥጥር የሚያደርግበት ሥልጣን አለው፡፡ በዚህ መልኩ ሌሎቹ የአገሪቱ የመንግሥት የሥራ መዋቅሮች ሳይቀሩ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠሩበት አሠራር አላቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሠራርም አንዱ የመንግሥት አካል ብቻውን በዘፈቀደ ውሳኔዎችን መስጠት የሚችልበትን ዕድል በመንፈግ ጉዳዮች በምክክርና በሰጥቶ መቀበል ድርድር አገርን በሚጠቅሙበት ሁኔታ እንዲወሰኑ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የአሜሪካ ፌደራላዊ ሥርዓት አንዳንዴ የሥልጣን ክፍፍል ሥርዓት ተብሎ ይጠራል፡፡

የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥርን በተመለከተ በዓለም ላይ ወጥ የሆነ አሠራር ባይኖርም በዴሞክራሲያዊ አገሮች ውስጥ በመንግሥት የሥልጣን አካላት መካከል የሥልጣን ክፍፍልና የቁጥጥር አሠራር መኖሩ የተለመደ ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ዴሞክራሲያዊ አገር ሕገ-መንግሥት ውስጥ ከሁሉም ነገር በላይ ዋና መመዘኛ ተደርጐ የሚታየው ቁም ነገር የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር መርህ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የወቅቱ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ከሌሎች አገሮች ሕገ-መንግሥቶች ጋር ሲነጻጸር የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥርን በተመለከተ በመርህ ደረጃ የተጋነነ ችግር አለበት ሊባል ባይችልም አንዳንድ ጥያቄ ሊነሣባቸው የሚገቡ መሠረታዊ ድክመቶች አሉበት፡፡

የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥርን በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ ዙሪያ የሚታየው አንዱና ዋናው ድክመት አገሪቱ በምትከተለው ፓርላሜንታዊ ሥርዓት በአገሪቱ ትልቁ የሥልጣን አካል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆኖ እያለ ነገር ግን የሥራ አስፈጻሚ አካሉ፣ ከሥራ አስፈጻሚ አካሉም ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአግባብ በላይ የሆነ ሥልጣን እንዲኖረው ያደረገ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር በሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ በቀጥታ የሚመረጥ ሳይሆን እንደ ማንኛውም የፓርላማ አባል በአንድ ወረዳ ሕዝብ ብቻ የሚመረጥ ሆኖ እያለ በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠው ሥልጣን ግን በሌሎች አገሮች በመላው ሕዝብ ከሚመረጥ አንድ የአገር ፕሬዝዳንት ሥልጣን ጋር የሚመጣጠን ነው ማለት ይቻላል፡፡ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የአገሪቱ ርእሰ መስተዳድር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ፣ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥና የአገሪቱ የውጭ ፖሊሲ የበላይ አስፈጻሚ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን፣ የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶችን፣ ዋናው ኦዲተርን፣ የምርጫ ቦርድ አባላትንና የተለያዩ የሲቪል ሹመቶችን በራሱ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡

ከዚህ የምንረዳው የብዙኃን ፓርቲ ባህል ገና ሥር ባልሰደደበት በእኛ አገር ከአንድ ከፍተኛ አብላጫ ድምፅ ካለው ገዥ ፓርቲ የሚመረጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ሹመት በመስጠት ሥልጣኑ ብቻ ሁሉንም የመንግሥት መዋቅሮች በበላይነት የመቆጣጠር ሰፊ ዕድል ያለው መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ይህ በአንድ የምርጫ ወረዳ ሕዝብ የተመረጠ ጠቅላይ ሚኒስትር በመላው የአገሪቱ ሕዝብ የተመረጠውን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመበተን የሚያስችለው ሥልጣን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 60 ቁጥር 1 ተሰጥቶታል፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው የሚኒስትሮች ምክር ቤትም በሕገ- መንግሥቱ ምዕራፍ 3 ክፍል 1 ሥር ከተዘረዘሩት የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች መካከል ከአንቀጽ 18 እና 25 በስተቀር ሐሳብን በነፃ የማራመድ መብትን ጨምሮ ሌሎቹን የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ባስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የማገድ ሥልጣን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 93 ተሰጥቶታል፡፡

ይህንን ያህል ከፍተኛ ሥልጣን የተሰጠው የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ በሥልጣኑ ላይ ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግበት የሚያስችል ግልጽ አሠራር በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ አልሰፈረም፡፡ የአገሪቱ ከፍተኛው የሥልጣን አካል ነው የተባለው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጐዳ ከፍተኛ ጥፋት ፈፅመው ቢያገኛቸው ሥልጣናቸውን እንዲለቁ ወይም የትምምን ድምፅ /Vote of confidence/ እንዲሰጥባቸው የማድረግና እንዲከሰሱ የመወሰን ሥልጣን /power of impeachment/ በግልጽ አልተሰጠውም፡፡

ከሁሉም በላይ የሚደንቀው፣ ከፍተኛው የአገሪቱ ሥልጣን በአገሪቱ ፕሬዝዳንት ሳይሆን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ሥር መሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ በግልጽ ሰፍሮ እያለ፣ ሕገ-መንግሥቱ በተደጋጋሚ (ከሁለት ጊዜ በላይ) ያለመመረጥ ገደብ እንዲጣልበት ያደረገው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ሳይሆን በፕሬዝዳንቱ ላይ ነው፡፡ በአገር መሪዎች እንደገና የመመረጥ ጉዳይ ላይ ገደብ መጣል አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው የአገር መሪዎች በያዙት ከፍተኛ ሥልጣን ለረዥም ጊዜ ያለ አግባባ በመጠቀም አገርንና ሕዝብን እንዳይጐዱ ታስቦ ቢሆንም የአገራችን ሕገ-መንግሥት በጣም በሚያስገርም ሁኔታ ትርጉም ያለው ሥልጣን በእጁ በሌለው በፕሬዘደንቱ ላይ ገደብ እንዲጣል ሲያደርግ፣ ከፍተኛና እውነተኛ ሥልጣን በእጁ በሚገኘው ጠቅላይ ሚኒስትር ላይ ግን ምንም ዓይነት ገደብ አላስቀመጠም፡፡

እንዲህ ዓይነት አሠራር ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው በሌሎች አገሮችም ያለ ቢሆንም እንደኛ የፓርቲዎች ዴሞክራሲያዊ ባህልና አገራዊ የዴሞክራሲ ተቋሚት ባልጠነከሩበት አገር በአገሪቱ ፖለቲካዊ ሕይወት የአገር መሪዎች ሚናና ተፅዕኖ ቀላል እንዳልሆነ እየታወቀ፣ በአገሪቱ ርእሰ

መስተዳድር የሥልጣን ዘመን ላይ ገደብ እንዲጣልበት ስላልተደረገ የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ ፊት ምን ያህል በሥልጣን እንደሚቆዩ ባይታወቅም እስካሁን ድረስ ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በላይ ለዐሥራ ስምንት ዓመታት አገሪቱን በበላይነት ለመምራት ችለዋል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደፊትም ቢሆን ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታው ሂደት መጠናከር አንድ ዋና እንቅፋት ሆኖ የሚቀጥለው ይኸው በመሪዎች የሥልጣን ዘመን ላይ ገደብ አለመጣሉ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱን አስተሳሰብ ብዙውን ጊዜ "በጠቅላይ ሚኒስተር የሥልጣን ዘመን ላይ ገደብ አለመጣል በኛ የተጀመረ ሳይሆን እነ እንግሊዝም በመሰሉ አገሮችም የተለመደ ስለሆነ ለምን እንቃወመዋለን?" በማለት ለማጣጣል ሲሞክር ይታያል፡፡ ለገር ግን ኢትዮጵያ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በማጣት ረገድ ከሌሎች አገሮች የባሰ ጉዳት የደረሰባት አገር በመሆኗ ምክንያት በዚህ ረገድ ከራሷ ችግር ጋር የሚጣጣም የተለየ አሠራር ብትከተል ጠቃሚና አስፈላጊ ስለሚሆን በዚህ ረገድ ኢህአዴግ የሚያቀርበው መከራከሪያ ከግልና ከድርጅት ጥቅም አኳያ ካልሆነ በስተቀር ከአገር ጥቅም አኳያ አሳማኝ አይደለም፡፡

በሥልጣን ላይ የሚገኙት መሪዎች የቱንም ያህል አገርን የመምራት ዕውቀትና ብቃት ቢኖራቸው፣ የቱንም ያህል ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ፖሊሲዎችን ቢያራምዱ በሥልጣን ዘመናቸው ላይ ግልጽ የሆነ ገደብ በማስቀመጥ የሚያራምዷቸው ፖሊሲዎች የራስን ሥልጣን ከማስጠበቅ ያለፈ አገራዊ ትርጉም ያላቸው መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ እስካልቻሉ ድረስ በሕዝብ ዘንድ ልባዊ ተቀባይነት /Legitimacy/ ሊያገኙ አይችሉም፡፡ በተለይም አሁን በአገራችን ከሚታዩው የኀብረተሰቡ ፖለቲካዊ ሥነ-ልቦና አንጻር በሥልጣን ዘመኑ ላይ ገደብ ሳያስቀምጥ አገርን የሚጠቅም ፖሊሲ ከሚያራምድ መሪ ይልቅ በሥልጣን ዘመኑ ላይ ግልጽ ገደብ አስቀምጦ አገርን የማይጠቅም ፖሊሲ የሚያራምድ የአገር መሪ በብዙ ርቀት እንደ አገር ወዳድና እውነተኛ መሪ በሕዝብ የመወደድና የመታመን ዕድል ሊኖረው ይችላል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ኢህአዴግ በርካታ የልማት ሥራዎችን እየሠራ ባለበት ሁኔታ በርካታ ሰዎች በአገሪቱ ለሚታዩት በጎ ሥራዎች ዕውቅና መስጠትም ሆነ ማመስገን ሲተናነቃቸው የሚታየው ያለ ምክንያት ሳይሆን ኢህአዴግ ከምንም ነገር በላይ ለፖለቲካ ሥልጣኑ ቀጣይነትና የበላይነት ቀናዒ የሆነ ድርጅት መሆኑን በርግጠኛነት የሚገነዘቡ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የሰዎች አስተሳሰብ ጤናማና ትክክለኛ ነው ሊባል ባይችልም፣ ኢህአዴግ በዚች አገር ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ለማምጣት ቁርጠኛ አቋም መውሰዱን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ሕዝቡን ማሳመን እስካልቻለ ድረስ በዚች አገር ላይ ወርቅን ማዝነብ የሚያስችል ሥራ ቢሠራ እንኳ የሚገባውን ያህል ሊመሰገንና ሊታመን የማይችልበት ሁኔታ

ቋሚ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም። ይህ ደግሞ የእኛ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የአብዛኛው የዓለም ሕዝብ ባህሪ ነው። በብዙ ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች ማንኛውም ጥሩ የሚባል የአገር መሪ ወይም ፓርቲ ከሁለት ጊዜ በላይ በድጋሚ የመመረጥ ዕድሉ የጠበበ ሆኖ የሚታየው ያለ ምክንያት ሳይሆን በየትኛውም ሁኔታ የሰው ልጅ የለውጥ ፍላጎት ተፈጥሯዊና ገደብ የለሽ በመሆኑ ነው።

የሥልጣን ዘመኑን የገደበ፣ ነገር ግን ጠቃሚ ፖሊሲ የሌለው የአገር መሪ ይኑረን ብለን ልንመኝ ባንችልም ለወደፊቱ የኢትዮጵያ መሪዎች የራስን የሥልጣን ዘመን ገድቦ ከማሳየት በላይ የሕዝብ ልባዊ ተቀባይነትንና ፍቅርን የሚያስገኝ ሌላ ርምጃ አለ ማለት አይቻልም። ግማሽ ዕድሜአቸውን በእሥር ቤት ያሳለፉት ታላቁ የፖለቲካ ሰው ኔልሰን ማንዴላ ለደቡብ አፍሪካ ምን በጎ ነገር አመጡለት? ብለን ብንጠይቅ ጥቂት ጥቁሮች የፖለቲካ ሥልጣን ከመያዛቸው ባለፈ የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኑሮ ከመቀዬር አንጻር ትርጉም ያለው ለውጥ አምጥተዋል ማለት አይቻልም። ማንዴላ በሥልጣን ላይ በቆዩበት በእነዚያ ጥቂት ዓመታትም ለዘመናት ሲጠራቀም የኖረ የአገር ችግርን ሊፈቱ ይችሉ ነበር ተብሎም አይጠበቅም።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ማንዴላን በዓለም ላይ ባለ ታሪክ፣ ተወዳጅና ተደናቂ ያደረጋቸው ምስጢር ሌላ ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ከሥልጣን በመውረድ ዕድሜ ልክ የደከሙለት ትግል ለግል የሥልጣን ፍላጐታቸው ሳይሆን ለአገራቸው መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ በመቻላቸው ነው። ከዚህ በተቃራኒ ማንዴላ ነፃ ያወጣሁትን አገር የፖለቲካ ሥልጣን ለሌላ ሰው አሳልፌ አልሰጥም ብለው በሥልጣን ላይ ያለ ገደብ ቢቆዩና የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግር መፍታት ችለው ቢሆን ኖሮ እንኳን፣ ማንዴላ ለዛሬው ዝናቸውና ክብራቸው ባልበቁ ነበር። የዚምባቡዌ የነፃነት አባት የሚባሉትን ሮበርት ሙጋቤን በሌላ የታሪክ ገጽታ ላይ እንዲቀመጡ ያደረጋቸው ደግሞ ከዚምባቡዌ ሕዝብ መራብና መታረዝ በላይ ሥልጣን ላይ ተጣብቀው ለመሞት በመምረጣቸው ነው ማለት ይቻላል። የኤርትራ የነፃነት ትግል ግንባር ቀደም መሪ የሆኑት ፕሬዝዳንት ኢሣያስም ከነፃ አውጪነት ታሪካቸው በተቃራኒ ዛሬ ከምንም ነገር በላይ ለራሳቸው የሥልጣን የበላይነት ቀናኢ የሆኑ ሰው ሆነው በመገኘታቸው ትናንት የነፃነት አባት አድርጐ ባከበራቸው የኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ዛሬ ምን ያህል የመረረ ተቃውሞ እየገጠማቸው እንደሆነ በገሃድ እየታየ ነው።

ስለዚህ በወደፊቱ የአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ልዩ ሐውልት ሊቆምለት የሚገባው የአገር መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በራሱ የሥልጣን ዘመን ላይ ገደብ በመጣልና በፈቃዱ ከሥልጣን በመውረድ አዲስ የፖለቲካ ባህል መትከል የሚችል መሪ ይሆናል። ምክንያቱም ከሁሉም በላይ

አገሪቱ ከነባራዊው አስቸጋሪ የፖለቲካ አዙሪት ወጥታ ወደ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ብልፅግና ጉዳና በአስተማማኝ ሁኔታ ልታመራ የምትችለው በእውነተኛና በሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር መኖር ነው፡፡ የዕድሜ ልክ የፖለቲካ የሥልጣን የበላይነት እንዲኖረን የሚያስችለንን ሴራ ውስጥ ውስጡን እየሸረብን በየቴሌቪዥኑና ሬዲዮ ጣቢያው የቱንም ያህል ስለ ነፃ ምርጫ፣ ዴሞክራሲና የልማት ዕድገት ስናወራ ብንውል በሕዝቡ ዘንድ ይህም ተግባራችን የፖለቲካ ሥልጣን የማራዘሚያ ስልት ተደርጐ ከመታየት ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ እንኳንስ በአፋችን የምናዎራው ነገርና በተግባርም የምናሳዩው የልማት ሥራ የፖለቲካ ሥልጣን የማራዘሚያ ስልት ተደርጐ ከመታየት አይድንም፡፡

ከሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ጋር በተያያዘ ሌላው ሊጤን የሚገባው ጉዳይ በማዕከላዊ መንግሥትና በክልሎች መካከል ያለው ግንኙነት ነው፡፡ በዚህ ረገድ አገሪቱ በብሔር- ብሔረሰቦች ባለቤትነት እንድትያዝ ከመደረጓ ጋር በተያያዘ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ አንዳንድ ክልሎች የተሰጧቸው መብቶች በፌደሬሽን ውስጥ ከሚታይ ግንኙነት በላይ በኮንፌደሬሽን ውስጥ ወደሚታይ ዓይነት ግንኙነቶች ያዘነበሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከላይ በተለያዩ ርእሶች ለማየት እንደሞከርነው ከፌደራል አከላለሉና የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ከሚለው መርህ ጋር በተያያዘ ክልሎች ያሉአቸው መብቶች በአንድ ነባር ሉዓላዊነት ያለው አገር ውስጥ ከሚኖር የፌደራል አደረጃጀት በላይ የተለያዩ አገሮች ወደ ፈጠሩት የኮንፈደሬሽን ግንኙነት የሚያዘነብል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊነሡ የሚገባቸውን ጉዳዮች በበቂ ሁኔታ ቀደም ባሉት ክፍሎች ስለአዩናቸው አሁን በዚህ ክፍል መድገሙ አስፈላጊ አይሆንምና ቀሪዎቹን ድክመቶች ብቻ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር፡፡

የፌደራል አደረጃጀት ከሚገለፅባቸው ባህርያት መካከል ያልተማከለ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አስተዳደር መኖር ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን የወቅቱ ሕገ-መንግሥት በፖለቲካ አስተዳደር ረገድ የሚያሳዩውን ቸርነት ያህል በኢኮኖሚ አስተዳደር ረገድ ንፉግ ሆኖ ይታያል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የፌደራል መንግሥትን ሥልጣንና ተግባር በሚዘረዝረው አንቀጽ 51 ቁጥር 5 ___፣ "የመሬት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የታሪክ ቅርሶች አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ ሕግ ያወጣል" የሚል ሲሆን፣ የክልል ሥልጣንና ተግባርን በሚዘረዝረው አንቀጽ 52 ሥር የሚገኘው ቁጥር 2(መ) ደግሞ___፣ "የፌደራል መንግሥቱ በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል" ይላል፡፡

ከእነዚህ ሁለት የሕገ-መንግሥቱ አንቀጾች እንደምንረዳው የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤቶች ክልሎች ናቸው ወይስ ፌደራል መንግሥት? የሚለው ጥያቄ ዕንቆቅልሽ መሆኑ

እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ክልሎች መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን የማስተዳደር እንጂ ሕግ የማውጣት መብት የላቸውም፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ኢኮኖሚን ከመሬትና ከተፈጥሮ ሀብት ለይቶ ማየት ስለማይቻል ክልሎች በአካባቢያቸው በሚገኝ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ላይ ሕግ የማውጣት መብት ከሌላቸው በአገሪቱ የኢኮኖሚ አሐዳዊነት ቀርቷል ማለት የሚቻል አይሆንም፡፡

ለምሳሌ አንድ የክልል መንግሥት የአካባቢውን ልዩ ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በመሬት ወይም በሌላ የተፈጥሮ ሀብት ላይ አንድ ሕግ ላውጣ ቢል፣ ወይም ደግሞ ፌደራል መንግሥቱ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያወጣው ሕግ የማይስማማው ሆኖ ቢያገኘው ላለመቀበል የሚያስችለው መብት የለውም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በሕገ-መንግሥቱ ለክልሎች በግልጽ የተሰጠው መብት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን የማስተዳደር ብቻ ነው፡፡ ሁሉንም የተፈጥሮ ሀብት በሚመለከት ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለክልሎች መስጠት ተገቢ ነው ባይባልም ቢያንስ ግን መሬትን ጨምሮ በተወሰኑ አካባቢያዊ ባህሪ ባላቸው የተፈጥሮ ሃብቶች ክልሎች የባለቤትነትና ሕግ የማውጣት መብት ከሌላቸው የቱንም ያህል ፖለቲካዊ መብት ቢኖራቸው የተሟላ መብት ባለቤት ሆነዋል ማለት አይቻልም፡፡

ከፋይናንስ ገቢና ወጭ አንጻርም ሲታይ ክልሎች በአሁኑ ወቅት የኢኮኖሚ ነፃነት አላቸው የሚያስብል ሁኔታ አይታይም፡፡ የፖለቲካ ሥልጣንን ከራሳቸው ቆንጥረው ወይም ከፍለው ለፌደራል መንግሥቱ ሰጥተዋል የሚባሉት ክልሎች ከራሳቸው ተርፎ ለፌደራል መንግሥቱ ፈሰስ የሚያደርጉት ገንዘብ የለም፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግን ፌደራል መንግሥቱ በዓመት ከሚመድበው አጠቃላይ አገራዊ በጀት ውስጥ 1/3ኛ አካባቢ የሚሆነው ለክልሎች የሚሰጥ ድጐማ ነው፡፡ ለምሳሌ ከ2002 ዓ.ም የፌደራል መንግሥቱ 64.5 ቢሊዮን ብር ዓመታዊ በጀት ውስጥ 20.9 ቢሊዮን ብሩ ለክልሎች ድጐማ የተመደበ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በኢኮኖሚ ረገድ ክልሎች ምን ያህል የፌደራል መንግሥቱ ጥገኛ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ወደፊት የአገሪቱ የኢኮኖሚ መሠረት እየሰፋና የክልሎች አቅም እየጐለበተ ሲመጣ እየተለወጠ ሊመጣ ቢችልም፣ በአሁኑ ወቅት በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል ያለው የገቢ ርእስ ክፍፍል ሚዛኑን ያልጠበቀ መሆኑንም ያሳያል፡፡ ምክንያቱም የውጭ ንግድን ጨምሮ በፒ ኤል ሲ /PLC/ ደረጃ የተቋቋሙ የንግድ ዓይነቶች በሙሉ በፌደራል መንግሥቱ ሥር በመሆናቸው ከፍተኛውን የአገሪቱን ገቢ እየሰበሰበ የሚገኘው ፌደራል መንግሥቱ ነው፡፡ አንድ ክልል የኢኮኖሚ ነፃነት በሌለው ሁኔታ የፖለቲካ ነፃነት ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ስለሚያስቸግር ሕገ-መንግሥቱ በዚህ ረገድ ሊሻሻል የሚገባው ድክመት አለበት ማለት ይቻላል፡፡

ይህ ሲባል ግን በሕገ-መንግሥቱ መሠረት ክልሎች ከኢኮኖሚ የተሻለ የፖለቲካ ነፃነት አላቸው ለማለት ነው እንጂ፣ በአሁኑ ወቅት በሕገ-መንግሥቱ የሰፈረው የክልሎች የፖለቲካ መብት በተግባር እየዋለ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ ከላይ ቀደም ሲል ያዬነው በመንግሥት ምሰሶዎች መካከልም ሆነ በፌደራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል የሚታየው የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ከእነ ችግሮቹና ጉድለቶቹም ጭምር ቢሆን በተግባር የሚውልበት ሁኔታ በአገራችን ቢኖር ኖሮ የፌደራል አደረጃጀት ጀማሪ አገር እንደመሆናችን መጠን ብዙም ባልከፋ ነበር፡፡ ነገር ግን አገሪቱ ጥብቅ ድርጅታዊ ማዕከላዊነት ባለው አንድ ፓርቲ ሥር በሆነ ሁኔታ የምትተዳደር በመሆኑ ምክንያት አገሪቱ ከሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አንጻር በሕገ-መንግሥት ደረጃ ፌደራላዊ፣ በተግባር ግን አሐዳዊ አስተዳደር ያለባት አገር ነች ማለት ይቻላል፡፡

በፌደራል መንግሥቱ ሦስቱ ምሰሶዎች መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ሁኔታ ስናይ የሥራ ትብብር እንጂ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አለ ማለት ያስቸግራል፡፡ ሕግ አውጭ የሆነው ፓርላማ ከበቂ በላይ በሆነና የሌሎች ፓርቲዎችን የድምፅ እገዛ በማይጠይቅ መጠን በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያለ ሲሆን፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት ደግሞ አንድም የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ በውስጡ ሳይኖር ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግና በአጋር ድርጅቶቹ የተሞላ ነው፡፡ ሕግ አስፈጻሚ የሆነው የሚኒስትሮች ምክር ቤትም በተመሳሳይ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በገዥው ፓርቲና በአጋር ድርጅቶቹ የተሞላ ሲሆን፣ የዳኝነት ሥርዓቱን የሚመሩት ሰዎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመረጡ ከመሆኑም በላይ ከዚያም በታች ባለው እርከን የሚገኙት ዳኞች ቢያንስ ስለ ኢህአዴግ ያላቸው በጎ አመለካከት ሳይረጋገጥ ሊሾሙ የሚችሉበት ዕድል አለ ማለት አይቻልም፡፡

ስለዚህ እነዚህ በዚህ ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያሉ የመንግሥት መዋቅሮች ሲቻል አንዱ የሌላውን ገመና እየደበቀለት፣ ሳይቻል ደግሞ ርስ በርስ ተመካክረውና ተደጋግፈው ይሠራሉ እንጂ አንዱ በሌላው ላይ ቁጥጥር የሚያደርግበት አሠራር አለ ማለት አይቻልም፡፡ ሌላው ቀርቶ አንድ የኢህአዴግ አባል የሆነ የፓርላማ አባል በማንኛውም ጉዳይ ከፓርቲው የተለየ አቋም ማራመድ በማይችልበት ሁኔታና የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን እንኳንስ ስለ መንግሥት መዋቅሮች ድክመትና ስለ አንድ ባለሥልጣን ድክመት ዘገባ ማቅረብ በማይደፍሩበት አገር ስለ መንግሥት መዋቅሮች የርስ በርስ ቁጥጥር ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ በ2000 ዓ.ም የአገሪቱ የኦዲት ቢሮ የመንግሥት የፋይናንስ አሠራርን የሚተች አንድ ሪፖርት ለፓርላማው በማቅረቡ ከአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይቀር ምን ያህል ዘለፋና ቁጣ እንደደረሰበት በይፋ አይተናል፡፡ ከአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች በስተቀርም አልፎ አልፎ የመንግሥት ሹማምንት

ግምገማ እንደሚካሄድባቸውና ርምጃ እንደሚወሰድባቸው የምንሰማውም በገዥው ፓርቲ ውስጣዊ ግምገማ ነው እንጂ ለመገናኛ ብዙኃንና ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ አይደለም። ስለዚህ የፓርቲ ማዕከላዊ አሠራር እንደዚህ ጥብቅና ሚስጥራዊ በሆነበት አገር በመንግሥት መዋቅሮች መካከል የሥራ ክፍፍልና ትብብር እንጂ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አለ ማለት አይቻልም።

በፌደራሉ መንግሥትና በክልሎች መካከል ያለውን ግንኙነትም ስናየው ምን አልባት የባሰ እንጂ የተሻለ ሆኖ አናገኘውም። የሁሉም ክልሎች ምክር ቤቶችና የመሪነት ቦታዎች ሙሉ በሙሉ በገዥው ፓርቲና በአጋር ድርጅቶቹ አባላት የተያዙ ናቸው። በእዚች ሰፊ የቆዳ ስፋት ባላትና ከ76 ሚሊየን በላይ ሕዝብ በሚገኝባት አገር አንድ ክልል ሳይሆን አንድም ወረዳና ቀበሌ በተቃዋሚ ፓርቲ የሚተዳደር የለም። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢያንስ የፓርላማ መቀመጫ ባሸነፉባቸው ከ170 ያላነሱ የአገሪቱ ወረዳዎች የወረዳና የቀበሌ መስተዳድሮችን በሕዝብ ምርጫ አሸንፈው ሊይዙ የማይችሉበት አሳማኝ ምክንያት ባይኖርም በአገሪቱ እውነተኛ ዴሞክራሲ ባለመኖሩና በራሳቸው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ድክመት ምክንያት ጭምር አንድም የአገሪቱ ወረዳ ወይም ቀበሌ እስካሁን በተቃዋሚዎች የሚተዳደር ሊሆን አልቻለም። አንድ አገር በዚህ ዓይነት የአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ የበላይነት እየተመራ ባለበት ሁኔታ ተገቢ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ይቅርና የብዙኃን ፓርቲ ሥርዓት በዚች አገር በተግባር አለ ብሎ ማመንን እጅግ አስቸጋሪ ያደርገዋል። የሁሉም የአገሪቱ ክልሎች መሪዎች አካባቢያቸውን የሚያስተዳድሩበት ፖሊሲና መመሪያ የሚወጣላቸው ጥብቅ ማዕከላዊነት ካለው ከፓርቲያቸው ሲሆን ሹመትን የሚያገኙትም ሆነ የሚያጡት ከሕዝብ ሳይሆን በዋናነት ከፓርቲው አመራር ነው። በሚያስተዳድሩት ክልልና ለሹመት ባበቃቸው ፓርቲ መካከል የጥቅም ግጭት ቢፈጠር ለክልሉ ጥቅም ወገንተኛ ሆነው ለመቆም የሚችሉበት ድፍረትም ሆነ አቅም የላቸውም። እስካሁንም በተግባር እንዳየነው አንዳንድ የቀድሞ የክልል ሹማምንቶች ስለ ፓርቲያቸው ስህተትና ገመና ደፍረው ሲናገሩ ያዳመጥነው በሥልጣን ላይ እያሉ ሳይሆን ሥልጣናቸውን ለቀው ወይም ተነጥቀው ከድርጅቱ ከወጡ፣ ወይም አገር ጥለው ከተሰደዱ በኋላ ነው።

ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በየትኛውም የአገሪቱ የክልል መንግሥትና በፌደራሉ መንግሥት መካከል ምንም ዓይነት መለስተኛ አለመግባባት እንኳን ተፈጥሯል ሲባል ሰምተን የማናውቀውና የሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ሕገ-መንግሥቶችና ፖሊሲዎች አንድ ዓይነት የካርቦን ቅጅዎች ሆነው የምናያቸው ያለ ምክንያት ሳይሆን በአንድ ጥብቅ ማዕከላዊነት ባለው ፓርቲ ሥር ታምቀው የሚገኙ በመሆናቸው ነው። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች አይደሉም በሚባሉት አጋር ድርጅቶች በሚተዳደሩት አናሳ (በሕዝብ ቁጥር) ክልሎች ሳይቀር ሕዝቡ የሚተዳደርበት

ሕግና ፖሊሲ የሚመነጨው በዋናነት ከየክልሎቹ በሕዝብ ከተመረጡ ምክር ቤቶች ሳይሆን በአማካሪነት ስም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮና ከፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በሚላኩ የኢህአዴግ ካድሬዎች መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ እንዲያውም ተጋነነ ካልተባለ በስተቀር ከባለ ሥልጣናት መብትና ነፃነት አንጻር አብዛኛዎቹ የወቅቱ የክልል መሪዎቻችን በደርግና በንጉሡ የአሐዳዊ ሥርዓት ሥር በየክፍላተ ሃገራቱ ከነበሩት ሹማምንት ያነሰ እንጂ የተሻለ ሥልጣንና ነፃነት አላቸው ማለት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ በፌደራል መንግሥትና በክልሎች መካከል ያለውም ግንኙነት ሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ከሰፈረው የፖለቲካ ነፃነት እጅግ በራቀ መጠን በፌደራላዊ ሳይሆን በአሐዳዊ መንግሥት ውስጥ የሚታይ ዓይነት ከላይ ወደ ታች የሚወርድ ማዕከላዊነትን የጠበቀ ግንኙነት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ክልሎች በአንድ ጊዜ በሁለንተናዊ መልኩ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ብቃት ላይ ሊደርሱ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡ ከላይ ዴሞክራሲ በእኛ ዓይነቱ ታዳጊ አገር የአተገባበር ቅደም-ተከተል ያስፈልገዋል እንዳልነው ሁሉ ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳይም ተገቢ በሆነ የአተገባበር ቅደም- ተከተል በሂደት እየሰፋ እንዲሄድ ካልተደረገ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ የቅደም-ተከተል አተገባበር ተፈፃሚ መሆን ያለበት ግልጽ የሆነ ሕጋዊ አሠራርና መተማመን በመፍጠር ነው እንጂ፣ በሕገ-መንግሥቱ ደረጃ ልቅና ከገደብ ያለፈ መብት ተሰጥቶ ሲያበቃ በፓርቲ ውሳጣዊ አሠራር እንደገና የተሰጠውን መብት ሙሉ በሙሉ በመቀማት ሊሆን አይገባውም፡፡ በተለይም አገሪቱ የዜጎች ሳይሆን የብሔር-ብሔረሰቦች አገር ነች በተባለበትና አንቀጽ 39ን የመሰለ ልግስና የበዛበት መብት ለክልሎች በተሰጠበት ሁኔታ በሕገ-መንግሥቱ የሰፈረው የክልሎች መብትና በተግባር ያለው ሁኔታ እንደዚህ የሰማይና የመሬት ያህል ተራርቆ ሲገኝ አንድ ወቅት ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ በቀላሉ የሚገመት አይሆንም፡፡

በፓርቲ የእዝ ሰንሰለት ተወጥሮ የተያዘ አንድ ክልል በአንድ አጋጣሚና ሁኔታ ከፓርቲው ቁጥጥር ቢወጣ ሊወስደው የሚችለው ርምጃ ከአገር መገንጠል መሆን የማይችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለዚህ የተሻለ አማራጭ የሚሆነው በሕገ-መንግሥት ለክልሎች የሚሰጠውን መብት በአንድ በኩል ተገቢ የአተገባበር ቅደም -ተከተልን ግምት ውስጥ ያስገባ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአገሪቱ አንድነትና የብሔር- ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አንጻር የተመጠነና የተጣጣመ እንዲሆን ማድረግ ነው እንጂ አንድ ጊዜ በሕገ-መንግሥት የተሰጠን መብት በፓርቲ ማዕከላዊነት ሰበብ በጓሮ በር እንደገና ለመቀማት መሞከር ተገቢ ካለመሆኑም በላይ ውሎ አድሮ የመገንጠል ጥያቄ አቀንቃኞችን የበለጠ የሚያጠናክር ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ በአጠቃላይ

ከሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አኳያ ሕገ-መንግሥቱ ሰፊ የፖለቲካ ነፃነት ለክልሎች የሰጠ ቢሆንም በተግባር ሲታይ ግን በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ነፃነት ክልሎች በፌደራል አደረጃጀቱ የሚገባቸውን ያህል ተጠቃሚ ሆነዋል ማለት አይቻልም፡፡

ከሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አንጻር ሌላው ጥያቄ ሊነሣበት የሚገባ ጉዳይ ሕገ-መንግሥቱ ለፌደሬሽን ምክር ቤት የሰጠው ሥልጣን ነው፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት በሌሎች አገሮች ሴኔት ወይም የላይኛው ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራውንና የክልሎች ውክልና የሚኖረውን ተቋም ለመተካት ተብሎ የተቋቋመ ምክር ቤት ቢሆንም የእኛ የፌደሬሽን ምክር ቤት በቅርፅም ሆነ በይዘቱ ከሌሎች አገሮች ሴኔቶች የተለየ ባህሪ ያለው ሆኖ ይታያል፡፡ ከቅርፅ አንጻር የሚታይበት ልዩነት በአብዛኛዎቹ አገሮች የሚገኙ ሴኔቶች የክልል መንግሥታት የሚወከሉባቸው ምክር ቤቶች ሲሆኑ የእኛ የፌደሬሽን ምክር ቤት ግን በዋናነት የክልሎች ሳይሆን የብሔር- ብሔረሰቦች ውክልናን የያዘ ምክር ቤት ነው፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላትን የመምረጥና የመላክ መብቱ የክልል ምክር ቤቶች ቢሆንም ሁሉም በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔር- ብሔረሰቦች ቢያንስ አንድ ተወካይና በአንድ ሚሊየን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ተወካይ የመላክ መብት አላቸው፡፡

ይህ መሆኑ በቀጥታ ሲታይ ምን ክፋት አለው? የሚል ጥያቄ ሊያሥነሣ ይችላል፡፡ ነገር ግን በሌሎች አገሮች የተለመደው ክልሎች የቱንም ያህል ትልቅም ይሁኑ ትንሽ በሴኔቱ ውስጥ የሚኖራቸው ውክልና እኩል ነው፡፡ ይህም የሚደረግበት ምክንያት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት /ኮንግረስ/ ውስጥ ብዙ የሕዝብ ቁጥር ያለው ክልል በዚያው መጠን ብዙ ውክልና ስለሚኖረውና ትንሽ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ክልሎች በዚያው መጠን ትንሽ ውክልና ስለሚኖራቸው ይህንን የተዛባ ሚዛን ለማስተካከል ተብሎ ነው በሴኔቱ ውስጥ ሁሉም ክልሎች የሕዝብ ቁጥራቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ እኩል ውክልና እንዲኖራቸው የሚደረገው፡፡ አሜሪካንን በምሳሌነት ብንመለከት - የአሜሪካን ኮንግረስ 435 የሕዝብ ቁጥርን መሠረት ባደረገ ምርጫ የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች ያሉት ሲሆን፣ ሴኔቱ ግን ከየስቴቱ ተመርጠው የመጡ ሁለት ሁለት አባላት፣ በአጠቃላይ አንድ መቶ ተወካዮች የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡ በሴኔቱ ውስጥ ከሠላሳ ሚሊየን በላይ የሕዝብ ብዛት ያለው የካሊፎርኒያ ግዛትም ሆነ ከአንድ ሚሊየን በታች የሆነ የሕዝብ ብዛት ያላቸው በርካታ ግዛቶች እኩል ውክልና ነው ያላቸው፡፡ በዚህም ምክንያት ከኮንግረሱ በተለየ በሴኔቱ ውስጥ ከትልልቆቹ ግዛቶች ይልቅ በድምሩ ከፍተኛ ውክልና ያላቸው ትንንሾቹ ግዛቶች ናቸው፡፡ ይህም ማለት በሴኔቱ ውስጥ የድምፅ ብልጫ ያላቸው 26ቱ ትንንሽ

ስቴቶች ከሕዝብ ቁጥር አንጻር ሲታይ 16% የሚሆነውን የአሜሪካንን ሕዝብ ብቻ የሚወክሉ ናቸው፡፡

በእኛ አገር ሁኔታ ግን እንዲህ ዓይነቱ ሚዛን የለም፡፡ ምክንያቱም በፌደሬሽን ምክር ቤት ውስጥ ውክልና የሚሰጠው እያንዳንዱ ክልል ሳይሆን እያንዳንዱ ብሔረሰብ በመሆኑ በምክር ቤቱ ውስጥ የሚገኝ አንድ ክልል ማለትም የደቡብ ክልል መስተዳድር ብቻውን በፌደሬሽን ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ ድምፅ ያለው ሆኗል፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት 112 መቀመጫዎች ያሉት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ50% በላይ የሆነው ማለትም 62 መቀመጫ በደቡብ ክልል መስተዳድር የተያዘ ነው፡፡ ይህም ማለት በአገሪቱ ካሉት ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ ስምንቱ ክልሎች በአንድ ጉዳይ ላይ አንድ ዓይነት አቋም ቢኖራቸው እንኳ ውሣኔ ለማፅደቅ የሚያስችል በቂ ድምፅ የሌላቸው ሲሆን፣ ነገር ግን ከዘጠኙ ክልሎች አንዱ የሆነው ደቡብ ክልል የፈለገውን ውሳኔ የሌሎቹ ክልሎች ድጋፍ ሳያስፈልገው ማፅደቅ ይችላል ማለት ነው፡፡

አንድ የአገሪቱ ክልል በዚህ መልክ ከሌሎቹ ሁሉም ክልሎች የበለጠና ብቸኛ የሆነ የመወሰን መብት /veto power/ ባገኘበት ሁኔታ የፌደሬሽን ምክር ቤት ዴሞክራሲያዊ ተቋም ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ በአሁኑ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ተቋም ነው እየተባለ የሚተቸው በውስጡ የሌላውን ዓለም ውሳኔ ውድቅ ማድረግ የሚችሉ አምስት የጸጥታው ምክር ቤት አባል አገራት ስለአሉበት ሲሆን የእኛ አገር የፌደሬሽን ምክር ቤትም ከዚያ በባሰ ሁኔታ በአንድ ክልል አብላጫ ድምፅ ቁጥጥር ውስጥ የወደቀ ነው፡፡ የአገራችንን ሕገ-መንግሥት ለማሻሻል የሚቀርብን ጥያቄ አንድ ሐረሪን የመሰለ የአገራችን አነስተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለው ክልል ብቻውን ውድቅ ማድረግ እንደሚችለው ሁሉ የፌደሬሽን ምክር ቤት በአንድ ጉዳይ ላይ ውሣኔ የማሳለፍ ዕድልም በአንድ ክልል ቁጥጥር ሥር የወደቀ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአገራችን በቁጥር ብዙኃን ከሆነው ሕዝብ ይልቅ በቁጥር አናሳ የሆነው ሕዝብ የበለጠ የመወሰን መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የደቡብ ክልል እየተዳደረ የሚገኘው የኢህአዴግ አባል በሆነና ከኢህአዴግ ፍላጐት ቁጥጥር ሊወጣ በማይችል ድርጅት በመሆኑ ምክንያት ለጊዜው ችግር የሌለው መስሎ ቢታይም ነገ ከነገ ወዲያ በኢህአዴግ ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን እየተቀየረ ሲመጣ ግን የደቡብ ክልል በፌደሬሽን ምክር ቤቱ ላይ ያለው ብቸኛ የበላይነት የአገሪቱን የፖለቲካ መረጋጋት የሚያውክ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ዞሮ ዞሮ ይህ የደቡብ ክልል ብቻውን የፌደሬሽን ምክር ቤትን አብላጫ ድምፅ የመያዙ ጉዳይ የበለጠ የሚያረጋግጥልን አገሪቱ ምን ያህል ሕገ-መንግሥታዊ ብቻ ሳይሆን መዋቅራዊ በሆነ ሁኔታም የዜጐች ሳይሆን የብሔር-ብሔረሰቦች ንብረት የተደረገች መሆኗን ነው፡፡

እዚህ ላይ የፌደሬሽን ምክር ቤት የብሔር-ብሔረሰቦችን እንጂ የክልሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተቋቋመ ምክር ቤት አይደለም የሚል ክርክር ሊነሣ ይችላል፡፡ ነገር ግን አገሪቱ በውስጧ ባሉት ብሔር-ብሔረሰቦች ቁጥር ልክ ከሰባ በላይ ክልላዊ መንግሥታት ሊኖሯት አይችልም ተብሎ በዘጠኝ ክልሎች ብቻ እንድትዋቀር እስከተደረገ ድረስ የፌደሬሽን ምክር ቤት ውክልናም ይህንን መሠረት አድርጎ መዋቀር ነበረበት እንጂ ብሔር-ብሔረሰቦችን በተናጠል ቆጥሮ ውክልና በመስጠት ከሕዝብ ቁጥር ብዛትም ሆነ ከክልሎች የኃይል ሚዛን አንጻር በአንድ ምክር ቤት ውስጥ አንድን ክልል ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ ማድረግ በየትኛውም መመዘኛ ትክክል ሊሆን አይችልም፡፡

ይህ ከዚህ በላይ ሊቀርብ የተሞከረው ትችት ከፌደሬሽን ምክር ቤቱ ቅርፅና አንድ ክልል ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ እንዲሆን ከመደረጉ ጋር በተያያዘ ሲሆን፣ ከይዘት አንጻርም ፌደሬሽን ምክር ቤቱ ጥያቄ ሊነሣበት የሚችል አካል ነው፡፡ በሌሎች አገሮች የክልሎች ሚዛናዊ ውክልና የሚንፀባረቅባቸው ሴኔቶች እንደ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ የማውጣት መብት ያላቸው ሲሆን የእኛ የፌደሬሽን ምክር ቤት ግን ሕግ የማውጣት መብት አልተሰጠውም፡፡ አንድ የክልሎችም ሆነ የብሔር-ብሔረሰቦች ሚዛናዊ ውክልና እንዲንፀባረቅበት የሚፈለግ ምክር ቤት ሕግ የማውጣት መብት እስከ ሌለው ድረስ በሕዝብ ብዛት ውክልና የተቋቋመው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የክልሎችን ጥቅም የሚነካ አንድ ውሳኔ ቢወስን ውሳኔውን በተወሰነ ደረጃ ሊገታ ወይም ሊቀናቀን የሚችልበት ዕድል አይኖረውም፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤቱ በተወሰኑ የአገሪቱ የጋራ ጉዳዮች ላይ ክልሎችን ወክሎ ሕግ የማውጣት ሥልጣን እስከ ሌለው ድረስም ምክር ቤቱ ትርጉም ያለው ሥልጣን አለው ማለት አይቻልም፡፡ በአሁኑ ወቅት የፌደሬሽን ምክር ቤት ብዙ ጊዜውን የሚያጠፋው ስለ ሕገ-መንግሥት ዜጎችን በማስተማርና የብሔር-ብሔረሰቦችን ባህል በማስተዋወቅ ሆኖ የምናየውም ያለምክንያት ሳይሆን እንደ ሌሎቹ አገር ሴኔቶች ከሕግ-ማውጣት ጋር የተያያዘ ትርጉም ያለው ኃላፊነት ስላልተሰጠው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው የፌደሬሽን ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ የሚያካሂደው ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ መሆኑም በዚሁ ምክር ቤቱ ሰፊ ጊዜን የሚጠይቁ ኃላፊነቶች ያልተሰጡት በመሆኑ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤቱ በተወሰኑ አገራዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች ላይ ከተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጋራ፣ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ደግሞ በራሱ ሕግ የማውጣት መብት ቢኖረው ኖሮ በአገሪቱ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አሠራርን በማጠናከር ረገድ የተሻለ ሚና ሊኖረው ይችል ነበር፡፡ ፌደራላዊ ሥርዓትን ከሚከተሉ አገሮች መካከል ዴንማርክ፣ እሥራኤል፣ ኒውዚላንድና ጋናን የመሳሰሉት አገሮች

ከሌሎች በተለየ ሁኔታ አንድ ሕግ አውጭ ፓርላማ ብቻ /Unicameral Legislative/ ያላቸው ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ፌደራላዊ ሥርዓትን የሚከተሉ አገሮች ግን እንደ ኢትዮጵያ ሁለት ምክር ቤቶች ያሉአቸውና ነገር ግን ሁለቱም ምክር ቤቶች ሕግ የማውጣት ሥልጣን የተሰጣቸው /Bicameral Legislative/ ምክር ቤቶች ያሏቸው ናቸው፡፡

በአገራችን የፌደሬሽን ምክር ቤት ይዘት ላይ ብዙውን ጊዜ አከራካሪ ሆኖ የሚደመጠው ሌላው ጉዳይ የፌደሬሽን ምክር ቤቱ ሕገ-መንግሥት የመተርጐም ሥልጣን የተሰጠው መሆኑ ነው፡፡ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በሌሎች አገሮች ሴኔቶች ሕግ ማውጣት ሥልጣን ስለሚኖራቸው ሕገ-መንግሥት የመተርጐም ሥልጣን የላቸውም፡፡ በምርጫም ሆነ በተለየ ውክልና የሚቋቋሙ ምክር ቤቶች በባህሪያቸው ሞያዊ ተግባር የሚያከናውኑ ሳይሆን ፖለቲካዊ ውሳኔ የሚሰጡ በመሆናቸው ምክንያት ሕግን የመተርጐም ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡ በአብዛኛው የዓለም አገሮች እንደሚታየው ሕገ-መንግሥትንም ሆነ ማናቸውንም ሕግ የመተርጐም መብት ያላቸው በውክልና የተቋቋሙ ምክር ቤቶች ሳይሆኑ የሞያ ብቃት፣ ገለልተኛነትና ነፃነት ያላቸው የሕግ ባለሞያዎች የሚገኙባቸው ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡

በርግጥ በእኛ አገር ሕገ-መንግሥትን የመተርጐም ከፍተኛና ሞያን የሚጠይቅ ኃላፊነት ለፌደሬሽን ምክር ቤት የተሰጠው በአንድ በኩል ምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን ይህ ሥልጣን የብሔር-ብሔረሰቦች ተወካዮች ለሚገኙበት ለፌደሬሽን ምክር ቤት የተሰጠበት ዋና ምክንያት የአገሪቱ ባለቤቶች ብሔር-ብሔረሰቦች ናቸው ስለተባለ እንዲህ ዓይነቱን ከፍተኛ ሥልጣን ከእነሱ እጅ አውጥቶ በባለሞያዎች ለተቋቋመ የዳኝነት አካል አሳልፎ መስጠት አደገኛ ውጤት ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተሰጋ ይመስላል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ሕግ የማውጣቱን፣ ሕግ የማስፈፀሙንም ሆነ ሕግ የመተርጐሙን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ በፖለቲካ ኃይሎች እጅ ስለሚያስገባው በሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ተግባር ላይ ከፍተኛ ጉድለት ይፈጥራል፡፡

ከሁሉም በላይ ደግሞ ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው በፌደሬሽን ምክር ቤቱ ውስጥ ከ50% በላይ የሆነውን መቀመጫ የያዘው የደቡብ ክልል ስለሆነ ሕገ-መንግሥቱን የመተርጐም ሥልጣን የተሰጠው ለፌደሬሽን ምክር ቤት ነው ቢባልም በሌላ አነጋገር ሕገ-መንግሥቱን የመተርጐም መብት ያለው ብቸኛ አካል ደቡብ ክልል ነው ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሕገ-መንግሥታዊ ትርጉም ሊሰጠው የሚገባ አንድ ጉዳይ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ቢቀርብና ያ-ጉዳይ በአጋጣሚ የደቡብ ክልልን ጥቅም የሚነካ ሆኖ ቢገኝ ተገቢ ውሳኔ የማግኘት ዕድል አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ሕገ-መንግሥትን የመተርጐም ጉዳይ በአንድ ክልል እጅ በወደቀበት ሁኔታ ደግሞ

ትክክለኛ የሥልጣን ቁጥጥርና ክፍፍል በአገሪቱ አለ ማለት አይቻልም፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት በተለይም ከክልሎች አስተዳደርና ፋይናንስ ጋር በተያያዙ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ቢሰጠውና ሕገ-መንግሥትን የመተርጐም ሥልጣን ግን ራሱን ለቻለና በነፃነት ለሚሰራ ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ቢሰጥ በአገሪቱ የተሻለ የሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር አሠራር እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

ሌላው በፌደሬሽንም ሆነ በተወካዮች ምክር ቤት ላይ ሊነሣ የሚገባው ድክመት የምክር ቤት አባላት ከፓርቲ መስመር ወጥተው ውሳኔ የመስጠት ባህል /Bipartisanship/ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 ቁጥር 4 እና 5 ___፣

*"የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ ተገዥነታቸውም ሀ, ለሕገ-መንግሥቱ፤ ለ, ለሕዝቡ፤ እና ሐ, ለኅሊናቸው ብቻ ይሆናል፡፡ ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፡፡ አስተዳደራዊ ርምጃም አይወሰድበትም፡፡" ይላል፡፡*

ነገር ግን እስካሁን በተግባር እንደታየውም ሆነ የኢህአዴግ ባለሥልጣናት በግልጽና በድፍረት ሲናገሩ እንደሚደመጡት፣ የገዢው ፓርቲ አባላት ከፓርቲያቸው ውሳኔ ውጭ የሕዝቡን ጥቅምም ሆነ የራሳቸውን ኅሊና መነሻ አድርገው ድምፅ ሊሰጡ አይችሉም፡፡ ኢህአዴግ ለምክር ቤቱ የሚያቀርበው አጀንዳ የቱንም ያህል ለሕዝብ የሚጠቅም ይሁንም አይሁንም፣ ለኢህአዴግ ከሁሉም በላይ ትልቁ ቁምነገር የፓርቲ ማዕከላዊነት ስለሆነ የድርጅቱ አባላት የኢህአዴግን አጀንዳ ከመደገፍ በስተቀር የመቃወም መብት የላቸውም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በምክር ቤት ውስጥ ያለ አሠራር ከራሱ ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የማይጣጣም ከመሆኑም በላይ የራሱን የፓርላማውን የሚኖር አስፈላጊነትና መሠረታዊ የዴሞክራሲ አስተሳሰብን የሚጻረር አሠራር ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ የምክር ቤት አባላት ተገዥነታቸው ለሕገ-መንግሥቱ፣ ለሕዝቡ፣ እና ለኅሊናቸው ብቻ ይሆናል ባለበት ሁኔታ፣ የምክር ቤቱን አባላት ተገዥነታችሁ ለፓርቲ ነው ብሎ ተፅዕኖ ማድረግና ይህንንም ያለኀፍረት በግልጽ መናገር ከሕገ-መንግሥቱ መርህ የሚጻረር አስተሳሰብ ነው፡፡

ከዚህም በላይ የአንድ ፓርላማ አስፈላጊነት የተለያዩ የሕዝቡ ጥቅሞች፣ ፍላጐቶችና አስተሳሰቦች በአግባቡ እንዲወከሉ ለማድረግ ሆኖ እያለ በመቶዎች የሚቆጠሩ ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ተወክለው የመጡ የምክር ቤት አባላትን ለአንድ ፓርቲ አመለካከት ብቻ ተገዥ እንዲሆኑ ማድረግ ራሱን የፓርላማ አስፈላጊነትን የሚጻረር አስተሳሰብ ነው፡፡ የፓርቲ አባላት

የፓርቲ ዲሥፕሊን ኖሮአቸው በተወሰኑ መሠረታዊ ርእዮተ-ዓለማዊና ስትራቴጂክ ጉዳዮች ከፓርቲያቸው ጋር አብረው መቆማቸው አስፈላጊ ቢሆንም በሁሉም ዝርዝርና ጥቃቅን ጉዳዮች ሁሉ አንድ ዓይነት ድምፅ እንዲሰጡ ማድረግ ግን የግለሰብ ነፃነትን የሚጻረር ብቻ ሳይሆን ፓርቲዎች የአብሮ መሥራትና የመቻቻል ባህል እንዳያዳብሩ እንቅፋት የሚሆን አስተሳሰብ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፓርላማ አሠራር በዚህ ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ አስተሳሰብ የታሰረ በመሆኑ ምክንያት በኢህአዴግ ዘመን የሽግግር መንግሥቱን ጨምሮ በታዩት አራት ፓርላማዎች አንድም ጊዜ ከአንዳንድ ጥቃቅን ድርጅታዊና ግላዊ ጉዳዮች በስተቀር ሥራ-አስፈጻሚ አካሉ ወይም ገዥው ፓርቲ ለፓርላማ ያቀረባቸው ሕጎች ውድቅ መሆን ይቅርና በአንድም የገዥ ፓርቲ አባል ተቃውሞ ቀርቦባቸው አያውቅም፡፡

ለኢህአዴግ የፓርላማ አባልነት ትርጉም እንዲህ ከሆነ፣ በአሁኑ ወቅት ለምን ከ300 በላይ የሆኑ የኢህአዴግ አባላት በደመወዝና በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች የአገሪቱን ሀብት እያራቆቱ እንደሚገኙ ዕንቆቅልሽ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም በምክር ቤቱ ውስጥ የሚገኙ የኢህአዴግ አባላት እንዲሰጡ የሚጠበቀው አንድ ዓይነት ድምፅ እስከሆነ ድረስ ሁሉም የኢህአዴግ አባላት የያዙት መቀመጫ በአንድና በሁለት የኢህአዴግ አመራሮች ብቻ ቢወከል የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ እነዚህ የኢህአዴግ አባላት ሕገ-መንግሥቱ እንደሚለው ለመረጣቸው ሕዝብና ለኅሊናቸው ተገዥ ሆነው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያየ ድምፅ የሚሰጡበት ዕድል እስከሌለ ድረስ ለሚከፈላቸው ደመወዝ የሚመጥን ሚና በፓርላማው ውስጥ አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ በፓርላማው ውስጥ በአንድ በኩል በሌሎች አገሮች እንደሚታየው በተወሰነ ደረጃ የገዥውን ፓርቲና የሥራ-አስፈጻሚውን አካል ፍጹማዊ የበላይነት ለመቀነስ የሚያስችል አሠራር ለመፍጠር፣ በሌላ በኩል ደግሞ በፓርቲዎች መካከል አብሮ የመሥራትና የመቻቻልን /Bipartisanship/ ባህል የሚያሳድግ አሠራር ለመፍጠር እንዲቻል የምክር ቤት አባላት በመሠረታዊ ርእዮተ-ዓለማዊና ስትራቴጂክ የሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ከፓርቲያቸው ጐን የመቆማቸው አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚያ በመለስ ባሉ ዝርዝር ጉዳዮች ግን በነፃነት ድምፅ የመስጠት መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ ያልሆነ ባህል በገዥው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥም ያለ ነው፡፡ በፓርላማው የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ማንም ያቅርባቸው ማንም በይዘታቸው ብቻ እየመዘነ የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ድምፅ በመስጠት ይህንን ባህል በአሁኑ ወቅት ለመስበር በጐላ ሁኔታ ጥረት እያደረገ የሚገኘው ኢዴፓ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከሥልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር ጋር ተዛማጅነት የሌለው ቢሆንም የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቁጥር የበዛ መሆኑ በራሱ እንደ አንድ ድክመት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

በሕገ-መንግሥቱ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ቁጥር 547 ሲሆን ይህ ቁጥር ከሌሎች ከእኛ አገር የሕዝብ ብዛት የሚመጣጠን የፓርላማ አባላት ቁጥር ካላቸው አገሮች ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ በዓለም ላይ ካሉ ፓርላማዎች ከእኛ አገር ጋር የሚመጣጠን ቁጥር ያላት አገር ህንድ ነች፡፡ የህንድ ፓርላማ አባላት ቁጥር ከእኛ አገር በአምስት ብቻ የሚበልጥ ማለትም 552 ሲሆን፣ ህንድ ግን ከአንድ ቢሊዮን በላይ የሕዝብ ብዛት ያላትና በብሔር-ብሔረሰቦችም ሆነ በኃይማኖቶች ብዛት በብዙ ርቀት ከኢትዮጵያ የበለጠ የውስጥ ልዩነቶችን ያቀፈች አገር ነች፡፡ በቆዳ ስፋትና በኢኮኖሚ ግዙፍ የሆነችውና ከ305 ሚሊየን በላይ የሕዝብ ቁጥር ያላትን አሜሪካንን በተጨማሪ ምሳሌነት ብናይም ያላት የኮንግረስ አባላት ቁጥር ከእኛ በ112 ያነሰ ማለትም 435 ብቻ ነው፡፡ የአብዛኛዎቹ የዓለም አገሮች የፓርላማ አባላት ቁጥር ሲታይም በአማካይ ከ150 እስከ 300 ድረስ ብቻ ነው፡፡

ስለዚህ የኢኮኖሚ አቅሟ ደቃቅ የሆነችው ኢትዮጵያ ከእነ አሜሪካ የበለጠ ግዙፍ ፓርላማ ያላት መሆኑን ተገቢ የሚያደርገው አሳማኝ ምክንያት ስለሌለ አሁን ያላት የፓርላማ አባላት ቁጥር ወደ 300 አካባቢ ዝቅ ቢል ለአገሪቱ ኢኮኖሚም ሆነ ጥራት ላለው የፓርላማ ሥራ የሚያግዝ ይሆናል፡፡ በፓርላማው ውስጥ በሚገኙት 13 ቋሚ ኮሚቴዎች ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉት አባላት ብዛት ሌሎች የትብብር ኮሚቴዎችን ጨምሮ ከ250 የሚበልጥ ስላልሆነና አንዳንድ የፓርላማ አባላትም በፓርላማ ውስጥ እንኳንስ የጐላ ተሳትፎ ማድረግና በአምስት ዓመቱ የሥራ ጊዜ ውስጥ አንድ ጊዜም እንኳ የመናገር ዕድል ሳያገኙ የሚመለሱበት ሁኔታ ስላለ ለተለያዩ አናሳ ብሔረሰቦች የሚሰጠው ልዩ ውክልና እንደተጠበቀ ሆኖ ከ250 እስከ 300 ሺ የሚሆን ሕዝብ በአንድ የፓርላማ ተወካይ እንዲወከል ቢደረግ ጥቅም እንጂ ጉዳት አይኖረውም፡፡ ሌሎች በየክልሉና በየወረዳው የሚገኙ ምክር ቤቶች ቁጥርም በዚህ መልኩ እንዲመጠን ቢደረግ በየአምስት ዓመቱ በአገሪቱ የሚካሄደው ምርጫ ወጭ ቆጣቢ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ጭምር ይረዳል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ አከራካሪ ናቸው ብለን በዚህ የጽሑፍ ክፍል ውስጥ ልናያቸው የሞከርንና ሌሎችም ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ወደፊት እንዲሻሻሉ ለማድረግ የሚቻለው ራሱ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የተቀመጠው ሕገ-መንግሥቱን ለማሻሻል የሚያስችለው አንቀጽ ሲሻሻል ነው፡፡ ይህ ሕገ-መንግሥቱን ስለማሻሻል በአንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል __፣

*"በዚህ ሕገ-መንግሥት ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነፃነቶች በሙሉ፣ ይህ አንቀጽ፣ እንዲሁም አንቀጽ 104 ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ*

*ይሆናል፤ ሀ, ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምፅ ብልጫ ሲያፀድቁት፣ ለ, የፌደራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያፀድቀው፣ እና ሐ, ፌደሬሽን ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያፀድቀው ነው።"* ይላል።

አንድ ሕገ-መንግሥት እንደተራ ሕግ በየጊዜው መለዋወጥ የማይገባው ስለሆነ የአንድን አገር ሕገ-መንግሥት በቀላሉ እንዳይሻሻል አድርጐ ማውጣት ተገቢ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። የዚህን በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 105 የሰፈረ የማሻሻያ ሐሳብ ግትርነት ብቻ ሳይሆን ጨካኝነት፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊነትና ኢ-ፍትሐዊነት ግን በቃላት ለመግለፅ መሞከር አስቸጋሪ ነው። በሕገ-መንግሥቱ ዋና ክፍል ምዕራፍ ሦስት ውስጥ የሚገኙትንና ራሱን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ አንቀጽ ለማሻሻል ያለው ዕድል በሆነ ተአምራዊ ኃይል ካልሆነ በስተቀር የተለያዩ ጥቅም፣ ፍላጐትና አስተሳሰብ በሰፊው ባለበት እንደ ኢትዮጵያ ባለ አገር ማሻሻል የማይቻል ነው። ለማንም አንብቦ ለመረዳት ለሚችል ሰው አንቀጽ 105 ምን ማለት እንደሆነ በራሱ ግልጽ ቢሆንም የበለጠ ለመረዳት እንዲቻል የሚቀጥለውን ምሳሌ ለማየት እንሞክር።

ይህንን ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ሕገ-መንግሥቱን ስለማሻሻል የተቀመጠውን አንቀጽ 105ን አሁን በሥልጣን ላይ ያለውም ሆነ ወደፊት ወደ ሥልጣን የሚመጣ አንድ ፓርቲ ማሻሻል ያስፈልጋል ብሎ ሐሳብ ቢያቀርብ፣ በመጀመሪያ የማሻሻያ ሃሣቡ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 104 መሠረት ለውይይት መቅረብ የሚችለው የሕዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤቶች በ2/3ኛ ድምፅ ሲደግፉት ወይም ከአገሪቱ ክልሎች ውስጥ 1/3ኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ ሲደግፉት ነው። የቀረበው የማሻሻያ ሐሳብ በዚህ የውሳኔ ሂደት አልፎ ለውይይትና ለውሳኔ ከቀረበ በኋላ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው ግን ሁሉም በአገሪቱ የሚገኙ የክልል ምክር ቤቶች ውሳኔውን በአብላጫ ድምፅ ሲደግፉት ብቻ ነው።

ይህም ማለት የማሻሻያ ሃሣቡ ከ99.7% በላይ በሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የክልል ምክር ቤቶች ተቀባይነት ቢያገኝና ከ0.3% በታች በሆነው የሐረሪ ክልል ሕዝብ ምክር ቤት የማሻሻያ ሃሣቡ በአብላጫ ድምፅ መደገፍ ሳይችል ቢቀር ውድቅ ይሆናል ማለት ነው። እንግዲህ የ99.7% ሕዝብ ፍላጐትና ውሳኔን የ0.3% ሕዝብ ውሳኔ ውድቅ /Veto/ የሚያደርገው ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ የውሳኔ አሰጣጥ በምን ዓይነት መመዘኛ ዴሞክራሲያዊም ሆነ ፍትሐዊ ሊባል እንደሚችል ሕገ-መንግሥቱንም ለአረቀቁት ሰዎች ግልጽ ከሆነ እጅግ ተአምር ነው። ከሁሉም በላይ ለሁሉም የሕገ-መንግሥት አንቀጾች የወደፊት መሻሻል መሠረትና መነሻ ሊሆን

የሚችለውን ይህንን አንቀጽ 105ን ለማሻሻል ብቸኛ ዕድል ሊኖረው የሚችለው ኃይል የወቅቱን የክልል መንግሥታት ኮትኩቶ ያሳደገው ኢህአዴግ ካልሆነ በስተቀር ወደፊት የቱንም ያህል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ ቢመጣ ያለ አግባብ ሕግን የሚጥስ ተግባር በመፈጸም ካልሆነ በስተቀር በሕግ አግባብ ይህንን አንቀጽ በቀላሉ ሊያሻሽለው አይችልም፡፡

ምክንያቱም እውነተኛ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወደፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም የአገሪቱ ክልሎች ሙሉ በሙሉ በአንድ ምርጫ አሸንፎ ሥልጣን የሚይዝ የፖለቲካ ድርጅት በቀላሉ ሊኖር አይችልምና ነው፡፡ ቀደም ሲል በሌላ ርእስ ላይ ለማየት እንደሞከርነው ተቃዋሚዎች ከብዙዎቹ የአገሪቱ ክልሎች ይልቅ ቀድመው ማሸነፍ የሚችሉት የጥቂቶቹን ክልሎችና የማዕከላዊ መንግሥቱን ሥልጣን ነው፡፡ በሂደት ዴሞክራሲው እየሰፋ ሲሄድም አገሪቱ ብዙ ውስጣዊ ልዩነቶች ያሉባት አገር እንደመሆንዋ መጠን በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች የተለያዩ ፓርቲዎች ሥልጣን የሚይዙበት ሁኔታ መፈጠሩና በጥምር መንግሥትነት ሥልጣን የመያዝ ዕድል እየሰፋ መምጣቱ አይቀርም፡፡ በዚያ ዓይነቱ ሁኔታ ደግሞ የመገንጠል ጥያቄዎች የበለጠ አስጊ እየሆኑ የሚመጡ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ኢህአዴግ ማድረግ እንደቻለው ክልሎችን በፓርቲ ማዕከላዊነት ጠልፎ በመያዝ እንደልብ መቆጣጠር የሚቻልበት ዕድል አይኖርም፡፡ ለዚህም ነው አገሪቱ ወደባሰ አደጋ ከማምራቷ በፊት አንቀጽ 105ን ከማንም በላይ የማሻሻል ዕድል ያለው ኢህአዴግ ነው ለማለት የሚያስችለን፡፡

አለበለዚያ ነገ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ የመንግሥት ሥልጣን ቢይዝና አብዛኛዎቹ ብቻ ሳይሆኑ አንድ ክልል ብቻ እንኳን በሌላ ተቃዋሚ ፓርቲ ሥልጣን የሚተዳደር ከሆነ ሕጋዊ በሆነ መንገድ አንቀጽ 105ን ሊያሻሽል የሚችልበት ዕድል ጠባብ ነው፡፡ አሁን አንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሲሉ እንደሚደመጡትም ሥልጣን በያዙ ማግሥት ሕገ-መንግሥቱን ቀዳደው የሚጥሉት ከሆነ ከፍተኛ አካባቢያዊ ስሜት በተጠናከረበት በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ወደምን ዓይነት አደጋ ውስጥ ልትገባ እንደምትችል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ ኢህአዴግን የችግሩ አካል ብቻ ሳይሆን የመፍትሔው አካልም አድርጐ ማየት ይጠቅማል የምንለውም ለኢህአዴግ የተለየ ፍቅር ኖሮን ሳይሆን ጉዳዩ ከአገር ህልውና ጋር በጥልቀት የተቆራኘ ትርጉም ያለው በመሆኑና አንዳንድ በኢትዮጵያ ወደፊት መምጣት ያለባቸው በጎ ለውጦችም የኢህአዴግን ሚና የግድ የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው፡፡ በ97 ዓ.ምቱ ምርጫ የሕዝብን ቀልብ በከፍተኛ ደረጃ ስቦ የነበረውና የአገሪቱን አጠቃላይ ወቅታዊ ሁኔታና የፖለቲካ የኃይል አሰላለፍ በአግባቡ መገንዘብ ተስኖት የነበረው የቅንጅት ዓይነቱ ስብስብ በኢትዮጵያ መንግሥት የመሆን ዕድል ቢያገኝ ኖሮ የአገሪቱን ዕጣ-ፈንታ ከድጡ ወደ ማጡ ሊያደርገው

ይችል እንደነበር ሁለት ሦስት ጊዜ ቆም ብለን ማሰብ ያለብንም ይህንን ዓይነቱን አሳሳቢ ጉዳይ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የሆኖ ሆኖ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በአገሪቱ የወደፊት ህልውና ላይ እንዲህ ዓይነት አደጋ ያረገዘ ሰነድ የሆነበት ምክንያት ከመጀመሪያው ሕገ-መንግሥቱ የተረቀቀውና የጸደቀው አብሮ በመኖር የትምምን መንፈስ ሳይሆን በከፍተኛ የጥርጣሬ መንፈስ በመሆኑ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ እንደ ኢትዮጵያ ላለ የፌደራል አደረጃጀትም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት አዲስና ጀማሪ ለሆነ አገር ሕገ-መንግሥትን የማሻሻል ጉዳይ ለጊዜው ቀለል ባለ መንገድ የሚቻል ቢሆን ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ብዙዎቹ መንግሥታት አገርን ለማደራጀት የተጠቀምንባቸው ፅንሰ-ሐሳቦችና የአሠራር ዘዴዎች ከሌሎች አገሮች የተቀዱ ስለሆኑ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እስኪጣጣሙ ድረስ በየጊዜው የመሻሻልና የመቀየር ዕድላቸው ሰፊ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ስለዚህ ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ጉዳይ ለተወሰኑ ዓመታት ቢቻል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌደሬሽን ምክር ቤት 2/3ኛ ድምፅ፣ ይህንን ማድረግ አደጋ ያስከትላል ተብሎ ከተሰጋም ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያዎቹ በአጠቃላዩ ሕዝብ ተሳትፎ በሚካሄድ ሕዝበ-ውሣኔ በአብላጫ ድምፅ የሚወሰኑበት ሁኔታ ቢመቻች የተሻለና በርግጥም ሕገ-መንግሥቱን በአግባቡ ለማሻሻል የሚያስችል ይሆናል፡፡ ሕገ-መንግሥቱ አግባብ ባለው ሁኔታ የመሻሻል ዕድል እንዲኖረው ማድረግ ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ ሌሎቹን ከአገር ህልውና ጋር የተያያዘ ከባባድ ጉዳዮች ትተን ቀላል የሚባሉ እርማቶችን ለማድረግ እንኳ ሕገ-መንግሥትን የማሻሻል ጉዳይ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ በአንድ ቀላል ምሳሌ ልንረዳ እንችላለን፡፡ ይኸውም የአሁኑ የአገራችን ሕገ-መንግሥት ሲረቀቅና ሲጸድቅ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት የሥልጣን ዘመን በተመለከተ አንድ ስህተት ተሠርቷል፡፡ ሕገ-መንግሥቱ ሲረቀቅ የፕሬዝዳንቱ የሥልጣን ዘመን ከአገሪቱ የፓርላማ የሥራ ዘመን አንድ ዓመት በልጦ ስድስት ዓመት እንዲሆን የተደረገው በየአምስት ዓመቱ የመንግሥት ለውጥ ሲካሄድ ሊፈጠር የሚችለውን የሥልጣን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ ቢሆንም፣ ነገር ግን በየአምስት ዓመቱ አንድ ጊዜ ይህንን የተሰጋውን ክፍተት ለመሙላት የማያስችል ስህተት ተሠርቷል፡፡ ይኸውም ክፍተቱን በቋሚነት ለመሙላት መፍትሄ ይሆን የነበረው የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን ከፓርላማው የሥራ ዘመን እኩል አምስት አመት እንዲሆን ተደርጐ ፕሬዝዳንቱ የሚሾመው ግን ሁልጊዜ አዲስ ፓርላማ ከተቋቋመ ከአንድ ዓመት በኋላ ቢሆን ነበር፡፡ ይህ መሆን ሲገባው ያለአግባብ የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት እንዲሆን በመደረጉ በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ የፓርላማውና የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን በአንድ ጊዜ እኩል የሚያልቅበት ዕድል ይኖረዋል፡፡ የፕሬዝዳንቱ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት እንዲሆን የተደረገው ግን ይህ እንዳይሆን ታስቦ ነበር፡፡ ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው ሕገ-መንግሥት

በሰዎች የሚዘጋጅ ሰነድ እንደመሆኑ መጠን አግባብ ባለው ሁኔታ ለመታረምና ለመሻሻል የሚያስችል አሠራር ሊቀመጥለት የሚገባ ሰነድ መሆኑን ነው።

ስለዚህ የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት ሊሻሻል ይገባዋል ብለን የምናምን የፖለቲካ ኃይሎች ከምንም ነገር በላይ ትኩረት መስጠት የሚገባን ለሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 105 መሻሻል መሆን ይገባዋል። አንቀጽ 105 በቅድሚያ መሻሻል ባልቻለበት ሁኔታ ስለ አንቀጽ 39ም ሆነ ስለ ሌሎቹ ሕገ-መንግሥታዊ አንቀጾች መሻሻል ብንጮህ ዋጋ አይኖረውም። በአጠቃላይ የወቅቱን የአገራችንን ሕገ-መንግሥት በአግባቡ ስንመረምረው - የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት በአንቀጽ 39 አማካይነት በዓለም ላይ ከፍተኛው ለጋስ ሕገ-መንግሥት ሲሆን ፣ በአንቀጽ 105 አማካይነት ደግሞ በዓለም ላይ ከፍተኛው ንፉግና ግትር ሕገ-መንግሥት ሊባል የሚችል ነው።

ኢዮፓ

ኢዮፓ

## ምዕራፍ አምስት

## *የውጭ ጉዳያችን የትኩረት አቅጣጫ*

አገራችን ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን የመንግሥትነት ታሪክ ያላትን ያህል በዚያው መጠን የውጭ ግንኙነት ታሪኳም ረዥም ዕድሜ ያስቆጠረ ነው። ኢትዮጵያ በአክሱም ዘመን ቀይ ባህርን ተሻግራ የመንን ጭምር ትገዛ የነበረች አገር ስትሆን፣ በንግድም ሆነ በሃይማኖት ጉዳይ ከሮም፣ ከፋርስ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅም ሆነ ከሜዲትራንያን አካባቢ አገሮች ጋር የነበራት ግንኙነት ረዥም ዕድሜ ያስቆጠረ ነው። በቅርቡ የአገራችን ታሪክም በተለይም ከአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት የውስጥ ጉዳይን ጭምር በመወሰን ረገድ ወሳኝ ስፍራ የነበረው ነው። ከ20ኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮም በተለይም ከአድዋ ጦርነት በኋላ ኢትዮጵያ የቅኝ

ገዥዎች ጥቃት ሰለባ በመሆንም ሆነ በአካባቢዋ አንድ ጠንካራ የቅኝ ገዥዎች ተቀናቃኝ አገር በመሆን የተጫወተችው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ በዓለማችን በተከሰተው የቀዝቃዛው ጦርነትም ኢትዮጵያ በአንድ በኩል በአፍሪካ ቀንድ ስትራቴጂክ አቀማመጥ ያላት አገር በመሆንዋ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአካባቢው አገሮች ጋር የሚያሻኩቱ ከብሔራዊ ደኅንነትዋ ጋር የተያያዙ የተለያዩ ጥቅሞች ያሏት አገር በመሆንዋ ምክንያት በአካባቢው ጉልህ የዲፕሎማሲ ሚና ያላት አገር እንድትሆን አድርጓታል፡፡ በነፃነት ታሪኳ ምክንያት ኢትዮጵያ በአፍሪካውያን ዘንድ የተሰጣት የአርአያነት ቦታ የሠንደቅ ዓላማዋን ቀለማት ለሌሎች ከማውረስም በላይ አፍሪካን በአሕጉራዊ ድርጅት ዙሪያ ለማሰባሰብና በዚህም ምክንያት የኃያላን መንግሥታትን ትኩረት ለመሳብ አብቅቷታል፡፡ ወደፊትም ኢትዮጵያ ውስጣዊ ችግሯን በአግባቡ መያዝ ከቻለች በሁለንተናዊ መልኩ በአካባቢው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ የጐላ ሚና የምትጫወት አገር ሆና መቀጠልዋ የሚያጠራጥር አይሆንም፡፡

ከቀዝቃዛው ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ ማለትም በዘመነ ግሎባላይዜሽን አብዛኞዎቹ የዓለም አገራት የሚያራምዱት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተቀራራቢ ይዘት ያለው እየሆነ ቢመጣም ኢትዮጵያ ከአካባቢው አገሮች ጋር ባላት አንዳንድ የጥቅም ግጭቶች ምክንያት የዲፕሎማሲ ሁኔታዋ ውጣ ውረድ የበዛበት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በአገሪቱ የቆዬም ሆነ የቅርብ ታሪክ የተለያዩ የአገሪቱ የፖለቲካ መሪዎች ወይም ቡድኖች ሥልጣን ለመያዝ ሲሉ ከውጭ ኃይል ጋር የሚተባበሩበት አጋጣሚ የታዬ ቢሆንም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በውስጥ ጉዳዮቻቸው ያላቸውን የከፋ መከፋፈል ያህል በውጭ ጉዳይ ላይ ብዙውን ጊዜ የተከፋፈለ አቋም ሲያራምዱ አይታዩም፡፡

በአሁኑ ወቅትም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በውስጥ ጉዳዮቻቸው ከገደብ ያለፈ አለመግባባትና መናቆር የሚታይባቸው ቢሆኑም ከአንዳንድ ከውጭ ኃይሎች ጋር ተባብረን ለኢትዮጵያ የሚበጅ ለውጥ እናመጣለን የሚል ቅዠት ውስጥ ካሉ ፓርቲዎች በስተቀር አብዛኞዎቹ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች በውጭ ጉዳይ ላይ ይህንን ያህል የከፋ ልዩነት አላቸው ማለት አይቻልም፡፡ ልዩነቶች አሏቸው እንኳ ቢባል ጥቃቅን ከመሆናቸውም በላይ ሁሉም የመንግሥት ሥልጣን ሲይዙ ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለማራመድ እንደሚገደዱ እስከ አለንበት የኢህአዴግ ዘመን ድረስ በታሪክ ተደጋግሞ ታይቷል፡፡ ኢህአዴግ መንግሥት ከሆነ በኋላ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የልብ ወዳጆቹ ከነበሩት የውጭ ኃይሎች ጋር ጭምር በአገሪቱ ጉዳይ ለመጣላት እንደተገደደው ሁሉ ዛሬ ከሻዕቢያ ጋር ሲያብሩ የሚታዩት

ተቃዋሚዎችም ነገ የመንግሥት ሥልጣን ለመያዝ ቢበቁ እነሱም በተራቸው በውጭ ጉዳይ ላይ ከኢህአዴግ ተመሳሳይ አቋም ማራመዳቸው እንደማይቀር መገመት ይቻላል፡፡

ኢህአዴግ መንግሥት ከመሆኑ በፊትም ሆነ በኋላ የኢትዮጵያና የኤርትራን ግንኙነት በተመለከተ ያራመዳቸው ተደጋጋሚ ስህተቶች መኖራቸው ጉልቶ የሚታይ ቢሆንም ከአጠቃላይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አንጻር ግን ኢህአዴግ ከድክመቱ ይልቅ ጥንካሬው ያመዝናል ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን የአንድ አገር የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የውስጥ ሁኔታው ነጸብራቅ እንደመሆኑ መጠን ከውስጣዊ ድክመቶቻችን ጋር በተያያዘ በውጭ ጉዳያችንም የሚታዩ አንዳንድ ድክመቶች አሁንም አሉብን፡፡

### 5.1 በውጭ ግንኙነታችን ዙሪያ የሚታዩ መሠረታዊ ድክመቶች

የመጀመሪያው የውጭ ጉዳይ ድክመታችን የሚመነጨው ከልማዳዊ አስተሳሰባችን ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ብዙውን ጊዜ አገራችንን በጠላት የተከበበች ደሴት አድርገን ስለምንቆጥር (በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ቢኖረው) ሁልጊዜም የውጭ ኃይሎችን የስጋት ምንጭ አድርገን እናያለን፡፡ የውጭ ኃይሎችን የስጋት ምንጭ አድርገን እንድናይ ያደረጉን የተለያዩ ታሪካዊ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም ከውጭ ኃይሎች ጋር የሚያጋጩን የጥቅም ጉዳይ መሆኑን ዘንግተንና ያለአግባብ ለጥጠን ተፈጥሮአዊና መለኮታዊ ትርጉም ልንሰጠው እንሞክራለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ኩሩና አትንኩኝ ባይ ስለሆን ይህንን ኩራታችንን ለማጥፋት ሲሉ የውጭ ኃይሎች እንደማይተኙልን አድርገን የምናስብ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የአገራችን ከአንድ ሦስተኛ በላይ የሆነው ሕዝብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ መሆኑን ረስተን ኢትዮጵያ “የክርስቲያን ደሴት” ስለሆነች የውጭ ኃይሎች ሊያጠፏት እንደሚፈልጉ አድርገን እናስባለን፡፡

እንዲህ ዓይነት ተገቢ ያልሆነ አስተሳሰብ ይዘው ኢትዮጵያን ሊተናኮሏት የሚፈልጉ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ሊኖሩ ቢችሉም ሁሉም የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ እንዲህ ዓይነት የጠለቀ ጥላቻ አላቸው ብሎ ማሰብ ግን በራሱ ጤናማ የውጭ ግንኙነት እንዳይኖረን እንቅፋት የሚሆን ነው፡፡ የውጭ ኃይሎች ምንጊዜም ለኢትዮጵያ የማይተኙላት ጠላቶችዋ ናቸው ብለን በማሰባችን (Siege mentality) ምክንያት ከእነዚህ የውጭ ኃይሎች ጋር በመግባባትና በመተባበር ችግራችን ይፈታል ብለን ከማሰብ ይልቅ ከውጭ ኃይል ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ሁሉ በስጋትና በጥርጣሬ ዓይን ማየትን እንመርጣለን፡፡ ተገቢ ስጋትና ጥርጣሬ መኖሩ በራሱ የሚጠላ ነገር ባይሆንም መጠኑን ያለፈ ሲሆን ግን በውጭ ግንኙነታችን ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ መኖሩ አይቀርም፡፡ ምዕራባውያን ብዙውን ጊዜ ጥቅማችንን ወደፊት ይቀናቀናል

ብለው የሚሰጉት ወይም በጠላትነት የሚያዩት የውጭ ኃይል ሲኖር ራሳቸውን በተለያየ መንገድ አሥርጉ በማስገባት ቋንቋውንና ባህሉን፣ ድክመቱንና ጥንካሬውን ጠንቅቀው ማወቅን የሚመርጡ ሲሆን እኛ ግን ጠላት ነው ብለን ከምናምነው ኃይል ራስን በይፋ ማግለልና ማራቅ ጠቃሚ ስልት መስሎ ይታየናል፡፡

ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ከጐረቤት አገሮች ጋር አስተማማኝ መግባባት ላይ መድረስ ያልቻለችውና በንግድም ሆነ በመሰረተ-ልማት ትርጉም ያለው ትስሥር መፍጠር ሳትችል የቀረችው ከሌሎች ውጫዊ ምክንያቶች በተጨማሪ በራስዋም በኩል ጐረቤቶቼ ምን ጊዜም ለእኔ አይተኙልኝም የሚል ቋሚ ስጋትና ጥርጣሬ ውስጥ የምትገኝ አገር በመሆንዋ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ቋሚ ስጋትና ጥርጣሬ በፖሊሲ ደረጃ ተጽፎ የማይገኝ ቢሆንም እንደ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ የዚህ ዓይነቱ የቆዬ አስተሳሰብ ያጠላብን መሆኑ የሚካድ አይሆንም፡፡ ብዙውን ጊዜ በኩራት ለመናገር የምንፈልገው ጥቃት የማንወድ፣ የውጭ ወረራ ሲመጣብን በጋራ መዋጋት የምንችልና በዚህም ምክንያት የአገራችን ነፃነት እስከዛሬ አስከብረን ስለመኖራችን ነው እንጂ እስካሁን ድረስ ከጐረቤቶቻችን ጋር አስተማማኝ ወዳጅነትና ትስሥር መፍጠር አለመቻላችንን እንደድክመት ቆጥረን ስንናገረውና ስንቆጭበት አንደመጥም፡፡

እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ጐረቤቶቻችን ምን ያህል ታሪካዊ ጠላቶቻችን እንደሆኑ አክርሮ የሚናገረውን የአገር መሪ እንደ ጀግናና አገር ወዳድ፣ መልካም ጉርብትና እፈልጋለሁ ብሎ በመስጠትና በመቀበል መርህ መደራደር የሚፈልገውን መሪ ደግሞ እንደ አገርን የማይወድና ወኔ-ቢስ አድርገን የምናይበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙበት በውጭ ግንኙነት ቋሚ ጠላትም ሆነ ቋሚ ወዳጅ የሚባል አገር የለም፡፡ በአገሮች መካከል ለጠብም ሆነ ለፍቅር መነሻ የሚሆነው የአገር ጥቅም ጉዳይ እስከሆነ ድረስ የግጭትና የአለመግባባት ምንጭ የሆነውን የአገር ጥቅም ጉዳይ የሰላምና የትብብር ምንጭ እንዲሆን ማድረግ የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለዚህ ተገቢ ጥርጣሬና ስጋት መኖሩ ጠቃሚና የሚገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያውያን ከጐረቤቶቻችንም ሆነ ከሌላው የውጭ ዓለም በጋራ ጥቅም ተሳስረን በሰላምና በፍቅር አብረን መኖር እንደምንችል ጥልቀት ያለው እምነት ካልፈጠርን በስተቀር ሁልጊዜም አገራችን በጠላት የተከበበች ደሴት እንደሆነች አድርገን ማሰቡ የትም ሊያደርሰን አይችልም፡፡

ሁለተኛው ድክመታችን የሚመነጨው ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም የውስጥ ብሔራዊ መግባባት የሌለንና ከርስ በርስ ግጭትና ጦርነት የጸዳን ካለመሆናችን ጋር በተያያዘ ነው፡፡

የውስጥ አንድነት የሌለው አገር ለግጭትና ለብጥብጥ የተጋለጠ ከመሆኑ አንጻር በንግድ፣ በኢንቨስትመንትም ሆነ በቱሪዝም የውጭ ትኩረትን ለመሳብ የማይችል ከመሆኑ በተጨማሪ በማንኛውም መስክ ምንጊዜም ጠንካራና ጤናማ የውጭ ግንኙነት ሊኖረው አይችልም፡፡ በአንድ በኩል በውስጥ ጉዳዩ የተከፋፈለን አንድ አገር ሌሎች አገሮች ደካማ አድርገው ስለሚያዩት ከዚህ ዓይነቱ አገር ጋር ያላቸውን የጥቅም ግጭት በኃይል እንጂ በድርድርና በስምምነት ለመፍታት ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡ በመስጠትና በመቀበል መርህ የሚደረግ ድርድርና ስምምነት የራስን ብቻ ሳይሆን የጋራ ጥቅምን የሚያስከብር ስለሆነ ለአገሮች ብዙውን ጊዜ ሁለተኛ እንጂ የመጀመሪያ ምርጫ አይደለም፡፡ በርግጥም አገሮች ከግለኝነት ስሜት ወጥተው ለጋራ ጥቅም ራሳቸውን የሚያስገዙ ቢሆኑ ኖሮ እስካሁን በዓለማችን የታዩት አብዛኞዎቹ አውዳሚ ጦርነቶች ባልተከሰቱ ነበር፡፡

ስለዚህ አንድ አገር ውስጣዊ አንድነት የሌለው ሆኖ ሲገኝ ከዚያ አገር ጋር የጥቅም ግጭት ያላቸው አገሮች የጋራ ጥቅምን ከመሻት ይልቅ ባላንጣችን የሚሉት አገር ደካማና ጥቅሙን መጠዬቅ ወይም ማስከበር የማይችል ደካማ አገር ሆኖ እንዲቀጥል መፈለጋቸው የተለመደ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከዚሁ የአገራዊ መግባባት ማጣት ጋር በተያያዘ ለውጭ ኃይሎች ዓላማ መሳካት ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የውስጥ ኃይሎች ይፈጠራሉ፡፡ አገራዊ መግባባት በሌለባቸው አገሮች ከመንግሥት ሥልጣን ውጭ የሆኑ የፖለቲካ ኃይሎች ከምንም ነገር በላይ በአገራቸው የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ ስለሚፈልጉ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ" በሚል ተገቢ ያልሆነ አስተሳሰብ ከአገራቸው ጥቅም በተፃራሪ ከቆመ የውጭ ኃይል ጋር ሳይቀር የሚተባበሩበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ክስተት በሌሎች በርካታ የዓለም አገሮች ጭምር የተለመደ ቢሆንም ለዚህ ከአፍሪካ ቀንድ የተሻለ ምሳሌ አለ ማለት ግን አይቻልም፡፡ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች የሚባሉት - ኢትዮጵያ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ኬንያ እና ጂቡቲ አንዳቸው የሌላቸውን ተቃዋሚ ሲቻል በግልጽ፣ ሳይቻል በድብቅ በመርዳት በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባታቸው እስካሁን ድረስ ያልተቋረጠ ድርጊት ሆኖ ቀጥሏል፡፡ እነዚህ በድህነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ኩታ ገጠም አገሮች በመካከላቸው ያለውን ግንኙነት ከቅራኔና ከግጭት ምንጭነት ይልቅ ወደ ዘላቂ የትብብር ግንኙነት መቀዬር ተስኗቸው በንግድም ሆነ በመሠረተ ልማት ግንኙነት የቅርብ-ሩቅ ሆነው በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ አገሮች ከሁሉም በፊት ግንኙነታቸውን ሊያጠናክሩበት ከሚገባቸው ከንግድና ከኢንቨስትመንት አንጻር አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ካላቸው ቅርበት የበለጠ እያንዳንዳቸው

ከቻይናና ከዱባይ ጋር የበለጠ ቅርበት አላቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ ከአገር ጉብኝት አንጻር ብዙ ኢትዮጵያውያን ከኬንያ ይልቅ አሜሪካንን የሚጐበኙ ሲሆን፣ በዚያው መጠን ብዙ ኬንያውያን ከኢትዮጵያ የበለጠ አሜሪካን ይጐበኛሉ፡፡ የአፍሪካ ቀንድ ግንኙነት ከኢጋድ ምሥረታ በኂላ የተሻለ ግንኙነት እየታየበት ነው ሊባል ቢችልም አባል አገሮቹ ገና እርስ በርሳቸው በጥርጣሬና በስጋት ከመተያዬት ስላልወጡና የውስጥ ቅራኔአቸውንም መፍታት ስላልቻሉ ግንኙነታቸው የቱንም ያህል መሻሻል አልቻለም፡፡

አንድ አገር በዜጐቹ መካከል ብሔራዊ መግባባት ፈጥሮና ውስጣዊ አንድነቱን ጠብቆ ትኩረቱን ሙሉ በሙሉ በአገር ግንባታ ላይ ማዋል ካልቻለ ውስጣዊ ችግሩ በውጭ ግንኙነቱም ላይ መንፀባረቁ አይቀርም፡፡ ጠንካራ ብሔራዊ መግባባት በውስጡ የፈጠረ አገር እሱ ጐረቤቶቹን የሚያይበት ብቻ ሳይሆን ጐረቤቶቹም እሱን የሚያዩበት አመለካከት ስለሚቀየር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ዘላቂ የውጭ ግንኙነትና ትብብር ከጐረቤቶቹ ጋር ለመመሥረት የተሻለ ዕድል ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያም በውስጧ ጠንካራ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር እስካልቻለች ድረስ የውጭ ግንኙነትዋ ችግር ያለበት ሆና መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል፡፡

ሦስተኛው የአገራችን የውጭ ግንኙነት ድክመት የሚመነጨው ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን በበቂ ሁኔታ ማክበር ካለመቻላችን ጋር በተያያዘ ነው፡፡ በአገራችን ዴሞክራሲ መስፈኑና ሰብአዊ መብት መከበሩ ከጐረቤቶቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት በማሻሻል ረገድ የሚኖረው በጎ አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይም ከምዕራባውያኑ ጋር ያለንን ግንኙነት በመወሰን ረገድ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጉዳይ ከፍተኛ ድርሻ ያለው ነው፡፡ በአሁኑ የግሎባላይዜሽን ዘመን አገራችን በሁለንተናዊ መልኩ በሚኖራት የትብብርም ሆነ የርዳታ ጥያቄ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥያቄ ቋሚ ቅድመ-ሁኔታ ሆኖ መቀጠሉ አይቀርም፡፡ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት አለመከበር በራሱ በዜጐች መካከል ብሔራዊ መግባባት እንዳይኖር ምክንያት ስለሚሆን አገሪቱ በምዕራባውያኑ ዘንድ የሚኖራትን ገጽታ በማበላሸት ዘንድ የማይናቅ ድርሻ ያለው ነው፡፡ አገሪቱ ውስጥ በሚኖረው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ችግር ከፖለቲካ መድረኩ የተገለሉ ኃይሎች አንዱ የትግል ስልታቸው የአገሪቱን መንግሥት የውስጥ ገመና ለውጭ ኃይሎች ማጋለጥ ስለሚሆን ከዚህ አንጻር የመንግሥት ተቀናቃኞች ዋና መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት አለመከበር ነው፡፡ በአሁኑ የኢንፎርሜሽን ዘመን ምዕራባውያን በራሳቸውም መንገድ የአንድን አገር የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ሁኔታ የሚከታተሉበት በቂ መንገድ ስላላቸው በአንድ አገር የዲፕሎማሲ ጥረት ያለአግባብ ሊታለሉ የሚችሉበት ዕድል የጠበበ ነው፡፡

ምዕራባውያን በአንድ አገር አንገብጋቢና በሌላ ጉዳይ የማይተካ የራሳቸው ጥቅም ሲኖራቸው አምባገነናዊ ከሆነ ሥርዓትም ጋር ለመተባበር ወደ ኋላ የማይሉ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በቻሉት መጠን ግን የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጉዳይን የትብብራቸው ቅድመ-ሁኔታ በማድረግ በአገሮች ላይ ግፊትና ጫና መፍጠራቸው የማይቀር ነው፡፡ ግፊትና ጫናውን በመቀበልና ባለመቀበል ሂደት በሚፈጠረው ውጥረትም ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን በሚፈለገው መጠን ማክበር የተሣናቸው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች የውጭ ግንኙነታቸውም በዚያው መጠን የተረጋጋና ጤናማ መሆን ይሳነዋል፡፡ ኢትዮጵያ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት በአምንስቲ ኢንተርናሽናል፣ በሂውማን ራይትስ ዎች፣ በዓለም አቀፍ የጋዜጠኞች ማኅበርና በአሜሪካን ስቴት ዲፓርትመንት ሪፖርቶች በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ጥሰት ያለማቋረጥ ስትከሰስ መቆየትዋ በራሱ ውስጣዊ የፖለቲካ ችግሯን የማባባስና ገጽታዋን የማበላሸት እንደምታ ያለው ከመሆኑም በላይ ከምዕራባውያን አገሮች ልታገኝ ትችል የነበረውን የቱሪዝም፣ የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የብድርና የርዳታ ፍሰት በመቀነስ ረገድ የተጫዎተው አሉታዊ ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ወደፊትም የአገራችን የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ሁኔታ በሚገባው መጠን መሻሻል እስካልቻለ ድረስ የውጭ ግንኙነታችን በችግር የተሞላ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ይሆናል፡፡

ዞሮ ዞሮ እነዚህ ከዚህ በላይ ለመጥቀስ የተሞከሩት ከልማዳዊ አስተሳሰቦቻችን፣ ከብሔራዊ መግባባት ማጣታችንና ከዴሞክራሲና ከሰብአዊ መብት አለመከበር ጋር በተያያዘ ያሉብን ውስጣዊ ድክመቶች እስካልተፈቱ ድረስ የውጭ ግንኙነታችን መሠረታዊ በሆነ መልኩ ሊለወጥ የማይችል ቢሆንም አሁንም ሆነ ወደፊት የውጭ ግንኙነታችን በሁለንተናዊ መልኩ እንዲሻሻል የሚያስችል ጥረት ማድረግ የግድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እንደማንኛውም ጤናማ የውጭ ግንኙነት እንዲኖረው የሚፈልግ አገር የጋራ ጥቅምንና ብሔራዊ ደኅንነትን መሠረት ያደረገና ሰላምን፣ የልማት ዕድገትንና ዴሞክራሲን የሚያጠናክር ሆኖ መቃኘት ያለበት ቢሆንም ከአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር በዓለም አቀፍ፣ በአሕጉርና በአካባቢ ደረጃ የምናራምደው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በየደረጃው የተለያዩ የቅድሚያ የትኩረት አጣጫዎች ሊቀመጡለት የሚገባ ነው፡፡

### 5.2 የውጭ ግንኙነታችን የትኩረት አቅጣጫ በዓለም-አቀፍና በአሕጉር ደረጃ

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ልታራምደው የሚገባት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በዋናነት ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ትኩረት መስጠት የሚገባው ሲሆን ዋና ዓላማውም አገሪቱ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም፣ በብድር፣ በርዳታ፣ በቴክኒክ ድጋፍና በመሳሰሉት ጉዳዮች

ከውጭው ዓለም ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም በከፍተኛ መጠን ማሳደግ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ አገሪቱ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ባሳለፈችው ሂደት የአገኘችው ውጤት ብዙም አበረታች ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከውጭ ንግድና ከኢንቨስትመንት አንጻር የተወሰኑ አበረታች ለውጦች የታዩ ቢሆንም በዐሥራ ስምንት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ሊታይ ከሚገባው ለውጥ አንጻር ሲመዘን በመስኩ የታዬው ለውጥ እጅግ አዝጋሚ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንዲያውም ይህንን ያህል አዝጋሚ ለውጥ ማየት የተቻለበት አንዱ ምክንያት በንግድና በኢንቨስትመንት መስክ የሚደረግ ግንኙነት ብዙውን ጊዜ ከዴሞክራሲና ከሰብአዊ መብት ጋር የተያያዘ ቅድመ-ሁኔታ የማይቀርብበት በመሆኑ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር የተያያዘም ከአንዳንድ የኤዥያና የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ጋር የተሻለ ግንኙነት መኖሩ ከቅድመ-ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችለውን ችግር በተወሰነ ደረጃ ቀንሶታል ማለት ይቻላል፡፡ እንደ ቻይና ከመሳሰሉት አገሮች ጋር የሚደረገው ግንኙት በአንድ በኩል በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ስም የሚቀርብ ቅድመ-ሁኔታን ለማምለጥ የሚያስችል ነፃነት ለታዳጊ አገሮች የሚሰጥ ሲሆን በሌላ በኩል ግን የታዳጊ አገር መንግሥታት የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብትን ጉዳይ ችላ እንዲሉ የሚያደርግ ሁኔታ በመፍጠር አሉታዊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ የሆነ ሆኖ ለውጭ ንግድና ለኢንቨስትመንት ማደግ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ግብኣቶች አለመሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት በአገራችን አሁን ከሚገኝበት በተሻለ ደረጃ ተከብሮ ቢሆን ኖሮ በመስኩ የተሻለ ውጤት ሊመዘገብ ይችል ነበር፡፡

አገራችን በውስጧም ሆነ በአካባቢዋ አስተማማኝ ሰላም ሊሰፍንባት ባለመቻሉም የአገራችን የቱሪዝም ፍሰትም ብልጭ ድርግም ከማለት አልፎ ቋሚና ከፍተኛ የሚባል ዕድገት ማሳየት አልቻለም፡፡ አገራችን ከሌሎች የአካባቢው አገሮች ጋር ሲነጻጸር የተሻለና የተለያዬ ምርጫ የሚሰጥ የቱሪዝም መስህብ ያላት አገር ብትሆንም በዋናነት በመሰረተ ልማት ውስንነት፣ በሰላም እጦትና ራስን በአግባቡ ማስተዋወቅ ባለመቻል ምክንያት አገራችን በቱሪዝም ውጤታማነት ከእነ ኬንያና ታንዛኒያ በእጅጉ ወደ ኂላ የቀረች ሆናለች፡፡ ቱሪዝም የአገራችንን የአገልግሎት ዘርፍ በማነቃቃትና የውጭ ምንዛሪ ግኝታችንን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት የሚገባው ቢሆንም በመስኩ ያለንን እምቅ አቅም እስካሁን በአግባቡ ልንጠቀምበት አልቻልንም፡፡ ከእኛ ያነሰ የቱሪዝም መስህብ ያላት ኬንያ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታገኘው ከቱሪዝም ሲሆን በዓመት በአማካይ ከ800 ሚሊየን ዶላር ያላነሰ ገንዘብ ታገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ ግን በቱሪዝም መስኩ አማካይነት የምታገኘው ገቢ ከኬንያ ከሦስት እጥፍ ያነሰ ማለትም 280 ሚሊየን ዶላር አካባቢ ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ሌላ ክፍል ለመግለፅ እንደተሞከረው አሁን ከምንገኝበት የድህነት ደረጃና ከውጭ ምንዛሪ ከፍተኛ ፍላጐታችን አንጻር የውጭ ርዳታና ብድር የግድ የሚያስፈልገን ቢሆንም በዚህ ረገድም አገሪቱ መጠቀም የሚገባትን ያህል እየተጠቀመች ነው ማለት አይቻልም፡፡ ቀደም ካሉ ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በመጠንም ሆነ በዓይነት ከውጭ የምናገኘው ርዳታና ብድር ከፍተኛ እድገት የታዬበት ቢሆንም እያገኘነው ያለነው ርዳታና ብድር ሁልጊዜ በብዙ ውጣ ውረድ የሚገኝና ቀጣይነቱም በቋፍ ላይ ያለ ነው፡፡ አገሪቱ እያገኘችው ያለው ርዳታና ብድር ከአገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት ጋር ተያይዞ ብዙውን ጊዜ “ታገደ-ተለቀቀ” በሚል ውዝግብ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ አስተማማኝ በሆነ የልማት ዕቅድ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡

ከመጠን አንጻርም ሲታይ በቀድሞዎቹ ሥርዓቶች ይገኝ ከነበረው የተሻለ ነው ሊባል ቢችልም ሌሎች አገሮች ከሚያገኙት የርዳታ መጠን አንጻር ሲመዘን ግን በጣም ትንሽ የሚባል ሲሆን፣ አገሪቱ ከምታገኘው የርዳታ መጠንም ውስጥ የዕለት ደራሽ ከሆነው ሰብአዊ ርዳታ ውጭ የሆነው የልማት ርዳታ ከ10% በታች ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት አገሪቱን በተሻለ ሁኔታ እየጠቀማት የሚገኘውና ከአገሪቱ በጀት 1/3ኛ የሚሆነውን መጠን የሚሸፍነው ርዳታ በዓለም ባንክ በኩል የሚገኘው የበጀት ድጐማ /PBS/ ሲሆን እሱም አንድ የፖለቲካ መሪ ወይም ጋዜጠኛ ታሰረ በተባለ ቁጥር ለድርድር የሚቀርብ ነው፡፡ ከአውሮፓ ኅብረትም ሆነ ከዓለም ባንክ አቅጣጫ የሚመጣው ርዳታ ጨክኖ የቆመበት ሁኔታ እስካሁን ባይኖርም አገሪቱ ውስጥ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ጉዳይ ላይ አንድ አወዛጋቢ ክስተት በተፈጠረ ቁጥር ጥያቄ ውስጥ የሚገባና አብዛኛውን ጊዜ በብዙ ልመናና ደጅ ጥናት የሚገኝ ነው፡፡

በአጠቃላይ አገሪቱ በእንዲህ ዓይነት አስቸጋሪና በቋፍ ላይ የሚገኝ ሁኔታ ውስጥም ሆና የማይናቅ መጠን ያለው ርዳታና ብድር እያገኘች ቢሆንም አገሪቱ ከውጭ ግንኙነት አንጻር በምዕራባዊያኑ ተመራጭ የሚያደርጋት ሌላ የአካባቢ ጉዳይ ባይኖር ኖሮ ይህንንም ያህል ርዳታና ብድር ባላገኘች ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ከምትገኝበት አካባቢያዊ ስትራቴጂና በተለይም በአሁኑ ወቅት የዓለም ስጋት የሆነውን ሽብርተኝነት ከመዋጋት አንጻር ምዕራባውያኑ የግድ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲቀጥል ስለሚፈልጉ እንጂ ኢትዮጵያ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ጥሰት እንደሚደርስባት ተደጋጋሚ ክስ ቢሆን ኖሮ እስካሁን አብዛኛው የርዳታና የብድር ምንጯ በደረቀ ነበር፡፡ ሽብርተኝነትን መዋጋት ለኢትዮጵያ ከማንም በላይ የራስዋ አጀንዳ ቢሆንም ይህንን ሁኔታ የኢህአዴግ መንግሥት ለአገሪቱም ሆነ ለራሱ ድርጅታዊ ጥቅምም የሚጫወትበት አንድ ጥሩ ካርታ መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡ ከቻይና ጋር የሞቀ  ወዳጅነት መፍጠርም ሌላው ምዕራባውያንን ለማስፈራራት ኢህአዴግ የሚጠቀምበት የመጫወቻ ካርታ ሲሆን ይህም በራሱ

ምዕራባውያኑ ሳያምኑበትም ቢሆን የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ሆነው እንዲቀጥሉ አስገዳጅ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ጊዜያዊ አጀንዳ በአንድ ወቅት ጊዜ ሊያልፍበትና ለድብብቆሽ ጨዋታ የማይጠቅምበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ከምዕራባውያኑ ጋር የሚኖረንን ግንኙነት የተሻለና ዘላቂ ለማድረግ የሚያዋጣው ለአገራችን በሚበጅ መጠንና ሁኔታ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት አያያዝን ማሻሻል ነው፡፡ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን በአገራችን እንዲከበር ማድረግ የሚገባን የውጭ ኃይሎችን ለማስደሰትና በእነሱም እጃችን ተጠምዝዘን ባይሆንም ዞሮ ዞሮ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት መከበር ከማንም በላይ ራሳችንን የሚጠቅመን እስከሆነ ድረስ እግረ መንገዱን የውጭ ርዳታና ብድር ለማግኘት ቢጠቅመን የሚጠላ አይሆንም፡፡ ኢህአዴግ ለምዕራባውያን ግፊት “ተንበርካኪ” በመሆን የማይታማና ይህም አንዱ ጠንካራ ጐኑ የሆነ ድርጅት ቢሆንም፣ አርቆ አሳቢ በሆነ ስልት አገሪቱ ከውጭ ኃይሎች ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም በአግባቡ እንድታገኝ በማድረግ ረገድ ግን ቀላል የማይባል ድክመት እንዳለበት በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡

አንድ የቅርብ ጊዜ ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ ከአንድና ከሁለት የማይበልጡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በምርጫ 97 ወቅት በወሰዱት አቋም በመደናገጥና ቂም በመያዝ ብቻ ሁሉንም የረድኤት ድርጅቶች የሚያስከፋ አዲስ ሕግ በማውጣት ኢህአዴግ ምን ያህል ለራሱ ድርጅታዊ ደኅንነት ሲል የአገርን ደኅንነት የሚጐዳ ርምጃ ለመውሰድም ቢሆን ወደኋላ እንደማይል አሳይቷል፡፡ ይህ የኢህአዴግ የእልህ ርምጃም የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በተወሰነ ደረጃ በማባባስ ረገድ አገሪቱን የማይናቅ ዋጋ አስከፍሏል፡፡

ሌላው አገሪቱ ከዓለም አቀፍ ግንኙት አንጻር ደካማ አቋም እንዲኖራት አድርጓት የቆዬው ጉዳይ የአገሪቱ ዲፕሎማቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውንና ትኩረታቸውን ከኢኮኖሚ ይልቅ ለፖለቲካ ዲፕሎማሲ ሥራ የሚያጠፉ መሆናቸው ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጎ ለውጦች እየታዩ መሆኑን መካድ ባይቻልም ለረዥም ጊዜ ግን አብዛኛዎቹ በውጭ አገር የሚገኙ የቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ወይም የኢህአዴግ ፅሕፈት ቤቶች መሆናቸውን ለይቶ ለማወቅ በሚያስቸግር ደረጃ በድርጅታዊ የፖለቲካ ሥራ ተጠምደው የሚውሉ ነበሩ፡፡ በየውጭ አገራቱ የሚገኙ የአገሪቱ ዲፕሎማቶች ለአገሪቱ ከውጭ መንግሥታት በቂ ርዳታና ብድር ማስገኘት ወይም ንግድና ኢንቨስትመንትን መሳብ ይቅርና ቢያንስ በውጭ አገር ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በአግባቡ ስለ አገራቸው በቂ መረጃና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ የቻሉ አልነበሩም፡፡ ብዙዎቹ ዲፕሎማቶች በአገራዊ ኃላፊነታቸው ከማተኮር ይልቅ ብዙውን ጊዜ

በየአገራቱ የሚገኙ የኢህአዴግ ተቃዋሚዎችና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚያወጡትን መግለጫ በማስተባበል ሥራ ላይ ማተኮርን ይመርጡ ስለነበር ለአገሪቱ የሚጠቅም በቂ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ማካሄድ አልቻሉም፡፡ ይህ የአገሪቱ ዲፕሎማቶች ድክመት ከአገሪቱ የሚሊኒየም ክብረ በዓል ዋዜማ ጀምሮ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ከኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አንጻር ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች አገሮችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስለ ኢትዮጵያ በጎ አመለካከት እንዲኖራቸው ከማድረግ በተጨማሪ ራሳቸውን ከፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ በማድረግ በውጭ አገር ኗሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ከፖለቲካ ልዩነታቸው ባሻገር አገራቸውን በዕውቀታቸውና በገንዘባቸው የማልማት ድርሻ እንዲኖራቸው ማሳመን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በውጭ አገር ነዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ዙሪያ የሚታየው የከረረ የፖለቲካ ሁኔታ በዋናነት ሊለዝብ የሚችለው ከአገሪቱ የውስጥ ሁኔታ መስተካከል ጋር ተያይዞ ቢሆንም የአገሪቱ ዲፕሎማቶች ከልባቸው የአገር ወገንተኝነት ይዘው ቢሠሩ ቢያንስ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የአገሩንና የኢህአዴግን ጥቅም ለያይቶ በማየት ኢህአዴግን ለመጉዳት ብሎ አገሩን የሚጐዳ ተግባር ከመፈጸም እንዲቆጠብ ማድረግ ይቻላል፡፡ በርግጥ በቁጥር ቀላል የማይባሉ በውጭ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሠራተኞች የሥራ ጊዜያቸውን ሲጨርሱ የአገራቸውን መንግሥት አውግዘው የውጭ ጥገኝነት ጠይቀው የሚቀሩ መሆናቸው ሲታይ ቀድሞውንም እነዚህ ሰዎች የአገርን አደራ ለመሸከም የሚያስችል የሞራል ብቃት የሌላቸው እንደነበሩ ያሳያል፡፡

በውጭ አገር ኗሪ የሆኑ ዜጐቻችን በኢትዮጵያ የሚጠበቅባቸውን ፖሊቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ሚና በአግባቡ እንዲጫወቱ ከተፈለገም በመንግሥት ሊደረግላቸው ከሚገባ ልዩ ልዩ ማበረታቻ በተጨማሪ ከዜግነት ጋር በተያያዘ ያለባቸው የሕግ ችግርም ሊፈታ ይገባዋል፡፡ ለትውልደ ኢትዮጵያዊያን ቢጫ ካርድ በመስጠት በኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው መደረጉ አንድ በጎ ጅምር ቢሆንም የተሟላ የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ የሚያስችል መፍትሄ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው ነገር ግን በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱ ዜጐቻችን ፍላጐቱ እስካላቸው ድረስ ጥምር ዜግነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሕግ እንዲኖር ቢደረግ ለአገራችን የማይናቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በአሕጉር ደረጃ ኢትዮጵያ ልትከተለው የሚገባት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በብዙ ጉዳዮች በአገር አቀፍ ደረጃ ሊካሄድ ከሚገባው ፖሊሲ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም በአሕጉር ደረጃ የበለጠም ሆነ ያነሰ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊገኝ የሚችለው የኢኮኖሚ ጥቅም በተመሳሳይ መጠን በአፍሪካ ስለማይገኝ አሕጉራዊ የዲፕሎማሲ ትኩረታችን ከኢኮኖሚ ይልቅ ወደ ፖለቲካ ዲፕሎማሲ ሊያዘነብል ይችላል፡፡ ወደፊት ከሩቅ ግብ አንጻር የበለጠ የኢኮኖሚ ትስሥር የሚያስፈልገን ከአፍሪካ አገሮች ጋር መሆኑ የማይቀር ቢሆንም አሁን ሁሉም ድሀ በሆነበት ሁኔታ መሠረት ለመጣል ከመሥራት ያለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊገኝ የሚችለውን የኢኮኖሚ ጥቅም በቀላሉ ሊተካ የሚችል ሁኔታ በአፍሪካ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ስለዚህ ከኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ አንጻር ሊደረግ የሚገባውን ጥረት በአግባቡ ማከናወን ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢትዮጵያ በአሕጉር ደረጃ ያላትን ተደማጭነት የበለጠ የሚያጠናክር የፖለቲካ ዲፕሎማሲ መሥራት ይጠበቅባታል፡፡

ኢትዮጵያ ከመጀመሪያው ጀምሮ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምሥረታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተችና አሁንም የአፍሪካ ኅብረት ለደረሰበት የተሻለ ደረጃ ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ እያበረከተች የምትገኝ አገር እንደመሆንዋ መጠን በአሕጉሩ ውስጥ ግጭትን ለማስወገድ በሚደረጉ ጥረቶችና በሰላም አስከባሪ ኃይልነት ያላትን ተሳትፎ የበለጠ አጠናክራ መቀጠል ይጠበቅባታል፡፡ በኔፓድ አማካይነት በአፍሪካ መልካም አስተዳደርን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እየተደረገ ያለውን ጥረት በማጠናከር ረገድም ኢትዮጵያ እያሳየች ያለውን ተነሳሽነት የበለጠ አጠናክራ መቀጠል ይጠበቅባታል፡፡

ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና እንድትቀጥል የሚያስችላት የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ የመሆንዋ እውነታ በመሆኑ በዚህ ረገድ ወደፊት ጥያቄ ሊነሣበት በማይችል ደረጃ የአፍሪካ ኅብረት መዲናነትዋን በዘላቂነት የሚያረጋግጥ ተግባር ማከናወን ይጠበቅባታል፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ኅብረት ቋሚ መዲና ሆና መቀጠልዋ በአሕጉር ደረጃ ብቻ ሳይሆን እግረ መንገዱን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚኖራትን የዲፕሎማሲ ተሰሚነት የሚያጠናክር ጥቅም ያለው በመሆኑ ምንጊዜም ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊጠናከር የሚገባው ቁም ነገር ነው፡፡ አዲስ አበባ የአፍሪካውያን የርስ በርስ መገናኛ ብቻ ሳትሆን ሌላውም ዓለም ከአፍሪካ ጋር የሚገናኝባት መዲና መሆንዋ የበለጠ እየተጠናከረ ሲመጣ የቱሪዝም አቅሟም በዚያው መጠን እየሰፋና እየተጠናከረ ስለሚመጣ የአፍሪካ ኅብረት መዲናነትዋ ከኢኮኖሚ ጥቅምም አኳያ የማይናቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት መዲና መሆንዋ ከውጭ ግንኙት አንጻር የሚኖረው ከፍተኛ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ ውስጣዊ ሰላሟንና ዴሞክራሲዋን በማጠናከር ረገድም የራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከመሠረተ ልማት ግንባታ አንጻር ብቻ ሳይሆን በሰላምና በዴሞክራሲ ረገድም መጥፎ ገጽታ ይዛ የአፍሪካ የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆና በቋሚነት

ልትቀጥል ስለማትችል ይህ የአፍሪካ ኅብረት መዲና ሆና የመቀጠል ፍላጐትዋ ለሰላምና ለዴሞክራሲ መኖር ጠንክራ እንድትሰራ የራሱን በጎ ጫና ሊያሳድር ይችላል፡፡

በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካ የርስ በርስ የመገማገሚያ መድረክ /APRM/ ራሳቸውን በቀዳሚነት ለመገምገም ፈቃደኛ ከሆኑ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ለመሆን መብቃትዋም ከዚሁ ገጽታዋን ለመገንባት ካደረባት በጎ ፍላጐት ጋር የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ ከብሔራዊ ጥቅሟ ጋር በተያያዘ የዲፕሎማሲ ዘመቻ ማድረግ ሲያስፈልጋትም በየአገሩ ብዙ መዞር ሳያስፈልጋት ብዙ የዓለም ዲፕሎማቶችን በአገሯ ውስጥ ለማግኘት ያላት ዕድልም ከዚሁ የአፍሪካ ኅብረት መዲና ከመሆኗ ጋር የተያያዘ በመሆኑ አዲስ አበባ የአፍሪካ ቋሚ የዲፕሎማሲ መዲና ሆና የመቀጠሏ ጉዳይ በማንኛውም ወቅት በአሕጉር ደረጃ ከሚኖረን የውጭ ግንኙነት አንጻር ቀዳሚ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ ከዚህ አሕጉራዊ ዲፕሎማሲ አንጻር መንግሥት በአሁኑ ወቅት እየሠራው የሚገኘው አበረታች ሥራ የበለጠ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

### *5.3 የውጭ ግንኙነታችን የትኩረት አቅጣጫ በአፍሪካ ቀንድ ደረጃ*

በዓለም አቀፍና በአሕጉር ደረጃ ኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ጥረትን አጠናክራ መቀጠልዋ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሁሉም በላይ ግን የበለጠ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት የሚጠበቅባት በአፍሪካ ቀንድ ማለትም ኩታ ገጠም ከሆኑት  የቅርብ ጐረቤቶችዋ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም በዓለም አቀፍና በአሕጉር ደረጃ ኢትዮጵያ የሚኖራት የውጭ ግንኙነት የቱንም ያህል ችግርና ጉድለት ቢኖርበት የበለጠ ገጽታዋ ሊበላሽና የውጭ ኢንቨስትመንትና ዕርዳታ ልታጣ ትችላለች እንጂ እንደ አገር ህልውናዋን ጠብቃ መቀጠልዋ አይቀርም፡፡ ከጐረቤት አገሮች ጋር ያላት ግንኙነት ግን በዋናነት ከሰላሟና ከአጠቃላይ ብሔራዊ ደኅንነትዋ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ስለሆነ በዚህ ደረጃ የሚከሰት የውጭ ግንኙነት ድክመትና ስህተት አገራዊ ህልውናዋን ጭምር አደጋ ውስጥ የሚከት ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህ አገሪቱ በዓለም አቀፍና በአሕጉር ደረጃ የምታካሂደው የውጭ ግንኙነት የራሱ የማይተካ ፋይዳ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ይህ ዓለም አቀፋዊና አሕጉራዊ ግንኙነትዋ ኢትዮጵያ ከጐረቤት አገሮች ጋር ባላት ግንኙነት የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያግዛት ሊሆን ይገባዋል፡፡

ዞሮ ዞሮ አንድ አገር ቀጥተኛ የጥቅም ተጋሪዎች የሚኖሩት በአካባቢው ከመሆኑም በላይ በዓለም አቀፍም ሆነ በአሕጉር ደረጃ የሚኖረው ተቀባይነትም ከጐረቤቶቹ ጋር ባለው ተነፃፃሪ ጥቅም የሚመዘን ስለሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በአካባቢው የሚኖረው የዲፕሎማሲ የበላይነት

በየደረጃው ለሚገኙ ሌሎች ግንኙነቶች ዋና መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ነው ማለት ይቻላል፡፡ በአፍሪካ ደረጃ የሚገኝ የአካባቢ ዲፕሎማሲ ከአጭር ጊዜ ግብ አንጻር በዋናነት ከሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ከሩቅ ጊዜ ግብ አንጻር ግን ዘላቂ የኢኮኖሚ ጥቅምም ሊገኝ የሚችለው ከጐረቤት አገሮች ጋር በሚኖር የተጠናከረ ግንኙነት ስለሆነ የአካባቢ ዲፕሎማሲ ከሁሉም በላይ ልዩ ትኩረትና ጥረትን የሚጠይቅ ነው፡፡

በተለይም አገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት አካባቢያዊ ሁኔታ በብዙ ጥቅሞችና ቅራኔዎች የተወሳሰበ በመሆኑ በዚያው መጠን ውስብስብ የዲፕሎማሲ ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከሁሉም ጐረቤቶቿ በተለየ ብቸኛ የባህር በር የሌላት አገር መሆንዋ፣ ከሁሉም ጐረቤቶቿ ጋር ያልተቋጨ የድንበር ውዝግብ ያላት አገር መሆንዋ፣ ከአብዛኛዎቹ ጐረቤቶቿ ጋር ድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የምትጋራ መሆንዋ፣ ራስዋን ጨምሮ ሁሉም ጐረቤቶቿ አስተማማኝ የፖለቲካ መረጋጋትና ዴሞክራሲ ያልሰፈነባቸው መሆናቸው፣ ከሁሉም ጐረቤቶችዋ ጋር ተመሳሳይ ቋንቋና ባህል የሚጋራ ሕዝብ ያላት መሆንዋ፣ ከሁሉም ጐረቤቶቿ ጋር የስደተኞች ዝውውር ያለባት አገር መሆንዋ፣ አንዳንዶቹ ጐረቤቶቿም የሽብርተኝነት አደጋ የሚታይባቸው መሆናቸው፣ ከሁለት ጐረቤቶቿ ጋር በቋፍ የሚገኝ የጦርነት ፍጥጫ ላይ የምትገኝ መሆንዋና በሌሎችም ተጨማሪ ምክንያቶች ኢትዮጵያ በአካባቢዋ ያለው የውጭ ግንኙነት በፈርጀ ብዙና ውስብስብ ችግር የተሞላ እንዲሆን አድርጐታል፡፡ ከዚህ ለመረዳት የምንችለው ኢትዮጵያ በአካባቢው አስተማማኝ ሰላም አግኝታ ወደ ዘላቂ የኢኮኖሚ ብልፅግና ለመሸጋገር የወቅቱም ሆነ የወደፊቱ የአገሪቱ መንግሥታት ምን ያህል ዕረፍት የሚነሣ አታካች ኃላፊነት የሚጠብቃቸው መሆኑን ነው፡፡

በታሪካችን ተደጋግሞ እንደታየው በየጊዜው በአገሪቱ የፖለቲካ ሥልጣን ላይ የተፈራረቁ ኃይሎች ተመሳሳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለማራመድ የሚገደዱትም ያለ ምክንያት ሳይሆን ከዚሁ የአካባቢው ሁኔታ ውስብስብና አስቸጋሪ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ጐረቤቶቻችን አብዛኛውን ጊዜ በአገራችን ለሚገኙ የአማፂ ኃይሎች  ወዳጂ፣ ለመንግሥታቶቻችን ግን ጠላት ሲሆኑ የምናያቸው ያለ ምክንያት ሳይሆን የአካባቢው ሁኔታ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለጐረቤቶቻችንም ጭምር ውስብስብና አስቸጋሪ ስለሆነባቸው ነው፡፡ ይህንን እውነታ አምነን ሳንቀበል ሁልጊዜም ራሳችንን በጠላት እንደተከበበ ደሴት አድርገን ብንቆጥር የአለንበት ችግር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ከማድረግ ባለፈ መፍትሄ ሊሆነን አይችልም፡፡ ስለዚህ በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአካባቢው ያለን የውጭ ግንኙነት የጋራ ጥቅምንና መግባባትን መሠረት ወደ አደረገ ጤናማ ግንኙነት እንዲለወጥ ከፈለግን ከውጭ ግንኙነት

አንጻር ያለንን ልማዳዊ አስተሳሰብ መቀዬር፣ በውስጣችን የተሻለ ብሔራዊ መግባባት መፍጠር፣ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን በተሻለ ሁኔታ ማስፈን የግድ ያስፈልገናል፡፡ ነገር ግን እነዚህ መሠረታዊ ቅድመ-ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር የውጭ ግንኙነታችንን ወደ ተሻለ ሁኔታ ለመለወጥ የምናደርገው ጥረት ይቁም ሊባል ስለማይችል ባለንበት ሁኔታም ውስጥ ሆነን በርካታ ቁምነገሮችን ለማከናወን እንችላለን፡፡

ከጎረቤት አገሮች ጋር ባለን ግንኙነት ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሰጥተን ልንፈታው የሚገባን ጉዳይ ከድንበር ማካለል ጋር በተያያዘ ያለብንን ውዝግብ ነው፡፡ ከእያንዳንዱ ጎረቤት አገር ጋር በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት በአግባቡ የተከለለና ገደቡ የታወቀ ድንበር እስካልተፈጠረ ድረስ ከየአገራቱ ጋር በሚፈጠር ማናቸውም አለመግባባት የድንበር ጉዳይ የግጭት ምንጭ ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለብን ችግር እስካሁን በአግባቡ መፈታት ሳይችል የቀረው በአንድ በኩል ለጉዳዩ ተገቢ ትኩረት ካለመስጠትና ከየአገራቱ ጋር በግልጽ ተነጋግሮ በመስጠትና በመቀበል መርህ ችግሩን በዘላቂነት የመፍታት ፍላጎት ከማጣት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድንበሩን በቋሚነት ለማካለል በሚደረገው ጥረት ነባራዊ ሁኔታው ተለውጦ ያልተጠበቀ ግጭት እንዳያጭር በመስጋትም ጭምር ነው፡፡ በተለይም አብዛኛው በድንበር አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ አርብቶ አደርና ድንበር ዘለል የሆነ እንቅስቃሴ የሚያደርግ በመሆኑ ምክንያት የድንበር ማካለልን ጉዳይ ውስብስብና አስቸጋሪ አድርጎት ቆይቷል፡፡

የድንበር ጉዳይ ውስብስብና አስቸጋሪ መሆኑ ዛሬም ሆነ ወደፊት እንደሚቀጥል ግልጽ ቢሆንም ችግሩን ለመጭው ትውልድ እያንከባለሉ ከማስተላለፍ ይልቅ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከፍሎ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲፈታ ማድረጉ የተሻለ አማራጭ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከኢትዮጵያ አንጻር ችግሩ እንዳይፈታ ተጨማሪ ምክንያት እየሆነ ያለው ስለ አገር ዳር ድንበር ጉዳይ ያለን ልማዳዊ አስተሳሰብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያውያን ስለ አገራችን "የራሷን የማትሰጥ - የሰው የማትፈልግ" የሚል በአባባል ደረጃ ምክንያታዊና ተወዳጅ የሆነ መፈክር ያለን ቢሆንም በተግባር ሲታይ ግን ማናቸውም ዓይነት የድንበር ማካለል ውሳኔን በቀላሉ ለመቀበል ዝግጁ ሆነን አንታይም፡፡ በዚህ ረገድ ያለብን ችግር ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በኢህአዴግ ዘመን ይበልጥ ብሶበታል ሊባል ይችላል፡፡

በአንድ በኩል ኢህአዴግ የኤርትራን መገንጠል አስመልክቶ ካራመደው አቋም ጋር ተያይዞ በብዙ ሕዝብ ዘንድ ለአገር አንድነትና ለዳር ድንበር ጉዳይ ግዴለሽ ተደርጎ በመታየቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢህአዴግም በሂደት ያለ ዓመሉ የእወደድ ባይነት ፖለቲካ ሰለባ እየሆነ በመምጣቱ ምክንያት የድንበር ውዝግብን ጉዳይ በድፍረት ለመፍታት የሚችልበት ዕድል የበለጠ

የጠበበ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከሱዳን ጋር ያለንን የድንበር ውዝግብ ለመፍታት ሲሞከር በአንድ በኩል ተገቢ ከሆነ ምክንያታዊ ስጋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሥርዓቱን በጭፍን ለማጥላላት ከሚመነጭ ፍላጐት “መሬታችንን ለሱዳን ሸጡት” የሚለው ከዋሽንግተን ዲስ ተነሥቶ ኢትዮጵያን የሚያጥለቀልቀው የወሬ ማዕበል አስቸጋሪ እንቅፋት እየሆነ ሲሆን፣ ከኤርትራ ጋር ያለው የድንበር ውዝግብም በትግራይ ሕዝብ ልዩ ክትትል የሚደረግበት በመሆኑና ህወኀት ውስጥ ልዩነት ሊፈጥር የሚችል አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት ውጤቱ አገርን የሚጐዳም ይሁን የሚጠቅም በወቅቱ የአገራችን መሪዎች በቀላሉ የሚደፈር ሆኖ አልተገኘም፡፡

ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብም ሆነ እንደ መንግሥት በዚህ ዓይነቱ ጨዋታ ከቀጠልንበት ከጐረቤቶቻችን ጋር ባለን ግንኙነት እንደተለመደው የዛፍ ላይ እንቅልፍ እንጂ የተረጋጋ ሕይወት ልናገኝ አንችልም፡፡ ይልቁንም የተሻለ የሚሆነው አገራችን በርግጥም የራሷን የማትሰጥ የሰው የማትፈልግ መሆኗን ከአንገት ሳይሆን ከልብ በማመን ጥቅማችንን በአግባቡ ሊያስጠብቅ በሚያስችል መጠን በመቀበልና በመስጠት መርህ ተገዥ በመሆን ከጐረቤቶቻችን ጋር ያለንን የድንበር ውዝግብ በድፍረት መፍታት እንጂ እዳን ለመጭው ትውልድ አለባብሶ ማስተላለፍ ከማንም ኃላፊነት ይሰማኛል ከሚል መንግሥትም ሆነ ትውልድ የሚጠበቅ ተግባር አይሆንም፡፡ ሕዝቡና መንግሥት በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸውን የየድርሻ ኃላፊነት መወጣት መቻላቸው የማይተካ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገሪቱ የምንገኝ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ድንበርን ለማካለል በመንግሥት የሚደረግን ሙከራ ሁሉ ከአገራችን ጥቅም መከበር አኳያ የሚኖረውን እንደምታ በውል ባልተገነዘብንበትም ሁኔታ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጥቅም ለማዋል መሞከር ለአገር ብቻ ሳይሆን ከራስ ድርጅታዊ ጥቅምም አኳያ የማያዋጣ ስልት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡

ተቃዋሚዎች አገሪቱ ከየጐረቤቶቹዋ ጋር ያላት የድንበር ውዝግብ ዛሬ ሳይፈታ ቀርቶ እኛም ነገ ለመንግሥትነት ሥልጣን ብንበቃ እንደ ኢህአዴግ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተን ከመቸገር ይልቅ፣ ችግሩን ኢህአዴግ በአግባቡና የአገሪቱን ጥቅም ባስጠበቀ ሁኔታ ፈቶት እንዲያልፍ እኛም በጐ ግፊት ብናደርግ የበለጠ የብልህነት ስልት ይሆናል፡፡ ኢህአዴግም ያለ ዓመሉ የእወደድ ባይነት ፖለቲካ ሰለባ ሆኖ የአገሪቱን የድንበር ውዝግቦች አድበስብሶ በማለፍ ለመጭው ትውልድ ዕዳ ከማውረስ ይልቅ የአገራችንን ጥቅም በአግባቡ ለማስጠበቅ በሚያስችል መጠን በመስጠትና በመቀበል መርህ ችግሩን በድፍረት ፈቶት ቢያልፍ በዚህ ረገድ የአገሪቱ የታሪክ ባለውለታ ለመሆን ሊበቃ ይችላል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያለውን የድንበር ፍጥጫ ከልማዳዊ አስተሳሰብና ከእወደድ ባይነት ፖለቲካ በፀዳ አመለካከት ልንፈታው የማንችል ከሆነ የባድመ አካባቢ የኢትዮጵያና የኤርትራ “ ካሽሚር” ሆኖ ለዘላቂ

ሰላምና ወዳጅነት ሳይሆን ለዘላቂ ግጭትና የሰላም እጦት ምክንያት ሆኖ መቀጠሉ የማይቀር ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ መታወቅ ያለበት ቁምነገር ከጐረቤቶቻችን ጋር ያለንን የድንበር ውዝግብ ዛሬ እኛም ሆን እነሱ በድህነት ውስጥ ሆነን ልንፈታው ካልቻልን ነገ በተሻለ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ሆነን እንፍታህ ብንለው የበለጠ ውስብስብና አስቸጋሪ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከሌሎች ጐረቤቶችዋ በተሻለ በልማት እያደገች ከሄደችና በተለይም ነዳጅን ጨምሮ የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶቹዋን መጠቀም የምትችልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ከጐረቤቶቹዋ ጋር ያላት የድንበር ውዝግብ ወደ የግዛት ይገባኛል ጥያቄ እያደገ ሊመጣና ችግሩን ከድጡ ወደ ማጡ ሊያሸጋግረው ይችላል፡፡ በኢኮኖሚ ከሌሎች ጐረቤቶቻችን ቀድመን ብናድግ በዲፕሎማሲው ረገድ ተፅዕኖ የማሳደር አቅማችንም በዚያው መጠን የሚያድግ ቢሆንም ከኢኮኖሚ እድገታችን ጋር በተያያዘ የተፈጥሮ ኃብታችንን ለመጠቀም የሚኖረን አቅምና ፍላጐትም አብሮ ስለሚያድግ ከጐረቤቶቻችን ጋር የሚኖረንን ግንኙነት በዚያው መጠን ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ ዛሬ በአገራችን የምሥራቁ ክፍል ያለው የሰላም ሁኔታ ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሰና መልኩን እየቀዬረ የመጣው ከዚሁ የአገራችን አቅም እየተገነባ መምጣት ጋር ተያይዞ እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል፡፡

በ1999ዓ.ም አንድ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት የተካሄደ ጥናት እንዳረጋገጠው ከዐሥር የማያንሱ የውጭ መንግሥታት በሶማሊያ በእነ ዳሂር አዌይስ ሲመራ የነበረውን የእስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት ሲረዱ መገኘታቸው፣ የሶማሊያን ተቀናቃኝ ኃይሎች ለማስታረቅ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በተደረገው ጥረትም ከሶማሊያ ጋር ምንም ዓይነት ድንበር የማይጋሩት ኤርትራና ግብፅ ዋና ተዋናይ ሆነው መታየታቸው፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር በነዳጅ ፍለጋ ሥራ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የቻይና ዜጐችን ጭምር በጭካኔ ሲጨፈጭፍ መታዬቱ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃንና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከሁሉም የአገሪቱ አካባቢ በተለየ ለኦጋዴን ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ኦጋዴንን ከዳርፉር ጋር ለማመሳሰል ሲጥሩ መታየታቸው ያለ ምክንያትና እንዲሁ በአጋጣሚ ሳይሆን ኢትዮጵያ ከጐረቤቶችዋ ጋር ያላት የጥቅም ግጭት አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ችግር ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ጥቅም ያለፈ አገራዊ ትርጉም ያለው መሆኑን ሁሉም የአገሪቱ ዜጐችና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭምር በኃላፊነት ስሜት ካልተገነዘቡት የአገራችን ብሔራዊ ጥቅም በአግባቡ ተጠብቆ ሊቀጥል አይችልም፡፡ በ1999 ዓ.ም የኢትዮጵያ

ጦር ወደ ሶማሊያ እንዲዘምት ሲደረግ በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ዜጎች ሻዕቢያን በጠላትነት መፈረጅ ስህተት ነው በሚል ሰበብ ጭምር ድርጊቱን መቃወማቸው ከዚህ የአገርንና የድርጅትን ጥቅም በአግባቡ ለያይቶ ለማየት ካለመቻል የመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚያ ወቅት በሶማሊያ ጉዳይ ላይ እንደ አገር የኢትዮጵያ፣ እንደ ድርጅት የኢህአዴግ፣ እንደ ውጭ ኃይል የአሜሪካ ጥቅም ድንገት ተገጣጥመው የተገኙበት አጋጣሚ እንደ ነበር የማይካድ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ከሁሉም በላይ የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በማስቀደም ዘመቻውን በተባበረ ድምፅ መደገፍ አለመቻላችን አገራችን በአካባቢው ያለችበትን አደጋ በእኩል መጠን እንዳልተገነዘብነው በግልጽ አሳይቶ አልፏል፡፡ ዛሬም ሆነ ወደፊት በሥልጣን ላይ ያሉና የምንጠላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶች ለመጉዳት ብለን የአገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ተፃረን የምንቆም ከሆነ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በአንድ በኩል ህወሃትና ኢህአፓን ጨምሮ በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ሲፈጽሙት የነበረን ታሪካዊ ስህተት መድገም ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም በአግባቡ አስጠብቆ ለትውልድ ለማውረስ ያለመቻልን ውጤት የሚያስከትል አደገኛ ድክመት ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በነገራችን ላይ በፓርላማ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ በሶማሊያ በደርግ ጊዜ በተወረረችበት ወቅት ህወሃትና ኢህአፓ በወቅቱ የወሰዱት አቋም ስህተት እንደነበር ጠቅሼ ማናገሬን በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ "አቶ ልደቱ ዕድሜ ጠገብ አይደሉም" በማለት ወደ ፍሬ ጉዳዩ መግባት ሳይፈልጉ በደፈናው አጣጥለው አልፈውታል፡፡ የሚገርመው ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚያ የፓርላማ ስብሰባ ላይ ስለ ነቢዩ መሐመድ ታሪክ ብዙ ሲያወሩ ሰምቻቸው ስለነበር ዕድሜ ጠገብ መሆንና ታሪክን የማወቅ ጉዳይ ግንኙነት ካላቸው ርሳቸውም በነቢዩ መሐመድ ዘመን ዕድሜ ጠገብ እንዳልነበሩ ጠቅሼ ልሞግታቸው ፈልጌ የነበር ቢሆንም ከርሳቸው ንግግር በኋላ የመናገር ዕድል ሳላገኝ ቀረሁ፡፡

ከድንበር ጉዳይ ቀጥሎ በተመሳሳይ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ሰጥተን ልንፈታው የሚገባን ጉዳይ ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ ወንዞቻችን ዙሪያ ያለብንን የአለመግባባት ችግር ነው፡፡ ከውሃ ጋር በተያያዘ ከኬንያ፣ ከሶማሊያ፣ ከሱዳንና ከግብፅ ጋር ለግጭት ምክንያት የሚሆን ግንኙነት ያለን ሲሆን፣ የውሃ ጉዳይ በተለይም ከግብፅና ከሱዳን ጋር ቢያንስ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሲያጋጨን ቆይቷል፡፡ ከኬንያና ከሶማሊያ ጋር ያለን የውሃ ግንኙነት እስከ አሁን የቀጥተኛና ከፍተኛ ግጭት ምክንያት የሆነበት አጋጣሚ አለ ባይባልም ኢትዮጵያ በወንዞችዋ ከመጠቀም አቅሟ ማደግ ጋር በተያያዘ ወደፊት የውሃ ጉዳይ ከእነዚህም አገሮች ጋር ከፍተኛ የግጭት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ የውሃ አጠቃቀም ጉዳይ በኬንያ ፓርላማ መነጋገሪያ አጀንዳ እስከመሆን ደርሶ መታዬቱም ይህንኑ የወደፊት ስጋት የሚያጠናክር ነው ማለት ይቻላል፡፡

በውሃ ጉዳይ ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን አለመግባባት በአግባቡ ፈተን ውሃን የግጭት ሳይሆን የትብብር ምንጭ ለማድረግ እስካሁን ያልበቃነው ከሞላ ጎደል ከላይ በድንበር ጉዳይ ለመጥቀስ ከሞከርናቸው ምክንያቶች ጋር በተያያዘ ሲሆን፣ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚኖረን አማራጭ መፍትሄም የድንበር ጉዳይን ለመፍታት የሚያስችሉንን ተመሳሳይ መርሆዎች ጥቅም ላይ በማዋል ይሆናል፡፡ የውሃን ጉዳይ ጎረቤቶቻችንም ሆኑ እኛ ከግለኝነት ስሜትና አስተሳሰብ ተላቀን አሁን ባለንበት ደረጃ ዓለም አቀፍ የውሃ አጠቃቀም መርህን መሠረት ባደረገና የጋራ ጥቅም መርህን በተከተለ መንገድ ካልያዝነው በስተቀር የውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታችን እየተሻሻለ በሄደ መጠን ችግሩ የበለጠ አስቸጋሪና ውስብስብ እየሆነ መምጣቱ አይቀርም፡፡ በርግጥ በአሁኑ ወቀት በአንድ በኩል በናይል ኢንሸቲቭ አማካይነት የውሃ አጠቃቀምን በተመለከተ በናይል ተፋሰስ አገሮች መካከል የተሻለና አበረታች መግባባት እየተፈጠረ መምጣቱ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የውሃ እጥረታችንን በዘላቂነት ሊፈታ የሚችል የከርሰ ምድር ውሃ በአገራችን ስለመኖሩ አንዳንድ በጎ ዜናዎች እየተሰሙ መሆናቸው የውሃ ጉዳይ ወደፊት የሚሰጋውን ያህል የግጭት ምንጭ እንደማይሆን እያመላከቱ ቢሆንም ከድንበር ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከላይ ያነሳናቸውን ነጥቦች ግምት ውስጥ በማስገባት ችግሩን በተቻለ ፍጥነት መፍታት የበለጠ የሚመረጥ ይሆናል፡፡ በውሃ ጉዳይ ላይ በሚደረግ ድርድር አንዱ ተፅዕኖ ማሣደሪያ ነጥብም ቀዳሚ ተጠቃሚ የመሆን ጉዳይ ስለሆነ አገራችን በውሃ ሃብቷ ለመጠቀም እያደረገችው ያለው ጅምር ጥረት ሳይስተጓጎል የበለጠ ተጠናክሮ በፍጥነት መቀጠል ያለበት ነው፡፡ ከውሃውም ሆነ ከድንበር ጉዳይ ጋር በተያያዘም ኢህአዴግ በማንኛውም ሁኔታ ማለትም በአስገዳጅ ሁኔታ (under duress) ጭምር የተፈረሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተቀባይነት እንዳላቸው አድርጐ በተደጋጋሚ የሚያራምደው የተሳሳተ አቋምም በአግባቡ መመርመርና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ ነው፡፡

ከድንበርና ከውሃ ጉዳይ ቀጥሎ ከሁሉም በተለየ ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ ከኢኮኖሚና ከጸጥታ ደህንነታችን ጋር በተያያዘ በውጭ ግንኙነታችን ወደፊት አስቸጋሪ ፈተና የሚሆንብን የባህር በር ማጣት ጉዳይ ነው፡፡ ኢህአዴግ አገርን በመበደል ወደፊት በታሪክና በትውልድ ፊት ተወቃሽ መሆን ካለበት ኢትዮጵያን የባህር በር ከማሳጣቱ በላይ ተወቃሽ የሚያደርገው ድርጊት አይኖርም፡፡ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከሁሉም የአፍሪካ ቀንድ ጎረቤቶቹዋ በተለየ ብቸኛ የባህር በር የሌላት አገር ለመሆን የበቃችበትን ምክንያት ኢህአዴግ ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ ኤርትራን በሚመለከት ካራመደው አቋም ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡ ቀደም ባለው የኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ በኢህአዴግ የትጥቅ ትግል ወቅት የኤርትራ ጉዳይ በጎላ ሁኔታ አከራካሪ የፖለቲካ አጀንዳ የነበረ የመሆኑን ያህል የኤርትራ ጉዳይ በውስጡ የባህር በር ጥያቄን ያህል

ትልቅ አገራዊ ጉዳይ አፍኖ የያዘ እንደ ነበር ተገቢ ትኩረት ሳያገኝ መቅረቱ አሁን ለገጠመን ችግር ቀዳሚ ምክንያት ነበር ማለት ይቻላል።

በኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ ዙሪያ ከኤርትራ መገንጠልም በላይ ለቀሪዋ ኢትዮጵያ የወደፊት ህልውና የበለጠ አደገኛ የሚሆነው የባህር በር ማጣት ጉዳይ መሆኑን የኤርትራን ነፃነት ይደግፉ የነበሩ ብቻ ሳይሆን የኤርትራን መገንጠል ይቃወሙ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ኃይሎች ጭምር በአግባቡ የመገንዘብ ድክመት ስለነበረባቸው የኤርትራ መገንጠል የመጨረሻ ውጤት ሕዝብንና ግዛትን ማጣት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ በማድረግ ሊጠናቀቅ ችሏል። የኤርትራን መገንጠል የሚደግፉትም ሆነ የሚቃወሙት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በወቅቱ ጉዳዩን ከአገሪቱ የሩቅ ግብ፣ ጥቅም አንጻር በተሻለ ሁኔታ ተገንዝበውት ቢሆን ኖሮ ሲቻል ኤርትራ ከኢትዮጵያ የማትገነጠልበት፣ ሳይቻል ደግሞ የኤርትራ መገንጠል ኢትዮጵያን የባህር በር ሳያሳጣ በሰላም የሚፈጸምበት ሰፊ ዕድል ኤርትራ ከስልሳ ዓመት ቅኝ ተገዥነት በኋላ ከኢጣሊያ ነፃ ከወጣችበት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ እስከ ቅርቡ የ1985ቱ የኤርትራ የሕዝበ-ውሳኔ ሂደት ድረስ ነበር ማለት ይቻላል።

የንጉሡና የደርግ ሥርዓቶች የኤርትራን ችግር ኢትዮጵያን የባህር በር በማያሳጣ መልኩ መፍታት ሳይችሉ የቀሩት ታላቁ ዲፕሎማት አክሊሉ ኃብተወልድ ከነበራቸው የአርቆ አሳቢነት እይታ በተቃራኒ የተለያዩ አንፃራዊ አማራጮችን ግምት ውስጥ ከማስገባት ይልቅ ችግሩን በኃይል አማራጭ ብቻ እንፈታዋለን ብለው በማሰብ እስከ መጨረሻው ድረስ ውስጣዊና አካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ ግትር አቋም ለማራመድ በመምረጣቸው ነበር። ምክኒያቱ ይህ ባይሆን ኖሮ ጉዳዩ ይበልጥ ባልተወሳሰበበት በንጉሡ ዘመን ችግሩን በተሻለ ሁኔታ ለመፍታት ተደጋጋሚ ዕድሎች ነበሩ። በማንኛውም ጉዳዩ ወደ ኋላ ተመልሶ መፍረድ (Hind sight) አስቸጋሪና አጠያያቂ ቢሆንም ኤርትራ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ከኢጣልያ ቅኝ ግዛት ነፃ ወጥታ በእንግሊዝ የሞግዚት አስተዳደር በነበረችበትና የወደፊት ዕጣ-ፈንታዋ ምን መሆን እንደሚገባው በተባበሩት መንግሥታት ደረጃ ውይይት ይደረግ በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያ አሰብን በባህር በርነት ይዛ ከኤርትራ ጋር ግን ተለያይታ መቆየት የምትችልበት ሰፊ ዕድል ነበራት። በወቅቱ ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ቀርበው ከነበሩት ሦስት አማራጮች ውስጥ አንዱና የኤርትራን ነፃ አገር ሆኖ መቀጠል ይደግፉ በነበሩት የኤርትራ የፖለቲካ ኃይሎች ሳይቀር ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው አማራጭ "አሰብ የኢትዮጵያ አካል እንዲሆን ተደርጐ ኤርትራ ነፃ አገር ሆና እራሷን ችላ ትቀጥል" የሚል ስለነበር ይህንን አማራጭ በወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀብሎት ቢሆን ኖሮ ከኤርትራ ጋር የሰላሣ ዓመት ጦርነት ለማሳለፍም

ሆነ በመጨረሻም የባህር በር ለማጣት አንዳረገም ነበር፡፡ አሁን ላይ ሆነን ያንን የተሻለ አማራጭ የንጉሡ ሥርዓት ለምን ሳይቀበል ቀረ? ብለን መውቀስ የማይቻልና የማይገባ ቢሆንም የንጉሡ ሥርዓት ሁለቱ አገሮች በአዲስ መልክ የፈጠሩትን ፌደሬሽን በአግባቡ ይዞ አለመቀጠሉና ከፌደሬሽኑ መፍረስ በኂላ የነበሩ ሌሎች ተጨማሪ ዕድሎችና አማራጮችን በአግባቡ ሳይጠቀም መቅረቱ ግን ማስወቀሱ አይቀርም፡፡

ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥቱ አማካይነት “አሰብ ብቻ ሳይሆን ኤርትራ ሙሉ በሙሉ ከእናት አገርዋ ጋር መቀላቀል አለባት” በማለት ያደረገችው ትግል በዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ መጨረሻ ላይ በመደገፉና “ኢትዮጵያ ወይም ሞት” የሚል መፈክር ይዘው በታገሉ ኤርትራውያን ትግል ጭምር ኢትዮጵያና ኤርትራ ከስልሣ ዓመታት መለያየት በኂላ በፌደሬሽን እንደገና ለመቀላቀል በቅተዋል፡፡ ይህ ውጤት በራሱ የንጉሡን ሥርዓት ሊያስመሰግን የሚገባው ቢሆንም ፌደሬሽኑ ከዐሥር ዓመታት ቆይታ በኂላ አክራሪ የአንድነት ደጋፊ በሆኑ ኤርትራውያንና ራሳቸው ንጉሡ ውስጥ ውስጡን ባደረጉት ግፊት ጭምር እንዲፈርስ መደረጉ ግን አሁን ለገባንበት ችግር በዋናነት ምክንያት የሆነና የሚያፀፅት ታሪካዊ ስህተት ለመሆኑ በብዙ የውስጥና የውጭ ጸሐፊዎች ሲተች የኖረ ክስተት ነው፡፡

የፌደሬሽኑ መፍረስ የፌደሬሽኑን መኖር ከልብ ይደግፉ ለነበሩት ኤርትራዊያን ብቻ ሳይሆን ከመጀመሪያውም ኤርትራ ከእናት አገርዋ ከኢትዮጵያ ጋር ፈጽሞ እንዳትቀላቀል ፍላጎት ለነበራቸው ኤርትራውያንም ጭምር ዋና የመታገያ አጀንዳ ሆኖ አገልግሏቸዋል፡፡ በርግጥ ሁለቱ አገሮች አንድ ሆነው እንዳይቀጥሉ የውጭ ኃይሎች የነበራቸው ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ የሆኖ ሆኖ ለስልሳ ዓመታት ተለያይተው የኖሩት ኢትዮጵያና ኤርትራን ይቅርና በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያም ራስዋ በፌደራል ሥርዓት የምትተዳደር አገር መሆንዋ ሲታይ የያኔው የኢትዮጵያና የኤርትራ ፌደሬሽን መፍረስ ከጽንፈኛ አስተሳሰብ የመነጨ ስህተት መሆኑን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ ፌደሬሽኑ ከፈረሰ በኂላም የፌደሬሽኑ መፍረስ ከፍተኛ ተቃውሞ እየገጠመው ሲመጣ ፌደሬሽኑን እንደገና ወደ ነበረበት ለመመለስ ከመሞከር ይልቅ ተቃውሞውን በኃይል ለማፈን በመሞከሩ ችግሩ ውሎ አድሮ የፈረሰውን ፌደሬሽን እንደገና ወደ መመለስ ሳይሆን ወደ ተሟላ የነፃነት ጥያቄ እንዲሸጋገር አድርጎታል፡፡

ጥያቄው ወደዚህ ደረጃ ከተሸጋገረም በኂላ በንጉሡ ዘመንም ሆነ በኂላ በደርግ ዘመን ቢያንስ እስከ 1981ዓ.ም ድረስ የኤርትራ የመገንጠል ጥያቄ ኢትዮጵያን የባህር በር በማያሳጣበት ደረጃ በሰላምና በድርድር የመፍታት ዕድል የነበረ ቢሆንም ዕድሉን መጠቀም ሳይቻል ቀርቷል፡፡ አንዳንድ ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ያላቸው የውጭም ሆኑ የውስጥ ኃይሎች የሚያራምዱትን

ትንኰሳ በየትኛውም ዓይነት ድርድርና ውይይት ማስቀረት የማይቻል ቢሆንም የኃይል አማራጭ የኤርትራን ጉዳይ በከፍተኛ መጠን እንዳባባሰውና እንዳወሳሰበው ግን መካድ አይቻልም፡፡ የኤርትራ ችግር ወደኋላ ሊመለስ በማይችልበት መጠን የተበላሸ ደረጃ ላይ የደረሰው በደርግ ጊዜ ቢሆንም ኢህአዴግም የኤርትራ መገንጠል ቢያንስ ኢትዮጵያን የባህር በር ሊያሳጣ በማይችል ሁኔታ እንዲፈጸም ለማድረግ የነበረውን ዕድል ሳይጠቀምበት ቀርቷል፡፡ በትጥቅ ትግል ወቅት ራሱ ሻዕቢያ ለሪፈረንደም ያቀርባቸው የነበሩ አማራጮች ሰፋ ያሉና ውኅደትን፣ ፌደሬሽንንና የተሟላ ነፃነትን የሚያካትቱ የነበሩ ቢሆኑም በ1985 ዓ.ም ሪፈረንደሙ ሲካሄድ ግን እነዚህ ሚዛናዊ አማራጮች መቅረባቸው ቀርቶ ጉዳዩ “ነፃነት ወይስ ባርነት” በሚል ዓይነት ተገቢ ያልሆነ አማራጭ እንዲቋጭ ተደርጓል፡፡

ኢህአዴግ በአንድ በኩል የትጥቅ ትግል እያደረገ በነበረበት ወቅት ወደፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ አገርን የማስተዳደር ዕድል በእጁ እንደሚወድቅ የተሟላ ግምት ስላልነበረው፣ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥትም ለመሆን ከበቃ በኋላ የባህር በርን በመጠቀምና ሕጋዊ ባለቤት በመሆን መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት በአግባቡ መገንዘብ ተስኖት ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ በማድረግ ረገድ በየሂደቱ ተደጋጋሚ ታሪካዊ ስህተት ፈፅሟል፡፡ የኢህአዴግ ቀዳሚ መሥራች የሆነው ህወሃት የትጥቅ ትግሉን በጀመረበት ወቅት የጥቁር አገር የሆነችውን የራሱን አፍሪካዊ አገር ኢትዮጵያን በዓለም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ “ቅኝ ገዥ” አድርጐ በመክሰስ “የኤርትራ ጥያቄ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ነው” ብሎ አቋም መያዙ የመጀመሪያውና ትልቁ ስህተት ነበር፡፡ ህወሃት በዚያ ጊዜ እንዲህ ዓይነቱን ምንም ዓይነት የታሪክ ድጋፍ የሌለው አቋም መያዙ በወቅቱ በሁለንተናዊ መልኩ ጠንካራ ድርጅታዊ አቅም ከነበረው ከሻዕቢያ ድጋፍ አግኝቶ ተጠናክሮ ለመውጣት የወሰደው ታክቲካዊ ርምጃ ተደርጐ ሊታይ ቢችልም ድርጅታዊ አቅሙ በከፍተኛ ደረጃ ተጠናክሮ ራሱን ከቻለም በኋላ “የኤርትራ ጥያቄ ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት ጥያቄ ነው” የሚለውን አቋሙን ለመቀዬር አለመሞከሩ ከሻዕቢያ ጋር በነበረው ግንኙነት የባህር በርን በሚመለከት ለድርድር የሚቀርብ ሌላ አማራጭ እስከ መጨረሻው እንዳይኖረው አድርጐታል፡፡

ኢህአዴግ የኤርትራን ጥያቄ ያለአግባብ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አድርጐ ማየቱን እስከ መጨረሻው ይዞ ከመቀጠል ይልቅ በሂደት ይህንን አቋሙን አንዳንድ ጊዜ ሲናገር እንደሚደመጠው የሰላሣ ዓመቱን የርስ በርስ ጦርነት የመገንጠልን መብት በማክበርም ጭምር ቢሆን ማቆም ያስፈልጋል ወደሚል አቋም ቢያሻሽለው፣ ወይም ደግሞ ለማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለው መብት መከበር

አለበት ብሎ እንደሚያምነው ሁሉ የኤርትራም ጉዳይ በዚሁ አግባብ ሊፈታ ይገባዋል ወደሚል አቋም ቢቀይረው ኖሮ በኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት መብት ላይ የመደራደር ዕድል ይኖረው ነበር። ነገር ግን ኢህአዴግ አንድ ጊዜ የያዘውን የተሳሳተ አቋም ኃይማኖቱ አድርጐ እስከ መጨረሻው ይዞ መቀጠልን በመምረጡ መንግሥትም ከሆነ በኋላ የባህር በር ጥያቄን ለድርድር ለማቅረብ የሚያስችል ድፍረት ሳያገኝ ቀርቷል። ቢያንስ ደርግን ከሥልጣን አስወግዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት ከሆነ በኋላ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ የኤርትራን ነፃ መንግሥትነት ማወቁን ለዓለም ተሽቀዳድሞ ከማወጅ ይልቅ በቅድሚያ በኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ ላይ የድርድር ሐሳብ ቢያቀርብ ኖሮ ሻዕቢያ በወቅቱ የኤርትራን ነፃ አገርነት ሕጋዊ ለማድረግ ከነበረው ከፍተኛና ቀዳሚ ፍላጐት የተነሣ የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ ከመቀበል የተለየ አማራጭ አይኖረውም ነበር።

በዚያ ወቅት ከምንም በላይ ሻዕቢያ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚችለው ቁም ነገር የኤርትራን ነፃነት ሕጋዊ ማድረግ ስለነበር እንደነ ፑንት ላንድ ሕጋዊ ዕውቅና የሌለው አገር መንግሥት ከመሆን ወይም የሠላሳ ዓመቱን ጦርነት እንደገና ማለቂያ ወደ ሌለው ጦርነት ከማራዘም ይልቅ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት መብት አክብሮ ሕጋዊ ነፃነትን ማግኘት የማይመርጥበት ምክንያት አልነበረም። በወቅቱ ኢህአዴግ እንደ የኢትዮጵያ መንግሥትነቱ የሚያቀርበው የድርድር ሐሳብ ኤርትራ በሕዝበ-ውሳኔ ነፃ ለመውጣት መቻሏን ጥያቄ ውስጥ የማያስገባ ሆኖ እስከቀረበ ድረስም ጥያቄው የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ድጋፍ ማግኘቱም አይቀርም ነበር። በወቅቱ እንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣን በነበሩት በሄርማን ኮኸን አማካይነት በለንደኑ የሰላም ድርድር ወቅት ተነሥቶ ኢህአዴግ ሃሣቡን ሳይቀበለው መቅረቱ የሚያሳየንም የባህር በር ጥያቄን በተመለከተ የዓለም ዓቀፉን ኅብረተሰብ ድጋፍ ማግኘት የማይቸግረን ጉዳይ መሆኑን ነው።

ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት በባድመ ጉዳይ በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የተወሰነውን ውሳኔ ሳይቀር ባለ አምስት ነጥብ የሰላም ቅድመ-ሁኔታ በሂደቱ ላይ በመቀርቀር እንዳይፈጸም ማድረግ እንደቻለው ሁሉ - ያኔም ለአገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ተቆርቋሪ በመሆን ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝበትን የድርድር ሐሳብ ቢያቀርብ ኖሮ ውጤት ማግኘት የማይቻልበት ምክንያት አልነበረም። ኢህአዴግ እንዲህ ዓይነቱን ርምጃ ወስዶ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ሆና ለመቀጠል ከነበራት ሰፊ ዕድል በተጨማሪ አጠቃላይ የአገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታም ሆነ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብ የሚኖረው ተቀባይነት አሁን ከሚታዬው በብዙ እጅ የተለየ በሆነ ነበር።

በወቅቱ ኢህአዴግና ሻዕቢያ በነበራቸው አገራዊ የጋራ ጥቅምን መሠረት ያላደረገ የተዛባ ድርጅታዊ ግንኙነት ኢትዮጵያ የኢኮኖሚና የጸጥታ ዋስትናዋ የሆነውን የባህር በሯን ማጣትዋ አንዱና ዋናው ነገር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በወቅቱ የኤርትራ ሕዝብ እንዲያካሂደው የተደረገው ሕዝበ-ውሳኔም የተለየ ይዘት እንዲኖረው ሊደረግ ይችል ነበር። በዚያ ወቅት ከነበረው የኤርትራ ሕዝብ ስሜት አንጻር የመገንጠሉ ጉዳይ ሊቀር ይችል ነበር ብሎ ማሰብ ባይቻልም ከሕዝበ-ውሳኔው በፊት ስለ ሁለቱ አገሮች የወደፊት ዕጣ-ፈንታ ነፃ የሐሳብ ውይይት የሚደረግበትና በሕዝበ-ውሣኔውም ላይ ሰፊ አማራጮች የሚቀርቡበት ዕድል ተመቻችቶ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያና ኤርትራ ሲቻል በኮንፌደሬሽን መልክ አብረው የሚኖሩበት፣ አለዚያም ሁለት ነፃ አገራት ሆነው በሂደት እንደገና ወደ አንድ አገርነት ሊመለሱ የሚያስችላቸው ጤናማ ግንኙነት በመካከላቸው እንዲኖር ማድረግ በተቻለ ነበር። ነገር ግን በኢህአዴግና በሻዕቢያ መካከል የነበረው ግንኙነት ከመጀመሪያው የጋራ አገራዊ ጥቅምን መሠረት ያላደረገና በቂ ጥንቃቄ ያልተደረገበት ስለነበረ ኢህአዴግ የ1985 ዓ.ምቱን ሪፈረንደም ሻዕቢያ በመረጠው መንገድ ከማስፈጸም ባሻገር በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ ኤርትራዊያንን መብት ለማስከበርም ሆነ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት መብት ማስከበር የሚያስችል ምንም ዓይነት ተጨባጭ ርምጃ ሳይወስድ ቀርቷል። ይህ ሁኔታ በመጨረሻ ሁለቱን አገሮች ወደ በጎ ግንኙነት ሳይሆን በብዙ አሥር ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት ወደ ሆነ ዘግናኝ ጦርነት አስገብቷቸዋል። በጣም የሚያሳዝነው በአገር ጉዳይ ይህ ሁሉ ስህተት ከተፈጸመም በኋላ ኢህአዴግ አንድም ቀን የኢትዮጵያና የኤርትራን ግንኙነት በተመለከተ ስህተት መሥራቱን አምኖ ሲቀበልም ሆነ ሲፀፀት ታይቶ አለማወቁ ነው።

የሆነ ሆኖ በዚህ የተሳሳተ መንገድ የተከሰተው የሁለቱ አገሮች መለያየትም ሆነ ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ የመሆኗ ጉዳይ በመጥፎ የታሪክ አጋጣሚ የተከሰተ መራራቅ ቢሆንም ከእንግዲህ ሁኔታው በኃይል የሚለወጥበት ዕድልም ሆነ አስፈላጊነት አለ ማለት ግን አይቻልም። ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ ሕግ የምትገዛ አገር እንደመሆንዋ መጠን ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያገኘውን የኤርትራ ነፃነት ማክበርም ሆነ የእኔ የምትለው የባህር በር በአሁኑ ወቅት በእጇ የሌለ የመሆኑን ሃቅ አምኖ መቀበል ይጠበቅባታል። ይህ ማለት ግን ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ከኤርትራ ጋር እንደገና መዋሐድም ሆነ የባህር በር እንዲኖራት አትፈልግም ማለት ስላልሆነ ይህንን ፍላጎትዋን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እውን ለማድረግ አጀንዳ ይዛ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ሥራ ልትሰራ አይገባትም ማለት አይደለም።

ኢህአዴግ ይህንን ለማድረግ ፈቃደኛ ባይሆንም ማንም ወደፊት በአገሪቱ የሚኖር ኃላፊነት የሚሰማው መንግሥትና ትውልድ የባህር በር ጉዳይን አገራዊ አጀንዳ አድርጐ ሊታገልለት ይገባል፡፡ የወቅቱ ትውልድም በአንድ በኩል የተሳሳተ የችግር አፈታት ዘዴ ስለባ በመሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጊዜና ሁኔታዎች ዕድለኛ ሳያደርጉት ቀርተው በሱ ጊዜ በታሪክ አንድ የነበሩት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ለሁለት መከፈላቸውና ኢትዮጵያም በር የተዘጋባት አገር ለመሆን መብቃትዋ አሳዛኝ ገጠመኝ ቢሆንም ቢያንስ ግን ጉዳዩ አገራዊ አጀንዳ ሆኖ ለትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፡፡ ኢዴፓ ከኢህአዴግ በተለየ በፖለቲካ ፕሮግራሙ ውስጥ የኤርትራንና የባህር በር ጥያቄን ጉዳይ በአጀንዳነት ያካተተው በስሜታዊነት ወይም የእወደድ ባይነት ፖለቲካ ለማራመድ ብሎ ሳይሆን እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው የአዲሱ ትውልድ ፓርቲ ጉዳዩ የትውልድ አጀንዳ ሆኖ እንዲቀጥል የማድረግ ታሪካዊ ግዴታ አለብኝ ብሎ ስለሚያምን ነው፡፡ በኢህአዴግ ዐይን እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ እንደ ፖለቲካ ቂልነትና ጠብ ያለሽ በዳቦ ተደርጐ የሚታይ ቢሆንም፣ ለእንዲህ ዓይነቱ ዓላማ መታገል አዲስ ነገር ሳይሆን በሌሎች አገሮችም ሲካሄድ የኖረ ነው፡፡

ሶማሊያ የኦጋዴን የይገባኛል ጥያቄዋን በሕገ-መንግሥቷ ጭምር አካታ በሰላምና በሕግ ሳይሆን በጦርነት ስትፋለመን መኖርዋ ሲታይ፣ ኤርትራም በተፅዕኖ - ነገር ግን በሕግ አግባብ የፈረሰባትን ፌደሬሽን ምክንያት አድርጋ በአካሄደችው ትግል በጦርነት ነፃ አገር መመሥረት መቻልዋ ሲታይ፣ ኢትዮጵያ እንደ ሶማሊያና ኤርትራ በጦርነት ሳይሆን በሰላምና በሕግ ያለ አግባብ የተነጠቀችውን የባህር በር ባለቤትነት መብት ማስመለስ እፈልጋለሁ ብላ ብትታገል ለኢህአዴግ ነውርና ወንጀል መስሎ የሚታየው ለምንድነው? ለመሆኑ ኢህአዴግ በአሁኑ ወቅት የራሷ ሉዓላዊነት ባላት በታይዋን ላይ የቻይና መንግሥት ያለውን የይገባኛል ጥያቄ ደግፎ ከመቆም ይልቅ ራሱ የባህር በር አልባ ለአደረጋትና ራሱ እያስተዳደራት ለምትገኘው እናት አገሩ መብት ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ዲፕሎማሲያዊ ትግል ቢያካሂድ ነውር መስሎ የሚታየው ለምንድነው?

በነገራችን ላይ የባህር በር ጉዳይ ኢህአዴግ እንደሚያስበው በገንዘብ ኪራይ ከሚገኝ የወደብ አገልግሎት እጅግ የሰፋና የተለየ ትርጉም ያለው ነው፡፡ ወደብ በዋናነት ሸቀጥን ለመጫንና ለማራገፍ የሚያገለግል አንድ ለዚሁ ተግባር ተብሎ ግንባታ የተካሄደበት የባህር ጠርዝ ላይ የሚገኝ ቦታ ሲሆን የባህር በር ግን ሰፊ የኢኮኖሚና የአገር ደኅንነት ትርጉም ያለው የአገር አካል ነው፡፡ አንድ የባህር በር ያለው አገር በወደብ አገልግሎት፣ በመርከብ ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በመዝናኛ አገልግሎት፣ በቱሪዝም አገልግሎት፣ በዓሣ ምርትና በመሳሰሉት

ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከሚያገኘው ጥቅም በላይ በባህር በር ባለቤትነቱ የሚኖረው የብሔራዊ ደኅንነት ዋስትና በዋጋ ሊተመን የማይችል ከፍተኛ ጥቅም ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በጅቡቲ በኪራይ የምንገለገልበት ወደብ በሰው አገር ላይ የሚገኝና የተገነባ ብቻ ሳይሆን የሰው አገር አቋርጠን ሂደን የምናገኘውና በሰው አገር አስተዳደራዊ ቁጥጥር ሥር ያለ ወደብ በመሆኑ አገራችን የጸጥታም ሆነ የኢኮኖሚ ህልውናዋ በተወሰነ ደረጃ በራሷ ሳይሆን በሌሎች ቁጥጥር ሥር የወደቀ ሆኗል፡፡ የባድመ ጦርነት በፈነዳበት ወቅት በግልጽ እንደታየው ሻዕቢያ በአሰብና በምፅዋ ወደብ የነበረውን የኢትዮጵያ ንብረት ሁሉ ወርሶ ወደቦቹን እንዳንጠቀምባቸው ሲዘጋብን በወቅቱ ጅቡቲን የመሰሉ ጎረቤቶቻችን ከሻዕቢያ ጋር ቆመው ቢሆን ኖሮ አጠቃላይ የኢኮኖሚም ሆነ የጸጥታ ህልውናችን ከፍተኛ አደጋ ውስጥ ይወድቅ ነበር፡፡

በየጊዜው እዬናረ የሚሄደው የወደብ አገልግሎት ወጭ በኢኮኖሚያችን ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ የሰው አገር ወደብ እኛን ብቻ የሚያገለግል እንደ አለመሆኑ መጠንም በወጭና በገቢ ንግዳችን ሊገጥመን የሚችለው መጉላላትና ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ሚስጥራችን በሌሎች እጅ መውደቁ፣ በአጠቃላይም በማንኛውም ወቅት ከሚፈጠርብን ከፍተኛ ጫና በተጨማሪ ከዚህ ሁሉ ችግሮቹም ጋር የወደብ አገልግሎቱን በድንገት ሙሉ በሙሉ ልናጣው የማንችልበት አስተማማኝ ዋስትና ስለሌለን በተለይም የኢኮኖሚ ቀውስና ጦርነት በገጠመን ጊዜ አገራዊ ህልውናችን አጠቃላይ አደጋ ውስጥ ሊገባ እንደሚችል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

ከህልውናችን ጋር የተያየዙ ከፍተኛ ጉዳዮች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀላል ችግር ሊባል ስለሚችለውና የኢትዮጵያ ሾፌሮች በጅቡቲ ስለሚደርስባቸው ተፅዕኖ ስንሰማ እንኳ ለአንድ አገር የባህር በር ማጣት ምን ያህል መረገም እንደሆነ ልንረዳው እንችላለን፡፡ የባህር በር የማጣትን ጉዳይ የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው ኢኮኖሚያችን የበለጠ እያደገና እየሰፋ ሲመጣ ችግሩ የሚቀለል ሳይሆን በዚያው መጠን የበለጠ ውስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ የሚመጣ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በአሁኑም ሆነ በወደፊቱ የአገራችን የውጭ ግንኙነት አንድ ከባድ ፈተና የሚሆንብን ከባህር በር እጦታችን ጋር የተያያዘው ችግራችን በመሆኑ በዚህ ረገድ ከእኛ ዕድሜ በላይ የሆነ የረዥም ጊዜ የውጭ ጉዳይ ዕቅድ ይዘን መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

የባህር በር ችግራችን ሊፈታ የሚችልበት አንድ መንገድ ወደፊት ኢትዮጵያና ኤርትራ ለጋራ ጥቅማቸው ሲሉ በፍቅርና በአንድነት አብረው ለመኖር ከሚኖራቸው ዕድል ጋር በተያያዘ ስለሆነ ሁለቱ አገሮች ጤናማ በሆነ ግንኙነት መልሰው ወደ አንድነት ለመምጣት የሚያስችላቸውን ግልጽ አቋምና ዕቅድ ይዞ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ኤርትራና ኢትዮጵያ አንድነት ቢፈጥሩ ጥቅሙ የጋራ እንጂ የኢትዮጵያ ብቻ ስላልሆነ ይህንን የአንድነት

ፍላጐታችንን በድፍረት ለኤርትራ ሕዝብ መግለፅ ሊያሳፍረን አይገባም፡፡ ቢያንስ ባለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ኢትዮጵያውያን አንድነትን በጉልበት ለማምጣት መሞከር በመጨረሻ ምን ዓይነት አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል በተግባር የተማርነውን ያህል፣ ኤርትራውያንም በበኩላቸው እንደተመኙት መገንጠል በራሱ የሰላምና የብልፅግና ደሴት ሊያደርግ እንደማይችል በተግባር መማር ችለዋልና - ሁላችንም በየፊናችን የተማርነውን ቁምነገር ይዘን እንደገና ለመዋሐድ ብናስብ ብልህነት ነው እንጂ ለማንኛችንም ሽንፈት መስሎ ሊሰማን አይገባም፡፡ አሁን ግን በተግባር እንደሚታየው ሁላችንም በመለያዬታችን የደረሰብንን ጉዳት ውስጣችን እያወቀው እንደገና ልንዋሐድ ይገባናል ብሎ መጠዬቅ ለሁላችንም ሽንፈት መስሎ ታይቶናል፡፡

ሌላው ቀርቶ እንደገና ከመዋሐድ በመለስ ሁለቱ አገሮች በመግባባት ሊለዋዎጧቸውና የጋራ ተጠቃሚ ሊሆኑባቸው የሚችሉ ተነፃፃሪ ጥቅሞች ያሉአቸው ቢሆንም በሁለቱም በኩል እንዲህ ዓይነቱን ሐሳብ ደፍሮ ማንሣት የሚፈልግ የለም፡፡ በሁለቱም በኩል በሥልጣን ላይ የሚገኙት የፖለቲካ ባለሥልጣናት የአገሮቻቸውን ጥቅም ርስ በርስ ከገቡበት የጥላቻና የመናናቅ ስሜት አብልጠው ማየት ባለመቻላቸው የሁለቱንም አገሮች ችግር በዘላቂነት ሊያስወግድ ስለሚችለው መፍትሔ ደፍሮ መነጋገር አልተቻለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ትናንት ኤርትራ ከተገነጠለች አንገታችን ተቆረጠ ማለት ነው በማለት ከማንም በላይ የአንድነት ጠበቃ ነኝ ሲሉ የነበሩ ሰዎች ሳይቀሩ ዛሬ አጉል እልህ ውስጥ ገብተው ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ እንደገና መዋሐድ ፈጽሞ መስማት የማይፈልጉ ሰዎች ሆነዋል፡፡

በኢትዮጵያም ሆነ በኤርትራ በኩል አሁን እየታየ ካለው የጥላቻና የእልህ ስሜት አንጻር እንኳን እንደገና ወደ አንድነት መምጣትና በባድመ ዙሪያ ያለውንም ችግር በቀላሉ መፍታት የማይቻል የሚመስል ቢሆንም በፖለቲካ ሂደት ሊለወጥ አይችልም የሚባል ነገር የለምና ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ግልጽነትና ድፍረት ባለው መንገድ ተቀራርበን መነጋገር እስከቻልን ድረስ ያለንበት ሁኔታ መለወጥ የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ ሁለቱ አገሮች ከ60 ዓመታት መለያየት በኋላ በጥሩ የታሪክ አጋጣሚ እንደገና ተዋሕደው፣ ከአርባ ዓመት አብሮ መኖር በኋላ ደግሞ በመጥፎ የታሪክ አጋጣሚ እንደገና እንደተለያዩት ሁሉ በሌላ በጎ የታሪክ አጋጣሚ ደግሞ እንደገና መልሰው አንድ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

እንዲያውም የወደፊት ዕጣ-ፈንታችን በትብብርና በአንድነት ብቻ የሚፈታ መሆኑን አምነን ወደዚያ ግብ የሚያደርሰንን ጉዞ አሁኑኑ በግልጽነትና በድፍረት ተነጋግረን ካልጀመርነው በስተቀር በድንበር ዙሪያ ያለንን አለመግባባት በመፍታት ብቻ ችግራችንን በዘላቂነት ይፈታል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል፡፡ ቀድሞውንም የድንበር ግጭቱ የሌሎች ቅራኔዎችና አለመግባባቶች መገለጫ

በመሆኑ በራሱ ለዘላቂ መፍትሄ የሚያበቃን አይሆንም፡፡ በመካከላችን የተፈጠረውንና ለረዥም ጊዜ እየዳበረ የመጣውን የጥላቻ፣ የቂም በቀልና፣ የመናናቅ ስሜት እርግፍ አድርገን ትተን በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን መነጋገር እስካልጀመርን ድረስ በየትኛውም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ውሳኔ ችግራችን በዘላቂነት ይፈታል ብሎ ማሰብም አይቻልም፡፡ በአሁኑ ወቅት በሁለቱም አገሮች በመንግሥትነት ሥልጣን ላይ ያሉት የፖለቲካ ኃይሎች ሥር ከሰደደው መቃቃራቸው በመነጨ ይህንን ማድረግ ቢተናነቃቸውም እንኳ ቢያንስ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በአጭር ጊዜ መጀመርና መጠናከር አለበት፡፡ እጅግ ዘግይቶ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራውያን ወደ ኢትዮጵያ እንደገና ገብተው በልማት ተሳታፊ ሆነው እንዲኖሩ የተወሰነው ውሣኔ ተገቢና የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው ነው፡፡ ከመጀመሪያውም በጦርነቱ ወቅት ኤርትራውያኑ በዚያ ሥርዓት በሌላው ሁኔታ በጅምላ ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ መደረጋቸው ትልቅ ስህተት ነበር፡፡ ኤርትራውያኑን በዚያ ሁኔታ በጅምላ ከማባረር ይልቅ ለኢትዮጵያ የጸጥታ ደኅንነት ስጋት እንደማይሆኑ የሚታመንባቸው ኤርትራውያን ተለይተው ሕግና ሥርዓትን አክብረው በኢትዮጵያ እንዲኖሩ ማድረግ ተችሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የኤርትራ ውስጣዊ ሁኔታም ሆነ የሁለቱ አገር ሕዝቦች ግንኙነት አሁን ከሚገኝበት በብዙ እጥፍ የተሻለና የተለየ በሆነ ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ የኢትዮጵያን የባህር በር የማግኘት ጥያቄ ለመፍታት በኤርትራ በኩል ያለው ዕድል ቀዳሚውና ቅርቡ መፍትሔ ቢሆንም ይህ ምኞት በተለይም ከሻዕቢያ ባህሪ አንጻር እንደምናስበው በቀላሉ ሊሳካ የማይችልበት ሁኔታም ሊኖር እንደሚችል ግምት ውስጥ በማስገባት ከባህር በር ፍላጐታችን ጋር በተያያዘ በአካባቢው ያሉ ሌሎች አማራጭ ዕድሎችን ሁሉ ሳንታክት ማንኳኳት ይኖርብናል፡፡ ሁሉም በአገራችን ዙሪያ ያሉ ጐረቤቶቻችን ሰፊ የባህር ጠረፍ ያላቸው አገሮች በመሆናቸው ከእነዚህ አገሮች ጋር ተነፃፃሪ ጥቅም ከመለዋወጥ ጀምሮ እስከ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አንድነት መፍጠር ድረስ ሊደረግ በሚቻል ጥረት የባህር በር ፍላጐታችን አንድ ወቅትና አንድ ቦታ ላይ ሊሳካ የማይችልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ የአፍሪካ ቀንድን በሚመለከት ልናራምደው የሚገባን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የባህር በር ባለቤት ለመሆን ያለንን ፍላጐት ለማሳካት የሚያስችል የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዕቅድ ይዞ መካሄድ ከቻለ በኤርትራ፣ በጅቡቲም ሆነ በሶማሊያ ይህንን ፍላጐታችንን ለማሳካት የሚያስችሉ ዕድሎች መኖራቸው አይቀርም፡፡ እንዲያውም በዚህ ረገድ ሰፊ አማራጮችን ይዘን ዓላማችንን ለማሳካት ከጣርን ከኢትዮጵያ ጋር አንድነት በመፍጠር ሊገኝ የሚችለውን ተነፃፃሪ ጥቅም ቀድመው ለማግኘት ሲሉ ጐረቤቶቻችን በጎ ፉክክር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ከውጭ ግንኙነታችን ጋር በተያያዘ ያለን ልማዳዊ አስተሳሰብ ካልተቀዬረ፣ በውስጣችን የተሻለ ብሔራዊ መግባባት ካልተፈጠረና የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ደረጃችን ካልተሻሻለ በስተቀር በውጭ ግንኙነታችን ዙሪያ ያሉብን ችግሮች በወሳኝ መልኩ ሊፈቱ የማይችሉ ቢሆንም በአንድ በኩል በእነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች ዙሪያ ለውጦችን በፍጥነት ለማምጣት እየጣርን፣ በሌላ በኩል አሁን በምንገኝበትም ሁኔታ ሊሞከሩና ሊሳኩ የሚችሉ ተግባሮችን አሟጠን ለማከናወን የሚያስችል ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ኢትዮጵያውያን ጠንካሮችና ዕድለኞች ሆነን በእኛ በኩል የሚጠበቁትን ሁሉንም ተግባራት በብቃት ማሳካት ብንችል እንኳን የውጭ ግንኙነት ጉዳይ በአንድ ወገን ጥረትና ፍላጐት ብቻ ሊሳካ የሚችል ባለመሆኑ በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ራሳችንን ከማንኛውም የውጭ ጥቃት የመከላከል ዝግጁነት ያስፈልገናል፡፡ የአገራችን የውጭ ግንኙነት መግባባትን፣ ሰላማዊነትን፣ ሕጋዊነትንና የጋራ ጥቅምን መሠረት አድርጐ መከናወን የሚገባው ቢሆንም ብሔራዊ ደህንነታችን በራሳችን በጎ ፍላጐትና ጥረት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ውጫዊ ሁኔታዎች ሊወሰን የሚችልበት ሰፊ ዕድል ስላለ ሁልጊዜም በቂ ወታደራዊ ዝግጅት ያለን አገር ሆነን መገኘታችን ምትክ የሌለው ኃላፊነት ነው፡፡ ኢትዮጵያ በአካባቢው ብቃት ያለው ወታደራዊ ዝግጅት ያላት አገር መሆኗም ከአቅም በላይ የሆነ የውጭ ጥቃት ሲመጣባት እራሷን ለመከላከል የሚያስችላት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ወታደራዊ ዝግጁነትዋ በራሱ ሌሎች በጦርነትና በወረራ ፍላጐታቸውን ለማስፈጸም የሚኖራቸውን ፍላጐት ከምንጩ እንዲደርቅ በማድረግ ረገድም የማይናቅ የሰላም ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡

## መደምደሚያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እዚህም እዚያም የተነካኩ በርካታ ርእሰ ጉዳዮች ቢኖሩም በዋናነት ለማየት የተሞከረው የወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ባህል የሚገኝበትን ደረጃና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች መሠረታዊ በሚባሉ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች ዙሪያ ያሉንን ዋና ዋና ልዩነቶች ነው፡፡ ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ አጀንዳዎች ጋር በተያያዘ በመካከላችን የሚታዩት ልዩነቶች ከሌሎች አገሮች ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር በጣም የሰፉና መሠረታዊ ናቸው ሊባሉ ቢችልም ልዩነቶቹ ወደፊት በሕዝብ ፍላጐትና ምርጫ ሊዳኙ እንደሚችሉ ታሣቢ በማድረግ ጤናማ ልዩነቶች ናቸው ብሎ መቀበል ይቻል ይሆናል፡፡

የዚህ ጽሑፍ አንዱና ዋናው ዓላማ የወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ጠቃሚ ባልሆኑ ጉዳዮች ከመነታረክ ወጥቶ ወደ ትክክለኛ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ አገራዊ ጉዳዮች /Issues/ ክርክር እንዲገባ ማድረግ ስለሆነ በጽሑፉ ውስጥ ሊዳሰሱ በተሞከሩት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሰከነና ጤናማ የሆነ ውይይትና ክርክር በአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ሊካሄድ ይገባዋል፡፡ ማንኛውም የአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ ይመለከተኛል የሚል ዜጋ በዚህ ጽሑፍ በተዳሰሱት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ የሚሰማውን የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ትችት እንዲያቀርብ ጸሐፊው በዚህ አጋጣሚ በአክብሮት ይጋብዛል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በአገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ከሚታዩብን ልዩነቶች በላይ ከአገራችን የወቅቱ የፖለቲካ ባህል አንጻር የሚታዩብን ድክመቶችና ችግሮች እጅግ ውስብስብና ከባድ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ የሚታዩብን ችግሮች ውስብስብና ከባድ መሆን ብቻም ሳይሆን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ይፈታሉ ተብለው የማይጠበቁም ናቸው፡፡ ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው የምንፈልገው መጠንና ፍጥነት የፖለቲካ ባህላችን እየተሻሻለ አለመምጣቱ ብቻ ሳይሆን፣ ችግሩ በዚሁ ከቀጠለ ለአጠቃላይ አገራዊ ህልውናችን አደገኛ ስጋት እየሆነ የሚመጣ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

የዘመናዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በአገራችን ማቆጥቆጥ ከጀመረ በርካታ ዐሥርት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥም ቢያንስ የሦስት ተተካኪ ትውልድ ዘመንን ሊሸፍኑ የሚችሉ ሦስት መንግሥታት የተፈራረቁ ሲሆን በዚያው መጠን የኢትዮጵያም ሕዝብ በብዙ አስቸጋሪ ውጣ-ውረዶች ውስጥ ለማለፍ ተገዷል፡፡ ይህ ያለፍንበት አስቸጋሪ ሂደት እንደ ሕዝብና አገር በቂ ትምህርት ለመቅሰምና የተሻለውን አቅጣጫ ለመያዝ ሊያበቃን ይገባ የነበረ ቢሆንም እኛ ግን ይህንን ለማድረግ ሳንታደል ቀርተናል፡፡ የአገራችንን ፖለቲካ ከጥላቻና ከአካላዊ ግጭት ወደ

ጤናማ የሐሳብ ግጭት መቀዩር ተስኖን በብዙ ደም አፋሳሽ ጦርነቶችና የርስ በርስ ግጭቶች ውስጥ ለማለፍ ተገደናል፡፡ ከጥላቻና ከቂም በቀል አዙሪት መውጣት ያልቻለው የእስካሁኑ የአገራችን የፖለቲካ ባህል ሁላችንንም እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ተሸናፊዎች እንዳደረገንና ለበጎ ውጤት እንዳላበቃን በገሃድ የምናየው እውነታ ቢሆንም ከዚህ አዙሪት ሰብሮ ለመውጣት የሚያስችለንን ዕውቀት፣ ቅንነትና ድፍረት እስካሁን ማግኘት አልቻልንም፡፡ ሌላው ቀርቶ በቅርቡ ምርጫ 97ን ተከትሎ በአገራችን ከተከሰተው የፖለቲካ ምስቅልቅል በተወሰነ ደረጃ በአግባቡ መማር ተስኖን እንደ መንግሥት፣ እንደ ገዥ ፓርቲ፣ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲም ሆነ በአጠቃላይ እንደ ሕዝብ ዛሬም እንደ ትናንቱ የተለመደውንና ሁላችንም ተሸናፊ የሆንበትን የፖለቲካ ባህል ይዘን መቀጠልን መርጠናል፡፡ ይህ ሳይውል ሳያድር መቀየር ያለበት አገራዊ አደጋ ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በጎላ ሁኔታ እንደታየው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች የሚታዩብን መሠረታዊ ችግሮች በዋናነት ተገቢ የሆነ ብሔራዊ መግባባት ከማጣታችን የሚመነጩ ናቸው፡፡ ብሔራዊ መግባባት በአገራችን እንዲፈጠር በቅድሚያ በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት የምንገኝ የፖለቲካ ኃይሎች አንዳችን በሌላችን ላይ ጣታችንን መቀሰር አቁመን ሁላችንም የእስካሁኑ የአገሪቱ ችግሮችም ሆነ የወደፊቱ መፍትሔዎች አካል መሆናችንን አምነን መቀበል ይጠበቅብናል፡፡ ሁላችንም በየፊናችን ስለ አገር አንድነት፣ ስለ ሕዝቦች እኩልነት፣ ስለ ሰብአዊ መብት፣ ስለ ሰላምና ስለ ዴሞክራሲ መቆረቆራችንን አንዳችን ከሌላችን በላይ ተቆርቋሪዎች ነን እያልን ስንመጻደቅ ከመኖር ይልቅ በቅድሚያ ሁላችንም የአንድ አገር ልጆች መሆናችንን አምነን በመቀበል አንዳችን ለሌላችን ተገቢውን ክብርና ዕውቅና መስጠት፣ ርስ በርስ መደማመጥና መተማመን ይጠበቅብናል፡፡

አገሪቱ አሁን ለምትገኝበት አሳፋሪ ሁኔታ ሁላችንም የየድርሻችንን ተጠያቂነት አምነን መቀበል ይኖርብናል፡፡ በዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ እምነት የአገራችን የፖለቲካ ባህል የተበላሸ በመሆኑ ጉዳይ ላይ ይብዛም ይነስም ሁላችንም እንደ ዜጋ፣ እንደ ሕዝብና አገር የተጠያቂነት ድርሻ አለብን ማለት ይቻላል፡፡ የወቅቱ የተቃዋሚዎች ትግል የሚጠበቅበትን ውጤት እንዳያመጣ በማድረግ ረገድም የገዥው ፓርቲ ተጠያቂነት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው የተጠያቂነት ድርሻ የእኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ነው ማለት ይቻላል፡፡ አገሪቱ ተገቢ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲ አግኝታ በዘላቂነት የዴሞክራሲ፣ የሰላምና የብልፅግና አገር እንዳትሆን በማድረግ ረገድ ደግሞ ከማንም በላይ ትልቁ የተጠያቂነት ድርሻ የገዥው ፓርቲ የኢህአዴግ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች በተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ አሁንም ሆነ ወደፊት በመካከላችን ልዩነቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢያንስ ግን በጋራ አገራዊ አጀንዳዎቻችን ዙሪያ በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን አብረን የመሥራት ፍላጐቱና ድፍረቱ ሊኖረን ይገባል፡፡ እንደ እስካሁኑ አንዳችን ሌላችንን በጠላትነት እየፈረጅን ሰላም ወዳድ ነን ማለትን፣ መደማመጥንና አብሮ መሥራትን እዬነቀፍንና እያወገዝን የአንድነት ጠበቆች ነን ማለትን፣ በጭፍን እየደገፍንና በጭፍን እየተቃወምን ትግላችን ለዴሞክራሲ ነው ማለትን ርግፍ አድርገን ትተን ስለ ዴሞክራሲና ሰላም በአፍ የምናወራውን በተግባር ሆነነው እስካልተገኘን ድረስ ከአጉል ተስፈኝነት ወጥተን ራሳችንንም ሆነ አገራችንን የእውነተኛ ለውጥ ባለቤት ለማድረግ አይቻለንም፡፡

የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ስለ አገሪቱ የፖለቲካ ታሪክ አንብቤ ለመረዳት ከሞከርኩትና ከዚያም በላይ ለአለፉት ዐሥራ ሰባት ዓመታት ራሴ የአገሪቱ የፖለቲካ ተዋናይ ሆኜ በተግባር ካገኘሁት ተሞክሮ በመነሣት ስለ አገሪቱ ወቅታዊ ፖለቲካ ያለኝን አተያይ በተመለከተ ራሴን ከይሉኝታ፣ ከጥላቻና ከእወደድባይነት የፖለቲካ አስተሳሰብ በምችለው መጠን ነፃ በማድረግ ይህንን ጽሑፍ በድፍረት ለመጻፍና ለማሥነበብ በቅቻለሁ፡፡ እኔም ሆንኩ አባል የሆንኩበት የፖለቲካ ፓርቲ ስለ ወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ በደረስንበት ግንዛቤ አገራችን ከእንግዲህ አዲስና ምክንያታዊ የሆነ ሦስተኛ የፖለቲካ አማራጭ ያስፈልጋታል ብለን አምነናል፡፡ ይህ ከረዥም ጊዜ የትግል ተሞክሮ በኋላ የያዝነው የሦስተኛ አማራጭነት አቅጣጫ በአገራችን በገዥ ፓርቲና በተቃዋሚነት የጠበበ መመዘኛ ሲካሄድ የኖረው የፖለቲካ ጽንፈኝነት ሲፋጭና ሲጋጭ ኖሮ በመጨረሻ ከውስጡ የፈጠረው ለአገር መድኅንነት የሚበቃ ትክክለኛ አማራጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንዲህ ዓይነቱን ለአገራችን የፖለቲካ ባህል አዲስ የሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት ማራመድ ምን ያህል አስቸጋሪና ከባድ ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን ብንገነዘብም በፖለቲካ ሂደቱ ውስጥ ያለን ተሳትፎ የተሻለ ትርጉም ያለው እንዲሆን ከመፈለጋችን በመነጨ ለእንዲህ ዓይነቱ አዲስ የፖለቲካ ባህል ፋና-ወጊ የመሆኑን ድርሻ በድፍረት ለመውሰድ ወሥነናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አዲስና ምክንያታዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ አገራችን ከነበረችበት የተበላሸ የፖለቲካ ባህል አንጻር ለጊዜው የተወዳጅነት ዕድል የሌለው (unpopular)፣ በሂደት ግን ትውልድንና አገሪቱን ለተሻለ ውጤት የሚያበቃ ትክክለኛ አስተሳሰብ መሆኑን በመገንዘብ መርጠነዋል፡፡ የዛሬው ትውልድ ካለፉት ትውልዶች ሁሉ የተሻለ በጎ ታሪክ ሠርቶ፣ ከራሱም በላይ የወደፊቱ ትውልድ የሚጠቀምበትና የሚኮራበት ታላቅ ተግባር አከናውኖ ማለፍ ካለበትም የሚያዋጣው መንገድ እስካሁን በአገራችን ሲራመድ ከኖረውና ሁላችንንም ተሸናፊ ሲያደርገን ከቆዬው

የፖለቲካ ባህል ራሱን አላቆ ይህንን ሦስተኛ የምክንያታዊነት ፖለቲካ በድፍረት ማራመድ ነው ብለን አምነናል፡፡

የሦስተኛ አማራጭነት ሚናችን ትርጉምና ይዘት ምን እንደሆነ በመጽሐፉ ውስጥ በተነሱት የተለያዩ የመወያያ ርእሰ ጉዳዮች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በበርካታ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች ዙሪያ የምናራምዳቸው አቋሞች ከሌሎች ፓርቲዎች አቋሞች የተለዩ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሦስተኛ አማራጭነት ሚናችን በዋናነት የሚንፀባረቀው በፖለቲካና በኢኮኖሚ አጀንዳዎቻችን ሳይሆን ከመቻቻል፣ ከዕውቅና መስጠትና ከአብሮ መሥራት የፖለቲካ ባህል ጋር በተያያዘ በምናራምዳቸው የትግል ስልቶቻችን ነው፡፡ በመጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች ለማሳየት እንደተሞከረውም፣ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ሦስተኛ አማራጭ ሆኖ መቅረብ ማለት ምን ማለት እንደሆነም ለማንኛውም የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ በቅርበት ለሚከታተል ዜጋ ለመረዳት እምብዛም የሚያስቸግር አማራጭ አይደለም፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - በእስካሁኑ የፖለቲካ ባህላችን ከተለመደው በጭፍን የመደገፍና በጭፍን የመቃወም ጤናማ ያልሆነ ስልት ነፃ በሆነ መንገድ ፖለቲካን በምክንያታዊነት ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ከእስካሁኑ የጥላቻ፣ የስሜታዊነትና የኩርፊያ የፖለቲካ ባህል መላቀቅና በምትኩ የመደማመጥ፣ የመቻቻል፣ ዕውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት አዲስ የፖለቲካ ባህልን በአገራችን ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - እንደ አመችነቱ ቦታና ጊዜ እየመረጡ ሳይሆን የመደራጀት መብት ከአገሪቱ ሕገ-መንግሥት እስካልተፋቀ ድረስ በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ብቸኛ የትግል ስልት አድርጐ ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ለሕግ የበላይነት፣ ለተቋማት ግንባታና ለዴሞክራሲያዊ ሂደት ልዩ ትኩረት በመስጠት በአንድ በኩል የአገሪቱን ሕጐችና ተቋማት እያከበሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ምክንያታዊ ትችትና ተቃውሞ እያቀረቡ ሂደቱን ቀጣይ የሚያደርግና የበለጠ የሚያጠናክር የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - ለአገሪቱ ሁለንተናዊ ችግሮች ሁልጊዜ በሥልጣን ላይ የሚገኙ መንግሥታትንና ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን ብቻ ተጠያቂ አድርጐ ማየትና ማውገዝ

ሳይሆን ሌሎችንም ሆነ ራስን የአገሪቱ ችግሮችና መፍትሄዎች አካል አድርጐ ማየት ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት- በሕዝብ ዘንድ ጊዜያዊ ድጋፍ ለማግኘት ሲባል ሕዝብ ምን ለማዳመጥ ይፈልጋል? እያሉ የእወደድባይነት /Populist/ ፖለቲካ ማራመድ ሳይሆን አገርንና ሕዝብን እስከጠቀመ ድረስ ጊዜያዊ የሕዝብ ትችትና ተቃውሞን እየተቀበሉም ጭምር እውነቱን ተናግሮ ከመሸበት የማደርን የሃቀኝነት ፖለቲካ ማራመድ ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - በእስካሁኑ የፖለቲካ ባህላችን እንደተለመደው ተቀናቃኝ ኃይልን ተገቢ ባልሆነ ፍረጃ፣ በስም ማጥፋትና በአሉባልታ ዘመቻ ሳይሆን በአጀንዳ ጥራትና በሐሳብ የበላይነት ታግሎ ማሸነፍ ማለት ነው፡፡

በጥቅሉና በአጭሩ ሦስተኛ አማራጭ መሆን ማለት - በአገራችን ፖለቲካ የመንግሥት ሥልጣን በጠበንጃና በኃይል የሚያዝበት አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበጥሶ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር ባለቤት የሚሆንበትን አዲስና ወደኂላ የማይመለስ ጨዋ የፖለቲካ ባህል በአገራችን እንዲተከል ለማድረግ መታገል ማለት ነው፡፡

ይህ ሦስተኛ አማራጭነት ሌሎቹ የአገራችን የፖለቲካ ኃይሎች እስካሁን ይዘውት የመጡትን ስልት እንደያዙ በቀጠሉበት ሁኔታ የኢዴፓ ወይም የጥቂት ፓርቲዎች አማራጭ ስልት ብቻ ሆኖ እንዲገኝ የሚፈለግ አይደለም፡፡ ሦስተኛው አማራጭ ዛሬ የፋና-ወጊነቱን ሚና ለመውሰድ በደፈረ አንድ ፓርቲ የተጀመረ ቢሆንም ነገ የሁሉም ፓርቲዎችና በአጠቃላይም የአገሪቱ ሕዝብ የፖለቲካ ባህል መገለጫ መሆን የሚገባው ስልት ነው፡፡ በወደፊቱ የአገራችን ፖለቲካም ኢህአዴግ በሰላማዊ ትግል ተሸንፎ ሥልጣኑን መልቀቅ የሚችለውም ሆነ የሚገባው በዚህ የሦስተኛ አማራጭነት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ተቀባይነት አግኝቶ የዛሬውና የመጭው ትውልድ የፖለቲካ ባህል መገለጫ እስካልሆነ ድረስ አንድ ፓርቲ ብቻውን ቢይዘውም - ባይዘውም አገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት መቻሏ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ህልውናዋን ጠብቃ መቀጠሏም አጠራጣሪ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ሰዎችንና የፖለቲካ ድርጅቶችን በተለያዩ ምክንያቶች እየተቃወሙና እያወገዙም ብቻ ሳይሆን እየጠሉም መኖር ይቻል ይሆናል -፤ ይህንን የሦስተኛ አማራጭነት መርህ እየተቃወሙና እየጠሉ ግን እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ወደፊት መራመድ ከቶውንም የማይቻል ይሆናል ___ አራት ነጥብ!

ኢ.ዮ.ፓ
ኢ.ዮ.ፓ
ኢ.ዮ.ፓ

## *አሉባልታና የአገራችን ፖለቲካ*

### *መግቢያ*

በፖለቲካም ሆነ በማንኛውም አገራዊ ጉዳይ አሉባልታን ከቁም ነገር ቆጥሮ መጻፍም ሆነ ጊዜ ወስዶ መወያየት የሚወደድ ነገር አይደለም፡፡ አሉባልታ ከጥንት ጀምሮ በአገራችን ሲተረተለትና ሲዘፈንለት የኖረ፣ በየዕለቱ ማኅበራዊ ግንኙነታችን ተለይቶን የማያውቅ መሠረታዊ ችግራችን ቢሆንም እስካሁን ድረስ አገራዊ መፍትሄ የሚያስፈልገው ችግራችን አድርገን አይተነው ግን አናውቅም፡፡ ሙስናን፣ ዝሙትን፣ ዝርፊያን፣ ሥራ አጥነትን፣ ጉጂ ልምዶችን፣ በሽታን፣ ድህነትንና ማይምነትን የመሳሰሉ ማኅበራዊ ችግሮቻችን "ችግር" መሆናቸውን ከማወቅ አልፈን አገራዊ መፍትሔ እንደሚያስፈልጋቸው በየመድረኩ የምንነጋገር ቢሆንም ለትልቁ የአገር በሽታ ለአሉባልታ ግን እስካሁን የሚገባውን ዕውቅና አልሰጠነውም፡፡

ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት አሉባልታ በተለምዶ አነጋገር የማይረባ የመንደርና የሥራ ፈቶች ልቅምቃሚ ወሬ ተደርጐ ስለሚታይና በጥንቱ ባህላችንም ሆነ በተለይም ከግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን መመጣት ጋር ተያይዞ አሉባልታ ምን ያህል በውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ትግል አደገኛ የፖለቲካ መሣሪያና ስልት ሆኖ ጥቅም ላይ እንደሚውል በቂ ግንዛቤ መፍጠር ባለመቻላችን ነው።

አሉባልታ በአገራችን ሁሉም አካባቢዎች ዘርና ሃይማኖት ሳይለይ በቤተሰብ ውስጥ ትዳርን የሚያፈርስ፣ ወዳጅነትንና ጓደኝነትን የሚያቃቅር፣ ጉርብትናን የሚያናጋ፣ አሠሪና ሠራተኛን የሚያጣላ፣ የንግድ ሽርክናን የሚያውክ፣ የአምልኮ ቦታን የሚበጠብጥና ከዚያም አልፎ የፖለቲካ ድርጅቶችንና መንግሥትን ጭምር እያመሰ የሚገኝ ሥር የሰደደ አገራዊ ችግራችን ነው ማለት ይቻላል። የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ከብዙ አገራዊ ችግሮቻችን መካከል አሉባልታ አንዱ አሳሳቢ ችግራችን ነው ብዬ ማመኔ እንደተጠበቀ ሆኖ - ለአለፉት ዐሥራ ሰባት ዓመታት በተቃውሞ ትግሉ ውስጥ በነበረኝ ቆይታ ለመገንዘብ እንደቻልኩት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከአሉባልታ የከፋና የበለጠ ሌላ ችግርና ጠላት አለባቸው ብዬ አላስብም። ብዙውን ጊዜ ተቃዋሚዎች በውስጣችን ለሚያጋጥመን መፈረካከስ ምክንያት አድርገን የምናቀርበው የገዥውን ፓርቲ አፈናና ሠርጐ ገብነት ቢሆንም በእኔ አመለካከት ግን ሚዲጫ በሌለው ሁኔታ የበለጠ እያፈረሰን የሚገኘው ዋናው ጠላታችን አሉባልታ ነው።

ተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ሰዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን አንድን ሰው ማጥቃት ሲፈልጉ፣ ወይም በውስጣቸው የአስተሳሰብና የአሠራር ልዩነት ተፈጥሮ አንዱ ሌላውን በምክንያታዊ የሐሳብ ክርክር ማሸነፍ ሲያቅተው ቀላል ስልት ሆኖ የሚታየው የአሉባልታ ዘመቻን ማካሄድ ነው። ከአሉባልታዎች ሁሉ ደግሞ በቀላሉ ሌሎችን ሊያስፈራራና ሊያሳምን የሚችለው ዘዴ አንድን ሰው ቶሎ ብሎ በሰርጐ ገብነት መፈረጅና የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ በጥርጣሬ እንዲታይ ማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ ያ- በሰርጐ ገብነትና በጥርጣሬ እንዲታይ የተደረገ ሰው የቱንም ያህል ለአገሪቱም ሆነ ለፓርቲው የሚጠቅም ሐሳብ ቢያቀርብ ተቀባይነት የማግኘት ዕድሉ እጅግ የጠበበ እየሆነ ይመጣል። በዚህም ምክንያት ብዙውን ጊዜ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል የሆኑ ሰዎች በሰርጐ ገብነት እንዳይጠረጠሩ ሊያደርጋቸው የሚችለው ዋናው ዘዴ ገዥውን ፓርቲ አክሮና አምርሮ መቃወም ሆኖ ስለሚታያቸው የቱንም ያህል አሳማኝ ሆኖ ቢያገኙት ገዥው ፓርቲ የሚሠራቸውን በጎ ሥራዎች ማድነቅና ማመስገን አይፈልጉም። ይህም በራሱ ተቃዋሚዎች ምክንያታዊ ፖለቲካ እንዳያራምዱና የአገራችን አጠቃላይ የፖለቲካ ባህልም ከጥላቻና ከፍጥጫ የፖለቲካ ባህል እንዳይወጣ አንድ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል።

የኢዴፓ ሰዎች ይህንን አደጋ በውል መገንዘብ በመቻላችን ጥቅምት 20 ቀን 1992 ዓ.ም ፓርቲያችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመሠርት እኛን ሊያፈርሰን የሚችለው ዋናው ጠላታችን በውስጣችን የሚፈጠር አሉባልታ ስለሆነ እሱን አጥብቀን መዋጋት አለብን የሚል አቅጣጫ አስቀምጠን ነበር ትግላችን የጀመርነው፡፡ በወቅቱ ይህን ወደፊት በውስጣችን ይፈጠራል ብለን በርግጠኛነት የገመትነውን የአሉባልታ ፈተና በአግባቡ ለመቋቋም የሚያስችለንን ስልትም ለማስቀመጥ ሞክረን ነበር፡፡ ይኸውም ብዙውን ጊዜ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ የአሉባልታ መነሻና ማቀጣጠያ ሆኖ የሚያገለግለው ስልት ይፈጸም የነበረው አንድን የፓርቲ አባል በሰርጎገብነት በመፈረጅ ስለነበር በዚህ ረገድ ሊፈጠር የሚችለውን ክፍተት በአግባቡ ለመዝጋት ከቻልን ችግሩ ይፈታል ብለን ገምተን ነበር፡፡

በወቅቱ የሰርጎገብነት ተልዕኮ የያዘን አንድ ሰው ወደ ፓርቲያችን ፈጽሞ እንዳይገባ ማድረግ የሚያስችል አቅምም ሆነ ስልት ሊኖረን እንደማይችል ርግጠኞች ስለነበርን ሌሎች ፓርቲዎች እንደሚያደርጉት ፓርቲያችንን ከሰርጎገብነት ነፃ እናደርገዋለን የሚል አጉል ቅዠት ውስጥ አልገባንም፡፡ መፍትሄ ሆኖ ያገኘነው በፓርቲያችን ውስጥ ምንም ዓይነት በሕግ ሊያስጠይቁ የሚችሉና ከሰላማዊ ትግል ስልት ውጭ የሆኑ ተግባራትን ላለመፈጸም ሲሆን፣ ይህንንም ማድረግ እስከቻልን ድረስ ወደ ፓርቲያችን ሰርጎ የሚገባ ሰው ቢኖር የከፋ ችግር ሊከሰት ስለማይችል ብዙ መጨነቅ እንደሌለብን ወሰን፡፡ ስለዚህ የሰርጎገብነት ተልዕኮ የያዙ ሰዎች ወደ ፓርቲያችን ሰርገው መግባታቸውን በተጨባጭ የምናውቅበት ሁኔታ ቢኖር እንኳ ለላካቸው አካል ሊያቀርቡት የሚችሉት መረጃ ሕጋዊና ሰላማዊ ተግባራትን የምናከናውን መሆኑን ስለሚሆን እንቅስቃሴአችንን በተግባር ሊያደናቅፍ የሚችል ሌላ ተግባር ላይ እስካልተሰማሩ ድረስ እንዳላየን ልናልፋቸው ይገባል የሚል አጠቃላይ አቅጣጫ አስቀመጥን፡፡

ይህ አቅጣጫችን በበታች መዋቅሮቻችን ውስጥ ብዙም ውጤታማ ያልነበረ ቢሆንም ቢያንስ ግን በፓርቲው አመራር ደረጃ የአሉባልታን በር ለማጥበብ በእጅጉ ረድቶናል፡፡ ነገር ግን የኢዴፓ ሰዎች አብዛኛዎቻችን "አብዮት ልጇን ትበላለች" ብሎ በሚያምነው የግራ ፖለቲካ ውስጥ ያላለፍንና የዚያ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህል ልምድ የሌለን ስለሆን የአሉባልታን አመጣጥ በመረዳት ረገድ የራሳችን ጉድለት ነበረብን፡፡ ይኸውም የኢዴፓ ሰዎች በወቅቱ በውል ያልተረዳነው ቁምነገር የፓርቲያችን እንቅስቃሴ በሰፋና በተጠናከረ ቁጥር የአሉባልታ ችግር ሊፈጠር የሚችለው በውስጣችን ብቻ ሳይሆን ከዚያ በሰፋ መጠን ከማንኛውም ውጫዊ አካል ጭምር መሆኑን ነበር፡፡ የፓርቲያችን እንቅስቃሴ እየሰፋና የኅብረተሰቡን ትኩረት እየሳበ ሲመጣ ከራሱ ከኅብረተሰቡ፣ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ከገዥው ፓርቲ፣ በስደት ከሚገኙ ፓርቲዎች፣

በአገር ውስጥና በውጭ ከሚገኙ መገናኛ ብዙኃን፣ በተለይም ደግሞ ከግል ጋዜጦች በየቀኑ እየተቀፈቀፈ በእኛ ላይ የሚነዛውን የአሉባልታ ማዕበል መቋቋም በቃላት ሊገለፅ በማይቻል ደረጃ አስቸጋሪ እየሆነብን መጣ፡፡

የሚገርመው እንዲህ ዓይነቱ አሉባልታ ለዓመታት ሳይቋረጥ የሚነዛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አሉባልታውን የሚሰማውና የሚያነበው አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍልም ሳይቋረጥ የአሉባልታው ታማኝ አድማጭና አንባቢ ሆኖ መቀጠሉ ነው፡፡ በተለይም በአንዳንዶቹ የግል ጋዜጦች የሚሠራጨው አሉባልታ በተደጋጋሚ ከእውነት የራቀ መሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች እየታየም ኅብረተሰቡ መቼም ጊዜ ቢሆን እነዚህን ጋዜጦች ተፀይፎ አልገዛም የሚልበት ወቅት አልነበረም፡፡ አዲስ ጫሂ ርእስ ይዘው በወጡ ቁጥር ሕዝቡ ተሽቀዳድሞ ስለሚገዛቸው ጋዜጦቹ የበለጠ የፈጠራ ወሬ እንዲጽፉ የሚያበረታታ እንጂ ከስህተታቸው እንዲታረሙ የሚገፋፋቸው ሁኔታ አልነበረም፡፡ እንዲያውም የተወሰኑ ለተወሰነ ጊዜ እየከሰሩ ለመሥራት አቅሙ የነበራቸው ጥቂት ጋዜጦች ካልሆኑ በስተቀር ብዙ ዜና ሳያጮሁና የፈጠራ ወሬ ሳይጽፉ የሞያውን ሥነ-ምግባር አክብረው ለመሥራት የሞከሩ ጋዜጦች አንባቢ አጥተው ከሥራ ውጭ ሲሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ በፊት ገጽ ላይ የሞያው ሥነ-ምግባር ከሚፈቅደው ውጭ ጫሂና አስደንጋጭ ዜና ይዞ የሚወጣ አዲስ ጋዜጣ ግን ለኅትመት በበቃበት በመጀመሪያው ቀን በሽሚያ የሚገዛበት ዕድል ሲኖረው ታይቷል፡፡

ከዚህ የምንረዳው በኅብረተሰባችን ውስጥ በተለይም ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አሉባልታ መጻፍ የሚያሸልም እንጂ የሚያስቀጣ ተግባር አለመሆኑን ነው፡፡ እጅግ ክቡር የሆነውና የትውልድን አስተሳሰብ በመቅረፅ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው የጋዜጠኝነት ሞያ የኅብረተሰብን አክብሮት የሚያገኘው አሉባልታ በመጻፍ ከሆነ ሕዝባችን በምን ዓይነት አደገኛ የአስተሳሰብ ችግር ውስጥ እንደሚገኝ ከዚህ በላይ በቂ ማሳያ ያለ አይመስለኝም፡፡ በእውነቱ አብዛኞዎቹ በአገሪቱ የምንገኝ የፖለቲካ መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና በፖለቲካ ጉዳይ በየአካባቢያችን ሐሳብ ስንለዋወጥ የምንውለው የኅብረተሰብ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜአችን የምናጠፋው የአስተሳሰብ አንድነትና ልዩነትን መሠረት ያደረገ ቁምነገር ላይ ስንነጋገር ሳይሆን የአገራችንን ችግሮች የበለጠ የሚያባብስ አሉባልታ ስናወራ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላው ዓለም ያልተለመደና ያልተሞከረ አዲስ ነገር በእኛ አገር እንዴት ተደርጐ ሊጀመር ይችላል የሚል ክርክር ሊያሥነሣ ቢችልም በእኔ እምነት ግን አገራችን ወደ አዲስና ጤናማ የፖለቲካ ባህል መሸጋገር ካለባት ከሁሉም አስቀድሞ የሚያስፈልጋት "የፀረ-አሉባልታ" ሕግና ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

አሉባልታ በአገራችን በተለይም በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ ምን ያህል ሥር የሰደደ በሽታ እንደሆነ ብዙ ማስረጃዎችን እየተነተኑ ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም ከእኔ የግል ልምድና ተመክሮ አንጻር ግን አሉባልታ ምን ያህል በከፋ ደረጃ በአገራችን እንደተንሰራፋ ለማስረዳት ብዙ ርቆ መሄድ አስፈላጊ መስሎ አልታዩኝም፡፡ ለአሉባልታ አስከፊ በሽታነት ለዛሬውም ሆነ ለመጭው ትውልድ ምስክርነት ለመስጠት ከማንም በላይ የእኔ የግል ሕይወት በቂ ማስረጃ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ለአለፉት ዐሥራ ሰባት ዓመታት በትግሉ ውስጥ ባለፍኩበት ሂደት በእኔ ላይ የተካሄደው የአሉባልታ ዘመቻ እግረ መንገዱን ችግሩ በአገራችን ምን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑን ሊያሳይ ይችላል ብዬ ስለ አመንኩ በእኔ ላይ የደረሰውን ሁሉ ላሥነብባችሁ ወድጃለሁ፡፡

ከአራት ዓመት በፊት በተወሰነ ደረጃ ከዚህ ጽሑፍ ጋር ተቀራራቢነት ያለው “የአረም እርሻ” የሚል መጽሐፍ አሳትሜ ለንባብ ማብቃቴ ይታወሳል፡፡ ሆኖም የአረም እርሻን በጻፍኩበት ወቅት በእኔ ላይ እየተካሄደ በነበረው “የልደቱን መጽሐፍ አታንብቡ” የሚል ከፍተኛ የአሉባልታ ዘመቻ ምክንያት በርካታ ሰዎች መጽሐፉን ሳያነቡ ቀርተዋል ብዬ ስላመንኩና በአሁኑ ወቅትም በፖለቲካ ሂደቱ ውስጥ የነበረውን ዕውነታ ለመረዳት በሕዝቡ ውስጥ የተሻለ መነሳሳት እየታየ በመሆኑ፣ በተጨማሪም በአለፉት አራት ዓመታት ከአሉባልታ ጋር በተያያዘ በርካታ አዳዲስ ሁኔታዎች ተከስተው ስላለፉ መጽሐፉን በዚህ ወቅት ለንባብ ማብቃቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነቱን በትግሉ ሂደት ውስጥም ቢሆን በግል ሕይወቴ ዙሪያ የተከሰተን ጉዳይ ዕድሜ ሰጥቶኝ በሕይወቴ የመጨረሻ ዘመን ላይ የግለ ታሪኬ /Biography/ አካል አድርጌ ብጽፈው ይመረጥ ነበር፡፡ ነገር ግን በአንድ በኩል ዛሬም ሆነ ነገ ሰዎች እንደኔ በፖለቲካው ሂደት በሚኖራቸው ተሳትፎ በተመሳሳይ ሁኔታ የአሉባልታ ተጠቂ እንዳይሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአሉባልታ አደገኛነት በአገራችን ፖለቲከኞችም ሆነ በሕዝቡ ዘንድ በአግባቡ መታወቅ ያልቻለ የፖለቲካ ባህላችን ብልሹና ደካማ ሆነ ወደፊትም እንደሚቀጥል በመገንዘብ ይህንን ጽሑፍ ለንባብ እንዲበቃ ማድረግ ወቅታዊና አስተማሪ መስሎ ስለታየኝ በአሁኑ ወቅት ልጽፈው መርጫለሁ፡፡ ጽሑፉ እኔ በፖለቲካ ሂደቱ ውስጥ ያለፍኩበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ በሰባት አንቀጾች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ በጽሑፉ ውስጥ የሌሎች ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ድክመት ለመተቸት ሙከራ ሳደርግ በትግሉ ውስጥ ለተከሰቱት አንዳንድ ድክመቶችና ችግሮች ሌሎችን ብቻ ሳይሆን ራሴንም የተጠያቂነት ድርሻ ያለኝ አድርጌ የማይ መሆኔን፣ በጽሑፉ ውስጥ የአንዳንድ ግለሰቦችን ስም ለማንሳት የተገደድኩትም ከግለሰቦቹ ጋር የተለየ የግል ቂምና ጠብ ኖሮኝ ሳይሆን በትግሉ ውስጥ ያሉትን ድክመቶችና ችግሮች አንባቢ በአግባቡ እንዲገነዘባቸው

ለማድረግ የግለሰቦቹ ስም መጠቀሱ የግድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን አንባብያን በቅድሚያ ሊገነዘቡት ይገባል እላለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ "በአብዛኛው" "በከፊል" "ጥቂት" "ብዙዎች" "አንዳንድ" "በዋናነት" "ሁሉም" የሚሉትና እነዚህን የመሣሰሉት ቅጽሎች (Adjectives) አንባቢን ወደ አልተፈለገ አጠቃላይ ፍረጃ (Generalization) ላለማስገባት ተብለው ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆናቸው በአንባብያን ዘንድ ልዩ ትኩረት ቢሰጣቸው ተገቢ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመጽሐፉ የተለያዩ ክፍሎች በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው "ሕዝብ" የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በፖለቲካው ሂደት ቢያንስ የደጋፊነትና የተቃዋሚነት የጎላ የተሳታፊነት ሚና ያለውን በቁጥር ውስን የሆነ የኅብረተሰብ ክፍል እንጂ በቀጥታ የአገሪቱን አጠቃላይ ሕዝብ የሚወክል ተደርጎ ባይታይ ይመረጣል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ለትምህርት (Academic) እና ለምርምር ጉዳይ ታስቦ ያልተጻፈ በመሆኑ ምክንያት የምርምር ጽሑፍ መመዘኛዎችን አሟልቶ ያልቀረበና ሥነ-ጽሑፋዊ ይዘቱም የሚገባውን ያህል ጥንቃቄ ያልተደረገበት በመሆኑ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅሁ አሉባልታን አዳምጦ የተሳሳተ ግንዛቤ ከመያዝ ይልቅ አንብቦ የመረዳትን ጥቅም ከልብ በመገንዘብ መጽሐፉን ማንበብ ለጀመራችሁ አንባብያን በሙሉ መልካም ንባብ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፡፡

አመሰግናለሁ፡፡

ኢዮፒ

## *ምዕራፍ አንድ*

## *አሉባልታ በቅድመ ቅንጅት*

እንደ አብዛኛው የአገሬ ሕዝብ አገሬን የምወድ ሰው መሆኔ በተለምዶ አነጋገር መረገም ሳይሆን መታደል መሆኑን ተጠራጥሬ አላውቅም፡፡ ከአብዛኛው የአገሬ ሕዝብ በተለየ ፖለቲካን አፍቃሪ መሆኔ ግን ርግማን ይሁን መታደል እስካሁን ርግጠኛ አይደለሁም፡፡ በርግጠኛነት ልናገር የምችለው ግን በፖለቲካ ተሳትፎዬ ምክንያት የሰው ልጅ ከውድ ሕይወቱ በመለስ ሊያጣቸው የሚችሉ በርካታ ጠቃሚ ጉዳዮችን በአንፃራዊነት ለጊዜውም ይሁን እስከወዲያኛው ለማጣት ተገድጃለሁ፡፡ ነገር ግን የፖለቲካ አፍቃሪና ተሳታፊ በመሆኔ አንድም ቀን ተፀፅቼ አላውቅም፡፡ የኅሊና ሰላምና በእራስ የመተማመን ስሜትም ከእኔ ርቀው ባያውቁም - ሰው ነኝና በትግሉ ሂደት በተፈራረቁብኝ በርካታ ችግሮች መጠን ሞራሌም ሆነ ተስፋዬ ሲወጡና ሲወርዱ መኖራቸው ግን አይካድም፡፡

የተቃውሞ ትግሉን የተቀላቀልኩት ኢህአዴግ አገሪቱን በተቆጣጠረ በዓመቱ 1984 ዓ.ም ላይ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ትግሉን ለመቀላቀል የበቃሁት በትግሉ ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ በማድረግ እንዲህ እንደ ዛሬው ታዋቂና አነጋጋሪ (controversial) የፖለቲካ ሰው እሆናለሁ ብዬ አስቤና አቅጄ ሳይሆን በወቅቱ በንግድ ሥራ ላይ ስለነበርኩ ቢያንስ እንደ አንድ ዜጋ ትግሉን በገንዘብ መዋጮ ማገዝ ይጠበቅብኛል ብዬ በማሰብ ነበር፡፡ ነገር ግን እኔ ካሰብኩት በላይ ጥሪው ከባድ ነበርና እንደ ወራጅ ውሃ እያሳሳቀ ትግሉ በውስጡ አሰመጠኝ፡፡ እኔም አንድ ጊዜ የጨበጥኩትን ነገር በቀላሉ ካለመልቀቅ መንቻካ ባህሪዬ በመነጨ ያለስስት ሁለመናዬን ለፖለቲካው ሥራ በማዋሌ በኢኮኖሚ ረገድ ኑሮዬ ቆርቁዟል፤ ከሌሎች ጓደኞቼ በተለየ እስካሁን ትዳር መመሥረትና ልጅ መውለድ ሳልችል ቀርቻለሁ፤ በፖለቲካ ምክንያት አምስት ጊዜ ታስሬ የተፈታሁ ቢሆን በነበረብኝ የሥራ ጫናም በጤናዬ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ደርሷል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ባሳለፍኩት የትግል ሂደት ባልተቋረጠ ሁኔታ ሞራሌንና ስብእናዬን በመፈታተን ረገድ ከፍተኛ ጉዳት ሲያደርሱብኝ የኖረውና አሁንም እያደረሰብኝ ያለው አሉባልታ ነው፡፡ አሉባልታ በምክንያትና በተጨባጭ መረጃ ተደግፎ የማይቀርብ፣ ዛሬ አንድ ቦታ ላይ በአንድ ሰው ተጭሮ ነገ እንደቋያ እሳት አገሩን የሚያዳርስ ፈጣንና አደገኛ የጥፋት መሣሪያ በመሆኑ እንደ እኔ ያለ የራሱ ሬዲዮ ጣቢያም ሆነ ጋዜጣ የሌለው ተራ ግለሰብ በቀላሉ ሊቋቋመው የሚችል ተራ ባላንጣ አልሆነም፡፡

ትግሉን በተግባር ከመቀላቀሌ በፊትና ከተቀላቀልኩም በኋላ ለተወሰኑ ጥቂት ዓመታት በአሁኑ ወቅት በርካታ ሰዎች እንደሚያስቡት እኔም የአገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች በኢህአዴግ ዙሪያ ብቻ ያሉና ኢህአዴግ ከሥልጣን ቢወገድ ችግሮቻችን ሁሉ ከኢህአዴግ ጋር አብረው በነው እንደሚጠፉ አድርጌ አስብ ነበር፡፡ በሂደት ይህ አስተሳሰብ ትክክል እንዳልሆነና ችግሩ በገዥው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በጎላ መልኩ በተቃዋሚው ጐራና በአጠቃላይም በሕዝባችን ውስጥም ያለ ችግር መሆኑን ከተገነዘብኩ በኋላ ግን በተቃዋሚው ውስጥ ካሉ አንዳንድ አስተሳሰቦችና ግለሰቦች ጋር መጋጨት መጀመሬ ውሎ አላደረም፡፡ ያለንበት ጊዜ ከጥንቱ የእነ ልጅ ኢያሱ ዘመን የተለየና የራቀ ነው ብዬ በማሰብ በዚያን ወቅት በእኔና በሌሎች መካከል የሚፈጠሩት የሐሳብ ግጭቶች በዴሞክራሲያዊ መድረክ በውይይትና በክርክር ይፈታሉ የሚል የጠነከረ እምነት የነበረኝ ቢሆንም እየቆየሁ ግን ዛሬም እንደቀድሞው የአገራችን የፖለቲካ ባህል ልዩነትን የሚፈታበት ሳይሆን የሚጨፈልቅበት የተለመደ ስልት አሉባልታ መሆኑን እየተገነዘብኩ መጣሁ፡፡

የአሉባልታ ጥቃት ሰለባ መሆን የጀመርኩት በአሁኑ ወቅት መኢአድ ተብሎ በሚታወቀውና ቀድሞ መዐሕድ ተብሎ ይጠራ በነበረው ፓርቲ አባል በነበርኩበት ወቅት ነበር፡፡ በዚያ ገና የ23 ዓመት ወጣት በነበርኩበት ወቅት አባል በሆንኩበት ፓርቲ የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና የወጣት ክንፉ ሊቀመንበር ሆኜ ለአንድ ዓመት ያህል ከሠራሁ በኋላ የፓርቲውን የወደፊት እንቅስቃሴ በምን ዓይነት መንገድ ማሻሻልና ማጠናከር እንደሚገባ በተፈጠረ የሐሳብ ልዩነት በወጣት ክንፉና በፓርቲው አመራሮች መካከል አለመግባባት ተከሰተ፡፡ በወቅቱ በቀኝ-አዝማች ነቅዓጥበብ በቀለ ይመራ የነበረው የፓርቲው አመራር ከወጣት ክንፉ ይነሳ የነበረውን ተገቢ የሆነ ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ የሚያስችለው ፍላጐትም ሆነ አቅም ስላልነበረው "የወጣት ካውንስሉ መሪዎች መዐሕድን ለማፍረስ ሰርገው የገቡ አባላት ናቸው" የሚል ቅስቀሳ ጀመረ፡፡ በወቅቱ በዚያ ፓርቲ ውስጥ ትግሬ የሆነ ሰው ሁሉ የህውሃት አባል እንደ ሆነ ተደርጐ ይታይ ስለነበረም "ልደቱ በእናቱ ትግሬ ነው"፣ አንዳንድ ጊዜም "ኤርትራዊ ነው" የሚል አሉባልታ መሰራጨት ጀመረ፡፡ ይህንን ወሬ በፓርቲው ውስጥ መስማት የቻለው ሰውም በወቅቱ ያነሳው የነበረው ጥያቄ "ትግሬ ቢሆን ምን ችግር አለው?" የሚል ሳይሆን "በእውነቱ ልደቱ የትግሬ ትውልድ አለው ወይስ የለውም?" የሚል ነበር፡፡ በነገራችን ላይ "ልደቱ ትግሬ ነው" የሚለው ወሬ በቅርቡ ቅንጅት ውስጥ ችግር በተፈጠረበት ወቅትም አንድ አነጋጋሪ ጉዳይ ሆኖ "ልደቱ ስሙን ቀይሮ ነው እንጂ የቀድሞ ስሙ ገብረመድኀን ነበር" ተብሎ ኢንተርኔት ላይ ሳይቀር ይጻፍ ነበር፡፡

በመዐሕድ ውስጥ የተፈጠረው አለመግባባት በውይይት መፈታት ባለመቻሉ በመጨረሻ ከመቶ ሃያ በላይ የምንሆን የወጣት ካውንስሉ አባላት ተቃውሞአችንን ለመግለፅ በድርጅቱ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የእረሃብ አድማ መታን፡፡ የድርጅቱ አመራሮች ለተፈጠረው ችግር ተገቢውን መፍትሄ እንደሚሰጡ ቃል ገብተው የረሃብ አድማው ከተበተነ በኋላ በሌላ የስብሰባ ቀጠሮ በነበረን ቀን እንደገና ተመልሰን ወደ ድርጅቱ እንዳንገባ በር ተዘጋብን፡፡ በዚህም ምክንያት የተገባው ቃል እንዲከበር በመጠየቅ ለሁለተኛ ጊዜ የድርጅቱ ግቢ ውስጥ የረሃብ አድማው ተጀመረ፡፡ በውይይት ችግሩን ለመፍታት ፍላጐት ያልነበራቸው የወቅቱ የድርጅቱ መሪዎችም ፖሊስ በመጥራት የረሃብ አድማው በኃይል እንዲበተንና የወጣት ካውንስሉ መሪዎችም እንድንታሰር አደረጉ፡፡ ከእሥር ተፈተን የደረሰብንን ግፍ ለሕዝቡ ለማጋለጥ በማሰብ ሆቴል ተከራይተን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት አሥር ደቂቃ ሲቀረን “ጋዜጣዊ መግለጫ የሚሰጡት መዐሕድን ሊያፈርሱ ነው” ተብሎ የተነገረው የሆቴል ባለቤት የከፈልነውን ቀብድ እንኳ ሳይመልስልን ወደ ሆቴሉ እንዳንገባ ከለከለን፡፡ ሕገ-ወጥ የሆኑ ሰዎች ረብሻ ሊፈጥሩብኝ ነው በማለት ፖሊስ ጠርቶም እንደገና አሳሰረን፡፡ የመዐሕድ መሪዎች በማግሥቱ “ድርጅቱን ለማፍረስ የሞከሩ ሰርጐገቦች ተመነጠሩ” የሚል መግለጫ በጋዜጣ ጭምር አሳትመው ለሕዝብ አሰራጨብን፡፡ እኔን በሚመለከትም ወደ ድርጅቱ ሠርጌ የገባሁ የደኅንነት አባል እንደሆንኩ ተደርጐ በሰፊው ተወራ፡፡ በወቅቱ ከአንድ ብዙም ተነባቢ ካልነበረ ጋዜጣ በስተቀር በየጋዜጣው ዝግጅት ክፍል በአካል እየሄድን እውነቱን ለሕዝብ እንዲያቀርቡ ብንማጸንም በእኛ ላይ የደረሰውን በደልና አፈና ደፍሮ መጻፍ የቻለ አንድም ጋዜጣ ማግኘት ሳንችል ቀረን፡፡ በዚያ ወቅት ነበር በፖለቲካ ባህላችን የምናየው ችግር ምን ያህል ሥር የሰደደ የኅብረተሰብ ችግር እንደሆነና ሕዝቡም ስለተቃዋሚ ፓርቲዎችና ስለግል ጋዜጦች የተዛባ ግንዛቤ እንዳለው ይበልጥ እየተረዳሁ የመጣሁት፡፡

በዚያን ወቅት በፖለቲካው መድረክ ያሉ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ምሁራን የሚባሉ ሰዎች፣ ጋዜጣና ሬዲዬ ጣቢያ የመሳሰሉ መገናኛ ብዙኃን ላይ የሚሠሩ ጋዜጠኞች ተራ ውሸት ይዋሻሉ ብዬ ስለማላስብ ፖለቲካው ውስጥ ገብቼ የማዬው ነገር ሁሉ ህልም እንጂ እውን አልመስለኝ እያለ እቸገር ነበር፡፡ ታዲያ በዚያን ጊዜ - እንደ ዛሬው በአሉባልታ ቆዳዬ የደነደነ ስላልነበረም ትንሽ ነገር ያለአግባብ በተወራብኝ ቁጥር ከመናደድ አልፌ እንቅልፍ አጥቼ የማድርበት ጊዜ ይበዛ ነበር፡፡ ሰዎች እውነቱን እንዲያውቁ ብዬ ለማስረዳት የማጠፋው ጉልበትና ጊዜም ቀላል አልነበረም፡፡ እየቆየሁ ስሄድ ግን በየቀኑ እየተፈጠረ የሚነዛውን አሉባልታ ሁሉ ለማስተባበል መሞከር ራሱን የቻለ የሙሉ ጊዜ ሥራ እንደሚሆንና በዚያም ሁኔታ ፖለቲካውን በአግባቡ ማካሄድ እንደማይቻል እየተረዳሁ ስለመጣሁ አሉባልታውን የማስተባበሉን ጉዳይ ለጊዜና ለሂደት

እየተውኩ የፖለቲካ ሥራው ላይ ማተኮሩን መረጥኩ፡፡ ቀስ በቀስም ስለሚወራብኝ አሉባልታ የሚሰማኝ የንዴት ስሜት እየቀነሰ መጣ፡፡ በነገራችን ላይ በዚያ ጊዜ እኔን በሰርጐገብነት ሲከሱ የነበሩት የመዐሕድ መሪ ቀኝ-ዝማች ነቅዓ-ጥበብ በቀለ ከወቅቱ የደህንነት ኃላፊ ከአቶ ክንፈ ገ/መድኅን ጋር  ወዳጅነት እንደነበራቸው ያወቅሁት በቅርቡ “የጋዜጠኛው ማስታወሻ” የሚለውን መጽሐፍ ሳነብ ነው፡፡ በዚያ መጽሐፍ ላይ የ80 ዓመት አዛውንት የነበሩት ቀኝ-አዝማች - “ሕዝቡ እንዲያምነኝ ትንሽ አስረህ ብትለቀኝ ምንአለበት” እያሉ አቶ ክንፈን ይጠይቁ እንደ ነበር ሳነብ፣ ቀኝ-አዝማቹ በወቅቱ እኔን “አንተ ጐረምሳ እንታገል እያልክ አትበጥብጠኝ - የኔ ኃላፊነት ፕሮፌሰር ዐሥራት ከእሥር ተፈተው ድርጅቱን እስኪረከቡኝ ድረስ ሻማዋ እንዳትጠፋ መጠበቅ ነው” ይሉኝ የነበረውን አስታውሼ ተገረምኩ፡፡

ከላይ በገለፅኩት ሁኔታ ከመዐሕድ ከተለዩን በኋላ በወቅቱ “አማራጭ ኃይሎች” እየተባለ ይጠራ በነበረው የተቃዋሚ ፓርቲዎች ስብስብ ውስጥ የነበሩ ሰዎች በትግሉ ውስጥ የነበረንን ሚናና ማንነታችን ያውቁ ስለነበር ቢሮአቸውን እንድንጠቀምበት ፈቅደውልን ከነሱ ጋር አብረን መሥራት ጀመርን፡፡ በዚያ ስብስብ ዙሪያ የነበሩት ሰዎች በሕዝብ ውስጥ ትልቅ ስምና ዝና ያላቸውና በትምህርት ደረጃቸውም አንቱ የተባሉ  ስለነበሩ የተሻለ ያታግሉናል ብለን ጠብቀን የነበረ ቢሆንም ግምታችን ትክክል ሆኖ ሳናገኘው ቀረን፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብረናቸው ለሦስት ዓመታት ያህል ብንሰራም መግለጫ ከመጻፍ አልፎ ሕዝቡን እያነቁና እያደራጁ ትግሉን የማጠናከር አቅሙም ሆነ ፍላጐቱ እንደሌላቸው ስንረዳ በእነሱ ተስፋ ቆረጥንና ከአንድ ዓመት ዝግጅት በኋላ ከመዐሕድ ቀደም ሲል የተባረርነውን ወጣቶች ብቻ ሳይሆን በርካታ ከተለያዩ አቅጣጫ መሰባሰብ የቻልን ወጣቶች ጥቅምት 20 ቀን 1992 ዓ.ም ኢዴፓን አቋቁመን ትግሉን በአዲስ መንፈስና ስልት ጀመርነው፡፡

ካለፍንበት የትግል ሂደት የተገነዘብነውን ልምድ መሠረት በማድረግም ትግላችን በሦስት አቅጣጫ - ማለትም አገርን የማይጠቅሙ የገዥውን ፓርቲ ፖሊሲዎችና አስተሳሰቦች መታገል፣ በተቃዋሚው ጐራ ውስጥ የሚታዩ ለትግሉ መጠናከር እንቅፋት የሆኑ አመለካከቶችንና አሠራሮችን መታገል፣ በሕዝባችንም ውስጥ ለረዥም ጊዜ ሥር ሰደው የሚገኙ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንቅፋት የሆኑ ኋላቀር የፖለቲካ አመለካከቶችን መታገል መሆኑን ይፋ አደረግን፡፡ በዚህ ጊዜ አዲስ የአሉባልታ ዘመቻ ከየአቅጣጫው በአዲስ መልክ መፈንዳት ጀመረ፡፡ በአንድ በኩል በመዐሕድ አካባቢ የነበሩ ሰዎች ቀደም ሲል በኛ ላይ የፈጸሙትን በደል በማስታወስ በኢዴፓ ውስጥ ያሉ ሰዎች ወደፊት ከተጠናከሩ ለኛ በጎ አመለካከት አይኖራቸውም በሚል ስጋት “ኢዴፓ በወያኔ ሆን ተብሎ የተፈጠረ ፓርቲ ነው” የሚል ቅስቀሳ ሲጀምሩ፣ በሌላ

በኩል ደግሞ እንደ ኢህአፓ የመሰሉት ድርጅቶች አገር ውስጥ ያሉ አንዳንድ የግል ጋዜጦችን በመጠቀም ኢዴፓ ከጀርባው ልዩ ተልዕኮና አጋዥ ኃይል ያለው በውጭ ኃይሎች የተቋቋመ ፓርቲ እንደሆነ አስመስሎ የሚያቀርብ ወሬ ማሠራጨት ጀመሩ፡፡

በተለይም "ኢትኦጵ" በመባል ይታወቅ የነበረው ጋዜጣ በእያንዳንዱ የጋዜጣው ሳምንታዊ እትም በተለያዩ የብዕር ስም ፀረ-ኢዴፓ የሆነ ዘመቻ ጀመረ፡፡ በአንድ እትሙም ላይ ኢዴፓን ከጀርባ ሆነው የሚያንቀሳቅሱት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ አቶ ብርሃነ መዋና አቶ ክቡር ገናን የመሳሰሉ ሰዎች እንደሆኑ አድርጐ ፃፈ፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህ የተጠቀሱ ሰዎች እንኳን ከጀርባ ሆነው ኢዴፓን ሊመሩና - እነዚህ ሰዎች ውስጥ ሁለቱን ማለትም ዶ/ር ብርሃኑንና አቶ ብርሃነ መዋን ፓርቲውን ከማቋቋማችን በፊት ቢሮአቸው ድረስ ሄደን የፓርቲያችን መሪዎች እንዲሆኑ በተደጋጋሚ ለምነናቸው ፈቃደኛ ሊሆኑ አልቻሉም ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በወቅቱ የሠጡን መልስ "እኔ በብዙኃን ድምፅና አስተሳሰብ ልገዛ የማልችል ሰው ስለሆንኩ ኢትዮጵያ ውስጥ የፓርቲ አባል ሆኜ መሥራት አልፈልግም" የሚል ሲሆን፣ አቶ ብርሃነ መዋ ግን በወቅቱ የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ስለነበሩ የሰጡን መልስ "ወደፊት ሁኔታዎች ሲመቻቹልኝ እቀላቀላችኋለሁ - አሁን ግን የንግድ ምክር ቤቱን ኃላፊነት ለቅቄ ልመጣ አልችልም" የሚል ተገቢ መልስ ነበር፡፡

ዞሮ ዞሮ ኢዴፓን ከመሠረትን በኋላ ለሚነዛው አሉባልታ ብዙም ትኩረት ሳንሰጥ የፓርቲያችንን ሥራ ማጠናከሩ ላይ ትኩረት አድርገን መሥራት ቀጠልን፡፡ ፓርቲያችን የተቋቋመበት ወቅት ብሔራዊ ምርጫ በአገሪቱ ሊካሄድ የተቃረበበት ወቅት ስለነበር በተለያዩ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና በየክርክር መድረኩ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ እየተገኘን ዓላማችንን ለሕዝብ ማስተዋወቅ ጀመርን፡፡ ከግምታችን በፈጠነ አጭር ጊዜ ውስጥም በአገር ደረጃ መታወቅ ቻልን፡፡ በዚያው መጠን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚወራው አሉባልታም የበለጠ እየተጠናከረ መጣ፡፡ አብዛኞዎቹ ተቃዋሚዎች ኢዴፓ ወያኔን ዴሞክራት ለማስመሰል የተፈጠረ ፓርቲ ነው የሚለውን ቅስቀሳ አጠናክረው ሲቀጥሉበት፣ ሕዝቡ ውስጥ ደግሞ የተዘበራረቀ ወሬ መናፈስ ጀመረ፡፡ በተለይም እኔን በሚመለከት ከኢህአዴግ አፈንግጦ የወጣ ሰው ነው፣ የሲ አይ ኤ ወኪል ነው፣ ጀርመን አገር የነበረ የንጉሣዊ ቤተሰብ ነው፣ ከአሜሪካን አገር የመጣ የቀድሞ የኢህአፓ አባል ነው፣ ጉንደሬ ነው፣ ጉጃሜ ነው፣ ትግሬ ነው የሚሉና የተለያዩ መሰል ወሬዎች መናፈስ ጀመሩ፡፡ በወቅቱ እህቶቼና ጓደኞቼ በየቀኑ ቢያንስ ሦስትና አራት ስለ እኔ በየታክሲው የተወራ አዲስ ነገር ማታ ማታ ይነግሩኝ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜም ሰዎች ስለ እኔ

የዚህ ዓይነት የፈጠራ ወሬ በየታክሲውና በየካፍቴሪያው የሚያወሩት በአካል እናውቀዋለን እያሉ ስለነበር ጓደኞቼና ዘመዶቼ ከሰዎች ጋር በሐሳብ የሚጋጩበት አጋጣሚም ብዙ ነበር።

የፓርቲያችን ዕውቅና እየገነነ ሲመጣ ከተቃዋሚው ጐራና ከሕዝቡ በተጨማሪ የገዥው ፓርቲ አባላትም ለራሳቸው በሚጠቅም መልኩ አሉባልታ የማሠራጨቱን ተግባር ተቀላቀሉት። ተቃዋሚውን ጐራ ይደግፋል በሚባለው ኅብረተሰብ ውስጥ "ልደቱ የኛ ሰው ነው" እያሉ በማውራት ተቃዋሚዎች የሚያራምዱትን አሉባልታ የማጠናከር ሥራ ሲሠሩ፣ ለራሳቸው አባላትና ደጋፊዎች ደግሞ "ልደቱ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍልን እንኳ በአግባቡ መጨረስ ያልቻለ ሥራ ፈት ዱርዬ ነው" እያሉ መቀስቀስ ጀመሩ። ተወልጄ ባደግሁበት አካባቢ ደግሞ በወቅቱ ተሰርቆ የነበረ "አፍሮ-አይገባ" በመባል የሚታወቅ የቤተክርስቲያን መስቀል ስለነበር በዚያ መስቀል ሥርቆት የእኔ እጅ እንዳለበትና በአጭር ጊዜም ልታሰር እንደምችል ማስወራት ጀመሩ። እንዲያውም አንድ ቀን ምሽት ላይ በፋና ሬዲዮ ጣቢያ ስሜን በግልጽ ሳይናገሩ "ከዚህ ቀደም በታቦት ሽያጭ ተጠርጥረው ታስረው የነበሩ ሰዎች የፖለቲካ መሪዎች ሆነው ብቅ ብለዋል" በማለት በአድማጭ አስተያየት ስም እንዲነገር ተደረገ። አንዳንድ በወቅቱ የኢህአዴግ አባላት የነበሩ ወዳጆቼም እኔን ለማሰር በመንግሥት በኩል እንደተወሰነ ከከፍተኛ ባለሥልጣናት እንደሰሙ በመግለፅ ከቻልኩ ወደ ውጭ አገር እንድሰደድ ምክር ሰጡኝ። እኔም ለመታሰር ይቅርና ለመጠርጠር የሚያበቃኝ ምንም ነገር በዙሪያዬ እንደሌለ በራሴ በመተማመን ለአሉባልታው ብዙም ትኩረት ሳልሰጠው ሥራዬን ቀጠልኩ።

በዚህ ሁሉ የአሉባልታ ውዥንብር ውስጥ ሆነን በ1993 ዓ.ም በተካሄደው የአካባቢ ምርጫ ከሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች የበለጠ ከ2800 በላይ እጩ ተወዳዳሪ በአዲስ አበባ በማቅረብ በምርጫው ከፍተኛ ተሳትፎ ማድረግ ቻልን። በተመሠረትን በስምንት ወራት ውስጥም በዚያ ምርጫ ሁለት የፓርላማ መቀመጫና ዐሥራ አራት የአዲስ አበባ ምክር ቤት መቀመጫ በማሸነፍ የሕዝብ ውክልና አገኘን። ከሁሉም በላይ በዚያ ምርጫ ላይ ባካሄድነው ሁለንተናዊ ተሳትፎ አዲስ የፖለቲካ መነቃቃት በሕዝቡ ውስጥ መፍጠር ቻልን። በአንድ በኩል በምርጫ ጉዳይ ላይ ቅድመ-ሁኔታ እያስቀመጡ ራሳቸውን ከምርጫ ሂደት ሲያገልሉ የነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በእኛ ተሳትፎ ማደግ ተደናግጠው የተሻለ ለመሥራትና በምርጫ ሂደት ለመሳተፍ የተገደዱ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ ትግልም ሆነ በምርጫ ለውጥ ሊመጣ አይችልም ብሎ ያስብ የነበረው ሕዝብ ነባራዊ አስተሳሰቡን እንዲፈትሽና በምርጫ ለመሳተፍ እንዲነሣሳ ለማድረግ ተቻለ። ኢዴፓ የፈጠረውን አዲስ ተነሳሽነት በገሃድ ማየት የቻሉና ያን ክስተት የበለጠ ማበረታታት ይገባቸው የነበሩ በርካታ የተማሩ ሰዎችም እኛ

ማድረግ ያልቻልነውን እንዴት ኢዴፓዎች ሊያደርጉት ይችላሉ በሚል ክፉ ቅናት ይመስላል-- “ልደቱ ኢህአዴግን እንደዚህ በድፍረት በመድረክ የሚከራከረውና የሚቃወመው ምንም ዓይነት ችግር እንደማይደርስበት ከኢህአዴግ ዋስትና ተሰጥቶት ነው” በማለት በሰፊው ማውራትና ማስወራት ጀመሩ። በተለይም ኢዴፓ የአልጀርሱን ስምምነት በመቃወም በሕዝብ ውስጥ ሰፊ ሥራ ሠርቶ መስቀል አደባባይ ላይ የተሳካ ሕዝባዊ ስብሰባ ካካሄደና የ140ሺ የሕዝብ የተቃውሞ ፊርማ አሰባስቦ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ለአፍሪካ ኅብረት ከላከ በኋላ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግን መታገላቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ኢዴፓን በማዳከም ተግባር ላይ ተጠመዱ።

በዚህ ሁኔታ የተወሰነው ሕዝብ በየቀኑ በሚሰማው የፈጠራ ወሬ ምክንያት በጥርጣሬ እያየን፣ አብዛኛው ሕዝብ ደግሞ እያደነቀንና እየደገፈን እንቅስቃሴያችንን የበለጠ እየተጠናከረ በመጣበት 1993 ዓ.ም ላይ የህወነትን መከፋፈል ተከትሎ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የተፈጠረውን ብጥብጥ ምክንያት አድርጎ ኢህአዴግ የመጀመሪያውን ኃይለኛ ምት አሳረፈብን። በተፈጠረው ብጥብጥ ተሳትፈዋል በሚል 112 የፓርቲያችንን ቁልፍ አባላትና ከአመራሩ ውስጥ እኔና አቶ ሙሼን ጨምሮ ከየመንገዱ አፍሶ አሰረን። እኔም አመፁን በተንቀሳቃሽ ስልክ ያስተባበርከውና የመራኸው አንተ ነህ ተብዬ ለሁለት ወር ከሃያ ቀን ሸዋሮቢት ታሰርኩ። የእስሩ ጊዜ አጭር ቢሆንም ለመጀመሪያው አምስት ቀናት ቀን ሁለት ዳቦ እየበላሁ፣ ለ50 ቀናት ያህል የት እንደታሰርኩ ሳይታወቅና ፍርድ ቤት ሳልቀርብ፣ ለ50 ቀናት የለበስኩትን ልብስ ሳልቀይርና ምንጣፍና የሌሊት ልብስ ሳይኖረኝ፣ በአንድ ክፍል ውስጥ 520 እስረኞች እግራችንን ዘርግተንና በጀርባችን ተንጋለን መተኛት በማንችልበት ሁኔታ ታስሬ፣ የወባ በሽታ ታምሜ ከሞት ከተረፍኩና ዐሥራ ስድስት ኪሎ ግራም ክብደት ከቀነስኩ በኋላ ምንም ዓይነት ተጨባጭ መረጃ ሳይቀርብብኝ በ5000 ብር ዋስትና በፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈታሁ። ያ - የእስር ቤት ቆይታዬ ሥርዓቱን መታገሌ ትክክልና የሚገባ መሆኑን የበለጠ አረጋገጠልኝ። በእስር ቤት ቆይታዬ ሥርዓቱ ምን ያህል የሰብዓዊ መብት አያያዝ ጉድለት ያለበት መሆኑን ከመረዳቴም በላይ እስር ቤት ገብቼ እስከምወጣ ድረስ በዙሪያዬ በአጃቢነት የነበሩ የጸጥታ ሠራተኞች ይናገሩትና ይሠሩት የነበረው ነገር ሁሉ አገሪቱ ምን ያህል በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መሆኗን የሚያረጋግጡልኝ ነበሩ።

በተፈታሁበት ዕለት በቴሌቪዥን ስታይ እኔ መሆኔን ለማወቅ በሚያስቸግር ደረጃ ተበሳቁዬ ስለነበር ሕዝቡ ስለ እኔ ከፍተኛ ሐዘን ተሰማው። ይህም በራሱ በእኔም ላይ ሆነ በኢዴፓ ላይ የሚወራውን አሉባልታ ለጊዜው ያስታገሰው ቢሆንም በዚያም ወቅት ቢሆን “ልደቱ ኢህአዴግን እንደልቡ የሚናገረው ዋስትና ተሰጥቶት ነው” ሲሉ የነበሩት አሉባልተኞች

ቅኝታቸውን ወዲያውኑ ቀየር አድርገው "ልደቱ የታሰረው ሆን ተብሎ እውነተኛ ተቃዋሚ መስሎ እንዲታይ ተብሎ ነው" በማለት ማውራት ጀመሩ። በወቅቱ እንዲህ ዓይነቱን ወሬ በእኔ ላይ ያስወሩ የነበሩት ሰዎች በርግጥም በዚያን ወቅት ኢህአዴግን ፊት ለፊት መቃወም ይቅርና የኢህአዴግን መሪዎች በዓይናቸው አተኩረው ለማየት የሚፈሩ ነበሩ። አንዳንዶቹ በጣም ደፍረናል በሚሉበት ወቅትም ኢህአዴግን በጽሑፍ ለመተቸት የሚሞክሩት በእውነተኛ ስማቸው ሳይሆን በብዕር ስም ነበር። በተለይም አብዛኛዎቹ ምሁራን የሚባሉ ሰዎች የራሳቸው ድክመትና ፍርሀት ለመደበቅ ሲሞክሩ የሚታዩት እኛን የኢህአዴግ መልክተኞች አስመስለው በማውራት ነበር።

ከእሥር ተፈተን ወደ ፓርቲያችን ስንመለስ ብዙ ነገሮች ተለዋውጠው፣ በፓርቲው ውስጥ እኛ የማናውቀው መዋቅር ተፈጥሮና የፓርቲውን እንቅስቃሴ ተቆጣጥሮት አገኘን። ተሠርቶ የጠበቀን መዋቅር ጤናማ እንዳልሆነ በመገመት ነገሮች ከመታሰራችን በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ለማድረግ ስንሞክር "አዲሱ መዋቅር መፍረስ የለበትም" በሚል ፓርቲው ውስጥ እኛን የሚቃወም አንድ ራሱን የቻለ አንጃ ተፈጥሮ ብቅ አለ። የፓርቲውን አሠራርና የዲሲፕሊን ደንብ በመጠቀም ይህንን አንጃ ከአንድ ዓመት ትግል በኋላ አሸንፈን ፓርቲውን ወደነበረበት መመለስ ቻልን። በዚህ ሂደት ተሸናፊ ሆነው ከፓርቲው የተባረሩት ዐሥራ አንድ ሰዎችና ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከፓርቲው የተለዩት የአሁኖቹ የአንድነት ፓርቲ አባላት አቶ ግዛቸው ሽፈራውና አቶ መሐመድ ዓሊ በፓርቲው የውስጥ አሠራር መሠረት ተሸንፈው መውጣቸውን አምነው ከመቀበል ይልቅ እኔንና ሌሎች ጥቂት የፓርቲያችንን አመራሮች በስም እየጠቀሱ "አምባገነኖች ናቸው" የሚል አዲስ የአሉባልታ ዘመቻ ከፈቱብን። አቶ ግዛቸውና አቶ መሐመድ ከእኛ ፓርቲ ከወጡ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥም የመዐሕድ አመራር ሆነው መሾማቸውን ሰማን። ቀሪዎቹ ዐሥራ አንድ ሰዎች ውጭ አገር ከሚገኙ ፓርቲዎችና ሬዲዮ ጣቢያዎች የገንዘብ ርዳታ እየተደረገላቸው "ኮከብ" የምትባል የእኛን ስም ብቻ ለማጥፋት የተሰማራች ጋዜጣ አቋቁመው በውጭ ከሚገኙት ሬዲዮ ጣቢያዎች ጋር ወሬ እየተቀባበሉ ዘርዝሬ ልጨርሰው በማልችለው መጠን የአሉባልታ ዘመቻ ለብዙ ወራት አካሄዱብን። በዚያች ጋዜጣ ማንበብ ሰልችቶኝ እስከማቆም ድረስ እኔን በሚመለከት ብቻ በየሳምንቱ ዕትም ላይ ከአራት ያላነሰ አዳዲስ የፈጠራ ዜና ይጻፍ ነበር። በነገራችን ላይ አቶ መሐመድ ዓሊና ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በተመሳሳይ ሁኔታ ከድርጅታቸው ከመኢአድ ተነጥለው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል ሲሆኑም ኢንጂነር ኃይሉ ሻወልን አምባገነን ብለው ለመሳደብ የቀደማቸው አልነበረም።

1995 ዓ.ም ላይ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ በተመለከተ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማኀበራት የሚሳተፉበት አንድ የውይይት መድረክ አዘጋጅቶ ጋበዘን፡፡ በወቅቱ ኢህአዴግ ፈቃደኛ ስላልነበረ ይመስለኛል በዚያ መድረክ ላይ ከሌሎች ሲቪክ ማኀበራት ተነጥሎ የኢትዮጵያ መምህራን ማኀበር አልተጋበዘም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መምህራን ማህበሩ ካልተጋበዘ በስተቀር እኛም አንሳተፍም የሚል አቋም ያዙ፡፡ ኢዴፓ ግን የመምህራን ማህበሩን አለመጋበዝ አውግዞ በውይይት መድረኩ ላይ ግን እንደሚሳተፍ አስታወቀ፡፡ ይህንን ጉዳይ ሰበብ አድርገው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢዴፓ በእንዲህ ዓይነቱ መድረክ ላይ ያለ ቅድመ-ሁኔታ የሚሳተፈው ከመጀመሪያ ኢህአዴግን ዴሞክራት ለማስመሰል የተቋቋመ ፓርቲ ስለሆነ ነው የሚለውን አሉባልታ እንደ አዲስ ጀመሩት፡፡ ውዝግቡ የተነሣው መምህራን ማህበሩ ለምን አልተጋበዘም? በሚል ሆኖ እያለ - ኢዴፓን ለማውገዝ ሲባል ብቻ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችና የተወሰኑ ጋዜጦች “ከእንግዲህ በውይይትና ክርክር መድረክ ላይ ከኢህአዴግ ጋር መቀመጥ ኢህአዴግን ዴሞክራት ማስመሰል ነው” የሚል የከረረ አቋም በመያዝ በኢዴፓና በኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ላይ “ቅጥረኞች ናቸው” የሚል ዘመቻ ከፈቱ፡፡

በነገራችን ላይ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ ለአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተ ባለውለታ ድርጅት ቢሆንም እንዳለመታደል ሆኖ ድርጅቱ በገዥውም ፓርቲ ሆነ በኢህአዴግ በበጎ የሚታይ አልነበረም፡፡ አንዳንድ የኢህአዴግ ሰዎች ኢንተር አፍሪካ ግሩፕን ሆን ብሎ የሥርዓቱን ገመና ለማጋለጥ የሚሠራ ድርጅት አድርገው ያዩት የነበረ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚው ጐራ ድርጅቱን ኢህአዴግን ዴሞክራት ለማስመሰል የሚሠራ አድርጐ ያየው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ እያንዳንዱን የክርክር መድረክ ከማካሄዱ በፊት በክርክሩ አካሄድ /Modality/ ላይ በሚደረገው ውይይት ገዥውን ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚዎችን ለማሳመንና ለማግባባት በሚያደርገው ጥረት የሚገጥመው ፈተና ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በሚያዘጋጃቸው የክርክር መድረኮች በዋናነት ተጠቃሚው የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ቢሆንም ተቃዋሚዎች ራሳችንን በአግባቡ ለሕዝብ ለማስተዋወቅና የምርጫ 97ቱ ዓይነት የሕዝብ መነሳሳት ለመፍጠር የቻልነው በዋናነት ኢንተር አፍሪካ ግሩፕ በፈጠረልን ዕድል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን የፖለቲካ ባህላችን በተጠናወተው ሁሉንም ነገር የመጠራጠር አባዜ አንድም ቀን ለኢንተር አፍሪካ ግሩፕ የሚገባውን ምስጋና አቅርበንለት አናውቅም፡፡

በዚያው ዓመት ላይ ኢዴፓ የብሔራዊ ዕርቅ አስፈላጊነትን በተመለከተ መስቀል አደባባይ ላይ አንድ ሕዝባዊ ስብሰባ አዘጋጀ፡፡ ብሔራዊ ዕርቅ የሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች አጀንዳ

መሆኑን በማመንም ስብሰባውን ከሌሎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ማዘጋጀት እንዲቻል ኢዴፓ ደብዳቤ ፅፎ ጋበዛቸው፡፡ በወቅቱ ፓርቲዎቹ በደፈናው ስብሰባው ላይ መሳተፍ አይመቸንም የሚል መልስ ስለሰጡ ኢዴፓ ብቻውን ስብሰባውን የማካሄዱን ሥራ ገፋበት፡፡ በኋላ ላይ ስብሰባው ሊካሄድ ሦስት ቀናት ብቻ ሲቀሩት የተቃዋሚ ፓርቲዎቹ መሪዎች የሆኑት ፕሮፌሰር በየነ፣ ዶ/ር መረራና ኢንጅነር ኃይሉ ሻዎል በኢትኦጵ መፅሔት ላይ ከትልልቅ ፎቶግራፎቻቸው ጋር በመውጣት በሰጡት ቃለ-መጠይቅ “ኢዴፓ የብሔራዊ ዕርቅን በሚመለከት ሕዝባዊ ስብሰባ የሚያካሂደው ከሥልጣኑ ሊወርድ እየተንገዳገደ የሚገኘውን የኢህአዴግን ዕድሜ ለማራዘም ብሎ ነው” በማለት በድፍረት አወገዙ፡፡ በወቅቱ እነዚህ የፓርቲ መሪዎች እንዲህ ዓይነት የማያዋጣ የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲያካሂዱ አንድም ጋዜጣ ብሔራዊ ዕርቅ እስካሁን የእናንተስ ጥያቄ አልነበረም ወይ? ወይንስ ከእንግዲህ ብሔራዊ ዕርቅ ኢትዮጵያ ውስጥ አያስፈልግም የሚል አዲስ አቋም ያዛችሁ ማለት ነው ወይ? በማለት ሊጠይቃቸው የደፈረ አልነበረም፡፡ እንዲያውም ኢዴፓ ያሰበውን ስብሰባ አካሂዶ ከጨረሰ በኋላ ብዙም ውሎ ሳያድር እነዚሁ የፓርቲ መሪዎች ለአገራችን ብሔራዊ ዕርቅ ያስፈልጋታል እያሉ ያለኀፍረት እንደገና መናገር ጀመሩ፡፡

በዚያው ሰሞን የተቃዋሚዎች ርስ በርስ መናቆር አሳስቦናል በማለት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌና አቶ አበበ ወርቄ ተቃዋሚዎችን የማቀራረብ አንድ የሽምግልና ሥራ ጀመሩ፡፡ በተደረገው ጥረትም ከላይ የጠቀስኳቸው ሦስቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢዴፓን ቅጥረኛ ነው ማለታቸውን በድንገት አቆሙና ከኢዴፓ ጋር አብረው ለመሥራት ተስማምተው አንድ ኀብረት የማቋቋም ሥራ በሽማግሌዎቹ አደራዳሪነት ተጀመረ፡፡ ኀብረቱን ለማቋቋም የሚያስፈልገው ስምምነት ከተደረገና መተዳደሪያ ደንብና ስያሜ ተዘጋጅቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በድንገት “ኢዴፓ ጋር አብሬ ለመሥራት እምነት የለኝም” የሚል አዲስ አቋም ይዘው በመምጣታቸው ኀብረት የመፍጠር ጥረቱ ሳይሳካ ቀረ፡፡ በወቅቱ ኢዴፓ ለኀብረቱ መቋቋም ከሌሎቹ የተሻለ በጎ ፍላጐትና ጥረት አሳይቶ ስለነበርም ሽማግሌዎቹ አመስግነውትና በተፈጠረው ነገርም አዝነው የሽምግልናው ሂደት ቆመ፡፡

ይህ በሆነ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሦስቱ ድርጅቶች በዚያ የሽምግልና ሂደት ስምምነት ላይ የተደረሰበትንና በኢዴፓ አርቃቂነት የተዘጋጀውን መተዳደሪያ ደንብና ስያሜ ይዘው ኢዴፓን ያገለለ “ትብብር ለዴምክራሲና ለአንድነት” የሚል ኀብረት ማቋቋማቸውን በኢየሩሳሌም ሆቴል በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ለሕዝብ ይፋ አደረጉ፡፡ በወቅቱ ኢዴፓ ለምን በውስጣቸው እንደሌለ በጋዜጠኞች ሲጠየቁም “ኢዴፓ ከእኛ ጋር ለመሥራት ፈቃደኛ አልሆነም”

የሚል የሃሰት መልስ ሰጡ። እኛም በሆነው ነገር እጅግ ተገርመን አብሮ መሥራት ያልፈለገው አካል ማን እንደሆነ እውነቱን እንዲመሰክሩ ሽማግሌዎቹን አግኝተን አነጋገርናቸው። ነገር ግን ሽማግሌዎቹ “በተፈጠረው ችግር እናዝናለን” ከማለት በስተቀር “በይፋ ወጥተን እንዴት አድርገን እንዲህ ዓይነቱን ጉዳይ ለሕዝብ እንናገራለን” በማለት ሃቁን ለሕዝብ ለመመስከር ሳይደፍሩ ቀሩ።

እንግዲህ ይህ ሁሉ የአሉባልታ ዘመቻ አገር ውስጥ እየተካሄደ ባለበት ወቅት በውጭ አገር በሚገኙ የተቃዋሚ ሬዲዮ ጣቢያዎች “ኢዴፓ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ነው” የሚልና “ልደቱ ተቃዋሚውን ጐራ ለመበተን የተሰማራ ሰርጐገብ ነው” የሚለው ዘመቻ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ሳይቋረጥ እየተካሄደ ነበር። በተለይም “ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተሳሳተ የፖለቲካ አቋም ያላቸው ሰው እንጂ ጠላት ናቸው ብዬ አላምንም፣ ሰላማዊ ትግሉም በዋናነት ሊካሄድ የሚገባው ውጭ አገር ሳይሆን አገር ውስጥ ነው” በማለት በአንድ ውጭ አገር በተካሄደ ስብሰባ ላይ ከተናገርኩ በኋላ “ግልገል አምባገነን” የሚል ቅፅል ስም ወጥቶልኝ ያለማቋረጥ ከሦስት ዓመት በላይ ለሆነ ጊዜ የኔን ስም የሚያጠፋ የአሉባልታ ዘመቻ ተካሄደብኝ። በተለይም ኢህአፓ ፕሮፌሰር በየነንና ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትን ውጭ አገር ለስብሰባ ጋብዞ በወሰደ ቁጥር በየምግብ ጠረጴዛው ሳይቀር የወሬ ርእስ ተደርጐ የሚወራው የኔ “ወያኔነት” ሆነ። በወቅቱ ኢህአፓ እሱ ወደፊት ወደ አገር ቤት ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ አንድም ጠንካራ ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥሮ ማየትን ስለማይፈልግ የሙሉ ጊዜ ሥራው የኢዴፓን ስም ማጥፋት ሆኖ ነበር።

1995 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ላይ ኢህአፓ ከዚህ ዓላማው ጋር በተያያዘ በሱ ቁጥጥር ሥር የሚመራ አንድ አገር አቀፍ ኅብረት እንዲቋቋም ጥረት እያደረገ ነበር። አገር ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች አንድ ላይ ተባብረው “ኢዴፓ ከተቃዋሚዎች ጋር አብሮ ሊሠራ የማይፈልግ አፈንጋጭ ነው” እያሉ ቅስቀሳ በሚያካሂዱበት በዚያን ወቅት ኢህአፓም ምንም ዓይነት ግብዣ ሳያቀርብልንና ፈቃደኛነታችን ሳይጠይቅ “ኢዴፓ በምንፈጥረው አገር አቀፍ ኅብረት ውስጥ አልሳተፍም ብሎ አፈነገጠ” የሚል ተመሳሳይ ቅስቀሳ በውጭ አገራት ያካሂድ ነበር። በዚህ ሁኔታ አገር ውስጥና ውጭ አገር የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ርስ በርስ እየተጋገዙ “ኢዴፓ አብሮ መሥራትን አይፈልግም” የሚል የሕዝቡን ስሜት የሚነካ ቅስቀሳ በሐሰት ሲያካሂዱብን በወቅቱ “ኢዴፓ የወያኔ ተለጣፊ ነው ብላችሁ የምታምኑ ከሆነ ለምን አብሮን ሊሠራ አይፈልግም እያላችሁ ትከሱታላችሁ?” ብሎ ለመጠየቅ የሞከረ አንድም ጋዜጣ ግን አልነበረም።

በመጨረሻ ኢዴፓ ጭራሽ አብሮ እንዲሠራ ሳይጋበዝ አፈንጋጭ የሚል ቅስቀሳ ሆን ተብሎ እየተካሄደበት መሆኑን ቀስ በቀስ ሕዝቡ እንዲያውቀው ማድረግ ሲጀምር በኢህአፓ የሚመራው አስተባባሪ ኮሚቴ ሊቋቋም በታሰበው ኅብረት ውስጥ እንድንገባ የሚጠይቅ ግብዣ ላከልን፡፡ እኛም ፈቃደኛ በመሆን 1995 ዓ.ም ክረምት ላይ ሜሪላንድ ላይ በተካሄደው የኅብረቱ ስብሰባ ላይ በመገኘት ዐሥራ አራት ፓርቲዎችን ያቀፈው ኅብረት አባል ሆን፡፡ እኛን ለማግለል ተብሎ በሦስት ፓርቲዎች አገር ውስጥ ተቋቁሞ የነበረው ኅብረትም የሦስት ወራት ዕድሜ እንኳ ሳይኖረው ተበትኖ ሦስቱም ፓርቲዎች አሜሪካን አገር የተቋቋመው ኅብረት አባል ሆኑ፡፡ ፕሮፌሰር በየነም ኢህአፓ በሰራው ድርጅታዊ ሥራ እንደተለመደው የኅብረቱ ሊቀመንበር ሆነው ወደ አገር ውስጥ ገቡ፡፡ በወቅቱ እነዚህ ሁሉ በአገር ውስጥም ሆኑ በውጭ አገር የሚገኙና ኢዴፓን ተለጣፊ ነው እያሉ ሲቀሰቅሱ የኖሩ ፓርቲዎች በምን ሁኔታ ኢዴፓን አምነውት አብረውት መሥራት እንደጀመሩ የጠየቃቸው ባይኖርም የዚያ ኅብረት አባል በመሆናችን ብቻ በኛ ላይ ይካሄድ የነበረው የአሉባልታ ዘመቻ ለጊዜው ተገታ፡፡

አዲሱ የእነ ኢህአፓና የእነ ፕሮፌሰር በየነ ስልትም ብዙም ውጤታማ ባልሆነ የአሉባልታ ዘመቻ ኢዴፓን ለማዳከም ከመሞከር ይልቅ በኅብረት ስም በብዙ ፓርቲዎች ውስጥ ተውጦ እንዲደበዝዝ በማድረግና ተነጥሎ የማይበረክትን ሁኔታ በመፍጠር ቀስ በቀስ ማዳከም እየሆነ መጣ፡፡ እኛም የሚፈጠሩት ኅብረቶች ቅን ዓላማ ተይዞ የሚፈጠሩና መዝለቅ የሚችሉ አለመሆናቸውን እያወቅን ሊወራብን የሚችለውን አሉባልታ በመፍራት ብቻ በኅብረት ስም አብረን መጓዝን መረጥን፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ አንድ አዲስ ኅብረት ተፈጠረ በተባለ ቁጥር ሕዝቡ በደስታ ስለሚፈነድቅና በደፈናው ውጤት ይመጣል ብሎ ስለሚጠብቅ የሚፈጠሩት ኅብረቶች ውጤት ሊያመጡ አይችሉም ብለን ለሕዝቡ ብንነግረው ሃሣባችንን የሚቀበልበት ይቅርና ጆሮ ሰጥቶ ሊያዳምጥ የሚችልበት ዕድል አልነበረም፡፡ ፓርቲያችንን ስንመሰርት ከኢህአዴግ በተጨማሪ በተቃዋሚዎችና በሕዝቡ ውስጥ የሚታዩ ችግሮችን በይፋ ለመታገልና ምክንያታዊ ፖለቲካ ለማካሄድ የነበረንን ፍላጐትም አሉባልታውን መቋቋም እያቃተን ሲመጣና የበለጠም እንዳይባባስ በመስጋት ወደጐን እየገፋነውና እንደሌሎቹ ተቃዋሚዎች በሥርዓቱ ላይ የከረረ ተቃውሞ የማቅረቡን ስልት አጠናክረን መቀጠሉን እኛም ገፋንበት፡፡ ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው ግን በርግጥም ትልቁ ስህተታችን በዚያን ወቅት ይነዛብን የነበረውን አሉባልታ መቋቋም ተስኖን የነባሩ የአገራችን የፖለቲካ ባህል ሰለባ ለመሆን መገደዳችን ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በኢህአፓ ተነሳሽነት በአሜሪካን አገር ተመሥርቶ አገር ውስጥ የገባው ኅብረት ለመንግሥት የእንደራደር ጥያቄ ከማቅረብ ያለፈ አንድም የሚጨበጥ ሥራ ሳይሰራ ዓመት ሊሞላው ተቃረበ። በአንድ በኩል አገር ውስጥ ያለን ፓርቲዎች በተናጠል ተንቀሳቅሰን ውጤት የሚታይበት ሥራ እንዳንሰራ ኅብረቱ በወር አንድ ቀን የወረቀት መግለጫ በማውጣትና የጋዜጣ ቃለ-መጠይቅ በመስጠት ብቻ አለሁ እያለ አባል ፓርቲዎች በሕዝቡ ውስጥ ትኩረት እንዳናገኝ አደረገን። በሌላ በኩል ደግሞ ውጭ አገር ኗሪ በሆነው ሕዝብ ከመሰልቸቱ የተነሣ በራሱ ተንቀሳቅሶ ሕዝብን መሰብሰብም ሆነ ማደራጀት የማይችለው ኢህአፓ የኅብረቱን ስም ተጠቅሞ በውጭ አገራት የኢዴፓና የመኢአድ የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ የሚያዳክሙ አዳዲስ ኮሚቴዎች ማቋቋም ጀመረ። በዚህ ጊዜ ህልውናው አደጋ ውስጥ መግባቱን የተገነዘበው መኢአድ ራሱን ቀድሞ ከኅብረቱ አገለለ። ኢዴፓ ከኅብረቱ ፈጥኖ መውጣት እንደተለመደው በአፍራሽነት ሊያስፈርጀኝ ይችላል ብሎ በመስጋት በኅብረቱ ውስጥ እየተፈጠሩ ያሉ ችግሮችን በይፋ እያሳወቀ እስከሚቀጥለው የኅብረቱ ጉባዔ ድረስ በኅብረቱ አባልነት መቆየትን መረጠ።

በመካከል ኅብረቱ የትም እንደማይደርስ የተገነዘቡ አንዳንድ በውጭ አገር የሚገኙ ሰዎች የ97 ዓ.ም ምርጫ ከመቃረቡ በፊት ኢዴፓና መኢአድ ተዋሕደው ቢሠሩ ለውጤት ይበቃሉ በሚል የሽምግልና ጥረት ጀመሩ። ፈጽሞ ሊሆን ይችላል ብለን ባልገመትነው ሁኔታ መኢአድ “ኢዴፓ የወያኔ ተለጣፊ ነው” የሚለውን ቅስቀሳውን አቁሞ ከኢዴፓ ጋር ለመዋሐድ መወሰኑን አሳወቀ። እኛም እየሆነ ያለው የፖለቲካ መገለባበጥ ቢያስገርመንም የሚሳካ ከሆነ ብንሞክረው ይሻላል በሚል አጉል ተስፋ ምን ዓይነት ውኅደት ለመፍጠር እንደሚቻል ለመደራደር ፈቃደኛነታችንን ገለፅን። ድርድሩ ተጀምሮና በጥሩ ሁኔታ ተካሂዶ ወደ መጠናቀቁ ሲደርስ መኢአድ “የውሕዱ ፓርቲ ስም መኢአድ መባል አለበት፣ የውሕዱ ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ዋና ጸሐፊና ዋና ዋናዎቹ ሌሎቹ ኃላፊነቶች በመኢአድ ካልተያዙ በስተቀር ውኅደቱን አንፈልገውም” የሚል አቋም መያዙን ኢንጂነር ኃይሉ በማቅረባቸው የውኅደቱ ድርድር ተቋረጠ።

የሁለቱን ፓርቲዎች ውኅደት ሕዝቡ በጉጉት ይጠብቀው ስለነበረም የድርድሩ መቋረጥ አስደንጋጭ ዜና ሆነ። ድርድሩ ለምን እንደተቋረጠ ከጋዜጠኞች ለሚቀርብልን ጥያቄ በእኛ በኩል ኢንጂነር ኃይሉ በእጃቸው ፅፈው ያቀረቡትን ቅድመ-ሁኔታ በመረጃነት አቅርበን በምን ምክንያት እንደተቋረጠ ሃቁን ለመናገር ስንሞክር - መኢአድ ግን እንደተለመደው “ኢዴፓን አላምነውም” የሚል አሉባልታውን እንደገና መንዛት ጀመረ። ቀደም ሲል እንደሆነውም በወቅቱ አደራዳሪ የነበሩት ሽማግሌዎች እውነቱን ለሕዝብ ወጥተው እንዲመሰክሩ ብንጠይቃቸውም ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። ከመኢአድ ጋር ለመዋሐድ የተደረገው ጥረት በዚያ መልኩ ቢከስምም ፓርቲያችን

በተለያዬ ጊዜ ከኢዳግ፣ ከኢዲዩና ከመድኅን ጋር ለመዋሐድ ያደረገው ጥረት በመሳካቱ በሂደት ኢዴፓ የአራት ፓርቲዎች ውሕድ ሆኖ ወደ ኢዴአፓ-መድኅንነት ለመሸጋገር ቻለ።

1996 ዓ.ም ክረምት ላይ በኅብረቱ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ አሜሪካን ተመልሰን ሄድን። ኢዴአፓ-መድኅን ከኅብረቱ ጋር አብሮ የማይቀጥል መሆኑ በዚያን ወቅት ግልጽ እየሆነ መጥቶ ስለነበር ኢህአፓዎች ገና ዓመታዊ ስብሰባው ከመካሄዱ በፊት በእኔ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ጋብ አድርገውት የነበረውን የአሉባልታ ዘመቻ እንደገና አጠናክረው ጀመሩት። ኢትኦጵ ጋዜጣ "የአቶ ልደቱ ወንድም የድሬዳዋ ከንቲባ ሆነው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሾሙ" የሚል ዜና ይዞ ወጣ። ከአባቶቻችን ስም መመሳሰል በተጨማሪ በዚያ የጋዜጣ የፊት ገጽ ዜና ላይ የወጣው የእኔና ከንቲባ ሆነው ተሾሙ የተባሉት የአቶ ሲሳይ አያሌው ፎቶ ግራፍ የተወሰነ መመሳሰል ይታይበት ስለነበር ዜናው በሕዝቡ ውስጥ ትኩስና አነጋጋሪ ሆኖ ብቅ አለ። በተለይም በውጭ አገራት ይኸ ዜና የእኔ "ወያኔነት" ማረጋገጫ ተደርጐ በሰፊው እንዲናኝ ተደረገ። የሚገርመው ይህ ዜና በሕዝቡ ውስጥ ሲሰራጭ ከአንዳንድ ሰዎች በስተቀር የአብዛኛው ሰው ትኩረት "የልደቱ ወንድም ከንቲባ ሆኖ ቢሾም ምን ችግር አለው?" የሚል ሳይሆን "እውነት የልደቱ ወንድም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሾመ ወይ?" የሚለው ጥያቄ ላይ ነበር። በወቅቱ ስለተሠራጨው ዜና በአንዳንድ የግል ጋዜጦች ተጠይቄ አቶ ሲሳይ አያሌው የሚባሉት ሰው የእኔ ወንድም ስለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ስለመፈጠራቸውም የማላውቅ መሆኑን ከገለፅኩ በኋላ ወሬው በተወሰነ ደረጃ ቢቀዘቅዝም እስካሁን ድረስ ያን ዜና እውነት አድርገው ያመኑ ሰዎች ያጋጥሙኛል። በነገራችን ላይ ይህ ወሬ ከተወራ ከአንድ ዓመት በኋላ አቶ ሲሣይ አያሌውና እኔ በአጋጣሚ አንድ ካፍቴሪያ ውስጥ ተገናኝተን ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋወቅን። እኔና ርሳቸውን በተመለከተ ስለተወራው ወሬ አንስተንም ትንሽ ተሳሳቅን። አቶ ሲሣይ አያሌው በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ውስጥ የአንድ ክፍለ ከተማ ሥራ-አስኪያጅ ሆነው እየሠሩ ይገኛሉ።

ለእኔ ግን በወቅቱ አስደንጋጭ የሆነብኝ እንዲህ ዓይነት የፈጠራ አሉባልታ በእኔ ላይ መወራቱ ሳይሆን ሕዝቡ ዜናውን ያየበት መንገድ ነበር። ምክንያቱም ከመጀመሪያው ዜናውን ያነበበ ሰው "የልደቱ ወንድም ከንቲባ ሆኖ ቢሾም ምን ችግር አለው?" ማለት ሲገባው የበለጠ ያስጨነቀው "ዜናው እውነት ነው ወይስ ውሸት?" የሚለው ነበር። ይኸ የሚያሳየው ዜናው እውነት ቢሆን ኖሮ በብዙው ሰው አስተሳሰብ የእኔ "ወያኔነት" ተረጋገጠ ማለት ነው። ለእኔ ይኸ ዓይነቱ አስተሳሰብ ያረጋገጠልኝ የአገራችን ፖለቲካ ምን ያህል መሠረታዊ ችግር ውስጥ የወደቀ መሆኑን ነበር። ምክንያቱም እኔና አቶ ሲሳይ አያሌው በአጋጣሚ ሆኖ ወንድማማች መሆናችን እውነት ሆኖ ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ ሲቻል የሚያስደስት እንጂ የሚያስደነግጥ ሊሆን አይገባውም

ነበር፡፡ ሁለት ወንድማማቾች በአመለካከት ተለያይተው የሁለት ተቀናቃኝ ፓርቲዎች አባል ሆነው ቢገኙ ሊመሰገንና ሊቀናበት የሚገባ ጉዳይ መሆን ነበረበት እንጂ የሰዎችን አቋም ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባ የሚችል ተደርጐ መወሰድ አልነበረበትም፡፡ ምክንያቱም ፖለቲካ የአስተሳሰብ መገለጫ እንጂ የዘርና የውርስ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስገራሚ አስተሳሰብ በሕዝባችን ውስጥ ሲታይም ነው - ለምን አሉባልታ በአገራችን ፖለቲካ ይህንን ያህል ቦታ ኖረው? የሚል ብቻ ሳይሆን ለመሆኑ ስለምንፈልገው የፖለቲካ ለውጥ በአግባቡ እናውቃለን ወይ? የሚል ጥያቄ እንዲነሣ የሚያስገድደው፡፡

አሜሪካን አገር በተጠራው የኅብረቱ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ሁለት ጉዳዮች አከራካሪ ሆነው ነበር፡፡ የመጀመሪያው የኅብረቱ ሊቀመንበር ማን ይሁን? የሚል ሲሆን ሁለተኛው በ97 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ላይ ምን አቋም ይኑረን? የሚለው ነበር፡፡ የኅብረቱ ሊቀመንበር ማን ይሁን? በሚለው አጀንዳ ላይ እኔ እጄን አውጥቼ - ኅብረቱ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ፕሮፌሰር በየነ ሊቀመንበር መሆን እንደሌለባቸው እስከዚያ ጊዜ ድረስ እርሳቸው የመሯቸው አምስት ኅብረቶች እንዴት ውጤታማ ሳይሆኑ እንደቀሩ በዝርዝር በማስረዳት ተቃወምኩ፡፡ በዚህ ጊዜ ፕሮፌሰር በየነ የእኔን የተቃውሞ ሐሳብ እንደ ድፍረት በመቁጠር ተናደው “ልደቱ ከዚህ ስብሰባ ካልወጣ በስተቀር በስብሰባው አልቀጥልም” በማለት ረግጠው ለመውጣት ተገለገሉ፡፡ እኔም በድጋሜ እጄን አውጥቼ “ዶክተር በየነ - እርስዎ ሊቀመንበር እንዳይሆኑ መቃወም መብቴ መሆኑን ዘንግተው ከስብሰባ ይውጣልኝ በማለትዎ አዝናለሁ፡፡ እርስዎና እኔ አምባገነን ናቸው ብለን የምንታገላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ግን ፊታቸው ላይ ቆሜ ሥልጣናቸውን ለቀው በማሳየት ዓርአያ እንዲሆኑ ስጠይቃቸው እንደርስዎ ከስብሰባ ይውጣልኝ አላሉኝም፡፡ እርስዎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲን አመጣለሁ ብለው በመታገልዎ አዝናለሁ” በማለት ተናገርኩኝ፡፡ በመጨረሻም ፕሮፌሰር በየነ ቢለመኑም የያዙትን አቋም መቀዬር ስላልቻሉ “ልደቱ ከስብሰባው ይውጣ - አይውጣ?” በሚለው ጉዳይ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ ተወስኖ አብዛኛው ሰው ሊወጣ አይገባውም የሚለውን አቋም በመደገፉ በስብሰባው እንድቀጥል ተደረገ፡፡ የሚገርመው ውጤቱ በአጋጣሚ ጥሩ ቢሆንም በዚያ ዓይነት መሠረታዊ የመብት ጥያቄ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ መደረጉ በራሱ አሳፋሪና ስህተት መሆኑን ግን ተገንዝቦ ሊቃወም የሞከረ ሰው አልነበረም፡፡

ሁለተኛው አከራካሪ የነበረው አጀንዳ ስለ 97 ዓ.ምቱ ብሔራዊ ምርጫ ምን አቋም እንያዝ? የሚለው ነበር፡፡ በዚህ አጀንዳ ላይ በተደረገው ውይይት ወደ ምርጫው ከመግባታችን በፊት ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ የሚያደርጉ ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀምጠን እነሱ ከተመለሱልን ብቻ ነው ምርጫው ውስጥ የምንሳተፈው የሚል አቋም እንዲያዝ ተደረገ፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን

ይህንን የኅብረቱን አቋም እንደማይቀበለው ወዲያውኑ ገለፀ፡፡ ምርጫው ነፃና ፍትሐዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ግፊትና ትግል ሁሉ ማድረግ ቢኖርብንም በምንም ዓይነት ቅድመ-ሁኔታ አቅርበን ከምርጫው ራሳችንን ማግለል የለብንም ብሎ ተከራከረ፡፡ እነ ፕሮፌሰር በየነ ግን ከምርጫው ራሳቸውን እንደማያገሉ አስቀድመው የሚያውቁት ቢሆንም ለጊዜው የኅብረቱ መሪዎች የመሆኑን ዕድል ላለማጣት ሲሉ ብቻ የእነ ኢህአፓን አቋም ተቀብለው ወደ አገር ቤት ተመለሱ፡፡

ኋላ ላይ ግን በተግባር እንደታየው እነ ፕሮፌሰር በየነ ከውጭ የሚላከውን ገንዘብ አሚጠው ከተጠቀሙ በኋላ ከእነ ኢህአፓ ፍላጐት ውጭ በምርጫው በመሳተፋቸውና ከምርጫው በኋላም ፓርላማ በመግባታቸው ከውጭ አገሩ የፖለቲካ ኃይል ጋር ሳይወዱ በግድ ለመለያየት በቁ፡፡ በዚህም ምክንያት እነሱም እንደኛው "ከሃዲ" ተብለው መሰደብንም ቀመሱት፡፡ በምርጫው ላይ ቅድመ-ሁኔታ አስቀምጠን ራሳችንን ማግለል አንፈልግም የሚለውን አቋም ኢዴአፓ-መድኅን በዚያ ስብሰባ ላይ ሲወስድ ከኅብረቱ ጋር አብሮ እንደማይቀጥል ለእነ ኢህአፓ ግልጽ ስለነበር ገና ስብሰባው ሳይጠናቀቅ በእኔ ላይ የአሉባልታው ዘመቻ እንደ አዲስ ተከፈተ፡፡ ኢትኦጵ ጋዜጣ "አቶ ልደቱ የኅብረቱን ስብሰባ በድብቅ በቴፕ ሲቀርፁ ተያዙ" የሚል ዜና ፅፎ ማውጣቱን እዚያው ስብሰባው ላይ እያለሁ ከአገር ቤት ተደውሎ ተነገረኝ፡፡ የሚገርመው ይህንን ዐይን ያወጣ የጋዜጣ ውሸት ሁሉም የኅብረቱ ስብሰባ ተሳታፊዎች የሰሙ ቢሆንም ከመካከላቸው አንድም ሰው እንኳ ለሃቅ ተቆርቋሪ ሆኖ እውነቱን ለሕዝብ ለመመስከር የሞከረ አልነበረም፡፡ የመንግሥት ጋዜጠኞችን በውሸታምነት ሁልጊዜ ሲከሱ የሚደመጡት የተቃዋሚ መሪዎች የእኔ ስም በግል ጋዜጦች እንደዚያ ሆነ ተብሎ በተደጋጋሚ እንዲጠፋ መደረጉን እያዩ አንድም ቀን ድርጊቱን ሲተቹ ተደምጠው አያውቁም፡፡ የሆነ ሆኖ ከዚያ ስብሰባ ከተመለስን ብዙም ሳይቆይ ኢዴአፓ-መድኅን ከኅብረቱ መውጣቱን ይፋ አደረገ፡፡

ኢትዮ

## ምዕራፍ ሁለት

## ከቅንጅት ምሥረታ እስከ ምርጫ 97 - አሉባልታ የረገበበት ወቅት

መስከረም 1997 ዓ.ም ላይ እነ ፕሮፌሰር መስፍንና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ምርጫው ከመድረሱ በፊት ኢዴአፓ-መድኅንና መኢአድ አንድ ላይ ሊሠሩ የሚችሉበት ሁኔታ የግድ መፈጠር አለበት በማለት አዲስ እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡ ይህንን ሃሣባቸውን ሲያማክሩንም "ከዚህ ቀደም ሞክራችሁ አይታችሁታል - መኢአድ ጋር እንዴት አብሮ መሥራት ይቻላል?" የሚል ጥያቄ አቀረብንላቸው፡፡ እነሱም "አሁን አዲስ መፍትሔ ታይቶናል፡፡ ይኸውም ሁለቱ ፓርቲዎች የግድ አብራችሁ እንድትሰሩ ለማድረግ በማሰብ እኛም በአጭር ጊዜ አንድ አዲስ ፓርቲ በማቋቋም አብረናችሁ ልንሰራ አስበናል፡፡ እኛ በመካከላችሁ ከተገኘን ሁለቱ ፓርቲዎች አብራችሁ የመሥራታችሁ ዕድል የሰፋ ይሆናል" አሉን፡፡ እኛም በተለመደው ቂልነታችን ሃሣባቸውን በቅንነት በማየት ፈቃደኛነታችንን ገለፅንላቸው፡፡ መኢአድም አሁንም እንደገና ኢዴአፓ-መድኅን የወያኔ ተለጣፊ ነው የሚለውን ቅስቀሳውን አቁሞ ከእኛ ጋር አብሮ ለመሥራት ወሰነ፡፡ በነገራችን ላይ በዚያን ወቅት በየክፍላተ-ሃገሩ የሚገኙ የመኢአድ አባላት ብዙውን ጊዜ "ልደቱ ወያኔ ነው" እያሉ ለሕዝቡ ሲያወሩ ይከርሙና እንደገና መኢአድና ኢዴአፓ-መድኅን አብረው ሊሠሩ ተስማሙ የሚል ዜና በድንገት ሲነገር ሲሰሙ ግጭት እየተፈጠረባቸው መቸገራቸውን በተደጋጋሚ ለፓርቲያቸው በምሬት ቅሬታ ያቀርቡ እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡

እነ ፕሮፌሰር መስፍን የጀመሩት ጥረት ከተወሰነ ውጣ ውረድ በኋላ ተሳካና ታኅሣስ 1997 ዓ.ም ላይ መኢአድ፣ ኢዴአፓ-መድኅን፣ ኢዴሊና አዲስ የተመሠረተው ቀስተዳመና በአንድ ላይ ሆነው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተባለውን ስብስብ ለመፍጠር በቁ፡፡ ቅንጅት ሲመሠረት ገና የአንድ ሳምንት ዕድሜ ያልነበረው ቀስተዳመናም ጉለሌ አካባቢ የነበረውን የኢዴአፓ-መድኅን ቢሮ በጊዜያዊነት በመጠቀም እንደ አንድ ፓርቲ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡ እነ ፕሮፌሰር መስፍን በዚያን ወቅት ደጋግመው ይናገሩ እንደነበረው ቀስተዳመና ሁለቱን ፓርቲዎች ማለትም ኢዴአፓ-መድኅንና መኢአድን አብረው እንዲሰሩ የማስቻል እንጂ ራሱን ችሎ እንደ ፓርቲ ጠንክሮ የመውጣት ምንም ዓይነት ፍላጎት አልነበረውም፡፡

በወቅቱ ቅንጅት የሚባለው ስብስብ ለስድስት ወር ጊዜ ማለትም ምርጫው እስኪጠናቀቅ ድረስ ብቻ እንዲያገለግል ታስቦ የተቋቋመ ሲሆን የጋራ ዓላማውም አራት ቁምነገሮችን ማከናወን ነበር፡፡ ይኸውም - የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም መቅረፅ፣ በ97 ዓ.ም ብሔራዊ ምርጫ ላይ በአንድ የምርጫ ጣቢያ ላይ ሳይደራረቡ መወዳደር መቻል፣ የምርጫውን ዘመቻ በጋራ ማካሄድና ለምርጫው ዘመቻ የሚያገለግል ገንዘብ በጋራ ማሰባሰብ የሚሉ ነበሩ፡፡ ቅንጅት እነዚህን ግልጽና

ውስን ዓላማዎች እስከ ምርጫው ፍጻሜ ድረስ ለማስፈጸም ሲመሠረት በውስጡ የተፈጠሩ የመጀመሪያ አከራካሪ ጉዳዮች በዋናነት ሁለት ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው የቅንጅቱ የውስጥ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ምን ዓይነት ይሁን የሚለው ነበር፡፡ በወቅቱ ኢዴአፓ-መድኅን እስካሁን በሌሎቹ ኅብረቶች ተደጋግሞ እንደታየው ልዩነት በመካከላችን ሲፈጠር በቀላሉ እንዳያፈርሰን ቅንጅቱ ውሳኔዎችን በድምፅ ብልጫ ሳይሆን በመግባባት (consensus) ብቻ ይወሰን፣ መግባባት የፈጠርንባቸውን ጉዳዮች ብቻ በጋራ እየሠራን ልዩነት የተፈጠረባቸውን ጉዳዮች ግን ፓርቲዎቹ በተናጠል እየሠራናቸው ብንቀጥል ይሻላል የሚል ሐሳብ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ይህንን ሐሳብ በዋናነት ፕሮፌሰር መስፍን አጥብቀው ስለተቃወሙት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ፡፡ በርግጥም ኋላ ላይ ፓርቲዎች የራሳቸው ህልውና ያላቸው መሆኑ እየተረሣ ህልውናቸውን የሚያሳጣ ከባድ ጉዳይ ሳይቀር የግድ በአብላጫ ድምፅ መቀበል አለባቸው መባሉ ለቅንጅቱ መፈረካከስ አንድ ምክንያት መሆኑ ታዬ፡፡

ሁለተኛው በቅንጅቱ ምሥረታ ወቅት የነበረው ልዩነት ቅንጅቱን ማን በሊቀመንበርነት ይምራው? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የቅንጅቱ ሊቀመንበር እንዲሆኑ በቀስተ-ደመና በኩል ሐሳብ ሲቀርብ ኢዴአፓ-መድኅን በግልጽ ተቃውሞውን አቀረበ ፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን በወቅቱ ለዚህ ተቃውሞው ያቀረባቸው ምክንያቶችም በዋናነት ሦስት ነበሩ፡፡ የመጀመሪያው መኢአድና ኢዴአፓ-መድኅን ለረዥም ጊዜ በአለመግባባትና ሽኩቻ ውስጥ የነበሩ ፓርቲዎች በመሆናቸው የእነዚህ ፓርቲዎች የቆዬ ችግር ወደ አዲሱ ቅንጅት እንዳይዛመት የቅንጅቱ መሪ ከእነዚህ ከሁለቱ ፓርቲዎች ውጭ ቢመረጥ ይሻላል የሚል ነበር፡፡ ሁለተኛው - በወቅቱ ቅንጅት በምሥረታ ሂደት ላይ እንደሆነ ይፋ እንደተደረገ ኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን እነ ፕሮፌሰር በየነና ዶ/ር መረራ ጭምር በይፋ "ቅንጅት የቀኝ ኃይሎች ስብስብ ነው" በማለት የዐማራዎች ድርጅት እንደሆነ አድርጐ የሚያሳይ ቅስቀሳ ማካሄድ ጀምረው ስለነበር እንዲህ ዓይነቱ አፍራሽ ቅስቀሳ በተለይም ወደፊት በምርጫው ወቅት በደቡብና በኦሮሚያ ክልል ተጠናክሮ ሊቀጥል ስለሚችል እንዲህ ዓይነቱን አደገኛ ቅስቀሳ ለመመከት ይቻል ዘንድ የቅንጅቱ መሪ የዐማራ ተወላጅ ባይሆን ይመረጣል የሚል ሲሆን፣ ሦስተኛው - ኢንጂነር ኃይሉ የድርጅታቸው መሪ ሆነው ካየነው ልምድ ጥሩ የአመራር ብቃት የማይታይባቸውና በተለይም ተናግረው የማሳመን ችሎታ የሌላቸው ሰው በመሆናቸው ቅንጅቱን ሊመሩት አይገባም የሚል ነበር፡፡

በወቅቱ ይህንን ሐሳብ ኢዴአፓ-መድኅንን ወክዬ ያቀረብኩት እኔ ስለነበርኩ ፕሮፌሰር መስፍን እንዴት እንዲህ ዓይነት ሐሳብ ታቀርባለህ? ብለው የተናገሩኝ ንግግር ከባድና

የሚያስደነግጥ ስለነበር ስሜቴን መቆጣጠር አቅቶኝ እንዳነባ ጭምር ያስገደደኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢህአዴግን ሳልፈራ የምቃወም ሰው ለምን ኢንጂነር ኃይሉን ተቃወምክ ተብዬ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ነን በሚሉ ሰዎች አፍራሽ ተደርጌ ከመታየት በላይ ለእኔ አስደንጋጭ ነገር አልነበረም፡፡ የሆነ ሆኖ ይህንን ሐሳብ ቀስተዳመናዎች አጥብቀው በመቃወማቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቶ ኢንጂነር ኃይሉ የቅንጅቱ መሪ እንዲሆኑ ተደረገ፡፡ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ለምን ኢንጂነር ኃይሉ ሊቀመንበር መሆን እንዳለባቸው በወቅቱ ሲያቀርቡልን የነበረው ምክንያትም "ኢንጂነር ኃይሉን ሊቀመንበር እስካላደረግነው ድረስ መኢአድ የቅንጅቱ አባል ሆኖ ሊቀጥል አይችልም" የሚል ነበር፡፡ በእኛ በኩል "ታዲያ በእንዲህ ዓይነቱ እኔ ሊቀመንበር ካልሆንኩ ቅንጅት ሆኜ አልቀጥልም በሚል ሰው እየተመራን እንዴት አብረን ልንሰራ እንችላለን?" በማለት ስንጠይቃቸውም የሚሰጡን መልስ "ኢንጂነር ኃይሉ እኛ በዙሪያው እስካለን ድረስ አፈንግጦ የትም ሊደርስ አይችልም፣ መሃላችን አድርገን መፈናፈኛ እናሳጣዋለን" የሚል ነበር፡፡ በነገራችን ላይ በዚያን ወቅት እንደ ዛሬው ማንነታቸውን ጠንቅቀን ባናውቃቸውም በወቅቱ የቅንጅቱ መሪ ሊሆኑ ይገባቸዋል ብለን በኛ በኩል ሽንጣችንን ገትረን ስንከራከርላቸው የነበረው ዶክተር ብርሃኑ ነጋን ነበር፡፡ ቅንጅቱ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ስህተት የፈፀመው ከዚህ በላይ በገለፅኳቸው ሁለት ውሳኔዎቹ ቢሆንም እስካሁን ድረስ በቅንጅቱ ዙሪያ ከነበሩ ሰዎች ውስጥ አንዳቸውም ስለ ጉዳዩ በድፍረት ለሕዝቡ ሲናገሩ ተደምጠው አያውቁም፡፡ በነገራችን ላይ ኋላ ላይ በሂደት ለመረዳት እንደቻልነው ዶክተር ብርሃኑ የቅንጅቱ መሪ ሆነው ቢሆንም ኖሮ ቅንጅት በባሰ ፍጥነት ከመፍረስ የሚድን አልነበረም፡፡

ቅንጅት በዚህ መልክ ተመሥርቶ እንቅስቅሴ ከጀመረ በኋላ በኢዴአፓ-መድኅንም ሆነ በእኔ ላይ ይወራ የነበረው አሉባልታ ለጊዜው መቆም ቻለ፡፡ የእነ ኢህአፓም ትኩረት በአጠቃላይ በቅንጅቱ ላይ ማነጣጠር ስለጀመረ በምርጫው ወቅት በደቡብ ክልል ይንቀሳቀሱ የነበሩት አንዳንድ የነፕሮፌሰር በየነ ድርጅት ሰዎችም ሕዝቡን "ከመረጣችሁ እኛን ምረጡ፣ እኛን መምረጥ ካልፈለጋችሁ ግን የነፍጠኞች ድርጅት የሆነውን ቅንጅትን ከመምረጥ ይልቅ ኢህአዴግን ብትመርጡ ይሻላል" እያሉ መቀስቀስ ጀመሩ፡፡ ኢህአፓ ግን በወቅቱ በራሱ መንገድ በቅንጅቱ ላይ በግልጽ ለመቀስቀስ አልተመቸውም ነበር፡፡ ኢህአፓ ብዙውን ጊዜ አምርሮ የሚጠላው አገር ውስጥ በምርጫ የሚሳተፍ ፓርቲን ቢሆንም ለሌላ ጥቅም ብሎ ራሱ ያቋቋመው ኅብረት ሳይታሰብ በእነ ፕሮፌሰር በየነ ተጠምዝዞ ምርጫው ውስጥ ስለገባበት የምርጫ ተሳትፎን በግልጽ ለማውገዝ ተቸግሮ ነበር፡፡

ኢህአፓ በመጨረሻው ሰዓት ኅብረቱ ከምርጫው ራሱን ያገላል የሚል ተስፋ የነበረው ቢሆንም ኅብረቱ ምርጫውን ከመሳተፍም አልፎ ፓርላማ በመግባቱ በመጨረሻ ኢህአፓ እነ ፕሮፌሰር በየነን በከሃዲነት በመፈረጅ ከእነሱ ጋር ለመለያየት ተገደደ፡፡ እነ ፕሮፌሰር በየነም የዐሥራ አራት ድርጅቶች ስብስብ ከነበረው ኅብረት ውስጥ ሁለት ድርጅቶችን ብቻ ይዘው የቀሩ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ግን ራሳቸውን "ኅብረት" ወይም "ኢዴኀህ" ነን እያሉ ሲጠሩ ይደመጣሉ፡፡ የሚገርመው ኢዴአፓ-መድኀንን ያለምንም ጥፋት ሲያወግዙትና ህልውና እንደሌለው አድርገው በሃሰት ሲፅፉ የነበሩ አንዳንድ ጋዜጠኞች ግን እነ ፕሮፌሰር በየነ በምን መመዘኛና መንገድ ኅብረቱን ሊወክሉ እንደሚችሉ ለመጠየቅ ሞክረው አያውቁም፡፡ እንዲያውም ይባስ ብለው "ኅብረቱ የሰጠው መግለጫ" እያሉ ዜና ሲዘግቡላቸው ኖረዋል፡፡

ቅንጅቱ ከላይ በገለፅኩት ሁኔታ ከተመሠረተ በኋላ ኢዴአፓ-መድኀን አዘጋጅቶ የሰጠውን የምርጫ ማንፌስቶ ይዞ በመውጣት በአጭር ጊዜ የኅብረተሰቡን ትኩረት ማግኘት ቻለ፡፡ በተለይም የምርጫ ቅስቀሳው ተጀምሮ ክርክሮች በመገናኛ ብዙኃን መደመጥ ሲጀምሩ ሕዝቡ ስለ ቅንጅቱ ውስጣዊ ድርጅታዊ ሁኔታ የሚያውቀው ነገር ባይኖርም ቀልቡ ይበልጥ እየተሳበና በቅንጅቱ አማካይነት ለውጥ የማግኘት ፍላጎቱ በፍጥነት እያደገ መጣ፡፡ ቅንጅት ግን በወቅቱ ቀድመው ድርጅታዊ ሥራ ሲሠሩ በቆዩት በመኢአድና በኢዴአፓ-መድኀን አማካይነት ለምርጫው እጩ ተወዳዳሪዎችን ከማቀረብና በየክርክር መድረኩ እየተገኘ የምረጡኝ ዘመቻ ከማካሄድ ባለፈ እንደ አንድ የፖለቲካ ስብስብ አብሮ መሥራት ብቻ ሳይሆን በአባል ድርጅቶቹ መካከል መግባባትና መተዋወቅ እንኳ መፍጠር ተስኖት ውስጥ ውስጡን እየታመሰ ነበር፡፡ በአጭሩ በሕዝቡ ዘንድ ጠንካራ ተደርጐ ይታይ የነበረው ቅንጅት በዚያን ወቅት አባላቱ እርስ በርስ መደማመጥና መግባባት የማይችሉበት "ባቢሎን" ሆኖ ነበር፡፡ ብዙዎቹን በቅንጅቱ ውስጥ የነበሩትን ልዩነቶች ትቼ ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉትን ጥቂት ልዩነቶች እንደሚከተለው ለማየት ልሞክር፡፡

የመጀመሪያው ልዩነት ከቅንጅቱ አባል ድርጅቶች ውስጥ የማንኛው ፓርቲ እጩ በቅንጅቱ ስም ሊወዳደር እንደሚገባው በመመደብ ዙሪያ የተፈጠረ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለምርጫው ቅንጅቱን ወክለው እጩ ተወዳዳሪዎችን ለምርጫ ቦርድ የማቅረብና የማስመዝገብ መብት የነበረው ቅንጅቱ እንደ ቅንጅት ሳይሆን አራቱ የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች ስለነበሩ ሁሉም ፓርቲ የየራሱን እጩ ለማስመረጥ ጥረት ማድረጉ የማይቀር ነበር፡፡ በወቅቱ በርካታ እጩዎች ማቅረብ የቻሉት መኢአድና ኢዴአፓ-መድኀን ስለነበሩ ድርድሩ በዋናነት ይካሄድ የነበረው በሁለቱ

ድርጅቶች መካከል ነበር፡፡ ቀስተዳመናና ኢዴሊ በቁጥር ከዚህ ግባ ሊባል የሚችል እጩ ስላልነበራቸው በድርድሩ ሂደት አደራዳሪ ከመሆን ያለፈ የጐላ ተሳትፎ አልነበራቸውም፡፡

በድርድሩ ዙሪያ ቀዳሚ የልዩነት ምንጭ የነበረው እጩዎችን በመምረጥ ረገድ የትምህርት ደረጃ ምን ያህል ክብደት ይኑረው? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን በወቅቱ የተማሩ ሰዎችን በተመለከተ ከነበረው አመለካከት በመነጨ ያቀረባቸው አብዛኛዎቹ እጩዎች የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ስለነበሩ የትምህርት ደረጃ የተሻለ ክብደት እንዲሰጠው ፈልጐ የነበረ ሲሆን፣ መኢአድ ደግሞ በአብዛኛው አቅርቧቸው የነበረው እጩዎች በትምህርት ደረጃቸው ብዙም ያልገፉ ስለነበሩ የትምህርት ደረጃ ዝቅተኛ ክብደት እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር፡፡ በመጨረሻ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በአስታራቂነት የቀረበውን አማካኝ መመዘኛ ሁለቱም ፓርቲዎች ተቀብለን ድርድሩ ሊጀመር ቻለ፡፡ ድርድሩ ተጠናቆ ውጤቱ ሲታወቅ አብዛኛዎቹ ኢዴአፓ-መድኅን ያቀረባቸው እጩዎች ተመራጭ ሆነው በመገኘታቸው መኢአድ ውጤቱን አልቀበልም ብሎ አፈነገጠ፡፡

በተለይም መኢአድ ጠንካራ ነኝ ብሎ በሚያምንበት ዐማራ ክልል ከ80% በላይ የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች ድርድሩን በማሸነፋቸው፣ አዲስ አበባ ላይ ለተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ከሚገባቸው ሃያ ሦስት እጩዎች ውስጥ ዐሥራ ስምንቱን ኢዴአፓ-መድኅን አሸንፎ በሁለት ወረዳዎች እኩል በመውጣቱና ለአዲስ አበባ ምክር ቤት መቅረብ ከሚገባቸው እጩዎች ደግሞ ከ60% በላይ ኢዴአፓ-መድኅን በማሸነፉ መኢአድ የድርድሩ ውጤት ተሽሮ ሌላ መፍትሔ ካልተሰጠኝ በስተቀር ከቅንጅቱ ተነጥዬ ብቻዬን እወዳደራለሁ የሚል አቋም ያዘ፡፡ ከዚህ በኋላ እነ ፕሮፌሰር መስፍን "ቅንጅቱ በዚህ ምክንያት ከሚፈርስ ኢዴአፓ-መድህኖች መኢአድ የሚጠይቀውን ቦታ ልቀቁለትና እባካችሁ ቅንጅቱን አድኑት" ብለው መማፀን ጀመሩ፡፡ መኢአድ ያቀረበው ጥያቄ ፈጽሞ ተገቢ ያልነበረ ቢሆንም ኢዴአፓ-መድኅን በወቅቱ ቅንጅቱን ከመፍረስ የማዳን ፍላጐት ስለነበረው ዐማራ ክልልን ያለምንም መመዘኛ ከመኢአድ ጋር ግማሽ ለግማሽ በመካፈልና በአዲስ አበባና በተለያዩ ክልሎች መኢአድ ይሰጠኝ ብሎ የጠየቃቸውን ቦታዎች በመልቀቅ ችግሩ እንዲፈታ አደረገ፡፡ ኢንጂነር ኃይሉ በውስጣችን እስካለ ድረስ የትም ሊደርስ አይችልም ሲሉ የነበሩት እነ ፕሮፌሰር መስፍንም ኢዴአፓ-መድኅንን ያለአግባብ እየተጫኑ ሁሉን ነገር እንዲቀበል ከማድረግ በስተቀር በመኢአድ ላይ የገመቱትን ተፅዕኖ ማሳደር ሳይችሉ ቀሩ፡፡

እጩ የማቅረቡ ድርድር በዚያ መልኩ ተጠናቆ ፓርቲዎች በድርድሩ ውጤት መሠረት እጩዎቻቸውን ለምርጫ ቦርድ አቅርበው ካጠናቀቁ በኋላ እጩ ማስመዝገቢያው የሚጠናቀቅበት

የመጨረሻው ቀን ላይ ሌላ አስደንጋጭ ዜና ከምርጫ ቦርድ በኩል መጣ። የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች በተስማማንበት መሠረት ሳይሆን መኢአድ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል ያሉትን እጩዎች ሙሉ በሙሉ ማስመዝገቡንና በዚህም ምክንያት በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍል የኢዴአፓ-መድኅንና የመኢአድ እጩዎች ርስ በርስ እንደሚወዳደሩ ከምርጫ ቦርድ ተደውሎ ተነገረን። ኢዴአፓ-መድኅን ግን በዚያን ወቅት በምርጫ ቦርድ ያስመዘገበው በድርድሩ ያለፉለትን እጩዎች ብቻ ስለነበር በዚያ ባለቀ ሰዓት ያላስመዘገባቸውን ግማሽ የሚሆኑትን እጩዎች እንደገና ሊያስመዘግብ የሚችልበት ዕድል አልነበረውም። በድርድሩ የወደቁትን እጩዎቹን ማቅረብ ብቻም ሳይሆን መኢአድ ከሌሎቹ የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች በተለየ የራሱን የምርጫ ምልክት መርጦ ለምርጫ ቦርድ እንዳሳወቀም ሰማን። በኋላ ላይ ኮፒው ደርሶን እንዳየነው የመኢአድ የምርጫ ምልክት ከአንገት በላይ የሆነ የሰው ምስል ነበር።

በወቅቱ መኢአድ ለምን ይህንን እንደፈፀመ ሲጠየቅ አሁንም በድርድሩ ውጤት ቅሬታ እንዳለውና ካስፈለገ የእጩዎች ምዝገባው በምርጫ ቦርድ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደገና ተደራድሮ እጩዎቹን ከምርጫው ሊያስወጣ እንደሚችል መልስ ሰጠ። ይህ አስደንጋጭ ሁኔታ የተፈጸመበት ቀን የእጩዎች ምዝገባ የሚጠናቀቅበት እሑድ ዕለት ስለ ነበር የቅንጅቱ አመራሮች ከየአለንበት ተደዋውለን ስብሰባ ለማካሄድ ብንሞክርም ኢንጂነር ኃይሉ ስብሰባው በዚያን ቀን እንዳይካሄድ በመከልከላቸው ሳንሰበሰብ ቀረን። እንደ አጋጣሚ ሆኖ እጩዎች የማቅረቢያው ዕለት በምርጫ ቦርድ በኩል ለሦስት ቀናት ማለትም እስከ ሮብ ድረስ በመራዘሙ በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ለሰኞ ከሰዓት በኋላ የቅንጅቱ ስብሰባ እንዲጠራ ተደረገ። ያ ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ሰኞ ጧት ፕሮፌሰር መስፍንና ዶ/ር ብርሃኑ ለእኔና ለአቶ ሙሼ ስልክ በመደወል በፕሮፌሰር መስፍን ቤት እንድንገናኝ ቀጥረውን ተገናኘን።

በተገናኘንበት ወቅት በእነ ፕሮፌሰር መስፍን በኩል መኢአድ አሁንም ኢዴአፓ-መድኅን እንዲለቅለት የሚፈልጋቸው ቦታዎች እንዳሉ ተነግሮን “ምን ብናደርግ ይሻላል?” በሚለው ጉዳይ ላይ መነጋገር ጀመርን። በእኛ በኩል ከዚያ በኋላ ሊያዋጣ የሚችለው ከመኢአድ ውጭ ያሉት ቀሪዎቹ ሦስቱ ፓርቲዎች ብቻቸውን እንዲሰሩ ማድረግ መሆኑን ገለፅን። እነ ዶ/ር ብርሃኑም ኢንጂነሩ ከመጀመሪያው የቅንጅቱ መሪ እንዲሆኑ መደረጉ ስህተት መሆኑን አምነው ነገር ግን በዚህ ምክንያት ቅንጅቱ ፈርሶ ሕዝቡ ከሚያዝን ተገቢ እንዳልሆነ ብናውቅም ኢዴአፓ-መድኅን አሁንም የመኢአድን ጥያቄ ተቀብሎ እንደገና ቅንጅቱን ከመፍረስ እንዲታደገው፣ ከዚያ በኋላ ግን መኢአድ ቀሪዎቹን እጩዎቹን ከምርጫው ካስወጣና እጩ የማስመዝገቢያው ጊዜ በተጠናቀቀ ማግስት የመጀመሪያ ሥራችን የሚሆነው የቅንጅቱን ምክር ቤት ሰብስቦ ኢንጂነር

ኃይሉ ሻውልን ከሊቀመንበርነት ማውረድ እንደሚሆን በመግለፅ ይህንን ሃሣባቸውን እንድንቀበላቸው ፕሮፌሰር መስፍንና ዶ/ር ብርሃኑ የልመና ያህል ተማፀኑን። ሰዎቹ ቃላቸውን ይጠብቃሉ ወይም የሚናገሩትን በተግባር ያውሉታል የሚል የተሟላ ተስፋና እምነት ያልነበረን ቢሆንም በወቅቱ በቅንጅቱ ላይ የተጋነነ ተስፋ ጠብቆ የነበረውን ሕዝብ ላለማሳዘን ብለን መኢአድ የጠየቀውን ተጨማሪ ቦታ ለመልቀቅ ተስማማን። በዚህም ኢዴአፓ-መድኅን የራሱን ጥቅም ያላግባብ ለመኢአድ አሳልፎ በመስጠት ቅንጅትን ለሁለተኛ ጊዜ ከመፍረስ አደጋ አዳነው።

ሰኞ ከሰዓት በኋላ የተጠራው የቅንጅቱ ሥራ-አስፈጻሚ ስብሰባ ከዚህ በላይ በጠቀስኩት መሠረት በስምምነት እንዲጢናቀቅ ተደርጐ በሁለት ቀናት ውስጥ መኢአድ ቀሪዎቹን ያለ አግባብ ያስመዘገባቸውን እጩዎችና ያስገባውን የምርጫ ምልክት ከምርጫ ቦርድ እንዲያስወጣ ተደረገ። ነገር ግን እጩ የማስመዝገቡ ሥራ ሮብ ከተጠናቀቀ በኋላ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ኢንጂነር ኃይሉን ከሥልጣን ለማውረድ መሞከር ይቅርና ለመተቸትም እንኳ ድፍረቱን አጡ። እንዲያውም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሚያስገርም ሁኔታ የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ጥረት ቀስተዳመናን በቅንጅቱ ውስጥ የበላይ የሚያደርግ ድርጅታዊ ሥራ ቀን ከሌሊት መሥራት ሆነ። በዚህም በግራው የፖለቲካ ባህል መሠረት በታክቲካዊ ትብብር ሰበብ ሌሎችን አጥፍቶ ወደ ሥልጣን የመንጠላጠሉ ስልት በእኛ ላይ እየተሞከረ እንደሆነም እየገባን መጣ። ከዚያ በኋላ እንዲህ ዓይነቱ ኃይል ጋር ፖለቲካ ለመሥራት መሞከር ከንቱ መሆኑን በመገንዘብ በእኔ በኩል በቅንጅቱ ውስጥ ከነበረኝ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነት ለቀቅሁ። በወቅቱ ሕዝቡ የነበረበትን ስሜት ግምት ውስጥ በማስገባትም ጉዳዩን ለሕዝቡ ያላሳወቅሁ ቢሆንም ኋላ ላይ በፓርቲዬ ውሳኔ እንደገና ወደ ሕዝብ ግንኙት ኃላፊነቴ እስከተመለስኩበት ጊዜ ድረስ ለሦስት ወር ያህል የቅንጅቱ ሕዝብ ግንኙት አልነበርኩም። ነገር ግን በወቅቱ ዐሥራ አንድ የሚሆኑ የቅንጅቱ አመራሮች እንደፈለጉ በየፊናቸው ለሚዲያ መግለጫ የሚሰጡበት ሁኔታ ስለነበር የእኔ ሕዝብ ግንኙነት መሆን ያን ያህል ጠቃሚ ቁምነገር አልነበረም።

የሚገርመው ግን እስካሁን ድረስ በአንድ በኩል መኢአድ ምን ያህል ቅንጅቱን ለማፍረስ ጥረት እንዳደረገ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢዴአፓ-መድኅን ምን ያህል ቅንጅቱን ከመፍረስ ሲያድነው እንደነበረ አንድም የቅንጅት አመራር የነበረ ሰው ሃቁን ለሕዝብ ደፍሮ ሲናገር አልተደመጠም። የቅንጅት መሪዎች ከእሥር ቤት ከወጡ በኋላ ምን ያህል ርስ በርስ ሲናከሱ እንደከረሙና አንድ ላይ መቆም ተስኗቸው ከሰባት እንደተበተኑ፣ ቀድሞውንም ቅንጅቱ አንድ ያልነበረ ድርጅት በመሆኑ ምክንያት ኢዴአፓ-መድኅን ብቻ ሳይሆን መኢአድም ሆነ ኢዴሊ በቀድሞ ማንነታቸው የቀጠሉ መሆኑ በተግባር በታዩበት በአሁኑ ወቅት እንኳ ሰዎች ለቅንጅቱ

መፍረስ ምክንያት ሊያደርጉ የሚፈልጉት ኢዴአፓ-መድኅንንና እኔን ነው፡፡ እንዲያውም ብዙ ሰዎች ዛሬም ድረስ የሚያስቡት ቅንጅቱ እንደ አንድ ወጥ ህልውና የነበረው ድርጅት የራሱን እጩዎች ለምርጫ አቅርቦ የተወዳደረ እንደሆነና ኢዴአፓ-መድኅንም ከስሞ የነበረ ድርጅት እንደሆነ አድርገው ነው፡፡

እውነታው ይህ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኢዴአፓ-መድኅን ብቻ ሳይሆን ቀድሞ የቅንጅቱ አባል የነበሩት መኢአድም ሆነ ኢዴሊ የቀድሞ ህልውናቸውን ይዘው ባልተንቀሳቀሱ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ራሱን እንደሌለ የሚቆጥረው የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ቀስተ-ዳመና ፓርቲ እንኳ እስካሁን ድረስ በምርጫ ቦርድ በኩል ያለው ህልውና አልተሰረዘም፡፡ ቅንጅት የራሱ የምርጫ እጩ ተወዳዳሪ ይቅርና እስከፈረሰበት ጊዜ ድረስ የግለሰብ አባልም ኖሮት አያውቅም፡፡ ቅንጅትን የፈጠሩት አራቱ ፓርቲዎች ስለነበሩ ቅንጅት የራሱን ዕጩ የማቅረብም ሆነ የግለሰብ አባል የመመልመል ሥልጣንና መብትም ኖሮት አያውቅም፡፡ የቅንጅት አባል ነን በማለት ሲናገሩ ስናደምጣቸው የነበሩ ሰዎች ሁሉ እንዲህ ዓይነቱን ንግግር ሲናገሩ የከረሙት ሕዝቡን ለማደናገርና ኢዴአፓ-መድኅንን የከሰመ አስመስሎ ለማቅረብ ነበር እንጂ ከወቅቱ የቅንጅቱ ሊቀመንበር ከኢንጂነር ኃይሉ ጀምሮ ማንኛችንም እስከ መጨረሻው ድረስ በግለሰብ ደረጃ ቅንጅት የሚባል ፓርቲ አባል ሆነን አናውቅም፡፡

ሌላው በቅንጅቱ ውስጥ አከራካሪ የነበረው ጉዳይ ቅንጅቱ በ97ቱ ምርጫ ሊያሸንፍ የሚችለው እስከምን ድረስ ነው? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ገና ቅንጅቱ ከመቋቋሙ በፊት ጀምሮ በ97 ዓ.ም ምርጫ አሸንፈን መንግሥት እንሆናለን ብሎ ያምን የነበረው መኢአድ ብቻ ሲሆን፣ ቅንጅቱ እየተቋቋመ በነበረበት ወቅት ቀስተ-ዳመና እንደ ፓርቲ የነበረውን አቋም ባላውቅም የፓርቲው መሪ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግን "በዚህ ምርጫ አዲስ አበባን ብናሸንፍና ከሠላሳ የማያንስ የፓርላማ መቀመጫ ማሸነፍ ብንችል ትልቅ ታሪካዊ ድል ነው" በማለት ይናገሩ እንደነበር በርግጠኛነት አውቃለሁ፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን ከምርጫው በፊትም ሆነ በምርጫው ወቅት በዚያ ምርጫ ለመንግሥትነት የሚያበቃ ውጤት እናገኛለን የሚል ብዥታ ኖሮት አያውቅም፡፡ ነገር ግን የምርጫው ዘመቻ እየተሟሟቀና ቅንጅት የሕዝቡን ትኩረት የበለጠ እያገኘ መምጣት ሲጀምር ዘንድሮ ምርጫውን አሸንፈን መንግሥት እንሆናለን የሚለው ስሜት በቅንጅቱ አመራሮች ዙሪያ የበለጠ እያደገ መጣ፡፡ በተለይም ከዚያ በፊት የሕዝብ ድጋፍና አድናቆት ምን ማለት እንደሆነ አይተውት የማያውቁት አዳዲሶቹ የቅንጅት መሪዎች በየመንገዱ "ቪቫ" ሲባሉና ፊርማቸውን ሲጠየቁ መንግሥት ለመሆን የተቃረቡ ስለመሰላቸውና ሁኔታዎች ከዚያ በኋላ ሊለወጡ ይችላሉ ብለው ስላልገመቱ ምርጫው ተጠናቆ ሥልጣን ላይ ለመፈናጠጥ ተቻኰሉ፡፡

ኢዴፓ
ኢዴፓ
ኢዴፓ

እንዲህ ዓይነቱ የስሜት ግለት ኢዴአፓ-መድኅንን እያሳሰበው ስለመጣም የቅንጅቱ አመራር “በምርጫው የምንጠብቀው ከፍተኛ ውጤት ምን ይሆናል?” በሚለው አጀንዳ ላይ እንዲወያይበት ጥያቄ አቀረበ፡፡

መጀመሪያ ላይ ጥያቄውን ትርጉም የለሽና መጥፎ አስተሳሰብ አድርጎ በማየት ላለመቀበል ተፈልጎ የነበረ ቢሆንም ኋላ ላይ በኢዴአፓ-መድኅን ግፊት ጉዳዩ የውይይት አጀንዳ ሆኖ መቅረብ ቻለ፡፡ በውይይቱ ላይ በእኛ በኩል በዚህ ምርጫ የመንግሥትነት ሥልጣን የማሸነፍ ዕድል ስለማይኖረን ልናገኘው ስለምንችለው ከመንግሥትነት ያነሰ ለውጥ ራሳችንን ከወዲሁ ማዘጋጀት እንደሚገባን የሚያሳስብ ሐሳብ ስናቀርብ፣ በኢንጂነር ኃይሉ በኩል ደግሞ ዘንድሮ የመንግሥትነት ሥልጣን ማሸነፋችን የሚያጠራጥር አይደለም የሚል አቋም ቀረበ፡፡ በወቅቱ እኛ ባቀረብነው ሐሳብ ብዙ ሰዎች ተደናግጠው የነበረ ሲሆን፣ ለምሳሌ ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ __“እኔ ዘንድሮ እዚህ ትግል ውስጥ የገባሁት እኮ ወያኔ ይወድቃል ብዬ ነው፣ እንዴት እንዲህ ዓይነት የማይረባ ሐሳብ ታቀርባላችሁ?” በማለት አምርረው አኩርፈውኝ እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ ለውይይት በቀረበው አጀንዳ ላይ በቀላሉ መግባባት ሊፈጠር ስላልቻለም እኔና ኢንጂነር ኃይሉ በጉዳዩ ላይ ያለንን አቋም በተመለከተ የውይይት መነሻ የሚሆን ሐሳብ በጽሑፍ ለቅንጅቱ እንድናቀርብ ተወሰነ፡፡

ከሳምንት በኋላ እኔና ኢንጂነር ኃይሉ እንድናቀርብ የተጠየቅነውን የመነሻ ጽሑፍ ይዘን ቀረብን፡፡ ኢንጂነር ኃይሉ ይዘው በቀረቡት አጭር ጽሑፍ በእያንዳንዱ ክልል ምን ያህል መቀመጫ በማሸነፍ በምርጫው የመንግሥት ሥልጣንን እንደምንረከብ አስረዱ፡፡ በወቅቱ ኢንጂነር ኃይሉ እናሸንፋለን ለሚለው አቋማቸው አሳማኝ ምክንያት አድርገው ያቀረቡት “ሕዝቡ ወያኔ በቅቶታል፡፡ ለውጥ ለማምጣት  በሚገባ ተዘጋጅቷል፡፡ በየሄድንበት አካባቢ የምናየው የሕዝብ ስሜት ይህንኑ የሚያረጋግጥ ስለሆነ ዘንድሮ ማሸነፋችን አይቀርም” የሚል ነበር፡፡ ከእዚህ የኢንጂነር ኃይሉ አስተሳሰብ በተፃራሪ በእኔ በኩል “በዚያ ምርጫ መንግሥት ለመሆን የሚያስችል ውጤት ማግኘት አንችልም” ለሚለው አቋሜ ያቀረብኳቸው ዋና ዋና መከራከሪያ ምክንያቶችም የሚከተሉት ነበሩ__፡፡

አንደኛ በዚያን ወቅት ገዥው ፓርቲ በነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ሥልጣኑን ለመልቀቅ እንዳልተዘጋጀ ግልጽ ነበር፡፡ የአገሪቱን ኢኮኖሚ፣ ሁለንተናዊ የቢሮክራሲና የጸጥታ ተቋማት በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር የያዘ ገዥ ፓርቲ ሥልጣኑን በፈቃደኛነት ለመልቀቅ ዝግጁ እስካልሆነ ድረስ በዚያ ወቅት ተቃዋሚዎች ከሥልጣን ልናወርደው የምንችልበት አቅም ስለሌለን ምርጫውን ላለማሸነፍ በራሱ በቂ ምክንያት ነበር፡፡ ገዥው ፓርቲ ሥልጣኑን ለመልቀቅ ለምን

አልተዘጋጀም? ለሚለው ጥያቄ ምክንያቱን “መድሎት” በሚለው መጽሐፌ ውስጥ በሠፊው ስለገለፅኩት እዚህ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይሆንም፡፡

ሁለተኛ - በወቅቱ ቅንጅቱ በምርጫው ለፓርላማ መቀመጫ መወዳደር ከሚገባው 547 ወረዳዎች ውስጥ በ130 ወረዳዎች የሚያቀርበው እጩ አጥቶ አልተወዳደረም ነበር፡፡ ይህም ማለት ገና ምርጫው ሳይካሄድ 130 የፓርላማ ወንበር በገዥው ፓርቲ ተሸንፈናል ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ - ትግራይን፣ አፋርን፣ ሶማሌን፣ ሐረሪን፣ ጋምቤላንና ቤንሻንጉልን በመሳሰሉት ክልሎች በራሱም ሆነ በአጋር ድርጅቶቹ አማካይነት ገዥው ፓርቲ የነፍጠኛ ድርጅት ተደርጐ ከሚታየው ከቅንጅቱ የተሻለ የመመረጥ ዕድል እንደ ነበረው ግልፅ ነበር፡፡ እነዚህ ክልሎች ከፓርላማው ውስጥ 79 መቀመጫ የሚሸፍኑ ስለሆነ ቅንጅት ከዚህ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን ወንበር በእነዚህ ክልሎች ሊያጣ እንደሚችል አስቀድሞ የታወቀ ነበር፡፡ ኋላ ላይ የምርጫው ውጤት እንዳረጋገጠውም ቅንጅት በእነዚህ ክልሎች አንድም መቀመጫ ሳያሸንፍ ቀርቷል፡፡

አራተኛ - በአንዳንድ የኦሮሚያና የደቡብ ክልል ወረዳዎች ገዥው ፓርቲ የራሱ ድጋፍ ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከገዥው ፓርቲ በተጨማሪ በደቡብ የእነ ፕሮፌሰር በየነ ፓርቲዎች፣ በኦሮሚያ የእነ ዶ/ር መረራ የእነ አቶ ቡልቻ ፓርቲዎች ከቅንጅቱ የተሻለ የመመረጥ ዕድል ነበራቸው፡፡ የምርጫው የመጨረሻ ውጤት እንዳሳየውም እነዚህ ሦስት የብሔር ድርጅቶች በግል የተወዳደሩትን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ጨምሮ በአጠቃላይ 64 መቀመጫዎችን አሸንፈዋል፡፡ በአንዳንድ የደቡብና የኦሮሚያ አካባቢ ቅንጅቱ የተሻለ የመመረጥ ዕድል ይኖረዋል ተብሎ ቢገመት እንኳ በየምርጫ ክልሉ ኢህአዴግ፣ ቅንጅትና እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው በኦሮሚያና በደቡብ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች በአንድ ላይ ስለምንፎካከር ተቃዋሚውን ጎራ የሚደግፈው ሕዝብ ድምጽ ለሁለት ስለሚከፈል ኢህአዴግ በአነስተኛ ድምፅ በብዙ ቦታዎች የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖረው ግልጽ ነበር፡፡ ኢህአዴግ በእነዚህ ትልልቅ ክልሎች በተቃዋሚዎች ድምፅ መከፋፈል ምክንያት ቢያንስ አርባ-አርባ መቀመጫዎችን ቢያሸንፍ እንኳ ቅንጅት ከሰማንያ ያላነሰ መቀመጫ ሊያጣ እንደሚችል ግልጽ ነበር፡፡ በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ቅንጅቱ ቢያንስ እስከ 353 መቀመጫ ሊያጣ እንደሚችል አስቀድሞ የሚገመት ነበር፡፡ ይህም ማለት ምርጫው በሆነ ተአምር ሙሉ በሙሉ ነፃና ዴሞክራሲያዊ ሆኖ ቅንጅት ከዚህ ከ353 ወረዳዎች ውጭ ያሉትን ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ቢያሸንፍ እንኳ በፓርላማው ሊያገኝ የሚችለው መቀመጫ 194 ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ቁጥር መንግሥት ለመመሥረት ከሚያስፈልገው ከ274 መቀመጫ ውስጥ በ80 መቀመጫ ያነሰ ስለሆነ

በዚያ ምርጫ ቅንጅቱ መንግሥት ለመሆን በሚያበቃ ደረጃ በምንም ተአምር ሊያሸንፍ የሚችልበት ዕድል አልነበረም፡፡

አምስተኛ - ቅንጅት በመላው አገሪቱ ባሉ የምርጫ ጣቢያዎች በቂ የምርጫ ታዛቢዎች አሰማርቶ ምርጫውን ከመጭበርበር ለመከላከል ቢያንስ ከ90 ሺ ያላነሱ ታዛቢዎች ማሰማራት ያስፈልገው ነበር፡፡ ይህንን ያህል ታዛቢ ማቅረብ ደግሞ በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ጨርሶ የሚቻል አልነበረም፡፡ በአንዳንድ ምርጫ በተወዳደርንባቸው የገጠር ወረዳዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ታዛቢዎችን ማቅረብ ይቅርና እጩ ሆነው ከቀረቡት ሰዎች በስተቀር አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ አባላት አልነበሩንም፡፡ መጨረሻ ላይም በተግባር እንደታየው ቅንጅቱ በአጠቃላይ በአገሪቱ የአቀረባቸው ታዛቢዎች ከ15 ሺ ያነሱ ነበሩ፡፡ ይህም ማለት ከሰባ አምስት ሺ በላይ ታዛቢዎች ሊቀመጡባቸው የሚገቡ የምርጫ ጣቢያዎች ኢህአዴግ የፈለገውን ነገር እንዲፈፅም ክፍት ነበሩ ማለት ነው፡፡ በእነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች ምርጫውን ከመጭበርበር መከላከል ይቅርና ምርጫው ተጭበርብሯል አልተጭበረበረም ብለን ለመከራከር እንኳ የሚያስችለን በቂ መረጃ ማግኘት የምንችልበት ዕድል አልነበረንም፡፡ ስለዚህ በተለይም ከላይ ገዥው ፓርቲ ሥልጣኑን ለመልቀቅ እንዳልተዘጋጀ ከገለፅኩት ጋር ተያይዞ ሲታይ በቂ የምርጫ ታዛቢ ሳያቀርቡ ከመጀመሪያው ምርጫውን እናሸንፋለን ብሎ ማሰብ ከህልም ሩጫ የተሻለ ግምት አልነበረም፡፡

ስድስተኛ - 85% የሚሆነውንና መጻፍና ማንበብ የማይችለውን የገጠሩን የአገራችንን ሕዝብ እንዴት አድርገን በአግባቡ ድምፁን ሊሰጥ እንደሚችል ማስተማር የምንችልበት አቅም አልነበረንም፡፡ የቅንጅቱ ዝርዝር ዓላማ፣ ስምና ምልክት ምን እንደሆነ በአግባቡ የማያውቅ በሚሊየን የሚቆጠር ሕዝብ መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ በአገራችን ራሱ ምርጫ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የማይረዳው ሕዝብ ቀላል ቁጥር ያለው አይደለም፡፡ በተለያዩ የምርጫ ወቅቶች እንዳየነውም በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማ የሚኖሩ እናቶች ሳይቀሩ ድምፅ መስጫው ክፍል ውስጥ ከገቡ በኋላ ነበር - ማንነው የምመርጠው? እንዴት አድርጌ ነው የምመርጠው? የሚለውን ጥያቄ የሚጠይቁት፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን መራጭ በአካል እያገኙ ስለምርጫው አፈጻጸም ማስተማር ባልተቻለበት ሁኔታ በርግጠኛነት ምርጫውን እናሸንፋለን ማለት የሚቻል አልነበረም፡፡ በየገጠሩ ምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን በፈለገው መልኩ የመጠቀም ዕድል የነበረው ከማንም በላይ በያንዳንዱ ቀበሌ የተጠናከረ ድርጅታዊ አቅምና መዋቅር የነበረው ገዥው ፓርቲ ብቻ ነበር፡፡

እነዚህን ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸውን ምክንያቶች በዝርዝር ለተሰብሳቢው ካቀረብኩ በኋላ በ97ቱ ምርጫ በርግጠኛነት ለማሸነፍ የምንችለው ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ልንቋቋም በምንችልባቸው በአዲስ አበባና ከሠላሳ ሺ ሕዝብ በላይ ኗሪ በሚገኝባቸው በአንዳንድ የአገሪቱ ከተሞች እንደሚሆን፣ ከዚህ በመነሣትም አዲስ አበባ መስተዳድርን አሸንፈን ልንረከብ እንደምንችልና በፌደራል ፓርላማው ከሰማንያ ስድስት ያላነሰ መቀመጫ ልናሸንፍ እንደምንችል፣ ይህንን ውጤት በአግባቡ ይዘን ከተጠቀምንበትም ከአምስት ዓመት በኋላ በሚካሄደው አገራዊ ምርጫ መንግሥት ለመሆን የሚያበቃንን ዕድል ማግኘት እንደምንችል ገለፅኩ፡፡ በወቅቱ ማንኛውም የቅንጅቱ አመራር የራሱን መከራከሪያ ሐሳብ በማቅረብ የእኔን ሐሳብ ለመሞገት ያልሞከረ ቢሆንም እኔና ኢንጂነር ኃይሉ ባቀረብነው የውይይት መነሻ ሐሳብ ላይ ድምፅ እንዲሰጥ ሲደረግ ዘንድሮ አዲስ አበባን ነፃ ካወጣን ትልቅ ታሪክ ነው ሲሉ የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ አብዛኛው የቅንጅቱ አመራሮች በፍላጐት ወይም በምኞትና በነባራዊ እውነታ መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ መረዳት ተስኗቸው በዘንድሮው ምርጫ ምርጫውን አሸንፈን መንግሥት እንሆናለን የሚለውን አቋም በመደገፋቸው የእኔ ሐሳብ ውድቅ ሆነ፡፡

በነገራችን ላይ ይህንን በእኔና በኢንጅነር ኃይሉ የቀረበ የውይይት መነሻ ጽሑፍ አቶ ገብረክርስቶስ የተባሉት የመኢአድ አባልና የቅንጅቱ ቃለ-ጉባዔ ጸሐፊ የነበሩት ሰው ከአንድ ዓመት በፊት ስለ ቅንጅት ጽፈው ባሳተሙት ቅንጅት ከየት ወዴት? በሚለው መጽሐፍ ላይ ሙሉ በሙሉ አውጥተውታል፡፡ በወቅቱ የቅንጅቱ አመራር የሰጠው ድምፅ ተጨባጭ ምክንያትን መነሻ ያደረገ ሳይሆን በደፈናው መንግሥት የመሆን ፍላጐትንና ምኞትን ብቻ መነሻ ያደረገ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በርግጥ እነ ኢንጂነር ኃይሉ ከመጀመሪያው ያን ያህል እጩ ተወዳዳሪ ከኢዴፓ-መድኅን ያለአግባብ ለመንጠቅ ሲጥሩ የነበሩት ምርጫውን እናሸንፋለን የሚል ጠንካራ እምነት ስለነበራቸውና ቅንጅቱ ምርጫውን ካሸነፈ ደግሞ በቅንጅቱ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመምረጥ የሚያስችለውን የድምፅ ብዛት መኢአድ አስቀድሞ እንዲይዝ ይፈልጉ ስለነበር ነው፡፡

የኢንጅነር ኃይሉ ሐሳብ ድጋፍ አግኝቶ የቅንጅቱ የጋራ አቋም እንዲሆን ከተወሰነ በኋላ የቅንጅቱ የምርጫ ዘመቻ ምርጫውን እናሸንፋለን የሚለውን አቋም አጉልቶ እንዲያሳይ ተወሰነ፡፡ በነገራችን ላይ ይህንን ዓይነቱን ውሳኔ የምርጫው ውጤት ምንም ይሁን ምን በእኛም በኩል የምንጋራው ነበር፡፡ ምክንያቱም ምርጫውን እናሸንፋለን የሚል ስሜት በሕዝቡ ውስጥ መፍጠር ካልቻልን በስተቀር ኢዴፓ-መድኅን የገመተውን አነስተኛ ውጤትን ማግኘት እንደማይቻል ርግጠኞች ስለነበርን ነው፡፡ ምርጫውን አሸንፈን መንግሥት የምንሆንበት ዕድል እንዳልነበረ ርግጠኞች የነበርን ቢሆንም የምርጫ ቅስቀሳው "እናሸንፋለን" በሚል መንፈስ እንዲመራ የኛም

ፍላጐትና እምነት ነበር፡፡ እኛ እንፈልግ የነበረው ቅንጅቱ ከላይ ከጠቀስኳቸው ነባራዊ ምክንያቶች በመነሣት ምርጫውን እንደማያሸንፍ እንደ ድርጅት በውስጡ መተማመን ፈጥሮ ለሕዝቡ ግን እስከ ምርጫው ፍጻሜ ድረስ "የእናሸንፋለን" ቅስቀሳ ካደረገ በኋላ የሚገኘውን ውጤት ተቀብሎ ትግሉን የበለጠ አጠናክሮ እንዲቀጥል ነበር፡፡ ነገር ግን ቅንጅቱ አስቀድሞ ከመንግሥት ያነሰ ውጤትን ለመቀበል ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት ስላልነበረው ከምርጫው በፊት የተጠቀመበትን የ"እናሸንፋለን" ቅስቀሳ ከምርጫውም በኋላ የምር አድርጐ ቀጠለበት፡፡ ቅንጅቱ ከምርጫው ፍጻሜ በኋላ ሕዝቡን በትክክለኛው አቅጣጫ አስገብቶ መምራት ያልቻለበትና ኋላም ላይ "ፓርላማ አንገባም፣ አዲስ አበባንም አንረከብም" ወደሚል አውዳሚ ውሳኔ እንዲሄድ ያስገደደው ይኸው ዘንድሮ ምርጫውን በየትኛውም መንገድ አሸንፈን የግድ መንግሥት መሆን አለብን የሚለው ከተጨባጩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጋጭ ምኞትና ተስፋ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የሆኖ ሆኖ ከቅንጅት ምሥረታ ጀምሮ እስከ ግንቦቱ ምርጫ ድረስ በአንድ በኩል ሁሉም ፓርቲ በሥራ ተጠምዶ ስለነበር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢዴፓ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶት በነበረው በቅንጅት ውስጥ አባል ሆኖ እየሠራ ስለነበር በኢዴፓም ሆነ በእኔ ላይ አሉባልታ ለማውራት የሚያመች ወቅት አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት ያ ወቅት የአሉባልታ ሳይሆን ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ አድናቆትና ድጋፍ ከሕዝቡ ያገኘንበት ጊዜ ሆኖ አለፈ፡፡ በተለይም ከምርጫው ሰባት ቀን በፊት ሚያዚያ 30 ቀን 97 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ የተካሄደው የቅንጅት ሕዝባዊ ስብሰባ በደመቀ ሁኔታ ታሪካዊ ዕለት ሆኖ አለፈ፡፡ ለእኔ እንደማይመጥነኝ ስለማውቅ የማያስደስተኝና የሚከብደኝ አባባል የነበረ ቢሆንም "ልደቱ ማንዴላ!" የሚለው መፈክርም በየጐዳናው ገኖ የተሰማው በዚያ ዕለት ነበር፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የቅንጅት ወደ ውድቀት መንደርደርና የአሉባልታ መንሰራራት

የምርጫ 97ን የመጨረሻ ውጤት እንዳየነው ቅንጅት እንዳሸነፈ በገኘው ፓርቲ የታመነለት አዲስ አበባ መስተዳድርንና 109 የፓርላማ መቀመጫ ሆነ። ይህ ውጤት እኛ አስቀድመን መገመት ከቻልነው ብዙም ያልራቀ ቢሆንም የቅንጅቱ አመራሮች የእኛን የቅድሚያ ግምት እንደመጥፎ ሟርት እንጂ ከተጨባጩ ፖለቲካዊ ሁኔታ የተነሣ ተገቢ ትንታኔና ትንበያ አድርገው ሊወስዱት አልፈለጉም ነበር። ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ምርጫው ሊጭበረበር እንደሚችል እኛም አስቀድመን ርግጠኞች የነበርንና ይህም ምክንያት ምርጫውን ልናሸንፍ አንችልም ካልንባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የነበረ ቢሆንም፣ በአብዛኛው ታዛቢ ባላቀረብንባቸው የምርጫ ክልሎች ምርጫው ተጭበርብሯል ብለን እንኳ ተጨባጭ መረጃ ልናቀርብ በማንችልበት ሁኔታ "ምርጫው ስለተጭበረበረ ውጤቱን አንቀበልም" ወደሚል የማይገባ ጫፍ ራሳችንን በመግፋት ትግሉን አደጋ ውስጥ ከተትነው። የቆጡን አወርድ ብላ የብብትዋን ጣለች እንዲሉ በዚያ ምርጫ ወቅት ያገኘነውን ውጤት አስጠብቀን መቀጠል አለመቻል ብቻ ሳይሆን ከአምስት ዓመት በኋላ በሚደረገው አገራዊ ምርጫ ልናገኝ ይገባን የነበረውን የመንግሥትነት ድል ከወዲሁ የሚያሳጣ ታሪካዊ ስህተት ሠራን።

በምርጫው ዘመቻ ወቅት ከነበረው የጋለ ቅስቀሳ ጋር በተያያዘ ሰዎች በእኔ ላይ የሚያነሡት ጥያቄ እንዳለ በተደጋጋሚ እሰማለሁ። ይኸውም "በቅስቀሳው ወቅት እናሸንፋለን የሚል ጠንካራ ቅስቀሳ ስታደርግ የነበርከው አንተ ነህ - ነገር ግን ከምርጫው በኋላ አንተ ለዘብተኛ ሆነህ ቀረብክ" በማለት ሊወቅሱኝ የሚሞክሩ ብዙ ሰዎች ያጋጥሙኛል። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ እንዲያነሡ ያደረጋቸው ለውጥ በእኔ ዙሪያ ማየታቸው ሊካድ የሚችል አይደለም። ምክንያቱም ከምርጫው ማግስት ጀምሮ እኔም ሆንኩ ኢዴአፓ-መድኅን በጠነከረ ሁኔታ ቅንጅቱ ውስጥ ስናራምደው የነበረው አቋም- "ምርጫው መጭበርበሩን አንድ ጊዜ ለሕዝቡ ካሳወቅን በኋላ የምርጫውን አጠቃላይ ውጤት አንቀበልም ወደሚል አቋም መሄድ አይጠቅመንም፤ ከተቻለም ሕዝብ ምርጫው ተጭበርብሯል የሚለውን ስሜቱን በሰላማዊ ሰልፍ አንድ ጊዜ እንዲገልፅ አድርገን በእጃችን የገባውን ውጤት አስጠብቀን፣ ፓርላማ ገብተንና አዲስ አበባን ተረክበን ለበለጠ ውጤት ትግሉን አጠናክረን መቀጠል ይገባናል እንጂ ውጤቱን

አንቀበልም የሚለውን አቋም ከገፋንበት የማንወጣበት አጣብቂኝ ውስጥ ራሳችንንም ሆነ ትግሉን እናስገባዋለ" የሚል ነበር፡፡

ነገር ግን እነዚህ እኔን ለመውቀስ የሚሞክሩ ሰዎች የሚሳሳቱት ይህንን በእኔ ዙሪያ ያዩትን ለውጥ ከእኔ የግል ፍላጐትና ጥቅም ጋር አያይዘው ማየታቸውና ለትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል ሲባል እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ በእኔና በኢዴአፓ-መድኀን ብቻ ሳይሆን በሁሉም የቅንጅቱ አመራሮች መታየት የነበረበት መሆኑን አለመገንዘባቸው ነው፡፡ ከምርጫው በፊት እኔም ሆንኩ ሌሎቹ የቅንጅቱ አመራሮች በሕዝቡ ውስጥ ምርጫውን እናሸንፋለን በሚል ቅስቀሳ የለውጥ ስሜት መፍጠር ባንችልና በምርጫው እንሸነፋለን የሚል ትንሽ ምልክት እንኳ አሳይተን ቢሆን ኖሮ በምርጫው ቀን ያገኘነውን ውጤት ማግኘት ይቅርና ሕዝቡ ከመጀመሪያው በመራጭነት በበቂ መጠን ወጥቶ ሊመዘገብ አይችልም ነበር፡፡ ስህተቱ ከምርጫው በፊት እናሸንፋለን ብለን መቀስቀሳችን ሳይሆን ከምርጫው ቀን በኋላ ያንኑ በምርጫው ቅስቀሳ ወቅት የተጠቀምንበትን ስልት ይዘን ለመቀጠል መሞከራችን ነው፡፡ እንኳን በእኛ አገር ሁኔታና በሌሎቹ የምርጫ ባህል በዳበረባቸው አገሮችም የምርጫ ዘመቻዎች የከረሩና ስሜት የበዛባቸው መሆናቸው የተለመደ ነው፡፡

በቅርቡ በአሜሪካን የተካሄደውን ፕሬዘዳንታዊ ምርጫ በምሳሌነት ለማየት ብንሞክር - በቅድሚያ በሄላሪና በኦባማ፣ ኋላ ላይም በኦባማና በማኬይን መካከል እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ የነበረው የተካረረ ፉክክር ሲታይ ከምርጫው በኋላ ሁኔታዎች ይረግባሉ ብሎ ማሰብ የሚያስቸግር ነበር፡፡ ነገር ግን በቅድሚያ ሄላሪ ሽንፈቷን ከመቀበል አልፋ ከኦባማ ጐን ቆማ ለፓርቲዋ ስትቀሰቅስ፣ ማኬይንም መሸነፋቸውን ባወቁ በደቂቃዎች ውስጥ ኦባማን እንኳን ደስ አለህ በማለት ሲያደንቁና ሲያመሰግኑ ስናይ ከዚህ ልንማር የምንችለው ትልቅ ቁምነገር የሚቻለውን ያህል የተሻለ ውጤት ለማምጣት ፖለቲከኞች በምርጫ ዘመቻ ወቅት የከረረ ዘመቻ ማካሄዳቸው የተለመደና የሚገባ ስልት መሆኑን ነው፡፡ እኛም ሆን ሌሎች የአፍሪካ አገር ፖለቲከኞች ከሰለጠኑት አገሮች ፖለቲከኞች የሚለዩን እናሸንፋለን የሚለውን የምርጫ ዘመቻ ስሜት የርስ በርስ ግጭትና መገዳደል እስከሚያሥነሳ ድረስ በእልህ የምንገፋበት መሆኑ ላይ ነው፡፡

ስለዚህ ሰዎች በምርጫ ቅስቀሳው ወቅትና ከምርጫው በኋላ በእኔ ዙሪያ ያስተዋሉት ለውጥ በድንገት የተከሰተ የፖለቲካ አቋም ለውጥ ሳይሆን ለትግሉ ደኅንነትና የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ሆን ተብሎ የተያዘና ሊያዝም የሚገባው ስልት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ተገቢ ስልት የቅንጅቱ አመራሮች በአንድ ላይ አራምደነው ቢሆን ኖሮ ሕዝቡም የስልታችንን ትክክለኛነት

በአግባቡ ተገንዝቦ ሲደግፈን የማይችልበት ምክንያት አልነበረም፡፡ ችግሩ በዕድሜና በትምህርት ደረጃቸው አንቱ የተሰኙት የቅንጅቱ መሪዎች የተሳሳተውን አቅጣጫ በመከተላቸው ምክንያት ሕዝቡ በአብዛኛው በወጣቶች እየተመራ ካለው ከኢዴአፓ-መድኅን አቋም ይልቅ የእነዚህን ሰዎች አቋም ትክክለኛ አድርጐ እንዲያይ መገደዱ ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ቅንጅቱ በዚህ ዓይነት አሳሳቢ ውዝግብ ውስጥ በገባበት በዚያ ወቅት ነበር የወደፊቱ የቅንጅቱ ዕጣ -ፈንታ ያላማራቸው ፕሮፌሰር መስፍን ራሳቸውን ከቅንጅቱ አመራር ያገለሉት፡፡ ነገር ግን ፕሮፌሰር መስፍን በዚያን ወቅት ራሳቸውን ከአመራርነት ሲያገልሉም ሆነ ከሁለት ዓመት የእሥር ቤት ቆይታ በኋላ ሲፈቱ የጉዳዩ ባለቤት ለሆነው ሕዝብ እርሳቸው ከኃላፊነት የለቀቁበትን እውነተኛ ምክንያት ሊነግሩት አልደፈሩም ነበር፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ራሳቸውን ከቅንጅት አመራር አግልለው እንደነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የተናገሩት የቅንጅት አመራሮች ከእሥር ቤት ወጥተው መፈረካከስ ከጀመሩ በኋላ ነበር፡፡ በእኔ አመለካከት ፕሮፌሰር መስፍን ራሳቸውን በድብቅ ከኃላፊነት አግልለው በዝምታ ከመቀመጥ ይልቅ እንደ አንድ ኃላፊነት እንደሚሰማው አመራር በወቅቱ ሕዝቡ የቅንጅቱን ውስጣዊ ሁኔታ እንዲገነዘብ መናገር የሚገባቸውን እውነት ተናግረው ቢሆን ኖሮ በሰዎች ዘንድ ካላቸው የተሻለ የመታመን ሁኔታ አንጻር በቅንጅት ውስጥ የተፈጠሩ ችግሮች ቀድመው የሚታረሙበት ዕድል በተፈጠረ ነበር፡፡

የሚገርመው ግን ፕሮፌሰሩ "ቅንጅት የቅቤ ገበያ ሆኗል" ብለው ራሳቸው ከአመራርነት መልቀቃቸውን እያዎቁ ኢዴአፓ-መድኅን ያላግባብ ከቅንጅቱ ተገፍቶ እንዲዎጣ ሲደረግ ግን ቅንጅቱ በውስጣዊ ችግር እየታመሰ መሆኑን ለሕዝቡ በአግባቡ አሳውቀው ከባሰ ውድቀት እንዲድን ከማድረግ ይልቅ ይባስ ብለው የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎችን "ቅንጅቱ በሚላችሁ መንገድ ካልሄዳችሁ ጆሮአችሁን የሚቆርጥ ጽሑፍ እጽፍባችኋለሁ" በማለት ማስፈራራትን መረጡ፡፡ የኢዴአፓ-መድኅንን ከቅንጅት መለዬት የሥልጣን ሽኩቻና አፍራሽነት አድርገው ሲዎቅሱ እንዳልነበረው ዛሬ እሳቸውም ተራቸው ደርሶ በእነ ኢንጅነር ግዛቸው ከአንድነት ፓርቲ ተባረዋል ሲባሉ ግን የተፈጠረውን ልዩነት በዴሞክራቶችና በጡንቸኞች መካከል የተፈጠረ ልዩነትና የመርህ አለመከበር ጉዳይ አድርገው ሲያቀርቡት ተደመጡ፡፡ ድርጊቱ የተፈጸመው በርሳቸው ላይ ስለሆነ በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን እየቀረቡ አንድነት ፓርቲን ሲያወግዙ፣ ምርጫ ቦርድ ድረስ ሄደው ክስ ሲያቀርቡና የተቃውሞ እንቅስቃሴ በማስተባበር ጭምር የአንድነት ፓርቲ ጉባዔ በረብሻ እንዲበተን ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ቅንጅት ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በተደጋጋሚ የራሱን መርህ እየጨፈለቀ ኢዴአፓ-መድኅን በርሳቸው ሽምግልና ጭምር የማይገባውን እዳ ሲከፍል እንደኖረ

በገሃድ እያወቁ በዝምታ እንዳላለፉ ሁሉ ችግሩ በሳቸው ሲደርስ ግን የመርህ ጉዳይ ክፉኛ ሲቆጠቁጣቸው ማየታችን ስለርሳቸው የሞራል ታላቅነት የነበረን ግምት ምን ያህል የተሳሳተ እንደነበር አረጋግጦልን አልፏል፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን መብቱንና ህልውናውን ለማስከበር የወሰደው እርምጃ እንደ ከሃዲነትና አፍራሽነት እንዳልተቆጠረበት ሁሉ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ለመብታቸው መከበር የሚያደርጉት ትግል ግን በተለየ ሁኔታ የመርህ ማስከበር ጉዳይ ተደርጎ እንዲታይ ተሞከረ፡፡ ራሳቸውን እንደ አንድ የድርጅት አመራር ሳይሆን የቅንጅቱም ሆነ የአጠቃላይ ትግሉ የነፍስ አባት አድርገው የሚቆጥሩት ፕሮፌሰር መስፍን በሆስፒታል አልጋ ላይ ተኝተው ስለ ቅንጅቱ የውስጥ ችግር መናገር ከጀመሩበት ወቅትም ለቅንጅቱ ችግሮች እኔን፣ እንጂነር ኃይሉንና ዶ/ር ብርሃኑን በደፈናው ተጠያቂ ከማድረግና በፖለቲካ አመራርነት አብረዋት ሰርተው የማያውቋትን ወ/ሪት ብርቱካንን ያለምንም ተጨባጭ መነሻ “ጠንካራ መሪ ናት” እያሉ ከማድነቅ በስተቀር እውነቱን በተሟላ ሁኔታ ለሕዝብ ሲመሰክሩም ሆነ ራሳቸውን በቅንጅቱ ዙሪያ የተፈጠሩ ችግሮች አካል አድርገው ሲናገሩ ተደምጠው አያውቁም፡፡ በርግጥ ፕሮፌሰር ከምርጫው በፊት ከቅንጅቱ ራሳቸውን አግልለው እያለ ጉዳዮን ለሕዝብ ሳያሳውቁ መቆየት የፈለጉት ለቅንጅቱና ለትግሉ ደህንነት ከነበራቸው ተቆርቋሪነት ሳይሆን ከግል ፍላጐታቸው አንጻር ቅንጅቱ የት ሊደርስ እንደሚችል ራስን ገለል አድርጐ መቆየት የብልጠት አካሄድ ሆኖ እንዳገኙት በእኛ በኩል የተረዳነው ከእስር ቤት ከወጡ በኋላ በተለያዩ ጉዳዮች የተጠቀሙበትን ተመሳሳይ ስልት ካየን በኋላ ነበር፡፡

ብዙውን ጊዜ ስለ ሃቀኛነት፣ ስለሰብአዊ መብትና ስለ የሞራል የበላይነት በመናገር የሚታወቁት ፕሮፌሰር መስፍን በእኔ ላይ ሲነዛ የከረመው ያ-ሁሉ የፈጠራ አሉባልታና የጥላቻ ዘመቻ በሃሰት መሆኑን በሚገባ እያወቁ አንድም ቀን ግን ድርጊቱን በግልጽ ለማውገዝ ፈልገው አያውቁም፡፡ እንዲያውም እኔ ምን ያህል በቅንጅቱ ምሥረታ ወቅት ራሴን ሳይሆን ዶ/ር ብርሃኑን የቅንጅቱ መሪ ለማድረግ እንደጣርኩ እያዎቁ፣ በመጨረሻም ከእኔ ፍላጐት ውጭ በግዴታ ወደ ቅንጅቱ አመራርነት መርጦ የላከኝ ፓርቲየ መሆኑን እያዎቁና የቅንጅቱን ውኅደት ለመፈጸም ከተስማማን በኋላ በተደረገው ምርጫም እኔ ምንም ዓይነት የምረጡኝ ማግባባት /Lobby/ እንዳላደረግሁ ራሳቸው በአዲስ ነገር ጋዜጣ መስክረው እያለ የእኔ ንፅህና በሕዝቡ ዘንድ መታወቁን ስላልፈለጉት ብቻ ያለምንም ተጨባጭ መረጃ እኔም ከኢንጅነር ኃይሉና ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር በሥልጣን እሻኰት እንደነበር አድርገው ሲከሱኝ ተስተውሏል፡፡ በርግጥ በሳቸው የግል ግፊትና አንጋሽነት የፓርቲ ሊቀመንበር ለመሆን ከበቃችውና በኋላም ላይ በተወሳሰበ ግፊት የእሥር ሰለባ ሆና የሌሎች የመታገያ አጀንዳ እንድትሆን ከተደረገችው ከወ/ሪት ብርቱካን በስተቀር እስካሁን በአገራችን በፕሮፌሰር መስፍን ያልተወገዘ የፖለቲካ መሪ ስለሌለ እኔም

ተመሳሳዩ ዕጣ ቢደርሰኝ የሚያስደንቅ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ስለ ፕሮፌሰር መስፍን ባሰብኩ ቁጥር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የማላውቃቸውን አንዳንድ ሰዎች ያላግባብ ሳመልክ በመኖሬ ጥልቅ ፀፀትና ጥፋተኝነት ይሰማኛል፡፡

ሌላው ከምርጫው በኋላ በቅንጅቱ አመራር ውስጥ አከራካሪ የነበረው ጉዳይ ሕዝቡን ፓርላማ እንግባ-አንግባ ብለን እናወያየው የሚለው አቋም ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በእኛ በኩል "ሕዝቡ ፓርላማ እንድንገባ የወሰነው የምርጫው ዕለት ድምፁን ሲሰጠን ነው፡፡ ሕዝቡ አንድ ጊዜ በምርጫ ካርድ ውክልናውን ከሰጠ በኋላ እንደገና ተመልሶ ፓርላማ የመግባት (Second mandate) ጥያቄ ማቅረብ በየትም አገር ተሠርቶ የማያውቅ ስህተት ነው፡፡ ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት ጉዳይ ላይ መወያየት ያስፈልጋል ተብሎ ከታመነም ጉዳዩን እኛው በፓርቲ ደረጃ ተነጋግረን ልንተማመንበት ይገባል እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ጥንቃቄ የሚጠይቅ /sensitive/ ጉዳይ በአዳራሽ ስብሰባ ለሕዝብ ውይይት ማቅረብ ተገቢ አይደለም፡፡ ሕዝቡ አንድ ጊዜ በሌሎች ኃይሎች ቅስቀሳ ተገፍቶ የሚሰጠው ስሜታዊ ውሳኔም ኋላ ትግሉን የሚጐዳ ሆኖ ቢገኝ ውሳኔውን ለመቀየር የማንችልበት አጣብቂኝ ውስጥ ያስገባናል" በማለት ሕዝቡን ለማወያየት የቀረበውን ሐሳብ ተቃወምን፡፡

ነገር ግን ቅንጅቱ ይህንን የእኛን ሐሳብ በድምፅ ብልጫ ውድቅ በማድረግ ሕዝቡ ይጠየቅ የሚለውን ውሳኔ አሳለፈ፡፡ እኔም በግሌ ተቃውሞየን በእለቱ ቃለ-ጉባዔ እንዲመዘገብልኝ ከማድረግም አልፌ እኔ በተመረጥኩበት ወረዳም ሕዝቡን በአጀንዳው ላይ ለማወያየት በተጠራው ስብሰባ ላይ አልገኝም በማለት ተቃውሞየን ገለፅኩ፡፡ የፈራነው አልቀረም አዲስ አበባ ከተማ ላይ በአራት ወረዳዎች በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ በጭብጨባና በፉጨት "ፓርላማ አትግቡ" የሚለው አቋም ገኖ ወጣ፡፡ በወቅቱ በየስብሰባ አዳራሹ የተገኘውና "አትግቡ" እያለ ያጨበጭብና ያፏጭ የነበረው ሰው ግን ለትግሉ መጠናከር በጎ አሳቢ መሆኑ ይቅርና የቅንጅት ደጋፊ ይሁን የኢህአዴግ ሊታወቅ የሚችልበት መንገድ አልነበረም፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ አጀንዳ ላይ በመርካቶ ራስ ቲያትር የተካሄደውን ሕዝባዊ ስብሰባ የመሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ነበሩ፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በመሩት በዚያ ስብሰባ ላይ "ፓርላማ አትግቡ" የሚለው አስተያየት በጭብጨባና በፉጨት ታጅቦ ገኖ መቅረቡን ካዳመጡ በኋላ በመጨረሻ ግራ ሲገባቸው "ያላችሁትን አዳምጠናል - በመጨረሻ ግን እኛ የምንወሥነው ውሳኔ ምንም ይሁን ምን እንደምትቀበሉት ቃል ግቡልኝ?" ብለው በመጠየቃቸው ከተሰብሳቢው የቀረበላቸው ጥያቄ "እናንተ የምትወስኑትን መቀበል ካለብንማ ለምን ይህንን ስብሰባ ማካሄድ አስፈለጋችሁ?" የሚል ነበር፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ

በወቅቱ በደፈናው "እኛ ለእናንተ የማይጠቅም ውሳኔ አንወስንም - እመኑን!" ከማለት በስተቀር ተሰብሳቢውን የሚያረካ መልስ መስጠት አልቻሉም ነበር፡፡

ከእነዚህ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በተጨማሪ በአጀንዳው ላይ የሲቪክ ማኀበራት ተወካዮችን፣ ተዋቂ ግለሰቦችንና የቅንጅቱን ከላይ እስከታች የሚገኙ አመራሮች በሦስት የተለያዩ መድረኮች ለማወያየት በተደረገው ሙከራ ግን "ቅንጅት ፓርላማ መግባት አለበት" የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት አገኘ፡፡ ነገር ግን በወቅቱ በሥራ ላይ የነበሩት አንዳንድ የግል ጋዜጦች የራሳቸው ዓላማና ፍላጐት ስለነበራቸው "ፓርላማ አትግቡ" የሚለውንና በሕዝባዊ ስብሰባዎቹ ላይ በጭብጨባና በፉጨት የቀረበውን ሐሳብ ከአግባብ በላይ በማጮህ ተከታታይ ዘመቻ አካሄዱበት፡፡ ኢህአዴግም ጧት ማታ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ሆን ብሎ "ቅንጅት ፓርላማ መግባት አለበት" በማለት ደጋግሞ በመቀስቀስ ቅንጅቱና የቅንጅቱ ደጋፊ የሆነው ሕዝብ ቅስቀሳውን በተቃራኒው እንዲያነቡትና "አንገባም" ወደሚል እልህ ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው፡፡ ቅንጅቱም ራሱ በፈጠረው ስህተት ቀስ በቀስ የመሪነት ሚናውን እያጣና ለትግሉ የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን በራሱ ተወያይቶ መወሰን የማይችልበትን አጣብቂኝ በራሱ ላይ እየፈጠረ መጣ፡፡

በዚህ ወቅት በቅንጅቱ ውስጥ አከራካሪ የነበረው ሌላው ጉዳይ ተቃዋሚዎችም ሆኑ ገዥው ፓርቲ የምርጫውን መጭበርበር አስመልክቶ ያቀረቡትን ክስ ተከትሎ የተጀመረውን የማጣራት ሂደት የሚመለከት ነበር፡፡ በእኛ በኩል በዚያ ኢህአዴግም ምርጫው ተጭበርብሯል በሚል ከሳሽ ሆኖ በቀረበበት ሁኔታ የምርጫ ማጣራት ሂደት ውስጥ መግባት የበለጠ ኢህአዴግን የሚጠቅም ዕድል የሚፈጥር ሂደት እንደሚሆን በመገመት፣ ከመጀመሪያው የማጣራቱ ሂደት ውስጥ መግባት የለብንም ብለን ተከራክረን ነበር፡፡ ምክንያቱም አንድ ጊዜ የማጣራት ሂደት ከተካሄደ በኋላ ምርጫው ተጭበርብሯል ብለን ልናቀርብ የሚገባንን የፖለቲካ ተቃውሞ እንኳ ማቅረብ እንዳንችል የሚያደርገን ከመሆኑም በላይ የማጣራቱ ሂደት ኢህአዴግ በመጀመሪያው ምርጫ ከአቅሙ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ያጣቸውን አንዳንድ ቦታዎች እንደገና እንዲነጥቀን ዕድል ይፈጥርለታል ብለን በማመን ብንቃወምም ሃሣባችን ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም መጨረሻ ላይ ተቃዋሚዎች አንድ ድምፅ፣ ገዥው ፓርቲ አንድ ድምፅ፣ ምርጫ ቦርድ አንድ ድምፅ ይዘው በማጣራቱ ሂደት የሚፈጠሩ ልዩነቶችን በአብላጫ ድምፅ እንዲወስኑ የሚያደርገውንና በእዚህ ዓይነቱ ውሳኔ ቅሬታ ከተፈጠረም መጨረሻ ላይ ፍርድ ቤት የሚወሥነውን ውሳኔ የመጨረሻና አሣሪ አድርገው ፓርቲዎች እንዲቀበሉ የሚያስገድደውን ስምምነት ያለ ቅንጅቱ አመራር ውሳኔና ትዕዛዝ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በግላቸው ምርጫ ቦርድ ድረስ ሂደው ፈርመው መጡ፡፡

ይህ ስምምነት እንዲፈረም የተደረገው እኔና ኢንጅነር ኃይሉ ሻዎል በቤት ውስጥ እገታ በነበርንበት ወቅት ስለነበር ከእገታው ነፃ እንደዎጣሁ ይህንን በቅንጅቱ ሳይሆን በግለሰብ ውሳኔ የተፈረመውን ስምምነት በመቃወም ዶ/ር ብርሃኑ ውክልና ሳይሰጣቸው በግል ፍላጐታቸው የፈረሙት ስምምነት መሆኑን ቅንጅቱ ለምርጫ ቦርድ ማሳወቅ እንዳለበት ብጠይቅም ተቀባይነት ሳላገኝ ቀረሁ። በወቅቱ ከቅንጅቱ አመራሮች የተሰጠኝ መልስ “ዶ/ር ብርሃኑ ከቅንጅቱ ዕውቅና ውጭ ሄዶ መፈረሙ ተገቢ ባይሆንም አንድ ጊዜ ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ስምምነቱን አንቀበልም ብንል የቅንጅቱን አሠራር የተዝረከረከ አድርጐ ስለሚያሳይ ዝም ብለን ብንቀበለው ይሻላል” የሚል ነበር። እኔም ከዚያ የቅንጅቱ ውሳኔ በኋላ ለዚህ ለግለሰቦች ዝናና ክብር ሲል ትግሉን የሚጐዳ ከፍተኛ ስህተት የሚፈፅም አካል የሕዝብ ግንኙነት ሆኜ አልሠራም በሚል ለሁለተኛ ጊዜ ከኃላፊነቴ ለቀቅሁ።

በወቅቱ ከኃላፊነት መልቀቄ በጋዜጦች የተዘገበና እኔም በቅንጅቱ ውስጥ አሳሳቢ ልዩነት እንደተፈጠረና በጉዳዩም ላይ ግልጽ ውይይት እንዲደረግበት ጋዜጦች ግፊት እንዲያደርጉ በግልጽ ጥያቄ አቅርቤ የነበረ ቢሆንም በቅንጅቱ ውስጥ ስለተፈጠረው ልዩነት እኔ እንዳልናገር ተፅዕኖ ለማሳደር ከመሞከር በስተቀር የችግሩን ምክንያት አጣርቶና መርምሮ እውነቱን ለሕዝብ ለመግለፅ የደፈረ ጋዜጠኛ አልነበረም። በወቅቱ ጋዜጠኞችም ብቻ ሳይሆኑ አብዛኛው የቅንጅት ደጋፊ የሆነው ሕዝብ እኔን “ልዩነት መስማት አንፈልግም - አፍህን ዝጋ” ማለትን መረጠ እንጂ ለእኔ ጆሮውን ለመስጠት ፍላጐት አልነበረውም። ኋላ ላይ በተግባር እንደታየውም የማጣራቱን ሂደት ተከትሎ በተካሄደው የድጋሜ ምርጫ ኢህአዴግ ዐሥራ ሁለት ተጨማሪ የፓርላማ ወንበሮችን ከቅንጅቱ መቀማት የቻለ ሲሆን ዶ/ር ብርሃኑ በፈረሙት ስምምነት መሠረትም ቅንጅቱ ከዚያ በኋላ የምርጫውን ውጤት አልቀበልም ብሎ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከሕግ አንጻር የወንጀል ድርጊት ተደርጐ እንዲታይ ሆነ።

እኛም ከጊዜ ወደ ጊዜ ቅንጅቱ ራሱን ወደ ከፍተኛ አደጋ እያስገባ መምጣቱን በግልጽ እያዩነው - ነገር ግን ከቅንጅቱ ተነጥለን ብንዎጣ እንደተለመደው ሊነዛብን የሚችለውን አሉባልታ በመፍራት ብቻ አብረን መቀጠልን መረጥን። በርግጥ ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው መጨረሻ ላይ የአሉባልታውን ዘመቻ መጋፈጣችን ላይቀር ከቅንጅቱ ቀደም ብለን ተለይተን ቢሆን ኖሮ ጥሩ ይሆን ነበር እያልን እንፀፀታለን። በተወሰነ ደረጃ ከምርጫው ማግሥት ጀምሮ ቅንጅቱን ለቀን ወጥተን ቢሆን ኖሮ የተሻለ ሊሆን ቢችልም ከምርጫው በፊት ከቅንጅቱ ወጥተን ቢሆን ግን ቅንጅቱ በምርጫው ለሚገጥመው ሽንፈት እኛን ተጠያቂዎች አድርጐ ማቅረቡ ስለማይቀር በእኛ ላይ ይደርስ የነበረው ጉዳት የበለጠ የከፋ ሊሆን ይችል እንደነበር ይሰማናል።

መቼም ሁሉም ነገር ካለፈ በኋላ ሲያስቡት ቀላል መስሎ የሚታይ ቢሆንም የኛ ትልቁ ስህተት ከመጀመሪያው ቅንጅቱን መቀላቀላችን መሆኑ ግን በማያጠራጥር ሁኔታ ግልጽ እየሆነልን መጥቷል። በርግጥ ከቅንጅቱ በግፍ ተገፍተን መውጣታችንን በደንብ በተገነዘቡ ሰዎች ዘንድ እስከ መጨረሻው አባረናችኋል እስከተባልንበት ጊዜ ድረስ በቅንጅቱ ውስጥ መቆየታችን ከፍተኛ ድጋፍና አድናቆት አስገኝቶልናል ማለት ይቻላል።

የሚገርመው ግን ገና ያኔ ቅንጅቱን በመመሥረት ላይ በነበርንበት ወቅት "እናንተ ሰዎች ከእነዚህ ሰዎች ጋር አብራችሁ ልትሰሩ አትችሉም፤ የራሳችሁን ድርጅት ይዛችሁ ብቻችሁን ብትቀጥሉ ይሻላችኋል" እያሉ ይመክሩን የነበሩ ሰዎች በቁጥር ቀላል የሚባሉ አልነበሩም። አሉባልታን እንደጦር በመፍራት ብቻ እነዚህ ሰዎች የመከሩንንና የራሳችንም ልቦና የሚያውቀውን እውነት መቀበል ተስኖን ሳጠፋነው ጥፋትም ዛሬ ደፍረን ይቅርታ ብንጠይቅ የሚገባ ይሆናል። በነገራችን ላይ ከፓርቲያችን ውጭ የነበሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ በፓርቲያችንም ውስጥ ያሉ አንዳንድ አመራር አባላት ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር አብሮ መሥራት እንደማይቻል ርግጠኛ የነበሩ ቢሆንም፣ ብዙውን ጊዜ እንደምንም ብለን አብረናቸው ለመሥራት እንሞክር እያልኩ በሌሎቹ ላይ ጫና እፈጥር የነበረው እኔ ስለነበርኩ በዚህ ረገድ ለተሠራው ስህተት የበለጠውን ተጠያቂነት መውሰድ ያለብኝ እኔ እንደሆንኩ ይሰማኛል። የሚገርመው ግን ከኢዴአፓ-መድኅን አመራሮች መካከል ከሌሎቹ ተቃዋሚዎች ጋር አብረን መሥራት የለብንም የሚል ከሁሉም የበለጠና የከረረ አቋም የነበራቸው ዶ/ር ኃይሉ አርዓያ ሲሆኑ በእኔ ምትክ የቅንጅቱ የሕዝብ ግንኙነት እንዲሆኑ ከወከልናቸው በኋላ ግን ከማንም በላይ የአብሮ መሥራት ጠበቃ ሆነው መቅረብ ጀመሩ። እሳቸው ብቻም ሳይሆኑ ዶ/ር ኃይሉ የትግራይ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ "እሳቸውን አምናችሁ እንዴት አብራችሁ ትሰራላችሁ" ይሉን የነበሩት የመኢአድ ሰዎች ሳይቀሩ እኔን ከቅንጅቱ ለማራቅ ሲሉ ብቻ ከዶ/ር ኃይሉ ጋር እጅና ጓንት ሆነው መሥራት ጀመሩ። የሆነ ሆኖ በዶ/ር ኃይሉ ዙሪያ ያዬሁት ድንገተኛ የአቋም ለውጥ ለእኔ ያልተጠበቀና እጅግ አስደንጋጭ ነበር። ዕድሜ እዬገፋ ሲሄድ ሥልጣን የበለጠ የሚያጓጓ ወይም የሚናቅ ስለመሆኑ ግን እስካሁን ርግጠኛ አይደለሁም።

በወቅቱ በቅንጅት ዙሪያ የነበረው ስብስብ ከባህሪና ከትግል ልምድ አንጻር አብሮ መሥራት የማይችል ነበር ማለት ብቻ ሳይሆን ስለ አገሪቱ አጠቃላይ ፖለቲካ ተቀራራቢ የሆነ ግንዛቤና ተመሳሳይ ዓላማም የነበረው አልነበረም። አብዛኛዎቹ ምርጫው በተቃረበበት ወቅት አገሪቱ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ ሊከሰት ነው ብለው ትግሉን የተቀላቀሉት ሰዎች ከዚያ በፊት በሰላማዊ ትግልም ሆነ በምርጫ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አይመጣም ብለው በማመን ትግሉ

ውስጥ ደፋ ቀና በምንለው ሰዎች ላይ ይስቁና ይሳለቁ የነበሩ ናቸው። እነዚህ ሰዎች በጥቂት ወራት ውስጥ የትግሉ ግንባር ቀደም ታጋይ ሆነ ብለው በማመን ኢህአዴግን፣ ተቃዋሚውን ጐራ፣ ሕዝቡን፣ በአጠቃላይም የአገሪቱን ፖለቲካ በተመለከተ ያራምዱት የነበረው አቋም ኢህአዴግ መንግሥት በሆነ ማግሥት ቀድመን ትግሉን የተቀላቀልን ሰዎች በዚያን ጊዜ ራሳችን የነበረንን በልምድ ያልታሸ ግልብ አመለካከት ያስታውሰን ነበር። አብዛኛዎቹ ትግሉን በአናቱ የተቀላቀሉት እነዚህ በሩቅ ስናደንቃቸውና ስናመልካቸው የኖርን ምሁራን ዋናው ልምዳቸው ዳር ቆሞ በትግሉ ውስጥ የሚሣተፉ ሰዎችን መተቸትና መጐንተል ስለነበር ድርጅት ውስጥ ገብተው ራሳቸው አመራርና ውሳኔ ሠጭ ሲሆኑ ግን "ከበሮ በሰው እጅ" እንዲሉ የሚይዙ የሚጨብጡትን አጥተው ሲደነባበሩ ታየ።

እነዚህ ሰዎች ምንም ባልደከሙበት ትግል ውስጥ በአጭር ጊዜ ተቀላቅለው ተዋቂና ባለዝና መሆን ስለቻሉ ብቻ በቅንጅቱ ውስጥ ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር የነበራቸው ፍላጐት ምንም ዓይነት ገደብ ያልነበረው ነው። መንግሥት በአጭር ጊዜ ተለውጦ እነሱ የድሉ ባለ ታሪክና ባለ ሥልጣን እንደሚሆኑ እጅግ ቋምጠው ስለነበር ከመንግሥት ሥልጣን ያነሰ ለውጥን እንደለውጥ ቆጥረው ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም። ለብዙ ዓመታት በተካሄደው ትግል የከፈሉት ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ስላልነበረ ይበላሻል ወይም ይጨናገፋል ብለው የሚጨነቁለት ሂደትም አልነበረም። ይህም ነው እንደነ ዶ/ር ብርሃኑን የመሳሰሉት የድል አጥቢያ ታጋዮች ከመጀመሪያው ትግሉ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት ለረዥም ጊዜ ለመክፈል ከልባቸው ተዘጋጅተው ወደ ትግሉ ስላልገቡ ጥርሳቸውን ነክሰው በሰላማዊ ትግሉ ሊቀጥሉበት ያልፈለጉት።

እነዚህ ሰዎች ትግሉን በአጭር ጊዜ ተቀላቅለው ወደ አደጋ እንዲያስገቡት በመፍቀድ ረገድ በትግሉ ውስጥ ትንሽ ውለን ያደርነው ሰዎች የሰራነው የራሳችን ጥፋት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕዝቡም እነዚህ ሰዎች ትግሉን ገደል እንዲከቱት በማድረግ ረገድ የማይናቅ የራሱ ድርሻ ነበረው ማለት ይቻላል። ሕዝቡ ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ? እስካሁንስ የት ነበራችሁ? ብሎ ለመጠየቅ ሳይሞክር በአንድ ጊዜ ሆ! -ብሎ እነዚህን ትግሉን በአናቱ የተቀላቀሉ ሰዎችን ተከተላቸው። በቅንጅቱ ውስጥ ምን ዓይነት መሠረታዊ ችግርና ልዩነት እንዳለ ፈጽሞ በማያውቅበት ሁኔታም ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች የሚናገሩትን ነገር ሁሉ እውነትና ትክክል ነው ብሎ ማመን ብቻ ሰዎቹን እንደ ፈጣሪ አመለካቸው። እነደ እኔ ዓይነቱን "ዶ/ር" የሚል የስም ቅጥያ የሌለው ሰው የሚያቀርበውን ሐሳብ አምኖ መቀበል ይቅርና ጆሮውን ሰጥቶ ማዳመጥ የሚፈልግ ሰው ግን እምብዛም ጠፋ። ሕዝቡ አንድ ሰው የሚያቀርበውን ሐሳብ የሚመዘነው

በውስጡ በያዘው ፍሬ ነገር መሆኑ ቀርቶ በዋናነት በተናጋሪው ማንነት ሆነ፡፡ በዚህ ረገድም ከእኛ ደጋፊዎች በተሻለ የኢህአዴግ ደጋፊዎች ጥቅምና ጉዳታቸውን በአግባቡ መመዘን የሚችሉ ከመሆኑም በላይ ስለመሪዎቻቸው የተሻለ ግንዛቤና አክብሮት ያላቸው መሆኑን ለመረዳት ችያለሁ፡፡

እኔ ከቅንጅቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነቴ ከለቀቅሁ በኋላ የተፈጠረው ሌላው ልዩነት የጥምር መንግሥት ጥያቄን በተመለከተ ነበር፡፡ በፓርቲ ደረጃ ምንም ሳንወያይበትና ስለ ጉዳዩ የምናውቀው ነገር ሳይኖር "ቅንጅቱና ኀብረቱ የጥምር መንግሥት ጥያቄ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ አቀረቡ" የሚል ዜና በጋዜጣ ላይ ተጽፎ አነበብን፡፡ በዚያ ቅንጅቱም ሆነ ኀብረቱ የምርጫ ማጣራት ሂደት ውስጥ በነበሩበት ወቅት የጥምር መንግሥት ጥያቄ ማቅረብ ትርጉም የለሽና ተቀባይነት ሊያገኝ የማይችል ብቻ ሳይሆን የተቃዋሚውን ዓላማ ሥልጣንን የመቀራመት ፍላጐት አድርጐ የሚያሳይ ስለነበር በኢዴአፓ-መድኅን የሥራ አስፈጻሚ ስብሰባ ላይ በወቅቱ ቅንጅት ውስጥ ተወካይ የነበሩትን እነ ዶ/ር ኃይሉ አርዓያን ለምን የጥምር መንግሥት ጥያቄ እንደቀረበ ጠየቅናቸው፡፡ እነ ዶ/ር ኃይሉም ቅንጅት ውስጥ ስለ ጥምር መንግሥት ጥያቄ የተደረገ ውይይትም ሆነ የተወሰነ ውሳኔ እንደሌለና በጋዜጣ ስለወጣው ዜና ምንም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገለፁልን፡፡ በአጋጣሚ ሆኖ በማግሥቱ ፓርላማ ይገባ-አይገባ? በሚለው አጀንዳ ላይ ለመነጋገር የቅንጅቱ አመራሮች ስብሰባ በግሎባል ሆቴል ተጠርቶ ስለነበር በዚያ ስብሰባ ላይ እኔ ራሴ በአካል ተገኝቼ ቅንጅቱ የጥምር መንግሥት ጥያቄ ለመንግሥት ማቅረብና አለማቅረቡን ጠየቅሁ፡፡

በወቅቱ ይህንን ጥያቄ ስጠይቅ መድረኩ ላይ የነበሩት ኢንጂነር ኃይሉ፣ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያና፣ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ሲሆኑ፣ እንጂነር ኃይሉ በቁጣ - "ያልተጻፈ አታንብብ! -እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ቅንጅት አላቀረበም" ብለው መለሱልኝ፡፡ እኔም በአጋጣሚ ዜናው የወጣበትን ጋዜጣ በእጄ ይዤው ስለነበረ - "እኔ ያልተጻፈ አይደለም የማነበው - ጋዜጣውን ሊያነቡት ይችላሉ" በማለት ጋዜጣውን ከሩቅ ዘርግቼ አሳየኋቸው፡፡ እሳቸውም እንደገና ተደናግጠው "እንዲህ ዓይነት ውሳኔ እስካሁን አልወሰንም፤ በእኛ በኩል የምናውቀው ዶ/ር ብርሃኑ የጥምር መንግሥት ጥያቄን አስመልክቶ በግሉ ያዘጋጀውና ወደፊት ለውይይት የሚያቀርብ አንድ ጽሑፍ መኖሩን ነው፡፡ ቅንጅቱ እናንተን ሳያማክር እንዲህ ዓይነት ውሳኔ ሊወስን አይችልም" ብለው መለሱልኝ፡፡ በወቅቱ ኢንጂነሩ ይህንን መልስ ሲመልሱ ዶ/ር ብርሃኑ ከጐናቸው መድረክ ላይ ተቀምጠው የነበረ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ምንም ዓይነት አስተያየት ሳይሰጡ በዝምታ ማለፍን መረጡ፡፡

እየሆነ ያለው ነገር ግራ ቢያጋባንም የቅንጅቱን ሊቀመንበር ቃል እንደ ትክክለኛ መልስ በመቁጠር እኛም ዝምታን መረጥን፡፡ ይህ በሆነ በማግስቱ እሁድ ማታ አቶ ኤሊያስ ክፍሌ የተባለ የራሱ መገናኛ ብዙኃን ያለው ሰው ከአሜሪካ ደውሎ ቃለ-መጠይቅ እንድሰጠው ጠየቀኝ፡፡ በዚያ ቃለ - መጠይቅም ቅንጅት ለምን የጥምር መንግሥት ጥያቄ ለመንግሥት እንዳቀረበ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ከአንድ ቀን በፊት ኢንጂነር ኃይሉና ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያ የሰጡኝን መልስ በማስታወስ -ቅንጅት እስካሁን ለመንግሥት ያቀረበው የጥምር መንግሥት ጥያቄ እንደሌለና በጋዜጣ ቀረበ ተብሎ የተዘገበው ጽሑፍም ዶ/ር ብርሃኑ በግላቸው ወደፊት ውይይት እንዲካሄድበት ያዘጋጁት ጽሑፍ መሆኑን ገለፅኩለት፡፡ ይህንን ቃለ-መጠይቅ በሰጠሁ በማግሥቱ ፋና ሬዲዮና የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን የሰጠሁትን ቃለ-መጠይቅ በመጥቀስ "የጥምር መንግሥት ጥያቄን አስመልክቶ በቅንጅት አመራሮች መካከል የሐሳብ ልዩነት ተፈጥሯል" የሚል ዜና ሠሩበት፡፡ ዜናውን ያዳመጠው ሕዝብም ልዩነት ተፈጠረ በመባሉ ብቻ ተደናገጠ፡፡

ይህ በሆነ በማግሥቱ አዲስ ዜና በመባል ይታወቅ የነበረው የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ጋዜጣ ላይ ኢንጂነር ኃይሉ፣ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያና ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ከነ ፎቶግራፋቸው ወጥተው ቅንጅቱ የጥምር መንግሥት ጥያቄ አላቀረበም ብዬ እኔ የተናገርኩት ውሸት እንደሆነና ቅንጅቱ ጥያቄውን ተነጋግሮበትና አምኖበት ለመንግሥት እንዳቀረበው አድርገው ቃለ-መጠይቅ ሰጡ፡፡ ከሁለት ቀን በፊት በመድረክ ላይ ራሳቸው የተናገሩትን ሽምጥጥ አድርገው ክደው ሦስት አንቱ የተባሉ ትልልቅ ሰዎች ተማክረው ሲዋሹ ለመጀመሪያ ጊዜ በማዬቴ በሆነው ነገር ደንግጬ ከዚያ ቀን በኋላ ለማንኛውም መገናኛ ብዙኃን መግለጫ መስጠት የማልፈግል መሆኑን በይፋ መግለጫ ጽፌ በመበተን ከመገናኛ ብዙኃን ጋር የነበረኝን ግንኙነት ለሁለት ወር ያህል አቋረጥኩ፡፡ በወቅቱ በዚህ ጉዳይ እውነቱን አጣርቶ ለሕዝብ ለማሳወቅ የሞከረ አንድም ጋዜጠኛ አልነበረም፡፡ እስከዛሬ ድረስም በቅንጅቱ ዙሪያ ከነበሩ ሰዎች አንዳቸውም በዚህ ጉዳይ ላይ ስለተፈጸመው የፖለቲካ ቅሌት ለመናገር ሲሞክሩ ሰምቼ አላውቅም፡፡ በነገራችን ላይ በዚያን ወቅት የጥምር መንግሥት ጥያቄ ለመንግሥት እንዲቀርብ የበለጠ ግፊት የተደረገው በእነ ፕሮፌሰር በየነ በኩል ሲሆን፣ እንደዚያ ለማድረግ የተገደዱትም የዚያ አጀንዳ አራማጅ የነበሩት እነ ኢህአፓን ለጊዜው ለማስደሰት ብለው ነበር፡፡

እየቆዬ በቅንጅት ውስጥ የሐሳብ ሽኩቻው እየጠነከረና እየተካረረ ሲመጣ ችግሩን ለመፍታት የተፈለገው በውይይትና በክርክር አልነበረም፡፡ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ኢዴአፓ-መድኅን የፓርቲ ህልውናውን ጠብቆ እስከቀጠለ ድረስ ከፊታችን ይመጣል ብለው የሚጠብቁት የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ሲገባ እንደልባችን ሊያሠራን አይችልም ብለው ስለገመቱ

የ"እንዋሐድ" ጥያቄ በድንገት ይዘው ብቅ አሉ። በዚያ በውስጣችን መተማመን ባጣንበት፣ ከኢህአዴግ ጋር በከፍተኛ ፍጥጫ ውስጥ በነበርንበትና በአጠቃላይም በውጥረትና በህልውና አደጋ ውስጥ በነበርንበት ጊዜ የእንዋሐድ ጥያቄ መምጣቱ ለጤና ሳይሆን እኛን እንዳናንሰራራ አድርጐ ለማጥፋት መሆኑ ግልጽ የነበረ ቢሆንም ከላይ በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደሞከርኩት አሁንም ከእነሱ ብንነጠል ሊከፈትብን የሚችለውን የአሉባልታ ዘመቻ በመፍራት የውኅደቱ ድርድር ውስጥ ለመግባት ተስማማን።

የውኅደት ድርድሩን ለማካሄድ የተቋቋመው ኮሚቴ ውሕዱ ፓርቲ ስለሚኖረው የፖለቲካ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የመጀመሪያ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለውይይት አቀረበልን። የቀረበው የመተዳደሪያ ደንብ ረቂቅ አራቱ ፓርቲዎች ውኅደቱን ሙሉ በሙሉ ፈፅመው እስከሚያጠናቅቁ ድረስ የሽግግር ጊዜ መተዳደሪያ ደንብ ሆኖ እንዲያገለግል የቀረበ ነበር። ነገር ግን ረቂቁ ቀርቦ ስናየው ገና አዲስ ውኅደት ለሚፈጥሩ አራት ፓርቲዎች ሳይሆን ለአንድ ወጥ ማንነት ያለው ፓርቲ የተዘጋጀና ከጀርባ ለሚሰራ ድርጅታዊ ሥራ አመች ተደርጐ የተቀመረ ደንብ ሆኖ አገኘነው። ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወሃዱ ፓርቲዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚኖራቸው አመራር ከፓርቲዎቹ በውክልና ተውጣጥቶ መቋቋም የነበረበት ቢሆንም እነ ዶ/ር በርሃኑ ግን እነሱ የፈለጉትን ዓይነት አመራር በድርጅታዊ አሥራር መፍጠር እንዲያመቻቸው በመፈለግ አመራሩን የሁሉም ፓርቲዎች ተወካዮች አንድ ላይ ተሰብስበው በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ እንዲመርጧቸው የሚያደርግ ደንብ አስቀድሞ እንዲዘጋጅ ተደረገ። የውኅደት አመቻች ኮሚቴው በዚህ ሁኔታ ሥራውን ሠርቶ ከአጠናቀቀ በኋላ አራቱ ፓርቲዎች ውኅደቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተስማሙበትን ሰነድ ለመፈራረም ለመስከረም 14/1998 ዓ.ም ቀጠሮ ተያዘ። ነገር ግን ይህ ሰነድ በፓርቲዎቹ ከመፈረሙ በፊት ሁሉም ፓርቲዎች የየራሳቸውን የጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት ውኅደቱን የመፍጠር ውሳኔ በየፓርቲዎቻቸው እንዲያስወስኑ ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ፓርቲዎቹ የየራሳቸውን ጉባዔ ገና ከማድረጋቸው በፊት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ከየፓርቲው ተመርጠው ወደ ቅንጅቱ መሄድ ያለባቸውን ሰዎች አስቀድመው በምስጢር በመምረጥ እነዚያን ሰዎች የማስመረጥ ከፍተኛ ዘመቻ በየፓርቲዎቹ ውስጥ ማካሄድ ጀመሩ። ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ድርጊታቸውን እሥር ቤት ውስጥ ሆነው ባሳተሙት መጽሐፍ "እነ ልደቱን በድምፃችን ለመቅጣት ተግተን መሥራት ጀመርን" በማለት በኩራት ጠቅሰውታል። አቶ ገብረ ክርስቶስ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ ደግሞ ይህንን የዶ/ር ብርሃኑ ድርጅታዊ ሥራ "የስታሊን ተግባር" ብለው ገልጸውታል። ሦስቱ ድርጅቶች ጉባዔያቸውን አካሂደው ካጠናቀቁ በኋላ ኢዴአፓ-መድኅን ጉባዔውን መስከረም 11 ቀን 98 ዓ.ም ለማካሄድ ወሰነ። እነ ዶ/ር ብርሃኑም ከኢዴአፓ-መድኅን

ተመርጠው ወደ ቅንጅቱ እንዲሄዱላቸው የፈለጓቸውን ሰዎች ለማስመረጥ የእኛን ፓርቲ የጉባዔ አባላት አንድ በአንድ በአካል እያገኙ ለማሳመን ሞከሩ። ከየ ክፍላተ-ሀገራቱ ለጉባዔው የሚመጡ አባሎቻችንን ሳይቀር ገና አውቶቡስ ተራ ሲገቡ ጠብቀው በማግኘት በኢዴአፓ-መድኅን ጉባዔ ላይ እነማን መመረጥ እንዳለባቸው ለማሳመን ሞከሩ።

በወቅቱ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ዓይነት የጣልቃ ገብነት ተግባር በእኛ ፓርቲ ላይ እንዲፈጽሙ ያስገደዳቸው ሌላ ነገር ሳይሆን ቅንጅቱ የውኅደቱን ሥራ በተግባር ሲጀምር ሁሉን ነገር እነሱ በፈለጉት መንገድ ለመፈጸም የሚያስችሏቸውን ሰዎች ከኛ ፓርቲ ለማግኘትና በአንፃሩ ደግሞ እኔን ጨምሮ እንቅፋት ይሆኑብናል ብለው የሚሰጉባቸውን ሰዎች ከቅንጅቱ አመራርነት እንድንገለል ለማድረግ ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲህ ዓይነቱን ሴራ ተግተው ይሠሩ የነበረው በሌላ ምክንያት ሳይሆን በአዲስ አበባ መስተዳድር ውስጥ ከቅንጅቱ አባል ፓርቲዎች ውስጥ ከፍተኛውን መቀመጫ ያሸነፈው ኢዴአፓ-መድኅን ስለነበር ይህ ፓርቲ ቀድሞ ድርጅታዊ ህልውናውን ካላጣ በስተቀር የእሳቸው የአዲስ አበባ ከንቲካ የመሆን ፍላጐት ችግር ሊገጥመው ይችላል ብለው ስለሰጉ ነበር።

እነ ዶ/ር ብርሃኑ ለእዚህ ዓላማቸው እንዲረዳቸው በማሰብም የኢዴአፓ-መድኅን ጉባዔ ሊካሄድ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት በወቅቱ "መዝናኛ" ይባል በነበረው ጋዜጣ ላይ "ልደቱና አቦይ ስብሃት ነጋ በድብቅ ተገናኝተው ተወያዩ" የሚል ዜና እንዲወጣ አደረጉ። በወቅቱ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ምን ያህል የዘቀጠና የትም የማያደርስ ሥራ እየሠሩ እንደሆነ የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች በደንብ እናውቅ ስለነበር የእነሱን ሴራ ሊያከሽፍ የሚችል ድርጅታዊ ሥራ እኛም በበኩላችን መሥራት ጀመርን። አመራር አባላቱ ብቻ ሳንሆን አብዛኛዎቹ የጉባዔ አባሎቻችን ጭምር በወቅቱ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ምን እየሠሩ እንደሆነ ያውቁ ስለነበር ጉባዔው ተጀምሮ የውኅደቱ ጉዳይ ለውይይት ሲቀርብ አብዛኛዎቹ የጉባዔ አባሎቻችን በዚህ ወቅት ከቅንጅቱ ጋር ውኅደት መፍጠር የለብንም የሚል የተቃውሞ ሐሳብ አቀረቡ።

ነገር ግን አመራሩ ፓርቲው በዚያን ወቅት ውኅደት መፍጠር አልፈልግም ብሎ ቢወስን ሊከፈትበት የሚችለውን የአሉባልታ ዘመቻ በመፍራት የሚሻለው ውኅደቱን አንፈልግም ማለት ሳይሆን ውኅደቱን ለመፍጠር ተስማምተን ነገር ግን የውኅደቱ አፈጻጸም ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበትና የፓርቲያችንን ዓላማና ጥቅም በአግባቡ የሚያስጠብቅ፣ እየታየ ያለውን መረን የለቀቀ አምባገነናዊ አካሄድም በአግባቡ የሚገታ እንዲሆን ማድረግ ነው በማለት ተከራክሮ ጉባዔውን ማሳመን ቻለ። ከዚህ አጠቃላይ መግባባት በመነሣትም መስከረም 14 ቀን 98ዓ.ም አራቱ ፓርቲዎች ውኅደት ለመፍጠር የሚያካሂዱትን ስምምነት ኢዴአፓ-መድኅንም

እንዲፈርም፣ ነገር ግን የኢዴአፓ-መድኅን የዕውቅና ሰርተፍኬት ለምርጫ ቦርድ ተመልሶ ፓርቲው ህልውናውን እንዲያጣ መደረግ ያለበት አራቱ ፓርቲዎች መስከረም 14 ተስማምተው በሚፈርሙት ሰነድ ላይ የሰፈሩት ስምምነቶች ሙሉ በሙሉ በትክክልና በተግባር መፈፀማቸው ከተረጋገጠና ውኅደቱ በሁሉም ከላይ እስከ ታች የሚገኙ መዋቅሮች ከተፈጸመ በኋላ መሆን እንዳለበት ጉባዔው ወሰነ።

ጉባዔው ከዚያ ቀን ጀምሮ ኢዴአፓ-መድኅንን የሚወክሉትን ዐሥራ ስምንት የማዕከላዊ ምክር ቤት አባላት ከመረጠ በኋላ በእኔ በኩል ለጉባዔው ንግግር እንዳደርግ እድል እንዲሰጠኝ ጠይቄ የቅንጅት ሰዎች ከእኔ ጋር ላለመሥራት መወሰናቸውንና ከዚያ በኋላ እኔ አመራር ሆኜ ወደ ቅንጅቱ ብላክ ሰዎች በእኔ ላይ ካደረባቸው ጥላቻ በተነሳ የቅንጅቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ችግር ጭምር ለመፍጠር ወደኋላ እንደማይሉ፣ ስለዚህ ለቅንጅቱ ህልውና ሲባል እኔ ወደ ቅንጅቱ የሥራ አስፈጻሚ አመራር ሆኜ እንዳልሄድ ጉባዔው እንዲወስን በእንባ ጭምር ተማፀንኩ። ነገር ግን ይህንን አቋሜን ይዤ ለረዥም ጊዜ ብከራከርም ጉባዔው ጥያቄዬን ሊቀበለኝ ፈቃደኛ አልነበረም። እንዲያውም ይባስ ብሎ እኔ በውስጡ የሌለሁበት ሥራ አስፈጻሚ ወደ ቅንጅቱ እንዳይላክ ጭምር ወሰነ።

በጉባዔ የተመረጠው የማዕከላዊ ኮሚቴ ከውስጡ ውኅደቱን ሊያስፈፅሙ የሚችሉ አምስት የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ሲመርጥም እነ ዶ/ር ብርሃኑ ወደ ቅንጅቱ ተመርጠው እንዲሄዱላቸው የፈለጓቸውን ሦስት ሰዎች ማለትም ዶ/ር አድማሱ ገበዬሁን፣ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያንና አቶ ክፍሌ ጥግነህን የእነ ዶ/ር ብርሃኑን ሴራ ለማክሸፍ ሲል የማዕከላዊ ኮሚቴአችን ሆን ብሎ ሳይመርጣቸው ቀረ። በዚህ ሁኔታ የኢዴአፓ-መድኅን ጉባዔ የእነ ዶ/ር ብርሃኑን የተለማማጆች /Amateurs/ ድርጅታዊ ሴራ ያከሸፈ ሆኖ ተጠናቀቀ። ውስጥ ውስጡን በቂ ድርጅታዊ ሥራ ሰርቻለሁ ብለው በርግጠኛነት ተማምነው የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ የእኛ ጉባዔ በዚያ መልኩ መጠናቀቁን ሲሰሙ ተደናግጠው እኔን ፈልገው በማግኘት "ምን እየሠራችሁ ነው?" በማለት ጠየቁኝ። እኔም "አንተ የምትሸርበውን ሴራ እያፈረስን ነው፣ የምትሰራውን የማናውቅ አይምሰልህ፣ እኛን ልታሸንፈን የምትችለው በፍቅርና በሃቅ እንጂ እንዲህ ዓይነት የተንኮል ሥራ በመሥራት አይደለም፣ በዚህ መልኩ አሸንፋቸዋለሁ ብለህ አስበህ ከሆነ ተስፋህን ቁረጥ" ብዬ በቀጥታ መለስኩላቸው። እሳቸውም "እንተያያለን" ብለው በመዛት ተለዩኝ።

በወቅቱ የእነ ዶ/ር ብርሃኑ ፍላጐት ከእኛ ፓርቲ ውስጥ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያን የቅንጅቱ ምክትል ሊቀመንበር፣ አቶ ክፍሌ ጥግነህን የቅንጅቱ የውጭ ግንኙት ኃላፊ፣ ዶ/ር አድማሱ ገበዬሁን ደግሞ የቅንጅቱ የጥናትና ምርምር ኃላፊ አድርጎ እኔን የቅንጅቱ የወጣቶች ጉዳይ

ኃላፊ፣ ዶ/ር ሙሉ ዓለም ታረቀኝን የሴቶች ጉዳይ ኃላፊ ለማድረግ ነበር፡፡ የሚገርመው እኛ ለ14 ዓመታት በትግሉ ውስጥ ስንወጣና ስንወርድ "በሰላማዊ ትግሉ ለውጥ አታመጡም" እያሉ የሞቀ ቢሮአቸው ውስጥ ተቀምጠው ይመጻደቁብን የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ የመንግሥት ለውጥ ሊመጣ ነው ብለው በመቋመጥ ትግሉን በተቀላቀሉ በጥቂት ወራት ውስጥ የእኛ የሹመት ደልዳይ አድርገው ራሳቸውን ሲያስቀምጡ ትንሽ እንኳን ይሉኝታና ኀፍረት አይሰማቸውም ነበር፡፡

መስከረም 14 ቀን 98 ዓ.ም ውኅደት ለመፍጠር የሚያስችለው ስምምነት በሚፈረምበት ዕለት የቅንጅቱ የመጀመሪያ አራት አመራሮች እንዲመረጡ ስምምነት ላይ ተደርሶ ስለነበር በዚያ ምርጫ ላይ ሊፈጸም የታሰበውን ሴላ ሴራ አስቀድመን ገምተን ስለነበር ያን ሴራ ለማክሸፍ የሚያስችለንን አንድ ሌላ የጥንቃቄ ዝግጅት በእኛ በኩል አደረግን፡፡ ይኸውም ቀደም ብዬ እንደገለፅኩት እነ ዶ/ር ብርሃኑ የቅንጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ሲረቀቅ ለእነሱ ድርጅታዊ ሥራ እንዲያመቻቸው በማሰብ ከየፓርቲው የቅንጅቱ ዋና አመራር ለመሆን የሚመጡትን አራት ሰዎች ራሱ ፓርቲው ብቻ ሳይሆን የቅንጅቱ ምክር ቤት አባላትም ከየፓርቲዎቹ ሊመረጡ የሚገባቸውን ሰዎች የመጠቆም መብት እንዲኖረው አድርገው ነበር፡፡ ይህንን ቀዳዳ ለመዝጋት ስንልም በእኛ በኩል ፓርቲው መርጦ ከሚልከው ሰው ውጭ በሌላ የቅንጅቱ አመራር አባል የሚቀርብን ማናቸውም ዓይነት ጥቆማ የኢዴአፓ- መድኅን ሰዎች ሁላችንም ላለመቀበል አስቀድመን ተስማማን፡፡

እነዚህን ቅድመ ጥንቃቄዎች ካደረግን በኋላ ውኅደቱን ለመፍጠር የሚደረገውን ስምምነት ለመፈረምና አራቱን የቅንጅት መሪዎች ለመምረጥ መስከረም 14 ቀን 98 ዓ.ም ግሎባል ሆቴል በተጠራው ስብሰባ ላይ ተገኘን፡፡ በዚያ በእነ ዶ/ር ብርሃኑ ድርጅታዊ ሥራ ሁሉም ነገር ከጀርባ ተሠርቶ በተመቻቸበት ስብሰባ ላይ አራቱ የቅንጅቱ መሪዎች እንዲመረጡ ሲደረግ ኢንጂነር ኃይሉ በወቅቱ አሜሪካ የነበሩ ቢሆንም እንደ አንድ ቅንጅቱን በአግባቡ ሲመሩ እንደነበሩ መሪ በሌሉበት በከፍተኛ ድምፅ የቅንጅቱ ዋና ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ፡፡ ኢንጅነር ኃይሉን ከሊቀመንበርነት እናወርዳለን በማለት ከምርጫው በፊት ሲፎክሩ የነበሩት እነ ዶ/ር ብርሃኑ በወቅቱ ከኢንጅነር ኃይሉ በፊት ልደቱን መምታት የሚመረጥ ስልት አድርገው ስላገኙት ኢንጅነርን በሌሉበት ድርጅታዊ ሥራ ሠርተው አስመረጧቸው፡፡ ቀደም ሲል ለኢዴአፓ-መድኅን ሊሰጠው ታስቦ የነበረው ቦታ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርነት ቢሆንም ለዚያ ቦታ የታሰቡት ሰው ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያ በፓርቲያቸው በኩል ተመርጠው ያልተላኩ መሆኑ ሲታወቅና ተመርጬ የተላኩት እኔ (ልደቱ) መሆኔ ሲታወቅ ለእኛ ፓርቲ ሊሰጥ ታስቦ የነበረው ቦታ ለቀስተ-ዳመና እንዲሰጥ

ኮሪደር ላይ ተወሰነ፡፡ በዚህም መሠረት እስከዚያ ዕለት ድረስ በየትኛውም የቅንጅቱ መዋቅር ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ላልነበራትና ለመጀመሪያ ጊዜ በቅንጅት ስብሰባ ላይ በዚያ ዕለት ለተገኘችው ለወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበርነቱ እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ በነገራችን ላይ ወ/ሪት ብርቱካን በምርጫ 97 ወቅት የማንኛውም ፓርቲ አባል ያልነበረች ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ዶ/ር ብርሃኑ የሚመራው የቀስተ-ደመና ፓርቲ አባል የሆነችው የግንቦቱ ምርጫ ካለፈ ከሦስት ወር በኋላ ማለትም ጳጉሜ 97ዓ.ም ላይ ነው፡፡ ወ/ሪት ብርቱካን በቅንጅቱ ውስጥ ይህንን ከፍተኛ የሥልጣን ቦታ በዶ/ር ብርሃኑ አማካይነት እንድትይዝ የተደረገው በቀስተ ዳመና ፓርቲ አባልነት ከተመዘገበች 20 ቀን ባልሞላ ጊዜ ነበር፡፡ የተሠራው ሥራ እጅግ አስቂኝ ቢሆንም ወ/ሪት ብርቱካን ወደ ፖለቲካው መድረክ እንድትመጣ ከማንም ባላነሰ እኔ ቀደም ሲል ጥረት አደርግ ስለነበር በግሌ በእሷ መመረጥ ደስታ እንጂ ቅሬታ ስላልተሰማኝ ይህንኑ ስሜቴን በወቅቱ መድረክ ላይ ወጥቼ ገልጬላታለሁ፡፡

ከኃላፊነት አንጻር በአራቱ ቦታዎች ውስጥ ብዙም ትርጉም የሌለው 2ኛው የምክትል ሊቀመንበርነት ቦታ ደግሞ ለእኔ እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ አራተኛው የጸሐፊነት ቦታ ለኢዴሊ የተሰጠ ሲሆን በወቅቱ ኢዴሊ ለዚህ ቦታ በእጩነት ያቀረበው ሊቀመንበሩን ዶ/ር አለማዮሁ አረዳን የነበረ ቢሆንም ፓርቲያቸው ከጀርባ የተሠራበትን ሴራ እንደኛ አስቀድሞ ለማፍረስ ተዘጋጅቶ ስላልነበረ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ዶ/ር አለማዮሁን ከመቀበል ይልቅ በወ/ሪ ብርቱካን በኩል ሌላ እነሱ የሚፈልጉት ሰው እንዲጠቆም በማድረግ የጸሐፊነቱ ቦታ ለአቶ ሙሉነህ እዩኤል እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ በነገራችን ላይ አቶ ሙሉነህ ኢዮኤል ቀደም ሲል የኢዴአፓ-መድኅን አባል የነበሩ ሲሆን ምንም ዓይነት መልቀቂያ ከኢዴአፓ-መድኅን ባልወሰዱበት ሁኔታ የኢዴሊ አባል ሆነው የተገኙት ቅንጅቱን ለመፍጠር ድርድር ይደረግ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ አቶ ሙሉነህ ቅንጅቱ ለምርጫ 97 ውድድር ሲቀርብ እርሳቸው በትውልድ አካባቢያቸው የፓርላማ እጩ ሆነው እንዲቀርቡ ተጠይቀው የነበረ ቢሆንም የግል ሥራዬን ማጣት አልፈልግም በማለት በእጩነት ለመቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆኑ የቀሩ ሰው ናቸው፡፡ እኚህን ሰው ከፓርቲያቸው ውክልና ውጭ ለዚህ ከፍተኛ ኃላፊነት በድርጅታዊ ሥራ እንዲመረጡ ያደረጓቸው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ነበሩ፡፡ የሚገርመው ግን ይህ ሁሉ ደባ መፈጸሙን በወቅቱ የኢዴሊ ሊቀመንበር የነበሩት ዶ/ር አለማየሁ አረዳ ያውቁ የነበረ ቢሆንም ያኔም ሆነ ዛሬ በተለያዩ ጋዜጦች ላይ የተድበሰበሰና ዙሪያ ጥምጥም የሚሄድ ቃለ መጠይቅ ከመስጠት አልፈው የተሟላውን እውነትና በራሳቸውም ላይ የደረሰውን በደል በግልጽ ለመናገር ድፍረት አግኝተው አያውቁም፡፡

በነገራችን ላይ የቀስተዳመና ሊቀመንበር የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በወቅቱ ከቅንጅቱ አራት ቀዳሚ አመራሮች ውስጥ አንዱ ላለመሆን የፈለጉት የአዲስ አበባ ከንቲባ እንደሚሆኑ ርግጠኛ ስለነበሩና የጊዜ እጥረት ያጋጥመኛል ብለው ሰግተው ስለነበር ሲሆን ከጀርባ ሆነው እንደዚያ ዓይነት ድርጅታዊ ሥራ ለመሥራት የፈለጉትም በአንድ በኩል እሳቸው ከውጭ ሆነው እንደልባቸው ሊያዟቸውና ሊያሽከረክሯቸው የሚችሉ ሰዎች የቅንጅቱን አመራር እንዲይዙት፣ በሌላ በኩል ደግሞ እርሳቸው የቅንጅት መሪ ለመሆን በሚፈልጉበት ጊዜ በቀላሉ ሊያስወግዷቸው የሚፈልጓቸው ሰዎች ቦታውን ይዘው እንዲጠብቁላቸው ስለፈለጉ ነበር። በርግጥ ኢንጂነር ኃይሉ ሻዎል ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተደረጉት እንደ ሌሎቹ ሰዎች መጠቀሚያ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ ታስቦ ሳይሆን እርሳቸው ዋና መሪ ካልሆኑ በስተቀር መኢአድ ውኅደቱን ሊቀላቀል አይችልም ተብሎ ስለታሰበና አንድ ጊዜ ውኅደቱ ከተፈጸመና መኢአድ ሕጋዊ ህልውናውን ካጣ በኋላ ግን ርሳቸውን በተለመደው ድርጅታዊ አሠራር በቀላሉ ከሥልጣን ማስወገድ እንደሚቻል ታስቦ ስለነበር ነው። የቅንጅት አመራሮች ከእሥር ቤት ከወጡ በኋላ ኢንጂነር ኃይሉ በአድማና በውግዘት ከመሪነታቸው እንዲወገዱ የተደረገውም በሌላ ምክንያት ሳይሆን ያንን ጊዜያዊ አገልግሎታቸውን ጨርሰዋል ተብሎ ስለታሰበ ነበር።

ከዚያ የቲያትር ምርጫ በኋላ አራቱ ድርጅቶች ውኅደቱን ለመፍጠር የሚያስችላቸውን ሰነድ በይፋ ፈረሙ። በወቅቱ የተፈረመው ሰነድ አራቱ ድርጅቶች በምን ሁኔታ ውኅደት ለመፍጠር መስማማታቸውን የሚያሳይ ቢሆንም በማግስቱ ለኅትመት የበቁት አንዳንድ ጋዜጦች ግን “አራቱ ፓርቲዎች ተዋሐዱ” የሚል የተሳሳተ ዜና ለሕዝብ ዘገቡ። በወቅቱ አራቱ ፓርቲዎች መዋሐድ ይቅርና አራቱን የቅንጅት መሪዎች ከመምረጥና እንዴት አድርገው ወደፊት ውኅደቱን እንደሚፈፅሙት ከመፈራረም ያለፈ ገና ዋናውን የውኅደት ሥራ አልጀመሩትም ነበር።

## ምዕራፍ አራት

## ቅንጅትን ለውድቀት ያበቁት የመጨረሻ ክስተቶች

ውኅደት ለመፍጠር የሚያስችለው ቅድመ-ሁኔታ ከተፈረመ ከሳምንት በኂላና ኢንጂነር ኃይሉ ከአሜሪካ እንደተመለሱ ውኅደቱን በተግባር የማስፈጸም ሥራ ተጀመረ። የመጀመሪያው ሥራም ቀደም ብሎ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ሆን ተብሎ እንዲቀመጥ በተደረገው መሠረት አራቱ የቅንጅቱ መሪዎች ቀሪዎቹን የቅንጅቱን የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የኃላፊነት ድልድል እንዲፈጽሙ ማድረግ ነበር። በርግጥ በዚያን ወቅት ከአራቱ ሰዎች አንዱ እኔ ሆኜ መገኘቴ የእነ ዶ/ር ብርሃኑን ድርጅታዊ ሥራ በማክሸፍ ያገኘነውና ድርጅታዊ ህልውናችንን አስጠብቀን ለመቀጠል ያበቃን ውጤት ነበር። አራቱ ሰዎች የሥራ አስፈጻሚ አባላቱን የሥራ ድልድል መሥራት ስንጀምር ወሳኝና ቁልፍ የሆኑትን ኃላፊነቶች በሙሉ እየመረጡ መኢአድና ቀስተዳመና መከፋፈል ጀመሩ። እኔ ተቃውሞ ለማሰማት ብሞክርም ሦስቱ ሰዎች ማለትም ኢንጂነር ኃይሉ፣ ወ/ሪት ብርቱካንና አቶ ሙሉነህ አስቀድመው ለብቻቸው ተማክረው ስለሚመጡ ሃሳብ በአንድ በሆነ ድምፅ የሚፈልጉትን መወሰን ቻሉ።

በእኔ በኩልም ውሣኔዎቹ ተገቢ ባለመሆናቸው ያለኝን ልዩነት በማስመዝገብ በአብላጫ ድምፅ እስከተወሰነ ድረስ ግን ውሳኔውን የምቀበለው መሆኑን ገለፅኩ። ነገር ግን ውሳኔው ለቅንጅቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲቀርብ ተገቢ ውሳኔ አለመሆኑ ግልጽ ሆኖ ስለታዬ አራቱ መሪዎች እንደገና ተገናኝተን በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የሥራ ድልድል ላይ በመወያየት አዲስ ውሳኔ እንድናመጣ ተወሰነ። በውሳኔው መሠረት አራቱ አመራሮች እንደገና ብንሰበሰብም ሦስቱ አመራሮች ሃሣባቸውን መቀዬር ስላልፈለጉ ተመሳሳይ ውሳኔ እንደገና ለቅንጅቱ ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ ተመልሶ ቀረበ። ሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴውም አዲስ ውሳኔ እንድታመጡልኝ እንጂ ያንኑ ውሳኔ መልሳችሁ እንድታመጡ አልተጠየቃችሁም በማለት አሁንም ውሳኔውን ሳይቀበለው ቀረ። በወቅቱ በእኔ በኩል እየተሠራ ያለው ሥራ አሳዛኝና አሳፋሪ ቢሆንም ጉዳዩ በአብላጫ ድምጽ

ኢ.ዩ.ፓ

እስከተወሠነ ድረስ ውሳኔውን ተቀብለን የውህደትን ቀጣይ ሥራ እንድንሠራ ጠይቄ የነበረ ቢሆንም በኢዴአፓ-መድኅን ላይ እየተሠራ የነበረው በደል በግልጽ አፍጥጦ የሚታይ ስለነበር የቅንጅቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔውን ሊቀበለው አልቻለም፡፡

በዚህ ወቅት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ቆም ብለው ሲያስቡት የውኅደቱ ሂደት ገና ሲጀመር በሥራ-አስፈጻሚ ድልድል ደረጃ ይህንን ያህል ችግር ከገጠመው በሁሉም መዋቅሮች ውኅደቱን እነሱ በፈለጉት ሁኔታ እስከታች ድረስ ማጠናቀቅ ከባድ እንደሚሆንና አንድ ቦታ ላይም ሲመረው ኢዴአፓ-መድኅን ሊያፈነግጥ እንደሚችል ገመቱ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በወቅቱ "ፓርላማ ይገባ-አይገባ" የሚለው ክርክር በውስጣችን እየተካረረ መጥቶ ስለነበር ኢዴአፓ-መድኅን የተናጠል አቋም እንዳይወስድ በመስጋትና አዲስ አበባ መስተዳድሩን ልንረከብበት የሚገባን መስከረም 30 ቀን 98 ዓ.ም ከመድረሱ በፊትም ኢዴአፓ-መድኅንን አስቀድሞ እንዲከስም ማድረግ አስፈላጊ መስሎ ስለታያቸው እነ ዶ/ር ብርሃኑ ሌላ አዲስ ስልት በድንገት ይዘው ብቅ አሉ፡፡ ይኸውም የተጀመረውን የውኅደት ሂደት እንዲቆም አደረጉና ምርጫ ቦርድ ከሰኔ 97 ዓ.ም በኋላ ቅንጅቱ ህልውና የለውም ብሎናል የሚለውን ምክንያት በማድረግ ሁሉም ፓርቲዎች ውኅደቱን ፈጽመናል ብለን የዕውቅና ሰርቲፍኬታችንን ለምርጫ ቦርድ እንመልስና አዲስ ሰርቲፍኬት እንጠይቅ የሚል ሐሳብ አቀረቡ፡፡

በእኛ በኩል አንደኛ የውኅደቱ ሂደት በሥራ-አስፈጻሚ ደረጃ እንኳ ያልተጠናቀቀና ገና የፓርቲዎቹን የበታች መዋቅሮችንና አባላትን ማዋሃድ፣ የፓርቲዎቹን ሀብትና ንብረት ማዋሃድ፣ የፓርቲዎቹን በውጭ የሚገኙ የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች ማወሃድ እንደሚቀረን በመግለፅ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የኢዴአፓ-መድኅን ጠቅላላ ጉባዔ ውኅደቱ ሙሉ በሙሉ መስከረም 14 በተገባው ስምምነት መሠረት እስከታችኛው መዋቅር እስካልተጠናቀቀ ድረስ የዕውቅና ሰርቲፍኬታችንን ለምርጫ ቦርድ እንዳንመልስ የወሰነ መሆኑን በማስታወስ የቀረበውን ጥያቄ እንደማንቀበለው አሳወቅን፡፡

ምርጫ ቦርድ ዕውቅና የላችሁም ብሎናል ለሚለው ምክንያትም - ውኅደቱን በአግባቡ እስከምንፈጽም ድረስ የቀድሞውን ጊዜ ያለፈበትን የቅንጅት ዕውቅና በአራቱ ፓርቲዎች ጥያቄ አቅራቢነት እንደገና አድሰን መጠቀም እንደምንችልና እንዲያውም በዚያ ከገዥው ፓርቲ ጋር የከረረ ፍጥጫ ባለንበት ወቅት በእጃችን የሚገኙትን የፓርቲ ዕውቅናዎች ለምርጫ ቦርድ አሣልፎ ሰጥቶ ሌላ አዲስ ዕውቅና መጠዬቅም የህልውና አደጋ ሊያስከትል የሚችል የተሳሳተ ስልት መሆኑን ለመግለፅ ሞከርን፡፡ ነገር ግን እነ ዶ/ር ብርሃኑ የኢዴአፓ-መድኅንን ህልውና በአቋራጭ ለማጥፋት ያላቸው ብቸኛ መንገድ ውኅደቱን ያለ አግባብ በዚያ ሁኔታ ተግባራዊ

ማድረግ ሆኖ ስለታያቸው ሃሣባቸውን መቀዬር አልፈለጉም፡፡ ያንን ተገቢ ያልሆነ ጥያቄያቸውን በውይይትና በምክክር ማስፈጸም እንደማይችሉ ስለገባቸውም በውጫዊ የሕዝብ ግፊት እኛን ለማንበርከክ ያስችለናል ብለው ያመኑበትን አብዮታዊ ስልት በመቀዬስ በበርካታ ጋዜጦች ላይ የእኔን ስም የማጥፋት ሰፊ የአሉባልታ ዘመቻ ከፈቱ፡፡

ቅንጅቱ በዚህ ዓይነት የውኀደት ውዝግብ ዙሪያ በነበረበት ወቅት በተመሳሳይ ሁኔታ ፓርላማ የሚከፈትበትና አዲስ አበባ መስተዳድርን ልንረከብ የሚገባን መስከረም 30 ቀን እየቀረበ በመምጣቱ ፓርላማ እንግባ-አንግባ? በሚለው ጥያቄ ላይ ቅንጅቱ የከረረ ውዝግብ ውስጥ ገባ፡፡ ይህ አጀንዳ በቅንጅቱ ውስጥ ገና አከራካሪ መሆን እንደ ጀመረ ኢዴአፓ-መድኅን በፓርቲ ደረጃ ተነጋግሮ በጉዳዩ ላይ አቋም መያዝ ችሎ ነበር፡፡ የኢዴአፓ-መድኅን ማዕከላዊ ኮሚቴ በጉዳዩ ላይ ገና በሐምሌ ወር ሰፊ ውይይት አድርጐ ፓርላማ መግባትም ሆነ አዲስ አበባን መረከብ የግድ አስፈላጊ ነው ብሎ የወሰነው በአንድ ድምፀ ተአቅቦ ብቻ፣ በሙሉ ድምፅ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀደም ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ቅንጅቱ በውጭ አገር ኗሪ በሆኑት አክራሪ የፖለቲካ ኃይሎች፣ አገር ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ጽንፈኛ የግል ጋዜጦች፣ በእነዚህ ኃይሎች ቀስቃሽነት በተፈጠረው የሕዝብ ስሜትና በገዥው ፓርቲ ስልታዊ ፕሮፓጋንዳ ጭምር እየተገፋ በመሄድ ጉዳዩን ከራሱና ከትግሉ ጥቅም አንጻር በሚገባው መዝኖ ውሳኔ መስጠት ወደማይችልበት ደረጃ ደረሰ፡፡

በተለይም ኢንጂነር ኃይሉ አሜሪካን አገር ሄደው በአንድ መድረክ ባካሄዱት ስብሰባ ላይ ቅንጅቱ ገና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ላይ ባልደረሰበት ወቅት ውጭ አገር ኗሪ የሆነውን ደጋፊ ለማስደሰት ሲሉ "ፓርላማ ላለመግባት ወሥነናል" ብለው ከተናገሩ በኋላ እሳቸው የተናገሩት ቃል እንደ ፈጣሪ ቃል ተቆጥሮ የቅንጅቱን በነፃነት ተነጋግሮ የመወሰን ዕድል ፈተና ውስጥ ከተተው፡፡ ዶ/ር ብርሃኑን ጨምሮ አብዛኛዎቹ የቅንጅት አመራሮች ቀደም ሲል ፓርላማ መገባት አለበት የሚለውን አቋም ሲያራምዱ የነበረ ቢሆንም ኋላ ላይ ግን "ፓርላማ አትግቡ" የሚለው አቋም እየተጋጋለ ሲመጣ በአንድ በኩል ፓርላማ ይገባ ብለው ቢወስኑ በጋዜጣ ሊወራባቸው የሚችለውን አሉባልታና "ከሃዲ" ተብሎ ለጊዜው መሰደብን በመፍራት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሆነ ግርግር መንግሥት ለመሆን የሚቻልበት ዕድልና አጋጣሚ ምንአልባት ሊፈጠር ይችል ይሆናል ብሎ በመገመት ፓርላማ ይገባ ብሎ መወሰንን እንደ ጦር እየፈሩት መጡ፡፡

ይህም ሆኖ ከኢዴአፓ-መድኅን ሰዎችና ከመኢአድ ውስጥ ከሻለቃ አድማሱ መላኩ፣ ከቀስተ ደመና ውስጥ ደግሞ ከዶ/ር ሽመልስ ተክለ ጻድቅ በስተቀር ፓርላማ መግባትን በግልጽ የሚደግፍ ሰው እየጠፋ ቢመጣም በውስጡ ግን አብዛኛው ሰው ፓርላማ መግባትን የሚደግፍ

መሆኑ የማያጠራጥር ነበር፡፡ ይህንን በማወቅም አጀንዳው ለመጨረሻ ጊዜ ለውይይት በቀረበበት ስብሰባ ላይ በእኛ በኩል ሰዎች ይህንን ጉዳይ ከውጫዊ ተፅዕኖ በፀዳ ሁኔታ በነፃነት እንዲወስኑት በማሰብ በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ እንወሥነው የሚል ሐሳብ አቅርበን የነበረ ቢሆንም እነ ኢንጂነር ኃይሉ ውሳኔው በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ ቢወሰን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል አስቀድመው ስለገመቱ ተረባርበው ሃሣባችን ተቀባይነት እንዳያገኝ አደረጉት፡፡ እንዲያውም “በዚህ ጉዳይ ላይ ማንኛውም ሰው የሚኖረው አቋም በኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ መታወቅ አለበት” በማለት ለማስፈራራት ሞከሩ፡፡

በወቅቱ አርቲስት ደበበ እሸቱ ከጉኔ ተቀምጦ የነበረ ሲሆን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት “ፓርላማ መግባት አለብን” ሲለኝ እንዳልነበር ኢንጅነር ኃይሉ ከላይ የጠቀስኩትን ማስፈራሪያ ከተናገሩ በኋላ ግን ወዲያውኑ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ “ልደቱ - እኔ ከዚህ በኋላ ሃሣቤን ቀይሬአለሁ - በግልጽ ፓርላማ ይገባ ብዬ በመወሰን ራሴን ችግር ውስጥ ላስገባ አልችልም” አለኝ፡፡ አርቲስት ደበበ በዚያን ወቅት ስብሰባው ውስጥ ባደረገው ንግግርም “እኔ ዕድሜ ልኬን ቲያትር ስሰራ ነው የኖርኩት -ይችኛዋ ቲያትር ግን አልተመቸችኝም” በማለት ትንሽ አሳቀን፡፡ በአጠቃላይ በዚያ የውሳኔ ሂደት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሐሳብ ነፃነት ስንታገል ኖረናል በማለት የሚመፃደቁ የአገራችን የፖለቲካ ልሂቃን እንኳንስ ለሕዝብ የሚተርፍ የራሳቸውንም መብት ለማስከበር የሚያበቃ ድፍረት እንደሌላቸው ተገንዝበናል፡፡ በአገራችን ፖለቲካ የምሁራኑ ተሳትፎ ለምን እንደቀጨጨም ሆነ በርካታ የአገራችን ምሁራን ለምን ለእነ ኮሌኔል መንግሥቱና ለእነ ጎምሳ አለቃ ለገሠ አስፋው አጨብጫቢና ታዛዥ ሆነው እንደኖሩም በሚገባ መረዳት የቻልነው በዚያ ሂደት ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በመጨረሻም ድምጽ መስጠቱ እንዲቀር ተደረገና ቅድመ-ሁኔታ አቅርበን እንግባ በሚል ሰበብ በውጤቱ ፓርላማ አለመግባትንና አዲስ አበባን አለመረከብን ያስከተለ ውሳኔ በስምምነት እንዲወሰን ተደረገ፡፡ በነገራችን ላይ የዚህ አማራጭ ውሳኔ ሐሳብ አመንጭ የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ሲሆኑ ይህ ውሳኔ በተወሰነ በሦስኛው ቀን “ቅንጅቱ የወሰነው ፓርላማ ላለመግባት ነው እንጂ አዲስ አበባን ላለመረከብ አይደለም” የሚል አስቂኛና አስገራሚ የሆነ መከራከሪያ ፈጥረው አዲስ አበባን ለመረከብ ቅንጅቱ የማያውቀው ኮሚቴ በድብቅ አቋቁመው ጥረት ሲያደርጉ ተደርሶባቸው ሙከራው እንዲከሽፍ ተደርጓል፡፡ ዶ/ር ብርሃኑ በመጨረሻ ሰዓት በቀዬሱት በዚህ ስልት እኛን ፓርላማ እንዳንገባ በማድረግ ከፖለቲካ ውጭ ካደረጉ በኋላ እሳቸው የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነው ሊቀጥሉ ፈልገው ነበር፡፡ ነገር ግን ፓርላማ ይገባ-አይገባ? የሚለው አጀንዳ ለውይይት በቀረበበት ወቅት በእኛ በኩል ይህ ውሳኔ አዲስ አበባን አለመረከብንም የሚጨምር

ውሳኔ ስለመሆኑ በግልጽ ቃለ-ጉባዔ ላይ እንዲመዘገብ አድርገን ስለነበር የዶ/ር ብርሃኑ ጥረት መፈናፈኛ አልነበረውም፡፡ ኋላ ላይ አዲስ አበባን ለመረከብ ጥረት እያደረጉ መሆኑ ተደርሶባቸው ለምን ይህንን እንዳደረጉ በስብሰባ ላይ ተጠርተው ሲጠየቁ "እኛ አዲስ አበባን አንረከብም ከምንል ለመረከብ ጠይቀን ኢህአዴግ ከለከለን ብንል የተሻለ የፖለቲካ መልስ ይሆናል ብዬ ነው" የሚል አስቂኝ መልስ ሰጡ፡፡

ይህ ፓርላማ ይገባ-አይገባ? የሚል አጀንዳ መጨረሻ ላይ በቅንጅቱ ምክር ቤት ቀርቦ ውይይት ሲደረግበት በነበረበት ወቅት በዋናነት የእኛን ፓርቲ አቋም ይዘው በግልጽ ይከራከሩ የነበሩት አቶ ሙሼ ሰሙ፣ አቶ አብዱራህማን አህመዲንና ዶ/ር ሙሰ[illegible]ሰም ታረቀኝ ነበሩ፡፡ ይህንንም ያደረግነው ያለ ምክንያት ሳይሆን በወቅቱ ያለ ኀፍረት "ልደቱ የሚያቀርበው ማንኛውም ሐሳብ ትክክል ቢሆንም ባይሆንም መቀበል አንፈልግም" የሚሉ ኢንጅነር ግዛቸውን የመሰሉ አንዳንድ የቅንጅቱ አመራሮች ስለነበሩና እነዚህ ሰዎች እኔን ለመቃወም ሲሉ የቀረበውን አጀንዳ ለመቃወም የበለጠ እንዳይገፉፉ በማሰብ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህም ሆኖ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያምና አቶ ግዛቸው ሽፈራው በውይይቱ መሃል አቋርጠው እየወጡ በውጭ አገር ለሚገኙ መገናኛ ብዙኃን "ልደቱ ፓርላማ መግባት አለብን እያለ እየበጠበጠን ነው፡፡ እኛ ግን ፓርላማ ይገባ ብለን ሽንጣችንን ገትረን እየተሟገትን ነው" እያሉ መግለጫ ይሰጡ ነበር፡፡ በርግጥ "ልደቱ እየበጠበጠን ነው" የሚለው አባባል ተጋኖ የቀረበ ቢሆንም በወቅቱ ፓርላማ መገባት የለበትም ብሎ ከዶ/ር ያዕቆብና ከአቶ ግዛቸው በላይ በከረረ ሁኔታ የሚከራከር ሰው አልነበረም፡፡ እንዲያውም ዶ/ር ያዕቆብ በወቅቱ ያደረጉት ንግግር በኋላ ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥንም ላይ ቀርቦ እንደታየው "የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የለውጥ አጋጣሚዎችን በከንቱ አሳልፏል፡፡ ይህንን የለውጥ አጋጣሚ ግን በአግባቡ በእጃችን መጨበጥ አለብን፡፡ ፓርላማ መግባት ይህንን የለውጥ አጋጣሚ የሚያበላሽ ስለሆነ ልንቀበለው አይገባም" የሚል ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ዶ/ር ያዕቆብና አቶ ግዛቸው አንድ ቀን ከስብሰባ ወጥተው ጐን ለጐን እያዎሩ ሲሄዱ እኔን ከቅንጅቱ ለማስወገድ ስላላቸው ፍላጐት በግላቸው ያወሩትን ወሬ በወቅቱ የቅንጅቱን ቃለ-ጉባዔ በየቀኑ እያተመ ያወጣ የነበረው ኢፍቲን ጋዜጣ ለንባብ አብቅቶት ነበር፡፡ የሚገርመው ግን እነዚህ ግለሰቦች በመንገድ ሲሄዱ ሳይቀር በግላቸው የሚያወሩትን ወሬ እየተከታተለ የሚመርጅና ቤታቸው ውስጥ ሆነው ሲያነጥሱ ጭምር የሚሰማቸው ኃይል መኖሩ እየታወቀ የቅንጅት ሰዎች "በስብሰባ ላይ የምንነጋገረውን ምስጢር ለመንግሥት የሚያቀብልብን ልደቱ ነው" እያሉ በሰፊው ያስወሩ ነበር፡፡ ነገር ግን በዚያን ወቅት የቅንጅቱ ስብሰባዎች ቃለ-ጉባዔ በኢፍቲን ጋዜጣ ይወጣ የነበረው እኔ ራሴን ከቅንጅቱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊነቴ አግልዬ

በስብሰባ በማልገኝበት ወቅት ጭምር ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ እነ ወ/ሪት ብርቱካን ከእሥር ቤት ወጥተው የራሳቸውን አንድነት ፓርቲ ካቋቋሙ በኋላም በስብሰባ የሚነጋገሩበት ጉዳይ ቃል በቃል ጋዜጣ ላይ በዝርዝር እየወጣ እያነበብነው ነው፡፡ ዛሬ ግን ያ- የፈረደበት "ልደቱ" የሚባል ሰው በውስጣቸው ስለሌለ የሚወነጅሉትን ሰው ማወቅ ተስኗቸው ግራ ተጋብተዋል፡፡

ፓርላማ የመግባት-ያለመግባት ጉዳይ ከላይ በገለፅኩት መልኩ ከተወሰነ በኋላ መንግሥት በቅንጅቱ ላይ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለማፍረስ የሚንቀሳቀስ ኃይል ነው የሚለውን ቅስቀሳውን የበለጠ አጠናክሮ ቀጠለበት፡፡ ቅንጅቱ የህልውና አደጋ ውስጥ መሆኑ ግልጽ እየሆነ በመጣበት በዚያ ወቅት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ግን የዕውቅና ሰርቲፍኬታችንን ለምርጫ ቦርድ አስረክበን አዲስ ዕውቅና እንጠይቅ የሚለውን አቋማቸውን የበለጠ ገፉበት፡፡ በእኛ በኩልም "በመጀመሪያ ደረጃ የውኅደቱ ሂደት ሳይጠናቀቅ የፓርቲያችንን ህልውና ልናጠፋ አንችልም፡፡ ይህንን የማድረግ መብትም የፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባዔ አልሰጠንም፡፡ በሌላ በኩል እንዲህ ዓይነት ግልጽ አደጋ በቅንጅቱ ላይ ባንዣበበበት ወቅት ምርጫ አጭበርብሯል ብለን እየከሰሥነው የምንገኘው ምርጫ ቦርድ ገና አዲስ ዕውቅና ይሰጠናል ብለን በእጃችን የያዝነውን የፓርቲ ዕውቅና አሣልፈን አንሰጥም" በሚለው አቋማችን ፀናን፡፡ ፍጥጫው እየተባባሰ ሲመጣ ጉዳዩን ራሳችን እንደገና ተሰብስበን እንወያይበት የሚል ግፊት ከአንዳንድ የራሳችን ፓርቲ ሰዎች ስለመጣ የኢዴአፓ-መድኅን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ተሰብስበን በጉዳዩ ላይ እንድንወያይበት ተደረገ፡፡

በዚያ ስብሰባ በወቅቱ ከነበርነው የኢዴአፓ-መድኅን 18 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ውስጥ ከዶ/ር አድማሱ ገበዬሁ በስተቀር ዐሥራ ሰባታችን የተገኘን ሲሆን የተጠዬቅነውን ውኅደት በዚያ ወቅትና ሁኔታ መፈጸም ይገባናል አይገባንም? ብለን ከመወያየታችን በፊት "ለመሆኑ ይህ አመራር ባጠቃላላ ጉባዔው ከተሰጠው ኃላፊነት አንጻር በዚህ ጉዳይ ላይ አዲስ ውሳኔ የመወሰን መብት አለው ወይ?" የሚል የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ በመነሣቱ በቅድሚያ በዚህ የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ ላይ ውይይት አደረግን፡፡ በተደረገው ውይይትም "የእኛ ኃላፊነት ጠቅላላ ጉባዔው ወስኖ የሰጠንን ኃላፊነት ማስፈጸም ነው፤ ጠቅላላ ጉባዔው ደግሞ የወሰነው የኢዴአፓ-መድኅን ሰርቲፍኬት ለምርጫ ቦርድ መመለስና ህልውናው ማክተም ያለበት የውኅደቱ ሂደት በስምምነቱ መሠረት ሙሉ በሙሉ መፈፀሙ ከተረጋገጠ በኋላ ነው ስለሚል ይህንን ውሳኔ አክብረን የማስፈጸም እንጂ ይህንን የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ወደኋላ ሂደን ልንነጋገርበት ሥልጣን የለንም" የሚል ክርክር በአንድ በኩል ሲነሳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ "የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔ የመሻር

ሥልጣን የሌለን ቢሆንም ቢያንስ ጉዳዩ አሳሳቢ ከመሆኑ አንጻር እንወያይበት” የሚል ሐሳብ ቀረበ፡፡

እነዚህ ሁለት አቋሞች በቀላሉ በውይይት መታረቅ ባለመቻላቸው ድምፅ እንዲሰጥባቸው ተደረገ፡፡ በተሰጠው ድምፅም አሥር ለሰባት በሆነ ድምፅ “የጠቅላላ ጉባዔውን ውሳኔ የመሻር መብት እስከሌለን ድረስ በጉዳዩ ላይ መወያየትም ትርጉም የለውም” የሚለው አቋም አሸነፈ፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የኢዴአፓ-መድኅን ጠቅላላ ጉባዔ በቅንጅቱ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ችግር ሊከሰት እንደሚችል አስቀድሞ ያውቅ ስለነበር በጉዳዩ ላይ ለአመራሩ የሰጠው መመሪያ ግልጽና የማያሻማ ስለነበር ከዚህ የተለየ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ዕድል አልነበረም፡፡ በመጨረሻ የኢዴአፓ-መድኅን ማዕከላዊ ምክር ቤት ተሰብስቦ የወሰነውን ውሳኔ ለቅንጅቱ አመራሮች በደብዳቤ አሳወቅናቸው፡፡

እነ ዶ/ር ብርሃኑ ኢዴአፓ-መድኅን በጉዳዩ ላይ እነሱ የሚፈልጉትን ውሳኔ እንዲወስን የሚችሉትን ያህል ድርጅታዊ ሥራ ለመሥራት ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀር ባደጉበት የግራ ፖለቲካ ልምድ መሠረት በስድስት የግል ጋዜጦች ሕዝቡን የሚያሸብርና ግራ የሚያጋባ ከፍተኛ የአሉባልታ ዘመቻ በእኔ ላይ ከፈቱ፡፡ በአንድ በኩል ህልውናችንን የሚያሳጣንን ከውኅደቱ ስምምነትም ሆነ ከጠቅላላ ጉባዔአችን ውሳኔ ውጭ የሆነውን ያን ዓይነት የተሳሳተ ውሳኔ በአሉባልታ ዘመቻ ተገደን እንድንቀበል የሚያስችላቸውን ጥረት እያደረጉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቅንጅቱን ምክር ቤት ስብሰባ በመጥራት በጉዳዩ ላይ የጋራ ውይይት እንድናካሂድበት ጋበዙን፡፡ በዚያ ስብሰባ ላይ ኢዴአፓ-መድኅን የዕውቅና ሰርተፍኬቱን ለምርጫ ቦርድ አስረክቦ ሙሉ በሙሉ ህልውናውን እንዲያጣ የቀረበለትን ጥያቄ ለምን ሊቀበለው እንደማይችል ቀደም ሲል ከላይ የጠቀስኳቸውን ምክንያቶች በማቅረብ በዝርዝር አስረዳ፡፡

ነገር ግን በወቅቱ የቅንጅቱ የምክር ቤት አባላት በደፈናው “ከእኛ ውሳኔ አትነጠሉ” ከሚል ትርጉም የሌለው አባባል በስተቀር ለምን ሕጋዊ ህልውናችንን እንዲያከትም ማድረግ እንዳለብን ያቀረቡልን አሳማኝ ምክንያት አልነበረም፡፡ እንዲያውም ዶ/ር ብርሃኑ በወቅቱ በስብሰባው ላይ እጃቸውን አውጥተው ያቀረቡት ሐሳብ “እኛ እናንተ ይፈጠራል የምትሉት የህልውና አደጋ እስካሁን አልታዩንም፡፡ እናንተ እንደምትሉት የህልውና አደጋ የሚመጣስ ከሆነ እናንተ ከእኛ ተነጥላችሁ ለመዳን ትፈልጋላችሁ ወይ? በዴሞክራሲ አሠራር የምታምኑ ከሆነስ ለምን አብዛኛው የቅንጅቱ አባል የሚወሥነውን ውሳኔ አትቀበሉም?” የሚል ነበር፡፡

ለዚህ የዶ/ር ብርሃኑ ጥያቄ በእኔ በኩል በወቅቱ የሰጠኋቸው መልስ "በመጀመሪያ ደረጃ ዶ/ር ብርሃኑ እንደምትለው ከሰማይ በታች የሆነ ነገር ሁሉ በድምፅ ብልጫ ይወሰናል የሚል የዴሞክራሲ መርህ የለም፡፡ የአብላጫ ድምፅ ውሳኔ ተቀባይነት የሚኖረው በአንድ በኩል የተስማማንበትን አሠራርና ሕጋዊነትን የተከተለ ውሳኔ ሆኖ ሲገኝ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአብላጫ ድምፅ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው መሠረታዊ ህልውናችንን የማያሳጣን ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ሕጋዊ አሠራርም ሆነ ህልውና በሌለበት ሁኔታ የአብላጫ ድምፅ የሚባል ዴሞክራሲያዊ አሠራርም ሊኖር አይችልም፡፡ እንኳን ገና በቅንጅት ደረጃ ባሉ የራሳቸው ህልውና ባላቸው ፓርቲዎች መካከልና አንድ ወጥ የሆነ ህልውና ያለው ሰላማዊ ትግል አካሂዳለሁ የሚል ፓርቲ አንድ ቀን ድንገት ብድግ ብሎ ከዛሬ ጀምሮ ትግሌን የማካሂደው በሰላማዊ ትግል ሳይሆን በትጥቅ ትግል ነው ብሎ በድምፅ ብልጫ ቢወስን፣ እንዲህ ዓይነቱን ሕገ-ወጥ ውሳኔ የዚያ ፓርቲ አባል የሆነ ማንኛው ሰው እንዲቀበል የሚገደድበት አሠራር አይኖርም፡፡ ሁለተኛ ወደፊት የህልውና አደጋ ቢፈጠር እናንተ ከኛ ተለይታችሁ ልትድኑ ትፈልጋላችሁ ወይ? ላልከው ጥያቄ የኛ መልስ አዎ-እንፈልጋለን የሚል ነው፡፡ አብረን መዳን የምንችልበትን አማራጭ መንገድ እየነገርናችሁ የግድ አብረን እንጥፋ የሚል ውሳኔ ካልተቀበላችሁ የምትሉን ከሆነ እኛ ራሳችንን ማዳን እንፈልጋለን፡፡ በፖለቲካ አብረን እንዳን እንጂ አብረን እንጥፋ የሚል የይሉኝታና የሞኝነት ውሳኔ በእኛ በኩል ቦታ የለውም" የሚል ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ይህንን አባባሌን የያዘውን የቪዲዮ ካሴት የመኢአድ ሰዎች እኔን የጐዱና ያጋለጡ መስሏቸው በውጭ አገር ለሚገኙ ደጋፊዎቻቸው ያሰራጩት መሆኑን ከሁለት ዓመት በፊት ሰምቻለሁ፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት መኢአድና ቀስተዳመና ኢዴአፓ-መድኅን በዚያ ሁኔታ የግድ ህልውናውን በአጭር ጊዜ ማጣት አለበት ብለው ወሥነው ስለነበር ስብሰባው ጉንጭ አልፋ ከመሆን አልፎ ወደ መግባባት መንፈስ ሊመጣ አልቻለም፡፡ በመጨረሻም በእኔ በኩል የሚከተለውን የማያዳግም አቋም ለምክር ቤቱ ስብሰባ አቀረብኩ -፡፡

"በቅንነት ከኢዴአፓ-መድኅን ጋር አብረን መሥራት ይጠቅመናል ብላችሁ ካሰባችሁ በቅድሚያ የቅንጅቱን ጊዜ ያለፈበት ፈቃድ እንደገና አድሰን በመጠቀም ውኅደቱ በስምምነታችን መሠረት ሙሉ በሙሉ እንዲጠናቀቅ አብረን መሥራት እንችላለን፡፡ ቅንጅቱ የቀድሞ ህልውናውን እንደገና አድሶ እንዲቀጥል ለማድረግም ለምርጫ ቦርድ መቅረብ ያለበትን ማመልከቻ አብሮ ለማቅረብ ኢዴአፓ-መድኅን ዝግጁ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚያቅታችሁ ከሆነ ግን ለጊዜው ኢዴአፓ-መድኅንን ተውትና እናንተ ሦስቱ ፓርቲዎች ለምርጫ ቦርድ የየፓርቲዎቻችሁን ሰርተፍኬቶች በመመለስ የምትፈልጉትን ውኅደት ፈፅሙ፡፡ ሦስቱ ፓርቲዎች

በዚህ መንገድ ሂዳችሁ በርግጥም የቅንጅቱን ህልውና ማስጠበቅና የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አጠናክራችሁ መቀጠል ከቻላችሁ ያኔ - እኛ ዛሬ የታዬን ስጋት ስህተት መሆኑ በተግባር ስለሚረጋገጥ ስለ ስህተታችን እናንተንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ በይፋ ተንበርክከን ይቅርታ እንጠይቃለን። ነገር ግን አሁን እናንተ በመረጣችሁት መንገድ ሂዳችሁ የቅንጅቱንም ሆነ የትግሉን ህልውና አጣብቂኝ ውስጥ ካስገባችሁት ለአጠፋችሁት ጥፋት የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ የሚገባችሁ እናንተ ትሆናላችሁ። ስለዚህ በእነዚህ አማራጮች ከኢዴአፓ-መድኅን ጋር አብሮ የመሥራትና ያለመሥራቱ አማራጭ በእናንተ እጅ ያለ ነው" በማለት ከተናገርኩ በኋላ ከስብሰባው ፈቃድ ጠይቄ ተሰናብቼ ወጣሁ።

ከዚያ ስብሰባ ማግስት ጥቅምት 17 ቀን 98 ዓ.ም እነ ዶ/ር ብርሃኑ የቅንጅቱን ምክር ቤት እንደገና በመሰብሰብ የኢዴአፓ-መድኅንን ተወካዮች በተመለከተ ጨርሶ ውሳኔ ለመስጠት የሌላቸውን ሥልጣን በመጠቀም እኔና አቶ ሙሼ ሰሙን "ከቅንጅቱ አመራርነት አግደናል" የሚል ውሳኔ በመስጠት ለሕዝብ ይፋ አደረጉ። ቅንጅቱ እንዲህ ዓይነት ውሳኔ የመወሰን ሕጋዊ መብት ያለው ስለመሆኑና አለመሆኑ ምንም ዓይነት ማጣራት ሳያደርጉ ጋዜጦችና በውጭ አገር የሚገኙ ሬዲዮ ጣቢያዎች ዜናውን አሙሁት። የቅንጅቱን የወቅቱን ጥያቄ አንቀበልም የሚለው ውሳኔ የልደቱና የሙሼ የግል ውሳኔ ሳይሆን እንደ ፓርቲ የኢዴአፓ-መድኅን መሆኑን እያወቁ "ልደቱ የድርጅቱን ማኅተም አላደርግልን አለ" የሚል ቁንፅል አሉባልታ መንዛት ጀመሩ። ችግሩ ወደዚህ ዓይነት ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሕገ-ወጥነት ማምራቱን ኢዴአፓ-መድኅን ሲገነዘብም ወዲያውኑ አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ከቅንጅት አባልነቱ ራሱን የነጠለ መሆኑንና ከዚያ በኋላ በቅንጅቱ ውስጥ በሚፈጸሙ ማናቸውም ድርጊቶች ምንም ዓይነት ኃላፊነት የማይወስድ መሆኑን በይፋ ደብዳቤና መግለጫ ለቅንጅቱና ለሚመለከታቸው አካሎች ሁሉ አሳወቀ።

የእኛ ፓርቲ ይህንን ዓይነት ርምጃ ወስዶ ራሱን ከቅንጅቱ በይፋ ካገለለ በኋላ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ከአርባ ቀን በፊት ከኢዴአፓ-መድኅን ሊቀመንበርነታቸው በጉባዔ ውሳኔ የተሰናበቱትን ዶ/ር አድማሱ ገበዬሁን በማስፈረምና ሕገ-ወጥ ማኅተም አሰርተው በማተም በአራቱ ድርጅቶች ስም የውኅደት ጥያቄ ጥቅምት 18 ቀን 98 ዓ.ም ላይ ለምርጫ ቦርድ አቀረቡ። ለዚህ ላቀረቡት ጥያቄ ገና መልስ ሳያገኙም በማግስቱ ጥቅምት 19 ቀን ለተከታታይ ቀናት የሚካሄድ የሕዝብ የሰላማዊ አመፅ ጥሪ ሰነድ ዶ/ር ብርሃኑ ለቅንጅቱ ለውይይት ማቅረባቸውን ሰማን። ይህንን በሰማን በማግስቱም ቅንጅቱ ለሕዝቡ ተከታታይ የሰላማዊ አመፅ ጥሪ ስለማድረጉ በጋዜጣ ተሰራጨ። በዚህ ጥሪ መሠረትም ጥቅምት 21 ቀን አመፁ የመኪና ጥሩንባ በማስማት ተጀምሮ በማግሥቱ ጥቅምት 22 ቀን ወደ ከፍተኛ አመፅና ግድያ ተሸጋገረ። ከዚያ ዕለት ጀምሮም በዚያ

የአመፅ ጥሪ ላይ ተሳትፈዋል የተባሉት የቅንጅቱ አመራሮች እየታደኑ መታሰር ጀመሩ፡፡ የእኛ አለመታሰር ተጨማሪ ውስብስብ ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችልም እነ ዶ/ር ብርሃኑ እኛን ያለአግባቡ ገፍትረው ከቅንጅቱ በማስዎጣት ከዚያ የአመፅ ጥሪ ተጠያቂነት እንድንድን አደረጉን፡፡

ይህ ሁኔታ ከተከሠተበት ከሁለት ሳምንት በፊት ጀምሮ በእኔ ላይ ሞቅ-ፈዘዝ እያለ ሲወራ የነበረው አሉባልታ በከፍተኛ ደረጃ ፈንድቶ በመውጣት እንደ ማዕበል አገሩን አጥለቀለቀው፡፡ የአሉባልታው ዓይነትና ደረጃ ምን ይመስል እንደነበረ ከመግለፄ በፊት ግን ትንሽ ወደኋላ መለስ ብዬ እኔ ከሰኔ ወር 97 ዓ.ም ጀምሮ በምን ሁኔታ ላይ እገኝ እንደነበር ለማሳየት ብሞክር ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

ከምርጫው በኋላ የመጀመሪያው የሰኔ የተቃውሞ አመፅ ከተጀመረበት ዕለት ጀምሮ ወደ ውጭ እንዳልወጣ ፓስፖርቴን የተቀማሁ ሲሆን የእኔ እንቅስቃሴም ሙሉ በሙሉ በደኅንነት ቁጥጥር ሥር ውሎ ነበር፡፡ አመፅ ከተጀመረበት ዕለት ጀምሮ ለ12 ቀን ያህል -ማለትም ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ያለምንም ምግብ በቢሮዬ ውስጥ ታግቼ የነበር ሲሆን ለ9 ቀናት ደግሞ በመኖሪያ ቤቴ ታግቼ ነበር፡፡ በወቅቱ ኣለኤ እገኝበት የነበረው አሳሳቢ ሁኔታም በዓለም አቀፍ ደረጃ እስከ ኮፊ አናን ድረስ ደርሶ ኣነጋጋሪ ጉዳይ ሆኖ ነበር፡፡ ሕዝቡም ስለእኔ ደኅንነት ተፈጥሮበት የነበረው ጭንቀት እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡

በነገራችን ላይ ዶ/ር ብርሃኑ ያለ ቅንጅቱ ውሳኔ የምርጫ ማጣራቱን ሂደት በሚመለከት ከኢህአዴግ ጋር ስምምነት መፈራረም የቻሉትም እኔና ኢንጂነር ኃይሉ በእገታ ላይ በነበርንበት በዚያን ወቅት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ እኔና አቶ ሙሼ ከቅንጅቱ ታግዳችኋል እስከተባልንበትና በእኔ ላይ የሚወራው አሉባልታ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እስከፈነዳበት ወቅት ድረስም የእኔ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ በደኅንነት ክትትል ሥር ነበር፡፡ በየቀኑ ሦስት ወይም አራት የሚሆኑ መኪናዎች፣ ከ7 እስከ 10 የሚደርሱ የደኅንነት ሠራተኞች በቋሚነት ተመድበው ለ120 ቀናት ያህል ያልተቋረጠ ክትትል ያደርጉብኝ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ክትትል በሚያደርጉብኝ የደኅንነት ሰዎች በየቀኑ ከስድብ ጀምሮ በቦክስ እስከመመታት የሚደርስ እንግልት ይደርስብኝ የነበረ ሲሆን ለዚያን ያህል ጊዜ ብቻዬን ከሰዎች ጋር ተገናኝቼ የማውራትም ሆነ ምግብ ቤት ውስጥ ገብቼ የመመገብ ነፃነት አልነበረኝም፡፡ አንዳንድ ጊዜም ከፊትና ከኋላ የሚከተሉኝ የደኅንነት መኪናዎች ሆን ብለው በሚፈጥሩብኝ ማዋከብ በቀላሉ ነድቼ ቤቴ ለመግባት የምቸገርበት ወቅት ነበር፡፡ ከእኔ ጋር የታዩና የተገናኙ ሰዎች ሳይቀሩ በይፋ ግልጽ ማስፈራራትና ክትትል ይደረግባቸው ነበር፡፡

በወቅቱ የቅንጅቱ ሰዎች በአንድ በኩል “ልደቱ ከአቦይ ስብሃት ጋር በድብቅ ተገናኘ፣ የቅንጅቱን ምስጢር አሣልፎ ለመንግሥት እየሰጠ ነው፣ ፓርላማ እንግባ እያለ የሚበጠብጠን እሱ ነው” እያሉ ሕዝቡ ውስጥ እያስወሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እነ ዶ/ር ብርሃኑ ከኢህአዴግ ባለሥልጣናትና ከውጭ አምባሳደሮች ጋር በየቀኑ ሲገናኙ “ሌሎቻችን በሙሉ ችግሩ በሰላም እንዲፈታ እንፈልጋለን፣ ነገር ግን ልደቱና ኢንጂነር ኃይሉ ናቸው የከረረ አቋም ይዘው አመፅ እንድናሥነሳ የሚገፋፉን” እያሉ ሌላ ገጽታ ያለው ቅስቀሳ በእኔ ላይ ያደርጉ ነበር። እንዲያውም ዶ/ር ብርሃኑ በዚያን ሰሞን ለንደን ሄደው ከእኛ ፓርቲ የድጋፍ ሰጭ ኮሚቴዎች ጋር በተገናኙበት ወቅት “ኢህአዴጎች በልደቱ ላይ ያላቸው ጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፣ ብትመክሩትና ከአገር በአስቸኳይ ቢወጣ ይሻላል፣ አለበለዚያ ግን በአጭር ጊዜ ሊገሉት ይችላሉ” በማለት ተናግረው ነበር። ይህንን የሰሙት የእኛ ደጋፊዎች ከለንደን ደውለው ሲያነጋግሩኝም በወቅቱ በእኔ በኩል የሰራሁት ወንጀል ስለሌለ የምጠፋበት ምክንያትና ፍላጐት እንደሌለኝ፣ ልጥፋ ብዬ ባስብም ፓስፖርቴን በመንግሥት ስለተቀማሁ ከአገር መውጣት እንደማልችል ነበር የነገርኳቸው። በአጠቃላይ በዚያ ወቅት ይሰራ በነበረው የፖለቲካ ቲያትር የኢያጐን ገጸ-ባህሪ ይዘው ይተውኑ የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ነበሩ።

ለረዥም ጊዜ በዚህ ሁኔታ ሁለት መልክ ያለው አሉባልታ እየሞቀም እየቀዘቀዘም በእኔ ላይ ሲካሄድ ከቆዩ በኋላ የቅንጅት መሪዎች ከመታሰራቸው ሁለት ሣምንት በፊት ጀምሮ በከፍተኛ መጠን የፈነዳው አሉባልታ አንድ አቅጣጫ ይዞ ጐልቶ ወጣ። እነ ዶ/ር ብርሃኑ በውኅደቱ ጉዳይ እጃችን በቀላሉ እንደማይጠመዘዝ ሲገባቸው “ልደቱ ማኅተም አላደርግልን አለ፣ በሱ ምክንያትም ቅንጅቱ ህልውናውን ሊያጣ ነው” የሚል ቅስቀሳ ጀመሩ። ሕዝቡም በውስጣችን ምን እንደተፈጠረ በውል ባልተረዳበትና እውነቱን ባላወቀበት ሁኔታ የእነ ዶ/ር ብርሃኑን አሉባልታ በመስማት ብቻ “ልደቱ እንዴት ማኅተም አላደርግም ይላል? በሱ ምክንያት ቅንጅት ህልውናውን ሊያጣ ነው ወይ?” የሚል ሽብር ውስጥ ገብቶ እኔን በጭፍን ማውገዝ ጀመረ። ከማውገዝም አልፎ አንዳንዱ ጭፍን የቅንጅት ደጋፊ “ልደቱን እንገለዋለን” የሚል ዛቻ ውስጥ ገባ። ለመጨረሻ ጊዜ በቅንጅቱ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ተሣትፌ ስወጣ ወ/ሮ ላቀች የሚባሉ በወቅቱ የኢዴአፓ-መድኅን አባል የነበሩ ሰው ከኋላዬ እየተከተሉ የተናገሩኝን እስካሁን አስታውሰዋለሁ። “ልደቱ! ብዙ ወጣቶች አንተን ለመግደል መንገድ ላይ ገጀራ ይዘው እየጠበቁህ ነው! እባክህን ሕይወትህን ለማትረፍ ስትል ማህተሙን አድርግላቸው” ነበር ያሉኝ።

እነ ዶ/ር ብርሃኑ የተለያዩ ጋዜጦችን እያፈራረቁ “ልደቱ ማኅተም አላደርግም ብሎ ቅንጅቱን ሊያፈርሰው ነው” የሚለውን የፈጠራ ቅስቀሳቸውን የበለጠ አጠናክረው ቀጠሉበት።

የሚገርመው ግን ከሰኔ 97 ጀምሮ ቅንጅቱ ሕጋዊ ዕውቅና ስላልነበረው በእኔ ምክንያት ሊያጣው የሚችለው ምንም ዓይነት ህልውና በዚያን ወቅት አልነበረውም፡፡ ቢኖረው ኖሮ በዚያን ወቅት የውኅደት ጥያቄ ማንሣትም ሆነ ለምርጫ ቦርድ ዕውቅና ይሰጠኝ ብሎ የሚያመለክትበት ምክንያትም አይኖርም ነበር፡፡ ለምርጫ ቦርድ አመልክቶም አዲስ ዕውቅና የማግኘቱ ጉዳይ በእኔም ሆነ በኢዴአፓ-መድኅን እምቢተኝነት ሊደናቀፍ የሚችልበት ምክንያት አልነበረም፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን ያለ አግባብ እምቢ ብሎ ቢሆን እንኳ ኖሮ እሱ እንደ ፓርቲ የቅንጅቱ አባል መሆኑ ይቀራል እንጂ ከኢዴአፓ-መድኅን ውጭ ያሉት ሦስቱ ፓርቲዎች በቅንጅት ስም ሕጋዊ ዕውቅና መጠየቅና ማግኘት ይችሉ ነበር፡፡ ኢዴአፓ-መድኅንም ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለ አግባብ ህልውናዬን ልታጠፉ አትሞክሩ አለ እንጂ ከእኔ ተለይታችሁ ቅንጅትን አታቋቁሙ ብሎ ጠይቆ አያውቅም፡፡ ለአለፉት ሦስት ዓመታት በቅንጅት ዙሪያ የነበሩ ሰዎች ለሰባት ተከፍለው ሁሉም በየፊናቸው "ቅንጅትን የምወክለው እኔ ነኝ" እያሉ ሲሻኮቱም አንድም ቀን ኢዴአፓ-መድኅን የቅንጅት የአካልም ሆነ የመንፈስ ወራሽ እኔ ነኝ ብሎ ጠይቆ አያውቅም፡፡ ስለዚህ ቅንጅትን ልደቱ ወይም ኢዴአፓ-መድኅን አፈረሰው የሚለው አባባል ስም ለማጥፋት ተብሎ የተነዛ አሉባልት እንጂ ፈጽሞ እውነትነት አልነበረውም፡፡

ቅንጅት በወቅቱ የሚፈርስ ህልውና ያልነበረው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ህልውና ኖሮትም ቢሆንና በእውነት እነ ዶ/ር ብርሃኑ እንዳስወሩት "ልደቱ" የሚባል አንድ ግለሰብ አፍርሶት ከሆነ በእውነትም ቅንጅት መፍረስ የሚገባው ለአገርና ለሕዝብ የማይጠቅም ደካማ ድርጅት ነበረ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የፈጠራ አሉባልታ በእኔ ላይ የሚያስዎሩት የዎቅቱ የቅንጅት አመራሮች "ልደቱ ቅንጅትን አፈረሰው" ማለትን የመረጡት ቅንጅትን እንደ ድርጅት ይዘው ለመቀጠል የነበረባቸውን ድክመት ለመደበቅ ሲሉና እኔን በሕዝብ ለማስጠላትና ሲቻልም ለማስገደል ከዚህ የተለየ አሳማኝ ምክንያት በእጃቸው ስላልነበረ ቢሆንም በወቅቱ ይህንን የፈጠራ አሉባልታ የሚሰማውና ቅንጅት መንግሥት ሆኖ ችግሬን ይፈታልኛል ብሎ ይጠብቅ የነበረው ሕዝብ "ልደቱ የሚባል አንድ ግለሰብ የሚያፈርሳችሁ ደካሞች ከሆናችሁ - ለእኔስ ምን ትጠቅሙኛላችሁ?" ብሎ ለመጠየቅ አለመሞከሩ ግን የሚገርም ነበር፡፡ ሕዝቡ ይህንን ተገቢ ጥያቄ በወቅቱ ለመጠየቅ ያልሞከረ ቢሆንም የቅንጅት ሰዎች የአገርን ኃላፊነት ሊረከቡ የማይበቁ ደካሞች እንደነበሩ ግን ከእስር ቤት ከወጡ በኋላ ከሰባት በመበታተን ቀድሞውንም ያፈረሳቸው ኢዴፓ ወይም ልደቱ ሳይሆን የራሳቸው ደካማ ባህሪና ማንነት መሆኑን ሕዝቡ ሊገባው በሚችል መጠን በተግባር አሳይተውታል፡፡

ሌላው የሚገርመው ቅስቀሳ “ልደቱ ማኅተም አላደርግም አለ” የሚለው ክስ ነበር፡፡ ይህንን ክስ የሚሰማ ማንኛውም ኅሊና ያለው ሰው በዚያን ወቅት መጠየቅ ይገባው የነበረው ጥያቄ “ልደቱ ማኅተም እንዲያደርግበት የተጠየቀው ሰነድ ምን ይዘት ያለው ነው? ልደቱ በዚያ ሰነድ ላይ ማኅተም ቢያደርግ ሊያስከትል የሚችለው ውጤት ምንድ ነው?” ብሎ ነበር እንጂ፣ ልክ እኤን እንደ አንድ ቢሮውን ቆልፎ እንደጠፋ የመዝገብ ቤት ሹም በመቁጠር “ልደቱ እንዴት ማኅተም አላደርግም ይላል?” ብሎ መውቀስ ተገቢ አልነበረም፡፡ በወቅቱ እኤ እንደዚያ ዓይነቱ ሰነድ ላይ ማኅተም እንዳደርግ ፓርቲየ ያልፈቀደልኝ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያን ወቅት በዚያ ሰነድ ላይ ማኅተም ማድረግ ሊያስከትል ይችል የነበረው ውጤት እንደ ሌሎቹ ድርጅቶች ሁሉ ኢዴአፓ-መድኅን እንዲጠፋ ማድረግና ለትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል ምንም ዓይነት ፋይዳ በሌለው ሁኔታ ከሌሎቹ ጋር ተጠራርጐ እሥር ቤት መግባትና በመጨረሻም ትግሉ ተንኮታክቶ ከተዳከመ በኋላ ሌሎቹ የቅንጅት መሪዎች እንዳደረጉት ኢህአዴግን ይቅርታ ጠይቆና ለሞቱት ሰዎች ኃላፊነት ወስዶ ከእሥር ቤት መውጣት ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ለትግሉም ሆነ ለራስ የማይጠቅም ውርደት ውስጥ ኢዴአፓ-መድኅን ባለመግባቱ ሊመሰገን እንጂ ሊወቀስ ባልተገባውም ነበር፡፡

በወቅቱ ኢዴአፓ-መድኅን እንደዚያ ዓይነቱን አቋም የወሰደው አንዳንድ ሰዎች እንደሚገምቱት እሥር ቤት ላለመግባት ፈርቶም ሳይሆን እንደዚያ ዓይነቱ አካሄድ ለራሱም ሆነ ለትግሉ እንደማይጠቅም ስላመነበት ነው፡፡ ነገር ግን ያንን አቋም የወሰድነው ላለመታሰር ብለን እንኳ ቢሆን አቋማችን ስህተት ሊሆን አይችልም ነበር፡፡ ራስን ከማይገባና ውጤት ከሌለው አደጋ ማዳን ከአንድ ብልህ ፓርቲ የሚጠበቅ ርምጃ ነው፡፡ መታሰርን በራሱ ዓላማ አድርጐ በጀብደኝነት እሥር ቤት የሚገባ ፓርቲም ሆነ የፓርቲ መሪ ለትግሉና ለአገር ይቅርና ለራሱም ደኅንነት ኃላፊነት የማይሰማው ሰው ነው፡፡ እኛ በዚያን ወቅት ገና በሕዝብ እንዳንታማ በሚል ፍርሀት በግብዝነት የተሳሳተ ውሳኔ ወሥነን እሥር ቤት ገብተን ቢሆን ኖሮ ዛሬ ከዶ/ር ብርሃኑ፣ ከኢንጂነር ኃይሉ ወይም ከወ/ሪት ብርቱካን መካከል አንዱን ከመሆን አልፈን ለትግሉ የምናበረክትለት ምንም የተለየ ተአምር ሊኖር አይችልም ነበር፡፡ መታሰር በራሱ የጀግንነትና የሃቀኝነት መግለጫ፣ አለመታሰር ደግሞ የወያኔነት ማረጋገጫ ሆኖ የሚታይ ከሆነም በዚያ ወቅት እኛ ብቻ ሳንሆን እነ ፕሮፌሰር በየነ፣ ዶ/ር መረራንና አቶ ቡልቻን ጨምሮ ከቅንጅቱ 60 የምክር ቤት አባላት ውስጥ እነ ዶ/ር አድማሱ ገበዬሁን፣ ሻለቃ አድማሱ መላኩን፣ አቶ መሐመድ ዓሊን ዶ/ር አለማዬሁ አረዳንና ዶ/ር ሽመልስ ገ/ፃዲቅን ጨምሮ 27 አመራር አባላት አልታሰሩም ነበር፡፡ ነገር ግን በወቅቱ አለመታሰር የወያኔነት ማረጋገጫ ተደርጐ ይቀርብ የነበረው ለጥቂት የኢዴአፓ-መድኅን አመራሮች ብቻ ነበር፡፡

ይልቁንስ ቅንጅት በወቅቱ የእኛን አቅጣጫ ተከትሎ ቢሆን ኖሮ ትግሉ ዛሬ የተሻለ ደረጃ ላይ ይደርስ የነበረ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩትና በአደባባይ ጭፍጨፋ የሞቱት ንፁሃን ወጣቶች ከእንደዚያ ዓይነቱ አሰቃቂ አደጋ በዳኑ ነበረ፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ - እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋም "ለምን አልታሰራችሁም" ብሎ እኛን ለመውቀስና ለመተቸት መሞከር ክፋት እንጂ በጎ አስተሳሰብ ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኛ ፍላጐት ምንም ይሁን ምን የመታሰርና ያለመታሰር ጉዳይ ከኛ ቁጥጥር ውጭ የሚፈጸም መሆኑንና ገዥውም ፓርቲ ለራሱ ዓላማና ጥቅም ሲል እኛን የማሰርና ባለማሰር ዙሪያ ሊጫዎት የሚችለው የራሱ ፖለቲካ ያለው መሆኑን ማጤን ይገባ ነበር፡፡

የቅንጅት ሰዎች በወቅቱ በእኔ ላይ እንዲህ ዓይነት የአሉባልታ ዘመቻ ሲያካሂዱ የነበረው እኔ ራሴን ለመከላከል የማልችልበትን ሁኔታ በመፍጠርም ጭምር ነበር፡፡ የቅንጅት አመራሮች ከስድስት የበለጡ ጋዜጦችን ለአሉባልታ ዘመቻቸው በእኔ ላይ አሰማርተው የነበረ ሲሆን ሌሎች ጋዜጦችን ደግሞ የቅንጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ራሳቸው ቢሮአቸው ድረስ እየሄዱ በማባበልና በመደለል ቢያንስ ከእኔ ጋር ምንም ዓይነት ቃለ-መጠይቅ እንዳያደርጉና ስለ እኔ በጎ ነገር እንዳይፅፉ አሣምነዋቸው ነበር፡፡ በመጨረሻው ወቅት ላይ ከእነሱ ትዕዛዝ ወጥተው የእኛን ሐሳብ ያስተናግዱ የነበሩት ሪፖርተርና ጥቂት የእንግሊዝኛ ጋዜጦች ብቻ ነበሩ፡፡

እነ ዶ/ር ብርሃኑ "ልደቱ ማንተም አላደርግም ብሎ ቅንጅቱን ሊያፈርሰው ነው" የሚለውን ቅስቀሳቸውን ለተወሰኑ ቀናት ካካሄዱ በኋላ "አቶ ልደቱና አቶ ሙሼ ከቅንጅቱ ታገዱ" የሚል መግለጫ በመስጠት አከታትለው ወደ ሌላ ይዘት ያለው አዲስ የአሉባልታ ዘመቻ ተሸጋገሩ፡፡ "ልደቱ ቤቱን ለቆ ሸራተን ማደር ጀመረ፣ ልደቱ ከሼክ አላሙዲን 17 ሚሊየን ብር ወሮታ ተቀበለ፣ ልደቱ ጥይት በማይበሳውና አንድ ሚሊየን ብር በተገዛ ኮብራ መኪና መሄድ ጀመረ" የሚሉ ዜናዎችን በጋዜጣና በተለያዩ ስልቶች በሕዝቡ ውስጥ አሠራጩ፡፡ በዚያን ወቅት ኢትኦጵን የመሰሉት ጋዜጦች በፊት ገጻቸው ላይ ብቻ ስለ እኔ በአንድ ጊዜ ከሦስት ያላነሰ ዜና ይዘው ይወጡ ነበር፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ዜና ለተወሰኑ ቀናት ካካሄዱ በኋላ ስሜ ብቻ ሳይሆን ሕይወቴም በፍጥነት እንዲጠፋ ስለፈለጉ "ሕዝቡ በቁጣ ተነሥቶ የልደቱን ቤት አቃጠለው፣ የልደቱ መኪና በሕዝብ በድንጋይ ተደበደበች፣ ልደቱ መንገድ ላይ በሕዝብ ተደበደበ፣ ልደቱ ፓርላማ እንዳይገባ 70 ሺ ሕዝብ ፈረመ" የሚሉ የፈጠራ ወሬዎችን በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ በአንድ ጊዜ እንዲዛመት አደረጉ፡፡ በነገራችን ላይ ልደቱ ፓርላማ እንዳይገባ ልደታ ወረዳ ውስጥ የ70 ሺ ሕዝብ ፊርማ አሰባስበናል በማለት በውጭ ለሚገኙት የቅንጅት ደጋፊዎች በኢንተርኔት ያሳወቁት ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ነበሩ፡፡ የሚገርመው በዚያ ወቅት

ምንም ዓይነት ፊርማ የማሰባሰብ ሥራ ያልተሞከረ ሲሆን በአጠቃላይም በ97ቱ ምርጫ በልደታና በቂርቆስ ወረዳዎች በመራጭነት የተመዘገበው የሕዝብ ቁጥር ከ60 ሺ. ያነሰ ነበር፡፡

እነ ዶ/ር ብርሃኑም ሆኑ ጋዜጦቹ በወቅቱ በእኔ ላይ እንዲህ ዓይነቱን ወሬ ማስወራት የፈለጉት ስሜን ከማጉደፍና እኔን በሕዝብ ዘንድ እንድጠላ ከማድረግ በላይ ከተቻለም ሕዝቡ በስሜት ተነሳስቶ መንገድ ላይ ጨፍጭፎ እንዲገለኝ ለማድረግ ጭምር ነበር፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነቱ "በሕዝባዊ ርምጃ" ስም ሰዎችን የማጥፋት አብዮታዊ ስልት የግራ ፖለቲከኞች ያደጉበትና የተካኑበት ስልት በመሆኑ በመገዳደል የፖለቲካ ሂደት ውስጥ የኖሩት የቀድሞዎቹ የኢህአፓ አባላት እነ ዶ/ር ብርሃኑ ይህንን ማድረጋቸው የሚያስደንቅ አልነበረም፡፡ የሚገርመው ለ120 ቀን ከበውኝ የከረሙት ደህንነቶችም የእኔና የአቶ ሙሼ ካዋንጅቱ መታገድ በይፋ ከታወጀና "ልደቱ ትግሉን ከድቶ ወያኔ ሆነ የሚለው" አሉባልታ በሕዝብ ውስጥ እውነት መስሎ መታመኑን ካዩ በኋላ ሙሉ በሙሉ ከአጠገቤ ጠፉ፡፡ እኔ ግን ይህ ሁሉ መዓት ሲወራ የተለመደው የዕለት ተዕለት ኑሮዬ ሳይለወጥ ቢሮ እየገባሁ እሰራና አርጌ መኪናዬን በሕዝብ መካከል እየነዳሁ ወንዝ ዳር ላይ የሚገኘው መኖሪያ ቤቴ እየገባሁ አድር ነበር፡፡ ቀኔ አልተቆረጠችም ነበርናም በወቅቱ ከሕዝብ ይቅርና ከማንም ግለሰብ ምንም ዓይነት ጥቃት በአካሌም ሆነ በሕይወቴ ላይ ሳይደርስብኝ አልፏል፡፡

በእኔ ላይ እየሆነ ባለው ነገር በደስታ መፈንደቅ የጀመሩት የኢህአዴግ ካድሬዎችም በበኩላቸው "ልደቱን የእኛ አደረግነው - እንግዲህ ምን ትሆኑ?" እያሉ በሕዝብ ውስጥ በሰፊው በማውራት አሉባልታውን እውነት የሚያስመስልና የሚያጠናክር ስልታዊ ዘመቻ ማካሄድ ጀመሩ፡፡ በርግጥ እነዚህ ከሁለት አቅጣጫ በእኔ ላይ የተከፈቱ ዘመቻዎች ርስ በርስ ተደጋግፈው በእኔ ላይ የተነዛውን አሉባልታ በሕዝቡ ውስጥ የማያጠራጥር እውነት አስመሰሉት፡፡ መጨረሻ ላይም ሌሎቹ የቅንጅት መሪዎች ታስረው እኔና ሌሎቹ የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች ሳንታሰር ስንቀር የእኔ አለመታሰር በእኔ ላይ ሲወራ ለከረመው አሉባልታ ሁሉ የእውነትነት ማረጋገጫ ሆኖ ቀረበ፡፡ ቀደም ሲል ሲወራ የነበረውን አሉባልታ በመጠኑ ይጠራጠሩ የነበሩ ሰዎች ሳይቀሩ "ልደቱ ሳይታሰር የቀረው በርግጥም ወያኔ ስለሆነ ነው" ብለው ለማመን ተገደዱ፡፡ በዙሪያዬ የነበሩ ዘመዶቼና ጓደኞቼም ማን እንደገደለኝ ሊታወቅ በማይችልበት ሁኔታ ሕይወቴን በሚያሳጣ አደጋ ውስጥ እንደሆንኩ በማወቅ በጭንቀት ተዋጡ፡፡ ለ14 ዓመት ጥርሴን ነክሼ ከታገልኩት ከኢህአዴግ በላይ ያለአግባብና ሳልጠይቃቸው በማይገባኝ ስም "ማንዴላ" እያሉ እየጠሩ ሊያመልኩኝ የደረሱ የራሴ ደጋፊዎችና አድናቂዎች ሳይቀሩ በአንድ ጊዜ "በገጀራ እንገለዋለን" እያሉ የሚዝቱብኝ ጠላታቸው አደረጉኝ፡፡ ቀድሞውንም የእኔን ትክክለኛ አቋም በውል ሳይገነዘቡ

የኢህአዴግ ተቃዋሚነቴን ብቻ በማየት በስሜት የወደዱኝ ሰዎች፣ በኋላም ላይ የያዝኩትን አቋምና አመለካከት በውል ሳይገነዘቡት በስሜት ጠላቶቼ ሆነው መቆምን መረጡ፡፡

በዚያን ወቅት አንድ ምሽት ላይ እቤቴ ስገባ የገዛ ታናሽ እህቴ የሚወራውን አሉባልታ መቋቋም ተስኗት ሰውነቷ እየተንቀጠቀጠና እንባ እየተናነቃት ፊቴ ላይ ቆማ ምን እንዳለችኝ እስካሁን  አስታውሰዋለሁ፡፡ "እባክህ አንተ ልጅ! ይህንን ማነተም የሚሉት ነገር ከፊታቸው ወስደህ ወርውርላቸው! ለራስህም ሆነ ለኛ ሕይወት እዘንልን" ነበር ያለችኝ፡፡ የሚገርመው ግን በዚያ ነፍስን አስጨናቂ በሆነ የሽብር ወቅት እኔ ብቻዬን አልነበርኩም፡፡ "በአቋምህ ፅና" የሚሉኝ ጓደኞቼና ወዳጆቼ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ በርካታ ከሃቁ ዝንፍ የማይሉ የኢዴአፓ-መድኅን አባላት ከጐኔ ነበሩ፡፡ በዚያ የአሉባልታ ዘመቻው አገሩን እንደቋያ እሳት ባጥለለበት ወቅት ከትግል ጓደኞቼ ውስጥ አንዱ የሆነው ሙሼ ሰሙ የተናገረው ነገር እስካሁን ድረስ ጆሮዬ ላይ ሲያቃጭል ይሰማኛል፡፡ "ልደቱ! ከ75 ሚሊየን ሕዝብ ጋር ነው የተጣላነው - ግን ሃቁ ከእኛ ጋር ነውና አትጠራጠር እናሸንፋለን" ነበር ያለኝ፡፡ በርግጥ በዚያን ወቅት እኔም ሆንኩ ሌሎቹ የኢዴአፓ-መድኅን በአቋማችን የፀናን አመራሮች የያዝነው አቋም ፓርቲያችን ከጣለብን ኃላፊነት አንጻር ሕጋዊ አቋም ብቻ ሳይሆን ለኢዴአፓ-መድኅንም ሆነ ለአጠቃላይ ትግሉ ደኅንነት የሚጠቅም ትክክለኛ አቋም እንደነበር ቅንጣት ያህል ጥርጥር ስላልነበረን ለእነ ዶ/ር ብርሃኑ ሴራ እንድንንበረከክ የሚያደርገን ምንም ነይነት ጭንቀትም ሆነ ብዥታ በውስጣችን አልነበረም፡፡ በእኛ ስሜት ውስጥ የነበረው እውነታ ይህ ቢሆንም በወቅቱ በተካሄደብን ከፍተኛ የአሉባልታ ዘመቻ ምክንያት ግን ሕይወታችን በከፍተኛ አደጋ ውስጥ ወድቆ እንደነበር መካድ አይቻልም፡፡

ቅንጅት እኔና አቶ ሙሼን ከቅንጅቱ አግጃለሁ የሚል ውሳኔ ይፋ ካደረገና ኢዴአፓ-መድኅንም ይህንን ውሳኔ ተከትሎ ራሱን ከቅንጅቱ ማግለሉን ይፋ ባደረገ ማግስት ቅንጅቱ ሊታመን በማይችል ፍጥነት ሕዝቡን የመኪና ጥሩንባ ከማጮህ ጀምሮ በቤቱ ውስጥ በመቀመጥ እንዲያምፅ የሚጠይቀውን ጥሪ ይፋ አደረገ፡፡ ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ እስከ ጥቅምት 98 ዓ.ም ድረስ እኛን በአመፀኝነት ሲከሱ የነበሩት እነ ዶ/ር ብርሃኑ እኛን ከቅንጅቱ አባረርን ካሉ በኋላ ግን ሕዝቡን ለአመፅ ለመጥራት የሁለት ቀን ትዕግሥት እንኳን አልነበራቸውም፡፡ በዚያ ሕዝቡ በከፍተኛ የፖለቲካ ውጥረት ውስጥ በነበረበት ወቅት ያለምንም ድርጅታዊ ዝግጅት የተጠራው አመፅም አቅጣጫውን በፍጥነት ቀይሮ በአጭር ጊዜ ለከፍተኛ የሕዝብ እልቂትና ለቅንጅት አመራሮች መታሰር ምክንያት ሆነ፡፡ እነ ዶ/ር ብርሃኑ እንደቀላል ነገር ተቻኩለው ያወጁት የሰላማዊ አመፅ ጥሪ እነሱ ሊቆጣጠሩትና ሊመሩት በማይችሉት ሁኔታ አቅጣጫውን እየቀየረ መምጣቱን ሲያዩ በቀስተ ደመና ስም "የአመፅ ጥሪው ላይ የለንበትም" የሚል በዶ/ር

ብርሃኑ እጅ የተፈረመ መግለጫ አውጥተው ለሕዝብ መበተን ጀምረው የነበረ ቢሆንም መልዕክታቸው በበቂ መጠን ለሕዝብ ከመድረሱ በፊት እነሱ እሥር ቤት ለመግባት በቁ፡፡

እነ ዶ/ር ብርሃኑ በዚያን ወቅት በትነውት የነበረው መግለጫ በብዙ መገናኛ ብዙኃን ላይ በተለያዩ ጊዜ ወጥቶ የታዩ ቢሆንም ቀስተ-ደመናዎች በውኀደት አንድ ሆነናል ካሉት ከቅንጅቱ ተለይተው በዚያን ወቅት ለምን እንዲህ ዓይነት መግለጫ ለመስጠት እንደቻሉ ግን እስካሁን ሲጠየቁ ሰምተን አናውቅም፡፡ ኋላ ላይ እንዴትና ለምን ቅንጅቱ በዚያ ፍጥነት ያን "ከገዥው ፓርቲ አባላት ጋር እሳት አትጫጫሩ" የሚል ጭምር የሰላማዊ አመፅ ጥሪ ለሕዝብ ሊያቀርብ እንደቻለ ከብዙ ጊዜ በኋላ ለመስማት እንደቻልነው ወደዚያ ዓይነቱ አደገኛና ችኩል ውሳኔ ቅንጅቱ የገባው በጣም በሚያስገርም ምክንያት ነበር፡፡ ይኸውም እነ አቶ ሙሼ ከቅንጅት ታግደዋል በተባልን ማግስት አንድ የቅንጅቱ አመራር አባል የሆነ ሰው ወደ ቅንጅቱ ቢሮ በድንገት በመሄድ "አንድ አዲስ መረጃ ይዤ መጣሁ" በማለት ለቅንጅቱ አመራሮች ይነግራቸዋል፡፡ መረጃው ምን እንደሆነ ሲጠየቅም "እነ ልደቱ ከኛ ቀድመው ነገ ሕዝቡን ለሰላማዊ አመፅ ለመጥራት እየተዘጋጁ መሆኑን ትክክለኛ መረጃ ደርሶኛል" ይላቸዋል፡፡ ወዲያውኑም የቅንጅቱ አመራሮች በሰሙት ነገር ይደናገጡና አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ አደረጉ፡፡

በዚያ ስብሰባ ላይ "በምንም ዓይነት ሁኔታ እነ ልደቱ ከእኛ ቀድመው ሕዝቡን ለአመፅ መጥራት ስለማይገባቸው እኛ ልንቀድማቸው ይገባል" ተብሎ ይወሰንና ዶ/ር ብርሃኑ ለሁለት ሳምንት ያህል ሲያዘጋጁት ነበር የተባለው የሰላማዊ አመፅ ጥሪ ምንም ዓይነት ውይይት ሳይደረግበት በዚያው ዕለት ለጋዜጦች እንዲላክ ተደርጐ በማግሥቱ ለኅትመት በበቁ ጋዜጦች ጥሪው ለሕዝብ ለመሰራጨት በቃ፡፡ እንግዲህ ያ አገር ይመራል ተብሎ ይጠበቅ የነበረው ቅንጅት የዚያ ዓይነት ጥሪ ለሕዝብ ያቀረበው በሰከነ ሁኔታ በተመከረበትና አፈፃፀሙና ውጤቱ አስቀድሞ ተጠንቶ ዝግጅት በተደረገበት ሁኔታ ሳይሆን በውሸት መረጃ ላይ ተመሥርቶ "እነ ልደቱን እንቅደማቸው" በሚል አሳዛኝ የሆነ ምክንያት ነበር፡፡

በነገራችን ላይ በምርጫው ሰሞን በቅንጅት መሪዎች ላይ ሊካሄድ ስለ ታሰበ የግድያ ሙከራ፣ የኢህአዴግ ከፍተኛ የጦር መኰንኖች እየኰበለሉ እንደሆነ፣ ኢህአዴግ በምርጫው ውጤት ተደናግጦ እየተፈረካከሰ ስለ መሆኑና ስለ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች በእነ ዶ/ር ብርሃኑ ጋዜጣ በአዲስ ዜና ላይ ይምጣ የነበረው ዜና ሁሉ ይገኝ የነበረው ለአርቲስት ደበበ እሸቱ ስልክ በመደወል ወሬ ከሚያቀብሉ ማንነታቸው ከማይታወቅ የቅንጅት ደጋፊ ነን ከሚሉ ሰዎች ነበር፡፡

በወቅቱ አርቲስት ደበበ በስልክ እንዲህ ዓይነቱን ወሬ በሰማ ቁጥር በየኰሪደሩ እየተንጐራደደ “ይህ መንግሥት አልቆለታል!” እያለ ማውራት ያስደስተው ነበር፡፡

የቅንጅት ደጋፊ የሆነው ሕዝብ ቅንጅቱ በዚህ ደረጃ የነበረበትን መሠረታዊ ውስጣዊ ድክመት ምንም ባላወቀበት ሁኔታ ቅንጅቱን እንደ አንድ ጠንካራና በአጭር ጊዜ ለመንግሥትነት እንደሚበቃ ኃይል አድርጐ ተመልክቶት ስለነበር ይኸ ኃይል ራሱንም ሆነ ትግሉን በአጭር ጊዜ አንኮታኩቶ መቀመቅ ሲያስገባውና የሕዝቡን ምኞት ውሃ ሲቸልስበት ሕዝቡ እንዲህ ዓይነቱ አደጋ የተፈጠረው በራሱ በቅንጅቱ ድክመት ነው ብሎ ራሱን ማሳመን አልቻለም፡፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ በእኔ ላይ ሲወራ የነበረውን የመሰሪዎች አሉባልታ ያለ ምንም አሳማኝ መረጃ እንደ እውነት በመቁጠር ብቻ ሕዝቡ የቅንጅቱን አደጋ ውስጥ የመግባት ተጠያቂነት ያለ አግባብ በእኔ በአንዱ ተራ ግለሰብ ላይ ሊወረውረው ፈለገ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## አሉባልታ ከቅንጅት ውድቀት ማግሥት

የቅንጅቱ መሪዎች እሥር ቤት ከገቡ በኋላ አብዛኛዎቹ አገር ውስጥ ይታተሙ የነበሩት ጋዜጦች ከሥራ ውጭ ስለሆኑ የእኔን ስም የማጥፋቱን ሥራ ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ የሚተላለፉ ሬዲዮ ጣቢያዎች ተረከቡት፡፡ በወቅቱ “ትንሣኤ” በመባል ይታወቅ የነበረው ከጀርመን አገር ወደ አገር ውስጥ ይሰራጭ የነበረው የቅንጅት ሬዲዮ ጣቢያ ከኢህአዴግም በላይ ቅንጅቱን ያፈረስኩትም ሆነ የቅንጅት መሪዎችን እየጠቆምኩ ያሳሰርኳቸው እኔ እንደሆንኩ አድርጐ በማቅረብ ሰፊ ቅስቀሳ ጀመረ፡፡ በውጭ አገር ሬዲዮ ጣቢያዎች የሚሠሩ እንደ አቶ አዲሱ አበበ የመሰሉት ጋዜጠኞችም ስልታዊ በሆነ መንገድ በእኔ ላይ የሚሠራጨውን አሉባልታ የማጠናከር ተግባር ላይ ተሰማሩ፡፡ በተለይም በአሜሪካን ድምፅ የአማርኛው ፕሮግራም የአድማጮች መድረክ ያለ ምንም ተጨባጭ መረጃ የእኔን ስም በማጥፋት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰዎች ሰፊ ሽፋን በመስጠት ዘመቻው በእኔ ላይ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ በዚያ የቅንጅት ሰዎች እየታደኑ ይታሰሩ በነበረበት ወቅት ማንነታቸው የማይታወቅ ሰዎች በየሬዲዮ ጣቢያው እንዲቀርቡ እየተደረገ ኢህአዴግ እነ ማንን ማሰር እንዳለበት በራሱ ማወቅ የሚያቅተው ድርጅት

ይመስል - “የቅንጅቱን ሰዎች ልደቱ ለወያኔ እየጠቆመ አስጨረሳቸው” የሚል ቅስቀሳ ለሕዝብ በሰፊው እንዲሠራጭ ተደረገ፡፡ በቅንጅት ውስጥ ምንም ዓይነት ኃላፊነት ያልነበራቸውን እነ አቶ ይስሃቅ ክፍሌን የመሰሉ ሰዎች በቪኦኤ ለቃለ-መጠይቅ እየተጋበዙ “ልደቱ ከቅንጅት ቢሮ በፖሊስ እንድንባረር አደረገን” በማለት ተናገሩ፡፡ በወቅቱ ግን የቅንጅት አመራሮች በታሰሩበት እለት በመንግሥት ከተዘጋው አንድ ቢሮ ውጭ ቅንጅት አዲስ አበባ ውስጥ ሌላ ሊዘጋ የሚችል ምንም ዓይነት ቢሮ አልነበረውም፡፡ ቢኖረውም ኖሮ መንግሥት የቅንጅትን ቢሮ ለመዝጋት የኔን ትብብር የሚፈልግበት ምንም ዓይነት ምክንያት አልነበረውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አቶ አዲሱ አበበ ምንም ዓይነት ተጨባጭ መረጃ ሳይኖረው ከአቶ ብርሃነ መዋ ጋር ቃለ መጠይቅ ባደረገበት ወቅት “ልደቱ የቅንጅት መሪዎች በመታሰራቸው አልጸጸትም ብሏል” በማለት በሃሰት ወነጀለኝ፡፡ በዚያው ሰሞንም እኔ ምንም ባልተጠየኩበት ሁኔታ “አቶ ልደቱ ቃለ-መጠይቅ ላለመስጠት ስልኩን ዘጋብን” ተብሎ በቪኦኤ ተነገረ፡፡ በአጠቃላይ በዚያ ሰሞንም ሆነ ከዚያ በኋላ በቪኦኤ እኔን በሚመለከት ይተላለፉ የነበሩ ዘገባዎች በጉላ ሁኔታ ሚዛናዊነት የጎደላቸው ነበሩ፡፡ በተለይም አቶ አዲሱ አበበ ሬዲዮ ጣቢያውን ልክ እንደ ግል ንብረቱ በመቁጠረ የእኔን ቃለ-መጠይቆች አዛብቶና ቆራርጦ በማቅረብ፣ በአድማጮች መድረክ እኔን በመደገፍ የሚቀርቡ አስተያየቶችን በማፈንና እኔን የሚቃወሙትን በሰፊው በማቅረብ ይፈጽም የነበረው ተግባር ከአንድ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሬዲዮ ጣቢያ ከሚሠራ ጋዜጠኛ ፈጽሞ የማይጠበቅ ነበር፡፡ በወቅቱ አቶ አዲሱ በቅንጅት ምክንያት በአገር ክህደት ወንጀል ተከሰው ከነበሩት ጋዜጠኞች መካከል አንዱ ስለነበር በቅንጅት ዙሪያ የነበረውን ሁኔታ የሚዘግብበት መንገድ እንደ አንድ በሥርዓቱ ተጠቂ የሆነ ሰው ነው እንጂ እንደ አንድ ነፃና ገለልተኛ ጋዜጠኛ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ችግሩ እንዲታረም የቪኦኤ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችን በተደጋጋሚ ያነጋገርኩ ቢሆንም “እንዲህ ዓይነት ችግር ቪኦኤ ውስጥ መኖሩን እናውቃለን፤ እንዲታረምም እናደርጋለን” ከማለት ተስፋ ያለፈ በወቅቱ ተጨባጭ መፍትሄ አልሰጡኝም፡፡ በርግጥ ከቅርቡ ጊዜ ወዲህ እኔን በሚመለከት በቪኦኤ ዙሪያ የነበሩ ችግሮች እየተሻሻሉ መጥተዋል፡፡ የሆኖ ሆኖ በግሌ አቶ አዲሱ አበበ የማይጠበቅ በደል ፈጽሞብኛል ብዬ ባምንም ቪኦኤ ሊደነቁ የሚገባና አገርን የሚጠቅሙ በርካታ በጎ ጎኖች አሉት ብዬ ስለማምን መቼም ቢሆን ለሬዲዮ ጣቢያውም ሆነ በውስጡ ለሚገኙት አብዛኛዎቹ ጋዜጠኞች ያለኝ አድናቆትና አክብሮት ጥያቄ ውስጥ ገብቶ አያውቅም፡፡ በጀርመን ድምጽ የአማርኛው ፕሮግራም በኩልም እንደ ቪኦኤ በከፋ መልኩም ባይሆን እኔን የሚጎዱ የተለያዩ ፕሮግራሞች ተሠርተዋል፡፡ በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የሬዲዮ ጣቢያው ወኪሎች ለአለፉት አራት ዓመታት (ከአንድ ቀን በስተቀር) ኢዴፓንም ሆነ እኔን የማነጋገር ፍላጎት

አልነበራቸውም፡፡ በአብዛኛው ቃለ-መጠይቅ የመደረግ ዕድል የምናገኘው ጋዜጠኛ ይልማ ኃይለ እየሱስ ወደ ኢትዮጵያ ለሥራ ሲመጣ ነው፡፡

በአንድ በኩል ይህ በቲያትር ወይም በፊልም ካልሆነ በስተቀር በገሃዱ ዓለም በአንድ ሰው ሕይወት ላይ ይደርሳል ተብሎ የማይገመት መዓት በእኔ ላይ በሬዲዮና በጋዜጣ ጭምር ሲወራ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱ ውስጥ በተፈጠረው ዓመፅ ምክንያት ያ-ሁሉ ብጥብጥና ግድያ ሲካሄድና የአዲስ አበባ ሕዝብ ለአሥር ቀናት ያህል ከቤቱ እንዳይወጣ ሲደረግ እንደማንኛውም ሰው እኔም የነበርኩት አዲስ አበባ ውስጥ ወንዝ ዳርቻ ላይ በሚገኘው መኖሪያ ቤቴ ውስጥ ነበር፡፡ በወቅቱ በቤቴ ውስጥ ከእኔ፣ ከታናሽ እህቴ፣ ከቤት ውስጥ ሠራተኞችንና ከሁለት ድንክ ውሻዎች በስተቀር ሰባራ ዱላም ይዞ ቤቴ በር ላይ የሚቆም ዘበኛ አልነበረኝም፡፡ በቤትና በተንቀሳቃሽ ስልኬ እየደወሉ "ቤትህ ድረስ መጥተን በገጀራ ልናርድህ ነው" በማለት የሚያስፈራሩ ያልታወቁ ሰዎች ስለነበሩ በዚያን ወቅት ቤቴ በሐዘን ድባብ የተዋጠ ነበር፡፡ ከአሁን አሁን ከየትኛውም አቅጣጫ ሰዎች መጥተው ሊገሉት ይችላሉ በሚል ስጋትም ወዳጅ ዘመዶቼ ሁሉ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ ነበሩ፡፡

አዲስ አበባ የተጀመረው አመፅ እየተጋጋለ በመጣበት አንድ ቀን ጧት ላይ የእኔ ቤት አጠገብ ላይ በድንገት የሰዎች እሪታና ጫጫታ ተከሰተ፡፡ ጫጫታውንና እሪታውን ተከትሎም የተኩስ እሩምታ መሰማት ጀመረ፡፡ በወቅቱ ከአሁን አሁን ሰዎች መጥተው ልደቱን ይገሉታል በሚል ጭንቀት ውስጥ የነበረች የቤት ውስጥ ሠራተኛችን ጫጫታውንና ተኩሱን እንደሰማች እንደ እብድ እየዘለለች እኔ ወዳለሁበት ክፍል በመግባት "ልደቱ! ልደቱ! ሊገሉህ መጡ! ሊገሉህ መጡ!" በማለት ፊቴ ላይ ወድቃ ተንፈራፈረች፡፡ በእኔ በኩል በማንኛውም ከፊቴ ያለ ደቂቃ እንደዚያ ዓይነት አደጋ በእኔ ሕይወት ላይ ሊከሰት እንደሚችል ርግጠኛ የሆንኩ ያህል ራሴን አሳምኜ ስለነበር ከተቀመጥኩበት ሳልንቀሳቀስ የሚመጣውን መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡ በወቅቱ ያን ጊዜ በሰላም ላልፈው አልችልም ብዬ በመገመት ኑዛዜዬን ሁሉ ጽፌ አስቀምጬ ስለነበር ጭንቀቴ ለእኔ መሞት ሳይሆን በዚያ ሁኔታ እኔን ለመቅበር ስለሚቸገሩ ቤተሰቦቼ ነበር፡፡ ነገር ግን ትንሽ ቆይቶ ጫጫታውም ተኩሱም ቆመ፡፡ በኋላ ላይ የቤት ውስጥ ሠራተኛችን ወጥታ የሆነውን ነገር ለማጣራት ስትሞክር ግርግሩ የተከሰተው የኛ ሰፈር ወጣቶች ከእኔ ቤት አለፍ ብሎ ከሚገኝ አንድ ድልድይ ላይ ጉማ አቃጥለው መንገድ ዘግተው ስለነበር እነሱን ለማባረር ከመጣ የፖሊስ ኃይል ጋር ግጭት ተፈጥሮ እንደነበር ለማወቅ ቻልን፡፡

በዚያ ብዙ ወጣቶች በየጉዳናው እየተገደሉ በነበረበት ወቅት ቅንጅትን ያፈረስኩትና የቅንጅት ሰዎችን እየጠቆምኩ የማሳስረው እኔ እንደሆንኩ በሬዲዮ የሰማ አንድ የዋህ የቅንጅት

ደጋፊ እኔን ቢገለኝ የሚያስደንቅ አልነበረም፡፡ ለእኔ በእንዲህ ዓይነቱ ስሜት ውስጥ ሆኖ ሊገለኝ የሚችል የዋህ ሰውም ብዙም ጥፋት አለበት ብዬ ለማመን ያስቸግረኛል፡፡ ትልቁ ጥፋትም ሆነ ወንጀል የእንዲህ ዓይነቱን የዋህ ሰው ስሜት ለመበከል ሆን ብለው የፈጠራ አሉባልታ ያሰራጩብኝ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ናቸው፡፡ በወቅቱ በቅንጅት ዙሪያ የነበሩ ሰዎች በእኔ ላይ ምን ያህል ክፋት የተሞላበት ደባ እንደፈፀሙብኝ ከእኔም በላይ ገዥው ፓርቲ የማወቅ ዕድል ስለነበረው ርኅራሄ ተሰምቶት ይሆናል እንጂ እኔን ለመግደል ቢፈልግ ኖሮ ከዚያ የተሻለ በጎ አጋጣሚ አልነበረውም፡፡ በቀይና በነጭ ሽብር ዘመን የግራ ፖለቲከኞች ሲያደርጉት እንደታየው በወቅቱ የቅንጅት መሪዎች በእጃቸው እንደ ኢህአዴግ ጠበንጃውና ሥልጣኑ ቢኖራቸው ኖሮ የእኔን በአንድ የትግል ግንባር ውስጥ አብሬአቸው ልሞት የተሰለፍኩትን ሰው ሕይወት ለማጥፋት ወደኋላ እንደማይሉም ጥርጥር አልነበረኝም፡፡ ከዚህ አንጻር ከሥልጣን እንዲወርድ ለዓመታት የታገልኩት ኢህአዴግ በዚያ ወቅት እኔን በሚመለከት የወሰደውን አቋም ሳስበው በሕይወቴ ብዙ ነገሮችን ቆም ብዬ እንዳስብና እንዳገናዝብ አስገድዶኛል፡፡

ጉዳዩን ከግል ደህንነቴ ጋር ብቻ አያይዠ እያየሁት ሳይሆን የቅንጅት ሰዎች በሆነ ተአምር ለመንግሥት ሥልጣን በቅተው ቢሆን ኖሮ እነሱን እየተቃወሙና እየተቹ የሚሠሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የግል ጋዜጦች በዚች አገር ህልውና ይኖራቸዋል ብዬ ለማሰብም እጅግ ስለሚከብደኝ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በእኔ በአንድ ቤጋ ላይ ያንን ያህል የፈጠራ ዘመቻ ሲፅፉ የከረሙት ጋዜጠኞች እነሱ የሚደግፉት መንግሥት ሥልጣን ይዞ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮን የመሰለ ጉልበት ያለው መገናኛ ብዙኃን በእጃቸው ቢገባ በኢትዮጵያ ዳግም “የፍየል ወጠጤን” እያዘመሩ ኢትዮጵያን ሩዋንዳ ሊያደርጓት አይችሉም ብዬ ለመገመት ስለሚቸግረኝ ነው፡፡ ምክንያቱም በቅንጅት መሪዎችም ሆነ በእነዚያ ጋዜጠኞች ኅሊና ውሰጥ ትንሽ የዴሞክራሲና የሰብአዊነት እንጥፍጣፊ ቢኖር ኖሮ እኔ በይፋ ኢህአዴግ ሆኜ ብገኝ እንኳ በምንም መመዘኛ እንዲህ ዓይነት ሕይወቴን አደጋ ውስጥ የሚከት ሴራ በእኔ ላይ ሊፈፅሙ ባልተገባ ነበር፡፡ እነዚህ ሕይወታችንን መሥዋዕት ለማድረግ ጭምር በአንድ የትግል ጐራ አብረናቸው የተሰለፍን ሰዎች ቀደም ሲል ያለፉበትን የጭካኔና የአብዮታዊነት ባህሪ ደብቀውት እንጂ ቀይረውት ሰላማዊ ትግሉን እንዳልተቀላቀሉ የተረዳነውም በዚያ ወቅት ነበር፡፡ ቀደም ብሎ በቅንጅቱ ምሥረታ ወቅት አንዳንድ ወዳጆቻችን “አብዮት ልጅዋን ትበላለች” የሚለው መፈክር እንደገና በእናንተ መጀመሩ አይቀርም እያሉ ሊመክሩን ሲሞክሩ ብዙዎቹ የአዴአፓ-መድኅን ሰዎች የዚያ ዘመን ፖለቲከኞች ስላልነበርን ደርሶብን እስከምናየው ድረስ አባባሉን ፈጽሞ ልንረዳው የምንችል አልነበርንም፡፡

የሚገርመው ብዙ ትልቅና ዐዋቂ ሰዎች አሉባት በሚባለው አገራችን የእኔ አቋም ትክክልም ይሁን ስህተት በፖለቲካ አመለካከቴ ምክንያት በእኔ ላይ እንዲህ ዓይነት ክብደቱን ለመገመት የሚያስቸግር በደል ሲፈጸም፣ አገሪቱ ውስጥ የሚኖር አንድም ታዋቂ ሰው "ልደቱ አመለካከቱ ምንም ይሁን ምን እንዲህ ዓይነት በደል ሊፈጸምበት አይገባም፣ ነውር ነው!" ብሎ እስካሁን በይፋ ለመናገር የደፈረ የለም፡፡ ቢያንስ በእኔ በአንዱ ግለሰብ ምክንያት "ድሮስ ከወሎዬ ምን ይጠበቃል" እየተባለ ምንም በደል ያልፈጸመ በሚሊየን የሚቆጠር የትውልድ አካባቢዬ ሕዝብ በዘረኝነት በይፋ ሲሰደብ፣ አንድም ኀሊና አለኝ የሚል ታዋቂ ሰውም ሆነ መገናኛ ብዙኃን "ኧረ ይኸስ ነውር ነው!" ብሎ ለመናገር ሲሞክር አልታየም፡፡ እኔ ለረዥም ዓመታት የታገልኩት በኢትዮጵያዊነቴና ለኢትዮጵያ ብዬ ቢሆንም ልደቱ "ተሳሳተ" ወይም "ክህደት ፈፀመ" ተብሎ ሲታሰብ ግን "ድሮስ ወሎዬ" ተብሎ በእኔ ሰበብ ሕዝብ ሲሰደብ በመስማቴ ውስጤ እጅግ ከማዘኑም በላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሴን በሌሎች ጫማ ውስጥ አስገብቼ የአገራችን ፖለቲካ ከሌላ አቅጣጫም ጭምር እንድመለከተው አስገድዶኛል፡፡ ይህ ሁሉ ለእኔ ኢህአዴግን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲና እንደ አንድ ሕዝብ ሁላችንም ያለንበትን ሁኔታ ቆም ብዬ እንድመረምርና ነባራዊ አመለካከቴን እንድፈትሽ አስገድዶኛል፡፡ ብዙ እንድማርም ረድቶኛል፡፡

በዚያ ሕዝቡ ከቤት እዳይወጣ ተከልክሎ በነበረበት የረብሻ ወቅት በከተማው ውስጥ ስለነበረው ሁኔታ በየሰዓቱ ከጓደኞቼና ከተለያዩ ወዳጆቼ ጋር እየተደዋወልኩ አወራ ነበር፡፡ ታዲያ በዚያ ወቅት በየጐዳናው እየተገደሉና እየታሰሩ ከነበሩት ሰዎች ጉዳይ በበለጠ ብዙ ሰዎች በየአካባቢው ትኩረት ሰጥተው ሲያወሩ የሚውሉት ስለ እኔ "ቅንጅትን ማፍረስና ወያኔ መሆን" እንደ ነበረ ጓደኞቼና ወዳጆቼ ይነግሩኝ ነበር፡፡ የሚገርመው ስለ እኔ ሥራዬ ብለው ያወሩ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች "ልደቱ ሸራተን ውስጥ እዬኖረ ነው ወይም ጥይት በማይበሳው የአንድ ሚሊየን ብር መኪና ታጅቦ እየሄደ ነው" ብለው ሲያወሩ ይደመጡ የነበረው ሌላ ሰው ነገረን ብለው ሳይሆን "በዓይናችን በብረቱ አየነው" እያሉ ነበር፡፡ እንዲያውም አንዳንዶቹ "የሸራተን ሠራተኞች ነን" እያሉ በየአካባቢው እየዞሩ ስለ እኔ ያወሩ የነበሩ ሰዎች "ሸራተን ውስጥ አልጋ የምናነጥፍለትና ምግብ የምናቀርብለት እኛ ነን" ከማለት ጀምሮ "17 ሚሊየን ብር ከሼክ አላሙዲን እጅ ቆጥሮ ሲረከብ በዓይናችን አይተናል" እያሉ ያወሩ ነበር፡፡ እኔን የሚገርመኝ እነዚህ የእኔን ስም ለመበከል ሆን ብለው የተሰማሩ ሰዎች የዚህ ዓይነቱን የፈጠራ ወሬ ማውራታቸው ሳይሆን የእነዚህን ሰዎች ወሬ ከቁምነገር ቆጥሮ የሚያዳምጠው ሰው መኖሩ ነበር፡፡ ሌላው ቢቀር እንዴት ተደርጐ 17 ሚሊየንን ያህል መኪና ሊሸከመው የሚከብድ ገንዘብ ሁለት ሰዎች አንድ ቦታ ላይ ቆጥረው ሊረካከቡ እንደሚችሉ እንኳን ጥያቄ የሚያነሳ ሰው

አልነበረም፡፡ በሚሰማው ነገር ትንሽ እንኳን ጥርጣሬ ተሰምቶት ለመሆኑ ልደቱ የሚሄድበት ጥይት የማይበሳው መኪና ቀለሙ ምን ዓይነት ነው? ብሎ ለመጠየቅም የሚሞክር ሰው አልነበረም፡፡

አንዳንድ ከአዲስ አበባ በብዙ ርቀት ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም ልደቱ በሕዝብ ተጨፍጭፎ መገደሉን ዘመድ ደውሎ ከአዲስ አበባ ነገረን እያሉ ያወሩ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ሟርት ሲሰሙ በመደንገጥ እየደወሉ ያነጋግሩኝ የነበሩ ወዳጆቼና ዘመዶቼ ብዙ ነበሩ፡፡ በዚያን ወቅት የአንዳንድ ሰዎች ክፋት ምን ያህል ጥልቀት ያለው እንደሆነ የተገነዘብኩበትን ሌላ አንድ ገጠመኝ ላጫውታችሁ፡፡ ከግንቦቱ ምርጫ ጀምሮ እስከ ጥቅምቱ ብጥብጥ ድረስ በአብዛኛው ስጠቀምበት የነበረው ተንቀሳቃሽ ስልክ በምርጫው ጊዜ የዘመቻ ሥራ ለመሥራት በርካታ ተንቀሳቃሽ ስልክ ያስፈልገን ስለነበር በዚያን ወቅት አንድ የቅንጅት ደጋፊ የሆነ ነገር ግን እኔ ከዚያ በፊት የማላውቀው ሰው ለጊዜው ያዋሰንን ስልክ ነበር፡፡ ያንን ስልክ ከምርጫ በኋላ ባለቤቱ ለጊዜው ስለማልፈልገው ተጠቀምበት ስላለኝና ስልክ ቁጥሩን በአድራሻነት ለብዙ ሰዎችና ጋዜጠኞች ጭምር ሰጥቼው ስለነበር በብጥብጡ ወቅት ጭምር ቤቴ ውስጥ ተቀምጬ እጠቀምበት የነበረው ያንን ስልክ ነበር፡፡ ብጥብጡ ቁሞ ከቤቴ ከመውጣቴ በፊት ያ ስልክ በድንገት ከአገልግሎት ውጭ ተደረገብኝ፡፡

በወቅቱ ስልኩ ለምን እንደተቋረጠብኝ ምክንያቱን ያላወቅኩ ቢሆንም የድሮውን ስልኬን ከፍቼ መጠቀም ጀመርኩ፡፡ ሰዎችም እኔን ለማግኘት ፈልገው በዚያ ቁጥር ለመደወል ሞክረው ስልኩ እንደማይሠራ ሲገነዘቡ በቀድሞው ስልኬ እየደወሉ ያገኙኝ ጀመር፡፡ ይህ በሆነ ከሦስት ቀን በኋላ አንድ ጓደኛዬ ደውሎ የተዘጋውን ስልክ አንድ ሰው አንስቶ እንዳነጋገረው ነገረኝ፡፡ እኔም የስልኩ ባለቤት መስመሩን ከእኔ ላይ አዘግቶ (ምን አልባትም ተሰረቅሁ ብሎ) ወደ ራሱ እንዳስመለሰው ስለገባኝ ሳይነግረኝ እንደዚያ በማድረጉ ብቻ አዝኜ ዝም አልኩ፡፡ የስልኩ ባለቤት መስመሩን መጠቀም ከጀመረ በኋላ ለአንድ ሳምንት ያህል ሰዎች እየደወሉ ልደቱን ፈልገን ነበር? እያሉ ሲጠይቁት፣ያ ሰውዬ "አይ ይህ ስልክ የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ስልክ ነው፣ ልደቱ ተውሶት ነበር አሁን ግን መልሶታል" በማለት መልስ ሲሰጥ ከረመ፡፡ የሚገርመው አንዳንድ ሰዎች ይህንንም አባባል ምንም ሳይጠራጠሩ እውነት ነው ብለው አምነው ነበር፡፡

ይህ ሁሉ የተቀነባበረና ተከታታይ የአሉባልታ ዘመቻ በእኔ ላይ ሲሰራ ከቅርብ ወዳጆቼና ጓደኞቼም በተጨማሪ እውነቱን ከመጀመሪያው የተረዱና ስለ እኔ ሆነው የሚከራከሩ በርካታ እኔ የማላውቃቸው ሰዎች በየአካባቢው ነበሩ፡፡ በተለይም የአገራችንን የፖለቲካ ባህል በደንብ የሚያውቁ ወይም ስለ ቅንጅት ሰዎች ማንነት በሆነ አጋጣሚ በቅርበት ለማዎቅ ዕድል

የነበራቸው፣ ወይም ከራሱ ከአሉባልታው የርስ በርስ ግጭት በመነሣት በእኔ ላይ የሚወራው ነገር ሁሉ ተራ ፈጠራ መሆኑን የሚረዱ በርካታ ሰዎች በየአካባቢው ነበሩ፡፡ በየቀኑ እየደወሉ “አይዞህ! በአቋምህ ፀንተህ ቀጥል፣ እኛም ከጐንህ ነን፣ ይህ ሁሉ አሉባልታ ለምን እንደሚወራብህ ገብቶናል” በማለት ሞራሌ እንዳይነካና ተስፋ እንዳልቆርጥ ያፅናኑኝና ይፀልዩልኝ የነበሩ ሰዎች በቁጥር ቀላል አልነበሩም፡፡ “ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው” እንደሚባለው አብዛኛው ሰው ግን በእኔ ላይ የሚወራውን አሉባልታ ለረዥም ጊዜ ደጋግሞ ከመስማቱ የተነሣ ልደቱ ትግሉን ከድቶ ወያኔ ሆነ ብሎ በርግጠኛነት አምኖ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በተለይም በጋዜጣና በሬዲዮ ውሸት የማይነገር መስሎ የሚታየው ግንዛቤው ዝቅተኛ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍል የሚባለውን ሁሉ ወዲያውኑ አምኖ በመቀበል እኔን በየአካባቢው ለማማትና ለመሳደብም ሆነ በእኔ ላይ ለማዘንና ለመዛት ብዙም ጊዜ አልወሰደበትም ነበር፡፡

የእኔ ስም እንደዚያ መጥፎና ከባድ አገራዊ አጀንዳ ሆኖ ሕዝቡን ሲያነጋግር በነበረበት ወቅት በእኔ ውስጥ የነበረውን ጽናትና ብርታት እንዴትና ከየት እንዳገኘሁት ግን እስካሁን ድረስ ለእኔ ለራሴም ዕንቆቅልሽ ይሆንብኛል፡፡ በእኔ ላይ እየሆነ ስለነበረው ነገር በውስጤ ምንም ዓይነት ንዴት፣ ፍርሀት፣ ቁጭትም ሆነ ፀፀት ሊታመን በማይችል ደረጃ ያልነበረ ቢሆንም በዚያ ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር እንደገና ተቀላቅሎ መኖር ግን ማንም ሰው ሊገምተው እንደሚችለው በወቅቱ ለእኔ ቀላል ወኔ የሚጠይቅ ውሳኔ አልነበረም፡፡ በርግጥ ሚስትና ልጆች የሌሉኝ ወንደላጤ መሆኔን እንደዚያን ወቅት ወድጄው አላውቅም፡፡ በተለይም በዚያ ትንሹም ትልቁም ስለ እኔ “ከሃዲነትና ቅጥረኝነት” ሲያወራ በነበረበት ወቅት ነፍስ ያወቁና ትምህርት ቤት የሚውሉ ልጆች ቢኖሩኝ ኑሮ ምን ያህል ነብሳቸው ልትሰቃይ እንደምትችል ሳስበው ብቸኝነቴን በምክንያት የሆነ ነው ብዬ የበለጠ እንድወደው አድርጐኛል፡፡ እህቶቼ፣ የቅርብ ዘመዶቼና ጓደኞቼ በእኔ ምክንያት ምን ያህል ስቃይ እንዳዩ ሳስበው፤ ሌላው ቀርቶ የክርስትና ልጄ የሆነው የ10 ዓመቱ አማኑኤል አማሪው የእኔን ስም ሰዎች ሲያነሱ በሰማ ቁጥር እንዴት በንዴት ከሰዎች ጋር ለመጣላት እንደሚፋጠጥ ስሰማ እኔ ወድጀና ፈቅጀ የሚመጣውን አደጋ ሁሉ በጸጋ ለመቀበል በገባሁበት ችግር ሌሎች ሲሰቃዩ እንደማየት ውስጤን ያደማው ነገር አልነበረም፡፡

ከአዲስ አበባው ብጥብጥ ፍጻሜ በኋላ ሕዝቡ ወደ መደበኛ ሕይወቱ ሲመለስ እኔም ወደ መደበኛ ሕይወቴ መመለስ ነበረብኝ፡፡ በዚያ ወቅት ከቤቴ ስወጣና ሕዝቡ በየመንገዱ ሲያዩኝና ሲያገኙኝ ምን ሊልና ሊያደርግ እንደሚችል በርግጠኛነት ባላውቅም ይህንን እውነታ በድፍረት ከመጋፈጥ የተለየ ምርጫም ሆነ ፍላጐት ግን አልነበረኝም፡፡ በርግጥ ራሱን በእኔ ቦታ አስቀምጦ ማሰብ ለሚሞክር ለማንኛውም ሰው በዚያን ወቅት ሕዝቡ ውስጥ እንደገና ተቀላቅሎ የተለመደ

ተራ ሕይወትን ለመቀጠል መወሰን ቀላል ውሣኔ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ በእኔ አእምሮ ውስጥ የሚንሸራሸረው ጥያቄ እንዴት ብዬ በሕዝቡ ውስጥ ልታይ ወይም ልንቀሳቀስ የሚል ብቻ አልነበረም፡፡ ይህንን ለማድረግ ፍላጐቱ ባይኖረኝ ኖሮ እንኳ የኢኮኖሚ አቅሜ ከዚያ የተለየ ኑሮ ለመኖር ስለማያስችለኝ ወደ ነበርኩበት ሕይወት መመለስ የምርጫ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ግዴታዬም ነበር፡፡

ሾፌር፣ አጃቢና ጉዳይ አስፈጻሚ መቅጠር፣ ጥቁር መስታወት ያለው መኪና መግዛትና ሰላማዊ በሚባል የሀብታሞች ሰፈር ቤት ገዝቼ ወይም ተከራይቼ መኖር የማልችል ድሀ እስከሆንኩ ድረስ ሕዝቡን በድፍረት ከመቀላቀልና  ሊሆን የሚችለውን ሁሉ በጸጋ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ለእኔ ከባዱ ጥያቄ እንደማንኛውም ተራ የአገሪቱ ዜጋ ጸጉሬን ለመስተካከል፣ አሮጌ መኪናዬን ለማስጠገን፣ ምግብ ቤት ገብቼ ለመመገብ፣ ታምሜ ለመታከምም ሆነ ሌሎች ለኑሮዬ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ለማግኘት ስሞክር የቀድሞ ደምበኞቼ ሳይቀር በዚያ ወቅት ስለ እኔ ምን እንደሚያስቡና እንዴት አድርገው ሊያስተናግዱኝ እንደሚችሉ በርግጠኛነት መገመት የምችልበት ሁኔታ አለመኖሩ ነበር፡፡ ይህንን በወቅቱ እኔ የነበርኩበትን አስቸጋሪ ሁኔታ አስቀድመው ለመገንዘብ የቻሉ በውጭ አገር የሚኖሩ ጓደኞቼና ዘመዶቼ ለጊዜው ወደ ውጭ አገር ሄጄ ጊዜውን እንዳሳልፈው ግፊት አድርገውብኝ የነበረ ቢሆንም በእኔ በኩል ግን ችግሩን በድፍረት ከመጋፈጥ በስተቀር ሌላ መፍትሄ ለማሰብም ሆነ በሽሽት መልክ ራሴን ለመደበቅ ዝግጁ አልነበርኩም፡፡

የሆነ ሆኖ ከቤታችሁ አትውጡ የሚለው የመንግሥት ትዕዛዝ ተነሥቶ መደበኛ ሥራ በተጀመረበት የመጀመሪያው ቀን ከቤቴ ወጥቼ ወደ ቢሮዬ ተጓዝኩ፡፡ ከተማው ከሰነበተበት አደጋ ገና በአግባቡ ያላገገመ መሆኑ በግልጽ ይታይ ነበር፡፡ በጎዳናው ላይ በዝግታ እየነዳሁ ስጓዝ ከግራም ከቀኝም የሚመለከተኝ አብዛኛው ሰው የሚያሳየኝ ስሜት መገረም፣ መናደድ ይሁን መደንገጥ ለመለዬት የሚያስቸግርና ግራ የሚያጋባ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች ጋር አይኔና አይናቸው በድንገት ሲገጣጠም ተደናግጠው ፊታቸውን የሚያዞሩ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ግራ በተጋባ ሁኔታ ፈገግ ብለው እጃቸውን ከፍ በማድረግ ሰላምታ ይሰጡኛል፡፡ አንዳንዱ ደግሞ የ20 ዓመት አሮጊት የሆነችውን መኪናዬን ያለ አጃቢ ብቻዬን እየነዳሁ ሲያዬኝ፣ ጥይት በማይበሳው የሚሊየን ብር መኪና ታጅቤ እንደምሄድ ከሰማው ጋር እየተጋጨበት ግራ በተጋባ ስሜት ውስጥ ሆኖ በመገረም ያየኛል፡፡

በዚህ ሁኔታ ተጉዤ ቢሮዬ ደርሼ ከመኪናዬ ስወርድ የሕንጻው ጠባቂዎች በጨዋ መንፈስ ተቀብለው ደህንነቴን ጠየቁኝ፡፡ ከነሱ ጋር ሰላምታ ተለዋውጬ ወደ ቢሮዬ ስሄድም የበሩ ቁልፍ

ተሰባብሮ በሌላ ተንጠልጣይ ቁልፍ ተቆልፎ አገኘሁት። የሕንጻው የጥበቃ ሠራተኞችም ከሳምንት በፊት ፖሊሶች የቢሮዬን በር ሰብረው ገብተው እንደነበርና መዛግብቱንና ኮምፒዩተሩን ጭነው እንደወሰዱት ነገሩኝ። የቢሮው ቁልፍ በፖሊስ እጅ መሆኑን እንደተረዳሁም በቢሮዬ አካባቢ በሚገኝና አዘውትሬ ወደምጠቀምበት አንድ ካፍቴሪያ ሻሂ ለመጠጣት ጉራ አልኩ። የካፌው ሠራተኞች በእውነት የሚያዩት እኔን መሆኑን የተጠራጠሩ በሚመስል፣ ነገር ግን በጨዋ ስሜት ተቀብለው ስለ ደህንነቴ አጥብቀው በመጠየቅ በአግባቡ አስተናገዱኝ። ከካፍቴሪያው ወጥቼ አስፓልቱ ዳር ላይ ጫማዬን እያስጠረግሁ ትንሽ ተቀመጥኩ። በጎዳናው ላይ አላፊ -አግዳሚው ሰው መንገድ ዳር ላይ ተቀምጬ ጫማዬን እያስጠረግሁ የሚያዩኝ ሰው እኔ (ልደቱ) መሆኔን ሲያረጋግጥ ድንግጥ -ይልና ወዲያውኑ አካባቢውን ተዟዙሮ በማስተዋል ይመለከታል። እንደምገምተው አካባቢውን ተዟዙረው የሚቃኙት ሰዎች የእኔ አጃቢዎች የት እንደቆሙ ለማየት በመፈለግ ነበር። ጫማዬን ካስጠረግሁ በኋላ ብሔራዊ ቲያትር፣ ፒያሳና አራት ኪሎ አካባቢ በዝግታ እየነዳሁ ተዘዋውሬ ሳበቃ ሂልተን ሆቴል ገብቼ ማኪያቶ እየጠጣሁ ትንሽ ጊዜ አሣለፍኩ። ከቤቴ ከወጣሁ ጀምሮ በዙሪያዬ ያየሁትን ነገር ሁሉ በመገምገምም ከእነ ችግሮቹዋም ቢሆን ሕይወት ጉዞዋን ልትቀጥል እንደምትችል ተገንዝቤ በጊዜ ወደ ቤቴ ተመልሼ በሰላም ገባሁ።

ከዚያ ዕለት ጀምሬ ከቀድሞ አኗኗሬ ምንም ባልተቀዬረ ሁኔታ የፀሐይ መነፅር እንኳን ማድረግ ሳያስፈልገኝ የዕለት -ተዕለት ኑሮዬን መምራት ጀመርኩ። ጸጉር ቤት፣ ምግብ ቤት፣ ሻይ ቤት፣ ገበያ፣ ጋራዥ፣ ነዳጅ ማደያ፣ ክሊኒክ፣ በአጠቃላይ ለኑሮዬ የሚያስፈልገኝን አገልግሎት የማገኝበት ቦታ ሁሉ እየሄድኩ ኑሮዬን በሰላም መቀጠል ቻልኩ። በወቅቱ ፊቱን አክፍቶ የተቀበለኝ አንድም የቀድሞ ደንበኛዬ የሆነ ሰው አልነበረም። እኔን ሲያዩ ግራ የሚጋቡ፣ የሚደነግጡ፣ የሚገረሙ ሰዎችና በውስጣቸውም የሚሰድቡኝና የሚረግሙኝ ሰዎች መኖራቸው ባያጠራጥርም ለእኔ ከሰው ኀሊና በላይ መንፈሳዊ ተአምር ሆኖ በሚሰማኝ መጠን እስካሁን ድረስ አንድም ሰው በአካሌ ላይ ጉዳት ለማድረስ ይቅርና ግልጽና ፊት ለፊት በሆነ ሁኔታ በድፍረት ኃይለ ቃልም ተናግሮኝ አያውቅም። ስልክ ደውለው ከሰደቡኝ ጥቂት ስሜታዊ ሰዎችና ከተማ ውስጥ መኪና እየነዳሁ ሳልፍ “አዬሽው ያን ሌባ” በማለት ከርቀት ሲናገሩ ካደመጥኳቸው ሁለት ሰዎች በስተቀር ፊት ለፊት ሊሰድበኝ እንኳ የሞከረ ሰው እስካሁን አጋጥሞኝ አያውቅም። እንዲያውም በሚገርም ሁኔታ በቁጥር ቀላል የማይባሉ ሰዎች ከዚያ የአሉባልታ ማዕበል ተርፈው “የበለጠ በጽናትህ ኮራንብህ” በማለት ሲያበረታቱኝ፣ “አይዞህ እውነት ቦታውን አይለቅምና ተስፋ እንዳትቆርጥ” እያሉ ሲያፅናኑኝ፣ “አድናቂዎችህ ነን” በማለትም

እንድፈርምላቸውና አብሬያቸው ፎቶ እንድነሳ ሲጠይቁኝ በሕይወት ተርፌ እንደገና ለማየት በቃሁ፡፡

በዚህም አገራችን ውስጥ ክፋትና መሰሪነት የጥቂት ሰዎች እንጂ የሕዝብ ባህሪ አለመሆኑን ፈጽሞ ሊያጠራጥር በማይችል ሁኔታ ከራሴ ተጨባጭ ሕይወት መረዳት ችያለሁ፡፡ አንዳንድ የቅንጅት አመራሮች በወቅቱ እግዚአብሔር ያስፈታችሁ ለማለት እሥር ቤት ድረስ ሄዶ የሚጠይቃቸውን ሰው ከራሳቸው መታሰር በላይ የእኔ በሰላም መኖር እያበሳጫቸው "ለመሆኑ ልደቱ በሕዝብ መሃል መንቀሳቀስ ይችላል?" ብለው ደጋግመው እንደሚጠይቁ ስሰማ በእኔ ሕይወት የታዬው ተአምር እኔን ብቻ ሳይሆን ክፉ የተመኘኋቸውን ሰዎች ጭምር የሚያስደንቃቸውና የሚያስተምራቸው መሆኑንም ተረድቻለሁ፡፡ ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ የልደቱ ነፍስ ከዚህ ሁሉ መዓት ተርፋ መቀጠል የቻለችበት አጋጣሚ ሊኖር አይችልም ነበር፡፡ የሚገርመው በምን ዓይነት ፈተና ውስጥ እንዳለፍኩ እኔ ራሴ በውል ተገንዝቤው አላውቅም፡፡ "ለካስ በከባድ ፈተናና በመከራ ውስጥ አልፌአለሁ?" ብዬ ራሴን የምጠይቀው ብዙውን ጊዜ ሰዎች በመንገድ ላይ አግኝተውኝ - "ለመሆኑ ቁመህ ትሄዳለህ? ፅኑ ሰው ነህ! እኔ አንተ ላይ የደረሰው ደርሶብኝ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ራሴን አጥፍቸ ነበር" በማለት መገረማቸውንና በፅናቴ መደነቃቸውን ሲገልፁልኝ ነው፡፡

ማርታ ጆሴፍ የምትባል የ13 ዓመት ካናዳዊ የአንድ ጓደኛዬ ልጅ በቅርቡ አገር ቤት ለጉብኝት መጥታ ነበር፡፡ አንድ ቀን ለአለፉት ሦስት ዓመታት በእኔ ላይ ስለደረሰው ሁሉ ተረኩላት፡፡ ማርታ በእኔ ላይ የደረሰውን ሁሉ ካዳመጠች በኋላ እንደኛ አገር ሰው ከንፈሯን በሐዘን ለመምጠጥ ወይም "እኔ ብሆን ራሴን አጠፋ ነበር" ማለትን አልፈለገችም፡፡ አንድ ከፍተኛ ሎተሪ እንደደረሰው ሰው እየተደሰተች "ልደቱ! ይህንን የሕይወት ታሪክህን ወደፊት ሆሊውድ ሄጀ በፊልም እንድሠራውና ሚሊዬነር እንድሆን ፍቀድልኝ" ብላ አሳቀችኝ፡፡ ይህ የማርታ አባባል በእውነትም በእኔ ላይ የደረሰው ሁሉ መጥፎ አጋጣሚ ሳይሆን ትውልድን ሊያስተምር የሚችል ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ አሣይቶኛል፡፡ በእውነትም ይህ ዓይነቱ አሰቃቂ ሁኔታ በእኔ ሕይወት ላይ ለምን ደረሰ ብዬ አንድም ቀን ለማማረርና ለመፀፀት ሞክሬ አላውቅም፡፡ "ሁሉም ነገር ለበጎ ነው" ይባል የለ---?

እንዲያውም ለአንባቢ ለማመን በሚያስቸግር መጠን ለአለፉት ሦስት ዓመታት ሕይወቴ ያለፈበትን ክስተት እንደ አንድ የወደፊት ታሪኬን ሊያሳምር የሚችልና በቀላሉ ተፈልጎ የማይገኝ ታሪካዊ ገጠመኝ አድርጌ ነው የምቆጥረው፡፡ አንድም ቀን ለምን እንዲህ ዓይነቱ በደል ያለ አግባብ በእኔ ላይ ደረሰ ብዬ ፈጣሪዬን አማርሬም ሆነ ተበሳጭቼ አላውቅም፡፡ ትግሉ ውስጥ

ገብቼ የወጣትነት ዘመኔን መሥዋዕት ካደረግሁ አይቀር ያመንኩበትን ሰርቼ በዚህ ዓይነቱ ሊረሳ የማይችልና ትርጉም ያለው የሕይወት ገጠመኝ ውስጥ ማለፌን በደስታ ተቀብዬዋለሁ። ደረጃው ቢለያይም ኢዴአፓ-መድኅን ውስጥ ያሉ የትግል ጓደኞቼ ሁሉ በዚህ ዓይነቱ ችግር ውስጥ ራሳቸውን አሳልፈዋል። ሙሼ፣ አብዱረህማን፣ መስፍን፣ ሶፊያ፣ ፅጌ፣ ነፃነት፣ እንዳለና ሌሎችም በአዲስ አበባና በየክፍላተ ሀገሩ የሚገኙ በርካታ አባሎቻችን ያለፉበትን መከራ ሲያወሩ በገጽታቸው ላይ የሚነበበው ስሜት ኩራትና በራስ መተማመን እንጂ ፀፀትና ቁጭት ሆኖ አያውቅም። ጉዳዩን በጥልቀት ልንመረምረው ከሞከርንም የአገራችን የፖለቲካ ሂደት በዚህ ዓይነቱ ምስቅልቅል ውስጥ ካላለፈ እንዲሁ በቀላሉ ለተሻለ ውጤት ሊበቃ አይችልም።

በርካታ የኢዴአፓ-መድኅን አባላት አምነውበት በያዙት የፖለቲካ አቋም ምክንያት ብቻ እንደ ወንጀለኛ ተቆጥረው በራሳቸው ዘመዶችና ጓደኞች ሳይቀር መገለልና መወገዝ ሲደርስባቸው፣ ከሥራ ቦታቸውና ከተከራዩበት ቤት ሲባረሩ፣ በማንም ፖለቲካ ምን ማለት እንደሆነ ግንዛቤው በሌለውና በሞቀ ቤቱ ተቀምጦ ለትግሉ አንድም ቀን አስተዋፅኦ ባላበረከተ ሰው ከሃዲና ቅጥረኛ እየተባሉ ሲወገዙና ሲተፋባቸው ከርመዋል። ይህ ሁሉ ግን ለእኔም ሆነ ለሌሎቹ የኢዴአፓ-መድኅን አባላት ብዙ ሰዎች ከሩቅ ሆነው እንደሚገምቱት "ለዚህ ዓይነቱ ሕዝብ መታገል ምን ይጠቅማል" ብለን ተስፋ እንድንቆርጥ ሳይሆን "የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ጉዳይ ከእስካሁኑ የበለጠ መራራ ትግልና መሥዋዕትነት ገና ያስፈልገዋል" ብለን እንድናምን ያደረገን ታሪካዊ አጋጣሚ ሆኗል። በርግጥ እንኳንስ እኛ በብዙ ሴራና ጥላቻ በጎደፈው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተዘፈቅነው ሰዎች ይቅርና - አገራችን ሸክ መሐሙድ አላሙዲንን የመሰለ ከ50 ሺ በላይ ለሆኑ ዜጐች የሥራ ዕድል የፈጠረና የበርካታ በሞት አፋፍ ላይ የነበሩ ዜጐችን ሕይወት የታደገ ሰው፣ ኃይሌ ገ/ስላሴን የመሰለ አገሩን በዓለም የአትሌቲክስ መድረክ ደግሞ ደጋግሞ በታላቅ ክብር ያስጠራና አገርና ሕዝብን በልማት እየረዳ የሚገኝ ጀግና ሰው፣ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅን የመሰለ ለሰላምና ለዕርቅ ታታሪ የሆነ አዛውንት ሰው የሚታማበትና የሚወገዝባት አገር ስለሆነች በእኛ ላይ የደረሰው ሃሜትና ውግዘት እምብዛም የሚያስደንቅ አይሆንም።

የአዲስ አበባው የጥቅምት ግርግር ከቆመ ከሳምንት በኋላ ኢዴአፓ-መድኅን የታሸገበትን ቢሮ አስከፍቶና አፀዳድቶ መደበኛ ሥራውን ጀመረ። በሚገርም ሁኔታ በርካታ የፓርቲው አባላት ነገሮች ወደፊት እንደሚለወጡ ርግጠኛ በሆነ ወኔና ኩራት "ዛሬም ኢዴአፓ-መድኅን ነን" በሚል ጽናት ትግላቸውን ቀጠሉ። ኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ ራሱን በይፋ ከማግለሉ በፊት አምኖበትም ባይሆን ለብዙኀኑ ድምፅ በመገዛት ፓርላማ ላለመግባት ከቅንጅቱ ጋር አብሮ ወስኖ

ስለነበር ሌሎቹ የቅንጅት ሰዎች እንዳደረጉት የቅንጅቱን ውሳኔ በቀላሉ ሽሮ ፓርላማ ዘሎ መግባትን አልመረጠም፡፡ ጉዳዩ ተገቢ ውሳኔ የሚጠይቅ መሆኑን በመገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፓርቲያችን ጠቅላላ ጉባዔውን በመጥራት አጠቃላይ ሂደቱን ከገመገመ በኂላ ፓርላማው ከተከፈተ ከሦስት ወር በኂላ ማለትም ፓርላማ ለመግባት የሚቻልበት የጊዜ ገደብ ሊቃጠል ሦስት ቀናት ብቻ ሲቀሩት ከቅንጅቱ ጋር ሆኖ የወሰነውን ውሳኔ በአግባቡ በጉባዔ ውሳኔ በመሻር ፓርላማ ገባ፡፡ ፓርቲው አዲስ አበባን ለመረከብ ያደረገው ጥረት ግን አብዛኛዎቹ ከሌሎቹ የቅንጅት አባል ፓርቲዎች በሕዝብ የተመረጡ ሰዎች የአሉባልታውን ጫና ተቋቁመው መቀመጫቸውን ለመረከብ ፈቃደኛ መሆን ስላልቻሉ ሳይሳካ ቀረ፡፡ ኢዴአፓ-መድኅን ፓርላማ በገባበት ወቅት እነ ፕሮፌሰር በየነ፣ ዶ/ር መረራና አቶ ቡልቻ ከሦስት ወር በፊት ፓርላማ ሲገቡ ምንም ስህተት መስሎ ያልታዬው ሰው ሁሉ "እነ ልደቱ ፓርላማ ገቡ" ብሎ እንደገና ሃሜትና አሉባልታውን መንዛት ጀመረ፡፡

በእኔ በኩል ገና ፓርላማ ለመግባት ከመወሰናችን በፊት ከቅንጅቱ በይፋ ከተለዬን በሁለት ወር ውስጥ በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረውን የአሉባልታና የአስተሳሰብ ምስቅልቅል በመጠኑም ቢሆን ለማስተካከል ይረዳ ይሆናል ብዬ በማሰብ "የአረም እርሻ"ን ጽፌ ለኅትመት አበቃሁ፡፡ መጽሐፉ ታትሞ ገበያ ላይ ሲውል ሐሳብን በሐሳብ ለመመከት አቅሙ ምን ጊዜም ቢሆን ኖሯቸው የማያውቀው በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ አክራሪ የቅንጅቱ ደጋፊዎች በሚያሳፍር ሁኔታ "የልደቱን መጽሐፍ እንዳታነቡ" የሚል ቅስቀሳ ጀመሩ፡፡ ጥላቻና ፖለቲካን መለዬት ያልቻሉ ደካማ ሰዎች እንደሚጠበቀው የአረም እርሻን ሳያነቡ የቀሩ ቢሆንም ሁሉንም ነገር አንብቦ ለመረዳት ፍላጎት የነበረው ምክንያታዊ የኅብረተሰብ ክፍል ግን የአረም እርሻን ተሻምቶ በማንበብ በቅንጅቱ ውስጥ ስለነበረው ሁኔታ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ቻለ፡፡

ከአረም እርሻ በተጨማሪም መስከረም 11 ቀን 98 ዓ.ም የተካሄደው የኢዴአፓ-መድኅን ጠቅላላ ጉባዔ በወቅቱ ቅንጅቱን አስመልክቶ የተወያዩባቸውንና የወሰናቸውን ውሳኔዎች በግልጽ የሚያሳይ የቪዲዮ ፊልም በአገር ውስጥና በውጭ አባዝተን በማሰራጨት በተወሰነ ደረጃ ሰዎች እውነቱን እንዲረዱት ለማድረግ ሞከርን፡፡ በርግጥ ያን ፊልምም አንዳንድ ሰዎች በካሜራ ቴክኒክ የተቀናበረ ቲያትር አስመስለው ለማስወራት ሲሞክሩ ታይተዋል፡፡ ከአረም እርሻ ጋር በተያያዘ በወቅቱ ኅብረተሰቡ የነበረበትን አመለካከት የሚያሳዩ የተወሰኑ ገጠመኞችን አስታውሳለሁ፡፡ አንዳንድ ሰዎች የእኔን መጽሐፍ ከገዙ በኂላ የእኔን መጽሐፍ እያነበቡ መሆናቸውን ሰዎች እንዳያውቁባቸው በመፍራት ሽፋኑን ገንጥለው ወይም በጋዜጣ ሸፍነው ያነቡ ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ መንገድ ላይ መጽሐፍ አዟሪዎች የእኔን መጽሐፍ እንዲገዙ ሲያሳዩዋቸው እኔ ላይ

ካደረባቸው የመረረ ጥላቻ የተነሣ ሰይጣን የታያቸው ያህል “በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!” በማለት ያማትቡ እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡ “የአረም እርሻን የፃፉት መለስ ዜናዊና ተፈራ ዋልዋ ናቸው” ተብሎ ሲዎራ በመስማትም መጽሐፌን ሳታነበው እንደቀረችም አንዲት ነርስ በቅርብ ጊዜ ለራሴ ነግራኛለች፡፡

ከሁሉም በላይ አስገራሚው ገጠመኝ ግን፣ አንድ ጓደኛዬ አንድ አዛውንት ወዳጁ እኔ በያዝኩት የፖለቲካ አቋም ከልባቸው እንደተቀዩሙ ስለሚያውቅ እውነቱን እንዲረዱት በማሰብ የአረም እርሻን ገዝቶ ይወስድላቸዋል፡፡ ሰውዬውም የመጽሐፉን ሽፋን በደንብ አገላብጠው ካዩ በኋላ “ባላነበው ይሻለኛል” ብለው መጽሐፉን ይመልሱለታል፡፡ ጓደኛዬም “ለምን?” በማለት አዛውንቱን ሲጠይቃቸው- “አይ - ልደቱ አደገኛ ጸሐፊና ተናጋሪ ስለሆነ መጽሐፉን ካነበብኩት ሊያሳምነኝ ስለሚችል ቢቀርብኝ ይሻላል” በማለት መልስ እንደሰጡት ነግሮኛል፡፡ በርግጥ አዛውንቱ ስሜታቸውን በግልጽ ተናገሩት እንጂ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ አፍጥጦ ከሚታዬው ሃቅ ራስን ሆን ብሎ በማሸሽ አንድ ጊዜ የያዙትን የተሳሳተ አቋም ለዘለዓለም ይዘው ለመቀጠል የሚፈልጉ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ በቁጥር ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡

በአሉታዊ ጐኑ እንዲህ ዓይነት ገጠመኞች የነበሩ ቢሆንም በአረም እርሻ ዙሪያ በርካታ በጎ ገጠመኞችም አይቻለሁ፡፡ አንድ አሜሪካን አገር የሚኖር የእኛን አቋም የተረዳ ሰው የአረም እርሻን በሙሉ በቃሉ ኢንተርኔት ላይ በማንበብ ብዙ ሰዎች እውነቱን እንዲረዱ ለማድረግ ሞክሯል፡፡ አንድ እኔን በአካል አግኝቶኝ የማያውቅ የአዲስ አበባ ነዋሪም የአረም እርሻን ካነበበ በኋላ ቀድሞ ይዞት የነበረውን የተሳሳተ አቋም በመቀየሩ ምክንያት ተደስቶ ከ200 በላይ መጽሐፍ በግል ገንዘቡ ገዝቶ የተሳሳተ አቋም ይዘዋል ብሎ ለሚገምታቸው ወዳጅ ዘመዶቹ ማደሉን አውቃለሁ፡፡

የሆነ ሆኖ እኛ ከምንናገረው በላይ ጊዜና ሂደት ወደፊት እውነቱን እያረጋገጠ እንደሚሄድ ርግጠኛ በመሆን ኢዴአፓ-መድህኖች እንደ በፊቱ ስለሚወራብን አሉባልታ መጨነቅን እርግፍ አድርገን በመተው ምክንያታዊ የፖለቲካ አቋማችንን የበለጠ አጠናክረን ቀጠልንበት፡፡ በእውነትም ሕዝቡ ቀስ በቀስ በቅንጅት መሪዎች ስህተት ምክንያት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረው ሰላማዊ ትግል በአንድ ጊዜ ተንኮታኩቶ በመውረድ እስረኛ የማስፈታት ትግል እየሆነ መምጣቱን በመገንዘብ በተወሰነ ደረጃ የእኛን አቋም የመረዳት አቅጣጫ ማሳየት ጀመረ፡፡ እኔም በቅንጅት የግርግር ፖለቲካ ምክንያት አከርካሪውን የተመታው የ14 ዓመት ትግላችን እንደገና አንሰራርቶ ወደነበረበት ለመመለስና የእኛን የሙሉ ጊዜ ተሳትፎ ለመጠዬቅ የራሱን ጊዜ እንደሚወስድ በመገንዘብ ዩንቨርሲቲ ገብቼ ለመማር ወሰንኩ፡፡

ከቅንጅቱ ከተለዩን ከ3 ወር በኋላ ራሴን አረጋግቼ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዲፓርትመንት በመግባት የማስተርስ ዲግሪዬን ለማግኘት የሙሉ ጊዜ ትምህርት ጀመርኩ፡፡ ያ -ሁሉ የአሉባልታ ዘመቻ በእኔ ላይ እየተካሄደ በነበረበት ወቅት በፖለቲካ ግርግርና ውጥረት በአገሪቱ ቁጥር አንድ ተብሎ በሚታወቀው ስድስት ኪሎ ዩንቨርሲቲ ገብቼ ሁለት ዓመት ተምሬ ለመመረቅ እስከምበቃ ድረስ አንድም የደረሰብኝ ችግር አልነበረም፡፡ የግቢው ተማሪዎችም እኔን ሲያዩ እርስ በርሳቸው ከመጠቃቀስ፣ ሲችሉም ጠጋ ብለው ስለ አጠቃላይ የፖለቲካው ሁኔታና በእኔ ላይ ስለሚወራው ነገር ጠይቆ ለመረዳት ከመሞከር ያለፈ መጥፎ ነገር አይቼባቸው አላውቅም፡፡ እንዲያውም አብረውኝ ይማሩ የነበሩ ተማሪዎች፣ መምህራኑና የዩንቨርሲቲው ሠራተኞች ያሳዩኝ የነበረው አክብሮት እኔን ራሴን የሚያስደንቀኝና ስለ ሰዎች የበለጠ አክብሮት እንዲኖረኝ ብዙ ያስተማረኝ ነበር፡፡

ጊዜና ሂደት ቀስ በቀስ በቅንጅቱና በኢዴአፓ-መድኅን ዙሪያ የነበረውን እውነት የበለጠ ግልጽ እያደረገው ቢመጣም አሉባልታን ዋና የፖለቲካ መሣሪያ አድርጐ የሚጠቀመው አውሬ ግን በቀላሉ ሽንፈቱን የሚቀበል አልነበረም፡፡ የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩ በኋላ ዶ/ር ብርሃኑ እኔን ዋና ገጸ-ባህሪ አድርገው ከጻፉት መጽሐፍ በተጨማሪ እኔን በሚመለከት ብቻ ሁለት መጽሐፍቶች ታትመው ለገበያ በቅተዋል፡፡ በዚህም በአገሪቱ ታሪክ ሦስት መጽሐፍ የተጻፈበት ብቸኛ የፖለቲካ ሰው ለመሆን ሳልበቃ አልቀረሁም፡፡ በነገራችን ላይ “ የልደቱ ባንዳዊ ስሌት” በሚል ርእስ ስለእኔ መጽሐፍ የፃፈው ማርቆስ እረታ የሚባል ሰው ሲሆን፣ ይህ ሰው በወሬ ደረጃ የወ/ሪት ብርቱካን ወዳጅ ነው ሲባል ከመስማት በስተቀር ስለ ሰውዬው ማንነት እስካሁን ምንም የማውቀው ነገር የለም፡፡ በአካልም አይቼው አላውቅም፡፡ “ማንነት ሲገለጥ” በሚል ርእስ ስለ እኔ መጽሐፍ የፃፈው ግን አቶ ታምራት ታረቀኝ የሚባል ለ14 ዓመታት ከእኔ ጋር አብሮ በትግሉ ውስጥ የቆዬ ሰው ሲሆን ይህ ሰው ይህንን መጽሐፍ በእኔ ላይ በጻፈ በሁለተኛው ዓመት የፓርቲ መረጃ በድብቅ እያወጣ በማቀበል ተወንጅሎ ከአንድነት ፓርቲ እንዲባረር ተደርጓል፡፡ ቀድሞ የኢህአፓ አመራር አባል የነበሩትና በኋላም ከእነ ዶ/ር ብርሃኑ ጋር ሆነው ኢትዮጵያ ውስጥ የግል ሬዲዮ ጣቢያ ለማቋቋም ጥረት ሲያደርጉ የነበሩት አቶ ክፍሉ ታደሰም በሚገርም ፍጥነት “ግንቦት 7” በሚል ርእስ ዋሽንግተን ዲሲ ባሳተሙት መጽሐፍ ዶ/ር ብርሃኑን ታላቅ የፖለቲካ መሪ፣ እኔን ደግሞ ለሥልጣን ብዬ ቅንጅትን ያፈረስኩ ሰው አድርገው ጻፉ፡፡

እኔን በሚመለከት ታትመው ከተሰራጩት መጽሐፍትና በተለያዩ ጋዜጦችና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ለንባብ ከቀረቡት ቁጥራቸውን ለመገመት ከማይቻለው በርካታ

መጣጥፎች በተጨማሪ እኔን ለማውገዝ ተብሎ የተዘጋጀ አንድ የሙዚቃ ክሊፕ፣ አንድ የትውልድ ቦታዬ የሆነውን ታሪካዊ ቦታ ላሊበላን ጭምር የሚያንቋሽሽ መንዙማና የተለያዩ በእኔ ላይ የሚሳለቁ ቀልዶች ታትመው ለሕዝብ ተሰራጭተዋል፡፡ በስሜ አንድ የተንቀሳቃሽ ስልክ የተሰዩመ ሲሆን እኔን የሚተቹ ዘፈኖች ጃንሜዳ በጥምቀት በዓል ላይና መስቀል አደባባይ በታላቁ ሩጫ ላይ ተዘፍነዋል፡፡ በነገራችን ላይ ከላይ የጠቀስኩት መንዙማ በማን እንደተዘጋጀ ባላውቅም የተሠራጨው ግን በአርቲስት ታማኝ በየነ አማካይነት ነበር፡፡ ታማኝ የማከብረው ወዳጅ ስለነበር ይህንን ለምን እንዳደረገ ልጠይቀውና ልወቅሰው በተደጋጋሚ ስልክ ብደውልለትም ሊመልስልኝ አልቻለም፡፡

ከእንደዚህ ዓይነቶቹ የጉሉ ጉዳዮች በተጨማሪም “ልደቱ ቅዳሜና እሁድ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከአቶ መለስና ከአቶ በረከት ጋር ግራውንድ ቴንስ ይጫወታል፣ ልደቱና መለስ ቤተ-መንግሥት ውስጥ ጫት ይቅማሉ፣ ልደቱ ታሞ መንግሥት ሳዑዲ ዐረቢያ በልዩ አውሮፕላን ልኮ አሳከመው፣ ልደቱ አዲስ ቪላ ቤት በ5 ሚሊየን ብር ገዝቶ ቦሌ እየኖረ ነው፣ ልደቱ በትልቅ ሰርግ ከአንዲት የትግራይ ልጅ ጋር ተጋባ፣ ልደቱ ለቅሶ ቤት ሄዶ ሰዎች አባረሩት፣ ልደቱ የተገኘበት ሠርግ ቤት ሰዎች አዳራሹን ጥለው ወጡ፣ ልደቱ አሹ የሚባል ሥጋ ቤት ለመመገብ ገብቶ ባለቤቱ እንዲወጣለት ጠዬቀው፣ የልደቱን እናት ሕዝቡ ቤተክርስቲያን እንዳትሳለም ከለከላት የሚሉና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው የፈጠራ ወሬዎች ለአለፉት ሦስት ዓመታት በእኔ ላይ ሲወሩ ከርመዋል፡፡ የሚገርመው እስካሁን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በእኔ ላይ ተወሩ ብዬ ከገለፅኳቸውና በግል ማስታወሻዬ ላይ በተለያዩ ጊዜ መዝግቤ ከያዝኳቸው ከ80 የበለጡ አሉባልታዎች ውስጥ በስህተት አንዱም እንኳን እውነትነት ያለው ሆኖ አያውቅም፡፡ የሚገርመው ግን ከዚህ ሁሉ ሂደት መማር ያልቻለውና ዛሬ ድረስ አንድ የአሉባልታ ነጠላ ዜማ በተለቀቀ ቁጥር እውነት ነው ብሎ ለመቀበል የማያቅማማው ሰው ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡

በእኔ ላይ በተወራው አሉባልታ ዙሪያ ስማቸው በጎላ ሁኔታ ሲጠቀስ የከረመውንና (መጠኑና ይዘቱ ቢለያይም) እንደኔው የመታማት ዕድል ያላቸውን ሸክ መሐመድ አላሙዲንንና አቶ ስብሃት ነጋን በምሳሌነት ብንወስድ ያ -ሁሉ አሉባልታ በሚወራበት ወቅት እነዚህን ሰዎች በአካል ለማወቅ የቻልኩበት ምንም ዓይነት አጋጣሚ አልነበረኝም፡፡ ከሸክ መሐመድ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ተገናኝተን ሰላምታ የተለዋወጥነው የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩ ከሁለት ዓመት በኋላ የሚለኒዬሙ በዓል አከባበር ብሔራዊ ምክር ቤት በይፋ በተቋቋመበት ዕለት አፍሪካ ኀብረት አዳራሽ ውስጥ በተካሄደው ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ በዚያ ስብሰባ ላይ ሸክ መሐመድና እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ስንገናኝ ሸክ መሐመድ “እስካሁን በቴሌቪዥን ላይ ነበር የማይህ፣ ደህና

ነህ ወይ?” ሲሉኝ በአካባቢያችን የነበረው ሰው ሁሉ ከዚያ በፊት የማንተዋወቅ መሆናችንን በመስማቱ ተገርሞ ርስ በርስ ተያዩ፡፡ የሚገርመው እስከ አሁን ድረስ የእኔና የሽክ መሐመድ ወዳጅነት እውነት መስሎ የሚታያቸው ብዙ ሰዎች ስላሉ ቢሮዬ ድረስ ቀጠሮ ይዘው እየመጡ ለተለያዩ ችግሮቻቸው ሽክ መሐመድን እንዳማልዳቸው የሚጠይቁኝ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡

እኔና አቶ ስብሃት ነጋም ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ተገናኝተን ሰላምታ የተቀያየርነው የቅንጅት መሪዎች ከታሰሩ ከአንድ ዓመት በኋላ የፈረንሳይ አምባሳደር ባዘጋጁት አንድ የኮክቴል ግብዥ ላይ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ከአቶ ስብሃት ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች በድንገት ተገናኝተናል፡፡ ከእነዚህ ድንገተኛ አጋጣሚዎች መካከል በቅርቡ የተገናኘነው ሸራተን ሆቴል በአንድ ስብሰባ የሻዪ ዕረፍት ላይ ነበር፡፡ በአጋጣሚ በዚያ የሻዪ ዕረፍት ላይ በአንድ ጠረንጴዛ ዙሪያ ሻዪ እንጠጣ የነበርነው እኔ፣ አቶ ስብሃት፣ አቶ ነቢዩ ሳሙኤልና ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ስለነበርን “አንች ልጅ - አቦይ ስብሃት ጋር ተገናኘሽ ተብለሽ የእኔ ዕጣ እንዳይደርስብሽ” በማለት ወ/ሪት ብርቱካንን ቀለድኳት፡፡ በዚያ አጋጣሚም እኔ፣ ወ/ሪት ብርቱካንና አቶ ስብሃት በአገራችን ስላለው የአሉባልታ በሽታ ትንሽ ተጨዋውተን ተለያዬን፡፡ የሚገርመው በዚያ የሻዪ ዕረፍት ላይ ሦስታችን አንድ ላይ ቁመን ስንጨዋወት በርካታ የነፃው-ፕሬስ ጋዜጠኞች አይተውን ስለነበር ፎቶግራፋችንን በማግስቱ ጋዜጣ ላይ እናዬዋለን ብዬ ጠብቄ ነበር፡፡ ነገር ግን የተገናኘነው እኔና አቦይ ስብሃት ብቻ ስላልነበርንና ወ/ሪት ብርቱካን በመካከላችን ስለነበረች ይመስለኛል ጋዜጠኞቻችን ዜናውን ሊጽፉት አልፈለጉም፡፡

ያ ሁሉ አሉባልታ በእኔ ዙሪያ ሲወራም እንኳን ሸራተን ማደርና ለአለፉት አሥር ዓመታት እሥር ቤት ስገባ ወይም ከአዲስ አበባ ስዎጣ ካልሆነ በስተቀር ከቤቴ ወጥቼ ለአንድም ቀን ሆቴልም ሆነ የሌላ ሰው ቤት ውስጥ ያደርኩበት ጊዜ የለም፡፡ ጥይት በማይበሳው የአንድ ሚሊየን ብር መኪና ታጅቤ መንዝም ይቅርና እንደማንኛውም ሰው እንደዚያ ዓይነቱ ውድ መኪና በከተማው ሲነዳ ከማየት በስተቀር እግር ጥሎኝ በተሳፋሪነትም እንኳ ውስጡ ገብቼ የማውቅበት አጋጣሚ የለም፡፡ ያኔም ሆነ ዛሬ የምነዳት መኪና የዛሬ ሃያ ዓመት የተፈበረከች ቶዮታ ኮሮላ ስትሆን ይህንን መጽሐፍ እስከጻፍኩበት ጊዜ ድረስም 280.500 ኪሎ ሜትር ተጉዛለች፡፡ የሚገርመው ዶ/ር ብርሃኑ ራሳቸው በጻፉት መጽሐፍ ውስጥ እሳቸው በምርጫው ወቅት ከኢህአዴግ ባለሥልጣናት ጋር መገናኘት ብቻ ሳይሆን ስለ ምርጫው ውጤት ከእነ አቶ በረከት ጋር አብረው እየጠጡ በውስኪ ይወራረዱ እንደነበረ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ

ወሬ በእኔ ላይ ሲዎራ (ያውም በሐሰት) ለምን በተለየ ሁኔታ ለሰዎች አስደንጋጭና ኃጢያት ሆኖ እንደሚታይ ሁልጊዜ ዕንቆቅልሽ ይሆንብኛል፡፡

ከቅንጅት ፖለቲካ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሰዎች ምን ያህል የአሉባልታ ልክፍት ይዟቸው እንደነበረ የሚያሳይ አንድ ሁለት ገጠመኞችን ላውራላችሁ፡፡ ከአንድ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች የሆኑና የተማሩ የሚመስሉ በርከት ያሉ ሰዎች በቡድን ላሊበላን ለመጐብኘት ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ከተማው ውስጥ የሚገኙ ቤተክርስቲያኖችን ከጐበኙ በኋላ ከላሊበላ 42 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን ይምርሃነ ክርስቶስ የተባለ ታሪካዊ ቤተክርስቲያን ለመጐብኘት ሚኒ ባስ ተከራይተው ይሄዳሉ፡፡ በጉዞ ላይ እንዳሉ መከረኛው የእኔ ጉዳይ የመወያያ ርእስ ሆኖ የጦፈ ወሬ ይጀመራል፡፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል የእለቱ ዋና የፖለቲካ ተንታኝ በመሆን የበላይነቱን ይዞ የነበረውና በሚኒ ባሱ ጋቢና ላይ የተቀመጠው ሰው “ልደቱን እኮ እኔ ከልጅነቱ ጀምሮ ባህር ዳር ከተማ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማር ነው የማውቀው፡፡ ከእኔ ጋር በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ አብረን ነው የተማርነው፡፡ በኋላም እንግሊዝ አገር ተመድቤ እየሠራሁ በነበረበት ወቅት ልደቱ ማስተርሱን ሊሠራ ለንደን መጥቶ ከእኔ ጋር እንገናኝ ነበር” በማለት ስለ እኔ ትግሉን መክዳት ርግጠኛ ሆኖ ያወራል፡፡ በአጋጣሚ በዚያን ሰዓት የሚኒባስዋ ባለቤትና ሾፌር የነበረው ሰው ከእኔ ጋር አብሮ ያደገ የቅርብ ጓደኛዬ ነበርና ልደቱን ከልጅነቱ ጀምሮ አውቀዋለሁ የሚለው ሰው የሚያወራውን ውሸት እሱ ምንም የማያውቅ መስሎ በዝምታና በትዕግሥት ሲያዳምጥ ይቆያል፡፡

ጉብኚዎቹ ያሰቡት ቤተክርስቲያን ደርሰው በተመስጦ ተሳልመውና ጸልዩው ወደ ላሊበላ ሲመለሱም ያ -ልደቱን አውቀዋለሁ የሚለው ሰው ተመሳሳይ ወሬ ማውራቱን ይቀጥልበታል፡፡ በዚህ ጊዜ መኪናዋን የሚነዳው የኔ የልጅነት ጓደኛ ስሜቱን ከዚያ በላይ መቆጣጠር ተስኖት መኪናዋን በድንገት ያቆምና “አንተ ሰውዬ አሁን ቤተክርስቲያን ተሳልመህ ከተመለስክ በኋላ እንኳን ውሸት ማውራትህን ብታቆም ምን አለበት! ልደቱ አንተ እንደምትለው ባህር ዳር ከተማ ተምሮ አያውቅም፡፡ ልደቱ ከእኔ ጋር በአንድ ወንበር ላይ ተቀምጦ አሁን አንተ በምትገኝበት እዚህ ላሊበላ ከተማ ነው የተማረው፡፡ አንተ እንደምትለው እንግሊዝ አገርም ለመማር ሄዶ አያውቅም፡፡ አሁን ላሊበላ ከተማ ስንደርስ አብረን ያደግንበትን ሰፈርም ሆነ ትምህርት ቤት ላስጐበኝህ እችላለሁ፡፡ በአንድ ሰው ላይ እንዲህ ዓይነት የሐሰት ዘመቻ ማካሄድ ምን ይጠቅምሃል?” በማለት በንዴት ይናገረዋል፡፡

በዚህ ጊዜ በሥራ ባልደረቦቹ ፊት ውርደት የደረሰበት ያ-ሰው የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ ትንሽ ለመከራከር ይወራጫል፡፡ ነገር ግን የጓደኛዬ አቀራረብ የሚያፈናፍን ስላልነበር

ሰውዬው ሃቁን አምኖ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አልነበረውም፡፡ ጓደኛዬን ይቅርታ ከጠዬቀው በኋላ “ወንድሜ! ምን ላድርግ ብለህ ነው - ሰው ሁሉ በልደቱ ላይ መናደዱን ሳይ እኔም እኮ የሱን ስም በማጥፋት ለአገሬ የምችለውን ያህል አስተዋፅኦ ላድርግ ብዬ ነው” በማለት የእኔን ስም ለማጥፋት እንደዚያ ተግቶ የሚሠራበትን ምክንያት ነገረው፡፡ እንግዲህ ይህ አገሪቱ በድህነት አቅሟ ያስተማረችው ዜጋ ሳይቀር ለአገሬ አስተዋፅኦ አበረክታለሁ ብሎ የሚያስበው የእኔን ስም በሃሰት በመበከል ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ሰው እየፈጸመው ያለው ድርጊት ከአንድ አገሬን እወዳለሁ ከሚልና ሃይማኖተኛ ነኝ ብሎ በየገዳማቱ ከሚዞር ሰው የማይጠበቅ ቢሆንም እኔ ግን አገርን እንመራለን ብለው ፓርቲ ያቋቋሙና ኅብረተሰቡ ብዙ እምነት የጣለባቸው አንቱ የሚሰኙ ሰዎች ከዚህ የበለጠ ብዙ አሳፋሪ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ እያየሁ የዚህ አንድ ዜጋ የሞኝነት ድርጊት ብዙም አላስደነቀኝም ነበር፡፡

ሌላው ከአንድ ዓመት በፊት ያጋጠመኝ፣ ኮልፌ አካባቢ አንድ ወዳጄ አዲስ ሆቴል መክፈቱን ሰምቼ ስለ ነበር ሆቴሉ ከተከፈተ ከአንድ ወይም ከሁለት ወር በኋላ አንድ ቀን አመሻሽ ላይ ከሌሎች ሁለት ጓደኞቼ ጋር ሆቴሉን እንይለት ብለን እንሄዳለን፡፡ ሆቴሉ ውስጥ ገብተን እራት ከበላን በኋላ ለዚያ ወዳጄ ሆቴሉን አድንቀንለት ወጣን፡፡ ምን አልባት በዚያ ሆቴል ውስጥ በግምት ከ45 ደቂቃ በላይ የቆዬን አይመስለኝም፡፡ ይህ በሆነ ከሦስት ወይም ከአራት ቀን በኋላ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ “ልደቱ ኮልፌ ሆቴል ከፈተ” ተብሎ መወራቱን አንድ ሌላ ወዳጄ ሰምታ ነገረችኝ፡፡ ይህ ወሬ በአጭር ጊዜ ተስፋፍቶ በአሁኑ ወቅት በአካባቢው የሚኖረው ሰው ሆቴሉን በርግጠኛነት የእኔ እንደሆነ አድርጐ ያምራል፡፡ አንዳንድ የሆቴሉ ደንበኞችም ትንሽ ጠጥተው ሞቅ ሲላቸው በክፉም ሆነ በበጎ ስሜት “የማን ቤት መሆኑን አውቀናል” ብለው እንደሚናገሩም ሰምቻለሁ፡፡

በዚያ የእኔ ስም የአገሩ መነጋገሪያ በሆነበት ወቅት ታናሽ እህቴ የገጠማት አንድ ገጠመኝ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭም ነበር፡፡ ይኸውም ታናሽ እህቴ በዚያ ክፉ ጊዜ በአንድ የግል የኢንሹራንስ ድርጅት  ተቀጥራ ትሰራ ነበር፡፡ ታዲያ ጧት ጧት ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ሆና ወደ መሥሪያ ቤት በሰርቪስ መኪና ስትሄድ የሰርቪሱ ሾፌር የሆኑት በዕድሜ ጠና-ያሉ ሰው የእህቴን ማንነት ስለማያውቁ በየቀኑ የእኔን ስም እያብጠለጠሉ መንዳት ይቀናቸው ነበር፡፡ ሽማግሌው ሾፌር በየቀኑ ስለእኔ የሚያወሩት ወሬ የፈጠራ ውሸት ቢሆንም ታናሽ እህቴ የሚናገሩትን በዝምታ ከማዳመጥ ውጭ ምንም ዓይነት አስተያየት ሰጥታ አታውቅም፡፡ ሽማግሌው ስለእኔ ማውራት የሱስ ያህል ሆኖባቸው ስለነበር አንድ ቀን በለመደ አፋቸው “ልደቱ እኮ አሣዳጊ ያልነበረው የድሀ ልጅ ነው፡፡ በልጅነቱ እኔ እረዳው ነበር” በማለት ይናገራሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ታናሽ እህቴ ትዕግስቷ ይሟጠጥና “አባባ! ለምን ዝም ብለው ሥራዎትን አይሠሩም” በማለት ትናገራቸዋለች፡፡ ሽማግሌውም በቁጣ “ምን ማለትሽ ነው?” በማለት ይጠይቋታል፡፡ እሷም “እርስዎ ትልቅ አዛውንት ነዎት፣ ከእርስዎ መማር ያለብን እውነትን እንጂ ውሸት መናገርን አይደለም፡፡ ስለ ልደቱ የሚናገሩት ሁሉ ውሸት ነው” አለቻቸው፡፡ ሽማግሌው ይህንን የእህቴን ንግግር ሲሰሙ በንዴት የሚነዱትን መኪና መሪ እየደበደቡ “አንቺ ደሞ የማነሽ ደፋር? እንዴት ውሸታም ብለሽ ትሰድቢኛለሽ? ለመሆኑ ልደቱን የት ታውቂዋለሽ?” በማለት ይጮሁባታል፡፡ እሷም ልደቱን ላውቀውም ላላውቀውም እችላለሁ፡፡ ነገር ግን እርስዎ ስለሱ የሚናገሩት ሁሉ ውሸት ስለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ፤ ከርስዎ ዓይነት ሽማግሌ እንዲህ ያለ ክፋት አይጠበቅም” በማለት በድጋሜ ትናገራለች፡፡ በዚህ ጊዜ አዛውንቱ ሾፌር በንዴት እየጮሁ እህቴን ብዙ ከሰደቧት በኋላ በመጨረሻ በከፍተኛ ምሬት ውስጥ ሆነው “መቼም ፈጣሪዬ የሱን ሞት ሳያሳየኝ አይገለኝም” በማለት ይናገራሉ፡፡ እህቴም “ቀድሞ የሚሞተውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ነው” ትላቸውና ጭቅጭቃቸው እዚያ ላይ ያቆማሉ፡፡ ይህ በሆነ በዐሥራ አምስተኛው ቀን ጧት ላይ ታናሽ እህቴ የመሥሪያ ቤቷ የማስታወቂያ ቦርድ ላይ አንድ ወረቀት ተለጥፎ ታያለች፡፡ ማስታወቂያውን ጠጋ ብላ ስታነበውም አዛውንቱ ሾፌር በህመም ምክንያት እንዳረፉና ቀብራቸውም በ9 ሰዓት እንደሚፈጸም አወቀች፡፡ እህቴ በህይወቷ ከነበሯት ገጠመኞች ሁሉ ይህ አጋጣሚ ለእሷ በጣም አስደንጋጭ እንደነበር አጫውታኛለች፡፡

ከአንዳንድ የትራፊክ ፖሊሶች ጀምሮ ልደቱን በማርቸዲስ፣ በቢ-ኤም ደብሊው፣ ወይም በኮብራ ቶዮታ “አሁን በዚህ እየነዳ ሲያልፍ አየሁት” ብሎ ሲያወራ የሚውለውን ሰው ብዛትማ ቤት ይቁጠረው፡፡ ከቅርብ ጓደኞቼ ጋር ምግብ ቤት ወይም ካፍቴሪያ ውስጥ ተቀምጬ የሚያዩኝ ብዙ ሰዎችም “ልደቱን ወፍራምና መላጣ ከሆኑ አጃቢዎቹ ጋር ሲጠጣ አዬነው” ብለው ማውራታቸው ሁል ጊዜ የተለመደ ነው፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ አትላንታ ውስጥ በአንድ ነዳጅ ማደያ ባለው ጓደኛዬ ድርጅት ውስጥ ለሁለት ሦስት ቀናት  ቆሜ በመታዬቴም “ልደቱ አትላንታ ውስጥ ነዳጅ ማደያ ገዛ” የሚለው ወሬ እኔን ቀድሞኝ ከአሜሪካ አዲስ አበባ ለመግባት የሳምንት ጊዜ አልፈጀበትም ነበር፡፡

ልንማርበት እንችላለን ብዬ በማሰብ የአሉባልተኞችን ጉዳይ የበለጠ አጉልቼ ለማሳየት ሞከርኩ እንጂ በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ጤናማና ቅን አስተሳሰብ ያላቸው በርካታ ዜጐችን ማዬቴን ዘንግቼው ግን አይደለም፡፡ እኔን በአካል ሳያውቁኝ እንደ ራሳቸው ጉዳይ ስለ እኔ ሆነው በያሉበት ሲከራከሩ የሚውሉና “ልደቱዎች” የሚል ቅፅል ስም የወጣላቸው በርካታ ሰዎች በየአካባቢው እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ስለእኔ የተቀኙልኝ፣ በየመገናኛ ብዙኀኑ በውጭም በአገር

ውስጥም ሽንጣቸውን ገትረው የተከራከሩልኝ፣ ልጆቻቸውን በእኔ ስም እስከ መጥራት የደረሱና በእኔ ምክንያት ከቅርብ ወዳጆ ዘመዶቻቸው ጋር እስከመጣላት የደረሱ ብዙ የዓላማ ወዳጆች አሉኝ። ሁሉም የቅርብ ወዳጆቼና ጉረቤቶቼ በዚህ የመከራ ወቅት ከጐኔ በመቆም ከልብ አኩርተውኛል። በውጭ አገር ኗሪ የሆኑ ጓደኞቼ እንደሌሎች የፓርቲያችን የቁርጥ ቀን ደጋፊዎች ኢዴአፓ-መድኀን በገንዘብ እጥረት እንዳይዘጋ በመርዳት ከከፈሉት መሥዋዕትነት በተጨማሪ የእኔን የግል ሕይወት በገንዘብ በመደገፍ ረገድ የዋሉልኝን ውለታ ባሰብኩ ቁጥር ስለ ሰው ልጅ ክብርና ስለ እውነት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ መሞት ቢቻል ተገቢ መሆኑን አስተምሮኛል።

በዚህ ባሳለፍኩት አስቸጋሪ ሂደትም የሰዎች አስተሳሰብና አቋም እንጂ እውነት ቦታዋን እንደማትለቅ በገሃድ አይቻለሁ። የሚገርመው ዶ/ር ብርሃኑ ከእሥር ከተፈቱ ከአንድ ዓመት በኂላ ለንደን ላይ በአንድ ስብሰባ ላይ ተገኝተው "በርግጠኛነት ልደቱ ወያኔ ነው ብለህ ታምናለህ ወይ?" ተብለው ተጠይቀው ነበር። ሁልጊዜም ፖለቲካን የአራዳነት ጨዋታ አድርገው የሚመለከቱት ዶ/ር ብርሃኑ ለዚህ ጥያቄ የመለሱት መልስ "ልደቱን ወያኔ ነው ያለው ሕዝቡ ነው እንጂ እኛ መቼ አልነው?" የሚል ነበር። ይህ መጽሐፍ በረቂቅ ደረጃ ተጠናቆ በእርማት ላይ እያለም ፕሮፌሰር መስፍን አሜሪካን አገር በሚገኝና "አንድ ኢትዮጵያ" በሚባል የአማርኛ ሬዲዮ ጣቢያ "ልደቱ ወያኔ ነው ስለመባሉ ምን አስተያየት አለዎት?" ተብለው ተጠይቀው ነበር። ፕሮፌሰር መስፍን ለዚህ ጥያቄ የሰጡት መልስ "ልደቱ ወያኔ ስለመሆኑ ማንም ሰው ተጨባጭ መረጃ አቅርቦ አያውቅም። ሰዎች በልደቱም ላይ ሆነ በሌሎች እንዲህ እያሉ የሚያስወሩት የሰዎችን ስም ለማጥፋትና በሕዝብ ለማስጠላት ነው" የሚል ነበር። ነገር ግን ፕሮፌሰር መስፍን በውጭ አገር ለሚደመጥ ሬዲዮ ጣቢያ ይህንን ስለ እኔ የተናገሩትን ሃቅ አገር ውስጥ ለሚገኘውና በማንም በላይ እውነቱ ሊነገረው ለሚገባው ሕዝብ በግልጽ ለመናገር ሲደፍሩ አልታየም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ቀድሞ የኢዴአፓ-መድኀን አመራር አባል የነበሩትና በኂላ ላይ ቅንጅት መሆን መርጫለሁ ያሉ አንድ ሌላ ሰውም ከአንድ ዓመት በፊት በአንድ በውጭ አገር በሚገኝ የኢንተርኔት መገናኛ ብዙኃን ቀርበው በውጭ ነዋሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ጋር ሲወያዩ "ለመሆኑ ልደቱ ወያኔ ነው የሚባለውን ነገር እርስዎ ያምኑበታል ወይ?" ተብለው ተጠይቀው ነበር። ይህ አንቱ የተሰኙ ሰው ለዚህ ጥያቄ ሊሰጡት የፈለጉት መልስ "አምናለሁ" ወይም "አላምንም" የሚል አልነበረም። የእርሳቸው መልስ "ልደቱ ወያኔ ነው የተባለው መቼ ነው? እኔ ሰምቼ አላውቅም" የሚል ነበር። ይህንን ያህል ዓመት ባልተቋረጠና ግልጽ በሆነ ሁኔታ በእኔ

ላይ የተካሄደውን የአሉባልታ ዘመቻ የቅንጅት አመራሮች አድበስብሰው ሊያልፉት የሚሞክሩ መሆናቸው በራሱ የሚያስደንቅ ቢሆንም፣ አንድ ለሰዎች መብትና ነፃነት እታገላለሁ የሚል የፖለቲካ መሪ የአንድ የሌላ የፖለቲካ መሪ ስም ያለ አግባብ ሲበከል በዝምታ ማየት በራሱ ትልቅ ስህተት መሆኑን እነዚህ ሰዎች አለመገንዘባቸው ግን የሚገርም ነው፡፡

በእኔ ላይ ሲወራ የከረመውን አሉባልታ ሰዎች እውነት አድርገው እንዲቀበሉና አእምሮአቸውን ከፊት አድርገው ምክንያታዊ ሆነው እንዳያስቡ የበለጠ ያስገደዳቸው የቅንጅት መሪዎች መታሰር ነበር፡፡ በሕዝቡ ውስጥ የነበረውና - “የቅንጅት መሪዎች ለስል ሕይወታቸው ምንም ሳይጉልባቸው ለእኛና ለአገር ሲሉ እሥር ቤት ገቡ” የሚለው የሕዝቡን አስተሳሰብ እጅግ ጠንካራ ስለነበር ብዙ ሰዎች በእኛ ዙሪያ ያለውን እውነት ለመስማማት ፈጽሞ ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ የቅንጅቱ መሪዎች ከታሰሩ በኋላ የአገሪቱ ፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢዴአፓ-መድኅንም ሆነ የእኔ እውነት አብረው እሥር ቤት ገብተው ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እነሱ እሥር ቤት ሆነው ስለ ቅንጅት መሪዎች ስህተትና ድክመት መነጋገር ይቅርና ስለ ወቅታዊም ሆነ ስለ ወደፊት የአገሪቱ የፖለቲካ ዕጣ-ፈንታ ለመወያየት መሞከር የሚቻል አልነበረም፡፡ ምክንያታዊ ፖለቲካ ማውራት እስካልተጀመረ ድረስ ደግሞ ሕዝቡ በቅንጅት ዙሪያ የነበረውን እውነታ በውል ተረድቶ የወደፊቱን አቅጣጫ በተሻለና በተለየ ሁኔታ ማሰብ እንዲችል ማድረግ የሚቻልበት ሌላ መንገድ ስላልነበረ እኔም ሆንኩ ኢዴአፓ-መድኅን አቅምና ሁኔታው በፈቀደልን መጠን በፓርላማ ውስጥ በሚደረግ ክርክር፣ ከዲፕሎማቶችና ከሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ጋር በምናደርገው ውይይትና በመገናኛ ብዙኃን በምንሰጣቸው መግለጫዎች ከማንም በላይ ለትግሉና ለራሳችን ስንል የቅንጅት መሪዎች ከእሥር እንዲፈቱ የበኩላችን ጥረት አድርገናል፡፡

እኛም ሆን ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች በወቅቱ ስለ ቅንጅት መሪዎች ስናቀርበው የነበረው ክርክር “ሰዎቹ የፖለቲካ እስረኞች ስለሆኑ የፖለቲካ መፍትሄ ሊሰጣቸውና ሊፈቱ ይገባል” በማለት የነበረ ቢሆንም መጨረሻ ላይ ግን ይህንን የኛንም ሆነ የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች አቋም ውድቅ በሚያደርግና በሚቃረን ሁኔታ የቅንጅት መሪዎች ኢህአዴግ ይል እንደነበረው ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ ወንጀል መሥራታቸውን በማመንና በመፀፀት መንግሥትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠዬቃቸው ይፋ ሆነ፡፡ ይህ የቅንጅት መሪዎች የይቅርታ ጥያቄ ከማንም በላይ ከምርጫው በኋላ በንፁሃን ዜጐች ላይ በተፈጸመው የግድያ ርምጃ ኢህአዴግን ከተጠያቂነት ነፃ የማውጣት ጥቅሙ የበለጠ ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ግን የቅንጅት መሪዎች የመጨረሻ ውጤት ጥፋትን አምኖ ይቅርታ መጠዬቅ ሆኖ መጠናቀቁ ኢዴአፓ-መድኅን ከመጀመሪያው ከነሱ በተቃራኒ ቅንጅቱ እንዲሄድበት መርጦት የነበረው ስልት

ምን ያህል ትክክለኛና የተሻለ እንደነበር የሚያረጋግጥ ሆኗል፡፡ ስለዚህ የቅንጅቱ መሪዎች ከእሥር ቤት መውጣት - ማለትም መፈታታቸው እነሱን ብቻ ሳይሆን በእነሱ ምክንያትም ታስሮ የነበረውን የፖለቲካ ትግል አብሮ እንዲፈታ ስለሚያደርገው፣ ከዚያ በተጨማሪ ይቅርታ መጠዬቃቸው ከራሳቸው የወደፊት የፖለቲካ ህልውና አንጻር የሚያስከትለው መዘዝ ከባድ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የእኛን አቋም ትክክለኛነት ከማረጋገጥ አንጻር ግን ትልቅ ፋይዳ ስለነበረው መፈታታቸው በእጅጉ አስደስቶናል፡፡

ከእውነቱ ሁልጊዜ ራሳቸውን ማሸሽ የሚፈልጉት የቅንጅቱ አክራሪ ደጋፊዎች የይቅርታ ጥያቄውን እንዳልተጠዬቀ አድርገው ሊያድበሰብሱት ሞክረው የነበረ ቢሆንም የቅንጅት መሪዎች “ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር” በሚል አድራሻ በጻፉት ማመልከቻ በተነሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውን አምነው በመቀበል መንግሥትንና ሕዝብን በፊርማቸው ይቅርታ የጠየቁበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ ተደርጐ ከእሥር ቤት በይቅርታ ተለቀቁ፡፡ በዚያም ወቅት የይቅርታ ጥያቄውን ለማድበስበስ የሞከሩ በርካታ ሰዎች ሳይቀሩ ቀደም ሲል እኛን እንደጥፋተኛ ይቆጥሩ የነበሩ የቅንጅት መሪዎች የመጨረሻ ውጤት ይቅርታ መጠየቅ መሆኑን እዬቆዩ ሲገነዘቡ የእኛን ትክክለኛነት ከማመንም አልፈው በድፍረት ይቅርታ ጠይቀውናል፡፡

ኢዴአፓ-መድኅን የቅንጅት መሪዎች መፈታትን አስመልክቶ የተሰማውን ደስታ በጋዜጣዊ መግለጫ ባሳወቀበት ወቅትም ከይቅርታ ጥያቄው ጋር በተያያዘ ከጋዜጠኞች ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ምንም ስህተት ሳይሰራና ሳያጠፋ በቅንጅት ሰዎች የውሸት ውንጀላ ከፍተኛ በደል የደረሰበት ኢዴአፓ-መድኅንም ይቅርታ ቢጠየቅ ተገቢ መሆኑን ገልፆ ነበር፡፡ የቅንጅት መሪዎች የኢህአዴግ መንግሥትን ምሕረት አድርግልን ብለው ይቅርታ ሲጠይቁ አይቶ እንዳላዬ አድበስብሶ ለማለፍ የሞከረው ጭፍንና እውነትን በድፍረት አምኖ መቀበል የማይችለው ደጋፊያቸው ኢዴአፓ-መድኅን እንዴት ይቅርታ ልጠዬቅ ይላል በማለት እንደገና እኛን ለመተቸት ሞከረ፡፡ እነዚህ የቅንጅት ደጋፊዎች ለግለሰቦች ዝናና ክብር ሳይሆን ለአገርና ለትግሉ ጥቅም የሚቆረቆሩ ሃቀኛ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ኢዴአፓ-መድኅንን እንዴት ይቅርታ ልጠዬቅ ይላል ብለው ከመተቸት ይልቅ በቅንጅት መሪዎች የሃሰት ውንጀላ ተታለው ኢዴአፓ-መድኅንን ያለ አግባብ ሲወነጅሉ በመክረማቸው እነሱም ጭምር ከልብ ተፀፅተው ይቅርታ ሊጠይቁት በተገባ ነበር፡፡ ሌሎች እውነተኛ የአገሪቱና የትግሉ ተቆርቋሪ የሆኑ ሰዎች ግን መሳሳታቸውን በትክክል ሲገነዘቡ ማንም ሳይጠይቃቸው ይቅርታ ከመጠየቅ ወደኋላ አላሉም፡፡

በአጭሩ ምርጫውን ተከትሎ በተፈጠረው ችግር አብዛኛው ሰው ሲደግፍም ሆነ ሲቃወም የሚታየው በተጨባጭ ምክንያት አልነበረም፡፡ በተለይም የቅንጅት አክራሪ ደጋፊ የነበረው

የኅብረተሰብ ክፍል ራሱ እንደ አንድ ደጋፊ የቅንጅቱን ማንነት፣ ጥንካሬና አካሄድ ይገመግምበት የነበረው መንገድና ምክንያት በስህተት የተሞላ ስለነበር ይህንን የራሱን ስህተት አምኖ ላለመቀበል በመፈለግ ብቻ በአይኑ አፍጥጦ የሚያዬውን ሃቅ ሁሉ ለመካድ ሲሞክር ታይቷል፡፡ ምክኒያቱ ይህ ባይሆን ኖሮ ማንም የተወሰነ የማመዛዘን አቅም ያለው ሰው ቢያንስ ዛሬ ላይ ሆኖ ቅንጅትና ኢዴአፓ-መድኀን ያራመዱትን አቋም በአግባቡ መለስ ብሎ ለመረዳት ሊሳነው ባልቻለ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የቅንጅት መሪዎች እንደ ሃቀኛና ትክክለኛ፣ የኢዴአፓ-መድኀን መሪዎች ደግሞ እንደ ከሃዲና ስህተተኞች ተደርገን ስንታየ የቆየነው ከዚህ በታች በዝርዝር በምናያቸው ጉዳዮች ሕዝቡ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዞ ስለነበር ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ኢዴፓ
ኢዴፓ
ኢዴፓ

## ምዕራፍ ስድስት

## አሉባልታ ያደበዘዛቸው ሃቆች

በዚህ አሉባልታ ገኖ የሁሉም ነገር ገዥ በሆነበት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ በሚገኘው ኅብረተሰብ ዘንድ ኢዴአፓ-መድኅን ያላግባብ ጥፋተኛ ተደርጐ እንዲታይ ያደረጉ በርካታ ምክንያቶች ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት - ኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ ራሱን ሲነጥል ሕዝቡ የመነጣጠሉ ችግር የተፈጠረው በኢዴአፓ-መድኅን ትዕግስት ማጣት ወይም ኢዴአፓ-መድኅን ከትግሉ ደኅንነት ይልቅ የራሱን የድርጅትና የሥልጣን ጥቅም በማስቀደሙ ነው ብሎ  በማመኑ ነበር፡፡ ይህ የሕዝብ ግንዛቤ እውነት ወይም ትክክል ቢሆን ኖሮ የቅንጅት መሪዎች ከእሥር ቤት ከወጡ በኋላ ከሁለት ሳይሆን ከሰባት ባልተከፋፈሉ ነበር፡፡ የኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ የመነጠል ችግር የተከሰተው ሕዝቡ እንደገመተው በልደቱ እና በጓደኞቹ አስቸጋሪነት ቢሆን ኖሮ ቀሪዎቹ የቅንጅቱ መሪዎች ያውም በአንድ እሥር ቤት ውስጥ ለሁለት ዓመት አብረው ከኖሩና የበለጠ ከተዋወቁ በኋላ ከእሥር ቤት ሲወጡ ከመከፋፈል ይልቅ አብረው በቀጠሉ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢዴአፓ-መድኅንን በጋራ ሆነው ሲያጠቁት የነበሩት ሰዎች እውነተኛ ባህሪያቸው ተደብቆ የማይቀር በመሆኑ ኢዴአፓ-መድኅን ከውስጣቸው ከወጣ በኋላም በተለመደው ባህሪያቸው የበለጠ ስብእናቸውንና ክብራቸውን በሚያሳጣ መጠን ርስ በርስ ሲናቆሩና ሲበታተኑ ታይቷል፡፡ በእኛ ላይ ተባብረው ያወጅዋት “አብዮት ልጅዋን ትበላለች”

ዘመቻ እንደ ዕቁብ ቀስ በቀስ ለሁሉም እየተዳረሰች እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በገሃድ አይቷል፡፡ ስለዚህ ከመጀመሪያው መለያዬቱ የተፈጠረው በኢዴአፓ-መድኅን ምክንያት ሳይሆን በእነዚህ ሰዎች መሰሪና አምባገነናዊ ባህሪ ስለመሆኑ በአሁኑ ወቅት ራሳቸው እያሳዩት ከሚገኙት ተጨባጭ ድርጊት በላይ ለሕዝቡ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ሁለተኛው ሕዝቡ ኢዴአፓ-መድኅንን ጥፋተኛ አድርጐ ይፈርድ የነበረበት ምክንያት በቅንጅት አባል ድርጅቶች መካከል ውኅደት ከተፈጸመ በኋላ ኢዴአፓ-መድኅን ያለ አግባብ አፈንግጧል ብሎ በማመኑ ነበር፡፡ ከላይ ቀደም ብዬ ለመግለፅ እንደሞከርኩት የቅንጅት አባል ድርጅቶች ውኅደት ለመፈጸም የሚያስችለንን ስምምነት ተፈራረምን እንጂ ውኅደቱን በተግባር መፈጸም ቀርቶ ገና በአግባቡ እንኳ ሥራውን ሳንጀምር ነው የተለያዬ ነው፡፡ ይህንን ከመጀመሪያው ጀምሮ ስንናገር ሊያምነን የፈለገ ሰው ባይኖርም ዛሬ ግን ይህ አባባላችን እውነት እንደነበር ማንም ሰው እኛን መጠዬቅም ሆነ ማመን ሳያስፈልገው የቀድሞው የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች በአሁኑ ወቅት ምን ላይ እንደሚገኙ ብቻ በማየት እውነቱን መረዳት ይቻላል፡፡

ይኸውም እኛ ከቅንጅቱ ከተነጠልን በኋላ አብረው ይሠሩ ከነበሩት ሦስት ድርጅቶች ውስጥ መኢአድና ኢዴሊ አሁን እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት እንደ ኢዴአፓ-መድኅን ሁሉ በቀድሞው የፓርቲያቸው ዕውቅናና ስያሜ ነው፡፡ “አራቱ ፓርቲዎች ውኅደት ፈጥረዋል - ከዚህ በኋላ ኢዴአፓ-መድኅን የሚባል ፓርቲ ሊኖር አይችልም” እየተባለ ይነገር የነበረው እውነት ቢሆን ኖሮ ዛሬ በኢንጂነር ኃይሉ የሚመራው መኢአድም ሆነ በዶ/ር አለማዬሁ አረዳ የሚመራው ኢዴሊ ሕጋዊ ዕውቅና ኖሮአቸው ሊሠሩ አይችሉም ነበር፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች አሁን በመኢአድና በኢዴሊ ስም እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት ተዋሕደው ጠፉ የተባሉትን ፓርቲዎቻቸውን እንደገና ፈጥረዋቸው ሳይሆን ቀድሞውንም እንደ ኢዴአፓ-መድኅን ሁሉ የእነሱም ህልውና በእጃቸው የነበረ በመሆኑ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ በሁለት ተከፍሎ በዶ/ር ብርሃኑና በወ/ሪት ብርቱካን የሚመራው ቀስተ ዳመና ከየፓርቲያቸው አፈንግጠው ወይም ተባረው ከነሱ ጋር የቆሙ ሰዎችን ስሜት ለመጠበቅ ሲባል አዲስ ስም አውጥተው መጠቀምን ስለ ፈለጉ እንጂ እስከ አሁን ድረስ ቀስተ ዳመና የሚባለው ፓርቲ በምርጫ ቦርድ ሕጋዊ ዕውቅናው አልተሰረዘም፡፡

ከዚህ የምንረዳው ሕዝቡ ውኅደት ተፈጽሞ እንደነበረና ኢዴአፓ-መድኅን የሚባል ፓርቲ ሊኖር እንደማይችል ሲነገረው የነበረው ሁሉ ኢዴአፓ-መድኅንን ያለ አግባብ ለማጥፋት ሲደረግ የነበረ ሴራ እንጂ እውነትነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ “ውኅደት ተፈጥሯል” ይባል የነበረውን ፈጠራ እንተወውና ከሰኔ 97 ዓ.ም ጀምሮ የቅንጅቱ መሪዎች እስከታሰሩበት ጊዜ ድረስ

ራሱ ቅንጅት የሚባል ፓርቲ በስሜት እንጂ በተግባር አልነበረም፡፡ ለዚህም ነው በኋላ ላይ እነ አቶ አየለ ጫሚሶ ቅንጅት የሚባል አዲስ ፓርቲ በቀላሉ ማቋቋም የቻሉት፡፡ እነ አቶ አየለ ቅንጅት በሚል መጠሪያ አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም ሲጠይቁ በወቅቱ በቅንጅት ስም በምርጫ ቦርድ የተመዘገበ ሌላ ፓርቲ ቢኖር ኖሮ ስያሜውን ለእነ አቶ አየለ ለመፍቀድ የሚያስችል የሕግ ክፍተት አይኖርም ነበር፡፡ የሁለት ጣት ምስል የሆነውን የምርጫ ምልክትም ኢዴአፓ-መድኅን ይዞ እንዲቀጥል የተደረገው በ97ቱ ምርጫ የቅንጅት አባል ሆነው ለምርጫ ከተወዳደሩት አራት ፓርቲዎች ውስጥ በ2000 ዓ.ምቱ የአካባቢ ምርጫ መወዳደር የቻለውና ምልክቱን በዚያ ወቅት በባለቤትነት ለመጠየቅ ብቸኛ መብት የነበረው ኢዴአፓ-መድኅን ስለሆነ ነው፡፡ መኢአድና ኢዴሊ እንዲህ ዛሬ በድሮው ስማቸው መጠራታቸው ላይቀር በ2000 ዓ.ምቱ የአካባቢ ምርጫ በስማቸው ቀርበው የምርጫ ምልክቱ ለእኛም ይገባናል የሚል ጥያቄ አቅርበው ቢሆን ኖሮ ኢዴአፓ-መድኅን በተለየ ሁኔታ ምልክቱን የሚያገኝበት ዕድል ባልኖረው ነበር፡፡ በአጠቃላይ በየትኛውም ምክንያት ኢዴአፓ-መድኅንን የተፈጸመን ውንደት ያለአግባብ እንዳፈረሰ አድርጐ መውቀስ የሚያስችል ምንም ዓይነት አሳማኝ ምክንያት የለም፡፡ በሆነ ተአምር አራቱ ፓርቲዎች ውንደት ፈፅመዋል ከተባለም መወቀስ ያለበት ኢዴአፓ-መድኅን ብቻ ሳይሆን ሁሉም በአሁኑ ወቅት በየፊናቸው የተበተኑት ፓርቲዎች ናቸው፡፡

ሦስተኛው ሕዝቡ ኢዴአፓ-መድኅንን ጥፋተኛ አድርጐ እንዲፈርድበት ምክንያት ሆኖ ይቀርብ የነበረው ጉዳይ ፓርላማ የመግባትና ያለመግባት ጉዳይ ነው፡፡ ቅንጅት በወቅቱ ፓርላማ ላለመግባትም ሆነ አዲስ አበባ መስተዳድርን ላለመረከብ የወሰነው ውሳኔ ከሦስት ዓመት በፊት አከራካሪ ነበር ሊባል ቢችልም በአሁኑ ወቅት ግን ውሳኔው ትክክል ነበር ብሎ ብዙም በድፍረት የሚከራከር ሰው ስለማላይ በውሳኔው ትክክል መሆንና አለመሆን ላይ ብዙ መናገር አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ ነገር ግን ኢዴአፓ-መድኅንን ፓርላማ ገባ ብለው እንደ ከሃዲና አላዋቂ ይወቅሱት የነበሩ ሰዎች ክርክራቸው ቢያንስ በአሁኑ ወቅት ውሃ ሊቋጥር እንደማይችል ሁለት ምሳሌዎችን በመጥቀስ ለማስረዳት ልሞክር፡፡

ኢዴአፓ-መድኅንን ፓርላማ ገባ ብለው ሲያጥላሉ የነበሩት የቅንጅቱ አባል ድርጅቶች በሙሉ ወደፊት በአገራችን በሚካሄደው ምርጫ ለመሳተፍ በአሁኑ ወቅት ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ሲገልፁ እየሰማን ነው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች ወደፊት በምርጫ የሚወዳደሩት ለሌላ ጉዳይ ሳይሆን በሕዝብ ተመርጠው ፓርላማ ለመግባትና የተለያዩ የክልል ምክር ቤቶች ውስጥ ለመግባት ነው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች ዞሮ ዞሮ ትግሉን ወደፊት የሚቀጥሉበት መንገድ ራስን ለምርጫ በማቅረብ ከሆነ ፓርላማ አንገባም የሚልን ውሳኔ በመወሰን አምስት ዓመት ከማባከን

ይልቅ ያኔውኑ ፓርላማ ለመግባትና አዲስ አበባ ምክር ቤትን ለመረከብ ወሥነው ቢሆን ኖሮ ትግሉ ዛሬ ወደ አንድ ከፍተኛ ደረጃ ይሸጋገር እንደነበር አጠራጣሪ አይደለም፡፡ አዲስ አበባ መስተዳድርን በእጃችን ይዘን በሙሉ ኃይላችን ፓርላማ ገብተን ቢሆን ኖሮ በአሁኑ ወቅት እንነጋገር የነበረው ስለመንግሥት ለውጥ እንጂ ስለ ምርጫ መሳተፍና አለመሳተፍ አይሆንም ነበር፡፡ በተለይም ቅንጅት የአገራችን ርእሰ-ከተማ የሆነችውንና የአገሪቱ 75% የሚሆነው የተማረና ባለሀብት የሆነው ሕዝብ የሚኖርባትን አዲስ አበባን ተረክቦ ቢሆን ኖሮ ከድርጅት ጥንካሬ አንጻር ዛሬ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርስ የነበረ ከመሆኑም በላይ ቢያንስ ስብሰባ ለማድረግ ይፈቀድልኝ እያለ አዲስ አበባ ላይ ኢህአዴግን ደጅ መጥናቱን ያቆም ነበር፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ኢህአዴግ ስብሰባ ለማካሄድ የፈቃድ ጥያቄ የሚያቀርበው ለቅንጅት ይሆን ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቅንጅት አዲስ አበባን መረከቡ ቢያንስ ከአዲስ አበባ ሕዝብ ጋር በቀላሉ ለመገናኘት የሚያስችለው የራሱ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያ እንዲኖረው ያስችለው ነበር፡፡

የቅንጅት መሪዎች ሁለት ዓመት ታስረውና ትግሉንም የበለጠ አዳክመው በመጨረሻ በይቅርታ ጥያቄ ከመፈታታቸው ውጭ ፓርላማ ላለመግባት መወሰናቸው ለመንግሥት የአቀረቧቸው ስምንት ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲመለሱ በማድረግ ረገድም ምንም ያበረከተው አስተዋጽኦ የለም፡፡ እንዲያውም ስምንቱ ቅድመ-ሁኔታነት ቀርበው የነበሩት አገራዊ ጉዳዮች ላይ ኢህአዴግ ለድርድር ራሱን እንዲያቀርብ ማድረግ የቻልነው ፓርላማ ገብተን ሰላማዊ ትግሉን መቀጠል የቻልነው ፓርቲዎች መሆናችን በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ በሚገኘው የድርድር ሂደት በግልጽ ታይቷል፡፡ ከሁሉም በላይ ከእሥር ቤት ወጥተው አዲስ ፓርቲ ካቋቋሙ በኋላ የቅንጅቱ የመንፈስና የሞራል ወራሾች ነን የሚሉት እነ ወ/ሪት ብርቱካን የፓርላማ አባል የሆኑ አባሎቻቸው ፓርላማው ውስጥ ውክልና እንዲያገኙ ለፓርላማው ማመልከቻ በመጻፍ ጠይቀዋል፡፡ የቅንጅቱን ውሳኔ ባለመቀበል ፓርላማ ለመግባት የመጀመሪያው ሰው የነበሩት አቶ ተመስገን ዘውዴም በኋላ ላይ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር ሆነው በክብር ሲመረጡ ታይቷል፡፡ መኢአድም የድርድር ሂደቱ ውስጥ ከገባ በኋላ ፓርላማ ውስጥ ውክልና አለኝ ብሎ የሚያምን ድርጅት ስለመሆኑ ፈራ ተባ እያለም ቢሆን ሲናገር ተደምጧል፡፡ የቀድሞ የቅንጅት አመራር የነበሩት ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያምም ቅንጅት ፓርላማ ላለመግባት መወሰኑ ስህተት እንደነበር በቅርቡ በይፋ አምነው ተናግረዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ፓርላማ በመግባትና ባለመግባት ጉዳይ ኢዴአፓ-መድኅን ተሳስቶ ነበር ብሎ ለመውቀስ የሚቻልበት አሳማኝ ምክንያት የሌለ መሆኑን ነው፡፡

አራተኛውና አንዳንድ ሰዎች ኢዴአፓ-መድኅንን የተሳሳተ አድርገው ለማየት የተገደዱበት ሌላው ምክንያት ኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ ባይነጠል ኖሮ የተሻለ ወይም የተለየ ውጤት ሊመጣ ይችል ነበር ብለው ከማሰባቸው የመነጨ ነው። በወቅቱ ቅንጅቱ በውስጡ የተፈጠሩትን የአቋም ልዩነቶች በአሉባልታ ዘመቻና በአፈና ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ችሎ ቢሆንና በተለይም የኢዴአፓ-መድኅንን አቅጣጫ ተከትሎ ቢሆን ኖሮ በርግጥም ኢዴአፓ-መድኅን ከቅንጅቱ ባይነጠል ውጤቱ በብዙ እጅ ከአሁኑ የተለየና የተሻለ በሆነ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ ቅንጅት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ልዩነቱን ለመፍታት ካለመፈለጉም በላይ ራሱን እና ትግሉን አደጋ ውስጥ የሚከት አቋም ማራመድ ስለመረጠ ከዚህ አካል ጋር አብሮ መቀጠል ጥፋቱንና አደጋውን ከመጋራት ያለፈ ሌላ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አልነበረም። እስከ መጨረሻው ድረስ የሚሉንን ሁሉ በጸጋ ተቀብለን ብንቀጥልም ኖሮ አንድ ቀን ተጽዕኖው አስመርሮን የሐሳብ ልዩነት ስናሣይ በእኛ ላይ "የፍየል ወጠጤ" መዘመሩ የማይቀር ነበር። እኛ ከቅንጅቱ ከተለየን ከሁለት ዓመት በኋላ በግልጽ እንደታየውም በኢንጂነር ኃይሉና በዶ/ር ብርሃኑ መካከል፣ ወይም በእነ ኢንጂነር ግዛቸውና በእነ ፕሮፌሰር መስፍን መካከል መለያየት ሲፈጠር እኛም ሚናችሁን ለዩ ተብለን ከአንዱ ጋር መደቆሳችን የማይቀር ነበር።

እኔም ሆንኩ ሌሎቹ የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች በወቅቱ ቅንጅት በተሳሳተ መንገድ እየሄደ መሆኑን በርግጠኛነት እያወቅን ከቅንጅቱ መለየታችንን ብቻ እንደ ስህተት ቆጥረን አብረን ተጉዘን ቢሆን ኖሮ ከእነሱ ጋር አብረን ለሁለት ዓመት ከመታሰርና በመጨረሻም እንደነሱ የኢህአዴግን መንግሥት ይቅርታ ጠይቀን ከመፈታት ወይም በአቋማችን ጸንተን ዕድሜ ልክ በእሥር ከመማቀቅ የተለየ ሌላ ልናመጣው የምንችል ለውጥ አልነበረም። እነሱ በሄዱበት መንገድ ሌላ ለውጥ ማምጣት የሚቻል ቢሆን ኖሮ እኛም አብረናቸው ባልኖርንበት ሁኔታ እነሱ የሚፈለገውን ለውጥ ከማምጣት የሚያግዳቸው ምክንያት አልነበረም። እንዲያውም ኢዴአፓ-መድኅን አቋም ወስዶ ራሱን ከቅንጅቱ ባይነጥል ኖሮ ትግሉ አሁን በሚገኝበት ደረጃም ምንም ዓይነት እርሾ ሊኖረው ባልቻለም ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ኢዴአፓ-መድኅን ራሱን ከቅንጅቱ በመነጠል ቅንጅት ሕዝቡ ከውጭ ሆኖ ከሚገምተው በተለየ በከፍተኛ ችግርና ድክመት ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በድፍረት ለመናገር ባይችል ኖሮ ሕዝቡ ስለ ቅንጅት ቆም ብሎ የማሰብና አመለካከቱን የመፈተሽ ዕድል በቀላሉ አይኖረውም ነበር። ኢዴአፓ-መድኅን የቅንጅቱን ገመና በድፍረት መናገር ባይጀምር ኖሮ "ቅንጅት መንፈስ ነው" የሚለው ከፖለቲካ እውነታ የሚጻረር አደገኛ አምልኮት የወደፊቱን የትግል ጉዞ ክፉኛ ተብትቦ መያዙ አይቀርም ነበር።

ስለዚህ እኔም ሆንኩ ሌሎች የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች ያለ እምነታችን በጭፍን ከቅንጅቱ ጋር አብረን ቀጥለን ቢሆን ኖሮ ከዕምነታችን ጋር ታስረን ከመማቀቅ ወይም በአሁኑ ወቅት በትግሉ ውስጥ ዶ/ር ብርሃኑ፣ ወ/ሪት ብርቱካን ወይም ኢነጅነር ኃይሉ ከሚገኙበት ሁኔታ የተለየ ወይም የተሻለ ሚና ሊኖረን አይችልም ነበር። ስለዚህ በየትኛውም መመዘኛ ብናየው የኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች ራሳችንን በድፍረት ከቅንጅቱ መነጠል መቻላችን ቢያንስ ከሌሎቹ ዘግይተው ከተበታተኑት የቅንጅቱ አመራሮች በተሻለ የአቋም ሰዎች መሆናችንን የሚያሳይና ሊያስመሰግነን የሚገባ ነበር እንጂ በተቃራኒው ሊያስወቅሰንና ሊያስወግዘን የሚገባ አይደለም።

ከመጀመሪያው ቅንጅቱ በኢዴአፓ-መድኅን አቅጣጫ መሄድ ችሎ ቢሆን ኖሮ ራሱንም ሆነ ትግሉን ከውርደትና ከውድቀት ማዳን ይችል እንደነበር እኛ ከምንናገረው በላይ እያንዳንዱ ሂደት ስለ ራሱ የሚመሰክር መሆኑ አሁን አሁን በግልጽ እዬታዬ ነው። ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ከቅንጅቱ አመራሮች ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ባካሄድኩት ስብሰባ "እናንተ አሁን በምትሄዱበት አቅጣጫ ሂዳችሁ በእውነት ትግሉን ለተሻለ ውጤት ካበቃችሁት እኛ ተሳስተናል ማለት ነውና ያኔ ስለጥፋታችን የኢትዮጵያን ሕዝብም ሆነ እናንተን በይፋ ተንበርክከን ይቅርታ እንጠይቃለን። ነገር ግን በዚህ መንገድ ሄዳችሁ የቅንጅቱንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አጣብቂኝ ውስጥ ካስገባችሁት ይቅርታ የምትጠይቁት እናንተ ትሆናላችሁ" በማለት የተናገርኩት የፖለቲካ ግምት እውነቱን ለመሸሽ ለማይፈልግ ለማንኛውም ሰው ቢያንስ የቅንጅት አመራሮች የኢህአዴግን መንግሥት ይቅርታ ጠይቀው ከእሥር ሲፈቱ የተረጋገጠ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም።

በቅንጅቱ ዙሪያ የተፈጠረው ችግርና፣ ችግሩም በትግሉ ላይ ያስከተለው አደጋ በአንድ በኩል የቅንጅቱ መሪዎች በተከተሉት የተሳሳተ ስልት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የቅንጅቱ ደጋፊ የሆነው ሕዝብ አግባብ ባልሆነና በተሳሳተ መመዘኛ የተሳሳተ ስልት የተከተሉትን የቅንጅት መሪዎች በመደገፉ ምክንያት የተከሰተ እንጂ በኢዴአፓ-መድኅን ምክንያት የተፈጠረ ችግር አይደለም። አንዳንድ "ልደቱ ተሳስቷል" ብለው የሚያምኑ ሰዎች በአጋጣሚ ሲያገኙኝ በዎቀሳ መልክ የሚያቀርቡልኝ አባባልና እኔ ለአባባላቸው ብዙውን ጊዜ የምሰጣቸው መልስ በዚህ ረገድ በቅንጅቱ ደጋፊዎችና በእኛ በኢዴአፓ-መድኅን ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ ማሳየት የሚችል ይመስለኛል። እነዚህ አንዳንድ የቅንጅቱ ደጋፊዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች በአጋጣሚ ሲያገኙኝ ርግጠኛ በሆነ ስሜት "ልደቱ -እኛ እኮ ትግሉን የደገፍነው አንተን አይተንና በአንተ ተማምነን ነበር -፤ አንተ ግን መጨረሻ ላይ ከዳኸን" ይሉኛል። እኔም ለዚህ ዓይነቱ አባባላቸው ብዙውን ጊዜ የሚከተለው ዓይነት መልስ በጥያቄ መልክ ልሰጣቸው እሞክራለሁ። "በእውነት

እኔን አይታችሁ ትግሉን ከደገፋችሁ - ታዲያ ለምንድን ነው በእኔና በሌሎቹ የቅንጅት መሪዎች መካከል የአቋም ልዩነት ተፈጠረ ሲባል የእኔን አቋም ለማዳመጥ እንኳ ዕድል ሳትሰጡኝ ሌሎቹን ተከትላችሁ መንዝ የመረጣችሁት?" እላቸዋለሁ፡፡

እስካሁን ድረስ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ካቀረብኩላቸው ሰዎች ውስጥ በደፈናው "ብዙ ሰው ተቃዎመህ" ከማለት በስተቀር አሳማኝ መልስ ሰጥቶኝ የሚያውቅ አንድም ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ በእኔ በኩል እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ለማቅረብ የምገደደው ያለ ምክንያት አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ከምርጫው በኋላ በእኔና በሌሎቹ የቅንጅት አመራሮች መካከል የምርጫውን የማጣራት ሂደት አስመልክቶ የተፈጠረው ልዩነት መሠረታዊ ስለሆነ ሕዝቡ ልዩነቱን በግልጽ ለማወቅ መሞከር አለበት በማለት ሃሣቤን በጋዜጣ መግለፅ ስጀምር በወቅቱ በሥራ ላይ የነበሩት ጋዜጦችም ሆኑ የቅንጅት ደጋፊ የነበረው ሕዝብ "በዚህ ወቅት ልዩነት መስማት አንፈልግም" በማለት የእኔን አፍ ለማዘጋት እንጂ እኔ የምለውን ለመስማት ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ እነዚህ "አንተን አይተን ትግሉን ደገፍን" የሚሉኝ ሰዎች ሁሉ ከእኔና ከኢዴአፓ-መድኅን በተፃራሪ የቆሙት ሰዎች በዕድሜአቸውና በትምህርት ደረጃቸው የገዘፉ መሆናቸውን በማየት ብቻ የእኛን በትምህርትና በዕድሜ በኩም ያልገፋነውን ሰዎች አስተሳሰብ ቆም ብለው የማዳመጥ ፍላጐት አልነበራቸውም፡፡ የቅንጅት ደጋፊ የነበረው ሕዝብ በተለመደው የአገራችን ብሂል "የተማረ ይግደለኝ" በሚል ስሌት እንጂ ሃቁን ጠለቅ ብሎ በመመርመር ሚዛናዊ አቋም ለመያዝ ያደረገው ሙከራ አልነበረም፡፡ ስለዚህ በፖለቲካ ሂደት ሰዎችን በ"ከሃዲነት" መፈረጅ ተገቢ ባይሆንም "ክህደት" ተፈፅሟል ከተባለ ግን "የተማረ ይግደለኝ" በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ "ታሪካዊ ክህደት" የተፈጸመብን እኛ ነን እንጂ እኛ በሌሎች ላይ ክህደት አልፈፀምንም፡፡

ከዐሥራ አራት ዓመታት በላይ ጥርሳችንን ነክሰን በመታገል በትግሉ ዙሪያ እንዲሰለፍ ያደረግነው አንድ ደጋፊ በመጨረሻው ሰዓት የመንግሥት ሥልጣን በእጃችን ሊገባ ነው ብለው ትግሉን የተቀላቀሉ ጥቂት ምሁራንን በስሜት ተከትሎ በመንዝ በእኛ ላይ ክህደት ከፈፀመ በኋላ በተቃራኒው እኛን በከሃዲነት ለመክሰስ ቢሞክር ሙከራው የራስ ስህተትን ለማድበስበስ ከመሞከር ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ዶክተርና ፕሮፌሰር የሚል ቅፅል ያላቸው ሰዎች ሁሉ የፖለቲካ ሊቅ መስለው የሚታዩት የዋህ ሰው በዚህ ረገድ ቢሳሳት የሚያስደንቅ ባይሆንም "ትግሉን የተቀላቀልኩት ልደቱን አይቼ ነው" በማለት በጋዜጣ ላይ ሲናገሩ የተደመጡትና ለምነን የፓርቲያችን መሪ ያደረግናቸው እንደ ዶ/ር ኃይሉ ዓርዓያ ያሉት ሰዎች ሳይቀሩ በትግሉ ሂደት አቋም የሚጠይቅ ፈታኝ ሁኔታ ሲፈጠር ከቀድሞ የትውልድና (Generation) የዩንቨርሲቲ ጓደኞቻቸው ጋር እንጂ ከእኛ ጋር በጽናት አብረው ሊቆሙ አልቻሉም፡፡ ለሁሉም "የተማረ

ይግደለኝ" የሚለው ተገቢ ያልሆነ አባባላችን "የተማረ ያድነኝ" ወደሚል በጎ አባባል ቢቀዬር የሚገባ በሆነ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ለአለፉት አምስት ዓመታት ኢዴአፓ-መድኅን ወይም ልደቱ ቅንጅትን በወያኔ ሰርጎ ገብነት ወይም በግል ሥልጣን ፍለጋ አፈረሱት እየተባለ ይወራ የነበረው አሉባልታ በሙሉ ምን ያህል መሠረተ ቢስ እንደነበረና ኢዴአፓ-መድኅንና ቅንጅት ለመለያየት የበቁት ወሳኝ በሆኑ የፖለቲካ ጉዳዮች መሠረታዊ የሆነ የስትራቴጂና የአስተሳሰብ ልዩነት ስለነበራቸው መሆኑን ነው፡፡

የሆነ ሆኖ ይህንን በእኔ ላይ የደረሰ የአሉባልታ ዘመቻ ያነበበ ወይም የሰማ ሰው እውነታውን ለምን በቀላሉ ሊገነዘበው አልቻለም ብሎ መፍረድ ያስቸግራል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህ ሁሉ ለምን በአንተ ላይ ደረሰ? ሰዎችስ ያለ ምንም በቂ ምክንያት በአንተ ላይ ይህንን ያህል እንዴት ሊረባረቡ ይችላሉ? ይህንን ያህል የተወራብህ አንተ ራስህ የሰራኸው ትልቅ ስህተት ቢኖር ይሆናል የሚሉ ጥያቄዎችና ግምቶች በውስጣቸው እንደሚፈጠር መገመት ይቻላል፡፡ የወቅቱን የትግል እንቅስቀሴ ውስጣዊ ሁኔታ ጠለቅ ብሎ አለማየትና አለመገንዘብ እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችና የሐሳብ ግጭቶች ለመፍጠር የሚያስችል አንድ ምክንያት ቢሆንም ዋናው ምክንያት ግን የቆየ የፖለቲካ ባህላችንም ሆነ የግራ ፖለቲካ አመለካከት በአገራችን ያመጣብንን ጣጣ በውል አለመረዳት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከጥንት ጀምሮም ሆነ በተለይም የግራ ፖለቲካ ወደ አገራችን ከገባ በኋላ ኢትዮጵያ ያለፈችበት የፖለቲካ ሂደት በብዙ ተመሳሳይ ገመናዎች የተሞላ ነው፡፡ "በአብዮት ልጅዋን ትበላለች!" መፈክር በአንድ የፖለቲካ ሰው ላይ እንዲህ ዓይነት ግፍና በደል ሲደርስ እኔ የመጀመሪያም - የመጨረሻም አይደለሁም፡፡ ከእኔ በፊት በርካታ የፖለቲካ ሰዎች በአራመዱት ዓላማና የሐሳብ ልዩነት ምክንያት ብቻ - ወላዋይ፣ በራዥ፣ ከላሽ፣ ቅጥረኛ፣ መሃል ሠፋሪ፣ አንጃኛ፣ የውስጥ አርበኛ፣ ወዘተ እየተባሉ በራሳቸው የትልግ ጓደኞች የተለያየ ዓይነት ግፍ የተፈጸመባቸው፣ በእስር ቤት ሲማቅቁ የኖሩና ውድ ሕይወታቸውን ጭምር ያጡ ሰዎች በቁጥር ቀላል የሚባሉ አይደሉም፡፡ ከእነዚህ በዬራሳቸው ዙሪያ ከነበረው እውነት ጋር ተቀብረው ዛሬ አስታዋሽ ካጡት በርካታ የትግል ሰዎች በተለየ እኔ ዛሬ በሕይወት ቆሜ ስለአለፍኩበት ሂደት ምስክርነት ለመስጠት መቻሌን ሳስበው በተሻለ ጊዜ የተፈጠርኩ እጅግ ዕድለኛ ሰው እንደሆንኩ ይሰማኛል፡፡ እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ወረርሽኝ ከእንግዲህ በኛ ይብቃ! ለማለት ዕድል ከማግኘቴም በተጨማሪ ትላንት በእኔ ላይ የፈጠራ ድርሰት እየፃፉ የተጨበጨበላቸው ግለሰቦችም ዛሬ ራሳቸው በሰርጎ ገብነትና ምስጢር በመሸጥ እየተከሰሱ በአደባባይ ሲዘለፉ ለማየት በቅቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ እንዲህ ዓይነቱ ደግሞ ደጋግሞ የሚከሰት የፖለቲካ ነውር የሚያረጋግጥልን የአገራችን ፖለቲካ ዛሬም ከግራ-ርእዮተ ዓለም በሽታ ያልተላቀቀ መሆኑን ነው፡፡ የግራ ርእዮተ-ዓለም ለሶሻሊስት ሥርዓት ግንባታና ለወዛደሩ መደብ የበላይነት መስፈን የሶሻሊዝም አርበኞች የመደብ ጠላቶቻቸውን ማንኛውንም ዓይነት ኢ-ሞራላዊ ተግባር ጭምር ተጠቅመው እንዲያጠፏቸው በድፍረት ይመክራል፡፡ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም በኋላ እነዚህ የግራ-ኃይሎች ርእዮተ-ዓለማችንን ለውጠናል እያሉ ቢሆንም ማንነታቸውም ሆነ ስልታቸው ሳይለውጥ ዛሬም በአገራችን የፖለቲካ ሂደት በገዥ ፓርቲነትም ሆነ በተቃዋሚነት የበላይነትን ይዘው ቀጥለዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በእኔ ላይ እንዲህ ዓይነቱን አስቀያሚ ድርጊት የፈጸሙት እኔ በተለየ ሁኔታ አስቸጋሪ ፍጡር ሆኜ ወይም እነሱ በተፈጥሮአቸው መጥፎ ስብእና ያላቸው ሰዎች ሆነው አይደለም፡፡ ችግሩ እነዚህ ሰዎች ለአለፉት 40 ዓመታት ባለፉበት የግራ ፖለቲካ ባህል በማንኛውም የክፋት መንገድ የሌሎችን ስብእናና ህልውና ጭምር አጥፍቶ የራስን ፍጹማዊ የበላይነት ለማረጋገጥ ሲባል የሚካሄደው የርስ በርስ መበላላት የተፈቀደና ትክክለኛ ተደርጐ የሚቆጠር የትግል ስልት በመሆኑ ነው፡፡

የግራ ፖለቲካ አራማጆች በሶቪዬት ኅብረት ስታሊን፣ በቻይና ማኦ፣ በኩባ ካስትሮ፣ በእኛም አገር ኰሎኔል መንግሥቱ ሆነው እንደታዩት በአንድ አገር ላይ ቢበዛ ከአንድ ድርጅት - ቢያንስ ደግሞ ከአንድ ግለሰብ በላይ ተሰሚነትና ወሳኝነት የሚኖረው ሁለተኛና ሦስተኛ አካል እንዲኖር ስለማይፈለግ ይህ ፍላጐታችን እውን እንዲሆን ሌሎችን ማዋረድና መግደል የተለመደ ተግባር ነው፡፡ በአገራችን ፖለቲካ ይህ ዓይነቱ ድርጊት የትናንት ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዛሬም እውነታ በመሆኑ ነው በእኔም ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈጸም የታየው በርግጥ በተመሳሳይ ብልሹ የፖለቲካ ባህል በሌሎች ሕይወት ላይ የደረሰው አደጋ በእኔ ላይ ሳይደርስ በመቅረቱ በዚህ አጋጣሚ የጊዜውን የተሻለ መሆንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነት በዚህ አጋጣሚ አመስግኜ ማለፉ የሚገባ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ደዌ ጋር የተጣቡ ሰዎች ትግሉን ለቀው ገለል እስካላሉ ድረስ፣ ወይም እነዚህ ሰዎች ይህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህላቸው ከትናንት እስከ ዛሬ አውዳሚ ሆኖ መቀጠሉን ተገንዝበው ከልባቸው እስካልተለወጡ ድረስ ወይም ሕዝባችን ለዚህ ዓይነቱ ብልሹ የፖለቲካ ባህል መጠቀሚያ መሆን የማይችልበት ብቃት ፈጥሮ መገኘት እስካልቻለ ድረስ እንዲህ ዓይነቱ አጸያፊ ተግባር ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ይህ ዓይነቱ ብልሹ የፖለቲካ ባህል እስከ ቀጠለ ድረስም ለሕዝባችንና ለአገራችን ጥቅም የሚበጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችንም ሆነ የፖለቲካ መሪዎችን በአገራችን መፍጠር ይቻላል ብሎ መገመት ያስቸግራል፡፡ አዲሱ ትውልድ ከእንግዲህ የራሴን ጉዳይ በራሴ መወሰን አለብኝ ብሎ መነሳሳት ያለበትም ይህንን መሠረታዊ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል በውል በመገንዘብ ሊሆን ይገባዋል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

### አዲስ ተስፋ የፈነጠቀ ታሪካዊ ጅማሮ

የዚህን መጽሐፍና የመድሎት መጽሐፍን የመጀመሪያ ረቂቅ አጠናቅቄ አንዳንድ ሰዎች ትችትና አስተያየት እንዲሰጡበት ከበተንኩት በኋላ ሐምሌ መጀመሪያ 2001 ዓ.ም ላይ ለሁለት ወር ቆይታ ወደ ሰሜን አሜሪካ ሄጄ ነበር፡፡ እኔ ከአሜሪካ ከመመለሴ በፊት ኢህአዴግ የመጪውን ምርጫ ሂደት አስመልክቶ ኢዴፓን ጨምሮ በፓርላማ መቀመጫ ላላቸው ለአራት ዋና ዋና ተቃዋሚ ፓርቲዎች የድርድር ግብዣ እንዳቀረበ በኢዴፓ አመራሮች በኩል ሰማሁ፡፡ ድርድሩም ነሐሴ መጨረሻ 2001 ዓ.ም ላይ ተጀመረ፡፡ ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ በአምስት የፓለቲካ ፓርቲዎች የተጀመረው ድርድር ገና ብዙም ሳይገዝ ከተደራዳሪዎቹ ፓርቲዎች መካከል አንዱ የሆነውና ስምንት ፓርቲዎችን በውስጡ ያሰባሰበው መድረክ ፈጽሞ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ራሱን ከድርድሩ ሂደት ሲያገልል ቀሪዎቹ አራት ፓርቲዎች ማለትም ኢህአዴግ፣ ኢዴፓ፣ ቅንጅትና መኢአድ ግን በድርድሩ ሂደት ቀጠሉ፡፡ ተደራዳሪ ፓርቲዎቹ በማንኛውም ምርጫ ነክ በሆነ ጉዳይ ላይ ያለምንም ገደብ ለመደራደር ከተስማሙ በኋላ በቅድሚያ ግን የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ በጋራ ለማውጣት ስለተስማሙ ድርድሩ በዚህ አጀንዳ ላይ ተጀመረ፡፡ እኔም መስከረም መጀመሪያ 2002 ዓ.ም ላይ ከአሜሪካ ከተመለስኩ በኋላ የድርድሩን ሂደት ተቀላቀልኩ፡፡

በቅድሚያ በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ፣ በመቀጠልም በሥነ-ምግባሩ የማስፈጸሚያ ስልት ላይ አራቱ ፓርቲዎች የጀመሩት ድርድር አጅግ አሰልችና እልህ አስጨራሽ በሆነ ሁኔታ ለሁለት ወራት ያህል ተካሄደ፡፡ ድርድሩ ሲጀመር በተደራዳሪ ፓርቲዎቹ መካከል ከነበረው የፍጥጫና የእልህ ስሜት አንጻር ድርድሩ የትም የማይደርስ መስሎ ታይቶ የነበረ ቢሆንም በሂደት ግን ከተለመደው የተለየ የመግባባትና የሰጥቶ መቀበል መንፈስ እየተፈጠረ መጣ፡፡ በተለይም ኢህአዴግ ቀድሞ ከሚታወቅበት የግትርነት ባህሪው ፈጽሞ በተለየ ሁኔታ በድርድሩ ሂደት የትዕግስተኝነትና የሌሎችን ሐሳብ በቅንነት የመቀበል ባህሪ በማሳየቱ ድርድሩ ወደ ውጤታማነት እየተቀየረ መጣ፡፡ በዚህም ምክንያት በድርድሩ ተሳታፊ የነበሩ

ሁሉም ፓርቲዎች ተገቢ ያልሆነ ምክንያት ፈጥሮ ድርድሩን ከማቋረጥ ይልቅ ድርድሩ በስምምነት ወደሚቋጭበት አቅጣጫ መግፋት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻም ለድርድር በቀረቡት አጀንዳዎች ዙሪያ የሁሉንም ተደራዳሪ ፓርቲዎች ስሜትና ፍላጐት በበቂ ሁኔታ የሚያስተናግድ ውጤት ላይ በመደረሱ እስከ መጨረሻው ዕለት ድረስ ወደ ስምምነት ሊመጣ አይችልም ብለን ብዙዎቻችን ገምተነው የነበረው መኢአድ ሳይቀር የድርድሩን ውጤት በጸጋ ስለተቀበለው የመጀመሪያው ዙር ድርድር በስምምነት ተቋጨ፡፡ በቀጣይነትም ከምርጫ ጋር ተያያዥነት አላቸው በተባሉ 16 የተለያዩ አጀንዳዎች ዙሪያ ድርድሩን በተፈጠረው በጎ የሰጥቶ መቀበል የድርድር መንፈስ ለመቀጠል ስምምነት ላይ ተደረሰ፡፡ እነዚህ በቀጣይነት ድርድር እንዲካሄድባቸው የተያዙ አጀንዳዎችን እነ ኢህአፓን የመሰሉ ድርጅቶች ከሚያቀርቡት “የሽግግር መንግሥት ይቋቋም” ጥያቄ በስተቀር ሁሉም በአገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች ከረዥም ጊዜ ጀምሮ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ በሚያካትት ሁኔታ የተቀረፁ ነበሩ፡፡ ሁሉም ተደራዳሪ ፓርቲዎች ያለምንም ማቅማማት የመጀመሪያውን ዙር የድርድር ውጤት በጸጋ እንዲቀበሉ ያስገደዳቸውም ይኸው በአገራችን የፖለቲካ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ክስተት ነበር፡፡

ክስተቱ ለረዥም ዓመታት በጠላትነት ሲተያዩ በነበሩት ተደራዳሪ ፓርቲዎች መካከል የፈጠረው አዲስ መንፈስ ከፍተኛ ስለነበር የተደረሰበት ስምምነት በፓርቲዎች ዋና መሪዎች እንዲፈረም ተወሰነ፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረትም ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የብዙ አገራት አምባሳደሮች በተገኙበት በሸራተን ሆቴል በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፣ በኢንጂነር ኃይሉ ሻወል፣ በአቶ አየለ ጫሚሶና በእኔ እንዲፈረም ተደረገ፡፡ በዚያ የፊርማ ሥነ-ሥርዓት በአገራችን በፅንፈኛ ፖለቲካ አራማጅነታቸው በግንባር ቀደምትነት ሊጠቀሱ የሚችሉት የሁለቱ ድርጅቶች(የኢህአዴግና የመኢአድ) መሪዎች የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስና ኢንጂነር ኃይሉ እጅ ለእጅ ሲጨባበጡ መታየታቸው አስገራሚም አስደሳችም ክስተት ሆነ፡፡ በተለይም የጥላቻና የኩርፊያ ፖለቲካ በአገራችን እንዲወገድ ከሁሉም ፓርቲዎች ቀድሞ ከጽንፈኝነት ፖለቲካ የጸዳ የሦስተኛ አማራጭነት ሚና በመያዝ ምክንያታዊ ፖለቲካ ሲያራምድ ለነበረው ለኢዴፓ እለቱና ክስተቱ ልዩና ታሪካዊ ሆነ፡፡ በዚህም ምክንያት በፊርማው ሥነ-ሥርዓት ላይ በእኔ በኩል ባደረኩት አጭር ንግግር የድርድሩ ሂደት የጥላቻና የኩርፊያ ፖለቲካ፣ በአጠቃላይም የዜሮ ድምር ፖለቲካ በአገራችን እየመሸበት መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቼ ተናገርኩ፡፡ አባባሉም በብዙ መገናኛ ብዙኃን ጉልቶ የሚደመጥ የዚያን ሰሞን ጥቅስ ለመሆን በቃ፡፡ እኔና ኢንጂነር ኃይሉ ሻወልም ከቅንጅት መፍረስ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በዚያ የፊርማ ሥነ-

ሥርዓት ላይ እጅ ለእጅ ለመጨባበጥ ብቻ ሳይሆን ጐን ለጐን ቆመን በጎ ሐሳብ ለመለዋወጥ በቃን፡፡

በአጠቃላይ የዚያ ድርድር ውጤታማነት የመገናኛ ብዙኃንን ትኩረት የሳበ ከመሆኑም በላይ በሕዝቡ ውስጥ አዲስ የተስፋ ድባብ ፈጠረ፡፡ በአጭር ጊዜም ለስምምነቱ በጎ አመለካከት የነበራቸው በአገሪቱ የሚገኙ ሌሎች 65 የፖለቲካ ፓርቲዎች አራቱ ፓርቲዎች ባጸደቁት የሥነ-ምግባር ደንብ ሰነድ ላይ ከተወያዩና የራሳቸውን የማዳበሪያ ሐሳብ ከጨመሩበት በኋላ ሰነዱ የጋራ ሰነዳቸው እንዲሆን በሙሉ ድምፅ በመወሰን የሂደቱን ተስፋ ሰጪነት የበለጠ አደመቁት፡፡ በድርድሩ ሂደት ተሳታፊ የነበርን ፓርቲዎችም ርስ በርስ ከመወቃቀስ ይልቅ የድርድሩ ሂደት የፈጠረውን በጎ መንፈስ አጉልቶ የሚያሳይና ስለወደፊቱም የአገሪቱ ፖለቲካ ተስፋ ሰጭ የሆነ የሐሳብ ልውውጥ ላይ በአልተለመደ ሁኔታ ትኩረት ሰጥተን ታየን፡፡ ይህ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የተፈጠረ አዲስ መንፈስም ኢዴፓ የሚያራምደው የምክንያታዊነት ፖለቲካ ምን ያህል በሌሎችም ፖለቲካ ፓርቲዎች ተቀባይነት እያገኘ እንደመጣ የሚያሳይ ሆነ፡፡ ከቅንጅት መሪዎች ይቅርታ ጠይቀው ከእሥር መፈታት በኋላ ቀስ በቀስ እየጠራና እየተጠናከረ የመጣው የኢዴፓ አቋምም የድርድሩን ሂደት በስምምነት መቋጨት ተከትሎ በሕዝብ ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት እያገኘ መጣ፡፡

በሥነ-ምግባር ደንቡ ላይ ይህ ዓይነት ስምምነት ከተደረሰ ከሁለት ሳምንታት በኋላም የቀድሞ የቅንጅት አመራር ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ የሆኑት ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ምክትል ሊቀመንበር ሆነው ይሠሩበት ከነበረው ከአንድነት ፓርቲ ኃላፊነታቸው በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸውን አሳወቁ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ በሪፖርተር ጋዜጣና በአሜሪካን ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያ "የቅንጅት አመራሮች ላጠፉነው ከፍተኛ ጥፋት የኢትዮጵያን ሕዝብ ተንበርክከን ይቅርታ ልጠይቀው ይገባል" የሚል መግለጫ ሰጡ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለቅንጅት መፍረስ እኔ (ልደቱ) ተጠያቂ ተደርጌ ስወቀስ መኖሬ ስህተት እንደሆነና ለቅንጅት መፍረስ ተጠያቂዎቹ ርሳቸውን ጨምሮ ሁሉም የቀድሞ የቅንጅት አመራሮች መሆናቸውን በይፋ አጋለጡ፡፡ በቅንጅት ውስጥ ለተፈጠረው ችግር ዋናው ምክንያትም የግራ ፖለቲካ አራማጅ ከነበረው ትውልድ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል ጋር የተያያዘ መሆኑን በግልጽ ተናገሩ፡፡ ቅንጅት ፓርላማ ላለመግባት የወሰነው ውሳኔም ስህተት እንደነበር በድፍረት መሰከሩ፡፡ ይህ የዶ/ር ያዕቆብ የይቅርታ ጥያቄ በትግሉ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት ከደረሰ በኋላ ዘግይቶ የመጣና አንዳንድ የተዛቡ አመለካከቶች የተንፀባረቁበት ቢሆንም ሕዝቡ በቅንጅት ዙሪያ ስለተፈጠረው ችግር የነበረውን ግራ መጋባት በተወሰነ ደረጃ በማጥራት ረገድ የተጫወተው ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም፡፡ በተለይም ኢዴፓ

እንደ ፓርቲ ከመጀመሪያው ጀምሮ ሲያራምደው የነበረው አቋም ምን ያህል ትክክልና ቅንጅትን ከውድቀት ሊታደግ የሚችል እንደነበር ሕዝቡ በሂደት እየፈጠረ የመጣውን ግንዛቤ የበለጠ የሚያጠናክር ሆነ፡፡

ዞሮ ዞሮ አዲስ የተስፋ ድባብ በተፈጠረበት በዚያ ወቅትም በተወሰነ ደረጃ አደብ መግዛት ጀምሮ የነበረው የአሉባልታ አውሬ እንደገና ነፍስ ዘርቶ መንፈራገጡ አልቀረም፡፡ በአንድ በኩል በቂ ባልሆነ ምክንያት ራሱን ከድርድሩ ሂደት በአገለለው በመድረኩ የመሰሪነት አካሄድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በውጭ አገር በሚገኙ ጽንፈኛ የፖለቲካ ኃይሎች ጨዋታ የሚመራ አዲስ የአሉባልታ ዘመቻ ከኢህአዴግ ጋር ተደራድረን ለዚያ ስምምነት በበቃነው ፓርቲዎች ላይ ተከፈተ፡፡ በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ ከጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ጋር መድረክ ላይ ሲጨባበጡ በታዩት በኢንጅነር ኃይሉ ላይ ሰፊ የአሉባልታ ዘመቻ ተከፈተ፡፡ ኢንጅነር ኃይሉ ዘግይተውም ቢሆን ወደ ሰጥቶ የመቀበል የድርድር ፖለቲካ መምጣታቸው ሊያስመሰግናቸው የሚገባ ደፋርና ትክክለኛ አቋም ቢሆንም በተቃራኒው እንደ ኃጢያት ተቆጥሮባቸው "ሸጡን" "ከዱን" የሚል መጠነ ሰፊ ዘመቻ ተከፈተባቸው፡፡ ኢንጅነር ኃይሉ እንዲህ ዓይነት አስቀያሚ የአሉባልታ ዘመቻ በሳቸው ላይ መከፈቱን ሲያዩ በተመሳሳይ ፈተና ውስጥ ስላለፉት ስለ ኢዴፓና ስለመሪዎቹ በውስጣቸው ምን ሊያስብ እንደሚችሉ ባይታወቅም አሉባልታውን በሚያስገርም ሁኔታ ፊት ለፊት ሲጋፈጡት ታይተዋል፡፡

በአጠቃላይ በድርድር ሂደቱ በአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች አዲስና በጐ የስሜት ድባብ ታይቷል፡፡ ይህ የስሜት ድባብ ወደ ፊት ምን ያህል ተጠብቆና የበለጠ ተጠናክሮ ይቀጥላል!? በሌሎች ለቀጣይ ድርድር በአጀንዳነት በተያዙ ጉዳዮችስ ተደራዳሪ ፓርቲዎች ምን ያህል ውጤታማ ስምምነት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ!? ምርጫ 2002 ምን ያህል የአገራችን ዴሞክራሲ ቀጣይነት ማረጋገጫ በሚሆን መጠን ነፃና ፍትሐዊ ሆኖ ይጠናቀቃል!? በወደፊቱ የአገራችን የፖለቲካ ሂደትስ አሉባልታ ምን ያህል ቦታ አግኝቶ ይቀጥላል!? የሚሉት ከባባድ ጥያቄዎች ለሁላችንም ፈተና ሆነው የሚቀጥሉ፣ ጊዜና ሂደት መልስ የሚሰጡባቸው ሆነው ከፊታችን ተቀምጠዋል፡፡

### ማጠቃለያ

በአጠቃላይ እኔም ሆንኩ ኢዴአፓ-መድኅን በዚህ ሁሉ ፈተና አልፈን ከዛሬ ደርሰናል፡፡ በትግሉ ሂደትም አሉባልታ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያልተለዩን የትግላችን ቀንደኛ ጠላት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ብዙ ሰዎች ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ እንደገና አንሰራርተን በፖለቲካ ትግሉ ልንቀጥል እንደማንችል ርግጠኛ የነበሩ ቢሆንም እኛ ግን ዛሬም በትግሉ ውስጥ የማይናቅ ሚና እየተጫወትን እንገኛለን፡፡ ድርጅታዊ ህልውናችንን በአግባቡ ጠብቀን ከመቀጠላችንም በላይ እኛን በከኃዲነት ከሚከሱት ፓርቲዎች በላይ ዛሬም በሕዝቡ ውስጥ እንደገና ገብተን መሥራት እንደምንችል በገሃድ ማሳየት ችለናል፡፡ ያሳለፍነውን ሂደት ወደኋላ ተመልሰን ለማስታወስ ስንሞክርም እኛን ዛሬ የሚያስጨንቀን ለምን ያ-ሁሉ በደልና ግፍ ያለ አግባብ ተፈጸመብን የሚለው አይደለም፡፡ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የሚታገል ግለሰብም ሆነ ድርጅት ከዚህም በላይ የሆነ መሥዋዕትነት ሊከፍል ይገባዋልና ያለፍንበት ሂደት ከባድም ቢሆን ሊያመፃድቀንና ሊያስቆጨን የሚችል ግን አይደለም፡፡ ስለ አለፈውና በእኛ ላይ ስለ ተፈጸመው በደል በማሰብም ስለ ወደፊቱ ለመዘናጋትም ሆነ በድለውናል በምንላቸው ሰዎች ላይ ቂምና በቀል የመቋጠር ፍላጐትም የለንም፡፡ ይልቁንም እኛን የበለጠ የሚያሳስበን እንደ አንድ ኅብረተሰብ ከዚህ ለአለፉት በርካታ ዓመታት ከታዬው ሂደት ምን ያህል ከልብ ተምረን የወደፊቱን ጉዟችንን ለተሻለ ውጤት ልናበቃው ተዘጋጅተናል? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

በዚህ ረገድ አንዳንድ አበረታች ለውጦች መኖራቸው እርግጥ ቢሆንም የሚጠበቀውን ያህል ከሂደቱ የተማርን መሆኑን የሚያሳዩ ለውጦች እየታዩ ነው ማለት ግን አይቻልም፡፡ ዛሬም

እኛ ከምንናገረው በላይ የተቃዋሚው ጐራ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት የተጓዘበት አቅጣጫ ምን ያህል በስህተትና በድክመት የተሞላ፣ ውጤቱም ትግሉን የበለጠ ከማዳከም አልፎ በኢህአዴግ ውስጥ ያለውን አክራሪ ኃይልና አስተሳሰብ የበለጠ አጠናክሮ ያለፈ እንደነበር ጊዜና ሂደት ራሳቸው እየመሰከሩ ባለበት ሁኔታ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ ያለን ሰዎች አቋማችንን በሃቅ ገምግመን ቢያንስ የወደፊቱ ጉዟችን ካለፈው የተሻለ እንዲሆን ልባዊ ፍላጐትና ተነሳሽነት እያሳዬን አይደለም፡፡ በተለይም አሉባልታ ከባዱና ቀዳሚው የተቃዋሚው ጐራ ጠላት መሆኑን ተገንዝበን እስካሁን በቁርጠኝነት ልንዘምትበት አልቻልንም፡፡ ዛሬም እንደ ትናንቱ አሉባልታን በመሸጥ መተዳደር የሚፈልጉ አንዳንድ ጋዜጦች በገበያው ውስጥ ያሉ መሆኑ በግልጽ እየታየ ቢሆንም ተቃዋሚዎች የእነዚህን ጋዜጦች ወዳጀነት ለማግኘት እንጂ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲገቡ ልንታገላቸው ስንሞክር እየታየ አይደለም፡፡ አሁንም ወደፊት መጓዝ የምንፈልገው ለዐሥራ ስምንት ዓመታት ተሸናፊ በሆንበት ተመሳሳይ የትግል ስልት መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው፡፡

አንድ ቦታ ላይ ቆም ብለን ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያለንና ጠንካሮች ነን ብለን የምናምን ተቃዋሚዎች፣ ደካማና የሕዝብ ድጋፍ የሌለው ነው በማለት በንቀት የምናየው ኢህአዴግን እስካሁን ማሸነፍ ያላስቻለን ስህተትና ድክመት ምን እንደሆነ በሃቅ ራሳችንን በመገምገም አዲስ ስልትና አቅጣጫ መቀዬስ አልቻልንም፡፡ በውጭ አገር በስደት እያረጁ የሚገኙት እንደነ ኢህአፓ ያሉት ፓርቲዎች፣ በየዓመቱ አንድ አዲስ ኅብረት ፈጥረው የሚያፈርሱት እነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ በሠላሳ አምስት ዓመት የነፃነት ትግል አንድ ወረዳ ነፃ ማውጣት ያልቻሉት እነ ኦነግ፣ በምርጫ 97 ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ የነበረውን ሰላማዊ ትግል እንክትክቱን ያምጣነው የቀድሞው የቅንጅት መሪዎች፣ አንዳችን በሌላው ላይ ጣታችንን ከመቀሰር በስተቀር አንድም ቀን እኛም ስህተትና ድክመት አለብን ብለን ራሳችንን ለመገምገምና ለመተቸት ደፍረን አናውቅም፡፡

እስካሁን ራሱን በድፍረት በመገምገምና ሁላችንም የየራሳችን ድክመትና ጥንካሬ አለብን በማለት ካለፈ ስህተቱ ለመማር እየሞከረ የሚገኘው ብቸኛ ፓርቲ ኢዴፓ ቢሆንም ይህ ርምጃው እንደ ወንጀል ተቆጥሮበት ዛሬም እንደትናንቱ የአሉባልታና የፍረጃ ሰለባ እየሆነ ይገኛል፡፡ በአንድ በኩል ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ቢያንስ ምክንያታዊ ፖለቲካ ለማራመድ ቆርጦ የተነሣውን ኢዴፓን በበጎ ዓይን አይቶ የተሻለ መግባባት መፍጠር ሲገባው በተለመደ ጭፍን አመለካከቱ በኢዴፓም ላይ የተለያዩ ተፅዕኖዎች ማድረጉን የቀጠለበት ሲሆን (በአሁኑ ወቅት አንዳንድ በጐ ለውጦች እየታዩ ቢሆንም)፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ በቁጥር ቀላል የማይባል የኅብረተሰብ ክፍል በኢዴፓ ላይ የሚደርሱትን ተጽዕኖዎች በሙሉ የአስመሳይነት

ድርጊቶች አድርጐ እያያቸው ይገኛል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በኛ ላይ ባደረባቸው ገደብ የሌለው ጥላቻ ምክንያትም በትግሉ ሂደት ሕይወታችን ተሰውቶና አስከሬናችን በእሳት ተቃጥሎ ቢያዩ እንኳ “የሞቱት ሊያስመስሉ ነው” የሚሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም የተመሠረቱበትን ዓላማ እርግፍ አድርገው ትተው ኢዴፓን ወያኔ የሚያስመስሉበትን ሴራ ሲሸርቡ መዋልን የዕለት ተዕለት ሥራቸው አድርገውታል፡፡ ከእንግዲህ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ እንደ ኢዴፓ ዓይነቱ ምክንያታዊ የፖለቲካ ድርጅት በመንግሥትም ሆነ በሕዝቡ ተቀባይነት ሳያገኝ ከቀረ የወደፊቱ የአገራችን ፖለቲካ ዕጣ-ፈንታ ካለፈው ያልተሻለና በችግር የተሞላ ሆኖ እንደሚቀጥል ግልጽ ቢሆንም ሁሉም መለዎጥን ጠልቶ በነባራዊ ባህሪውና ማንነቱ ቀጥሎበታል፡፡ በተለይም የተቃዋሚው ጐራ ደጋፊ የሆነው ሕዝብ እስካሁን ድረስ የትግሉን አጠቃላይ ችግርና የትግሉን መሪዎች እውነተኛ ማንነትና ባህሪ በውል መመዘንና መገንዘብ ተስኖት ዛሬም እንደ ትናንቱ በስሜትና በውዥንብር እየዋዥቀ ይገኛል፡፡ ተቃዋሚዎችም ሆን የእኛ ደጋፊ የሆነው ሕዝብ ስለ ራሳችንም ሆነ ስለ ሌሎች ከምናራምደው ያረጀና በእስካሁኑ የትግል ሂደት ደጋግመን ተሸናፊ እንድንሆን ካደረገን አስተሳሰባችን ተላቀን አዲስና ደፋር አቋም መያዝ የማንችል ከሆነ “ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሉም ይጓዛል” የሚለው የኢህአዴግ ስላቅ ለአለፉት ዐሥራ ስምንት ዓመታት ብቻ ሳይሆን ለመጪዎቹም ዐሥራ ስምንት ዓመታት እውን የማይሆንበት ምክንያት አለ ማለት አይቻልም፡፡

ኢዴፓ